@OLDBOOKSPDF



@OLDBOOKSPDF

## መቅድም

ይህን ፣ "ወንጀለኛው ዳኛ" ብዬ ስይሜ ላንባቢዎች የማቀርበ ውን ልብወለድ ታሪክ ፣ በ፲፱፻፷፬ (ይህም በኢትዮጵያ የሰራተ መንግ ስት ለውጥ ከመደረጉ በፊት ማለት ነው) በተውኔት (በትያትር) መልክ አዘጋጅቼ ፣ "የሊም እግሮች" ብዬ ከሰዬምሁት ሌላ ልብ ወለድ ጋራ እንዲታተም ፈቃድ ለሚሰጡ ባለስልጣኖች ከመቅረቡ በፊት ፣ የዋጋውን ግምት ማወቁ ጠቃሚ ስለ መሰለኝ ፣ በመጠነኛ ዋጋ ያትማል እዬተባለ ይወራለት ለነበረ አንድ ማተሚያ ቤት አቅርቤው ነበር ። ነገር ግን ማተሚያ ቤቱ ላንድ መጽሀፍ ፩ ብር ፲፰ (አንድ ብር ካስራ ሰባት ሳንቲም) ሂሳብ ስለ ጠዬቀኝና ሌሎችም ከዚህ ያብልጥ እንጂ ያነሰ እንደማይጠይቁ የሚያውቁ ሰዎች ስለ ነገሩኝ ፣ የተጠዬቀው ዋጋ ከባድ መስሎ ታይቶኝ ፣ ምናልባት በቅርቡ በኢትዮጵያ የተቋቋመው የወረቀት ፋብሪካ ስራውን ሲያስፋፋ ፣ የወረቀት ዋጋ ዝቅ ይልና ፣ በዚያው መጠን ዝቅ ባለ ዋጋ ለማሳተም የሚቻልበት ጊዜ ሩቅ አይሆን ይሆናል ብዬ ገምቼ ለማቆዬት ወሰንሁ ። ከዚያ በሁዋላ ፣ በጅ እንደ ተጻፈ መልኩ ሳነበው ፣ ፊት ልብ ሳባደርግ ያለፍሁዋቸው አንዳንድ ጉድለቶች እዬሁብት ። ከኒያ ጉድለቶች አያንተኛው መርዘሙ ነበር ። እዬመላለስሁ ባነበብሁት ቁጥር ፣ ከልክ ያለፈ ረዥምም እዬሆነ ይታዬኝ ጀመር ። ለማሳጠር ያደረግሁት ሙከራም አሳቡን ሳያጎድል ፣ መሰረት አሳቡን ሳይነካ ፣ ወደ ፈለግሁት መጠን ፣ ወይም ልክ ሳያደርስልኝ ቀረ ። ስለዚህ መቆዬቱ የማይቀር ከሆነ ፣ ከማሳጠር ይልቅ አንዲያውም መሰረት አሳቡ ሳይነካ ፣ እንዳለ ሆኖ ማስፋፋትና ከተውኔትነት ወጻሁን መልኩ ፣ ወደ ልብወለድ ታሪክነት መለወጡ የሚሻል መስሎ ታዬኝና ፣ ሳመንታ ትንሽ ጊዜ ካሳለፍሁ በሁዋላ ፣ ይህን የመጨረሻ አሳቤን ተከትዬ መስራት ጀመርሁ ።

ወንጀለኛው ዳኛን መጀመሪያ በተውኔት መልክ ስጀምረውም ሆነ መጨረሻ በልብወለድ ታሪክ መልክ ስጨርሰው ፣ አይነተኛ አላማዬ የጊዜውን የኢትዮጵያ ሰራተ ማህበርና በዚያ ሰራተ ማህበር ውስጥ ከዘመናዊው ትምህርት ቤት እዬተማረ የሚወጣውን ትውልድ የሚገጥመውን ችግር ለኔ እንደ መሰለኝ ፣ እንደ ታዬኝ ፣ በቃላት አጉልቶ ስሎ ማሳዬት ነው ። ይህን አላማ መንጊቼ ወይም ስቼ እንደሆን መቸም ፈራጆች አንባቢዎች ናቸው ።

@OLDBOOKSPDF

ስለ ኢትዮጵያ ስራተ—ማህበርና በውስጡ ከተከፈቱት ዘመናውያን ትምህርት ቤቶች እዩተማሩ ስለ ወጡት ወጣቶች ከመግለጽ በፊት ፣ በጠቅላላው ስራተ-ማኅበር ምን እንደ ሆነና ከማህበሩ አባሎች ጋር ያለው ግንኙነትስ እንዴት እንደ ሆነ መመርመርና ለመረዳት መሞከር ይጠቅማል ብዬ ስለማምን ፣ ጠቅላላ አሳብ ሊመስጠት ያክል የሚከተለውን መግለጫ አቀርባለሁ ።

አንድ ስራተ-ማህበር ለማህበሩ አባሎች ስጋዊና መንፈሳዊ ኑሮ የሚያስፈልጉት ሁሉ ፣ ማለት የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ ፣ የማህበራዊ ኑሮ ያስተዳደር ፣ የሀይማኖትና እነሱን የመሳሰሉት ስራቶች ካገሩ ጠባይ ፣ ታሪክ ፣ ስልጣኔ ፣ ባህል ፣ ልማድ ፣ ህግና ወግ ጋር ባንድነት ተሳስረው ፣ ተዛምደውና ተዋህደው የተሰሩበት ጠቅላላ ፣ ወይም አቢይ ስራት ነው ። እንዲህ ያለው ስራተ-ማህበር በውስጡ እዩተወለዱ ፣ እያደጉ ፣ እዩኖሩ ለሚያልፉት ተከታታይ ትውልዶች ፣ ወይም አባሎች ከፈጣሪ በሚያገኙት ልዩ ልዩ የባህርይ ስጦታ ላይ ፣ ሰውን ከሌላው ፍጥረት ሁሉ ለይቶ ፣ "ሰው" የሚያሰኙትን ያካልና የመንፈስ ጸጋዎች የሚሰጥና እንዱ ህዝብ ከሌሎች የሚለይባቸውን ምልክቶች ሁሉ የሚፈጥር ከመሆኑ ሌላ ፣ እሱም በፈንታው ፣ በውስጡ እዩተከታተሉ ኖረው ከሚያልፉት ትውልዶች ፣ ወይም አባሎች ከሚቀበለው አዳዲስ እውቀት ፣ አዳዲስ ፍጥረትና ፣ አዳዲስ ሀይል እዩተመገበ የሚያድግ ፣ የሚጠነክርና የሚዳብር ህያው ነው ። ህያው በመሆኑም እንደ ህያዋን ሁሉ ከሱ ቀድሞ ከነበረው ስራተ-ማህበር ከስጋው ስጋ ከነፍሱ ነፍስ ነስቶ (ተቀብሎ) የሚወለድና ከሱ በሁዋላ የሚከተለውን ስራተ-ማህበር ፣ ከስጋው ስጋ ፣ ከነፍሱ ነፍስ ሰጥቶ የሚወልድ ነው ።

የሰዎች ስራተ-ማህበር እንደ ሰዎች ህያው ነው ካልንም ፣ ስራተ ማኅበርን ለማጥናትና ለማስተዋል የሰዎችን ኑሮ እንደ ምሳሌ አድርጎ መጥቀሱ ምናልባት ያገለግል ይሆናል ።

አንዳንድ ጊዜ ፣ ሰዎች ከስጋ ልጆቻቸው ሌላ ፣ ወይም በስጋ ልጆች ፈንታ ፣ የማር ፣ ወይም ፣ የህግ (በጋልኛ የጉዲፈቻ) ልጆች ይኖሩዋቸውዋል ። ነገር ግን እንዲህ ያሉት የህግ ልጆች ፣ ለህግ ወላጆቻቸው የንብረት ወራሾች ይሆናሉ እንጂ ፣ ምንም ቢሆን ከስጋ ወላጆች ወደ ስጋ ልጆች የፍጥረትን ህግ ተከትሎ ለሚወርደው የባህርይ ሆነ ያካልና የመንፈስ ጸጋ ወራሾች ሊሆኑ አይችሉም ። እንዲሁም አንድ [illegible] የመጣ ፣ [illegible] ስራተ-ማህበር ያገሩ የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚክ ፣

@OLDBOOKSPDF

የማህበራዊ ኑሮ ወዘተርፈ . . . ከታሪኩ ፣ ከስልጣኔው ፣ ከባህሉ ፣ ከል ማዱ ፣ ከህጉና ከወጉ ጋር ተዛምደውና ተዋህደው ከተሰሩበት ፣ ከቀደመው ስራተ–ማኅበር ከስጋው ስጋ ፣ ከነፍሱ ነፍስ ነስቶ (ተቀብሎ) ሊወለድ አይችልም ። እንዲያ ሆኖ ሊወለድ ባለመቻሉም ፣ ልክ የሰዎች የማር ፣ ወይም የሕግ (የጉዲፈቻ) ልጆች ሊሕግ ወላጆቻቸው የንብረት እንጂ የባህርይ ሆነ ያካልና የመንፈስ ወራሾች ሊሆኑ እንደማይችሉ ፣ እሱም ለቀደመው ስራተ–ማህበር ያካልና የመንፈስ ጺጋዎች ወራሽ ሊሆን አይችልም ፤ ባእድ ሆኖ እንደ መጣ ፣ ለዘላለም ባእድ ሆኖ ባይቀር ባእድ እንደ ሆነ ብዙ ይቆያል ። ሊዛመድ የሚችለው እንዲሁ እንዳለ በጥ ንታዊው ስራተ–ማህበር ላይ በመጫን ፈንታ ፣ ወይም የጥንታዊውን ስራተ–ማህበር ፣ ቦታ ጨርሶ ልውረስ በማለት ፈንታ ፣ ከሱ ጋር የተጋባ እንደሆነ ፣ ከራሱ አዩስጠ ከጥንታዊው ስራተ–ማህበር ለመቀበል ፈቃደኛ የሆነ እንደ ሆነ ነው ። ነገር ግን ራሳቸውን ከፍ ፣ ሌሎችን ዝቅ አድርገው የሚመለከቱ ግለሰቦች ፣ ዝቅ አድርገው የሚመለከቱዋቸውን ወገኖች መግ ዛት እንጂ ከነሱ ጋር መጋባት እንደማይፈቅዱ ፣ ራሳቸውን ከፍ ፣ ሌሎ ችን ዝቅ አድርገው የሚመለከቱ ስራተ– ማህበሮችም ፣ ዝቅ አድርገው የሚመለከቱዋቸውን ስራተ–ማህበሮች አጥፍተው ፣ ቦታቸውን መው ረስ ፣ ወይም በነሱ ላይ መጫን እንጂ ከነሱ ጋር መጋባት ፣ መዛመድ ፣ ወይም መደባለቅ አይፈቅዱም ።

ስለዚህ ባእዱ ስራተ–ማህበር ከተወለደበት አገር ስራተ–ማህበር ይዞት የመጣውን ያካልና የመንፈስ ውርስ ፣ በገባበት አዲስ አገር ህዝብ ላይ ይጭንበታል ። ከዚያ በሁዋላ በዚያ ባእድ ስራተ–ማህበር ውስጥ፣ የሱን ያስተሳሰብና ያሰራር ልማድ ተከትሎ የሚመሠረተው ሁሉ ፣ ማለት የፖለቲካው ፣ የኢኮኖሚው ፣ የማኅበራዊ ኑሮው ፣ ያስተዳደሩ ፣ የኑሮ ልማዱና እነሱን የመሳሰለው ልዩ ልዩ ስራት ካገሩ ህዝብ አስተሳሰብ፣ አሰራርና ጠቅላላ ያኗኗር ልማድ ፍጹም የተለዩ ፣ ፍጹም ባእድ ስለሚሆን ፣ ይህን የህዝቡ የቆዩ ያኗኗር ልማድ በጽኑ የሀ ይማኖት ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ ኑሮ እምነቶች ላይ የተመሠረተ ከሆነ ፣ በባእዱና በባላገሩ ስራተ–ማህበር መሀከል ግጭት መፈጠሩ የማይቀር በመሆኑ ፣ ሰላም አይኖርም ። ህዝቡ እንዲያ ባሉ ጽኑ እምነቶች ላይ የተመሰረተ ያኗኗር ልማድ ከሌለው ግን ፣ ባእዱን ስራተ–ማህበር ለማስቀበል የሚኖረው ችግር ምናልባት ያን ያክል አይሆን ይሆናል።

የኢኮኖሚክ ቅኝ አገዛዝ ፣ የማህበራዊ ኑሮ ቅኝ አገዛዝ ፣ የባህል ቅኝ አገዛዝ የሚሉት እንዲህ ያለውን ፣ ከውጭ መጥቶ ባንድ አገር ህዝብ ላይ የሚጫነውን ባእድ ስራተ–ማህበር ነው ።

@OLDBOOKSPDF

የያዝነው ምዕተ-አመት ከገባ ከጥቂት አመታት በሁዋላ ጀምሮ፣ በኢትዮጵያ የደረሰው ይህን የመሰለ ነው ። ምንም እንኳ ኢትዮጵያ ከ፲፱፻፳፰—፲፱፻፴፫ ላምስት አመት ብቻ በፋሺስት ኢጣሊያ ከመወረርዋ በቀር ፤ በሌሎች ያፍሪቃ አገሮች የደረሰው ፣ በቅኝ ገገርዎች ለረዥም ጊዜ የመግዛት ክፉ እድል ባይገጥማት ፣ ገዥዎችዋ አገራቸው በልማት ወደ ሁዋላ የቀረች በመሆንዋ ፤ "አውሮጳውያን ፣ ወይም ባጠቃላይ ፈረንጆች በደረሱበት የልማት ደረጃ ቶሎ እንድትደርስ ፡ እነሱ የሚሰጡትን ትምህርትና ምክር ፣ ስራታቸውን ጭምር መቀበል ያስፈልጋል" ብለው በማመን ለፈረንጆች በፈቃዳቸው በራቸውን በሰፊው መክፈት ብቻ ሳይሆን፡በብዙ መንገድ የፈረንጆችን ስራት ተቀብሎ መከተል የእዋቂነትና የስልጡንነት ምልክት፡የኢትዮጵያን የቆዩ ስራት እንደ ያዙ መቆየት ያላዋቂነትና የሁዋላ ቀርነት ምልክት ሆኖ እንዲታይ ያደፋፍሩ ስለነበረ ፣ በተለይ በከተማ ፣ የፈረንጆች ስራት ፣ የኢትዮጵያን የቆዩ ስራት እየገፋ ቦታ ማስለቀቅ ከጀመረ ቆየት ብሎዋል ። ነገር ግን ጥንታዊው የኢትዮጵያ ስራት ቦታውን ለባእዱ ስራት እንዲያስረክብ በሀግ የተፈረደበት ከፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ በሁዋላ ነው ።

ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ከመውረርዋ በፊት ፣ ሀገ መንግስት ለመመስረት ፣ የመማክርት ሸንጎ ለመክፈት ፣ በጥቂት ቦታዎች ዘመናውያን ትምህርት ቤቶች ለማቋቋም ፣ በደመወዝ የሚተዳደር የጦር ስራዊት ለማሰልጠንና እነሱን የመሳሰሉ አንዳንድ አዳዲስ ነገሮች ለመፍጠር ተጀምሮ የነበረው ውጥን ፣ ከወረራው በሁዋላ ተሻሽሎና ተጠናክሮ ፣ በዚያ ላይ ያስተዳደር ፣ የህግ ፣ የፍርድ ስነ-ስራትና እንደነሱ ያሉ ፣ የኢትዮጵያን ህዝብ ኑሮ የሚነኩ ስራቶች ተጨምረውበት-የቆዩው የኢትዮጵያ የኑሮ ስራት ከስር እንዲለ ፣ ይህ የፈረንጆች እንግዳ ስራት ባዋጅ በላዩ ተጫነበት ። ነገር ግን እንግዳው ስራት ፣ ለጠቅላላው ህዝብ ብቻ ሳይሆን ለባለ ስልጣኖችና ለዩስራው ክፍል መሪዎች ጭምር ባእድ ስለ ነበረ ፣ በስራ ላይ ማዋሉ ቀላል አልነበረም ። ስለዚህ ወጣቶች ከዘመናውያን ትምህርት ቤቶች እዩተማሩ እስኪወጡ ድረስ ፣ በጥንታዊው ያስተሳሰብና ያሰራር ልማድ ሲሰሩ የኖሩት ፣ የፍርድ ይሁን ያስተዳደር ባለስልጣኖች ፣ በዚያው በኖሩበት ያስተሳሰብና ያሰራር ልማድ መቀጠሉ ይቀናቸው ስለ ነበረ ፣ ባእዱ ስራት በህግ የታወቀውን ያክል በግብር ይታወቅ ነበር ለማለት አያስደፍርም ።

ወጣቶች ከውጭ አገርና ከኢትዮጵያ ዘመናውያን ትምህርት ቤቶች እዩተማሩ መውጣት ከጀመሩ በሁዋላ እንኩዋ ፣ ካዲስ አበባና ካንዳንድ ከተሞች ተርፈው ፣ በዩስራው ክፍል ሰፊውን ገጠር ለማዳ

@OLDBOOKSPDF

ረስ ሊበቁ አልቻሉም። በዮሐንስ ከራም ቢሆን በስልጣን ላይ ከቆዩት ጥንታውያን ያስተዳደርና የፍርድ ባለስልጣኖች ስር መስራት ስለ ነበረባቸውና ፣ በሁለቱ ወገኖች መሀከል አለመግባባት ስለ ነበረ ፣ የኢትዮጵያ የልማት እርምጃ ተስፋ እንደ ተደረገው ሊፋጠን አልቻለም።

ጥንታውያኑ ባለስልጣኖች ፣ የፈረንጆችን ጥበብ ብቻ ሳይሆን የፈረንጅን ያስተዳደርና የኑሮ ስራት ወዳገራቸው ማስገባታቸውና ህዝቡ የራሱን የኑሮ ልማድ እዬተወ አዲሱን እንዲከተል ማደፋፈራቸው ፣ ውሎ አድሮ ለስልጣናቸው ተጻራሪ የሚሆን ሁኔታ ሊያስከትል እንደ ሚችል ያስተዋሉ አይመስልም ። የዚያ ጊዜ እምነታቸው ፣ በጠቅላላው የፈረንጅ ትምህርት ፣ ማለት ጥበቡም ሆነ የኑሮ ስራቱ ፣ ስልጠናቸውንና እንዲሁም ሊነኩ የማይገባቸውን ስራቶች ሳይነካ ፣ ወደ ጎን ትቶ ፣ ላገራቸው ሀብትን ፣ ለነሱ ኀናንነትን የሚሰጥ ብቻ ይሆናል የሚል እምነት የነበራቸው ይመስላል ።

ከሌላ ወገን ወደ ፈረንጅ አገር እዬተላኩ ተምረው ከሚመለሱት ሌላ፣ አዲስ በገባው ባእድ ስራተ-ማህበር ውስጥ በዬከተማው ከተከፈቱት ዘመናውያን ትምህርት ቤቶች እዬተማሩ የሚወጡት ወጣቶች ፣ ስላገራቸው ተምረው የሚያውቁበት ፣ በምንም መልክ ተሰናድቶ የሚቀርብላቸው ነገር አልነበረም ። እንዲሁም ስላገራቸው ራሳቸው ደህና ሆነው ተሰናድተው የሚያስተምሩዋቸው መምህራን አልነበሩዋቸውም ። በዬገቡበት ትምህርት ቤት የሚማሩት ፣ እጅግ አስፈላጊዎች ከሆኑት ፣ ከፍተኛ ትምህርቶች ጀምሮ እስከ ዝቅተኞች ፣ ለምሳሌ እንደ ያለባበስ ፣ ያበላል ፣ የጭዋታና በጠቅላላው የኑሮ ልማድ እስከሉት ድረስ ፣ በባእዱ ትምህርት ቤት እጅ የሚቀርብላቸውን ነበር ። ስለዚህ ስላገራቸው እንዲማሩ በምንም መልክ ተሰናድቶ የሚቀርብላቸው ነገር አለመኖሩና ፣ ኢትዮጵያውያን አስተማሪዎች ሳይቀሩ ስለ ኢትዮጵያ በማስተማር ፈንታ ፣ ስለ ፈረንጅ አገር የሚያስተምሩዋቸው ፣ "ኢትዮጵያ ሊማሩት የሚገባ ነገር ምንም ባይኖራት ነው" ብለው ሲያምኑ ይችላሉ ፣ ቢያምኑም አይፈረድባቸውም ። ስለዚህ ወጣቶች መጀመሪያ ከዘመናዊው ትምህርት ቤት አዲሱን ትምህርትና ጥበቡን ከባእዱ የኑሮ ስራት ጋር ተምረው እንደ ወጡ ፣ ከብዙ ሚሊዮን ህዝብ መሀከል ፣ ዘመናዊውን ትምህርት የመማር እድል ማግኘታቸውን ለሕዝባቸው ሀጥርያት ለመሆን እንደ ተጠሩ ቆጥረውት ፣ በፍጹም ያገርና የወገን ፍቅር ፣ የተማሩትን ላልተማረው ወገናቸው ለማካፈል ተሰና

@OLDBOOKSPDF

ድቃው በየትመደበቡት ቦታ ይገራሉ ። እዚያ የማያውቁት ፣ ያላ ለበት ፣ እንዲያውም ያልጠረጠሩት ፣ በጽኑ እምነት ላይ የተመሠረተ ያለ ተባለበ ፣ ያሰራርና የኑሮ ፣ ወዘተርፈ . . . ሰራት ይገጥማቸውና ፣ ያሳብም የምንትም መታወክ ይፈጠርባቸዋል ። ይሁን እንጂ ከትምህርት ቤት ሲወጡ የነበራቸውን እምነት ተከትለው ፣ ወደ ግባቸው ለመድረስ መጣጣራቸው አይቀርም ። ገር ግን ወደዚያ ግብ ለመድረስ የያንዳን ዳቸው ሙከራ ፣ ወይም ትግል እንደየመንፈሳቸው ብርታትና ድካም ነው ። እንዳንዶቹ ፣ ትንሽ ካንገራገሩ በሁዋላ ፣ የጠቅላላውን ህዝብ ስሜት ደጀን አድርጎ የሚቃወማቸውን ሀይል መጋፋት የማያዛልቃቸው መሆኑን ሲያዩ ፣ የቆዩውን ስራት ጠልቀው ባያወቁትም ፣ በሱ ከሚያምኑት ባለስልጣኖች ካልተስማሙ መኖር እንደማይችሉ በመረዳት ፣ ተስማምተው ለመስራት እርቅ-ሰላም ያደርጋሉ ። ሌሎች ፣ እንዲያውም አዝማሚያውን አይተው ባለስልጣኖች አስቀድመው እንዳቀዱት ፣ በዘመናዊ ትምህርት የተባሉ አእምሮዋቸውን ለነሱ መሳሪያ እንዲሆን በሙሉ ፈቃደኝነት ይሰጡታል ። እሁንም ሌሎች ፣ ከዘመናውያን ጋር ጥንታውያንን የሚነቅፉ ፣ ከጥንታውያን ጋር ዘመናውያንን የሚነቅፉ ፣ በሴት ወፎች በፈር የሴት ወፎችን ፣ ባይጦች በፈር አይጦችን ለመምሰል ፣ መልካቸውን እየለዋወጡ የሚያሳዩ አይጠፉም ። በዚህ ታሪክ አይነተኞች ተሜዎችች አድርጌ እንዳቀረብሁዋቸው ፣ እንደ ጥላ ሁንና እንደ ሰፊያ ያሉት ቅኖች ፣ መንፈስ ጠንካሮችና አላሚዎች ደግሞ እንሱ ከተማሩት የኑሮ ስራት ሌላ ፣ ያገራቸውን ህዝብ ከተያዘበት የድህነትና የድንቁርና በሽታ የሚያድነው መድሀኒት እንደሌለ በፍጹም ልብ አምነው ፣ ያን እምነት በመከተል ፣ እስከ መጨረሻው ድረስ ወገናቸውን ለመርዳት የሚያደርጉት ጥረት ሁሉ ወዳቀዱት የተቀደሰ ግብ በማድረስ ፈንታ ፣ ካንዱ ችግር ሲወጡ ወደ ባሰ ችግር እየመራ ሲያገባቸው ይታያል ።

እንግዲህ ፣ ለማጠቃለል ያክል ፣ ቀደም ብሎ እንደ ተመለከተው ፣ ታሪካችን መጀመሪያ ለማሳዩት የሚሞክረው ፣ ወይም የመጀመሪያ አላማው ፣ ካንድ ወገን የኢትዮጵያ ባለስልጣኖች አገራቸውን እፋ ጥኖ ፈረንጆች በደረሱበት የልማት ደረጃ ለማድረስ በመመኘት ያልተሰናዱበት ፣ የማያውቁት ባእድ ስራት አግብተው ፣ በግብር ጥንታዊውን ያሰራር ልማድ እንከተል ሲሉ ፣ ከሌላ ወገን ፣ ስለ ፈረንጆች ማህበር እንጂ ስላገራቸው ምንም ትምህርት ከማይሰጥባቸው ትምህርት ቤቶች ተምረው የሚወጡ ወጣቶች ፣ ያን ተምረው ያወቁትን

@OLDBOOKSPDF

ባእድ ስራት ላልተማረው ወገናቸው ለማካፈል ሲፈልጉ ፣ በሁለቱ ወገኖች መሀከል ያለውን አለመግባባትና ከዚያም የተነሳ የሚፈጠረውን ግጭት ነው ።

መቸም ፣ ማናቸውም ስራተ-ማህበር መጀመሪያ ሲሰራ በነበረበት እንዳለ የሚቀር ፣ የማይለወጥ ፣ ወይም የማይሻሻል ሊሆን እንደማይችል የታወቀ ነው ። ነገር ግን አዲሱ ስራት ለጥንታውያኑ እንግዳ እንዳይ ሆን ፣ ጥንታዊው ስራት ላዲሱ ትውልድ እንግዳ እንዳይሆን ፣ ከውጭ የመጣው እቤት ከቆዬው ስራት ጋር በሚስማሙበት መንገድ ተዛ ምደው ፣ ተዋህደው ፣ ለውጡ ከውስጥ እንዲፈጠር ፣ አዲሱ ስራት ከጥ ንታዊው ስራት ከስጋው ስጋ ፣ ከነፍሱ ነፍስ ኑሶ (ተቀብሎ) እንዲ ወለድ ያስፈልጋል ።

የወንጀለኛው ዳኛ ሁለተኛ አላማው ፣ እንደ መልካም አስተናጋ ጆች ሁሉ ፣ የሚያስተናግዳቸውን (አንባቢዎቹን) የአርባ ዘጠኝ ምእ ራፍ ረዥም ጉዞዋቸው እንዳይቸካቸው ፣ ልዩ ልዩ ታሪክና ልዩ ልዩ ወሬ እያለዋወጠ ፣ እያጫወተ ደስ ሊማሰኝት መሞከር ስለ ሆነ ፣ ይህ ሙከራው የተሳካ ውጤት እንዲኖረው ተስፋ አደርጋለሁ ።

በመጨረሻ እዚህ ላይ ማስታወስ የምወደው ፣ "ፍቅር እስከ መቃ ብር" በተባለው መጽሀፌ ፣ ያማርኛን ፊደሎች ለመቀነስና ባንድ አይ ነት የሚጸፉትን ፣ "አድራጊንና ተደራጊን" የሚያመለክቱ ቃላት ለመ ለዩት ፣ ተደራጊውን በሚያመለክተው ቃል ላይ የማጥበቂያ ምልክት እንዲደረግበት አቅርቤው የነበረውን አሳብ ነው ። ያን አሳብ እዩን ቀና የጻፉ በርከት ያሉ ቢሆኑም ፣ "የተለመዱትን ፊደሎች ማስቀረ ትና የተለመደውን ያጻጻፍ ስራት መለወጥ አይገባም" ከማለት በቀር ፣ እኔ እስከማስታውሰው ድረስ ፣ ሌላ የሚያጠግብ ምክናያት ያቀረቡ ያሉ አይመስለኝም ። ስለዚህ ፣ በዚህ መጽሀፍም ፣ "በፍቅር እስከ መቃ ብር" ያቀረብሁትን አሳብ ተከትዬ ፣ ካንድ በላይ ከሆኑት ባላንድ ድምጽ ፊደሎች ፣ አንዳንዱን ብቻ ይዤ የቀሩትን ጥያቸዋለሁ ። ሁለተኛ እንደ "ኋ ቧ ሯ ቧ ሟ ቷ ኗ" ያሉትንና እነሱን የመሳሰሉትን "ዲቃላ" ፊደሎች ሁሉ ፣ እንዲሁም እንደ "ጕ ቊ ኵ ኰ" ያሉትን ጎዶሎ ፊደሎች ከነርባታቸው ጥያቸዋለሁ ። ከዚህ ሌላ ፣ ባንድ አይነት ተጽፈው አድራጊና ተደራጊ ፣ ወይም ባለሁለት ትርጉም የሆኑትን ቃላት፣ አድራጊውን ከተደራጊው ፣ አንዱን ትርጉም ከሌላው ፣ በማጥበቂያ

ምልክት ለመለየት [illegible] ወይም 'አያያዥ' የሚባለውን የዜማ ምል ክት (-)ወይም ነጥብ በሚጠብቀው ፊደል ራስጌ እንዲሆን አድርጊያለሁ ።

@OLDBOOKSPDF

እንዲሁም ፣ ካንድ ቃል ፊደሎች ውስጥ ፡ « ውሂጥ » ፊደል ሲኖር ፣ ይህ የማጥበቂያ ምልክት በዚያ ፡ "ውሂጥ" ፊደል ምትክ እዬ ሆነ ፣ ተከታዩን ፊደል የሚያጠብቅ ይሆናል ። ለምሳሌ ፡ "ይዘልላል" "ይዘላል" "ል" "ውሂጥ" "ይበርራል" "ይበራል" "ር" "ውሂጥ" "ይፈዝዛል" "ይፈዛል" "ዝ" "ውሂጥ" "ይፈስሳል" "ይፈሳል" "ስ" "ውሂጥ"

@OLDBOOKSPDF

## ምእራፍ ፩

# ከወዳጅ ጠላት ያድን !

ሶፊያ ሙላትና ጥላሁን ፊይሳ ተጣልተው ከተለያዩ ፣ አምስት ቀን አልፎዋቸው ነበር ። በስድስተኛው ቀን ፣ ሲመጣ በመስኮት ስላ ዩችው ፣ ልብዋ ወራሪ እንደ ገባው መሽበር ፣ አካብዋ የሚሄድበትን ሳያውቅ ወዲያና ወዲህ መሮጥ ሲጀምር ፣ ሆን ብላ ሳይሆን ፣ እንዲሁ የቤትንት ደመ-ነፍስዋ ስለ ገፋት ብቻ ፣ ቶሎ ተነስታ ፊትዋን ማባበስ ፣ ጠጉርዋን ማስተካከልና አልጋዋን በቅጥ በቅጥ ማድረግ ጀመረች። ነገር ግን ፣ አንዱን እንኳ ደህና አድርጋ ለማጠናቀቅ ጊዜ ሳታገኝ በሩን መላልሶ ስለ መታ ፣ ሁሉንም ትወችና ፣ ትንሽ ቆም ብላ ፣ መሸ በርዋን እንዳያውቅባት ፣ ጸጥ ያለች መስላ ለመታየት ፣ የምትለውንና የምታደርገውን ስታስብ ቆይታ ፣ በርጋታ ሂዳ ስትከፍትለት ፣ የጅና የቃል ሰላምታ ብቻ ሰጥቶዋት ገባ ።

ሶፊያ ልብዋ ያልተሸበረ ፣ መንፈስዋ ያልተቸገረ መስላ ለመታ የት ፣ ጥላሁን ሲገባ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲተዋወቅ እንደ መጣ እንግዳ ሰላምታውን በትህትና መልሳ ፣ ፊትዋን የውሸት ፈገግታ አልብሳ ፣ ከሚያውቃት ሶፊያ ሌላ ሆና ተቀበለችው ። ብቻ ፣ የትህትና ሰላምታ ፣ የውሸት ፈገግታ ፣ ወይም በጠቅላላው ያልሆኑትን መምሰል ፣ ለማ ያውቅ እንደሆን እንጂ ለሚያውቅ አያገለግልም ። የሚያውቅ መቸም ያውቃል ! ይልቁንም ሶፊያ ያንለት የነበረችበት ሁኔታ ፣ እንኩዋንስ ደህና አድርጎ ለሚያውቃት ለጥላሁን ፣ አንድ ቀን አይቶዋት ለማ ያውቅ እንግዳም ቢሆን ፣ ያ ሁሉ የትህትና ሰላምታ ፣ ያ ሁሉ የግድ ፈገግታ ፣ ውሸት መሆኑን ይመሰክራል ። አይኖችዋ ካባበጡ መክደ ኖዎቻቸው መሀል ፣ እንደ ተላጠ ሽንኩርት ሶረን ሆነው ፣ ያፍን ጫዋ ጫፍ ተመቶ እንዳጎረበ ቀልቶ ፣ ፊትዋ ያለመጠን ተንሳቁሎ ስትታይ ፣ ስታለቅስ የሰነበተች መሆንዋ ይታወቃል ።

ጥላሁን እንዲያ ተጎሳቁላ ፣ እንዲያ ተለውጣ ሲያያት ፣ ድንገጠ፣ የመጣለት ጉዳይ ፣ ሲያስበው ፣ ሲያጠናው የሰነበተው ጉዳይ ጠፋውና ፣ ገብቶ በቆመበት እንዳለ ፣ የቤቱን ወርድና ቁመት ለመስፈር እንደ መጣ ሁሉ ፣ አይኖቹን ላይና ታች ፣ ቀኝና ግራ እያዘዋወረ ፣ ዝም ብሎ ግራና ግድግዳውን ይመለከት ጀመር ።

@OLDBOOKSPDF

"አትቀመጥም ? ይሄው ወንበርኮ አለ" አለች ሶፊያ ፊትዋ የውሸት ፈገግታውን እንደ ለበሰ፣ ወንበሩን ካሌጋው አጠገብ ትንሽ ሳብ አድርጋ እያስቀመጠች ። አይኖችዋ እሱን ለማየት ፣ እሱዋ እንዳያዩ ለመከልከል ይታገሉ ነበር ።

"እግዚአብሄር ይስጥልኝ " አለ ጥላሁን ፣ ትንሽ እንደ መስገድ ብሎ እወንበሩ ላይ ሲቀመጥ ። ከዚያ እሱዋ የሚለውን ለመስማት፣ እሱ የሚለውን የሚጀምርበት ቃል በመፈለግ ፣ ዝም ብለው እመርዶ ቤት እንደ ተቀመጡ አንገታቸውን ደፍተው ዘለግ ያለ ጊዜ ከቆዩ በሁዋላ ፣

"ሶፊ" አለ ፣ አንገቱን እንደ ደፋ መሬት መሬት እያዩ ። "ሶፊ ዛሬ ሁለት ነገሮች .....ልለምንሽ ነው የመጣሁ ። አንዱ መሰንበቻውን ስናገረውም ፣ ሳደርገውም ለሰንበትሁት ይቅርታ እንድታደርጊልኝ ነው ። በተለይ በመጨረሻው ቀን - የነገ ሳምንት መሆኑ ነው መሰለኝ - የተናገርሁትን ምን ሰይጣን ባፌ እንዳስቀመጠው ሳላውቅ ካፌ ከወጣ በሁዋላ ጆሮዎቼ ሰሙት እንጂ አስቤ የተናገርሁት እደለም ። ያንለት የተናገርሁት ስላንች ካለኝ አሳብና ስሜት ጋር እንደ ማይቀራረብ እንቺም ታውቂያለሽ ። ሁለተኛው ...." አለ ጥላሁን በሻከረ ድምጽ፣ አንገቱን ከደፋበት ቀና አድርጎ እሱዋን እያየ ። "ሁለተኛው ፣ ትምህርታችንን እንደ ጨረስን ልንጋባ ወስነን ስለ ነበረው ነው። ስለሱ አሳብሽን ለወጥሽ ? አሳብሽን ለውጠሽ እንደሆን ግልጥ አድርገሽ. . . እንድትነግሪኝ ነው።" ሶፊያ አንገትዋን እንደ ደፋች መሬት መሬት እያዩች ዝም አለች ።

" ተናገሪ እንጂ " አለ ጥላሁን፣ መሬቱን በግርዋ እዬቆረቆረች ዝም በላለች ።

"ምን ልናገር" አለች ፣ እንባ ያንሳቀለው ፊትዋ የውሸት ፈገግታውን እንደ ለበሰና አንገትዋን ደፍታ እንደ ተቀመጠች ።

"በተናገርሁትም ሆነ ባደረግሁት በላስቀየምሁሽ ይቅርታ እንድ ታደርጊልኝና ስለ ጋብቻችን አሳብሽን ለውጠሽ . . . . እንደሆነ እንድ ትነግሪኝ ለመንሁሽኮ !!"

"ይቅርታ አድርጊልኝ" ያልከው . . እንዲያው ነው ። የኔ ይቅር ማለት ምን ሊያደርግልህ ? ይቅር አለማለቴስ ምን ሊጎዳህ ? ስለዚህ . . . እሱን ተወው ። ሌላው . . ." አለችና አሁንም አንገትዋን ደፍታ ዝም አለች ።

@OLDBOOKSPDF

"ሴላዉ ፣ ምን ፣ ተናገሪ እንጂ!"

"... ሀ ፣ እሁ ማለት ያማረው 'እሁ ያለ ማነው' እለ ይባ ባል ፣ አሳብህን መለወጥ ስትፈልግ ጊዜ እኔን 'አሳብሽን ለውጪ እንደሆን ንገሪኝ' ትለኛለህ ! አንተ አሳብህን ለመለወጥ መፈለግህን አውቄዋለሁ ፣ ሰምቻለሁ ! ስለዚህ ለምን ምክናያቱን በኔ ለማድረግ ትፈልጋለህ ? ለምን ሌላ ለማግባት መፈለግህን ግልጥ አድርገህ አት ናገርም ? ወይ... ወዶ መጥላት ባ - ባንት አልተጀመረም ፣ የነበረ ነው" አለች ሶፊያ ፣ ልቅሶዋን ለመዋጥ እያታገለች ። "ብቻ የጠላ ሰው ሌላ የወደደ ሰው 'በቃሽኝ ፣ ሌላ ወድ .. ወድጃለሁ' ይላል እንጂ ፣ እንዲህ እንዳንተ በሰው ንፍስ አይ... አይጫወትም ! እንዲህ እንዳ ንተ 'ነይ' ብሎ ጠርቶ ወሻ ይመስል 'ሂጅ ወዲያ' አያለ አያባርርም ሉብም እንዲህ በንፍሴ ትጫወታለህ ?" አለችና ትንፋሽ እስኪያጥራት ስቅቅ ብላ ታለቅስ ጀመር ።

እውነተኛ ስሜት እንደ ተዳፈነ እሳት ለመቀጣጠል ትንሽ ይበቃ ዋል ፣ እውነተኛ ስሜት እንደ ተዳፈነ እሳት ቆስቁሰው ካቀጣጠሉትግ እንዳይታይ መሸፈን አይቻልም ! ሶፊያ ትምህርት ቤት ሲዘጋ ለእረ ፍት ሀረር ሄዳ በቆዩችበት ፣ ጥላሁን ሌላ ቤት መውደዱን ሰምታ ነበረ ። ሁኖላ ፣ የሱ አመል መለወጥ ፣ ሲያያት መቅበጥበጡ ፣ መበሳ ጨቱ ፣ በትንናኙ ቁጥር ጥል መጫሩና መሳደቡ ፣ በመጨረሻ ፣ እንዲ ያውም በስልክ ጠርቶዋት ብትሄድ መልሶ ፣ "ወጭ አልፈልግሽም" ብሎ ማባረሩ ፣ ይህ ሁሉ የሰማችው ወሬ እውነት መሆኑን የሚያረ ጋግጥ መስሎ ተሰማት ። ስለዚህ እምነትዋን ፣ ምኞትዋን ፣ ተስ ፋዋን ፣ ደስታዋን ከመሰረተችበት ከጥላሁን በመለዩትዋ ፣ እሱን በማ ጣትዋ ፣ ፍጹም ባዶነት ተሰምቶዋት ፣ ከታች የምትረግጠው ፣ ከላይ የምትጨብጠው አጥታ ፣ ግራ ገብትዋት እዩተሰቃዩችና እዩተጨ ነቀች ፣ ቤትዋን ዘግታ ስታለቅስ ነበር የሰነበተች ። ነገር ግን ፣ ድን ገት ሲመጣ ስታየው ፣ እንዲያ ግራ የገባት መሆንዋን ፣ እንዲያ መሰቃ የትዋን ፣ ለሱ ማሳዩት የሴትነት ኩራትዋ አልፈቅድላት ስላለ ፣ እው ነተኛ ስሜትዋን ትህትና በበዛበት ግብዝ ሰላምታና በውሸት ፈገግታ ለመሸፈን ሞክራ ነበር ። ታዲያ ገብቶ ትንሽ እንደ ቆዩ ፣ ለሰነበተች በት ጨካኝ ስቃይ ምክንያት የሆነውን ነገር ሲያነሳባት ፣ የቆሰለ ልብ ዋን ሲነካካባት ፣ የፈጠረችው የውሸት ዘዴ ሁሉ እውነተኛ ስሜት ዋን ለመሸፈን ፣ ለማዳፈን ሊበቃ አልቻለም ! ለመናገር ብትፈልግ ሳግ እያደናቀፋቸው ለዩብቻ ተለያይተው ከፍና የሚወጡት ቃሎች

@OLDBOOKSPDF

ሲያያዙና እሳብዎ ሊገልጹ አልቻሉ ፤ ስሜትዎን ፤ ጭንቀትዎን በቃል ፈንታ ዝም ብላ በመረር ልቅሶ ፤ በንባ ትገልጽ ጀመረች፤ እውነት ነው ፤ የልብን አዘን ፤ ጭንቀትን ቃል ሁሉ ቢሰበሰብ የንባን ያክል ፤ የሳግን ያክል ሊገልጽ አይችልም !

እንዲያ ስቅቅ ብላ ስታለቅስ ሲያያት ፤ ጥላሁንን ግራ ገባው ። ‘ያን ያክል የሚያስለቅሳት ምንድነው ? የሰማው ወሬ እሰት ይሆን ? አዮ . . እሱማ እንዴት እሰት ይሆናል ? ከማይጠረጥረው ጉዋደኛው የሰማው ከመሆኑስ ሌላ ፤ የጽሁፍ ማስረጃ በጁ ይዞ የለ ? እሱስ እውነት ነው ! ሀረር ለእረፍት ሄዶ በቆዩችበት ፤ አባትዋ የሀብታም ጉዋደኛቸውን ፤ ያቶ ሲሳይን ልጅ ፤ ደምሴን እንድታገባ በማባበልም ፤ “ እረግምሻለሁ” ብለው በማስፈራራትም እሺ እሰኝተዋት ነገሩ ያለቀ፤ የደቀቀ መሆኑ የማይጠረጠር ነው ! ታዲያ ይህ ሁሉ ለቅሶ ምን ይባላል ? ስትሰጠው የኖረችውን ቃል ፤ ስትሰጠው የኖረችውን ተስፋ ሁሉ አብላ ፤ እምነትዋን እጉድላ የሀብታም ልጅ ፈልጋ ከሄደች በሁዋላ ፤ በገንዘብ ከሰወጠችው በሁዋላ ፤ ይህ ሁሉ ልቅሶ ምን ይባላል? እንዲያው ግብዝነት ነው ! “የሴቶች እንባ ‘ና’ ሲሉት የሚመጣ ፤ ‘ሂድ’ ሲሉት የሚሄድ ፤ ታዛዥ ሎሌያቸው ፤ አጫዋች ሎሌያቸው ነው” እንደሚሉት ሆኖ ነው እንጂ ፤ እውነት ይህ ሁሉ እንባ ካዘነ ልብ የሚፈስ ቢሆን ኖሮ ፤ ይህን ሁሉ እንባ ያፈሰሰ ልብ ደርቆ በተቃጠለ ነበር !

ጥላሁን በሌላ ሰው መለወጡ ፤ ክብሩ መነካቱና ፍቅሩን መቆጣቱ ልቡን አሻክሮት ፤ ስሜቱን እምርሮት ፤ እስዋ ስታለቅስ አይናቿን ሳያረግብ በላይዋ ተክሎ በውስጡ የሚሙዋገቱትን ተቃራኒ አሳቦች ሲያዳምጥ ቆይቶ ፤ አሳቡን እንደገና አይኖቹ ወደ ተተከሉበት መልሶ ሁኔታዋን ሲያይ አሳዘነችው ። ብቻ ምን ያድርግ ? እንደ ድሮው ቢሆን ፤ እንዲያ ባለው ልቅሶ ፍቁን መድሀኒት ነበረው ! ያንለት ግን እንዲያ ያለውን መድሀኒት ሊያደርግ አይችልም ፤ ቢያደርግም የሚሰምር አልመሰለውም ! ድሮ በማይረባ ነገር እንዲሁ “ውሀ ቀጠነ ፤ ከሰል ጠቆረ” ብላ ስታለቅስ እንደ ትንሽ ህጻን እቅፍ አድርጎ ያነሳና እደረቱ ላይ ጥሎ እዩደባበሰ ፤ ራስዋን ፤ ፊትዋን ፤ አንገትዋን ሁሉ እዩሳሳመ ሲያባብላት ወዲያው ትመለስ ነበር ። እዚያ እንደ ተኛች ፤ በደረቱ ለፋትና ምቾት ፤ እቅፍ ፤ ድግፍ አድርገው በያዝዋት ክንዶቹ ብርታት ስትደነቅ ፤ እሩ በሚዳብሳቸው ሀዋሳትዋ የሚያስተላልፈው የፍቅር መልእክት ልብዎን በደስታ ሲያዘምረው ፤ በተ

መስጦ ፤ በእንክር@OLDBOOKSPDFውም ፤ የልቅሶው ምክንያትም ጨርሰው ይረሱና ፡ "አንተን ብቻ እወዳለሁ ፤ አንተን ብቻ አምና ለሁ ፤ አንተን ብቻ አመልካለሁ ፤ አሜን !" ብላ ተናዛ ፣ ታሳርጋለች ። ከዚያ እንዳላከረፈች ፣ እንዳላለቀሰች ፣ ምንም ምን እንዳልሆነ ሁሉ ልፊያው ፣ ጭዋታው ፣ ደስታው ይቀጥል ነበር ! ያንለት ግን እንዲያ እንዳያደርግ እሱን ከድታ ሌላ ሰው የመውደድዋ አሳብ የሾህ አጥር ሆኖ እንዳይቀርባት ከለከለው ። ዝም ብሎ እንዳይተዋትም ምንም ብት ከዳው ፣ ምንም ሌላ ብትወድ ከልቡ ሊያወጣት ፣ ሊጠላት አል ቻለም ። ስለዚህ ፣ ልቅሶዋ እዩጸና ሲሄድ አሙዋምቶ የሚጨርሳት ስለ መሰለው ፣ ከሚያውቀው ፣ ከለመደው ሌላ ፣ ልቅሶዋን የምትቶ ውብት ፣ ጸጥ የምትልበት ዘዴ ባባቡ እዩፈለገ ዝም ብሎ ይመለከታት ነበር ።

"እውነት ቢሆን ነው !" አለች ሶፊያ ባሳብዋ ፤ አልቅሳ ከደከ መች በሁዋላ አእምሮዋ ትንሽ ማሰብ ሲጀምር ። አመሉ ከመክፋቱ ፣ ከመለወጡ ሌላ ያን ያክል ስታለቅስ እፊትዋ ቆሞ በግዴለሽነት የሚ ያያት ፣ የሰማችው ወሬ ርግጥ ቢሆን ነው ! ድሮ ያን ያክል ስታለቅስ ይቅርና ፣ እሰዋ እጥፍታ ስታኮርፍ እንኩዋ አቅፎ እዩደባበሰ ፣ ፊት ዋን ሁሉ እየሳመ ያባብላት ፣ ምህረት ይለምናት የነበረው ፣ ያን ለት ያን ያክል የምታጎርፈው እንባ እንዳለች ደንጋይ የተደፈነ ልቡን ትንሽ ዘልቆ አልነካው ያለ ፣ እንዲያ መናገር እስኪያቅታት ላግ ሲያ ንገላታት የተኛ ስሜቱ ትንሽ አልንቀሳቀስ ያለ እንደ ሰማችው ፣ የም ታምናት ጉዋደኛዋ እንደ ነገረቻት ፣ ሌላ ልጅ ፣ የሽመቤት እስታጥቄ የምትባለዋን ልጅ ወዶ ፣ እስዋን ለማጨት ስለ ወሰነ ነው !

ከልቅሶዋ በሁዋላ ፣ የጥላሁን ጨርሶ መለወጥ የሰማችውን ወሬ የሚያረጋግጥ መሆኑን ባሳብዋ ስታሰላስል ቆይታ ፣ ምንም ልብዋ ባይስማማ ግንኙነታቸው እንዳለቀ አድርጋ ፣ ግንኙነታቸው ያለቀ አስመስላ ለመናገር አሰበች ።

ከዚያ ሰአትዋን አዩችና ፣ መሀረብዋን ከቦርሳዋ አውጥታ ፊት ዋንም ፣ አይኖችዋንም ፣ ጠራርጋ ካደረቀች በሁዋላ ፣

"፫ ምስት ሰአት ቀጠሮ ስላለኝ አሁን ልሄድ ነው ፤ እንግዲህ አንተም ብትሄድ . . . ይሻላል " አለች ፣ እያመነታች ።

"መሄዱንስ . . . እሺ እሄዳለሁ ፤ ብቻ ለለመንሁሽ ሖልስ አልሰ ጠሽኝምኮ !"

"ለምኑ ?"

@OLDBOOKSPDF

« በላሳዘንሁሽ ይቅርታ እንድታደርጊልኝና ስለ ጋብቻችን ቁርጡን እንድትነግሪኝ ለምኘሽ ነበር ።”

“ሳለቀ ነገር ሁሉስ ምን ያደርጋል ? አሁን ሁሉም አልቆዋል ፤ ስለዚህ . . . ብንተወው ይሻላል ።”

“እም ፤ ሁሉም አልቆዋል ! እንዲህ ከቃልሽ ልሰማው ብዬ ነው እንጂ ማለቁን አውቄያለሁ ፤ ሰምቻለሁ ። ደግ ነው ይለቅ ፤ ግዴለም . . . . ይለቅ” አለ ጥላሁን ፤ በሻከረ ድምጽ ።

“ሶፊ” አለ ፣ እንደ ገና እንገቱን ወደሰዋ ቀና አድርጎ ሁለቱም መሬት መሬት እያዩ ሲያስቡ ከቆዩ በሁዋላ ። ‘ሶፊ’ መቸም ያንቺና የኔ ነገር ‘አልቆዋል’ ብለሻል ፤ ደግ ነው ይለቅ ። እኔ አንቺን የምወድብት ልብ ቢኖረኝ እንቺ እኔን እንድትወጂኝ የማደርግበት ምንም ነገር ስለሌለኝ ፣ የኔ መውደድ ብቻ ባልና ሚሽት አድርጎን ሊኖር አይችልምና ግዴለም . . . ይለቅ ። ብቻ ሲያልቅ ፣ ስንለያይ ፣ የምን ለያይበትን ምክናያት ሁለታችንም ጥርት አድርገን አውቀነው እንለ ያይ ። ቅድም ስትናገሪ እንደ ሰማሁሽ ፣ እኔን ለመተው የወሰንሽበት ምክናያት ፣ እኔ ሌላ ሴት ወድጄ አንቺን . . . በመጥላቴ መሆኑን የተናገርሽ መሰለኝ ። ይህ የግፍ ድርብ ነው ፣ ሶፊ ! ከኔ የበለጠ የምትወጂው አጋጥሞሽ እሱን ለማግባት ብትፈልጊ ፣ ቁዋው ለመቆጥ የሚመር ፣ አዘኑ ለመሸከም የሚያስቸግር ቢሆንም ፣ ምክናያቱ ሊገባኝ ይችላል ! ነገር ግን . . . በህይወቴ እንኩዋንስ ካንቺ የበለጠ ያንቺን ያክል የምወደው ምንም እንደሌለ እያወቅሽ፣ ለኑሮዬ አለኝ ብዬ እምነቴን ፣ ደስታዬን ፣ ተስፋዬን ሁሉ የመሰረትሁበት ያንቺ ፍቅር መሆኑን እያወቅሽ፣ ይህን ሁሉ ከኔ ወሰድሽ ፣ ይህን ሁሉ ከኔ ቀምተሽ ለሌላ ሰው መስጠትሽ አንሶ፣ ደግሞ እንደገና ይህን ያደረግሽበት ምክናያት እኔ የማልታመን ፣ ከሀዲ ስለሆንሁ ለማስመሰል መሞከርሽ ፣ በውነት የግፍ ድርብ ነው ! አላስቀየምሁሽም አልልም ፤ አስቀይሜሻለሁ ። ብቻ እንዳስቀይምሽ ያደረገኝ የፍቅሬ ጽኑነት ነው ። ከደምሴ ሲሳይ ጋር ልትጋቡ ውል መጨረሳችሁን ከሰማሁበት ቀን ጀምሬ ያለሁት እኔ ፣ እኔ አይደለሁም ! አንቺን የማጣቱ ፣ አንቺን ከማጣቱ ጋር እምነቴ ፣ ደስታዬና ተስፋዬ ሁሉ ከንቱ ሆኖ የመቅረቱ አሳብ፣ በዚያ ላይ የቅናት ይሁን የጥቃት ፣ ወይም የፍራት ስሜት ተጨምሮ ባንድ ላይ በአእምሮዬ የፈጠረው ውሽንፍር በምናገረውና በማደርገው የማላዝዝ አድርጎኛል ። እንዲያ ባለሁኔታ ባለሁበት ጊዜ ፣ ለምናገረውም ሆነ ለማደርገው ባለቤት ባልሆንሁበት ጊዜ ነው ባነጋገሬና

@OLDBOOKSPDF

ባድራጎቴ ያሳዘንሁሽ ። ስለዚህ እንዲህ ላለው አድራጎቴ ፣ ቁጣዩን መግታት የማልችል አውሬ፣ ቀላል፣ ባለጌ በመሆኔ ንቀፊኝ ፤ ዝለፊኝ፤ ናቂኝ ! ነገር ግን ከሀዲ ያደለሁትን ከሀዲ አትበይኝ ።”

ጥላሁን ቀስ ብሎ ጀምሮ ፣ በተናገረ መጠን ሞቅ እያለው ስለ ሄደ ፣ ስሜቱ ገፋፍቶት፣ ለሰዋ ያለው ፍቅር ምን ያክል ሀያል መሆኑን መናዘዝ ሲጀምር፣ እሰዋም እሱን ትታ ሌላ ለማግባት የወሰነች ለመምሰል የውሸት ዘዴ ማሰናዳቱን ረስታ ፣ የመምሰል ጦርነቱን ትታ ፣ ድል የመሆን ፣ የመማረክ ምልክት ታሳይ ጀመር !

“ውሸ . . . ውሸትህን ነው ” አለች፣ እንደገና እንባዋ ጣምራ ጣምራ ሆና እዬረገፈና ሳግዋን ሰመዋጥ እዬታገለች ። “ አሁን እን ዳልኸው የም. . . የምትወደኝ ብትሆን ኖሮ ፣ እንዲህ አታ . . . አታደ ርገኝም ፤ እንዲህ አታ . . .አታንገላታኝም ነ. . . ነበር ! እንዲህ በው ሸት የምታታልለኝ ፣ የፈለግኸውን እስክታደርግ ነው ። ከ. . . .ከ. . . ከየሽመቤት አስታጥቂ ጋር ል . . ሊትጋቡ መጨረሳችሁን ሰ. . .ሰ. . ሰምቻለሁ ፤ ሰምቻለሁ ! ” አለችና ፊትዋን በሁለት እጆቹዋ ሸፍና፣ እልጋዋ ላይ ወድቃ፣ ትንፋሽዋ እስኪቆረጥ ስቅቅ ብላ ታለቅስ ጀመር።

“ምን ?” አለ ጥላሁን ፣ ሳያስበው ከተቀመጠበት እንደ ኩዋስ ነጥሮ ተነስቶ እየተንቀጠቀጠ ።

“ምን አልሽ ?” አለ፣ እንደገና ። ሶፊያ ልቅሶዋ አላናግራት ስላለ አልመለሰችለትም ። ፊትዋን በሁለት እጆችዋ ሸፍና ፣ አልጋ ላይ እንደ ወደቀች ልቅሶዋን ቀጠለች ።

“ እኔ ነኝ የሽመቤት አስታጥቂን ላግባ የጨረስሁ ? እንዲህ ያለ ውን ውሸት ማንም አልነገረሽ ! አንቺ የፈጠርሽው ነው ! ” አለ፣ አፉቱ ወድቃ ስታለቅስ እንደ ትንታግ በንዴት የቀሉ አይኖቹን ዘቅ ዝቆ በሰዋ ላይ ተክሎ ።

ሶፊያ ስታለቅስ ብዙ ቆይታ ትንሽ ስትረጋጋ ፣ ከወደቀችበት ተነስታ እንባዋንም፣ ሌላውንም ካይንዋና ከፍዋ በመሀረብዋ ትጠራ ርግ ጀመር ። አይኖችዋና ከንፈሮችዋ አብጠው ፣ በጠቅላላው ፊትዋ በንፋሎት የበሰለ ብርንዶ መስሎ ፣ ከጥቂት ጊዜ በፊት ከነበረችው ብርንዶ መስሎ ፣ ከጥቂት ጊዜ በፊት ከነበረችው ሌላ ሆነች ።

“ውሸት መፍጠሬ ለምን ብዬ ይሆን !” አለች ፊትዋን ወደሱ ስትመልስ አይንዋን እያባበሰች ።

@OLDBOOKSPDF

“ምን አውቃለሁ ! እኔን ጥጥሽ ሌላ ለማግባት ፣ ደምሴ ሲሳይን ለማግባት ምክንያት እንዲሆንሽ ይሆናል ! ለሱ ነው ! እንግዲያ እንዲህ ያለ ወሬ ፣ እንዲህ ያለ . . ምን ልበለው ? እንዲህ ያለ . . . ሰይጣን ካልሆነ በቀር ፣ ህሊና ያልተፈጠረበት ካልሆነ በቀር ሊያወራው የማይችል ውሸት የነገረሽ ካለ አታጋጥሚኝም ? በይ አሁን አጋጥሚኝ ! አጋጥሚኝና እውነት ሆኖ ከተገኘ ፣ ከዚያ በሁዋላ . . . ሰው አትበይኝ! ከዚያ በሁዋላ . . . እኔም ሰው ነኝ ብዬ ከሰው ጋር . . . አልኖርም ! ”

ሶፊያ ምንም እንኳ የጥላሁንን መከዳት ፣ አስከዳች የተባለችዋ ልጅ ከማስረጃ ጋር ከነገረቻት ፣ በጣም ከምታምናት ጉዋደኛዋ የሰማችው ቢሆንና ፣ የሱ አመል መለዋወጥ የሰማችውን ወሬ እውነት አስመስሎ የሚያሳይ ቢሆን ፣ ያ ወሬ ውሸት መሆኑን አፈትዋ ቆሞ እዬ ተንቀጠቀጠ ከብርቱ ስሜትና ምሬት ጋር ሲነግራት ፣ እሱን የበለጠ አመነች ።

የወደዱት መከዳት አለመከዳቱ ከስሜቱ ይታወቃል ! የወደዱት መከዳት አለመከዳቱን ብዙ ምስክሮች ምለው ከሚመሰክሩት ፣ ስሜቱ የሚመሰክረው የበለጠ ስለሚያስረዳ ፣ ከገባ ጀምሮ ከተናገረውም ሆነ ካደረገው ሁሉ የመንፈሱን ጭንቀትና የስሜቱን ሙቀት ተመልክታ ፣ ወዳጅዋ ፣ ምስጢረኛዋ ፣ ትድስት ይግዛው ከማስረጃ ጋር የነገረቻት ወሬ ውሸት መሆኑን ተረዳች ፤ አረጋገጠች ። ወዲያው የሰው ወሬ ሰምታ ስለ ጠረጠረችው ህሊናዋ በውስጥዋ ድምጹን ከፍ አድርጎ እዬ ጮኸ አስዋን ሲወቅስ ፣ ልብዋ ወሬ ነጋሪዋን ሲረግም ፣ አንገትዋን እንደ ደፋች ስታዳምጥ ቆይታ ቀና አለችና አይኖችዋ እዬተርገበ ገቡ ፣ ከንፈሮችዋና ጉንጮችዋ እዬተንቀጠቀጡ ዝም ብላ ትመለከተው ጀመር ። እኒያ የሚርገበገቡ አይኖችዋ ፣ እኒያ የሚንቀጠቀጡ ከንፈ ሮችዋና ጉንጮችዋ ፣ ልብዋ ይቅር ብሎ ይቅርታ የሚለምን መሆኑን የሚናገሩ ይመስሉ ነበር ! እንዲያ ባሏጋዋ ጫፍ እግሮችዋን ወደ መሬት ዘርግታ እንደ ተቀመጠች አንገትዋን ወደሱ አቃንታ ፣ አፍዋን ከፍታ ፣ አይኖችዋ እዬተርገበገቡና ከንፈሮችዋ እዬተንቀጠቀጡ ስቅ መለከተው ከተቀመጠችበት አፍሶ ፣ በደረቱ አቅፍ-ጭንቅ አድርጎ ይዞ ፣ ባፉ ሁለመናዋን እዬዳሰሰ ፣ ያ የሰንበተችበት የሚያስፈራራ ጭንቅ ፣ ያ ጨካኝ ጣእር እውነት አለመሆኑን ፣ ቅዠት መሆኑን ፣ ያለፈ የማይመለስ መሆኑን እንዲነግራት ፣ እንዲያረጋግጥላት የምት ለምን ትመስል ነበር ! ጥላሁን የፊትዋን መለወጥ ፣ የከንፈሮችዋንና የጉንጮችዋን መንቀጥቀጥ ሲያይ ፣ ልቡ እንደ መሸበር ብሎ ሲናገር

@OLDBOOKSPDF

ያለበው ጠፋውና ዝም ብሎ ቆሞ ይመለከታት ጀመር ። ሶፊያ ስትጠብቅ ብዙ ቆይታ ፣ እሱ ምንም አለመንቀሳቀሱን ስታይ በረዥሙ ተነፈሰችና “ ታዲያ . . . የሰማሁት እውነት ካልሆነ ፣ ውሸት ከሆነ ፣ ለምን እንዲህ . . . ተሰወ‍ጥህብኝ ? ለምን አመልህ እንዲህ . . . ከፋብኝ ? ለምን ለማየት እንኳ እንዲህ . . . ጠላኸኝ ?” አለች ፣ ለመስማት በሚያስቸግር ደካማ ድምጽ ።

“አልነገርሁሽም ? ነገርሁሽኮ ! ከደምሴ ሲሳይ ጋር ውል መዉረላችሁን ስሰማና . . . እውነት መሆኑን ከወረቀቱ ላይ ፣ ቢታ . . . አጸምሮየ ታጠከና ፣ ተበሳጨሁና በምናገረውም ፣ በማደርገውም ማዘዝ አቃተኝ ።”

“ማነው እንዲህ ያለ . . . ውሸት የነገረህ ?”

“የነገረኝ . . . ምን ያደርግልሻል ? ውሸት ከሆነ ውሸት ነው በቃ ።”

“ጠላትን ማወቅ አይጠቅምም ? አንተና እኔ እንድንለያይ ያልሆነውን ሆነ ብሎ ውሸት የሚያወራ ፣ ላንተም ለኔም ጠላታችን ነውኮ!” አለች ፣ በደካማ ድምጽ ። “ ደግሞስ . . . ወረቀት ያልኸው የምን ወረቀት ነው ?”

“ያውልሽ እንብቢው ” አለ ፣ አንድ በረዥሙ የተጻፈ ወረቀት ከኪሱ አውጥቶ ።

ሶፊያ ወረቀቱን ተቀብላ ግንባርዋን ቋጥር ፣ ፊታ እያደገረች ስታነብ ፣ በመጨረሻ የምትለውን ለመስማት ቸኩሎ ፣ ልቡ በሀይል እዬመታ ወዲያ ወዲህ ይንቀራጠጥ ነበር ።

“ነሐሴ 15 ቀን 19 . . . .

ለምወድህ ጉዋዴ ፣ ወንድ ይራድ አሰታጥቂ ፦

እንደምን አለህልኝ ? ያዲስ አበባን መንቻካ ዝናብና ብርድ እንዴት ዘለቅኸው ? እዚህ ሰው ሁሉ፣ ‘ የዘንድሮውን የመሰለ ጥሩ ክረምት አይተን አናውቅም’ እያለ ይደነቃል ። እኔም በራሴ ስሜት ይሁን ወይም ሰው እንደሚለው በክረምቱ ልዩነት ፣ ሀረርን እንደ ዘንድሮ ወድጄው አላውቅም ። ከዘነበ በሁዋላ ሁልጊዜ በጠቅላላው ያየሩም ሆነ የሰማዩ ጥራትና የጸሀይ ድምቀት እቤት መቀመጥ ስለማያስችልህ፣ እዬዞርህ የፍጥረትን ውበት እንድታደንቅ ያስገድድሀል ። ከከተማው ምእራብ ፣ አኮረብታው ላይ ወጥተህ ዙርያውን ስትመለከት ፣ መሬት

@OLDBOOKSPDF

በልዩ ልዩ የተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ቡቃዮች ለምልማ ፣ ተሸልማ ፣ እን ዳገሩ ሰው የዘንድሮን ልዩ ክረምት እያወደሰችና እያሞገሰች ስትዘምር የምትሰማ ይመስልህና ሳታስበው ፣ ሳታውቀው አንተንም ያካባቢው የደስታ ማእበል ጠርጎ ወስዶህ አብረህ ስትዘምር ፣ አብረህ ስትጨ ፍር ትገኛለህ ። ይገርማል ! 'ደስታም ሆነ ሀዘን እንደ ተስቦ በሽታ በንክኪ ይተላለፋል' የሚባለው ለካ ለዚህ ነው !

ክረምቱን ሁሉ ሶፊና እኔ ቁርስና ራት ካልሆነ ፣ ምሳ የሚባል ነገር አንድ ቀን አፋችንን ነክቶት አያውቅም ! ከቁርስ በሁዋላ ተያ ይዘን አንዳንድ ጊዜ ወደ ኮረብታው ፣ ሌላ ጊዜ ወደ ሜዳው እንሄ ድና እዚያ ንቦች ለማር ወለላቸው የሚፈልጉትን ካበባ ወዳበባ እዩዞሩ ሲቀስሙ ፣ ወፎች ምግባቸውን ከቀጥቋዋጦ ወደ ቀጥቋዋጦ እዩበረሩ ሲለቅሙ ፣ ብራብሮዎች በዩጉዋዳቸው እያረበረቡ ሲጨፍሩ ፣ ከነሱ ጋር እዩዞርን ፣ እዩበረርን ፣ እዩጨፈርን የሚያደርጉትን ሁሉ ስናይ ፣ ስናጠና እንቆይና ሲደክመን ፣ ክፍት ቦታ ፈልገን ሳር ይሁን አሸዋ ፣ ጉርብጥብጥ ይሁን ደልዳላ ሳንመርጥ ፣ እዚያ ጎን ለጎን ተጋድመን ንቦች ፣ ወፎችና ብራብሮዎች ሲያደርጉ ባዩነውና ባጠናነው ላይ መነ ጋገር ፣ መከራከር እንጀምራለን ። መቸም በክርክር ሶፊ እንደማት ቻል ታውቃለህ ። ትረታኛለች !

መጀመሪያ የሶፊና የኔ ጉዋደኝነት አፋዊ ብቻ ነበር ። ሁዋላ ሁዋላ ወደ ውስጥ እዩገባ ፣ እዩጠለቀ ሄደ ። በመሀከላችን የልብ ሙቀትና የመንፈስ ምጥቀት የሚሰጥ ውስጣዊ ጉዋደኝነት ተፈጠረ። እዚያው እንዳለን ዝናብ ሲመጣ የኔን ኮት የጋራ ለብሰን ፣ የጋራ ተከ ናንበን ፣ ተደጋግፈን ፣ ተቃቅፈን ፣ ካንድ ዛፍ ስር ፣ ወይም ካንድ ደንጋይ ጥግ እንደ ተቀመጥን ፣ መጀመሪያ የሰዋ ልብ የፍቅር ዳንኪራ እዩመታ ሲጨፍር የኔው ይሰማና ይከተላል ! ከዚያ እያንዳንዱ ያካ ላት ክፍላችን ፣ ሁለመናችን ፣ የልባችንን የፍቅር ቅኝት ተከትሎ አብሮ ሲጨፍር ፣ አብሮ እልል እያለ በደስታ ሲዘፍን ፣ በዙርያችን እንደ መዓት የሚወርደውን ዝናብ ሳናይ ፣ ከላያችን የሚነጉደውን ነጎድጉ ዋድ ሳንሰማ ፣ ዝናቡ በርቶ ፣ ሰማዩ ጠርቶ መሬቱ ደርቆ እናገኘዋ ለን ! እንዲህ ያለ ግሩም ነገር ገጥሞህ ያውቃል ? በዙርያህ ያለውንና የሚሆነውን ሁሉ እንዳታይ አይንህን የሚያወር ፣ እንዳትሰማ ጆሮ ህን የሚያደነቁር ፣ እንኩዋንስ በውን በልም ታይቶ የማያውቅ አዲብ ድንቅ አለም ገልጾ የሚያሳይና እዚያ አግብቶ በደስታ የሚያስክር ፍቅር አይተህ ታውቃለህ ? እኔ ዘንድሮ ብቻ አዩሁ ። ሶፊ አሳዩችኝ!

@OLDBOOKSPDF

ሶፊ ግሩም ናት ፤ ሶፊ ልዩ ናት ! ሶፊ ከሄዋን በቀር በሌላ ሴት አት መሰልም ! ለሄዋን ፍቅር ሲል አዳም አምላኩን ክዶ በራሱና በዘር ምንዝሩ የሞት ፍዳን እንዳመጣ ፣ እኔም ለሶፊ ፍቅር ስል የምወደውን ጉዋደኛየን ፣ ጥላሁንን ከድቼ ፣ የሰው ተፈርዶንና የሚያሳፍር ነውርን በራሴ እንድሸከም ተገደድሁ ! ምን ላድርግ ? ወድጄ አይደለም ፣ ከኔ የበለጠ ሀይለኛ ፣ ፍቅር የሚሉት ይሉኝታ ቢስ ጌታ አስገድዶኝ ነው ! ሁለታችንም ትምህርታችንን የምንጨርስ የዛሬ ዓመት ስለሆነ ፣ ወዲያው እንድንጋባ ተዋውለን ጨረስን ። አባትዋና አባቴ እዚሁ ሀረር አብረው አደገው ፣ አብረው የሸመገሉ ጉዋደኞች ስለሆኑ ፣ ሁለታችን ለመጋባት ተስማምተን መጨረሳችንን ስንነግራቸው ፣ የደስታቸውን ብዛት የምገልጽበት ቃል አላገኝም ። እሱቴ ለጊዜው በኮሌጅ አካባቢ ነገሩን ካንተ በቀር ሌላ ሰው እንዳያውቀው ! አደራ ፥— የሚወድህ ወንድምህ ፣ ደምሴ ቢላይ ።”

እንብባ ስትጨርስ ወረቀቱን እንደ ጨበጠች እንዲሁ ሳታስበው፣ እንዲሁ ግብንዋን ፣ እሱን ለማየት እንደ ፈለገች ሁሉ አንገትዋ ተቃ ንቶ አይኖችዋ በሱ ላይ ተተከሉ ። ነገር ግን አታየውም ነበር ። አይ ኖችዋና ፊትዋ ደም የማይዘዋወርባቸው ፣ ሀይወትና ሙቀት የሌላቸው የቀዝቃዛ ምስል አይኖችና ፊት ይመስሉ ነበር ። እንዲያ አንገትዋ በገዛ እጇ ተቃንቶ ፣ አይኖችዋ በገዛ እጃቸው በሱ ላይ ሲተከሉ ፣ የም ትናገር መስሎት ወዲያ ወዲህ መንቆራጠጡን ትቶ ቆመና የምትለ ውን ለመስማት ፣ ቁርጡን ለማወቅ አይኖቹንም፣ አፉንም ከፍቶ ቢጠ ብቅ፣ ድርቅ ብላ በተቀመጠችበት ምንም ሳትተነፍስ ብዙ ስለ ቆዩች፣

“ታዲያስ ? አሁንስ ምን ትያለሽ ? አሁንም እሰት ነው ትያለሽ፣ ተናገሪ እንጂ !” አለ ጥላሁን፣ የደምሴን ወረቀት እንደ ያዘች ፍዝዝ ብላ ሲያያት ፣ ለጊዜው በውስጡ የተጻፈው ለደምሴ ያላትን የፍቅር ትዝታ የቀሰቀሰው መሰሎት ቁጣው እንደገና በፊቱ ሲነድ እዩታዩ። እርስዋ ግን እንኩዋንስ ልትመልስ ጩኸቱን የሰማችና ቁጣውን ከፊቱ ያየች አትመስልም ነበር ። ድርቅ ብላ እንደ ተቀመጠች ዝም ብላ ቆዩችና፣ ፊትዋን እንደገና ወደ ጨበጠችው ወረቀት መልሳ ትመለከት ጀመር ። አሁን ማንበብ አደለም - መመልከት ብቻ ነው ። አንዳን ዱን መስመርና አንዳንዱን ፊደል ትኩር አድርጋ ስትመለከት ብዙ ትቆይና፣ ከዚያ ወደ ሌላ መስመር፣ ወደ ሌላ ፊደል አልፋ ያን ያክል ወይም ከዚያ የበለጠ ጊዜ አትኩራ ስትመለከት ትቆያለች ። ጥላሁን ያን ያክል ሙሆ ሲጠብቃት ፣ ምንም እንዳልሰማች መልስ ካለመስጠ

@OLDBOOKSPDF

ትዋም ሌላ ፣ ከፊትዋም ሆነ ከጠቅላላ ሁኔታዋ ያዩው ለውጥ የጤን ነት ስላልመሰለው ፣ ቁጣው ወደ ስጋት ተለወጠና ፣ አይኖቹን ከሰዋ ሳይነቅል ፣ ቀስ ብሎ ወደ ወንበሩ ተመልሶ ተቀምጦ ፣ ዝም ብሎ ይመለከታት ጀመር ።

ሶፊያ የወረቀቱን መስመሮችና ፊደሎች ፣ ጥላሁን እስዋን አተኩ ረው ሲመለከቱ ረዥም ጊዜ ከቆዩ በሁዋላ ፣ አሁንም ወረቀቱን በጅዋ እንደ ያዘች ወደሱ ቀና ብላ ፊት - ለፊት ትመለከተው ጀመር ። ያሁኑ አስተያየት ከቅድሙ ልዩ ነው ! ያሁኑ የቀዝቃዛ ምስል ፣ የበድን አስ ተያየት አይደለም ! ያሁኑ አስተያየት ህይወትና ሙቀት ያለው ስሜት የሚገልጽ አስተያየት ነው !

" ጥላዩ ! " አለች ፣ በደካማ ድምጽ ፣ ውሀ ያዘሉ አይኖችዋን በሱ ላይ እንዳሳረፈች ዝም ብላ ከቆዩች በሁዋላ ። ያ አይነት አጠራር ድሮ በሰላሙ ጊዜ ፣ ድሮ መጠራጠራቸውና የልብ መቸካከራቸው ሳይመጣ ትጣራበት የነበረ ፣ ሀረር ደርሳ ከተመለሰች ካፍዋ ሲወጣ ሰምቶት የማያውቅ ስለ ነበረ ፣ ድንገት ሲሰማው ልቡ እንዳከርማ ለሁለት ተር ተር ብሎ የተሰነጠቀ መሰለው ። ከሰዋ አፍ መውጣቱን ተጠራጠረና አቤት ለማለት እንኳዋ ስላልደፈረ ፣ አይኖቹንና አፉን ሰፋ አድርጎ ከፍቶ ብቻ ዝም ብሎ ይመለከታት ነበር ።

" ጥላዩ ! " አለች ፣ ደገመችና ።

"ም . . . ምንድነው ? "

"እባክህ እመነኝ ፣ እኔ እንዳመንሁህ እብ-እባክህ እመነኝ !"

"ምኑን ልመንሽ ? "

"በዚህ ወረቀት የተጻፈው ሁሉ አንድ እውነት የለበትም ፤ ሁሉም ውሸት . . . ውሸት ነው ፤ እባክህ እመነኝ ። "

"እንዴት ፤ ደምሴ ያልሆነውን . . . ውሸቱን ጻፈ ማለትሽ ነውና? ለምን ብሎ ? " አለ ፣ እንደገና ተነስቶ አፊትዋ ቆሞ ፣ ማረፊያ አጥ ተው ወዲያ ወዲህ የሚንከራተቱ አይኖችዋን ዘቅዝቆ እየተመለከተ ።

"ይህን ወረቀት . . . ደምሴ አልጻፈውም ፤ የደምሴ ጽፈት አይደለም፤ የሌላ ሰው ጽፈት ነው ። "

የማን ? "

" የ . . " ብላ ልታወጣው እጉሮርዋ ያደረሰችውን ስም እንደገና መልሳ በምራቅዋ ውጣ ዝም አለች ።

@OLDBOOKSPDF

“የማን ? ተናገሪ እንጂ ! ንገሪኝ እንጂ !” አለ ጥላሁን ፣ እንደ መቆጣት ብሎ ።

“አንተና እኔ እንዳንጋባ ተንኮል ሲሰራ የሚኖረው ፣ የወዳጅህ የ. . . የወንድይራድ አስታጥቂ ነው ።”

“ምን ?” አለ ጥላሁን ፣ እንደ ብራቅ ጆሮ በሚያደነቁር ጩኸት ራሱን በትልቅ ዱላ እንደ ተመታ የሰራ አካላቱ ደንዝዞ የገዛ ጩኸቱ አልተሰማውም ። እንዲያ ደንዝዞ ፣ እንዲያ ፈዞ ፣ እንደ ቆመ ብዙ ከቆዬ በሁዋላ ፣ ወደ ወንበሩ ተመልሶ ተቀምጦ ሶፊያ ያለችውን ክፉ ነገር ከደጉ ፣ ከሚያምነው ወዳጁ ፣ ከወንድይራድ ጋር ለማገናኘት ቢሞክር አልገናኝለት አለ ! እንደ ወንድይራድ ያለ ደግ ሰው እንኪዋንስ በወዳጁ በጠላቱ ላይስ ቢሆን እንዲህ ያለ ክፉ ፣ እንዲህ ያለ ወራዳ ተንኮል ይሰራል ? ለምን ብሎ ? እንዲያውስ ሶፊያና ደምሴ ለመጋባት ፣ መዋዋላቸውን ቢያውቅ ቅናቱና ጥቃቱ የራሱን ፣ የጥላሁንን ያክል እንገብግቦት ፣ መጽናናት አቅቶት የነበረ እሱ አደለም ? እንዲያውስ አባትዋ በማባበልም ሆነ በማስፈራራት ሐሳብዋን እንዳያስለውጥዋት ቶሎ ህጋዊ በሆነ ቃልኪዳን እንዲተሳሰሩ ፣ በህግ እንዲተሜጩ ሁል ጊዜ የሚወተውት ማን ሆንና ነው ፣ ወንድይራድ ሁለቱ እንዳይጋቡ ተንኮል ሲሰራ ንዋሪ የሆን ? ይህ ጭራሽ የማይመስል ነገር ነው !

ጥላሁን እንግቱን ደፍቶ እንደ ተቀመጠ የጉዋደኛው ፣ የወንድይራድ ስእል ፣ ደግነቱ ፣ ሩህሩህነቱና ታማኝነቱ በልዩ ቀለም ጎልተው የሚታዩበት ስእል ፣ ሶፊያ እንዲያ ያለ ወራዳ ውሸት በማውራትዋ ፣ ጥላሁን ሰምቶ ዝም በማለቱ ሁለቱንም የናቀና የተጸየፈ ፣ ሁለቱንም የታዘበ የሚመስል ስእል ባይን ህሊናው ፊት ቆሞ ስለታዬው ፈራና ፣ የበደለኛነት ስሜት ተሰማውና ፣ በሸንን ውስጥ ተንቀልፍቶ ቆይቶ እንደ ነቃ በድንጋጤ ቀና ብሎ አይኖቹን እያርገበገበ ዝም ብሎ ይመለከታት ጀመር ።

“ታዲያ . . .” አለ ፣ እንዲያ ዝም ብሎ ሲመለከታት ቆይቶ ። “ታዲያ እንዲህ ያለውን ነገር ነው አመንኝ የምትይኝ ? ላንቺና ለኔ ጋብቻ ከኔና ካንቺ የበለጠ የሚቾኩለው ወንድይራድ ‘ጋብቻችንን ለማሰናከል ተንኮል ይሰራል’ ብለሽ ስትነግሪኝ ነው እንዳምንሽ የምትፈልጊ ? ወንድይራድ ለኔ ምን መሆኑን ታውቂያለሽ፣ ሶፊ !”

“በጣም የምትወደው ፣ በጣም የምታምነው ጉዋደኛህ መሆኑን አውቃለሁ ። ሲያደርገው የኖረውን እስከ ዛሬ ያልነገርሁህም ፣ የምንጋባበት ቀን ደርሶ ስንጋባ ፣ ተስፋ ቆርጦ የሚያደርገውን ይተውና ወዳ

@OLDBOOKSPDF

ጅነታችሁ እንደ ጸና ይኖር ይሆናል ብዬ ተስፋ በማድረግ ነበር ። አሁንም ቢሆን ፤ በዚህ ወረቀት የተጻፈው ሁሉ ውሸት መሆኑንና እኔ ካንተ በቀር አገባለሁ ብዬ ቃል የሰጠሁት ሰው አለመኖሩን ፤ እንዲሁም ደምሴ ይህን ይሁን ፤ ወይም ይህን የመሰለ ሌላ ወረቀት ስለኔ ሊጽፍ የማይችል መሆኑን ስነግርህ ካመንከኝ የወንድይራድን ነገር እንተወው ! ”

“እዎ ፤ የወንድይራድን ነገር ብንተወው ይሻላል ። ወንድይራድን እንዲህ ያለ ነገር ያደርጋል ብዬ መጠርጠር ይቅርና መስማቱም ይከብደኛል ፤ ስለዚህ እንተወው ። መቼም ለኔ . . ‘አሳቤን አልለወጥሁም’ በዚህ ወረቀት የተጻፈው ሁሉ ውሸት ነው ካልሽኝ ይበቃኛል ፤ አምንሻለሁ ። ‘ወረቀቱን ወንድይራድ ነው እንጂ ደምሴ አልጻፈውም’ ያልሽው ግን ፤ ግምት ስለሆነና ግምትም ስህተት ሊሆን ስለሚችል ፤ እመኚኝ አትበይኝ ! ”

“ጥላዬ ፤ ከደምሴና ከወንድይራድ ጋር ካንደኛ ደረጃ እስከ ኮሌጅ አብረን እየተማርን ፤ ሳንለያይ ስለ መጣን ፤ የሁለቱን ጸፈት ፤ የራሴን ጸፈት የማውቀውን ያክል አውቀዋለሁ ! ደግሞ . . . ” አለችና አንገቷን ደፍታ እንደ ገና ዝም አለች ።

“ደግሞ ምን ? ” አልሁ ፤ ትናገራለች ብዬ ሲጠብቅ ዝም ብላ ስለ ቀረች ።

“ወንድይራድን አንተ ትወደዋለህ ፤ ታምነዋለህ እንጂ ፤ እሱ እንደማይወድህ ፤ እንደሚቀናብህና ሊጎዳህ እንደሚፈልግ አውቃለሁ ። ይህን ሁሉ እያወቅሁ እስከ ዛሬ ሳልነግርህ የቆየሁብትን ምክንያትም ቅድም ነግሬህአለሁ ። ብቻ ተሳስቻለሁ ። ቀደም ብዬ ብነግርህ ኖሮ አሁን የደረሰው አይደርስም ነበር ። ወንድይራድ ማን መሆኑን ቀደም ብለህ ብታውቅ ኖሮ ተቆርቋሪ መስሎ የነገረህንና ራሱ ጽፎ የሰጠህን አምነህ ይህን ያክል እስክምንለያይበት ጫፍ ድረስ አትገፋኝም ነበር ! ስለዚህ ፤ ምንም እንኩዋ ‘ወዳጅህን ጥላ’ ማለት የሰይጣን ምክር ቢሆን ፤ ‘ከወዳጅ ጠላት ያድንህ ! ’ ማለት ምርቃት ስለሆነ ወንድይራድ የወዳጅ ጠላት መሆኑን አምነህ ፤ ለወደፊት ካልተጠነቀቅህ ሁለታችንም የምንጎዳ መሆናችንን ስለ ተረዳሁ ብትወድም ፤ ባትወድም ተንኮሉን እስከ ማስረጃው ዛሬ መግለጽ አለብኝ ። ብቻ ይህን ከማድረጌ በፊት እሱንም ፤ እኔንም ‘ይቅር ለእግዚአብሄር’ እንድትለን ቃል ግባልኝ ” አለች ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ አይኖችዋን ፍጥጥ አድርጋ የጥላሁንን አይኖች ፊት ለፊት እያየች ።

@OLDBOOKSPDF

“እሱስ ክፉ ሰሪ ነው አልሽ ፤ እንቺስ የሰራሽው ክፉ ነገር አለ ? ያለዚያ . . . እንቺን ፣ ‘ይቅር ለእግዚአብሄር’ የምልበት ምክናያት ምን ድነው ? ”

“እሱ ክፉ ስለ ሰራ ፣ እኔ ክፉ ሰራውን ገልጨ በሱ ላይ የነበረ ሀን ክንቱ ተስፋ ፣ የነበረሀን ክንቱ አለኝታ ስለማሳጣህ ፤ ”

ሶፍያ ስለ ወንድይራድ የተንኮል ስራ ርግጠኛ ሆና እየደጋገመች በተናገረች መጠን ፣ ጥላሁን ጉዋደኛው ፣ ‘ሰራው’ የተባለውን ተንኮል ለማወቅ መፈለጉ ቀስ እያለ ይታይበት ጀመር ።

“ቅድም ስላንቺና ስለ ደምሴ ውል ማሰር ለኔ የነገረኝና ወረቀቱን የሰጠኝ ወንድይራድ መሆኑን ርግጠኛ ሆነሽ ስትናገሪ ሰማሁሽ ፤ ወሬውን የነገረኝና ወረቀቱን የሰጠኝ እሱ መሆኑን ማን ነገረሽ ? እኔ ነገርሁሽ ? ”

“አንተ አልነገርሽኝም ፤ ሌላ የነገረኝ ሰውም የለም ። ግን እኔ እሱ መሆኑን አውቃለሁ ! በል እሱ አደለም በል ! እሱ አደለም ብለህ የክብር ቃልህን ስጥና እኔ ስለሱ የተናገርሁት ፣ አሁንም፣ ‘ልናገር’ ያልሁት ሁሉ ውሸት ይሁን ፤ እኔም ከወዳጅህ አጣልቼ ጥፋቴን ነውሬን ለመሸፈን የምሞክር ፣ ውሸታም ልሁን ! በል እንግዲህ ሁሉም በዚህ ይለቅ” አለች ፣ ዘና ብላ ከተቀመጠችበት ሲቃ እንደ ቀሰቀሳት ሰውነትዋ ሁሉ ነቅቶ ። ጥላሁን አልመለሰም ፤ አንገቱን ደፍቶ ዝም አለ።

“በል እንግዲህ የለመንሁህን እሺ በለኝ ” አለች ስትጠብቅ ቆይታ ፣ አንገቱን በደፋበት ዝም ብሎ ስለቀረ ።

“ስለ ጋብቻችን አሳብሽን ያልለወጥሽ መሆንሽን ተረዳሁ ፤ አመንሁ ። የፈለግሁት ይህን ብቻ ነው ። ሌላው ምንም አደል ። ወንድይራድ ሳምነው ሊከዳኝ ፈልጎ እንደሆነ . . በፈለገበት ቦታ እቆዩዋለሁ ። ”

“የለም ጥላየ ! ፈሪ ጠላት ፣ ይልቁንም የወዳጅ ጠላት ፣ የሚመጣበትን ጊዜና ቦታ አስታውቆ መጥቶ አያውቅም ! ፈሪና የወዳጅ ጠላት ተሸሽጎ ነው የሚጎዳው ! ስለዚህ ጠላትን አውቆ ፣ ተጠንቅቆ መጠበቁ ነው የሚሻለው ። በል አሁን ‘ይቅር ለእግዚአብሄር’ በልና ወንድይራድ ለኔም ፣ ላንተም ምን እንደሆነ ልንገርህ ። ”

“እሺ ፤ ‘ይቅር ለእግዚአብሄር’ ብያለሁ ። ”

@OLDBOOKSPDF

“ወንድይራድ ጋር ከቤት ጋር ስንተዋወቅ ፣ ሁለተኛ ደረጃ ሳለ ጀምሮ እንዳገባው ያጫወተኝ ነበር ” አለች ፡ እንግትዋን ደፍታ ትንሽ ስታስብ ቆይታ ቀና አለችና ። “እንዳይቀዩም እያለሳለሰሁ የጋብቻ ነገር የማስብበት ጊዜ ገና መሆኑንና ሌላም ልዩ ልዩ ምክንያት እየፈጠርሁ መሸሽ ብሞክር አስቀኝ ስላለ ፤ ለሱ የወንድምነት ካልሆነ ሌላ ስሜት የሌለኝ መሆኔን ስነግረው ተቆጥቶ ካመት በላይ ንግግር ከለከለኝ ። ከዚያ ብዙ ጊዜ ደህና ኖረን ካንተ ጋር መዋደዳችንንና ትምህርታችንን ስንጨርስ እንድንጋባ መስማማታችንን ሲያውቅ ፣ እንደ ገና አገርሽቶበት ጭቅጭቁን ጀመረ ። የልቤን በልቤ አድርጌ ስስቅለት የፈቀድሁ መስሎት እረፍት ይከለክለኛል ። ፊት ስነሳው ፣ ‘ወይ እንቺን ፣ ወይ ጥላሁንን ፣ ወይ ሁለታችሁንም እገድላለሁ ! ’ እያለ ያስፈራራኛል ። አንድ ቀን ካልተውኸኝ በጉዋደኛህ ላይ ተደርበህ የምታስቸግረኝንና የሁለታችንን ነፍስ ለማጥፋት መዛትህን ለፖሊስም ፣ ለጥላየም እነግርና ጉድህ ይወጣል ’ ስላልሁት ፈርቶ ነው መሰለኝ ከዚያ ወዲህ ዘዴውን ለወጠ ። እሱን እንደማላገባው ቢያውቅም አንተን እንዳላገባ መጣሩን አልተወም ፤ ወደፊትም እንደማይተው አውቃለሁ ። ስለዚህ ነው በወጥመዱ እንዳትገባለት ማን መሆኑን እንድታውቅ የፈለግሁ ።

አዲሱ ዘዴው ፣ እኔን ማስቸገሩንና ማስፈራራቱን ትቶ ፣ በማያውቁት በኩል ያኑ የተንኮል ስራውን መስራት ነው ። ካዲሱ ዘዴ አንዱ ይህ ወረቀት ነው ፣ ሌላው . . . አለችና ራስዋን እየወዘወዘች መሬት ስታይ ቆይታ ፣ “ጥላየ ፣ ‘ይህ አሁን የደረሰው ክፉ ፈተና ደግሞ እንዳይደርስ ማስጠንቀቂያ ይሆናል ’ ብዬ ባላስብና ፣ ‘በውስጡ የተጻፈው ስላንተ ያለኝን ስሜት ትንሽ እንኩዋ የማይለውጠው መሆኑን ስነግርህ አትጠረጥረኝም ’ ብዬ ባላምን ፣ ይህን ወረቀት አላሳይህም ነበር ። እንካ አንብበው ፤ አባባ የጻፉልኝ ነው ” ብላ አንድ ወረቀት ከቦርሳዋ አውጥታ ስትሰጠው ተቀብሎ ያነብ ጀመር ።

“ይድረስ ከልጄ ፣ ከወዳጄ ፣ ከሶፊያ ፤—

ከቶ እንደምን አለሽ ? እኔ አንቺ የምወድሽ ልጄ እንደ እህል ከምትርቢኝና እንደ ውሀ ከምትጠሚኝ በቀር የእምላክ ክብሩ ይስፋ ደህና ነኝ ፤ እናትሽም ደህና ናት ። ከናፍቆትሽም ሌላ ስላንቺ የምሰማው ወሬ ደህና ስላልሆነ ግራ ገብቶኝ ተቸግሬአለሁ ። ያ ፣ ያ አስታጥቄ ልጅ ፣ ወንድይራድ በቅርቡ እዚህ መጥቶ ‘ማን እንደ ወለደውና ከየት እንደ መጣ የማይታወቅ ፣ እንደ ውሻ ቡችላ በልጆች ፣ በተማሮች ፍር

@OLDBOOKSPDF

ፋሪና የጅ ጥራጊ ያደገ ፣ 'ጥላሁን የሚባል ሰው አገባለሁ' ብለሽ እኔ አባትሽ ቆሜ እዩሄድሁ ፣ አፈር ሳይጫነኝ ፣ አባት እንደሌለሽ ብቻሽን መወሰንሽን ፡ ነግሮን እናትሽ ጭምር ስናለቅስ ሰነበትን ። ምነው ልጄ ፣ ምን አደረግንሽ ? አቻሽን ስታገቢ አይተን ፣ ደስ ብሎን ወደ መቃብራችን ብንሄድ ምን ቸገረሽ ? ተከብረው የሚያስከብሩ ፣ ብዙ የመኩዋንንት ልጆች ደጅ እየጠኑሽ ፣ እድልሽን ለምን ዘቅዝቀሽ ወደ ታች ትጥይዋለሽ ? እባክሽ ይቅርብሽ ! ከፈቃዴ ከወጣሽ መቸም ሌላ ማድረግ ባልችል ለመካድና ለመርገም ስልጣን አለኝ ። ነገር ግን የወለዱትን መካድና መርገም እጅን በጅ እንደ መቁረጥ ስለሆነ ፣ እባክሽ እጄን በጄ ቆርጬ እዩተስቃየሁ ወደ መቃብሬ እንድሄድ አታድርጊኝ ! ነገር ግን መቸም የዛሬ ልጆች የውቀታችሁ መጀመርያ የወላጆቻችሁን ፈቃድ መተላለፍ ስለሆነ ፣ የኔን ፈቃድ ጥለሽ ፈቃድሽን ለመፈጸም ከቆረጥሽ ፣ ከእድሜዬም ሌላ ይህ ያንቺ አድራጎት የሞቴን ቀን ባስር እጥፍ ማፋጠኑ የማይቀር በመሆኑ ፣ ባይሆን ጋብቻሽን ሳጭር ጊዜ ፣ እኔ የማደረጃጀውን አደረጃጅቼ እስክሞት እንድታቆይው አደራ እልሻለሁ ። አባትሽ ቀኛዝማች ሙላት አራጌ ።"

እንብቦ ሲጨርስ ፣ ሳይተኛ አድሮ እንቅልፍ እንደ ከበደው ፣ ራሱን ባንድ እጁ ደገፍ ፣ አይኖቹን ገርበብ አድርጎ ፣ ዝም ብሎ ቀረ። ከዚያ እንዲያ አይኖቹን ገርበብ አድርጎ ትንሽ እንደ ቆዩ ፣ የወንድይራድ ስእል እንደ ገና ታዬው ። አሁን እንደ ቅድሙ በንጹህነቱ ፣ በታማኝነቱ ፣ በታላቅነቱ አምኖ ፣ ከርቶ ሶፍያ በውሸት ስላማችው ፣ ጥላሁን ታማሶ በመስማቱ ፣ ሁለቱንም ስለ ታዘባቸውና ስለ ናቃቸው በመጸየፍ ዘቅዝቆ የሚያይ አደለም ! አሁን የሚያየው የወንድይራድ ስእል ሲሰርቅ ተይዞ እንዳይመቱት ስለፈራ ፣ ጅራቱን በሁዋላ ጉያው ሸጉጦ እንደሚቅበዘበዝ ደካማና ሌባ ውሻ ሹክክ ያለ ነው !

"እንዴት ! ይህ . . . ይህን ያደረገ እኔ የማውቀው ወንድይራድ ነው ? ወይስ . . . ሌላ" አለ ጥላሁን ፣ አይኖቹን ከድኖ እንደ ተቀመጠ ድምጹን አሰምቶ ። የሚያስብ እንጂ የተናገረ አልመሰለውም ነበር !

"የምታምነው ጉዋደኛህ ፣ ወንድይራድ አስታጥቂ ! " አለች ሶፍያ ።

"እ ? " አለ ፣ ከንቅልፉ እንደባነነ አይኖቹን እያርገበገበ ።
" ለምን ? ምን ይጠቀማል ? "

"ይበቀላል ! "

"እኔንና አንቺንስ ይሁን ፣ አሁን እንደ ነገርሽኝ ከሆነ ምክናያት አለው ። ሽማግሌው አባትሽ ምን አደረጉት ? ለምን ይህን ያክል እዝ

@OLDBOOKSPDF
ነውና ተስፋ አጥተው ህይወታቸውን ለማሳጠር እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል ?”

“የሳቸው አልታዩወም ፤ እሳቸው አዝነው እስከዚህ የሚደርሱ አልመሰለውም ። የነገራቸውን ሲነግራቸው ፤ በውድም ሆነ በግድ እንተን እንዳላገባ የሚከለክሉኝ ብቻ መሰለው ። ወዲያውምኮ . . . በቀል የሚኮለኩለው ሰው ፤ እንደ ጋሪ ፈረስ ከያዘው መንገድ በቀር ቀኝና ግራ አያይም።”

“እዎ ፤ እንዲያ ቢሆን ነው” አለና ሁለቱም ትንሽ ዝም ብለው ከቆዩ በሁዋላ ፤

“ህ ! ” አለች ሶፍያ ፤ የቅርታ ፈገግታ ፈገግ ብላ ።

“ምን ? ” አለ ጥላሁን ።

“አሁን ደግሞ አንድ ነገር ትዝ አለኝ ! ”

“ምን ? ! ”

“ያንተና የየሽመቤት ጋብቻም ከወንድይራድ ተንኮል አንዱ ክፍል መሆኑ ! የሁሉም ፈጣሪ ወንድይራድ መሆኑ ! ”

“እንዴት ? እባክሽ ! ” አለ ጥላሁንም ፤ እንደሷ የቅርታ ፈገግታ ፈገግ ብሎ ።

“ለኔ ወሬውን የነገረችኝ ቅድስቴ ናት ። ለቅድስቴ የነገረቻትና የጸፍህላትን የፍቅር መግለጫ ያሳዩቻት ግን ፤ የሽመቤት አስታጥቴ ራሰዋ ናት ። እየህ ? ወንድይራድ ፤ ካንድ ወገን እህቱን አባብሎም ይሁን አስፈራርቶ ፤ እንዲህ ያለ ጎስቋዋላ ተንኮል ለመስራት መሳርያ እንድትሆንና ውሸቱን እውነት አስመስላ አሰናድታ ፤ በማምናት ምስጢረኛየ ፤ በቅድስቴ በኩል ለኔ እንድታስተላልፍ አደረጋት ። ከሌላ ወገን አንተ አይንህን ጨፍነህ ፤ ጆሮህን ደፍነህ እንደምታምነው ስለሚያ ሳንተውቅ ፤ ራሱ የጻፈውን ‘ደምሴ ጻፈልኝ’ ብሎ ፤ እንደ ተቆርቋዋሪ ሳንተ ውቅ ፤ ራሱ የጻፈውን ‘ደምሴ ጻፈልኝ’ ብሎ ፤ እንደ ተቆርቋዋሪ ሰጠህ ። በዚህ ሁለታችን የምናምናቸው ጉዋደኞቻችን ከማስረጃ ጋር የነገሩንን ይዘን ፤ እሰበሳችን ተናኩረን እንድንለያይ አደረገ ! እስቲ እንዲህ ያለውን ተንኮል ተመልከተው ! የሰይጣናት አለቃ ራሱ ካልሆነ ሌላ ተራ ሰይጣን እንኩዋ ሊሰራው የማይችል ፤ ጥሩ ተንኮል አደለም ? ”

“ይገርማል ! እውነትም ወንድይራድን ሳላውቀው እኖር ኖርዋል ! ተንኮለኛነቱን ብቻ ሳይሆን ይህን ያክል አዋቂ መሆኑንም አላውቅም ነበር ! ‘ይቅር ለእግዚአብሄር’ ብዬ ቃል ባልገባ ፤ እፍንጫ

@OLDBOOKSPDF

ውን ወዲያ ከፊቱ ማጥፋት ይገባኝ ነበር ! ነገር ግን ይቅር ብያለሁ ፤ ግዴለም ይቅር ! ” አለ ፣ በመገረም ራሱን ቀስ አድርጎ እየወዘወዘ ። ከዚያ የሶፍያ አባት የጻፉትን ወረቀት እንደ ገና ሲመለከት ቆዩና፣ “ይህ ወረቀት ከተጻፈ ብዙ ጊዜውኮ ነው ሶፊ ? ዓመት ሊሆነው ምንም አል ቀረውም ። ታዲያ ይህን ያክል ጊዜ ካንቺ ጋር ሲቆይ ለምን···· አላ ሳዩሽኝ ? ” አላት ።

“ ምን ብዬ ላሳይህ ? ዛሬም ግድ ባይሆንብኝ አላሳይህም ነበር ! ”

“እኔኮ አሁን የተጻፈበትን ቀን እስካይ ፣ ሀረር ደርሰሽ ከተመለ ስሽ የጻፉልሽ መስሎኝ ነበር ። ወንድይራድ በቅርቡ ሀረር አለመሄዱን እያወቅሁ ለምን እንዲህ እንደ መሰለኝ አላውቅም ! ”

“የለም ፣ ከኔ ጋር ብዙ ቆይቶዋል ። እንዲያውም ዘንድሮ ሀረር አልሄድም ብዬ ነበር ፤ የሄድሁ ቀደም ብለው ይህን ወረቀት ስለ ጻፉ ልኝ ፣ በጣም አሳስቦኝ ነበርና ሄጄ ባረጋጋቸው የሚሻል ስለ መሰለኝ ነው ። ”

“ታዲያ . . . ሆነልሽ ? ተረጋጉልሽ ? ”

“መችም መጀመርያ እንደ ደረስሁ ወንድይራድ የነገራቸው ሁሉ አንድ እውነት የሌለበት መሆኑንና አዲስ አበባ ትምህርቴን ስጨ ርስ ወደ ፈረንጅ አገር ሄጄ ቢያንስ ፣ ቢያንስ ሶስት ዓመት ሳልቀጥል ለማግባት አሳብ እንደ ሌለኝ ከነገርሁዋቸው በሁዋላ ፣ አብሬያቸው ቆይቼ እስክመጣ በሱ ወረቀት የጻፉትን ስሜት አላዩሁባቸውም ፤ ተረጋ ግተዋል ማለት አይደለምን ? ”

“የነገርሻቸው ሁሉ እውነት ነው ? ወይስ . . . . ለማረጋጋት ! ”

“ለማረጋጋት አልሁኮ ! ” አለች ፣ ፊትዋ በቅርታ ፈገግታ አጊጦ፣ እንባ አጥቦ ባጠራቸው አይኖችዋ የሱን አይኖች እስከ ስር መሰረታ ቸው ጠልቃ እያዩች ።

“ለማረጋጋት ! ” አለ ጥላሁን ፣ እንደ ትንሽ ህጻን በቅፉ ይዞ በደስታ የሚዋኙ አይኖችዋን በፈንታው ቁልቁል ጠልቆ እያዩ ።

@OLDBOOKSPDF

ምእራፍ ፱

# ልዩ ዋጋ ለማይከፍል ልዩ አስተያየት አይገባውም !

የሶፍያ ያስተማሪነት ፣ ጥላሁን የህግ ትምህርታቸውን በያዙት አመት
ጨርሰው ስራ እንደ ያዙ ፣ ለመጋባት ተስማምተው ጨርሰው ያ ቀን እስ
ኪደርስ ሁለቱም በናፍቆት ይጠብቁ ነበር ። ነገር ግን ፣ የሶፍያ ወላጆች
ይልቁንም አባትዋ ጥላሁንን እንድታገባ የማይፈቅዱ መሆናቸው የታ
ወቀ በመሆኑ ፣ ውሳኔአቸውን የልብ ወዳጆቻቸውና ምስጢረኞቻቸው
እንኳ እንዳያውቁባቸው ሸሽገውት ነበር ።

አንድ ቀን ጥዋት ፣ ሶፍያ ከመኝታ ክፍል ጉዋደኛዋን ፣ ቅድስትን
ፍለጋ ወደ ስብሰባ አዳራሽ ስትሄድ ፣ በመንገድ አንድ የኮሌጅ ተላላኪ
የተደፈነ ኤንቬሎፕ ሰጣትና ቶሎ ከፍታ ብታይ ፣ ያለፈው ፈተና
ውጤት ሆኖ አገኘችው ። በተፈተነችባቸው ትምህርቶች ሁሉ አልፋለች !
ያውም በከፍተኛ ደረጃ ! ደስታውን አልችለው ብላ ፣ በቆመችበት የም
ትሆነውን አጣች ! ከዚያ ቅድስትን መፈለጉን ትታ ፣ ደስታዋን ለጥ
ላሁን ለማካፈል ወረቀቱን በቦርሳዋ ከታ ወደሱ ቤት ሮጠች ። የጥላ
ሁን ቤት አሁን የትምህርት ሚኒስቴር ከሆነው ትንሽ ዝቅ ብሎ ከኮ
ሌጁ ቅርብ ነው ። ስትደርስ ጥላሁን እቤቱ ተቀምጦ ያነብ ነበር ።

“የምስራች ! ” አለች ፣ በሩን ከፍታ ስትገባ ፊትዋ ሁሉ እንደ
ጎህ ሰማይ ወገግ ብሎ ።

“የምስራች ! ናፍቃኝ ባይኔ ስትሄድ የነበረችውን ልጅ አገኘሁ !”
አለ ጥላሁን ፣ የምስራች ያለችበትን ምክናያት ሳይጠይቅ እቅፍ አድ
ርጎ አፍዋን ሰሞ ።

“የምስራቹ ! ምን እንደሆነ አትጠይቀኝም ? ያውልህ !” አለች ፣
የፈተናዋን ውጤት ከቦርሳዋ አውጥታ ። ጥላሁን ፈተናውን በከፍተኛ
ደረጃ ማለፍዋን ሲያይ ፣ ከስዋ የበለጠ ደስ ያለው መሆኑ ከፊቱ እየ
ታዩ ፣ እንደገና እቅፎ ምጥጥ አድርጎ አፍዋን ሳመና ፣ “ይህ ፈተናውን
በከፍተኛ ደረጃ ስላለፍሽ ፣ የቅድሙ ናፍቀሽኝ ስለ መጣሽ ነው ” አለ ፣
በቅቱ እንደ ያዛት አይንዋን ጠልቆ እያዩ ።

@OLDBOOKSPDF

"ያንተስ ! አልመጣም ? " አለች ፤ ከቅፉ ወርዳ ጎን ለጎን እንደ ተቀመጡ ።

"አላገኘሁትም፤ ዛሬ ወይም ነገ ሳላገኘው አልቀርም ።"

"የሚያርመው ማን እንደሆነ አውቀሀል ?"

" አንትዋን ነው አሉ !"

" አንትዋን ? አለች ፤ የድንጋጤ ምልክት በፊትዋ እዮታዩ ።"

" አዎ ፤ አንትዋን ፤ ምነ ?!"

"ምንም አደል ፤ እንዲያው ነው " አለች ፤ ትንሽ ፍዝዝ ብላ አይ ኖችዋን ሳታረግብ ፊት ለፊት እግድግዳው ላይ ተከላ ።

" ስለ አንትዋን የምታውቂው ነገር አለ መሰለኝ፤ ምንድነው ?!"

"ስለ አንትዋን የማውቀው ነገር የለም ። ብቻ ወንድይራድ መሰን በቻውን ከአንትዋን አልተለዩም ። ሁለቱ ያለድሮዋቸው ባንድ ሺርሽር ሲሉ ፤ ወይም ብቻቸውን ቁጭ ብለው ሲያወሩ ይታያሉ ። ስለዚህ፤ ' ወንድይራድ ያለድሮው ለምን አንትዋንን ባለሙዋል አደረገው ' ብዬ . . . እንዲያው ለግቼ ነው ።"

" ለማየቱ እኔም ባንድ ላይ እያቸዋለሁ፤ ነገር ግን ምን የሚያስጋ ነገር አለ ?"

"ወንድይራድ ለሀብታም አባቱ ወንድ ልጅ አንድ እሱ ብቻ ስለ ሆነ፤ በገንዘብ እንደ ልቡ እንደሚጫወት ታውቃለህ ፤ ስለዚህ . . . መችም መነኩሴ ገንዘብ ወዳጅ ነውና የተንኮል መሳርያው እንዳያደር ገው ለግቼ ነው ። "

" አንትዋን በወንድይራድ ገንዘብ ተገዝቶ ፈተናውን ምን ያደር ገው ብለሽ ስጋሽ ?"

" እኔ እንጃ ! ብቻ ስጋሁ ። የሕግ ክፍል ፈተና ውጤት ከተሰጠ ቆይቶዋል አሉ ፤ ያንተ ለምን እስካሁን ቆዬ ?"

"የኔ ብቻኮ አደለም ፤ አንተትነህ ጥሩ ሰውና ታሪኩ ሰይፈም ትና ንት አግኝቻቸው፤ 'ገና መልስ አላገኘንም ' አሉኝ ፤ ሌሎችም ገና የሚ ጠብቁ አሉ ።"

" ታሪኩ ሰይፈማ፤ 'ወድቀሀል' ተብሎ ጠገሩን ይነጭ ነበር ፤ "

"መቼ ?"

@OLDBOOKSPDF

“ ያወቀው ትምንት ከጥቅር በሁዋላ ነው አሉ ፤ ተበሳጭቶ ከዚህ ይሁን ከረመው ሰው ሲጣላ ሲሄድ ፣ ጉዋደኞቹ ከበው ሲገለግሉት ያዬሁ ባሬ ነው ።”

“ እስቲ ተነሺ ወደ ኮሌጅ እንሂድ ” አለ ፣ እሱም ትንሽ እንደ መከጋት ብሎ ።

ጥላሁን ካንደኛ ደረጃ ጀምሮ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እስኪ ጨርስ በፈተና አንድ ፣ ወይም ሁለት ጊዜ ሁለተኛ ሆኖ እልፎ ይሆናል። በቀረሬ አንደኛነቱን ለቆ አያውቅም ። ወደ ኮሌጅ ካለፈም ፣ ሁለቱን አመታት አንደኛነቱን ከታላቅ ማእረግ ጋር እያገኘ ነበር ያለፈ ። ይል ቁንም ለከፍሉ ትምህርት ከተመደቡት ሌላ ፣ በህግ ፣ በፖለቲካ ፣ በታ ሪክ ፣ በስነ ጽሁፍና በሌሎች ልዩ ልዩ ጉዳዮች የተጻፉትን መጻህፍት በሰፊው አንባቢና አጥኚ በመሆኑ ፣ ያስተያየቱ ስፋትና የአእምሮው ብስ ለት ፣ በኮሌጅ አካባቢ በልዩ ልዩ ችሎታቸውና ስጦታቸው ስመጥር እንደሆኑት ጥቂት ፣ ምርጥ ተማሪዎች ስሙ የተጠራ ነበር ። በያመቱ የፈተና ወራት አልፎ የፈተና ውጤት በሚታወቅበት ጊዜ ፣ ተማሮች በኮሌጅ ግቢ ጥቂትም ፣ ብዙም ሆነው እየተሰበሰቡ እነማን እንዳለፉና ለነማን እንደ ወደቁ የሚጠይቀው ሲጠይቅ ፣ የሚያወራው ሲያወራ የጥላሁን ማለፍ ልክ በያመቱ እንደሚደረገው ፈተና የማይቀርና የተለ መደ ሆኖ ፣ ‘ አለፈ ? ወይስ ወደቀ ? ’ ተብሎ ስለሱ አይጠየቅም ነበር። ስለዚህ ፣ በሶስተኛው አመት የኮሌጅ ፈተና ‘ ወደቀ ሲባል ’ ጥላሁንን የሚያውቁ ሁሉ ከመገረማቸውም በላይ ማመን አቃታቸው ። ጥላሁን የመርዶውን ወረቀት ሲያይ ፣ ከእየር ወርውረው እንደ ጣሉት ደንገዞ የነበረበትን ሳያውቅ ብዙ ቆየ ። ድንዛዜው ትንሽ እንደ ማለፍ ሲልና ሰውነቱን ማወቅ ሲጀምር ፣ ለመራመድ ቢሞክር ራሱን ስላዞረውና መሬቱን አጥርቶ ማየት ስላልቻለ ፣ እዚያው በነበረበት ጎንበስ አለና ፣ በጁ ደባብሶ ያገኘው ምን መሆኑን ሳያውቅ ቁጭ አለ ። ራሱን በሁ ለት እጆቹ ደግፎ እንደ ተቀመጠ ፣ ማዞሩን ሲተወውና ሀዋሳቱ በት ክክል መስራት ሲጀምሩ ፣ የከፋው ነገር ሁሉ ሰራዊት እርስ በርሱ ተያይዞ ተከታትሎ መጣበት ። ውርደቱ ፣ አስራምስት አመት የደከመ በት ትምህርት ውሀ በልቶት መቅረቱ ፣ ከፍተኛ ትምህርት ተምሮ በተ ማረው ትምህርት ‘ ደከመኝ ’ ሳይል ወገኑን ለማገልገል የነበረው ምኞት ከንቱ ሆኖ መቅረቱ ፣ ስራ አጥቶ መንገላታቱ ፣ ከሶፊ ጋር ለመ ጋባት ያቀደው ከንቱ ምኞት ሆኖ መቅረቱና እነዚህን የመሰለው ሁሉ መውደቁን ተከትሎ ፣ መውደቁን አጅቦ በሚያስፈራ ሰልፍ ተሰልፎ

@OLDBOOKSPDF

ሲመጣ ታዬውና የሚሄድበት ፣ የሚገባበት እንደ ጠፋው ፣ ግብኑና ተነስቶ ፣ ወዳንድ አቅጣጫ አራት አምስት እርምጃዎች ከተራመደ በሁዋላ ቆመ ። ከዚያ እንደገና ተቀምጦበት ወደ ነበረው ቦታ ሂዶ ቆመና ‘ወደ ማን ልሂድ ፣’ አለ ፣ ድምጹን ከፍ አድርጎ ። ‘ወደ እንትዋን ወደ ህግ ክፍል አሳፊ ፣ ወይስ ወደ ሊቀ መንበሩ ፣ ምን ለማለት ፣’ ከዑሌጁ ሹማምት ወደ ማን እንደሚሄድና ሂዶ ምን እንደሚል ቅጡ ጠፍቶት ፣ እንደ ታገተ አውሬ ወዲያ ወዲህ እያለ ብቻውን ሲናገር ፣ የተመለከተው ቢኖር እብድ ባለው ነበር ! በመጨረሻ ሁሉንም ትቶ ወደ ቤቱ ሂደ ።

ሌሊቱን እንቅልፍ ባይኑ አልዞረም ። “የወንድይራድ ጥረት የኔ ንና የሶፊን ጋብቻ ለማሰናከል ከሆነ ፣ ከዚህ የበለጠ መሰናከል የሰይጣ ናት እለቃ ራሱም መፍጠር አይችል ! መቸም ትምህርቴ እንዲህ በውዝፍ ከቀረና ትምህርቴን ጨርሼ ራስ የሚያስችል ስራ ካልያዝሁ ሶፊን ማግባት አልችልም ። እሳማው ፣ የፈለገው ይህ ከሆነ ፣ ሆነለት ! ሶፊ እንዳለችው ባይጠቀምም ተበቀለ ! እንትዋንስ ፣ ያንትዋን ጥቅም እንጂ በቀል አይደለም ! እንተዋን በጣም ጥቅም ወዳጅ መሆኑ የታወቀ ነው ። የጥቅም ፍቅር የጸናበትም በዚያው መጠን ህሊናው የደከመ ወይም ጨርሶ የሞተ መሆን አለበት ፣ ‘ይሉኝታና ጥቅም ባንድ አይገኙም’ የተባለው ለዚህ ነው ! ስለዚህ ህሊና የለሹ ፣ ይሉኝታ ቢሱ ፣ እንተዋን ለጥቅም ሸጠኝ !” እያለ አልጋው ላይ እንደ ተንጋለለ አይኖቹን በጨለማው አፍጦ ብቻውን ሲሙዋገት ፣ አንዳንድ ጊዜ ወንድይራድንም እንትዋንንም ገድሎ ቢያመልጥ ፣ ወይም ቢያዝ ሊደርስ የሚችለው መልካምና ክፉ ነገር ሁሉ በዬመልኩ እዬተለዋወጠ ሲታዬው ከዚያ እንትዋንን ከሶ በጉባኤ ካስወቀሰው በሁዋላ እንደ ተለመደው ከታላቅ ማእርግ ጋር ሲያልፍ ፣ ወይም ያንትዋንን ስም በከንቱ ስላጠፋ እሱ ተወቅሶ ከትምህርት ቤት ሲወጣ ፣ ይህ ሁሉ ተሰብስቦ በራሱ ሲታመስ ፣ ሲተራመስ ፣ ሌሊቱ ከተገባደደ በሁዋላ ፣ ሁሉንም ትቶ ለመድገም መጠዬቁ የተሻለ መሆኑን ወሰነ ።

በነጋው ወደ ህግ ክፍል አሳፊ ሂዶ ፣ ካንደኛ ደረጃ ጀምሮ ሁለተኛ ደረጃውን እስኪጨርስ ሁለት ጊዜ ብቻ ሁለተኛ ከመሆኑ በቀር አንደኛ እዬሆነ ፣ የገባበትን ክፍል ሁሉ እዬመራ የመጣ ለመሆኑና ኮሌጅ ከገባም ፣ ባለፉት አመታት ፣ ከታላቅ ማእረግ ጋር ለማለፉ ማስረጃውን ካሳዬ በሁዋላ ፣ ባለፈው ፈተና ፣ “ወድቀሀል” የተባለውን ፈጽሞ የማያምን ቢሆንም ፣ እስተማሪውን በነውር መክሰስና ማሳጣት ለሱም

@OLDBOOKSPDF

ሆን በጠቅላላው ለትምህርት ቤቱ መልካም አለመሆኑን በመገንዘብ፣ ሁሉንም ትቶ ለመድገም እንዲፈቀድለት ብቻ የሚለምን መሆኑን በጣም አስተዛዝኖ ተናገረ ።

“ጥላሁን ፣ በህግ ክፍል በጣም ከምንኮራባቸው ተማሪች አንደኛው፣ የመጀመሪያው አንተ ስለሆንህ መውደቅህን ስሰማ ኩመጠን ያለፈ ነው ያዘንሁ፤ እመነኝ ! ብቻ . . . በተለይ ዘንድሮ በዩክፍሉ ከታች ወደላይ የሚያልፉት ተማሮች ብዛት ፣ በክፍልም ሆነ በሌላው ድርጅት ከኮሌጁ አቅም በላይ በመሆኑ ፣ የወደቀ ተማሪ ምንም ቢሆን እንዳይደግም ጥብቅ ውሳኔ ስላለ ፣ አብሬህ ከማዘን በቀር ምንም ላደርግልህ አልችልም ፤ በግድ ሂደን ሊቀመንበሩን እንለምናቸው ትል እንደሆን አብሬህ ልሂድ” አሉ የህጉ ክፍል አላፊ ። ከዚያ ጥላሁንን አስከትለው ወደ ሊቀመንበሩ ሄደው ፣ ጥላሁን ኮሌጁን ከሚያኮሩ ተማሪዎች የመጀመሪያው መሆኑን እዩመሰከሩ ፣ ልዩ አስተያየት ተደርጎ ለመድገም ይፈቀድለት እንደሆን ቢጠይቅዋቸው ፣

“ጥላሁን ምን አይነት ተማሪ መሆኑን አውቃለሁ፤ ምስክር አልሻም ። ብቻ ልዩ አስተያየት የሚባለው አንድ ጊዜ አይጀመር እንጂ ከተጀመረ የት እንደሚያልቅ መወሰን አስቸጋሪ ነው ። አንድ ጊዜ በልዩ አስተያየት በር ከከፈትን ፣ በዚያ እንግባ የሚሉት መብዛታቸው ስለማይቀርና እንዲያ የሚሉትን ሁሉ መቀበል ስለማንችል ፣ ዘንድሮ . . ልዩ አስተያየት የለም ፤ በጣም አዝናለሁ ” አሉ ሊቀመንበሩ ፣ የጅ ሸንጣቸውን ይዘው ለመውጣት ሲነሱ ። ጥላሁን ሁለቱን ባለስልጣኖች እዚያው እንደ ቆሙ ትቶዋቸው እዩተከዘ ወጣ ። ቁርጡን አውቆ ፣ ተስፋውን ቆርጦ ወጣ ።

ከዚያ ቀን ጀምሮ መቀመጥና ማንበብ ፣ ማጥናት ፣ መጻፍ ስላቃተው ፣ ቀኑን ሙሉ ሲዞር እዩዋለ ይገባ ጀመር ። እቤቱ ገብቶ ሲቀመጥ ፣ ከፉው አሳብ ሁሉ ባንድ ላይ ተሰብስቦ ፣ ተደበላልቆ ፣ ከፀሀሪው የበለጠ መልኩን አክፍቶ ፣ በራሱ ውስጥ ሲታመስና ሲተራመስ ፣ ከቦ ሊበላው ያሰፈሰፈ መስሎ ይታዩውና ቤቱን ጭምር ፈርቶት ፣ ጠልቶት ወጥቶ ወደ ከተማ ይሸሻል ። ራሱን ፈርቶ ፣ ከራሱ ሸሽቶ ወደ ከተማ ይሄዳል ! ሶፊ ልታጽናናው ፣ ልታበረታታው ትመጣና ገና ስታዩው ከሰላምታዋ እንባዋ እዩቀደመ ፤ እንደገና እሰዋን ማጽናናቱ ስለባሰበት ፣ ከራሱም ሆነ ከሰዋ ሸሽቶ የሚያመልጥበት ፣ የሱም ሆነ የሰዋ ጭንቀት እንዳይታዩውና እንዳይሰማው ለጊዜው ማታለያ ፣ መሸንገያ ፍለጋ ወደ ከተማ ይሄዳል !

@OLDBOOKSPDF

የመውደቂንና [illegible] ያለመቻሉን መርዶ ከሰማ በሁዋላ ፡ በተ ከተሉት ጥቂት ቀኖች ፡ አዲስ አበባን ከዳር እስከ ዳር አዳርሶ ፤ አፋዊ መልክዋን ብቻ ሳይሆን ውስጠ - ምስጢርዋን ጭምር አዩ ፤ አወቃት። ችግሩን የሚያስረሳው የመሰለው ሁሉ አንድ አልቀረውም ። በዩሲኒማ ቤቱ ፡ በዩ ቡና ቤቱ ፡ በዩጠጅ ቤቱ ፡ በዩሱቁ ፡ በያደባባዩ ፡ በዩ ቤተክርስቲያኑ ፡ በዩመስጊዱ እየዞረ ፡ ይገባና ፡ በገባበት ሰው ጠፍቶት እንደሚፈልግ አይኖቹን እያዘዋወረ ትንሽ ሲመለካከት ቆይቶ ይወጣል። ከዚያ እንዱን አስፋልት መንገድ ይዞ ፡ ዳር ዳሩን በልዩ ልዩ ቅጥና መልክ የተሰሩትን ጥሩ ጥሩ ቤቶችና የሚኖሩባቸው የውጭ አገር ሰዎች መሆናቸውን አይቶ ፡ የመቆጨት ይሁን የመገረም ለይቶ የማያውቀው ስሜት ስለሚሰማው ፡ ሳያስበው ራሱን በመገረም እዩወዘወዘ ሲሄድ ይቆይና ፡ ያን ትቶ ሰርጥ መንገድ ሲያገኝ ፡ እዚያ ገብቶ አይቶት የማ ያውቀውን ጉዳ - ጉድ ሁሉ ያያል ። አንድ ቀን እንደ መስንበቻው አስ ፋልቱን መንገድ ይዞ ሲሄድ ፡ ወደ ጎን የሚያስገባ ኮረኮንች ሰርጥ መን ገድ አገኘ ። እዚያ ትንሽ ቆም ብሎ ሲያመነታ ከቆዩ በሁዋላ ፡ አስ ፋልቱን ትወና ኮረኮንቻውን መንገድ ተከትሎ ገባ ሲል ፡ ቆሻና ግራ የተሰሩት አርጌ የንጨት ቤቶች ሁሉም እድሜያቸውን በኖራና በሌላ ልዩ ልዩ ቀለም ሸሽገው ፡ የሚበዙት በራቻውን በዝጉርጉር የጨሌ መጋ ረጃ አስጊጠው ፡ በዚያ የሚያልፍ ወንድ ካንዱ ቢያመልጥ ሌላው እንዳ ይስተው ፡ በተጠንቀቅ ተሰልፈው የሚጠብቁ መስለው ያገኛቸዋል ፤ ባንዳንዱ በራፍ ከቀለሙና ከጨሌው መጋረጃ የበለጠ ቤቱን አስጊጠው አድምቀው የሚያሳዩ ጥሩ ጥሩ ቆንጃጅት ፡ ጨሌውን ግራና ቀኝ ገለጥ አድርገው ፡ እመሀል ቆመው ይታያሉ ። ካንድ ይሁን ከሁለት ዓመት በፊት ፡ ሴትኛ አዳሪዎች ሁሉ ከዋና ዋና መንገዶች እየለቀቁ ወደ ውስጥ ገብተው እንዲሰፍሩ ታዝዞ ስለነበረ ፡ ያ የነሱ ሰፈር መሆኑን ተረድቶ ፡ እንዲያ ባለው ሰፈር እንግዳ በመሆኑ ፡ ትንሽ እንደ ማፈር ይልና አንገቱን ደፍቶ ሲሄድ ፡ ‘ጋሽ !’ ትለዋለች የመጀመ ርያዋ ፤ እንዳልሰማ ዝም ብሎ ያልፋል ። “የኔ ሸጋ !” ትለዋለች ሁለ ተኛዋ ። አሁንም ልቡ ፈጥኖ እዩመታ ፡ ዝም ብሎ ያልፋል ። ‘ፍቅሬ’ ትለዋለች ሶስተኛዋ ። ጥላሁን የራሱን አሳብና የግሮቹን ርምጃ ማስተባበር አቅቶት ፡ ባሳቡ ‘ልግባ አልግባ’ እያለ ሲያመነታ እግ ሮቹ ርምጃቸውን ስለሚቀጥሉ ፡ ብዙዎቹን ቤቶች አልፎ ወደ መጨረ ሻው ለመድረስ ሲያቃርብ ፡ የምትጋብዘው ልጅ ብታምርም ባታምር ፡ ቀና ብሎ እንኳዋ ሳያያት ዝም ብሎ ይገባል ። እዚያ ቆይቶ ራሱን እዩወቀሰ ፡ እዩተናደደ ይወጣና ወደ መጣበት እንዳይመለስ ግብዣዋ

@OLDBOOKSPDF

ውን የገፋባቸውን ልጆች ፈርቶ ፣ በወር ብሎ እንኳ ሳያይ ፣ ወደ ፊት መሄድ እንደ ጀመረ ፣ በኮረኮንቻው መንገድ ጎን ስርጾ ወደ ውስጥ የሚገባ ረዥም የጭቃ መንገድ ሲያገኝ ፣ ቶሎ እዚያ ገብቶ ጉዞውን ይቀጥላል ። በዚያ የጭቃ መንገድ ዳር ዳር የሚታዩት ቤቶችና እዚያ የሚኖሩት ሰዎች ደግሞ ሌሎች ናቸው !

በዚያ ጭቃ መንገድ ቀኝና ግራ ፣ በወጣ ገብ መስመር ተቀጣጥለው እስከ መጨረሻ የሚታዩት ቤቶች ፣ ጣራዎቻቸው ካሮጌ ቆርቆሮ ቁርጥራጭና ከሳር ባንድ ላይ የተደረተ ድሪቶ ለብሰው ፣ የሚበዙት ምርጋቸው እየተቀረፈተ ስለ ወደቀ ፣ ግድግዳና ማገራቸው ብቻ ገጠሊጋቸው ያለቀና እጥንቃቸው ተቀጣጥሎ የቆመ አስከሬኖች መስለው ፣ ሁሉም ወደ ጎን አሽገድደው ቆመው ሲታዩ ፣ ሳይወድቁ ቢውሉ ሳይወድቁ የሚያድሩ ፣ ቢያድሩ የሚውሉ አይመስሉም ! የመንገዱና የግራ ቀኝ መፋሰሻዎች ጭቃ ፣ ከመሬት አፈርና ከሰማይ ዝናብ ሌላ ፣ የጸዳት ቦታ ከሌላቸው ቤቶች ጥግት ጥዋት እየወጣ የሚፈሰው ቆሻሻ ተጨምሮበት ፣ ያዘባ እንጂ የጭቃ መልክ የለውም! የሰፈሩ ህጻናት ብዛት ሲታይ ፣ ከያንዳንዱ አሮጌ ቤት ስር እንደ ምስጥ የሚፈሉ እንጂ “እኒያን ሁሉ የቤቱ ባለቤቶች የሚወልዱዋቸው ናቸው” ብሎ ማመን ያስቸግራል ! ሁሉም አይኑ በሽተኞች ፣ ሁሉም ፊታቸው በሙሉ አፍንጫ ብቻ እንደ ሆነ ሁሉ ንፍጥ የሚታይበት ፣ ሁሉም እንዳልታጠበ የወተት ዕቃ ዝንብ የሰፈረባቸው ፣ ሁሉም ሆዳቸው አካላታቸውን ጭምር እንደሚበላ ከሆድ በቀር ሌላ አካል ጎልቶ የማይታይባቸው ፣ ሁሉም እንደ ህጻናት ከመጫወት እንደ ገገምተኛ መብላት ብቻ የሚያምራቸው ፣ ሁሉም አውር እድል ከድሆች እንዲወለዱ ስላደረጋቸው ብቻ ፣ የህጻናትን መብት ተነፍገው ፣ ገና ከመወለዳቸው በበሽታና በችጋር ወህኒ ኖረው እንዲያረጁ የተፈረደባቸው ናቸው ! እንዲያ ባለው መንገድ ከቤት እናቶችና ከህጻናቱ በቀር ብዙ ወንዶች አይታዩም ። ህጻናቱ አንዳንድ ቦታ በሳር ላይ ተኝተው ፣ አንዳንድ ቦታ ተቀምጠው ፣ አንዳንድ ቦታ እንደ መቃብር ሀውልት ዝም ብለው ቆመው ይታያሉ ። እንዲሁም ባንዳንዱ ቤት በር-አፍ ከሰፈረባቸው ዝንብ ጋር እንደ ዶሮ ሚጩት እናቶቻቸውን እመሀል እያደረጉ ከበው ሲንጫጩ እሚታዩ አሉ ።

“እማ . . . ማ ፣ ን . . . ፍሮ . . !” ይላል ባንዱ ቤት በር አፍ እናቶቻቸውን ከበው ከተቀመጡት ህጻናት አንዱ - በልቅሶ ዜማ ። ‘ን . . ፍሮ . . !’ ይላሉ ፣ እህቶቹና ወንድሞቹ ዜማውን ተቀብለው ።

@OLDBOOKSPDF

“ቆዩ አልበሰለ . . . ም እለሁ ዋዮሁት ! ቅጠሉም ፣ ኩበቱም ርጥብ ሆኖ እዩጢስ እሳቱ አልነደ ስላለ አልበሰለም ፤ እባካችሁ ትንሽ ቆዩ ትላለች እናትዬዋ ።

“ን . . . ፍር ! ” ይላሉ በሌላው ቤት በር - አፍ እናታቸውን ከበው የተቀመጡት ህጻናት ፣ እንደ ሌሎች በልቅሶ ዜማ ።

“የሰጠሁዋችሁ ይበቃችሁዋል ፣ የተረፈው ያባታችሁ ነው ፣ ሁሉ ንም አራግፌ ለናንተ ሰጥቸ ለሱ ምን ላቆዬው ? ሰጋዩን ላቀርብለት ነው ? ” ትላለች እናትዮዋ ፣ ልጆችዋንም ፣ እድልዋንም እያማረረች ።

ጥላሁን ከሰራምስት ዓመት በላይ አዲስ አበባ ሲቀመጥ ፣ እንዲያ ያለ መንገድና ባካባቢው እንደሚታዬው ያለ ጉድ አይቶ አያውቅም ። ስለዚህ ፣ ምንም እንኩዋ እዚያ እዬኖረ ላለመደው ፣ ባካባቢው የሚ ታየው ሁሉ እጅግ የሚያስቅቅና ከሽታው መከፋት የተነሳ ወደ ውጭ ካልሆነ ወደ ውስጥ መተንፈስ ስለማይቻል ፣ አልፎ እስኪሄዱ የሚያ ስጨንቅ ቢሆን ፣ ያን የኑሮ ዝቃጭ ፣ ያን የኑሮ አተላ የሚኖሩት ፍጥ ረቶች ሁኔታ ሁሉንም ያበረሳውና ፣ ቆሞ ሲመለከት ፣ እናቶቻቸውን ከበው በልቅሶ ዜማ ንፍሮ የሚለምኑት ህጻናት ሁሉ የዝንብ ሰራዊታ ቸው እጅቦዋቸው እየሮጡ መጥተው እሱን ይከቡና ፣ “ጋሽ ቆሎ እግዛ ብት ፍራንክ ፣ ጋሽ ንፍሮ እገዛበት ፍራንክ ፣ ጋሽ ዳቦ እገዛበት ፍራ ንክ ፣ ጋሽ ለናቴ እሰጣት ፍራንክ ፣ ፍራንክ ፣ ፍራንክ ፣ ፍራንክ ! ” እያሉ ሲንጫጩበት ፣ ከነርሱም ፣ ከዝንቡም ቶሎ ለመገላገል ፣ ያለ ውን ሳንቲም ሁሉ አራግፎ አከፋፍሉዋቸው ሸሽቶ ወደ ቤቱ ይመለ ሳል ።

ጥላሁን ፣ ከተማ ለከተማ መዞር የጀመረው ፣ ሰሞኑን የገጠመው ከፉ እድል ያስከተለው ብስጭት እንዳይሰማውና የሶፊያን ሀዘን እንዳ ያይ ፣ ማታለያ ፣ መሸሸጊያ ፍለጋ ነበር ። ብቻ ማታለያ ምን ጊዜም ቢሆን ከማታለያነቱ አልፎ መድሀኒት ሲሆን ስለማይችል ፣ ሲዞር ውሎ ሲገባ በሽታው ፣ ሸሽቶት የሄደው የሚያስፈራራ አሳብ እቤቱ ይቆ ዬዋል ! እንዲያውም ከተማ ለከተማ ሲዞር በዬመንገዱ ፣ በያደባባዩ ፣ በዬቤተ ክርስቲያኑ ፣ በዬመስጊዱ የሚያየው የችግረኛው ፣ የበሽተኛው ፣ የለማኙ ፣ ኧረ የስንቱ ብዛትና ሁኔታ ! ነገ እሱ ስራ አጥቶ ሲቸገር ሊደ ርስበት የሚችለውን እያሳሰበ ፣ ከቦ የሚያስፈራራውን አሳብ በማስረ ሳት ፈንታ ፣ የባሰውን ያስፈራራው ስለ ጀመረ ፣ በመጨረሻ መውጣ ቱን ትቶ ፣ ከከበበው አሳብ ጋር ትግሉን ቀጠለ ።

"ህ! ግሩም@OLDBOOKSPDF አለ አንድ ቀን! አሊጋው ላይ እንደ ተንጋለለ እጆቹን በራሱ ሁዋላ አወሳስቦ ተንተርሶ ፣ አይኖቹን እጣራው ላይ ተክሎ፣ በራሱ ውስጥ የሚተራመሰውን ያሳብ መንጋ ዝም ብሎ ሲያይ ቆይቶ ።

"ግሩም ነው! ስምንት ዓመት አንደኛ ደረጃ፣ አራት አመት ሁለተኛ ደረጃ፣ ሶስት አመት ኮሌጅ፣ አስራምስት ዓመት! ያስራምስት አመት ትምህርት፣ ያስራምስት አመት ድካም እንዲሁ ከንቱ ሆኖ፣ እንዲሁ ውሀ በልቶት መቅረት! ወይ ወንድይራድ! ያን ያክል ስወድህ፣ ያን ያክል ሳምንህ፣ ሳላውቅ ብበድልህስ የተቀየምህ መሆንህን ሳትነግረኝ፣ በፊትህ እንኩዋ ሳታሳዩኝ እንዴት በመበቀል ታሳውቀኛለህ? እውነትም ሶፊ እንዳለችው ፈሪ ነህ! 'ፈሪ የወዳጅ ጠላት ተሸሽጎ ነው የሚጎዳው' ያለችው እውነትዋ ነው። ፈሪ የወዳጅ ጠላት ስለ ሆንህ፣ ሳልጠረጥርህ በወዳጅነትህ ተሸሽገህ ገደልከኝ! ያውም ክፉ አገዳደል! ስትገድለኝ ብቻ ሳይሆን፣ ከገደልከኝ በሁዋላም ስቃዩ ሲሰማኝ የሚኖር አገዳደል!"

ጥላሁን ወንድይራድን ካለበት ባሳቡ እምጥቶ፣ እፊቱ አቁሞ፣ ሲዘልፍና ሲወቅስ፣ በሩ መጀመሪያ በለስታ፣ ሁዋላ በሀይል ሲመታ ሳይሰማ ቆይቶ፣ በመጨረሻ ሰማና ከንቅልፉ እንደ ባነነ ደንግጦ ሄዶ ሲከፍት፣ አሰፋ በረደድ የሚባለውን ጉዋደኛውን ፊት ለፊት ቆሞ አገኘው። አሰፋ መደንገጡ ከፊቱ ይታይ ነበር።

"ደህና ነህ?" አለ አሰፋ።

"ምን ምን ሆነህ? ደህና አደለህም?" አለ ጥላሁን በፈንታው፣ የጉዋደኛውን ድንጋጤ ከፊቱ ሲያይ።

"ደህና አደለህም ወይ ስልህ ደህና አደለህም ወይ ትለኛለህ?"

"ደንግጠህ ሳይህ ጊዜኮ ምን ደረሰብህ ብዬ ነው።"

"መኖርህን የጎረቤትህ ልጅ ነገሮኝ ከሩብ ሰአት በላይ በሩ እስኪሰበር ብደበድብ መልስ ሳጣ ጊዜ በጣም ደንገጥሁ።"

"በጣም አዝናለሁ፤ አልሰማሁም" አለ ጥላሁን፣ የጉዋደኛውን እጅ ይዞ ወደሚቀመጥበት ወንበር እዬመራ።

"ተኝተህ ኖሮዋል?" አለ አሰፋ፣ ሁለቱም ከተቀመጡ በሁዋላ።

"የምን እንቅልፍ? ወንድሜ! እንኩዋንስ ቀን ሌሊት መተኛት አቅቶኛል!"

@OLDBOOKSPDF

"ታዲያ እንዴት ነው ያን ያክል በር ስመታ ያልሰማኸኝ ? መጀመርያ እንደ ደንቡ ለስስ አድርጌ መታሁ ፤ ከዚያ መልስ ሳጣ ጊዜ ፣ ጠንከር አድርጌ እመታ ጀመር ። ለዚያም መልስ ስላጣሁ ፣ የለህም ብዬ መንገድ ስጀምር ፣ ቆሞ ይመለከተኝ የነበረ የጐረቤትህ ልጅ እቤት ውስጥ መኖርህን አረጋግጦ ስለ ነገረኝ ፣ እንደ ገና ተመልሼ በሩ እስኪሰበር በኃይል እደበድብ ጀመር ።"

"የሞትሁ መስሎህ ኖሮዋል ?" አለ ጥላሁን ፣ የቅርታ ፈገግታ ፈገግ ብሎ ።

"እረ ጠላትህ ይሙት ወንድሜ ! ምን በወጣህ ? ብቻ . . ወደ ኮሌጅ ብቅ ሳትል ስለ ሰነበትህና ፣ አሁን ደግሞ መኖርህን ልጁ ከነገረኝ በሁዋላ ፣ በሩን በሀይል ብመታ መልስ ስላጣሁ ፣ የተኛህ መስሎኝ ነበር ማለቴ ነው እንጂ . . . ሞትማ ለምን ?"

"ወደ ኮሌጅማ ምን ላደርግ እመጣለሁ ?" አለ ጥላሁን ፣ ፊቱ ትንሽ እንደ መከረር ሲል እዩታዩ ።

"እሱስ እውነትህ ነው ! ለጊዜው መምጣት አያስፈልግም ። ብቻ ለወደፊቱ . . . ሶፊም ፣ ሌሎች ጉዋደኞችህም ስላሉ ሲመችህ ብቅ ብትል ፣ ከኮሌጅ ጋር ግንኙነትህን ባታቋርጥ . . . መልካም ነው ብዬ ነው ። በኮሌጅ . . ብዙ ወዳጅ አለህ ! ሁሉም ወዳጅህ ነው ! እውነቱን ነው የምነግርህ ጥላሁን ፤ ዘንድሮ ባንተ በደረሰው ያላዘነ አንድ የለም !" አለ አሰፋ ፣ በጥላሁን ፊት የቁጣ ምልክት ስላዩ እሱ በተናገረው የተቆጣ መስሎት–ሲናገር እዩተደናገረው ።

"ሀ ! በኔ በደረሰው ያላዘነ አንድም የለም ! አንትዋንና . . . አዎ ፤ ሌላው ግዴለም ፤ አንትዋንም በኔ በደረሰው አዘነ ? " አለ ጥላሁን ፣ የወንድይራድን ስም ካፉ ሊወጣ ሲል እንደገና መልሶ ውጦ ።

"ያንትዋን ስሜት በተለይ እንዴት እንደ ሆነ አላውቅም ፤ ብቻ በጠቅላላው በኮሌጅ ስላንተ ያላዘነ እንደሌለ አውቃለሁ ።"

"አንትዋን አያዝንም ፤ ፈተናየን በትክክል መስራቴን እያወቀ ጥሎኝ ሊያዝን አይችልም !"

"ፈተናህን በትክክል ለመስራትህ ርግጠኛ ከሆንህ በምን ምክና ያት የሚጥልህ ይመስልሀል ? በመሀከላችሁ ቂም አለ ? ወይስ . . ምንድነው ? አልገባኝም ! "

"የቂም አደለም ፤ የጥቅም ጉዳይ ነው ። እዩህ ? አሰፋ !" አለ ጥላሁን ፣ የቀኝ እጁ ጣቶቹን ዘርዘር አድርጎ ላሰፋ እያሳዩ ። "የተሰጡኝ ጥያቄዎች እንደነዚህ አብረውኝ እንደሚኖሩት ጣቶች ደህና አድ

@OLDBOOKSPDF

ርጌ የማውቃቸው ናቸው ! እንዳንተዋን ልቡ በፍቅረ - ንዋይ ሰክሮ አእምሮውን ያልሸፈነው ፈታኝ ቢጠይቀኝ መልሳቸውን ተቀምጦ ማሰብና በወረቀት መጻፍ ሳያስፈልገኝ ፣ ቆሜ ፣ ያላንድ ስህተት በቃሌ መስጠት እችላለሁ ! ”

“የምን ጥቅም ነው ? አንትዋን አንተን በመጣል የሚያገኘው ጥቅም ምንድነው ? ”

“እሱን ለጊዜው እንተወው ፤ ጊዜ ይግለጸው ! ”

“እሺ እሱን እንተወው ፤ ጊዜ ይግለጸው ። ፈተናህን በትክክል ለመስራትህ ይህን ያክል ርግጠኛ ከሆንህ ፣ ለምን እንደ ገና እንዲታይ ልህ ፣ እንዲመረመርልህ አትጠይቅም ? ”

“መጀመርያ ፈተና እንደ ገና እንዲታይ ለማድረግ ገንዘብ ማስያዝ አለ ! የማስይዘው ገንዘብ ከየት አመጣለሁ ? ሁለተኛ ገንዘቡ በታምር ተገኝቶ ፈተናው ይታይ የሚባል ቢሆን ፣ ማነው የሚያየው ? እዚህ ያሉት አስተማሪዎች አይደሉም ? ታዲያስ ! እዚህ ያሉት አስተማሪዎች፣ ‘ተማሪው አልተሳሳተም ፤ የተሳሳተው አስተማሪው ነው ’ ለማለት እውነትና ድፍረት ያላቸው ናቸው ? ዛሬ አንትዋን በኔ ያደረገውን በዩጊዜው ካሁን ቀደምም ፣ ወደፊትም በሌሎች ተማሮች ያላደረጉና የማያደርጉ ናቸው ? ወይስ ዛሬ አንትዋንን ማጋለጥ ራሳቸውን ማጋለጥ መሆኑን የማያውቁ ደንቆሮዎች መሰሉህ ? ይህ እንኳዋ ከንቱ ነው ፤ እንተወው ። ከዚህ የበለጠ ያሳዘነኝ ሌላ ነው ! ”

“ምን ? ” አለ አሰፋ ፣ የልቡን ሐዘን እንደ መስተዋት የሚያሳይ ፊቱን ወደ ጉዋደኛው መለስ አድርጎ ፤

“እንዳልደገም መከልከሉ ። ”

“እሱ እንኳዋ መችም . . ደንቡ ነው ። ስለዚህ የሚወቀስ ቢኖር ደንቡ ነው እንጂ ሰው አይደለም ። ደንቡም ቢሆን የኮሌጁን ደረጃ ከሌሎች አገሮች ኮሌጆች ተመዛዛኝ እንዲሆን ታስቦ የወጣ ነው ። ”

“አውቃለሁ ፤ ብቻ ያሳዝናል ! ”

“ ምኑ ? ”

“ሁሉም ። የደንቡም ሆነ የባለስልጣኖች ሁኔታ ሁሉ በውነት የሚያሳዝን ነው ! ”

“እንዴት ? ! ”

“ከየት ጀምሬ ልንገርህ ? እስቲ . . ደንቡን ላቆይና ስለ ኮሌጅ ባለስልጣኖች አሰራር ልጠይቅህ ። ይህ ደንብ የሚባለው እያለ ብዙ ባንዳንድ ነገሮች ያላለፉ ተማሮች ልዩ አስተያየት እየተደረገላቸው ደግመው አያውቁም ? ”

@OLDBOOKSPDF

"እዎ ! የተማረው ክርያ·ግብ ችሎታ ብርቱ መሆኑ ከታወቀ ፣ ባንዳንድ ነገር ባያልፍም ልዩ አስተያየት ይደረጋል ።"

"እየውልህ እንግዲህ ! እኔ ከንደኛ ደረጃ ጀምሬ እዚህ እስከደ ርስ ፣ አንድ ጊዜ እንኩዋ ባንድ ነገር ወድቄ አላውቅም ! በሁለተኛ ደረጃም ሆነ ባለፉት አመታት የኮሌጅን ፈተናዎች ከማእረግ ጋር ሳልፍ የቆዩሁ ነኝ ! ከዚህም ሁሉ ሌላ" አለ ጥላሁን ፣ አንገቱን ቀና አድ ርጎ ከስሜት ጋር ። "ከሁሉም የበለጠ የምኮራበት ፣ ሁለተኛ ደረጃ ከደረስሁ በሁዋላ መንግስት እስኪረዳኝ ድረስ ፣ ያዳሬ ተማሪዎችን ጫማ ጠርጌ ፣ ልብስ አጽድቼ ፡ በሚልኩኝ ሁሉ እየተላከሁ የነሱን ፍርፋሪ በልቼ ፣ ውራጃቸውን ለብሼ ፣ ከዘበኛ ጋር አድሬ የመጀመርያ ደረጃ ትምህርቴን የጨረስሁ ነኝ ! ለዚህ ሌላ ምስክር አልጠራም ፤ ላገ ልግሎቴ ዋጋ ፍርፋሪያቸውንና ውራጃቸውን ይሰጡኝ ከነበሩት መሀ ከል አንዱ ምስክር አንተ ነህ ! ታዲያስ ! ልዩ አስተያየት የሚባል ነገር ከኖረ ፣ እንዲህ ባለ ችግር አልፎ ፣ እንዲህ ያለውን ችግር አሸንፎ ፣ እዚህ ለደረሰ ፣ ያ ልዩ አስተያየት ሊደረግለት አይገባም ?"

"በኮሌጅ ውስጥ ስላንተ ያላዘኑና ያልተቆረቆረ የለም ያልሁህኮ ይህን ሁሉ በመመልከት ነው" አለ አሰፋ ፣ አንገቱን ደፍቶ እዬ ተከዘ ።

"ነገር ግን በኮሌጅ ባለስልጣኖች ዘንድ ፣ እንዲህ ያሉት ተማ ሮች ዋጋ የላቸውም ! በነሱ ዘንድ ፣ ልዩ አስተያየት ሊደረግላቸው የሚገባ ፣ በልዩ ጊዜ ልዩ ዋጋ ሊከፍሉ ይችላሉ ለሚባሉት ነው እንጂ እንደኔ ላሉት አይደለም ! በል እንግዲህ ይህን እንተወው ፤ ግዴለም ! አሁንም ይህን እንተውና ደንብ ስላልኸው እንነጋገር ።" አሰፋ አንገ ቱን እንደ ደፋ እዬተከዘ ዝም አለ ።

"ከሁሉ አስቀድሞ" አለ ጥላሁን ፡ እሱም ዝም ብሎ ትንሽ ሲያ ስብ ቆዩና ። "ከሁሉ አስቀድሞ ፡ ደንብ ከባለቤት እንጂ ከምንደኞች ሊወጣ አይገባም ። የሚፈልገውን እንደሚፈልገው አስርቶ የሚጠቀም በትን ደንብ ማውጣት የባለቤት ፈንታ ነው እንጂ ፡ ለሥራ የሚቀጠሩ ምንደኞች ፈንታ አይደለም ! የናንተ ደንብ ግን ፣ ምንደኞች ለነሱ እን ደሚስማማ አድርገው አውጥተው ፣ ባለቤቱ ጥቅምና ጉዳቱን ሳያይ ፣ እንዲሁ አይኑን ጨፍኖ የተቀበለው ነው ። የዚህ ደንብ አላማም ቅድም አንተ እንዳልኸው የኮሌጁን ክብር መጠበቅ ነው ። መልካም ! የደ ንቡ አላማስ ይህ ይሁን ፤ በጠቅላላው የትምህርቱ አላማስ ወጣቶችን በብዛት እንደዬችሎታቸው ፣ እንደዬዝንባሌያቸው ልዩ ልዩ ትምህርት

@OLDBOOKSPDF

አስተምሮ ኢትዮጵያን ባጭር ጊዜ ራስዋን ማስቻል ነው? ወይስ እነ ዚህንም ጥቂቶችን ፣ ብዙ ደክመውና ተደክሞባቸው ፤ ይብዛም ይነስ ፍሬ በሚሰጡበት ጊዜ አንገታቸውን እዬቀሰፉ ለኮሌጁ ክብር መስ ዋእት አድርጎ ማቅረብ ነው ? እስቲ መልስልኝ ፤ በል መልስልኝ ።"

እስቲ አባክህ አትበሳጭ ! አለ አሰፋ ፣ ጥላሁን እዬተበሳጨ ስለ ተናገረ ።

"መቸም በጠቅላላው" አለ ቀጠለና ። "በጠቅላላው የትምህ ርቱ አላማ የኮሌጅን ክብር ለመጠበቅ ሳይሆን ፤ የኢትዮጵያን ወጣቶች እንደ ተቻለ በብዛት በልዩ ልዩ ትምህርት ማሰናዳት መሆኑ የታወቀ ነው ። ነገር ግን የኮሌጁ ከፍተኛ ደረጃ ካልተጠበቀ ፣ ከዚህ ጨርሰው ለከፍተኛ ልዩ ትምህርት ወደ ውጭ አገር ሲላኩ ፤ ያንዳንድ አገር ዩኒ ቨርሲቲዎች ፣ አንድ ወይም ሁለት አመት በዝቅተኛ ትምህርት ቤት ሳያሰናዱ በቀጥታ አይቀበሉዋቸውም ። ስለዚህ የደንቡ አላማ ኮሌ ጁን ለማክበር ብቻ ሳይሆን ጊዜ ሳይባክን ከኛ ኮሌጅ ጨርሰው የሚ ሄዱ ተማሮች በቀጥታ የሄዱለትን ትምህርት ተምረው እንዲመለሱ ለማ ድረግ ጭምር ነው ።"

"የለም አሰፋ" አለ ጥላሁን ፣ እንደ ተበሳጨ ራሱን እዬወዘወዘ ፤ "የለም አሁን እንዳልኸው አይደለም ። ከዚህ ኮሌጅ ጨርሰው ወደ ውጭ የሚላኩትን ተማሮች ፣ የሰለጠኑት አገሮች ዩኒቨርሲቲዎች በቀ ጥታ የማይቀበሉዋቸው የሆኑ እንደሆነ ፣ 'የኮሌጃችን ክብር ይነካል' ተብሎ ነው እንጂ ፣ ለተማሮችም ሆነ ባገሪቱ ጥቅምስ ፣ ብዙ ዘመን የደከሙትንና የተደከመባቸውን ወጣቶች ከንቱ አድርጎ ከማስ ቀረት ፤ እንዳልኸው አንድ ወይም ሁለት አመት ለመሰናዶ መጨመር አስፈላጊ ቢሆን እንኳ ፤ እሱን ጨምሮ ትምህርታቸውን ማስጨረሱ ብዙ ጊዜ እንደሚበልጥ የታወቀ ነው ።"

"የምትለው እውነት ሊሆን ይችላል ። ደንቡን የሚደግፉ ሰዎች ደግሞ ፣ 'ያንደኛ ደረጃ ትምህርት የተቻለውን ያክል ሰፋ ብሎ ከተ ሰጠ ፣ ያገሪቱ የገንዘብና የድርጅት አቅም መጠነኛ ስለሆነ ፤ ለሁለተኛ ደረጃና ለኮሌጅ ትምህርት ፣ ብርቱዎችን ብቻ እዬመረጡ ፤ የተገኘውን መጠነኛ ገንዘብና ድርጅት ፣ ጥቂትም ቢሆኑ በነሱ ላይ ማዋሉ ይጠ ቅማል' ብለው ያምናሉ ። ይህ መቸም ያከተያየት ጉዳይ ነው ።"

"ይህ ያስተያየት ጉዳይ አይደለም ። ያስተያየት ጉዳይ ነው ተብሎ የሚታለፍ ማንንም የማይጐዳ ሲሆን ነው እንጂ ፣ ካንድ አገር ሕዝብ ፣ ከብዙ ሚሊዮን ህዝብ ኑሮ ጋር የተያያዘ ነገር ፣ ያስተያየት

@OLDBOOKSPDF

ጉዳይ ነው ተብሎ ሊታለፍ አይገባም ። 'ያንደኛ ደረጃ ትምህርት እንደ ቀቻሉ ሰፋ ብሎ ከተሰጠ ፣ ከዚያ በላይ ብርቱዎችን ብቻ እየመረጡ ማስተማር የበለጠ ይጠቅማል ' የሚሉት ኢትዮጵያ ቶሎ ራስዋን እንዳትችል የሚፈልጉ ፣ ኢትዮጵያን መጉዳት የሚፈልጉ ናቸው።”

“እንጃ ፤ ትንሽ አልጨከንህባቸውም ?” አለ አሰፋ ፣ የቅርታ ፈገግታ ፈገግ ብሎ ።

“የለም አሰፋ ፤ ይህም ሲያንስ ነው ! እዩህ ፣ ያንደኛ ደረጃ ትምህርት አሁን በሚሰጥበት ሁኔታ ፣ የገበሬ ልጅ ግብርና ፣ የነጋዴ ልጅ ንግድ ፣ ሴሎችም እንዲሁ ከዮተወለዱበት ቤተሰብና ካካባቢያቸው እንደዩባህላቸው እዩተማሩ አድገው ራሳቸውን የሚችሉበትን ስራ አስትቶ ፣ አስረስቶ በዚያ ፈንታ ምንም ሳይሰጣቸው አባክኖ ፣ መንፈሳቸውን ገትቶ ፣ አውኮ ይተዋቸዋል ። እነዚህ ልጆች በውጭ ቁዋንቁዋ ፣ ወይም ከውጭ ቋዋንቋዋ በሚብሰ ፣ እንኩዋንስ ለልጅ ላዋቂ በማይገባ ፣ ያማርኛ ትርጉም የሚማሩት ልዩ ልዩ ትምህርት ምን ማለት መሆኑን ማስተዋል እንኩዋ የሚጀምሩ በሁለተኛ ደረጃ ከቆዩ በሁዋላ ነበር ። ነገር ግን ሁለተኛ ደረጃ የተፈቀደ ቅድም እንዳልኸው ብርቱ ለተባሉት ጥቂቶች ስለሆነና ብዙው ባክኖ ፣ ቤቱ ለቤትኛ አዳሪነት ፣ ወንዱ ለሌብነትና ለወንበዴነት ብቻ ተሰናድቶ የሚለቀቅ ስለሆነ ፣ ይህን አሳብ ይጠቅማል የሚሉት ኢትዮጵያን መጉዳት የሚፈልጉ አይደሉም ትላለህ ?”

“እኮ ! እንዳንተ ምክር የሆነ እንደሆነ ፣ ብርቱውም ፣ ደካማውም ፣ ብልሁም ፣ ደንቆሮውም ባንድ ላይ ተሰብስቦ በሁለተኛ ደረጃና በኮሌጅ ይታጐር ነው የምትለው ! አይደለም ?”

“ተው እንዲህ አትበል አሰፋ ! በሽተኛ ካልሆነ ጤናማ ሆኖ የሚወለድ ሁሉ ደካማም ፣ ደንቆሮም አይደለም ። በሽተኛና አእምሮው የጎደለ ሆኖ የሚወለድ ምናልባት ከብዙ ሺህ አንድ ቢገኝ ነው ። የቀረው ሁሉም ቢያንስ ቢያንስ አንዳንድ የተፈጥሮ ዝንባሌና ችሎታ የሌለው የለም ። ችግሩ እንዲህ ያለውን ፣ በያንዳንዱ ልጅ የሚገኝ የተፈጥሮ ችሎታና ዝንባሌ በመከታተል እዩመረመሩ ፣ ሁሉንም እንደዩችሎታውና እንደዩዝንባሌው ለማስማራት ስላልታሰበበትና ፣ የትምህርቱ አሰጣጥም ለዚህ ያታቀደ አለመሆኑ ነው ። ይህ ነው ምክንያቱ አሰፋ ! የብዙ ልጆች ደካምና ያወላጆቻቸው ተስፋ ከንቱ ሆኖ የሚቀረው ፣ በትምህርቱ ድርጅትና የትምህርቱን አሰጣጥ በሚያስማሩት ሰዎች ደካማነት ነው እንጂ ፣ በልጆች ደካማነትና ደንቆሮነት አይደለም ! ብቻ

@OLDBOOKSPDF

የሚያሳዝነው ፣ በድርጅቶችና በትምህርቱ አስማሪዎች ጉድለት እዩተከ ሰሉ ፣ እዩተወቀሱ ፣ የሚቀጡ ልጆችና ወላጆቻቸው ፣ ከዚያም በመ ጨረሻ አገሪቱ መሆናቸው ነው ! ሁ-ሁ-ሁ!" አለ ጥላሁን ፣ ንግግሩን አቁሞ ትንሽ ሲያስብ ፤ አሰፋ የተናገረው ስላስገረመው የአሽሙር ሳቅ ስቆ ። 'ይገርማል ! ለሁለተኛ ደረጃና ለኮሌጅ ትምህርት ብርቱዎችን ብቻ መምረጥ ያስፈልጋል ' አልሸኝከ አሰፋ ! እውነት የተማረ ሰው በገዛ ከምንመርጥበት ጊዜ ደርሰናል ? የሚመርጥኮ የጠገበ ነው እንጂ የተራበ አይደለም ! እዩተቸገረ ፤ እዩራበው ልምረጥ የሚል የድሀ ዘመናይ ይባላል ! ኢትዮጵያ ትምህርት አልጠገበችም ፤ ገና እንደ ተራበች ናት ! ከቀለም አንስቶ ፣ በቴክኒክ አልፎ እስከ ታችኛው የጅና የሙያ ትምህርት የተማሩ ሰዎች በጣም ፣ በብዛት ፣ ያስፈልጉ ዋታል ! ስለዚህ እነዚህ ሁሉ ልዩ ልዩ ትምህርቶች ፣ በየደረጃቸው እስከ መጨረሻ ተደራጅተው የሚሰጡበትን ዘዴ አበጅቶ ፣ የደከሙና የተደከመባቸው ወጣቶች ፣ እንደዩገንባሴያቸው ወደ ተዘጋጁላቸው ድርጅቶች እዩተሰማሩ ፤ ተጠቅመው እንዲጠቅሙ ማድረግ ነው እንጂ፣ ብዙ ከተከሰረባቸው ወጣቶች ጥቂቶችን መርጠን ብዙዎችን እንበትን ማለት ምን እንደሚባል . . . እንጃ ፤ አላውቅም !" አለ ጥላሁን ፣ ከስ ሜቱ መጋል የተነሳ ፊቱ ቀልቶ ።

"ይቅርታ አድርግልኝ ፣ ጥላሁን " አለ አሰፋ ፣ የጥላሁንን መበ ሳጨት ሲያይ ማዘኑ ከፊቱ እዩታዩ ። " ይቅርታ አድርግልኝ ፤ ሰም ኑን ስለ ደረሰው . . ችግር የሚበጅ ነገር እንድንፈልግ ለመመካከር መጥቼ ፣ ሳላስበው ወደሚያበሳጭ ክርክር መራሁህ መሰለኝ ።"

"የለም አሰፋ ፤ በዚህ ነገር መነጋገራችን በጣም ነው ደስ ያለኝ። እንዲህ ባለው ጠቅላላ ችግር ሁሉም በዩቦታው ፣ በዩጊዜው ፣ ሊነጋ ገርበት ይገባል ። ችግሩ ካለ ፣ ዛሬ ባይሆን በሌላ ጊዜ፣ ለሁሉም በዩ ተራ ይደርሳል ! እስካሁን ቆይቶ . . . አሁን በኔ እንደ ደረሰ ።"

"እሱስ እውነት ነው ፤ ብቻ እንዲህ ያለው ጠቅላላ ችግር ባን ተና በኔ ደረጃ ያሉ ሰዎች ተከራክረው አብነት የሚያገኙለት አይደለም ብዩ ነው እንጂ ። ስለዚህ አሁን እሱን እንተውና ወዳንተ ጉዳይ እንመለስ ። አሁን ምን ለማድረግ ነው ያሰብህ ?"

"በውነቱ እስካሁን 'ይህን አሰቤ ወሰንሁ' የምለው የለም። ወደፊት ስለማደርገው ለማሰብ ቁጭ ስል የጠራሁትም ፣ ያልጠራሁትም ፣ ልዩ ልዩ አሳብ ባንድ ላይ ተሰብስቦ በራሴ ውስጥ እዩተተራመሰ ሲንጫጫ፣ ያደነቁረኝና ሁሉንም ጣጥዩው ተነስቼ ዞሬቄን እሄዳለሁ ። መችም . .

@OLDBOOKSPDF

የሚቻል ከሆነ ፡ ለጊዜው ስራ ፈልጎ ከመያዝ በቀር ሌላ ማማረጫ የለ ። ብቻ ችግሩ ፡ አንድ ሰው ፡ 'ወደቀ' ከተባለ ፈላጊ የለውም ! የትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን የመስርያ ቤቱም በር ይዘጋበታል ! አንዳንድ የሰራተኛ ችግር ያለባቸው የተገኙ እንደሆነ እንኳ ፡ እንደ ማናቸውም የወደቀ ነገር ሁሉ በርካሽ ሊወስዱት ነው የሚፈልጉ !"

"ትንሽ መታገስ ያስፈልጋል እንጂ ፡ ልብ የሚመኘው ባይሆን ፡ ለጊዜው ከችግር የሚያድን ስራ የሚጠፋ አይመስለኝም ።"

"ዘላቂም ይሁን ጊዜያዊ ፡ በመጠኑ ይስማማል የሚባል ስራ እስኪገኝ መታገስ የሚችሉት መኖርያ ያላቸው ናቸው ! እኔ ከዚህ ወር መጨረሻ በሁዋላ ፡ ከኮሌጅ አገኘው የነበረውን እንኳ አላገኝም ፤ ይቋረጣል"

"ላነጋግርህ የመጣሁ ስለሱ ነበር ።"

"ስለምኑ ?"

"ይስማማኛል የምትለው ስራ እስኪገኝ ስለምትቆይበት ። ምንም እንኳ አንተ ያስብኸውን ባላውቅ የኮሌጁንም ፡ የትምህርት ሚኒስቴርንም ሹሞች አነጋግሬያቸው ነበር ። ከኮሌጅ ምንም ተስፋ የሚደረግበት መልስ አላገኘሁም ። ከትምህርት ሚኒስቴር ግን ፡ የጠቅላይ ግዛቶች ጽህፈት ቤት ዲሬክተር ፡ በዱዳር አገሩ ለተከፈቱት ትምህርት ቤቶች አስተማሪዎች ጠፍተው ብርቱ ችግር ስለ ተፈጠረ ፡ እንኳዋ ንስ አንዳንቶ ሶስት አመት ኮሌጅ ተምረው ፡ እስራ ሁለተኛ ደረጃ ተምረው የወደቁትንም በደስታ የሚቀበሉ መሆናቸውን ነገረኝ ። ደመወዙ ሁለት መቶ ብር ነው ። ስለዚህ . . በሁለት መቶ ብር ደመወዝ ዳር አገር ድረስ ከምትሄድ ፡ እዚሁ አዲስ አበባ የሚስማማህ ስራ ፈልገን እስክናገኝ ፡ ከኔ ጋር ለመቆየት ፈቃድህ ቢሆን በጣም ደስ ይለኝ ነበር ፤ ጥላሁን እባክህ እሺ በለኝ ።"

"እግዚአብሄር ይስጥልኝ ፡ አሰፋ " አለ ጥላሁን ፡ ዝም ብሎ እዩተከዘ ሲያስብ ቆይቶ ። ስለኔ የኔን ያክል እንደምታስብ አውቃለሁ ። ብቻ . . . እንኳዋንስ ስራ እስካገኝ ለሁልጊዜም ካንተ ጋር መቀመጥ ጭራሽ የማይከብደኝ ቢሆንም ፡ ላጭር ጊዜ ካዲስ አበባ ገለል ብዬ መቆዬት የምፈልግበት ምክናያት ስላለኝ ፡ ያቀረብህልኝን የወንድምነት መስተንግዶ ባለመቀበሌ እባክህ አትቀየመኝ ። ስለ አስተማሪነቱ ስራ ግን . . . ትንሽ አስቤበት ነገ ብነግርህ ይዘገያል ?"

"ኢሱስ አይዘገይም ፡ ዘንድሮ ከሀረር የመምህራን ማሰልጠኛ የወጡት አስተማሪዎች ሁሉ ፣ 'አዲስ አበባና እጅግ ቢርቅ በዳጠቅላይ ግዛቱ ዋና ከተሞች ካልሆነ ገጠር ሄዳችሁ አስተምሩ ከተባልን ስራ ውን እንተዋለን' ስላሉ 'እንዲያውም ብዙ የገጠር ትምህርት ቤቶች አመቱን ያላስተማሪዎች ሳያሳልፉት አይቀሩም' እዬተባለ ተፈርቶ ዋል ። ብቻ . . . 'ከአዲስ አበባ ገለል ብዬ መቆዬት የምፈልግበት ምክናያት አለኝ' አልህ እንጂ ፣ እንደኔስ ቢሆን አብረን ሆነን እዚሁ ደህና ስራ ፈልገን ብትይዝ እወድ ነበር!"

"አሁን እንደ ነገርሁህ ፣ ላጭር ጊዜ ካዲስ አበባ ወጥቼ የምቆይበት ምክናያት ባይኖር ፣ አንተ ቤት መቀመጡን በገዛ ቤቴ እንደ ተቀመጥሁ ነበር የምቆጥረው ፤ እመነኝ አሰፋ!" አለ ጥላሁን ፣ የጉዋደኛውን እጅ በሁለት እጆቹ ጭብጥ አድርጎ ይዞ ፣ አይኖቹን ጠልቆ እያዬ ።

@OLDBOOKSPDF

@OLDBOOKSPDF

## ምእራፍ ፫

# ከጠረጠሩ፡ ከፉ ያልጠረጠሩትን መልካም መስማት ያስደነግጣል

ጥላሁን በፈተና የመውደቁንና ፣ መደገም የማይፈቀድለት የመሆኑን መርዶ ከተረዳ በሁዋላ ፣ ራሱን አስችሎ ሶፊን ለማስተዳደር የሚያበቃው ስራ ሊያገኝ የማይችል በመሆኑ ፣ ልታገባው እንደማትፈልግ አምና ፣ ይህኑ የማትፈልገው መሆንዋን ካፍዋ የሰማ እለት የህይወቱ መጨረሻ የሚሆን መስሎ እየታየው ፣ እየፈራ ፣ ከሰዋ ጋር እንዳይገናኝ፣ ሲገናኙም አብረው የሚቆዩበት ጊዜ የተቻለውን ያክል እንዲያጥር ፣ ይጣጣር ነበር ።

ካሰፋ በረደድ ጋር ተሰነባብተው ከተለያዩ በሁዋላ ፣ እንደ ገና ወደ ሺልጋው ተመልሶ ፣ እንደ ልማዱ ተንጋሎ ፣ የማያዩ አይናቹን አፍጦ ሺማራው ላይ ሰቅሎ ፣ በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ ይገኛል የተባለውን ያስተማሪነት ስራ ባሳቡ ያወጣ ያወርድ ጀመር ።

“ኧረ ለመሆኑ” አለ ፣ ዝም ብሎ ሲያስብ ቆዩና ። “እንዲያው ለመሆኑ ፣ አስተማሪ ሆኜ ዳር አገር ብሄድ የማስተምራቸውን ልጆች ምን ያክል ን.ጠቅማቻዋለሁ ? ላስተማሪነት የሚያስፈልገው መሰናዶ የሌለኝ ከመሆኔ ሌላ ፣ የተፈጥሮ ዝንባሌና ስጦታ አለኝ ? የለኝምኮ ! የተፈጥሮ ዝንባሌየ ፣ ችሎታየ ፣ ስጦታየ ፣ ጥሪየ ህግ ስለሆን ዳኛ ፣ ወይም ጠበቃ ሆኘ ዳር አገር ብሄድ የምሄድበትን አገር ህዝብ እንደምጠቅም አይጠረጠርም ነበር ! አስተማሪ ሆኖ መሄዱ ግን ፣ ካዲስ አበባ ለመሸሽ ያክል ካልሆነ በቀር ፣ ሶፊ . . . ትንሽ በትንሽ ችላ ስትለኝ ፣ ፊትዋን ስታዞርብኝ ፣ መጀመርያ በስርቆሽ ፣ ሁዋላ በገሀድ ከሌላ ሰው ጋር ስትሄድ ፣ መጨረሻ ስታገባ ፣ ላለማየት ካልሆነ በቀር ራሴንም ፣ የማስተምራቸውንም እንደማይጠቅም የታወቀ ነው ! አለና በትምህርት ቤት ሳለ ትምህርቱን ሲጨርስ ፣ ጥሩ ስራ ይዞ ሶፊን አግብቶ ፣ እሱና ሶፊ እየተረዳዱ ፣ ወገኖቻቸውን ከድህነትና ከድንቁርና በሚወጡበት መንገድ እየመሩ ፣ ለመኖር ወስና ያስቀመጠው እቅድ እንዳልነበረ ሆኖ ፣ እሱ ቀርቶ ሌላ የሚኖርበት ፍሊጋ በጨለማ

እዩዳበሰ መጨነቁ [illegible] ነው ! ለካ ሰው ይህን አደር ጋሰሁ ፣ ይህን እሆናለሁ ብሎ የኑሮውን ጎዳና በረዥሙ የሚያቅደው እንዲያው በማያዝዝበት ፣ በሌሎች ስልጣን ገብቶ ነው! ለካ ሰው በኑሮው ሊያዝዝ ቢችል ፣ ለሚኖርበት ደቂቃ ብቻ እንጂ ፣ ከዚያ አልፎ ትናንትም ፣ ነገም የሱ አደሉም ! ትናንት የታሪክ ፣ ነገ የውር እድል ናቸው ! '
ሲል በር ተደጋግሞ ተመታ ። ነገር ግን ጥላሁን አሳቡን ለራሱ እዩተናገረ አልሰማም ። 'ወዩው ጉድ !' አለ ቀጠለና ፤ 'የሰው ህይወትኮ ለባለቤቱ ብቻ አደለም ፤ የሰው ህይወት ይልቁንም አቅም የሌለው ሰው ህይወት ፣ ገነኞች እንደሚቆራቆዙበት ጥንግ ፣ ልዩ ልዩ ሀይል ያላቸው ተጫዋቾች የሚጫወቱበትና ፣ ከዚያ ከንዱ የበረታው ተጫዋች ወደ ግቡ የሚለጋው ነው ! ህይወቴ የኔ ብቻ ፣ እኔ ብቻ የማዝበት ቢሆን ኖሮ ፣ እኔ የምመራውን ሙንገድ ተከትሎ ፣ እኔ ወዳቀድሁት ግብ እንዳይደርስ ሌሎች ፣ ስልጣንና ገንዘብ ከንዳቸውን ያበረታው ሀይለኞች ወደ ግባቸው ባልለጉት ነበር ! ወንድይራድ የገንዘብ ፤ አንትዋን ያቡትግሪኑት ስልጣን ሀይላቸውን አስተባብረው ፣ ሕይወቴን ከግቤ ወደ ግባቸው ለጉት ! ብቻ ከሀይለኞች ሁሉ ሀይል ፣ የእድል ሀይል ፣ የእግዚአብሄር ሀይል ስለሚበልጥ ፣ ምናልባት ህይወቴን ፣ እንደ ለጉት ወደ ግባቸው ሳይደርስ ይህ ሀይል ፣ የግዜር ሀይል ደግሞ ወደ ሌላ መልሶ ይለጋው ይሆናል ! ወዴት ? እንጃ!"

በለሰለስታ ይመታ የነበረው በር በሀይል እዩተደጋገመ ስለ ተመታ ጥላሁን ደንግጦ ተነሳና ፣ እዩሮጠ ሄዶ ሲከፍት ሶፊያ "ጥላየ ፣ ደህና አደለህም ? "ብላ መልስ ለመስጠት ጊዜ ሳትሰጠው ፣ እቅፉ ላይ ወደቀች ። ተቃቅፈው ብዙ ከቆዩ በሁዋላ ፣ ሲላቀቁ እንቅልፍ ማጣትና የአሳብ ውሽንፍር ተረዳድተው አንገላተውት ፣ አይኖቹ ቀልተው ፣ ፊቱ ጠውልጎ ፣ ተጎሳቁሎ አዩችና ፣ ልብዋን ፈንቅሎ የመጣባትን ልቅሶ እንዳያይባት አንገትዋን ደፍታ በመሀረም አፍንጫዋን የምትጠር ግና አይኖችዋን የምታሻሽ ለመምሰል እየተጨነቀች ፣

"ያን ፣ ያን ያክል በር ስመ . . ስመታ ለምን ዝም አልከኝ ? ተኝተህ ኖር . .ኖሮዋል?" አለች ፣ ምንም እንባዋን መሸፈን ብትችል ሲታገድ የማይችል ሳግ ንግግርዋን እያቋዋረጠው ።

"አትምጪ የምልኮ ይህን ፈርቸ ነው ፤ ሶፊ!" አለ ጥላሁን ፣ በትካዜ መሬቱን እያዩ ።

"አላለቅስም ጥላየ ፤ በቃ ዳግመኛ አላለቅስም !" አለች ፣ እፍንጫዋንም ፣ አይኖችዋንም ፣ በመሀረምዋ እዩጠራረገች ፣ የውሸት ፈገ

@OLDBOOKSPDF

ግታ ፈገግ ብላ ። "በር ስመታ ብዙ ቆየሁኸ ፤ ለምን ዝም አልህ ? ተኝ ተህ ኖርዋል ?"

"መተኛትስ አልተኛሁም ፤ ብቻ አበሩ አንድ ነገር ነግሮኝ ፡ አሱ ሰበ ያመጣው ዛፍ ቅርንጫፍ በራሴ ሲንቻቻ ጆሮየን ደፍኖት ኖሮዋል መሰለኝ ፤ አልሰማሁም "አለ ፡ በቅርታ ፈገግ ብሎ ።

"እየውልህ ! እኔን 'አታልቅሽ ስልሽ አትሰሚም' ብለህ ትቆ ጣለህ ፤ አንተ "እባክህ ራስህን እንዳይ አትበጥብጥ ፤ እባክህ አትበ ሳጭ' ስልህ እሺ አትልም ። እየው ጥላዬ ! በሰው ያልደረሰ አልደረሰ ብህም ፤ ዛሬ ባንተ የደረሰው የደረሰባቸው ለንት ናቸው ? ታዲያ እነሱ ሁሉ ከመሬት ጠፉ ? አሉኮ ! ይኖራሉ! አንተም ሳትበሳጭ ፡ በርጋታ ካሰብህበት ምናልባት ትንሽ ጊዜ ይወስድ እንደሆነ እንጂ ፡ ወዳሰብ ኸው ለመድረስ ምንም አያቅትህም ። "

"የለም አልበሳጭም ፡ ሰፈ " አለ ፡ ጉንጭዋን ፡ ግንባርዋን ፡ ፊት ዋን ሁሉ በማባበል እየደባበሰ ። 'ሊመትሊሽ አልበሳጭም ። አበሩ የነ ገረኝን ሳሰላስል በር መመታቱን አልሰማሁም' ያልሁሽ .. በብስጭት አደለም ። "ትምህርት ሚኒስቴር አስተማሪ ይፈልጋልና ሳጭር ጊዜ አስ ተማሪ መሆን ትፈቅድ እንደሆነ የሚቀበሉህ መሆናቸውን አረጋግጠ ውልኛል ስባለኝ ፡ የማልችለው መስሎ ተሰማኝና አሱን ሳወጣ ፡ ሳወርድ ነበር ግለቴ ነው ።"

"ይህማ ጥሩ የምስራች ነው ጥላዬ ፤ የት አገር ?" አለች ፊትዋ ሁሉ በደስታ በርቶ ።

"ዳር አገር"

"አዲስ አበባ ቢሆን . . ጥሩ ነበር ፤ ባመቱ መጨረሻ እንደ ገና መፈ ተንና ትምህርትህን መጨረስ ትችል ነበር ። ብቻ . . . ግዴለም ይሁን!' አለች ትንሽ ስታስብ ቆይታ ።

"ዳር አገር ነው" ፡ አለ አይኖቹን ሳያረግብ ፊት–ለፊት እግድግዳው ላይ ተክሎ ። እንዲያ ፍዝዝ ብሎ አይኖቹን እግድግዳው ላይ እንደ ተከለ ፡ ግንባሩ ቁጥር ፡ ፊታ ሲል አሳቡ ርቆ መሄዱ ይታወቅ ነበር ። 'ዳር አገር ነው' አለ እንደ ገና ፊቱን ከግድግዳው ወደ ሰፊ ሲመልስ በስ ጨት ብሎ ። "ዳር አገር ነው እንጂ ከተማማ ፡ መሀሉማ ለተመረጡት ተቆጥቦ ፡ ተጠብቆ ይቀመጣል ! ከመሀል የሚባረረው ሁሉ ፡ ችግሩ ፡ በሽ ታው ፡ ሞቱ ፡ ድንቁርናው እዩሸሸ እዚያ በሚኖረው ሕዝብ ላይ ቁጭ

@OLDBOOKSPDF

ቱን በሚወጣበት ፣ ቂሙን በሚበቀልበት ፣ እውቀት ፣ ምቾትና ጤና እን ዳይገቡ በሩ የሁዋሊት በተዘጋበት ፣ የሀያኛው መቶ ዘመን ጸሀይ ጮራ ዋን ባልፈነጠቀችበት ዱር አገር ነው ! እንዲያ ባለው ዱር አገር ብድር ከፋይ ወገን ያለው አስተማሪ ፣ ሀኪም ፣ ዳኛ ፣ ደህና አስተዳዳሪ አይሄ ድም ! እንደኔ ላሉት ቦታ ሊገኝ የሚችል እዚያ ነው ! ነገር ግን . . .” ብሎ ሊቀጥል ሲል ፣

“ታዲያስ ?” አለች ሶፊያ ፣ አቋርጣ ። “ታዲያ ከፋህ ? የምትፈል ገው ይህን አልነበረም ?”

“ምኑን ?”

“አሁን ባልከው ሁኔታ ያሉትን መርዳቱን ። ሙሉ አገልግሎት ህን ፣ ህይወትህን እንኩዋ ቢሆን ለተጠቁትና ፍትሮት ለጎደለባቸው መስዋእት አድርጎ መስጠቱን ! አልተሳሳትሁ እንደሆነ ይህን ነበር ይመ ስለኛል-ሁልጊዜ ከፍህ ሲወጣ የምሰማው ! ሁልጊዜ ስትናገር እሰማህ የነበረ ። ለመኖር ያክል የሚበቃ ብቻ መተዳደሪያ ካገኘህ ከከፍተኛ ማእ ረግ ሆነ ፣ ከሀብትና ሀብት ሊሰጠው ከሚችለው ድሎት ሁሉ ፣ በተማ ርከው ትምህርት ወገኖችህ የተሻሻለ ኑሮ እንዲኖሩ ፣ ህዝቦች ሁሉ ኑሮ ዋቸውን እንዲያሻሽሉ ፣ መርዳት የሚሰጥህን ደስታ ብዙ እጥፍ ጊዜ እንደምትመርጥ ነበር ! ታዲያስ ! አሁን አንተ እንዳልከው ከመሀል የሚ ባረረው ድንቁርና ፣ ችግር ፣ በሽታና ሞት ቁጭቱን ከሚወጣበት ፣ እው ቀት ፣ ጤናና ምቾት እንዳይገቡ በር የሁዋሊት ከተዘጋበት ፣ የዘመኑ ብር ሀን ጮራውን ካልፈነጠቀበት ህዝብ የተጠቃ ፣ ፍትሮት ያጣና ርዳታ የሚገባው አለ ? እንዲያ ያለው ህዝብ ፣ እንዲያ ካለው ኑሮ እንዲወጣ ከመታገልስ የተሻለ አገልግሎትና መስዋእትነት አለ ? ወይስ ያ ስትመ ኘው የኖርከው መስዋእትነት አይኑን አፍጦ ሊገጥምህ ሲመጣ ጊዜ ፈርተህ ልትሸሸ ነው ?”

“የለም ሶፍዬ” አለ ፣ ስሜቱ ከብስጭት ወደ መለዘብ መለስ ብሎ የቅርታ ፈገግታ በፊቱ እየታዬ ። “አላስጨረስሽኝም እንጂ ለመሸሽ አደለም ። አዬሽ ? በማያውቀውና ባልተሰናዳበት ስራ የሚቀመጥ ሰው፣ አገልግሎቱ ለራሱ እንጂ ሊገለገሉ ለሚገባቸው ወገኖች አይደለም። እን ዲያውም ፣ እንዲያ ያለው ሰው ፣ የሚፈለግበትን አገልግሎት መስጠት የማይችል ከመሆኑም በላይ ፣ አውቀውና ተሰናድተው ሊያገለግሉ የሚ ችሉትና አገልግሎት ፈላጊዎች እንዳይገናኙ ቦታ ይዞ ፣ በመሀከላቸው እጥር ሆኖ የሚከለክል ነው ። ስለዚህ ፣ እኔም ለግቸ ባላቢ ሳወጣ፣ ሳወ ርድ የነበረ ፣ ባስተማሪነት እንዳልተሰናዳሁ እያወቅሁ ፣ ለጊዜው ስለ ቸገ

@OLDBOOKSPDF

ረኝ ብቻ ስራውን ጀ.ገር ብሄድ ፤ ለዚያ ስራ የተሰናዱትንና ሲጠቅሙ የሚችሉትን ቦታ መያዜ ፤ በተለይ አገልግሎት የሚፈልገውን የዳር አገር ህዝብ አይጎዳም ወይ በማለት ነው ። በዳኝነት ይሁን በጥብቅና ፤ "ዳር አገር ስራ ተገኝቶ የሚሄድ ሰራተኛ ጠፋ" ቢሉኝ ኖሮ ፤ እንኳንስ አሁን ትምህርቴ ተቋርጦ ፤ ባይቋረጥም በፈቃዴ አቋርጬ እስካ ሁን ባገኘሁት ትንሽ እውቀት ለመርዳት ወደዚያ መሄድ እንደምመ ርጥ አትጠራጠሪ ።"

"አልጠረጥርህም ፤ እስከ ዛሬም የማውቅ አሁን እንዳልኸው መሆ ንህን ነው ። ብቻ ቅድም የዳር አገርን ኑሮ ገሀነም አስመስለህ ፤ እዚያ ለስራ የሚሄዱትን የተኮነኑ ፤ የማይሄዱትን ታዳጊ መላእክት ያልዋቸው፤ የጸደቁ ነፍሳት አድርገህ ስትናገር ፤ ዳር አገር መሄድን ገሀነም እንደ መሄድ የጠላኸው ስለ መሰለኝ . . ከማውቀው አሳብህ የተለዩ ሆነብኝና ትንሽ ቸገረኝ ።"

"እደለም ፤ የዳር አገር ህዝብ ስለሚኖርበትና ፤ ወደዚያ ለስራ የሚ ሄዱት ሰዎች ስለሚመረጡበት ሁኔታ እዬተበሳጨሁ የተናገርሁት ጠቅ ላላ ነው ፤ ስለራሴ አደለም ። እዬኸ ሰሬ ፤ ዳር አገር ለስራ መላክ ያለመ ወደድ ፤ የመጋዝ ፤ የወገን-የለሽነት ፤ የመናኛነት ምልክት ሆኖ ታዬና ፣ እውቀት ፤ ችሎታ ፣ እውነተኛነት ፤ ወገን ያላቸው ፤ ዳር አገር ሲባል ከሰ ራው ቀድሞ ይህ ክፉ ምልክት እዬታያቸው ፤ ወደዚያ መሄዱን ጠሉት። ከሌላ ወገን ደግሞ እውቀት ፣ ችሎታ ፣ በጎ ፈቃድና እውነተኛነት ያላ ቸው ሰራተኞች በዬክፍሉ ባለመሄዳቸው ፤ የዳር አገር ኑሮ ተሻሽሎ ተወ ዳጅ የሚሆንበት ጊዜ እዬቀረበ በመሄድ ፈንታ እዬራቀ ሄደ ። ታዲያ እይውልሽ እንዲህ ያለ . . . መውጫ የሌለው አዝዋሪት ተፈጠረና ፤ የዳር አገር ህዝብ የዜግነት ተግባሩን ሳያጎድል ፤ የዜግነት መብቱ የጎደለበት መሆኑ ሲታይ ያበሳጫል ። ይህ ነው . . ያበሳጨኝ ።"

ጥላሁን የዳር አገርን ችግር ሲተርክ ፤ ሶፍያ አይኖችዋን ሳታረግብ ቦዘዝ አድርጋ ፤ ፊት ለፊት ፤ እግድግዳው ላይ ተክላ ስትታይ ፤ አሳብዋ እንሱን እዚያ ትቶ ሩቅ የሄደ ይመስል ነበር ። ተናግሮ ሲጨርስ ፤ እንዲያ አይኖችዋን እግድግዳው ላይ እንደ ተከለች ሁለቱም ዝም ብለው ከቆዩ በሁዋላ ፤

"እዎ ፤ በጣም ያሳዝናል !" አለች ፤ ዝምታው እንደ ቀሰቀሳት ሁሉ በተተከሉበት ፈዘው ፣ የቆዩ አይኖችዋን እያርገበገበች ። እዎ ፤ በጣም ያሳዝናል ! ብቻ ፤ ይህ አሁን አንተ እንዳልኸው ጠቅላላ ችግር ነው ።

@OLDBOOKSPDF

ጠቅላላ ችግርንም የሚያስወግደው ጠቅላላ ፈቃድ ፣ ጠቅላላ መሰናዶና ጠቅላላ ትጥቅ ነው ። ስለዚህ እስቲ . . . ጠቅላላውን ችግር ለጠቅላላው ፈቃድ ፣ ለጠቅላላው መሰናዶና ትጥቅ ትተን ወደ ራሳችን ችግር እን መለስ ” አለች ፣ አይኖችዋን ከግድግዳው ወደሱ መልሳ ። ጥላሁን ልቡ ከስሩ እንደ ተናጋ ፣ የሰራ አካላቱ ህንጻ ከመሰረቱ ቀስ ብሎ እንደሚ ሸሽ ፣ ጠቅላላ ዝለት ፣ ጠቅላላ ድካም ተሰማውና ራሱን እንደ ማዞር ፣ አይኖቹን እንደ መሸፈን ስባደረገው እንገቱን ደፍቶ ዝም አለ ። ሶፊያ ትንሽ ቀደም ብላ የትምህርት ሚኒስቴር የሚሰጠውን ያስተማሪነት ስራ ተቀብሎ ወደ ዳር አገር እንዲሄድ ስትገፋፋውና ወደ ሁዋላ እንዳይሸሽ መንገድ መንገዱን ስትዘጋበት ፣ ከስዋ እንዲርቅላትና ከሱ ነጻ እንድት ሆን የፈለገች መስሎ ተሰምቶት ነበር ። ነገር ግን እንዲህ ያለውን ነገር መስማትም ፣ ማወቅም ስለማይፈልግ ፣ ስለሚፈራ ፣ ምንም እንዳልተሰ ማው ሁሉ በፍጹም ግምናናነት ስለ ራሱም ፣ ስለዳር አገርም ሲነግራት በጥልቅ አሳብ ተውጣ ቆይታ ፣ “ጠቅላላውን ትተን ወደ ራሳችን ችግር እንመለስ” ስትል ያን መስማት የማይፈልገውን ፣ የጠላውን ፣ ፈርቶት የሚሸሸውን ፣ የጋብቻቸውን ነገር ልታነሳ ነው ብሎ ፣ ልቡ እንደሚቃ ጠል ሻማ እዩቀለጠ በውስጡ የሚፈስ መሰለውና ጠቅላላ ዝለት ፣ ጠቅ ላላ ድካም ስለ ተሰማው ፣ የተደፋ ራሱን በሁለት እጆቹ ደግፎ ዝም አለ። ፤

“ጥላዬ ደህና አይደለህም ? ” አለች ሁኔታውን ስታይ ደንግጣ አልመለሰም ።

“ጥላዬ” አለች በድንጋጤ ከተቀመጠችበት ተነስታ እፊቱ ተን በርክካ ።

“እ? ደህና ነኝኮ ! አንድ ነገር ትዝ ብሎኝ ነው ” አለ ፣ እፊቱ ተንበርክካ ሲያያት እንደ ማስተጋባት ብሎ ።

“ያመመህ መስሎኝ በጣም ደነገጥሁ ” አለች ፣ ተነስታ ወደ መቀመጫዋ ሄዳ ስትቀመጥ ።

“ደህና ነኝ ። ‘ወደ ራሳችን ችግር እንመለስ !’ ብለሽ ነው . . . ንግ ግርሽን ያቋረጥሽ ፤ ስለ ራሳችን ችግር ምን ልትይ ነበር ?” አለ የማ ይቀረውን ለመስማት ፣ ሸሽቶ የማያመልጠውን መርዶ ለመረዳት ያለ ውን ድፍረት ሁሉ አጠራቅሞ ።

“ወደ ራሳችን ችግር ያልሁ እንኩዋ እንዲያው ነው እንጂ ችግሩ እኔን የሚጨምር አይደለም ፣ ምንተ የራስህ ብቻ ነው” አለችና ቀጥላ

@OLDBOOKSPDF

ለመናገር ያሰበችውን የምትጀምርበት አጥታ እዬፈለገች ሳጭር ጊዜ ዝም በላለች፤ ጥላሁን የባሰውን ግራ ገብቶት ግንባሩን ኮስተር አድርጎ ምንም ሳይናገር ይመለከታት ጀመር።

"አዬሁ ጥላዬ ! ያንተ አያንተኛ ችግርህ፤ ብዙ እያወቅህ ራስህን ብቻ አለማወቅህ፤ ትክክለኛ ፍርድ ለሁሉ እዬተመኘህ ለራስህ ብቻ ትክክለኛ ፍርድ የማትሰጥ መሆንህ ነው ! እንዲህ ያለውን ምን ትለዋ ለህ ?" አለች፤ የተቸገረ ስሜትዋን በሚገልጽ አዘንተኛ መልክ የተኮሳተረ ፊቱን እያየች።

"እንዴት ? ምን ማለትሽ ነው ?"

"አዎ፤ ሁልጊዜ ስለ ራስህ የምትሰጠው ፍርድ ትክክለኛ አይደለም። እያወቅህ አላውቅም፤ እዬቻልህ አልችልም ትላለህ ። ይህ ራስን አለማ ወቅ አይባልም ? ለምሳሌ ትድግም፤ 'ዳር አገር አስተማሪ ሆኜ የሄድሁ እንደሆነ ባስተማሪነት በላልተሰናዳሁ፤ ከንቱ ላልጠቅም፤ የሚጠቅሙ ትን ቦታ ይገፔ አገልግሎት የሚፈልገውን ህዝብ እንዳለሁ' አልኸኝ። ይህ እውነት አይደለም ። እውነተኛው ነገር በማናችውም ትምህርት ላን ደኛ ደረጃ አስተማሮች ለመሆን ከሚሰናዱት ሰዎች የበለጠ መሰናዶ ያለህ መሆንህ ነው ። ምክናያቱም ለኮሌጅ መግቢያ የሚያስፈልገውን ከፍተኛ ትምህርት ሁሉ ያጠናቀቅህና፤ ሰስት አመት ኮሌጅ ሊሰጠው ከሚችለው ትምህርት በላይ ያለህ ከመሆንህ ሌላ፤ የምታውቀውን ለም ታስተምራቸው ሁሉ የምታስተላልፍበት ፤ የጠበቆች የግል ንብረት የሆን የማስረዳት ችሎታ አለህ ። ኧረ ለመሆኑ ባስተማሪነት መሰናዳት ማለት እንዴት ነው ? መጀመርያ የሚያስፈልጉትን ትምህርቶች ማወቅ፤ ከዚያ የሚያውቁትን ለማያውቁት እንዲቀበሉት አድርጎ ለማስተላለፍ መቻል አይደለም? ታዲያ በዚህ ባስተማሪነት የሚሰናዱት ካንተ ይሻላሉ ? አይመስለኝም ። ስለዚህ ፤ 'ባስተማሪነት ስላልተሰናዳሁ ያስተማሪነት ስራ ይገፔ ዳር አገር ብሄድ እዚያ ያለውን ህዝብ እጎዳለሁ' ብለህ የም ትሰጋው ስጋት ከንቱ ስጋት ነው፤ ጥላዬ ። ከሚያስፈልገው ትምህርት፤ ከችሎታውም ሌላ የመርዳት ፈቃድና ያገልግሎት ፍላጎት ያለህ ስለሆ ንህ፤ የምትሄድበትን አገር ህዝብ እንዲያውም ባስተማሪነት ከተሰናዱት የበለጠ ትጠቅመዋለህ እንጂ አትጎዳውምና ሂድ እባክህ ጥላዬ፤ ጥሩ አጋጣሚ ነው፤ ሂድ !"

ጥላሁን አንገቱን ደፍቶ፤ ግንባሩን ቋጥር ፈታ እያደረገ፤ ሶፊያ የም ትለወን እዬሰማ፤ የሱ አስተማሪ ሆኖ ዳር አገር መሄድ እውነት እስዋ እንደምትለው እዚያ ያለውን ህዝብ የሚጠቅም፤ ወይስ እሱ እንደሚ

@OLDBOOKSPDF

ለው የሚጎዳ መሆኑ[illegible] ልጅታ ፡ ከሰዋ ርቆ እንዲሄድ ፡ አንድ ጊዜ ከሄደ መመለሱ በማያጠራጥርበት አገር እንዲሰደድ ያን ያክል የምትለምንበትን ምክናያት ይመረምር ነበር ። በመጨረሻ ፡ ያ የተናገረችው ሁሉ ፡ ያን ያክል የምታባብለው ሁሉ ያን ቀደም ብሎ የጠረጠረውን ፡ ወዲያ ሂያላትም ነጻ ለመሆን መፈለግዋን የሚያረጋግጥ መስሎ ስለ ተሰማው ፡ አንገቱን በደፋበት መሬት መሬት እያዩ ሲተከዝ ቆይቶ ፡

"ምክር ነው ? . . ወይስ ትእዛዝ !" አለ ፡ ፊቱን ወደሰዋ ቀና አድርጎ ።

"ምክርም ፡ ትእዛዝም አይደለም ፤ ልመና ነው ።"

"እሺ እሄዳለሁ" አለና እንደ ገና አንገቱን ደፍቶ ይተክዝ ጀመር።

"ጥላዬ ፡ አንድ ሌላ ነገር ልለምንህ !" አለች ፡ እሰዋም እንደሱ አንገትዋን ደፍታ መሬት እያዩች ስትተክዝ ብዙ ቆይታ ።

"ምን ?"

"ቀድመህ እሺ በለኝና ።"

"አሁን ልትነግረኝ ነው ፤ 'በህግ ትምህርትህ ተመርቀህ የሚያስከብር ፡ የሚያኮራ ፡ የሚያስቀና ቤትና ኑሮ የማትሰጠኝ ከሆንህ ፡ ያንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተማሪ ሆንህ በመቶ አምሳ ፡ ወይም በሁለት መቶ ብር ደመወዝ ፡ የምመኘውን ኑሮ ልታኖረኝ አትችልምና ፡ እንግዲህ አንተም አቻህን ፡ እኔም አቻየን እንድንፈልግ እንድያችንን ተሰነባብተን እንለያይ' ልትለኝ ነው ፤ ባትነግረኝ ምን ቸገራት ? እኔ ከሄድሁ የፈለገችውን ብታደርግ ማን ይከለክላታል ? የለም ትንገረኝ ፤ ትንገረኝና አንድያየን ቁርጡን እውቄ ፡ ካዲስ አበባ ጋር የሚያያይዘኝን ማሰርያ ሁሉ ቆርጬ መሄዴ ይሻለኛል ፤ ካዲስ አበባ ጋር የሚያያይዙኝ ትምህርቴና እሰዋ ነበሩ ፤ ትምህርቴ ቀርቶዋል ፤ እሰዋም ትቅር ! ከዚያ በሁዋላ አዲስ አበባን ዘወር ብዬ ሳላይ ፡ ሳላመነታ በምሄድበት እሄዳለሁ !" እያለ በውስጡ ሲከራከር ቆይቶ ፡ የምትለውን ሳይሸበር ፡ በርጋታ ለመስማት ወስኖ ፡ ግንባሩ እንደ ተቋጠረ ፡ ፊቱ እንደ ከበደ ቀና ብሎ ይመለከታት ጀመር ።

"በል እንጂ" አለች ፡ ስሜቱ በውስጡ ያለማቋረጥ ሲለዋወጥ የሚያሳይ ፊቱን እያዩች ።

"ምን ልበል ?"

"እምቢ ሳትለኝ ቀድመህ ቃል ስጠኝና የምለምንህን ልንገርህ እልሁሀኮ ! አልሰማኸኝም ?"

@OLDBOOKSPDF

"ብምቸግለሁ ፤ ልትነግሪኝ የምትፈልጊውን ንገሪኝ ።"

"ቀድመህ እሺ በሌና ፡ እምቢ ላትል ቃል ስጠኝና !"

"የምችለው ከሆነ . . እ . . ሺ !"

"እባክህ . . በምትሄድበት . . ውሰደኝ !" አለች ፡ አይኖችዋ በቅጽበት እንባ ሞሉተው ።

ከጠረጠሩት ክፉ ፡ ያልጠረጠሩትን መልካም ነገር መስማት ያስደነግጣል ! ከጠረጠሩት መርዶ ፡ ያልጠረጠሩትን የምስራች መስማት ልብን አሸብሮ ፡ አሳብን አደናግሮ ይሉትን ፡ ያደርጉትን ፡ ይሆኑትን ፡ ይይዙትን ያሳጣል !

ጥላሁን ክፉ ለመስማት ተሰናድቶ ሲጠብቅ ፡ በጠበቀው ፈንታ ሌላ የሰማ ስለ መሰለው ፡ የሰማውን ማመን አቅቶት ፍዝዝ ብሎ አይን አይንዋን ብቻ እያዩ ዝም አለ ። "እውነትዋን ነው ? ወይስ እንዲህ ብላ ነበር እንድላት ይሆን ? 'ማጣራት አለብኝ' " አለ ፡ ዝም ብሎ አይን አይንዋን እያዩ ብዙ ቆይቶ ፡ ድንጋጤው ትንሽ እንደ ማለፍ ካለለት በሁዋላ ። ከዚያ ቃፍኖ እንደ ቆዩ በረዥሙ ተነፈሰና ፡ "ምን አልሽ?" አለ ።

"እባክህ ወደምትሄድበት ውሰደኝ ፤ አላስቸግርህም ፤ እንዲያውም አንተን ብቻ ሳይሆን አላማህን ጭምር ስለምወድ ፡ እረዳሀለሁ ፤ ድጋፍ እሆንሀለሁ !"

"ትምህርትሽስ ? ይህ አመት ብቻ ነው'ኮ የቀረሽ ።"

"ቢመቸኝ ፡ ጊዜ ባገኝ እጨርሰዋለሁ ፤ ካልተመቸኝም . . ይቅር !"

"እስቲ አስቢበት ፤ በሁዋላ እንዳትጸጸች ፤ ጊዜ እንስጠውና አስቢበት !"

"ምንም ያክል ጊዜ ብቆይ ፡ ያሁኑን አሳቤን ልለውጥ አልችልም ጥላየ ! ትምህርትኮ የኑሮ መሳርያ ፡ የህይወት አገልጋይ ነው እንጂ ራሱ ኑሮ ፡ ራሱ ህይወት ስላልሆነ ፡ ማንም ቢሆን ኑሮውንና ህይወቱን ለመ ሳሪያው ፡ ለትምህርት አይለውጥም ! የኔም ኑሮየና ህይወቴ ፡ ይበጅ ይክፋ ፡ ካንተ ኑሮና ካንተ ህይወት ጋር እንደማይለያይ ሆኖ ስለ ተቆራኘ፣ ለመለየት ብፈልግ እንኳዋ አልችልምና እባክህ እሺ በለኝ ። ጥለኸኝ ከሄድህ ፡ እንኳዋንስ ትምህርቴን ልጨርስ . . እንጃ !" አለች ፡ እንገትዋን ደፍታ እንደ ተቀመጠች እንባዋ መንታ መንታ ሆኖ እየረገፈ ።

ጥላሁን በፈተና መውደቋን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ፡ የሰነበተበት ጥርጣሬ፣ ፍራቱ ፡ ጭንቀቱ ሁሉ መሰረት የሌለው፣ ከንቱ መሆኑን ተረዳ !

@OLDBOOKSPDF

ህይወት ፣ ኑሮው ፣ ይበጂ ይከፋ ፣ ከሶፊያ ህይወትና ኑሮ ጋር ሊለያይ እንደማይችል ሆኖ የተሳሰረ ስለሆነ ፣ ሲወድቅ እንኳዋ ብቻውን እንደማ ይወድቅ ፣ ሶፊያ አብራው እንደምትወድቅ እምንትዋን ፣ የውነተኛ ስሜትዋን ፣ በቃልዋ ከተናገረችው ይልቅ ፣ ባይኖችዋ ከምታፈሰው እንባ ተረዳ ! የምትሰውን ሁሉ 'እንዲህ ብላ ነበር' እንዲላት ሳይሆን ፣ ስሜትዋ አስገድዶዋት ፣ ከልብዋ የምትል መሆንዋን እንባዋ ስለ ነገረው ተረዳ ! ልብ አገዞ ሲያለቅስ ምስክሩ እንባ አደለም ? ስለዚህ እንደ ወደቀ ወድቃ ፣ በሚሰደድበት ተሰዳ ፣ ለችግሩ ሁሉ ተካፋይ ለመሆን የተናገረችው 'ብላ ነበር' ለመባል ሳይሆን እውነትዋን ፣ ከልብዋ መሆኑን ልብዋ ራሱ እያለቀሰ በሚያፈሰው እንባ ስላስረዳው ፣ በልዩ ልዩ ዘዴ ሲፈትናት ያሰበውን ሁሉ ትቶ ፣ ልትፈተን የማይገባትን ፣ እውነተኛይቱን ፣ ታማኝቱን ፣ ሲፈትናት በማሰቡ ተጸጽቶ ፣ ከተቀመጠበት ተነስቶ እግሮችዋ ስር ወደቀ ።

"ማረኝ ሶፊ ! እባክሽ ይቅር በይኝ የኔ እመቤት! " አለ ፣ እንደ ተንበረከከ እግሮችዋን በሁለት እጆቹ ይዞ ፣ ራሱን በጉልበቶችዋ መሀከል ቀብሮ ። "እባክሽ ማረኝ ፣ እንቺን የገጠመኝ ፣ እንቺን ያመጣልኝ መልካም እድሌ ተጣልቶኝ ሲተወኝ ፣ እንቺም ከሱ ጋር ፣ እንቺም ካመጣሽ እድሌ ጋር አብረሽ የምትሄጂ፣ የምትተይኝ መስሎኝ ፈርቼ ፣ እንቺም እንደ እድሌ ፊትሽን ያዞርሽብኝ እንደሆን ፣ ችላ ያልሽኝ እንደሆን ፣ እሱን ማየቱ ሞት መስሎኝ ፣ እንዲህ ያለውን የቁመና ሞት እንዳላይ የምሸሸግበት ፣ የምጠፋበት ስፈልግ ነው የሰነበትሁ ! እንደ እድል የማትለወጪ መሆንሽን ተረድቼ ፣ የፍራትን ፣ የጭንቀትንና የጥርጣሬን ፈተና መቋቋቁም ያልቻልሁ ደካማ ፣ ጎደሎ ፣ በመሆኔ ማረኝ ! ከመጠን ያለፈ ነው የምወድሽ ፣ ሶፊ ! ከመጠን ያለፈ የሚወድም ፣ የሚወዳት እንዳታመልጠው ከመጠን ያለፈ ፈርቶ ቢያጠፋ ፣ ጥፋቱ የፍራት እንጂ የክፋት ባለመሆኑ ፣ ምህረት ሲለምን መከልከል ስለማይገባ ፣ እባክሽ ምህረት አድርጊልኝ ! "

"እባ . . እባ . . እባክህ በቃህ ! እባ . . እባክህ ተው ! " እያለች ካንድ ወገን ከሚተናነቃት መሪር ልቅሶ ፣ ከሌላ ወገን የሱን ራስ በጉልበቶችዋ መሀከል ከተቀበረበት ለማውጣት ፣ ስትታገል ቆይታ እንደ ምንም ብላ ከጉልበቶችዋ ወደ ደረትዋ ከፍ ካደረገችው በሁዋላ ፣ ልቦቻቸውን ባንድ ላይ ፣ ፊቶቻቸውን የሱን በስዋ ፣ የስዋን በሱ ሁዋላ አድርገው ፣ ተቃቅፈው ሁለቱም ያለቅሱ ጀመር ። ከዚያ ፣ የሁለቱም ልቦች ልቅሶው ቀርቶ ደስታ እንዲሆን አዋጅ ለማድረግ እንደ ተመ

@OLDBOOKSPDF

ካከሩ ሁሉ ፣ ከበሮዎቻቸውን አስተባብረው መምታት ሲጀምሩ ፣ ልቅ ሶውን ቀስ እያሉ እዬተወ ፣ ጸጥ እያሉ ሄደው ፣ ልቦቻቸው አስተባብ ረው የሚመቱትን የከበሮ ስልት ፥ መረግዱን ፣ ዝግሚውን ፣ ወረቡን እያዳመጡ ፣ ሰጊዜው ችግራቸውን ሁሉ ረስተው አብረው ሲዘምሙ፣ አብረው ሲወርቡ ከቆዬ በሁዋላ ፣ “እንዴት አድርጌ ነው የምወስድሽ?” አለ ፣ በደስታ የሚዋኙ ርጥብ አይኖችዋን ቁልቁል ጠልቆ እያዬ ።

“ባንድ መኖር የቆረጡ ወንድና ሴት የሚያደርጉትን አድርገን !” አለች ፣ እስዋም የሱን አይኖች ሽቅብ ጠልቃ እያዬች ።

“ተጋብተን ?”

“ተጋብተን ! ”

@OLDBOOKSPDF

## ምእራፍ ፬

# ቄስ እግዚአብሄር

ጥላሁንና ሶፊያ እንዲጋቡ ከወሰኑበት ቀን ማግስት ፣ ሁለቱም አንድ ላይ ባስተማሪነት እንዲቀጠሩ ለትምህርት ሚኒስቴር ማመልከቻ አቅርበው ፣ ጥላሁን ኢሉባቦር ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ፣ የኪ በምትባል የወረዳ ከተማ ተመደበ ። ሶፍያ ግን ፣ ሌላ አገር ካልሆነ የየኪ ትምህርት ቤት አንድ አስተማሪ ብቻ የሚያስተምርበት ስለሆነ ፣ "ለጊዜው እዚያ ቦታ የለም " ተብሎ ተመለሰች ። ከዚያ በሶስተኛው ቀን ፣ ማዘጋጃ ቤት ሄደው ጋብቻቸውን መዝገብ አስገብተው ተመለሱ ።

ሶፊያ ጥላሁንን ማግባቷን ወላጆችዋ የሰሙ እንደሆነ ችግር እንዳይፈጥሩ ፣ ጋብቻውን ከማዘጋጃ ቤት ውል አግቢና ከሁለቱ የውል አባቶች በቀር ማንም እንዳያውቀው አድርገው ነበር ።

“የገንዘብ ችግር ባይኖር . . . የውል አባቶቻችንን ፣ አሰፋ በረደድንና አለሙ ፈረደን ፣ ቅድስቲንና ሰዋስውን ፣ እንዲሁም አንድ ቄስ ብናገኝ ጨምረን ፣ ዛሬ ስንጫወት ብናመሽ እንዴት ጥሩ ነበር !” አለ ጥላሁን ፣ ከማዘጋጃ ቤት እንደ ተመለሱ ።

“ ለምን ? ”

“ ጋብቻችንን የምናከብርበት ሰርግ ነዋ ! ጋብቻ ያለሰርግ ሆኖ ያውቃል ? ! ”

“ሲመች ነዋ ! ብቻ ስላልተመቸ መኖር ይቅር አይባልምኮ ! ”

“ሰርጉስ እስቲ እሺ ይቅር ፤ ባይሆን እንኩዋ . . . ትንሽ ነገር አድርገን ጋብቻውን ፣ ‘ይበጅ ያድርገው’ ብሎ የሚባርከም አያስፈልግ?”

“ ቄስ ማለትህ ነው ? ”

“ አዎ ፤ የሚያስፈልግ ይመስለኛል ! ”

“ እንዲያው እንዲሁ ብቻውን ጠርተን ተጋብተናልና ጋብቻችንን ባርክልን እንለዋለን ? ወይስ . . . . እንዴት ነው ? ” አለች ሶፊያ እየሳቀች ።

@OLDBOOKSPDF

"ዛሬ ራታችንን ፣ ወይም ነገ ምሳችንን አብረን በልተን ፤ ሁኔታችንን ሁሉ ገልጸን ፣ የተጋባንበትን የምስክር ወረቀት እናሳያቸውና፡ "ይባርኩን" እንላቸዋለን ። ሰርግ ካልደገሳችሁ አልባርክም ይላሉ ?"

"ጥሩ ነው" አለች ሶፊያ ፤ ዝም ብላ ቆይታ አንድ አሳብ በራስዋ ብቅ ብሎ ስለ ታያት ትንሽ ፍርጥም አለችና ።

"ምን አሳቀሽ ?" አለ ጥላሁን ፣ ፍርጥም ስሜሏ አይቶ ።

"አንድ ነገር አስቤ ነው ፤ ሌላ ጊዜ እነግርሃለሁ ።"

"ለምን አሁን አትነግሪኝም ? ስንነጋገርበት ከቆየነው ጉዳይ ጋር የተያያዘ ነው ?"

"አዎ ፤ ቄሱን ነገ ፣ የለም ፣ ከነግወዲያ ለምሳ እንቅጠራቸው።"

"የምታውቂያቸው ቄስ አሉ ? ወይስ . . እኔ ልፈልግ ?"

"ቅድስት በላሴ ፣ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሚያስተምሩ ፣ ያዩትን ሆነ የሰሙትን ለማንም የማያወሩ ፣ በጣም ጥሩ ቄስ አሉ ፤ አንተም ሳታውቃቸው የምትቀር አይመስለኝም ።"

"እንጃ ! እዚያ እንኳ ብዙ ግንኙነት የለኝም ። ማን ይባላሉ?"

"ቄስ እግዚአብሄር" አለች ሶፊያ ፣ እዩሳቀች ።

"ምን ? ቄስ እግዚአብሄር ? ቄስ ገብረ እግዚአብሄር ? ቄስ ወልደ እግዚአብሄር ? ወይስ እንዲያው ቄስ እግዚአብሄር ?" አለ ፣ እሱም እዩሳቀ ።

"ምናልባት መጀመሪያ ለግቸው ወልደ እግዚአብሄር ሳይሆን አይቀርም ፤ አሁን ግን ሰው ለግሳጠር ይሁን ወይም በጣም ደግ ስለ ሆኑ እንዲያው እግዚአብሔር ይሏቸዋል" አለች ፣ ጥላሁንን ግራ ሲገባው አይታ እዩሳቀች ።

በሳልስቱ ጥላሁን ጉዳዩን ለማስፈጸም ወደ ትምህርት ሚኒስቴር ሲሄድ ፣ ሶፍያ ለጋብቻቸው ቡራኬ የሚያስፈልገውን መሰናዶ ስትቀጥል ዋለች ። በሰባት ሰአት ከሄደበት ሲመለስ ስራዋን ሁሉ ጨርሳ ፣ ተጣጥባ ፣ እንደ ተለመደው አጥሮ የተቆረጠ ጠጉርዋን ጥሩ አድርጋ አበጥራ ፣ ፊትዋን አሰማምራ ፣ ቀጭን ባለጥበብ ቀሚስና ኩታዋን ለብሳ ለሰርግ የሚጨማመረው ሌላ ሌላ ነገር ሲቀር ፣ በስሜትና በመልክ ጥሩ ሙሽራ ሆና ቆዩችው ። አልጋውና ጠረጴዛው እስዋ ራስዋ በትርፍ ጊዜዋ የጠለፈቻቸውን ጌጠኛ ያልጋና የጠረጴዛ ልብሶች ለብሰዋል ። በጠረጴዛው ላይ ውሀ የሞላ ጠርሙስ ከሁለት ብርጭቆዎች ጋር ተቀምጠዋል ። ካልጋው አንጻር አንድ ረዥምና ግዙፍ የሆነ ነገር

@OLDBOOKSPDF

ጠረጴዛውን በወር[illegible] አድርጎ ፣ ከላይ እስከ ታች በንጭ ልብስ ተሸፍኖ ቆሞዋል። በቀኝና በግራው ሁለት ፲ንጨት ወንበሮች አሉ።

ጥላሁን መጀመርያ ሲገባ ፣ የሶፊያን እንጂ የቤቱን መለወጥ አላስተዋለም ነበር ። እሰዋን እቅፍ - ጭንቅ አድርጎ ስሞ ፣ ከግር እስከ ራስዋ ሲመረምራት ፣ ሲያጠናት ቆይቶ ፣ የጀሮ ጉትቻ ፣ ያንገት ድሪና የክንድ አንባር እንኩዋ ሳትጨምር ፣ እንዲያ ያጌጠችና የተለወጠች በውበትዋ ብቻ መሆኑን ሲያረጋግጥ ገርሞት ፣ ደንቆት ፣ እንደገና ምጥጥ፣ ስምጥጥ አድርጎ ከሳማት በሁዋላ ፣ ቤቱን ሲያይ እሱም መልኩን ለውጦ ስላገኘው ፣ እሌላ ቤት የገባ መሰለው ።

“ ያ ምንድነው ?” አለ ፣ ጠቋዋሚ ጣቱን ተሸፍኖ ወደ ቆመው ትልቅ ነገር ቀስሮ ።

“ ቂቡ የላኩት ነው ፤ እስከመጣ እንደ ተሸፈነ ይቆዩኝ ብለዋል ። ”

“ መቼ ነው የሚመጡ ? ”

“ መምጫቸው ደርሶዋል ፤ ቶሎ ልብስህን ለውጥ ። ”

ጥላሁን ወደ ቁም ሳጥኑ ሁዋላ ዘወር ብሎ እጁንና ፊቱን ታጥቦ፣ ጠጉሩን አበጥሮ ፣ ነጭ ሸሚዙንና ጥሩ ሆኖ የተተኮሰ ካኪ ልብሱን ለብሶ ፣ ብቅ ሲል ከራሱ እስከ እግሩ ፣ ከግሩ እንደ ገና እስከ ራሱ አዪ ችና ፣ “ ትፍ-ትፍ ፣ ካይን ያድንህ ፤ በጣም አምሮብሀል ! ” አለች ፣ አይኖቹን ባይኖችዋ የጎድን ገረፍ አድርጋ እዬሳቀች ።

እውነትም ጥላሁን ያምራል ። እንደሚበዙት ጋሎች ዘመዶቹ ፣ ቁመቱ ሎጋ ፣ ትከሻው ደርባባ ፣ ከስጋ ውፍረት ይልቅ ያጥንት ስፋት ያለው ፣ ፊቱ ዘለግ ቢልም ትንሽ ሰፋ ብሎ አይኖቹ ፣ አፍንጫውና ከንፈሮቹ የፊቱን መጠን ይዘው ትንሽ ጎላ ጎላ ያሉ ስለሆኑ ፣ ሁሉም ባንድ ላይ ሲታይ ተስማምቶ ፣ ተካክሎ የተሠራ በመሆኑ ፣ ደስ የሚል ከመሆኑም ሌላ ፣ ያ ተቃራኒ የሌለበት ተስማምቶ ፣ ተካክሎ የተሠራ ጉልህ ፊቱ ፣ እንደ ተንኮልና እንደ ማታለል ያሉ ተቃራኒ ባህሪዎች በውስጡ ያልተፈጠሩ መሆኑን ጭምር ይናገራል ።

“ ጥላዬ ፤ ና እዚህ ቁም ” አለች ሶፍያ ፣ ተሸፍኖ በቆመው ትልቅ ነገር አንጻር ከጠረጴዛውና ካልጋው መሀከል ሄዳ ስትቆም ።

“ለምን ?” አለ ጥላሁን ፣ እንዳዘዘችው ከነበረበት ሄዶ በቀኝዋ ከቆመ በሁዋላ ።

“ ቂቡ አይመጡም ። ”

“ እንዴት ? ለምን ? ”

@OLDBOOKSPDF

“ አልጠራሁዋቸውም ?”

“ እንዴት ? አጣሻቸው ? ”

“ አልፈለግሁዋቸውም ! ” ጥላሁን ግራ ገብቶት ዝም ብሎ ይመለከታት ጀመር ።

“ በቀደም ጋብቻችንን እናሰባርክ ” ስትል አንድ አሳብ መጥቶብኝ ስለሳቅሁ ፡ ‘ ለምን ሳቅሽ’ ብትለኝ ፤ “ በሌላ ጊዜ እነግርሃለሁ ” ያልሁህን ታስታውሳለህ ? ”

“ አዎ ፤ አስታውሳለሁ ። ”

“ ቄስ እግዚአብሔርን አጠራለሁ ያልሁትንሳ ? ”

“ አስታውሳለሁ ። ”

“ ያው ቄስ እግዚአብሔር ፡ ያዩውን ሆነ የሰማውን ለማንም የማይናገር ! ” አለች ሰናያ ፡ ተሸፍኖ የቆመውን ትልቅ ነገር በጅዋ እመለከታ ።

“ እዩህ ? ” አለች ቀጥላ ፤ አንድ ጊዜ እሰዋን ፡ አንድ ጊዜ የተሸፈነውን ነገር እያለዋወጠ እዩተመለከተ ዝም ብሎ እንደ ቆመ ። “ እዩህ ? እስኪ ዛሬ ባሳብ ዞን በግብር ያደረግነውን በእግዚአብሔር ፊት ቶናዘን ፡ ወደ ፊት በጋብቻ ኑሮዋችን ለስበሳችንና ለሱ ታማኞች ለመሆን ከልባችን የምንመኝ መሆናችንን ቃል ገብተን ፡ ለዚህ ርዳታውንም ፡ በ ራኪውንም እንዲያደርግልን ብንለምነው አያደርግልንም ? ”

“ እውነትሽን ነው ፤ ግሩም የሆነ አሳብ ነው ! ” አለ ጥላሁን ባሳብዋ ደስ ብሎት ።

“በል እንግዲህ ፡ ማለት የምንፈልገውን እናስብና ልግለጠው ” አለችና ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት የሚሉትን ትንሽ ሲያስቡ ከቆዩ በሁዋላ ፡ ሰፊያ ቀስ ብላ ሄዳ የእግዚአብሔር ምስል የተሸፈነበት ነጭ ጨርቅ ዙርያውን የተያያዘባቸውን የወረቀት መርፌዎች ነቃቅላ ስታበቃ ፤ ጨርቁን ጠቅልላ ስታነሳ ፡ ከቀይ ዳማ ክርታስ በመቀስ እዩተቆረጠ በሰው ቅጥ ግሩም ሆኖ ተስተካክሎ የተሠራ ምስል ታዩ ። ምስሉ ገባሬ ሰናይ ሆኖ የሚቀድስ ቄስ የሚለብሰውን ልብሰ ተክህኖ ስለ ለበሰና ፡ ትንሽ ባለወርቅ ቀለም አክሊል በራሱ ስለደፋ ፡ ከፊቱ ከጆቹና ከግር ጫማዎቹ በቀር ፡ ሌላ አካላቱ አይታይም ። ከወርቁ አክሊል እዩተነሳ እንደ ጸሐይ ጮራ ወደ ውጭ የተፈነጠቀውና ፡ ባከሊሉ ዙርያ ስሌዳው የተቀባው ብሩህ ቀለም ባንድ ላይ ሲታይ ፡ የምስሉ ራስ በአውደ ብርሃን የተከበበ ይመስላል ። ፊቱን ለአሊዋ

ምንና ምን ቀለም @OLDBOOKSPDF የገባኝው አይታወቅም ፤ ብቻ ከቀይ ዳማም ትንሽ ጠየም ብሎ ፣ ያባትንትን ፍቅር ከመለኮትንት ግርማ ጋር አዋህዶ የሚገልጽ ነው ። የቅርቃ ፊገግታው ፣ የሁለቱ ወጣቶች ፍቅር ደስ አሰኝቶት ችግራቸው ያላነነው ይመስላል ። ሁለት ልጆቹን ከመ ንግስፊያው አውጥቶ ከላይ ወደ ታች አንግቦ ፣ ቅዱሳኑን የሚባርክ መስሎ ሲታይ ፣ እግዚአብሔር በገሀድ እዚያ የቆመ እንጂ የእግዚአብ ሄር ምስል አይመስልም ።

ጥላሁን ያን የሚያስገርም ምስል ፣ ልቡ በውስጡ ተንበርክኮ የሰገደ መስሎ ተሰማወና ፣ ሳይታወቀው አይኖቹን ዘግቶ ፣ እንገቱን ደፍቶ ፣ ብዙ ከቆዩ በሁዋላ ቀና ቢል ፣ ሶፊያም በግራ ጎኑ ቆማ ፣ እንደሱ አንገትዋን ደፍታ ሰባዩ ፣ የሚሰጡን በመሰማት የምትጠብቅ መሆንዋ ተሰማውና ፣ “ ሶፊያ ሶፊያ ሙላት ” አለ ፣ ሁዋላ ጥቅ እያለው እስኪሄድ ድረስ መጀመርያ በዝቅተኛ ድምጽ ፡“ ሶፊያ ሙላት ባሬ ሚሽቱ አድርጊ ሳገባሽ ፣ ሀብት ኖሮኝ ከሀብቱና ሀብት ሊሰጠው ከሚችሰው ሁሉ ድሎት ወይም ደረጃ ኖሮኝ ደረጃ ሊሰጠው ከሚች ሰው ክብሩና ኩራቱ ፣ ዝናዩ ፣ አስፍልቸለሁ ብዬ ተስፋ እንዳልሰጥሽ ይህ ሁሉ የሉኝም ። ከህጻንነቱ ጀምሬ አሁን እስከ ደረስሁበት የተኙ ጥዝሁበትን የህይወት ጎዳናየን መለስ ብዬ ሳየው ፣ ከችግር ጋር አዬ ታግሎ ፣ ሌሎችን አገልግለው ደለ በማለኝት ብቻ ደስ እንዲላቸው አድ ርጎ ፈጣሪ እስቀድሞ መድቦ ከፈጠራቸው ጋር የተጻፍሁ ይመስለኛል።

“ገና በህጻንነቴ ፣ እናቴ አባቴ ሞተው ፣ ወሊጋ በተወለድሁባት መንደር ላንድ ባለጸጋ ባላገር ፈኝነት ተቀጥሬ እቤቱ ስኖር ፣ ዳረጎት በርከት አድርጎ ከሚያጎርሰኝና ከሚጠጣው የጥንጫ ጭላጭ ከሚሰጠኝ በቀር እንኩዋ ከሚገዛልኝ የበለጠ ፣ ከብቶችን ሳርና ውሀ አጥግቤ በማ ሰሁ ግቢ ደስ ብሎት ‘ ተባረክ ልጄ ’ ሲለኝ ደስ ይለኝ ነበር ። ከዚያ ትንሽ ከፍ እንዳልሁ ፣ ላንድ ሀብታም ነጋዴ ተቀጥሬ ፣ አዲስ አበባ መጥቼ ላጭር ጊዜ አብሬው ስኖር ፣ ‘ደመወዝ አልጨመረልኝም ፣ ወይም ጥርቫ አልሰጠኝም ’ ብዬ ቅር የተሰኘሁበት ጊዜ ትዝ አይለኝም ። ቅር የሚለኝ ፣ ጤና እጥቼ ፣ ወይም በሌላ ምክንያት ሳልችል ቀርቼ ፣ አገልግሎቱ የጎደለ ሲመስለኝ ብቻ ነበር ። ከዚያ ትምህርት ቤት ገብቼ፣ የተማሪዎችን ፍርፋሪ እዩበላሁ ፣ ውራጃቸውን እዩለበስሁ ፣ ከዘበኞች ጋር እያደርሁ ፣ አገልግሎቴን ለበን አድራጊዎቼ እየሰጠሁ ስማርም በሎሌነት ተቀጥሬ ሳገለግል ከኖርሁበት ጊዜ የተለዩ ስሜት አልነ በረኝም ።

@OLDBOOKSPDF

“ ይህ ፣ ከህይወቴ ጓደኛ ብቻየን የተጉዋዝሁበት ፣ የመጀመርያው ምእራፍ ነው ። ምንም እንኳ ካገልግሎቱም ሆነ ፣ አገልግሎቱ ከሰጠኝ ደስታ ባትካፈይ ፣ ሚሽቴ ስትሆኝ ታሪኬን የማወቅ መብት ስላለሽ ብቻ ነው አሁን የነገርሁሽ ።

“ ከንግዲህ ወዲያ ግን ፣ በምጉዋዘው የህይወት ጎዳናየ ብቻየን አልሆንም ፣ ልትከተይኝ ፣ አብረን ልንጉዋዝ ነው ! ያገልግሎቱ አይነትና የትግሉ መጠን ቢለያይም ፣ ከችግር ጋር እዩታገሉ ማገላገሉ መቸም እድል ነውና ይቀጥል ይሆናል ! ከዚህ በፊት ራሳቸውን መርዳት እዩቻሉ ሌሎች ቢረዱዋቸው ፣ ሌሎች ቢያገለግሉዋቸው የሚወዱትን ፣ የተመቻቸውን ብቻየን አገለግል ነበር ። እንግዲህ ወዲህ ራሳቸውን መርዳት ቢወዱም የማይችሉትንና የማያውቁትን ፣ የተቸገሩትን ፣ አብረን ልናገለግል ነው ! ከዚህ በፊት እታገለው የነበረ ችግር በግሬ ሮጬ ፣ በጀ ሰርቼ የማሸንፈው ነበር ። ከንግዲህ ወዲያ አብረን የምንታገለው ችግር ከልዩ ልዩ አቅጣጫ የሚመጣ ፣ ልዩ ልዩ መልክና ባህሪ የሚኖረው ፣ እጅግ አስመራሪ ሊሆን ይችላል ። ብቻ እግዚአብሄር ረድቶን አሸናፊዎች ስንሆን ደስታችንም ያንኑ ያክል ይሆናል !

“ ስለዚህ ሶፊያ ሙላት ፣ ዛሬ ሚሽቴ አድርጌ ሳገባሽ የምጥልልሽ ጥሎሽና የማቀርብልሽ ገጸ በረከት ፣ ለወደፊቱም የማካፍልሽ ሀብት ፣ ባለማወቅ ራሳቸውን መርዳት የማይችሉ ወገኖቻችን አውቀው ራሳቸውን እንዲረዱና ኑሮዋቸውን እንዲያሻሽሉ እረፍት ሳያምረን ፣ ምቾት ሳያስረን ፣ የምንታገለው ትግልና በዚያ የምናገኘው ድል የሚሰጠው የህሊና ጥጋብ ፣ የልብ ደስታና የመንፈስ ኩራት ነው !

“ ይህን መልክት ከኔ ጋር ሆነሽ ስትፈጽሚ ፣ በሚደርስብሽ ሁሉ አልለይሽም ፤ አልተውሽም ! ደስታሽ ደስታየ ፣ ሀዘንሽ ሀዘኔ ፣ ህይወትሽ ሕይወቴ ፣ ሞትሽ ሞቴ ይሆናል ! ከዛሬ ጀምሮ ወደፊት ፣ በሕይወትሽ ሁሉ ፣ በጎ ይሁን ክፉ ፣ ከሚቀዳልሽ ጽዋ ተካፋይ ለመሆኔና ላንቺ ታማኝነቴ ከህይወቴ በፊት የማይለዩኝ ለሆኑ ምስክር ይሆን ዘንድ ፣ ከጽዋሽ እጠጣለሁ ። ለዚህ እግዚአብሄር ይርዳኝ !” ብሎ ከጠርሙሱ ውሀ ብርጭቆውን ሞልቶ ሰጥቶጥት ፣ ጎንሽ ከጠጣች በሁዋላ ፣ የተረፈውን ሁሉ አይናቹን ከእግዚአብሔር አይኖች ሳይነቅል ጠጥቶ ብርጭቆውን አስቀመጠ ።

ከዚያ ፣ “ ጥላሁን ፈይሳ ” አለች ሶፍያ ፣ መጀመርያ እሱን ሁዋላ የእግዚአብሄርን ምስል ፣ በጥልቅ ተመስጦ እያዩች ። “ ዛሬ ባሌ አድርጌ ሳገባህ ፣ በሁብትህ ድሎት ፣ በደረጃህ ኩራት ፣ አገኛለሁ

@OLDBOOKSPDF

ብዬ ተስፋ በማድረግ አይደለም ። ሀብታሞችና እሕሩግ ለሆኑ ወላጆች ያለናቸው እኔና ሀብታቸው ብቻ ስለሆንና ፣ ትምህርታቸውን አጠና ቀው የጨረሱ ሁሉ በሚደርሱበት ከፍተኛ ደረጃ ለመድረስ እንድ እጭር ርምጃ ብቻ የቀረኝ ስለሆንሁ ፡ የራሴ ሀብትና ደረጃ የሚሰጠኝ ምቾትና ኩራት እፊቴ ቆሞ እዮጠራኝ ፡ የባለ ጥገኝ ሆኘ የምቾትና የማ እርግ ፍርፋሪ የምፈልግበት ምክናያት የለም ።

“ ሀብት የሚሰጠውን ምቾትና ደረጃ ፡ የሚሰጠውን ኩራት ወደ ጎን ገፍቸ ፣ አንተን መከተል የፈለግሁባቸው ምክናያቶች ሌሎች ናቸው ። እስከ ዛሬ ድረስ ፡ እንዳታውቅብኝ በጣም ተጠንቅቄ በምስ ጢር አኑሬያቸው ነበር ። ነገር ግን ፡ ከዛሬ ጀምረን ባልና ሚስት ስን ሆን ፡ ባካሌም ይሁን ስበሜቴ ለብቻ ባለቤትነቴ መቅረቴ ስለሆነ ፣ እንሱንም አሁን እንግርሀለሁ ። እንዱ ቤትነቴ ፡ ሁለተኛው ኩራቴ ናቸው። መጀመርያ ‘ ቤትነቴ ሀብትንም ፣ ደረጃንም አስትቶ አንተን እንድ ከተል አደረገኝ ’ ያልሁትን ልግለጽልህ ።

“ የእሕሩግ ወላጆቼ ሀብት ዛሬ በከፊል ፡ ነገ በሙሉ የኔ መሆ ኑን አይና ፡ ነገ ትምህርቴን ጨርሼ ስወጣ የተረጋገጠ ደረጃ የሚጠ ብቀኝ መሆኑን አይና ፡ ልቤ በዚህ ሁሉ ደስ እንዲለውና እንዲመካ ባላሰበው ፡ ሀብትም ፡ ደረጃም ፡ ለኑሮየ መተማመኛ ፡ ለህይወቴ ዋስ ለመሆን የማይበቁ ሆነው ይታዩኛል ! ሁልጊዜ አንድ የጎደለ ነገር እን ዳለ ይሰማኛል ! በሀብቴና በደረጃየ ራሴን ችዬ ፡ ደስ ብሎኝ ፡ ለመ ኖር የምችል መሆኔን እእምሮየ ለልቤ መላልሶ ለማስረዳት በሞከረ ቁጥር ፡ ልቤ በመረዳትና በመልኩም ዕድሉ በመመኘት ፈንታ በጣም ይፈራብኛል መንፈሴም ጸጥ በማለት ፈንታ ይታወከብኛል ። ከዚያ የልብ ደስታና የመንፈስ ጸጥታ አግኝቼ ፡ ከፍራትና ከመታወክ ነጻ ሆኘ መኖር የምችልበትን ፍለጋ ስሄድ ፡ ከሁሉም ወንድ ብቻ ሆኖ ይታዩኛል ! ነገር ግን ማንኛውም ወንድ አይደለም ። ብርቱ ወንድ ! ባካልም ፡ በመንፈስም ትልቅ ወንድ ! ጥኋሁን ፣ አንተንና የትምህ ርት ቤት ጓደኞችህን ከወቅሁዋችሁ ብዙ ጊዜ ነው ፤ ከናንተም ሌላ ብዙ ወንዶች አውቃለሁ ። ነገር ግን ከሁሉም ያ ልቤ የፈለገው ወንድ፣ ያ ከሀብትና ከደረጃ ይልቅ ለልቤ ደስታን ፣ ለመንፈሴ ጸጥታን ፡ ለቤ ትነት ፍራቴ እምነትን ፡ ሊሰጠው የቻለ ወንድ አንተ ብቻ . . . ነህ !”

“ ሁለተኛ ፣ ከሀብት ሸሽቼ ወዳንተ እንድጠጋ ያደረገኝ ኩራቴ ነው ያልሁህን እገልጽልሀለሁ ።

@OLDBOOKSPDF

"ግና በልጅነቴ ፣ ያንደኛ ደረጃ ትምህርቴን ሳልጨርስ ፣ ገና የመልኬ ንጽሕ ስጋ ለብሶ ደም ሳይቀባ ጀምሮ ፣ በወላጆቼ ሀብት ጌቶች ለመሆን የፈለጉ ሁሉ 'እናግባ' እያሉ የሚልኩት አማላጅ ፣ ዘመዶቼን እህል ውሀ የሚቀምሱበት ጊዜ ያሳጣቸው ነበር ። እኔም 'አዲስ አዲስ አረመኔ መጣ ባሉኝ' ቁጥር ፣ የልጅነት ልቤ ኩራት መጠን ያጣ ነበር ። ነገር ግን ሁዋላ ሁዋላ ፣ ሁሉም ማግባት የሚፈልጉ ሀብቴን እንጂ እኔን አለመሆኑ እዬገባኝ ሲሄድ ፣ እኔ የተፈለግሁበት ፣ በመሀል ቤት ደላላ ሆኖ የወላጆቹን ሀብትና እነሱን ለማገናኘት መሆኑን እዬተረዳሁ ስሄድ ፣ ሁሉቱንና ከሀብታሞች መወለዴን ጠላሁ ፤ ራሴንም ናቅሁ ! ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ፣ ልቤ ሀብት የሚንቅ ፣ ከሀብቴ ለይቶ እኔን ብቻ የሚወድ ወንድ ይፈልግ ጀመር ። 'እንዲያ ያለ ወንድ ባገኝ ፣ እንኳንስ ሚስቱ አሽከሩ ሆኜ ባገለግለው የበለጠ ኩራት በተሰማኝ' እያልሁ ብመኝ ፣ ከሀብት ለሰው ፣ ከመገልገል ለማገልገል፣ ከመደሰት ለማስደሰት ፣ ቅድሚያ የሚሰጥ ፣ የመኖሩን ምክንያት ፣ የህይወቱን አላማ ለመጥቀም እንጂ ለመጠቀም አድርጎ የማያይ ወንድ አገኘሁ ። ጥላሁን ያ ወንድ አንተ ነህ ! ስለዚህ ሁሉን ትቼ አንተን የተከተልሁባቸው ምክንያቶች እነዚህ ናቸው ።"

"ጥላዬ ፣ እንደ ባል አወድሀለሁ ፤ ጥላሁን ፈይሳ እንደ ሰው ምኞትህንና አላማህን አከብራለሁ ። ስለዚህ ፣ እንዲህ ላለው ምኞትህና እንዲህ ላለው አላማህ ስትሰራ በሚደርስብህ ሁሉ አልለይህም ፤ አልተውህም ! ደስታህ ደስታዬ ፣ እዘንህ እዘኔ ፣ ህይወትህ ህይወቴ ፣ ሞትህ ሞቴ ይሆናል ! ከዛሬ ጀምሮ ወደፊት ፣ በህይወትህ ሁሉ ፣ ከፉም ይሁን በጎ ፣ ከሚቀዳልህ ጽዋ ተካፋይ ለመሆኔና ፣ ላንተ ታማኝነቴ ከህይወቴ በፊት የማይለዬኝ ለመሆኑ ምስክር ይሆን ዘንድ ፣ ከጽዋህ እጠጣለሁ ፤ ለዚህ እግዚአብሄር ይርዳኝ !" ብላ ከጠርሙሱ ውሀ ብርጭቆውን ሞልታ ሰጥታው ፣ ግማሹን ያክል ከጠጣ በሁዋላ ፣ የቀረውን ሁሉ ጠጣችና ብርጭቆውን አስቀምጣ አፍ ላፍ ሲገናኙ ፣ እግዚአብሔር ባረካቸው ።

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፭

# ዶክተር ሀዋስ በርሄ

ጥላሁንና ሰፊያ ጋብቻቸውን ካሰባረኩ በሁዋላ ፣ የኪ. ሄደው የሚሰሩትን የስራ ዝርዝር ተመካክረው አሰናዱ ።

1ኛ. የየኪ. ትምህርት ቤት አንድ አስተማሪ ብቻ እንዲያስተምርበት የተመደበ ስለሆነና ፣ የጥላሁንን ጊዜ በሙሉ የሚይዝበት ስለሆነ ፣ እሱ ለሌላ ስራ ፣ ያካባቢው ሕዝብ ዘመናዊ ኑሮ እንዲኖር ለመምራት ላሰቡት ስራ ፣ ጊዜ እንዲያተርፍ ፣ የትምህርት ቤቱን ትምህርት ሁለቱ ተከፋፍለው እንዲያስተምሩ ፤

2ኛ. የትምህርት ቤት ሥራቸውን ሲጨርሱ ፣ እስዋ ከፈረንጆች እንደ ተማረችው ፣ ላገሩ ሴቶች የቤት ባልትና ፣ የልጅ አስተዳደግ፣ እሱ ላዋቆች ያማርኛ ንባብና ጽሕፈት ፣ ከሂሳብ አራቱን መደቦችና እንዲሁም በጠቅላላው የኑሮ ማሻሻያ እንዲያስተምሩ ፤

3ኛ. ለመጀመርያ ከጥላሁን ደመወዝ የሚታሰብ ፣ ሲሆን ያራት ፣ ያለዚያም የሶስት ወር ብድር ያገኙ እንደሆነ ፣ መድሀኒት ገዝተው ፣ ከዚያም በሁዋላ ርዳታ የሚያገኙበት መንገድ ፈልገው ፣ ለየኪ. ህዝብ ጠለቅ ያለ የሀኪም እውቀት የማያሻው የህክምና አገልግሎት በነጻ እንዲሰጡ ፤

4ኛ. ያገሩ ህዝብ ያለውን ያክል ሀብቱን ፣ ጉልበቱንና አሳቡን አስተባብሮ በህብረት ከሰራ ፣ እንዳንድ አገሮች እንዳደረጉት ባጭር ጊዜ ኑሮውን ማሻሻል እንደሚችል እውቅ ስለሆነ፣እዚያ ያሉት ባለስልጣኖች ያለጥርጥር ፣ ደስ ብሎዋቸው ስለሚረዱዋቸው ፣ የህብረት ድርጅት እንዲያቋቁሙና፣እነሱ የድርጅቱ መሪዎች ሆነው፡በትምህርት ሆነ በማንበብ የሚያውቁትን ያክል አዳዲስ ያሰራርና ያኗኗር ዘዴ እንዲያስተምሩ ፤

5ኛ. የኪ ደርሰው አገሩንና ህዝቡን ካጠኑ በሁዋላ ፣ ለህዝቡ ኑሮ መሻሻል የሚረዳና እነሱ መስራት የሚችሉት ሌላ ስራ ቢኖር፣ እዚህ ከተመለከቱት ስራዎች ጋር ጨምረው እንዲሰሩ ተስማሙ ።

ከዚያ ጥላሁን ማዘዣውን አፋጥኖ ለማስወጣትና፣ ወዲያውም ብድሩ ለመድሀኒት መግዣ ያክል እንዲተርፈው ያራት ፣ ቢያንስ የሶስት ወር እንዲሆንለት ማመልከቻ ለማግባት ወደ ትምህርት ሚኒስቴር ሄደ ። ትምህርት

@OLDBOOKSPDF

ሚኒስቴር ሲደርስ ፡ ወደ ፎቅ ለመውጣት ደረጃውን እንዳጋመሰ ፡ ወንድይራድ አስታጥቄን ድንገት ከፎቅ ሲወርድ አገኘውና፡ ሁለቱም ደነገጡ ።

“ እ. . . ጥላሁን! ” አለ ወንድይራድ ፡ ደንግጦ እንደ ቆመ ጥርሱን አግጦ ። ከዚያ ቶሎ አስተጋብቶ ፡ ሁለቱን ደረጃዎች ሮጦ ወረደና ዘወር ብሎ ፡ ‘ ይቅርታህን ቸኩዬ ነው ፤ በሁዋላ አገኝሀለሁ ’ ብሎት ሲሄድ ፡ ጥላሁን ዝም ብሎ ቆሞ የወዳጅ ጠላቱን ካይኑ እስኪጠፋ ይመለከተው ነበር ። ከዚያ በቀጥታ ወደ ሂሳብ ክፍል ቢገባ ፡ ወደ ተመደበበት አገር በፍጥነት እንዲሄድ ማዘዣው ተጽፎ ስላገኘው ፡ የብድሩን ማመልከቻ አግብቶ ፡ ሁሉም በማግስቱ ፡ እጅግ ቢዘገይ በሳልስቱ የሚያልቅለት መሆኑን አረጋግጦ ወደ ቤቱ ተመለሰ ።

«ከሶስት ቀን በሁዋላ እዚህ እንዳናይህ » ተብለሀልሽ አለ ጥላሁን ሲመለስ ። ከወንድይራድ ጋር መገናኘቱን ሲነግራት አልፈለገም።

« ስንቅና መጓጓዣ ሳይሰጡህ ? »

« ሁሉም ከነገ ፡ ያለዚያም ከነገ ወዲያ አያልፍም » አሉኝ ።

« ለመድሀኒቱ መግዣ የፈለግነው ብድርም ይፈቀዳል አሉ ? »

« ያሰብነውን ለሂሳብ ሹሙ ገልጩለት ፡ ‘ማመልከቻ ጻፍና አሳብህን ደግፌ ለዋናው ዲሬክተር አቀርብልሀለሁ ’ ስላለኝ ማመልከቻ አግብቼ መጣሁ ። »

« አሁን ባለን ገንዘብ መግዛት የምንችለውን ያክል እንግዛና ፡ ንግ ብድሩን የፈቀዱልን እንደሆነ እንጨምራለን ፤ ድንገት ሳይፈቅዱ ቢቀሩም ጊዜ እንቆጥባለን » አለች ፡ ትንሽ ስታስብ ቆይታ ።

« እውነትሽ ነው ፤ በስንት እንግዛ ? »

« በሰላሳ ብር እንግዛ ! » አለች ፡ አዲስ አበባ የሚቆዩበትን ጊዜና ለዚያ የሚያስፈልጋቸውን ወጪ ከጠቅላላ ገንዘባቸው በጣቶቹዋ አጥቆች ላይ ባውራ ጣትዋ ደማምራና ቀናንሳ ። የጋራ ሀብታቸው እሰዋ ያመጣችው ሰላሳ አምስት ብር ፡ እሱ ከትምህርት ቤት እስከ ወጣበት ቀን ድረስ የሚደርሰውን ተሳስቦ ከመንግስት ተቀብሎ ፡ ለቤት ኪራይ ፡ ለመብራትና ለውሀ ፡ እንዲሁም ሳይከፈሉ የቆዩ አንዳንድ ጥቃቅን እዳዎች ከከፈለ በሁዋላ የተረፈው አስር ብር ተደምሮ ፡ በጠቅላላው አርባ አምስት ብር ነበር ። ስለዚህ ፡ ሶስት ቀን አዲስ አበባ ለሚቆዩበት አስራ አምስት ብር አስቀርተው ሰላሳው ብር ለመድሀኒት መግዣ እንዲውል ስለ ተስማሙ ወዲያውኑ ሊገዛ ሄደ ።

@OLDBOOKSPDF

“ ጥላሁን ፣ ማንን ታባርራለህ እንዲህ የምትሮጥ ? ” አለ አንድ ድምጽ ፣ በቤቱ አጠገብ የሚያልፈውን ኮረኮንቻ መንገድ ይዞ እዬተ ጣደፈ የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴን ጎዳና ሲገባ ። ጥላሁን ያ ድምጽ ከየት እንደ መጣ ስላላወቀ ፣ ቆም ብሎ ቀኝና ግራውን እዬዞረ ሲያማብር ፣ አጠገቡ ካለው ቤንዚን ማደያ ዶክተር ሀጎስ በርሄን ወደሱ እዬተመ ለከተ ሲስቅ አዬው ። ለጊዜው የጠራው ዶክተር ሀጎስ መሆኑን ስላላ ረጋገጠ ግር ብሎት ቆመ ።

« እስቲ ና ፣ ስትቸኩል ሳይህ ጊዜ ወደምትሄድበት በመኪና አደር ስህ እንደሆን ብዬኮ ነው ! » አለ ሀኪሙ ፈገግ እንዳለ ወደ ጥላሁን እያመራ ።

« ኦ . . እግዚአብሄር ይስጥልኝ ዶክተር ! እዚሁ ቅርብ ነው የም ሄድ ፤ሩቅ አይደለም ። ይገርማል ! መቸኩሌ አልታወቀኝም ነበር ። እቸኩል ኖሮዋል ? » አለ ጥላሁን ፣እሱም በፈንታው ሰላምታ ለመ ስጠት ወደ ሀኪሙ እያመራ ።

« መቸኮል ብቻ ነው ? መሮጥ ነው እንጂ ! ና ግባ ወደምትሄድ በት ላድርስህ » አለ ሀኪሙ ፣ ሰላምታ ከተሰጣጡ በሁዋላ አጠገቡ ወደ ቆመችው መኪናው እያመለከተ ።

« የለም ሩቅ አልሄድም ፤ እዚሁ መድሀኒት ቤት ነው የምሄድ»

« መድሀኒት ለማን ነው ? ላንተ ነው ? ወይስ ለዘመድ ! »

« አስተማሪ ሆኜ ቭር አገር ስለምሄድ ለኔም ፣ ብችል ባካባቢየ የሚኖረውን ህዝብ በመጠኑ . . : ለመርዳትም ነበር » አለ ጥላሁን እያ መነታ ።

« አስተማሪ ? ሀገን ትተህ ? » አለ ዶክተር ሀጎስ በድንጋጤ ።

« ለጊዜው. . . አቋዋረጥሁ ። »

« ለምን ? »

« ወድጄ ። »

« አላምንም ! ያልፈለግህበት ምክናያት ይኖርሀል እንጂ ፣ አንተ ትወድቃለህ ብዬ ጭራሽ አላምንም ! »

« ዶክተር ፡ እመነኝ ! በዚህ ዓለም ካለመቻሌ በቀር ህግን የምተ ውበት ምንም አይነት ምክናያት ፣ በህግ የምለውጠው ምንም አይነት ነገር የለም ! ባለመቻሌ ብቻ ከማናቸውም ነገር አብልጬ የምወደ ውን ሙያው ግድ ሆነብኝ ። »

@OLDBOOKSPDF

« ሲገባኝ አይችልም እንጂ ፣ ጥላሁን ! »

« ቀላልኮ ነው ፣ ዶክተር ! ወድቀሀል ትባልሁ ፤ ልድገም ብል ተከለከልሁ ፤ ስለዚህ የምወደውን ትቸ መሄድ ተገደድሁ ! »

« ወዮው ጉድ ! በል ና ግባ መድህኒት በርካሽ በምትገዛበት ቦታ ልውሰድህ ! » አለ ዶክቶር ሀጎስ ፣ አይኖቹን አመሬት ተክሎ ፣ እዩቶከዘ ሲያስብ ቆይቶ ።

ዶክቶር ሀጎስ ጥላሁንን ወደ ግል ማከሚያው ወስዶ ለሁለቱም ቡና አዝዞ ካስመጣ በሁዋላ ፣ « የምትሄድበት አገር ማን ይባላል ? » አለ ።

« የኪ ይባላል ፤ ኢሉባቦር ውስጥ ነው » አለ ጥላሁን ።

« እ ፤ የኪ ! በጣም ጥሩ አገር ነው ፤ አውቀዋለሁ ። »

« ምን ልታደርግ ሄድህ ? »

« ቢጫ ወባ ሲኖርባቸው ይችላል » ተብለው የሚጠረጠሩትን ቆላ አገሮች አዩዞርን ስናጠና ፣ በዚያ በኩል የኪ ፣ ሚዛን ተፈሪና ማጂ ድረስ ሄጀለሁ ። የኪ እንዲያውም አካባቢውን ስናጠና ሰፈራ ችን ነበር ፤ አገሩ መቸም አሁን እንዳልሁህ ጥሩ ነው ፤ ብቻ ምንም ያልተሰራበት ድንግል ነው ፤ ትምህርት ቤት እንኩዋ ያለበት አል መሰለኝም ነበር ። »

« አሁንምኮ እንደሌለ የሚቆጠር ነው ፤ አንድ አስተማሪ ብቻ የሚያስተምርበት ትምህርት ቤት አለ ይባላል ? »

« ቢሆንም ጭራሹን ከሌላቸው . . ይሻላል » አለ ሀኪሙ በዝቅተኛ ድምጽ ፣ አይኖቹን ባያረግብ ፊት - ለፊት ተክሎ ። ጥላሁን የሀኪሙን ፊት ሲያይ አሳቡ ወደ ሌላ የሄደ መሰሎ ስለ ተሰማው ፣ ዝም ብሎ ይመለከተው ጀመር ።

«በተለይ የምትፈልገው መድህኒት ከሌለ ፣ በጠቅላላው ላገሩ የሚያስፈልጉትን መድሀኒቶች እኔ አውቃቸዋለሁ ፤ ልጻፍልህ ? » አለ ዶክቶር ሀጎስ ፣ አይኖቹን ከተከለበት ወደ ጥላሁን መልሶ ።

« ላገሩ ከሚያስፈልጉት ሌላ የምፈልገው የለም ። »

« ጥሩ ! » አለና የማስታወሻ ደብተሩን አቅርቦ ፣ የመድሀኒት አይነት ፣ ብዛት ፣ ብሎ ፣ እርእስት ጽፎ ፣ አስምሮ እያሰበ ባርእስቱ ስር ይጽፍ ጀመር ። ሲጽፍ ቆይቶ ፣ ቀና ብሎ ያስብና እንደ ገና ይጽፋል ። ደግሞ እንደ ገና ቀና ብሎ አይኑን ጭፍን አድርጎ ግንባሩን እያሻሸ ሲያስብ ይቆይና ፣ ደግሞ እንደ ገና ይጽፋል ። እንዲህ ቀና እያለ ሲያስብ ፣ ጎንበስ ብሎ ሲጽፍ ፣ ቆይቶ ፣ ሲጨርስ ፣ የጻፈውን ለጥላሁን አነበበለት ።

@OLDBOOKSPDF

| የመድሀኒት አይነት | ብዛት |
| --- | --- |
| የወባ መከላከያና ያመማቸውን ማከሚያ | አምስት ሺህ ፍሬ |
| የራስ ምታት መድሀኒት (ኤ. ፒ. ሲ.) | አምስት ሺህ ፍሬ |
| የቁስል ማጠቢያ ( አልኮል ) | አምስት የፕላስቲክ ጠርሙስ |
| የቁስል መድሀኒት( አዮዲን ) | ሃያ አራት ብልቃጥ |
| የቁስል መድሀኒ (ፒኒስሊን ዱቄት) | አምስት የላስቲክ ጠርሙስ |
| የቁስል መድሀኒት( ፔኒስሊን ቅባት ) | አስር የፕላስቲክ ብልቃጥ |
| የቁስል ማሰሪያ | ሀያ አራት ጥቅል |
| የቁስል መለጠፊያ ትንሽና ትልቅ | ሁለት ሙቶ |
| ለተራ አይነማዝ( ጠብታ) | ስድስት ብልቃጥ |
| ለተራ አይነማዝ( ቅባት) | ስድስት ብልቃጥ |
| ላሜባ ሁለት አይነት | ከያይነቱ ሶስት ብልቃጥ |
| ለተራ ሆድ ቁርጠት ሶስት አይነት | አምስት አምስት ብልቃጥ |
| ለቁርጥማት ልዩ ልዩ | በጠቅላላው አስር ብልቃጥ |
| ለጉንፋን ሁለት አይነት | ከየይነቱ አምስት ብልቃጥ |
| ለቤትና ላካባቢ ተውላክ ማጽጃ(የሚበጠበጥ) | ሶስት ቆርቆሮ |
| ቬታሚን ልዩ ልዩ (ፍሬ) | ሶስት ጠርሙስ |

ከዚያ ተነስት ፣ የጻፈውን መድሀኒት ከፍቱም-ላጥኑም ፣ ከዩመላቢያ ወጭ ፣ እዩፈለገ አጠራቅሞ በጠረጴዛው ላይ በተራ አሰልፎ ፣ ከጽሁፉ ጋር አስተያይቶ ፣ ልክ መሆኑን ካረጋገጠ በሁዋላ ፣ ባንድ ትልቅ የፕላስቲክ ከረጢት ሙከተት ሲጀምር ፣

« ዶክቶር ፣ እኔኮ ያለኝ ሰላሳ ብር ብቻ ነው » አለ ጥላሁን ዝም ብሎ ሀኪሙ የሚያደርገውን ሲመለከት ቆይቶ ።

« ለምን ? »

«ለመድሀኒት መግዣ የያዝኩት ሰላሳ ብር ብቻ ነው ። »

« ለመንገደኛ ከሰላሳ የሚበልጥ ጉዳይ ሲኖር ስለሚችል ፣ ሰላሳውን ብር ከዚያ ላንዳንዱ አድርገው ፤ ይህ በነጻ የምሰጥህ ነው ። »

« በነጻ ? »አለ ጥላሁን ፣ በመገረም አይኖቹን በጥፍ አውጥቶ ።

« በነጻ ! »

« እንዴት ? ለምን ? »

« በነጻ ያገኘሁት ስለሆነ ! መድሀኒት አስመጪዎች ከሚያሰሙጡት መድሀኒት ሁሉ በነጻ ይልኩልናል ። ምክናያቱም እንዲያ ያለውን መድሀኒት ካዩን በሁዋላ ፣ በሽተኞቻችን ያን አይነት መድሀኒት

@OLDBOOKSPDF

እንዲገዙ እንድናግዝዛቸው ነው ። ስለዚህ ፣ አንድ ሳንቲም ያወጣሁበት አያለምና ፣ የመድሀኒቱ ጭንቅ ካልሆነ የይሉኝታ ሸክም እንዳይኩብ ድህ ተስፋ አለኝ » አለ ዶክተር ሀጎስ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ ።

« ከዚህ ሌላ የምነግርህ » አለ ሀኪሙ ፣ ከመሳቢያው ውስጥ ለሙና አድራሻው በሙሉ ያለበት መታወቂያ ወረቀቱን አውጥቶ ለጥላሁን ለመስጠት እጁን ዘርግቶ ። « ይህ በዝቶ የታዩህ መድሀኒት ፣ እሁን ስለሚያልቅ ፣ ይህን ይዘህ የኪ እንደ ደረስህ አድራሻህን ደህና አድር ገህ ጽፈህ የላክልኝ እንደሆነ በዩኒዘሪው ከኔም ፣ ከሌሎች ሀኪሞችም፣ እንዲሁ በነጻ ከሚያገኝ ት መድሀኒት የሚተርፋቸው ቢኖሩ ጨማምሬ፣ ልልክልህ የምችል መሆኔን ነው ። »

« ዶክተር » አለ ጥላሁን ፣ የዶክተር ሀጎስ ችሮታ ልቡን ጠልቆ ስለ ነካው ፣ ስሜቱን የሚገልጽበት አጥቶ ፣ አንገቱን እንደ ደፋ ዝም ብሎ ከቆዩ በሁዋላ ። « እንኩዋንስ አገኛለሁ ብዬ ተስፋ ሲኖረኝ ከምኞ ቴም እጅግ የራቀ ችሮታ ነው ያደረግህልኝ ። ስለዚህ ፣ እግዚአብሄር እንደ ዛሬው ፣ እንደኔ ባላሰብቪው ፣ ተስፋ ባላደረግኸው ፣ ከምኞትህ እንኩዋ በራቀ መልካም ነገር ደስ ያሰኝህ ! »

« አሜን ፤ በምትሄድበት ይቅናህ » አለ ዶክተር ሀጎስ ፣ ከተቀ መጠበት ተነስቶ የጥላሁንን እጅ በሁለት እጆቹ አጥብቆ ጨብጦ የስ ንብት ሰላምታ እዩሰጠ ።

« መድሀኒት ልትገዛ ሄደህ ምን ተጭነህ መጣህ ? » አለች ሶፊያ፣ ከረጢት ሙሉ መድሀኒቱን ተሸክሞ ሲገባ ።

« መድሀኒትክ ነው ! »

« አንድ ጭንት መድሀኒት በሰላሳ ብር ? »

« ተቀመጭ ላሳይሽና በስንት እንደ ገዛሁት ሁዋላ እንገርሻለሁ» አለና ከከረጢቱ እያወጣ ቢያይነቱ በጠረጴዛው ላይ ደርድሮ ካሳያት በሁዋላ ፣ አሁን በስንት እንደ ገዛሁት ልንገርሽ ? » አለ ።

« እስቲ ! »

« በነጻ ! »

« ደሞ በነጻ መግዛት እንዴት ነው ? » አለች ሶፊያ እዩሳቀች ።

« ዶክቶር ሀጎስ በርሄን ታውቂዋለሽ ? »

« ስሙን ነው ፤ መልኩን አይቸው ለላውቅም ። »

@OLDBOOKSPDF

" ቅድም ከቢሮ እንደ ወጣሁ ፣ እዚህ እቤንዚን ማደያው ተገናኝተን ከማንጋገር ፣ ከትምህርት ቤት መውጣቴንና አስተማሪ ሆኜ የኪ. ለመ ሄድ ለለምለናዳ መድሀኒት ልገዛ የምሄድ መሆኔን ስነግረው ፣ ትምህርቴ በመቋረጡ በጣም ሲያዝን ቆይቶ ' መድሀኒት በርካሽ ከምትገዛበት ልውሰድህ ' ብሎ ወሰደ ፤ እይውልሽ ይሆን ሁሉ መድሀኒት በነጻ ሰጥቶ ሰደደኝ ! ደግሞስ ይህ ብቻ መሰለሽ ? ' የኪ. እንደ ደረስህ እድራሻህን በትጽፍልኝ የምትፈልገውን መድሀኒት በፍጊዜው እልክልሀለሁ ' ብሎ፣ እይው የሱን አድራሻ ሰጠኝ ! " አለ ፕላሁን ፣ የሀኪሙን መታወቂያ ወረቀት ለሰፊያ እያሳየ ።

" የብዙ ጊዜ ወዳጅነት አላችሁ ? "

" እንኳዋንስ የብዙ ጊዜ ወዳጅነት የብዙ ጊዜ መተዋወቅ የለ ንም ። አንድ ቀን ' አዲሱ ሆቴና ኢትዮጵያ ' በተባለ ርእስ ላይ በኮ ሌጅ ንግግር ያደረግሁ እለት ታስታውሻለሽ ? ያን እለት ፣ አንዳንድ ጉዋደኞቼን ፍለጋ መጥቶ እዚያ ስለ ነበረ ፣ ከስብሰባው አዳራሽ ስን ወጣ ፣ ያላስተዋዋቂ ራሉን መጥቶ ፣ ማን መሆኑን ከነገረኝ በሁዋላ ፣ መጀ መርያ በተናገርሁትም ፣ ሁዋላ ካስተማርኝና ከተማሮች ስጠየቅ በመ ለስሁትም ፣ በጣም ደስ የተሰኘ መሆኑን እዩገለጸ ፣ እጄን በሁለት እጆቹ ጨብጦ አመሰግኖኝም ፣ መርቆኝም ሄደ ። ከዚያ ቀን በሁዋላ ፣ ከዛሬ በቀር አይቸው አላውቅም ። እይውልሽ መተዋወቃችን እዚህ ድረስ ነው ! "

" የሚያስገርም ነው ፤ ግሩም የሆነ አጋጣሚ ነው ! " አለችና ትንሽ ስታስብ ቆይታ ፣ ' ልጠንቁል ? ወይም ትንቢት ልናገር ? ' አለች እዩሳቆች ።

" ስለምን ? "

" ወደፊት ስለሚገጥመን ። "

" አትጠንቁይ ፤ ትንቢት ተናገሪ " አለ ፣ እሱም እንደ መሳቅ ብሎ ።

" ያው አይደለም ? ትንቢት የአራት ጥንቆላ የህዲስ ከመሆናቸው በቀር ጥንቆላና ትንቢት አንድ አይደለም ? "

" አንድ አይደሉም ፤ ' ትንቢት የእግዚአብሄር ፣ ጥንቆላ የሰይጣን መልእክቶች ናቸው ' ይባላል ! "

" እሺ ትንቢት ልናገር ። "

" እስቲ ! "

@OLDBOOKSPDF

"እግዚአብሄር በምንሄድበት አገር ፣ ባሕሩን ዘመድ ፣ አውሬውን ለማድ አድርጎ ፣ የማያውቁን ሁሉ እንዲወዱን ፣ እንዲረዱን አድርጎ ፣ የምንሰራውን ሁሉ የተቃና አድርጎ በጣም ደስ ያሰኘናል !"

"እሜ. . ን" አለ እዮሳቅ ።

"መሳቁን ትተህ ይህን ትንቢት ያናገረኝን አትጠይቀኝም ?" አለች ፣ እስዋም እዮሳቀች ።

"እሺ ፤ ምንድነው ?"

"ለጉዞዋችን መሰናዶ ለንጀምር የገጠመን ደስ የሚያሰኝ ገድ"

"እንዴት ?"

"እናባባና ሀረር የማውቃቸው ሽማግሌዎች ሁሉ እንደሚሉት ፣ ሰው ሳደን ፣ ለሙግት ፣ ለገበያ ፣ ወይም ለሌሎች አበይት ጉዳዮች ታጥቆ ከቤቱ ሲወጣ ፣ መጀመርያ ደስ የሚያሰኝ ነገር የገጠመው እንደሆን ! 'ጥሩ ገድ ነው' ይሉና በሚሄድበት ጉዳይ ቀንቶት ፣ ደስ ብሎት እንደሚመለስ ርግጠኛ ሆኖ ይሄዳል ፣ ግና ሲወጣ መጥፎ ነገር የገጠመው እንደሆነ ግን ፣ 'ክፉ ገድ ነው' ብሎ ፣ ይመለሳል እንጂ መንገዱን አይቀጥልም ። እኛም ዛሬ የጉዞዋችንን መሰናዶ ለመጀመር ገና ከቤትህ ስትወጣ የገጠመህ ደስ የሚያሰኝ ገድ ፣ በጉዞዋችን መጨረሻ የሚቆዩንን ደስ የሚያሰኝ ኑሮ የሚያመለክት ነው ። አዬህ ? ሀኪም ሀኪን 'ከንድ ቀን በቀር አይቼው አላውቅም አልህ' ነገር ግን ፣ የስራህን ስራ ከልብ ወዳጆች እንኳ ፣ እረ ከዘመዶች እንኳ የሚሰሩ ቢኖሩ በጣም ጥቂቶች ይሆናሉ ። ይህ በምንሄድበት አገር የማያውቁን ሁሉ የሚወዱን ፣ የሚረዱን መሆናቸውን የሚያመለክት ነው !"

"እሜ. . ን !" አለ አሁንም ፣ ራሱን እስከ ጠረጴዛው ዝቅ አድርጎ ሲሰግድ እዮሳቅ ።

"ይህ ያልሆነ እንደሆነ እውነቱ . . ." ብላ የምትጨርስበት ስታፈልግ ፣

« ጠንቋዋይ ልበልሽ ? » አለ ጥላሁን እቋዋርጦ ።

« አትበለኝ ! » አለች ፣ እየሳቀች ።

« ያገርማል ! » አለ ፣ ከቀልዱና ከሳቁ በሁዋላ ቶንሽ ዝም ብለው እንደ ቆዩ ።—

« የትምህርት ሚኒስቴር ወደ ዳር አገር የሚልከው አስተማሪ መፈለጉንና ፣ እኔ ከፈለግሁ የሚቀበለኝ መሆኑን አስፉ ሳይነግረኝ ፣ ውቤቱ በዛብህ የሚባል ጓዋደኛዬ የዬኬንና ያባቢውን ሁኔታ ተረቶ

@OLDBOOKSPDF

ተራቾች ባሳባቻው የፈጠሩት ፣ አንድ እጹብ ድንቅ የሆነ አለም እንጂ፣ በወኅኑ እዚህ በምንኖርበት ምድር ሊኖር የማይችል አስመስሎ ፣ ከፕቂቶች አመታት በፊት ጽፎልኝ ነበር ። ታዲያ ፣ « አንዳንድ ስለርሻ የተጻፉ መጻሮች ይገፎ ወደዚያ አገር ብሄድና ፣ የርሻ ስራ ብሰራ ፣ ባካባቢያ የሚኖረው ህዝብ የኔን ያሰራር ዘዴና ውጤቱን አያዩ ፣ ያሰራር ዘዴውንና በዚያም አድርጎ ኑሮውን ሊያሻሽል ይችል ይሆን ? » ብዬ ሳሰላስልና ፣ "ልሂድ ልቅር እያልሁ ሳመነታ ነበር ። አሁን 'እዚያው አገር መመደቢ ምን ዓይነት አጋጣሚ ነው ! ' ብዬ ገረመኝ ።»

« ወብቱ በዛብህ ማነው ? የማውቀው አይመስለኝም ። »

« ሁለተኛ ደረጃ ፣ እሱ አስራ ሁለተኛ ፣ እኔ ዘጠነኛ ክፍል ሁነን ልክ እንደ ጅራት ከሁዋላው ተለይቼ የማላውቅ ፣ በጣም የምወደው ጓደኛዬ ነበር ። ከዚያ ኮሌጅ ገብቶ ሁለተኛ አመቱን እንደ ጨረሰ ፣ ' ወድቶሀል ' ተብሎ ስለወጣ ፣ እዚህ ስራ አጥቶ በዩመስሪያ ቤቱ በር ሲለንብ ቆይቶ ፣ ተሰፋ ወደ መቁረጡና ተስፋ የቆረጡ ሰዎች የሚያደርጉትን ለማድረግ ወደ መድረሱ ላይ ከተቃረበ በሁዋላ ፣ አገር ግዛት ሚኒስቴር ይሁን ፣ ግንዘብ ሚኒስቴር እንጃ ! አንዳቻው በጸሐፊት ቀጥረውት ጎሬ ሄዶ ይሰራል ። »

« እንዲህ ያለውን ልጅ እንዴት ሳላውቀው ቀረሁ ? እንተም ስሙን ስታነሳ ሰምቸህ አላውቅም ! »

« እንጃ ! ምናልባት ከሀረር ሳቸመጭ ከኮሌጅ ለቆ ይሆናል! ብቻ … ሰው ሁሉ የሚገረምበት ፣ ' የት ይደርስ ይሆን ' የሚባል ፣ በጣም ብልህ ልጅ ነበር ! »

« ሰመሆኑ ምን ብሎ ጽፎልህ ነው በማታውቀው አገር ፣ እንዲያው እውር ድንብሩን ፣ ልትሄድ አስበህ የነበር ? »

« ሰው መሄጃ ሲያጣ ነው መውጫ ፍለጋ እውር ድንብሩን የሚዳብሰው ! » አለና የቅርታ ፈገግታ ፈገግ ብሎ ፣ ውብቱ የጻፈለትን ለማስታወስ ፣ አይኖቹን ባያረግብ-ፊት ለፊቱ ተክሎ ሲያስብ ቾንገሽ ቆዩ ።

«ጺ. . . ! አሁን ስንቱን አስታውቬ ልንገርሽ ? ብዙ ጊዜ ይጽፍልኛል ። አሁን ' ለመሄድ አሳሰበኝ ' ያልሁሽ ግን ፣ በተለይ የኪ የገዛውን መሬት ለማየት ሄዶ እንደ ተመለሰ የጻፈልኝ ነው ። ከጻጻፉ ማማርም ሌላ በጣም ረዥምም ስለሆነ ፣ ቆንጣጥዬ ብነግርሽ እንዳላበላሸው ወረቀቱን ፈልጌ ባገኘው ፣ ብሰጥሽና ብታነቢው ይሻላል ። ብቻ ከዚያ ረዥም ወረቀት ያልረሳሁት ፣ ወደፊትም ልረሳው የማልችል ፣ እንዲህ የሚለው ነው ። »

@OLDBOOKSPDF

« በጠቅላላው [illegible] አገር ነው ፤ የኬኛ አካባቢው ግን ልዩ ነው ! የኬኛ አካባቢው ልዩ እንዲሆን ጥንቱን የፈጣሪ ፈቃድ ስለሆነ ፣ ዙሪያውን የማያቋርጥ የተራራ ግንብ ገንብቶ በዚያ አጥርታል ! እዚያ ውስጥ ፈጣሪ የፍጥረቱን ህግ አሻሽሎ ፣ ጊዜን በበጋና በክረምት በመከፋፈል ፈንታ ፣ ሁሌ ጊዜ ክረምት ፣ ሁሌጊዜ በጋ እንዲሆን አድርጎታል ። እዚያ ውስጥ ፣ ቀኑ ለጸሐይ ፣ ሌቱ ለዝናብ እንዲሆን ተመድቦ ፣ ሁለቱም በስምምነት አገልግሎታቸውን ያለማቋረጥ እንዲሰጡ አድርጓል ። እዚያ ጸሐይ ያለመጠግግል እንጂ ፣ አያጠወልግም ! እዚያ ዝናብ አፈር ይከምራል እንጂ አይጠርግም ! እዚያ መሬት እንዲሁ አብቅላ ታብላለች እንጂ አትቃረስም ! ውሀ ይሞላል እንጂ አይደፈርስም ! ዛፍ ይረዝማል ፣ ይጠምራል እንጂ አይጣመምም ፤ አይጎብጥም ! እዚያ ጫካው ቡናውን ፣ ኮረሪማውን ፣ ማሩን ፣ ሸንኮሩን ፣ ሙዙን ፣ ፓፓያውን ፣ እንዲሁም ስሙና ቁጥሩ የማይታወቅ ብዙ ፍራፍሬ ራሱ ሰርቶ ፣ ጠብቆ ፣ ለሰውና ላውሬው ያከፋፍላል ። እዚያ አገር ስርቶት ለበሉ ፣ ከብት ላገለገሉት ሲፈለግ ብቻ ከጫካው ተፈልጎ ይመጣል እንጂ ጋጥ ፣ ወይም በረት አይሰራለትም ! እዚያ አገር ያለው ከሌላው ጋር መካፈል ፣ ትዋሪ ስራት ስለሆነ ፣ የሰበትና የንፍገት ፣ እንኪዋንስ ግብራቸው ስማቸው አይታወቅም ! እዚያ አገር አሰት መናገር ስለሌለ ፣ ድንገት በስቶት ፣ ወይም በደም ፍላት ተገፍቶ ነፍስ የሚገድል ቢኖር ፣ መጀመርያ መስክሮ እጁን የሚሰጥ ገዳዩ ራሱ ነው ! » ካለ በሁዋላ ፣ ወደ መጨረሻው እንዲህ ይላል ። ‹‹ንገርግን ፣ ‹ይህን ሁሉ አይተህ ፣ ይህን ሁሉ ሰምተህ ፣ እንዲያ ያለው አገር ያንተ በመሆኑ ፣ እንዲያ ባለው አገር ባለቤት በመሆንህ ፣ ደስታና ኩራት የተቀመጣህበትን መሬት አስለቅቀው ፣ አንስተው ፣ የሚያንሳፍፉህ ሲመስልህ ፣ ወዲያው እንዲያ ያለችዋ ወብ አገር በድንግልና ወደማርጀት መሄድዋ ፣ እንዲያ ያለው ህዝብ የጉልምስናን ሀይልና ደስታ ሳያውቅ ፣ ልዩ ልዩ በሽታና ችጋር በቀጥታ ወደርጅና የሚያስተላልፉት መሆኑ ሲታሰብህ ፣ ደስታህም ፣ ኩራትህም እንክት ፣ ንኩት ፣ ብሎው ይሰቁህና ከሩቅ ትወድቃለህ ፤ መሬት ትገባለህ ! › እይውልሽ ፣ ከዚያ ረዥም ደብዳቤ አልፎ አልፎ ልቤን ስለነኩት ፣ ያልረሳሁዋቸው እነዚህ ክፍሎች ናቸው ፤ ቆይ ፈልጌ አስጥሽና ታነቢዋለሽ ። »

« ታዲያ አውነት . . . አገሩና ሁኔታው ሁሉ እንዲህ እንደ ጻፈው ይሆን ? ወይስ . . . እንዲያው ራሱ ፈጥሮ የጻፈው ይሆን ፣ ! » አለች « ውቡ ከጻፈው የማስታውሰው ክፍል ነው » ብሎ ሲናገር ዝም ብላ ስታደምጥ ቆይታ ።

@OLDBOOKSPDF

« ትንሽ አጋኖ እንደሆን እንጂ ፈጥሮስ አይደለም ፤ ዶክተር ሀን ስም ‘ የሀገሩ ውበት ማመዛዘኛ የለውም ’ ብሎ ነገረኝ ። »

እሺ እስቲ . . . ያገሩ ውበትስ እሱ እጋኖ እንደ ጻፈውም ይሁን፣ ታዲያ አንተ ከርስቱ ርስት ፣ ከገንዘቡ ገንዘብ ሳይኖርህ ፣ ባዶ እጅ ህን ብትሄድ ፣ እንዲሁ ያን ከንቱ የሚበላሽ ውበት አይተህ አድንቀ ህም ፣ አዝነህም ፣ ለመመለስ ነው ? ወይስ ‘ምን አደርጋለሁ ’ ብለህ ነው ልትሄድ አስበህ የነበር ? »

« ርስትማ ውበቱ ፣ ‘ገዝቸልሀለሁ’ ስላለኝኮ ነው ፡ ‘ ለመሄድ አሰቤ ነበር ’ ያልሁሽ ! ያለዚያማ ምን ላደርግ እሄዳለሁ ? »

« ርስት ገዝቸልሀለሁ አለኝ አላልሽኝምኮ፤ ርስት ገዝቶልሀል እንዴ፤ እውነትም እንዴት ይወድሀል ! »

« ለኔ የገዛውን አምስት ጋሻ መሬት ሊያይ ሄዶኮ ነው ያገሩን ማማርና የሀዝቡን ሁኔታ አይቶ ፣ እንዲያ አድርጎ የጻፈልኝ ! »

« በገንዘቡ ነው . . . አምስት ጋሻ መሬት የገዛልህ ? » አለች ፣ በመ ገረም አይንዋን ሁሉ አውጥታ ።

« አዎ ፤ ብቻ በምን ያክል ገዛው መሰለሽ ? »

« በምን ያክል ገዛው ? »

« እንዱን ባምስት ብር ፤አምስቱን በሀያ አምስት ብር ! »

« ትቀልድብኛለህ መሰለኝ ! » አለች ሰፊያ እየሳቀች ።

« ቀልድ አይደለም ፤ ምሬን ነው ። ብቻ ምክንያት አለው ። »

« ምን ? »

« ጃንሆይ ኢሉባቦርን ሊጎበኙ ሄደው ፣ ‘የዚያ አገር ህዝብ የመ ሬት ችግር አለበት ’ ስላሉዋቸው ፣ እዚያ ያለው ብዙ ሺህ ጋሻ የመን ግስት መሬት ፣ ባምስት ባምስት ብር ለህዝብ እንዲሸጥ አዘው ተመ ለሱ ። ወዲያው እዚያ በጊዜው የተገኙት የመንግስት ባለስልጣኖችና ሰራተኞች ፣ ያን ሁሉ ጋሻ መሬት እንዳንድ ቀይ ሳንቲም ሳያወጡ በዘራሳቸው ፣ በዘመዶቻቸውና በወዳጆቻቸው ስም እዛውረው ፣ መዝ ገብ አግብተው ይጠብቁ ጀመር ። ከዚያ በሁዋላ ምን ልበልሽ ! መሬት ሊገዛ ለሚሄድ ሁሉ ፣ መጀመርያ ጋሻውን ባራትና ባምስት መቶ ብር ትንሽ ቆይተው ፣ ጋሻውን በሽህና በሁለት ሺህ ብር እዬቸበቸቡ ፣ ባንድ ጊዜ ፣ እንኩዋንስ ሰው ማነጋገር ማየቱም የሚያሰለቻቸው ጌቶች ሆኑ ! እይውልሽ ፤ በዚያ ጊዜ ነው ውበቱ የመንግስት ባለስልጣን ፣ ወይም ሰራተኛ ስለነበረ ፣ ‘ዉሀያ አምስት ብር አምስት ጋሻ መሬት ገዛሁልህ ’ ያለኝ ! »

@OLDBOOKSPDF

“ ቆይ እስቲ አልገባኝም ! ታዲያ አሁን እንዳልከው ከተደረገ ድሀው ምን አገኘ ? ”

“ አይ ፣ እንቺ ደግሞ ! ድሀውማ ካገኘ ፣ ድሀ መሆኑ ይቀርና በድሀ ላይ ጌታ መሆን ይቀርናል ? እንኳንስ ድሀው ከሀብታሞችም እዚያ ከነበሩት የመንግስት ባለስልጣኖችና ሰራተኞች ዘመዶች ፣ ወይም ወዳጆች በቀር ፣ ያገኙ ቢኖሩ ያለጥርጥር ጥቂት ይሆናሉ ፤ ድሀውስ ያው እንደ ልማዱ ፣ እኒያን ጥቂት ሰዎች ለማበልጸግ ምክንያት ሆነ ! ”

“ይገርማል ! መቼ ነው የጻፈልህ ? ”

“ሁለት አመት ያህል የሚሆን ይመስለኛል ። ”

“ታዲያ አሁን ያ መሬት ይኖር ይመስልሀል ? ”

“ ጌታ ይለወጥ እንደሆን እንጂ መሬቱማ የት ይሄዳል ? ”

“ እንዲያ ማለቴኮ ነው ! ከሁለት አመት ወዲህ አልጻፈልህምን? ”

“ የተገባበት ሁኔታ ደብ ስላላሰኝ ፣ ስለ መሬቱ እንሰማበት አላውቅም እንጂ እንጻጻፋለን ። ”

“ አሁን ከምንሄድበት ሩቅ ይሆን ? ”

“ ያው የምንሄድበት አገር ነው እንጂ ! እሱ አስገርሞኝኮ ነው . . . ይህን ነገር ያነሳሁልሽ ! ”

“ ነው እንዴ ! እውነትም እንዴት የሚያስገርም አጋጣሚ ነው ! እንግዲያ ያለ ጉዋደኛህ ለሌላ ሰው ባልሰጠው ፤ ወይም ባልሸጠው ! ”

“ አሁንማ ምን ያደርግልናል ? ለመስራት ካሰብነው የሚተርፍ ጊዜ ኖሮን የርሻ ስራ ለመስራት አንችል ! ”

“ አዎ እውነትህ ነው ፤ ጊዜ አይኖረንም ! ” አለች ፣ አይኖቹዋን ሳታረግብ ፣ ፊት ለፊት ትክር አድርጋ ። ከዚያ ቅር ያለው ፊትዋ በፈገግታ አጊጦ አይኖቹዋን ካተከረችበት ወደ ባልዋ መለስ አደረገችና “ ግብዝ ፣ ወይም ሰይጣን አትበለኝና አንድ ነገር ልንገርህ ። ”

“ ምን ? ”

“ እዚህ ሆነን እንደምንሰማው የዳር አገር ኑሮ ክፉው ነገር ሁሉ ተሰብስቦ የሰፈረበት ፣ እዩወደቁና እዩተነሱ ፣ እዩተንገላቱ ሲታገሉ የሚኖሩበት ” በመሆኑ ፈንታ ፣ ይህ ሁሉ የሌለበት ፣ እንዲያው . . . ደህና ሆኖ ያገኘነው እንደሆነ ፣ እኔ ደስ የሚለኝ አይመስለኝም ፤ የማዝን ይመስለኛል ።

“ እንዴት እባክሽ ? ” አለ ጥላሁን ፣ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ ።

@OLDBOOKSPDF

“ እዩህ ? እዚህ ሆነን የምንሰማው ሁሉ ፤ ሻር ሸገር ችግር ፤ በሽታ ድንቁርናና ሌላ ሌላውም ክፉ ነገር ሁሉ ተሰብስቦ ፤ ያገሩን ህዝብ የሚያሰቃይበት ፤ ከዚሁ ለስራ የሚሄዱት ፤ ገንዘብ ቢኖራቸው እንኳ ከለመዱት በሙሉ ባይሆን በከፊል የሚቀራረብ መብልና መጠጥ ፤ ልብስና መኖሪያ ፤ ቢታመሙ የህኪም ርዳታ ስለማያገኙ ፤ መንገላታት ፤ መጎሳቆሉ ፤ መቸገሩ ፤ እያስፈራራቸው ጥለው የሚሸሹበት ነው ። ታዲያ ፤ እኔ ከዚሁ ተሰናድቼ ፤ ታጥቄ የምሄድ ፤ እንዲያ ሌሎችን የሚያሸሽውን ችግር ፊት ለፊት ተጋሜ ድል የማድረግን ጀብድ ለማግኘት ነው ። አሁን እዚህ ሆኘ ሳስብ ፤ እዚያ ያለው ክፉ ነገር ተሰልፎ ሲቆዩኝ ፤ እኛ ከዚሁ ሄደን ገጥመን ፤ ተዋግተን ፤ ድል አድርገን ፤ የዚያ ክፉ ነገር ፤ ማለት የችግሩ ፤ የበሽታው ፤ የድንቁርናው እስረኛ ሆኖ የኖረውን ህዝብ ሁሉ ነጻ ስናወጣው ፤ እኛ ባስተማርነው ትምህርት እንደ ሌላው አገር ህዝብ ሁሉ ኑሮውን አሻሽሎ ፤ ‘እድሜ ለነሱ’ እያለ ፤ የደስታ ኑሮ ሲኖር ይታዩኛል ፤ ወዲያው አሁን እንዳደረግነው ሁሉ ፤ የደስታ መቀነት በሙሉ ለጦነቱ ሲሰራጭ ይሰማኛል ። ታዲያስ ? እንዲህ ባለ ስሜት ለጦርነት ተሰናድቶህ ፤ ታጥቀህ ፤ ተሰልፈህ ፤ ድል እንደምታደርግ ርግጠኛ ሆነህ ፤ ወደ ጦሩ ሜዳ ሄደህ ፤ እዚያ ስትደርስ ‘ጦርነት የለም ! ሁሉም ሰላም ነው ! ሁሉም እማን ነው’ ቢሉህ የድል አድራጊነት ክብር ሲቀርብህ አትሰቀቅም ? እንዴ የደስታም ! ዶስ ይልህል ! ” አለች ፤ እየሳቀች ።

“ ታዲያ እንዲህ ያለ ስሜት ስለ ተሰማሽ ‘ሚስዝ ፤ ወይም ሰይጣን ነሽ’ የምልበት ምክንያት ምንድነው ? ”

“እኔ የድል አድራጊነት ክብር ለማግኘት ደስ እንዲለኝ ፤ የዚያ አገር ህዝብ በችጋር ፤ በበሽታና በድንቁርና ቀንበር ታስሮ እንዲቆዩን የም ወድ በመምሰሌ ! ”

“ሰይጣን ለተቀደሰ ስሜትሽ እንዲህ ያለ ርኩስ ትርጉም የሚሰጥ ነው ! ” አለና ወደትራ ጠጋ አድርጎ ፤ ራስዋን እንደ ተንተራሰ በፊትዋ ላይ ያሉ አካላትዋ በዩበታቸው መኖራቸውን ለማረጋገጥ እንደ ፈለገ ሁሉ እየመላለሰ ሲደባብስ ፤ በሩ ተደጋግሞ በሀይል ስለ ተመታ ፤ ከሆረቱ ተነስታ ባይኖቻቸው ተጠያዩቁና ፤ እሱ እየተደጋገመ የሚመታውን በር ሊከፍት ሄደ ።

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፮

# ማሞ ወልደ ተንሳይ

ማሞ ወልደ ተንሳይ ፣ ትምህርት ሚኒስቴር በጠቅላይ ግዛቶች ትምህርት ቤቶች ጥና መምርያ ውስጥ ሰራተኛ ነው ። በያዘው ስራ ብዙ አመታት በመቆየቱ ፣ በያንዳንዱ ጠቅላይ ግዛት በሳሉት ትምህርት ቤቶችና እዚያ ስለ ተሰማሩት መምህራንም ፣ ሰራተኞችም ፣ መረጃ ሲፈለግ የሚጠየቅ እሱ ነው ። ማሞ ስለ ጠቅላይ ግዛቶች ትምህርት ቤቶችም ሆነ እዚያ በሳሉት መምህራንና ሰራተኞች ሲጠየቅ ፣ ከሱ የተሻለ አዋቂ አለመኖሩን ስለሚያውቅ ፣ የማያውቀውንም ቢሆን አላውቅም አይልም ። ከዚህ ሌላ በየጠቅላይ ግዛቱ ከሉሉት ሹማምንትና ሰራተኞች የበለጠ እየተዘዋወረ የጎበኘ በመሆኑ ፣ "የያንዳንዱን አገር ህዝብ ጠባይና ልማድ አውቃለሁ" ባይ ስለሆነ ፣ ለያገሩ ሊመደቡና ከዚያ ሊኖሩ የሚገባቸውን መምህራንም ፣ ሹማምንትም ፣ "ሊያሾምና ሊያሽር ይችላል" እየተባለ ስለሚወራ ብዙዎች ደጅ ይጠኑታል ። ብቻ የሚወራውን ያክል ባይሆንም ፣ በክፍሉ ብዙ ጊዜ የቆዩ በመሆኑ ፣ በዬጊዜው በሚለዋወጡት ሹማምንት ላይ ሀይል እንደ ነበረውና ፣ አንዳንድ ጊዜም ያለስጋት በስማቸው ይሰራ እንደ ነበረ የታወቀ ነው ።

ማሞ ቁመተ-ረዥሞች ከሚባሉት ትንሽ መለስ ብሎ ፣ በመጠኑ ወፈር ያለ ፣ በጥቁር መልክ ምንም እንኩዋ ከጥርሱ በቀር ፣ "ግሩም" የሚባል ነገር ባይኖረው ፣ ሁሉንም እንዲሁ እንዳለ ሲመለከቱት ደስ የሚል ፣ "የወንድ መልክ አለው" የሚሉት አይነት ነው ። ጥርሱ ግን እንደ ወሽት ጥርስ በመስመር ተካክሎ የተደረደረ ከመሆኑ ሌላ ፣ እህል አለነከሶት እንደማያውቅ ፣ ሁልጊዜ ንጹህ በመሆኑ ፣ ያዬው ሁሉ ያደንቅለታል ። እሱም ይህን አውቆ ፣ ጥርሱን ለማሳዬት በሚያስቅውም በማያስቅውም መሳቅ ለመደና ፣ በሁዋላ የሳቅ አመለኛ ሆኖ ፣ ለመናገር አፉን በከፈተ ቁጥር እየሳቀ ስለሚናገር ፣ ደህና አድርገው የማያውቁት ሰዎች ፣ ቁም ነገር ሲናገርም የሚያፌዝ ይመስላቸዋል ። ሰፊያና ጥላሁን አስተማሪዎች ለመሆን ማመልከቻቸውን ለትምህርት ሚኒስቴር ባቀረቡበት ጊዜ ፣ ምንም እንኩዋ እፊቱ ባይቀርቡ ፣ ማሞ ወልደ ተንሳይ

@OLDBOOKSPDF

ማን መሆኑን ደህና አድርገው አጥንተው ነበር ። ጥላሁን እንዲያውቃ እያንጋግረው እንጂ ፣ መልኩንም ደህና አድርጎ ያውቀዋል ።

ጥላሁን በሩን ሲከፍት ፣ ማሞ ወልደ ተንሳይን ሸንጥላውን ጥቅልል አድርጎ በመሸፈኛ ሸፍኖ ፣ ከዘራ አስመስሎ ይዞ ፣ የካፖርቱን እንገትጌ ወደላይ መልሶ ፣ ባርኔጣውን አድርጎ ፣ ቆሞ ስላገኘው ለጊዜው እንደ መደንገጥ ብሎ ገርገብ አለ ። ነገር ግን ወዲያው እስተጋብቶ ፣ ሁለት ርምጃዎች ወደፊት ተራመደና ፣ 'አቶ ማሞ ፣ ምን እግር ጣለህ ? ቤቴን ታውቀዋለህ?' አለ ፣ በፈገግታ ሰላምታ ለመስጠት ሁለት እጆቹን ዘርግቶ ።

"ጤና ይስጥልኝ አቶ ጥላሁን ፤ ኸ-ኸ-ኸ-ኸ-ኸ-!" አለ ማሞ ባንድ እጁ ባርኔጣውን ሲያነሳ ሌላውን ለሰላምታ ዘርግቶ ።

"እቤት አትገባም ? እባክህ ግባ ፤ ምንም እንኳ ቤቴ አለቃ የሚቀበሉባት ባትሆን . . ." ብሎ የሚጨርስበት ቃል ሲፈልግ ፣

"ኧረ ግዴለም እገባለሁ ፤ ኸ-ኸ-ኸ-ኸ!" አለና ማሞ ባርኔጣውን በሸንጥላው ሰክቶ ፣ ግርግዳውን አስጠግቶ አቁሞ ፣ ካፖርቱን እንደ ለበሰ ፣ ጥላሁንን ተከትሎ ገባ ። ጥላሁን ከሶፊያ ጋር ካስተዋወቀው በሁዋላ ፣ አጠገብዋ ተቀምጦበት የነበረውን ወንበር ትንሽ ሳብ አድርጎ አስቀምጠት ፣ እሱ አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀመጠና ፣ "ቤቴን ከዛሬ ቀደም አታውቀው ፤ ዛሬ ማን አሳዬህ ?" አለ ።

"እሰፋ በረደድ አመለከተኝ ፤ ኸ-ኸ-ኸ-!" አለ ማሞ ፣ ውብ ጥፉሉን ከዳር እስከ ዳር ገልጦ ፣ እዩልኝ እንደ ማለት አንድ ጊዜ ሶፊያን ፣ አንድ ጊዜ ጥላሁንን እያዩ ።

"አዎ ፤ እሰፋ ያውቀዋል" አለ ጥላሁን ፣ ስለ ማሞ ሁኔታ እንደ ማፈር በሳለ አንገቱን ደፍቶ ። ሶፊያም ሳቅ ስለመጣባት ፣ ከፊቱዋ እንዳይታይባት ፣ አንገትዋን ደፍታ መሬት መሬት ታይ ጀመር ።

"አቶ ማሞ ፣ እባክህ ፈቃድህ ይሁንና ቡና ፣ ወይም ሻይ እና ፍላ" አለ ጥላሁን ፣ አንገቱን ከደፋበት አቃንቶ ።

"እግዚአብሄር ይስጥልኝ ፤ አሁን ጠጥቼ ነው የመጣሁ ፤ ኸ-ኸ-ኸ-ኸ! ወዲያውም ቸኩያለሁ ፤ ኸ-ኸ-ኸ-!"

"እኔን ፈልገሽኝ እንደሆንክ ፣ ላሰፋ ብትነግረው ይጠራኝ ነበር ፤ ወይም ለሂሳብ ሹሙ ብትነግረው እዚያው ሰመጣ ይነግረኝና እንተ እዚህ ድረስ ከመድከም. . . እዚያው እመጣ ነበር ። ዛሬ እንኳ እዚ

@OLDBOOKSPDF

ያው ነበርሁ ፤ ማዘ[illegible] እንደሆን ብጠይቅ ፤ "ትጽፎ ለግ ናው ዲሬክተር ፊርማ ቀርቦዋል" ስላሉኝ ባንድ ላይ እንዲያልቅልኝ ሲሆን ያሬት ፤ ያለዚያም የሶስት ወር ደመወዜ በብድር እንዲሰጠኝ ማመልከቻ አግብቼ መጣሁ ።

"ለብድሩ ስላቀረብ'ከው ማመልከቻ የሰማሁት ነገር የለም ። ነገር ግን አሁን የመጣሁ ለሌላ ጉዳይ ነው ፤ ኸ - ኸ !" አለ ማሞ ፤ የሶፊያን ሁኔታ ሲያይ ሳቁን ባጭር ቆርጦ ።

"ሶፊና እኔ እዚያ ስንሄድ ፤ ለትምህርት ቤቱ ብቻ ሳይሆን ባካባቢው ለሚኖረው ህዝብ ጭምር ለማድረግ ያቀድነውን ብታውቅ በጣም ደስ ብሎህ እንደምትረዳን ርግጠኛ ነኝ ፤ ጊዜ አለህ እንደሆን ፍቀድልኝና ባጭሩ ልንገርህ"

"እቅዳችሁ ጥሩ እንደሚሆን አልጠራጠርም ፤ ብቻ የመጣሁበት ጉዳይ ሌላ ስለሆነና ስለምቸኩል ፤ ሌላ ጊዜ ብትነግረኝ . . . ኸ - ኸ - ኸ ኸ - ኸ !"

"አሁን ለጉዳዩ አፈጻጸምኮ . . ." ብሎ ጥላሁን ንግግሩን ሳይጨርስ ፤

"እንዴ ! እናግረው እንጂ ፤ ጥላየ ! 'ሌላ ነገር ልንግርህ ነው የመጣሁ' ይልሀልኮ !" አለች ሶፊያ ፤ ጥላሁንን አቋርጣ ።

"መስሪያ ቤት ሰው ስለ ቀጠርሁ ባልቸኩል ኖሮ ፤ እቅዳችሁን መስማት ባጣም በወደድሁ ፤ ስለ ትምህርት እንኩዋን ያቶ ጥላሁንን ፣ የማንንም አሳብ ማወቅ ለኛ ለትምህርት ሚኒስቴር ሰራተኞች ስለሚጠቅመን መስማት ይገባናል ። ብቻ አሁን ስለቸኮልሁ . . . ዋናው ዲሬክተር ልከውኝ ነውና የመጣሁ ፤ መልክቱን አድርሼ እንድሄድ ይቅርታ አድርጉልኝ ፤ ኸ - ኸ - ኸ - ኸ - !"

"ዋናው ዲሬክተር እኔ ዘንድ ላኩህ ?" አለ ጥላሁን ፤ እንደ መደንገጥ ብሎ ።

"አዎ ፤ እንግዳ ባይኖርባቸው እንዲያውም ራሳቸው ቢመጡ ይወዱ ነበር ፤ ኸ - ኸ - ኸ - ኸ - !"

"እንዴት ? ምንድነው ነገሩ ?" አለ ጥላሁን እንዲያ ያለ የማይታመን ነገር ሲሰማ ።

"በደረሰው ያልታሰበ ነገር በጣም አዝነው ፤ እሳቸው እንግዳ ስላለባቸው በሳቸው ስም ይቅርታ እንድለምንህ ነው . . . . እኔን የላኩኝ ፤ ኸ - ኸ - ኸ - ኸ - ኸ !"

@OLDBOOKSPDF

"ብድሩ የማይፈቅድ ሆኖ ? ወይስ . . . ሌላ ነገር ነው !"

"ስለ ብድር አደለም ፤ አንተ በተመደብህበት ያስተማሪነት ቦታ ቀድሞ ሌላ ሰው ተመድቦበት ኖሩዋል ። ነገር ግን መዝገብ ቤቶች ረስ ተው ፡ አንተ ማመልከቻ ስታቀርብ ፡ 'ቦታው ክፍት ነው' ብለው ላንተ እንዲሰጥ ዋናውን ዲሬክተር በስህተት አስፈረሙዋቸው ። አሁን ቀድሞ የተመደበው ሰው ሊሄድ መነጋገሩ ስለጠዬቀ ፣ ነገሩ ቢመረመር እው ነትም ቀድሞ የተመደበበት ሆኖ ተገኘ ። ስለዚህ ፣ መቸስ . . . እንደም ታውቀው አስቀድሞ የያዘውን ቦታ ያለምክንያት ለሌላ አሳልፎ መስ ጠት ያስቸግራል ፤ ለዚህ ነው ዋናው ዲሬክተር በጣም ያዘኑ ፤ ኸ - ኸ ኸ - ! "

ጥላሁንና ሶፊያ በድንጋጤ ዝም ብለው ሲተያዩ ከቆዩ በሁዋላ ጥላሁን ልቡን አረጋግቶ ፣ "ዋናው ዲሬክተር በዚህ ሊያዝኑ አያስፈል ግምኮ ፤ ሌላ ቦታ የሚገኝልኝ ከሆነ የኪ ቀረብኝ ብዬ አልቆረቆርም ።"

"ሌላ ያልተያዘ ቦታ ለጊዜው የለም እንጂ ቢኖርማ ደህና ነበር ፤ ለዚህ ነው ዋናው ዲሬክተር ያዘኑ ፤ ምናልባት ወደፊት ሊገኝ ይችል ይሆናል ፤ ነገር ግን መቸ እንደሚገኝ ርግጠኛ መሆን አይቻልም ! ኸ ኸ - ኸ "

እስከ ትናንት ፤ ኸረ እስከ ዛሬ ጥዋት ድረስ ፥ "ዳር አገር የሚሄ ድልን አጣን" እያላችሁ ትቸገሩ አልነበረም ? ወይስ የኔ ዳር አገር ለመ ሄድ መጓጓቅ ድንገት ዳሩን መሀል አድርጎ አስወደደት ይሆን ?"

"አሁን ዳር አገር ይሁን መሀል ፥ ክፍት ቦታ በጭራሽ አይገኝም! ኸ - ኸ - ኸ - ኸ - ኸ ! "

"ከመቸ ወዲህ ? በምን ምክንያት ?"

"የሰላም ጉዋዶች በብዛት የሚመጡ መሆናቸውና ፥ ከከተማ ይልቅ ወደ ዳር አገር ሄደው ለማስተማር መምረጣቸው ስለታወቀ ፥ 'ዳር አገር እንሄድም' የሚሉ ኢትዮጵያውያን ፥ ስራ የማያገኙ መሆናቸውን ተረድ ተው ፥ ሁሉም በዬተመደቡበት ለመሄድ ይቀዳደሙ ጀመር ፤ ኸ - ኸ - ኸ "

"የሰላም ጉዋዶች ዳር አገር ሄደው የፈለጉትን ተምረው ይመጡ እንደሆነ እንጂ ምን ሊያስተምሩ ?"

"አሁን ወደ ፖለቲካ ሄድህ ፤ ኸ - ኸ - ኸ - ኸ - ኸ - ኸ - ! እኛ የትምህርት ሰዎች ነን እንጂ የፖለቲካ ሰዎች አደለንምና ፥ ፖለቲካ ውን ለፖለቲካ ሰዎች ብንተውላቸው ይሻላል ፤ ኸ - ኸ - ኸ - ኸ ! "

@OLDBOOKSPDF

“እሱስ እውነትህ ነው ፤ ፖለቲካውን ለባለፖለቲካዎች እንተወው፤ ብቻ ከትምህርቱም ወገን ብንመለከተው ፣ የሰላም ጉዋዶች ኢትዮጵያው‑ ያን ባልተሰናዱበት እንኳ በኢትዮጵያውያን ፈንታ ሊተኩ ባልተገባም ፤”

“እሁንም ልክ እንደሱ ነው ፤ የሰላም ጉዋዶች ኢትዮጵያውያን ባልተሰናዱበት ፣ ቢያንስ ቢያንስ ለመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ነው የሚመጡ ፤ ኽ - ኽ - ኽ - ኽ - ኽ - ኽ - ኽ - ”

“እንዲህ ከሆነ ፤ እኔ እንኩዋ መስመሬ ሌላ ቢሆን ሶፊ አለች ፤ ባንዱ የሰላም ጉዋድ ፈንታ ቅጠርኖት ። ባገርዋ ቋዋንቋዋ ፣ ላገርዋ ልጆች ካንድ የሰላም ጉዋድ የተሻለ እንደምትጠቅም አንተም አትጠ ፈጥር ፤ ”

“አልጠረጥርም ፤ ላንተም ለስዋም ፣ ወደፊት ቦታ ይፈለግላችሁ ዋል ፤ ኽ - ኽ - ኽ - ኽ ! ”

“እቶ .... ይቅርታህን ፤ ስም መያዝ አይሆንልኝም ፤ አቶ ... ...” አለች ሶፊያ ፣ ቁጣዋን መዋጥ ብትሞክር አቅቶዋት ፣ አይኖ ችዋ ደም ለብሰው ።

“ማሞ ፤ ማሞ ወልደ ተንሳይ ” አለ ማሞ ፣ የሶፊያን ቁጣ ከፊ ቱዋ ሲያይ እንደ መሸበር ብሎ ።

“አዎ ፤ አቶ ማሞ ፤ ለመሆኑ ፣ ም... ምንድነህ ? ሰው ነህ ? ወይስ ... በሰው አምሳል የተፈጠርህ አውሬ !”

“እንዴት ? ምን ማለትሽ ነው ?”

“ከፉ አውሬ ፣ ጨካኝ አውሬ ነህ ፤ ሰውም እንደሆንህ ... የሰው ስሜት ያልተፈጠረብህ ፣ ደስታህን ከሰው ጭንቀት የምታገኝ ጭራቅ ነህ !” አለች ፣ ሰውነትዋ ሁሉ በንዴት እዬተንቀጠቀጠ ።”

“ምን አልሁ ? ምን ከፉ ተናገርሁ ? አቶ ጥላሁን ፣ ሰው የተላከውን ስለተናገረ ፣ ‘አውሬ ወይም ... ጭራቅ’ ይባላል ?” አለ ማሞ ፣ ሶፊያን ማየት ፈርቶ ፣ ወደ ጥላሁን ፊቱን መልሶ ።

“እባክሽ .. ዝም በይ ፣ ሶፊ !” አለ ጥላሁንም ቁጣዋን ስላዬ እዬ ፈራ ።

@OLDBOOKSPDF

"ዝም በል አንተ ደም.. የምትሀ.. ፊላ፤ ዝም በል!" አለች ፣ ትንሽታ መሬቱን በሀይል እየረገጠች ። "ከዚህ ወዲያ ምን ሊያደርግህ ኖሮዋል? የተመደብህበትን ስራ ፣ አንድ መኳዋንንት ርስቱን ለሚጠ ብቅለት ዘመዱ ይሁን? ምኑ ፣ እንዲሰጥለት ስለ ጠፉቀው ፣ አንተ ምንም ማድረግ እንደማትችል እውቁ አንስቶ ሳጠ! ይህ አይበቃም? ሳቁ ምን ይባላል? ሰው ከሆን ፣ ህሊና ካለው ፣ ሲሆን እንዲህ ያለ ግፍ ባልሰራ! ጥቅም አሸንፎት ቢሰራስ ፣ ደግሞ እንደገና ግፍ በሰራበት ሰው ላይ ፣ እቤቱ ድረስ መጥቶ መሳቅ የግፍ ድርብ አይደለም? ሂድ ውጣ ከዚህ!" ብላ ፣ ተቀምጣበት የነበረውን ወንበር ስትይዝ ፣ ጥላሁን እስዋን ለመ ያዝ ፣ ማሞ ለመሸሽ ፣ ሁለቱም ደንግጠው ተነሱ ። ነገር ግን ጥላሁን ደርሶ ከመያዙ ፣ ማሞ ሮጦ ከማምለጡ በፊት ፣ የወረወረችው ወንበር በትክሻው ላይ ንክትክት አለ ።

ማሞ ከቤት ሮጦ እንደ ወጣ ፣ ጃንጥላውንና ባርኔጣውን ከስቀመጠ በት ነጥቆ ፣ እየሮጠ ከመንገድ ገባ ። ቢሬሯን ግን ንዴትዋ ሲያልፍ ፣ ሲታማደው የማትችል ልቅሶ ስለ መጣባት ፣ እሊጋው ላይ በግንባርዋ ተደፍታ ፣ ምርር ብላ ማልቀስ ስትጀምር ፣ ጥላሁን ከወደቀችበት እን ስቶ ፣ በደረቱ አስደግፎ ፣ ያባብላት ጀመር ። እንዲያ በደረቱ እቅፎ ራስ ዋን ፣ ጀርዋን ፣ ማጉንበርዋን ፣ ጉንጭዋን እየሳመ ሲያባብላት ፣ ትንሽ በት ንሽ ጸጥ እያለች ፣ ሰላም እያገኘች ሄደ ፣ ሰውነትዋ በሰውነቱ ላይ ዘና ትኮሳትዋ በረድ ፣ ትንፋሽዋ ዘለግ ካለ ፣ ልቅሶዋም እንደ ንዴትዋ ማለፉን አዩና ፣ በደረቱ እንዳስተኛት እሳቡና ከሱዋ ወደ ሌላ ልክ ፣ ትንሽ ዝም ብሎ ከቆዩ በሁዋላ ፣ "ተይው ግዴለም፤ የኔ እመቤት! ርሸው!" አለ እይኑን እግሬው ላይ እንደ ሰቀለ የቅርቃ ሬግግታ ፈገግ ብሎ ።

"ሀ...! ይቅር ግዴለም፤ ድሮም እሷም እንኳ አውነት አልነበር! ላጭር ጊዜ እንደ ክርስቶስ ህዋርያት የታመሙትን ፈውሰን ፣ የተቸገሩ ትን ረድተን ፣ የማያውቁትን እያስተማርን ኑሯቸውን አሻሽለን ፣ ይህን ሁሉ እያዩን ፣ በዚህ ሁሉ ከያፉ ስንመሰገን እዩሰማን ደስ ብሎን ፣ በጥሩ እልም ውስጥ ኖርን! በወሬኛችን ባይሆን በልማችን ሰርተን ላጭር ጊዜ ደስ አለን! አዎ! መቸም ዋናው ነገር ደስ መሰኘቱ ነው! እልም ይሁን እውን ፣ ደስ ካሰኘ ሁሉም አንድ ነው! ብቻ ደስ እንዳለን ትንሽ እንድንቆይ ፣ እልማችን ባያጥር እንዴት ጥሩ ነበር!" አለና ፣ በቅቶ የያ ዛትን ሀጻን ፣ 'እሺሩሩ' እንደሚል እየ[illegible] አይኖቹን ከጣራው ላይ

@OLDBOOKSPDF

ወርድ በጥልቅ ሲያስብ ቆይቶ ፤ "አሁን መሄድ ብቻ ነው ! ሌላ ነገር የለም ! ግዴለም እንሂድ ፤ መሄድ የማያውቁትን አዲስ ነገር ያሳያል ፤ አዲስ ነገር ማየትም አዲስ አሳብ ይፈጥራል ፤ ስለዚህ እንሂድ !"

"ጥሩ ነዋ ፤ ወዴት ?" አለች ሶፍያ ፤ በትራሱ ላይ እንዳለች ቀና ብላ ፤ አይኖቹን ጠልቃ እያየች ።

"ወደ ውብቱ በዛብህ እንሂድ ፤ መሬታችን አለ እንደሆነ ፤ የግብርና ስራ እዩሰራን ፤ የምንመኘውን ያክል ባይሆን በመጠኑ ልንረዳ እንችል ይሆናል ፤ መሬቱ ባይኖርም ... አስቲ ምን ማድረግ እንደሚቻል ሂዶ ማየቱ አይከፋም !"

@OLDBOOKSPDF

## ምእራፍ ፪

# አድሩስ ጀባ !

ሶፊያና ጥላሁን ፣ ጎሬ የሚያቆያቸው ከፋ ይሁን በጎ ሳያውቁ፣ እዚያ እድላቸው የሚያኖያቸውን ለመግጠም ቆርጠው ፣ የቤት እቃቸውን ሁሉ ፣ አልጋቸውን ፣ ፍራሻቸውን ፣ ቁም ሳጥናቸውን ፣ ጠረጴዛና ወንበሮቻቸውን ፣ ሌላውንም ጥቃቅን ነገር ፣ ለቤቱ ባለቤት ሸጠው ፣ የጥቂት ቀኖች የቤት ክራይ ፣ የመብራትና የውሀ ክከፈሉ በሁዋላ ፣ በተረፋቸው ገንዘብ ፣ በጭነት ካሚዮን ተሳፍረው ለመጉዋዝ ተነሱ ።

"ጎሬ ድረስ ስንት ያስከፍሉናል ጋሽ ?" አለ ጥላሁን ፣ አዲስ ከተማ ሄዶ ፣ ለትምህርት ቤት ማደሻ የሚሆን ስሚንቶ ጭኖ ወደ ጎሬ ለመሄድ የሚሰናዳውን ፣ አቶ ዮሴፍ ብርሃኔ የሚባለውን ባለካሚዮን ።

" ስንት ናችሁ ?" አለ ባለካሚዮኑ ።

" ሁለት ። እኔና ባለቤቴ ብቻ ነን ።"

" ለሁለታችሁ አርባ ብር ትከፍላላችሁ ።"

" ምነው ጋሽ ፤ በጭነት መኪና መሄድ መጀመሪያየ አይደለምኮ ! ዋጋውን አውቀዋለሁ ።"

" በትናንት ዋጋ ዛሬ የሚገኝ ነገር የለም ፤ ወንድሜ ፣ የማናቸውም ነገር ዋጋ ሲያድግ ነው የሚያድር ። የመጨረሻ ዋጋ ሰላሳ ብር ነው፡ ክዚህ ያነሰ ካገኛችሁ አሌላጋ ፈልጉ ።"

" ከነጇ ጋር ለሁለታችን ቦታ ይገኛል ?"

"ላንዳችሁ ብቻ ይገኛል ።"

"ምን ከነጇ ሌላ ሁለት ሰዎች የሚያስቀምጥ ቦታ እፊት የለም ማለት ነው ?"

"እጋቢናው ውስጥ ካዩታንቲው ሌላ አንድ ሰው ብቻ ማስቀመጥ ነው የሚፈቀድ ።"

" ጋቢናውና አዩታንቲው . . ምንድን ናቸው ?"

"በጭነት መኪና ብዙ ጊዜ ክሂድህ እንዴት ጋቢናና አዩታንቲ ሳታውቅ ቀረህ ?" አለ አቶ ዮሴፍ ፣ እንደ መሳቅ ብሎ ።

@OLDBOOKSPDF

"ልብ ባልላቸው ይሆናል እንጂ . . ባልለማቸው የቀረሁ እንኳ አይመስለኝም ።"

"ጋቢና የፊት መቀመጫ ፤ አዩታንቲ የነጁ ረዳት ናቸው" አለ አቶ የቤፍ ፤ አሁንም እንደ መሳቅ ብሎ ።

"በዋጋ እንኳ ጎድተውናል ፤ ነገር ግን መቸስ ምን ይደረግ ! ምን ጊዜ ትነሳላችሁ ?"

"ሌሊት በዘጠኝ ሰአት ። እዚህ ካላደራችሁ አትደርሱብንም ።"

"የት እናድራለን ?"

"እዚህ ኢትዮጵያ ቡና ቤት ። እኛም ጭነታችንን ዘበኛ እንዲጠብቅልን እዚህ ነው የምናድር ።"

"እሺ መጥተን እናድራለን ።"

"እንግዲህ በቁርጥ መንገደኞች ከሆናችሁ ፤ ለከፍላችሁ አሁን ገንዘብ ከፍለህ ቈልፍህን ብትረከብ ይሻላል ፤ ወደ ማታ ከፍል ፈላጊው ብዙ ስለሆነ ይያዝብሀል ። ወዲያውም . . ከመኪናው ከራይ ቢያንስ . . ግማሹን ማስያዝ ደንብ መሆኑን ታውቃለህ ?"

"እሺ ግዴለም እከፍላለሁ" አለና ጥላሁን ለመኪናው አስራ ምስት ብር ፤ ለሆቴሉ ስድስት ብር ከፍሎ ፤ ቊልፉንና የደረሰኙን ተቀብሎ ፤ ወደ ቤቱ ተመለሰ ።

"እይውልሽ ዛሬ ሌሊት ፤ በዘጠኝ ሰአት ልንነሳ ለካሚዮን ከራይ ግማሽ ዋጋ ፤ አስራምስት ብር ፤ ለሆቴል ፤ ባልጋ ብቻ ፤ ስድስት ብር ከፍዬ ይህን የደረሰኝና ቊልፍ ተቀብዬ መጣሁ" አለ ጥላሁን ፤ እቤቱ እንደ ደረሰ ቊልፉንና የደረሰኙን ለሶፊያ እያሳዬ ።

"ውይ ጥላዬ ! የሌሎችን የደረሰኝኮ ነው ያመጣህ !" አለች ሶፊያ ፤ ደረሰኙን ስታይ እየሳቀች ።

"እንዴት ?" አለ ጥላሁንም ፤ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ ።

"እየውልህ ፤ ስዩም ገብረጻድቅና ጽዮን ሞገሴ የሚል የደረሰኝ ነው ።"

"ጽዮን ሞገስና ፤ ስዩም ገብረ ጻድቅ አንቺና እኔ ነንኮ !"

"እንዲህ ተባልን ? ለምን ስማችንን ለወጥኸው ?"

"ምናልባት . . ተከታታይ ቢኖርብን ፤ ወደ ኢሉባቦር መሄዳችን እንዳይታወቅብን ።"

"ጥንቃቄው አይከፋም ፤ ነፍስ እያወቅህ መሄድህን የሚያሳይ ነው ። ብቻ ማን ይከታተለን ብለህ ሰጋህ ?"

@OLDBOOKSPDF

"ምናልባት ያንቺ ዘመዶች የተከታተሉን እንደሆነ ብዬ ነዋ ! የኔማ በእግዚአብሔር ቸርነት . . ቀድመውኝ በሰሄዱ ፣ አከተላቸው እን ደሆን እንጂ ፣ 'ይከተሉኛል' ብዬ አልሰጋም !" አለ ፈገግ ብሎ ።

"ይድ ! ዝምበል !" አለች ሰናይ ፣ የሞቱ ዘመዶቹን ፣ 'አከተል እን ደሆነ' ከሳለ በጥፊ ለኮፍ አድርጋው ።

"ለመሆኑ ነገ ጥዋት የምንሄድ ከሆነ ፣ ሆቴል ማደር ለምን አስፈ ለገና ከራይ ከፈልህ ?" አለች ፣ ወዲያው ቀጥላ ።

"ባለሆሚዮን 'እዚህ አድራችሁ ካልቀሰቀስናችሁ አትደርሱብ ንም' አሉኝ ።"

"እውነት ነው ! ጊዜው ሲደርስ እነሱ ቢቀሰቅሱን ይሻላል ። እዚህ ሰጋቱም አያስተኛን ።"

"ብቻ . . ደስ ያሳለኝ ነገር ፣ አራት ከነጁና ከረዳቱ ሌላ ካንድ ሰው በቀር ማስቀመጥ አይፈቅድም ስላሉኝ ፣ አንቺ እውስጥ ከነሱ ጋር ፣ እኔ በብርድ ልብሴ ተጠቅልዬ አሳይ ከጭነቱ ጋር ተቀምጠን መጉዋ ዛችን ነው ።"

"እኔስ እንዳንተ በብርድ ልብሴ ተሸፋፍኜ ንጹህ አዬር እንደ ልቢ እያገኘሁ ፣ የፍጥረትን ውበት እያደነቅሁ ፣ እንዳልጉዋዝ እዚያ ውስጥ ፣ ከማላውቃቸው ሰዎች ጋር ተጨናንቄ የምሄድበት ምክናያት ከቶ ምን ይሆን ?"

"ቀን ነፋሱ ፣ ጥዋትና ማታ ውርጩ ፣ ላልለመደው ሰው አደገኛ ሊሆን ይችላል" ቢሳሉኝ ፣ እንዲህ ያለውን ነገር ሁሉ እስክትለምጅው . . ባንድ ጊዜ ከመጋፈጡ መጠንቀቅ ይሻላል በማለት ብቻ ነው ።"

"ይህን ነገር ደግመህ ታነሳና በማያውቁን ሰዎች ፊት ለንጨቃ ጨቅ አመላችንን እንዳናስቆጥር አጥህን ዝጋ ። የኔ ቦታ ካንተ ጋር እጭ ነቱ ላይ ነው ።"

"እሩቴ እልክሽን ወደጎን አቅይና ፣ የምነግርሽን በጥሞና ስሚ ። ጭነቱ ስሚንቶ መሆኑን ነግሬሻለሁ ። እንግዲህ ፣ 'ከታች ስሚንቶ እን ጥፌ ፣ ከላይ የጥቅምት ሌሊት ውርጭ እዬወረደብኝ ልጉዋዝ' ነውኮ የምትይው ! ታዲያ ይህ . . . በሽታን በቀጥታ መጋበዝ አይባልም ?"

"ለመሆኑ አንተ ከስሚንቶ ቅዝቃዜና ከጥቅምት ሌሊት ውርጭ ጋር የሰላም ውል ፈርመሀል ? ወይስ የምትከላከልበት መድሀኒት አለህ ወይስ የስሚንቶ ቅዝቃዜና ውርጭ እኔን በተለይ የሚፈልጉኝ ያባቻ ቸው ገዳይ ነኝ ? ጥላየ ፣ ካሁን ጀምረህ አንድ ነገር እንድታውቅልኝ

@OLDBOOKSPDF

እፈልጋለሁ ፤ ልብ አ[illegible] እንዲህ አንዳንድ የሚያስጋ ነገር በደረሰ ቁጥር እኔን ወደ ሁዋላ እየሸሸግህ ፣ እኔን እየተውህ ፣ አንተ ብቻ ሀን እየቀደምህ ስመጣም ታስብ እንደሆነ ፣ ይህ በጭራሽ የማልቀበለው ነው !” አለች ተቆጥታ ።

“እንዲህ ያለ ጥፋት ደግሜ ሳላጠፋ እምላለሁ ፤ ብቻ ያሁኑን ይቅር በይኝ ፤ የኔ እልከኛ !” አለ ጥላሁን ፣ ተቆጥታ እንደ ቆመች እቅፍ አድርጎ ይዞ እየሳቀ ። እሰዋም ቁጣዋን ትታ ትስቅ ጀመር ።

ባልና ሚስቱ ተያይዘው ባንድ ላይ ሲሉ ፣ በር ተደጋግሞ መመታቱን አልሰሙም ነበር ። ሳቁ ትንሽ ቀንስ ሲል ፣ በር መመታቱን ጥላሁን ቀድሞ ስለሰማ ፣ ጣቱን በከንፈሮቹ ላይ አድርጎ “እስ .. !” እለና ሂዶ ቢከፍት የቤቱን ጌታ ፣ አቶ በትሩ ዳመናን ከባለቤታቸው ጋር ፊት ለፊት ቆመው አገኛቸው ። ያቶ በትሩ ባለቤት ፣ ወይዘሮ ሸፍኔ በቀኝ እጃቸው አንድ ጀበና የፈላ ቡና ፣ በግራ እጃቸው ብዙ ፍንጃሎች ባንድ ላይ ሰክተው ይዘዋል ። አንድ ልጅ ድፎ ዳቦ ፣ ቀጫጭ በለበሰ ሞሰብ በራሱ ተሸክሞ ፣ ጠጅ የሞላ ማንቆርቆርያ በጁ አንጠልጥሎ ፣ ተከትሎ ዋቸዋል ።

“እንዴት ዋሉ አባባ ፤ እንዴት ዋሉ እማማ ” አለ ጥላሁን ፣ ወይዘሮ ሸፍኔና የተከተላቸው ልጅ የተሸከሙት ያልተለመደ ፣ እንግዳ ነገር በመሆኑ ግር ያለው መሆኑ ከፊቱ እየታየ ።

“እንዴት ዋልህ !” አሉ አቶ በትሩ ፣ ድንገተኛ የቁጣ ስሜት ሲሰማቸው ፊታቸው ትንሽ ጨምደድ ብሎ ። ነገር ግን ቁጣቸውን ጥላሁን ልብ አድርጎ ከመመልከቱ በፊት ፣ ስሜታቸው ተለወጠና ወዲያው የተጨመደደ ፊታቸው ፈገግ አለ ።

አቶ በትሩ በድሜም ይሁን በማእረግና በሀብት ከሳቸው ያንሳሉ የሚሉዋቸው ሁሉ ፣ ሲሆን እጅ ነስተው ፣ እጅ መንሳት ቢቀር ባፋቸው ብቻ እንኩዋ ፤ “ጤና ይስጥልኝ” በማለት ፈንታ ፣ “እንዴት ዋሉ፣ እንዴት አደሩ !” ሲሉዋቸው ፣ ልክ እንደ ሰደቡዋቸው ቆጥረውት ፣ ለጊዜው ግልፍ ይላቸውና የቁጣ መልክ ይታይባቸዋል ። ነገር ግን እንዲያ ያለውን እድሜ የማይከበርበት ጊዜ ፣ እንዲያ ያለውን የብልግና ወረርሽኝ ያ የፈረንጅ ትምህርት የሚሉት ነገር ባገሩ ሁሉ ላይ ያመጣው እንጂ ፣ በተለይ በሳቸው ብቻ የደረሰ አለመሆኑ ትዝ ሲላቸው ፣ ወዲያው በቁጣ የተከማተረ ልባቸው ለዘብ ብሎ ግልፍታቸው ያልፋል ። መጀመርያ ራሳቸው ያደጉበትን የጭዋ ልጅ አስተዳደግና ትህትና ለልጆቻ

ቸው ለማስተማር አጥብቀው ጥረው ነበር ። ከልጆቻቸው አንዱ መጥቶ፥ “ እንዴት አደሩ ! ” ሲላቸው ፥ ወይም አንዱዋ መጥታ ፥ “ለጠጉር ማስሪያ ፥ ወይም ለስኒማ መሄጃ ፍራንክ ያስፈልገኛል !” ስትላቸው ፥ “ወዩው ጉድ ! እባካችሁ ስለ እግዚአብሄር እናንተ ልጆች ፥ ሽማግሌ ሰው ፥ ‘ጤና ይስጥልኝ’ ይባላል እንጂ እንደ ጉዋደኛ ፥ ‘እንደምን አደርህ’ አይባልም ፤ ልጆች ካባታቸው ገንዘብ ሲፈልጉም ፥ ‘እባክዎ’ ማለት ነው እንጂ እንደ ገንዘብ አስቀማጭ ሰው ፥ ‘ገንዘብ ያስፈልገኛል ፤ አምጣ’ ማለት አይገባም ፤ ብልግና ነው ። እናንተ ብቻ ሳይሆን አሳዳጊያችሁን ጭምር የሚያሰድብ ነው ” ያሉዋቸው እንደሆነ ፥ ልጆች በበኩላቸው ባባታቸው አርጌ አስተሳሰብ ተቆጥተው ፥ ‘ባይፈልጉ ይተውት ፤ ብቻ አይጨቅጭቁን !’ ብለዋቸው ሲሄዱ ፥ ገርሞዋቸው ፥ ግራ ገብቶዋቸው ይቀራሉ ።

“ እንዲያው ለመሆኑ ” ይላሉ አቶ በትሩ ፥ አንዳንድ ጊዜ እሳቸው የፈረንጁ ትምህርት ያመጣውን የብልግናና የጌጥ ወረርሽኝ እዩነቀፉ፥ ልጆቻቸው ያባታቸውን እንደ ጣኦት ፥ ‘ስንዱልኝና ስምኑኝ’ ማለት እዩነቀፉ ሲጨቃጨቁ ፥ “ እንዲያው ለመሆኑ ፥ እኒያ ፈረንጆች ሽማግሌ ማዋረድን ፥ ስምና ማጌጥንና . . . ሌላ ሌላውን ብልግና ሁሉ ከሚያስተምሩዋችሁ ይልቅ ፥ ትንሽ ከብልሀታቸው ቀንሰው ቢያስተምሩዋችሁ አይሻልም ኖሮዋል ? እነሱ ጠበንጃውን ፥ መድፉን ፥ መኪናውን ፥ አሮብላውን ፥ ሽረ ስንቱን ! ሲሰሩ ፥ ለናንተ የሚያስተምሩዋችሁ ብልግናና ጌጥ ብቻ ! እስቲ . . . ከመርፌና ከዝራር ቁልፍ ያነሰ አለ ? ታዲያስ ! ‘ትምህርታቸውን ጨርሰው ተመረቁ’ ከምትሉዋቸው ያበሻ ልጆች መርፌ ፥ ወይም አዝራር ቁልፍ ሰርቶ ያሳዬ አንድ እንኩዋ አለ ? የለም ! እንደኔ እንደ ምኑ ከሆነ ፥ ‘ፈረንጆች ተንኮለኞች ናቸው’ ሲሉ ሰምቻለሁና ፥ ‘እኛን የጠቀሙ መስለው ፥ ብልሀት ብልሀቱን እዩሸሸጉ እንዲህ ያለውን . . . የብልግናና የጌጥ በሽታ ብቻ አምቀተው ባገራችን የሚያስተምሩ ፥ ያበሻን ሰው አስንፈውና አድክመው ፥ አበላሽተው፥ ሲገዙት ለመኖር እንዲመቻቸው ነው ፤ ይህን አትጠርጥሩ !”

እንዲህ ያለው ምክር ፥ እንዲህ ያለው ትምህርት ፥ ላቶ በትሩ ልጆች ያባታቸውን አላዋቂነት ከማረጋገጡና እንዲህ ካሉት አላዋቂ ሰው በመወለዳቸው የማያሳፍራቸው ከመሆኑ አልፎ ፥ ሌላ ምንም ዋጋ የሌለው በመሆኑ ፥ እስበሳቸው ተጠቃቅሰው ራሳቸውን እዩወዘወዙ ትተዋቸው ሲሄዱ ፥ እሳቸውም የልጆቻቸውን ሁኔታ አይተው ራሳቸውን እዩወዘወዙ ይቀራሉ ። በመጨረሻ እግቢ ፥ ወይም ባንዳንድ ድግስ ቦታ ከጉዋ

@OLDBOOKSPDF

ደቆቻቸው ሲገናኙ [illegible] ልጆቻቸው የሚያወሩት እሳቸው በል ጅቻቸው ላይ ከሚያዩት ጋር አንድ ሆኖ ስላገኙትና ፣ በሽታው ባገር ሁሉ የወረደ ወረርሽኝ መሆኑን ስለ ተረዱ ፣ እንዲህ ከሆነ የሳቸው ልጆች ብቻ ከመንጋው ልዩ ሲሆኑ እንደማይችሉ ተገንዝበው ፣ ድል ሆነው ! የልጆቻቸው ቃላት ፣ የልጆቻቸው ፈቃድ ፈጻሚ ሆኑ ። ይሁን እንጂ እንደ ፣ "እንዴት አደሩ ! ያስፈልገኛል !" ያሉትን ትህትና የጎደ ላቸው ቃሎች ከበታቾቻቸው በሰሙ ቁጥር ፣ ጆሮዎቻቸው መልመድ አቅቶዋቸው ፣ ሁልጊዜ ጊዜያዊ የግልፍታ ምልክት በፊታቸው መታ የቱ አልተዋቸውም ። ያኑስ ጥላሁን ፣ "እንዴት ዋሉ ?" ሲላቸው ድን ገት በፊታቸው ታይቶ ወዲያው የጠፋው የግልፍታ ምልክትም ፣ ለጆ ሮዎቻቸው ሁልጊዜ እንግዳ የሆነ ፣ ትህትና የጎደለው ቃል ድንገት የቀ ሰቀሰው ነበር ።

ጥላሁን ወይዘሮ ሽፍኔ የያዙትን ጀበናና የፍንጃል ስኒ ቶሎ ተቀ ብሎ ፣ ባልና ሚስቱን ደህ ነባና ፣ ከሶፊያ ጋር ሲያስተዋውቃቸው ፣ "ሶፊያ ሙሉቀ አቴ ናት ! አወቁልኝ አባባ ! በዚህ አገር ያላችሁኝ አይነተኞች ዘመዶቼ እናንተ መሆናችሁን ሁልጊዜ ስለምነግራት ፣ እሱዋ ሁለታችሁንም ደህና አድርጋ ታውቃችሁዋለች" አለ ።

"ኢትዮ ፣ የናት ያባትህ ልጅ ? አሉ አቶ በትሩ ፣ እንደ መገረም ብለው ።

"ያንቴ ልጅ ።"

"ኢ . . . ! ያው ነው ፤ ያንቴ ልጅ አት ናት ። እንዲህ እንደ ዛሬው እንተዋወቅ እንጂ ፣ ወዲህ ስትመጣ ብዙ ጊዜ አይቻታለሁኮ !" አሉ አቶ በትሩ ፣ እንዱን ወንበር ጎተት አድርገው ሲቀመጡ ። ባለቤታቸ ውም በሁለተኛው ወንበር ላይ ተቀመጡ ። ሶፊያና ጥላሁን ሌላ ወን በር በቤቱ ስላልነበረ ፣ ባልጋቸው ጠርዝ ላይ ጎን ለጎን ተቀመጡ ።

"ከዚህ መሄድህን እንጂ ወዴት እንደምትሄድኮ አልነገርከንም" አሉ አቶ በትሩ ፣ ሁሉም በየቦታቸው እንደ ተቀመጡ ።

"ጅማ . . ነው" አለ ጥላሁን ፣ ውሸት መናገር አስፈላጊ ስለመ ሆን አለመሆኑ ከህሊናው ጋር እየተከራከረ ።

"በስራ ነው ?"

"አዎ !" አለ ጥላሁን ፣ ቀና ብሎ ማየት በላፈረ አንገቱን ደፍቶ

ከዚያ አቶ በትሩንና ወይዘሮ ሽፍኔን ተከትሎ የመጣው ልጅ ፣ የመ ቤቱን ያደን ጥቅሻ ተመልክቶ የምሰቡን እሪያ ከነ ቀሚሱ ከላይ አነ ሳና ፣ ምሰቡን አቶ በትሩ ፊት ፣ ጀበናውንና ፍንጃሎችን ለወይዘሮ ሽፍኔ

@OLDBOOKSPDF

ፊት አስቀምጠ ወደ ግድግዳው ሂዶ ሲቆም ፣ አቶ በትሩ ፣ "በስመ አብ" ብለው ዳቦውን መቁረስ ፣ ወይዘሮ ሽፍኔ ቡናውን መቅዳት ጀመሩ ።

"አድሩስስ ?" አሉ አቶ በትሩ ፣ ዳቦውን በሰዎች ቁጥር ቆርሰው ሲጨርሱ ።

"እሳት እለ ?" አሉ ወይዘሮ ሽፍኔ ፣ ወደ ጥላሁን ቀና ብለው ።

"እሳት እወንድ ቤት ምን ሲያደርግ ይገባል እማማ ? ወዲያውስ . . ዳቦው በስሎ ፣ ቡናው ፈልቶ ከቀረበ በሁዋላ እሳቱ ምን ያደርጋል ?"

"ሳድሩሱ ነው ፤ ሂድ ከጎረቤት ፋጥና እሳት አምጣ" አሉ አቶ በትሩ ፣ ግድግዳ ተጠግቶ የቆመውን ልጅ ። ልጁ እዩሮጠ ሄዶ ከጎረቤት ፍም እሳት በገል እስኪያመጣ ድረስ የተቆረሰው ዳቦም ፣ የተቀዳው ቡናም ሳይታደሉ ቆዩ ። ከዚያ ወይዘሮ ሽፍኔ በትንሽ የጨርቅ እራፊ ቋጥረው የያዙትን እጣን ፈተው ፣ በግራ መሀል እጃቸው ላይ ካራገፉት በሁዋላ ፣ በቀኝ ጠቋሚ ጣታቸው ተጠንቅቀው ፣ ለውርወራ እንዲመች ሰብሰብ ፣ ክብብ አድርገው ፣ አመዱን ከፍሙም ፣ ከገሉም ላይ፣ "እፍ ! እፍ" ብለው አስወግደው ፣ ገልጠጥ ባለው ፍም ላይ አነጣረጥው ፣ እጣኑን ሲጥሉት ፣ ጥጥ የመሰለ ነጭ ጢስ እንደ አመልማሎ ሽብልል ብሎ ፣ እዩተጎተተ ወጥቶ ፣ ጣራውን እንደነካ ፣ ወዲያው የጣራውን ቅጥ ይዞ በሰፊው ተዘረጋ ።

አቶ በትሩ ከገሉ ተንጥቆ ፣ እንደ ተወረወረ ቀስት ቀጥታ መስመሩን ተከትሎ ፣ ሽቅብ ያረገው ነጭ ጢስ ጣራውን እስኪመታ አፋቸውንም ፣ አይናቻቸውንም ፣ በሰፊው ከፍተው ገም ብለው ሲመለከቱ ቆይተው፣ "እከ - ከ - ከ - ከ - ከ - አድሩስ ጀባ !" ሲሉ ሁሉም ባንድ ላይ ሳቁ ።

"ያመና ይሙት ፣ ግሩም የሆነ እድል አለህ ! እንዲህ ያልተበታተነ ፣ ያልባከኑ ፣ ከተነሳበት ቀጥ ብሎ ሂዶ በደረሰበት ቦታ ሲያርፍ በጸጥታ፣ በሰላም ፣ የሚስፋፋ አድሩስ ሳይበተንና ሳይባክን ቀጥ ብሎ ወደ ላይ ወጥቶ ፣ በሰላም የሚስፋፋ እድል ያለህ መሆንህን የሚያሳይ ነው ! እንዲህ ያለ ግሩም እድል ያላቸው ፣ እግዜር የመረጣቸው ጥቂት ናቸው! አድሩስ ጀባ!" አሉ አቶ በትሩ ፣ ያን "ግሩም እድል" እሳቸው ፈጥረው ለጥላሁን የሰጡት ይመስል ፣ ፊታቸው ኩራት በተቀላቀለበት ደስታ እዩበራ እጁን በሁለት እጆቻቸው ጥብቅ አድርገው ይዘው ።

"ለመሆኑ. . ." አድሩስ ጀባ፣ "ምን ማለት ነው ?" አለ ጥላሁን፣ ሳቁ እያቋረጠው ።

"አድሩስ እጣን ነው ። 'አድሩስ ጀባ' የጨሰውን እጣን ይበጅ ያርገው ! ያሳምረው ! ማለት ነው ።"

@OLDBOOKSPDF

"አሁን እንግዲህ . . . የጤሰው እጣን በጀ ማለት ነው ?"

"እንደ ቀስት ቀጥ ብሎ ቦዶ ጣራ ሲወጋ አላዩኸውም ? እንዲህ ያለም የለ !"

"እሺ ! የጣኑ ጤስ ግሩም እድል ፤ የቀና እድል አመለከተስ እን በል ! ታዲያ ያ ጢሱ አመለከተው ያሉት ግሩም እድል እዚህ ካለነው ፤ ካምስታችን መሀከል ለኔ የሚሆንበት ምክናያት ምንድነው ?"

"እድሩሱን ያጨስነው ላንተ ነዋ! በምትሄድበት መልካም እድል ይገጥምህ እንደሆን ለማወቅኮ ነው እድሩስን ያጨስነው ! አልገባህም?" ሲሉ አቶ በትሩ ፣ ሶፊያና ጥላሁን እንደገና ይስቁ ጀመር ።

"እስከ ዛሬ እንዲህ ያለ ጨዋታ ሲጫወቱ አይቸዎ አላውቅምኮ አባባ!" አለ ጥላሁን ፣ ዳቦውንም ፣ ቡናውንም ታድለው ሲበሉና ሲጠጡ።

"እስከ ዛሬማ . . . የምትኖርበትን ሁኔታ አብረን እዩናርን ስለም ናውቀው እድል መጠዬቅ አያስፈልግም ነበር ። አሁን በምትሄድበትኮ አገር ምን አይነት እድል እንደሚገጥምህ መጠዬቅ አስፈላጊ የሆነኮ አገር ስለምትለውጥ ነው ! " አሉ አቶ በትሩ ፣ በቁም ነገር ።

"እኔኮ የተደረገውም ፣ እርስዎ ያሉትም ሁሉ ለጭዋታ መስሎኝ ነው ! እውነትዎ ነው ?"

"እድሩስ እጭሰን እድልህን ለመጠዬቅና በቡና ለመሰነባበት ነው የነበረኝን ብርቱ ቀጠሮ አስተላልፌ የመጣሁ ፤ ለጨዋታ አደለም !"

"እና . . . በዚህ ሁሉ ያምናሉ ማለት ነው?" አለ ጥላሁን ፣ ሳይ ታወቀው አቶ በትሩን የተጸዬፋቸው መሆኑ ከፊቱ መኮስተርና ከከን ፈሮቹ መሸራመም እየታዬ ።

"የጭሱን አካሄድ ተጠንቅቀው ከጠበቁትና ደህና ትርጉም አዋቂ ከተገኝ የጣን ጭስ ምንም ቢሆን አያብልም ፤ ዛሬ ያዬኸውንና እኔ ያል ሁህን ሳትረሳ በልብህ ጽፈህ ያዝና ፡ እውነት ባይሆን ሁዋላ ታያለህ!"

ቡናው ከተጠጣ በሁዋላ ጠጅ ሳራቱም ተቀድቶ ጨዋታው ቀጠለ። ሶፊያና ጥላሁን ጠጅ መጠጣት ባይለምዱም አቶ በትሩንና ባለቤታቸ ውን ለመምሰል ፤ አስቀድተው የማዳቸውን እዬቀመሱ በፊታቸው ቢያ ስቀምጡትም እስከ መጨረሻው ደግሞ ወደፋቸው አልወሰዱትም ።

"መቸም . . . ደህና ተርጉዋሚ ከተገኘ የጣን ጭስም ፣ የቡና አሻ ራም ፣ 'ያብላሉ' አይባሉም ። ነገር ግን የዛሬ ልጆች አታምኑም እንጂ ከሁሉ፡ ደግሞ የሰውን እድል አስቀድሞ ለማወቅ የማያወላውል እሱም ነው።" አሉ አቶ በትሩ ፣ እንደ፡ን ብርጭቆ ጠጅ ጨርሰው ሁለተኛውን እንደ ያዙ ።

@OLDBOOKSPDF

“ሕልም ብዙ ሰዎች፣ ፈረንጆች ጭምር ያምናሉ ፤ ብቻ እኔ እልም ባይም . . . ተከታትየው አላውቅም ። ሕልም ለማመንም ሆነ ላለማመን ትርጉሙን ማወቅና መከታተል የሚያስፈልግ ይመስለኛል ” አለ ጥላሁን ።

“እውነትህ ነው ፤ እልም እንደ ተርጉዋሚው ነው ! ማለት ደህና ተርጉዋሚ ያስፈልገዋል ማለት ነው ። ደህና ተርጉዋሚ ካገኘህ ይልቁንም እንጋት ላይ የሚታይ ሕልም፣ ሕመሬት ጠብ አይልም ! አሁን . . ” አሉ አቶ በትሩ ፣ ከባለቤታቸው ባይን ጥቅሻ ፈቃድ እንደሚጠይቁ ሁሉ ፣ ሲናገሩ የነበረውን ያዝ አድርገው ፣ ወይዘሮ ሽፍኔን የጎድን እያዩ ። “አሁን . . . . ይቺ ስላንተ ፣ ባለፈው እሁድ ለሰኞ አጥቢያ ያለመችው ራእይ ነው እንጂ እልም አይባልም ፤ ግሩም ነው! እንጋት ላይ ከተኛ ሁበት ቀስቅሳ ስትነግረኝ ወዲያው ትርጉሙን ነገርሁዋት ፤ እስቲ ውሼቴ እንደሆነ ይኸው ትታዘበኝ ! እሰዋ እልም በግለም ባህታይ እንኩዋ አይተካከላትም ፤ መተርጎም ግን ምንም አታውቅ!” ሲሉ አቶ በትሩ ባለቤታቸውን እያዩ ፣ “እየጉድ አያ! ” አሉና ወይዘሮ ሽፍኔ ጠጃቸውን እንስተው “ሩቅ” አሉ ፣ የባላቸውን ሩክራ ያልተቀበሉ መሆናቸውን በሚያሳይ ፊት ።

“ይቺ ያለመችውን እንዴት እንደ ተረጎምሁት ልንገርህና ፣ እውነት ሆኖ ያላገኘኸው እንደሆነ ሁዋላ አባይ ትለኛለህ ! እልሙ እንዲህ ነው ። በግራ ጎንህ እንደ ደረሰች ልጃገረድ ያገነደረ ጡት አውጥተህ ፣ ሰው እንዳያውቅብህ እያፈርህ ፣ የምትሸሸግበት ልብስ እልበቃህ ብሎ፣ ትቸገር ነበር ። በምስጢር ያበቀልኸው ጡት ፣ ቢያሳፍርህም ከመጠን ያለፈ ስለምትወደው ፣ ወደ ላይ እዩጎተትህ ትጠባዋለህ ፤ ትስመዋለህ ፤ ያለዚያም እጅህን ከሱ አትለይም ። ይህን ምስጢር ያወቀ ምቀኛ ፣ ቀንቶ ጡትህን ሊቆርጥብህ ስለት ጩቤውን በልብሱ ውስጥ ሸሽጎ ሲመጣብህ ታይና ፣ መከላከያ ባጠገብህ ስታጣ ትሸሻለህ ፤ ቢሮጥም አይደርስብህም ። ከዚያ እንደ ሮጥህ አንድ ረዥም ተራራ ላይ ወጥተህ ቆመህ፣ እጅህ እንደ ልማዱ ጡትህን ሊዳብስ ቢሄድ ጡትህ በቦታው የለም!” ሲሉ አቶ በትሩ ፣ ጥላሁን እንደ ሙደንገጥ ብሎ አይኖቹን በሰፊው ከፍቶ ያያቸው ጀመር ። “ አይዞህ አትፍራ ፤ እልሙ ገና አላለቀም !” አሉና አቶ በትሩ የልሙን ታሪክ ቀጠሉ ። “ጡቱ ወደምታምር ወይዘሮ ተለውጦ ፣ ያች ወይዘሮ ባጠገብህ ቆማ ታያለህ ። ያንጊዜ እተራራው ላይም ከተራራው በታች ዙርያገባውም አይን ቢወጉ የማያሳይ ጨለማ ነበር። እዚያ ቆማችሁ ትንሽ ከቆያችሁ በሁዋላ ፣ ሁለታችሁም ባንድ ላይ

@OLDBOOKSPDF

አፋችሁን ስትከፍቱ የሚገኘው ውብት ሕልይ ይወጣና ያ አገርና አካባቢው በሙሉ ብርሃን ይሆናል ፤ ፍጹም ቀን ይሆናል ! ሕልሙ ይህ ነው ። አሁን ይህን ሕልም እኔ እንዴት እንደ ተረጎምሁት ልንገርህ ” አሉ አቶ በትሩ ፤ ጥባሁንና ሶፊያ ወንድምና እኅት መሆናቸውን እንደ ጠረጠሩ ሁሉ መጀመርያ ጥባሁንን ፤ ከዚያ ሶፊያን ፤ ከዚያ እንደገና ጥባሁንን እያለዋወጡ ትኩር አድርገው አዩተው ።

«በግራ ጎን የ ሚወጣና የሚጠበት ፤ የሚሰሙት ፤ ሁልጊዜ የሚዳብሱት ጡት ማለት ናት ። ሄዋን ከዳም ጎን የወጣች ስለሆነች ፤ በሱ ላይ የተመሰረተ ትርጉም ነው። ጡት ማውጣትህ ነወር ሆኖ ተበም ተህ እያፈርህ ለመሸሸግ መጣጣርህም የምታገባትን ሴት በምስጢር የምታገባ መሆንህን የ ሚያመለክት ነው ። ለሴት ሔዘቢ በልብሱ ውስጥ ሸሽጎ ጡተህን ሲቀርቡ የመጣብህ ሰው ምናልባት . . ለማግባት ያሰብሃትን ልጅ የሚወነ ፤ የፍቅር ተወዳዳሪህ ፤ በምስጢር ለማግባት መፈለግህን አውቆ ሲቀድምህ ፤ ወይም አሳብህ ፍጹሚ እንዳያገኝ ሲያበና ከል ፈልጎ ይሆናል ። ይህ ተወዳዳሪህ ፤ ይህ ምቀኛህ ፤ ብርቱ ሳይሆን አይቀርም ። ብርቱ መሆኑን የሚያመለክት የምትቃወምበት መሳሪያ ፈልገህ ስታጣ መሸሽህ ነው ፤ ሸሽተህ ግን ታመልጠዋለህ ። ከዚያ ትልቅ ተራራ መውጣትህ ፤ ሸሽተህ በምትሄድበት አገር ትልቅ ሹመት ትሾማለህ ማለት ነው ። ተራራ መውጣት ከፍተኛ ሹመት ፤ ከፍተኛ ማእርግ ማግኘት ነው ። እተራራው ላይ እንደ ቆምህ ጡትህ ወደምታ ምር ወይዘሮ መለወጡና ፤ ያች ወይዘሮ ባጠገብህ ቆማ መታየትዋ ሸሽ ተህ ወደምትሄድበት ቦታ ስትደርስ ፤ በምስጢር እንድታገባ የተገደድ ሀበት እስጊ ምክንያት የሚያሰጋ መሆኑ ቀርቶ ፤ ሚስትህ መሆንዋ በግ ሀድ ይታወቃል ማለት ነው። እተራራው ላይ ቀኝና ግራ ቆማችሁ ካፋ ችሁ የሚወጣው ጸሀይ በዙርያው ጨለማ የተጫጫነውን አገር ብርሃን ማድረግ ለምትሾሙበት አገር ቀን ታወጡለታላችሁ ፤ የምትገዙትን ህዝብ ደስ ታሰኙታላችሁ ማለት ነው ። እየውይህ ልጄ ፤ እኔ እባትህ እንዲህ አድርጌ ነው ሕልም የምተረጉም ! ደግሞ ሕልም ደህና ተርጉ ዋሚ ካገኘ ፤ ምንም ቢሆን አያብልም ! ይደርሳልና ተጠንቅቀህ ጠብ ቀው ! ሕልም አትናቅ ልጄ » አሉና አቶ በትሩ ፤ አራተኛውን ብርጭቆ ጨልጠው ሲያስቀምጡ ፤ የመሄድ ምልክት መሆኑን ተረድተው ባለ ቤታቸው ወይዘሮ ሽፍኔም ፤ ሶስተኛውን ጨርሰው ብርጭቆዋቸውን አስቀመጡና የባለቤታቸውን አይን ይመለከቱ ጀመር።

«እንግዲህ . . »አሉ አቶ በትሩ ፤ የባለቤታቸውን ለመነሳት መሰ ናዳት ሲያዩ እሳቸውም ለመነሳት እዩታጡ ። «እንግዲህ . . . እግዜአ ብሄር በምትሄድበት ሁሉ ቀኑን ይምራህ ፤ ልጄ ። ለኛ ትቀርብናለህ

@OLDBOOKSPDF

እንጂ ሳንተማ . . 'የሰው አገሩ ምግባሩ' እንደሚባለው መልካም ምግባር ስላለህ የሄድህበት ሁሉ አገርህ ፣ ባእዱ ሁሉ ዘመድህ ነው ! 'ይህ ወንድምሽ' አሉ አቶ በትሩ ወደ ሶፊያ እያዩ ። 'ይህ ወንድምሽ' ሰው አይባልም ፤ መላክ ነው ! እዚህ ሰፈር ሲኖር ፣ የሁሉ ረዳት ፣ የሁሉ አገልጋይ ሆኖ ነው የኖረ ። በተለይ የኔንማ ተይው ፤ ለኔ የሱ መሄድ ብርቱ ጉዳት ነው። ይች ቤት ከተሰራች ፣ ተከራይቶ እየገባ የወጣውን ሰው ቁጥሩን አላውቀውም ፤ እጅግ ብዙ ነው ። ነገር ግን እንደ ወንድምሽ ያለ ሰው ገብቶባት አያውቅም ። 'የደግ ሰው ቅርስ ደግ ሰው ይሰባል' ይባላልና 'ምናልባት የሱ ቅርስ እንደሱ ያለ ደግ ሰው ስቦ ያመጣልኝ ይሆን ?' ብዬ . . ነው እንጂ ኪታውን ሰባራ ሰንጣራ ሳጥን ሳይቀር ገዝቼ እቤት ውስጥ እንዲቀር ያደረግሁ ወድጄው አደለም ! እግዚአብሄር አይለይህ ልጄ ፤ ና ሳመኝ ! » አሉ አቶ በትሩ ሲነሱ ። ጥላሁን እቅፎ ቀኝና ግራ ጉንጮቻቸውን ሲስም ፣ ዝቅ ብሎ ጉልበታውን ባለመሳሙ የግልፍታ ስሜታቸው አስረስቶዋቸው መልሰው አልሳሙትም ።

አቶ በትሩና ባለቤታቸው ከወጡ በሁዋላ ፣ ሶፊያና ጥላሁን በልሙም ፣ በትርጉሙም በጣም ተገረሙ ።

«ይህ . . እልም ብለው ከንትርጉሙ የነገሩን እውነት ነው ? ወይስ . . ስለጋብቻችን የሰሙት ነገር ኖሮ ፣ ያን የሰሙትን በልም ያወቁት አስመስለው መናገራቸው ይሆን ! » አለች ሶፊያ ፣ በመገረም መልክ ።

« ስለጋብቻችን እንኩዋ እስቲ ማዘጋጃ ቤት ውሉን ካገቡትም ሆን እንዲሁ አብረን ሲያዩን በግምት ከሚያወሩት ግንኙነት ካላቸው ፣ ከነሱ ሊሰሙ ይችላሉ እንበል ፤ 'ጋብቻህን ለማሰናከል የሚጥር ፣ ብርቱ ምቀኛ አለህ 'ያለቱንስ ማን ነገራቸው እንላለ ን? » አለ ጥላሁን ።

«እንግዲህ ይህ የነገሩን እውነት እልም ነው ማለት ነዋ !»

«እንጃ! እኔ . . . ነውም ፣ አደለምም ለማለት እቸገራለሁ !» አለና ጥላሁን ዝም ብሎ ሲያስብ ቆይቶ «አንድ ነገር ሳልነግርሽ !» አለ ።

«ምን ?»

«ጥርጣሬ ፣ ወይም . . . ግምት ነው እንጂ በርግጥ የሆነ ነገር ነው ብዬ የማምንበት እንኩዋ አደለም !»

«ምንድነወ ኩ ?»

«የትምህርት ሚኒስቴር ሰራዮን ያስከለከለኝ ወንድይራድ ይመስለኛል ። »

«ሴንዴት ! » [illegible] @OLDBOOKSPDF እንደ መደንገጥ ብላ ።

«መጨረሻ ወደ ትምህርት ሚኒስቴር የሄድሁ እለት ፎቁን ስወጣ እሱ እላይ ቆይቶ እዮተንደረደረ ሲወርድ በደረጃው መሀከል ድንገት ተገናኘን ። ያንጊዜ ሁኔታውን ብታይ ትገረሚ ነበር ! ተመልሶ ወደላይ ሊሮጥ ከቃጣ በሁዋላ እንደገና ልብ ገዝቶ ቆመ ። ከዚያ ምንም ሳይና ገር ፣ የድንጋጤ ፈገግታ ብቻ ፈገግ ብሎ ፣ ቆስ እያለ ሶስት አራቱን ደረጃዎች እንደ ወረደ ዘወር አለና ፣ ‘ቸኩዬ ነው ያላነጋገርሁህ ፤ በሁ ዋላ እንተያያለን !’ ብሎኝ ሄደ ። ከዚያ በሁዋላ ግዋ ወልደ ተንሳይ መጥቶ ያው . . የሰማሽውን . . ነገረን ። »

«አዎ ፤ ትክክለኛ ግምት ነው ! » አለች ሶፍያ ፣ ዘለግ ያለ ጊዜ አን ገትዋን ደፍታ ስትተክዝ ፤ ከቆዩች በሁዋላ ፣ እንደገና ቀና ብላ የባልዋን አይኖች ትርታ ባስጊጣቸው አይኖቹዋ ጠልቃ እያዩች ።

«ያንጊዜ ያልነገርሁሽ የምናደርገውን አውቀን ስላልወሰን ፣ በተ ጨማሪ ግራ የሚያገባና የሚያበሳጭ ነገር መንገር . . . ያው በብስጭት ላይ ብስጭት ከመከመር በቀር አይጠቅምም ብዬ ነበር ። አሁን የምና ደርገውን ወስነናል ፤ መንገዳችን ተጠርጎዋል ። እንግዲህ የወንድይራድ ተንኮል ለጉዞዋችን የሚያገለግል ተራ ወሬ ነው እንጂ ፣ የሚያበሳጨን ወይም የሚያሳዝነን ሊሆን አይገባም ፤ የኔ እመቤት !» አለ ጥላሁን ፣ እቅፍ አድርጎ ይዞ ግንባሩዋን ከሳመ በሁዋላ ።

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፰

# አዲስ ከተማ

አንዳንድ ተመልካቾች ፥ “አዲስ ከተማ የኢትዮጵያ ናሙና ናት የሚሉት ስህተት አይደለም ። አዲስ ከተማ ትንሽ ኢትዮጵያ ናት ! አዲስ ከተማ በልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የተፈጠረው ፥ የተሰራውና የተፈራው ሁሉ ፥ ግለት ፥ ሰዉ ፥ ሀብቱ ፥ ባህሉ ፥ ስራቱ ፥ ቋንቋዋው ፥ እምነቱ ፥ ይህ ሁሉ ባንድ ላይ የሚታይባት ትንሽ ኢትዮጵያ ናት ! አዲስ ከተማ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርሶች ፥ ከዘመናዊት ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ሸቀጦች ፥ ቤተ ክርስቲያኑ ከቤተ መስጊዱ ፥ ቄሱ ከሸኩ ፥ እስላሙ ከክርስቲያኑ ፥ ይሁዲው ካረመኔው ጋር ፥ ባንድ ላይ የሚታዩባት ትንሽ ኢትዮጵያ ናት ! አዲስ ከተማ መንዜው ከነባናው ፥ ጅሜው ከነቡናው ፥ ዶርዜው ከነሸማው ፥ ከፋው ከነበርጨማው ፥ አዳሉ ከነጩቤው ፥ አሩሲው ከነቅቤው ፥ ወለጌው ከነብረቱ ፥ ጉራጌው ከነንሰቱ ፥ ጎጃሜው ከነማሩ ፥ ትግሬው ከነክራሩ ፥ ሌላውም ሁሉ እንዲሁ ለትርኢይት እንደ ተደራጀ በጥቂት በጥቂቱ እየተቆነጠረ ተመጥኖ ፥ የሚታይባት ትንሽ ኢትዮጵያ ናት !”

አዲስ ከተማ በኢትዮጵያ ከሚሰራውና ከሚፈራውም ሌላ ፥ ኬላ እየሰበረ ፥ ቀረጥ ሳይከፈልበት ከሚገባው የውጭ አገር ዕቃ ባብዛኛው መደብር ስለሆነች ፥ ያዲስ አበባ ወይዛዝርና መኩዋንንት ፥ ሸማግሌና ባልቴት ፥ ወጣቶችና ህጻናት የውጭ አገር እቃ በርካሽ ለመግዛት እዚያ መሄድ አለባቸው ! አዲስ ከተማ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርስዋ ፥ የዘመናዊት ኢትዮጵያ ህገብዋና የስራ ፍሬዋ ፥ ባንድ ላይ የሚታዩባት ስለሆነች ፥ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ከልዩ ልዩ አገር በብዛት የሚመጡ አገር ጎብኝዎች እዚያ መሄድ አለባቸው ! አዲስ ከተማ ገጠሬው በየክፍሉ ያፈራውን ጭኖም ሆነ ተሸክሞ እያመጣ ለከተሜው ቸርቻሪ የሚሸጥባት ስለሆነች ፥ ከያቅጣጫው የሚመጣው ገጠሬ ሁሉ እዚያ መሄድ አለበት ! አዲስ ከተማ ኩሊው ተሸክሞ ፥ ደላላው ደልሎ ፥ አታላዩ አታሎ ፥ ለማኙ ለምኖ ፥ ሌባው ሰርቆ ፥ የእለት ራቱን የሚያገኝባት ስለሆነች ፥ ሁሉም እዚያ መሄድ አለበት !

አዲስ ከተማ ይህ ሁሉ ተሰብስቦ ፥ በዚያ ላይ በጉ ፥ የተጫነውና ሌጣው አህያ ፥ ጋሪው ፥ መኪናው ተጨምሮ ፥ ሁሉም ባንድ ላይ

እየታመሰ ፡ እየተግፈጠረ ፡ ሁሉም ባንድ ላይ እየተጋፋ ፡ እየተላፋ ፡ ወደፊት ፡ ወደ ሁዋላ ፡ ወደ ቀኝ ፡ ወደ ግራ ዙሪያውን ሲጎርፍ ፡ ሁሉም ባለበት እንዳለ እየፈላ ፡ እየተብላላ ፡ ገንፍሎ ዙርያውን የሚፈስ መስሎ ሲታይ ፡ ያ ትርእይት እንከዋንስ ለማያውቀው እንግዳ ፡ አዘውትሮ እዚያ ለሚሄድም ሁልጊዜ አዲስ ፡ ሁልጊዜ እንግዳ ነገር ነው ! በተለይ ወደ አስራ አንድ ሰአት ግድም ፡ ገኸርው ሳይገዛ ፡ ሻጩ ሳይሸጥ ፡ ጎብኚው ሳይጎበኝ የሚቀረው ጊዜ አጭር በመሆኑ ፡ ኩሲው ተሸክሞ ፡ ደላላው ደልሎ ፡ አታላዩ አታሎ ፡ ለማኙ ለምኖ ፡ ሌባው ሰርቆ የለት ራቱን ሳያገኝ ምሺት በመቅረቡ ፡ ሁሉም የችኩላ ምልክት በዮፊቱ እየታዩ ፡ መታመሱና መተራመሱ ፡ መጋፋቱና መላፋቱ እጥፍ ይሆናል ! ሁሉም የለት ድካሙ ፍሬ ፡ የለት እድሉ ፡ የሚወሰነው በተረፈው አጭር ጊዜ መሆኑ እየተሰማው ፡ የልቡ ፍጥነት እጥፍ ፡ የግሩ እርምጃ ግማሽ ይሆናል !

"ምን ጉድ ነው ይሄ ? ዛሬ እዚህ ምን አለ ?" አለች ሶፊያ ወደ ኢትዮጵያ ቡና ቤት ሲሄዱ የተከራዩት ታክሲ ግፊያው ከባድ በሆነበት ቦታ ሲደርስ ፡ መንቀሳቀስ አቅቶት እንደ ቆመ ።

"በተለይ በዚህ ሰአት ፡ ባስራ አንድ ሰአት መርካቶ ሁልጊዜም እንዲህ ነው ፡ እሜቴ " አለ ታክሲ ነጂው ።

"መርካቶ ሁልጊዜም እንዲህ ነው ? አይ ፡ እንዴት አምልጦኛል ? እንዲህ መሆኑን ባውቅ ሁልጊዜ እምመጣው ን !" አለች ። እውነትም ሶፊያ አዲስ አበባ ከሶስት አመት በላይ ስትቀመጥ ፡ አዲስ ከተማን አንድ ቀን አይታው አታውቅም ።

የነጥላሁን ታክሲ መንገድ ተዘግቶበት በቆመበት እንዳለ ፡ ካለ ባበሳቸውና ከጠቅላላ ሁኔታቸው ገጠሬዎች የሚመስሉ ሰዎች አራት ሆነው ፡ በታክሲው አጠገብ እየተጋፉ ሲያልፉ ፡ አንድ የከተማ ሰው ከጎን ጥልቅ አለና ፡ ካራቱ መጨረሻ የሚሄደውን እናጥሎ ባዶ እግሩን በጫማ ሲረግጠው ፡ "አይ . . . !" ብሎ ጮኸ ገጠሬው ።

"ለምን ትረግጠኛለህ ?" አለ የከተማው ሰው ፡ የገጠሬውን ቀኝና ግራ ትከሻዎች በሁለት እጆቹ ይዞ በሀይል እየነቀነቀ ።

"ጫኸቴን ቀሙኝ ያለው ነገር መጣ ! አንተ ረግጠኸኝ . . . ደግሞ መልሰህ እኔን 'ረገጥኸኝ' ቀለኛለህ ? በል አሁን ልቀቀኝ ፡ ልቀቀኝ ብዬሀለሁ !" አለ ገጠሬው ፡ ሽመሉን ለማንዘር ወደ ሁዋላ ቀስሮ ።

@OLDBOOKSPDF

"እዚህኮ ዱላ የለም ፤ የህግ አገር ነው ጌታ !" አለ እዚያው ከሚጋፉት አንዱ ፣ የገጠሬውን እጅ ከነቪመሉ ከሁዋላው በኩል በሁለት እጁ ይዞ ።

"ምን አጣላችሁ ? ተዉ ተገላገሉ" አለ ሌላው ፣ እንዲሁ ከሚተራመሰው መንገደኛ ወጥቶ በገጠሬውና በጠብ ጫሪው መሀል ገብቶ ። ወዲያው በገላጋዮች ስም ከቀኝ ከግራ ፣ ከፊት ከሁዋላ የተጠራቀሙት ሰባት ሆነው ፣ ሁሉም ፣ "ተገላገሉ" እያሉ እዮሙሁ ፣ ገጠሬውን እመሀል አድርገው እንደ ኳዋስ እዮተቀባበሉ ሲደበድቡት፣ እሱ መጀመርያ የረገጠውን ሰው አንገት በግራ እጁ ሰንጎ ይዞ ፣ በቀኝ ደሞ እስኪነስረው አፍንጫ አፍንጫውን ይጠቀጥቀው ጀመር ። ወዲያው ፣ "ተገላገሉ" እያሉ ከሚሆሁት አንዱ ከገጠሬው ኪስ አንድ በጨርቅ የተጠቀለለ ነገር አውጥቶ አገዛ ኪሱ ውስጥ ሲከት ሶፊያ አዩችና ፣

"እየው ፤ እየው ገንዘቡን ሲወስድበት ! ወሰደበትኮ !" ከማለትዋ ፣ ጥላሁን ከታክሲው በሮ ወጥቶ ፣ ገንዘቡን የወሰደውን ሰው አንድ ጊዜ በጡጫ አፍንጫውን ነጠረቀና ሲወድቅ ሲንገዳገድ ፣ "በል ቶሎ ገንዘቡን መልስለት" አለ ፣ ሁለተኛ ለመድገም ጡጫውን እንደ ደገነ ።

ጥላሁን ፣ "ገንዘቡን መልስለት" ሲል ገጠሬው ሰምቶ ኪሱን ቢዳብስ ገንዘቡን ስላጣው ፣ " ገንዘቤን ፤ አምስት መቶ ብሬን !" ብሎ ጮኸ ፣ ይዞት የነበረውን ሰው ለቀቀና ፣ ጥላሁን የመታውን ሰው እንደ ያዘ ፤ ሁለት ለስምንት የቡጢ ጦርነት ገጥመው ይጠቃጠቁ ጀመር ። ጥላሁን በቅጥበት ሁለቱን ዘረጋቸው ፤ ደቂቃ ሳይሞላ ሁለቱን ሌሎች ከወደቁት ጉዋደኞቻቸው ጋር ጨመራቸው ፤ ሶፊያ የገጠሬውን ዱላ ከወደቀበት አንስታ አንዱን ወቃችው ፤ የገጠሬው ጉዋደኞች ሲደርሱ ፣ የወደቁት ከወደቁበት እዮተውተረተሩ ተነስተው ጦርነቱ ለድስት ለስምንት ሆኖ ነበር ። ብቻ ወዲያው ፖሊሶች ከሩቅ ፊሽካ እዮነፉ ሲመጡ ፣ ሕዝብ ከነሱ ጋር ባንድ ላይ ግልብጥ ብሎ መጥቶ የጠቡን ቦታ ገብያ ስላደረገው ፣ ጦርነቱ ቆመ ። በጦርነቱ ጊዜ በጦሩ ሜዳ ከጦረኞች በቀር ማንም አልነበረም ። ባካባቢው ሱቆች በዩበረንዳው የነበረው ህዝብ ሳይቀር ሸሽቶ ነበር ። የነጥላሁን ታክሲ ነጂ እንኩዋ በቦታው አልነበረም ። ስምንቱ ሌቦች ለካስ በሌብነት ስራቸው ባካባቢው ስመጥሮች ኖረው ፣ ሲሸሹ ሲሞክሩ ፖሊሶች አባረው ባኮርማጅ እየደበደቡ ባንድ ላይ ሲያግቱዋቸው ፣ ጥላሁንና ሶፊያ በግርግሩ መሀከል ማንም ልብ ሳያደርጋቸው ፣ ሾፌከው እታክሲ

@OLDBOOKSPDF

ቸው ውስጥ ገብተው ፣ ወደ ኢትዮጵያ ቡና ቤት ሄዱ ። ስምንቱን ሌቦችና አራቱን ገጠሬዎች ፖሊሶች ወደ ጣቢያ ወሰዷቸው ።

"ወይኔት ሄደው ኖሮዋል ጋሼ ?" አለ ጥላሁን ፣ እሱና ሶፊያ እታክሲው ውስጥ ገብተው እንደ ተቀመጡ ፣ ነጂው ከነበረበት አዩሮጠ መጥቶ ሲገባ ።

" እጅህ ስለት ምሳር እንዳጥደድህበት የመታውን ሁሉ እዩገን ደስ ሲያጋድም ፣ ከተሸሸግሁበት ሱቅ መስኮት ሆኜ ታምር እመለከት ነበር ! እረዳይ ! ያንተ እናት ብቻ ወንድ መሰድሁ ያበሉ ፣ ያንተ ሚስት ብቻ ወንድ አገባሁ ትበል !" አለ ነጂው ፣ በጥልቅ አንድን ቆት እንገቱን እዩወዘወዘ ።

"እሱ እንኪዋ እንዲያው ሲቀልዱ ነው ! ብቻ . . . ለምን ተሸሽጉ ? እንዲህ ባለ እምባጉዋሮ ጊዜ ጉዋደኛ ሲሆን ይረዳል ! ያለዚያም ይገላግላል እንጂ ይሸሽጋል ?"

" እሱ ድሮ ቀረ ፣ ዛሬ ሰው ሲደባደብ ፣ እንኪዋንስ የሚገላግል ፣ የቆሰለ የሚረዳ ፣ ነፍስ ቢወድቅ ሬሳ የሚያነሳ አይገኝም ! ሁሉም መሸሽ ነው ! ያ ፣ መንገዱን ግጥም አድርጎ ፣ ይዞ አላንቀሳቅሰን ብሎ የነበረው ሕዝብ ሁሉ እናንተ መደባደብ መጀመራችሁን እንዳዩ ወዲያው የውሀ ሽታ ሲሆን . . . አላዩሀልኝም ?"

"እውነትም ጠላቶቻችን መብዛታቸውን ሳይ ለጊዜው የሚያሸን ፉን መስሎኝ ፣ ሰግቼ . . . እይኔ የሚገላግል ሰው ዞሩያውን ቢፈልግ አንድ እንኪዋ አጣሁ ። ያን ሁሉ ሰው ምን ዋጠው ?" አለች ሶፊያ ።

"ፖሊሶች እምባጉዋሮ በተነሳበት ፣ ወይም አደጋ በደረሰበት አጠገብ ያገኙትን ሁሉ ግማሹን ፣ 'ተባባሪ ነህ' ግማሹን 'ለምስክር ነት ትፈለጋለህ' ፣ እያሉ ነድተው ወስደው እጣቢያ እያጎሩ ፣ እዚያ ድብደባው ፣ ከተላላኪ ጀምሮ እዚያ ላለው ሁሉ መገላገያ መክፈሉና ከሁሉም ደግሞ መጨረሻ በሌለው ቀጠሮ ስራ መፍታቱ ሰውን ሁሉ ስላስመረረው ፣ እምባጉዋሮና አደጋ ሲያይ ፖሊሶችን እዩፈራ ከመገላገልም ፣ ከመርዳትም መሸሽ ይወዳል" አለ ታክሲ ነጂው ።

ሶፊያና ጥላሁን ከታክሲ ነጂው ጋር እያወሩ ኢትዮጵያ ቡና ቤት ሲደርሱ ፣ እስራ ሁለት ሰአት ግድም ስለነበረ ፣ የቡና ቤቱን እደባባይና በረንዳውን ሰው ሞልቶት ነበር ።

ባለካሚዮናቸው ፣ እቶ ዮሴፍ ብርሃኔና እዩታንቲው ገብረ ሚካኤል ተከኤ እካሚዮናቸው ላይ ወጥተው ፣ ጭነት እያስተካከሉ ሸራ ሲያለብሱ ቆይተው ፣ ገብረ ሚካኤል ገና እካሚዮኑ ላይ እንዳለ ፣ እቶ ዮሴፍ መውረዱ ነበር ።

@OLDBOOKSPDF

"ምነው ! አደጋ ደረሰ ? " አለ አቶ ዮሴፍ ፤ የጥላሁንን ያበጠና የተላላጠ ፊት ሲያይ እንደ መደንገጥ ብሎ ።

"አ ! ትንሽ ነው ! ምንም አይል ። እዚህ ታች አምባጉዋሮ ተነስቶ ፤ እኛንም ሳናስበው ስቦ አግብቶን ፤ እዚያ ፊቴን ትንሽ ሙዋጨ ሩኝ ። እሱዋ ባለቤቴ ሾዮን ናት " አለ ጥላሁን ፤ ንግግሩን ከደረሰው አደጋ ወደ ሌላ ለመምራት ስለ ፈለገ ሶፊያን በጁ እያመለከተ ።

አቶ ዮሴፍ ፤ ለሶፊያ በፈገግታ የጅ ሰላምታ ከሰጠ በሁዋላ ፤ ባንድ እጁ ወገቡን ደገፍ አድርጎ ፤ ሽራ የተከናነበ ካሚዮኑን ትንሽ ሲመለከት ቆዬና ፤ "እየውልህ እኔም . . . 'የጥቅምት ቀንና የቆንጆ ሳቅ እያታለህ' የሚሉት ያባቶች ማስጠንቀቂያ ትዝ ሲለኝ ጊዜ ፤ ጭነቴን ሽራ አልብሼ መውረዴ ነው " አለ ፤ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ ጥላሁንን እያዬ ።

" ተረቱ ምን ማለት ነው? " አለ ጥላሁን ፤ እሱም እንደ መሳቅ ብሎ።

"የጥቅምት ቀን ፤ ልክ እንደ በጋ ሰማዩ ወለል ብሎ ጠርቶ ጸሀዩ ሲሞቅ ፤ 'በጋ ነው' ብለህ ተታለህ ጭነትህን ሳታለብስ የተውኸው እንደሆነ ፤ ሌሊት ዝናብ ባይጥል ከዝናብ የማያንስ እንዝብ ወርዶ ወረትህን ሁሉ ውሀ አስበልቶብህ ያድራል ፤ ትክስራለህ ማለት ነው !" አለ አቶ ዮሴፍ ፤ የሶፊያን እዚያ መኖር ስላስታዎሰ ምሳሌውን ሳይጨርስ እመሀል መንገድ አቁሞ ።

" የቆንጆ ሳቅ ያሉትስ ? " አለ ጥላሁን ፤ አቶ ዮሴፍ የማይቀጥል መሆኑን ሲያይ ።

" እሱም . . . ያው ነው " አለ አቶ ዮሴፍ ፤ ሳያስብ በጀመረው ምሳሌ ትንሽ የማፈር ምልክት በፊቱ እዬታዬ።

" ይጨርሱልን እንጂ ! እኛ ተማሮች ነን ፤ እንዲህ ያሉትን ምሳሌዎች ማወቅ እንፈልጋለን ። "

"በጣም ስንተዋወቅ እጨርሰዋለሁ ። "

ከዚያ አቶ ዮሴፍ ፤ ሻይ እንዲጠጡ ሶፊያንና ጥላሁንን ጋብዞዋቸው ፤ እበረንዳው ላይ ያልተያዘ ጠረጴዛ አግኝተው ከመቀመጣቸው ፤ ጥላሁን በፊቱ የደረቀው ደም ስለ ጨመደደውና ባይኑ የመላው ትቢያ እዬቆረቆረ ስላስቸገረው ፤ አቶ ዮሴፍን ይቅርታ ለምኖ ፊቱን ለመታጠብ ወደ ውስጥ ገባ ።

@OLDBOOKSPDF

ከዚያ ሲመለስ በውነቱ ሁሉ ታውኮ ፤ ወባ እንደ ያዘው ሰው እየተንቀጠቀጠ መጣ ።

"ጥላዬ ፡ ምን ሆንህ ?" አለች ሶፊያ ፤ ሁኔታውን ገና በሩቅ ስታይ በጣም ደንግጣ ። ከመደንገጥዋ የተነሳ ፤ ስሙ መለወጡን እንኳ ረስታ ፤ በውነተኛ ስሙ ጠራችው ። አቶ ዮሴፍም ደንግጦ ስለነበረ ምን እንደ ተናገረች በቅጡ ያዳመጣት አይመስልም ።

"ጨርሶ ሲገባኝ የማይችል ፤ ሲሆን የማይችል ነገር ነው ! ፊቴን ታጥቤ ፎጣ ስላጣሁ ፤ በመሀረሜ ልጠርግ እጄን እኪሴ ብከት ያውልሽ፤ ይህን አገኘሁ !" ብሎ አንድ ባደፈ የጨርቅ እራፊ ተጠቅልሎ የተቋጠረ ነገር ከኪሱ አውጥቶ እፊትዋ በጠረጴዛው ላይ ወርውሮ ሲጥል ፤ ያ እፊትዋ የወደቀ ነገር መብረቅ እንደሆነ ሁሉ ደንግጣ ፤ ሳትናገር ብዙ ቆዩች ።

"ሌባው ከነጠፈው ኪስ አውጥቶ በገዛ ኪሉ ሲከተው ያዩነው !" አለች ሶፊያ ፤ እፍዋን ይዛ ዝም ብላ ከቆዩች በሁዋላ ፤ ምስጢር እን ደምትናገር ቀስ ብላ በሹክሹክታ ።

"አዎ ፤ አምስት መቶ ብር ። ብቻ እንዴት እኔ ኪስ ተገኘ ? እንዴት ሆኖ መጣ ?" አለ ጥላሁን ፤ አይኑን ሁሉ ካፎቱ ጎልጉሎ አውጥቶ ፤ አንድ ጊዜ ሶፊያን ፤ አንድ ጊዜ አቶ ዮሴፍን እያለዋወጠ እያዩ ።

"ፖሊሶች ሲመጡ ከሌቦች ጋር ተያይዛችሁ ኖሮዋል ?" አለ አቶ ዮሴፍ ፤ ሶፊያ ታሪኩን ባጭር ከተረከችለት በሁዋላ ።

"አዎ ፤ ፖሊሶች ፊሽካ ሲነፉ ለመሸሽ ቢሞክሩም ስለ ያዝናቸው እንታገል ነበር " አለ ጥላሁን ።

"የመርካቶ ሌቦች አጥማጆች ናቸው ። ፖሊስ ሲደርስባቸውና እንደማያመልጡ ሲያውቁ ፤ የሰረቁት ነገር ከነሱ ጋር እንዳይገኝ የሚ ያደርጉት ዘዴ ብዙ ነው ። የሰረቁትን ገንዘብ ቢመቻቸው ወደሰረቁ በት ኪስ መልሰው ፤ ባይመቻቸው አጠገባቸው ባገኙት ፤ በማንም ሰው ኪስ ከተው ፤ ተይዘው ሲበረበሩ የሚበዛውን ጊዜ ባዶዋቸውን ነው የሚገኙት ። እጃቸው ልክ እንደ ዛር እጅ ፤ ከሰው ኪስ ገንዘብ ሲያወጣም ሆነ መልሶ ሲከት የሚያየውም ፤ የሚሰማውም የለ ! ዛሬም የሆነው ይህ ነው ። ከፖሊሶች እንደማያመልጡ ሲያውቁ ፤ እንደ ተያ ያዛችሁ ከኪሳቸው አውጥተው ባንተ ኪስ ከተውታል ። ብቻ እግዜር መከሮህ ቶሎ ባትሸሽ በሌብነት ተይዘህ የምትታሰር አንተ ነበርህ !" አለ አቶ ዮሴፍ እዩሳቁ ።

@OLDBOOKSPDF

" አሁን ምን ላድርግ ?" አለ ጥላሁን ፣ የሚያደርገው ግራ ገብቶት ።

"አሁንማ . . . እግዜር እንደ ፈረደብህ ያምስት መቶ ብር ጌታ ከመሆን በቀር መቸስ ምን ታደርጋለህ ?"

"ይተዉ አይቀልዱ ፤ ያ ድሀ ገንዘቡን ማግኘት አለበት ፤ ይልቅ ይችሉ እንደሆነ እባክዎ ይርዱኝ " አለ ጥላሁን ፣ ባቶ ዮሴፍ ቀልድ መቀየሙን በግልጽ እያሳዩ ።

"እንዴት አድርጌ ልርዳህ ? የሰውዬውን ስም ታውቀዋለህ ? ስሙስ ቢታወቅ ፣ መኖሪያው ካልታወቀ የት ብለን እንፈልገዋለን ?" አለ አቶ ዮሴፍ ፣ የጥላሁንን መቀየምና መጨነቅ ሲያይ ቀልዱንም ፣ ሳቁንም ትቶ ማዘኑ ከፊቱ እየታየ ።

"ወደ ፖሊስ ጣቢያ ነው የሄዱ ፤ እባክዎ እኔ ጣቢያውን አላውቀውምና ፣ ረዳትዎ እዚያ እንዲወስደኝ ይንገሩልኝ ።"

"መውሰዱንስ እኔ እወስድሀለሁ ፤ እዚህ ቅርብ ነው ፤ ብቻ አሁን አስራ ሁለት ሰአት ስላለፈ ፣ ባላገሮች ካልታሰሩ በቀር እዚያ አይገኙም ፤ 'ገንዘቡን ለፖሊሶች አስረክበን እንምጣ' ትል እንደሆነ ተነስ ልውሰድህ ። ነገር ግን አንድ ነገር እወቅ ፤ ለፖሊስ ያስረከብከው ገንዘብ 'ለባላገሩ ይደርሳል' ብለህ አታስብ !"

"መቸም ፖሊሶች የሰው ህይወትና ንብረት በታማኝነት ሲጠብቁ የሚኖሩ ባላደራዎች ስለሆኑ ፣ ቢሰጡ ይስጡት ፣ እምነታቸውን አጉድለው አደራቸውን ቢበሉ ፣ ከኔ ራስ ይውረድና እነሱን ሁዋላ እግዜር ይጠይቃቸው !"

"ለመሆኑ ፣ እስቲ እኔ እንደማውቃቸው አደራ በላዎች ያልሆኑ ፣ አንተ እንደምትመኘው ምለው የተቀበሉትን አደራ አክባሪዎች የሆኑ ፖሊሶች ፣ እግዜር ዛሬ ሌሊት ፈጥሮ ይደርና አሁን የምንሰጣቸውን ገንዘብ ነገ ጥዋት ለባለገንዘቡ የሚመልሱ ይሁኑ እንበል ። የሰውዬውን ስም ካላወቅህ ፣ የማን ገንዘብ ነው ብለህ ታስረክባቸዋለህ ? እነሱስ ማን ብለው ፈልገው ይሰጡታል ?"

"ይህ አያስቸግርም ፣ ጋሽ ። ገንዘቡ የተሰረቀበትን ቦታና ጊዜ ከተሰረቀበት ዝርዝር ሁኔታ ጋር ስንነግራቸው ፣ የኛን ቃል ዛሬ ገጠሬዎችና ሌቦች ሲመረመሩ ከሰጡት ቃል ጋር አስተያይተው ፣ ገንዘቡ የማን መሆኑን ማረጋገጥ እንደማያስቸግራቸው የታወቀ ነውና፣ 'ይነሱ እንሂድ እባክዎ !' ሲል ጥላሁን ተነስቶ ቆመ።"

@OLDBOOKSPDF

“እይ ! እይ ! እዚያ ፣ ጥላዬ !” አለች ሶፊያ ፣ ወዳጥሩ በር ጠቁዋሚ ጣቱዋን ቀስራ ።

አራት አደፍ አደፍ ያለ ልብስ የለበሱ ሰዎች ፣ ዘመድ ቀብረው እንደሚመለሱ አዘንተኞች አንገታቸውን ደፍተው ፣ በዝምታ ቀስ እያሉ መጥተው እበረንዳው ስር ፣ አደባባዩ ላይ ፣ ባንድ እጅብ ብለው ቆመው ቆይተው ፣ ለናቶ ዮሴፍ በማይሰማ ድምጽ እስበሳቸው ትንሽ ተነጋግ ሩና ፣ ግራ ቀኝ ሳያዩ ፣ በነጥላሁን ፊት እያለፉ አንድ ጠረጴዛ ከበው ተቀመጡ ።

“እነሱ አይደሉም ? እነሱ ናቸውኮ!” አለች ሶፊያ ።

“እነማን ?” አለ አቶ ዮሴፍ ።

“የዚህ ገንዘብ ጌቶች ፤ ገጠሬዎች!”

ጥላሁን ሳይታወቀው ከቆመበት ቁጭ ፣ ብድግ ፣ ደግሞ እንደገና ቁጭ አለና ባፉ ምንም ሳይናገር ዝም ብሎ አንድ ጊዜ ሶፊያን ፣ አንድ ጊዜ አቶ ዮሴፍን እያለዋወጠ ትንሽ ሲያይ ቆይቶ ፣ ገንዘቡን በኪሱ ይዞ ገጠሬዎች ወደ ተቀመጡበት ሄደ ።

“ቆይ እስቲ ፤ ሄደህ እንዴት ትላቸዋለህ ?” አለች ሶፊያ ። ጥላ ሁን ደስታውን እንጂ የሰዋን ጥያቄ በሳልሰማ ዝም ብሎዋት ሄደ ።

“ጤና ይስጥልኝ ፤ እንዴት ሆናችሁ ?” አለ ፣ ገጠሬዎች በተቀ መጡበት ሲደርስ ። ሶስቱ ቀና ብለው ትንሽ ተመለከቱትና ፣ ከዚያ በፊት የማየታቸው ትዝታ ቢሰማቸውም የት እንዳዩት ጠፍቶዋቸው እስበሳቸው የጥያቄ አይን ከተለዋወጡ በሁዋላ ፣ “ ምን እንሆናለን ? ለመሆኑስ የት ኖሮዋል የምንተዋወቀው ?” አለ አንዱ ። አራተኛው ክርናቸውን በጠረጴዛው ተክለው ፣ የተደፋ ራሳቸውን በመዳፋቸው አስደግፈው እንደ ተቀመጡ ቀና እንኳዋ አላሉም ነበር ። “በጊዜ ከሌ ቦች ጋር” ብሎ ጥላሁን የሚተዋወቁበትን ለመናገር ከመጀመሩ ፣ ራሳ ቸውን ደፍተው የተቀመጡት ገጠሬ ቀና ብለው አዩና ፣ “ ኸረ የደረ ናው ጊዮርጊስ !” አሉ አቋዋርጠው ። ከዚያ ተነስተው ፣ አንድ እጁን በሁለት እጃቸው ይዘው እዬሳሙ ፣ “ እሱ ነውኮ ! ያ የነገርሁዋችሁ እሱ ነውኮ ! ገንዘቤን ባይሆን ነፍሴን ያዳነ እሱ ነውኮ ! እንደ ክር ስቶስ ያለዳው በሰው እዳ መከራ የተቀበለ እሱ ነው ፤ እዩት ፊቱን !” ሲሉ ገንዘባቸውን የተቀሙት ሰው ፣ ሶስቱ ጉዋደኞቻቸው ተነስተው፣ ጥላሁንን ከበው ፣ “ያዩሁበት ጠፍቶኝ ነው እንጂ አንድ ቦታ ያዩ ሁት መሆኑማ ትዝ ብሎኝ ነበር !” አሉ አንዱ ። “እኔምኮ . . . ያው

@OLDBOOKSPDF

ሆኖብኝ ነው !" አሉ ሁለተኛው ። " እኔስ መጀመርያ ገር እሰኝ እንጂ ሁዋላ ያኰሁበት ቦታም ትዝ ብሎኝ ነበር !" አሉ ሶስተኛው ።

አራቱ ገጠሬዎች ጥላሁንን አመሀከላቸው አድርገው ሲንጫጩ ፣ እዚያ ያለው ሁሉ ከየጠረጴዛው ፊቱን ወደነሱ መልሶ ሲያፈጥ አይቶ ፣ "እስቲ እንቀመጥና ቀስ ብለን እንነጋገር" አለ ጥላሁን ።

"እስቲ እባካችሁ እዩት ! ያልወለዱት ፣ ያልተዛመዱት ልጅ እንዲያው . . . ለእግዚር ብሎ ይህን ያክል መከራ ይቀበላል?" አሉ ገንዘባቸውን የተሰረቁት ሰው ፣ ከተቀመጡ በሁዋላ የጥላሁንን ያበ ጠና የተላላጠ ፊት በጃቸው ለጉዋደኞቻቸው እያመለከቱ ።

"አ ! ለኔ አያስቡ ምንም አደለ ! ይልቅ የገንዘቡ ነገር እንዴት ሆነ ?" አለ ጥላሁን ፣ ባለገንዘቡን አግኝቶ እዳውን እስኪያስወርድ የቸኮለውን ያክል ፣ ካገኛቸው በሁዋላ ስለ ገንዘባቸው መጥፋት ስሜ ታቸውንና የሚሉትን ለማወቅ ፈልጎ ።

"ገንዘቤማ ፣ በሮቼ ስላለቁ ያንድ በሬ ዋጋ እተርፋለሁ መስሎኝ የማላውቅበትን ፣ አድርጌው የማላውቀውን ፣ ልንግድ ባራጣ ተበድሬ ! ማር ገዝቼ አምጥቼ ፣ የሸጥሁበት ገንዘብማ እንዲሁ እንዳለ ቀልጦ ቀረ ! በሊሶች ! " ሌቦችን መረመርን" አሉን ፤ እኛንም የላስነው የቀመስነው አንድ ሳይቀር ሲያናዝዙን አምሽተው . . . "ለጊዜው ምንም ፍንጭ አልተገኘም ፤ እስቲ ደሞ ነገ ተመለሱ" ብለው ሰደዱን ። የነ ገን ቁርጥ አውቄ እንግዲህ መሰደድ ነው ፤ አገሬ አልገባም ፤ መሰ ደድ ነው ! ያ . . . አራጣ አበዳሪው ፣ ቾኮል ቢሰውር ፣ አገሬ አያስ ቀምጠኝም ፤ ከፉ አውሬ ነው !" አሉ ገጠሬው ፣ አይናቻቸውን ሳያ ረግቡ ፊት-ለፊት ተክለው ፣ ያቶ ቾኮል ቢሰውርን ገንዘብ ሳይዙ አገ ራቸው ቢገቡ የሚገጥማቸውን ችግር እያዩ ።

ጥላሁን የገጠሬውን ስሜት በቃል ከተናገሩት የበለጠ ባይናቸ ውና በጠቅላላ ሁኔታቸው ያዩው ስለነገረው ፣ በጣም አዝኖ ፣ ልቡ ተነክቶ ፣ ዳግመኛ ሊጠይቃቸው አልቻለም ። ግራ እጁን በሁለት እጃ ቸው ይዘው እንደ ተቀመጡ ፣ ምንም ሳይናገር ፣ በቀኙ ገንዘቡን ባደፈ የጨርቅ እራፊ ተጠቅልሎ እንደ ተቋዋጠረ ፣ ከኪሱ አውጥቶ እፊታ ቸው በጠረጴዛው ላይ ቁጭ ሲያደርገው ፣ እጁን እንደ ጨበጡ እዚ ያው ደርቀው ቀሩ ። ጉዋደኞቻቸውም ያ ባደፈ ጨርቅ ተጠቅሎ እፊ ታቸው የተቀመጠ ነገር ያፍዝ ፣ ያደንዝዝ እንዳለው ሁሉ አፍዞዋ ቸው ፣ አይኖቻቸውን በሱ ላይ ተክለው ዝም አሉ ።

"እስቲ ፍቱና [illegible] @OLDBOOKSPDF አለ ጥላሁን ፤ በዝቅተኛ ድምጽ ። ከዚያ አራቱ ጉዋደኛሞች እስበላቸው ሲተያዩ ትንሽ ቆይተው ፤ አንደኛው ቀስ ብለው ፤ ቁጥጠሮውን ፈተው ፤ ሁለት ጊዜ መላልሰው ቆጠሩና ፤ 'ልክ ነው ፤ አምስት መቶ !' አሉ ፤ በዝቅተኛ ድምጽ ፤ ራሳቸውን ቀና አድርገው ጉዋደኞቻቸውን እያዩ ።

"ከስደት አዳንኸኝ ! ማተቤን ከመቁረጥ አዳንኸኝ ! ላገሬ ፤ ለቤቴ ፤ ለሚስቴና ለልጆቼ አበቃኸኝ !" አሉ ባለገንዘቡ ፤ በተሰበረ ድምጽ ። ጥላሁን የሰውዬውን እንባ ያዘሉ አይኖች ሲያይ ፤ እንጀቱ በውስጡ ሲላወስ ተሰማውና ወዲያው የሱም አይኖች እንባ ሞሉ ።

"አዲስ አበባን ረግሜ ልሄድ ነበር ፤ እንደናንተ ያላችሁ ሰዎች ካላችሁበት አልረግመውም !" አሉ ከባለገንዘቡ ጉዋደኞች አንዱ ።

"እዋ ! አጋንንቱና መላእክቱ በተስኪያን አብረው መኖራቸውን አታውቅም ?" አሉ ሌላው እንደ መሳቅ ብለው ።

"በሉ እንግዴህ እግዜር በደህና አገራችሁ ያግባችሁ" ብሎ ጥላሁን ሲነሳ ፤ ባላገሮቹ እንዲጋበዝላቸው በጣም አጥብቀው ለመኑት ። ነገር ግን እንግዳ የሚጠብቀው መሆኑን ስላስረዳቸው ኢያዘኑ ተሰናበቱት ።

"ገንዘብ ለማግኘት አጥብቀው የሚጨነቁ ብዙ ሰዎች ፤ ራሴን ጭምር አውቃለሁ ። ያገኙትን ገንዘብ ለመስጠት ይህን ያክል የሚጨነቁ ግን ፤ ዛሬ ከናንተ በቀር አይቼ አላውቅም !" አለ አቶ ዮሴፍ ፤ ጥላሁን ሲመለስ ።

"እኛም ገንዘብ ብናገኝ እንወዳለንኮ ፤ ብቻ የሌሎችን ሰርቀን አይደለም !" አለ ጥላሁን ፤ እንደ መሳቅ ብሎ ።

"የሆነ ሆኖ ፤ ያን ያክል የተጨነቃችሁበት ነገር ስለሆነላችሁ እንኩዋን ደስ አላችሁ" አለ አቶ ዮሴፍ ። "ይህ ቡና ቤት ከሌሎች ከሚመረጥባቸው ምክንያቶች አንዱ ይህ ነው " አለ ቀጠለና ።

"ምኑ ?" አለ ጥላሁን ።

"ከማናቸውም የኢትዮጵያ ክፍል አዲስ አበባ መጥቶ የሚሰነብት ሰው ፤ ትልቅ መኩዋንንት ፤ ወይም ዘመድ ያለው ካልሆነ መሳፈሪያው መርካቶ ነው ። መርካቶ የሰፈረም ለምሳ ባይሆን ለራት ፤ ለራት ባይሆን ለምሳ ፤ ኢትዮጵያ ቡና ቤት የማይመጣ የለም ። ኢትዮጵያ ቡና ቤት መርካቶ የሰፈረ ገጠሬ መፈለጊያ ፤ የገጠሬ ማጥመጃ ነው ። እዚህ ባትሰናር እነዚህን ገጠሬዎች አታገኛቸውም ነበር ።

@OLDBOOKSPDF

"ገጠሬው አዲስ ከተማ የሚሰፍርበትና ፣ አዲስ ከተማ የሰፈረ ገጠሬ ኢትዮጵያ ቡና ቤት ሳይደርስ የማይቀርበት ምክናያት አለ ? "

"ጣሊያኖች አገራችንን በያዙ ጊዜ ፡ አራዳን ፡ ካዛንቺስን ፡ ፖፖላሬንና ወዲያኛውን ክፍል ሁሉ ፣ ለፈረንጅ መኖሪያ ፣ መርካቶንና ወዲህኛውን ክፍል ፣ ያበሻ መኖሪያ እንዲሆን በሁለት ክፍለውት ነበር። በዚህ ምክናያት ጥሩ ጥሩ ውድ ሆቴሎች ፣ ሱቆችና መኖሪያ ቤቶች እዚያ ሲሰሩ ፣ ላበሻ ኑሮ የሚሆኑ ሸቀጦች የሚሸጡባቸው ሱቆችና ፣ ላበሻ አቅም የሚሆኑ ርካሽ ሆቴሎች እዚህ ተሰሩ ። በዚያ ሳቢያ ፣ ጣሊያኖች ከሄዱ በሁዋላም ፣ ለፈረንጅ የተሰሩት ጥሩ ጥሩ ውድ ሆቴሎች ፣ ሱቆችና መኖርያ ቤቶች ለፈረንጆችና እንደ ፈረንጅ ለሚበሉ ፣ እንደ ፈረንጅ ለሚለብሱ ፡ እንደ ፈረንጅ ለሚኖሩ አበሾች ሲሆኑ ፣ መርካቶና ባካባቢው የተሰሩት ፣ ላበሻ ኑሮ የሚሆኑ ሸቀጦች የሚሸጡባቸው ሱቆችና ፣ ላበሻ አቅም የሚሆኑ ርካሽ ሆቴሎች ደግሞ ፣ እንዳበሻ ለሚበሉ ፣ እንዳበሻ ለሚለብሱና እንዳበሻ ለሚኖሩ አበሾች እንደሆኑ ቀሩ ። ማለት ወዲያኛው ፣ ውዱ ክፍል አዲስ አበባ ፣ የፈረንጅ አበሻ ክፍል ፣ ወዲህኛው ፣ ርካሹ ክፍል አዲስ አበባ ፣ ያበሻ አበሻ ክፍል ናቸው ። ስለዚህ ፣ ገጠሬዎች ፈረንጅ አበሾች ስላልሆኑ ፣ አዲስ አበባ ሲሰንብቱ ሲመጡ ወደ ውዱ ፣ ወደ ፈረንጅ አበሻ ክፍል አይሄዱም ፤ ወደርካሹ ፣ ወዳበሻው አበሻ ክፍል ነው የሚመጡ ። መርካቶ የሚሰፍር ገጠሬ ሁሉ ፣ ኢትዮጵያ ቡና ቤት የሚሰበሰብበት ምክናያት ደግሞ ፣ ስለ ምግቡ ነው ። እዚህ አንድ ሰው ጥሩ ምግብ እስኪጠግብ በልቶ አንድ ብር ፣ አንድ ጠርሙስ ጥሩ የማር ጠጅ ጠጥቶ አምሳ ሳንቲም ፣ በማር ጠጅ ፋንታ አንድ ትልቅ ብርጭቆ ሺና ወይም የወይን ጠጅ ቢጠጣ ፡ ሀያ አምስት ሳንቲም ፣ ላዝማሪ ሀያ አምስት ሳንቲም ይከፍላል ። ማለት አንድ ሰው እስኪጠግብ በልቶና ጠጥቶ ፣ ደስ እስኪለው ተጫውቶ ፣ የሚከፍለው አንድ ብር ከሰባ አምስት ፣ ወይም አንድ ብር ካምሳ ሳንቲም ብቻ ነው ። በብዛት ሆነ ባይነትና በጽዳት ፣ ከዚህ ተመሳሳይ የሆነ ምግብ በዚህ ዋጋ ከሌሎች ከፍተኛ ቡና ቤቶች አይገኝም ። ኢትዮጵያ ቡና ቤት መኝታ ብቻ ውድ ነው ። ስለዚህ ከገጠር ከሚመጡ ነጋዴዎች ፣ ከዩጠቅላይ ግዛቱ ለሹመት ከሚመጡ ዳኞችና ፣ ከያገሩ በይግባኝ ከሚመጡ ተሙዋጋቾችና እንዲሁም ፣ ባዲስ አበባና በጠቅላይ ግዛቶች መሀከል ከባድ መኪና ከሚነዱ ሾፌሮች ፣ በጣም የሚበዙት መኝታቸውን ገቅተኛ ደረጃ ባላቸው ሆቴሎች ቢያደርጉ እንኳ ፣ ምግባቸውን የሚመገቡ እዚህ ነው ።

@OLDBOOKSPDF

"ላዝማሪ ሃያ አምስት ሳንቲም ይከፈላል ያሉት ደሞ ምንድነው?" አለ ጥላሁን ፣ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ ።

"በዩጠረሲዛው እዩዞሩ እንግዶችን የሚያጫውቱ ባልና ሚስት አዝማሪዎች ስላሉ ፤ ለንሱ ሁሉም በነፍስ ወከፍ ሃያ አምስት ሳንቲም መክፈል ግዴታ ነው ። ከዚያ በላይ መክፈል ግን ከልክል ነው።"

"እንዴት ጥሩ ነው !" አለች ሰፊያ ።

"ለዚህኮ ነው ከያገሩ የሚመጣው ሁሉ እዚህ የሚሰበሰበው ! አዝማሪዎች የእንግዶችን ስም ባያውቁም ፤ ብዙች ከዩጠቅላይ ግዛቱ መምጣታቸውን ስለሚያውቁ ፤ እንዲሁ በድምሩ የጠቅላይ ግዛቶችን ስም እያነሱ ሲያወድሱ ፤ ከንግዶች መሀከል እንደ ኢትዮጵያ ስራት ፣ ግጥም መስጠት የሚፈልጉም እዩገጠሙ ላዝማሪዎች ሲሰጡ ጭዋታው ደስ ያሰኛል ። ስለዚህ ፤ ኢትዮጵያ ቡና ቤት ምግብ ብቻ ሳይሆን ጭዋታ ጭምር በመጠነኛ ዋጋ የሚገኝበት በመሆኑ ፣ በተለይ የገጠሬዎች መሰብሰቢያ ነው" አሉ አቶ ዮሴፍ ።

እውነትም ኢትዮጵያ ቡና ቤት ፤ ስሙ ቡና ቤት ይባል እንጂ አዲስ ከተማ ከሚገኙት አይነተኛ ሆቴሎች ሁሉ ብልጫ ያለው ነው ። የመጀመርያ ስሙ መርካቶ ቡና ቤት ነበር ፤ በሁዋላ ፣ ከኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች በልዩ ልዩ ምክንያቶች አዲስ አበባ የሚሰበሰቡት ሰዎች የሚያዘወትሩት መሆኑ ሲታወቅ ፣ ኢትዮጵያ ቡና ቤት ተባለ ።

ከውጪ ሲያዩት ጥራት አያምርም ። ጣሊያኖች ኢትዮጵያን በያዙበት ጊዜ ፤ በዚያ አካባቢ ለሀል ማጠራቀሚያዎችና ማደያዎች እንዲሆኑ ካሰሩዋቸው ህንጻዎች አንዱ ነው ። በሁዋላ ፣ አቶ ብናምነው መልካም የሚባሉ ነጋዴ ገዝተው ፤ ውስጥ ለውስጥ የሚከፋፈለውን ከፋፍለው ፤ የሚቀጣጠለውን ቀጣጥለው ሆቴል አደረጉት ። አቶ ዮሴፍና እነ ጥላሁን ፣ ሴሲቱን መጓዝ ስላለባቸው ፣ በጊዜ ራት በልተው ለመተኛት ፤ ወደ ምግብ ቤት ሲገቡ ፤ ገና ብዙ ሰው አል ተቀመጠም ፤ አዝማሪዎች ፤ ዘለቅ ጎላና ትሁኔ ብቻ ጥግ ይዘው ተቀምጠው ፤ ጠጅ እዩጠጡ ገብያ እስኪደራ ይጠብቃሉ ። በዚያ ክሶ ስት መቶ የማያንስ ሰው ባንድ ጊዜ ሊያስቀምጥ በሚችል ሰፊ አዳ ራሽ ፤ አረንጉዋዴ የገበታ ልብስ የለበሱ የምግብ ጠረጴዛዎች መስ መር መስመራቸውን ይዘው ተደርድረው ፣ በላያቸው ሽልምልም የወ ረቀት ፎጣ የተሰኩባቸው ብርጭቆዎች በክብ በክብ እዩሆኑ ተቀም ጠው ፤ መጀመርያ ጊዜ ከውጭ የሚገባ ሰው ሁሉንም ባንድነት ሲያይ፣ ብዙ ባለልዩ ልዩ ቀለም ያበባ መደቦች ወዳሉበት ያትክልት ቦታ የገባ

@OLDBOOKSPDF

እንጂ ፣ ወደ ምግብ ቤት የገባ አይመስለውም ! ሶፊያ ገና ስትገባ ካዳራሹ ትልቅነትም ሌላ ፣ የጠረጴዛዎችንና የብርጭቆዎችን ያቀማመጥ ስራት ፣ ከገበታ ልብሶችና ከወረቀት ፎጣዎች የቀለም መስማማት ጋር አይታ ፣ ያስተናባሪዎችን ምርጫ ታደንቅ ጀመር ። ከራታቸው ጋር አቶ ዮሴፍ ጠጅ ፣ ሶፊያና ጥላሁን ብርዝ አዘው ሲበሉና ሲጠጡ ትንሽ እንደ ቆዩ ፣ ሰዉ እዬተከታተለ ገብቶ አዳራሹን ሞላው ። ወዲያው ዘለቀና ትሁኔ አደግድገው ቆመው ዘለቀ ቅኝቱን ለማስተካከልም፣ ሰሚዎችን ለማስጠንቀቅም መሰንቆውን በወፍራም ፣ በመሀከለኛ ፣ በቀጭን እያለዋወጠ ሲገዘግዝ ቆዩና ትሁኔ በመሰንቆው ታጅባ ፣ በጊዜው ባላፍላ የነበረውን ፣ "ሰመመኔ" የተባለውን ዘፈን መዝፈን ስትጀምር ባዳራሹ ጸጥታ ሰፈነ ።

"ትሁኔ ያፍዋ ቅድ ጠባብ ቢሆንም ከንፈሮቹዋ ወፈር ፣ አፍንጫዋ አጥር ብለው ክብብ ያለ ፊት ፣ ጥቃቅን አይኖችና ጥሩ ዞማ ጠጉር ያላት ፣ ሰዎች ፣ "የደም ቡዳት" የሚሉዋት ፣ በጣም ደስ የምትል ፣ ትንሽ ውብ ፍጥረት ናት ። ከዚያች ትንሽ ፍጥረት የሚወጣው ድምጽ ግን ማንንም ልብ ብርቱ ፣ ማንንም ልበ ደንዳና ማርኮ ለማስርና ፣ አዝዞ ለማስጨፈር ልዩ ሀይል የተሰጠው ነው ። ስትዘፍን ከድምጽዋ ስብር ጋር ተስማምቶ ከፍ ዝቅ ፣ ሳብ ገፋ እያለ የሚወርበው ሰውነትዋ ተመልካቹን ሁሉ ሳያውቅ ፣ አለውዱ ፣ ከሰዋ ጋር ይወዘውዘዋል ፤ እንደሰዋ ያስወርበዋል ።

"ሰመመኔ ፤ ሰመመኔ"

"እባክህ ስለግዜር ፣ እንቅልፍ አትከልክለኝ ፣ ወግድልኝ ካይኔ" ስትል ፣ እውነት ሰመመን ፣ እንደ ያዛት እንገትዋን ዘንበል አድርጋ ፣ አይኖችዋን እያስለመለሙችና ፣ እንቅልፍ የከለከላትን ሽጋ ካይንዋ ፊት እንደምታባርር እጅዋን እያራገበች ፣ ያዳራሹ ሰው ሁሉ እጁን እንደሰዋ እያራገበ ያወካ ጀመር ። ውካታው ጸጥ ሲል ፣

"ሰመመኔ ፤ ሰመመኔ ፤
"እባክህ ጡር ፍራ ፣ ወግድልኝ ካይኔ ፤
"ሰመመኔ ፤ ሰመመኔ ፤
"አንተ እርፈህ ተኝተህ እንቅልፍ አጣሁ እኔ ።
"ሰመመኔ ፤ ሰመመኔ ፤

"እባክህ ስለግዜር ፣ በህልሜ አትምጣብኝ ፣ ላላገኝህ በውኔ" አለች ፣ ሆድ ቁርጠት እንዳመማት እምሽክ ፣ ድቅቅ እያለች ።

@OLDBOOKSPDF

ከዚያ ዘለቀ [illegible] አስተካክሎ ፣ ዜማውን ሲለውጥ ትሁኔም "ሰመመኔን" ትታ ከዬጠቅላይ ግዛቱ የመጡትን ሰዎች በድምር ለማ ሰደሰት ፣ በያገራቸው ማወደስ ጀመረች ።

"ወሎ የበቀለ እንደዚህ ማማሩ ፤
"ከቶ ከውሀው ይሆን ? ወይንስ ካፈሩ ፤
"በጥብጨ ልቀባው የወሎን አፈር ፤
"እንደ ወሎዎቹ ምናልባት ባምር ።
"ታናሽና ታላቅ ፣ ሻኛና ፍሪንባ ፣ ምልቶለት ከቤቱ
"ምነው ያ ጎንደሬ ልብ ሰርቆ መብላቱ ?
" ጎንደሬ ኩሩ ነው ፤ ጎንደሬ ጭዋ ነው ፤ ለምን ትላላችሁ ?
"የሰው ልብ ሰርቆ ሲበላ እያያችሁ ?
"ፍቅር ካገር ጣፋ ፤ ፍቅር ተወደደ ፤ አወጣ ሚሊዮን ፤
"የፍቅር አመለኛ ፣ የኔ ቢጤ ድሀ ፣ ምን ይውጠው ይሆን ?
"ስልቻዬን ይዤ ፣ ልሂድ ወደ ጎጃም ፣ ፍቅር ልሸምት ፤
"እዚያ ነው አገሩ የሚበቅልበት ፤
"እዚያ ነው አውድማው የሚመርትበት ።
"በግሬ ቆሜ እዬሄድሁ ሳለሁ በሕይወቴ ፤
"አስማተኛ ሸዋ ፣ አውጥቶ ወሰደው ልቤን ከደረቴ ።
"ተው እባክህ ማረኝ ፣ አንት የትግሬ ጀግና ፣ የሚያደንቅህ ሁሉ፤
"ምን ያደርግልሀል ፣ እኔን ደካማዋን ቤት ማርኮ መግደሉ ?
"ሰዎች ስለእግዚአብሔር ፣ ያን የሀረር ቆቱ ፣ ማልዱኝ እባካችሁ ፤
" ልቤን ማርኮ ወስዶ ፣ ግብኔን የምሄድ ፣ በድን ሆንሁላችሁ ።
"እሱን ካላገኘሁ ሌላ እንድወድበት ፤
"ፈትቶ ይላክልኝ ልቤን ካሰረበት ።
"አንት የወለጋ ልጅ ፣ ጨካኝ አረመኔ ፤
"ገድለኸኝ አትቀርም ፤ በወንጀል ተከስሰህ ሳትሞት እንደኔ ፤
"አንተ እንደ ገደልኸኝ ፣ ለሞት መናዘዜ ፣ አይቀርም ምን ቢሆን፤
"እዚህ ባላገኝህ ፣ በወዲያኛው አለም አገኝህ እንደሆን ።"

"የዚህ ቤት ጭዋታኮ ሌሊቱን ያገባድደዋል ፤ በጊዜ ለመነሳት እንቅልፍ እንዳይጫጫነን ፣ ብትፈቅዱልኝ ራት እኔ ልከፈልና ወደዬ ምኝታችን ብንሄድ ይሻላል " አለ አቶ ዮሴፍ ። ነገር ግን ፣ ጥላሁን "አይታጣም" ስባለ ፣ አቶ ዮሴፍ የባልና ሚስትን ድርሻ ተቀብሎ ፣ የራሱን ጨምሮ ፣ እንዱን በሩቅ ቆሞ ይመለከት የነበረ አሳላፊ ጠቅሶ ሲከፍል ፣ አሳላፊው አፍሮ ባይኑ ማረፊያ እስኪያጣ ድረስ አትኩሮ ሲመለከተው ቆይቶ ፣

@OLDBOOKSPDF

"ይህን ሰው አውቀዋለሁ" አለ አሳላፊው ከሄደ በሁዋላ ።

"አሳላፊውን ?" አለ ጥላሁን ።

"አዎ አሳላፊውን ፤ ብቻ አይነተኛ ሥራው ሌላ ነው" አለ አቶ ዮሴፍ ሳቅ ብሎ ።

"ምን ?"

"ሁዋላ እነግርሀለሁ"

"እስቲ ግጥም ልስጥሽ ተቀበይኝ ፣ የኔ ልጅ" አሉ አንድ ካለባበሳቸውም ሆነ ካነጋገራቸው ከገጠር የመጡ የሚመስሉ ሽማግሌ ፣ ትሁኔ እንግዶቹን በያገራቸው ስታወድስ አቋዋርጠው ።

"ነገር በሆዴ ውስጥ ታፍኖ ሲነድ" አሉ ገጠሬው ፣ ዘለቅ መስንቆ ምቱን ፣ ትሁኔ ግጥምዋን አቋዋርጠው ሲጠብቁ ።

"ነገር በሆዴ ውስጥ ታፍኖ ሲነድ ፤
"አንጀቴ ተቃጥሎ ሲሆን ነው አመድ ፤
"እስቲ ልተንፍሰው ምናልባት ቢበርድ ።
"ግፍ ስለ ሰራብኝ ሀይለኛ ጠላት ፤
"ፍት ፣ ርት ፍለጋ ብሄድ ፍርድ ቤት ፤
"የፍርድ ግልብጦሽ እናቱን ጅራት ፤
"በኔ ተፈረደ ያመት እስራት ።
"ጨርሸ ስወጣ ያመት እስራቴን ፤
"ተወርሶ አገኘሁት በሙሉ ንብረቴን ፤
"ፈርሶ ፣ ውድም ብሎ አገኘሁት ቤቴን ፤
"እንዲህ ያል የግፍ ግፍ ተሰርቶ እማያውቅ ፤
"ለምን ተሰራብኝ ብዬ ብጠይቅ ፤
"ግፍ ሰሩብኝ ብሎ ትልቅ ሰው መክሰስ ፤
"ክብረነክ" ነው አሉኝ ፣ ከማሳሰርና ከማስወረስ አልፎ ለሞት የሚያደርስ ።
"የግዜር እንደራሴ እዚህ በመሬት ፤
"መንግስት ነው ብዬ በፍጹም እምነት ፤
" ወደሱ ብመጣ አቤት ለማለት
"እሱም ያጥቂ ረዳት ሆኖ አገኘሁት ።
"የመከራ ውዝፍ አለብኝ መሰለኝ ፤
"ያን ሊያስከፍለኝ ነው ወዲህ 'ሂድ ሂድ' ያለኝ " ብለው ሊቀጥሉ ሲሉ ገጠሬው ገጣሚ ፣

"ሰው ይፈልግዎታል" አላቸው ፣ አቶ ዮሴፍ ገንዘብ ሲከፍል አትኩሮ የተመለከተው አሳላፊ ጎንበስ ብሎ ።

@OLDBOOKSPDF

"ማንን ? እኔን ?" አለ ገጠሬው ፣ ጠጋ ብሎ ከሚያንጋግራቸው አሳላፊ መሸሽ እንደ ፈለጉ ፣ እንደ ተቀመጡ ወደሁዋላ ገለል ብለው።

"አዎ እርስዎን"

"ማን የሚባል ሰው ?"

"ስሙን አልነገረኝም"

"ማንን እፈልጋለሁ አለ ?"

"እርስዎን አልሁኮ !"

"ማን ብሎ ማለቴኮ ነው"

አሳላፊው ፣ ገጠሬው ለጠዬቁት መልስ በመስጠት ፈንታ ፣ ከኪሱ አንድ ነገር ሸሽጎ አድርጎ እያሳዬ ፣ ወደ ጆሮዋቸው ጠጋ ብሎ ለሩቅ ሰው በማይሰማ ድምጽ ትንሽ ካነጋገራቸው በሁዋላ ፣ የድንጋጤ መልክ እዬታዬባቸው ተከትለውት ወጡ ።

"እውነትም ገጠሬው ፣ የመከራ ውዝፍ ቀርቶዋቸው ኖሮዋል ፤ ያውና ሊያስከፍል ወሰዳቸው ፤ ሰውዬው ፖሊስ ነው" አለ አቶ ዮሴፍ ፣ ራሱን እዬወዘወዘ ።

"አሳላፊው ?" አለ ጥላሁን ፣ በመገረም ።

"እንሱ ሰውን ለማጥመድ ምን የማይሆኑት አለ ? ሁሉን ይሆናሉ።"

"ገጠሬው ምን አደረጉ ?" አለች ሶፊያ ።

"ማጥማቸው ሁሉ ባለስልጣኖችንና መንግስትን የሚያማርር ነውኮ! ልብ አላረግሽውም ?" አለ አቶ ዮሴፍ ።

@OLDBOOKSPDF

## ምእራፍ ፲፱

# ወልመራና በርፌታ

ሶፊያና ጥላሁን አፍላ እንቅልፍ ላይ እንዳሉ ፣ የበሩ መዝጊያ በሀይል ሰበ ተመታ ፣

“ማነው ?” አለ ጥላሁን ፣ ከንቅልፉ በርግጎ ተነስቶ ።

“የጎሬ መኪና አዬታንቲ ! ተነስተናል ፤ ተነሱ ! ” አለና ገብረ ሚካኤል ፣ እውስጥ ያሉት መለግት አለመስማታቸውን ለማረጋገጥ ያክል እንኳዋ ሳይጠብቅ ፣ እዬርጠ እንደ መጣ እዬርጠ ተመለሰ ።

“ ስንት ሰአት ነው ?” አለ ጥላሁን ፣ አዬታንቲው ያልሄደ መስሎት ። ከዚያ መልስ ስላጣ ፣ ሰአቱን ለማየት የራስጌ መብራቱን አበራ።

“አሁን ስንት ሰአት ሆኖ ነው የቀሰቀሱን ?” አለች ሶፊያ ፣ እንቅልፍ እያድቀሰቀሳት ።

“ ስምንት ተኩል ” አለ ጥላሁን ።

“በዘጠኝ ሰአት ነው የምንነሳ አላላችሁም ነበር ?”

“ ዘጠኝ ሰአት መንገድ የምንይዝበት ይሆናል ! ”

ጥላሁንና ሶፊያ ቶሎ ተነስተው ፣ የብርድ ልብሳቸውን ተከናንበው ፣ ትናንሽ ሻንጣዎቻቸውን እያንጠለጠሉ ፣ ካሚዮኑ ባለበት ሲደርሱ ፣ አቶ ዮሴፍ ቀደም ብሎ እካሚዮኑ ውስጥ ገብቶ መሪውን ይዞ ተቀምጦ ነበር ።

“የጭነት መኪናን የጎማ ጤና ለመጠበቅ በቀዝቃዛ መሄድ አስፈላጊ በመሆኑ ፣ እንቅልፍ ሳትጠግቡ ስለ ቀሰቀስናችሁ ይቅርታ አድርጉልን ፤ ቢሆንም እንክሳችሁዋለን ። ከታች ለስሚንቶው ቅዝቃዜ መከላከያ ፍራሽ አንጥፈንላችሁዋልና ፣ በብርድ ልብሳችሁ ላይ ሸራውን ደርባችሁ ፣ የቀራችሁን እንቅልፍ መጨረስ ትችላላችሁ ” አለ ፣ አቶ ዮሴፍ ባልና ሚስቱ ሰላምታ ሲሰጡት ።

“ እግዜር ይስጥልን ” አለ ጥላሁን ።

“አብሮ ይስጠን ። በጀርባ መሰላል አለላችሁ ፤ በሱ ወጥታችሁ ምንጣፉችሁን የምታገኙት ወደ ግንባር ነው ፤ የመድሀኒት ሳጥናችሁም እዚያ ነው ። ”

@OLDBOOKSPDF

“ ከግንባር . . ከፀሩ መሆኑ አይሻልም ? ” አለች ሶፊያ ፤ ምናልባት አደጋ ቢደርስ እዳር ከመሆን መሀከሉ የሚሻል ስለ መሰላት።

“ ሽራ ደርባችሁ የምትፈልጉትን ያክል እዩር ለማግኘት የምትችሉ በግንባር ፤ ወይም በሁዋላ ፤ እዳር ላይ የሆናችሁ እንደሆነ ብቻ ነው ። ሽራ ደርባችሁ እመሀል የሆናችሁ እንደሆነ እዩር አታገኙም ፤ ትታፈናላችሁ ። የሁዋላው ዳር ደግሞ . . . በተለይ በመጥፎ መንገድ ላይ ያንጥራል ፤ አትችሉትም ። ስለዚህ . . ከሁሉም የሚሻለው ግንባሩ ነው ” አለ አቶ ዮሴፍ ።

ሶፊያና ጥላሁን ፤ በካሚዮኑ ሁዋላ ተጣብቆ በቆመው መሰላል ወጥተው ፤ በግንባር በተነጠፈላቸው ፍራሽ ላይ ያን የስሚንቶ ከዳን ወፍራም ሽራ ደርበው ሲተኙ ፤ አቶ ዮሴፍ ባደረበት ክፍል የረሳው ነገር ኖሮ ፤ ከካሚዮኑ ወጥቶ ወደ ሆቴል ተመልሶ ገባ ።

ጨለማው ገና እንደ ከበደ ነበር ። ይልቁንም ሌሊቱ ደመናማ ስለ ነበረ ፤ ጨለማውን ደብለስ አክብዶት ነበር ። ያ ጥቁር ደመና ደርቦ ምድርን ከጽንፍ እስከ ጽንፍ የተጫነው ጥቁር ጨለማ ፤ ያዲስ አበባን ህዝብ በሙሉ አንቆ ፤ አስጨንቆ ፤ እንደ ያዘው ሁሉ ፤ ያን ትናንት ባስራ አንድ ሰአት ፤ ንግስቱን እንደሚፈልግ የንብ ሰራዊት እዩተደራረበ ይታመስ እንደተራመሰ ፤ የነበረውን አዲስ ከተማ ህዝብ በሙሉ እፍን ድፍን እያደረገ እንደ ያዘው ሁሉ ዝምታው ፤ ጭልታው ያስፈራ ነበር ! መላ አዲስ አበባ የሚተነፍሱ ፤ የሚንቀሳቀሱ ፤ ህያዋን ነፍሳት የማይኖሩባት ፤ የሙታን አለም ፤ እንደሆነች ሁሉ ፤ ዝምታው ፤ ጭልታው ፤ ልብ ያባባ ነበር ! የሰማይ ከዋክብት እንኳ ፤ ሁሉም ተሸሽገው ፤ አንዳንዶቹ ብቻ የተሸሸጉበትን የደመና መጋረጃ በትንሹ ገለጥ አድርገው እያመለቁ ዘቅዝቀው ሲያዩ ፤ ያን በሲኦል ግርማ ወርዶ ያዲስ አበባን ህዝብ ተጭኖና አፍኖ ዝም ያሰኘ ጉግማ ጨለማ የፈሩ ይመስሉ ነበር !

“ የውጪ ጨለማ ከቤት ጨለማ የተለዩ ነው ? እዚህ ያስፈራል ! ” አለች ሶፊያ ፤ ያ አዲስ አበባን የሙታን አለም ያስመሰለ ጨለማ እንደ ፍርሀት ያለ ነገር በልብዋ ፈጥሮ ።

“ ጨለማው ያው ነው ፤ ብቻ እውጪ አድረሽ ስለማታውቂ ፤ እንግዳ ነገር ሆኖብሽ ነው ፤ አይዞሽ ! ” አለ ጥላሁን ።

“ ደግሞ ሁሉም ዝም ማለቱስ ? ዶሮ እንኳ ለምን አይጮህ ? ”

“ ዶሮ የሚጮህበት ጊዜ ምናልባት አልፎ እንደሆን ! ”

@OLDBOOKSPDF

አቶ ዮሴፍ ተመልሶ ፣ ኢካሚዮኑ ውስጥ ገብቶ ሞተሩን ሲያስነሳ ፣
ካሚዮኑ በሌሊት ከንቅልፉ በመቀስቀሱ እንደ ተቆጣ ሁሉ ፣ በሀይል
"እርርር!" አለና ፣ እዘያው በቆመበት እንዳለ ሲያጉረመርም ፣ ሲያ
ኩተመትም ብዙ ቆዬ ። ከዚያ አቶ ዮሴፍ ቀስ እያለ ፣ እያባባለ
መንገድ ሲመራው ፣ እንዲሁ በዝቅተኛ ድምጽ እያጉረመረመ ፣ እያን
ጎራጎረ ፣ ሲሄድ ቆይቶ ፣ የወሊጋንና የኢሉባቦርን አውራ ጎዳና እንደ
ያዘ ፍጥነቱ እዬጨመረ ፤ እዬጨመረ በሄደ መጠን ፣ ያካባቢው ዝምታ
የሱን ድምጽ ብዙ እጥፍ ጊዜ ስላጎላለት ፣ የውሎ መንገድ እስኪሰማ
እያጉራራ ይነጉድ ጀመር ! ከዚያ ልክ እንደ ሞተር መጋዝ ፣ "እርር
ርም ፣ እርርርርም ፣ እርርርርም !" እያለ ፣ ያን በሬቱ የተዘረጋ ከባድ
ጨለማ እየሰነጠቀ ፣ ካዲስ አበባ ወጥቶ ፣ የገፈርሳን ኩሬ ዞሮ ፣ መና
ገሻ መንደር ደረሰ ። ከዚያ ቀጥለው ያሉት በርፈታና ወልመራ
ናቸው ።

በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ልማድ ፣ በቤተክርስቲያን አጠገብ ሲታ
ለፍ ትንሽ ቆም ብሎ ሳያማትቡና ሳይሳለሙ ማለፍ አይገባም! ቤተ
ክርስቲያን ክርስቲያኖች እዬተሰበሰቡ ፣ ክርስቶስ የሰውን ዘር ከሲኦል
ግዛት ነጻ ለማውጣት ራሱን መስዋእት አድርጎ መስጠቱን ፣ ለሰው
ዘር ቤዛነት በመልእልተ መስቀል ሲጋው እንዲቆረስና ደሙ እንዲፈስ
መፍቀዱን ፣ በአክብሮ በእንክሮ የሚያስታውሱባት ፣ የተቀደሰች ፣ የተ
ባረከች ቦታ ናት ።

ወልመራና በርፈታም ፣ እንዲሁ የተቀደሱ ቦታዎች ናቸው ። ወል
መራና በርፈታም ፣ የኢጣሊያ ፋሽስቶች ኢትዮጵያን ወርረው ሕዝብ
ዋን በባርነት ቀንበር ሊጠምዱ በመጡበት ጊዜ ፣ ላገራቸው ነጻነት ራሳ
ቸውን መስዋእት አድርገው የሰጡ ሰማእቶችና ፣ በብርቱ ጠላታቸው ላይ
ድልን የተቀዳጁ ጀግኖች የሚታወሱባቸው የተቀደሱ ቦታዎች ናቸው።
ስለዚህ ፣ በበርፈታና በወልመራ ሲታለፍ ፣ አንድ አፍታ ቆም ብሎ ፣ እነ
ዚህ እተቀደሱ ቦታዎች ላይ ፣ ለኢትዮጵያ ነጻነት መስዋእት የሆኑትን
ሰማእቶችና ታምር የሰሩትን ጀግኖች ትንሽ አስታውሶ ፣ በአክብሮና
በእንክሮ ተሳልሞ ማለፍ ይገባል !

በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. የፋሽስት ጦር የኢትዮጵያን ሠራዊት በሰሜንና
በደቡብ ድል አድርጎ ፣ በሚያዝያ ወር መጨረሻ ግድም አዲስ አበባ
ሲገባ ፣ ከጦር ሜዳ ከተመለሱትና አዲስ አበባ ከቆዩት መሀከል ፣ መን
ፈሳቸው ድል መመታትን ያልተቀበለ ፣ ልባቸው መሸነፍን የተጸየፈ፣
ኢትዮጵያውያን ትግላቸውን ለመቀጠል በዱር ፣ በገደል ተሰማሩ ! ለነ

@OLDBOOKSPDF

ዚያ አርበኞች ፣ ለኒያ ልበኩሩ ጀግኖች ፣ ድል መሆን የሚንዳንዳቸው ነፍስ ከስጋቸው እዬተለዩች ስትሄድ ብቻ ነበር! በኒያ ልበኩሩ ፣ በኒያ መንፈሰ ጽኑ ጀግኖች ዘንድ ፣ ነፍስና ስጋቸው አብረው እያሉ የጠላትን ድል አድራጊነት ተቀብሎ ለጠላት መታጠቅ ፣ ለጠላት ባሪያ መሆን ፣ ፍጹም የማይታሰብ ነበር!

በወልመራ ፣ በመናገሻ አካባቢና በሜጫ ተሰግርተው የጠላትን እንቅስቃሴ የሚጠባበቁ አርበኞች ፣ ወሊጋንና ኢሉባቦርን የሚይዘው የፋሽስት ሰራዊት በዬቀኑ ካዲስ አበባ እዬተነሳ ፣ ሆለታና አዲስ አለም እያረፈ ፣ ወደ ምእራብ ሲጉዋዝ እዬተመለከቱ ፣ የሚያጠቁበት ዘዴ ይፈልጉ ፣ ያጠኑ ነበር ።

ሆለታና አዲስ አለም ፣ ባዲስ አበባና በምእራብ መሀከል ለሚጉዋ ዘው የፋሽስት ሠራዊት ፣ ለጦርነት ጊዜ መሳፈሪያና መረማመጃ ጣቢያ ዎች ከመሆናቸውም ሌላ ፣ ባካባቢያቸው ብዙ እህልና ከብት ስላለ ፣ ለዘለቃው የምግብ ማሰናጃዎችና ማከፋፈያዎች ጭምር እንዲሆኑ የጠ ላት ድርጅት ተጀምሮ ነበር ። ታዲያ ይህን በሜታና በመታለያ ክፍል ያሉት አርበኞች ስለሰሙ ፣ በነዚህ በሁለቱ ጣቢያዎች ያለውን የጠ ላት ጦር ለመምታትና ፣ የተጀመረውን ድርጅት በውጥኑ ለማበላሸት ስለ ፈለጉ ፣ እዚያ አካባቢ የነበሩትን ፣ አንድ ብዙ ተከታይ የነበራቸው ፊታውራሪ አርበኛ ፣ እንዲመሩዋቸው ሄደው ጠዬቁዋቸው ።

"መቸም ሆለታንና አዲስ አለምን ባንድ ጊዜ መምታት እንችል! አቅማችን አይፈቅድም ። ለመምታት ከቆረጥን ፣ በልዩ ልዩ ጊዜ ፣ አንድ ባንድ ፣ መምታት አለብን ። መጀመሪያ ሆለታን መምታት ነው። የሆለ ታን ጦር ሳይጠነቀቅ ፣ አደጋ ጥለን ለማሸነፍ እንችል ይሆናል ። የማን ችለው ካዲስ አበባ ለርዳታ የሚመጣውን ጦር ነው" አሉ ፊታውራሪ ፣ አሳቡ ቢማርካቸውም ፣ አደገኛ መሆኑን በሚገልጽ ፊት ።

"ጌታየ የሆለታን ጦር ለመምታት ከተስማሙ ፣ ካዲስ አበባ ለርዳታ የሚመጣውን ጦር እኔ እግደዋለሁ ! "አለ የመታለያ ክፍል አርበኞች ወጣት መሪ ። ወጣቱ መሪ እጅግ ግፋ ቢል ሰላሳ አሙት ቢሆነው ነው!

"እንዴት አድርገህ ?" አሉ ፊታውራሪ ፣ የወጣቱን ቃል ማመን ያቃታቸው መሆኑ ከፊታቸው እዬታዬ ።

"የሆለታን ወንዝ ድልድይ ካፈረስነው ፣ ታንክና ብረት ለበስ . . . ወታደር መኪና ሊሻገር አይችልም ። ከዚያ በሁዋላ . . . የፈረንጅ እግ ረኛ ጦር ምንም ቢሆን አያሸንፈንም! " አለ የሜታና የመታለያ አር በኞች ወጣት መሪ ።

@OLDBOOKSPDF

"ስንት ሰው [illegible] ፊታውራሪ ፤ የወጣቱን በራሱ መተማመን ልባቸው እያደነቀ ፤

"ዛሬ መቶ ባለጥሩ መሳሪያ አለኝ ፤ ነገ ሁለትም ፤ ሶስትም መቶ አሳጣ "

"ታዲያ እውነት ነገ ጥዋት ድልድዩን እፍርሰህ ፤ ሌሊቱን መከላከያ ፤ እርድ አበጅተህ እድረህ . . . ጥዋት እዚያ ሶስት መቶ ወታደር ማሰለፍ ትችላለህ ?"

"እይጠራጠሩ ጌታዩ ! እንዲያው በጠቅላላው ፤ ካዲስ አበባ ለሚመጣው ርዳታ ምንም አይስጉ ፤ እሱን ለኔ ይተዉት !"

"ደግ እንግዲህ ፤ ነገ ልክ እሰባት ሰአት ላይ ፤ በምሳ ጊዜ ፤ እኔ ሆለታን እመታለሁ ፤ ብቻ ወሬው ቀድሞ ስራችን እንዳይበላሽብን እደራ!",

የመታሊያ እርበኞች መሪ ፤ "ካዲስ አበባ ለርዳታ የሚመጣውን ጦር ለማገድ እስከ ሶስት መቶ ሰው አለኝ " ያለ ፤ ፊታውራሪ ጀርባቸው ነጻ መሆኑን ሲያውቁ ያለስጋት ፤ እሳባቸው ሳይከፋፈል ፤ የሆለታን የጠላት ጦር እንዲመቱ ብሎ ነው እንጂ ፤ በውነቱ ከምሳ ሰው የበለጠ አልነበረውም ፤ ከዚያውም ቢሆን ፤ የሚበዛው ጥሩ ትጥቅ የሌለውና ፤ በጦር ያልተፈተነ ነበር ። ብቻ መቸም የወጣት ጀግኖች አይነተኛ ባህሪ ፤ "እናሸንፋለን እንጂ እንሸነፋለን " አለማለትና ፣ አደጋን ማየት አለመቻል ስለሆን ወጣቱ መሪ ድልድዩ ፎርሶ ብረት ለበስ መኪና እጦርነቱ ውስጥ የማይገባ ከሆነ ፤ የፈረንጅ እግረኛ ጦር ምንም ያክል ቢበዛ፡ "ያሸንፈን ይሆናል" ብሎ የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል እንኳዋ ስጋት እልነበረውም !

ፊታውራሪና የሚታው መሪ በተነጋገሩበት ቀን ማግሥት ፤ ወጣቱ መሪ እምሳ ያክል ሰው ይዞ ሄዶ ፤ ወደ ሆለታ የሚሄደውን መንገደኛ ሁሉ አግዶ ፤ የሆለታን ወንዝ የብረት ድልድይ ለማፍረስ ቢታገል ፤ ብጥቅ የማይል ሆነ ። ያ ድልድይ ያለ ድማሚት እንደማይፈርስ ቁርጡ ታወቀ ። ምን ይሻላል ? ወጣቱ መሪ ተጨነቀ ! ድልድዩ ካልፈረሰ ከሁለት ክፉ ነገሮች አንዱን መምረጥ ግድ ሊሆን ነው ። ፊታውራሪ ሆለታን ለመምታት ከቦታቸው ሳይነሱ ቶሎ ሄዶ ማቆም ፤ ወይም ጦርነቱን እስኪጀምሩ መቆዩትና ፤ በሁዋላ ከሳቸው ጋር ተደባልቆ ፤ ካዲስ አበባ ረዳት ቢመጣም ፤ ተከበብ ቢሆንም ፤ የሚመጣውን ሁሉ አብሮ መቀበል ! እግዚአብሄር ቢል ካዲስ አበባ ረዳት ሳይደርስ ስራቸውን ጨርሰው ወደ ጫካቸው ይመለሱ ይሆናል ። ከፊተኛው ያለ ጥርጥር የሁዋለኛው ማግረጫ ይሻላል ! ወጣቱ መሪ ባሳቡ ይህን ወስኖ ሳለ ፤ አንድ

@OLDBOOKSPDF

ሌላ አሳብ ድንገት ብልጭ አለበት ፤ በርፌታ! ወልመራ ውስጥ ፣ በር ፈታ ምንም አይነት ጦር ፣ በምንም ያክል ብዛት ቢመጣ ፣ ሊግገድ የማ ታብችል ! ጥሩ ማነቂያ በር ናት ። "እዚያ መሄድ ነው !" አለ ወጣቱ ባሳቡ ፣ ልቡን ያሞቀው የደስታ ጸዳል በፊቱ ወገግ ብሎ እዩታዩ ። ወዲያው የድልድይ ማፍረሱን ወሬ እንዳይናገር ታግዶ የቆዩው መንገደኛ እንዲለቀቅ ካደረገ በሁዋላ ፣ እቅዱን ለሰዎቹ ነግሮ ፣ ጊዜ ሳያልፍ በር ፈታ ለመድረስ ሩጫ ሆነ ። ካምሳው ፣ አስራ ሰባቱ ሩዋጮች ብቻ ፣ ከመሪያቸው ጋር ሊሮጡ ቻሉ ።

ፊታውራሪ በበኩላቸው ፣ ሆሊታ ያለው የጠላት ጦር ስለሚመታ በት ዘዴ ከወጣቱ መሪ ጋር ተስማምተው ከተለያዩ በሁዋላ ፣ በውስጣ ቸው የክፍል አለቆች የሆኑትን ጠርተው እንዲሰናዱ ነግረዋቸው ነበር። በነጋው ጥዋት ፣ የሰፈሩበት ሜካ በታምር ፣ በንጨት ፈንታ ሰው አብ ቅሎ አሳድጎ ፣ እንዳደረ ሁሉ እዚያ የሚታዩው ሰው ብቻ ሆነ ! ያ ፣ ሰው ሁሉ እያንዳንዱ ወደ ግጥሚያው ለመሄድ የሚነሳበት ጊዜ ረዝ ሞበት ፣ ሄዶ ለመግጠም ቸኩሎ ሲንቆራጠጥ ! በልጉዋም እንደ ተገታ ሎሌ ፈረስ በያለበት ሲቅበጠበጥ ! የተመልካችን ወኔ ይቀሰቅስ ነበር ! ያ ሰው ሁሉ እያንዳንዱም ፣ በዬጉዋዱም ፣ እዩሳቀና እዩፈነደቀ ፣ ትጥ ቁን ሲያሰማምር ፣ ደስታና ጭዋታ ወዳለበት ፣ ያመትባል ቦታ የሚሄድ እንጂ ሞት ወዳለበት ለመሄድ የሚሰናዳ አይመስልም ነበር ! ፊታው ራሪ ራሳቸው ፣ ሆሊታን መትተው ፣ እዚያ ያለውን የጣሊያን ወታደር ፈጅተው ፣ መሳሪያውን ማርከው ፣ ወደሜካቸው የመመለሳቸው ወሬ በሰፈው ሲነዛ ፣ በጣሊያኖች መሀከል የሚፈጥረው ፍራትና በኢትዮጵ ያውያን መሀከል የሚፈጥረው ኩራት እዩታያቸው ፣ የመነሻው ጊዜ እስኪደርስ ቸኩለው ፣ ሰአታቸውን በዬደቂቃው እያዩ ፣ ከወዲያ ወዲህ ይንቆራጠጡ ነበር ! በንዲህ ያለ አሆሁዋን ፊታውራሪና አርበኛ ሰራ ዊታቸው ወደ ግጥሚያው ለመነሳት በቋዋፍ እንዳሉ ፣ የድልድዩን መፍ ረስና ፣ የመታለያው ወጣት መሪ ጦር ተሰናድቶ ቦታ መያዙን አይቶ ለመምጣት የተላከው ፈረሰኛ ተመልሶ ደረሰ ። ፈረሱ አረፋ ደፍቆ ፣ በላብ ተጠምቆ ፣ ከላይ ከላይ ይሣትት ነበር !

"ታዲያስ እንዴት ነው?" አሉ ፊታውራሪ ፣ ቆም ብለው ፣ መላክ ተኛው ከፈረስ ወርዶ ወደሳቸው እዩሮጠ ሲመጣ ።

"ጌታዩ ፣ ምንም የለ" አለ መላክተኛው ።

"እንዴት ምንም የለ! ድልድዩ አልፈረሰም ?" አሉ ፊታውራሪ ደንግጠው ።

"አልፈረሰም ።"

"ያ ልጅ . . . @OLDBOOKSPDF ጦር መሪ እዚያ የለም ?"

"የለም ።"

"እዚያ በጭራሽ ሰው የለም ?"

"ከመንገደኛ በቀር ሌላ የሚታይ ሰው የለም ።"

እዚያ የነበረው እያንዳንዱ አርበኛ ፣ መላክተኛው ያመጣውን ወሬ ሲሰማ ፣ በኋ የጨበጠውን ድል መንጭቀው እንደ ወሰዱበት ተቆጥቶ፣ "ሄደን እንግጠምና የሆነው ይሁን !" እያለ ሲንጫጫ ብዙ ከቆዩ በሁዋላ ፣ ፊታውራሪ እንደ ምንም እንዲረጋጋና ጸጥ እንዲል አደረጉት ።

"ግሩም ነው ! 'ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም ' የሚሉት ደረሰኮ !" አሉ ፊታውራሪ ፣ ባጠገባቸው ለነበሩ ሽማግሌ አርበኛ ።

"እዎ ! ከልጅ ጋር ይጫወቱዋል እንጂ አይመካከሩም ! ከልጅ ጋር የመከረ ልጅ ይሆናል ፣ ጌታዬ !" አሉ ሽማግሌው አርበኛ ።

"የሱን ቃል በሙሉ እምነን ፣ መላክተኛ ልከን ሳናረጋግጥ ፣ አደጋ ብንጥልኮ ጉድ ልንሆን ነበር ! ምናልባት እንጃ ! እግዜር ይቅበለኝ እንጂ ፣ ያን ልጅ ጠረጠርሁትኮ !" አሉ ፊታውራሪ ፣ የሜታና የመታለያ መሪ ፣ ያን ያክል በማያወላውል አሆሁዋን ድልድዩን የሚያፈርስና ሶስት መቶ ሰው ይዞ ፣ ካዲስ አበባ የሚመጣውን ረዳት ጦር የሚያግድ መሆኑን ካረጋገጠላቸው በሁዋላ ፣ እቦታው ላይ እንኩዋ ባለመገኘቱ ጠርጥረውት ።

የሜታና የመታለያ መሪ በበኩሉ ፣ ካስራ ሰባት ተከታዮቹ ጋር ላባቸውን እዩጠረጉ ፣ ከሆለታ ድልድይ ሮጠው በርፈታ ሲደርሱ ሰባት ሰአት ግድም ነበር ። ሰባት ሰአት ሆለታ ያለው የጣሊያን ስራ ሰባት ሰአት ግድም ነበር ። ሰባት ሰአት ሆለታ ያለው የጣሊያን ስራ ዊት እዩተገዘናና ምሳ ሲበላ ፣ ፊታውራሪ ትናንት እንደ ተስማሙት አደጋ የሚጥሉበት ሰአት ነው ። ያ ሰአት አደጋውን ሆለታ በራዲዮ ላዲስ አበባ የሚያስታውቅበት ስለሆነ ፣ ካዲስ አበባ ለርዳታ የሚላከው ጦር እዚያ እስኪደርስ ፣ ገና ትንሽ ጊዜ ያስፈልገዋል ። ካዲስ አበባ ለርዳታ የሚላከው ጦር ቀድሞዋቸው በርፈታን ያለፈ እንደሆነ ፣ ሌላ የሚታገድበት ቦታ ስለሌለ ፣ የፊታውራሪ አርበኛ ጦር ተከብቦ የሚያልቅ መሆኑ እንደሚያስፈራራ ከፉ ቅዠት ፣ ፊት ፊታቸውን እብሩዋቸው ሲሮጥ ይታያቸው ነበር ። ስለዚህ ፣ ወጣቱ መሪና ተከታዮቹ ትንፋሽ እስኪያጥራቸው ፣ ወደ ውጭ በተነፈሱ ቁጥር ፣ የቀራቸው ትንሽ ትንፋሽ የሚያልቅ እዩ መሰላቸው አስር አስር ጊዜ ከጉሮሮዋቸው እዩመለሱ በምራቃቸው እዩዋጡ ሲሮጡ ፣ እግዜር ይመስገን ፣ የጠላት ጦር ቀድሞዋቸው በርፈታን ሳያልፍ ደረሱ ! ከንግዲህ ወዲያ ፣ ሆለታን የሚመታው ያርበኞች

@OLDBOOKSPDF

ጦር በምንም ሁኔታ አይከበብም ! ከንግዲህ ወዲያ ፣ እነሱ ሳያልቁ በር ፈታን የሚያልፍ የጠላት ጦር የለም ! እነሱን ጨርሶ በርፈታን ለማ ለፍ የሚችል የጠላት ጦር ሊመጣ አይችልም እንጂ ቢመጣ እንኳ፣ እንዲያ ያለው ጦር ፣ እነሱን ለመጨረስ የሚያስፈልገው ጊዜና ድካም እጅግ ብዙ ስለሚሆን ፣ ከዚያ በሁዋላ ሆለታ እስኪደርስ ፣ ያርበኞች ጦር ስራውን ጨርሶ ወደ ጫካው ይመለሳል !

ወጣቱ መሪ ይህን ባሳቡ እያሰላሰለ እሱም ፣ ጉዋደኞቹም ትንፋ ሻቻውን አጠራቅመው እንደ ልብ መተንፈስ ከቻሉና ፣ ትንሽ ካረፉ በሁዋላ ፣ ከሆለታ ድልድይ አብረዋቸው ሩጫ ከጀመሩት አምሳ አርበ ኞች የሚበዙት ስላልደረሱ ስጋት አደረበትና ፣

"ጎበዝ ! ወንድሞቻችን የሚደርሱልን አልመሰለኝም ! ጉድ እን ዳንሆን ቶሎ ቦታ ብንይዝ ይሻላል " አለ ።

"አስራ ስምንት ብቻ ነንኮ የኔ ጌታ ! አስራ ስምንት ሆነን ግይ ጨው የኢትዮጵያን ሰራዊት በሙሉ ድል ያደረገውን ጦር እንግጠም?" አለ አንዱ ።

"አስራ ስምንት ባገሩ ጫካ ውስጥ ብዙ ነወኮ ! ጠላት የማያው ቀውን መሸሻ ፣ መሸሸጊያ ፣ መውጫ ፣ መውረጃ ስለምናውቅ ፣ ይህ ሽሽ ጎሽ እዬተጫወትን ያደግንበት ጫካችን አጋልጦ ለጠላት ስለማይሰጠን፣ ይህ ሁሉ የኛ ረዳት ስለሆነ ፣ ከዚህ ሁሉ ጋር አስራ ስምንት ብዙ ነው!" አለ ወጣቱ መሪ ከስሜት ጋር ።

"ልክ ነው ! " አለ ጠያቂው ፣ ጥያቄው ልክ አለመሆኑን ቶሎ ተረ ድቶ ። "ልክ ነው ! " አሉ ሌሎችም እዬተቀባበሉ ። ወዲያው ቦታ ቦታ ቸውን ያዙ ።

ካዲስ አበባ ወደ ሆለታ ፣ ከዚያም ወደ ምእራብ የሚሄደው አውራ ጎዳና ፣ ከመናገሻ መንደር ወጥቶ የምእራብን አቅጣጫ እንደያዘ ትንሽ ከቀጠለ በሁዋላ ፣ ወዳንድ ጫካ የለበሰ ኮረብታ ሲደርስ ፣ ወደ ሰሜን ይታጠፋል ። ከዚያ በኮረብታውና ከኮረብታው በታች እንዲሁ ጫካ በለበሰ ገደላማ መሬት መሀከል ፣ የሰሜንን አቅጣጫ እንደ ያዘ ወዳንድ ትንሽ ሸጥ መሳይ እስኪደርስ በጠባቡ ያልፍና ፣ ሸጥዋን ተሻግሮ ፣ እን ደገና ወደ ምእራብ ይመለሳል ። ይህ ጎዳናው ከምእራብ ወደ ሰሜን ከሚታጠፍበት ጀምሮ ሸጥዋን እስኪሻገር የሚያልፍበት ቦታ ፣ ይህ ግራ ቀኙ ጫካ በለበሰ ኮረብታና ገደላ ገደል የታጠረ ጠባብ መተላለፊያ ፣ ይህ ነው አስራ ስምንቱ አርበኞች ከብዙና ከብርቱ የጠላት ሰራዊት ጋር በሚያደርጉት ትግል እንደሚረዳቸው ፣ አብሮዋቸው ተሰልፎ ከሀ

@OLDBOOKSPDF

ደበኛ ጠላታቸው ጋር እንደሚዋጋቸው ፣ በመሳሪያው ጥራትና በሰራዊቱ ብዛት በሚመካ ጠላታቸው ላይ ድል እንደሚያቀዳጃቸው ፣ እምነታቸውን የጣሉበት ቦታ ! ይህ ነው የበርሬታ በር !

ወጣቱ መሪ ፣ ካሰራ ሰባቱ አርበኞች ሰድስቱን ፣ ከሸጥዋ ላይ ፣ ከጎዳናው ከፍ ብሎ ፣ ማለት ከበሩ መውጫ ጀምሮ እስከ ኮረብታው አናት እስከ በሩ መግቢያ ፣ በግማሽ ክብ መስመር ዘርዘር ብለው ፣ ጫካ እዩ ለበሱ ፣ እንዲቀመጡ አደረጋቸው ። አራቱን እዚያው በበሩ አካባቢ በኑ በሩ ዛፎች ወጥተው ፣ እንዳይታዩ ቅጠል እዩለበሱ እንዲቀመጡ አደረጋቸው ። ስድስቱን በሁለት እኩል ከፍሎ ፣ ከበሩ መውጫ ፣ በሆለታ ግንባር ፣ ከጎዳናው ቀኝና ግራ ሸሽጎ አስቀመጣቸው ። አንዱን ፣ የጠላት ጦር ሲመጣ ከሩቅ የሚታይበት ፣ ከፍተኛ ቦታ ፈልጎ ፣ እዚያ ተሸሽጎ እንዲጠብቅና ሮጦ ተመልሶ እንዲያስጠነቅቃቸው ፣ ቃፊር አድርጎ ወደ ፊት ላከው ። ከዚያ ሁሉም በዩተመደቡበት ቦታ ፣ ሳይታዩ ፣ ጠላትን ማጥቃት የሚችሉ መሆናቸውን ዞሮ አይቶ ፣ ካረጋገጠ በሁዋላ ፣ ጦርነቱ ሲጀመር እሱ የሚሰጠውን ትእዛዝና ፣ እያንዳንዱ አርበኛ ሊያደርገው የሚገባውን አስጠንቶ ሲጠባበቅ ፣ ተኩስ ተሰማ ። የመጀመርያው ብዙ ሰዎች አከታትለው በተራ የተኮሱት ፣ የጠበንጃ ተኩስ ይመስል ነበር። ከዚያ የመትረዩስና የከባድ መሳርያ ተኩስ ተከተለ ።

"ወይ ወንድሜን ! ጌታነህን ገደሉት !" አለ የጌታነህ የቅርብ ጉዋደኛ ከተሸሸገበት በሮ ወጥቶ ።

"በያላችሁበት ርጉ ! ደመኞቻችንን የምንበቀል እዚህ ነው !" አለ መሪው ።

ጌታነህ ቃፊሩ ነው።

ቃፊሩ እንደ ታዘዘው ፣ ሳይታይ የጠላትን ጦር ከሩቅ ለማየት የሚችልበት ምቹ ቦታ ሲፈልግ ፣ ከፍተኛ ቦታ ሲያገኝ ግልጥ እዩሆነበት ፣ ጫካ ለበስ ቦታ ሲያገኝ ዝቅተኛ እዩሆነበት ፣ ከጉዋደኞቹ እዩራቀ እዩራቀ ሄዶ ፣ በመጨረሻ አንድ ገታ በብዛት በበቀለበት ሜዳ መሀል፣ ባጫጭር ቁጥቋዋጦ የተከበበ ጉብታ አገኘ ። እዚያ ከመቀመጡ ድንገት ካንድ ምእራፍ በማይበልጥ ርቀት ፣ እንደ ግመል ጉዋዝ ጅራት ካንገት ፣ አንገት ከጅራት ተቀጣጥሎ ፣ ካዲስ አበባ አቅጣጫ አውራውን ጎዳና ይዞ እዩተጎተተ የሚመጣ ነገር አዩ ። ያ ፣ ከግንባር ሲያዩት የግመል ጉዋዝ የሚመስል ነገር ፣ የጣሊያን ወታደር የተጫኑ የካሚዮን ጉዋዝ ነው። ከሩቅ የግመል ሻኛ መስሎ የሚታዩው ፣ በያንዳንዱ ግልጥ ካሚዮን ውስጥ ባንድ ላይ እጅብ ብሎ የቆመው ወታደር ነበር ። ወታደሩ

@OLDBOOKSPDF

ከቡተሳፈረበት ካሚዮን ፣ "ፋቼታ ኔራ ፤ ቤላ አቢሲኒያ" የሚባለውን፣ ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ሲወሩ ያወጡትን ዘፈን እዩዘፈኑ ያላንዳች ስጋት ይጉዋዙ ነበር ።

ቃሬሩ ፣ ሮጦ ሄዶ ጉዋደኞቹን ለማስጠንቀቅ ጊዜ የማይበቃው ፣ የጠላት ጦር የሚቀድመው መሆኑን ስላወቀ ፣ ሌላ የማስጠንቀቂያ ዘዴ ፈልጎ አገኘ ። በተኩስ ማስጠንቀቅ ! ... ጦርነቱን እዚያው መጀመር...! ከተሸሸገበት ቁጥቋጦ ሃያ ሜትር ያክል ራቅ ብሎ ፣ የገታ ሳር የሸፈነው የቀበሮ ጉድጉዋድ ስላዬ ፣ በጉንብሱ ሮጦ እዚያ ጉድጉዋድ ሲገባ ፣ ካንገት በላይ ያለ አካሉና ዘጠኝ ጎራሽ ረሽ ም ለበኑ ወጭ ቀሩ ። እንሱንም ቢሆን የገታው ሳር ሸፍኖዋቸው አይታዩም ነበር ።

የመጀመርያው ካሚዮን ግንባሩን አሳልፎ ጎኑን ሲሰጠው ፤ ጌታነህ ፡ "በስመ አብ" ብሎ ተኩስ ጀምሮ ፣ በሶስት ጥይት ሲስት ጣሊያኖች ከካሚዮኑ አውርዶ እስኪጥል ፣ ከነሱ ወገን አንድ ጥይት እንኩዋ አልተተኮሰም ! አደጋው ድንገት ስለ ተጣለባቸው ፣ በመሀከላቸው ድብልቅልቅ ሆኖ ፣ ልብ እስኪገዙ ትንሽ ጊዜ ወሰደባቸው ። ከዚያ የመትረዬስ ውሽንፍርና የፈንጂ ነጎድጉዋድ ከያቅጣጫው ጌታነህ መጀመርያ በተሸሸገበት ቁጥቁዋጦ ላይ ወርዶ ፣ ቁጥቁዋጦውን ከነበቀለበት ጉብታ ደብዛውን ሲያጠፋው ፣ ጌታነህ የሚልከው እያንዳንዱ ጥይት አንዳንድ ጣሊያን ከካሚዮኑ እዩዘነጠለ ያወርድ ነበር ! ለበኑ የጎረሰው ዘጠኝ ጥይት እስኪያልቅ ፣ በሚያስገርም ፍጥነት ዘጠኝ ጣሊያኖች እያወረደ ጥሎ ፣ እንደገና አንዳንድ እያጎረሰ ፣ በሶስት ጥይት ሶስት ጣሊያኖች አውርዶ ፣ የሬሳውን ቁጥር አስራ ሁለት አደረሰው ። ከዚያ በሁዋላ ፣ የተቀበረበት ጉድጉዋድ ባጠገቡ እንደ ነበረው ቁጥቁዋጦ ደብዛው ሲጠፋ ፣ ያንጊዜ የሱም ለበን ደምጽ ጠፋ ! የጌታነህ ለበን ዝም ካለ በሁዋላ ፣ ጣሊያኖች ጠበንጃና መትረዬስ ፣ ከባድ መሳርያም ሲተኩሱ ፣ ፈንጂ ሲወረውሩ ፣ ዘለግ ያለ ጊዜ ቆይተው ፣ የሚመልስላቸው ስላልነበረ፣ ብዙ ሆነው ሜዳውን እዩዞሩ የጠላቶቻቸውን ሬሳ ሲፈልጉ ፣ አንድ ጠመንጃ ብቻ እንጨቱ ሲነድ አገኙ ። በጠመንጃው አካባቢ ተበታትኖ የሚታዩው የሰውነት ፍርፋሪ ፣ የስንት ሰው መሆኑን ሊያስረዳ አይችልም !

መቸም አንድ ሰው ባንድ ጠመንጃ ፣ በዚያ አጭር ጊዜ ውስጥ ፣ አስራ ሁለት ሰው ሊገድል አይችልም ! አንድ ሰው ተኩሶ ፣ ቀለህ እስፈንጥሮ ፣ ጥይት አቀባብሎ ፣ እንደገና እስኪተኩስ ትንሽ ጊዜ ያስፈልጋል ! ያ ተኩስ ግን ብዙ ሰዎች በተራ እያከታተሉ የተኮሱት እንጂ ፣ ያንድ ሰው እጅ ፣ ባንድ ጠመንጃ የተኮሰው አይመስልም ! ብቻ እዚያ

@OLDBOOKSPDF

የተገኘው አንድ ጠመንጃ ብቻ በመሆኑ ፣ ጣሊያኖች ግራ ገብቶዋቸው፣ በተራ ሰበን ጠመንጃ ፣ እንዲያ ባለ ፍጥነት ፣ ተከታትሎ አስራ ሁለት ሰው የገደለ አንድ ሰው መሆኑን ማመን አቃታቸው ። ስለዚህ ፣ እስከ ተራራው ጥግ ሄደው ፈልገው የሰው ምልክት ሲያጡ ፣ ተመልሰው ያን ታምር ፣ ያን ትንግርት የሰራ አንድ ጀግና በመሆኑ ተገርመው ፣ የሰውነቱን ፍርፋሪ ሰብስበው ከቀበሩ በሁዋላ ፣ የክብር ሰላምታ ሰጥተው ፣ የደረሰውን አደጋና ሬሳ የሚያነሳ እንዲላክላቸው አስፈላጊ መሆኑን በሬዲዮ ላዲስ አበባ ካስታወቁ በሁዋላ ፣ ሬሳ ጠባቂ አንድ ሽምባሽ ወታደር ጋር ትተው ጉዞዋቸውን ቀጠሉ ።

የጉዋዙ ግንባር - ቀደም ካሚዮን ነጂ በርፈታ በር ኮረብታ ሲደርስ ፣ ጎዳናው ከምእራብ ወደ ሰሜን የሚታጠፍ መሆኑን ባሰር ሜትር ያክል ርቀት ስላዩ ፣ በተሽከርካሪ ደንብ ጥሩንባ ነፉ ። ለምጣቱን ለሚጠባበቁት ጥሩ ማስጠንቀቂያ ነው ! የወጣቱ መሪ ሰዎች በዮተመደቡበት ቦታ እንዳሉ ፣ ጣታቸውን በዮጠበንጃቸው ምላጭ ላይ አስቀምጠው ፣ ልባቸው በዮደረታቸው ውስጥ የሚመታው የሲታ ዳንኪራ ማታቸውን ሲያንቀጠቅጠው እንዳይተኩሱ አዩሰን ፣ መሪያቸው ሳይተኩስ እንዳይተኩሱ ታዝዘው ስለነበረ የሱን ርችት ይጠባበቁ ነበር ። ወዲያው ግንባር - ቀደሙ ካሚዮን ብቅ አለ ። ከዚያ ሁለተኛው ፣ ከዚያ ሶስተኛው ፣ ከዚያ አራተኛው ! የጀግኖች መሪ ምን ሆኑ ? ለምን አይተኩሱ! የመጀመሪያው ካሚዮን ሽጥዋን ሲሻገር ፣ በሩን ሲወጣ ፣ ምንም ያክል አልቀረው ! ደግሞ ያምስተኛው ካሚዮን አፍንጫ ታዬ ፣ ከምስተኛም በሁዋላ እንደነሱ የሚያስጎመዥ የወታደር ጭነት እስኪከብዳቸው የተጫኑ ገና ብዙ አሉ !

አምስተኛው ካሚዮን በሩን ገብቶ ፣ ግንባር - ቀደሙ በሩን ሲወጣ አምስት ሜትር ያክል ሲቀረው ፣ የጀግኖች መሪ ፣ “በስመ አብ ” ብሎ ተኩሱን ባረከ ፣ ርችቱን አሳዩ ! ወዲያው ፣ በግንባር የተሰለፉት ከፊቶቻቸውን በግማሽ ክብ መስመር ከበው የተሰለፉት ከጎን ፣ እዛፍ ላይ ያሉት ከላይ ከሰማይ ፣ እገደል ውስጥ ያሉት ከስር ፣ ሁሉም ባንድ ላይ ተኩሰው ብዙ ጣሊያኖች ሲጥሉ ፣ ጣሊያኖች ተኩሱ የመጣበት ልዩ ልዩ አቅጣጫ አደናግሮዋቸው ፣ ጠላታቸው ከሰማይ ይምጣ ከምድር ግራ ገብቶዋቸው ፣ ባላቸው መሳሪያ ሁሉ በበርፈታ ጫካ መደዳውን መእት አወረዱበት ። ጣሊያኖች ጠላቶቻቸው እዚያ በቅርብ ፣ አንዳንዶችም ካሰር ሜትር ባነሰ ርቀት መሸሸጋቸውን ሳያውቁ ፣ አላማቸው ከሰባና ከሰማንያ ሜትር ውጪ ነበር ። ጠላቶቻቸው በቅርብ መሆናቸውን እስኪያውቁ ትንሽ ጊዜ ፣ ምናልባት ያምስት ደቂቃ ጊዜ ወሰደባቸው ።

@OLDBOOKSPDF

በዚያ ጊዜ ያለቀው ጣሊያን እጅግ ብዙ ነው ። አንዳንድ አርበኞች የተሸሸጉበት ቦታ እንደ ታወቀ ፣ ብዙ የጅ ቦምብ ወደዚያ ተወርውሮ በዙሪያቸው ስለ ወደቀ ፣ ሁለቱ በቀላሉ ቆሰሉ ። ከዚያ የጣሊያኖች ምልክት ሰጪ ባለተዩ እርሳስ ፣ አመልካች ጥይት ተኩሶ ፣ እርሳሱ ቀይ ጅራቱን እየጎተተ ሄዶ በግንባር ያሉት አርበኞች ፣ መሪያቸው ጭምር በተሸሸጉበት አጠገብ ሲያርፍ ፣ እዚያ ያለው የጣሊያን መሳሪያ ሁሉ ያን አካባቢ ደብዛውን ለማጥፋት እፈሙዙን ወደዚያ ማዞሩን አይቶ ፣ "የካሚዮኑን የበንዚን ጋን !" እለ የጅግኖች መሪ ፣ ወደ ካሚዮኑ የበንዚን ጋን እንጣጥሮ ሲተኩስ በሀይል ጮሆ ። ወዲያው የመጀመሪያው ካሚዮን የነዳጅ ጋኑ በለ ተመታ ፣ እንደ ቦምብ ፈነዳ ! ከዚያ ሁለተኛው ፣ ከዚያ ሶስተኛው ! እሳቱ ጢሱን እስኪያሸንፈው ፣ ያን ጠባብ መተላለፍያ ጢስ ድፍን አድርጎ ስላፈነው ፣ ጣሊያኖች እንኳዋንስ ጠላቶቻቸውን ሊያዩ ፣ እስበሳቸው መተያየት ስላቃታቸው ፣ ብዙዎች ወደ ኮረብታውና ወደ ሜዳው ፎጠው ለመውጣት ሲሞክሩ ፣ አርበኞች እየተቀበሉ ፈጇቸው ።

በዚያ ጊዜ ፣ ጣሊያኖች ሜዳው ሁሉ ብዙ ሽህ የጠላት ጦር መኸን የሚዋጋበት መስሎቸው ፣ በጠባብ መተላለፊያ ውስጥ እንደ ታንኩ ጢስ አፍኖዋቸው ፣ መተያየት አቅቶዋቸው ፣ ይተራመሱ በነበሩበት ጊዜ ፣ ያን ጊዜ ነው የታፈሩ ፣ የጊታንህ የቅርብ ወዳጅ ፣ በላቸው ፣ የጠበንጃው ቃታ ስለ ነከሰበት ወዲያ አምዘግዝጎ ጥሎ ፣ ጎራዴውን መዞ ፣ ጣሊያኖችም ፣ እሰቃውም ሳያዩት እጠላቶቹ መሀከል የገባ ! በላቸውን ሲያይ ፣ ጉርሙም ጎራዴውን መዞ ተከተለው ። ሁለቱ ጀግኖች እጠላት መሀከል ገብተው የብዙ ጠላት ራስ ከቆረጡ በሁዋላ ፣ በጠላት መሀከል ድብልቅልቅ ፈጥረው እስበሱ በሳንጃ እንዲዋጋ ካደረጉ በሁዋላ ፣ አልተመለሱም ፤ እዚያው ቀሩ ! እሳቱ ወዳራተኛው ካሚዮን ተላለፈ ። አራተኛው ካሚዮን ጥይትና ቦምብ የተጫነ ስለነበረ ፣ ፈንጂው ከተያዘ በሁዋላ ፣ ፈንድቶ እስኪያልቅ ድረስ ፣ መሬት እንዳለች ተገልብጣ ማህለትች በሌለው አዘቅት የምትወርድ ይመስል ነበር ፤ ህልፈተ ዓለም የሆነ ይመስል ነበር !

"ቀን ሲከፋ ያሳደጉት ውሻ ይነክሳል" እንደሚሉት ፣ ያን እለት በጣሊያኖች ቀን ከፍቶባቸው ፣ የገዛ መሳሪያቸው ከጠላቶቻቸው ጋር ፣ ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋር አድሞ ፈጃቸው ! እበሩ ውስጥ ፣ እወጥመዱ ውስጥ ባልገቡት ካሚዮኖች ውስጥ የነበሩት እንኩዋ ፣ ተኩሱን ሲሰሙ፣ ከሁዋላ እዩሮጡ ሄደው እወጥመዱ ውስጥ እዩገቡ ሁለም አለቁ ።

@OLDBOOKSPDF

ከስራ አራት ወደ ወሊጋ ሲሄድ ካዲስ አበባ የተነሳ የካሚዮን ጉዋዝ ፣ አንዱ ስንቅ ፣ አንዱ ቦምብና ጥይት ፣ አስራ ሁለቱ ወታደር የተጫኑ ነበሩ ። በልማዱ ፣ "አንድ የወታደር መጫኛ ካሚዮን ሰላሳ ወታደር ከነመሳሪያው ይጭናል" ስለሚባል ፣ ያን እለት ባስራ ሁለቱ ካሚዮኖች ተጭነው የነበሩት ወታደሮች ሶስት መቶ ሰድሳ ያክል ነበሩ ማለት ነው ። ይህን ያክሉ እንኩዋ ባይሆኑ ከሶስት መቶ እንደማያንሱ አይጠረጠርም ። ከነዚህ የተረፉ አለመኖሩን ፣ እነዚህ ሁሉ ማለቃቸውን ፣ የተጫኑበትን ስንቅና ብዙ መሳርያ ፣ ያባንድ ተከካከይ የወልመራና የመኖትኛ ባላገር መከፋፈሉን ያስረዳል ። በዚህ አንጻር ካርበኞች ወገን ስድስቱ ሞተው ሁለቱ በቀላሉ ቢቆስሉ ፣ አስሩ ምንም ጉዳት አልደረሰባቸውም ።

ይህ በርሬሳ በር የተሰራ ታምር ፣ ይህ አስራ ስምንት አርበኞች አንድ ሙሉ ሆኖ የተደራጀ የጣሊያን ሰራዊት ከብዙ ካሚዮን ጋር ባጭር ጊዜ ውስጥ ፣ ወሬ ነጋሪ እንኩዋ ሳይተርፍ መጨረሳቸው ፣ በቅርብና በሩቅ ተሰፋፍቶ ሲነዛ ፣ በጣሊያኖች ልብ ያነደደውን ቁጣ ያክል በኢትዮጵያ አርበኞች ልብ የጀግንነት ሲቃ አንድዶ ፣ ጣሊያኖች የበርሬሳን ቂም ለመበቀል ፣ አርበኞች የበርሬሳ ድል በጀግንነት እንጂ በእድል የተገኘ አለመሆኑን ለማስመስከር ፣ እዚያው በርሬሳና ወልመራ ውስጥ ልክ በሳምንቱ ፣ እንደገና ገጠሙ ።

የሚጊታና የመታሊያ መሪ ፣ ፊታውራሪ ሆለታን በተቃጠሩበት ቀን ሳይመጡ በመቅረታቸው ተቀይም ፣ ከሳቸው ጋር እንደገና ስለ ጦርነት ነገር መመካከር አልፈለገም ። በዚያ ጊዜ ፣ ሚጫ ውስጥ አንድ ሌላ ያርበኞች መሪ ስለነበረ ፣ ምክሩን ከሱ ጋር አደረገ ። የሚጫው መሪ ፣ ከወንድሞቹና ካሽከሮቹ ሌላ ፣ የሚጫን አርበኞችና ከማይጨው የተመለሱ ቁጥራቸው በርከት ያለ ፣ የክብር ዘበኞች ይመራ ነበር ። ያዳበርጋና የወልመራ አርበኞችም ከሚጫው መሪ አርበኞች ጋር ተጨምረው ነበር ። ስለዚህ በሁለቱ መሪዎች መሀከል የነበረው ያርበኞች ጦር ከሶስት መቶ በላይ ቢሆን እንጂ አያንስም ። ጣሊያኖች ፣ ከሳምንት በፊት በጠፋባቸው ጦር ምትክ ፣ "ከዚያ የበለጠ ጦር ወደ ወሊጋና ወደ ኢሉባቦር እንልካለን" ብለው የውሸት ምስጢር ወሬ እንዲወራና ፣ ይህ የውሸት ምስጢር በዘዴ ወጥቶ ላርበኞች እንዲደርስ አድርገው ነበር ። አርበኞች የጠላት ጦር ያልፋል በተባለበት ቀን ፣ ከንጋቱ ቀደም ብለው ፣ ሳይታዩ ፣ ወደ ወልመራ ሄደው ፣ እዚያ አንጥፈው ይጠባበቁ ጀመር ። ሰባት ሰአት ሊሆን ትንሽ ሲቀረው ፣ ባዲስ አበባ ግንባርም ፣ በሆለታ ግንባርም ፣ የተላኩት ቃፊሮች እየሮጡ ተመልሰው ከየተላኩበት ወገን የጠላት ጦር መምጣቱን አስታወቁ ።

“እንደ ዛሬ ሳምንቱ ! የዛሬ ሳምንትም በዚህ ሰአት ነበር የመጡ” አለ የሚታው መሪ ሰአቱን አይቶ ።

@OLDBOOKSPDF

“ብቻ የዛሬ ሳምንት ፣ ጠላት እዚህ እንደሚጠብቃቸው ሰላላወቁ እንደ ዛሬ አልተጠነቀቁ ይሆናል ፤ ዛሬ ብርቱ ጥንቃቄ ሳያደርጉ አይቀሩም” አለ የሚጫ አርበኞች መሪ ።

“ዛሬ ጠላት እዚህ እንደሚጠብቃቸው ያውቃሉ ? ”

“ባያውቁ ይከቡን ኖሮዋል ? ካዲስ አበባና ከሆለታ ጦር ወዲህ መላካቸው መከበባቸውኮ ነው ! ”

“ከበው ምን ያደርጉናል ? እዚህ ጫካ ቢገቡ ተመልሰው እንደማ ይወጡ የታወቀ ነው ፤ ባዲስ አበባና በሆለታ ግንባር ከበው ቢቀመጡ ወደላይ ወደ ተራራው ፣ ወደታች ወደ ሸጡ ፣ ጫካ ለጫካ መገናኛው በኛ እጅ ነው ፤ ሰለዚህ ቢከቡን ፣ ባይከቡን ልዩነት ያለው አይመስለ ኝም !” አለ የሚታው መሪ ።

“ አሆ . . . ! እዚህ ጫካ ውስጥ እንዳለን መከበባችንስ መጥፎ ነው ፣ የኔ ወንደም ። ከዚህ እንዳንወጣ ከበው እዩጠበቁ ፣ በከባድ መሳሪያ በአይሮፕላንና በመርዝ ጫካውን ቢደበድቡ እዚሁ እናልቃለን ። ምና ልባት ያለውትሮዋቸው ዛሬ በዚህ አካባቢ አይሮፕላኖች መብዛታቸ ወም ለዚህ ይሆናል ። ምናልባት . . . ሁለት እቅዶች ይኖሩዋቸዋል ። አንዱ አሁን በቁጠርሁዋቸው መሳሪያዎች እዚሁ እንዳለን መደብደብ፣ ሁለተኛው . . . ጀግንነታቸውን ማሳዩት ፈልገው እንደ ሆነ ፣ ከዚህ ስበው አውጥተው ፣ እሚዳው ላይ በብረት ለበስ መውጋት ! ታዲያ ሁለቱም ለኛ አይመቹም ! ”

“እኛ ስበን ፣ አታለን እጫካው ውስጥ ብናገባቸውስ ?” አለ የሚ ታው መሪ ፣ ችንሽ ሲያስብ ቆይቶ ።

“እሱን ማድረግ ከቻልን ግሩም ነው ! እነሱን እጫካው ውስጥ ማግባት ከቻልን ፣ ያይሮፕላን ፣ የከባድ መሳሪያ ፣ ወይም የመርዝ ስጋት አይኖርብንም ። ያንጊዜ እነሱና እኛ ብቻ እንሆናለን !” አለ የሚጫው ጀግና ፣ ያለታንክና ያለአይሮፕላን ፣ ጣሊያን . . ለኢትዮጵያ ፣ ብቻ ለብቻ ሲገጥሙ የሚሆኑት ሁኔታ ሰለታዩው ፣ ሲታ ከተቀመጠበት ሲያነሳው ሲቃጣ እዩታዩ ።

አርበኞች ጠላቶቻቸውን ወደጫካው ውስጥ የሚስቡበትን ዘዴ ተመካከረው ፣ ወሰነው ፣ ቦታ ቦታቸውን ለመያዝ ሲጣደፉ ፣ ከሆለታ ወገን የጣሊያኖች ጦር ግንባር የመድፍ ተኩስ የሚመስል ነገር ተሰማ። ወዲያው ፣ አንድ በጣም የሚያምር ፣ ምላላ ፣ ሀምራዊ አለሎ ፣ ረኝም

@OLDBOOKSPDF

ሀምራዊ ጅራቱን [illegible] ሰንጥቆ ሳይን እስኪደቅ ሽቅብ ከወጣ በሁዋላ ፣ ባዩር ላይ የግልብጥብጦሽ ቅርኢዶት እንደሚያሳይ ፣ በቅጽበት አፍንጫውን ከላይ ወደታች ፣ ጅራቱን ከታች ወደላይ ፣ ገለ ባበጠና ፣ እንዲሁ ያን ረጅም ጅራቱን እዩንተተ ወርዶ በርፌታ ላይ አረፈ ። አርበኞች ያሉበትን ፣ ጠላት ያለበትን አመልካች መሆኑ ነው ። ወዲያው ካዲስ አበባ ከመጣው ፣ የጣሊያን ጦር ግንባር ፣ “ ድም ፣ ዥሩም-ዥሩም-ዥሩም ፣ ድም ! ” አለ የበርፌታን በር ያለመ የመድፍ እርሳስ ፣ ሁለት ጊዜ ተተኩሶ ፣ መጀመሪያ እርሳሱ በመድፉ ሀይል ከቀለሁ ሲወጣ ፣ ሁለተኛ አላማውን ሲመታ ነው ! “ደም ፣ ዥሩም-ዥሩም-ዥሩም፣ ድም !” አለ ሌላው ፣ ከሆለታ ግንባር ። ከዚያ ሳምስት ወይም ለስድስት ደቂቃዎች ያክል የመድፍና የልዩ ልዩ ከባድ መሳሪያዎች ነጎድጉዋድ በርፌታ በር ላይ ወረደ ! በርፌታና ባካባቢው ያለው ሁሉ ፣ ርጥብ ቅጠል ሳይቀር ፣ በፈንጂው ብዛት ተጋግሎ ነደደ ! ደግነቱ ከረምት ስለ ሆነ ታጠሉው ከዚያ ሊስፋፋ አልቻለም ። ከዚያ ያዲስ አበባና የሆለታ ጦር ግንባር አዛዦች እግረኛውን ሁሉ ከሁለት ወገን ወደ በርፌታ በር እንዲገባ ትእዛዝ ሰጡ ። ነገር ግን እዚያ ምንም አልተገኘም ! ከዚያ በቁጣ ከመንገዱ በላይ ፣ ጫካው እስከ ተራራው እንዲበረበር አዘዙ ። የዛሬን እያርገውና የጫካው መዘጋና አጥምጣም እሰበሱ ተቆላልፎ ፣ ባንድ ላይ ተማግሮ ፣ የተሰራ የሚመስል ፣ ካንድ አቅጣጫ ወደ ሌላ እንደ ልብ መዘዋወር የማይቻልበት ፣ አልፎ አልፎ በሚገኙት ያውሬ ዎችና የረኞች መሽሎክለኪያ ትናንሽ መንገዶች እንኳ አጎንብሶ ፣ ያውም በተራ ካልሆነ ፣ ቀና ብሎ ጎን ለጎን መሄድ የማይሞከርበት በጣም አስቸጋሪ ጫካ ነው ። ያ ጫካ ላልለመደውና ላላወቀው ፣ እንደ ሜታና መታለያ አርበኞች ፣ ድብብቆሽ እዩተጫወቱ ላላደጉበት ፣ እንኩዋንስ የተሸሸገን ፣ ያለበትን ጠርቶ የነገረን ሬሳን ማግኘት የማይቻልበት ፣ አስቸጋሪ ጫካ ነው ! በዚያ አስቸጋሪ ጫካ ፣ በዚያ እጅ እግር አሳስሮ ለጠላት በሚሰጥ ወጥመድ ውስጥ ፣ ከስምንት መቶ እስከ ሺህ የሚሆን የጣሊያን እግረኛ ጦር አርበኞችን እንዲፈልግ ታዝዞ ገባ ! ይህ ነበር አርበኞች የተመኙት ! ይህ ሆኑላቸው ! እዚያ የነበረው የጣሊያን እግ ረኛ ጦር ካዛዦቹና ከባለከባድ መሳሪያዎች በቀር አንድ ሳይቀር፣ እስከ መጨረሻው ወታደር ገብቶ ካበቃ በሁዋላ ፣ እንዳይመለስ በር ለመዝ ጋት የተመደቡት አርበኞች መመለሻውን ዘግተው ተኩስ ከፈቱ ። ጊዜ ባለፈ መጠን ፣ ተኩሱ የጣሊያን ጦር አዛዦች ትእዛዝ ከሚሰጡበት ቦታ እዩራቀ ፣ ወደጫካው ውስጥና ወደተራራው ስር እዩጠለቀ ሲሄድ፣ እዚያ ውስጥ የጦርነቱ ሁኔታ እንዴት እንደሆነ መረጃ የሚያመጣ

@OLDBOOKSPDF

ቸው ጠፍቶ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው መወሰን አቃታቸው ። ከስምንት መቶ እስከ አንድ ሺህ የጣሊያን ጦር የገባበትን ጫካ ባይሮፕላንና በከባድ መሳርያ መምታት ፣ ወይም በጫካው ላይ መርዝ መጣል የማይቻል መሆኑን ሲያዩ ፣ ያንጊዜ ብቻ ፣ ሁለቱ የጣሊያን ጦር አዛዦች መጀመሪያ በቁጣ ተገፍተው የሰጡት ትእዛዝ ትክክል መሆን አለመሆኑን መመርመርና ብርቱ ጥፋት ማጥፋታቸውን ፣ ምህረት የማያገባቸው ባለዳዎች መሆናቸውን ተረድተው ፣ በራሳቸው ፈርደው ፣ እዳቸውን ለመክፈል ወሰኑ ። ሁለቱ አዛዦች ያዣዥ ጎራዴያቸውን እየመዘዙ በዩጃቸው ፣ የጅ ቦምባቸውን በዩኪሳቸው ይዘው ፣ እጫካው ውስጥ ገብተው ፣ ትንሽ እንንብሰው እየተሽሎከለኩ እንደ ሄዱ ፣ ካርበኞች ጋር በቅርብ ስለ ተገናኙ ፣ ጠላት ሲመቱበት የዘረጉትን ጎራዴ ጫካው ከዩጃቸው ሲቀማቸው ፣ የጅ ቦምባቸውን ከዩኪሳቸው እያወጡ እንዲሁ ሁለት ፣ ሁለተኛው ሶስት አርበኞች ከገደሉ በሁዋላ ፣ እነሱም በብዙ ጥይት ተደብድበው እዚያው ወደቁ ። ጥሩ አዛዦች ባይሆኑ ጥሩ ጀግኖች መሆናቸውን አስመሰከሩ ። እንደ አዛዦች ግን ያንጊዜ የወልመራን የጣሊያን ጦር የመሩት ሁለቱ መኰንኖች ፣ ተራ ወታደር የማይሳሳተው ስህተት መሳሳታቸው ፣ የጦርነትን ስልት ሀሁ ለማያውቅ መሀይም እንኳ ግልጽ ነው ።

የጣሊያን አዛዦች ፣ አርበኞች በርፈታ በር አንጥፈው እንዳለፈው ሳምንት አደጋ ለመጣል የሚጠብቁ ለመሆናቸው ባገኙት ውሸት መረጃ መሰረት ፣ በዚያ ባለፈው ሳምንት ያለቁትን ጣሊያኖች ደም ለመመለስና ፣ ወደፊት ያን የመሰለ ድፍረት ለሚሞክሩ ፣ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ምሳሌ የሚሆን ቅጣት ለማሳየት ፣ ከመጠን ያለፈ ቸኩለው ነበር ። ስለዚህ ፣ በርፈታን ከደበደቡ በሁዋላ ፣ ጠላታቸው ያመለጣቸው መሆኑን ሲያዩ ፣ ቁጣቸው የመበቀል ችኮላቸውን ያከል ጽኑ ሆኖ ፣ የወልመራን ጫካ አስቀድመው በከባድ መሳሪያና ባይሮፕላን ሳይደበድቡ ፣ እግረኛው ጦር ሁሉ ገብቶ እንዲበረብር አዘዙ ። ለዚያ ጣሊያኖች በሰው ፣ በመሳሪያም ሆነ በክብር ፣ እጅግ ውድ ዋጋ ከፈሉ !

ያንለት ፣ የወልመራን ጫካ እንዲበረብሩ የታዘዙት የጣሊያን እግረኛ ወታደሮች ፣ መውጫ መውረጃውን ፣ መሸሻ መሸሸጊያውን ፣ በማያውቁት ጫካ ገብተው ፣ እያንዳንዳቸው ሲተኮስባቸው ከመስማትና የነሱ ተራ ደርሶ እስኪወድቁ ፣ ምን እንደሚጠብቃቸው አያውቁም ነበር ። ከፊታቸው ፣ ወይም ከሁዋላቸው ፣ ጎዋደኞቻቸው ሲወድቁ ከማየት በቀር ፣ ከየት እንደ ተተኮሰባቸው ፣ ወይም ማን እንደ ተኮሰባቸው ማየት አይችሉም ነበር ። የጀግንነት ወኔ ፣ የመሪዎቻቸውን ትእዛዝ አስ

@OLDBOOKSPDF

ጥሶ ፣ ቅጠል ለብሰው ከሚኖሩበት ዛፍ እዮወረወረ እያወረደ በላያቸው ከሚጥላቸውና ፣ ከተፈጥሮ ምሽጋቸው ውስጥ ነጥቆ እያወጣ ፊትለፊት ከሚያጋጥማቸው አብድ ጀግኖች በቀር ፣ የጠላታቸውን የጦር ግንባር ሊያዩ በማይችሉበት ጫካ ገብተው ፣ ከሰባት ሰአት ግድም ጀምሮ እስ ኪመሽ ድረስ ፣ ወደ ቁራ እንደሚነዳ የፍሪዳ መንጋ ፣ ተከበው እየተጸ በደጉ ሲነዱና ሲታረዱ ዋሉ ።

ካስራ ሁለት ሰአት በሁዋላ ፣ የጊዜው መምሸትና የጫካው ጥላ ባንድነት እጫካው ውስጥ ጨለማውን አከብደውት ፣ ላይን መከልከል ሲጀምር ፣ አርበኞች በተመደበው ቦታ እንዲገናኙ ጥሩንባ ተነፍቶ ፣ እዚያ ከተሰበሰቡ በሁዋላ ፣ በዩክፍላቸው ሲቆጠሩ ፣ ሀያው ጥሪውን አል መለሱም ። ሀያው አርበኞች ወልመራ ጫካ ውስጥ ለሁልጊዜ የቀሩ ናቸው ! በዚህ አንጻር ፣ ከስምንት መቶ እስከ ሺህ ከተገመተው የጠላት ጦር ፣ ተርፎ አዲስ አበባ የተመለሰው ፣ ሁለት ካሚዮን ሙሉ ብቻ ስለ ሆነ ፣ በቁጥር ስድሳ ያክል ወታደሮች ናቸው ማለት ነው ! ከነሱም ብዙች ቁስለኞች ነበሩ !

ስለዚህ ፣ ይህ የወልመራ ጫካና ያች የበርፈታ በር ፣ እኒያ ላገራ ቸው ነጻነት ራሳቸውን መስዋእት አድርገው የሰጡ ሰማእቶችና ፣ እኒያ በብርቱ ጠላት ላይ ድልን የተቀዳጁ ጀግኖች የሚታወሱባቸው ፣ የተቀ ደሱ ቦታዎች ፣ የቅዱሳን መቅደሶች በመሆናቸው ሊሳለሙዋቸው የሚ ገባቸው ናቸው !

ጣሊያኖች እኒህን የበርፈታንና የወልመራን ጦርነቶች ባንድነት፣ “ፒኮሎ ማይጨው” ትንሹ ማይጨው ፣ ወይም “ዳግሚያ ማይ ጨው” ብለው ሰዬሙት ።

@OLDBOOKSPDF

ምእራፍ ፲

# ከቅዱስ ቦታ ሰይጣን አይጠፋም !

አቶ ዮሴፍ ካሚዮን መናገሻ መንደር ሲደርስ ፣ ምንም እንኳ ሌሊቱ እየሸሸ ፣ ንጋቱ እየተበተነ በመሄዱ ፣ ጨለማው ቀስ ቢል ፣ ከመሬት ገና ጨርሶ አልለቀቀም ። የመናገሻ መንደር ነዋሪም ገና ከንቅልፉ አልነቃም ነበር ። ስለዚህ ካሚዮኑ በመንደሩ መሀከል ቀስ ብሎ ቁልቁ ወደ በርፌታ አመራ ። በርፌታ በር መዘጊያ ፣ መንገዱ ከምእራብ ወደ ሰሜን በሚታጠፍበት ለመድረስ አስር ሜትር ያክል ሲቀረው ፣ አቶ ዮሴፍ መብራቱን ከረዥም ወደ አጭር ፣ ካጭር ወደ ረዥም ፣ ደግሞ እንደገና ወደ አጭር ለዋውጦ ፣ ሁለት ጊዜ ጥሩንባ ክንፋ በሁዋላ ፣ በሩን ሲገባ የካሚዮኑን ፍጥነትም ፣ ድምጽም ቀንሶ ፣ የሰሜንን አቅጣጫ ይዞ ፣ ቀስ እያለ ይነዳ ጀመር ። ከዚያ መንገዱ እንደገና ወደ ምእራብ በሚታጠፍበት ደርሶ መብራቱን ካጭር ወደ ረዥም ሲለውጥ ፣ እሽጥዋ መሻገሪያ ላይ መንገዱ በትልልቅ ደንጋዮች ተቆዋርጦ ፣ ታጥሮ አዩ ። ከቅዱስ ቦታ ሰይጣን አይጠፋም ! “ አጋንንቱና መላእክቱ በተስኪያን አብረው መኖራቸውን አታውቅም ? ” እንዳለው የኢትዮጵያ ቡና ቤት ገጠሬ ፣ ከበርፌታ ፣ ከዚች ቅድስት ቦታ ፣ ከዚች የነጻነት ሰማእታት መቅደስ ፣ አጋንንት አይጠፉም ! የበርፌታ በር በምእራብ ከወልመራ መንደሮች ፣ በምስራቅ ከመናገሻ መንደር ፣ ራቅ ያለች ስለሆነችና ፣ እዚያ አደጋ የደረሰበት ቢጮህ የሚሰማው ስለሌለ ፣ ነጠላ ሰው ፣ ወይም ያልተጠነቀቀ ባለመኪና ሲያገኙ ፣ ወንበዴዎች አደጋ እዩጣሉ የሚቀሙባት ፣ አንዳንድ ጊዜም ተንኮለኞች ልጆች በጎዳናው መሀከል ደንጋይ እያስቀመጡ ፈጥነው በሚነዱ ባለመኪናዎች የሰው ፣ ወይም የመኪና ጉዳት የሚያደርሱባት ቦታ ሆናለች ። በርፌታ ፣ የኢትዮጵያን ነጻነት ለመግፈፍና ፣ ታሪክዋን ለማጉደፍ የመጡ የፋሽስት ወንጀለኞች የተቀጡባት በርፌታ ፣ የነጻነት ሰማእታት ያረፉባት በርፌታ ፣ አጥሮ ፣ አስከብሮ ፣ የሚጠብቃት አጥታ ፣ የወንበዴዎችና የተንኮለኞች ወንጀል መፈጸሚያ ሆናለች !

አቶ ዮሴፍ ፣ ሞተሩን ሳያጠፉ መኪናውን አቆመና ፣ ቀስ ብሎ ፣ ተጣጣፊ መቺረዩሉን በመቀመጫው ስር ከሸሸገበት አውጥቶ ፣ “ ከቶ

@OLDBOOKSPDF

እረኞች መንገዳችንን አጥረውታል ፤ ገረንኪየል እባክህ ውረድና ደንጋ ዩን አንሳ ” አለ፣ ድምጹን ከፍ አድርጎ ። ገረንኪየል አቶ ዮሴፍ ፣ ገብረ ሚካኤልን አሳጥሮ የሚጠራበት ነው ። ገረንኪየል ቶሎ ወጥቶ ጎዳናው ከታጠረባቸው ደንጋዮች አንዱን ሲያነሳ ጎንበስ እንዳለ ፣

“ እረኞች አይደሉም ፤ ጭዋ ሰዎች ናቸው ያጠሩት ፤ እንዳትቃና ፤ እንተከሉብህለን ! ” አለ አንድ ድምጽ ፣ ከጎዳናው ራስጌ ካለው ጫካ ውስጥ ።

“ ባለህበት ቆይ ! እንዳትንቀሳቀስ ! እንዳትላወስ ! ” አሉ ሌሎ ችም ፣ በልዩ ልዩ ድምጽ ፣ የመጀመሪያው ድምጽ ከመጣበት ጫካ እዮተቀባበሉ ። ብዙ መሆናቸውን ማስታወቃቸው ነው !

“ ምን ትፈልጋላችሁ ? የተሸሸጋችሁብትን ጫካ ተመልክቼዋለሁ፤ የያዝሁት መትረዬስ መሄድ ከጀመረ መልእክቱን ሳይፈጽም እንደማይ መለስ ታውቃላችሁ ! ስለዚህ ብትተዉንና መንገዳችንን በሰላም ብን ሄድ ይሻላል ! ” አለ አቶ ዮሴፍ ፣ የመትረዬሱን ካርታ ሲያቀባብል ልክ የተኩስ ያክል እንካኩቶ ።

“ እንዳይሳሳቱ ጌታ ፤ እኛም በምብ ይዘናል ። ጣትዎ የመትረዩ ሱን ምላጭ ከመንካቱ በፊት ፣ ከነካሚዮንዎ ወደ ሰማይ ይገናሉ ። ”

“ ግዴለም ፤ ካልተስማማን እሱን ሁዋላ እናያለን ፤ አሁን ምናል ባት የምንስማማበት መንገድ ይገኝ እንደሆን ፣ የምትፈልጉትን ንገ ሩኝ ። ”

“ ከርስዎ አንድ ሳንቲም አንፈልግም ፤ የጫኑዋቸውን ሰዎች እጅ ብቻ ከሰጡን መንገድዎን በሰላም ሊቀጥሉ ይችላሉ ።”

“ ምን ሰዎች ? ”

“ ጥላሁን ፈይሳ የሚባል ወንድና ሶፊያ ሙላት የምትባል ሴት ። ጥላሁን የሰው ልጅ አስኮብልሎ የሚሸሽ ወንጀለኛ ነው ! ”

“ ጥላሁን ፈይሳና ሶፊያ ሙላት የሚባሉ ሰዎች አልጫንሁም ። ”

“ እርስዎ አቶ ዮሴፍ ብርሃኔ አይደሉም ? ”

“ ነኝ ። ”

“ የካሚዮንዎ ቁጥርስ 850 አይደለም ? ”

“ ልክ ነው ። ”

“ ታዲያ . . ጥላሁንና ሶፍያ ከሚባሉ ሰዎች ትናንት ተስማምታ ችሁ ፣ ኢትዮጵያ ሆቴል አብራችሁ አድራችሁ ፣ ዛሬ አልጫኑዋቸ ውም ?

@OLDBOOKSPDF

" ጥላሁንና ሶፍያ የሚባሉ ሰዎች እንኩዋንስ ልጥን ሰማቸውን አልሰማሁም ፤ ካላመናችሁኝ ሰው ላኩና አሳዩ ።" ከዚያ ፣ እሜካው ውስጥ ያሉት ሰዎች እስበላቸው ሲመካከሩ ትንሽ ቆይተው ፣ አንድ ከላይ እስከ ትንድቦቹ ፣ ከታች እስከ አይኖቹ ስር ፣ በሁለት መሀረቦች ተሸፍኖ አይኖቹ ብቻ የሚታዩ ፣ ሽጉጡን እንደሚተኩስ በሬቱ አስቀ ድሞ የደገነ ሰው ብቅ አለ ።

" የላክነው ሰው አንድ ነገር ቢሆን ቅድም ያልነው መሆኑ ነው ! " አለ አንዱ ከሜካው ውስጥ ።

" ግዴለም አትሰጉ " አለ አቶ ዮሴፍ ።

መላክተኛው ሽጉጡን አስቀድሞ ፣ ገረንኪያል ክፍት በወጣበት በኩል እንገቱን አካሚዮኑ ውስጥ አስገብቶ አይቶ ፣ ካቶ ዮሴፍ በቀር ሌላ ሰው አለመኖሩን ሲያረጋግጥ ፣ " እዚህስ ማንም የለ ፤ ወደ ላይ . . . መውጫ አለ ? " አለ ።

" በጀርባ መሰላል አለ ፤ ውጣና እይ " አለ አቶ ዮሴፍ ።

ያንጊዜ ፣ ጥላሁን ሸራውን እንደ ለበሰ ፣ ቀስ ብሎ ፊቱን ከወደ ግንባር ወደ ሁዋላ አዞሮ ሲተኛ ፣ ሶፊያም እንደሱ ሆራ ተኛችና ፣ "ለምን ዞርህ ? " አለች በሹክሹክታ ።

"እንዲህ ይሻላል ፤ እንዳትንቀሳቀሺ ! " አለ እሱም በሹክሹክታ።

ወዲያው ጥላሁንንና ሶፊያን የሚፈልገው ሰው ፣ ሽጉጡን አስቀድሞ ደግሞ በመሰላሉ ወጣና ፣ አካሚዮኑ ላይ ቆሞ ዙሪያውን ትንሽ ከተመ ለከተ በሁዋላ ፣ ጭንቱ የተካከለ ፣ ጉርብጥብጥ ነገር የሌለበት ሆኖ ስለ ታዬው ፣ የሚፈልጋቸው ሰዎች እዚያ እንደሌሉ አመነ ። በመመ ለሰና ሸራውን እዬገለጠ በመፈለግ መሀከል ሲያመነታ ቆይቶ ፣ "አይ ከንቱ ድካም ነው ፤ እዚህ ምንም የለ ! " አለ ድምጹን አሰምቶ ፣ ለመ ውረድ ዘወር ካለ በሁዋላ ፣ ምንም እንኩዋ እዚያ ካሚዮን ላይ ሸራ ለብሶ የተጫነው ነገር ፣ እንዲያ ሲያዩት የተካከለና ምንም ትርፍ ነገር የሌለበት ቢመስል ፣ ከዚያን ያክል ድካም በሁዋላ ሸራውን ገልጦ አይቶ ሳያረጋግጥ መሄዱ ሁዋላ የሚያስጸጽት መሆኑ ስለ ተሰማው ፣ ሸራውን እዬገለጠ ለማየት ወሰኖ እንደገና ተመለሰ ።

ሁለት ረዣዥርም ሸራዎች በካሚዮኑ ቁመት ተሰፍተው እመሀከሉ ላይ ይተባለፋሉ ፤ ማለት ፣ አንዱ በሌላው ላይ ይደረባል ። ፈላጊው ሽጉ ጡን በቀኙ ይዞ ፣ በግራ እጁ አንዱን ክፍል ሸራ ከሁዋላ ጀምሮ ወደ ግንባር እዬጠቀለለ እዬገፋ ፣ ባዋቂ እጅ በጥሩ ስራት የተደረደረውን

@OLDBOOKSPDF

የሰሚንቶ ክረጢት አንድ ባንድ እያዩ አግንብር ደረሰ ። ከሰሚንቶ ከረጢት በቀር ሰው የለም ! "ኢሁ ´ . . ! እንዲያው ከንቱ ድካም ነው ! " አለ ፡ እንደገና እናንብሶ ያን ረጃጅም ሽራ ባንድ እጁ እየገፋ ። እንደ ንጹህ ክረጢት ሰው አይመሰለው ሲመረምር ወገቡ ስሁለት የተከፈለ መስሎ ስለ ተሰማው ፤ በጣም ደከመው ። አንዱን ክፍል ሽራ ከሁዋላ እስከ ግንባር ሲጠቅልል በውኑቱ ዝሎ ፤ ሽጉጡ ሁለት ጊዜ ከጁ ወደቀ ፤ እስመገባረቁም በሰሚንቶ ክረጢት ላይ ስለ ወደቀ ነው። ከዚያ የተጠቀለለውን ሽራ መልሶ በግንባር ወደ ሁዋላ እንደ ነበረ ዘርግቶ ስሚንቶውን እለብሶ ሲያበቃ ፤ ሁለቱቹንውን ሽራ ንገዱሙ ከሁዋላ ወደ ግንባር የመጠቅለሉ አላስ እስቀድሞ ስለደከመው ፤ ትንሽ አረፈና ስራውን ቀጠለ ። መቸም ከሁዋላው ጸጸት ለመዳን ያሉ ካሉም፡ የሚፈልጋቸው ሰዎች እዚሁ አጠገብ ቅርብ ነው ፤ ጠይም ገላላ መኪና ተሳፍረው እንዳሆን እንጂ ፤ እዚያ እንደሰሎ ሊሞል ይችላል ፤ ብቻ ሁዋላ ከመጸጸቱ የጀመረውን ዳር አውጥቶ መሄድ አለበት ። ስለዚህ ፤ እሁንም እንደ ፊቱ ሽራውን በግራ እጁ እየጠቀለለ ወደፊት እየገፋ ፤ የሰሚንቶውን የክረጢት ድርድር አንድ ባንድ እያዩ ሂዶ ፤ እግንባር ሊደርስ ትንሽ ሲቀረው ፤ እሽራው ውስጥ የሚንቀሳቀስ ነገር ያዩ መሰለው ወደንግጠ ቀና ሲል ፤ አሁንም ሽጉጡ ከጁ ወደቀ ፤ ነገር ግን ሊያነሳው ቶሎ ጎንበስ ብሎ እጁን ሲሰድ ፤ ሌላ እጅ ቀድሞ አንስቶ ሽቅብ በሱ ላይ ደግኖት አዩ ። የጥላሁን እጅ ነው ! " ትተንፍስና የገዛ ጥይትህን እንዳለ እግትሀለሁ ! " አለ ጥላሁን በሹክሹክታ ። "በል መሸፈኛህን ማልና ተቀመጥ " አለ ቀጠለና ፤ አሁንም በሹክሹክታ ።

" እሺ " አለ ሰውዬው ፤ እሱም እንደ ጥላሁን በሹክሹክታ ፤ መሸፈኛውን ፈትቶ ጥሎ እዩተንቀጠቀጠ እጥላሁን ፊት ሲቀመጥ ።

" እንድ ቃል ሳትጨምር ፤ ወይም ሳትቀንስ ፤ የምነግርህን ገዋደኞችህና መኪና ነጂው እንዲሰሙ አድርገህ ትደግማለህ ! "

" እሺ "

" ምንም የለ ፤ ደንጋዩ ከመንገድ ይነሳ " ሲል ጥላሁን በሹክሹክታ ፤

" ምንም የለ ፤ ደንጋዩ ከመንገድ ይነሳ " አለ እስረኛው ፤ በከፍተኛ ድምጽ ።

" አሁን ደንጋዩን እንስተህ ልትመለስ ትችላለህ ፤ ወንድም" አለ እሜካው ውስጥ ካሉት አንዱ ፤ እንዳንነበስ ትእዛዝ የሚጠባበቀ

@OLDBOOKSPDF

ውን ፤ ገረንኪየልን ። ገረንኪየል “እህ . . ! ” ብሎ በረገሮ ተን ፍሶ ፤ የሚነሱትን ድንጋዮች እያነሳ ፤ ለማንሳት የማይቻሉትን እያን ከባለለ ፤ መንገዱን ነጻ አድርጎ ወደ ካሚዮኑ ተመለሰ ።

“ ኅበዝ ፤ ውጡና እሚጻው ላይ ቆዩኝ ፤ ሽንት ሸንቼ እደርስባችሁ ዋለሁ ” አለ ጥላሁን ፤ ለስረኛው ቀስ ብሎ ።

“ ኅበዝ ውጡና እሚጻው ላይ ቆዩኝ ፤ ሽንት ሸንቼ እደርስባችሁ ዋለሁ ” አለ እስረኛው ፤ ለጉዋደኞቹ ።

“ብቻ መቀመጥ ትሻ እንደሆነ ፤ ከጅብ ጉድጉዋድ አጠገብ እን ዳትቀመጥ እደራህ ! ካደን የሚመለስ ፤ የንጋት ጅብ እዚያ ያገኝህ እንደሆን . . . ‘እግዜር ሰጠኝ’ ብሎ ወደ ጉድጉዋዱ ይዞህ ይገባል ፤ ልብ አድርግ ” አለ ፤ ከጉዋደኞቹ አንዱ እዩሳቃ ። ሌሎችም ባንድነት ሳቁና ወደ ሜዳው ለመሄድ ተነሱ ።

“ አሁን ወርጃለሁ ይሄዱ ጌታ ” ሲል ጥላሁን በሹክሹክታ ፤

“ አሁን ወርጃለሁ ይሄዱ ጌታ ” አለ እስረኛው ፤ እንደ ታዘዘው ድም ጹን ከፍ አድርጎ ። ወዲያው አቶ ዮሴፍ መኪናውን አስነሳ ።

“ በሰላም ሂዱ ! ” አሉ እነጥላሁንን ፈላጊዎች ፤ ወደ ሜዳው ሲሄዱ እዩተቀባበሉ ።

“ በሰላም ቆዩ ! ” አሉ አቶ ዮሴፍና ገረንኪየል መልሰው ።

ከዚያ ፤ አቶ ዮሴፍ በርፈታ ቆሞ የጠፋበትን ጊዜ ለማስተካከል ፍጥነት ጨምሮ እዩነዳ ፤ ጥላሁንና እስረኛው ፊት ለፊት ተቀምጠው እንደ ተፋጠጡ ፤ አዲስ አለምን አልፈው ቁልቁለቱን ትንሽ ከወረዱ በሁዋላ ፤ አንድ ሸለቆ መሳይ አጠገብ ሲደርሱ ፤ “ ጋሼ እባክዎ አንድ ጊዜ ያቁሙልኝ ፤ ሽንት መሽናት እፈልጋለሁ ” አለ ጥላሁን ። አቶ ዮሴፍ አልሰማ ብሎ ከብዙ ጩኸት በሁዋላ ለማና አቆመ ።

ጥላሁን ቀድሞ ተነስቶ እስረኛውን እዩነዳ ፤ ከካሚዮኑ ወርደው እሸለቆው ውስጥ ሲገቡ ፤ አቶ ዮሴፍና ረዳቱ አላዩም ነበር ። በሁዋላ ብቻ ሶፊያ ወርዳ ከበርፈታ እስረኛ ይዘው መምጣታቸውንና ፤ ስዩም እስረኛውን ይዞ ወደ ሸለቆው መሄዱን ስትነግራቸው ሁለቱም ተገ ረሙ ።

“ ለመሆኑ እንዴት ዝም ብሎ ታሰረ ? እንዴትስ ዝም ብሎ እዚህ ድረስ መጣ ?” አለ አቶ ዮሴፍ ።

“ ሽራ ሲጠቀልል ሽጉጡ ወደቀበትና ፤ ስዩም ቀድሞ አንስቶ ፤ “ የተናገርህ እንደሁ እዚሁ እገልሀለሁ ” ስላለው ፈርቶ ዝም አለ ። ከዚያ በሁዋላ ፤ ሽጉጡን በሆዱ ላይ አስመርኩዞ ተናገር ያለውን ሁሉ

@OLDBOOKSPDF

እንዲናገር አደረገው ። ደንጋዩ ከመንገድ እንዲነሳ ፣ ሰዎቹ ወደ ሚዳው እንዲሄዱ ፤ እርስዎ መኪናውን እንዲነዱ እዬጮኽ የተናገረው ሁሉ ሰዩም ቀስ ብሎ የነገረው ነው ። ከዚያ ሰዩም ሽጉጡን በሆዱ ላይ እንዳስመረኮዘበት ሳይንቃነቅ እዚህ ደረስን ። ”

አቶ ዮሴፍና ገረንኪያል ፣ ሶፊያ ታሪኩን ሲተርኩላቸው ፣ መናገር እስኪያቅታቸውና ሆዳቸውን እስኪያማቸው ከሳቁም ባሁዋላ እስዋ ከነገረቻቸው የሰውዬውን ሁኔታ በዩራሳቸው ስለው እያዩና እያሰቡ ስቀው አናባሩ አሉ ።

“ በል እንካ ተቀመጥና ጻፍ ! ” አለ ጥላሁን ምርኮኛውን ፣ እሸ ለቆው ውስጥ እንደገቡ አንድ ሉክ ወረቀትና ብርእ በግራ እጁ ከኪሱ አውጥቶ ። ምርኮኛው ወረቀቱንና ብርእን ተቀብሎ እንደ ፉመ ዝም ብሎ ማራኪውን ይመለከት ጀመር ።

“ ተቀመጥና ጻፍ አልሁህ ! ” አለ ጥላሁን ግንባሩን ከስቶር ፣ በቁጣ በቀሉ አይኖቹ ምርኮኛውን እያዩ ።

“ ምን ልጻፍ ? ” አለ ምርኮኛው ፣ አንድ ጠፍጣፋ ደንጋይ ላይ ተቀምጦ ማራኪውን ሽቅብ እዩተመለከተ ።

“ አሁን ልገድልህ ነው ! ስለዚህ ከመሞትህ በፊት የምትተወው መልእክት አለህ እንደሆን ጻፍና ለምትጽፍለት ሰው እንዲደርስልህ አደርጋለሁ ።

“ ለምን ትገድለኛለህ ? ”

“ ሰው የማጥፋት ሱስ ያደረብህ ፣ ክፉ ስለሆንህ ፣ ብዙ ንጹህ ሰው ከማጥፋትህ በፊት መጥፋት አለብህ ! ”

“ እንዴት ? ”

“ ያልበደለውን ሰው ማጥፋት የሚፈልግ ምን ይባላል ? ሰው የማጥፋት ሱስ ያደረበት አይደለም ? ”

እስረኛው አንገቱን ደፍቶ መሬት መሬት እያዩ ዝም አለ ።

“ እዎ ፤ ካላጠፋሁህ ብዙ ንጹህ ሰው ታጠፋለህ ፤ ስለዚህ መጥፋት አለብህ ። እኔን እንኳዋ ናምሄድበትን ስለማታውቅ ምንም አታደርገኝ ፤ ብቻ . . . ” ብሎ ጥላሁን ሊናገር ያሰበውን ሳይናገር ፣

“ ማን አያውቅም አለህ ? ” አለ እስረኛው አቋርጦ ።

“ ምኑን ? ”

“ የምትሄድበትን ። ”

@OLDBOOKSPDF

"ካወቅሁም ደህና ፤ የምሄድበትን ማወቅህ እንደጎዳልህ የሚያስገድደኝ ፣ ተጨማሪ ምስናያት ይሆናል ፤ በል የምትጽፈውን ጻፍ !" አለ ጥላሁን ፣ አይኖቹ በቁጣ እንደ ቀሉ ።

ምርኮኛው አይኖቹን ከማራኪው አንስቶ ሳያረግብ ፊት ለፊት እንደ ተከለ ፊቱ ቁጥር ፣ ፊታ ፣ ጥቁር ፣ ፊኒ እያለ በዬቅጽበቱ ሲለዋወጥ ፣ በውስጡ በዬቅጽበቱ ልዩ ልዩ ስሜት የሚለዋወጥበት መሆኑን ይገልጽ ነበር ! እንዲህ የውስጥ ስሜቱን ተከትሎ ፊቱ እዬተለዋወጠ ፣ አይኖቹን ሳያረግብ ፣ ፊት ለፊት ተክሎ ቆይቶ መጻፍ ጀመረ ። ሲጽፍ ፣ ሲጽፍ ቆይቶ ፣ ቀና ይልና ፣ ፊት ለፊት አትኩሮ ሲመለከት ቆይቶ ፣ አንዳንድ ጊዜ በፈገግታ ፣ አንዳንድ ጊዜ በቅርታ ፣ ወደ መጻፉ ይመለሳል ። እንዲህ ቀና ፣ ደፋ እያለ ደብዳቤውን ጽፎ ፣ ደምዱን ሳያስማ አንብቦ ሲያበቃ ፣ ፈርሞ "ያው !" አለ ለማራኪው ።

"አንብበው !" አለ ጥላሁን ።

"እጅግ የምወድህና የምትናፍቀኝ አባዬ ፤

ይህ ደብዳቤ የሚያመጣልህ መልእክት እንደሚያስቃይህና ፣ ብርቱ ግእር እንደሚሆንብህ ስለማውቅ ባልጽፍልህ እስቤ ነበር ። ነገር ግን እኔ የሆነውን ፣ እውነቱን ፣ ሳልገልጽልህ ቀርቼ ሌሎች የሆነውን ክፉ ነገር አባብሰው ፣ በዚያ ላይ ያልሆነውን ጨማምረው የነገሩህ እንደሆነ፣ ጨካኝ ስቃይ ይብስ ሳይጨክንብህ አይቀርም ብዬ እኔ ልጽፍልህ ወሰንሁ።

"አባዬ ! አንድ በዘመናዊው የሰነ ፍጥረት ፍልስፍና የማያምን ካናዳዊ መነኩሴ አስተማሪያችን ፣ በክፍል ካስተማረን ትንሽ ጠቅሼ ያደረግሁትን ለምን እንዳደረግሁት ስገልጽልህ ፣ ይቅርታ እንደምታደርግልኝና እንደምትጽናና ተስፋ አለኝ ።

"የአለም ታሪክ ፣ ፍጥረት ሁሉ በያይነቱ ፣ መጀመርያ ከተነሳበት መጨረሻ እስከሚደርስበት የትውልድ ድልድይ እዬሰራ የሚተላለፍበት ፣ የትውልድ ድልድይ ነው ። እያንዳንዱ የሕዝብ ፣ የንስሳት፣ ያራዊት ፣ ያእዋፍ ፣ የእጽዋት ፣ ወዘተ . . . ትውልድ ፣ በያይነቱ ድልድይ እዬሆነ ፣ የወለደውን ለሚወልደው ሲያስተላልፍ ፣ ያም በተራው የወለደውን ለሚወልደው እያስተላለፈ ፣ እንዲህ ወላጅ በልጁ እዬታደሰ ፣ ህያው እዬሆነ ፣ ጉዞው ይቀጥላል ። ስለዚህ ፣ በጉዞ መጨረሻ በአለው ላይ በያይነቱ የሚኖረው ፍጥረት ፣ ባንዳንዱ አስተላላፊ ትውልድ ፣ በድልድዩ የማስተላለፍ ችሎታ ማጣት ተቋርጦ ከሚ

@OLDBOOKSPDF

ቀረው በቆር ፣ ይገባ ይሆን ፣ ይቀጥል ይቆርቁዝ እንጂ ፣ ያው በጉዞው መጀመሪያ የነበረው ፣ ጉዞውን የጀመረው ነው ። የቤተሰብ ታሪክም ከዚህ ጠቅላላ የፍጥረት ታሪክ የተለዩ አይደለም ። ልጅ ድል ድይ ሆኖ አባቱን ለልጁ ማስተላለፍ አለበት ። ይህን ማድረግ የማይችል ልጅ የፍጥረትን ሕግ የሚያቃውስ ፣ ህገ ወጥ ከመሆኑ በላይ በትውልድ አዬታደለ አስከሱ የደረሰውን ያባቶች ህይወታዊ መስመር በማቋጥረጡ ፎንም ፣ ያባቶቹ ገዳይ ነው ። እንዲህ ያለ ልጅ ከሞቱ ልደቱ ያሳዝናል !

“ አባዬ ! አንተ ፣ አንተንና አባቶችህን ለኛ ለልጆችህ ግሩም አድርገህ ያስተላለፍህ መሆንህ አይጠረጠርም ። እኔንና እቴን የሸመቤትን ፣ አፈትህ ቁጭ አድርገህ ፣ ስለ እናት አባትህና ስለ አያቶችህ ፣ ስለ ቤቶችም ፣ በጎልማሳነትህ ጊዜ የነበሩ ሽማግሌዎችና ባልቴቶች ስታወራን ፣ እነሱን ባንተ እናያቸው ነበር ። ስራቸውና ያሰራራቸው ዘዴ ፣ እምነታቸውና ስሜታቸው ፣ ባንተ አልፎ ይታዩን ፣ ይሰሙን ነበር ። በጊዜው የሆነ ነገር በሚያወሩበት ፣ ወይም ያለፈ ታሪክ በሚተርኩበት ጊዜ ፣ ደስ የሚያሰኘውን በፈገግታ ፣ የሚያሳዝነውን በቅርታ ፣ ጀብዱን በሞቅታ ፣ ሲያወሩና ሲተርኩ ፣ በትዝታ ህያዋን ሆነው ይታዩህና ፣ ስሜታቸው ይሰማህና ፣ አንተም እንደነሱ የታሪኩን ሁኔታ ተከትለህ ፈገግ እያልህ ፣ ቅር እያለህ ፣ ሲቃ እያሞቀህ ፣ ታወራን ስለነበረ ፣ ያንተ ብቻ ሳይሆን ባንተ ውስጥ ካንተ በፊት የነበሩት አባቶች ህይወት ፣ ደስታቸው ፣ አዘናቸው ፣ አዬታዬንና እዬተሰማን እኛም ካንተና ከነሱ ጋር እንደ ሁኔታው ደስ ይለን ፣ ይከፋን ፣ ሞቅ ይለን ፣ ይክረሰሰን ነበር ። ስለዚህ አንተ አባቶችህን ህያዋን አድርገህ ካንተ ጋር እኖህደይ ፣ ባንተ አድሰህ ለኛ ለልጆችህ ሰጥተኸናል ! ለኛ ለልጆችህ አስተላልፈህልናል ። የሸመቤትም እንዳንተ ናት ። የሸመቤት እንዳንተ የታሪክ አደራዋን ለልጆችዋ ማስተላለፍ የምትችል ናት። የሸመቤት በርግጥ ያንተ ልጅ ናት ። እኔ ግን ወዮልኝ ! እኔ አዲስ አበባ ከመጣሁ በማላውቀው ምክንያት ፍጹም ሌላ ሆንሁ ። እኔ እንኳንስ ካንተ ካባቴ ያገኘሁትን ለልጆቼ ለማስተላለፍ ፣ ህይወቴን ሊኖሩት የሚገባ ለማድረግ የማልችል ፣ ብላሽ ሆንሁ ። ልብህ ለልቤ የሰጠው ፍቅር ፣ ደግነት ፣ ቸርነት ፣ ደቅር ባይነት ፣ በኔ ልብ ውስጥ በማላውቀው ኃይልና ፣ በማላውቀው የምስጢር እጅ ወደ መጥላት ፣ ወደ ክፋት ፣ ወደ ተንኮል ፣ ወደ በቀል ተለወጠ ። ስለዚህ ልቤ የሚወዱኝን ይጠላል ፤ መልካም በሚያደርጉልኝ ይቀናል ፤ ያልበደሉኝን መበቀል ይሻል ። ስለዚህ ወዳጅ የለኝም ፤ ተስፋ የለኝም ። ደስታ

@OLDBOOKSPDF

የለኝም ። ስለዚህ ፣ የምኖርበት አካባቢ ፣ በዙሪያዬ ያለው ሁሉ ፣ መውጫ ቀዳዳ የሌለው ፣ ጨለማ ፣ ወህኒ ስለሆነብኝ ከዚያ ለመውጣት በፊቴ ያገኘሁትን ሁሉ ማጥፋት የምፈልግ ወንጀለኛ ሆንሁ ! አባዬ ስንዴ ዘራህ ፣ እንክርዳድ ሆንሁ ! ወይን ተክልህ ፣ አሜኬላ ሆንሁ ! ሰው ወለድህ ፣ ሰይጣን ሆንሁ ! ለምን እንዲህ ሆንሁ ? እንጃ ! ምን ይሻለኛል ? አስመኖር ! አባዬ ብኖር ዕድሜዬን ሙሉ ወንጀል ስሰራ ፣ በሰራሁት ወንጀል ስፈራ ፣ የቀን አረፍት ፣ የሌሊት እንቅልፍ ፣ እጦቼ ስባክን ፣ ስባንን ከመኖር በቀር ፣ የመንፈስ ጸጥታና የልብ ደስታ የማይ ኖረኝ ከመሆኔም ሌላ ፣ ያንተን ፣ የደጉን አባቴን ስም በክፉ ባስጠራ የምኖር ፣ እኩይ በለሆንሁ ፣ መኖር የማይገባኝ ፣ ሞት የሚገባኝ መሆ ኔን ራሴ ፈርጄ ሀይወቴን በገዛ እጄ አባልፈያለሁ ። እውነቱ ይህ ነው! ሌላ ቢነግሩህ እንዳታምንና ሰው እንዳትጠረጥር አደራ ! አባዬ በመ ወለዴ እንጂ በምግባሬ አትዛን ፣ ደህና ሁን ። ልጅህ ወንድይራድ አስታ ጥቄ ። ”

“እንድልህለሁ አልሁ እንጂ ፣ ‘ራስህን ግደል ’ አላልሁምኮ ! ‘ለምን ራሴን ገደልሁ ’ ብለህ ጻፍህ? ” አለ ጥላሁን ፣ ምርኮኛው የጻፈ ውን ማታለያ እንብቦ ሲጨርስ ።

“ ራሴን ገዳዩ እኔ ስለሆንሁ ። ”

“ እንዴት ? ”

“ ስትሸሽ ‘ አላሸሽም ’ ብዬ ስከተልህ ብትገድለኝ ፣ ራሴን ገዳዩ እኔ እንጂ አንተ አይደለህም ። ”

“እግዜር ይስጥልኝ ፣ ጥሩ ፍርድ ነው ፣ በእግዚአብሄር ፊት መጠ የቁ ባይቀር ፣ በሰው ፊት ከመጠየቅ አዳንኸኝ ” አለ ጥላሁን ባሽሙር ።

“ እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅህ ፣ እንደ ንጉሤ ቆጥረኸው መናገር ትፈቅድ እንደሆን ፣ ከልፈለግህ መቸም እንቢታ የሙዋች መብት መሆ ኑን ታውቃለህ ” አለ ጥላሁን ።

“ ምን ? ”

“ ለምን ያን ሁሉ ሰው ይዘህ ተከተልኸን ? በጅህ ብንወድቅ ምን ታደርገን ኖሮዋል ? ”

“ እንጃ ! ምናልባት . . ” እለና መሬት መሬት እያዩ ዝም አለ ምርኮኛው ።

“ ምናልባት . . . መግደል ? ”

“ ሶፊን አልገድላትም ነበር ። የምትወደውን እጦታ ስታዝን ማየት የፈለገችው ሆናላት ደስ እንዳይላት ነበር የፈለግሁ ! ”

@OLDBOOKSPDF

"ከሶፊ ጋር የነበረኝ ግንኙነት ገና ከተራ ጉዋደኝነት ወደ ፍቅር መለወጥ ሲጀምር ፥ ፍቅራችን ሳይጸና ስለስዋ ይሰማኝ የነበረውን ስሜትና የተለዋወጥናቸውን የፍቅር መክፈቻ ቃላት ሳይቀሩ ፥ የነገርሁ ላንተ ብቻ መሆኑን ታውቃለህ ! ታዲያ ያንጊዜ ፥ 'ጥሩ ልጅ ናት ! ቶሎ አግባት' እያልህ በማደፋፈር ፈንታ ይህን ያክል ከወደድሀት ለምን አልነገርኸኝ ?"

" በመጀመሪያ የሁለታችሁ ፍቅር እንደ ብዙው የወጣቶች ፍቅር በተወለደ ማግስት ፥ ቢበዛ በሳልስቱ የሚሞት እንጂ እድሜ እዚህ የሚደርስ ስላልመሰለኝ 'መቸም አይሆን' ብዬ ነው . . . ካንገት በላይ 'ቶሎ አግባት' እልህ የነበር ። በሁዋላ ብጸጸትም አፈርሁ ። "

" ታዲያ የሁለታችሁን ፍቅር አልነገርኸኝ ፤ ሌላም የማውቅበት መንገድ እንዳልነበረ ታውቃለህ ! ምን በደለኝ ብለህ ነው ልትገድለኝ የፈለግህ ? "

"እስዋን ለመበቀል ነው እንጂ ፥ አንተስ ምንም አልበደልኸኝም"

" ለመሆኑ እስዋስ . . . 'እገባሀለሁ' ብላ ቃል ሰጥታህ ኖሮዋል?"

" የለም ።"

" 'እወድሀለሁ' ብላስ ? "

" የለም ።"

" ታዲያ የምትበቀላት ስለምን ነው ? "

ወንድይራድ አይኖቹን ሳያረግብ ፊት ለፊት ተክሎ ዝም ብሎ ሲመለከት ቆዩና ፥ "የምኖር ብሆን መጥላትህ እንኳ ደግሞ እንዳይገኝ ! አልነግርህም ነበር ! ነገር ግን መሞቴ ስለሆነ ፥ ብነግርህ ግዴለኝም "

አለ አይኖቹን ከተከለበት መልሶ ጥላሁንን ሸቅብ እያዩ ።

" ሶፊን ለመበቀል እዚህ ድረስ የደረስሁ ፥ አንተን የምወድህን ጉዋደኛየን ለመግደል እስከ መፈለግ የደረስሁ ፥ ስለ ወደድሁዋት አይደለም ። "

"ታዲያስ ? " አለ ጥላሁን ፥ በመገረም ምርኮኛውን ዘቅዝቆ እያዩ ።

" ሀረር ሁለተኛ ደረጃ አብረን ስንማር ፥ አባቴ የፈለግሁትን ያክል ገንዘብ እዪሰጠኝ ለቤቶች ልጆች ስጦታ እማርጨ መግዛት የምችል እኔ ብቻ ስለነበርሁ ፥ ሁሉም በኔ ላይ ይረባረቡብኝ እንደነበረ ትግሬህ አለሁ ። ብዙ ልጃገረዶች በኔ ምክናያት እስበሳቸው እዪተጣሉ ሲደባደቡና ፥ ባንዳንዶችም ያካል ጉዳት ሲደርስባቸው የነበረኝ ደስታ ይህን ያክል ነው ብሎ ለመገመት . . . ያስቸግር ነበር ። ሶፊ ብቻ ከቁም ነገር

@OLDBOOKSPDF

አትጽፈኝም ፤ ትክክ ተበጥናለች ። በዚህ ተናድጂ የሚከተሉኝን ሁሉ በጣም የምወዳቸውን ጭምር ትቼ እስዋን ፤ የምትሸሸኝን እከተል ጀመር ወደኋት አይለም ፤ የለም ! ያ ሁሉ ልሽገረድ ሲያመልከኝ ፤ እስዋ ብቻ ስለናቀችኝ ነዶኝ ፤ እንደ ምንም አደርጌ ፤ አይከፍሉ ክፍዬ ፤ ድል ከደ ረግሁዋት ፤ ከማረክሁዋት ፤ ካንበረከክሁዋት በሁዋላ ፤ እዚያው እንደ ተንበረከከች ትቻት ፤ ንቂያት ፤ ደቅድቂያት ስሄድ ፤ እስዋ እንደገና እያማጠነች ፤ እዩተለማመጠች ፤ እያለቀሰች ሁዋላ ሁዋላዋን ስትሮጥ ለማየት የነበረኝ ምኞት ጽኑ ስለነበረ ነው !" አለ ወንድይራድ ፤ ጥር ሱን ነክሶ ሲናገር ፤ ያንጊዜም በሰፊ ላይ ሊንቀል የማይችል ፤ ጥልቅ ቂም እንዳለው በፊቱ እዩታዩ ። "ነገር ግን . . . " አለ መሬት መሬት እያዩ ትንሽ ሲያሰብ ቆይቶ ቀና አለና ። "ነገር ግን ፤ እኔ እዚዋን ለማ ሸነፍ የማደርገው ጥረት . . . ማባበሉ ፤ መለማመጡ ፤ ወድ ገጼ በረከት ማቅረቡ . . በበዛ መጠን ፤ የስዋ ቸልተኛነትና ማይሰሸነት እንዲያውም እኔን ወደ ማንጠፕ ፤ ወደ መናቅ ፤ ወደ ማዋረድ እዩተለወጠ ሄዶ ፤ በመጨረሻ መጥላት ብቻ ሳይሆን ፊቷን ለማየት እንኳዋ እንደ ቆሻሻ ነገር ተጸየፈኝ ጀመር ። ያንጊዜ እብድ ሆንሁ ! በሁዋላ እስዋን በቀ ጥታ ባይሆንልኝ ፤ በጎድንም ቢሆን ለማጥቃት የስዋ የሆነውን ሁሉ ፤ እስዋ የምትወደውን ሁሉ ለማጥፋት ፎርጨ ተነሳሁ ! ሀ ! ከፉ ነገር ማድረግ አለመጀመር ነው እንጂ ፤ ከተጀመረ ፤ ከፉ መልካምን ስለማይ ወልድ ፤ ከፉ ከፉን እየወለደ ይራባል ፤ እልክ ከፉ ነው ፤ ከሰፊ ጋር እልክ ተጋብቼ ፤ በልክ ወንጀል መስራት ጀመርሁና አንዱ የሰራሁት ወንጀል ወደ ሌላ እዩገፋ ሲያራምደኝ እዚህ አደረሰኝ ። አንተን ሊመግ ደል ወደ መፈለግ አደረሰኝ ! ጥላዩ ! ብታምንም ፤ ባታምንም አንድ ነገር እንግርሀለሁ ። አንተን በጣም ነው የምወድህ ! ነገር ግን ሰፊን ለመበቀል ያለኝ ፍላጎት ካንተ ፍቅር እንኩዋ በላይ ስለሆነ ፤ ሰፊን በሙሉ መበቀያ አንተን በመግደል ብቻ መሆኑን ስላመንሁ ህሊናዩ በውስጤ ሲጮህ ፤ እሱን አፍኜ ልገልህ መጥቼ ነበር ። አሁን . . . አንተ ልትገድለኝ ነው ፤ ሰፊ . . ድል . . . ድል ልታደርገኝ ነው !" አለ እዩተከዘ ።

"ሊመሆኑ . . . ከከንቱነት ፤ ከግብዝነት ተነስተህ ፤ እንዲህ ያለ ከፉ ወንጀል በመስራትህ መጸጸትህ ቀርቶ ፤ አሁንም ከሞት አፋፍ ቆመህ የሚያስቆጭህ የሰፊ ድል ማድረግ ነው ?" አለ ጥላሁን የጥንት ወዳጁን በመገረም አይን እያዩ ።

"ስሞትም ከመሞቴ ይልቅ የሰፊ ድል ማድረግ እዩቆጨኝ ነው የምሞት !"

ጥላሁን ዝም ብሎ [illegible] @OLDBOOKSPDF ፡ "ተነስ !" አለ ፡ ሽጉጡን በወንድ ይራድ ላይ እንደ ደገነ ትንሽ ፈንጠር ብሎ ። ወንድይራድ እንደ ታዘዘው ተነስቶ ሲቆም ፤

"የኮትህንና የሱሪህን ኪሶች ሁሉ እዩገለበጥህ አሳዩኝ" አለ ጥላሁን ።

"ለምን ? በኪሴ ምን አለ ?"

"አትጠይቀኝ ፤ ዝም ብለህ ያዘዝሁህን አድርግ !"

ወንድይራድ የኮቱንና የሱሪውን ኪሶች እዩገለበጠ ለጥላሁን ሲያሳይ ፡ በሁሉም ከገንዘብና ከወረቀት በቀር ሌላ ነገር አልነበረም ። ከዚያ ጥላሁን ሽጉጡ የጐረሰውን ጥይት ሁሉ አራግፎ በገዛ ኪሱ ከትቶ፡ "ሽጉጥህም ፡ ደብዳቤህም እኒያውልህ ፤ በሽተኛ አልገድልም ፤ አንተ በሽተኛ ነህ ! እግዚር ይማርህ ፤ ወይ እሱ ይግደልህ !" አለ ባዶውን ሽጉጥና ወንድይራድ ላባቱ የጻፈውን ደብዳቤ ትንሽ ራቅ አድርጎ አስቀምጦ ። ወንድይራድ ግራ ገብቶት ፡ አንድ ጊዜ ጥላሁንን ፡ አንድ ጊዜ ሽጉጡንና ደብዳቤውን እያስዋወጠ እያዬ ዝም ብሎ ቆመ ።

"ያዝና ሂድ !" አለ ጥላሁን በቁጣ ። ወንድይራድ ባዶ ሽጉጡንና ደብዳቤውን ይዞ ካይኑ ሲጠፋ ፡ ጥላሁን ወደ ከሚፕን ተመለሰ ።

@OLDBOOKSPDF

## ምእራፍ ፲፭

# በኻርሮንድ ውበቱ

ከነቀምት ጎሬ መንገዱ ጥርጊያ ፣ ያፈር መንገድ ስለሆነ ፡ ከረ ምት ክረምት ባዲስ አበባና በጎሬ መሀከል ከአይሮፕላን በቀር የመ ንገድ መገናኛ ይቋረጣል ። ስለዚህ ፣ ያ ክረምት ከገባ ፣ ካዲስ አበባ ጎሬ መጀመሪያ መንገድ ጠራጊዎች ሆነው ከገቡት ካሚዮኖች መሀ ከል ፣ አንዱ ያቶ ዮሴፍ መኪና በመሆኑ ፣ እንደ ብርቅ ታይቶ ፣ ከትም ህርት ቤቱ ቅጽር ግቢ ገብቶ ሲቆም ተማሪወቹም ፣ አላፊ አግዳሚው ህዝብም ከበበው ።

“ጋሼ እዚህ ትንሽ ትቆዩ እንደሆነ ፣ ወዳደባባዩ ወጥቼ የውበ ቱን ቤት የሚያመለክተኝ ባገኝ ጠይቄ እስክመለስ ፣ ጽዮን እቃችንን ይዛ እዚሁ ከናንተ ጋር ብትቆዩኝ . . . ትቼገራላችሁ ?” አለ ጥላሁን አቶ ዮሴፍ እስቲጋሪ ይለኛል ብሎ እዩሰጋ ።

“እኛስ መቸም . . . የትምህርት ቤቱ ዘበኞች መጥተው ፣ ጭነ ቱን አሳይተን እስክናስረክብ መቆዩታችን ስለማይቀር ፣ ምንም አን ቸገር ። ይልቅ አንተ ከመድከምህ በፊት የምትፈልገውን ሰው የሚያ ውቁ ተማሪዎች ፣ ወይም ሌሎች እዚህ እንዳሉ ፣ ብንጠይቅ ይሻል እን ደሆን እንጂ !” አለ አቶ ዮሴፍ ።

“የማንን ቤት ነው የምትፈልግ ? እኔ ላሳይህ ጋሼ !” አለ ፣ አን ገዶችንና ያመጣቸውን ካሚዮን ከብበው እንደ ብርቅ ከሚመለከቱት ትናንሽ ህጻናት መሀከል አንዱ ።

“እኔ ላሳይህ ጋሼ” አለ ሌላው ፣ እሱም እንደ ጉዋደኛው ከመረ ዳት ወጥቶ ታላላቆችን እንኩዋ ለመርዳት መድረሱን ለማሳዩት ባለው የህጻናት ጉጉት ተገፍቶ ።

“እነሱ አያውቁትም ፤ እኔ ለሳይህ ጋሼ !” አለ ሶስተኛው ።

“የት ታውቀዋለህ ፣ አንተ ቀጣፊ ውላጅ ?” አለ የመጀመሪያው።

“እረ ቀጣፊ ውላጅ አንተ ፣ ደሞ ቀጣፊ ውላጅ ይላል ! አንተስ የት ታውቀዋለህ ?” አለ ሶስተኛው ። ከዚያ ፣ ገለባ እፊቱ ያገኘ ገለባ ውን ፣ ገለባ ያጣ አፈሩን እያፈሰ ፣ ገና ስሙን ያልሰሙትን ሰው ቤት

@OLDBOOKSPDF

እኔ አባይ፣ እኔ እ[illegible] ቢሉ፣ “ ቆዩ ግዴለም እትጣሉ፣ መጀመሪያ የምፈልገውን ሰው ልንገራችሁና ሁላችሁም ታሳዩኛላችሁ ። ውብቱ በዛብህ የሚባል ሰው ታውቃላችሁ ? ” አለ ጥላሁን ፣ በገላጋይ ወግ እመሀከላቸው ገብቶ ሁሉንም እያባበለና እዩላቀ ።

“ አ ! ያቶ ውብቱ ቤት ! የበሻሮንድ ቤት ! ያውልህ ! ይሄውልህ ጋሼ ! ” አሉ ህጻናቱ ፣ ሁሉም ጥሉን ረስተው ከትምህርት ቤቱ አጥር አጠገብ ባጭር ጥሬ ካብ ታጥሮ ፣ ግቢው በጽሬና ባበባ አትክልት ወደ ጌጠ ጥሩ ቤት እጃቸውን እንደ ጭራሮ እንጨብረው እዩተንጫጩ። ወዲያው ፣ አንድ ሰው አዲስ ባንድሮቨር እዩነዳ እዚያ ግቢ ውስጥ ሲገባ ልጆች አይተው ፣ “ እኒያው መጡልህ ጋሼ ! እባቸው ናቸውኮ ጋሼ! እቶ ውብቱ ናቸው ” እሉ አሁንም እዩተንጫጩ ።

“ እግዜር ይስጥልኝ ልጆች ! ሁላችሁም ጥሩ ልጆች ናችሁ ! ሁላችሁ ናችሁ ያሳያችሁኝ ! ” አለና ጥላሁን ፣ ዋጋቸውን የሁሉንም ጉንጭ አንድ ባንድ ደባብሶ ፣ ደስ አሰኝቶ ፣ ወደ ውብቱ ቤት ሄደ ። ካጭር ጊዜ በሁዋላ ፣ ጥላሁን ከውብቱና ከሁለት አሽከሮቹ ጋር ተመልሶ መጥቶ ባለቤቱንና እናቶ ዮሴፍን ከውብቱ ጋር አስተዋወቀ ።

“ እባቸው የዚህ ካሚዮን ጌታ ፣ አቶ ዮሴፍ ብርሃኔ ናቸው ፤ እሱ ወንድሜ ረዳታቸው አቶ ገብረ ሚካኤል ነው ፤ እስዋ የኔ ባለቤት ጽዮን ሞገስ ናት ” አለና ወደ ውብቱ ዘወር ብሎ ፣ “ እሱ ደግሞ አቶ ውብቱ በዛብህ ፣ የኢሉባቦር በሻሮንድ መሥሪያ ቤት ሹም ነው ” አለ ፣ ልጆች ሲሉ የሰማውን ደግሞ ።

“ ምክትል ሹም ” አለ ውብቱ ፣ ጥላሁንን እርሞ ።

“ ያውነው ፣ አንድ ደረጃ ፊሪ ! ” አለ አቶ ዮሴፍ ፣ እንደ ጫሳቅ ብሎ ። ከዚያ ፣ ውብቱ ሶፊያን ሲያነጋግር ፣ ጥላሁን ሂሳቡን ለመዝጋት ካቶ ዮሴፍ ጋር ከካሚዮኑ ትንሽ ራቅ ብለው እንደ ቆሙ ፣

“ ጋሼ ! ኑሮ ባያስገድድና ተግባር ባይኖር ፣ እንዲህ ከስዎ ጋር ሲጉዋዙ መኖር እንዴት ጥሩ ነበር ! ባለቤቴንና እኔን በጣም ደስ ብሎን ነው የመጣን ። እግዚአብሄር ይስጥልን ! ይሄው ቀሪው ሂሳብ ” አለ ፣ አስራ አምስት ብር ከኪሱ አውጥቶ ።

“ እኔ ደግሞ እንዳንተና እንደ ባለቤትህ ያሉ የጉዞ ጉዋደኞች ገንዘብ እዩከፈልሁ የማገኝ ብሆን ደስታውን ባልቻልሁት ! ይሄው የሰጠኸኝ ቀብድ ! ” አለ አቶ ዮሴፍ ፣ እሱም አስራ አምስት ብር ከኪሱ አውጥቶ ።

@OLDBOOKSPDF

"ምን ማለትዎ ነው ጋሼ ?" አለ ጥላሁን ፣ ግራ እንደ መጋባት ብሎት ።

" በጭንት ላይ የምናሳፍራቸውን ሰዎች ገንዘብ ማስከፈላችን የማይከድ ቢሆንም ፣ እንደናንተ ላሉ ሰዎች . . . ገና ታሪፍ አልወጣም ! " አለ አቶ ዮሴፍ ፣ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ ።

"እባክዎ ጋሼ ፣ባይሆን እንኩዋ ቀብዱን ልመልስ አይበሉ!" "ብርሃኔ ይሙት ከናንተ አንድ ሳንቲም አልወስድም ! በጭራሽ የማይደረግ ነውና ይልቅ በከንቱ እዚህ ስንጨቃጨቅ ሰው አናስጠብቅ! " ብሎ አቶ ዮሴፍ እንደ ቀብድ ተቀብሎት የነበረውን አስራ አምስት ብር በጥላሁን ኪስ ከቶለት ወደ ካሚዮኑ ተመለሰ ።

ውብቱ ፣ ጥላሁንንና ሰፊያን ይዞ እቤቱ ሲደርስ ፣ ምሽቱ አቻም የለሽ ፣ ያንድ ዓመት እድሜ ወንድ ልጅዋን ይዛ አታክልቱ ውስጥ እየተዘዋወረች ትጠብቅ ነበረ ። እንደ ደረሱ ፣ ከነልጅዋ ከንግዶቹ ጋር ተዋውቃ ሻይ ተሰናድቶ ስለነበረ ይዛቸው ወደ እንግዳ ቤት ገባች ።

ጥላሁን የጉዋደኛው ግቢ ሰፋትና እዚያ ያዩው ያበባም ፣ የፍሬም አትክልት ማግር ሲያስገርመው ፣ እቤት መጀመሪያ የንግዳ ቤቱን ፣ ሁዋላ የመብል ቤቱን እቃ ሲያይ ፣ ውብቱን እንደ ጉዋደኛ ማየት ምናልባት ሽቅብ መንጠራራት ሆኖ እንዳይቆጠርበት ፣ ከመሰጋቱ ሌላ ፣ " ወገንነቱንም ህዝብ ወደሚጨቁኑ ሹማምንትና መኩዋንንት ሳያዞር አይቀርም"ብሎ ጠርጥሮ ፣ እንደ ልቡ ከመጫወትና ፣ ትንሽ ከመዝናናት ተቆጥቦ አመሸ ።

በንግዳ ቤቱ ከዳር እስከ ዳር ግጥም ብሎ የተነጠፈው ወፍራምና ጌጠኛ የፋርስ ምንጣፍ እንኩዋንስ በግር መርገጥ በጅ መንካቱ ያሳሳል። ያን ሰፊ አዳራሽ በሁለት ክፍለው ፣ በሚያማምሩ ሸንኮሮች በተሰኩ ባለ ቆዳ ድጉስ ጠረጴዛዎች ዙሪያ ተደርድረው የሚታዩ ፣ ከባድና ውድ ወንበሮች ፣ ነሬ ይቅርና አዲስ አበባም በብዙ ኢትዮጵያውያን ቤት አይታዩም ። ባደንቃቸውና በቀለማቸው ከአካባቢው ጋር የሚስማሙ ፣ ጥልፍ መጋረጃዎች ፣ የከፍሉን ሪገ ኙም መስኮቶች ግሩም አድርገው አስጊጠዋቸዋል ። ከጥቁር ሸክላ በሰው አምሳል ተሰርተው ባራቱ ማእዘን ቆመው ፣ የሚታዩት ያበባ እቃዎች ፣ አበባ እስኪያብቡ ቸው በራሳቸው እዬተሸከሙ ራሳቸውን የቆሙ ተቋዋቁር ልጆች ይመሳሰላሉ ። ስዚህ ሁሉ ጌጥ ባንድ ላይ ንጉሳዊ ግርማ ለመስጠት የጃንሆይና የቲጊይቱ ፣ ያሊጋ ወራሹና የሀረሩ መስፍን ትላልቅ ፎቶ ስእሎች ፣ ባራቱ ግድግዳዎች ከፍ ብለው አዩ ተንግጸሩ ተቀምጠዋል ።

@OLDBOOKSPDF

ከንግዳ ቤት ወደ መብል ቤት ሲታለፍ ፣ የክብር እውድማ የሚያክል ሰፊ ፣ ክብ ጠረጴዛ ፣ ግሩም ሆኖ በተጠሰፈ የጠረጴዛ ልብስ እጊጠ በሚያማምሩ ክፋይ ወንበሮች ዙሪያውን ተከብቦ ፣ ልዩ የሆኑ የመብልና የመጠጥ እቃዎች እስኪከብደው ተሸክሞ ይታያል ። የተኛ ራብ የሚቀሰቅሱ ፣ ልዩ ልዩ ብስል ፍሬዎች በዩዛፉ ተንዠርገውና በዴቅርጫቱ ሞልተው ፣ ተትረፍርፈው ፣ የተሳሉባቸው ስሴዳዎች በግርግዳው ዙርያ ተንጠልጥለው ሲታዩ ፣ መብል ቤቱን የፍሬ አትክልት ቦታ አስመስለውታል! ይህን ሁሉ ፣ መብል ቤቱ ያጌጠበትን እቃና ያቆማመጡን ስነስራት ለማሳዬት ፣ የኤሌክትሪክ መብራት እንደማይበቃ ሁሉ ፣ በባለቅርጽ የዝሆን ጥርስ ቀንዲሎች የተሰኩ ሻማዎች እለፍ እለፍ እያሉ ፣ በብዙ ቦታ በርተው ይታያሉ ። "በኤሌክትሪክ ላይ ሻማ ! እስቲ እንዲህ ያለው ከቅንጦት በቀር ሌላ ምን ስም አለው ?" አለ ጥላሁን ባሳቡ ።

ከዚያ ፣ የውብቱን የጊትነት ኑሮ ፣ በትምህርት ቤት ሳለ ስለ ሀብትና ስለ ሀብታሞች ይናገረው ከነበረው ጋር እያስተያዬ ፣ በእርምሞ ይገረም ጀመር ። ሀብትን ሆነ ሀብታሞችን አጥብቆ ይንቅና ይጠላ የነበረው ውብቱ ፣ "ሀብትና ጣእት የፈጠሩዋቸውን ሰዎች መልሰው ለመግዛትና በክፉ መንገድ ለመምራት ሀይል ያላቸው ፣ የክፉ ስራ እማልክት ናቸው" እያለ ይሰብክ የነበረው ውብቱ ፣ ተለውጦ ፣ ሀብትን የሚያፈቅርና ሀብታሞችን የሚያከብር ከሆነ ፣ በሱ ላይ ያልተለወጠና የማይለወጥ ለመሆኑ ፣ የሱን ወዳጅነት አክብሮ የሚጠብቅ ለመሆኑ ምን መተማመኛ አለው ? ምንም !

ጥላሁን የውብቱን ከመጠን ያለፈ የድሎትና የቅንጦት ኑሮ ከተመለከተ በሁዋላ ፣ ስለሱ ያለውን ስሜት ፣ ማለት እንደ ድሮው መሆን አለመሆኑን እስኪያረጋግጥ ድረስ ፣ አገር ለመጎብኘት እንጂ በትምርቱ ወድቆ ፣ ስራ አጥቶ ፣ የሱን ርዳታ ፍለጋ መምጣቱን ላለመግለጽ ባሳቡ ወሰነ ። ስለዚህ ያን እለት ማታ ፣ ውብቱ ሲለፈልፍ ጥላሁን ያኮረፈ ላለመምሰል ያክል ፣ ያውም ላይሆንለት ፣ እልፎ እልፎ አንዳንድ ቃል በጭዋታው መሀል ከመጣልና ለተጠዬቀው ከመመለስ በቀር ፣ በጠቅላላው ከመናገር ተቆጥቦ አመሸ ። ከሱ ይልቅ ሶፊያ ውብቱንም ሆነ ባለቤቱን ከዚያ በፊት እንደምታውቃቸው ሁሉ ፣ እንግድነት ሳይሰማት ደህና ስትጫወት አመሸች ።

"እኔኮ ጎሬ ሲባል እንኩዋንስ እንዲህ ያለ የቤት እቃ ፣ ደረቅ የንጨት ወንበር የሚገኝበት አይመስለኝም ነበር ። እንዲህ ያለ እቃ

@OLDBOOKSPDF

እዚህ ይሰራል ? ወይስ .. ከየት ተገኘ?"አለች ፣ የንግዱ ቤቱንም የመ ብል ቤቱንም እቃ እያደነቀች ።

"የፈረንጅ አገር እቃ ነው " አለ ውብቱ ፣ ትንሽ እንደ መንጠ ራራት ብሎ ።

"እንተ እስመጣኸው?"

"የለም ፣ አንድ ያገለግሉትን ጊዜ ፈጽሞ ወደጎሩ የሚመለስ ፣ የጀርመን ቆንስል ስገብኝት መጥቶ ፣ በከተማችን ደህና ሆቴል ባለመ ኖሩ አገር ሲዞር እንዳይሄድ እዚህ እየተኖማይነው ፣ የሚዝምወርበት መኪና በመሰጠትም ፣ ማንኛውም ሌላ ነገርም በንረዳው ስንብቱን ነበርና፤ እሱ ያሻጠልኝ ነው ። አንድ ቀን ስለቤት እቃ ስንነጋገር ወደጎሩ መመ ለሱ ስለሆነ ፣ ሙሉ የቤት እቃዬን በርካሽ ዋጋ እሸጥልሃለሁ " ሲለኝ ጊዜ ፣ እኔም ፣ " ወሂዱ ከሆነ እውነትም በርካሽ ሳይሸጥልኝ አይቀ ርም ፤ ያለዚያም እሱ የመስተንግዶዬ ባለዳ ባለመሆን ፣ ጊኔ ለገንዘብ የማልሳሳ ለመምሰል ያክል ያወራነው ወሬ ብቻ ሆኖ ይቀር ይሆናል" ብዬ ፣ እቃውን እስጭኖ እዚህ ድረስ ሲልክልኝ ዋጋውን እስከ ማስጫ ኛው ልከፍል ተስማማሁ ። በሁዋላ ለካስ ውሉን የማይስት ፣ ቁም ነገራም ኖሮ ፣ ከዚህ እንደ ተመለሰ በአይሮፕላን አስጭኖ ሲልክልኝ ጊዜ ርካሽ ያለው .. አታንሺው ፤ ራስ ያዞራል ። በአይሮፕላን የተጫነበት ዋጋ ብቻ አንድ ጥሩ የሆነ ፣ ሙሉ የቤት እቃ ሊያስገዛ ይችል ነበር ። ብቻ መቸስ ምን ላድርግ ፤ አንድ ጊዜ ቃል የገባሁበት ነገር ሆነና አፍሬ ከፈ ልሁ ።

"መቸም .. እቃው ምንም ያክል ዋጋ ቢከፈልበት የሚያስጸጽት አደለም ፤ በጣም ግሩም ነው!"አለች ሶፊያ ፣ ለቅንጦት ብዙ ዋጋ መክ ፈል ከሚጠሉት ወገን ብትሆንም አስተናጋጆችዋን ላለማስከፋት ያክል።

"ያን ያክል ያስከፍለኛል ብዬ ያላሰብኩት በመሆኑ ለጊዜው ደንግ ጥሁ እንጂ . . . መጸጸትስ . . . አልተጸጸትሁም ፤ እንዲያውም ሁዋላስ ደስ አለኝ ። መቸስ . . .ሰው በዚህ አለም የሚኖረው አንድ ጊዜ ብቻ እንጂ፣ ሁለተኛ ተመልሶ አይኖር ! ስለዚህ ሀብት ያለው ሀብቱ ሊሰጠው የሚችለውን የደስታ ኑሮ መኖርና ማለፍ ይገባል ባይ ነኝ ። መቸም . . . ሀብት አስፈላጊነቱ መልካም ነገር ለማድረግ መሆኑን የሚክድ የለ ! ታዲያ. . ከደስታ የበለጠ መልካም ነገር አለ ?" አለው ውብቱ ፣ ጥላሁን ዝምታ ስላበዛ እሱን ለማናገር ጭምር ባሽሙር የጎድን እያዩ። ጥላሁን ሰምቶ እዳልሰማ ዝም አለ ።

@OLDBOOKSPDF

"ጥላሁንና እኔ ትምህርት ቤት ሳለን" አለ ቀጠለና ፤ "ጥላሁንና እኔ ትምህርት ቤት ሳለን ፤ ሀብት ምን መሆኑን ገና በቅጡ ሳናውቅ ፣ ስለ ሀብት እናስብና እንናገር የነበረውን ዛሬ መለስ ብዬ ሳስብ ይገርመኛል ።

"ሀብት በባህሪው ንጹህ ሆኖ የተወሰደውን ሰው የሚያበላሽ ፣ አንድ ጊዜ ካበላሸ ቢያጥቡት የማይለቅ ፣ ክፉ እድፍ ነው " እንል ነበር። ታዲያ አሁን ሳየው ፣ እውነተኛው ነገር የዚህ ግልብጥ ነው ፤ "እውነተኛው ነገር ፣ ሰውን ከንቀት ፣ ከውርደት ፣ ከችጋርና እነሱን ከሚመስለው ሁሉ እድፍ አጥርቶ ፣ ሰውን ሲፈጠር በተመደበለት የክብር ቦታ አቁሞ ፣ በውነተኛ የሰውነት መልኩ የሚያሳየው ሀብት ብቻ ነው!" ጥላሁን አሁንም ሰምቶ እንዳልሰማ ዝም አለ ።

"ጥላሁን ምን ትላለህ?" አለ ውብቱ ፣ ጉዋደኛውን በነድን ነት ጉቶ ለማናገር የሞከረው መከራ ሳይሳካለት ስለቀረ ።

"እ? ምን ልበል?"

"ስለ ሀብት ያለህ አስተያየት . . . ትምህርት ቤት ሳለህ እንደ ነበረው ነው? ወይስ. . ተለውጦዋል?"

"እኔኮ ገና አሁን ነው ከትምህርት ቤት የወጣሁ ፤ ስለዚህ . . እንኩዋንስ ፣ እምነቴን እደምታየኝ ልብሴንም አልለወጥሁ!" ሲል ጥላ ሁን ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ ሁሉም ሳቁ ።

"ግዴለም ፤ እዚህ አገር ከቆዬህ ሁሉንም ትለውጣለህ ፤ ልብስህ ንም አሳብህንም ትለውጣለህ ፤ እዚህ አገር መጥቶ ሁለመናውን የማይ ለውጥ የለም!" አለ ውብቱ ።

" ማን ያውቃል ፤ እለውጥ ይሆናል ፤ " አለ ጥላሁን ፣ እከርክር ውስጥ ሳለመግባት ።

" ያስጥርጥር ! አሁን ወስጄ መሬትህን ሳሳይህ ፍጹም እንደምት ለወጥ ርግጠኛ ነኝ ! "

" የምን መሬት ነው ? " አለ ጥላሁን ፣ ያን መሬት ፍለጋ እንዳል መጣ ሁሉ ።

" ምነው 'መሬት ገዝቼልሀለሁ' ብዬ ብዙ ጊዜ ጽፌልህ ! ረሳ ኸው ? "

" እ ! እሱን ነው ? እሱንስ አልረሳሁትም ፤ ብቻ . . ' መጥተህ እየው ' ብለኸኝ ሳልመጣ ስለቀረሁ ፣ ስሌላ ሰው ስጥተኸው ይሆናል ብዬ ነበር እንጂ ! "

" ካልፈለግኸው አንተ ራስህ ትሰጠዋለህ እንጂ ፣ እኔ ላንተ ብዩ የገዛሁትን ለሌላ ሰው እንደማልሰጠው ታውቃለህ ፣ ጥላሁን ! "

"አውቃለሁ" @OLDBOOKSPDF ጓደኛው ሀብታም ከሆነ ፣ "ሳይ ንቀኝ አይቀርም" ብሎ በመጠርጠር ብቻ ፣ የቅድሞሽ ፣ ቀቀይሞ በማምሸቱ እፍረት ተሰማውና ትንሽ እንገቱን እንደ መደፋት አደረገ ።

እርግጥ ፣ በፖለቲካ አስተያየት በኩል ውበቱ የድሮው ውበቱ ፣ ከጥላሁን ጋር ተማሪ ሳለ የነበረ ውበቱ አይደለም ። ሌላ ውበቱ ሆኖዋል። በትምህርት ቤት መቅደሙን እያወቀ ወድቀሀል ተብሎ ፣ ስራ ሲፈልግ ከብዙ ደጅ ጥናትና መንገላታት በሁዋላ ፣ ከመቸገሩ የተነሳ የተፈጠረበትን ሴሊት ከረገመና የመኖር ተስፋውን ወደ መቁረጥ ከቀረበ በሁዋላ ፣ ስራ አግኝቶ ጎሬ ሄደ ። እዚያ ፣ እንዲጋጣሚ ደርሶ የማያውቅ በረከት ከላይ ወርዶ ፣ አንዳንድ ጋሻ የመንግስት መሬት ባምስት ብር እንዲሸጥ ስለ ታዘዘ ፣ እጅግ ብዙ ጋሻ የቡና መሬት ገዝቶ ፣ ከዚያ በከተማው ዙሪያ እዩተቆጣጠረ ማሰራት የሚችለውን ያክል አስቀርቶ የተረፈውን በውድ ዋጋ ሽጦ ፡ ድንገት ባለብዙ ሀብት ሆኖዋል ! ከዚያም . . . ሀብት ካለ ምን የለም ? እድሜ ለሀብቱ ፣ የብዙ ዘመን አገልግሎትና የስራ ልምድ ካላቸው ቀድሞ የኢሉባቦር ምክትል በጅሮንድ ሆኖ ተሾሞዋል ! የኢሉባቦር ሰው ሁሉ እጅ የሚነሳው ፣ ጤና ይስጥልኝ እንጂ እንዴት ዋልህ እንዴት አደርህ የማይባል ፣ ገና ከሰላሳ አመት የማይበልጥ ጉልማሳ ሳለ ፡ እርስዎ እንጂ አንተ የማይባል ፣ ደግሞ ገና ከዚያ በላይ ላለው ደረጃ ሁሉ የታመነ ተስፋ ያለው ፣ ባገሩ አለ የተባለ ሰው ሆኖዋል ! በግል ኑሮውም የሚወዳትና የምትወደው ምሽት አግብቶ ፣ ልጅ ወልዶ ፡ ለቤቱ በስራው አይነት ልክ ፣ ብዙ ሴትና ወንድ ሎሌዎች ቀጥሮ ፣ በጥላ ጎሬ የማንም ፣ ያገሬ ገገፉ እንኳዋ በሴለው አይነት ቤት ደልቶትና ደስ ብሎት የሚኖር ፣ በዚያውም መጠን ስለ አለሙ ያለው እምነት ይሁን አስተያየት ፣ ጥላሁን በትምህርት ቤት ሳለ ከሚያውቀው ፣ ድሀው ውበቱ ከነበረው እምነትና አስተያየት ሌላ ሆኖዋል! ነገር ግን ይህ ሁሉ ፣ ይህ የውበቱን የፖለቲካ ይሁን የኢኮኖሚክና የማኅበራዊ እምነትና አስተያየት የለወጠው ነገር ሁሉ ፣ ለጥላሁን የነበረውን ፍቅር የሰናፍጭ ቅንጣት ያክል አልነካወም ፤ ለጥላሁን ያው የትምህርት ቤቱ ውበቱ ነው !

"እስቲ አባክህ እንዲያው . . . ጭምት ቢጠይቅህ ፣ 'ምን ሆንሁ' ብለህ ነው ፣ እሰው ቤት እንግዳ ሆነህ መጥተህ ያን ያክል ስታስቸግር ያመሸህ?" አለች ሶፊያ ፣ ከራት በሁዋላ ውበቱ የመኝታ ቤታቸውን አሳይቶዋቸው እንደ ተመለሰ ። ሶፊያ ለስዋ ግልጽ ባልሆን ምክንያት ፣ ባልዋ እንደ ህጻን አኩርፎ ውበቱን ሲያስቸግር ስላመሸና ፣ አቻምየለሽም ታዝባው ከንፈርዋን ስታበላልጥበት ያዩች ስለ መሰላት እፍራ ፣

ራት እልፉ ወደሚ @OLDBOOKSPDF ድና ምክንያቱን እስክትጠይቀው ቸኩላ ፣ ጊያንዳንዱ ደቂቃ አመት መስሎ ታይቶዋት ነበር ።

« ምናባቱን ላድርግሽ አታተኚ እንጂ ያልተቀየምሁ ለመምሰል ሞክሬ ነበርኮ ፣ ብቻ አልቻልሁም ፣ ይቅርታ አድርጊልኝ ሰሬ ! »

“ለመሆኑ ምን የሚያስቀይም ነገር አዩሁ ፣ ወይም ሰማሁ ከእንኳን ምንስ ጉዋደኛውን ፣ የወለደውን ልጁን ቢሆን . . እኖ ውብቱ ዛሬ እንቶን ሲቀበል ደስ ነሰው የበለጠ ደስ ብሎት የሚቀበል ሰው አለ ?”

“እውነትሽ ነው ፣ ... በመስተዋትዋ በኩል ደህ ነደለው የምለው ነገር የለም ። እኔም በዚህ ምክንያት ነው ደስ ያለኝ ለመምሰል ቀጣቀል የነበር ፣ ብቻ መጀመሪያ እቤት ስገባ ያዩሁት ፣ ጭራሽ ያልጠበቅሁት ነገር ልቤ ተቀየጠረች መፍታት አቃተኝ ።”

“እኮ ምንድነው ያዩሽው ?”

“እዩሽ ፣ ውብቱን ሳውቀውና ስወደው ዛሬ እንዳገኘነው ሆኖ አልነበረም ፣ አንቺ አታውቂውም እንጂ ሌላ ነበር ። እኔ የማውቀውና የምወደው ውብቱ ፣ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ደስ ብሎዋቸው የሚኖሩበት ሠራተኛ ማህበር ተፈጥሮ ፣ እሱም እዚያ ውስጥ እንደ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ፣ ከኢትዮጵያውያን ሁሉ ጋር ፣ ደስ ብሎት መኖር እንጂ ፣ በድሀ ሕዝብ መሀከል ብቻውን ሀብታም ሆኖ መኖር ፣ ሌላው ርቃኑን ይከድንበት ሲያጣ መሬት በሀገር ምንጣፍ እያስጌጠ መኖር የሚፈልግ አልነበረም ። በድሀ ህዝብ መሀከል ጌቶች ሆነው መኖር የሚፈልጉትን ሁሉ ‘በራቁት ድንጋዮች መሀከል በወርቅና በአልማዝ አጊጠው እንደ ተቀመጡ ጣኦቶች የሚቆጠሩ ናቸው’ እያለ የሚዘልፍ ነበር ፣ እኔ የማውቀውና የምወደው ውብቱ ጉልበቱን ፣ እውቀቱንና ሰርቶ የሚያገኘውን ሀብቱን ፣ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ደስ ብሎዋቸው ለሚኖሩበት ስራተኛ ማህበር መስዋእት አድርጎ ለመስጠት የማለ እንጂ ፣ ዛሬ እንደ ነገረን ‘ሀብት የደስታ ኑሮ ለመኖርና ለማለፍ ነው’ ብሎ የሚያምን አልነበረም ፣ ባጭሩ እኔ የማውቀውና በራሴ ውስጥ የነበረ ፣ እዚህም ስመጣ ‘አገኘዋለሁ’ ብዩ ተስፋ ያደረግሁት ውብቱ ፣ ከማናቸውም ነገር የኢትዮጵያን ህዝብ የኑሮ መሻሻል የሚያስቀድም ፣ ሀብት መሳሪያነቱ ለጠቅላላው ህዝብ የኑሮ መሻሻል ከሆነ ለብቻ ሲይዙት ፣ ውሎ አድሮ አገልጋይ መሆኑ እዩቀረ ተገልጋይ ከቶ የሚያሰራ ፣ ከቶ ጌታ መሆኑን የሚያምንና የሚጠላ ነበር ፣ ነገ ግን በዚያ ፈንታ ሌላ ውብቱ ፣ ጭራሽ የማላውቀው ውብቱ አገኘሁ ! ታዲያ . . . ፈልጌው በመጣሁት ፈንታ ሌላ ውብቱ ሳገኝ ፣ እኔ የማ

@OLDBOOKSPDF

ውቀው ውበቱ ይጠላው የነበረውን ሁሉ የሚወድ ፤ እኔ የማው ቀው ውበቱ ይቃወመው የነበረውን ሉሉ የሚደግፍ ፤ ሰው የሚ ኖረው ለጌጥና ለቄንጥ መሆኑን የሚያምን ውበቱ ሳገኝ አልደንግጥ ግራ አይገባኝ ? እውነቱን ልንገርሽ ደነገጥሁ ፤ ፈራሁ! እንዲያውም ይህን ያክል ከተለወጠ ፣ በትምህርቴ ወድቄ ፣ ስራ አጥቼና ተቸግሬ ፣ የሱን ርዳታ ፍለጋ መምጣቴን የነገርሁት እንደሆነ ፣ "ወግድ አላውቅህም" ብሎ እንዳያዋርደኝ ፣ አገር ለመንብኘት የመጣን መስለን ከሁለትና ከሶስት ቀን በሁዋላ የምንመለስበትን ዘዴ ሳሰላስል ነበር! ሁዋላ ግን ስለኔ ያለው ስሜት ምንም ያክል እንዳልተለወጠ ከሁኔታው ሁሉ ስለተ ረዳሁ . . . ምንም እንኩዋ መለወጡ በጠቅላላው ቢያሳዝነኝ ፣ ያላዘንሁ ለመምሰል ጠንክሬ ነበር ብቻ አቃተኝ . . . አላውቅበት አልሁ !"

"ለመሆኑ ይህን ያልኸውን ሁሉ መሆኑን ፣ እንዲህ እንዳልኸው መሆኑን ፣ ምን ጊዜ አገኘህና ተረዳኸው? ገና ዛሬኮ ነው የመጣን ጥላዬ! ለዚያውም ገና ከመግባትህ የቤቱን እቃ ስታይ ፣ እንደ ተቀጣ ህጻን ከንፈርህን እየሞጥሞጥህ ተቀመጥህ ! ለመናገር እንኩዋ ቢፈልግ . . . በገዛ ቤቱ መንገድ እያጠርህ ከለከልኸው!"

"ምን እንዳይናገር መንገድ አጥርበታለሁ ? መቸም . . .ምን መሆኑን ለመግለጽ የሚበቃ ያክል ተናግረዋልኮ ! 'ሰውን ሲፈጠር በተ መደበለት የክብር ቦታ እቁሞ የሚያሳይ ሀብት መሆኑን ፣ ሰው በአ ለም የሚኖረው አንድ ጊዜ ብቻ ስለሆነ ፣ ደስታ የተባለ ነገር ሁሉ እንዳያመልጥ ፣ በገባበት ገብቶ እያሳደዱ መደሰት አስፈላጊ መሆኑን፣ የሰው መኖር አይተነኝ አላማው ደስታ ስለሆነ ፣ ሀብት ሊሰጠው የሚ ችለውን የደስታ ኑሮ መኖርና ማለፍ የሚገባ ነው' ብሎ የሚያምን መሆኑን ፣ ይህን ሁሉ ነግሮናል ! ታዲያ ይህን ሰምቶ ምን መሆኑን ለመረዳት አንድ ማታ ያንሳል ነው የምትይ ? ለዚህ ረዥም ጊዜ ያስፈ ልጋል ?"

"የለም ጥላዩ ፤ እንዲያው መከራከር ፈልገህ እንደሆነ ነው እንጂ፣ ሀብትን እያጋነነ የተናገረውን ሁሉ ፣ አንተ እኩርፈህ ዝም ስላልህ ፣ አንተን ለማናገር በቀልድ መልክ የተናገረው መሆኑ ግልጽ ነበር ፤ ይህን አንተም ታውቃለህ ። እንደ እውነቱ ከሆነ አንተ የተቀዬምህ በቤቱ እቃ ነው ። ስለ ቤቱ እቃም ቢሆን ፣ ማንም ገንዘብ ለጌጥና ፣ ለቄንጥ ማባከን የማይወድ ሰው ፣ ለምሳሌ እኔ ፣ ወይም . . አንተ በሱ ቦታ ብንሆን ፣ እቃ መግዛት ከፈለግን ፣ እቃ መግዛቱን ጨርሰን ካልተውነው በቀር ፣ እሱ ካሰበው የተሻለ የቁጠባ ዘዴ ፈልገን የምና ገኝ አይመስለኝም ። ልብ አድርግ ፣ መጨረሻው ርሱ እንዳሰበው እለ መሆኑ ፣ እቃው እዚህ ሲደርስ ከነመቶው በላይ ዋጋ እንዲከፍል መጠየቁ ፣ እሱ . . ሌላ ነገር ነው ።"

@OLDBOOKSPDF

“ ታዲያ የቁጠባው ዘዴ የት ላይ ነው ? ”

“ ከሁሉ አስቀድሞ ፤ ውራጅ እቃ ለመግዛት መፈለጉ ለቁጠባ መሆኑ የታወቀ ነው ። በዚያ ላይ እንዲያ ያለው ውራጅ እቃ ፤ ‘ አገ ልግሎቱን ጨርሶ ወዳገሩ የሚመለስ የውጭ አገር ሰው ሲሆን ፤ ሙልሶ ጭና ስለማይወስደው አገር ውስጥ ከሚኖር ሰው በጣም በረከሰ ዋጋ ሳይሸጠው አይቀርም ’ ብሎ ቢገምት ፤ ‘ግምቱ ከውነት የራቀ ነው ’ ሊትል አትችልም ። ይልቁንም አቶ ውቤ እንደ ነገረን የቃ ውን ባለቤት ፤ ቆንስሉን ፤ እዚህ ሲያስተናግደውና ሲረዳው የሰነበተ ስለሆነ ፤ ‘ ቢያንስ ቢያንስ ልዩ አስተያየት ሳያደርግልኝ አይቀርም ’ ብሎ ቢገምት አሁንም ግምቱ ከመንገድ የወጣ ነው ሊባል አይች ልም ። ስለዚህ ፤ በኔ አስተያየት በቆንስሉ ይሉኝታ ቢሰነት እቅዱ ይታወስበት እንጂ ፤ አቶ ውቤ ጥሩ የቁጠባ እቅድ አቅዶ ኖሮዋል እላ ለሁ ። ”

“ ጥሩ ነው ፤ ይሁን ፤ ሊሆን ይችላል ፤ ሙችም . . . ነገር ከየት ወገን ቆመሽ እንደ ተመለከትሽው ነው ። ብቻ . . ያም ሆነ ይህ ፤ ቅድም እንዳልሁሽ ገና ስገባ ያዩሁት ስለ ውቤ በራሴ ውስጥ ይገኘው ከኖ ርሁት ፤ ስለሱ ከማስበው ጋር ባለመስማማቱ ተጋጭቶ ፤ በውስጤ መጥፎ ስሜት ፈጠረና ፤ ያን ስሜት ማስወገድ ፤ መሸፈን እንኪዋ አቅ ቶኝ ነው እንጂ ፤ ወድጄ ስላልሆነ . . በራሴ ፈርጃለሁ ! ይልቁንም መቀ የሜን ምሽቱ እንዳታውቅብኝ ፤ በማታውቀኝ በምሽቱ ፊት ቀልዬ እንዳልታይ ፤ ስሜቴን ለመሸፈን ብሞክር ባልችል ስለቀረሁና ማኩ ረፌን ያወቅችብኝ ስለመሰለኝ በጣም ነው የቆጨኝ ። ”

“ ታውቃለች እንጂ እንዴት አታውቅም ? እንዲያውም ታዝባህ ይሆን ፤ ወይስ . . እኔ እንጃ ፤ እንተን እያዩች ከንፈርዋን ስታበላጥ አይቻታለሁ ። በዚያ ላይ . . . እሱ ማዘኑ መልካም አይደለም ። ”

“ እሱ እንኪዋ አያዝንም ! ”

“ እንዴት አያዝንም ? ቤት አድራጊ ቤቱ አድራጎቱን ዋጋ ሲያሳጡ በት አያዝንም ? አንተ ሳትጠይቀው ራሱ እስዐ እምብት ጋሻ መሬት በገንዘቡ ገዝቶ ፤ ሳታስታውቀው ፤ ሳታስጠንቅቀው ድንገት ሁለት ራስህን በትመጣበት ደስ ብሎት ተቀብሎ ፤ ደስ ሲያሰኝህ ያን ያክል ሲሞገር እያዩኸው ፤ በማመስገን ፈንታ እንደገና ስታኮርፈው ማዘን ይብዛበት ? ”

“እንዲህ እመላሲስ መሆኔን ስለማያውቅ ፤ ይህን አመለቢስ ቴን ተቀብሎ ፤ ከናመስቢስነቴ ስለሆነ የሚወደኝ ፤ ይቀዩማል ብለሽ አትበዪ ። እያሆሽ በዚህ ሲጋት አይግባሽ ! ” አለ ጥላሁን ፤ ሁለት እጆ ቹን በትክሻዎችዋ ፊትን በራሱዋ ላይ አስደግፎ ሚስቱን እያባበለ ፣

@OLDBOOKSPDF

## ምእራፍ ፲፪

## ያሳዩ መብራቱ ደብዳቤ

“ ገና አልተነሳችሁም ? ቁርስ ደርሶዋል ትላለች እቾሚ ” አለ ውብቱ ፣ በማግሰቱ ጥዋት ወደ እንግዶች መኝታ ቤት ሄዶ በር እየ መታ ።

“ ተነስተናል ግባ ” አለ ጥላሁን ፣ ከምሽቱ ጋር ከመስኮቱ አጠገብ ቆመው የጥዋቱን ድምቀትና ያካባቢውን ውበት እየተመለከቱ ከሚያደንቁበት ። መቸም ካልዘነበ ፣ የጎሬ ጥዋት እጅግ ደስ የሚያ ሰኝ ፣ ልዩ ነው ። ውብቱ በሩን ከፍቶ ሲገባ ፣ እዚያ በመስኮት ቆመው እንደሚያደንቁት ደማቅ ጥዋት ፣ ፊቱ ሁሉ በደስታ ወገግ ብሎ አዩ ችና ፣ ሶፊያ በጣም ደስ አላት ። “ እውነትም አልተቀዩመም ፤ እንዴት ጥሩ ሰው ነው ! እንዴት ትልቅ ሰው ነው ! ” አለች በልቡዋ ።

ከቁርስ በሁዋላ ፣ ውብቱና ጥላሁን ሁለቱን ሴቶች እቤት ትተው ፣ መጀመሪያ ባንክ ፣ ከዚያ ወደ ጠቅላይ ግዛቱ ጽህፈት ቤት ሄደው ፣ ውብቱ ጥላሁንን ጠቅላይ እንደራሴው ባይኖርም ከዲሬክተሩና ከሌሎች ሹማ ምንት ጋር አገናኝቶ ፣ አስተዋውቆት እንደወጡ ፣ እዚያው አግቢው አጠገብ ፣ ወደ አንዲት ዛፍ ስር ሄደው ተቀመጡ ። ከጎሬ ተራራ ደግሞ በተለይ የጠቅላይ ግዛቱ ጽሕፈት ቤትና የንደራሴው መኖሪያ ያሉ በት በጣም ከፍተኛ ስለሆነ ፣ ከዚያ የኢሉባቦርን ዙሪያ ዘቅዝቆ ማየት እጅግ ደስ ይላል ። ይልቁንም ከዚያ ቦታ ወደ ሰሜን ፣ ከዚያ ወደ ምእራብ ፣ ከዚያም ወደ ደቡብ ሲመለከቱ ፣ አይን ሄዶ ፣ ሄዶ ፣ የሚያቆ መው ያጣና በመጨረሻ እጨለማ ውስጥ ገብቶ ይጠልቃል ። አሳብም አይን በሄደበት ተከትሎ ሄዶ ፣ እዚያው ይቀራል !

ጥላሁን አይኑን ሳያረግብ ወደ ሰሜን አቅጣጫ አተኩሮ ፣ አፉን ከፍቶ ፣ አንድ ቃል ሳይናገር ዝም ብሎ እንደ ተቀመጠ ብዙ ስለቆዩ፣ እዚያ በሚያየው የተመሰጠ መሆኑን ተረዳና ፣

“ እንዲህ ያለ አገር አይተህ ታውቃለህ ? ” አለ ውብቱ ። ጥላ ሁን አልሰማም ።

@OLDBOOKSPDF

"ምን ሆንህ ?" አለ ውብቱ ፣ ድምጹን ከፈተኛው ከፍ አድርጎ።

"እ ? ምን አልኸኝ ?" አለ ጥላሁን ፣ ከንቅልፉ እንደ ተቀሰቀሰ አይኖቹን እያሻሸ ።

"እንዲህ ያለ አገር አይተህ ታውቃለህ ወይ ብዬ ብጠይቅህ አልሰማኸኝም መሰለኝ ፤ ዝም አልኸኝ ።"

"አልሰማሁም ፤ ግሩም የሆነ ቦታ ነው ። ለመሆኑ ጎሬን ከተማ እንዲሆን ማነው የመረጠው ?"

"ራስ ተሰማ ሳይሆኑ አይቀሩም ፤ ብቻ . . . አጣርቸ አላውቅም ። ፴ንዳንድ እዚህ አገር የተሰሩ ሰራዎች ስማቸው ጎልቶ የሚሰማ ግን የራስ ናደው ነው ።"

"ላይን ደስ የሚያሰኝ ከመሆኑም ሌላ ፣ ለጤናም ተስማሚ ሳይ ሆን አይቀርም ።"

"አዩሩ ለጤና በጣም ተስማሚ ነው ፤ ስለዚህ ጎሬ የጠቅላይ ግዛቱ ዋና ከተማ ከመሆኑ ይልቅ ፣ የጥሩ አዬር ርዳታ ለሚያስፈልጋ ቸው በሽተኞች ማስታመሚያዎችና ማገገሚያዎች ተሰርተውበት ጤናቸው የታወከባቸው ሰዎች በህክምና እዬተረዱ የሚያርፉበት ቢሆን ጥሩ ነበር ። ለዋና ከተማነት ግን . . . በቂ ውሀ ካለመኖሩም ሌላ ፣ መሬቱ የሚበዛው ገደላማ ስለሆነ ፣ መንገዶችንና ሌሎችንም ፣ ለከ ተማ ህዝብ አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች አሙዋልቶ ለመስ ራት በጣም አስቸጋሪ ፣ ምናልባትም የማይቻል ይሆናል " አለና ውብቱ ፣ ሁለቱም ዝም ብለው ትንሽ እንደቆዩ ፣

"እስቲ እንካ ይህን ወረቀት አንብበው " አለ አንድ ወረቀት ከኪሱ አውጥቶ ።

"ላንተ የተጻፈኮ ነው !" አለ ጥላሁን ፣ ወረቀቱን ከታጠፈበት ዘርግቶ ፣ ገና አድራሻውን ከማየቱ ።

"ፈቅጀለሁ ፤ አንብበው " አለ ውብቱ ፣ ትንሽ ፍርጥም ብሎ ።

"ህምሌ ፲፮ ቀን . . .

የኪ ፤

ወንድሜ ፣ ወዳጄ ፣ አቶ ውብቱ በዛብህ ፤

ላንተና ለቤተሰብህ ጤንነት ያለኝን በጎ ምኞት እዬገለጽሁ ፣ የአክብሮትና የናፍቆት ሰላምታዬን አቀርባለሁ ።

አንተና ወይዘሮ እቻሜ ፣ "እንመጣለን" ብላችሁ ስንጠብቃ ችሁ መቅረታችሁን ሳታስታውቁን እንዲሁ ዝም ብላችሁ ስለ ቀራችሁ

ኪሴ እንኩዋ መኖሩ@OLDBOOKSPDFነው ፤ "እሲቃው የበደለው ጭፍራ ቢያኮርፍ ፤ ቅጣት ያተርፍ " የሚሉት ተረት እንዳይደርስብኝ ፤ ብበደልም እንዳልተበደልሁ ዝም አላለሁ ፤ የጠብ ግን ጭፍራ ባለመሆንዋ ፤ የማኩረፍ ነጻነት ስላላት ፤ አኩርፋችሁዋለች ።

አሁን ይህን ደብዳቤ ለመጻፍ አይነተኛ ምክንያት ወደ ሆነው ነገር ልመለስና ፤ አባክህ እኔን ባላይራ ላደረግኸኝ መሬት ፤ በስራው ወራት የሚያስራና ሰብሉን ጠብቆ የሚያሰበስብ ፤ የጥቅም ተካፋይ የሆነ ሁነኛ ሹም አድርግበት ። ቡናው በዱጊዜው ቢሰራና ሰብሉ አዩ ተጠበቆ ቢሰበሰብ ፤ ለስራውና ባሰራው የሚያስፈልጓውን ወጪ ችሎ ፤ ባለንብረቱን ራስ የሚያስችል ፤ ጥሩ መሬት ነው ። እኔን ስራዩ አልለቀኝ ስላለና ፤ እቤት ያሉትን አሽከሮች ጠብቁልኝ ስላቸው ከሴቦች ጋር እዩተሻረኩ ፤ በወዲያኛው አመት ሰብሉ እንዲሁ ባክኖ ቀረ ። በዚህ ባለፈው አመት ግን ፤ ምንም እንኩዋ ፍሬ ደህና አድርጎ እንዲያፈራ የመከነው ክሳዩ እዩተቀረጠ ባይከላለትና ፤ ባይቃረም ፤ እንዲሁ ጫካ ከበላው የተረፈውን አስለቅሞ ፤ እርቦ የሚወስድ አድርጌበት ነበር። ለኛ የደረሰው ሶስት እጅ እዚሁ ለንጋዴ ተሸጠ ፤ አምስት ሺህ ሁለት መቶ አምሳ ብር ሰለ ሆነ ፤ ይህን ገንዘብ በአቶ ደስታ አላላ እጅ ልኬልሀለሁና ፤ መቀበልህን ይዘን ወረቀት በሚሰጥህ ፤ በአቶ ሰይፈ ሚካኤል የማነ በኩል ጻፍልኝ ። ነገር ግን በደንብ እያሰራ ሰብሉን በጥንቃቄ ጠብቆ የሚሰበስብ ሁነኛ ሹም የማታደርግበት ከሆንህ ፤ ቢሸጥ ይሻላል ። ዛሬ እንደሉ ያለ ፤ ከከተማው የሚዋሰን መሬት ቢያንስ ቢያንስ ፤ እያንዳንዱ ጋሻ ከአራት ሺህ ብር ባነሰ ስለማይደፈር ፤ እኔን ከማያስወቅሰኝ እንድሸጠው ከባለንብረቱ ውክልና አስጥተህ እንድትልክልኝ አደራ እልሀለሁ ። ውሳኔህን ቶሎ ጻፍልኝ።

አክባሪ ወዳጅህ ፤
አሳዬ መብራቴ"

ጥላሁን ድምጹን ሳያሰማ ደብዳቤውን አንብቦ ሲጨርስ ፤ እንዲሁ ዝም እንዳለ ቀና ብሎ ጉዋደኛውን ይመለከት ጀመር ።

"ስላንተ መሬት የተጻፈ ነው ፤ ገንዘቡ ይኸው ። አዲስ አበባ ለመምጣት አስቤ ስለነበረ ፤ 'ይገርልህ እመጣለሁ' ብዬ ነበር ያቆዩሁት" አለ ውብቱ ፤ ያንሉት ጥዋት ከባንክ ያወጣውን አምስት ሺህ ሁለት መቶ አምሳ ብር በአንቬሎፕ እንዳለ ከኪሱ አውጥቶ ። ጥላሁን እስከዚያ ቀን ድረስ እንኩዋንስ ያምስት ሺህ ብር ጌታ ሊሆን ፤ አምስት ሺህ ብር ሂሳብ ሲማር በመጽሐፍ ፤ ወይም በወረቀት ላይ ካልሆነ ፤

@OLDBOOKSPDF

በጁ ቆጥሮ ስለማያውቅ ማወቅን አቅቶት ፤ የውብቱን ገንዘብ ተሸክሞ የተዘረጋ እጁ እያየ ዝም አለ ።

"እንካ እንጂ ፤ ያንተ ገንዘብኮ ነው!" አለ ውብቱ ።

"የቷ? እንዴት . . ?" አለና ጥላሁን ፤ አይኖቹ በጉዋደኛው ብር ተሸክሞ የተዘረጋ እጅ ላይ እንደ ተተከሉ ፤ አሳቡ ድንገት ያምስት ሺህ ሁለት መቶ አምሳ ብር ጌታ የሆነበትን ምክንያት ፍለጋ ሄደ ። "ለመሆኑ ይህ ነገር እውነት ይሆን ፤ ወይስ ውሸት ነው? ውብቱ የድሮ እም ነቱን ለውጦ ጌትነት የማያመልክ በመሆኑ እንደ ተቀዬመው አይቶ ሊፈታተነው የፈጠረው ተንኮል ይሆን ? እውነትስ ቢሆን ስርቶ ያላ ገኘውን ፤ ያልደከመበትን ገንዘብ መቀበል ይገባኛል? ያልሠራበትን ፤ ያልደከመበትን ገንዘብ የሚቀበል ከሆነስ ፤ በሰው ድካም ፤ በሰው ላብ ፤ በሰው ትከሻ በመኖራቸው ከሚንቀሳቀሰው ሰነፎች ፤ ተበሬዎች ፤ ልዩ ነቱ ምኑ ነው? "እንዲህና እንዲህ" የመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ እን ዲሰጣቸው በራሱ ውስጥ እየተንጫጩ ሲያስቸግሩት፡

"ምን ሆንህ?" አለ ውብቱ ።

"እ? ምንም አልሆንሁ ፤ እንዲያው . . . ገርሞኝ ነው!" አለ ጥላሁን፣ ትንሽ ፍርጥም ብሎ ፤ በራሱ ውስጥ ይተራመስ የነበረውን ልዩ ልዩ አሳብ ሲመለከቱ ፈዝዘው የነበሩ አይኖቹን እያሻሸና እያርገበገበ ።

"ምን የሚያስገርም ነገር አገኘህ?"

"መሬቱስ እሰቲ ይሁን ፤ ቡናው ደግሞ መቼ ሄጄ የተከልሁት ነው . . . አሁን አፍርቶ ፤ ተሸጦ ፤ ይህን ያክል ገንዘብ ያስገኘ ?"

"ስትተክለውና ደህና አድርገህ ስትሰራውማ አሰጣጡ እንዲህ አይደለም ፤ ሌላ ነው ። ይህ ፤ 'ወፍ ዘራሽ' ወይም ባጠቃላይ ስም ፤ 'የጫካ ቡና' ከሚሉት የተገኘ ነው ። ወፎች ከቡናው እሸት ስጋውን በልተው ፤ ወለላውን መጥጠው ፤ ፍሬው በዬወደቀበት እዬበቀለ ፤ በጊዜ ብዛት ከሚራባው ሌላ ፤ ከዚያ ሳይለቀም እዬፈሰሰ የሚቀረው ፤ በብዛት ይበቅልና ባንድ ላይ የጫካ ቡና ይሆናል ። ካሳዬ ደብዳቤ እንዳዬሽው ከዚያ የጫካ ቡና ፤ አስለቃሚው ላስለቀመበት ዋጋ ሩቡን አንስቶ ፤ ሶስቱ ሩብ የተሸጠበት ይህ ነው ፤ እንካ እባክህ!"

ጥላሁን ምንም እንኩዋ ጉዋደኛው ስለጫካ ቡና የነበረው ባሳቡ ለተነሱበት ጥያቄዎች ሁሉ በቂ መልስ ለመሆኑ ርግጠኛ ባይሆን ፤ ገንዘቡን ተቀብሎ ቆጠረና ፤

"አዎ ፤ አምስት ሺህ ሁለት መቶ አምሳ !" አለ ፤ ውብቱን ቀና ብሎ እያዬ ።

@OLDBOOKSPDF

“ከሱ ሰላሳ ብር የምከፍልህ ፤ እያንዳንዱ ጋሻ የተገዛበት አምስት ብር ፡ ለስም ማዛወሪያ አንድ ብር ፡ ድምር ስድስት ብር ፡ ባምስት ሲበዛ ሰላሳ ብር ይሆናል!” አለ ውብቱ ፡ ሰላሳውን ብር ለመቀበል እጁን ዘርግቶ ።

“ይህ መሬት የሰጠሽኝ እንጂ የገዛሁት አደለም ፡ ውብቴ ! ስለዚህ ሰላሳውን ብር ብትወስድም ባትወስድ ፡ “ውብቱ የሰጠኝ መሬት እንጂ ምንጊዜም ቢሆን የገዛሁት መሬት ነው”አልልምና ፡ ይህን አውቀህ ውሰድ ” አለ ጥላሁን ፥ ውብቱ የመሬቱን ዋጋ እንዲመልስለት የጠየቀው እሱን ፡ ጥላሁንን ባለዳነት እንዳይሰማው ብሎ እንጂ ፡ እውነት ገንዘቡን ፈልጎ አለመሆኑን ስለተረዳ ፡ ለስሜቱ ያን ያክል በመጠንቀቁ ልቡ ተነክቶ ።

“እሺ እንዳ ፈቀድህ ፤ ይቅር ” አለ ውብቱ ፡ እጁን ከዘረጋበት ሲሰበስብ ። “መቸም እዚህ ከደረስህ መሬትህን ሳታይ አትሄድ ! በተለይ አሁን ፡ ቡና የሚለቀምበት ጊዜ ስለሆነ በጣም ደስ ይላል ” አለ ቀጠለና ፡ ትንሽ ዝም ብለው ከቆዩ በሁዋላ ።

“እንዲያውም . . እዚያ ልንቀመጥኮ ነው የመጣን ፡ ውብቴ !” አለ ጥላሁን ፡ ጉዋደኛውን በቅርታ አይን እየተመለከተ ።

“ የኪ ? ”

“ አዎ ፤ የኪ ። ”

“ እዚያ በስራ ተመድበህል ? ”

“ ተመድቤ ነበር . . በሁዋላ ‘ እኔ የተመደብሁበት ስራ ለሌላ ፡ ቀድሞ ጠይቆ ለነበረ ሰው ተሰጠ ስለተባለ’ እዚያ አንተ የገዛህልኝ መሬት ትገዛ አለችኝና ፡ ‘ እሱን እያለማን ፡ ወዲያውም የዚያ ክፍል ህዝብ ኑሮውን እንዲያሻሽል በምክርም ፡ ሰርቶ በማሳየትም ፡ እየረዳን ጥቂት አመታት ብንቀመጥ ፤ እኛም . . ስለ ገጠሩ ኑሮ ልንማር ስለ ምንችል እንጠቀማለን ’ ብለን ሶፊና እኔ በዚህ ተስማማን ። ”

“ በጣም ጥሩ አሳብ ነው ፤ ለጊዜው . . . ምቾት ባለመኖሩ ትቸገሩ ይሆናል ፤ ነገር ግን የማይለመድ ነገር የለምና ትለምዱታላችሁ ። ወዲያውም እዚያ ከቆያችሁ ለኑሮ በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ገነሮች ፡ እዚያው ማሰናዳት ትችሉ ይሆናል ፤ ‘ ችግር ሲበረታ ለመፍጠር ያስገድዳል’ እንደሚሉት ነው ! ” አለ ውብቱ ፡ ፍርጥም ብሎ ።

“ ልክ ነው ፤ ወዲያውስ . . . ተቸግሮ ያስተማረን ህዝብ ተቸግሮ መርዳት አይገባም ? እኛ . . ባለዳዎች ነንኮ ! ህዝቡ በድሁ አቅሙ ፡ ከእ

ሰት ጉርሱና ከመ[illegible]@OLDBOOKSPDFችን እያስተማረ ለማሳደግ ውን ሀብቱን ባገለግሎት መክፈል አለብን ” አለ ጥላሁን ፣ ወብቱን ፊት ለፊት እያዩ ።

“ የኢትዮጵያ ልጆች እዩ-ተማሩ ማደግ መብታቸው አይደለም ፣ እዳ ነው ማለት ነው ? ” አለ ውብቱ ፣ ያሽሙር ፈገግታ ፈገግ ብሎ ።

“ እንዴታ ! መብታቸው ነው እንጂ ! ”

“ እኛስ የኢትዮጵያ ልጆች አይደለንም ? ”

“ ነን ”

“ ታዲያ በመብታችን ስለ ተጠቀምን ለምን ባለዳዎች እንሆናለን፣ ”

“ ሰውን ባለመብት የሚያደርገውኮ የፈጸመው ተግባር ነው ፣ ተግ ባሩን ሳይፈጽም በመብቱ የተጠቀመ ሁሉ ባለዳ ነው ። ”

“ እሱ እውነት ነው ፤ ብቻ እኛኮ . . . (እሱቱ ራሲንም በመንግ ስት ስራ ውስጥ እንደሌለሁ ፤ እንደ ህዝብ ልቁጠርና) እኛ ህዝብ ነን እንጂ መንግስት አይደለንም ። ህዝብ ደግሞ ፣ አንተ እንዳልከው ከሆነ በሀብቱም ፣ በጉልበቱም ፣ ሲፈጽም የሚገባውን ተግባሩን ከመፈጸም አላጎደለም ፤ በህዝቡ ሀብትና ጉልበት ሲፈጽም የሚገባውን ያልፈጸመ መንግስት ነው ማለት ነው ። ታዲያ እንዲህ ከሆነ ፣ መንግስት ተግባ ሩን ባለመፈጸሙ ባለዳዎች የምንሆን እኛ ነን ? ” አለ ውብቱ አሁ ንም ጉዋደኛውን ከሽሙር ፈገግታ ጋር የጎድን እያዩ ።

“ እንግዲህ . . ባንተ አስተያየት ፣ ኢያንዳንዳችን ለህዝብ ልንፈ ጽመው የሚገባን ተግባር የለም ማለት ነዋ ! ”

“ እንደ ህዝብ ፣ በማህበር አባልነታችን ፣ እንዳባል አዎ ፤ ከዚያ አልፎ የሚደረገው ግን ለራስ ዝናን ለማትረፍ እንደሆን እንጂ በተ ግባር ተራ ገብቶ የሚቆጠር አይደለም ። ”

“ ለመሆኑ መቸ ነው እንዲህ የሆንህ ? ” አለ ጥላሁን ፣ የቅርታ ፈገግታ ፈገግ ብሎ ።

“ ተለያይትን የቆዩንበት ጊዜኮ አጭር አይደለም ! ”

“ አዲስ ፍጥረት ሆነህልኮ ውብቴ ! እንደገና አንድ ብሎ ተፈ ጥሮ አሁን አንተ በደረስህበት ለመድረስ በጣም ያጥራል ! ብቻ እሱ ግዴለም ይሁን ፤ አሁን እያንዳንዳችን ለህዝብ የምንፈጽመው ተግባር የለብንም ወዳልከው እንመለስ” ሲል ጥላሁን ፤

“ እስቲ ለመናገር ያሰብሁትን ልናገርና ትቃጥላለህ ” አለ ውብቱ አቋርጦ ።

“ የጨረስህ መስሎኝ ነውኮ ፤ በል ጨርስ ። ”

" በትምህርት ቤት ሳለን " አለ ውበቱ ፣ የሚናገረው ከሰማይ እሱ ኪወርድለት እንደሚጠብቅ ጥንብ ዝም ብሎ ወደ ሰማይ ሲመለከት ቆይቶ፡ " በትምህርት ቤት ሳለን ፣ ' የኢትዮጵያ ተስፋ የተማረው ትውልድ ነው' ሲባል እንሰማ ስለነበረ ይሁን ፣ ወይም . . . ምን በራሳችን እንዳገባው አላውቅም . . እንዲያው እንዲሁ ዘመናዊውን ትምህርት ተምረው ከወጡት ሌላ 'ስልጣን ልያዝ' የሚል አይነት-ዶረቅ ይኖራል ብለን ባለማመን ፣ ትምህርታችንን ጨርሰን ስንወጣ ፣ መቸም ቢሆን ሳገራችን የባለቤትነቱ መብትና አላፊነት ከኛ ስለማያልፍ ፣ ኢትዮጵያን በቅጽበት ምድረ ገነት የሚያደርግ የኢኮኖሚክና የማህበራዊ ኑሮ እቅድ እዬሰራን ፣ በዚያ ላይ ፣ በዬጉዋዳችን መከራከርና በዬ ስብሰባው እዬተነሳን መናገር ስራ ብለን የያዝነው እንደነበረ ትዝ ይለኛል ። ነገር ግን ይህ አይነቱ አስተሳሰብ ከትምህርት ቤት አለምና ፣ ከዚያ ከልሙ አለም የማይወጣ ፣ ኢዚያው የሚኖር አስተሳሰብ ነው ። በዚህ በውኑ አለም ፣ ዘመናዊ ትምህርት መማር ፣ ወይም ማወቅ የስልጣን ባለቤት አያደርግም። መጽሀፉ 'ለሮጡ አደለም ፤ ለቀደሙም አደለም ፤ ለተመረጡ እንጂ !' እንደሚለው ፣ እዚህም ይትባሀሉ 'ለተማሩ አደለም ፤ ሳወቁም አደለም ለተወለዱ እንጂ ! ' ስለሆነ ፣ ተምረው ያወቁ ፣ በትውልድ የስልጣን ባለቤቶች ለሆኑት አገልጋዮች ብቻ ናቸው ! ይህ ነው እውነቱ የኔ ወንድም። ይህ ነው ልክ እንደ ዝቁዋላ ተራራ ቢገፉት ንቅንቅ የማይለው ሀቅ ፤ ታዲያ እንግዲህ ይህን መሰረት አድርገን ስንነሳ ፣ የመብቱ ሆነ የተግባሩ ባለቤቶች እኒያው ትውልድ የስልጣን ባለቤቶች ያደረጋቸው እንጂ አንተ ፣ ወይም እኔ ስላልሆን 'ለህዝብ የምፈጽመው ተግባር አለ ብኝ ፤ የምከፍለው እዳ አለብኝ ' እያልህ ባላገቡህ ገብተህ ህሊናህን እረፍት ባትነሳው ይሻላ . . ል ነው የምል ! " አለ ውበቱ ፣ አሁንም ያሾሙር ፈገግታው ከፊቱ ሳይጠፋ ፣ ቀልድ ይሁን ፣ ቁም ነገር ቅጡ በማይታወቅ ያነጋገር ስልት ።

" መቸም በዚህ . . . አሁን እውነት እንዲመስልልህ ከጥቅስ ጋጋታ ጋር ባንጎደጎድኸው ንግግርህ ፣ እንኩዋንስ ሌላ ሰው አንተ ራስህ እንደ ማታምንበት እርግጠኛ ነኝ " አለ ጥላሁን ፣ እሱም ጉዋደኛውን ካሽሙር ፈገግታ ጋር የጎድን እያዬ ።

" ለምን አባክህ ? " አለ ውበቱ እዬሳቀ ።

" እውነት አደለማ ! እንዲያው . . . በትንፋሽ የሚናድ ፣ መሰረት የሌለው ነው ! " አለ ጥላሁን ፣ ውበቱ አቅዋሙን ፣ ' እንደ ዝቁዋላ ተራራ ቢገፉት ንቅንቅ አይልም' ሳለው ማፍረሽ ።

“ እኮ ምን ነው እውነት ያደሰውና በትንፋሽ የሚናደው ? ”

@OLDBOOKSPDF

“ ሁሉም ! ለምሳሌ ፣ ትውልድም ይሁን ሀይል ‘ የስልጣን ባለ ቤት አደረጋቸው ’ የምትላቸው ክፍሎች ፣ ሀይል በያቸው እስካለ ድረስ የስልጣን ባለቤቶች እንደሆኑ ሊቆዩ ይችላሉ ፤ መብትና ተግባር ግን ዞሮ ዞሮ ምን ጊዜም ቢሆን የህዝብ ነው ። ”

“ እንዴት ? ”

“ እሺ ፤ መጀመርያ ከተግባር እንነሳ ። በተግባር በኩል ከህዝቡ እያንዳንዱ አባል በሀብቱ ፣ በውቀቱና በጉልበቱ ፣ እንደዬችሎታው ያባልነት መዋጮውን ማድረግ ተግባሩ ነው ። ከዚያ ወደ መብት ስና ልፍ እያንዳንዱ አባል ባደረገው መዋጮ ከውጭ ወሰኑ በጠላት እን ዳይደፈር ፣ ከውስጥ ጸጥታው እንዲከበር ሆኖ ፣ በዚያ ላይ የትምህርት፣ የጤና ፣ የመገናኛና ሌላ ሌላውንም ፣ ለሥልካም ኑሮ የሚያስፈልገ ውን አገልግሎት ሁሉ አግኝቶ መኖር የጠቅላላው ህዝብም ፣ የያንዳ ንዱ አባልም መብት ነው ። ስለዚህ ፣ መብትና ተግባር ዞሮ ዞሮ የህ ዝብ ነው ማለት ነው ። ባለስልጣኖች ፣ የመብትና የተግባር ባለቤት በሆነው ሕዝብ ስም ያስተዳዳሪነትና ያስተናባሪነት ዋጋቸውን እዬተ ቀበሉ ፣ አስተዳዳሪዎችና አስተናባሪዎች ብቻ ናቸው እንጂ ፣ የመብ ትና የተግባር ባለቤቶች አይደሉም ። ባለመብቱም ሆነ ባለተግባሩ ሕዝብ ነው ። ”

“ አልሰማኽኝም መሰለኝ እንጂ ፣ ‘ ይህ ከትምህርት ቤት አለም የማይወጣ ፣ እዚያው የሚኖር አስተሳሰብ ነው’ ብዬህ ነበርኮ ! ብቻ እስቲ ይሁን ጨርስ ፤ ‘እያንዳንዳችን ለህዝብ የምንፈጽመው ተግባር አለብን’ ያልኸውን ለማስረዳት ስትጀምር ነበር ያቋዋረጥሁህ ” አለ ውብቱ ።

“ እዎ ፤ አንዳንድ ጥያቄዎች ልጠይቅህ ነበር ። ‘ተግባሩን ሳይፈ ጽም በመብቱ የተጠቀመ ሁሉ ባለዳነው’ ስልህ ፣ ‘እዎን’ ያልኸኝ መሰ ለኝ ፤ ተሳሰቻለሁ ? ”

“ አልተሳሳትህም ብያለሁ ። ”

“ ከመብቱ አልፎ በሌሎች መብት የተጠቀመስ ባይነቱ ሠከ ፈል ባይችል ባገልግሎት የሚከፍለው እዳ የለበትም ? ”

“ እም . . እስቲ ግዴለም ፣ ‘አለበት’ እንበል ” አለ ውብቱ ጉዋደ ኛው ሊሄድበት ያሰበው የታዬው ስለመሰለው ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ

@OLDBOOKSPDF

" መ . . . መልካም ! እንግዳህ ፣ 'የኢትዮጵያ ህዝብ ሀያ አምስት ሚሊዮን ያክል ነው' ስለሚባል ፣ ባልተማሩ ግምት የዚያ ክፍለት አንድ እጅ በትምህርት እድሜ ያለ ትውልድ ነው ብንል . . . ከስ ምንት ሚሊዮን በላይ ይሆናል ማለት ነው ። ታዲያ መቸም . . የገሪቱ የገንዘብ ፣ ያስተማሪና በጠቅላላው የድርጅት አቅም ይህን ያክል ተማሪ ባንድ የትምህርት ጊዜ ማስተማር ስለማይችል ፣ ተራ ተሰጥቶ ፣ ትም ሀርቱ በቅደም ተከተል እንዲሰጥ ማድረግ ግዴታ ስለሚሆን ፣ በቅ ድሚያ በከተማ የሚኖሩ ልጆች ፣ እኔና አንተ ጭምር ፣ የትምህርት እድል አገኘን ። ልብ አድርግ ፤ የገጠሩ ህዝብ ከሌላው ሙዋጮው ጋር ለት ምህርት የሚያስፈልገውን መዋጮ ጭምር እዬከፈለ ፣ በሱ መዋጮና በገጠሩ ልጅ ኪሳራ ፣ የተማርነው እኛ የከተማ ልጆች ነን ። በሌላ አነ ጋገር ፣ እኛ የከተማ ልጆች ፣ በርከት ብለን ከተማ በመገኘታችን ብቻ፣ ከመብታችን አልፈን በገጠር ልጆች ሐብት ጭምር ተጠቃሚዎች ሆን ማለት ነው ። ስለዚህም ለገጠሩ ህዝብ ባይነት ባይሆን ባገልግሎት የምንከፍለው እዳ አለብን ። የለብንም ትላለህ ? " አለ ጥላሁን ፣ አይ ኖቹን በውብቱ ላይ ፍጥጥ አድርጎ ።

" እንግዲህ . . . ባለዳ መሆን ካማረህ ፣ እዳህን እዚያው ብቻህን ገፍግፍ እንጂ እኔን አትጨምረኝ ፤ እኔ ምንም እዳ የለብኝ ! " አለ ውብቱ ፣ እዬሳቀ ሲነሳ ። ከዚያ ሁለቱም እዬተሳሳቁ ወደ ቤት ተመለሱ።

@OLDBOOKSPDF

## ምእራፍ ፲፫

# ጎሬና አካባቢው

ሶፍያና ጥላሁን ጎሬ በሰነበቱበት ጊዜ ፣ እጅግ ደስ ብሎዋቸው ሰነበቱ ። ጎሬ የሙሽርነት በአላቸውን ለማክበር የሄዱበት ፣ የመደሰቻ ቦታ እንጂ ፣ ከስደት ጉዞዋቸው የመጀመሪያው ምእራፍ መሆኑ ሳይሰማቸው ሰነበቱ ። ጎሬ በገቡ በአራተኛው እለት ፡ ውብቱና እቻምየለሽ ለክብራቸው ታላቅ ግብዣ አደርገው ፣ ከከተማው ታላላቅ ሰዎች ጋር ስላስተዋወቋቸው ፣ በጎሬ ህዝብ መሀከል የእንግድነት ስሜታቸው ብዙ ጊዜ አብሮዋቸው አልቆዩም ። አንዳንድ የውብቱና የባለቤቱ የቅርብ ወዳጆች የሆኑ ሰዎች በዬተራ ራት እዬደገሱ ጋበዙዋቸው ። ዶክቶር ስቲዋርት የሚባሉት ፣ የጎሬ ህክምና ቤት አሜሪካዊ ሀኪምና ባለቤታቸው እንኳ ውብቱንና እቻምየለሽን ጭምር ራት ጋበዙዋቸው ። ዶክቶር ስቲዋርትና ባለቤታቸው ከጥላሁንና ከሶፍያ ጋር ባጭር ጊዜ ወዳጆች ሆነው ፣ ሀኪሙ ተራ በሽታዎችን ለማከም ጽፈው የሰጡዋቸው መመሪያ ለጥላሁንና ለሶፍያ ለሁዋላ ስራቸው በጣም ረዳቸው ።

እርግጥ ፣ ጎሬ የገቡ እለት ማታውን ፣ ጥላሁን የውብቱን ክልክ ያለፈ የቅንጦትና ያዲስ ዘበናይ ኑሮ ሲያይ ፣ ስለሱ የነበረው አሳብና በዚያ ላይ የመሠረተው ትስፋ ሁሉ ተናግቶበት ፣ እንዲያውም ገና ለገና "ጌታ ከሆነ ሳይንቁኝ አይቀርም" ብሎ የመጣበትን ጉዳይ እንኳ ሳይገልጽ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ እስከ ማሰብ ደርሶ ነበር ። ብቻ ይህ ጥርጣሬ መሰረት የሌለው መሆኑን እንዲያውም በመናቅ ፈንታ ተለማማጩና አባባዩ እሱ ውብቱ መሆኑን ፣ ስራውን ፈትቶና ከመንገዱ ወጥቶ እሱንና ሶፊያን ደስ ለማሰኘት የሚጥር ፣ የሚጨነቅ፣ መሆኑን አሳቡን ለወጠ ፤ እዚያ ምቁኛ እንጂ ብዙ የልብ ወዳጅ በማይገኝበት ቦታ ፣ ጥላሁንንና ሶፊያን በማግኘታቸው እሱና ሚስቱ ፣ እቻምየለሽ በጣም የተደሰቱ መሆናቸውንና ምክናያት እዬፈጠሩ አብረዋቸው የሚቆዩበትን ጊዜ ለማስረዘም የሚፈልጉ መሆናቸውን ከሁኔታው ስለ ተረዱ ፣ ጥላሁንም ሆነ ሶፊያ በቤታቸው እንጂ በወዳጆች ቤት የተቀመጡ ሳይመስላቸው ፣ ከመሰቀቅና ከይሉኝታ ስሜት ፍጹም ነጻ ሆነው ሰነበቱ ።

@OLDBOOKSPDF

ጥላሁንና ሶፊያ የጎሬን ህዝብ ብቻ ሳይሆን ፤ አገሩንም ፤ አዩሩንም በጣም ነው የወደዱት ። እውነትም ጎሬ የሚወደድ አገር ነው ። ጎሬ እንደ ስሙና እንደ ወሬው አይደለም ። ጎሬ አጥፍተው ከባድ ቅጣት የተፈረደባቸው እስረኞች ፤ ይልቁንም ባለ ስልጣኖችን የሚያስጉ ግዞተኞች ታስረው ከሚቀመጡባቸው ቦታዎች መሀከል ፤ እጅግ ስመጥር ስለሆነ ፤ ስሙንና ወሬውን ብቻ እንጂ መልኩን ለማያውቅ የሚሰጠው ስሜት ፤ አዩርና ጸሀይ እንደማይደርሱበት ፤ ከገደል ስር ፤ ወይም ከመሬት ታች ተቆፍሮ እንደ ተሰራ ወህኒ ነው ። ሄዶ ሲያዩት ግን እንዲህ አይደለም ! ሌላ ነው ። ሄዶ ሲያዩት ፤ ያዩሩ ጥራትና ያካባቢው ውበት ማመዛዘኛ የሌለው ፤ እጹብ ድንቅ ነው ! ጎሬ በሸንተ እገዘመራ መሀከል እንደ ተሰራ ማማ ካካባቢው ሁሉ በላይ ከፍ ብሎ ተሰርቶ ፤ ከዚያ ላይ ዙርያውን የተዘረጋውን የኢሉባቦር ለምለም መሬት አይን ሊያይ እስከሚችልበት ድረስ ዘቅዝቆ ሲመለከቱ ፤ እዝን ሁሉ ፤ ብስጭት ሁሉ ፤ ተስፋ መቁረጥ ሁሉ ይረሳና ፤ የመኖር ፤ የመስራት ፤ የደስታ ተስፋ ይታደሳል !

ጎሬ እንደ ስሙና እንደ ወሬው አይደለም ! ጥላሁንና ሶፊያም ጎሬን እንደ ሰሙት ፤ ለነሱም እንደ መሰላቸው ሆኖ ስላላገኙት ፤ ከሰሙትና ከመሰላቸው ፍጹም የተለዩ ሆኖ ስላገኙት ፤ በወጡ ቁጥር ደግሞ ሌላ አዲስ ጎሬ ፤ እንግዳ ጎሬ ፤ የሚያገኙ እዩመሰላቸው ፤ እቤት መቀመጥ አይወዱም ፤ ሲዞሩ ቢውሉ ይወዱ ነበር ። መቸም ካልዘነበ ጥዋት ተነስተው ሄደው የጎሬን አናት ፤ የጎሬን ቁንጭላላት ሳይሳለሙ ቁርስ ይቀምሳሉ ማለት ዘበት ነው ! ጥዋት ጥዋት ከቁርስ በፊት ፤ ሮጠው ወጥተው ከጎሬ ቁንጭላላት ፤ ኢሉባቦርን ከጽንፍ እስከ ጽንፍ በጥልቅ አንክሮ ዘቅዝቀው እዩተመለከቱ ሲደነቁ ይቆዩና ፤ ያን በጋ ከክረምት የሰማይ ዝናማትና የምድር ቀላያት ተባብረው እያጠጡት ፤ እንደ ገነት አትክልት ዘወትር ለምልሞ የሚኖር እጹብ ድንቅ አገር ፤ ከጎሬ ቁንጭላላት ዘቅዝቀው እዩተመለከቱ ሲገረሙ ይቆዩና ፤ ያን የዙሪያ ገባው እጽዋትና ጽጌያት የሚነዙትን ገነታዊ መአዛ ይዞ ሽቅብ ፤ ወደ ጎሬ ቁንጭላላት የሚያርግ አዩር እዩጠጡ ፤ በደስታ ሲሰክሩ ይቆዩና ወደ ቤት ሲመለሱ ፤ በቁርስ ስም ተሰናድቶ የሚቆያቸው ከባድ ምሳ አይመከታቸውም ። በልተው አይጠግቡም ። ቁርስ ከበሉ በሁዋላ ፤ እቻምየለሽ ድግሰዎን በያይነቱ አሰናድታ ትይዝና ፤ ውበቱ በላንድ ሮቨር እየዞረ በጎሬ አካባቢ ሊታዩ የሚገባቸውን ቦታዎች ሲያሳያቸው ውሎ ፤ ምሳቸውን እዚያው በሄዱበት ቦታ በልተው ፤ ሲጫወቱ ውለው ፤ እመኛሽ ላይ ደስ ብሎዋቸው ይመለሳሉ ።

@OLDBOOKSPDF

መቸስ በጎሬ አካባቢ ካዩዋቸው ቦታዎች ሁሉ ፣ እንደ ሶር ፏፏቴ በሶፊያ አእምሮ ውስጥ ተቀርጾ የቀረ የለም ። እስከ ብዙ ጊዜ ድረስ በህልሟዋ ይታያት ነበር ። የሶር ፏፏቴ ፣ ፍጥረት በገዛ እጅዋ እየተለዋወጠች እጅግ አስደናቂ የሆነ ትርኢይት ስትጫወት የምታይበት ቦታ ነው ።

የሶር ውሀ ከፏፏቴው በላይና በታች ፣ እንደ ሌሎቹ የኢሉባቦር ወንዞች ውሀ ሁሉ በክረምት የማይደፈርስ ፣ ምን ጊዜም ቀለሙን ሳይለውጥ ፣ ሀብረሰማይ እንደ መሰለ የሚኖር ነው ። ነገር ግን ያ ቀለሙ ሀብረ ሰማይ የመሰለ ውሀ ፣ እገደሉ አፋፍ እንደ ደረሰ ፣ አስማተኛ ምትሃት እንዳዞረበት ሁሉ ፣ ድንገት መልኩን ከውሀነት ወደ ወተትነት ይለውጥና ፣ ልብ በሚያባባ ግርማ እየተናደ እየወረደ ፣ እታች እገደሉ ስር በሰፊው ተዘርግቶ ከሚጠብቀው አለት ጋር ሲጋጭ ፣ ወደ ጉምነት ተለውጦ ፤ እንደገና ወደ መጣበት ፣ ወደ አፋፉ ይመለሳል ። ከዚያም አልፎ አፉሩን ሁሉ ይሞላዋል ። እዚያ ! ያ ፣ ወደ ጉምነት የተለወጠ ውሀ ከጸሀይ ጮራ ጋር ይገናኝና አካባቢውን በሙሉ ፤ ሜዳውን ፣ ወንዙን ፤ ሰማዩን ፣ ሥሬቱን ሁሉ ፤ በቀስተ ደመና ቀለም ሸልሞ ፣ አስጊጦ ያሳያል ! በውነት ግሩም ነው !

ሶፊያ ያን አስደናቂ ትርኢይት አይታ ስለማትጠግበው ፤ ውበቱ አንዳንድ ቦታዎች ለማሳዩት ይሁን ፤ ወይም እንዲሁ ለሽርሽር ይዞዋቸው በወጣ ቁጥር ፣ ሲመለሱ ካልመሸ ፤ ወይም ዝናብ ሆኖ መንገዱ የማያስሄድ ካልሆነ ፤ በሶር ፏፏቴ በኩል አልፈው ፤ እዚያ ትንሽ አርፈው ትርኢይቱን ሳይመለከቱ ወደቤት አይገቡም ። ፏፏቴውና እሱ ባካባቢው የሚፈጥረው ምትሀታዊ ትርኢይት ፣ ከዚያ ከሚያደንቁር ጩኸቱ ጋር ባንድ ላይ ፣ አንድ አይነት የመንፈስ ጸጥታ ፤ አንድ አይነት ውስጣዊ ሰላም ስለሚሰጣት ፣ ወደዚያ ለመሄድ ገና ጉዞ ሲጀምሩ የሚሰማት ደስታ ፣ ይህን ያክል ነው አይባልም ነበር ።

ሌላው ፤ ጥላሁንና ሶፊያ ጎሬ ፤ ከውብቱና ካቻምየለሽ ጋር በሰነበቱበት ጊዜ ካዩዋቸው ነገሮች ትዝታው ለብዙ ጊዜ አብሮዋቸው የኖረና ፣ ባሰቡት ቁጥር ያስቃቸው የነበረ ፣ ባሮ መልካን ያዩ ሄደው የደረሰባቸው ነው ። ባሮ መልካ በጎሬና በሞቻ መሀከል ፣ የባሮ ወንዝ ድልድይ ሲፈርስ ፣ ሰውም ሆነ ከብት በጋ በግር ፣ ክረምት በበድኑ የሚሻገርበት ሰፊ መልካ ነው ።

ሞቻ ፣ ከሌሎች የኢሉባቦር አውራጃዎች ሁሉ ፤ በማርና በኮረሪማ የሚበልጥ ፣ በቡና የሚሆንበ ፣ እጅግ ሁኔታም ስለሆነ ፣ ምንም እን

@OLDBOOKSPDF

ኩዋ ዘመናዊ መንገድና የመጓጓዣ ዘዴ ባይኖር ፡ በጎሬና በሞቻ መሀከል በጋ ከክረምት የማያቋርጥ ሲራራ ንግድ አለ ።

ክረምት ፡ ነጋዴ ልዩ ልዩ አይነት ልብስ ፡ ድርና ማግ ፡ መጠጥ በያይነቱ ፡ ጌጣጌጥና ሌላም በባላገር የሚፈለግና የሚወደድ ሸቀጣ ሸቀጥ ሁሉ ጭኖ ሄዶ ፡ በገንዘብ እየተመነ ፡ ለባላገሩ ህዝብ ሲያበድር ይከርምና ፡ ከጥቅምት ጀምሮ በጋውን በሙሉ ፡ ያን ክረምት ያበደረውን ከናራጣው በማር ፡ በኮረሪማና በቡና እየተከፈለ ወደ ጎሬ ሲጭን ይባጃል ።

ሞቻ ፡ ከቅርቀሀ እስከ ቀረሮ ፡ እስከ ሽመል የሚያበቅሉ የደጋ ፡ ወይና ደጋና የቆላ ክፍሎች ያሉት ፡ በውስጡ ሲጉዋዙ አቀበትና ቁልቁለት ፡ ጉራንጉርና ሸንተረር እየተተካከሉ ፡ ጉልበትን እንደ ልብ አጥፎና ዘርግቶ ለመራመድ ደልዳላ መሬት የሚናፈቅበት ፡ ጫካው ጥቅጥቅ ብሎ ሰማይ የማይታይበት ፡ ሲዘንብ በዝናቡ ፡ ዝናብ ሲያባራ በጫካው ጠፈጠፍ ምክናያት ፡ መሬቱ እንደ ጨቀዩ የሚኖርበት አገር ነው ! ስለዚህ ፡ ቡትለይ በክረምት ፡ ነጋዴው ሸቀጡን ጭኖ አገር ላገር እየዞረ ለባላገሩ ሲያበድርና በሁዋላም በሸቀጣ ሸቀጥ ያበደረውን በማር በኮረሪማና በቡና ሲቀበል የሚደርስበት ችግር ይህን ያክል ነው የማይባል ፡ በጣም ብዙ ነው ። ብቻ ትርፉስ ! ትርፉ ደግሞ ፡ ችግሩን የሚያስንቅ ፡ ችግሩን ጨርሶ የሚያስረሳ ነው ! ትርፉ ትርፍ አይባልም፤ ቅሚያ ነው ! የሞቻ ህዝብ በጋ ከክረምት ለፍቶ ፡ የሰውነቱን ላብ ካገሩ አፈር ጋር አደባልቆ ያፈራውን ፡ ነጋዴ በንግድ ስም ይቀማዋል ፤ ይዘርፈዋል ።

ባላገሩ የሁለት ብር ቁምጣ ሱሪ ፡ ወይም ድርና ማግ ፡ ወይም አቡጀዲድ ፡ ወይም የነዚህ ተመጣጣኝ ሌላ ሸቀጥ ባምስት ብር ይታሰብና ፡ ክረምት በብድር ወስዶ ፡ በጋ አንድ ፈረሱላ ቡና ፡ ወይም ሁለት ፈረሱላ ማር ፡ ወይም ኮረሪማ ይሰጣል ። እንግዲህ አንድ ፈረሱላ ቡና እንደ ጊዜው ገበያ ፡ ከሀያ አምስት እስከ አርባ ብር ፡ ኮረሪማና ማር ፈረሱላው ሀያ አምስት ብር ግድም ስለሚሸጥ ፡ የሁለቱን ብር ሸቀጥ እንደ አምስት ብር ሸቀጥ የተበደረው ባላገር ፡ በጥቂት ወራት ውስጥ እስከ አርባ ብር ድረስ በቡና ፡ እስከ አምሳ ብር ድረስ በማርና በኮረሪማ ይከፍላል ማለት ነው ! ከዚህ ሌላ ፡ በኪሎና በፈረሱላ መሀከል ለውጡ ምን እንደሆነ ባላገር ስለማያውቀው ፡ ነጋዴ ከባላገር ኩዊንታል ፡ ወይም መቶ ኪሎ ቡና ፡ ማር ፡ ወይም ኮረሪማ ይቀበልና ፡ አንዱን ኩዊንታል ባምስት ፈረሱላ አስቦ ያምስት ፈረሱላ ዋጋ ይከፍ

@OLDBOOKSPDF

ለዋል ። አምስት ፈረሱላ ሰማንያ አምስት ኪሎ ስለሆነ ፣ እንግዲህ ነጋዴው ፤ ከባላገሩ ፣ መቶ ኪሎ የንግድ እቃ ወስዶ ፣ ዋጋ የከፈለው ለሰማንያ አምስቱ ኪሎ ብቻ ነው ማለት ነው ! ታዲያ ይህ ምን ይባላል ? ቅሚያ አይባልም ? ዘረፋ አይባልም ? ዘረፋ ነው ! ስለዚህ እንዲህ ያለ በህግ የታወቀ ዘረፋ ጥቻ ስላለ ፣ ወያዚያ የሚገዋዘው ነጋዴ ከረምት ባርን በቢድሩ ሲሻገር የሚታዩው ትርእይት የሚያስገርም ነው ።

" ባሮ እንደ ሶር የሚያምር ፋዋፋዋቱ ይኖረው ይሆን " ? አለ ጥላሁን ፣ እንደ ተለመደው ውብቱና ባለቤቱ ስንታቸውን ሰንተው በላንድ ሮቨር እንግዶቻቸውን ይዘው ፣ ወደ ባሮ መልካ ሲሄዱ ።

" ስለ ባሮ ፋዋፋዋቱ እንኳዋ . . የሰማሁት የለም ። ባሮ እንደም ታውቀው ፣ ከታላላቅ ወንዞቻችን አንዱ ነው ፤ አካባቢው ያምራል ፤ ከዚህ ሌላ ባለቢድሩዎችን እናያለን ። ለቻሜና እኔም ወሬያቸውን ብቻ እዩሰማን እስከ ዛሬ አላዩናቸውም ነበር ፤ ዛሬ በናንተ ምክናያት ልናያቸው ነው " አለ ውብቱ ።

" ባለቢድሩዎች ምንድናቸው ? "

" የኢሉባቦር መርከበኞች ። "

" ትቀልዳለህ መሰለኝ ። "

" ቀልድ አደለም ፤ እውነቱን ነው ። እዚያ የባሮን ዳር ተከትለው የሚኖሩ ባላገሮች ፣ በጎሬና በጥቻ መሀከል የሚመላለሰውን ነጋዴ ተራ መንገደኛ ፣ አጋሰሱንና የንግድ እቃውን ሁሉ ከቅርቀህና . . ደን ገል ነው ? ምን ከሚሉት ባር መሳይ ነገር ፣ እንዲሁም ከዋንዛ እንጨት እዩፈለፈሉ በሚሰሩት ጀልባ የሚያሻግሩ እነሱ ናቸው ። ታዲያ እንዲህ ያሉትን ማየት አይገባም ? መርከበኞች መባልስ . . ያንሳቸው እንደሆን እንጂ ይበዛባቸዋል ? " አለ ውብቱ የቀልድ ሳቅ እንደ መሳቅ ብሎ ።

" እውነትም ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው ፤ ብቻ . . . በሳር መሳይ ነገር ሰውን ፣ ከብቱንና ይህን ያልኸውን ነገር ሁሉ ለማሻገር እንዴት ይችላሉ ? "

" እሱንኮ ነው ለማየት የምንሄድ ! "

" ግዴለህም ፤ ዛሬ ከንቅልፍህ ያስነሳህ ለቀልድ ቃኝቶሀል ! " አለ ጥላሁን ፣ ጉዋደኛውን የጎድን እያዩ ።

" ማነው እሱ ? "

@OLDBOOKSPDF

" ምን አውቃለሁ ፤ ውቃቢህ ይሆናላ ! " አለ ጥላሁን ፣ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ ። "ለመሆኑ ባሮን ያክል ወንዝ . . ድልድይ የለ ውም ማለት ነው ? " አለ ቀጠለና ።

" በባሮ ላይ የሰሚንት ፣ ወይም የብረት ድልድይ ለመስራት ፣ እንዳልኩሽ ወንዙ በጣም ትልቅ ስለሆነ . . የኢሉባቦር የገንዘብ አቅም አይችለውም ፤ የንጨት ድልድይ ቢሰራም . . ያው ባላገር በትእዛዝ ፣ የግብር ይውጣ የሚሰራው አይነት ስለሆነ ፣ ቢድሩ የሚሰጠውን አገል ግሎት ሊሰጥ የማይችል ከመሆኑም ሌላ ፣ ሳምንት አይቆይም ፤ ወዲያው ተሸሽገው ያፈርሱታል ። "

" ያፈርሱታል ? እነማን ? " አለ ጥላሁን ፣ በመገረም መልክ ።

" ባለ ቢድሩዎች ። "

" አሀ ! የነሱን ስራ እንዳይገድልባቸው ? "

" ልክ ነው ፤ ቢድሩ መኖሪያቸው ስለሆነ ፣ መኖሪያቸውን የሚጻ ረር ነገር እንዲኖር በጭራሽ አይፈልጉም ። "

" ባለ ቢድሩዎች እንደሚያፈርሱት የታወቀ ከሆነ ሹሞችስ ሳያ ውቁ እንዴት ቀሩ ? "

" ያውቃሉ እንጂ ! ከህዝብ መሀከል እዩኖሩ ህዝቡ ሁሉ የሚያ ውቀውን እንዴት ሳያውቁ ይቀራሉ ? "

" ታዲያ ካወቁ እንዴት ዝም ይሉዋቸዋል ? "

" ዝም አይሉዋቸውም ፤ ቶሎ ቶሎ እንዲያፈርሱ ያደፋፍሩዋቸዋል እንጂ ! " ሲል ውብቱ እዩሳቀ ፣ ሁሉም ይስቁ ጀመር ።

" ምን ማለትህ ነው ? " አለ ጥላሁን ፣ ቢስቅ ቆይቶ ።

" ባለቢድሩዎች ካላፈረሱ ሹሞች አያሰሩም ፤ ካላሰሩ ደግሞ ባላ ገሩን ፣ " እርፍደህ መጥተሀል ፤ ጭራሹን ቀርተሀል " እያሉ አስረው ፈትተው ፣ አስምጠው ፣ አስጨንቀው ብር የሚያስወልዱበት ምክና ያት ያንሳቸዋል ። ስለዚህ . . የራሳቸውን ጥቅም ለመጠበቅም ሆነ ከሹም ቁጣ ለመዳን ፣ ባለቢድሩዎች ቢያንስ ቢያንስ ባመት ሁለት ሶስት ጊዜ ድልድዩን ያፈረሱ እንደሆነ ፣ ባላገር ባመት ቢያንስ ሁለት ጊዜ እንዲሰራ ይታዘዛል ፤ ሹምም ሁለት ጊዜ ገንዘብ የሚሰበስብበት ምክ ናያት ያገኛል ማለት ነው ! አሁን ብልሀቱ ገባህ ? "

" ጭራሽ ሊገባኝ አይችልም ! "

" ቆ . . ይ ግዴለም ፤ እያደር ይገባሀል ! " ሲል ውብቱ ያሽሙር ፈገግታ ፈገግ ብሎ ፣ ላንድሮቨራቸው የባሮን ወንዝ ቁልቁል ማየት በሚቻልበት ከፍተኛ ቦታ ብቅ አለ ። ከዚያ ቦታ ፣ ባሮ ብቻ ሳይሆን

@OLDBOOKSPDF

ሞቻ በሙሉ ይታያል ። ዘቢያ ኮቃ ጤቻ ከባድ ሜካውን ለብሶ ፣ ለጥ እንዳለ በወርዱና በቁሙ ከዳር እስከዳር ሲያዩት የማይንቀሳቀስ ፣ ጸጥ ያለ ባህር እንጂ መሬት አይመስልም ።

ባሮ ከወደ ያቡብ ይመጣና በጎሬና ፣ በሞቻ አውራጃዎች መሀከል እጥፍ ፣ ዘርጋ እያለ ፣ ኢባብ-ወረድ መንገዱን ተከትሎ ወደ ጋን ቤላ ቆላ ዘቅዝቆ ይወርዳል ። ምንም እንኩዋ ጊዜው ወደ ጥቅምቱ መጨረሻ ላይ ቢሆን ባሮ ገና እንደ ተሾመ ነው ። እስከ አፉ ጢም ብሎ ሞልቶ ፣ ካፉ አፈተረፈ የሚተፋው ውሃ ፣ በጎሬ በኩል ያለውን ሜዳ በስፋት ፣ በያንስ ሁለት ኪሎ ሜትር ያክል ባህር አድርጎታል ።

" ይህ አይቸው የማላውቅ ባህር ምንድነው ? " አለ ውብቱ ፣ መኪናውን አቁሞ ።

" ክረምት ክረምት ባሮ ሲሞላ በዚያ በኩል ሰብሮ የሚመጣ ውሃ ነው " አለ ክውብቱ አሽከሮች አንዱ አብዲሳ ፣ ውሀው የሚሰብ ርበትን በጁ እያሳዩ ።

" ለምን አይቸው አላውቅ ? ያለፃሬ አይቸው አላውቅም ። "

" በጋ በጋ ፣ ክ . . ወደ ታህሳሱ መጨረሻ ጀምሮ ይደርቃል ። "

ከዚያ ፣ ከባሮ አፍ እዬተረፈ የሚፈሰው ውሀ ወደ ፈጠረው ባህር ዳር ሄደው ቆሙ ።

ኮረሪማ ፣ ማርና ቡና ለማምጣት አጋሰሱን እዬነዳ ወደ ሞቻ የሚጉዋዘውና ከዚያ ጭኖ የሚመለሰው ነጋዴ ፣ ለደጅ ጥናት ይሁን ለሙግት ፣ ወይም ለሌላ ጉዳይ ወደ ጎሬ የሚሄደውና እዚያ ቆይቶ የሚመለሰው ባለከብት ፣ ወይም እግረኛ አያቁዋርጥም ፣ ይሻገራል ።

መንገደኛው ፣ እነውብቱ ከወረዱበት ትንሽ ራቅ ብሎ ፣ የኮርቻ በቅሎ ያለው ግላስና ምቹውን እያነሳ በትከሻው ይዞ በበቅሎው ይቀመጥና ፣ ባላጋሰሱ የዳውላ መቀነቻውን አጠባብቆ ባጋሰሱ ይሆንና ፣ እግረኛው ነጠላውን ሰብሰብ አድርጎ በራሱ ይጠመጥምና ፣ ሁሉም እንደ መጣ እባህሩ ውስጥ ገብቶ ጉዞውን ይቀጥላል ። ባህሩ የተኛበት መሬት አሸዋማ በመሆኑ ፣ የሰው እግርም ሆነ የከብት ኮቴ እንደማይገባ የታወቀ ስለሆነ ፣ ውሀው ውስጥ ሲገባ የስጋት ምልክት የሚታይበት መንገደኛ የለም ። ታዲያ ፣ በበቅሎ የተቀመጠው እንዲያ እስከ ወገቡ ጠልቆ ፣ ከወገቡ በላይ ያለ አካሉ ብቻ እዬታዬ ፣ እግረኛውም እንዲሁ ከወገቡ በላይ ብቻ እዬታዬ ፣ ሁሉም ባንድ ላይ በባህሩ ውስጥ ሲሄድ፣ እንደ እነውብቱ ትንሽ ራቅ ብሎ ለሚመለከት ፣ በበቅሎ የተቀመጠው

ከበቅሎው አንገት @OLDBOOKSPDF ራስ አሞራ ፣ እግረኛው ባለንጣላ ራስ አሞራ ባህሩን ሞልቶ የሚንሳፈፍ እንጂ ፣ ብዙ ባለከብትና እግረኛ መንገደኛ የሚጉዋዝ አይመስልም ነበር ! ከዚያ በሁዋላ ደግሞ ያን ከባድ አፍ ትርፍ የፈሰሰው ውሀ የፈጠረውን ባህር ከተሻገረ በሁዋላ ፣ አይነተኛውን የባሮን ወንዝ ለመሻገር እጻር ሰፍሮ የሚጠባበቀውን የሰውና የከብት ብዛት ከሩቅ ሲያዩት ፣ መጠነኛ የሚዳ ገበያ ይመስላል ።

"እዚያ ማዶ ተሰብስቦ የሚታዬው ህዝብ ደግሞ ምንድነው ! " አለ ጥላሁን ።

"በቢድሩ ለመሻገር ተራ የሚጠብቀው ይሆናል ፤ አደለም እንዴ ? " አለ ውብቱ ፣ ወደ አብዲሳ ዞወር ብሎ ፤ አብዲሳ የዚያው አካባቢ ተወላጅ ነው ።

"ነው ጌታዩ " አለ አብዲሳ ።

"ሁሉም ቢድሩን ይጠብቃል ? አያስዋኙም ማለት ነው ? " አለ ጥላሁን ።

" ሁ ህ ! ባሮን በዋና ? ማን ይችላል ጌታዬ ! እዚያው ዙሪያ ከሚኖሩት ባላገሮች በቀር ፣ ባሮን ዋኝቼ እሻገራለሁ የሚል ያበደ ነው!" አለ አብዲሳ ።

እውነትም አብዲሳ እንዳለው ፣ ባሮን ሲሞላ በዋና የሚዳፈሩት የዚያው አካባቢ ባላገሮች ፣ ውስጠ - አዋቂዎች ፣ አብሮ በመኖር ከደን በሴውና ከዙዋሪቱ ተንኮል ጋር የተላመዱት ብቻ እንጂ ማንም ቢሆን ፣ ምንም ያክል ዋና ቢያውቅ ፣ "ባሮን በዋና እሻገራለሁ " ብሎ የሚሞክር የለም ። ስለዚህ ፣ አንዱ ቢድሩ ጭኖ ሄዶ ሌላው ሊጭን በተተካ ቁጥር ፣ ያ የመጨረሻ ቢድሩ እንደሆን ሁሉ ፣ ለራሱ ፣ ለከብቱ ወይም ለጭነቱ ቦታ ለመያዝ የሚሽቀዳደመው ፣ የሚታገለውና የሚጣላው ሲታይ ያስገርም ነበር ! ምንም እንኳ ያን እለት አራት የሰው ፣ ሶስት የከብትና ሁለት የቃ ፣ በድምር ዘጠኝ ቢድሩዎች ያለማቋረጥ እዬተመላለሱ ቢያሻግሩ ፣ የተሻገረው እዬተሻገረ በቀሪው ላይ አዲስ መጭው ስለሚጨመርበት ፣ አንድ ሰው እንኩዋ የተሻገረ አይመስልም ነበር !

"ታዲያ ወደዚያው እንሂድ እንጂ ምን እንጠብቃለን ? " አለ ጥላሁን ፣ መልካውን ባገጩ እያመለከተና ውሀው ውስጥ እስኪገባ ቸኩሎ ሙቤ እዬመታ ።

“የመጣነውምኮ እዚያ ለመሄድ ነበር ፤ መሄጃው ጠፋ እንጂ!” አለ ውብቱ ።

@OLDBOOKSPDF

“እንዴት ልትወስዱን ኖሮዋል ያመጣኸን ?”

“በጋ ይህ የምታየው ባህር ሁሉ አሸዋና ሳር ፤ ለጥ ያለ ሜዳ ነበር ። ስለዚህ ፡ ከረምት መጥቼ ስለማላውቅ ፤ በጋ እንዳዩሁት መስ ለኝ እንጂ . . እንዲህ ይሆናል ብዬ ጭራሽ አላሰብሁም ።”

“አሁን እኔ የማቀርበው አሳብ ፡ ልጆች ከመኪናው ጋር እዚህ እንዲቆዩ ፤ እኛ አራታችን ከነጋዴዎች በቅሎች ተከራይተን ወደባሮ ወንዝ እንድንሄድ ነው” አለ ጥላሁን ።

“በቅሎቱ ውሀ ውስጥ ከመነከር አያድንም ፤ በበቅሎ የሚሄዱትን አታይም እስከ ወገባቸው ተነክረው ?” አለ ውብቱ ።

“ታዲያ ብንነከር ምናለ? ሌሎች ተነክረው የለ ወዲያውም . . ጸሀዩ ብርቱ ስለሆነ ፡ ስንወጣ ባንድ ጊዜ ነው የሚያደርቀን ።”

“ነበቅሎስ . . ባቱ መከራየት ይሻላል ” አለች አቻምየለሽ ።

“ባቱ ወደ ቆላው ፤ ወደ ሴራቴ ካልሆነ እዚህ ማን ያገኛል ?” አለ ባልጥ ።

“እዚያ ዛፍ ስር ያሉትኮ ባቱዎች ናቸው ፤ አልጋቸውን አታ ይም ?”

“ባቱ ምንድነው ? አለ ጥላሁን ።

“ተሸካሚ ፤ ሰውን ባልጋ አድርገው የሚሸከሙ ናቸው ” አለች አቻሚ ።

“እንደ ሬሳ ? አለች ሶፊያ ፡ እዬሳቀች ።”

“እዚህ አገር አልጋ ተነጥፎላቸው ፡ በራስጌና በግርጌ መከዳ ተደ ርጎላቸው ፡ እዚያ ተቀምጠው ፤ ወይም ተኝተው ፤ ሰው ተሸክሞዋቸው የሚሄዱ ታላላቅ ሰዎች ናቸው ፡ ልጂ!” አለች አቻሚ ፡ እሰዋም እዬ ሳቀች ።

“ባቱ እንደነሴራቴ ባለ ቆላ እንጂ በደጋ የሚሰራ አይመስለኝም ነበር ። እዚያ የመኪና መንገድ ስላልተሰራና ፤ በቅሎም የወረደ እንደ ሆነ ንድፍት ቅጽበት ስለማያቆዬው ፤ ፈረንጆችና ታላላቅ ኢትዮጵያ ውያን የሚጉዋዙ አሁን አቻሚ እንዳለቸው አልጋ ተነጥፎ ፤ መከዳ ተደርጎላቸው በሰው ትክሻ ነው ። ልማዱን የጀመሩት በጎሬና በጋም ቤላ ፤ እንዲሁም በደንቢዶሎና በጋምቤላ መሀከል የሚመላለሱ ፈረን ጆች ናቸው ይባላል ” አለ ውብቱ ። ወዲያው ፤ አንድ መኩዋንንት

@OLDBOOKSPDF

ከበቅሎዎቻቸው ወርደው [illegible] ጋር ሲነጋገሩ ትንሽ ቆዩና ፣ ሄደው እተነጠፈው አልጋ ላይ ሲጋደሙ ፣ ሁለት ሰዎች ተሸክመዋቸው ውሀው ውስጥ ገቡ ። እውነትም ውሀው ከተሸካሚዎቹ ወገብ ስላለፈ ፣ አልጋው ላይ ለተኙት መኳንንት በጣም ሩቅ ነበር ።

በቅሎ መሄድ በማይችልበት የቆላ ክፍል ፡ ሰው የበቅሎን ሥራ መስራት የጀመረበትን ሁኔታ ውበቱ ሲተርክ ፡ ጥላሁን መስማቱ እንኳ ዘግንኖት ሳለ ፣ እዚያው ፣ እፊቱ ፡ አንድ መኳንንት ሁለቱን ሰዎች ባንድ ላይ ጠምደው ፣ እስከ ወገባቸው አባህር ውስጥ አጥልቀው ፣ እሳቸው ጫማቸውን እንኳ አንድ ጠብታ ውሀ ሳይነካው መሻገራቸውን ሲያይ ፣ የሚያደርገውን አጥቶ ፣ ጠባዩ ክፉና ፣ መነጫነጭ ፣ እዚያ አብረውት ያሉትን ሁሉ በመኳንንቱ አይን እያዩ ማበሻቀጥ ጀመረ ። ጥላሁን እየተበሳጨና እየተነጫነጨ የተናገረ አብዛኛውን ውበቱን ስለነበረ ፣ ሶፊያ ፣ "ምናልባት ውበቱ ይቀየሙና ይጣሉ ይሆን?" ብላ ሰግታ ነበር ። ውበቱ ግን የጉዋደኛው ጠባይ ድንገት የተለወጠበትን ምክናያትም ፣ ጉዋደኛውንም ደህና አድርጎ ያውቅ ስለነበር፣ አልተቀየሙም ። እንዲያውም ሳቅ ይዞት ፣ ሲስቅ ጥላሁን ያዩው እንደ ሆነ የባሰውን እንዳይቆጣ ብሎ ፣ ፊቱን እያዞረ ነበር የሚስቅ ። በሁዋላ እንዲያውም ጥላሁንን ደስ ለማሰኘትና መነጫነጩን ለማስተው፣ ወደ ነጋዴዎች እየሮጠ ሄዶ አራት ዳውላ የተጫኑ አጋሰሶች ባራት ብር ተከራይቶ መጣና ፣

"የኮርቻ በቅሎዎች ስላጣሁ አጋሰሶች ተከራይቸ መጣሁ" አለ ።

"አጋሰስ ፣ የኮርቻ በቅሎ ፣ ሁሉም ያው በቅሎ ነው እባክህ !" አለ ጥላሁን ፣ አጋሰሶችን ሲያይ እውነትም ስሜቱ ትንሽ እንደ መለወጥ ብሎ ።

"በቅሎማ አጋሰስ ይሁን የኮርቻ ሁሉም . . . ያው በቅሎ መሆኑ እውቅ ነው ፤ ብርቱ ልዩነት ያለው እቃው ላይ ነው ። የኮርቻ በቅሎ ሲሆን ፣ ከፊቱ ዛብ ከቀዳማ ጋር ተጣምሮ በጅ ስለሚጨበጥ ፣ ከታች ርካብ በቀኝና በግራ እግሮች ስለሚረገጥ ፣ የተቀማጩ ሚዛን በበቅሎው ጀርባ ላይ ይጠበቃል ። በጅ የሚጨበጥና በግር የሚረገጥ ነገር ከሌለ ግን ፣ በበቅሎ የተቀመጠው ሰው ቀኝና ግራ መዋለሉ አይቀርም ፤ ልማድ የሌለው ሰው ከሆነማ ትንሽ እንኳ እበቅሎው ጀርባ ላይ አይቆይም ፤ ወዲያው ይወድቃል" አለ ውበቱ ።

@OLDBOOKSPDF

እዚያ ያሉት ሁሉ [illegible] በቀር በቅሎ ፣ ወይም ፈረስ የመቀመጥ ልማድ ያላቸው ናቸው ። ሶፊያ ካገርዋ ወደ አዲስ አበባ ከሄደች በሁዋላ ፣ እሁድ እሁድና በሌሎች የበአላት ቀኖች ተምራ ጥሩ ፈረሰኛ ናት ። እንኩዋን በኮርቻ በሌጣ ፈረስ ስትጋልብ የስጋት ምልክት አይታይባትም ። አቻምየለሽ ግን ፣ የበቅሎ ጀርባ ባይንዋ ከማየት በቀር ተቀምጣበት አታውቅም ። ስለዚህ ፣ ውብቱ ኮርቻ ያልተጫነ በቅሎ የሚጥል መሆኑን ሲናገር ፣ ፍራት ገብቶ ሆድዋን ያሸብረው ጀመር ። ነገር ግን ፍራትዋ እንዳይታወቅባት ፣ ይልቁንም ከሶፊያ ያነሰች መስላ እንዳትታይ ፣ ጥርስዋን ነክሳ ዝም አለች ። ከዚያ በሁዋላ ፣ የሚወራውንና የሚሆነውን ሁሉ በመስማትና በማየት ፈንታ ፣ የምታየውም ፣ የምትሰማውም ያወዳደቁዋን ሁኔታ ብቻ ነበር ።

ቀኑ በጣም ጥሩ ስለነበርና ፣ እስኪመለሱ ዝናብ እንደማይዘንብ ስላመኑ ፣ የዝናብ ልብስም ፣ ጃንጥላም ሳይዙ ፣ ኮታቸውን እንኳ እያወለቁ እመኪናው ውስጥ ትተው ፣ በሸሚዝና በሱሪ ብቻ እንዳሉ እስከ ጉልበት የሚደርስ የላስቲክ ጫማ አድርገው ፣ በያጋሰሳቸው ላይ እዬተቀመጡ ውሀው ውስጥ ገቡ ። አቻምየለሽ መፍራትዋን አፍ አውጥታ አትናገር እንጂ ፣ ፊትዋ ሁሉ ተለውጦ በግልጥ ያሳይ ነበር ። ብቻ ልብ አድርጎ የተመለከታት ሰው አልነበረም ። ባልዋም በቅሎ ተቀምጣ የማታውቅ መሆንዋን ገና ያንለት ማወቁ ነው ።

ነጋዴው በሽባብ ሸብቦ እዬሳበ ፣ መጀመሪያ ውሀው ውስጥ ያስገባት ያቻምየለሽን አጋሰስ ነው ። ሌሎች ፣ እሰዋን ሲያዩ እተርትረው እዬተከታተሉ ገቡ ። ከዚያ ነጋዴው በቅሎዋን እዬሳበ ቀስ ብሎ (ፊት ለፊት) ሲሄድ ፣ አቻሚም ትንሽ በትንሽ ልብዋ እዬሞላ ፣ እዬተዝናናች ሄዳ ፣ ጆሮዎችዋ ሰዎች የሚያወሩትን መስማት ጀመሩ ። ከዚያ፣ ድንገት ቆመና ፣ በቅሎዋ የተሸበበችበትን ጠፍር ፈትቶ ባንገትዋ ጠምጥሞ ፣ ትቶዋት በጉዋደኞቹ ለመድረስ የውሀ ውስጥ ርምጃ በሚፈቅደው መጠን ፈጠን ፈጠን እያለ ሲሄድ ፣ አጋሰስዋም በሱ ለመድረስ መፍጠን ጀመረች ። አቻሚ ነጋዴውን ትቶዋት እንዳይሄድ መለመን እዬፈለገች ፣ ፍራትዋን እፍረትዋ አሸንፎ ዝም አለችት ።

“በጅ የሚጨበጥና በግር የሚረገጥ ነገር ስለሌለ ፣ ቀኝና ግራ መዋለል ፣ ከዚያ መውደቅ ነው !” አለ ውብቱ ቅድም የተናገረው ድምጽ እንደገና በጆሮዋ ። ከዚያ ጥርስዋን እንደ ነከሰች አይኖችዋን ጨፍና ፣ እጅዋን ወደ ፊት ሰዳ ብትዳብስ ፣ እውነትም የሚጨበጥ ነገር

የለ ! እግሮችዋም @OLDBOOKSPDF የሚረዳኝ ነገር ቢፈልጉ አላገኙ ! ወዲያው እጅ የሚጨብጠውና እግር የሚረግጠው ካጣ በሁዋላ ፡ ቀጥሎ የሚመጣው ቀኝና ግራ መዋለል መሆኑ ትዝ ስላላት ፤ ተመዛዝና ብትቀመጥም ወደ ቀኝ ያጋደለች መስሎ ተሰማትና ፡ ሚዛንዋን ለማስተካከል ሰውነትዋን በኃይል ገፍታ ወደ ግራ አጋደለች ። ከዚያ ወደ ግራ የተገፋችው ከመጠን ያለፈ መሆኑ ስለታወቃት ፡ እንደገና ወደ ቀኝ በሀይል ተገፋች ። ያንጊዜ የዳውላው መቀነቻ ላልቶ ኖሮ ፡ ዳውላው ይዞዋት ከኋትሎዋ ጀርባ ወደ ጎንዋ ሲዞር ፡ "ውብቱ" ብላ ጮሀ ፤ ውሀው ውስጥ ጥቡልቅ አለች ። ወዲያው ሁሉም ደንግጠው ከያጋሰሳቸው እየዘለሉ ውሀው ውስጥ ገብተው ቶሎ አወጡዋት ። ከዚያ ውብቱ አዝሎዋት ፤ ሰፊያና ጥላሁን አጅበዋት ፡ እስከ ባሮ ወንዝ መሻገሪያ ድረስ በግራቸው ሄዱና እዚያ አወረዱዋት ።

"እንግዲህ ራሳቸውን ዘቅዝቃችሁ በሆዳቸው አስተኙና ንቅንቁዋቸው ፤ ጌቶች " አለ ያጋሰሶች ጌታ ። እውነትም ነጋዴው እንዳለው ዘቅዝቀው ሲነቀንቁዋት ከመጠን ያለፈ ውሀ ወጣ ። ከወደቀችበት ለመነሳት ስትታገል ፡ ባፍር ፈንታ ውሀ እየሳበች ሰውነትዋን ሁሉ ሞልቶት የነበረው ውሀ ባፍዋም ፤ ባፍንጫዋም ወጥቶ አልቆ እንደ ልብዋ መተንፈስ ስትጀምር ፡ ሁኔታዋ ሁሉ ትዝ አላትና ሳቅ መጣባት ፤ እስዋን ሲያዩ ፤ ሁሉም ይስቁ ጀመር ። ሰፊያማ መቸም ስቃ አላባራ አለች ።

"ደመና ሳይዞር ልብሳችንን በጥሩ ውሀ እየለቃለቅን ጠምዝዘን ብንለብስኮ በላያችን ቶሎ ይደርቅ ነበር !" አለ ውብቱ ፤ ሳቁን ለማቁዋረጥ ጭምር ።

"እውነትህ ነው ፤ ተነስ እንሂድ" አለና ጥላሁን ከውብቱ ጋር ባንድ ወገን ሲሄዱ ፡ እቻሜና ሰፊያም በሌላ ወገን ሄደው ገላቸውንም ፤ ልብሳቸውንም በጥሩ ውሀ ለቅልቀው እየለበሱ መጥተው ፤ አንድ ጉብታ ላይ ተቀምጠው ባለቢድሩዎች ሰውን ፡ ከብቱንና ጭነቱን ሰዑብቻ ሲያሻግሩ ይመለከቱ ጀመር ።

ወንዙ እመሻገሪያው ላይ በስፋት ሁለት መቶ ሜትር ያክል በቁመት ከሰባ እስከ ሰማንያ ሜትር ያክል ፡ ደንጋይ የሌለበት ስለሆነ ፤ በተለይ ወደ መሀከሉ ላይ በጣም ፈጣን ፤ ፈረሰኛ ከመሆኑ በቀር ፤ ድንበሌ የለውም ። ከመሻገሪያው በላይና በታች ግን ፤ ደንጋያማ በመሆኑ ደንበሌው እዚህም ፤ እዚያም ፡ በዑቦታው ሲያናጥር ልጉቀም የያዙበት አጥባቂ አምባላይ መስሎ ፤ እየዘለለ ወደ ላይ ሲወ

@OLDBOOKSPDF

ጣና እንደገና ሲመ[illegible] ሁሉ ልቡ በደስታና በሲቃ ይዋ ላል ። ያ ከደንጋይ ጋር እየተማታ ወደላይ ጉኖ የሚመለሰው ውሀ ፣ ያ ደንበሌ ፣ ቀጥተኛ መንገዱን ትቶ ወደ ጎን እየተንተ እዬሄደ ፣ ክብ መስመር አበጅቶ ፣ እዚያ እንደ ትግሬ ዘፋኝ ዙሪያውን እዬተ ሽወረወረ የሚጨፍርበት ቦታ አልፎ አልፎ ይታያል ። አዘጥሪት ነውነ ተጠልፎ እዚያ የገባ ወዮለት ! መውጫ የለውም !

ባለቢድሩዎች እንደዬቢድሩዋቸው ትንሽና ትልቅነት ፣ ከሶስት እስከ አራት ሰዎች ድረስ ያሳፍሩና ፣ የሚቻለውን ያክል ወደ ላይ ከፍ ብለው በመልካው አናት ገብተው እዬቀዘፉ፣ እዬቀዘፉ ፣ ውሀው በጣም በሚጋልብበት ሲደርሱ ፣ ከመንገዳቸው ወጥተው በቅጽበት ከሰላሳ እስከ አርባ ሜትር ወደ ታች ከተወረወሩ በሁዋላ ፣ በሚያስ ገርም ፍጥነትና ዘዴ ፣ በስላች እዬቀዘፉ አሳብረው ፣ ከሚፈጥነው ረጋ ብሎ ወደሚሄደው ውሀ ይገባሉ ። ከዚያም ትንሽ በትንሽ እያሉ ፣ እንደገና ወደ መስመራቸው እዬገቡ ይሻገራሉ ። ቢድሩዎች ከሰላሳ እስከ አርባ ሜትር ወደ ታች በሚወረወሩበት ጊዜ ፣ ከፍጥነታቸው የተነሳ ፣ በውሀው ላይ በክንፍ የሚበሩ ነገሮች ይመስላሉ ! ያ ፈረ ሰኛ ውሀ ቢድሩዎችን የሚያደርጋቸውን ድርጊት ለመጀመርያ ጊዜ እዳር ሆኖ የሚመለከት ፣ ከተሳፈሩት ሰዎች ተርፎ የሚወጣ የሚኖር አይመስለውም ። ነገር ግን ፣ "ባሮ ከባለቢድሩ ሰው ቀምቶ በላ" ሲባል ተሰምቶ አያውቅም ።

ከዚያ ባለቢድሩዎች ሰው ማሻገሩን ትተው ፣ ከብት ማሻገር ጀመሩ ። ከብቶችን በቢድሩ የሚያስገቡዋቸው እስከ ፈረሰኛው ውሀ ለማድረስ ያክል ብቻ ነው ። እዚያ ሲደርሱ እዬዘለሉ ውሀው ውስጥ ገብተው በዋና ስለሆነ የሚሻገሩ ፣ ሰዎች ከሚሳፈሩባቸው ቢድሩዎች ጋር እንዳይጋጩ ፣ ሰውና ከብት ባንድ ጊዜ ማሻገር ክልክል ነው ። ስለዚህ ሰዎች ሲሻገሩባቸው የቆዩት ቢድሩዎች ቦታ ለቅቀው ፣ ከብ ቶች የሚሻገሩባቸው በተራ እንደ ተሰለፉ ፣ " መላሾ" የሚሉትን ያሞሌ ጨው ስባሪ ፣ ወይም አንኳር የያዙ ሰዎች ወደ አጋሰሶች ቀረብ እያሉ ፣ ትንሽ ያልሱዋቸውና መላሾውን እያሳዩዋቸው እቢድሩው ውስጥ ሲገቡ ፣ እሱን ፍለጋ ተከትለው ይገባሉ ። ከዚያ ጨው የቀ መሱት ጨዉን ተከትለው ፣ ያልቀመሱት የቀመሱትን ተከትለው ይገ ባሉ ። በዚህ አኳሁዋን ፣ ስድስት አጋሰሶች በሶስት ቢድሩዎች ከገቡ በሁዋላ ፣ ተመልሰው እንዳይወጡ ቶል ቶሎ የሚቀዝፉት እዬቀዘፉ ቢድሩዎችን የሚገፉት እዬገፉ ፣ ወደ ፈረሰኛው ውሀ ሲደርሱ ፣

@OLDBOOKSPDF

"ውይ . . . ! [illegible] ዎን ወሰዳት ! ሁሉንም ወሰዳቸው !" አለች ሶፊያ ፡ ከብቶች ሁሉ ከተሳፈሩባቸው ቢድሩዎች ተከታትለው እየዘለሉ ወ[illegible] ውስጥ ሲገቡ ስታይ እጆቹዋን እያርገበገበች ፤ ከተቀመጠችበት እንደ ኩዋስ ነጠራ ተነሰታ ። ጥላሁንም ፤ ውብቱና እቻሜም ደንግጠው ተነስተው ፡ እፋቸውን በሰፊው እዬከፈቱ ይመለከቱ፡ ጀመር ።

"አይዞዋችሁ አትስጉ ፤ ምንም አይሆኑ ። ከብት የቱም ዋና ስለሚዋኝ ፤ እንደ ሰው ተኝቶ ስለማይዋኝ ፡ ፈረሰኛ ውሀ ንቅንቅ አያደርገውም !" አለ አንድ የሶፊያንና የጉዋደኞቹዋን ድንጋጤ እዚያ አጠገብ ቆሞ ይመለከት የነበረ ነጋዴ ፡ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ ። እውነትም ቢድሩዎችን ከመንገዳቸው እያስወጣ ዘቅዝቆ ይወረውራቸው የነበረው ፈረሰኛ ውሀ ፡ ከብቶችን ምንም ያክል ገፍቶ መንገድ አላስለቀቃቸውም ። መንገድ መሪያቸው የቀደደላቸውን መስመር ሳይለቁ ፡ ሁሉም አፍንጫቸውን ውሃ እንዳይነካው አንገታቸውን ቀና አድርገው እስክስታ እንደሚወርዱ እያረገረጉ ፡ ወንዙን ቆርጠው ሲሄዱ እጅግ ደስ ያሰኙ ነበር ።

"ጤና ይስጥልኝ በኸርሮንድ ፤ እንደምን አሉ ። እሁንኮ ነው እርስዎ መሆንዎን ሰዎች የነገሩኝ ። ወይ ግሩም ! ይመጣሉ እዬተባለ ስንት ቀን ስንጠብቅ ኖረን ፡ ዛሬ ባላሰብንበት መጡ ?" አለ አንድ ሰው ፤ እዚያ ተሰብስቦ ከሚንጫጫው ብዙ ህዝብ መሀከል ተለይቶ ከሁለት ተከታዮቹ ጋር መጥቶ ፡ የውብቱን እጅ ካስቀመጠበት ሳያስበው ድንገት በሁለት እጆቹ ጨብጦ እስኪያመው በሀይል እያራገፈ። ሰውዬው በቁመቱ በጣም ረዥሞች ከሚባሉት መሀከል የሚቆጠር ባይሆንም ፡ ከመሀከለኞች በላይ የሆነ ፡ ወፍራም ስጋ ባይኖረውም ሸጥንተ-ሰፊ ፡ አይኖቹ ፡ አፍንጫው ፡ ከናፍሩ ፡ ጥርሶቹና ሌላው ቁጥር መልኩ ለዬብቻ "መጥፎ ነው" የሚባል ነገር ባይኖረውም ፤ ሁሉም ባንድ ላይ ሲታይ ደስ የማይል ፤ " ደም ግባት የጎደለው" የሚሉት አይነት ነው ። ባለባበሱም ፡ በድፍ መልኩ ወደ ቆዳነት የተለወጠ፤ ካኪ ባርኔጣ ከማድረጉና እስከ ጉልበት የሚደርስ የጎማ ጫማ በግሩ ከማጥለቁ በቀር ፤ እዚያ ከተሰበሰበው ነጋዴና ባላገር ምንም ያክል ልዩነት አይታይበትም ።

"ጤና ይስጥል . . .ኝ" አለ ውብቱ ጥርሱን ነክሶ ፤ ሰውዬው እጁን አጥብቆ ጨብጦ ስላሳመመው ለመላቀቅና ፡ ከተቀመጠበት ለመነሳት እዬተጣጣረ ።

@OLDBOOKSPDF

"የለም አይነሱ ፤ እዚያው ይሁኑ ፤ በግዜር አይነሱ" አለ ሰውዬው፡ ባንድ እጁ የውብቱን እጅ እንዳ ያዘ፡ በሌላው ትከሻውን ይዞ በሀይል ወደ ታች እየተጫነ ።

"አወቁኝ ?" አለ ቀጠለና ። "መልኬን አያውቁም ይሆናል፤ አዎን ስላልተገናኘን መልኬን አያውቁም ፤ ስሜን ግን እንደሚያውቁ ርግጠኛ ነኝ ። ልጅ ድባቤ ብሩ ግለት እኔ ነኝ ፤ እንግዲህ ይወቁኝ!"

"ልጅ ድባቤ ብሩ ፤ ልጅ ብሩ !" አለ ውብቱ ፡ ያን ስም ከዚያ ቀን በፊት መስማቱ ትዝ አልለው ስላለ ግር ብሎት ። "ይቅርታ ያድርጉልኝ ፤ ረስቸ ይሆናል" አለ ቀጠለና ፡ አይኑን ሳያረግብ በልጅ ድባቤ ብሩ ላይ እንዳ ተከለ ፡ ሊሰበር እስኪደርስ ተጨብጦ ቆይቶ በግድ የተለቀቀ ቀኝ እጁን በግራው እያሻሸ ።

"ባለ-ስራ አይደሉ ! ባለ ስራ ሰው ቢረሳ አይፈረድበትም ። እና . . . ባለ ስራ ስለሆኑ ረስተው ነው እንጂ ፡ የኔን ስም ሳይሰሙማ እንዴት ይቀራሉ ? ልጅ ድባቤ ብሩ ሲባል . . . ሀ . . . ሀ ! ልጅ ድባቤ ብሩ ሲባል . . . በሙሉ ኢሉባቦር የማያውቅ ይገኛል ? እሱን ግዴለም ፤ ወደ ፊት ይሰሙታል ! አሁን ይነሱ እንሂድ" አለ ድባቤ ።

"ወዴት !" አለ ውብቱ ግር እንዳለው ።

"ወደቤት ። መቸስ እዚህ ደርሰው ቤቱን ሳያዩና ፡ እዚያ ትንሽ አርፈው ቡና ሳይጠጡ አይሄዱ ! ይበሉ ይነሱ ፤ ይነሱ እንሂድ ጌታዬ" አለ ፡ ልመና ይሁን ትእዛዝ ቅጡ በማይታወቅ ያነጋገር ስልት ።

"እግዚአብሔር ይስጥልን ፤ ቤት ማየቱና ቡና መጠጣቱ ለሌላ ቀን ይሁንልን ፤ አሁን ልጆቻችንን ፡ ልብሳችንን እንከዋ ፡ እዚያ ከውሀው ማዶ ትተን ስለ መጣን መሄድ አለብን" አለ ውብቱ፡ ልጆችንና ልብሳቸውን ትተው የመጡበትን በጁ እያመለከተ ።

"አውቄያለሁ ፤ መቸ አጣሁት ፤ ልጆችንም ፡ ሁሉንም በዚያው ስናልፍ እንወስዳቸዋለን ። ቤቱምኮ በዚያው በኩል ነው ፤ ያ እቀቡቱ ላይ የሚታየው ነው"

"እግዚአብሔር ይስጥልን ፤ ሌላ ጊዜ እንመለሳለን ፤ ዛሬ እቤታችን እንግዶች ስለ ቀጠርን ቶሎ መመለስ አለብን ።

"እማይደረገውን ! እስቲ በዚህ አልፎ እኔ ቤት ገብቶ ሳያርፍና ቡና ሳይጠጣ የሄደ በኸሮንድ ፡ ዲኔክቴር ፡ ጠቅላይ ጸሐፊ ፡ ጠቅላይ . . . እንደራሴ እንከዋ ማነው ! ማንንም ሊጠይቁ ይችላሉ ። በለ

@OLDBOOKSPDF

ሂድ አንተ ባቴ ጥሯ !" አለ ድባቤ ፤ ከተከታዮቹ አንዱን ፤ ገና እን ውበቱ ወደ ቤቱ ለመሄድ መፍቀዳቸውን እንኳ ከቃላቸው ሳይሰማ። ውብቱ የሚለው ቅጥ ጠፍቶት ድባቤን ትቶ ጉዋደኞቹን ቢመለከት ፤ ሁሉም ሳቅ መጥቶባቸው ፤ እንዳይስቁ አፍረው ፤ መሬት መሬት እያዩ ሲቸገሩ አይቶ ሲስቅ ገቢ ፤ ተያይዘው ይስቁ ጀመር ፤ ድባቤም የሳ ቁበት ምክንያት ገብቶት ሳይሆን ፤ ሳቃቸው ተጋብቶበት አብሮዋ ቸው ይስቅ ጀመር ።

"ይቅርታ ያድርጉልን ጌታ ፤ እኛ በባቴ እንሂድም" አለች ሶፊያ ፤ ለትስቅ ቆይታ ።

"እኔ በባቴ ነው የምሄድ ጌና ቴ !" አለች አቻሜ ።

ከዚያ ላቻሜና ለድባቤ ባቴዎች ፤ ለቀሩት በትሉዎች ተርበው ላቸው መኪናዋ በቆመችበት ሲደርሱ ፤ በበቅሎ የተሻገሩት ውሀ ውስጥ የተነከረ ልብሳቸውን እዩጠመዘዙ ትንሽ ጠፈፍ ሲል ለብሰው ፤ ወደው ሳይሆን ድባቤ ፤ "መስተንግዶዬን ገፉ" ይለናል ብለው ፤ በይሉኝታ ተገደው ፤ መኪናዋን እዚያው ለጠባቂ ትተው ፤ አሽከሮች ጭምር ወደሱ ቤት ሄዱ ።

የድባቤ ግቢ በሰንሰልና በግራዋ ተከብቦ ታጥሮ ፤ በውስጡ ክል ፍኙና ካዳራሹ ፤ ከማድ ቤቱ ሌላ ፤ ብዙ ጎጆዎችና ጎጆ የሚመስሉ ጎተራዎች ይታያሉ ። እልፍኙ ባጡ ጥሩ ሆኖ ተከፍክፎ ፤ ግድግዳው በውጭም ፤ በውስጥም ፤ በበትና ባመድ ብጥብጥ የተለቀለቀ ፤ እን ዲሁም ወለሉና መደቦች ሁሉ በበትና ባመድ የተለቀለቁ ናቸው ። በመ ደቦች ላይ ባንዳንዶቹ ዳውጃዎች ፤ በሌሎቹ አጎዛዎች ተነጥፈውባቸዋል።

"ቶሎ ቁርስ አስቀርቢልን በላት እናትህን አንተ ፤ እና . . እና… አንተ ደግሞ ቶሎ የጣት ውሀ አምጣ " አለ ድባቤ ፤ እንግዶቹን ካስቀመጠ በሁዋላ ፤ ዘጠኝ ፤ ወይም አስር አመት ያክል የሚሆነው ልጁ እዚያ ቆሞ ስለነበረ ። ልጁ ካስታጠበ በሁዋላ ፤ ቀይ ቀሚስ የለበሰ ትልቅ መሶብ ተሸክሞ አምጥቶ ፤ በሁለቱ ባልና ሚስቶችና ባድባቤ ፊት አስቀመጠ ። ቀጥሎ በውበቱ አሽከሮች ፊት የተከደነ የሳጠራ መሶብ አምጥቶ አስቀመጠ ።

"እንካ አንተ ልጅ " አለ ድባቤ ፤ የመሶቡን እፊያ በቀሚሱ እንደ ተሸፈነ ከመሶቡ ላይ አንስቶ ። እንግዶች ቁርስ ተብሎ የቀረ በላቸውን ነገር ሲያዩ ሁሉም ደነገጡ ። ድንጋጤው ሲያልፍ ሴቶች ሳቅ መጥቶባቸው ፤ እንዳይስቁ ፈርተው ይጨነቁ ጀመር ። በንጀራ

@OLDBOOKSPDF

ሰም የቀረበው ፤ ከባቲላና ከጸጉሳ ዱቄት ባንድ ላይ ተደባልቆ የተጠፈጠፈ ፤ ያይን ምልክት የማይታይበት ፤ አወፋፈሩና መክረሩ ለከብት የሚሰጥ ደረቅ ጥረሽ እንጂ ፤ እንጀራ የማይመስል ነው ። በላዩ ትኩስ አብሲት የመሰለ ፤ አልፎ አልፎ ትላልቅ የባቄላ ክክ የተንጠባጠበበት ነገር ፈሶበታል ። ወጥ መሆኑ ነው ! ከዚያ ሁሉም እንደተማከሩ ባንድ ላይ ላሸከሮች ፤ ላብዲሳና ለጃለታ ወደ ቀረበላቸው ቢመለከቱ ፤ የባቄላና የስንዴ ድብልቅ ንፍሮ ቀርቦላቸው ስላዩ ፤ ሁሉም እሱን መመኘታቸውን የሚገልጽ አስተያየት ተለዋወጡ ።

"በሴላ ቀን እክላችሁዋለሁ ጎበዝ ፤ ዛሬ . . . ያልተጠነቀቅሁበት ቀን ሆኖ ነው " አለ ድባቤ ፤ ላሽከሮች ንፍሮ ስለ ቀረበላቸው ጌቶቻቸው የተቀየሙ መስሎት ።

"ኧረ በጣም ጥሩ ነው ፤ ተስማምቶናል " አሉ አብዲሳና ጃለታ እዩተቀባበሉ ።

"የጠባህት መድኃኒትኮ አላሻረኝም ፤ አሁን ብበላ ምንም አይለኝ ጥላዩ ?" አለች ሶፊያ ፤ ውሸቷዋን ፤ ብይ እንዳትባል ።

"ከበላሽማ አያሽርሽም ፤ ባትበይ ይሻላል " አለ ጥላሁን ፤ እጠውቆባት ። ሶፊያ ነፃ ወጣች ። እቻሚ ግን ሶፊያ የሰጠችውን ምክናያት እንዳትደግም ውሸት መሆኑ የሚታወቅ ስለሆነ ፤ ሌላ ምክናያት ፈልጋ ስላጣች ተጨነቀች ። ለመብላትም ብታስብ ሆድዋ ሁሉ ታወከባትና እፍኖ ውሀ ሲሞላ ፤ አይኖችዋ ሲቀሉ ባልዋ ተመልክቶ፡

"እንደ ገና ተሰማሽ ? እስቲ . . ወደ ነፋስ ውጪ " አለ ።
" እ·ም !" አለች እቻሚ ፤ "እዎን" ለማለት እፍዋን እንደ ገጠመች ግንባርዋን ወደ ላይ ገፍታ ።

"በሞትሁት ! ምን ሆኑ ?" አለ ድባቤ ፤ ለመቅመስ ቆርሶ ፤ በወጥ የነከረውን ቂጣ በጁ እንደ ያዘ ።

"ትድም ውሀ ውስጥ ወድቃ ሲያስታውካት ቆይቶ . . ትንሽ ተሽሎዋት ነበር ። አሁን እቤት ስለገባች ነፋስ ሲያንሳት ጊዜ . . . ሲመለስባት ነው መሰለኝ ። ወደ ነፋሱ ሂጂ ፤ ሁላታችሁም ሂዱና ሁዋላ ቡና ስንጠጣ ትመጣላችሁ " ሲል ውቤ ፤ እቻሚና ሶፊያ ደስ ብሎዋቸው እዩሮጡ ወጡ ። ውቤና ጥላሁን ግን ፤ ያን እንኩዋንስ መብላት ማየት የሚያስጸይፍ ነገር ፤ በይሉኝታ መብላት ጀመሩ፤ እያንዳንዱን ጉርሻ በያፋቸው ሲያንከራትቱ ቆይተው ፤ በሚውጡበት

@OLDBOOKSPDF

ጊዜ የተዘጋ ጉሮሮዋቸው አልከፈት እያለ በግድ እየታገሉ ፣ በግድ እየገፉ ፣ ሲውጡ እያያቸው ፣ ድባቤ ጥሩ ድግስ እንዳሰናዳ ሁሉ ፣ ቋጣውን በዶዮው ይነከርና ፣ አንድ ጊዜ በውብቱ ፣ አንድ ጊዜ በጥላሁን እጅ እያደረገ ፣

"እሾ ፤ እሾ ፤ ይብሉ አባክዎ የኔ ጌታ ፤ እኔን ደስ እንዲለኝ" ይላል ።

"እኔ አፈር ስበላ ፤ እንክት ፣ ምሽክ ስል ብሉልኝ እባካችሁ !" ይላል አሁንም በጃቸው የያዙትን ሳይበሉት በላይ በላዩ እየጨመረ ።

"እስቲ . . በጃችን የያዝነውን እንብላው ይተዉን እባክዎ !" አለ ውብቱ ፣ በሁለት እጁ የተሸከመው እንዳለ ደግሞ ይዞበት ሲመጣ ጊዜ ።

" ይችን ብቻ ፤ ሁለተኛ አልመጣም " አለ ድባቤ ።

"ይችን ነው ፤ በቃ እንግዲህ ፤ እርም ነው ፤ ያባቴን ስጋ ሁለተኛ አልመጣም ፤ በውጭ የተገኘ ነገር ባይጥምም እቤት ያደርሳል ብዬ ነውኮ !" አለ አሁንም በዶዮ የተነከረ ቂጣውን ይዞ ወደ ጥላሁን እያመራ ። ጥላሁን መከላከሉን ትቶ ይስቅ ጀመር ።

ድባቤ ፣ "ሁለተኛ አልመጣም" እያለ መላልሶ ከማለ በሁዋላ ፣ መሀላውን ጥሶ ማስቸገሩን ፣ መሀላ የማያቆመው መሆኑን ፣ ሲያዩ ውብቱና ጥላሁን በጃቸው የያዙትን በመብላት ፈንታ እመሶቡ ላይ እያስቀመጡ ፣ የሚሰጣቸውን መቀበል ሲጀምሩ ጊዜ ተዋቸው ።

"እንዲያው . . ሰው ባገሩ እንደሌለ እቤት ሳትገቡ ከውጪ እንዳትመለሱ ብዬ ነው እንጂ . . 'ለናንተ ፣ ለጌቶች የሚሆን ነገር አለኝ' ብዬኮ አይደለም !" አለ ድባቤ ፣ በተናገረው አምኖ ሳይሆን ፣ ከንግዶች ምስጋና ለመቀበል ሲል ።

" እረ በጣም ጥሩ ነው ፤ ያውም እንግዳ ይመጣብኛል ብለው ሳይጠነቀቁ በድንገት ! እንዲህ ያለም የለ !" አለ ውብቱ ።

"ያንድ ቀን ማስጠንቀቂያ ቀደም ብሎ ተሰጥቶኝ ቢሆን ኖሮማ... ሙቸ እንዲህ ነበር ! "

"አሁንም ቢሆን ምንም የጎደለ ነገር የ . . . ለ ፤ ምንም አያስቡ" አለ ውብቱ ፣ እነ አብዲሳ የሚበሉትን ንፍሮ አይኑ ሰርቆ ሲያይ አሳቡ ወደ ንፍሮው ሄደ ። "እስቲ እንዲህ ያለ ጥሩ ንፍሮ እያለ እሱን ቢሰጠን ሳይቸግረው . . ጥቁር ቂጣ በነጭ አብሲት አቅርቦ ፣ 'ካልፈ

@OLDBOOKSPDF

ችሁ’ እያለ የሚያበሳጭ ነው እለ ?” እለና ውብቱ ባሳቡ ፣ ከት ብሎ ሲስቅ ጊዜ ፤ ለጊዜው ሁሉም ደንገጡና ፤ በሁዋላ ፣ ምንም የሳቀበትን ባያውቁ አብረውት ሳቁ ።

“እናንተን ፤ የዛሬን ጌቶች ከድሮዎቹ ጋር ሳስተያይ በጣም ይገርመኛል !” እለ ድባቤ መሶብ ተነስቶ ፤ ሴቶችም ተመልሰው ፣ ቡና ሲጠጡ ።

“እንዴት ?” እለ ውብቱ ።

“የድሮ ጌቶች ከከተማቸው ወጥተው ወደ ባላገር መሄድ ሲያስቡ ፣ ቢያንስ አንድ ሳምንት አስቀድመው የሚተላለፉበትን መንገድ ሳይቀር ስለሚያስታውቁ ፤ በደረሱበት ሁሉ ሰንጋና ጠጅ ሳይቀር እየተደገሰላቸው ፤ ግብር ሲያበሉ ፤ መተያያ ሲቀበሉ ውለው ፣ አድረው፣ አንዳንድ ጊዜም ሰንብተው ነበር የሚመለሱ ። የዛሬ ጌቶች ግን ፣ እንዲህ እንደ ዛሬው ድንገት ብቅ ትሉና ፤ ‘መተያያ አምጡ’ ማለቱ ቀርቶ ቡና አፍልቶ ‘እባካችሁ ጠጡልኝ’ የሚል የተገኘ እንደሆነ እንኩዋ … ለዚያ ገንዘባችሁን ከፍላችሁ ትሄዳላችሁ ! እኔ.. በጣም ነው የምገረም ። እዚህ እኔ ቤት ስንት በኸሮንዶች ፤ ስንት ዲኒክቲቶሮች፣ ጠቅላይ ጸሐፊዎች . . ጠቅላይ እንደራሴዎች እንኩዋ ገብተዋል ! ታዲያ ሁሉም ቡና ጠጥተው ሲሄዱ ፤ እንዲያው ቢያንስ ቢያንስ አምሳ ብር ሳይሰጥ የሄደ የለም ። የጠቅላይ እንደራሴዎች ነገር መቸስ ሌላ ነው ፤ አቅማቸውም የዚያኑ ያክል ነው ! እንደራሴዎች፣ ‘የበሬ መግገ ይሁንህ ፤ የበቅሎ መግገ ይሁንህ’ ይሉና የተከተሉዋቸው ሰዎች ሳያዩ መቶ ፤ መቶ አምሳ ፤ እስከ ሁለት መቶ ብር እኪሴ ውስጥ ሽጉጥ ያደረጉልኝ አሉ ። መስጠቱ ብቻኮ አይደለም ! ያሰጣጡ መንገድ እንኩዋ ልዩ ነው ! የድሮ ጌቶች ሲሰጡ እንኩዋ ባሽከር እጅ ነው እንጂ በጃቸው አይሰጡም ነበር ። ‘ይህን ያክል ስጠው !’ ይላሉ ። የዛሬዎቹ ግን ስትሰጡ በጃችሁ ፤ ያውም ለብቻ፣ አሽከር ሳያያችሁ ነው ! እረ ልዩነታችሁ የት ተቀራርቦ ! እግዜር መንግስቱን ያጥናው እንጂ የዛሬን ጌቶች . . . የመሰለ የለም !”

“ይህ ሁሉ የምስጋና ጋጋታ ገንዘብ ስጡኝ ለማለት ነውኮ ! ገባቶዋችሁዋል ?” እለ ውብቱ በንግሊዝኛ ፤ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ ፣

“እቤቴ ካልገባችሁ ብሎ ያን ያክል ማስጨነቁስ እንዲያው መሰለህ ? ለዚህ ነውኮ ! መስጠት አለብህ” አለች ሚስቱም ፣ እንዲሁ በንግሊዝኛ ።

@OLDBOOKSPDF

ሲወጡ ፣ ውብቱ ድባቤን ለብቻው ወስዶ ፣ ስለ መስተንግዶው በጣም ካመሰገነው በሁዋላ እሱ እንዳለው ፣ "ሰዎች ሳያዩ ስድሳ ብር እኪሱ ውስጥ ሽጉጥ" አደረገለት ።

"አይ . . .ምን አሳሰብዎት ?" አለና ድባቤ ፣ ምንም እፍረት ሳይ ሰማው ውብቱ እኪሱ ውስጥ የሸጎጠለትን ገንዘብ ቶሎ አውጥቶ እፊቱ ይቆጥር ጀመር ።

"የበቅሎዎችንና የባቱዎችን ኪራይሳ . . . እኔ ከዚሁ ልከፈል መሰለኝ !" አለ ፣ ገንዘቡን ቆጥሮ እኪሱ ካገባ በሁዋላ ።

"የለም እሱንማ እኛ እንከፍላለን ፤ ስንት ነው ?" አለ ውብቱ ።

"ለባቱዎች ባሌጋ ሶስት ብር ፣ ለሁለት አሌጋ ስድስተ ብር ፣ ለበቅሎዎች ባንድ በቅሎ ሁለት ፣ ለሶስቱ ስድስት ፣ በድምሩ አስራ ሁለት ብር ነው ።"

ውብቱ ጥዋቱን እሱ ላንድ በቅሎ የከፈለው ኪራይ አንድ ብር ሰለ ነበረ ፣ አሁን ድባቤ የጠየቀው ኪራይ ትክክለኛ አለመሆኑን ቢያውቅም ፣ አፍሮ ፣ ያላንዳች ጥያቄ የተጠየቀውን ከፍሎ፣ እን ደገና አመሰግኖ ፣ እዚያው እንዲሰናበቱ ቢለምነው፣ ድባቤ ፣ "አይ ቃጣም" ብሎ እስከ መኪናው ድረስ አብሮዋቸው ሄደ ። ከዚያ የጫ ኑትን ልዩ ልዩ ድግስ እንዳይበሉ ከፉ እድል ድባቤን አገዞባቸው ፣ የጾም ውሎ ዋጋ ውብቱ ሰባ ሁለት ብር ከፍሎ ፣ ድግሳቸውን እንደ ጫኑ እዩተገረሙም፣ እዩሳቁም ፣ ተመልሰው እቤታቸው ገቡ ።

@OLDBOOKSPDF

## ምእራፍ ፲፩

## የኪ

አቻምየለሽና ውብቱ ፣ ጥላሁንንና ሶፊያን ጎሬ አብረዋቸው እንዲቆዩ ለማድረግ ይፈጥሩት የነበረው መላ ሁሉ ማለቅ አይቀርምና ፣ አልፎ ሁለቱ መንገደኞች ጉዞዋቸውን ወደ መጨረሻ መድረሻው የሚቀጥሉበት ጊዜ ሲደርስ መለያየቱ ፣ በተለይ ለሴቶቹ ሞት መስሎ ታያቸው።

ሶፊያና አቻምየለሽ አብረው የሰነበቱበት ጊዜ አጭር ቢሆንም፣ በዚያ አጭር ጊዜ በጣም ተለማምደው ፣ ከመዋደዳቸው የተነሳ በዱስማቸው ፣ መጠራራቱን እንኳ ትተው ፣ "ውሮ፣ ፉኖ" ነበር የሚባባሉ፤ አቻሜ ሶፊን-ፊት ክብ ስለሆነች ፣ "ውሮ" ትላታለች። ሶፊ በበኩልዋ ፣ አቻሜን አፍንጫዋ ትንሽ አጠር ያለ ስለሆነ ፣ "ፉኖ" ትላታለች። ስለዚህ ውሮና ፉኖ የተለያዩ እለት ተያይዘው ሲላቀሱ ፣ ተዋድዶ መለየት የተወው ሀዘን በዩልቡ የተኛበት ጎረቤት ሁሉ ፣ እነሱን ሲያይ ተቆስቅሶበት ፣ ከነሱ ጋር አብሮ ያለቅስ ጀመር።

ውብቱ ፣ ለጥላሁንና ለሶፊያ መሬታቸውን ለማስረከብና ፣ ወዲያውም ከየኪ ሹማምንት ጋር አስተዋውቆዋቸው ፣ እንዲረዱዋቸው አደራ ለማለት አብሮዋቸው መሄድ ስለ ነበረበት ፣ ከጎሬ እህዳር አጋማሽ ላይ ተነስተው ፣ በበቅሎ ቀስ እያሉ ተጉዘው የኪ እስኪደርሱ ፣ አምስት ቀን ፈጀባቸው። ከመስከረም እስከ ኅዳር፣ አንዳንድ ጊዜም እስከ ታህሳስ መጨረሻ ያለው ጊዜ ፣ በየኪና ባካባቢው ካመቱ ሁሉ እጅግ የሚያምር፣ ደስ የሚያሰኝ ወራት ነው። ያ ወራት መሬት ከማናቸውም ጊዜ የበለጠ ባበባና በፍሬ አጊጣ ፣ አምራ ፣ የምትታይበት ነው ። በመንገድ ሲሄዱ በቆኝና በግራ ፣ በግልጽ ቦታ ያለው የቡና ዛፍ ሁሉ ፍሬው ቀልቶ፣ ከእግር እስከ ራሱ ጃኖ የተከናነበ መስሎ፣ በከፊል ትላልቅ ዛፍ ያጠለበው እንዲሁ በከፊል ቀይ ፣ በከፊል ዳማ ፣ በከፊል አረንጉዋዴ ሆኖ፣ ነገር ግን ሁሉም ፍሬው ስለ ከበደው ራሱን ወደ መሬት አዘንብሎ ፣ ባንድነት ሲታይ፣ ለጌጥ በልዩ ልዩ ቀለም አገነጎርጉሮ እጅ ለማስነሳት ያለለፉት ይመስላል ። ያ ወራት ፣ በየኪና ባካባቢው ሁሉ ፣ ከቦቆሎውና ከዶንቃው እውጭ በሽቱ ከሚበላው የተረፈው እቤት ገብቶ ፣ "የድህ ድሀ

@OLDBOOKSPDF

ከሚባሉት በቀር ፣ አብዛኛው ሕዝብ ጠግቦ የሚያድርበት ወራት ነው። ያ ወራት ፣ ቡና ሲለቀም ከሩቅ የሚሰበሰበው ሙያተኛ የለቀመበትን ባለርስት ይሁን ጢሰኛ ባላገር ቡና የሸጠበትን ይዞ ፣ የልብስ መልበስ ልማድ ከሌላቸው በቀር ፣ ልብስ እያማረጠ ሲገዛ ፣ ስጋ እያማረጠ ሲበላ፣ ጠጅና አረቄ እያማረጠ ሲጠጣ የሚታይበት ወራት ነው ። ያ ወራት ፣ በተለይ የዚያ አገር ተወላጆች የሆኑት የቤት አባቶች ፣ ከምሽቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር ፣ ትናንሽ ልጆች እንኳ ሳይቀሩ ፣ ቡና የሸጡበት ገንዘብ እስኪያልቅ በልተው ፣ ጠጥተው ፣ ሰክረው ፣ ትናንትንም ነገንም ረስተው ፣ ዛሬን ብቻ ደስ ብሎዋቸው ለመኖር ወስነው ፣ ቤታቸውን ከፍት አድተዉ በዳዛሩ ስርና በዳመንገዱ ዳር እዳወደቁ የሚያድሩበት ነው ። ያ ወራት ፣ መብልና መጠጥ በሚሸጥበት ሁሉ ሌትና ቀን እዳ ተበላ ፣ እዳተጠጣ እንደ ሰርግ ቤት ሲዘፈን ፣ ርሀብና ችግር እንደገና ወደ የኪ ተመልሰው ሳይመጡ ፣ እንድያቸውን ተፈጥመው የሄዱ የሚ መስሉበት ነው ። በጠቅላላው የኪን በዚያ ወራት ለመጀመሪያ ጊዜ አይቶ የሚሄድ ደርሶ ሂያጅ ፣ በውበት ይሁን በሕዝብ ድሎት እሱን የመሰለ አገር በሙሉ ኢትዮጵያ እንደሌለ ይምሳል ።

እንዳጋጣሚ ውበቱ ሶፊያንና ጥላሁንን ይዞ የኪ ሲደርስ ፣ የየኪ ምክትል ወረዳ ገገር ወደ ሌላ አገር መዛወሩ ስለነበረ ፣ ቤቱን ከነቃው ለነጥላሁን ፣ የራሳቸውን ቤት ሰርተው እስኪወጡ ፣ አከራይተዋቸው ሄደ ። ስለዚህ ፣ ለነጥላሁን የራሳቸውንና የሌሎችንም ፣ ሲታዩ የሚገባ ቸውን የቡና መሬቶች የገንዘብ ሚኒስቴር ሹም ፣ እሳዩ መብራቱ እያ ዞረ ያሳያቸውና ፣ ሳዳርና ቀንም ለማረፍ ወደ ተከራዩት ቤት ይሄዳሉ ። ምግብ ግን ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት እሳዩ ቤት ነበር ። በሁዋላ እን ዲት አሽከር ካሳዩ ቤት መጥታ እዳረዳቻት ሶፊ ራስዋን ቻለች ። ይሁን እንጂ በምሳም ቢሆን በራት ጊዜ ካሳዩ ቤት ድግስ ሳይመጣ ቀርቶ አያውቅም ።

“ ታዲያ. . አገራችንን ወደዳችሁልን ?” አለ እሳዩ ፣ አንድ ቀን እንደ ተለመደው ሲዞሩ ቆይተው ተመልሰው እሱና ውበቱ ጠጅ፡ሶፊና ጥላሁን ብርዝ ይዘው እንደ ተቀመጡ ። ሶስት ሰዎች ግድግዳውን እዳ ተደግፉ ቆመው ነበር።

“ግሩም ነው፤ በውነት ግሩም ነው። እግዚአብሔር በመሬት የሚኖር ቢሆን ኖሮ፣ ምናልባት. . .ጎሬንም ፣ ይህን አገርም ፣ ስንገር መሬት ለማ ንም ሳያካፍል የግል ንብረቱ ያደርገው ነበር!” አለች ሶፊያ ፣ ምንም እንኳ አድንቆቱ ከልብዋ ቢሆን በቀልድ መልክ ።

@OLDBOOKSPDF

“እንዲያውም ካልሽስ ፡ እግዚር አንድ ጊዜ እዚህ ይኖር እንደ ነበረ የዚህ አገር ሰዎች ያወራሉ፤ አንዳንድ ምልክቶችም ዛሬውኑ ይታያሉ፤ ብቻ ያ ጊዜ መቼ እንደ ነበረ የሚናገር የለም ” አለ አሳዬም እንዲሁ በቀልድ መልክ ።

“ጨዋታ ከልቀረ እንዲህ ነው መጫወት ! እግዜር እዚህ ይኖር እንደ ነበረ የሚያመለክተው ምን ነው እባክህ? ከመለኮትንት ባህሪው ትንሽ ተቀርፍፎ እዚህ የቀረ አለ? ወይስ . . ብቻ ጎጃሞች ዘመዶችህ የበሙ እንደሆነ ከንፍስህ ፍዳህን እንዳይገፍፉት ተጠንቀቅ ” አለ ውብቱ እዩላቀ ።

“ለምን? ምን አደረግሀ ብለው ? ”

“አንድ ጎጃሜ እንደ ነገረኝ ፡ ጎጃሞች ፡ ‘እግዜር ጎጃምን ከሁሉም አሳምሮ ሰርቶ ፡ እዚያው ከሚፈስሱት ምርጥ ዘሮች በቀር ማንም እን ዳይደርስባት ዙሪያዋን በግዮን አጥሮ ያስቀመጣት ፡ እሱ ሲመጣ ማረ ፊያ እንድትሆነው ነው’ እያሉ ይፈክራሉ ፤ ይህን በነሱ ፊት ደፍሮ ‘አሌ’ የሚል የተገኘ እንደሆነ . . . እንከዋንስ እንዳንተ ከውጪ ጣቸው የወጣ ፡ ማንም ቢሆን አይምሩትም አሉ” አለ ውብቱ አሁንም በቀልድ መልክ ።

“እንጃ ፤ ከጎጃም በህጻንነቴ ስለ ወጣሁ እንደሆን እንጃ ፣ እንዲህ ያለውን ጭዋታ ያለባሬ ሰምቼው አላውቅም ። ይልቅስ ጎጃሞች ሌላ ነገር ይላሉ” አለ አሳዬ ፡ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ ። “ይልቅ. .ጎጃሞች በእሪት ዘፍጥረት ፡ ‘የኢትዮጵያ መሬት በሙሉ በግዮን የተከበበ ነው’ የሚለውን እዩጠቀሱ፡ ‘ኢትዮጵያ ማለት ጎጃም ናት ፤ ሌላው ሁሉ የፏ ዘርፍና ቅርንጫፍ ነው’ ሲሉ ሰምቻለሁ ” ሲል ፣

“ እንዲያ እንጃ ፤ የባሰውን አመጣው ! ” አለ ውብቱ ከዚያ ሁሉም ባንድ ላይ ይስቁ ጀመር ።

“ብቻ አሁን እሱን እንተውና” አለ አሳዬ ፣ እሱም ቢስቅ ቆይቶ። “አሁን እሱን እንተውና ፡ እግዜር እዚህ ይኖር እንደ ነበረ ምልክቱ ምንድርነው” ሳልኸው ፡ እዚህ ባጠገባችን አንድ ፣ እንዲሁ ጠቅላላ ቅጡን ሲመለከቱት ፡ ምርጥ ጠራቢ ተጠንቅቆ እንደ ጠረበው ዋዳት ገበታ ከታች ከመቀመጫው ትንሽ ሰብሰብ፡ ከላይ ከበብ ብሎ፣ ጠርዙ ሰፋ ያለ የሚመስል ፣ ስፋቱ ገሲጋሽ እግረኛ ፡ ባንድ ቀን ዞሮ የማይደ ርሰው ፡ ዙሪያውን በሌላ ቦታ የማይታዩ ፡ ተራ ያልሆኑ የልምላሜና ያበባ እጸዋት ያስጌጡት ፣ በተጨማሪ ፡ ወደጎን ተስፋፍተው ያካባቢውን

@OLDBOOKSPDF

ተራሮች ለመግፋት የሚ[illegible]ይ ረዝመው ሰማይ ለመንካት የሚንጠራሩ፣ እንደ እሞ ፣ ጎንጂና ተንጂ የሚባሉ የእጸዋት ነገስታት ግርማ ሞገስ የሰጡት ፣ እጹብ ድንቅ የሆነ መዋኛ አለ ። ከምስራቅ ይሁን ከምእራብ ፣ ከሰሜን ይሁን ከደቡብ ፣ የሚመጣበትን አቅጣጫ አሁን . እዚህ ተቀምጬ ማረጋገጥ የማልችለው ፣ በጣም ትልቅ ኸረት፣ ህብረ ሰማይ የሚመስል ፣ እጅግ የሚያምር ፣ መጠኑም ሆነ ቀለሙ በጋ ከክረምት የማይለወጥ ፣ ውሀ እየጥመለመለ እየመጣ ያን መጥኛ ይሞላል ። በኸረቱ ላይ ፣ መሰረቱ የተጣለበት ፣ ተሸካሚ አምዶቹ የታነጹበት ፣ በመሀል አሸጋጋሪ ቅስቱ የተሰካበት ፣ ምን እንደሆነና ያሰራሩ ዘዴ እንዴት እንደሆነ ፣ እንኳንስ ለኛ ለመሀይማኑ ፣ እንዲያ ላለው ሙያ ጠበብት ነን ለሚሉትም ምስጢሩ እስከ ዛሬ ገና ያልተገለጸ፣ የግሩም ግሩም የሆነ ድልድይ አለ ። ይህን ድልድይ አገሬው፣ "የግዜር ድልድይ" ይለዋል ። ያህ ድልድይ ፣ ይህ የተቀደሰ የግዜር ድልድይ ፣ ዛሬ በላዩ ጥቅጥቅ ያለ ደን በቅሎበት ሰው አያስተላልፍም ። ምናልባት የሰው መሸጋገሪያ የነበረውን ፣ ወደፊትም ሲመጣ የሚሸጋገርበትን ድልድይ ፣ ሰው እንዳያንድፈው እግዜር ራሱ ሆነ ብሎ በደን ማጠሩ ይሆናል ! ታዲያስ ምልክት ከሆነ የምትፈልገው ይህ ከምልክት የተሻለ አይለምን ለምሳሌ እንዲያ ያለውን መዋኛ ፣ ከከበበው ጊሚጊጥ ጋር በዚያ ጊዜ ፣ ልብ አድርግ ! ገና ድሮ ፣ የሰው እውቀት እዩተራቀቀ ሄዶ ዛሬ በደረሰ በት ሳይደርስ ፣ ሰማይን ያለ ዋልታና ምሰሶ ዘርግቶ ያቆመው ፣ ምድርን ያለ ካሰማ የቀሰረው ፣ እግዜር በረቂቅ ምስጢሩ ፣ ለራሱ ሲል የሰራው ካልሆነ ማን ሊሰራው ይችላል ? እንዲያ ያለውንስ ከምንና እንዴት እንደ ተሰራ ምስጢሩ የማይታወቅ ድልድይ ፣ ያዋቂዎች አዋቂ ፣ ራሱ ወደ መዋኛው ቦታ ሊሄድበት የሰራው ካልሆነ ፣ የእንዴት ያለ አዋቂ እጅ ስራው ሊባል ይችላል ? ለእነህ ጥያቄዎች ሌላ መልስ አታገኝም ። ቀላሉ መልስ ፣ እውነት የሚመስለው መልስ ፣ "ፊት አባቶቻችን ፣ አሁን እኛ፣ ካራቱ ማእዘን ተሰብስበን መጥተን ክፋት እስክናስተምራቸውና ፣ በዚህ ምክናያት ተቀይሞ እስኪተዋቸው ድረስ ፣ የዚህ አገር ተወላጆች ፣ እግዜር ለጉዋደኝነት ሰውን ፈጥሮ በገነት ሲያስቀምጠው ፣ 'ይሆንልኛል ብሎ እንዳሰበውና ተስፋ እንዳደረገው ደጎችና ንጹሆች ስለነበሩ ፣ የእረፍት ጊዜውን እዚህ እዬመጣ ከነሱ ጋር ያሳልፍ ነበርና ለዚያ ራሱ ያሰናዳው ነው ' ማለቱ ነው" ብሎ አሳዬ ልብወለዱን አውርዶ ሲጨርስ፣ ሁሉም አፋቸውን ከፍተው ሲሰሙ ቆይተው ባንድነት ሳቁ ።

@OLDBOOKSPDF

“እንዲህ ያለህ ድግግም ተጫዋች መሆንህን አላውቅም ነበርኮ! የት ሸሸገኸው ኖሮዋል?” አለ ውብቱ ፣ ከሌሎች ጋር ሲስቅ ቆይቶ ።

“እ-እ ፤ ቁጥብ ነው ! ጭዋታ እዩ-ፎጠቡ ካልተጫወቱት አይወደድ ምኮ ! ራስንም ፣ ተጫዋቹንም ያረክሳል ” አለና አሳዬ እዩሳቀ ፣ “ብቻ . . . ” አለ ቀጥሎ። “ብቻ አሁን ያልሁዋችሁኮ ብዙው እውነት ነው።”

“ምኑ ነው እውነት?” አለ ውብቱ ።

“ከዚህ ብዙ ሳይርቅ አንድ ዙሪያ ገባው በጣም የሚያምር ፣ ሰፊ ባህር መኖሩ ፤ ይህን ባህር ቀለሙም ሆነ መጠኑ በጋ ከክረምት የማይለወጥ ፣ ትልቅ ኽረት የሚመግበው መሆኑ ፣ በኽረቱ ላይ ከታች አሰራሩን ሲያዩት እጅግ የሚያስደንቅና ላዩ ደን የለበሰ ፣ ያገሩ ሰዎች ፣ ‘የግዜር ድልድይ’ የሚሉት መሸጋገርያ መኖሩ ሁሉ እውነት ነው ።’

“እውነትህ ነው ? ” አለ ውብቱ ።

“መብራቱ ይሙት ፤ ብትፈልግ ነገ ላሳይህ ። ”

“ነገማ . .ወዳገሬ ጉዞ ሳልጀምር እቀራለሁ ? እዚሁ ተስማማኝና . . .ቀረሁኮ ! እስቲ. . ከጠጁ ጨምረኝ እባክህ” አለ ውብቱ ፣ በብርጭቆው የነበረውን ጨልጦ ። ከዚያ ግድግዳ ተደግፈው የቆሙት ሶስት ሰዎች ፣ ለውብቱ ጠጅ ለመሙላት እዚያ ከተደረደሩት የጠጅ ጠርሙሶች አንዱን ይዘው ሲንጣጠቁ ፣ በመሀከል ወድቆ ስለ ተሰበረና ጠጁም ስለ ፈሰሰ ፣ ሶስቱም ደንግጠው ለመሮጥ ሲቃጡ ውብቱም ፣ ሶፊያና ጥላሁንም ሁኔታቸውን እዩተመለከቱ ይገረሙ ጀመር ። አሳዬ ብቻ ምንም የመገረም ምልክት ሳያሳይ ፣ ተነስቶ ጠጅ ከሞሉት ጠርሙሶች አንዱን አምጥቶ በውብቱም ፣ በራሱም ፣ ብርጭቆዎች አደረገና የተረፈውን እፊታቸው ባለው ጠረጴዛ ላይ አስቀምጦት ቁጭ ሲል ፣ ውብቱ መታገስ አቃተውና ፣

“ አሽከር ሲበዛ ትርፉ ይህ ነው! ለመሆኑ . . ትናንት መጥተህ ይህን ሁሉ አሽከር ምን ጊዜ ሰበሰብኸው ? ” አለ ፣ ጥላሁንን አተኩሮ እያዩ ።

“እኔ ? ኧረ አንድም የለኝ ወንድሜ ! ትናንት አንተ የላክህልን ሴት ብቻ ናት በቤታችን ያለች” አለ ጥላሁን ፣ ወደ አሳዬ ዘወር ብሎ ።

“ እንግዲያ እነዚህ ሰዎች ምንድር ናቸው ? ” አለ ውብቱ ፣ ሶስቱን ሰዎች ባገጩ አመልክቶ ።

“እስረኞች ናችሁ ? ” አለ አሳዬ ፣ ከቅርታ ፈገግታ ጋር ሶስቱን ሰዎች እያዩ ።

@OLDBOOKSPDF

“ኬ ? ” አለ አባይ ። [illegible] ታውቁታላችሁ ? ”

“ኧ! ”

“ሂዱና እዚያ ቁይታችሁ የሚሰጡዋችሁን ይዛችሁ ኑ ። ”

“ለመሆኑ የምን እስረኞች ናቸው ? ” አለች ሶፊያ ፤ ሰዎቹ ትእዛዛቸውን ተቀብለው ከወጡ በሁዋላ ። እኒያ ሶስት ሰዎች እስረኞች መሆናቸውን እንደ ሰሙ ውበቱም ፤ ሶፊያና ጥላሁንም እዚያ በምን ምክንያት እንደ ተገኙ ለማወቅ እስኪወጡ ቸኩለው ነበር ።

“ሲቸግራቸው ተበድረው ይበሉና ፤ መክፈል ሲያቅታቸው ይታሰራሉ ፤ እዚህ አገር ከስረኛው በጣም የሚበዛው ተበድሮ እዳ መክፈል የሚያቅተው ነው ፤ ወንጀል ሠርቶ የሚታሰር. . .ቢገኝም አልፎ አልፎ ነው ” አለ አባዬ ።

“በህግኮ ማንም ሰው ብድር ባለመክፈሉ አይታሰርም ። ብድሩን ያልከፈለበት ምክንያት ባለመቻሉ መሆኑ ከተረጋገጠ ነጻ ነው ” አለ ጥላሁን ።

“እ. . ይ! የኛ አገር ህግ ሌላ ነው! አሁን ያልኸው ያዲስ አበባ ህግ ይሆናል ። ብቻ ያዲስ አበባ ህግ እዚህ አይደርስም ፤ ይርቀዋል ! እንኳንስ ያዲስ አበባው የጎሬውም እዚህ አይደርስ ። ከስንት አንድ ቢደርስ እንኳ በጣም ደክሞ ፤ መልኩ ተለውጦ ነው የሚደርሰው ” አለ አባዬ ፤ ባሽሙር ።

“እ. . -ቪ ፤ ታዲያ ለምን ዛሬ እኛ ዘንድ መጡ?” አለች ሶፊያ ።

“እስር ቤት የሚበሉት የላቸውም ፤ የወህኒ ቤት ዘበኞችን ተለማምጠው ሲለቁዋቸው ፤ እንዲህ በዬሰዉ ቤት ሄደው ያገኙ እንደሆን በልተው ፤ ያሰነቁ ፤ ያስጠባቂ ፤ እስር ቤታቸው ተመልሰው ይገባሉ ። ስለዚህ . . . ሌላው ስለ ሰለቻቸውና ፤ ‘እናንተ እንግዶች በመሆናችሁ ራሳችሁን በመልካም ለማስተዋወቅ ጠቀም አድርጋችሁ ሳታጎርሱ አትቀሩም ’ ብለው ይሆናል ፤ ዛሬ ወደናንተ የመጡ ። ይርባቸዋል ። እንዳያችሁዋቸው ትእዛዝ በሰሙ ቁጥር አንዱ ከሌላው ቀድሞ ትእዛዙን ለመፈጸም የሚሻ ፤ ለሁሉም የሚበቃ ያልተገኘ እንደሆነ ፤ የሚገኘውን ያክል ለብቻው ለመውሰድ ነው ። ”

“እስር ቤት የሚበላ ከሌለ ከዬቤታቸው አይሄድላቸውም? ያለዚያስ . . እንዲህ ወጥተው መዞራቸው ካልቀረ ፤ በዬቤታቸው አዬበሉ እንዲመለሱ ቢደረግ ምን አለ ? ”

@OLDBOOKSPDF

“ኢቢታቸውም [illegible] ናቸው እንጂ የሚያገኙትማ ይሄድላቸዋል ።”

“እንዴት ? ሴላው ቢቀር ለራቡ ማስታገሻ ያክል እንኳ ፣ በቤታቸው ምንም የሌላቸው ሰዎች እሱ ማለት ነው?”

“ካገሩ ተወላጅ የሚበዛው ፣ ምናልባት ከመቶ ዘጠና አምስቱ እንበል ፣ ባገሩ ምቹነትም ይሁን በሌላ ምክናያት ፣ ስንፍና ስለሚያጠቃቸው ምንጊዜም ከሶስት ፣ ቢበዛ ካራት ወር በቀር ፣ ከችጋር ወጥቶ አያውቅም። ነገር ግን ከጥቂት አመታት ወዲህ ፣ ‘ችጋሩ በጣም እየከፋ ሄደ’ ይባላል ።”

“በመሻሻል ፈንታ እየከፋ ሄደ? እንዴት እባክህ?” አለ ጥላሁን ከሶፊያ አፍ ነጥቆ ።

“ያገሩ ህዝብ ስራ ቢያውቅም አይወድም ፤ ሰነፍ ነው ። ባመትአንድ ጊዜ ብቻ ሜካውን ያቃጥልና ሳያርስ ፣ ሳይቆፍር ፣ እንዲሁ በሆርዷ እዩ ወጋ ቦቀሉ ተክሉ ፣ ወይም ዶንቃ የሚባል ዘንጋዳ መሳይ በትኖ ፣ ሲደርስለት አብዛኛውን በሽቱ ፣ የተረፈውን ሰብስቦ አግብቶ ከሶስትና ካራት ወር በማይበልጥ ጊዜ በልቶ ይጨርሰዋል ። ከዚያ ቀጥሎ የጅማ ነጋዴ ብሩን ፣ የከፋ ነጋዴ በያይነቱ እህሉን ፣ እዩሜን መጥቶ እዚህ ሲሰፍርለት ፣ የሜካ ቡና ሲደርስ ከዚያ ለቅሞ ፈረሱላውን ባምስት ፣ ወይም በስድስት ብር ሂሳብ በቡና የሚከፍለው ከጅማ ነጋዴ ብር ባራጣ እዩ ተበደረ ፣ ከከፋ ነጋዴ እህል በውድ እዩሸመተ ፣ የነፍሱ ማቆያ ያክል እዩቀመሰ ፣ እንደምንም ነፍሱን የተከታዩ አመት ቦቀሎና ዶንቃ እስከ ሚደርሱበት ወራት ያደርስ ነበር ፤ ሳያደርስ የሚቀረውም ያን ያክል ነው! ብቻ ቢሆንም ካሁኑ ይሻል ነበር ይባላል ። አሁን ብር እዩሜን ይመጣ ከነበረው የጅማ ነጋዴ ፣ በዩቤቱ ደባል እዩሆኑ ከተቀመጡት ጥቂት ነጋዴዎች በቀር ፣ በከተማው ዙሪያ ሜካውን የድንኩዋን ከተማ ያደርገው የነበረው ሁሉ ቀረ ። ከሱ ጋር ፣ የሜካ ቡናን መያዣ አድርጎ፣ ከጅማ ነጋዴ ብር ባራጣ እዩተበደረ ከከፋ ነጋዴ እህል ሸምቶ ለነፍስ ማቆያ ያክል መቅመሱም . . ቀረ! ”አለ አሳዩ ፣ ያሽሙር ፈገግታ በፊቱ እዩታዩ ።

“ እንዴት ? አልገባኝም ! ” አለች ሶፊያ ።

“እኔንም ! ” አለ ጥላሁንም ።

“ ቆዩ ጉሮሮየን ሳርጥብና እቀጥላለሁ ፤ እናንተ እዩተተካከችሁ ብቻየን ስታስለፈልፉኝ ጉሮሮየ ደረቀ ” ብሎ ቀለደና አሳዩ ጠጅን ጨልጦ ፣ ብርጭቆውን እንደገና ሞልቶ አስቀምጦ ፤ ቀጠለ ።

@OLDBOOKSPDF

"ድሮ ማንም ሰው ፣ የኔ ፣ የግሌ ነው' የሚለው በቤቱ አካባቢ ያለውንና ፣ ከዚያም ራቅ ሲል በገንዘቡ ገዝቶ ፣ በጉልበቱ ሰርቶ ያለማውን ነበር እንጂ ፣ እንዲሁ ወፍ ዘራሹና አውቆ በቀሉ የጫካ ቡና ፣ ሁሉ ፣ ማንም ፣ 'የግሌ ነው' የማይለው ፣ ያገሩ ሕዝብ በህብረት የሚጠቀምበት ስለነበረ ፣ ሁሉም በዩበኩሉ ለብድሩ መያገር የሚያደርገውና ፡ ብድሩን ለመክፈል እንደሚችል እምነቱን የሚጥልበት ነበር ። አሁን ሁላችንም እንደምናውቀው ያን ጫካ ፣ ያን እግዜር ለዚህ አገር ህዝብ እዚህ የፈጠረለትን ጫካ ፣ ያገሩ ህዝብ እዚሁ እንዳለ ፡ 'ድርሻህ ይህ ነው' ሳይባል ፣ የሌላ ክፍል ሰዎች ከመንግስት በስጦታም ሆነ በግዢ ሰም ተከፋፈሉት ። እዚህ ያለው ህዝብ አገር አማን መስሎት ፡ ካያት ከቅድማያቱ ፣ ከዚያም በፊት ሲደረግ እንደ ነበረው ተበድሮ የበላውን ለመክፈል ባለስልቻ ስልቻውን ፣ ባለኬሻ ኬሻውን ፣ እዩጠቀለለ ይዞ ቡና ሊለቅም ወደዩጫካው ሲገባ ጊዜ ፣ አዲስ መጪው ባለርስት ፣ የወንጀለኛ መቅጫ አንቀጽ ምንትስ ፣ ንኡስ አንቀጽ ምንትሲውን እዩጠቃቀሰ ፣ እስር ቤት እያስገባ ያጉረው ጀመር ! ያን አይቶ ፣ ወይም ሰምቶ ፣ ስለፈራ ወደ ጫካ ቡና መሄዱን ትቶ እቤቱ የተቀመጠም ፣ ብድሩን መክፈል ስላልቻለ ፣ በባለዳነት እስር ቤት እዩገባ ይታጎር ጀመር ! በየትም ቢሄድ መንገዱ ሁሉ የሚያመራው ወደ እስር ቤት ብቻ ሆነ ! ታዲያ መጨረሻውስ ? መጨረሻውማ መቸስ . . . የሚከፍለው የሌለው አበዳሪ ስለማይኖረው ፣ አበዳሪ የሌለው የሚበላው ስለማይኖረው ፣ የሚበላው የሌለው ይሉኝታ ስለማይኖረው ፣ ይሉኝታ የሌለው የማያደርገው ነገር ስለማይኖረው . . . እዩትላችሁ ፣ 'ችግሩ ከማናቸውም ጊዜ እዩከፋ ሄደ' የሚባልበት ምክናያት ይህ ነው ! እኒያ ያያችሁዋቸው ሰዎች ሊያደርጉት የማይገባቸውን ሲያደርጉ ያያችሁዋቸውም በዚህ ምክናያት ነው ! ሀ - ሀ - ሀ - ሀ - ሀ ! " ብሎ አሳዩ ያሽሙር ሳቅ ሲስቅ ፣ ውብቱም አብሮት ይስቅ ጀመር ። ጥላሁንና ሶፊያ ግን እንኩዋንስ ሊስቁ አሳዩ እንዲያ ያለ የሚያሳዝን ታሪክ ተርኮ ስለሳቀና ውብቱም አብሮት ስለሳቀ ፣ ገርሞዋቸው አንገታቸውን ፣ ደፍተው ዝም አሉ ።

"ምነ አንገታችሁን ደፋችሁ ? ሳላውቅ የሚያሳዝናችሁ ነገር ተናገርሁ ? እኔኮ ይህን ያክል የምለፈልፈው እንድትስቁና እንድትጫወቱ ነው እንጂ እንድታዝኑ አደለም ! " አለ አሳዩ ፣ ያሽሙር ፈገግታው አሁንም በፊቱ ላይ እንዳለ ።

@OLDBOOKSPDF

" የሚያሳዝን እንጂ ምን የሚያስቅ ነገር ተናገርህና እንሳቅ ፣ እናንተም አውቃችሁ ነው እንጂ ፣ አሁን በተናገርኸው የሚያሳዝን ሁኔታ ሳታዝኑ ቀርታችሁ አይደለም የምትስቁ " አለ ጥላሁን ።

" እኔ እንኳ የሳቅሁ " አለ ውብቱ ፣ ሶፊያና ጥላሁን አሳዩ በተረከው በጣም ሲያዝኑ አይቶ ። " እኔ እንኳ የሳቅሁ በነገሩ ላይ ሆን ፣ አሳዩ ሲያወራ ያወራበት የነበረውን ሁኔታ እያዩሁ ነው ። በጠ ቅላላው ነገሩ የሚያሳዝን ነው ስላልኸው ግን ፣ ይህ በአለም ካለው ያልተሟላ ነገር ፣ በአለም ካለው ብዙ ጉድለት አንዱ አይነት ነው ። ይህን የመሰለና ምናልባትም የሚብስ ወደፊት ሊገጥምህ ስለሚችል እንዲያ እንዲያ ያለውን ጉድለት ባዩህ ቁጥር አዝነህና አንገትህን ደፍ ተህ አትገፋውምና ፣ ሆድህን አስፍተህ ፣ አብረህ ለመኖር ካሁኑ መሰ ናዳት አለብህ ። አንተ ካንድ ሌላ አለም ፣ የሊቃውንት አሳብ አቀበ ትና ቁልቁለቱን ፣ ጉድባና እንቅፋቱን ፣ እሾሁንና አሜካላውን ፣ ወዲያ አስወግዶ ፣ ሁሉንም ደልድሎ ፣ አስተካክሎ ከፈጠረው ፣ "ትምህ ርት ቤት " የተባለ ጥሩ የልም አለም ገና ትናንት ወጥተህ ወደዚህ ወደውነተኛው አለም የመጣህ እንግዳ ነህና ፣ እኔ የጥቂት አመታት እድሜ ቀድሜህ መጥቼ ስለ ቆዩሁበት ልምከርህ ።

" በትምህርት ቤት ስለዚህ አለምና ስለኑሮው የምንማረው ስዕ ሉን ፣ ወይም ምስሉን ነው እንጂ ፣ ራሱን አለሙንና ኑሮውን እንዳ ይመስልህ ! እንደምታውቀው ፣ ማናቸውም ነገር የሚሳለው ጥሩ ሆኖ ተካክሎ በተሰራ ወረቀት ፣ ወይም ሰሌዳ ላይ ስለሆነ ፣ ደህና ስአሊ ከሳለው ፣ ስዕሉ በጣም የሚያምር ፣ በጣም ደስ የሚያሰኝ ይሆናል ። ወደ ተሳለው ነገር ፣ ወደ ስእሉ ባለቤት ስትሄድ ግን በውስጡ ስንት ጉድ ታገኛለህ ! አለሙና ኑሮውም በትምህርት ቤት ስለው እንደሚ ያሳዩን የተደላደለና የተካከለ አይደለም ። ብዙ አቀበትና ቁልቁለት ፣ ብዙ ጉድባና እንቅፋት ፣ ብዙ ሾህና አሜካላ የሞላበት ፣ ብዙ የሚ ያሳዝንና የሚያስቅ ነገር ያለበት ነው ! ብቻ ወደድንም ጠላን ሁላችንም እንዲህ ባለው አለም ውስጥ መኖር ስላለብን ፣ እንዴት መኖር እንደምንችል መማር አለብን ! የተፈጥሮ ደካማነታችንን አሸንፈን ፣ በውስጡ አብረነው ከምንኖር ክፉና የሚያሳዝን ነገር ሁሉ ጋር ራሳችንን አስተዋውቀን ፣ እንዲህ ባለው አለም ማናቸውም ክፉ ነገር መኖሩ የማይቀር መሆኑን ተረድተን ሳንገረም ፣ ሳናዝን ኖረን ለማለፍ መማር አለብን ! እንዲህ ያለው አለም አቀበት ቁልቁለትን

@OLDBOOKSPDF

ወጥተው ወርደው ፣ ከከፉው ታግለው ፣ ቢወድቁ እንኳ ተንፈራግጠው ፣ ተፍገምግመው ተነስተው ፣ በግራቸው መቆምና ራሳቸውን መቻል የሚያውቁ ብቻ የሚኖሩበት ነው ! ከከፉ ታግለው ቢወድቁ ተንፈራግጠው መነሳት የማይችሉና በወደቁበት የሚቀሩ ፣ ድሮውንም ያለቦታቸው የበቀሉ አረሞች ቢሆኑ ነውና ፣ እንሱን መኖር ለሚያውቁት መሬት እንዲያቀልዘ ፣ እዚያው ከመተው በቀር ሌላ መንገድ የለም ! እንዲህ ያሉትን ከወደቁበት ለመነሳት የማይጣጣሩ እንሳለሁ ብሎ የሚሄድ ሁሉ ፡ ‘ አውፎ የወደቀ ሊያነሱት የሄዱትን ጎትቶ ይጥላል ’ እንደሚሉት ወድቆ ለከፉ እድላቸው ተካፋይ ይሆናል እንጂ፣ አንስቶ በመልካም እድሉ ተካፋዮች ሊያደርጋቸው አይችልም ! ስለ ዚህ እኔ ወንድምህ የምመክርህ ፡ ያዬኸውን የሚያሳዝንና የሚያስቅቅ ክፉ ነገር እንዳላዬህ ፣ የሰማኸውን እንዳልሰማህ ሆነህ ከሚጫወቱት ጋር እዬተጫወትህ ፣ ከሚስቁት ጋር እዬሳቅህ እንዳትወድቅና ራስህን ችለህ እንድትቆም ጠንክረህ መታገል ነው ። የወደቁት ያሉበትን የሚያሳዝን ሁኔታ ባዬህና በሰማህ ቁጥር ፣ “ልዘንና እንገቴን ልድፋ ’ ካልህ . . . እንዲያ ባለ ሁኔታ የሚገኙት ሰዎችና በምን ኖርበት አለም ያሉት አሳዛኝ ነገሮች ቁጥር ስፍር የሌላቸው ስለሆኑ ፣ ላንድ አፍታ እንኳ እንገትህን ሳታቃናና ጥርስህን ሳትገልጥ ወደ መቃብርህ መሄድህ ነው ! አይነተኛው ነገር መጀመሪያ ራስን ማውጣት ፣ ራስን መቻል ፣ የድህነትም ሆነ የሌላ እስረኛ ከመሆን ነፃ መውጣት ነው ! ከዚያ በሁዋላ ፣ ራሳቸውን መርዳት እዬፈለጉ ያልቻሉትንም መርዳት ትችላለህ ! እ . . . ይ . “ ከመቆም መውደቅን መርጠው የወደቁትን እያንቀላበስሁ ከነሱ ጋር ሳለቅስ እኖራለሁ’ ካልህ . . እንደነሱ ወድቀህ እንዳትቀር ወዮልህ ! የመሬት ሀብት ተቀባይ አጥቶ እዬተመለሰ መሬት በሚገባበት አገር እግዜአብሔር እም ቶህል ፣ ጠንክረህ ሀብት ብታበጅ ፡ ሀብት ካለ ምን አይኖርም ? የፈለግኸውን ልታደርግ ትችላለህ ! ያውልህ ፣ ፋርዳን ኩኖ ፣ ሚዳን ኩኖ ! ” ሲል ውብቱ ሁሉም ሳቁ ።

“ ይገርማ . . ል ! ” አለ ጥላሁን ፣ ከሌሎች ጋር ሲስቅ ቆይቶ ። “ ይገርማል ውብቴ ፣ ታውቃለህ ? አሁን . . በዚህ እውነቱን አሰት ፣ አሰቱን እውነት አስመስሎ ለማስረዳት በታደለ የሀሳዊ መሲህ አንደበትህ ለኔ ምክር አስመሰለህ ፡ እዚህ ያለነውን ሁሉ ደቀመዛሙርትህ ለማድረግ ስትሰብከን ፣ ሁለት ነፍሶች ስለ ነበሩት አንድ ሰው ተጽፎ ያነበብሁት ትዝ አለኝ ። የዚያ ሰው ሁለት ነፍሶች አንድዋ ስትሰራ ሌላዋ እዬተኛች ፣ ስትሰራ የቆዩችዋ ስተተኛ ፣

@OLDBOOKSPDF

ተኝታ የቆዩችዋ እዩነቃቸ ፤ ሁለቱም ለጥቂት ለጥቂት አመታት በትራ በውስጡ ይሰራሉ እንጂ ባንድ ላይ አይሰሩም ። ታዲያ ፤ ያ ሰው አንድዋ ነፍሱ በውስጡ ስትሰራ በነበረችበት ጊዜ የሆነውንና የተደረገውን ሁሉ ፤ ርስዋ ተኝታ ሌላዋ ስትተካ አያስታውሰውም ፤ ጨርሶ ይረሳዋል ” ሲል ሁሉም ሳቁ ። “ አስጨርሱኝ እባካችሁ ፤ ገና አልጨረስሁም ፤ ልጨርስ ” አለና ቀጠለ ። “ታዲያ ፤ ያ ሰው ካንዱዋ ነፍሱ ጋር ሳለ እንዲት ሴት ወዶ አገባና ፤ ሶስት አመት ያክል ከምሽቱ ጋር ደስ ብሎት እንደ ተቀመጠ ፤ አንድ ጥዋት ከንቅልፉ ሲነቃ ፤ ምሽቱን ሲያገባ የነበረችዋ ነፍሱ ተኝታ ሁለተኛዋ ነፍሱ በተራዋ ተተክታ ስለተነሳ ያን ጊዜ አካባቢው ሁሉ እንግዳ ሆኖ ታዬውና ፤ አይኖቹን እዩጠራረገ ወደ መስኮቱ ብቅ ሲል ጊዜ ፤ ምሽቱ የሚታጠበውንም ፤ የሚተኮሰውንም ፤ ልብሳቸውን አግበስብሳ ተሸክማ፣ ቶሎ አጥባና ተኩሳ ወደ ሌላ ስራዋ ለመመለስ ፤ በሁዋላ በር ወጥታ ወደ ማጠቢያው ቦታ ስትጣደፍ አዩ ። ከዚያ ፤ ባጠገቡ ያገኘውን መጥረጊያ ነጥቆ እዩሮጠ ወጣና ፤ ‘ቁሚ አንቺ ሌባ ፤ ቁሚ ብዬሻለሁ’ ሲል ሰምታ ፤ እንደ ሁልጊዜው መዳራት ፈልጎ የተከተላት መስሎዋት ቆማ እዩሳቀች ስትጠብቀው ፤ እንደ ደረሰ በያዘው ዱላ ወቅቶ ፣ ወቅቶ ፤ ዱላው ሲሰበርበት እንዳታመልጠው ወገብዋን ጥምጥም አድርጎ ይዞ የፖሊስ ያለህ እያለ ይጮህ ጀመር ። ወዲያው ጎረቤቶችም፣ ፖሊሶችም ደርሰው እንደምንም ብለው ካላቀቁዋቸው በሁዋላ ፤ ‘ምነው ጭዋው ሰው እንደ ባለጌ ምሽትህን እንዲህ ደም–አበላ እስከትሆን ደበደብሀት ? ’ ብለው ቢጠይቁት ፤ ‘ አሁን እንደምታይዋት ልብሴን ዘርፋ በጉዋሮ በር ስትሮጥ ተከትዬ እስክይዛት ድረስ አንድ ቀን እንኩዋ ፊትዋን አይቸው የማላውቅ ሌባ ናት ፤ በሕግ አምላክ ያዙልኝ፤ እንዳታመልጥ ’ አለ ። ፖሊሶች የዚያን ሰው ሁኔታ ሲያዩ ፤ የራሱን ጤናማነት ተጠራጥረው ፤ የባሰ አደጋ እንዳያደርስ ለማስመርመር ወደ ልዩ የአእምሮ ሀኪሞች ሲወስዱት ጊዜ ፤ ‘ ሁለት የማይተዋወቁ ነፍሶች በዩተራ በውስጡ የሚፈራረቁበት ከመሆኑ በቀር ሌላ የራስ በሽታ የሌለበት ’ መሆኑን ሀኪሞች አረጋገጡ ። ውቢቴ ፤ ይቅርታ አድርግልኝና ፤ አንተም ያን ሰው የመረመሩ ሀኪሞች እዚህ ተገኝተው ቢመረምሩህ ፤ በጥቂቱ ሁለት የማይተዋወቁ ነፍሶች እንደሚገኙብህ እኔ እርግጠኛ ነኝ ። ”

“ ታዲያ . . ” አለ ውቢቱ ፤ ከሌሎች ጋር ሲስቅ ብዙ ከቆየ በሁዋላ ። “ ታዲያ አንተ እንዳልኸው በጥቂቱ ሁለት ነፍሶች ካሉኝ ቢያንስ ቢያንስ የሁለት ሰው እድሜ ልኖር ነው ማለት ነውኮ ፤ ያውም

@OLDBOOKSPDF

እድሜየ ረዝሞ እንዳይቻከኝ በዱሰስት ፣ በያራት እሙቱ ነፍሶቹን እያለዋወጥሁ ! ይህማ ቢሾትስ ይገኛል ? ”

“ እሱን አላውቅም ! ብቻ ፣ ሁለት የማይተዋወቁ ነፍሶች እን ዳሉህ ርግጠኛ ነኝ ያልሁበትን ምክናያት ላስረዳ ” አለ ጥላሁን ።

“ እሺ እስቲ እንስማ ” አለ ውብቱ ።

“ አንድ በጣም የምወደውና የማከብረው ጉዋደኛ ነበረኝ ” አለ ጥላሁን ፣ አንገቱን ደፍቶ ግንባሩን እያሻሸ ትንሽ ሲያስብ ቆዩና ። “ያ ጉዋደኛየ”አለ ፣ ቀጥሎ ፤ ያ ጉዋደኛየ በትምህርት በጣም ብርቱ ነበር ። በገባበት ክፍል ሁሉ አንድ ጊዜ እንኳዋ ተቀድሞ አያውቅም ፤ ሁልጊዜም አንደኛ የሚሆን እሱ ነው ። በዚያ ላይ ፣ ከዚህም ሁሉ ይልቅ፣ ለትክክለኛ ፍርድና ለሰው ሁሉ የነጻነት መብት የነበረውን የተቃጠለ ስሜት፣ተወዳዳሪ በሌለው የአሳብ ጥራትና ያንደበት ትባት በዱስብሰባው ቆሞ በሚገልጽበት ጊዜ ፣ የማይደነቅ አልነበረም ! የኔ የሁልጊዜ ምኞቱና ጸሎቴ እንደሱ መሆን ነበር ።”

“ እኮ ታዲያ ይህን የምትለውን ጉዋደኛህን ከኔ ባለሁለት ነፍስ መሆን ጋር ምን አገናኘው ? አሁንኮ ልታስረዳን የነበረ እኔ የሁለት ነፍሶች ባለቤት መሆኔን ነው ፤ ረሳኸው ? ” አለ ውብቱ ፣ ሰሙ አይጠራ እንጂ ውዳሴው ለሱ መሆኑን ስላወቀ ትንሽም እንደ ማፈር ብሎ ።

“ አልረሳሁትም ” አለ ጥላሁን ። “አልረሳሁትም ፣ እዚያ ለመ ድረስ ነው ፤ ታገሰኝ ብቻ ። አሁን እንዳልሁት ፣ የሁልጊዜ ምኞቴና ጸሎቴ እንደሱ መሆን ስለነበረ ፣ በዱጊዜው በተማሮች ስብሰባ ሲና ገር ፣ ከንግግሩ ‘ሲረሱ የማይገባቸው ፣ ነዋሪዎች ናቸው’ ብዬ የገ መትሁዋቸውን ሀይለ ቃሎች እየመረጥሁ ላሳቤም ሆነ ለስራየ መሪ እንዲሆኑኝ ፣ እንደ ጸሎት መጽሐፍ ከጎኔ አልለያቸውም ። እባካችሁ ላንድ ደቂቃ ብቻ ታገሱኝና ሁለት ሶስቱን ላንብባችሁ ” አለና የማስ ታዎሻ ደብተሩን ከደረት ኪሱ አውጥቶ ያነብ ጀመር ።

“ 1ኛ ፦ ድህነትና ከመጠን ያለፈ ሀብታምነት ፣ የማኅበራዊ ኑሮ ደዌዎች ስለሆኑ ፣ ማህበሩ ጤናማ እንዲሆን ፣ ሁለቱም መጥፋት አለ ባቸው ። ድህነትን የሚወልደው ከመጠን ያለፈ ሀብታምነት ስለሆነ፣ ድህነትን ለማጥፋት እንዲያ ያለውን ሀብታምነት ማጥፋት ያስፈልጋል ።

2ኛ ፦ ሰው ራሱን ለመቻል የሚፈልገው ሀብት የተባረከ ስለሆነ፣ ልንደግፈው ይገባል ። ከዚያ አልፎ የሚፈልገው ሀብት ግን ሌሎች ራሳቸውን እንዳይችሉ መከላከያ ስለሆነ ፣ በሙሉ ኃይላችን ልንቃወ መው ይገባል !

ፎኛ፦የጤፍ ክምር ባለበት ቦታ ፤ የጤፍ አሚጅ እንጂ ጤፍ እንደማይኖር ፤ ሀብት ተሰብስቦ ባንድ ፤ ወይም በጥቂት ቦታ በተከመረበት ዙሪያ ፤ ድህነት እንጂ ሀብት አይኖርም ። መብት ተሰብስቦ ባንድ ፤ ወይም በጥቂት ቦታ በተከመረበት ዙሪያ ፤ ግዴታ እንጂ መብት አይኖርም ። ነጻነት ተሰብስቦ ባንድ ፤ ወይም በጥቂት ቦታ በተከመረበት ዙሪያ ፤ ባርነት እንጂ ነጻነት አይኖርም ! እንዲህ ባለ ያልተካከለ ፤ ጎርበጥባጣ መሰረት ላይ የቆመ ማህበርም ጸንቶ ሊኖር አይችልም ። ስለዚህ ፤ ማህበሩ ጸንቶ እንዲኖርና ፤ ሰላም እንዲሆን ፤ ከዙሪያው እዬተወሰደ በጥቂት ቦታ ተሰብስቦ የተከመረው ሀብት ፤ ስልጣን ፤ መብት ፤ ነጻነት ፤ ወደዬቦታው እንዲመለስ መጣጣር ፤ ተምሮ ማወቅ በተለይ በኛ ላይ የጣለው የተቀደሰ ተግባር ነው ። እነዚህን የመሰሉ ሀይለ ቃሎች እዚህ ውስጥ ብዙ አሉ ” አለ ጥላሁን ፤ የማስታዎሻ ደብተሩን አጥፎ ፊት ለፊት ይዞ እየነቀነቀ ።

“ነገር ግን ባስረዳ ባልሁት ጉዳይ ፤ አሁን ያነበብሁላችሁ ይበቃል ። ያ ጉዋደኛየ ፤ ያ አሁን ያነበብሁላችሁንና እነሱን የመሳሰሉትን ሀይለ ቃሎች በዩስብሰባው ሲናገር የድሆችና የደካሞች በደል ከነሱ የበለጠ የሚሰማው ይመስል የነበረ ወዳጄ ፤ ከጥቂት አመታት በሁዋላ ፤ ያን ሁሉ ረስቶ ፤ ያን ሁሉ ይናገርበት በነበረው አፉ ፤ ይህ አለም ታግሎ መጣል የሚችል ሀይለኛ ብቻ እንጂ ፤ ደካማ እንዲኖርበት የተፈጠረ አደለም ፤ ሀይል እንጂ ፤ መብት ዋጋ የለውም ፤ ድሀ እዬታረመ ፤ ከስሩ እዬተነቀለ ፤ ለሀብታም መሬት ማዳበርያ የሚሆን አረም ነው” እያለ በሙሉ እምነት ፤ ከሞቀ ስሜት ጋር ይሰብክ ጀመር ! ታዲያስ! ታዲያ . . . እንዲህ ያለው ሁለት ተቃራኒ አሳቦችንና እምነቶችን ምንም ሳያመነታ ፤ ምንም ሳይጠራጠር ፤ በሙሉ ሀይሉ ፤ የሚሰብክ ሰው ምን ይባላል ? ሁለት የማይተዋወቁ ነፍሶች ያሉት አደለም ? እሩ ስመሆኑ ውብቴ ፤ አሁን ከማስታዎሻየ ያነበብሁዋቸው ሀይለ ቃሎችስ . . ያንተ መሆናቸውን ታስታውሳለህ ? ”

“ እዎን አስታውሳለሁ ” አለ ውብቱ ፤ ሲስቅ ቆይቶ ። “አስታውሳለሁ ። ተማሪ ሳለሁ ፤ እንደ ተማሪ አስብ በነበርሁ ጊዜ የተናገርሁዋቸው ናቸው ። ብቻ አንተ አሁን እንዳመጣኸው ውሀ ያልነካው ፤ አዲስ ነገር ሁለት የማይተዋወቁ ነፍሶች ኖረውኝ ሳይሆን ፤ ያችው እንድዋ ነፍሴ ካካሌ ጋር ስላደገችና ስለ በሰለች ፤ የዛሬ አስተያየቴና እምነቴ በልጅነቴ ፤ ተማሪ ሳለሁ ከነበረኝ የተለዩ ስለሆነ ነው ። ”

@OLDBOOKSPDF

"ውብቱ የሚናገረው ከልቡ እንዳይመስላችሁ ! ስለ ተበላሹና.. ተበሩ ስለ ቆረጠ . . . አሽሙር ነው !" አለች ሶፊያ ፣ የባሏዋን ዘዴ ቢሰንት ለመጠገን ያክል ።

"እንዴት ? ምን ማለትሽ ነው ?" አለ ውብቱ ።

"አሁን የተናገርከው ሁሉ ከልብህ እንዳልሆነ አውቃለሁዋ !"

"እኮ ከልቤ አለመሆኑን እንዴት ታውቂያለሽ ?"

"አንተን አይመስልማ ! በምንም በምን ካንተ ባህሪ ጋር የሚስማማ አይለም ።"

"ምንድር ነው የኔ ባህሪ ?"

"አሁን ጥላየ ፣ ‹እንተ የተናገርሀቸው ናቸው› ብሎ የጠቀሰልን ጥሩ ጥሩ ሀይለ-ቃሎችኮ ከጽኑ እምነት ብቻ ፣ ባህሪው ድጥርስ ካልሆነ ጥሩ ምንጭ ብቻ የሚፈልቁ ናቸው ! ከድጥርስ ምንጭኮ ጥሩ አይፈልቅም አለች ሶፊያ !"

"አ . . ባህሪ !" አለ ውብቱ ፣ "ባህሪ ! ለመሆኑ ጊዜና አካባቢ የማይለውጠው ፣ ከሰው ጋር አብሮ ተወልዶ ፣ አብሮ አድጎ ፣ አብሮ አርጅቶ ፣ አብሮ የሚሞት ፣ ባካል ከወላጆች ከሚወርሰውና በመንፈስ ከፈጣሪ ከሚሰጠው ጸጋ ሌላ ፣ ባህሪ የሚባል ነገር አለ ? የለምኮ ፣ ሶፊ ! ሰው ከድሜውና ከሚኖርበት አካባቢ ጋር የሚለዋወጥ ፣ ቀን ቀንን እያባረረ ፣ ያለማቋዋረጥ ፣ ተከታትሎ ሲሮጥ ፣ እሱም አብሮ እዬሮጠ ላካሉ ብርታትን ፣ ለአእምሮው እውቀትን የሚሰጡትን ነገሮች ከቀኝ ከግራ ፣ ከፊት ከሁዋላ እዬቃረመ ፣ ራሱን በነሱ እያነጸ ፣ ከህጻንነት ወደ ጉልምስና ፣ ከጉልምስና ወደ ሽምግልና ፣ ከሽምግልና ወደ እርጅና በተላሰፈ መጠን ፣ መልኩን ብቻ ሳይሆን እምነቱንም ሆነ ስሜቱን ጭምር የሚለውጥና ፣ ህይወታዊ ሀይል ከፈጣሪ ታድሎ የተፈጠረ ፍጡር ነው እንጂ ፣ ይህ ባልሽ እንደሚለው በህጻንነት አካሉና በህጻንነት አእምሮው እንዳለ ፣ ገና እንደ ህጻን በሚናገርበትና ፣ እንደ ህጻን በሚሰራበት እንዳለ ፣ እዚያው ቆሞ ፣ እዚያው ደርቆ የሚቀር በድን አይደለም ! ነገር ግን ባልሽ ፣ "ሁለት የማይተዋወቁ ነፍሶች በዩፌናቸው የሚነዱህ መኪና ነህ" የሚለኝ በልጅነቴ ከነበረኝ ዛሬ ያለኝ እምነት የተለዩ ስለሆነ ነው ። ገና ህጻን ሳለሁ ፣ ለኔ ኑሮ የሚያስበውም ፣ የሚቸገሩም ፣ ሌሎች በነበሩ ጊዜ ፣ ያሳንዳች አሳፊነት አስበውና እናገረው ፣ እሰራውም ከነበረው ፣ ዛሬ ህጻንነትን አልፌ ፣ ጐልማሶችን ከሽማግሌች ወደሚለዩው ድንበር ደርሽ ፣ ከበሰልሁ በሁዋላ ፣ ዛሬ ለራሴ ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቤና ለደሆች ዘመዶቼ

@OLDBOOKSPDF

ኑሮ ጭምር አላፈንም ከተጣበቀው በሁዋላ ፣ ይህ አላፈንት ምን መሆኑን እንደማያውቁ ህጻናት ባለማሰቢና ባለመናገሬ ፤ "ሁለት የማይተዋወቁ ነፍሶች የሚለዋወጡብህ ነህ" ይለኛል ! እንግዲህ ለዚህ ምን ልበል ? ለዚህ ሌላ የምለው የለኝም ! ለዚህ የምለው ፤ "እናንተ ከልም አለም ገና ትናንት ወጥታችሁ የመጣችሁ ሁለት ህጻናት ፣ በዚህ በኛ የውን አለም አንድ አመት ፣ እንደኛ ብዙ አመታት እንኩዋ አልልም ፤ አንድ አመት ብቻ ቆይታችሁ እንደ ገና ስንገናኝ በዛሬው አስተያየታችሁ እንደ ጸናችሁ ያገኘሁዋችሁ እንደሆነ ያን ጊዜ . . . " ብሎ ነገሩን የሚያስርበት ቃል ሲፈልግ

"ያንጊዜ ሁለት የማይተዋወቁ ነፍሶች የሚለዋወጡብህ መሆንህን ታምናለህ !" አለ ጥላሁን ፣ አቋርጦ ።

" ያን ጊዜ . . በሰው ጥ ላይ የተመሰረተው ፣ ቀጥሚ የፍጥረት ህግ በናንተ ላይ አለመስራቱ ፤ አንድ ግድለት ቢኖርባችሁ መሆኑን ተረድቼ ፣ እያዘንሁ በጎደሎዎች ተራ እጽፋችሁዋለሁ !"

" የሰይጣን ደቀመዝሙር !" አለ ጥላሁን ፤ ከሌሎች ጋር ሲስቅ ቆይቶ ።

" ማን ?" አለ ውብቱ ።

" ማን ባዩ"

"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ! ምን አልሁህ ?" አለ ውብቱ ፣ እያማተበ ።

"መተዛዘንና መረዳዳት አያስፈልግም ፤ ደካማን መታገልና ጥሎ ካፈር እዮደባለቁ የመሬት ማዳበሪያ ማድረግ ነው" እያለ የሚያስተምር ምን ይባላል ?"

" እንደሱ አላልሁም !"

" አሁን ያልኸው ሁሉ ቃል በቃል ባይሆን መንፈሱ ይህ ነው" ሲል ጥላሁን ፡ በረኛው አገደው የሚባለው ያሳዩ አሽከርና ካሳዩ ቤት ድግስ ያመጡት እስረኞች ተከታትለው ገቡ ። ወዲያው በረኛው አገደው ወደሳዩ ጆሮ ጠጋ ብሎ የሚናገረውን በሹክሹክታ ተናግሮ ቆና ሲል ፣

" እንዴት ! አንተ የት ሄድህ ? ጠንክረህ ጠብቅ አላልሁህም ነበር ?" አለ አሳዩ በጣም ተቆጥቶ ።

" እሜቴ ለስራ አስጠርተውኝ ወደ ቤት ሄጄ ነበር " አለ በረኛው አገደው ።

@OLDBOOKSPDF

"ታዲያ አመለጡ ?"

"ማምለጥስ አንድም ያመለጠ የለ ፤ ሁሉንም አምጥቻቸዋለሁ።"

"የለቀሙትን እንዴ ያዙ ?"

"የለቀሙትን እንደያዙ ።"

"የት ናቸው ? ስንት ናቸው ?"

"ሰላሳ ናቸው ፤ የለቀሙትን ቡና ይዘው እውጭ ናቸው ።"

"ምንድር ነው ነገሩ ? ለኛም እካፍሉን እንጂ !" አለ ውብቱ ።

"ሌቦችን ያዩ ጥላሁንን ቡና ሲለቅሙ እግኝቼ ያዝሁ ነው የሚል ።"

"ሌቦች ? እዚህ አገር ሌባ የለም ይባል የል ? መግረፍ ነው ፤ የታባታቸው ! ሌላው ቢቀር . . ለሌሎች መቀጣጫ እንዲሆኑ መግረፍ ነው !" አለ ውብቱ ከተቀመጠበት ተነስቶ ።

"ቅድም እንደ ነገርሁዋችሁ ፣ ድሮ ባላገሩ በመንግሥት መሬት የጋራ ሲጠቀም ስለኖረ ፣ አሁንም መሬቱን የገዛው ሰው እጅ እስኪያ ደርገው ፤ በሱ መጠቀምን እንደ ሌብነት አይቆጥሩትም " አለና እሳዬ ሁሉንም ይዞዋቸው ፤ "ቡና ሰርቀው ለቀሙ" የተባሉት ሰዎች ወዳ ሉበት ወጣ ። የተለቀመው ሰላሳ ኬሻ እሸት ቡናም እዚያ ተከምሮዋል።

"እናንተ የሰው ሀብት የምትዘርፉበት ምክናያት ምንድር ነው ?" አለ እሳዬ በቁጣ ፡ እዚያ ተሰብስበው ለቆሙት ባላገሮች ።

"የማንን ሀብት ዘረፍን ጌታየ ?" አለ ከባላገሮቹ አማርኛ የሚ ያውቀው ።

"ይህ የለቀማችሁት ቡና የናንተ ነው ?"

"እኛማ . . የኛ ነው ብለን ነበር !"

"ምነው ስንት ጊዜ እንነገራችሁ ? በመንግስት እጅ ያለ ፣ ገና ያልተሸጠና ሰው ሀብቱንም ፣ ጉልበቱንም ፣ ያላሳለፈበት መሬት ያገሩ ህዝብ የጋራ ቢጠቀምበት ግዴለም ፡ ይፈቀዳል ። መንግሥት ለሰው የሸጠውና የገዛው ሰው ሀብቱንም ፣ ጉልበቱንም ያሳለፈበት መሬት ግን ፣ የዚያ ሰው የግል ንብረት ስለሆነ ፣ የሰው የግል ንብረት ስትደ ፍሩ ብትገኙ ትቀጣላችሁ አላልናችሁም ?"

"ብላችሁናል ፤ ብቻ . . . እኛስ ምን እንሁን ?"

"መሬት ከሌላችሁ ግዙ ፤ የመንግሥት መሬት ሞልቶላችሁዋል።"

@OLDBOOKSPDF

" ድሆች ነን በምን ገንዘብ እንገዛለን ? ወዲያውስ . . የገዛ መሬታችንን እንዴት እንገዛለን ? "

" የመንግስት ነበር ፤ መንግስት ለሳቸው ሸጦታ . . . ል ነው የምላችሁ " አለ አሳዬ ፣ " ለሳቸው " ሲል ጥላሁንን በጁ እያመለከተ ። " ከናንተ መሀከል " አለ ቀጠለና ፣ "ከናንተ መሀከል ብዙዎች ካሁን ቀደም እንዲሁ ስትለቅሙ ተገኝታችሁ ማስጠንቀቂያ ሰጥተን ለቀናችሁ ነበር ፤ ነገር ግን በመጸጸት ፈንታ ፣ ያኑ ጥፋት ስትደግሙ ስለ ተገኛችሁ . . . " ብሎ አሳዬ ያሰበውን ተናግሮ ሳይጨርስ ፣

" ልትለው ያሰብኸው ገብቶኛል " አለ ጥላሁን አቋርጦ ። "የለቀሙበትን ዋጋ ለያንዳንዱ ኬሻ የሚገባውን ከፈላቸውና ቡናህን ሰጥተውህ ይሂዱ" ማለትህ አይደል ? ገና ስታስበው ነው ከግንባርህ ያነበብሁት ፤ ጥሩ ፍርድ ነው እስማማበታለሁ " አለና ለያንዳንዱ ኬሻ አንዳንድ ብር ሂሳብ ፣ ለሰላሳው ሰላሳ ብር ሰጥቶ ፣ በነጋው ቢለቅሙ እንዲሁ በኬሻ አንድ ብር የሚከፍል መሆኑን ገልጾ አሰናበታቸው ።

"ታዲያ ልለው ያሰብሁትኮ ሳይገባህ ነው ገብቶኛል ያልህ " አለ አሳዬ ፣ ሰዎቹ ከሄዱ በሁዋላ ።

" ምን ልትል ኖሮዋል ? "

" ያንዳንድ ወር እስራት ፈርጅባችሁዋለሁ ልል ነበር ። "

" መጥፎ ፍርድ ኖሮዋል ፤ እንኩዋን አልገባኝ ። "

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፲፰

# የግራዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ ድግስ

ውብቱ ፡ ከነጥላሁን ጋር የኪ. ሰንብቶ ወደ ጎሬ ከተመለሰበት ቀን በፊት በነበረው ማታ ፡ የወረዳው ገዥ ፡ ግራዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ ፡ ለሱና ለንግዶች ፡ ለነጥላሁን ክብር ፡ የራት ግብዣ አድርገው ነበር ።

“ ከነገ ወዲያ ወደ ጎሬ የምመለስ መሆኔን ለወረዳው ገዥ ነግሬያቸው ፡ ለናንተ መተዋወቂያና ለኔ መሰነባበቻ ራት ይግበው ፡ ነገ ማታ እንድንጋበዝላቸው አደራ ብለዋል ” አለ ውብቱ ፡ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ፡ ጥላሁንና እሱ ቡና በሚሰተምበት ቆመው እያስለቀሙ ሲጫወቱ ።

“ እግዜር ይስጥልኝ ” አለ ጥላሁን ፡ ፍርጥም እንደ ማለትም ፡ ትንሽ እንደ መስገድም ብሎ ።

“ ግራዝማችን እንዷሁ በሩቁ ካልሆነ ፡ ደህና አድርጌ አላውቃቸውም ፤ እንደ ሰው አፍ ግን ፡ ከደህና ሰዎች ጋር የሚደረደሩ አደሉም ። ክፉ ፡ ቀናተኛና ጨካኝ ናቸው ይሉዋቸዋል ። ብቻ . . . ‘ ወሬ ሰማሁ ’ ብሎ ከሰው መጣላት ሊያቀልል እንደሚችል ፡ ወሬ ሰምቶ አለመጠንቀቅም ሊያስጠቃ ይችላልና ፡ መጠንቀቁ ምንም ቢሆን አይከፋም ” አለ ውብቱ ።

“ መጠንቀቅ መቸም . . . ለማንኛውም ቢሆን ጥሩ ነው ፤ ነገር ግን ክፉ ቢሆኑ ለራሳቸው ይባሳቸው እንጂ እኛን ምን ያደርጉናል ፤ በምን እንገናኛለን ማለቴ ነው ” አለ ጥላሁን ፡ “ ምን ያደርጉናል” ያለውን ቶሎ አርሞ ።

“ ጐሱን እንኩዋ ተወው ! በሚገዙት አገር እዬኖራችሁ በምን አትገናኙም ? ” አለና ውብቱ ፡ ትንሽ ዝም ብሎ ፊቱ ለፊት ሲመለከት ቆይቶ ፡ “ አንተና ሰፌ ፡ ያን . . ያን ጥሩ አሳባችሁን ፡ ያን የተቀደሰ ምኞታችሁን በስራ ተርጉማችሁ ውጤቱን ሳታሳዩን ፡ ካለመጠንቀቅ የተነሳ ተሰናክሎ ቢቀር . . ሁላችንም እናዝናለን ” አለ ፡ ማሾፉ ካይኑ ውሀው ወለል ብሎ እዬታዬ ።

@OLDBOOKSPDF

“ ምን የተቀደሰ ምኞታችንን ሳናሟላችሁ ! እ ? የዛሬን እያሮገውና የዚያ የተቀደሰ ምኞት ባለቤቱቱ አንተ አልነበርህ ?”

“ ልጅ ሳለሁ ! ገና የሚቻልና የማይቻል ፣ የሚሆንና የማይሆን መለዩት ሳላውቅ ! ”

“ ለመሆኑ ሰው ከልጅነት ወደዋቂነት ሲሸጋገር ፣ አስተያየቱ እዬ ጠበበ ይሄዳል ማለት ነው ?” አለ ጥላሁን ፣ ባሽሙር ውብቱን የጎ ድን እያዬ ።

“ መቸም . . . ‘ካዩሁትና ከሰማሁት አንድ አይቅረኝ’ ብሎ እደ ርስ ፣ እደርስ ፣ ላይ ላዩን መጋለብ የልጅ ፣ ያዩትን ጠልቆ እስከያ ውቁ እስመባከን ያዋቂ ባሕሪያዎች መሆናቸው . . የሚያከራክር አይ መስለኝም ! ” አለ ውብቱም ፣ የጉዋደኛውን ያሽሙር አስተያየት ባሽ ሙር አስተያየት መልሶ ።

“ ደግ እስቲ ይሁን ! ” አለ ጥላሁን ፣ ከርከሩን ባጭር መቁረጥ በለፈለን ።

በማግስቱ ማታ ፣ ውብቱ ፣ ጥላሁን ከነባለቤቱና አባዬ ከነባለ ቤቱ ከሌሎች ቀድመው እግራዝማች ዳኛቸው ቤት ደረሱ ።

ግራዝማች ዳኛቸው ዘለግ ፣ ወፈር ብለው ፣ ጠጉራቸው ከርደድ፣ አፍንጫቸው ሰፋ ፣ ከንፈራቸው ወፈር ያለ ፣ ጠየም ብሎ ጎላ ያለ መልክ ያላቸው ፣ ዕድሜያቸው በግምት ሰድሳ ግድም የሚደርስ ሰው ናቸው ። አባታቸው ፣ ባላምባራስ ፍሪሳ ከየትም ተጠራቅሞ ፣ “የጎን ደሬ ጦር” እዬተባለ ይጠራ በነበረው የመንግስት ሰራዊት ውስጥ ፣ አንድ አለቅነት ከገባር ጋር ተሰጥቶዋቸው ፣ “ አልጋ ” በሚባል የኢ ሉባቦር ክፍል ይኖሩ ስለነበረ ፣ ግራዝማች ዳኛቸው እዚያ ተወልደው፣ አድገው አስራ ዘጠኝ ፣ ወይም ሃያ ዓመት ያክል ሲሆናቸው ፣ ባምባ ጉዋሮ ነፍስ አጥፍተው ጫካ ገቡ ። ከዚያ ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ስትይዝ ፣ እዚያው በሽፍትነታቸው ብዙ አመታት እንዳሉ ቀጥለው በዋቻ ጫካ እዬተዘዋወሩ ፣ የጠላትን ግንባር በጦርነት ካልሆነ ፣ በሌላ በማናቸውም ምክናያት ሳያዩ ፣ አምስቱን ዓመት አሳለፉ ። ከዚያም በሁዋላ ፣ “ የግሚራና ያካባቢው ህዝብ በመንግስት ላይ ሸፈተ ” ተብሎ ሲዘመትበት ፣ በመንግስት ወገን ሆነው ፣ ቁጥር ስፍር የሌለው ህዝብ የፈጁና ብዙ መንደር አመድ ያደረጉ መሆናቸው ስለ ታወቀላ ቸው ፣ “ስመ ጥሩ ጀግና” ተብለው ፣ ካገልግሎታቸው ዋጋ ሽልማትና መጀመሪያ የምክትል ፣ ቀጥሎ የሙሉ ወረዳ ገዥነት እዚያው ዋቻ ውስጥ ባንዳንድ ክፍሎች ላይ ተሰጥቶዋቸው ፣ ላጭር ጊዜ ተዘዋወ

@OLDBOOKSPDF

ረው ገዝተዋል ። ወደ የኪ. ከተዛወሩ በሁዋላ ግን ፣ አስራ አምስት አመት ሙሉ ስላልተንቀሳቀሱ ፣ የኪ. የርስት እንጂ የግዛት አገራቸው መሆኑን ወደ መርሳቱ ደርሰዋል ። ምሽታቸው ፣ ወይዘሮ እጸገነት አሸ ብር ግን ፣ ግፋ ቢል ከሰላሳ አመት የማያልፉ ፣ ውብ ወጣት ወይዘሮ ናቸው ።

ግራዝማች ከሚወዱት ባላቸው ቀምተው ፣ ያለፈቃዳቸው በግድ አግብተዋቸው ፣ ምሽት ሆነው አብረዋቸው የሚኖሩ ስለሆኑ ፣ ሁል ጊዜ ያዘንተኛ መልክ ይታይባቸዋል ።

የግራዝማች ዳኛቸው ቤት መቸም ለየኪ. ፣ " እጅግ ጥሩ " የሚ ባል ነው ። ባጡ ቆርቆሮ የተከደኑ ፣ ግድግዳው ከውጭ ተለስኖ ኖራ የተቀባና ፣ ከውስጥ በባላበባ ወረቀት ያጌጠ ፣ ወለሉ እስከ ግድግዳው ጥግ ስጋጃ ምንጣፍ ግጥም ብሎ የተነጠፈ ነው ። ከዋናው በር አንጻር ግድግዳውን ተጠግቶ ፣ አንድ ከፍ ያለ ድልዳል ካለባለሉ የተነሳ ግራ ዝማች ፣ "ሀር" የሚሉት አበባ ምንጣፍ ተነጥፎ ፣ በራስጌና በግርጌ ባለ ጥልፍ መሸፈኛ መከዳዎች ተደርገውበት ይታያል ። ድልዳሉ ግራ ዝማች እንግዶች ካልጋበዙ በግብር ጊዜም ይሁን ፣ በሌላ ያዘቦት ቀን፣ እቤት ከቆዩ የሚቀመጡበት ነው ። እንግዶች ሲጋበዙ ግን ፣ ከድል ዳሉ ፊትለፊት ፣ ትንሽ ፈንጠር ብሎ በሚታዩው ረዥም ጠረጴዛ ነው እንግዶቻቸውን የሚጋብዙ ። ስለዚህ ፣ ያ ከዳር እስከ ዳር ስጋጃ ምንጣፍ ግጥም ብሎ የተነጠፈ ሰፊ አዳራሽ ፣ ግራዝማች ባዘቦት ቀን ከሚቀመጡበት ድልዳልና ከመብል ጠረጴዛው እስከ ወንበሮቹ በቀር ሌላ እቃ አይታይበትም ። በእቃ ፈንታ በግድግዳው ዙሪያ ተደርድሮ የሚታዩው አሽከር ብቻ ነው ።

ግራዝማችና ባለቤታቸው እዩተመካከሩ እንግዶች የሚቀመጡበ ትን ተራ ሳጋፋሪው ሲያሳዩ ፣ እንግዶች መምጣታቸውን አንድ አሽ ከር ገብቶ ስለነገረ ፣ አጋፋሪው ወጥቶ አስገባቸውና ፣ ውብቱ ሁሉንም በዩስማቸው ከግራዝማችና ከወይዘሮ እጸገነት ጋር ማስተዋወቅ ጀመረ።

" መቸም አቶ አሳዩ የብዙ ጊዜ ጭፍራዎ ስለሆን ማስተዋወቅ ባላሻም ፣ ከባለቤቱ ፣ ከወይዘሮ የውብዳርም እንደምትተዋወቁ እርግ ጠኛ ነኝ ። ብቻ አሳዩ በዩቀኑ የሚያውቁት ሰው ነው ። እኔም አው ቀዋለሁ ሲመስለኝ ፣ ለካስ ትንሹን ክፍሉን ኖሮዋል የማውቀው ! ብዙ ውን ገና አሁን ነው ያወቅሁት ። ያለጥርጥር እርስዎም ገና ያላወቁት ክፍል ይኖረዋልና ደህና አድርገው ይወቁት " ሲል ውብቱ እዩሳቀ ፣ ግራዝ ማችና ወይዘሮ እጸገነትም እዩሳቁ ላሳዩና ለባለቤቱ የጅ ሰላምታ ሰጡ ።

@OLDBOOKSPDF

"አቶ ጥላሁን" አለ ውብቱ ቀጥሎ ። "አቶ ጥላሁንና ባለቤቱ ወይዘሮ ሶፊያ ፣ በቀደም እንደ ነገርሁዎ ፣ እዚህ የግል ስራቸውን እዬ ሰሩ በትርፍ ጊዜያቸው አገሬውን በትምህርትና በጤና አጠባበቅ ፣ በሌላም ለመርዳት ምኞት አድሮባቸው የመጡ ናቸው ። ስማቸውን የነገርሁዎ አይመስለኝም እንጂ ፣ የመጡበትን ምክናያትማ በቀደም ነግሬዎታለሁ ። እሱ አቶ ጥላሁን ፈይሳ ፣ እስዋ ባለቤቱ ወይዘሮ ሶፊያ ሙላት ይባላሉ " ብሎ ሲጨርስ ፣ ግራዝማችና ባለቤታቸው መርዶ እንደ ነገርዋቸው ድንግጥ ሲሉ ፣ ድንጋጤው በፊታቸው ታዬ ። ለንግዶች የጅ ሰላምታ መስጠቱን እንኩዋ ረስተው ትንሽ ጊዜ ካለፈ በሁዋላ ነው ግራዝማች እንደገና ልብ ገዝተው ሰላም ያልዋቸው ። ከግራዝማች በሁዋላ ፣ ወይዘሮ እጸገነትም አይኖቻቸውን ከመሬት ሳያነሱ ፣ እጃቸውን ብቻ ልከው ሰላም አሉ ። ወዲያው የወረዳው ዳኛና የወረዳው ፖሊስ ሹም ከነባለቤቶቻቸው ገቡና ለባለቤቶች ሰላምታ ሰጥተው ፣ ከንግዶች ጋር አሳዬ ካስተዋወቃቸው በሁዋላ ፣ ግራዝማችና ባለቤታቸው የጠረጴዛውን አናት ይዘው ለራት ሲቀመጡ ። ከወይዘሮ እጸገነት ቀጥላ ሶፊያ ፣ ከዚያ ያሳዬ ባለቤት የውብዳር ፣ ከዚያ የዳኛው ባለቤት ፣ መጨረሻ የፖሊሱ ሹም ባለቤት ተቀመጡ ። በወንዶቹ ወገን ከግራዝማች ግራ ውብቱ ፣ ከሱ ቀጥሎ ስለንግድነቱ ጥላሁን ፣ ከዚያ የበኸርሮንድ ወኪል አሳዬ ፣ ከዚያ ዳኛው ፣ መጨረሻ የፖሊሱ ሹም ተቀመጡ ። መችም የመሰናዶው አይነትም ሆነ ብዛት ፣ ያሳላፊዎች ቅልጥፍና ጭምር የሚደነቅ ነበር ። ሶፊያና ጥላሁን ከጠጅ ይልቅ ብርዝ መምረጣቸው ግራዝማችን አስገርሞዋቸው "ሎሚ በልቶ ጠጅ የማይጠጣ ሰው 'ግማሽ እንጂ ሙሉ ህይወት ኖርሁ' አይበል !" ስላሉ ሁሉም ሲስቁ ቆዩና ፣

"ታዲያ እንግዶች . . . አገራችንን ወደውልን ይሆን ?" አሉ ግራዝማች ።

"በጣም እንጂ ! በጣም ነው የወደዱት ። መጀመርያ ካዲስ አበባ እንደ መጡ ጎሬን ሲያዩ ፣ እሱን የመሰለ አገር እግዜር በፈጠረው ምድር ሁሉ አይገኝም " ብለው ነበር ። በሁዋላ እዚህ መጥተው የኪን ሲያዩ ጊዜ ጎሬንም አስናቃቸው ። ወይዘሮ ሶፊያማ ፣ "እግዜር በመሬት የሚኖር ቢሆን ኖሮ ፣ ከየኪ በቀር ሌላ መኖርያ አይመርጥም ነበር " አለችን ሲል ውብቱ ፣ ሁሉም ባንድ ላይ ሳቁ ።

"እኔ መችም . . ." አሉ ግራዝማች ከሌሎች ጋር ሲስቁ ቆይተው ። "እኔ መችም . . . ከዚህ ከሞቻ ክፍል ወጥቼ ከጎሬ በቀር ሌላ አገር አይቼ አላውቅም ። ስለዚህም ፣ የሚያውቁትን ከሚያው

@OLDBOOKSPDF

ቆት ጋር ነው እንጂ ፣ ከማያውቁት ግመዛዘን አይገባምና ፣ በማውቀው መጠን ጎሬን የሚመስል አገር የሚገኝ አይመስለኝ ! ”

“ እንዴት ? ” አለ ውብቱ ።

“ አ . . . ስንቱን ብዬ ልንገርህ ? እንዲያው ለምሳሌ ፣ አንድ ከፍተኛ ቦታ ላይ ቆመህ ከተማውን በወርዱም ፣ በቁሙም ፣ ዘቅዝቀህ የተመለከትህ እንደሆን ፣ ሳር ቤት የምታየው ከስንት አንድ ነው ፤ ከዳር እስከ ዳር ሁሉም በቆርቆሮ ብቻ ግጥም ብሎ ተሽፍኖ ሲታይህ ያ ሁሉ ባንድ ላይ ፣ ባህር እንጂ መሬት አይመስልም ! ከዚያ ወርደህ ሱቅ የገባህ እንደሆን ፣ ገንዘብ ካለህ ፣ ራስ ደጃዝማቾች የሚለብሱትን ገዝተህ ልትወጣ ትችላለህ ! ከዚያ መብል ቢያምርህ ፣ እንደ ቤትህ የምግብ ጊዜ ደረሰ ፣ አልደረሰ ማለት ሳይኖርብህ ፣ በፈለግኸው ሰዓት ፣ ወደ መረጥኸው መብል ቤት ገብተህ የመረጥኸውን በልተህ ትወጣለህ ! መጠጥና ጭዋታ ብትፈልግ ፣ መሰሎችህ በሚገቡበት የጭዋታ ቤት ገብተህ ደስ ተሰኝተህ ትሄዳለህ ! አዬህ ? ጎሬ ባንድ ነገር ብትበሳጭ ፣ ወይም ቅር የሚያሰኝ ነገር ቢገጥምህ ፣ ወዳንድ የጭዋታ ቦታ ገባ ብለህ ብስጭትህንና ቅርታህን እዚያ ትተኸው ትወጣለህ ፤ ብስጭትና ቅርታ ተከትለውህ አቤትህ አይገቡም ! የኪ እዚህ ጫካ ውስጥ ከዝንጀሮ ፣ ከጦጣና ከጉሬዛ በቀር ምን ታያለህ ? ቤቱ እንደምታየው ሰው ቆሞ ሊገባበት የማይችል ፣ ከጥቂት ጭራሮዎች ተወንጋግሮ የተሰራ ፣ ካገሩ ሰው የሚበዛው ሀፍረቱን ብቻ በቅጠል ከድኖ ራቁቱን የሚሄድ ነው ! ከቤትህ ስትወጣ የት ገብተህ ? ከማንስ ጋር ትጫወታለህ ? በውነቱ ልንገርህ ፤ እኛ ለምደነው አይከብደንም እንጂ ፣ የኪ እንደ ጎሬ ባለ አገር የኖረ ሰው የሚኖርበት አገር አይደለም ! ብቻ ደግነቱ የገንዘብ ችግር ስለሌለብን ፣ እግዜር ይመስገን ሌላ ሌላው ቢቀር የምንፈልገውን መብልና መጠጥ በዬቤታችን ስለማናጣ አንመረርም ። ”

“ ይህም አንድ ነገር ነው ፤ ይልቁንም እኛን ፣ የበኸርሮንዱን መበሪያ ቤት ሠራተኞች የሚያጽናና ነው ! ” አለ ውብቱ ፣ ለቀልድ ያክል።

“ ምኑ ? እንዴት ? ”

“ በገንዘብ አለመቸገራችሁ ። እስከ ዛሬ ከዬሰው አፍ የሚሰማው የበኸርሮንድ መስሪያ ቤት ደመወዝ በጊዜ ስለማይከፍል የውንግስት ሰራተኛ የሆነ ሁሉ በብርቱ ችግር የሚኖር መሆኑ ነው ። ዛሬ ብቻ ከርስዎ አፍ ስንመሰገን መስማቱ ነው ! ስለዚህ በብዙ ወቃሽ መሀከል እንዲህ አንዳንድ የሚያመሰግን ሲገኝ ያጽናናልኮ ! ”

@OLDBOOKSPDF

“ሀ-ሀ-ሀ-ሀ [illegible] ግራዝማች ፣ ከባጥ በላይ ከፍ አድርገው ስቀው ። “በደመወዙ ነው የምንኖረው ? ” አሉ ቀጠሉና ። “የደመወዙን ነገር ተወው ! ደመወዙስ እጅግ ፈጠን ሲባል ሶስትና አራት ወር ሳይቆይ መጥቶ ያውቅ እንደሆነ . . . ያው የገዛ ሹማችሁን አቶ አባዬን ጠይቀው ! ደግሞስ . . . በጊዜ አይመጣም እንጂ ቢመጣ ለምን ይሆናል ? አንድ ትንሽ ቀዳዳ ሲደፍን ይችላል ? ”

“የገንዘብ ችግር የለብንም ሲሉ ጊዜኮ ነው ! ” አለ ውቤ ።

“ከዚሁ እንደምንም ብለን እናጣም ” ማለቴ ነዋ ! ርስት አለን ፤ በዚያ ላይ . . . የሹመት አገራችን ነው ። ሀ ! ሰው መችስ . . በተሸመበት አገር ፣ “ስጡኝ” ባይል ፣ “እንካ” መባሉ “አይቀርም ! በየትም ቢሆን ሹም አስቀምጦ የሚበላ የለምኮ ! ” አሉ ግራዝማች ትንሽ እንደ መሳቅ ብለው ።

“የሹም አይን ቡዳ ነው ፤ ትቶት የሚበላውን ሁሉ ይጣረራል ! ሲሉ ሰምተህ አታውቅም ? ” ሲል አሳዬ ፣ ሁሉም ሳቁ ።

“ጌታዩ ፣ ትውልድዎ እዚህ አገር ነው ? ” አለ ጥላሁን ፣ ከሳቅ በሁዋላ ሁሉም ዝም ብለው ትንሽ እንደቆዩ ።

“እንዴት ? መልኬ ሲጠቁር ጊዜ ነው ፣ የዚህ አገር ተወላጅ የመሰልሁህ ? ” አሉ ግራዝማች እንደ መሳቅ ብለው ።

“እረ ! እረ አይደለም ! ርስት አለኝ ሲሉ ጊዜ ነው . . የዚህ አገር ተወላጅ ነወት ወይ ያልሁ ! ” አለ ጥላሁን ፣ እንደ መደንገጥ ብሎ ።

“የዚህ አገር ተወላጅ ባይሆኑ ነው እንጂ ባለርስት የሆኑ ፣ የዚህ አገር ተወላጅ ቢሆኑማ ባለርስት አይሆኑም ነበር ! ” ሲል አሳዬ እዩ ሳቀ ሁሉም ይስቁ ጀመር ።

“የለም ፤ አደለሁም ” አሉ ግራዝማች ፣ ከሌሎች ጋር ሲስቁ ቆይተው ። “ትውልዴ ከዚህ ብዙ አይርቅም እንጂ እዚህ አደለም ። እዚሁ ሞቻ አውራጃ ውስጥ ‘አልጋ’ በሚባል ወረዳ ነው የተወለድሁ ። አባቴ በጎንደሬ አለቅነት ‘አልጋ’ በሚባል ወረዳ ገባር ተሰጥቶዋቸው ይኖሩ ስለነበር ፣ እዚያ ተወልጄ እዚያው ነው ያደግሁ ። ነገር ግን የወረዳ ገዥ ሆኘ እዚህ አገር አስራምስት አመት ያክል ስለኖርሁ፣ አገሬ የሚመስለኝ ይህ ነው ። ከጠላት ወረራ ወዲህ ወደ ተወለድሁበት አገር ሄጄ ስለማላውቅና ፣ ብዙ የኖርሁ እዚህ ከመሆኑም ሌላ ፣ የግል ርስት ያበጀሁበትም በመሆኑ አገሬ የምለው የኪን ነው ። ”

@OLDBOOKSPDF

" ወዳባትም እ[illegible]ጎንደርነ . . . ሂደው አያውቁም ? እሱን ቢያዩ ደግሞ ይወዱት ይሆናል ! " አለ ጥላሁን ።

" ጎንደር ? ጎንደርን ላባቴ ማን ሰጣቸው ?"

" የጎንደሬ አለቃ ነበሩ ያሉ መስሉኝ ! "

" አ . . . ! ‹የጎንደሬ አለቃ ፤ ወይም የጎንደሬ ጦር ፤ ማለት› ከጎንደር የመጣ ማለት አይደለምኮ ! በጥንቱ ስሪት ፤ ከየትም ተጠረቃቅሞ በዩኒፎርም ውስጥ ገባር እንደዩማኒሬት እዩተሰጠው ተሰርቶ የሚኖርና ፤ ለዘመቻ ሲፈለግ በታዘዘበት የሚዘምት ፤ ' የጎንደሬ ጦር' የሚባል ሰራዊት ነበር ። እንዲያ ባለው ጦር ላይ ትንሽም ይሁን ትልቅ አልቅና ያለው ፤ የጎንደሬ አለቃ " ይባል ነበር ። በዚህ አይነት ነው አባቴ የጎንደሬ አለቃ ነበሩ ያልሁ እንጂ . . . ጥንት አገራቸውስ ሸዋ ውስጥ ፤ መናገሻ ነው " አሉ ግራዝማች ።

"እግዜር ይስጥልኝ ፤ እስከ ዛሬ የማላውቀው ትምህርት ነው ያገኘሁ " አለ ጥላሁን ፤ በውነት ደስ ብሎት ።

ሌሎች ሲጫወቱ ሶፊያ ፤ ወይዘሮ እጸገነት አሳላፊዎችን የሚመሩበትን ዘዴና ያሳላፊዎችን መሰልጠን ዝም ብላ እዩተመለከተች ፤ በልብዋ ታደንቅ ነበር ። ወይዘሮ እጸገነት አንዳንድ ጊዜ ብቻ ሶፊን ለማነጋገር ወደሰዋ ዘወር ከማለታቸው በቀር ፤ አይኖቻቸውን ተጋባገሮቹ ከሚበሉትና ከሚጠጡት አይለዩም ። እንጀራ ፤ ወጥ ፤ ጠጅ ፤ ወይም ሌላ እዚያ ከቀረበው መጨመር የሚያስፈልግበትን ቦታ ከተመለከቱ በሁዋላ አፋቸው ሳይናገር ፤ ቀና ብለው የንጀራ ፤ የወጥ ፤የጠጅ ፤ ወይም የሌላውን አሳላፊ አይን ባይናቸው ፈልገው ይይዙና ፤ ስበው ወስደው የጎደለውን ነገር ሲያሳዩት ፤ ወዲያው የሚያስፈልገውን ነገር በሚፈልግበት ቦታ ይወስድና ይጨምራል ። የሚያስገርመው እንዳሳላፊዎች ብዛት ድምጻቸው አይሰማም ። እንጀራ እንዲጨመር በመ/ቤቱ አይን የታዘዘው እንጀራውን ፤ ባለበርበሬ ወጥ በርበሬ ወጡን ፤ ባላልጫ አልጫውን ፤ ባለ ስጋ ስጋውን ፤ ባለጠጅ ጠጁን ፤ እንዲሁም ሌላውን እዩያዘ ፤ ሁሉም ድምጹን አጥፍቶ ሲተላለፍ ፤ እያንዳንዱ የሚሄድበት መንገድ ለዩብቻ እንደ ተሰራለት ሁሉ ፤ እንኪዋንስ መተራመስና መገፋፋት መንካካት የለም !

" ግራዝማች ፤ ቅድም የኪን ከጎሬ እያመዛዘኑ ሲናገሩ ፤ የኪ ገንዘብ የሚገኝበት አገር ቢሆንም ፤ ህዝቡ የሚኖርበት ሁኔታ መጥፎ መሆኑን ግሩም አድርገው አስረዱን ። መቸም አንድ አገር ወደፊት

@OLDBOOKSPDF

የሚቀድም ፣ ወይም ወደሁዋላ የሚቀር ፣ እንደ መሪው አመራር ነው። ታዲያ እርስዎ የሚመሩት አገር ህዝብ ወደፊት እንዲራመድና ኑሮውን እንዲያሻሽል ያሰቡት ነገር አለ ? ” አለ ውብቱ ፣ ጠጁን ተጎንጭቶ ብርጭቆውን አፉቱ አስቀመጠና ።

“ ልክ ፣ ልናገር ስል ነው . . ካፌ ነጥቀህ የጠየቅኸኝ ! ሞት ካል ቀደመኝ ፣ እግዚአብሔር እድሜ ከሰጠኝ ፣ እጅግ ቢበዛ ባምስት አመት ውስጥ የኪን ዳግማይ ጎሬ ባላደርጋት . . ‘ ምን ብለህ ነበር ’ ትለ ኛለህ ! እስከ ዛሬም ድረስ የተጫጫወተብኝ ያ . . አባ ጎዳ ነው ። ጎሬ ልዩ ልዩ እቃም ፣ ልብስም ፣ ከሚሸጡ ህንዶችና አረቦች ፣ ስጋ ከሚ ሸጡ አበሾችና ከጠጅ ከማሪዎች ሁሉ ጋር ተነጋግሬ ፣ ሁሉም ‘ሱቅ መስራት እንችልም እንጂ አንተ ከሰራህልን ከራይህን እዩከፈልን እዚያ መጥተን እንከፍታለን ’ ብለውኝ ፣ ለሱቅ መስሪያ ገንዘብ ከሰ በሰብሁ በሁዋላ ፣ አባ ጎዳ ፣ ‘ የወረዳው ግዛት ከተማ በቅርብ ቀን ከየኪ ወደ ቴፒ ይዛወራልና እዚህ በከንቱ አትድከም ’ ሰላለኝ ፣ እኔም ፣ ‘ ከዛሬ ነገ ወደ ቴፒ እንዛወራለን ’ እያልሁ ብዙ አመት በዝኘ አሳለፍሁ ። አሁን ከተማው ሳይዛወር ራሱ ፣ አባ ጎዳ . . ተዛወረ ! ” አሉ ግራዝማች እዩሳቁ ።

“ ወዴት ? ” አለ ውብቱ ።

“ መንግስት ሰማያት ይሁን ገሀነመ እሳት የት አቅለታለሁ ! ” አሉ ግራዝማች ፣ አሁንም እዩሳቁ ።

“ ሞተ ? ”

“ ሞተ ። ”

“ ለመሆኑ አባ ጎዳ ምን ኖሮዋል ? ”

“ አባ ጎዳ ? ወሬውንም ሰምተህ አታቅ ? የተናገረው እመሬት ጠብ የማይል ፣ ትልቅ ቃልቻ ነበር ! ሙሉ ኢሉባቦር ነው ? ጅማ ነው ? ከፋ ነው ? እሱ ደጅ የማይደርስ ማን ኖሮዋል ! እምና እከረ ምቱ ላይ ፣ በሀምሌ ወር ሲሞት ፣ ከዚህ ሁሉ አገር የተሰበሰበው አዘ ንተኛ ዳስ አልበቃው ሰላለ ፣ በዩዛፉ ስር ሰፍሮ እዩተበላ ፣ እዩተጠጣ ፣ ሲለቀስ ስምንት ቀን ሙሉ እንኩዋንስ ዝናብ ደመና በሰማይ ሳይታይ ሰንብቶ ፣ አዘኑ እንዳለቀ ህዝቡ ወደያገሩ ከገባ በሁዋላ ፣ ታማዶ የቆ ዩውን ያክል መአቱን ሲያወርደው ጊዜ ጉድ ተባለ ! ”

“ ታዲያ . . እርስዎ እንዳሉት አባ . . . ማነው ስሙ ? የተናገረው እመሬት ጠብ የማይል ከሆነ መቸስ . . እሱ ቢሞት የተናገረው እዩ

@OLDBOOKSPDF

ዎት ! ስለዚህ ከተማው ወደ ሌላ መዛወሩ የማይቀር ከሆነ ፣ ባንድ ፊቱ እዚያ መድከም አይሻልም ?" አለ ውብቱ ባሸሙር ።

"አሁንስ 'እግዚአብሄር እንዳወቀ ያድርግ' ብዬ በየኪ ከተማ ዙሪያ ያለውን አስር ነው ? አስራ አምስት ጋሻ መሬት እስክልዬ ወደ ከተማው አግብቼ ፣ በትንሽ በትንሹ እያሸነሸንሁ ገንዘብ ላለው ሁሉ መምራት ጀምሬያለሁ ። የመመሪያው ዋጋ እንዳስገመትሁት ፣ ቢያንስ ቢያንስ ካራትና ካምስት መቶ ሺህ ብር አያንስም ። ታዲያ በዚህ የመንግስቱን መስሪያ ቤቶች ፣ የከተማውን ዋና ዋና መንገዶችና ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ቅድም እንዳልሁዋቸው ላሉት ነጋዶች መሳብያ የሚሆኑ ሱቆች መስራት ከተቻለ ፣ ሌላውን የተመራው ሰው በገንዘቡ ይሰራዋል" አሉ ግራዝማች ።

"አስርና አስራምስት ጋሻ መሬት ብዙ ነውኮ ግራዝማች ፤ ይህ ሁሉ መሬት ላንድ የወረዳ ግዛት ከተማ መስሪያ እንዲሆን መንግስት ይፈቅዳል ?" አለ ጥላሁን ።

"መንግስት እንኩዋንስ አስርና አስራምስት ሀያ ሰላሳ ጋሻ ቢሆን ምን ቸገረው ? መሬቱ የመንግስት አደል !

"ታዲያ የማን ነው ?'

"እዚህ የሚኖሩ ያንዳንድ ሰዎች ነው ።"

"አ ፤ የሰዎች የግል ርስት ነው ! ታዲያ ግምታቸውን ከፍሎ ለማስነሳት ገንዘቡ አይበዛም ?"

"የምን ግምት ነው የሚከፈለው ? መሬቱን ለራሴ አላደረግሁትምኮ ፤ ለከተማ ነው የተከለለው ! የትም ቢሆን ከተማ የሚያሰራ አገረ ገዥ ሁሉ ፣ ወደ ከተማ ለሚከለል መሬት ግምት ክፍሎ እያውቅም፤ ጠይቂያለሁ ።"

" መቸም . . . መንግስት ይሁን ከተማ ፣ ወይም ሌላ ፣ የሰው ርስት ሲወስድ ለባለርስቱ የሚገባውን ግምት ሳይከፍል የሚወስድ አይመስለኝም ። ህገ መንግስቱም . . . አንቀጽ አርባ አራት የሚለው ይህ ነው " አለ ጥላሁን ።

" ማነው እሱ ?" አሉ ግራዝማች ።

"የቱ ?"

"ይህ አሁን ' አንቀጽ መንግስቱ ነው ? ማን ' ያልከው ።"

@OLDBOOKSPDF

ዳኛውና ፖሊሱ እሲቃ ፣ ሞላሁን ግር ብሎት ሲቸገር አዩና ፣ ከግራዝማች ይሷቅ ለሱ አዝነው ፤

"ግራዝማች ህገ መንግስቱ ማለታቸው ነው ፤ ህገ መንግስቱ ማለታቸው ነው" አሉ ፤ ባንድ ላይ እንደ ተማከሩ ሁሉ ።

"አዎ ፤ ህገ መንግስቱ ማለቴኮ ነው ፤ ህገ መንግስቱ ከተማ እትሰሩ ይላል ?" አሉ ግራዝማች ፤ የፍረት ምልክት ሳይታይባቸው ፍጹም ጸጥ ባለ ፊት ።

"እ . . ! ህገ መንግስቱ መቸም . . . እንደሚያውቁት ፣ የህጉ ሁሉ መሰረት ነው ። ታዲያ እሱ ፤ 'የማንም ሰው ርስት ለህዝብ አገልግሎት የሚያስፈልግ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ፣ ሽማግሌዎች የገመቱትና ባለርስቱ የተስማማበት ፤ ሳይስማማ ቢቀር ፍርድ ቤት የወሰነው ግምት ፣ አስቀድሞ ሳይከፈለው ርስቱ ሊወሰድ አይችልም' ይላል" አለ ሞላሁን ፣ ባገረ ገዡ ፍጹም መሀይምነት በጣም ተገርሞ ።

"እዩሀ ፤ እኛ መቸም . . . ከጠቅላይ ግዛቱ በሚላክልን ማዘዣ ነው የምንሰራ ፣ ያለማዘዣ የምንሰራው አንድ ነገር የለም ፤ ይኸው እነሱ ሁሉ ይታዘቡ ። ነገር ግን ይህ አሁን ያልኸው ፣ ህገ መንግስቱ የሚባለው እስከ ዛሬ . . እኛ ዘንድ አልመጣም ፤ ቢመጣም . . . ከጠቅላይ ግዛቱ የታዘዘውን መቸም ሊሽር አይችል ። ስለዚህ . . . ባልታዘዝነው ልንሰራ እንችልም ።"

ግራዝማች ስለ ህገ መንግስት ሰምተው የማያውቁ መሆናቸውን ካነጋገራቸው ሁሉም ስለ ተረዱ ፣ ጭኖቻውን በዚያው መስመር መቀጠል እሳቸውን የሚያሳፍር መስሎ ተሰምቶዋቸው ፣ አቅጣጫውን ለመለወጥ በዩበኩላቸው ሲያስቡ ላጭር ጊዜ ዝም ብለው ቆዩና ፣

"እኔ እንኪዋ" አለ ውብቱ ። "እኔ ቅድም . . 'ለሚያስተዳድሩት ህዝብ የኑሮ መሻሻል ምን አሰበዋል' ስል እዚህ ስላለው የከተማ ህዝብ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው ስለየኪ ወረዳ ህዝብ ማለቴ ነበር ።"

"የየኪ ወረዳ ህዝብ . . ያው እንደ ሌላው አገር ህዝብ ሁሉ ጸጥታው እንዲጠበቅለት መንግስት ፖሊስ አድርጎለታል ፤ ፍርድ እንዳይጎድልበት በተለይ ዳኛ ሾሞለታል ፤ ግብር እዩጫኑ ጎሬ ድረስ እንዳይንገላታ ግብር ተቀባይ በችሎግንድ እዚሁ አድርጎለታል ፤ በዚህ ላይ የሚጎድል ነገር ቢኖር አቤቱታ እዱሰማ የተዛባውን ሁሉ የሚያስተካክል የበላይ አገረ ገዥ ሾሞለታል ። ከዚህ በላይ ለህዝብ ምን ይደረጋል! መቸስ . . . አርሰን አናበላው ! አርሶ እናብላህ ያልነው እንደሆ

@OLDBOOKSPDF

ደግሞ ፣ መቸም ባላ[illegible] የለው ። እንጀራ ጋግራችሁ ፣ ወጥ ሰርታችሁ አቅርቡልኝ ይል ይሆናል ፤ ሀ - ሀ - ሀ - ሀ - ሁ ! ” ሲሉ ግራዝማች ከባጥ በላይ ስቀው ፣ ሁሉም ከነገሩ ይልቅ በግራዝማች ሳቁ ። “ በውነት ራሴን ማመስገን ሆኖ አይቆጠርብኝና ” አሉ ግራዝማች ቀጥለው ። “ ራስህን አመስገንህ ” አትበለኝና ፣ ማንንም ብትጠይቅ የሚያረጋግጥልህን ነው አሁን የምነግርህ ። በዚህ ወረዳ ግዛት ከዳር እስከ ዳር ብትሄድ በህይወቱ ፣ በንብረቱ ፣ ወይም በመብቱ እንኳንስ ጉዳት የደረሰበት ምናልባት “ ይደርስብኝ ይሆናል ” ብሎ የሚሰጋ አንድ ሰው አታገኝም ! እንግዲህ ባላገር ለህይወቱ ፣ ለንብረቱና ለመብቱ እንዲህ ያለ መተማመኛ ካለው እርሶ ፣ ቆፍሮ ፣ ነግዶ ፣ ወይም ሌላ የሚሰራውን ሰርቶ ፣ ኑሮውን ማሻሻሉ የራሱ ፈንታ አደለም ? ገኸሮዎች ከዚህ አልፈው በያንዳንዱ ባላገር ቤት መሰናዶ መግባት ይኖርባቸዋል ? ”

“ ገኸሮዎች በዬባላገሩ ቤት እዬገቡ ያሰናዱ ” ማለቴ አደለም ፣ ግራዝማች ! በሩቁ እንኳ የባላገርን ቤት ያደኸያሉ ተብሎ የሚፈሩት ገኸሮዎች ፣ “ እቤቱ ገብተው ያሰናዱ ” እላለሁ ? ይህማ ትልቅ እርግማን ነው ! ” ሲል ውብቱ ፣ ሳቅ ውካታ ሆነ ።

“ ታዲያ እንዴት ነው ? ” አሉ ግራዝማች ሲስቁ ቆይተው ።

“ እርስዎ እንዳሉት ባላገር ትክክለኛ ዳኝነት ካገኘ ፣ ህይወቱ ፣ ንብረቱና መብቱ እንደሚጠበቁለት ካመነ ፣ ይህም አንድ ትልቅ ነገርኮ ነው ። ብቻ ጥያቄው ፣ ባላገር ፣ ‘ ይህ ሁሉ ተደርጎልኛል ’ ብሎ ያምናል ወይ ነው ” አለ ውብቱ ።

“ ማመን አለማመኑ . . . መቸስ የሱ ጉዳይ ነው ! ” አሉ ግራዝማች ።

“ ባላገር በቃል ብቻ ሲነገር የሚሰማውን ነው እንጂ የሚጠረጥር ፣ ሲደረግ ወይም ሲሆን ባይኑ ያዬውን ያምናልኮ ! ” ሲል ውብቱ እዬሳቀ ከግራዝማች በቀር ሁሉም ሳቁ ፤ ግራዝማች ብቻ የውብቱ ንግግር ዘይቤው ስላልገባቸው ፣ ሌሎቹ ሲስቁ እሳቸው ጠጃቸውን ተጎንጭተው ብርጭቆዋቸውን ቁጭ አደረጉና ፣

“ ይልቅስ ” አሉ ። “ ይልቅ እውነቱን እንነጋገር ካልን ፣ ዛሬ የመሸበት የጭዋ ልጅ ነው እንጂ ፣ ባላገርማ ቀን ወጥቶለታል ! ብቻ . . እያመሰግንም ፤ ‘ በቃኝ ’ አይልም ! ”

“ ባይበቃው ይሆናላ ! ” አለ ውብቱ ።

“ እንዴት ? እስቲ ምን ጎደለው ? ” አሉ ግራዝማች ።

@OLDBOOKSPDF

“ እዩ ግራዝማች [illegible] ፈርድ ዳኛ ፣ ህይወቱን ፣ ንብረቱንና መብቱን የሚጠብቁ አገረ ገዥና ፖሊስ ተደርገሉታል ’ ሲሉኝ ፡ ‘ እነዚህን ሁሉ ባላገር ለሱ አገልግሎት እንዲ ተቀመጡ ያምናል ወይ?’ ብዬ ብጠይቅዎ ፣ ‘ ምስጋና-ቢስ ቢሆን ነው የማያምነው’ ያሉኝ መሰለኝ ። እስቲ እኔም እንደርስዎ ባላገርን እንደ ምስጋና-ቢስ ልቁጠርና ፣ ‘ እኛ እዚህ ያለን ባለስልጣኖች ሁሉ ለሱ ጥቅም የተቀመጥን ነን ’ ልበል ! ብቻ የጭዋታችን መነሻ የባላገር ኑሮ መሻሻል መሆኑን እንዳንረሳ ! እንግዲህ ለምሳሌ ፣ አንድ ባላገር እኛ ከዩተወለድንበት የርስት አገራችን መጥተን በልዩ ልዩ ስም ከወሰድንበት ርስቱ የተረፈች ኩርማን መሬት ብትኖረውና ፣ እሰዋንም አንድ ሀይለኛ በግፍ የቀማው እንደሆን ፣ ለዳኛ አቤት ካለ ፣ ዳኛው መርምሮ በግፍ የተቀማ መሆኑን ሲያረጋግጥ ያስመልስለታል ። ይህ እውነት ከሆነ መቸም ትልቅ ነገር ነው! እንዲሁም ቅድም እርስዎ እንዳሉት አንድ በቁም የማታሰገባ ፣ ከጥቂት ጭራሮዎች የተወነጋገረች ጎጆውን ጠላት ሲያቃጥልበት የተነሳ መሆኑን ያወቀ ባላገር ፣ አስቀድሞ ለፖሊስ ያስታወቀ እንደሆን ፣ ጎጆው ትጠበቅለታለች ። ይህም ያለጥርጥር ትልቅ ነገር ነው ! ደግሞ አንድ ከተወለደ ጀምሮ ምቾት ምን እንደሆን የማያውቅ ፣ እድሜ ልኩን በችግር ሲጠራጦት የሚኖር ባላገር ፣ ይህም ከኑሮ ተቆጥሮ ጠላቱ ሊገድለው የዛተበት እንደሆን ፣ ላገረገዥ አቤት ካለ፣ የዛተው እንዲቀጣ ፣ የተዛተበት እንዲጠበቅ ገዥ ያዝዝና ፣ ባላገሩ ያኑ የችግር ህይወቱን ይቀጥላል። ይህም ትልቅ ነገር ነው ! ብቻ ይህ ሁሉኮ ግራዝማች ፣ ይህ ዳኛው ፣ ፖሊሱ ፣ አገረ ገዥ ፣ እያረጉት የተባለው ሁሉ እውነት መሆኑ ያጠራጥራል እንጂ ፣ እውነት እንኳ ቢሆን ፣ ባቤቱታ የመጡት ባላገሮች ያኑ የችግር ኑሮዋቸውን እንዲቀጥሉ ፣ በዚያው በችግራቸው ውስጥ እንዳሉ ፣ የሚጠብቅ ነው እንጂ ፣ ኑሮዋቸውን አንድ ቅንጣት እንኳ የሚያሻሽል አደለም ! ” አሉ ጠብቁ ፣ መብሉን ትቶ ግራዝማችን ፊት ለፊት እያዩ ።

“ እንግዲህ . . . ‘ የኑሮ መሻሻል ’ የምትለውን አንተ ትነግረን እንደሆን እንጂ እኔ ፍራሳ ይ . . ሙት ከዚህ በላይ . . አላቅም ፣ ሀ - ሀ ሀ - ሀ - ሀ ” አሉ ግራዝማች ፣ እንደ ልማዳቸው አብረዋቸው ያሉት ራሳቸውን እስኪያማቸው ከባጥ በላይ እዩላቁ ። ውብቱም ለቆ ዝም አለ ፡

“ በጠቅላላው የህዝብ መሻሻል ማለትኮ ግራዝማች ፣ እንደሚያውቁት ህዝቡ ጤናማ እንዲሆንና ካሁኑ ረዘም ያለ እድሜ እንዲኖረው የታከመ እንደሆን ፣ የርሻ ፣ የንግድና የሌላ ስራውን በዘመናዊ ዘዴ ስርቶ

ከሁት የበለጠ ውጤት እንዲያገኝ የተማረ እንደሆን ፣ የስራውን ውጤት በደህና ዋጋ ወደሚሸጥበት ወስዶ ፣ ሸጦ ፣ ባገኘው ገንዘብ ደህና እንዲበላ ፣ ደህና እንዲለብስ ፣ በደህና ቤት እንዲኖር መገናኛ ያገኝ እንደሆን ነው ” አለ ጥላሁን ፤ በግራዝማችና በውብቱ መሀከል የነበረው ንግግር በቆመበት ሁኔታ የአሳብ መሸካከር የተፈጠረ ስለ መሰለው ፣ ንግግሩን ለማስረዘምና የቅርታውን ስሜት ለማስረሳት ያክል ።

@OLDBOOKSPDF

“ እኮ ታዲያ . . . መቸም መገናኛ ማለት መንገድ ነው ! መንገድ መቸም ለሁሉም አስፈላጊ ነው ። ህዝቡን መንገድ እንዳይሰራና . . . አዲስ ዘዴ እንዳይማር ማን ከለከለው ? ” አሉ ግራዝማች ።

“ አዳዲስ ዘዴ ለመማርኮ መሪና አስተማሪ ያስፈልጋል ! ያለመሪ ፣ ያላስተማሪና ያለ ረዳት ፣ ባላገር ብቻውን ምን ሊያደርግ ይችላል ? ምን አቅም አለው ? ” አለ ጥላሁን ።

“ የባላገርን አቅም እናንተ አታውቁም ! እኔ ልንገራችሁ ! ባባቶቻችን ጊዜ ፣ የባላገር ገባር ሜካ መንጥሮ ፣ አርሶ ፣ ዘርቶ ፣ አርሞ ፣ አጭዶ ወቅቶ ፣ በጌቶቹ ጎተራ አግብቶ ፣ ቤታቸውን ሰርቶ ፣ አጥራቸውን አጥሮ፣ በተረፈው ጊዜ ሰራሉ ካዘመረው ግብር ከፍሎ ፣ በዚያ ላይ የሚመራበትን የሰውም ይሁን የከብት ተስሪ ቀልቦ ፣ ይህን ሁሉ አድርጎ ደስብሎት ፣ ሳያጉረመርም ይኖር ነበር ! አሁን ይህ ሁሉ የለበትም ፤ ከዚህ ሁሉ ነጻ ሆኖዋል ! ታውቃላችሁ ? በዚያ ጊዜ ፣ የመኳንንት ሎሌ ልብሱን እያጸዳ ፣ ትጥቁን እያሳመረ ፣ መሳሪያውን እየወለወለ ፣ ጦርነት ሲሆን በሚታዘዝበት መዝመት ፣ ሰላም ሲሆን ጌታውን ማጀብ ነው እንጂ ሥራ ፣ ‘ እንዲች ’ እርጎ በጥፍሩ አይነካም ! ” አሉ ግራዝማች የግራ እውራና ጠቋዋሚ ጣቶቻቸውን ጥፍሮች አንድ ላይ አፋጭተው። “ ገረዶች እንኳዋ ” አሉ ቀጠሉና ። “ ገረዶች እንኳዋ ፣ እቤት ውስጥ እንጀራ ከመጋገር ፣ ወጥ ከመስራትና ጠጅ ከመጣል በቀር የውጪን ሥራ ሁሉ ገባር ነበር የሚሰራው ! ታዲያ ይህን ሁሉ ያደርግ የነበረው ፣ “ ለራሱ ጥቅም መንገድ ለመስራት አቅም የለውም ትሉኛላችሁ ! ህ! ባላገር ካልለገመ ፣ ልልገም ካለም . . ልክ የሚያገባ ፣ ብርቱ ከያዘው አቅሙም ሆነ ሀብቱ ተገዞቆ አያልቅም ! ከራስ ጠጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ አቅምና ሀብት ብቻ ነው ! ” ሲሉ ሳቅ ሆነ ። ወዲያው ራት አለቀና ሰሀንም ፣ ትርፍራፊው እንጀራም ፣ ከዩፊቱ ተነስቶ ስንና ብርት የያዘ አሽከር ከግራዝማች ጀምሮ ሁሉንም እየዞረ ካስታጠበ በሁዋላ ፣ መጠጥ መጠጣቱ በገፍ ቀጥሎ አዝማሪው ፣ እድማሱ ረዳ አደግድጎ፣ መሰንቆውን በግራ እቅፉ አቅፎ ፣ መግረፊያውን በቀኝ እጁ ይዞ ገባና ለጥ

@OLDBOOKSPDF

ብሎ እጅ ነስቶ ፣ ቅንቱን ለማስተካከልና እድማሞችን ለማስጠንቀቅ፣ በቀጭን ፣ በወፍራምና በመሀከለኛ ድምጽ እየዝዘዘ ጨዝ ፣ ጨዝ ፣ ጭዝ ማድረግ ጀመረ ።

ግራዝማች ጀግንነታቸውንና ለጋስነታቸውን ብዙ ሰው ባለበት ካገማሪ ፣ ከዘፋኝና ካቅራሪ አፍ መስማትና ማሰማት አጥብቀው ስለሚ ወዱ ፣ ያንለትም አዝማሪው እድማሙና አቅራሪው ጉልላት ቀፈፈ ፣ ግብር ምሳሽ ሆኖ እስኪጠሩ አጓራሽ ራታቸውን በልተው ፣ መጠጥ በመ ጠት እዩጠጡ እንዲቆዩ ታዝዞላቸው ነበርና ፣ እድማሙ ከዚያ መምጣቱ ነው ።

“ እሰይ ና ወጻጁ እሰይ ናግ ምነው ” አለ እድማሙ ፣ አዝማሪ ዎች ሁልጊዜ ከውዳሴ በፊት የሚያስቀድሙትን መቅድም እየደጋገመ ።

“ እሰይ ና ወጻጁ ፣ እሰይ ናግ ምነው ፤
ደስ ይበለን ዛሬ ፣ የደስታ ምሺት ነው ።
የሸዋው ባላባት ፣ የወሎው ባላባት ፣ ዳኘቸው ፍሪሳ ፤
ጌታው የጌቶች ዘር ፣ ጌትነት የናቀ ፣ ኩራትን የረሳ ፤
ጌትነቱን ትቶ ፣ ለድሆች ሊያሳልፍ ፣ ያው ታጥቆ ተነሳ ።
ብትሰጠው ፣ ብትሰጠው ፣ ሁልጊዜ ብትሰጠው ፣ የማያልቅብህ ፤
አዞልህ ይሆናል ፣ ከብሩ ተራራ ፣ ብር እየተዛቀ ፣ እንዲቀርብልህ፤
ፈጥሮልህ ይሆናል ፣ የተሰወረ ምንጭ ፣ ጠጅ ያለማቋረጥ ፣ የሚ ያፈስልህ ፤
ፈጥሮልህ ይሆናል ፣ ሰንጋ እያደለበ ፣ የሚያቀርብልህ ፤
ዳኘቸው ፍሪሳ ፣ መቸም ለማርያም ልጅ ፣ ባለሙዋሉ ነህ ።
እብልቶ አጠጥቶ ፣ የራበው ሲጠግብ ፣ መስጠት የሚርበው ፤
ከዳኘቸው በቀር ፣ በየትም አላዩን ፣ ስማ ምስክር ነው ።
አባ ግፋው ዳኘ ፣ ጎራዴው ጎልድፎ ፣ ወዲያው አድፎበት ፤
ሳለው ፣ ወለወለው ፣ በፋሽስት አንገት ።
ዳኘቸው ጎራዴህ ፣ ባለብር ወለባ ፣ ሰገባው ከፋይ ፤
ጌትዬ ጎራዴህ ፣ ባለወርቅ ሽሆሮ ፣ የስራው ርቅት ፣ የሌለው መሳይ፤
እንደዚህ አጊጦ ፤

በወርቅ ተንቆጥቁጦ ፤
እንደ መልኩ ማማር ፣ ጠባዩ ባማረ ፤
ከመወደድ አልፎ ፣ ከቶም እንደ ጣኦት ፣ ይመለክ ነበረ ።
ዳሩ ምን ይሆናል ፤ ጠባዩ ክፉ ነው ፤ በመልኩ የሚያምኝ፣ በመልኩ አታላይ ፤

@OLDBOOKSPDF

ወዲያ ፈትሀ ማለው ፣ በመካከሉ ላይ ፤
ሰው ቆርጦሚበላ በዳደለምወይ ።
ዳኛቸው ትራዱህ ፣ ጥሩ ገበሬ ነው ፣ የሚያደንቀው ሁሉ ፤
እቀናው መንጥር ፣ ግሚራን በሙሉ ።
ፋሽስት ያልቻለውን ፣ ካይሮፕላን ጋራ ፤
ባሊያን ያልቻለውን ፣ ከመትረየስ ጋራ ፤ ካዳፍኖቸው ጋራ ፤
ዳኛቸውን ገጥሞ ፣ በሰናዲርና ፣ ባሮጌ ውጅግራ ፤
ለዘር አልተረፈም ፤ አለሩ ግሚራ ።
መንግስትን ሊወጋ ፣ ሸፍቶ ባባገር ፤
አባ ገፋው ዳኘ ፣ አቃጥሎ ጨረሰው ፣ አንድ ነፍስ ሳይቀር ፤
እግዜር እንዳገኘ ፣ አዳምና ሄዋን ፣ ካልፈጠረ በቀር ፤
ግሚራ ያስፈራል ፣ ምድረ በዳ ሆኖ ፣ ባዶውን እንዳይቀር ፤
ሴትም ወንዱም አልቀረም ፣ አልተረፈም ለዘር ።
አፀቱ እዚያ ግዶ ፣ የጣምች ከተማ ፣ የነበረው ደሮ ፤
አሁን በሉ ፈንቃ ፣ ይቃያል በሩቁ አመድ ተከምሮ ” ብሎ አድ
ማጡ ረዳ ፣ ገና ያሰናዳቸውን ግጥሞች ዘፍኖ ሳይጨርስና ፣ ከእንግዶችም
አንዳንዶቹ ግጥም ሳዝማሪው ለመስጠት ሲዘጋጁ ፣
“ እከ - ከ - ከ - ከ - ከ - ፤ እከ - ከ - ከ - ከ - ፤ ጃሎ መገን ፤ ኧረ ጃሎ
መገን ” እያለ ጉልባት ተፈሪ ከወጭ እያቅራራ ሲገባ ፣ አድማጩም
ሌሎችም እንደ መደንገጥ ብለው ዝም አሉ ። “ ጃሎ መገን ፣ ኧረ ጃሎ
መገን ” እለ ጉልባት ፣ ግጥሙ እስኪመጣለት መቅድሙን እየደጋገመ።
“ ልበሰው ፣ ልበሰው ፣ አባ ገፋው ዳኘ ፤ ሲሆን ተከናንቦ ፣ ያለዚ
ያም ልበሰው ፣ ልበሰው ፤
ለግን ይታጠቃል ፣ እንዳንተ ያለ ሰው ።
አባ ገፋው ዳኘ ፣ የሞቻው እንበሳ ፤
ተወ አትንኩት ፣ ሲነኩት አይወደም ፤ የነካኩት እንደሁ ፣ አጉራ
ርቶ ሲነሳ ፤
መሬት ትግባለች ትነዳለች ጢሳ - ጢሳ - ጢሳ ።
መጥቶ ነበር እዩተፎለለ ፣ እዩተጀነነ ፣ የፋሽስት ኮርማ ፤
ዳኛቸው በሞቻ ፣ እንበሳው በሞቻ ፣ መኖሩን ሳይሰማ ።
ሞኝ ነወይ ፣ ፋሽስት ሞኝ ነወይ ፣ ወይንስ ያበደ ፤
እንበሳ ሊያስወጋ ፣ ኮርማ የሰደደ ።
ኮርማ ቢሰበሰብ ፣ ምን ቁጥሩ ቢበዛ ፣ ቢሆን አንድ መንጋ ፤
ወዴት ታይቶ ያውቃል ፣ እንበሳን ሲወጋ ።

አባ ግፋው ዳኘ ፤ ገረማቸው ፤ ደንቃቸው ፤ ፋሽስቶችን እንኩዋ ጠላቶችህን ፤

@OLDBOOKSPDF

ድል ስትመታቸው ፡ በሰሩት ምንሽር ፡ በሰሩት አልቤን ።

ያው መጣልህ ፋሽስት መድፉን ፡ መትረዬሱን ፡ ቦምቡን ፡ ሁሉን አግተልትሎ ፤

አባ ግፋው ዳኘ ፡ ውጣ እንደ ልማድህ ፡ ተቀበለው ቶሎ ፤

መችም ጥፎዋቸዋል ፡ እግዚአብሄር ከጥንት ፤

መሳርያውን ላንተ ፤ እነሱን ላራዊት ።

መጥቶ ነበር ፋሽስት ፡ በመሳርያው ኮርቶ ፤

አባ ግፋው ዳኘ ፡ ልቡ ፡ ጀግንነት ፡ ወኔው ፡ ሁሉም አንተ ዘንዳ ፡
  መሆኑን ረስቶ ። ”

ጉልላት ሲያቅራራ ፡ ግራዝማች ወኔያቸው ተቀስቅሶ ፡ እንደ ተቀመጡ ከወዲህ ወዲያ ፡ ከወዲያ ወዲህ ፡ ሲንቆረጠጡ ቆይተው ፡ በመጨረሻ አላስችላቸው አለና “እየ ግሩም ! በል አንተ ! ” አሉ አቋርጠው ።

“ እየ ግሩም ፤ እየ ግሩም ! ” አለ ጉልላት እየደጋገመ ፡ ግራዝማች መድፊያውን እስኪሰጡት ።

“ እየ ግሩም ! የወንድ መመዘኛው ፡ ጠፋና ሚዛኑ ” አሉ ግራዝማች ።

“ እየ ግሩም ! የወንድ መመዘኛው ፡ ጠፋና ሚዛኑ ፤

ሴቶች የነበሩት ፡ አሁን ወንዶች ሆኑ ።

ተናደዱ ፡ ኧረ ተናደዱ ፡ ወንዶች ተቃጠሉ ፤

በወንድ ስም ፡ ወንድ ያደሰው ሁሉ ፡ አንተ በመባሉ ።

ደግ አደለም ፡ ደህና አደለም ፡ ያ ቀን መረሳቱ ፤

የወንድ ምርት ፡ ከወንድ ግርድ ፡ የተለዩበቱ ።

ኧረ ተው እንደያዘው ፡ እንዲሆን ፡ እንዲሆን ፤

ጉድ ይመጣል ፡ ጉድ ይፈላል ፡ ድንገት ይመጣና ፡ ያ የተረሳ ቀን ” ሲል ጉልላት ፡ “ቡርርርር . . . አካኪ ዘራፍ ! ” አለ ጣሰው ። ወለባ የሚባለው ፡ የግራዝማች አሽከር አቋቋርጦ ፡ እሱም እንደ ጌታው የተቀሰቀሰ ወኔውን መግታት አቅቶት ።

ጣሰው ጠመንጃውን ዘቅዝቆ ይዞ ፡ ወደፊትና ወደሁዋላ እያወናጨፈ ፡ ራሱን እንደ ባላውሌ እያንዘረዘረ ፡ “ቡርር . . . አካኪ ዘራፍ! ቡርርር . . . አካኪ ዘራፍ !” እያለ ገባና አንድ ጉልበቱን አንበርከኮ

ሌላ እግሩን ሸብረክ @OLDBOOKSPDF ፣ ፍከራውን ሲያንደቀድቀው ፤ ሁሉም ፤ ግራዝማች ጭምር ፤ አፋቸውን ከፍተው ይመለከቱት ጀመር።

"ቡርርር . . . አካኪ ዘራፍ ፤
"አካኪ ዘራፍ ! ጀውሳው ጣሰው !
እምቢተኛው ጣሰው !
እምቢ ! እምቢ ለራብ ፤ እምቢ ለጥማት !
እምቢ ! እምቢ ለመም ፤ እምቢ ለሞት !
እምቢ ! እምቢ ለሰማይ ፤ እምቢ ለመሬት !
እምቢ ! እምቢ ለሁሉ !
የግፋው ባሪያ ፤ የነበልባሉ !
የግፋው ባሪያ ጣሰው ወለባ !

አስር ለብቻው ፤ ማርኮ እሚገባ ! "እሰቴ እንደሁ መስክር" ሲል ወደ ግራዝማች አይኑን አፍጦ ፤ "እውነት ነው ፤ ምስክርህ ነኝ ጣሰው !" አሉ ግራዝማች ። ከዚያ ጣሰው ቀጠለ ።

"ጣሰው ፤ ጣሰው ፤ ጣሰው !
ለግዜር አይዳኝ ፤ እንኩዋንስ ለሰው !
ጣሰው ፤ ጣሰው ጣሳቸው !
ለጠላቶቼ ፤ ቅዣት ሆናቸው !
ጣሰው የግፋው ውሻ !
ከግፋው በቀር ፤ ከጌታው በቀር ፤ የለው መድረሻ !
አሳዶ ገዳይ ዋሻ ለዋሻ !"

አለና ጣሰው ከተንበረከከበት ተነስቶ ቆሞ ፤ ከውስጥ ግለቱ የተነሳ ላቡ ከግንባሩ ዘቅዝቆ እዬተንጠቀጠቀ ፤ እንዲያ ካለ ፍከራ በሁዋላ እንደ ተለመደው ፤ ለጌታው ያለውን ታማኝነት በለዘብታ ይገልጽ ጀመር ።

"እኔ አሽከርህ" አለ ጣሰው ። "እኔ አሽከርህ ፤ እኔ ያንተ አሽከር ፤

ያን ክፉ ቀን እግዜር መልሶ አያምጣው እንጂ ፤ ካመጣው ያው አብረን ነን ! በመከራ አብረን ፤ በደስታ አብረን ፤ በህይወት አብረን ፤ በሞት አብረን ፤

ሁልጊዜ አብረን !

እንኩዋን ወደ ሞት ፤ አያደርገውም እንጂ ፤ ወደ ገሀነም የምትሄድ ብትሆን ፤ እኔ . . . ባሪያህ እንደማልለይህ ታውቃለህ !" ሲል እዚያ ያሉት ሁሉ ይሳቁ ጀመር ።

@OLDBOOKSPDF

“ሀ - ሁ- ሁ- ሆ! ሁ- ሆ! እውቃለሁ ጣሰው ፤ አውቃለሁ ! እያ ሰገቡህ እንደሆን እንጂ ፣ አንተስ ከኔ መለየት እንደማትፈልግ አው ቃለሁ ፤ በማብረጃ ጠጅ አምጣላት !” አሉ ግራዝማች ፣ አሳላፊውን፣ እሳቸውም እዩሳቁ ። ጣሰው ባራት - ፈጅ ማብረጃ ጠጁን ይዞ ፣ በዚያ ሁሉ የቤት ሰጦና እንግዳ ፊት ቆሞ ሲጠጣ ፣ የተሰማው ኩራት እጅግ ከፍ ያለ መሆኑ ከሁኔታው ይታይ ነበር ።

እውነትም ፣ ጣሰው ግራዝማች ገና ባስራ ዘጠኝ ይሁን በሀያ አመታቸው ሰው ገድለው ሲሸፍቱ ጀምሮ ፣ ተለይቶዋቸው የማያውቅ፣ “ያሽከር መጀመርያቸው ነው” ማለት ይቻላል ። ነገር ግን ፣ አገሬ-ገዥ ከሆኑ እንኳን ፣ ከሱ በሁዋላ ለገቡላቸው አሽከሮች ፣- ይነስ ይብዛ ፣ ደመወዝ ሲሰጡ ፣ እሱ ውራጃቸውን ለብሶ ፣ ፍርፋሪያቸውን በልቶ ፣ እንዲሁ ሲፎክር እዩተመሰገነና ጀግንነቱም ፣ ታማኝነቱም በጌታው እፍ እዩተነገረለት ፣ በሰው ፊት በማብረጃ ጠጅ መጠጣቱ ፣ መብ ቃት ብቻ ሳይሆን ፣ ከሁሉ በላይ የሆነ እስመስሎ ፣ አኩርቶት ይኖ ራል ። ይህን ፣ የፈቃዱ ጌታ እስከ ሆነ ድረስ ፣ ለምንም አይለው ጠው !

@OLDBOOKSPDF

## ምእራፍ ፲፮

## ቀዩ ጠማ

ወብቱ ፣ ለጥላሁን የገዛለትን አምስት ጋሻ መሬት ፣ ባሳዬ መብራቱ መረኑት አስረከበት ፣ ጥላሁንና ባለቤቱን ፣ ሶፊያን ከየኪ ሹማምት ጋር አስተዋውቆና በተለይ የወረዳው ገዥ ፣ ግራዝማች ዳኘ እንዲረዷቸው አደራ ብሎ ወደ ጎሬ ከተመለሰ በሁዋላ ፣ አሳዬም አለቃውን ሸኝቶ ወደ ስራው ስለ ተመለሰ ፣ አዲስ ጎጆ ወጦች ፣ ሶፊያና ጥላሁን ፣ እንዳዲስ ጎጆ ወጦች ሁሉ ፣ የትዳርን ትግል ፣ የኑሮን ጦርነት ፣ ብቻ ለብቻ ተጋጠሙት ።

ቡና ለቀማ ከታህሳስ መጨረሻ በፊት ስለማያልቅ ፣ እስከዚያ ድረስ የጥላሁን አይነተኛ ስራው ቡና ማስለቀም ነበር ። ጥዋት ባንድ ሰአት ተነስቶ ፣ ቡና ወደሚለቀምበት ይሄድና ፣ እስከ ሁለት ሰአት ለለቀማ የሚመጡትን ሰዎች እንዳመጣጣቸው ተራ ድሮ ፣ ለዩሀያ አምስቱ አንዳንድ አስለቃሚ መድቦ ፣ ካሰማራቸው በሁዋላ ፣ ሁለት ሰአት ላይ ቁርስ ሊያደርግ ወደ ቤቱ ይመለሳል ። ሶፊም የውሀው መቅጃ ሩቅ በመሆኑ ውሀ የሚቀዱላት ደንበኞች ከማበጀትዋ በቀር ፣ ሌላውን የቤት ስራ ሁሉ ፣ የትምህርት ፣ የህክምና ፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ የህዝብ ርዳታ ስራ እስክትጀምር ድረስ እስዋ ፣ ራስዋ ነበረች የምትሰራ ።

ጥላሁን ወዲያው የኪ እንደ ደረሰ ፣ ቡናውን ሲሰርቁ ተይዘው የመጡትን ሰላሳ ሰዎች ሹማምቱ ፣ "ይገረፉ ፤ ይታሰሩ" ሲሉ ፣ እሱ ቡናውን አስቀርቶ ፣ ለሰዎቹ የለቀሙበትን ዋጋ ከፍሎ ማሰናበቱና ፣ ከዚያም ቀጥሎ እዳ መክፈል አቅቶዋቸው ወህኒ ቤት የታሰሩትን ሰዎች ሁሉ እዳቸውን አስቀድሞ እሱ ከፍሎ ፣ በቡና ለቀማ ስራ እንዲከፍሉት ማስፈታቱ ፣ እሱንና ሶፊን ከየኪና ካካባቢው ህዝብ ጋር ደህና አድርገው ስላስተዋወቁዋቸው ፣ በንግዶች ሊደርስ የሚችለው ችግር ሁሉ በነሱ አልደረሰባቸውም ።

አንድ ቀን ጥዋት ፣ ጥላሁን እንደ ተለመደው ቡና ለቃሚዎችን ካስለቃሚዎቻቸው ጋር በስራቸው አሰማርቶ ሲመለስ ፣ ሶፊያ ቁርሳቸውን እቤት የተጋገረ ዳቦ ፣ አይብና ማር ፣ የተጠበሰ እንቁላል ፣

@OLDBOOKSPDF

ከቡናና ከወተት ጋር ፍትፍ አስናድታ ፣ ሁለቱም በጠረጴዛው ላይ አስ ልፋ ፣ እርስፕ ከባልዋ ፊት ለፊት ተቀመጠችና እዩበሉ ፣ እዩጠጡ ፣ ይጫወቱ ጀመር ።

"ዛሬስ እንዴት ነው ? ብዙ ለቃሚ አገኘህ ?" አለች ሶፊያ ።

"ግሩም ነው እንጂ ! ከትናንቱ እንኳንዋ የዛሬው ይበዛል ። ትና ንት መቶ አስራ ሁለት ሰው ነበር ፤ ዛሬ መቶ ስሳሳ ሰው መጣ" አለ ጥላሁን ።

"እውነትም ግሩም ነው ፤ እንዲህ ከሆነ ለቀማህን ቶሎ ሳትጨ ርስ አትቀርም ።"

"እውነትሽ ነው ፤ ቀደም ብዬ ያሳዬን ምክር ብሰማ ኖሮ ፣ እስ ካሁን እገባድድ ነበር ። አላዩ ፣ 'የዚህ አገር ሰው እንኳንዋን አንድ ብር ከሀያ አምስት ሳንቲም ፣ በቀን ሁለት ብር ብትከፍለው ፣ እሱን ትቶ ንፍርና ቦርዴ ወዳለበት ነውና የሚሄደው ፣ ገንዘቡን ትተህ ወይም . . .ቀንስ አድርገህ ፣ ንፍርና ቦርዴ በርከት አድርገህ እያሰናዳህ ብታ ቀርብ ይሻላል' ብሎኝ ነበር ። ነገር ግን ሰው . . . ለሶስትና ላራት ቀን የሚበቃ ምግብ ሊገዛበት የሚችለውን ፣ ብር ከሀያ አምስት ሳን ቲም ትቶ ፣ አንድ ጊዜ ብቻ ሆዱን 'ለመሙላት ንፍርና ቦርዴ ፍለጋ ይሄዳል' ብዬ ካሳቤ አላገባሁትም ነበር !"

"የራበው ሰው . . . 'ነገ ነጭ በመረቅና ሥጋ እሰጥሀለሁ' ከሚ ሉት አሁን 'ቆሎ እንካ' ቢሉት የሚመርጥ መሆኑን አታውቅም ማለት ነው ?"

"እኔኮ ገንዘባቸውን 'ነገ እሰጣቸሁዋለሁ' ብዬ አላውቅም ፤ ሲሰሩ ውለው ማታ ከፍዬ ነው የማሰናብታቸው !"

"አንተስ አዎን ፤ ገንዘባቸውን በለቱ ትሰጣቸዋለህ ፤ ነገር ግን እነሱ በሰጠሀቸው ገንዘብ የሚበሉትን የሚሸምቱ በገበያ ቀን ብቻ ስለሆነ ፣ ገና ሶስት አራት ቀን ገበያ መጠበቅ ይኖርባቸዋል እኮ !"

"እሆ . . . ! እውነትሽ ነው ፤ ይህ አልታዩኝም ነበር ፤ ለካ ለብዙ ቀን ከሚሆን ገንዘብ ላንድ ጊዜ ብቻ የሚሆን ንፍር የሚያስመርጣ ቸው አለማወቅ አይደለም ፤ ራብ ነው !" አለ ጥላሁን ፣ መግላቷን ትቶ በቅርታ መልክ ግራውን ሽቅብ ሲመለከት ትንሽ ቆይቶ ።

"እ . . . ! በቃህ እንግዲህ ፤ አሁን ቁርስህን ብላ ። ባለፈ ራባ ቸው መቆርቆርህ ይቅርና ከንግዲህ ርዳቸው !"

"እኔ የምረዳቸው ስንት መብሉሽ ? ባገሩ ህዝብ መጠን ሲታይ ከፅ ፕር የማይገቡ ፣ ጥቂት ናቸውኮ !"

@OLDBOOKSPDF

"ከንግዲህ ወዲያ ፣ አንተ ብቻ ሠራተኛ የምትከፍለውን ከፋይ እንተ ብቻ አትሆንምኮ ፤ ጥላዬ ፡ ከንግዲህ ወዲያ ፣ አሰሪ ሁሉ ለቀን ሰራተኛ አንድ ብር ከሀያ አምስት ሳንቲም ከምሳ ጋር ፡ ከንፍሮና ከቦርዴ ጋር ሊከፍል ፡ ያለዚያ ሰራተኛ ላያገኝ ነው ! ስለዚህ እንዲህ ያለ ዋጋ . . . በመቅደድህ ፡ ዛሬ አንተ ዘንድ የሚሰሩትን ጥቂት ብቻ ለይምሰልህ የረዳህ ፤ እዚህ አካባቢ ያሉትን ሰራተኞች ሁሉ ነው ።"

"አሳዩም እንዲህ አለኝ" አለ ጥላሁን ፣ የቅርታ ፈገግታ ፈገግ ብሎ ።

"እንዴት ?"

"ከንግዲህ ወዲያ ፡ በንፍሮና በቦርዴ ብቻ ፡ የለቀማ ሆነ ያረ ምና የምንጣሮ ስራ የሚሰሩልን ሰራተኛ ላናገኝ ነው ፤ ወይ እንዳንተ ፣ ገንዘብ ጭምር መክፈል ፣ ያለዚያ ሁኛችን ሜካ ሰብሶ እንዲተር መተው ፣ ከሁለት አንዱን መምረጥ ሊኖርብን ነው" አለ ።

"ለመሆኑ አሁን አንተ የምትከፍለውን አሰሪው ሁሉ ቢከፍል አያዋጣውም ? ያስንዳዋል ማለት ነው ?"

"በጭራሽ አያስጎዳም ። እናሽ ! አሁን እኛ የምንከፍለው አንድ ቁንጣ ፡ ማለት አርባ ኪሎ ያክል ለቅሞ ሲመጣ ፡ ብር ከሀያ አም ስት ሳንቲም ከንፍሮና ከቦርዴ ጋር ነው ። እንግዲህ ገንዘቡና ምግቡ ባንድ ላይ ካንድ ብር ካምሳ እስከ አንድ ብር ከስድሳ ቢገመት . . . አርባ ኪሎ ቡና ለቅሞ ለሚያመጣ ሰራተኛ በጣም ፣ በጣም ያንሰው እንደሆን እንጂ መች ይበዛል ?"

"ያማ . . . ወጪውኮ ማስለቀምያ ብቻ አደለም !"

"አደለም ። ምንጣሮ ፣ አረም ፡ ግብር ፡ ሌላ ሌላም አለ ። ይሁን እንጂ ፣ ለዚህ ሁሉ የማስለቀምያውን ወጪ አራት ጊዜ ብታበዢው ከስድስት ብር አይበልጥም ! ታዲያ አርባው ኪሎ ቡና ሲቆሸር የጀ ንፈሉን ሲሶ ያክል ስለሚሆን ፣ ቅሽሩ አስራ ሶስት ኪሎ ያክል ይሆ ናል ማለት ነው ። እንግዴህ ፣ እሱን በጣም በርካሽ ፡ ማለት ኪሎ ውን በብር ሸጠሽ ወጪውን ሁሉ ከቀነስሽ በሁዋላ ፣ ሰባት ብር ይተ ርፍሻል ማለትኮ ነው !"

"እግዜአ . . . ! ምን ጉድ ነው እባክህ ? ታዲያ እሳቤ የተቆረቆ ረው . . . 'ለምን እንዲሁ በብላሽ . . . እንዲሁ በከንቱ አላሰራሁ' ብሎ ነው ?" አለች ሶፊያ ፣ ትንሽ እንደ መቆጣት ብላ ።

@OLDBOOKSPDF

“የለም ፤” አለ ጥላሁን ፤ ምፀቱ ስትቆጣ አይቶ ፈገግ እንደማለት ብሎ ። “የለም ፤ ወደ ፊት አሰሪዎች ሁሉ ፣ እንደኔ በምግብ ላይ ገንዘብ ጨምረው ካልከፈሉ ፣ ሰራተኛ የማያገኙ መሆናቸውን በጠቅላላ እነጋገር መግለጹ ነው እንጂ ፤ በራሱ በኩልስ በጣም ነው ደስ ያለው ! አሳዬ በጣም ጥሩ ሰውኮ ነው ፤ ሰፊ ! ምናልባት . . . አሳቡን በስራ ለመግለጽ ፣ ባሰራር ተርጉሞ ለማሳየት ፤ ድፍረት ያገ ሰው እንደሆን እንጂ ፤ ጥሩ አሳብ ያለው ሰው ነው ። ታውቂያለሽ ፣ እዚህ አገር በትንሽ ዋጋ ፣ ጋሻው ባምስት ባምስት ብር የተሸጠው የመንግስት መሬት ሁሉ በጁ ሲገኝ ፤ እሱ ካንድ ጋሻ በላይ የለውም ፤ ያውም ፤ “አንድ ጋሻ መሬት የገዛሁ ከጅማ የርሻ ትምህርት ቤት ተመርቄ የወጣሁ በለሆንሁ ፤ ለቡና ተክል ዘመናዊ ያሰራር ዘዴ ባገሬው እስተምርበታለሁ ብዬ ነው እንጂ አልገዛም ነበር” አለኝ ።

“እ . . . እኔኮ ‘ከንግዲህ በንፍሮና በቦርዴ ብቻ ማሰራት ቀረብን አለ’ ስትል ጊዜ ፣ ይህ አስተያየት የራሱ መሰለኝ ፣ ከመጣን ጀምሮ ሲናገርም ፣ ሲሰራም ከተመለከትሁት ጋር የማይስማማ ስለሆነ ገርሞኝ ነው ! ”

“የለም ፤ እግዚአብሄር ካዘለቀለት ያልንደፈ ፤ ጥሩ አስተያየት ያለው ሰው ነው ! በቅጡ ለማያውቀው ሰው ፣ ራሱን ከተመቸው ለማንም የማያስብ ፣ ግዴለሽ ፣ ሊመስል ይችላል ፤ ነገር ግን አይደለም ። ይልቅ አሁን እንዳልሁሽ ትንሽ ፍራት ያለው ይመስለኛል ። በተረፈ . . . በቁም ነገር ሲያነጋግርሽ ንግግሩ ጠርዝ የወጋ ፣ ያስተዋይ ሰው ንግግር ነው ። በቀድሞ ውብቱን ሸኝተን ስንመለስ ፣ ስለ ውበቱ ሀብት አንስተን ፤ ‘ ሀብት ሲበዛ ከሚያገለግልበት ፣ “አገልግሉኝ የሚልበት’ ጊዜ ይበልጣል ፤ በሀብታቸው ተገልግለው ፣ ደስ ብሎዋቸው የሚኖሩ ፤ በቅላሉ ሊቆጣጠሩት የሚችሉ ፣ መጠነኛ ሀብት ያላቸው ናቸው ። አሁን ውበቱ የሀብቱ አገልጋይ ወደ መሆኑ ደርሶዋል” ሲል ገረመኝ ።

“እኔም . . . ምንም እንኳ ካሳዬ ጋር የተዋወቅንበት ጊዜ አጭር ቢሆን ፣ በዚህ አጭር ጊዜ የሰጠኝ ስሜት ፤ ልክ አሁን አንተ እንዳልኸው ነው ። ነገር ግን ስለ ውበቱ . . . እንጃ ! አንተም ፣ አሳዬም ‘ተለውጦዋል’ እያላችሁ የምታዝኑበት . . . ልክ አይመስለኝም!”

“ምን እናድርግ ፤ የሚናገረውንና የሚያደርገውን አይተሻል ! መቸስ ሰው በሚናገረውና በሚሰራው ካልሆነ በምን ይገመታል ?”

@OLDBOOKSPDF

"እውነትህ ነው ፤ ውብቱ ሲናገር ፡ 'ድሀና ደካማ ሊኖሩበት ባልተፈቀደላቸው አለም ድንገት ፡ ከየትም ወርደው የተገኙ ተባዮች ፤ ወይም ወረርሽኞች ስለሆኑ ፡ ከመርዳት ይልቅ ማጥፋት የሚያጸድቅ' አስመስሎ ሲናገር ፡ ለሀብታሞችና ለብርቱዎች ምሉ የቆመ ጠበቃ ይመስላል ። ነገር ግን እንዲህ ያለው አነጋገር ፡ ያ ፡ አዲስ አበባ የነገርኸኝ ሁሉ ችግር ስለ ደረሰበት የብስጭት ነው ? ወይስ የምንት! አሽሙር ነው ! ወይስ ምር ! 'እውነቱ ይህ ነው' ለማለት በጣም ያስ ቸግራልኮ ጥላዬ ! ካንተ የተለዩ አሳብ ይዞ ስለ ተከራከረህ የተለወጠ መስሎህ ያን . . . በሱ ላይ የነበረህን ታላቅ ተስፋና እምነት አት ለውጥ ፤ እስቲ ትንሽ ቆይ እባክህ ! ምናልባት . . . በክርክር መልክ ወደ ፊት ሲገጥመን የሚችለውን ልዩ ልዩ ችግር ማመልከቱ ይሆ ናል !"

"እንዳጫሽ ባደረገው እንዴት ጥሩ ነበር ! ግን አደለም ፤ ውብቱ ተለውጦዋል" አለ ጥላሁን ፡ ምኞቱ ስለ ውብቱ ስትናገር አፉን ከፍቶ አይን አይንዋን ሲመለከት ቆዩና ። ከዚያ ከጠረጴዛው ባሻገር ባንጻርዋ ከተቀመጠበት ተነስቶ በጎንዋ ተቀመጠና ፡ "ወንበሩ ይቆረ ቁርሻል ፤ እዚህ ተቀመጭ" አለ ጭኑን እዮጠሩ ። ሶፊያ እንደ ታዘዘ ችው እጭኑ ላይ ተቀምጣ ፡ ያልታዘዘቸውን ፡ በሁለት እጆችዋ ጠጉሩን ወደሁዋላ ማለዘብ ስትጀምር ፡ አይኖቿ ቀና ብለው ካይኖችዋተገናኙ ፤ ከዚያ ከንፈሮቹ ከከንፈሮችዋ !

ትንፋሽ እስኪያጥራቸው ተሳስመው ፡ ጉንጮችዋን ፊት ለፊት በሁለት እጆቹ እንደ ያዘ ፡ አይኖቿን ከተከደኑበት ሲገልጽ እሱን በሰዋ አይን ውስጥ አዩና "መስታዋቴ ! ጉድለቴን ፤ እድፍ ጉድፌን ሁሉ የምታሳይኝ የኔ ጥሩ መስታዋት !" አለ በደካማ ድምጽ ። ከዚያ ደግሞ እንደገና አፍ ላፍ ተያይዘው ፡ አይኖቻቸውን ከድነው በፍቅር ባህር ጠለቁ ። እንዲያ እንዳሉ ፡ እንዲያ አፍ ላፍ ተያይዘው ፡ አይኖ ቻቸውን ከድነው በፍቅር ባህር እንደ ጠለቁ ፡ ባላምባራስ ጉደታ ራሳ እደጅ ቆመው እየመላለሱ ቢጣሩ የሚሰማቸው አጡ ።

" ኸረ እንዴት አደራችሁ ? ቤቶች ፤ ሰው የለም ? " አሉ ባላ ምባራስ ፤ በመጨረሻ ፡ "ሰው የለም" ብለው ለመሄድ እያመነቱ ። ያንጊዜ ብቻ ባልና ሚስት ሰሙና ፡ ሶፍያ ከባልዋ ጭን ተነስታ ፤ ቁርስ ያደረጉበትን እቃ ሰብስባ ፡ ወደ ሁለተኛው ክፍል ስትገባ ፤ ጥላሁን እንግዳውን ለማየት ወጣና ፡

" ጤና ይስጥልኝ አባቴ ፤ እሴን ነው የሚፈልጉ ? " አለ ።

@OLDBOOKSPDF

" አቶ ጥላሁን ግስት አንተ ነህ ? " አሉ ባላምባራስ ጉደታ ።

" አዎን ፤ እኔ ነኝ ።"

" እንዴት አደርህ ልጄ ? አንተ ቤት መጥቼ ፣ አንተን እንጂ ማንን እፈልግ መሰለህ ? እኔ ባላምባራስ ጉደታ ራሳ እባላለሁ ።"

" ታዲያ . . ወደ ቤት አይገቡም ? የማይቸኩሉ እንደሆነ ይግቡ እባክዎ ።"

" አንተ ወደ ስራ የማትቸኩል ከሆንህ እኔስ አልቸኩልም ፤ ስመተዋወቅና ወዲያውም አንዳንድ የምነግርህ ጉዳዮች ስላሉኝ . . ልነግርህ ነው የመጣሁ ።"

" እንግዲያስ እባክዎ ይግቡ አባቴ " ብሎ ጥላሁን ፣ መንገድ ለመምራት ቀድሞ ሲገባ ፣ ባላምባራስ ጉደታ ተከትለውት ገቡና ባላ ያቸው ወንበር ላይ ተቀመጡ ፤ እሱም አንድ ወንበር ጎተት አድርጎ ፣ ባንጻራቸው ተቀመጠ ።

ያገሩ ሰው ፣ " ቆዩ ጣማ " የሚላቸው ባላምባራስ ጉደታ ራሳ ፣ ዘለግ ብለው ፣ አካላቸውን ስጋ ያልከበደው ፣ ከድሚ ይሁን ከልማድ ፣ ከትከሻ ቸው ትንሽ ሰግደድ ያሉ ፣ ጠጉራቸው ከመብዛቱና ከመንጣቱ የተነሳ ነድፈው በራሳቸው ላይ የከመሩት ጥጥ የሚመስል ፣ ጢማቸው የደሰደሰ ያለው ፣ የሽማግሌ ፊታቸውን እንዳይሸሽግ ፣ መስመር ጠብቆው በጥን ቃቄ የከረፉት ፣ የንጭ ሀር ክፈፍ የሚመስል ፣ ሰባ አመት ያክል የሚሆናቸው ፣ ውብ ሽማግሌ ናቸው ። የሚናገሩት ደስ የሚያሰኝ ፣ ወይም የሚያሳዝን እንደ መሆኑ ፊታቸውን ፈካ ፣ ኮስተር ፣ እያደረጉ ሲናገሩ ፣ በንግግራቸው ፣ ባይኖቻቸውና በከንፈሮቻቸው የሚታዩው እንቅስቃሴና ጠቅላላ ንቃታቸው ፣ በተፈጥሮዎቻቸው ብልህ መሆናቸውን ያመለክታሉ። ጉዋደኝነታቸው ከጣሞት ጋር ስለሆነና ፣ የጣሞችን ቋዋንቋዋም ፣ ባህ ልም ፣ ደህና አድርገው ስለሚያውቁ ፣ ያገሩ ሰው ፣ " ቆዩ ጣማ " የሚባል ስም አውቆላቸዋል ። ያንለት ነጭ ተፈሪ ቅድ ሱሪና እጀጠባብ ፣ በዚያ ላይ ካኪ ኮት ለብሰው ፣ ባላረንጉዋዴ ጥለት ነጭ ኩታ ደርበው ፣ በጣም አምሮባቸው ነበር ።

" እኛ ቁርስ አድርገን ስንነሳ ነው የመጡ ! ቡና ይምጣልዎ አባቴ " አለ ጥላሁን ፣ እንግዳውን ።

" እሺ ልጄ ፤ የጥዋት ቡና አይገፋም !" አሉ ባላምባራስ ፣ ፈገግ ብለው ።

" ከወተት ጋር ወይስ . . . ብቻውን ? "

@OLDBOOKSPDF

“ ጋባ ወተት ይወዳል ፤ እኔም ጋባ ስፈህንህ ወተት እወዳለሁና ከወተት ጋር ይሁንልኝ ፣ ልጄ ! ” አሉ ባላምባራስ ፣ አሁንም በፈገግታ ።

ከዚያ ጥላሁን ሶፊያ ወዳለችበት ሂዶ ቡና ከወተት ጋር ፣ ዳቦ ጭምር እንድታመጣላቸው ነግሮዋት ተመለሰና አብሮዋቸው ተቀመጠ ።

“ ስሜን ቅድም ነገርሁህ መሰለኝ ፤ ባላምባራስ ጉዱታ ራጎ እባላ ለሁ ። የኪና በዙሪያው የሚታዬውን ጋራ–መለስ አገር ሲያሳዩ እጃቸውን ዘርግተው በራሳቸው ዙሪያ እያዞሩ ፤ “አባቴ ቀኛዝማች ራጎ ” አሉ ቀጠ ሉና ። “ አባቴ ፣ ቀኛዝማች ራጎ እንዲያውም . . . በራስ ተሰማ ጊዜ ፣ ግዛቱ ጭምር ተሰጥቶዋቸው አቅልጠው ገዝተውታል ! ታዲያ እሳቸው ሲሞቱ ሁሉም ቀረ ! ሁሉም ከሳቸው ጋር ሞተ ! ብቻ ግዴለም እያላ ዝንም ! ” አሉ ባላምባራስ ፣ ያባታቸው ጌትነትና የሳቸው ድህነት ባንድ ላይ የቀሰቀሱትን ሐዘን በውሸት ፈገግታ ለመሸፈን እዬተጣጣሩ።

“ ትልቅ ሰው ነበሩ ልጄ ! ” አሉ ፣ ፈገግ እንዳሉ ቀና ብለው ጥላሁንን እያዩ ። “ ሰው ሁሉ እንደ ታቦት አክብሮ ፣ ፈርቶ ፣ የሚ ወዳቸው ፣ ትልቅ ሰው ነበሩ ፤ በመቶ ሃያ አመታቸው ሞቱ ። ”

“ ኦ . . . ! መ ቶ ሃያ አመት ጥሩ እድሜ ነው ፤ መቼ ሞቱ?”

“ አ . . ! የሞቱበት ጊዜስ ሩቅ ነው ፤ ቢጠሩት አይሰማም !’

“ ታዲያ አሁን . . ግዛቱ ቢቀርብዎም የዚህ ሁሉ መሬት ባላባት ከሆኑ ፣ በሲሶ ያገኙት ብዙ ጋሻ መሬት አለዎ ማለት ነዎ ! ”

“ ብዙ ጋሻ መሬት ? አይ ልጄ ! አንዲት ጋሻ እዚህ እከተማው ዳር ተርፋኝ ነበር ፤ እሱዋም ሄደች ! ብቻ . . ትሂድ ምናባትዋ ፤ እላ ዝንም ! ”

“ ማን ወሰዳት ? ” አለ ጥላሁን ፣ በባላምባራስ ሁኔታ እንደ መገረም ብሎ ።

“ አይ ልጄ ! ዛሬ እሱን ልነግርህ አልመጣሁም ፤ የሱ ታሪክ በጣም ረዢም ፣ አውሎ የሚያሳድር ስለሆነ በሌላ ጊዜ እነግርሃ ለሁ ” ሲሉ ፣ ሶፊያ ፣ ባልዋ እንደ ነገራት ዳቦና ቡና ከወተት ጋር ይዛ መጣች ። ሶፊያ የለበሰችው ልብስ ፣ እንደ ባልዋ ረዥም ካኪ ሱሪና እጅጌው ቁምጣ የሆነ ሸሚዝ ነው ። ጠጉርዋን እሳጥራ ቆርጣ ፣ ባላምባራስ በሴቶች ላይ የሚያውቁት ያንገት ማተብ ፣ ወይም

@OLDBOOKSPDF

ድሪ ፣ የጆሮ ጉትቻ ፣ የክንድ አንባር ፣ ወይም ሌላ ጌጣጌጥ አይታይ ባትም ። ያመጣችውን ቁርስ በጠረጴዛው ላይ አስቀምጣ ፣ ቡናውን አንስ ፣ ወተቱን በዛ አድርጋ ስትቀዳላቸው ፣ ዝም ብለው ከግር እስከ ራሷ ሲመለከትዋት ቆዩ ። ከዚያ ስኩዋር በመንካ አውጥታ ቡናና ወተት በሞላው ስኒ ላይ እንደ ያዘች ፤

" ስንት ላድርግ ጌታ ፤ " አለች ።

" ሁለት መንካ አድርግልኝ ልጄ ፤ ሁለት መንካ ይበቃኛል " ሲሉ ሶፊ ላቅዋን እንደምንም ገትታ ፣ ሁለት መንካ ስኩዋር አድርጋ ላቸው ዘወር ብላ ሄደችና አባልዋ አጠገብ ተቀመጠች ።

" ዳቦው እንዳይበላሽ መልሰው ልጄ ፤ ጥዋት . . ትንሽ ቁርስ እቤት አድርጌያለሁ ፤ ቡና ግን ቢደጋገም ምንም አይደል " አሉ ባላምባራስ ። ሶፊያ አፍዋን ገጥማ ፣ ሳቅዋን ለማገድ እየታገለች ፣ ዳቦ የያዘውን ሰሀን ከባላምባራስ ፊት አንስታ እፊትዋ ስታስቀምጥ ፣ ጥላሁን በሳቅ መወጠርዋን አይቶ ፣ ደጋግመው ' አንተ ' ሲሉዋት ልብ አድርጎ አልሰማም ነበርና ፣ አፍሮ በቁጣ አይን ገላመጣት ። ባላምባ ራስ ግን ዳቦው ከፊታቸው እንደ ተነሳ ፣ ሶፊ ካንድ ወገን ሳቅ እዩከ ረኮራት ፣ ከሌላ ወገን እንዳትስቅ ባልዋ አይኑን አፍጦ እዩተቆጣት፣ የነበረችበትን ስቃይ ቀና ብለው ሳይመለከቱ ፣ ቡና በወተታቸውን ጠጥ ተው ሲጨርሱ ፣ አፋቸውን በጃቸው ጀርባ እዩጠራረጉ ያመሰግኑ ጀመር።

" እግዚአብሄር ይስጥልኝ ልጄ ፤ አዋይ አድባሩ ይቀበልህ ፤ ይቀ በላችሁ ። እንግዲህ አንተም ወደ ስራ ሳትቸኩል አትቀርምና ፣ የመ ጣሁበትን ጉዳይ ልንገርህና ልሂድ " አሉ ባላምባራስ ።

"እሺ አባቴ ይንገሩኝ " አለ ጥላሁን ። ነገር ግን ባላምባራስ አንድ ጊዜ ሶፊያን ፣ አንድ ጊዜ ጥላሁንን እያለዋወጡ እያዩ ዝም አሉ ።

" ምነው አባቴ ፤ የሰጉት ነገር አለ ? " አለ ጥላሁን ።

" የምሰጋበት ነገር እንኩዋ . . . የለም ። ነገር ግን ቢሆንም . . . ብቻህን ሳነጋግርህ ነውና የመጣሁ ፤ እሱ ልጂ ወደ ሌላ ቤቶ ዱን በወደድሁ ! "

" የቱ ልጅ አባቴ ? " አለ ጥላሁን ፣ ዘወር ብሎ ተመልክቶ እዚያ ግድም ምንም ልጅ ስላልነበረ ፣ ግራ እንደ መጋባት ብሎት ።

" እሱ ልጄ ! አንድ ጊዜ ወደ ሌላው ክፍል ሄዶ ቢቆይ አይቆ ዩምም ፤ ይቀየማል ? " አሉ የደሰደሰ ባለው ፈገግታቸው አገጫቸውን ወደ ሶፊያ አሹለው ። ያንጊዜ ሶፊያ አግዳው የቆዩችው ሳቅ አሸንፋ

@OLDBOOKSPDF

ትና ትንፈራፈር ጀመር ፤ ጥላሁንም ርሰዋን ተከትሎ ይስቅ ጀመር ። ባላምባራስ ፤ ግራ ገብቶዋቸው ፤ ዝም ብለው ባልና ሚሽቱን እዩተመለከቱ ፤ ምን ያክል የሚያስቅ ምን ነወር እንደ ሰሩ ራሳቸውን ሲጠይቁ ።

“ ሶፊያ ወንድ አደለችምኮ ! የኔ ባለቤት ናት ! ” አለ ጥላሁን ፤ ከሚሽቱ ጋር ሲስቅ ቆይቶ ። ከዚያ ባላምባራስ ትንሽ እንደ ማፈር አሉና እሳቸውም ይስቁ ጀመር ።

“ ወይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ! እንደ ዛሬ ጉድ ሁኜ አላውቅም ፤ እንደ ዛሬ ጉድ ተሰርቼ አላውቅም ፤ ራሳ ይሙት ! ምን እንዲህ አደረግሽኝ ልጄ ? ” አሉ ወዲያው ቆጥለው ።

“ ምን አደረግሁ ? ” አለች ሶፊያ ።

“ አሳሳትሽኝ ልጄ ፤ በጣም አሳሳትሽኝ ። እንደ ወንድ ሱሪና ሸሚዝ ለብሰሽ ፣ ማጉብና ድሪ ባንገትሽ ፤ ጉትቻ በጆሮሽ ሳታደርጊ ፣ ጠጉርሽን ቁንደላ ሳትሰሪ ፣ ወይም ጉተና ሳታደርጊ ሳይሽ ጊዜ ፤ ወንድ መሰልሽኝና ፣ ‘አንተ’ አልሁሽ ፤ ከዚህ የበለጠ መሳሳት አለ ? ”

“ ምንም አደል ፣ አልቀየምም ። ”

“የዛሬ ልጆች ፣ የዛሬ እመቤቶች የተማራችሁ ሆናችሁ ነው እንጂ ፣ የድሮዎች ቢሆኑማ ይቀየሙሉ ። ወንዱን ‘አንቺ’ ማለት ብርቱ ስድብ እንደ ሆነ ፣ ሴትዮን ‘አንተ’ ማለትም እንደ ስድብ የሚቆጠር ነው ።የድሮ ሴቶች ሲምሉ እንኳዋ “ ይህን ባደርግ ፣ ወይም ባላደርግ ፣ እውነት መቀነት በወገቤ አላዞርሁም ! ” ይላሉ ፤ “ እውነት ሴት አደለሁም ! ” ማለት ነው ። የዛሬዎቹ ግን . . ይል ቁንም ከላይ የምትመጡት ፣ ባህላችሁ : . ልዩ ነው ። “በይ እንግዲህ ልጄን ፣ ማለፊያዋን ወይዘሮ ፣ ‘አንተ’ ያልሁ ባላውቅ ነውና ማሪኝ ።”

“ እረ ! እረ እባክዎ ምንም አደል ” አለች ሶፊያ እዩሳቀች ።

“ እንኩዋንስ ልንቀዩም በጣም ነው ደስ ያለን አባቴ ። ሁለታችንም ይህን ያክል ስቀን አናውቅምኮ ! ” አለ ጥላሁንም ምሽቱን ተከትሎ ።

“ እሺ እንግዲህ ወደ መጣሁበት ጉዳይ ልመለስና ፣ ብትፈቅድልኝ . . ተነስቼ ልንገርህ ” አሉ ባላምባራስ ፣ ለመነሳት እዩሞከሩ ።

“ እረ በእግዚአብሄር አባቴ ፣ ምን ማለትዎ ነው ? ልጆችዎኮ ነን ! ‘ ስናገር ተነስታችሁ ስሙኝ ’ ማለትዎ እንደሆን እንጂ ፣ እንዲህ ያለው በጭራሽ አይታሰብም ! ” አለ ጥላሁን ፣ ሁለት እጆቹን ወደ ባላምባራስ ዘርግቶ እያማጠኑ ።

@OLDBOOKSPDF

"አደለም ልጄ ! እንደሱ ማለቴ አደለም ፤ ልቤ ሰላከበረህ ነው። መከበር በድግ፣ ወይም በሹመት ብቻ አደለም ፤ በስራ ትልቅነት ጭምር ነው ። ቂሶች ከከንድ ሙሉ በማይበልጥ ግምጃ ጠቅልለው የሚያዙት ታቦት የሚከበረው በሚሰራጡ የተቀደሰ ስራ ፣ በሚሰራጡ ታምር ነው እንጂ . . . በትልቅነቱ አደለም ! አንተም በሰራኸው የተቀደሰ ስራ ! በሰራኸው ታምር፣ልቤ ሰላከበረህ ነው እንጂ በድግሂህማ . . የትናንት ልጅ መሆንህን ይኸው አይ የለ ?"

"ምን ታምር ሰራሁ አባቴ?" አለ ጥላሁን ተገርሞ ።

"እናንተ ስትመጡ እኔ እዚህ አልነበርሁም ፤ ጊሜ እሚባል አገር ቤት ሰባለኝ ፣ እዚያ አምስት ወር ያክል ቆይቼ ገና ከትናንት ወዲያ ማታ ነው የመጣሁ ። ታዲያ . . እዚህ እንደ ደረስሁ ፣ ሊጠይቀኝ የመጣው ሁሉ ፣ በመንገድ ያገኘኝም ሁሉ የሚያወራ ያንተን የሚያስገርም ስራ፣ የሁለታችሁን ደግነት ነው ። በመጣህ ማግስት ይሁን ሳልበት. . ሰባ ይሁኑ አርባ ባላገሮች ቡናህን ሲለቅሙ ትይዘው ፣ እሹሞች ፊት ቀርበው ፣ ይታሰሩ ፣ ይገረፉ እያለ የተሰበሰበው ሁሉ ሲተች . . እንደገና አንተ፣ ባለሁበቱ ፣ በመቆጣት ፈንታ በማዘን ፣ ለለቃሙት ቡና ዋጋ ከፍለህ፣ አስለቅቀህ ፣ ሰደድሀቸው አሉኝ ! ሁለተኛ ፤ በዳ ታስረው ወህኒወን የሞሉትን ሰዎች ፣ እዳቸውን ከፍለህ አስፈትተህ ፣ አሁን ምባቸውንና ለመኖርያ የሚበቃቸውን እዬሰጠህ ፣ ደስ ብሎዋቸው ይሰራሉ አሉ።ከዚህ ሌላ አንተና ይህች እንደኔ የሚሰድባትን የምታባብል ባለቤትህ ፣ 'የታመመ ወዶት አለ ?' እያላችሁ ፣ በዬቤቱ እዬዞራችሁ ፣ ያላንድ ሳንቲም በሽተኞችን ስትፈውሱና ችግረኞችን ስትረዱ ትውላላችሁ አሉ! ልጄ፣ እንዲህ ያለ ግሩም ስራ ፣ እንዲህ ያለ ታምር የሚሰራ ፣ እስከ ዛሬ ፣ እን ኩዋንስ እዚህ ባይናችን ልናይ በሌላም አገር ፣ 'አለ' ሲሉ በጆሮዋችን ሰምተን አናውቅ! ይህን ሁሉ ስሰማ እጅግ ተገርሜ ፣ ባገሩ ሰው ስም መጥቶ ያመሰገነ ሰው እንዳለ ብጠይቅ ፣ 'የለም' ሰላሉኝ ፣ በዚህ አሳዋቂ ህዝብ ስም፣ 'እግዚአብሄር ይስጥህ ፣ እግዚአብሄር ለሁለታችሁም ይስጣችሁ' ለማለትና ወዳያውም ለመተዋወቅ ነው የመጣሁ ። እግዚአብሄር ለመልካሙ ስራችሁ እጥፍ ድርቡን ይክፈላችሁ" አሉ ባላምባራስ የእግ ዚአብሄርን ስም ሲጠሩ ፣ እሱ ወዳለበት ወደላይ እያዩ ።

"ስለ . . ስለ ተናገሩት ሁሉ እግዚአብሄር . . . ይስጥልን አባቴ " ብቻ . . . ብቻ አሁን ያሉትን ሁሉ . . አሁን ካሉት ሁሉ የሚበዛውን ያደረግነው ለራሳችን ጥቅም ስንል ነውኮ !" አለ ጥላሁን ፣ ባላምባራስ በተናገሩት ልቡ ተነክቶ የሚናገረው እዬተደናገረው።

@OLDBOOKSPDF

"እይ ፣ ልጄ... ! እናንተ ይህን ሁሉ ለሰው በመስራት ምን ጥቅም ታገኛላችሁ? ቢሆንስ .. ጥቅሙ ሳይነካል ሌላውን መጥቀም የሚወድ ዛሬ ይገኝ መሰለህ ? አይገኝም ! ሁሉም እኔ ብቻ ልጠቀም" ባይ ነው! ከዚህ ሌላ ምንም ካንተ ፣ ከተማርኸው ፣ እኔ ደንቆሮው ባላውቅ ፣ አገሬ ችንን ስለማወቀው ፣ ብትፈቅድልኝ .. አንድ ትንሽ ምክር ልስጥህ ። "አንድ አለቀምይ ፣ የከፋ ልብ መች ነው ጥልቅ አዘን የሚሰማው ? ቢሉት መልካም ሰሬና መልካም ሰሪ ያዩ እለት !" አለ "ይባላል ። ይህ ከፉ ሰው ፣ ይህ አገሬገዥያችን ፣ መልካም ሰሪና መልካም ሰሪ ደመኞቹ ናቸው ። አንድ ሰው በመልካም ስራው ሲመሰገን የሰማ እንደሆነ ፣ ያን ሰው ካላ ጠፋ እንቅልፍ አይወስደውም ! ስለዚህ ... በመልካም ስራህ ጉዳት እንዳይደርስብህ ፣ እኛም አይተን እንዳናዝን አለቱ. . እዮተጠንቀቅህ!"

"ግራዝማች ዳኘ ወዳጃችንኮ ናቸው ፣ አባቴ! "

"ነው! ማሰፊያ ፣ ማሰፊያ ፣ ወዳጅነታችሁን ያዝልቅልን ፣ ለናንተ ብቻ ሳይሆን ፣ እግዚአብሔር ለኛ ጭምር ሲል ወዳጅነታችሁን ያዝልቅልን ። ቢሆንም ፣ መጠንቀቁ ለማናቸውም ቢሆን አይከፋም ልጄ ። መቼም እስከ ዛሬ እንደምናወቀው ፣ ወዳጅነቱ ደህና አድርጎ አስኪያውቅና ፣ ወጥመዱን እንደሚይበልቅ አድርጎ ፣ አጥብቆ ፣ አስኪሰራ ነው! ከዚያ አልፎ አያውቅም! " አሉ ባላምባራስ ፍርጥም ብለው ።

"ራስዎ የሚያውቁት ግሰረኛ ኖሮዎ ነው እንዲህ የሚሉ? ወይስ በግምት ፣ ወይም እንዲሁ አሉባልታ በመሰማት ነው?" አለ ጥላሁን ።

"ምነው ልጄ? ራሴ የማውቀውን ይገፔ ነው እንጂ. . እንዴ ያለ ሽማግሌ ግምቱን ፣ 'ይሆናል' የሰማውን 'ይባላል' በማለት ፈንታ 'ነው' ብሎ ይናገራል? ካልቸኮልህ ፣ ምንም እንኩዋ የሱ ጉድ ተነግሮ ባያልቅ ፣ አንዳንዱን አሁን ልንገርህ "

"ግዴለም ሌላ ቀን ይነግሩናል " አለ ጥላሁን ።

"አስለቃሚዎች ካሉ ምን አስቸኮለህ ? ይንገሩን ጌታ " አለች ሶፊያ ።

"እሺ ደግ ፣ ይንገሩን " አለ ጥላሁንም ፣ ምንም እንኩዋ ግራዝማች ዳኘ ሲታሙ መስማቱ ቢቀፈው ፣ በሰው ፊት ሶፊን ባለመቃወም ።

"እሺ ልጆቼ " አሉ ባላምባራስ ጉዶታ ፣ እንገታቸውን ደፍተው ትንሽ ቆይተው ቀና አሉና ። "አንድ ደግ ሰው" አሉ ቀጥለው። "አንድ በበጎ ስራው ሰው ሁሉ የሚወደው የሚያመልከው ፣ እዚሁ አጠገባችን ፣ ቴፒ በምትባል ከተማ የሚኖር ፣ ሀብታም ሰው ነበር ። የዛሬ አስር አመት

@OLDBOOKSPDF

ግድም ፣ መሬት ረክሶ ስለነበረ ከመንግስትም ፣ ካንዳንድ ሰዎችም ፣ ብዙ ጋሻ መሬት መግዛቱን አገሬ ገዣችን ተመልክቶ ፣ "አውርሰኝ" አለው። ታዲያ ሰውዬው እንደልቡ ተናጋሪ መሳይ ነበርና ፣ በሰው ፊት ፣ "እርስ ዎን መቼ ወልጄዎ ነው የማወርስዎ ?" ሲል ጊዜ ፣ "ደፈርኸኝ" ብሎ፣ እቤቱ አስሮ እዩደበደበ ፣ ባሽከሮቹ ፊት የውርስ ወረቀት አስፈርሞ ለቀቀው ። ሰውዬው እንደ ተለቀቀ ፣ ጎሬ እዩተመላለሰ ፣ የክስ መጥሪያ እያመጣ እረፍት ስለነሳው ፣ አስገድሎ ሬሳውን እወንዝ ውስጥ ጥሎት እዚያ ተገኘ ። ሁዋላ ፣ ምን ሆነ መሰላችሁ ? መርማሪዎች መጥተው አገሬ ገዥው ቤት ተቀምጠው ፣ ድግሳቸውን ሲበሉ ሰንብቱና ፣ ሰው ዬው ከመገደሉ አንድ አመት ቀድሞ የሞተ ሰው ፣ "ገደለው" ብለው ባሰት እንዲመሰክሩ በገንዘብ የተገዙ ምስክሮች የሰጡትን ቃል ተቀብ ለው ተመለሱ ። ከዚያ በሁዋላ ዝም ዝም ተባለ ! ዛሬ ነፍሰ ገዳይም የገደለውን ሰው ርስት ወርሶ ተቀምጦዋል !

ሁለተኛ የዛሬ አምስት ይሁን ስድስት አመት አንድ የዳኜን ስም ብቻ ሳይሆን ስራውን ጭምር የሚያውቅ ፣ ጥሩ ዳኛ መጥቶ፣ አገሬ ገዥው ያለፍርድ ያሰራቸውን በፍርድ ፈትቶ እዩለቀቀ ፣ ያለፍርድ ርስቱን ለተ ቀማው እንዲለቀቅለት እዩፈረደ ፣ የሰውን ሁሉ ልብ ማረከው፤ ሰው ሁሉ "ለካ በሀይለኛም ሀይለኛ ፣ በዳኛም ዳኛ አለበት !" እያለ ከገዥው ወደሱ ተገለበጠ ። አንድ ቀን ፣ ሰው በተሰበሰበበት አስጠርቶ "ህዝብ አሳድ መህል" ብሎ ባሰት ወንጅሎ ፣ ሞት ቀረሽ አስደብድቦ ጣለው ። ከዚያ ሲድን ፣ አመት ሙሉ በጎሬና በዚህ መሀከል መጥሪያ የሚሉት ነገር አለ ! እሱን እዩያዘ ቢመላለስ ፣ ገንዘቡንና ጉልበቱን ከመጨረስ በቀር ሌላ ጥቅም የማያገኝ መሆኑን ሲረዳ ፣ ተስፋ ቆርጦ ፣ ከስራም ወጥቶ ቀረ ። ከሱ በሁዋላ ለመጡት ዳኞች ሁሉ ፣ የሱ ፣ ማለት ያገረ-ገዥው ግብረ በሎች ሆነው ፣ የሱን ግንባር እያዩ የሚፈርዱ ናቸው ። ሶስተኛ ልንገ ራችሁ? ወይስ ይበቃል ! ከፈለጋችሁ ከዚያ በሁዋላ ደግሞ ያደረገውን ልንገራችሁ።"

"ይቀጥሉ አባቴ" አለ ጥላሁን ፣ ከቅርታ ፈገግታ ጋር።

"አንድ ጥላሁን ፈይሳ የሚባል ጥሩ አስተማሪ ነበር" ሲሉ ባላ ምባራስ ፣ ሶፊና ጥላሁን በመገረም አይን ተያዩና ፣

"ማን?" አለ ጥላሁን !

"ጥላሁን ፈይሳ ። በስም ትገናኛላችሁ ባባት ስም እንጃ እንጂ።"

"ባባት ስምም ስለ ተገናኘን ገርሞኝ ነው ! ያባቴ ስም እንደሱ አባት ፈይሳ ነው።"

@OLDBOOKSPDF

“ኧረ የቅድስ ጊዮርጊስ ያለህ! በስም ከናባታቸው የሚገናኙ ገና እናንተን ማወቄ ነው፤ ይሁን ግዴለም” አሉና ታሪካቸውን ቀጠሉ።
“ታዲያ ይህ ሰው፣ ይህ ጥላሁን ፈይሳ፣ ቀድመውት ከመጡት አስተማሪዎች ሁሉ በሰው ዘንድ እጅግ የተወደደና የተመሰገነ ሆነ። ደመወዙን ሲቀበል፣ ምን ያክል ለቤቱ እንደሚያስቀር እሱና እግዜር ያውቃሉ እንጂ፣ ችግረኛው ሁሉ ‘ስጠኝ’ እንደሚለው ከሆነ . . . አንድ ብር እን ኩዋ የሚተርፈው አይመስልም ! አንድ ቀን አገረ-ገገርው አሽከሮቹን ልኮ ጥላሁንን አስደብድቦ፣ሚስቱን አስነጥቆ ሸሸጋት ። ልጄ፣ ጥላሁን ማለቱ ነው፤ መቸስ ጀግና ነው፤ ከደብዳቢዎቹ ሶስቱን በሽጉጥ አቁስሎ፣ አሱም ቆስሎ ወደቀ ። ትንሽ ሲሻለው፣ በፍርድ እንደማይሆንለት ስላ ወቀ በጄ ሲካስ ሜካ ገባ። አሁን ሁለቱ እዩተደባበ ተቀምጠዋል ። ጥላ ሁን ቀን ሜካ ይዋል እንጂ፣ መቸም ሰው የወደደው መልካም ነውና፣ ሌት አዳሩ እዚሁ ከተማ፣ ከኛ ጋር ነው፤ አንዳንድ ጊዜም፣ “ያገረ ገገሩን ግቢ ሲዞር አዩነው” የሚሉ አሉ ። ይህ አረመኔ፣ ይህ ያሉኝ አይል ጥላሁን ሜካ ከገባ በኋላ ፣ ትንሽ ቆይቶ ፣ የዱሮ ምሽቱን ቲፒ ርስቱ ላይ ወደ አሠራው ቤቱ ሰድዶ የጥላሁንን ሚሽት በገሀድ አግብቶ ተቀ መጠ ። “እዩትላችሁ እንዲህ ያለ ጉደኛ ነው!”

“እና አሁን አገረ ገዥው ቤት ያሉት . . . ሴት የአስተማሪው ሚሽት ናቸው ማለት ነው ?” አለ ጥላሁን፣ የቁጣ ምልክት በፊቱ እዩታዬ ።

“አዎ፤ ከምትወደው ባልዋ በመለየትዋ ሶስት ወር ታምማ፣ ‘ሞተች’ ከተባለች በሁዋላ፣ስትተርፍ በግድ ታገዛ ምሽት የሆነች ሴት ናት ልጄ ።”

ሶፊያና ጥላሁን አገረ-ገዥ ራት የጋበዙዋቸው እለት ወብቱ የጥላ ሁን ፈይሳን ስም ሲጠራ ግራዝማች ዳኘና ባለቤታቸው ለጊዜው የደ ነገጡት ትገዘ አላቸውና አሰበሳቸው ተያይተው ሁለቱም አንገታቸውን ደፍተው ዝም አሉ ።

“መቸስ . . . እንዲሁ በዩጥቃቅኑ ምክናያት እዩተደበደበ የሞተው፣ አካለ ሰንኩል ሆኖ የቀረው፣ ርስቱና ሌላ ሀብቱ የተዘረፈውማ ተቆ ጥሮም አይደረስ! አሁን ደግሞ ለሰው ርስት መቅሚያ አዲስ ዘዴ ፈጥ ሮዋል ። በከተማው አካባቢ ያለውን መሬት ሁሉ፣ ‘ለከተማ የተከለለ ነው’ እያለ አስራ አምስት ጋሻ መሬት ወስዶ፣አምስቱን ጋሻ በስንዝር በስንዝር እዩሸነሸነ ለጎሬ፣ ለጅማና ላዲስ አበባ ሰው ሸጦ በላው ።

@OLDBOOKSPDF

የቀረውን በጄ ይዞ በናውቃቸው ይዘናቸው ገባ። የኋላም አንድ ጋሻ ብትተርፈኝ፣ 'ለከተማ በተከለለው ውስጥ ናት' ብሎ ወሰዳት ። ይህ አገር ጅብ የሌለበት ፣ የተባረከ አገር ነበር ልጄ! ነገር ግን እግዚአብሄር በሌቶ የማይጠግብ ፣ ክፉ ጅብ እሱን አወረደብን !"

"ታዲያ ይህን ሁሉ የበላዮች አያውቁም ማለት ነውን?" አለ ጥላሁን።

"ምን አውቃብሁ ልጄ ! መቼም አገራችን ከአዲስ አበባ እሮቅ ናት ነው ! ነሬ የሚመጡት ጠቅላዮችም ካንድና ቢበዛ ከሁለት አመት በላይ ሳይቆዩ ስለሚመለሱ ፣ እንከትግንሰ እዚህ ዳር የሚደረገውን ፣ እዚ ያው ኢመሰረያ ቤታቸው ውስጥ የሚሆነውንም በቅጡ ሳያውቁት ነው እሱ ተመልሰው የሚሄዱ ! ስለዚህ፣ ብዙ የሚቆዩት የበታቾቹ ስለሆኑ ከድህ የሚዘርፈውን ለነሱ እያካፈለ ፣ ይሄው አስራምስት አመት ሙሉ ይችን አገር ግጦ በላት ! አስራ ምስት አመት በርስታቸው ካልሆነ በግዛታቸው የሚቀመጡ ሾሞች ግሬ ከሱ በቀር በሌላ አገር አይገኙም፣ ልጄ" አሉ ባላምባራስ፣ ራሳቸውን እየነቀነቁ።

"እኛ መቼም በላገር አገዛዝ ይልቁንም ስለ ባላገር አስተዳደር ምንም አናውቅ ፣ አባቴ ። በነውንም ሆኑ ከፋውን እንዲህ እንዲርስዎ ካላችሁ አዋቂዎች ለመማር ነው ተስፋችን። እስቲ አንድ ነገር ሳልረሳው፣ ቅድም ስለ ራስዎ ሲናገሩ፣ 'አንድ ጋሻ መሬት ብትቀረኝ እሱዋ ንም ወሰዳብኝ' ያሉ መሰለኝ፣ ባልሳሳት ። ታዲያ አሁን.. ምንም መሬት የለዎም ማለት ነውን?" አለ ጥላሁን።

"አሁን እዚህ ምንም የለኝም ። ድሮውንም ቢሆን እዚህ የነበረኝ በባላባትነቴ ፣ በሲሶ የደረሰኝ እንጂ የገዛሁት ፣ ወይም የወረስሁት ርስት አልነበረም ። በሲሶ የደረሰኝን ፣ ይህ ክፉ ሰው ፣ ይህ አገረ-ገዢያችን በዱምክንያት፡ ከኔ አዶወሰደ የትልልቆችን ሰዎች ወዳጅነት የገዛበትም አለ ! ራሱ ይዞ የሚበላውም አለ ። ነገር ግን ጌጫ ፣ አንድ ጋሻ ግለሬያ መሬት አለኝ ። እሱ በሲሶ የደረሰኝ አይደለም ! የገዛሁት ፣ ጣማ ርስቴ ነው ! ብታየው ደስ ያሰኝሀል ፣ ልጄ ። ቅል.. ጥ ያለ ፣ ቡና ብቻ ነው ! እሱም በጄ የተከልሁት !" አሉ ባላምባራስ ፣ የተከሉበትን እጃቸውን ዘርግተው እያሳዩ ።

"እስቲ አንድ ያልገባኝ ነገር አለ ፣ አባቴ ። ባላባቶች በሲሶ ባገኙ ትና በገዙት ፣ ወይም በወረሱት መሬት መሀከል ልዩነቱ ምንድ ነው ? ሁሉስ ያው.. ርስታቸው አይደለም ?" ይህን የጠዬቅሁበት ምክናያት ". . ጌጫ ያለው መሬቴ የገዛሁት ፣ ጣማ ርስቴ እንጂ ሲሶ አይደለም ሲሉ ስለሰማሁ ፣ በሁለቱ መሀከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ ነው" አለ ጥላሁን።

@OLDBOOKSPDF

" ሀ . . . ! ርስታቸው ነው እንጂ ! ሁሉም ፤ በሲሶ ያገኙትም ርስ ታቸው ነው ! " አሉ ባላምባራስ ፤ ራሳቸውን እየወዘወዙ ፤ ያሽሙር ሳቅ እንደ መሳቅ ብለው ። " አዎ ፤ በሲሶ ያገኙትም ፤ ምንም እንኳ ርስ ታቸው ባይሆን ፤ ርስታቸው ሆኖ . . . ይሄው እንደኔ በገ፣ ዎች ዘንድ ምግብ ያጡት ፤ በጥፋት መጉ የሚቆጠሩ ባላባቶች ፤ ወይም ቆርዎች ፤ ያገሩን ሁሉ ሲሶ መሬት ፤ ከንበጢ እየሸጡ ይበሉታል ! ሲሸጡት አላልቅ ያላቸ ውም ብዛቱ የሚያደርጉትን አሳጥቶ ፤ ራሳቸውን እያበጣበጠ ፤ ወደ ማበዱ አደርሶዋቸዋል ! "

" የባሰውን አጫለሙልኝ ! " አለች ሶፊያ ፤ የባላምባራስ ንግግር የማይፈታ እንቆቅልሽ ስለሆነባት እየሳቀች ።

" እንዴት አጫለምሁት ልጄ ? " አሉ ባላምባራስ እየሳቁ ።

" ባላባቶች በሲሶ ያገኙት መሬት እንደ ገዙት ርስት አደለም ወይ ? " ብሎ ባለቤቴ ቢጠይቅዎ ፤ ' ርስታቸውም ባይሆን ርስታቸው ሆኑ ' ሲሉ ጊዜ ፤ ርስት መሆንና አለመሆን ባንድ ላይ እንዴት እንደሚሆን ለልታ ዋኝ ስላለ ነው የባሰውን አጫለሙት ያልሁ ። "

" ካደረጉት ምን የማይሆን አለ ልጄ ? አይውልሽ ! የሲሶ መሬት የሚባለው ርስት ሳይሆን ሆኖ ! " አሉ ባላምባራስ ፤ አሁንም እየሳቁ ። ጥላሁንና ሶፊያም ተያዩና አብረዋቸው ይስቁ ጀመር ።

"እኮ እንዴት ? " አለች ሶፊያ በትብቅ ቆይታ ።

" እዎ - - ይ ! የዚህን ታሪክ ንገረኝ ካልሽኝ እዚሁ በትቀመጥንበት ውለን ማደራችን ነው ! አሁን ስራ ባላስፈታችሁ ይሻላል ፤ እኔም ከመ ጣሁ ያባዩሁዋቸው አንዳንድ አእሩግ ዘመዶች ስላሉኝ እስቲ . . . እን ሱን ልጠይቅ ። እሁን ካልጠዩቅሁዋቸው ያኮርፉና ፤ ከእንግዳ ጠብ ቻቸው እያቀምሉኝም ! " አሉ ባላምባራስ ፤ በቀልድ እንደ መሳቅ ብለው ።

" የለም አባቴ ፤ አሁን ስራ የሚያስፈቱን መስሎዎ ጭራሽ አይስጉ ! ለቡና ለቀማው እንደሆኑ አስለቃሚዎች ስላደረግን እኛን አያሳስብም። ስለዚህ . . ባለቤቴም ፤ እኔም ፤ ከርስዎ ጋር መጫወቱ በጣም ነው ደስ ያሰን ። ነገር ግን ' ዛሬ ካልጠዩቁን ' ብለው የሚቀዩሙ ሰዎች ካሉና፣ ' ያ . . እንግዳ ጠብታቸው ' የሚባለው እኛ የማናውቀው ነገር ፤ የሚቀመ ሰው ዛሬ ብቻ ከሆነ ፤ ይቆዩ ብለን አናስቸግርዎም ! " አለ ጥላሁንም ፍርጥም ብሎ ።

@OLDBOOKSPDF

"እንግዳ ጠብቃቸው" አይደለም ልጄ ! "እንግዳ ጠብቅ" ነው ! "እንግዳ ጠብቅ አታውቅም ?" አሉ ባላምባራስ ፣ እንደ መሳቅ ብለው ፣ ጥላሁንና ሶፊያም አብረዋቸው ሲስቁ ቆዩና ፣

"አናውቅም ! አስቲ ይንገሩን ! ምንድነው ?" አለ ጥላሁን ።

"በጭዋ ልጅ ወግ ፣ የጭዋ ልጅ ነኝ የሚል ሁሉ ፣ ጠጅ አቤት አስጥሎ ካልሆነ ፣ አስገዝቶ ማጠጣት ነውር ነው ። ጠጅ ለማዘውተር አቅም ያነሰው እንደሆነ እንኳንዋ ፣ ከራሱ ቆጥቦ ፣ ለሚያከብረው እንግዳ መጠባበቂያ ማስቀመጥ አለበት ። እንዲያ ያለው ፣ ድንገት ለሚደርስ ከባድ እንግዳ ተቆጥቦ የሚቀመጥ ጠጅ ፣ ከዚያ ትንሽ ዝቅ ባሉት ጭዋ ዎች ዘንድም ጠላ ነው ፣ 'እንግዳ ጠብቅ' የሚባለው" ሲሉ ባላምባራስ ፣ ጥላሁንና ሶፊያ አስበላቸው ተጠቃቀሰው ፣

"እኛ ቤትኮ 'እንግዳ ጠብቅ' አለ ፣ ጌታ ! ላምጣልዎ ?" አለች ሶፊያ። "አይ . . ልጄ! ስሙን እንኳዋ ሳታውቂት ?"

"ስሙን አንወቀው እንጂ እውነትዋ ነው" አለ ። እኛ ውሀ ፣ ወይም ብርዝ ካልሆነ ጠጅ መጠጣት ገና ስላልለመድን ፣ አንድ ወዳጃችን 'የቤት ጠጅ ነው' ብሎ ያመጣልንን፣ 'ለንግዳ ይሆናል' ብለን አስቀም ጠነዋል ! እባክዎ ይምጣልዎና አዩጠጡ እንጫወት" አለ ጥላሁን ።

"እሺ ልጄ ! የጭዋ ልጅ ጠጅ አይገፋም !" ሲሉ ባላምባራስ በራሳ ቸው ቀልድ አዩሳቁ ፣ ሶፊያ ቶሎ ተነስታ ፣ ትልቅ ማንቆርቆሪያ ሙሉ ጠጅ ከብርጭቆ ጋር አመጣችና ፣ ለባላምባራስ ቀድታ ሰጥታቸው ፣ ማን ቆርቆሪያውን ከጠረጴዛው ስር አስቀምጣው ተቀመጠች ።

"ምጣ ! ምጣ ምጣአ . . ! ግስሬያ ጠጅ ነው ! ከዋጡት በሁዋላ ባፍ የሚቆይ ፣ በውነት ጠጅ ማለት እንዲህ ነው !" አሉ ባላምባራስ ፣ ደጋግ መው ፣ 'ፉት' እያሉ አጣጣሙና ። "ባላምባራስ ጉደኛ ፣ የጠጅ ጣም አዋ ቂና ፣ ጠጅ ሲጠጡ ውለው ቢያድሩ ፣ ስካር የሚባል ነገር የማያውቁ ናቸው" እዩተባለ በሰፈሩ የሚወራላቸው ናቸው ። ጠጅ ወዳጅ መሆ ናቸው ግን ምስክር የማያሻው ፣ እውቅ ነው ! እላቸውም ጠጅ ወዳጅና ስካርን ፈጽመው የማያውቁ በመሆናቸው ይፈከሩበታል ።

"ይበሉ እንግዲህ የሲሶ መሬት ፣ 'ርስት ሳይሆን ርስት ሆነ' ያሉት ምን ማለት እንደሆነ ይንገሩን ፤ ለኛ ትልቅ ትምህርት ነው ፣ አባቴ" አለ ጥላሁን ።

@OLDBOOKSPDF

ባላምባራስ ለጥላሁን ምንም መልስ ሳይሰጡ ፣ ዝም ብለው ጠጃቸውን ጨረሱና ብርጭቆውን ሲያስቀምጡ ፣ ሶፊያ እንደገና ሞላችላቸው ። ከዚያ የሞላውን ብርጭቆ አጉድለው አስቀምጠው ፤

"እንግዲህ ንገረን ካላችሁ ፤ ታሪኩ ረዥም ነውና ፤ ትግስታችሁን ሁሉ አጠራቅማችሁ ስሙኝ" አሉ ፤ ውብ ፊታቸው በፈገግታ በርቶ ።

"ቅድም እንዳልሁዋችሁ" አሉ ፤ ቀጠሉና ፤ "ቅድም እንዳልሁዋችሁ ፤ አባቴ በጣም ትልቅ ሰው ነበሩ ። መጣፍና ማንበብ አይወቁ እንጂ ፤ ከጥንት ጀምሮ በቃል ሲነገር የወረደውን ያፍ ታሪክ ሲተርኩ ፣ ማንበብና መጣፍ የሚያውቁት አይተካከሉዋቸውም ። እሳቸው እንዳስተማሩን ፤ ሲሶ መሬት የሚባለው ፤ ቀላድን ተከትሎ የመጣ ነው ፤ ቀላድም ጋላን ተከትሎ የመጣ ነው ። 'ጋላ ከመምጣቱ በፊት ቀላድ የሚባል ነገር አልነበረም' ይባላል ልጄ"

"ጋላ ከየት ነው የመጣ ? አለች ሶፊያ ።

"ቆይኮ አትቸኩይ ! አትቸኩይ ። ልነግርሽ ነው ፣ ልጄ !" አሉና ባላምባራስ ፤ በመናገር ፋንታ ጠጃቸውን አንስተው ጠጥተው ብርጭቆውን በጠረጴዛው ላይ አስቀመጡ ። ከዚያ ሶፊያ ቶሎ ብላ ማንቆርቆሪያውን ከጠረጴዛው ስር አውጥታ ከሞላችላቸው በሁዋላ ወደነበረበት ልትመልሰው ስትቃጣ ፣ እንደገና ፤ "ፉት" ብለው ፤ "ምጣ-ምጣ-ምጣእ .... ! እሱ ማንቆርቆሪያ እጠረጴዛው ላይ ቢቆይ ይሻላል ልጄ ! እኔ እዬጠጣሁ በጨረስሁ ቁጥር ደፋ ቀና ከምትይ ! ወዲያውም እንዳይረሳ !" ሲሉ ቀልዳቸውን ፈገግ ብለው ፣ ጥላሁንና ሶፊያ ይስቁ ጀመር ። ከዚያ ባላምባራስ ታሪካቸውን ቀጠሉ ።

"ጋላ ፣ ወዲያ ፣ ወዲያ ፣ ካገር ዳርቻ ፣ የባህሩን ፣ የውቅያኖሱን ፣ ጠረፍ ይዞ ይኖር ነበር ። ከዚያ አንድ 'ሶማል' የሚባል ጦረኛ ህዝብ ከላይ ፣ ከምስራቅ ወገን ሲጫነው ጊዜ ፤ እዬሸሸ በሀረርጌ ፣ በባሌ በቦረና ፣ በኬንያ ፣ ዳር ዳሩን ሰፍሮ ፣ ሲመቸው ወደ ውስጥ ይገባና ዘርፎ እዬተመለሰ ፤ እዚያው ቆዬ ። በዚያ ጊዜ እነዚህ አገሮች ማለት እነሀረርጌ ፣ እነባሌ ፣ እነቦረና ፣ እነከፋ ፣ እነጅማ ፣ እነገሞ ጎፋና ሌሎችም በዚህ አካባቢ ያሉት ሁሉ ፤ ለኢትዮጵያ ንጉሰ በያመቱ ግብር የሚከፍሉ ንጉሶች ነበሩዋቸው ። 'ሶማልም እንዲሁ ለኢትዮጵያ ንጉሰ ይገብር ነበር' ይባላል ። በሁዋላ ፣ ሶማል መጀመሪያ ከነበረበት ፣ ከፀሐይ መውጫ ፣ አንድ 'ግራኝ' የሚባል ሀይለኛ ጀግና በኢ

@OLDBOOKSPDF

ትዮጵያ ንጉስ ላይ ተነስቶ ድል አደረገና ፣ አገሩን እስም አድርጎ አጠፋው ። 'ግራኝን የሚመስል ሰው በመሬት ተፈጥሮ አያውቅም' ይባላል ።

ስለ ግራኝ የሚነገረው ለግመን አስቸጋሪ ቢሆንም ፣ ሀይለኛነቱ ተወዳዳሪ የሌለው ፣ ከሁሉ የላቀ ፣ መሆኑን የሚያሳይ ነው ! "ቁመቱ አስራ ሁለት ክንድ ከስንዝር ፣ ከጋት ፣ ከሁለት ጣት ፣ የትከሻው ስፋት ስድስት ክንድ ፣ ከስንዝር ፣ ከጋት ፣ ጦሩ ሀያ አራት ክንድ ፣ የፈረሱ ቁመት ከኮቴው እስከ ጀርባው አስር ክንድ ፣ የፈረሱ ሽንጥ ከጭራ መብቀያው እስከ ጆሮው አስር ክንድ ከስንዝር ነበር" ይባላል። በሚያልፍበት መንገድ ገደል ያገኘ እንደሆነ ፣ በጁ ገፍቶ ይንደዋል፤ ትልቅ ዛፍ ያገኘ እንደሆነ ፣ ባንድ እጁ ነቅሎ ይወረውረዋል ። በግራኝ ፊት እንኩዋንስ ሰው ተራራው ሁሉ ይሸሻል ፤ ደኑ ሁሉ መሬት ገብቶ ፣ ትብያ ለብሶ ይሸሸጋል ! አንዳንዱን ቁጥቋጦ ከገደሉ ባንድ እጁ ፈንቅሎ ሲወረውረው ፣ ያንድ ቀን መንገድ ሂዶ የተተከለው ፣ ማንም ሊነቅለው ስለማይችል ፣ እስከ ዛሬ በየቦታው እንደ ተተከለ ይታያል ።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ግዛት እጅግ ሰፍቶ ፣ ያንድነት ማሰሪያው ባልቶ ፣ የገዥዎች ምቾት በዝቶ ሳለ ፣ እንዲያ ያለ ሀይለኛና ጨካኝ ጠላት ተነስቶ ሙሉ ኢትዮጵያን ብዙ አመት በዘበዛት ። ኢትዮጵያ በዚያ ሀይለኛ ጀግና ክንድ ተደብድባ ፣ ደቃ ፣ ወድቃ በሕይወትና በሞት መካከል ስትጣጣር ፣ እግዜር ትረፊ ብሎዋት የግራኝ ሀይል አለቀና ድል ሆኖ ሞተ ።

ነገር ግን ምንም ከሞት ብትተርፍ ፣ እስከታገግምና ከወደቀች በት ተነስታ ወሰንዋን ለማስከበር እስክትበቃ ፣ እጅግ ረዥም ጊዜ ወሰደባት ።

ባላምባራስ ጠጃቸውን ጨልጠው ብርጭቆውን ሲያስቀምጡ፣ ወዲያው ሶፊያ ትሞላላቸዋለች ። ከዚያ ለማጉደል ያክል ፉት ይሉና ይቀጥላሉ !

"ምጣ ፤ ምጣ ፤ ምጣእ . . . ! በዚያ ጊዜ ነው ልጆቼ ! በኢትዮጵያ ወሰን ከጸሐይ መውጫ እስከ ጸሐይ መግቢያ ሰፍሮ ምቹ ጊዜ ይጠብቅ የነበረው የጋላ ሰራዊት ፣ እንደ ብርቱ ማእበል ሰብሮ ገብቶ ኢትዮጵያን በየአቅጣጫው ያጥለቀለቃት ! ኢትዮጵያ ደክማ፣ ወድቃ፣ በወሰን ቆሞ ታገድ ፣ ወገድ የሚል ወንድ በጠፋበት ጊዜ ፣ ጋላ

@OLDBOOKSPDF

በምሥራቅ እስከ ትግሬ ፣ እስከ ወሎ ፣ በደቡብ እስከ ሐረርጌ ፣ ከዚያ እስከ ሸዋ ፣ በዚህ እስከ ጎጃም ፣ እስከ ቤጌምድር ተሰራበት ። ጋላ በዘላንነት የኖረ ህዝብ ስለነበረ ፣ በዩክፍሉ በጀግንነቱና ባመራር እውቀቱ የሚመረጥ ፣ የሰራዊት መሪ እንጂ ፣ የሁሉ ጠቅላይ ንጉስ አልነበረውም ። እንዲያ ያለው መሪ ፣ በጦርነት ጊዜ አዝማች ከመሆኑ ሌላ ፣ በሰፈረበት አገር ፣ መሬቱ በጋራ ቤት ለጎሳው መንጋ መሰማሪያና ፣ ላዝመራ ማዝመሪያ እንዲሆን ፣ ሊመድብና ሊያስተዳድር ለሚመራው ሕዝብ ባላደራ ነው ። በሁዋላ ጦርነት ቀርቶ በሳም ሆኖ ፣ በወራሪነት የገባው ጋላ በዩሰፈረበት ነዋሪ ሲሆን ፣ በዩጊዜው የጦር አዝማች መምረጡም ቀረና ፣ ሬት የተመረጡት ፣ መሪነትንም ሆነ አስተዳዳሪነትን እንደያዙ መቅረት ብቻ ሳይሆን ፣ ከነሱ በሁዋላ ዘራቸው እንዲወርስ አደረጉ ። ይሁን እንጂ ፣ የኢትዮጵያ ንጉስ እንደገና ሀይል አግኝቶ ፣ ጋላ የሰፈረበትን አገር ሁሉ ድል እያደረገ እስኪይዝ ድረስ ፣ የጋላ መሪዎች የሚመሩትን ሕዝብ ርስት ፣ በባላደራነት አስተዳዳሪዎች እንጂ ፣ 'ባለርስቶች ነን' ብለው አያውቁም ነበር ።”

ባላምባራስ ጉደታ ጠጃቸውን እዩጠጡ ፣ ስለ ጋላ ታሪክ አባታቸው ብዙ ጊዜ እዩመላለሱ ሲናገሩ በመስማት ፣ በቃል ያጠኑትን መድገም ከጀመሩ በሁዋላ ፣ የሚጠጡት መጠጥና የሚተርኩት ታሪክ ባንድነት ፣ ለሰውነታቸው ሞቅታና ደስታ የሰጡት መሆኑን ከፊታቸው መብራትና ካንደበታቸው መርታት ይታይ ነበር ። ታዲያ እንዲያ ርቱእ በሆነ አንደበት የሚተርኩትን ታሪክ የገዛ ጆሮዎቻቸው እዩሰሙ ልባቸው ተመስጦ ፣ አንዳንድ ጊዜ ባዶውን ፣ አንዳንድ ጊዜ ከነጠጁ ብርጭቆዋቸውን በጠረጴዛው ላይ ያስቀምጡ እዩመሰላቸው “ጨምሪልኝ” ማለት እንደሚፈልጉ ሁሉ ፣ ብርጭቆ የያዘ እጃቸውን መላል ሰው ወደ ሶፊያ ሲዘረጉ ሲያዩዋቸው ጊዜ ፣ እስዋና ጥላሁን መጀመሪያ እንደ ምንም ብለው ሳቃቸውን መግታት ቢችሉም ፣ ሁዋላ አላስችላቸው ብሎ ሳቁ ። ባላምባራስም ያደረጉትን ተገንዝበው እብረዋቸው ይስቁ ጀመር ።

“መጥፎ ልማድ አለኝ ! ከመጠጥ ይልቅ ወሬ ያሰክረኛል ። ወሬ ስጀምር አይኖቸም ፣ ጆሮዎችም ፣ ልቤ ጭምር ፣ አፌ የሚናገረውን ተከትለው ስለሚነጉዱ ፣ የማደርገውን . . . ሌላ ሰውነቴ የሚሰራውን አላውቅም !” አሉ ባላምባራስ እዩሳቁ ። “ወዲያውም . . . እናንተ ‘አንጠጣም’ ስላላችሁ ነው መሰለኝ ፣ በዚህ ጠጅኮ . . . ጨክነሁበት ። እንግዲህ ቢበቃኝ ይሻላል !” አሉ ቀጥለው ፣ ብርጭቆ ጠጃቸውን እንስተው እያዩ ።

“እውነታችን ነው ! እኛ ገና ስላለመድነው ጠጅ አንጠጣም ፣ እባክዎ እዩጠጡ እንጫወት ፣ አባቴ ” አለ ጥላሁን ።

@OLDBOOKSPDF

"እሺ ልጄ ፣ እሺ ። ታዲያ . . . የኢትዮጵያ ንጉሶች ጋላ የተሰ ራበትን አገር ሁሉ ወግተው ፣ እንደገና እንደያዙ ምን አደረጉ ይመስ ላችሁዋል ? ጋላ የተሰራበትን አገር እንደገና እንደያዙ ፣ የድሮ ወታ ደር እንደ ዛሬ በደመወዝ ስለማይተዳደር ፣ ያን የተያዘ አገር ሁሉ እንዲጠብቅ እዚያው በያለበት ለሚቀመጠው ሰራዊት መተዳደሪያ ፣ መሬቱ በቀላድ ተለካ ፣ ሲሶው ላገሩ ህዝብ እዩትተወ ፣ ሁለት እጁን መንግስት እንዲወስድ ተደረገ ። እንግዲህ ጉዱ እዚህ ላይ ነው ። ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ ! "መንግስት አገር ለሚጠብቅለት ሰራ ዊት በደመወዝ ፈንታ መትከያ ፣ መንቀያ ፣ እንዲሆንና እንዲሁም በጦር ድል ያደረገውን አገር ህዝብ ፣ ክርስቲያን ማድረግ በጊዜው የክ ርስቲያን ንጉስ አይነተኛ ተግባር ሆኖ ይታይ ስለ ነበረ ፣ ለቤተ ክር ስቲያን መትከያና ለሚያስተምሩ ካህናት መተዳደሪያ ፣ ሁለት እጁን ሲወስድ ፣ 'ላገሩ ህዝብ ተተወ' የተባለውን አንድ እጅ ፣ ወይም ሲሶ ፣ ከዚያ በፊት የህዝብ ተጠሪዎች ሆነው ርስቱን በባላደራነት ያስተ ዳድሩ የነበሩት መሪዎች ወይም ቆሮዎች ፣ ወይም ባላባቶች ፣ የግል ርስታቸው አድርገው ያዙት ! ወሰዱት ! እዩትላችሁ ፣ ልጆቼ ! 'ሲሶ መሬት የባላባቶች ርስት ሳይሆን ርስት ሆነ' ያልሁዋችሁ ለዚህ ነው ! ባላደራዎች ፣ ጠባቂዎች ፣ እንዲጠብቁለት 'አደራ' ያላቸውን ባለሀ ብቱን ፣ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ ፣ ርስትም ፣ አባትም ፣ እን ደሌለው አድርገው ፣ እነሱ ብቻ ካባት እንደ ተወለዱ ሁሉ ፣ 'ባላባ ቶች' ተብለው ፣ ርስቱንም ፣ ባላባትነቱንም ባሰት ስለ ወሰዱበት ነው ፣ 'ሲሶ መሬት ባላባት ለሚባሉት ጥቂት ሰዎች ፣ ርስት ሳይ ሆን ርስት ሆነ' ያልሁ !"

"ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ? ይህ በፍ . . . ጹም ሊሆን አይ ችልም !" አለ ጥላሁን ፣ ባላምባራስ ታሪካቸውን ሲተርኩ አይኖቹ በቁጣ ደም ለብሰው ፣ መታገስ ስላቃተው ፣ እንደ ተቀመጠ ሲቁነ ጠንጥ ቆዩና ።

"ሆና ኖረኮ ልጄ ! ሆና ኖረ ! ምጣ-ምጣ . . .!" አሉ ባላምባ ራስ ፣ ጠጃቸውን አንስተው አንድ ጊዜ ከተጎነጩ በሁዋላ ፣ "ከኖ ጡት በሁዋላ ባፍ የሚቆይ" ያሉትን ጠጅ እያጣጣሙ ብርጭቆውን በጠረጴዛው ላይ ሲያስቀምጡ ።

"ባላባት የተባሉት ጥቂት ሰዎች የህዝቡን ርስት እዩጠበቁ እን ዲያስተዳድሩ ህዝቡ ራሱ ባደራ የሰጣቸው መሆኑን መንግስት እያ ወቀ ፣ ከህዝቡ ርስት ሁለት እጁን መውሰዱ አልበቃ ብሎ ፣ ደግሞ የተረፈውን አንድ እጅ ካይነተኛው ባለርስት ፣ ከህዝቡ ወስዶ ለጠ ባቂዎቹ ርስት አድርጎ ይሰጣል ማለት የማይታመን ነው ፣ እባቴ !"

@OLDBOOKSPDF

አለ ጥላሁን ፤ መንግስት እንዲያ ያለ ፍርደ-ገምድል ፍርድ ይፈርዳል ብሎ ማመን አቅቶት ። ጥላሁን እዩ-ተበሳጨ ሲናገር ፣ ባላምባራስ ጠጃቸውን ጨልጠው ብርጭቆዋቸውን አስቀመጡና ፤

"አትበሳጭ ልጄ ፤ እዚህ አገር ደስ የሚያሰኝ ነገር የለም እንጂ የሚያበሳጭ አይገድምና አስቲ አትበሳጭ ፤ ልብህን አስፍተህ ያዘው !" አሉ ባላምባራስ ፈገግ ብለው ። ሰፊያ ጠጅ ልትቀዳላቸው ማንቆርቆሪያውን ይዛ ብትነሳ የብርጭቆውን አፍ በጃቸው ከድነው ፣ "በቃኝ" አሉ ። ታዲያ በመጠንም ቢሆን የንግድነት ስሜት ስለ ተሰማቸው ነው እንጂ ፤ ባለቤቶቹን የሰመዱዋቸው ቢሆኑ ኖሮ ገና ብዙ ይጨምሩ ነበር ።

"ምን ነበር ያልኸኝ ?" አሉ ባላምባራስ ፣ 'ጠጅ ይጨምሩ… አልጨምርም' ከሰፊያ ጋር ተከራክረው እንደምንም ካሸነፉዋት በሁዋላ ። 'እ… አዎ ፤ መንግሥት እያወቀ የህዝቡን ርስት ወስዶ እንዴት ለጠባቂዎች ርስት አድርጎ ይሰጣል ?' ነው መሰለኝ ያልህ ። መንግስት… መቸም መንግስት መጀመሪያ በጦርነት ድል አድርጎ ሲገባ ፣ እዚያ የነበረውን የመሬቱንም ይሁን የሌላውን ስራት ላያውቅ ይችላል ፤ እንዲሁም ህዝቡ ስለሚተዳደርበትና አንዳንድ በደል እንዳይደርስበት አገሩን ወግተው ከያዙት የመንግስት የጦር አለቆች ጋር የሚከራከሩም ፣ የሚመካከሩም እዚያው ባላባቶች የተባሉት ስለ ነበሩ ፣ ለህዝቡ የቆሙ እንጂ በህዝቡ ላይ ተንኮል የማይሰሩ መስሎት ፣ ለህዝብ የተመደበውን ሲሶ መሬት እነሱ እንዲረከቡ ሲጠይቁ ተረክበው ፣ 'ሳያከፋፍሉ አይቀሩም' በማለት ሰጥቶዋቸው ይሆናል ፤ ብቻ ይህ የኔ ግምት ነው ። እውነት ሲሆን ፣ ወይም ላይሆን ይችላል ። አይነተኛው ነገር ግን ፣ መንግስት አውቆ ይሆን ፣ ወይም ሳያውቅ ፣ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠረው ፤ ጠቅላላው ህዝብ ባገሩ እያለ እንደሌለ ተቆጥሮ ፣ መሬቱ ተወስዶ ፣ ሁለት እጁ ለዘማች ወታደር ፣ ለዘብ ጠባቂና ለባለማደሪያ መትከያ ፣ መንቀያ ፣ ለቤተ ክርስቲያን መትከያና ማገልገያ ፣ ለቤተ መንግስት ልዩ ልዩ አገልግሎት ስለ ተሰጠና ሲሶው ከመሀከሉ ለጥቂት እምነት አጉዳዮች ተሰጥቶ እዩ ሸጡ ፣ እዩለወጡ ስለሚበሉት ፣ እሱ ባለመሬቱ ፣ ጠቅላላ ህዝብ በርከት ብሎ በሰፈረበት ለመሬቱ ዋጋ ማሳደጊያ ሆኖ ፣ መሬቱን 'ለም' እያሰኘ ከመሬቱ ጋር አብሮ እዩተሸጠ ፣ እየተለወጠ ፣ ሲበላ የሚኖር መሆኑ ነው ። ይህ ነው አይነተኛው ነገር ልጆቼ ፤ የመንግስት ማወቅ ፣ ወይም አለማወቅ አይደለም ! ደግሞ… መንግስት ሳያውቅ ነው አይባልም ፤ እያወቀ ባይሆን ኖሮ ፣ ካወቀ በሁዋላ እንዲሻሻል ያደርግ ነበር !" አሉ ባላምባራስ ሲሄዱ ሲነሱ ።

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፲፯

# በእግዚር ዳኝነት ተስፋ የቆረጡ "ዳኝነት በጃችን" ሲሉ ፤ ወዮ ለሁሉ !

ጥላሁን ፣ ተቀጥሮበት የነበረውን ያስተማሪነት ስራ እንደማያገኝ መርዶውን ማሞ ወልደ ተንሳይ ካረዳው በሁዋላ ፣ ውብቱ ፣ "የኪ በሚ ባል አገር መሬት ገዝቼልሀለሁ" ብሎ ከጥቂት እመታት በፊት የጻ ፈለት ትዝ ሲለውና ፣ ወደዚያ ሄዶው የግብርና ስራ እየሰሩ እንዲኖሩ ለሶፊያ ሲነግራት ፣ ሌላ "አለኝ" የሚለው ፣ ተስፋ የሚያደርገው ነገር ስላልነበረው ነው እንጂ ፣ እሱም ሆነ ሶፊያ ፣ ስሙን ካልሆነ መልኩን የማያውቁትን የርሻ ስራ ሰርተው ፣ ራሳቸውንና ያገሩን ህዝብ ለመር ዳት የነበረው እምነት ይህን ያክል ጽኑ ሆኖ አልነበረም ። ነገር ግን ፣ የኪ እንደ ደረሱ ቡናቸውን እስለቅመው ያገኙት ገንዘብ ፣ ሁለቱም በከፍተኛ ደመወዝ የመንግስት ስራ ቢይዙ ኖሮ ፣ ሊያገኙ ከሚችሉት ብዙ ጊዜ የሚበልጥ ሆነ ።

ካምስቱ ጋሻ መሬት ሁለቱን በገንዘብ ፣ ሶስቱን በሲሶ ፣ አሰለቅመው በጠቅላላው ዘጠኝ መቶ ኬሻ ጀንፈል ቡና ሰላገኙ ፣ ይህን ሲያ ስቀሽሩት ሶስት መቶ ኬሻ ፣ ወይም ሶስት መቶ ኩዊንታል ያክል ሆነ። እንደ ነጋዴዎች አስተሳሰብ ፣ ኩዊንታሉ በመቶ ፈንቃ በሰማንያ አም ስት ኪሎ እዬታሰበ ወደ ፈረሱላ ሲለወጥ ፣ አንድ ሺህ አምስት መቶ ፈረሱላ መሆኑ ነው ። ታዲያ በዚያ አመት የቡና ዋጋ ውድ ሆኖ ጅማ ፈረሱላው በሳሳ ብር ይሸጥ ስለነበረ ፣ ጥላሁንና ሶፊያ አንድ ሺህ አም ስት መቶ ፈረሱላ ቡናቸውን ወደ ጅማ ቢልኩት ኖሮ ፣ አርባ አምስት ሺህ ብር በተሸጠ ነበር ። ወይም እዚያው ትንሽ ልቆይተው ቢከራከሩ ፈረሱላውን በሀያ ብር እንኩዋ ሸጠው ፣ ሰላሳ ሺህ ብር ሊያገኙ ይችሉ ነበር ። ነገር ግን የየኪ ነጋዴዎች ስላጭበረበሩዋቸውና ፣ ወዲያውም እላ ባቸው ከንግዱ ይልቅ ያተኮረው ተሎ የህዝብ አገልግሎት ስራቸውን ወደ ማጠንከሩ ስለነበረ ፣ እዚያው የኪ በርካሽ ፣ ፈረሱላውን ባስራም ስት ብር ሂሳብ ሸጠው ፣ ሃያ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር አገኙ ። ይህን ያክል ገንዘብ ለማግኘት ፣ እንኩዋንስ ተስፋ ሊያደርጉ ደፍረው ተመኝተውት የማያውቁ ነው !

መቸም መሄድ መልካም ነው። ሰው ያለበት ዙሪያው ጨለማ ሆኖ የሚያየውን ፣ የሚጨብጠውን ሲያጣ ፣ የሚያደርገው ቅጡ ጠፍቶት ግራ ሲገባው ፣ እንደ ምንም ብሎ ከዚያ መውጣትና መሄድ መልካም ነው። ጫካ ገብተው መንገዳቸው የጠፋባቸው ፣ አቅጣጫቸውን ያጡ ተጓዦች እዚያው ዙሪያውን ሲዞሩ ውለው ቢያድሩ ፣ በከንቱ ከመድከም በቀር መንገዳቸውን ፣ ወይም የሚሄዱበትን አቅጣጫ ሊያገኙ አይችሉም ። እዚያ እየዞሩ ጊዜያቸውን ፣ የአእምሮና የአካል ሀይላቸውን ከንቱ ከማባከን ይልቅ ፣ እሱን ትተው ባጠገባቸው ተራራ መሳይ ቢኖር ወደተራራው ፣ ተራራ ባይኖር ካጥምጣሞውና ከመዘጋው በላይ ከፍ ያለ ሆኖ፣ ዙሪያውን ሊያሳይ ወደሚችል ፣ ረዢም ዛፍ ወጥተው ፣ ከዚያ ዙሪያ ገባውን የተመለከቱ እንደሆን ፣ ከገቡበት ጫካ መውጫ መንገዳቸው ይታያቸዋል ! መንገዳቸውን ያገኛሉ ! ጥላሁን ያስተማሪነት ስራው ለሌላ ሰው መስጠቱን የሰማ እለት መሬት ስትዞርበት ፣ የነበረበት ቦታ መር ገጫ ! መጨበጫ ! መቆሚያ የሌለበት ፣ ባዶ መስሎ ሲታየው ፣ "ከዚህ መሄድ ነው ! መሄድ የማያውቁትን አዲስ ነገር ያሳያል ። አዲስ ነገር ማየትም አዲስ አሳብ ይፈጥራል ! መሄድ ነው መድሀኒቱ ! " ያለው እንዴት ልክ ነው ! እንዴት እውነት ነው ! ሶፊያና እሱ አዲስ አበባ ዙሪያው ጨለማ ሆኖ ፣ የሚያደርጉትን ማየት አቅቶዋቸው ፣ ተጨንቀው ሳለ ፣ ከዚያ ወጥተው ወደ የኪ ስለሄዱ ከራሳቸው አልፎ ፣ ተርፎ ፣ የተቸገሩትን እንደ ልብ ለመርዳት የሚያስችል ሀብት አገኙ ። ያገኙት ገንዘብ እንኳዋንስ ከትምህርት ቤት በወጡ ማግስት ባዶዋቸውን ለተሰደዱ ተማሪዎች ፣ ከሀብት ጋር ለኖሩም ትንሽ አይደል ! ብዙ ነው ።

"ነጋዴው ቆጥሮ ሲያስረክበኝ . . . ምን ልበልሽ ! የኔ መሆኑን ማመን አቃተኝ ! ከዚያ ውበቴ ያለው ትዝ አለኝ " አለ ጥላሁን ፣ ቡና የሸጠበትን ብር ተሸክሞ ገብቶ ለምሽቱ ካሳያት በሁዋላ ።

"ውበቴ ምን አለ ?" አለች ሶፊያ ።

"የኪን የመሰለ አገር አለመኖሩን ለማስረዳት ሲናገር ፣ 'መሬት የምትሰጠው ሀብት ተቀባይ አጥቶ እየተመለሰ ወደ መሬት የሚገባበት ፣ ሳይዘሩና ሳይተክሉ እየሰበሰቡ ብቻ የሚበሉበት አገር ነው !' ያለውን አታስታውሽም ?"

"እ ... ! አዎ ።"

" ታዲያ ... እንዲህ ባለ አገር የሚኖር ሰው እንዴት ድሀ መሆን ይችላል ? "

@OLDBOOKSPDF

"እዚህ ሀገር የሚኖረው ሁሉ ኮ ... እንዳንተ አምስት ጋሻ የቡና መሬት ያለው አይደለም !" አለች ሶፊያ ፡ ከቅርቃ ፈገግታ ጋር ቀና ብላ ባልዋን እያዩች ።

"አምስት ጋሻ የቡና መሬት የሌለውም ሀብታም መሆን ይቅር በት እንጂ ፡ ድሀ ሙሆን አይገባውም !"

"እንዴያ እንጂ ! ደሞ ድሀ የመሆን መብቱንም ቀማውና እንድያ ውን ሠድረኛ ይሁን ፤ ምናባቱ !" ብላ ሶፊያ ያሽሙር ሳቅ ስትስቅ ፡ ባል ዋም አብሮዋት ሲስቅ ቆዩና ፡

"እንዴት አትይኝም ይሉኝ ?" አሉ ።

"እሺ እቴ ፤ እንዴት ?"

"እንዴት ማለት መልካም ! እዩኘ ፡ ስቴት ጋሻ መሬታችንን በሲሶ ካበለቅም እንደ ተመለከትሁት ፡ ባለሲሶ ሁሉ ፡ ቢያንስ ቢያንስ ፡ ጥቂት ቀን በርተው ከሚሄዱት በቀር ፡ ካንድ ጎተራ ጀንፈል ቡና ያነሰ ያገኘ የለም ፤ ይህ እንግዲህ ለመጠነኛ ቤተሰብ ለአመት ቀለብና ልብስ ደህና አድርጎ የሚበቃ ነው ። ካንድ ጎተራ በላይ ያገኙም ብዙ ናቸው ። እን ግዲህ ልብ አድርጊ ፤ መሬት ሳይገዙ ፡ ጫካ መንጥረው ቡና ሳይተክሉ፡ ሳያርሙ ፡ ሳይኮተኩቱ ፡ ግብር ሳይከፍሉ ፡ በለቀማ ወራት ብቻ ኪሻን ጠቅሎ መጥቶ ይህን ያክል ... በሚገኝበት አገር ድሀ ሲኖር ይገባል ትያለሽ ? እቴ ፍሬጂ !"

"ሀ ፤ ባልተገባ ! ነገር ግን ... ያገሩ ሰው ይሄው እንደምታየው ድሀ ነው ! ' በቡና ለቀማ ወራት ብቻ ኪሻውን ጠቅሎ መጥቶ ላመት ቀለቡና ልብሱ የሚበቃውን ያገኛል ' የምትለውምኮ ፡ ከከምባታ ፡ ከወ ለጋ ፡ ከጎጃም ፡ ከወሎና ከሌሎች ፡ ከዚህ ሩቅ ከሆኑ ክፍሎች የሚመጣ ነው እንጂ ... ያገሩ ሰው አይደለም ።"

·"እኮ ለምን ? አገሬውስ ቢሆን ከስራ ያን ያክል ያገኝ የለ ? ለምን አይሰራ ? ስራ ጠፍቶ ነው ? ወይስ ... ምንድር ነው ?"

"ሀ ! አገሬውማ ፡ ያገሩ ሰውማ ... እንጃ ! ምናልባት መሬቱን እን ዳንተና እንደኔ ፡ ስራውን እንደ ባለሲሶዎች ከያገራችን መጥተን ፡ እሱ እንደሌለ ሁሉ እኛ ርስቱን ስንከፋፈለው ፡ በመሬቱና በስራው እሱ እን ደሌለ እኛ ከያገራችን መጥተን እሰበሳችን ስንገባበዝበት ሲያይ ፡ ገር ሞት ፡ ግራ ገብቶት ፡ ሰውንም እግዜርንም ታዝቦ ይሆናል ፡ ዝም ብሎ

@OLDBOOKSPDF

የሚመለከት ” አለች ሶፊያ ፣ ንግግርዋ አዝናበት የቆዩችውን ነገር ስለ ቀሰቀሰው ያዘን ስሜትዋ በፊትዋ እ^ታዩ ።

“ ሰውንም ፣ እግዜርንም ታዝበ ? ” አለ ጥላሁን ፣ የምሽቱ ንግግር አስገርሞት ።

“ ታዲያስ ! የዚህ አገር ህዝብ ሰው ብቻ ሳይሆን ፣ መንግስት ብቻ ሳይሆን ፣ እግዜር ጭምር ትክክለኛ ፍርድ እንደማይፈርድ ተረድቶ፣ በእግዜር ፍርድ ጭምር ተስፋ ቆርጦ ፣ ሰውንም ፣ እግዜርንም ፣ ታዝቦ ተቀምጦዋል ! ሰውም ፣ እግዜርም ትክክለኛ ፍርድ እንደማይሰጡ ያመኑ ፣ በሰውም ፣ በግዜርም ፍርድ ተስፋ የቆረጠ ፣ ለማን ይግባኝ እንደሚል ታውቃለህ ? ”

“ አላውቅም ፤ ለማን ይግባኝ ይላል ? ከግዜር በላይ ማን አለ ? ”

“ ህ ! ስራሱ ! አንዳንድ ጊዜ ሰው ራሱ ከግዜር በላይ ይሆናል! እግዜርንኮ ከሁሉ በላይ የሚያደርገው ፣ ስለ ፍርዱ ትክክለኛነት በሰ ዎች ዘንድ ያለው እምነት ነው ። እግዜር ትክክል የማይፈርድ መሆኑን ሰዎች ካመኑ ፣ ሰዎች በግዜር ዳኝነት ተስፋ ከቆረጡ ፣ ያን ጊዜ… ‘ዳኝ ነት በኛችን ’ ይላሉ ! ያንጊዜ እነሱ ፣ ራሳቸው ከግዜር በላይ ሆነው እንደ ታያቸው ይፈርዳሉ ! ያንጊዜ … ወዮ ለሁሉ ! ” አለች ሶፊ ፣ ፊት ዋን ቅርታ እንዳጠለለው ።

“ ዛሬ ምን ሆነሻል የኔ እመቤት ? ” አለ ጥላሁን ፣ የምሽቱን እን ግዳ ስሜት ከፊትዋና ከሁኔታዋ ሁሉ ሲያይ ፣ ልቡን ጭንቅ ጭንቅ ስላ ለው ፣ ከተቀመጠበት ተነስቶ አጠገብዋ ተቀምጦ ጉንጭዋን እዩደባ በሰ ።

“ምን ሆንሁ ? ምንም አልሆንሁ ” አለች ሶፊ ።

“ በፊትሽ ከሚታዩው … ምን ልበለው ? ከባድ ቅርታ ሌላ ፣ እንጋ ገርሽምኮ . . ሌላ ሆነብኝ ! የሚያሳዝን ነገር አገኘሽ ? ”

“ ያዘን ፊት ይታይብኛል ? ” አለች ሶፊ ፣ ለመሳቅ እዩሞከረች ።

“ በጣም እንጂ ! ”

“ አዎ ! ” አለች ፣ አይኖችዋን በዘዝ አድርጋ ፊት-ለፊት ተከላ ። “ አዎ ! እዚያ በምናከምበት ቦታ የተሰበሰቡት ሰዎች ፣ ዘንድሮ አገሩን የወረረው አንበጣ ስላደረሰው ጉዳት እያዘኑ ሲነጋገሩ ሰምቼ ፣ “ከዘን ድሮ በቀር ይህን አገር አንበጣ ወርሮት ያውቃል ወይ ? ” ብዩ ብጠይ ቃቸው ፣ “አልፎ አልፎ ይመጣል ፤ ብቻ ድሮ እምላከ እንደ ዛሬው

@OLDBOOKSPDF

ከስው ፋቅ በሳልነበር፣ ስው ተሰብስቦ ሲለምነው፣ ምንም ጉዳት ሳያደርስ፣ ወደያው ሀይለኛ ዝናብ ይልክና ያጠፋው ነበር ። አሁን ግን ከአምላክ ጋር ስለ ተጣላን እኛም አሱን ልመና እንሄድ፣ ብንለምነው ም አይሰማን” ሲሉኝ ጊዜ ገረመኝና፣ “ከግዜር ጋር ምን አጣላችሁ ” ብዬ ብጠይቃቸው የመለሱልኝን ልንገርህ ?

“መንግስት ከበቀልንበት መሬታችን፣ ካረፋችን ፡ እኛን ነቅሎ ሌሎችን፣ ሳፈናና ሳዩሩ ባእድ የሆኑትን፣ ከሩቅ አምጥቶ ሲተክል፣ ‘መቸም ከመንግስት በላይ ያለ ዳኛ አምላክ ነው’ ብለን፣ ህዝቡ ሁሉ፣ እርጊውና ህጻኑ ሳይቀር ተሰብስቦ፣ እሳት እዬነደደና ከርግ እዬታረደ፣ ሌት ተቀን ‘አቤት’ ቢባል ፣ ‘እግዜኦ’ ቢባል፣ ‘እሻፈረኝ አልሰማም’ አለ ። ከመንግስት ጋር ተስማምቶ ፣ ከመንግስት ጋር አድሞ፣ በደላችንን ‘አምቢ አላይም’ አለ ! ከዚያ በሁዋላ እኛም አዝነን፣ ቂም ይዘን ተጣነው ! ስለዚህ መጀመሪያ ቂም ይዘን ብንለምነው እንደማይሰማን ስለምናውቅ፣ ሁለተኛ እንዲህ እንደሱ ያለንዳች ምክንያት፣ እንዲያው በግፍ ተነስቶ የሚበድል ጠላት ፣ ‘ምን ያደርገኛል’ የሚል፣ የሚንቅ ጠላት ስለሆነ፣ ‘እንዲህ ያለውን ጠላት ቢቻል መበቀል፣ ያለዚያም እስኪቻል እንዲሁ ተጣልቶ መኖር ነው እንጂ እሱን ልመና መሄድ … ውርደት ነው ብለን ስለምናምን እንደ ተጣላን ቀረን’ አሉኝ ። እየውልህ፣ ዛሬ ይህን ሰምቼ መጣሁ ! እንዚህ … ፊቱታቸውን ሲሄዱ ሆዳቸው ከጥላና፣ እንዲሁም ደመ-ነፍሳቸው የሚያዝዛቸውን ሌላ የተፈጥሮ ግዳጅ ከፈጸሙ፣ ከዚያ አልፎ የሚያስብ አእምሮ፣ ከዚያ በላይ የማሰብ ችሎታ ያላቸው የማይመስሉ ሰዎች፣ የሰውን ብቻ ሳይሆን ያምላክን ፍርድ ጭምር ንቅፈው፣ ሰዎችን፣ መንግስትን ብቻ ሳይሆን እግዜርን ጭምር ለመበቀል፣ ጊዜ የሚጠብቁ መሆናቸውን ሰምቼ መጣሁ ። እስቲ እባክህ፣ እንዚህ … ‘ከጥንታዊው ሆነ ከዘመናዊው ስልጣኔ ፊታቸውን አዞረው የተቀመጡ፣ ምንም የማያውቁ ናቸው’ የሚሉዋቸው ሰዎች እለምና፣ የሰውም ሆነ የግዜር ስራትና ህግጋት ሁሉ፣ ሀይልና ስልጣን ያላቸው የሚበቀሉበት እንጂ አቅም የሌላቸው፣ ደካሞች ፍትርት የሚያገኙበት አለመሆኑን ተረድተው ፣ በደላቸውን ለመበቀል አቅም እስኪያገኙ ብቻ የሚጠብቁ ይመስሉህ ኖሮዋል ? ” አለች ሶፊ ቅርታ ያስዋበው ፊትዋን ወደ ባልዋ መልሳ ።

“ አዎ ! አሁንምኮ . . . እኔ እንጃ ! ምናልባት ኮርማ አርደውና እሳት አንድደው ሲጸልዩ ፣ መሬታቸውን ለባእድ የሰጠባቸው ባለስልጣን ያኔውኑ ሞቶ ባለማደሩ ፣ ሞቶ ባያድር በተከታዩ ሻገ

@OLDBOOKSPDF

ወይ በሳልሰቱ ፣ ወይም በሳምንቱ ፣ ሳይሞት በመቅረቱ ፣ በበለዩለት ውቃቢ ፣ ወይም አምላክ ፣ ማኩረፋቸው እንደሆን እንጂ ፣ እንቺ እን ደምትይው … አይመስለኝም ” አለ ጥላሁን ፣ የምሽቱን መንፈስ መቃወክ ስለ ተመለከተ ፣ ለማረጋጋት ንግግሩን ትንሽ በቀልድ አጠይም ።

“ ጥላዩ አትቀልድ ” አለች ቦሬ ፣ በ፡ ረጋጋት ፈንታ እንደ መቅየም ብላ ።

“ የለም ልመትልሽ ለመቀለድ አይደለም ” አለ ጥላሁን ውሽ ቱን ፣ ስትቀየም ስላያት እንደ መደናገጥ ብሎ ። “እውነቱን ነው ። እንቺ እንዳልሽው ‘ የሰው ፣ ማለት … የመንግሥትም ሆነ የግዜር ፍርድ ፣ እነሱ ትእዛዛቸውን የሚተላለፉትን የሚበቀሉበት ፣ የነሱ ፣ የብርቱዎች መበቀያ እንጂ ፣ የተበደለ ደካማ ፍትሑርት የሚያገኝበት ስላይደለ ፣ የተበደለ ፍርድ ለማግኘት ፣ ወይም (አንደኑ አባባል ፍርድ ማለት መበቀል ስለሆነ ) ለመበቀል ፣ ሀይል ማግኘት ያስፈልጋል’ በሚል ፍልስፍና አምነውና ተመርተው ፣ መንግስትንና እግዜርን ለመ በቀል የሚያስችላቸው ሀይል አስኪያገኙ ይጠብቃሉ ማለት አንጃ ። እንደ ፍልስፍና ለነሱ የሚረቅቅ ይመስለኛል ! ፍልስፍናውን ትተን አስታዊ ጥቅምና ጉዳቱንም ስናመዛዝን ፣ ጉዳቱ በጣም ያመዝናል ። ምንም ያክል ጊዜ ቢጠብቁ ፣ መንግስትንና እግዜርን ለመበቀል የሚ ያስችል ሀይል ሊያገኙ ስለማይችሉ ፣ በከንቱ እንዳይጎዱ ፣ እንዲህ ያለውን ከንቱ አሳብ መክርና አስተምሮ ማስተው ያስፈልጋል ” አለና ፣ ቃሉ ብሎ እጅዋን አጭንዋ ላይ ከለቀመጠችበት አንስቶ ፣ በጣቶችዋ የገዛ ከንፈሮቹን ሲያስዳብስ ፣ የቅርታ ፈገግታዋ ተመልሶ ፊትዋን ሲያስውበው አዩና ፣ ይቅር ማለትዋን ስለ ተረዳ ፣ ምስጋና ውን ለመግለጽ እንደ ፈለገ ሁሉ ፣ ከንፈሮቹን የሚዳብሱትን ጣቶች ዋን ሳመ ።

“ እንጃ ! ምናልባት አንተ እንደምትለው ይሆናል ! ነገር ግን እኔን በጣም ነው የከበደኝ ። ታውቃለህ ? ይህን ከሰማሁ በሁዋላ ምን ልበልህ ፣ ሙስራት አልቻልሁም ። ለህክምና የተሰበሰቡትን ሰዎች እዚያው እንዳሉ ትቻቸው መጣሁ ። እንዲያውም ትንሽ ስቆይ እዩተሻ ለኝ ሄደ እንጂ ፣ መጀመሪያማ ይህን አገር ትተን ቶሎ ወደ መጣንበት እንድንመለስ ልለምንህ እስካገኝህ ቸኩዬ ነበርኮ ! ”

“ እንዴት ? ለምን ? ”

“ ባለመሬቶቹ ተነቅለው ፣ በነሱ ቦታ ‘ከሩቅ መጥተው ተተከሉ’ ከተባሉት ባእዶች መሀከል ስለሆን ። ”

@OLDBOOKSPDF

" ታዲያ እኛ ብንሄድ የተነቀሉት ተመልሰው ይተከላሉ ? በኛ ፈንታ ሌላ ባእድኮ ነው የሚተከል ፤ እነሱን በመርዳት ፈንታ በነሱ መሳሪያነት ራሱን ለመርዳት የሚጥር ነው በኛ ፈንታ የሚተካ !"

" እሱስ እውነትህ ነው ፤ ያው የባእድ ለውጥ ነው ። ብቻ … እንዲህ ላለው ከፉ ነገር ተካፋይ ሆኖ አለመገኘቱ ፣ የህሊናን ወቀሳ ትንሽ ቀለል ያደርገው እንደሆን ነው እንጂ !"

" የጀመርነው ስራስ ? መጀመሪያ ወዲህ ስንመጣ ለህዝብ እን ሰጣለን ብለን ፣ ካሰብነው ፣ ከተመኘነው እንኩዋ አገልግሎት ሁሉ በላይ ለመስጠት በምንችልበት ሁኔታ ነውኮ ያለ ነው ? ይህን ጥለን እንድ ንሄድ ኖሮዋል ያሰብሽው ?"

" ይህ ታሰበኝማ ነው እንደ ገና የበረድሁ !"

" ሀ ! አንድ ነገር አሰብሁ " አለ ጥላሁን ፣ ሁለቱም አንገ ታቸውን ደፍተው ትንሽ ዝም ብለው ሲያስቡ ከቆዩ በሁዋላ ቀና ብሎ ።

" ምን ? "

" እሳቤ እንደ ነገረኝ ፣ ቡና ደህና ሆኖ በዘመናዊ መንገድ ከተ ሰራ ፣ እኛ ዘንድሮ ካምስት ጋሻ መሬት ያገኘነው ካንድ ጋሻ ብቻ ሊገኝ ይችላል ። ታዲያ ፣ እውነት እንዲህ ከሆነ ፣ እኛ ለራሳችን አንድ ጋሻ ብቻ አስቀርተን ፣ አራቱን በሩብ ፣ በሩብ ጋሻ እያሸነ ሸን ላሰራ ስድስት ሰዎች ርስት አድርገን ብንሰጥና ፣ እንደኛ በዘመ ናዊ ዘዴ እንዲሰሩት ብናስተምራቸው ፣ ወይም እየረዳናቸው እንዲ ያለሙት ብናደርግ . . . ለክፉ ነገር ተካፋዮች ሆነን ህሊናችን እንዳ ይወቅሰን ከመሸሽ የበለጠ የምንጠቅማቸው ይመስለኛል ፤ አይመስል ሽም ? ምናልባትም . . . ! " አለ ጥላሁን ፣ ድንገት በራሱ ያለው አሳብ ያኔውኑ እንደ ተፈጸመ ሁሉ ፣ ፊቱ በደስታ ፈገግ ብሎ ። " ምናልባትም ይህ የኛ አድራጎት አርአያ ሆኖ ፣ 'ይህን ያክል ጋሻ መሬት አለን ' ለማለት ያክል ፣ እንዲያው ለዝና ፣ ብዙ ጋሻ መሬት የሰበሰቡ ሰዎች ፣ ሰርተው ከማይጠቀሙበት መሬት ትንሽ ትንሽ እየ ቆነጠሩ እንኩዋ ቢሰጡ ፣ በኛ ምክናያት ብዙ ሰው ባለመሬት መሆን ቻለ ማለትኮ ነው ።"

" ይህ ጥሩ አሳብ ነው ጥላዬ ፤ በጣም ጥሩ አሳብ ነው ። የኛን ሳናውል ፣ ሳናሳድር ፣ አሁን እንስጣቸው ። ሌሎች የሚፈቅዱ ከሆነ … በፈቀዱ ጊዜ ይሰጣሉ " አለች ሶፊ ፣ በጥላሁን አሳብ እጅግ ደስ ብሎዋት ።

@OLDBOOKSPDF

" ሳናውል ሳናሳድር ፡ አሁን ማለት ምን ማለት ነው ? " አለ ጥላሁን ።

" ዛሬ ማለት ነው ። ብቻ ግዴለም ፤ ነገም ፡ ከነግወዲያም ይሁን ፤ ከዚያ ማለፍ ግን የለበትም ! " አለች ሶፊ ፡ እንደ መሳቅ ብላ ።

" ካሳዬም ፡ ከሌሎችም እንነጋገርበት እንጂ ። "

" ከማንም መነጋገር አያስፈልግም ፡ ጥላየ ! ለሰው ካማከር ሀማ . . . የምታማክራቸው ሰዎች ፡ የሌለ ችግር ፈጥረው እንዳትሰጥ ያደርጉሀል ! "

" የኛን ፡ የራሳችንን መሬት መስጠቱም ሆነ አለመስጠቱ ፡ ያንቺና የኔ ፈንታ ስለሆነ ፡ ይኸው ለመስጠት ወስኛለሁ ፤ ውሳኔያችን የጸና ነው ። ካሳዬና እሱ ከሚያመለክተን ሰዎች ጋር የምንመካከረው ስላሰጣጡ ዝርዝር ነው ። ለምሳሌ የዚህ አገር ጋሻ መሬት በድሮው ቀላድ አጣጣል የተጣለ ስለሆነ ፡ ባዲሱ የቀላድ መለኪያ ሲሰፈር ፡ 'አንዱ ጋሻ ብዙ ይሆናል ' ይባላል ። ስለዚህ ፡ እኛ የምናስቀረውን አንድ ጋሻም ሆነ ለሌሎች የምናከፋፍለውን አራት ጋሻ ፡ በቀያሾች ማስለካት ስለሚያስፈልግ ፡ ቀያሾችን አሳዬ ካሉበት ካላ ስመጣልን እኛ ... የት እንዳሉ እንኳ አናውቅም ። እንዲሁም ... ቅድም እንዳልሁት ስርተው የማይጠቀሙበትን መሬት ለሌላቸው በስጦታ ፡ ያለዚያም በመጠነኛ ዋጋ ለመሸጥ የሚፈቅዱ ቢኖሩ ... መቸም አሁን እግዜር ይመስገን ገንዘብ ስላገኘን ፡ አምስት ስድስት ጋሻ ገዝተን ጨምረን እንድናከፋፍል ነው ካሳዬና ካንዳንድ ደሀና ፡ ሰዎች ጋር እንነጋገር ያልሁ ።"

" እሺ ይሁን ፡ ጥሩ አሳብ ነው ። ይገርማል ! አሁን ያልኸው ሁሉኮ ስታስበው የሰነበትህ እንጂ ፡ ድንገት የመጣልህ ፡ አዲስ አሳብ አይመስልም !"

" እግዜር ይስጥልኝ ! " አለ ጥላሁን በቀልድ ።

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፲፰

# የመሬት ድልድል

ሶፊያና ጥላሁን ፡ ከመሬታቸው አንድ ጋሻ ብቻ ለራሳቸው አስቀ ርተው ሌላውን ለየኪ ጣማዎች ፡ ሽኩዎችና መሰንጎዎች ለማከፋፈል ስለ ወሰኑ ፡ የያንዳንዱን ድርሻ አይሽንሽኑ የሚደለድሉ ቀያሾች ከጎሬ እንዲያስመጣላቸው አሳዬ መብራቱን ሲጠይቁት ፡ አሳባቸውን ለማስ ለወጥ አጥብቆ ተከራክሮ ነበር ፤ አልሆነለትም ።

“ የመሬት ነገር ብዙ መዘዝ አለው ፡ ወንድሜ ። መቸም የድሮው ቀላድ ባዲሉ ሲለካ ብዙ እንደሚሆን የታወቀ ነው ። ታዲያ አሁን እናንተ አምስት ጋሻ መሬታችሁን ስታስለኩ ካምስቱ ጋሻ የሚተርፈ ውን ፡ ‘ ባለውለታዎች ነን ይሰጠን ’ የሚሉትም ፡ ‘ ይፈቀድልንና እንግዛ ’ የሚሉትም ይበዛሉ ። አገሬ ገዥውም ቢሆኑ ፡ እንዲህ ያለ ነገር ሲያ ገኙ ደስታቸው ነው ። ‘ ትርፉ በቀጥታ ለኔ ይገባል ’ ባይሉ ፡ በመ ንግስት ስም ወስደው በሁዋላ ወደ ራሳቸው የሚያዛውሩበት ዘዴ ምንም ቢሆን አያጡም ። ሌላ ሌላውም … አሁን ያልታዩን ብዙ ጭቅጭቅ አይጠፋ ። እንዲጋጠሚ ይህ ሁሉ ፡ አሁን የሚታዩንም ፡ የማይታዩንም ችግር ሁሉ ሳይደርስ ቀርቶ ፤ እንዳሰባችሁት መሬቱን ለነዚህ ሰዎች በሰላም ለማከፋፈል ብትችሉ እንኳ ፤ በምትሰጡዋ ቸው መሬት አይጠቀሙበትም ፤ ሸጠው ይጠጡበታል ። ስለዚህ ፤ እን ደኔ እንደኔ ፡ የመሬት ማከፋፈሉን ነገር ረስታችሁ ፤ እንደ ጀመራች ሁት በትምህርቱና በህክምናው መርዳታችሁን ብትቀጥሉ የሚሻል ይመስለኛል ” አለ አሳዬ ፡ ጥላሁን እቤቱ ሄዶ ሶፊያና እሱ የወሰ ኑትን ሲነግረውና ፡ ቀያሾችን እንዲየስመጣላቸው ሲለምነው ።

“ ባዋጁኮ … ባንድ ፤ በተወሰነ መጠን ፤ ለምሳሌ እንዲህ እንደኛ ባምስት ጋሻ ስም ተይዞ የቆዬ መሬት ፡ ባዲሉ የቀላድ መለኪያ ሲለካ ቢተርፍ ፡ ባለመሬቱ በትርፉ ፡ ‘ ገብሮ ’ ይባላል እንጂ ፡ መሬቱ አይወ ሰድበትም ። ከገበረበት ያው ርስቱ ስለሆነ ሊሸጠውም ፤ በስጦታ ሊሰ ጠውም ይችላል ። ደግሞ … ‘ የዚህ አገር ሰዎች በምትሰጡዋቸው መሬት አይጠቀሙበትም ፤ ሸጠው ይጠጡበታል ’ ላልከው ፡ በምን

@OLDBOOKSPDF

ለጣቸው መሬት እን[illegible]ስተማር የኛ ፈንታ ነው ። ይህ ትምህርት ፣ ከመሬቱ ስጦታ የማይለይ ፣ የሥራቱ ስጦታ ክፍል ነው ። አለ ጥላሁን ፣ ለሳዬን ፊት ፥ ለፊት ትኩር አድርጎ እያዬ ።

"እም . . . ! ሌሉ እንኩዋ እንጂ ! የዚህን አገር ኗንቅሬች ሀብት እንዲያበጁና ፣ ባበጁት ሀብት እንዲጠቀሙ ማስተማር ይህን ያክል ቀላል መሆኑ የሚያጠራጥር ነው !"

"እሱን ለኛ ተወው ፤ ግዴለም ፤"

"ምን ችገረኝ ፤ ሁዋላ እንዳትሸሹ እንጂ ! ሁዋላ ብቻ . . አባስ ጠንቀቅኸንም እንዳትሉኝ ፤ ውርድ ከራሴ ነው ፤ እኔስ ወጥቶልኛል !"

"ለመሆኑ እንዴት ነው አንተ እኒህን ሰዎች እንዲህ ዝቅ አድር ገህ የገመትሀቸው ? እንኩዋንስ ሰው ካስተማሩት መማር የማይችል እንስሳ አለ ?" አለ ጥላሁን ፣ በመገረም ።

"ይቅርታህን ፤ ተሳስተሀል ! እኔ የዚህን አገር ሰዎች ዝቅ አድ ርጌ አልገምታቸውም ። የሚያስተምራቸው ካገኙ ፣ ትምህርት የሚገባ ቸው ፣ በጣም ብልሆች መሆናቸውን አውቃለሁ ። 'እነሱን አስተ ምሮ ማሳመኑ ቀላል አደለም ' ያልሁህ ፣ በተለይ ስለ ሀብት ማበ ጀት ነው ። ሀብት ማበጀቱም ቢሆን ተሰኖዋቸው ሳይሆን ፣ 'መል ካም ነው ' ብለው ለለማያምኑ ብቻ ማሳመኑ ቀላል አይሆንም ማለቴ ነው ። ለምሳሌ መሬት ሳይዙ የቀሩ መሬት ጠፍቶ መሰለህ ? አደለም ። በመንግሥት እጅ የነበረው መሬት ሁሉ ጋሻው እስከ አምስት ብር ወርዶ እንዲሸጥ ተደርጎ የነበረ ፣ እንደነሱ ላሉት ሁሉ ተብሎ ፤ እነሱ ሳይከብዳቸው እንዲገዙ ተብሎ ነበር ። ነገር ግን እነሱ አልፈለጉም ። ለምክናያት ያክል ምን አሉ መሰለህ ? 'ለመሬታችን ባለቤቱ ማን ሆኖ ነው ለኛ የሚሸጥልን ? እኛስ ባለቤትነታችንን ትተን ንብረታችንን መልሰን በዋጋ የምንገዛበትም ምክናያት ምንድነው አሉ ። ?" ስለዚህ . . እንዲህ ያለ ምክናያት እዬፈጠሩ ፣ 'አንገዛም ' ስላሉ ነው ፣ ለነሱ የተባለወን መሬት ለነሱ በተተመነው ዋጋ ፣ የመ ንግስት ሰራተኛና ከሌላ ክፍል የመጣ ሰው ሁሉ . . የገዛው ። አንድ ቀን ያንተን በና ሰርቀው ሲለቅሙ ተይዘው መጥተው ስንጠይቃቸው ከመሀከላቸው እንዱ ያለወን አታስታውስም ? 'ለምን ሰው ገንዘቡን ያወጣበትንና ጉልበቱን ያደከመበትን ፣ ንብረቱን ትደፍራላችሁ ? የሚሸጥ ፣ የመንግስት መሬት ሞልቶ ገዝታችሁ እዬሰራችሁ አትጠቀ

@OLDBOOKSPDF

ሙም ወይ ፤’ ብዬ ብጠይቀው . . . ‘የገዛ መሬታችንን ለምን ብለን እንገዛለን ፤’ ነውኮ ያለኝ ፤ ትዝ አይልህም ፤”

“ አዎን አስታውሳለሁ ፤ ‘የምንገዛበት ገንዘብ የለንም ፤ ወዲያውም የገዛ መሬታችንን የምንገዛበት ምክንያት የለም ’ አሉ መሰለኝ ።” አለ ጥላሁን ፤ ቡና ሲሰርቅ የተያዘው ሰው ከተናገረው አሳቡ ያንደለወን ሞልቶ ።

“ አዎ ፤ ገንዘብ የሌላቸው ፤ ድሆች መሆናቸውንም ተናግረዋል ፤ ብቻ ይህ ሁሉ ምክንያት ነው ፤ እውነት አይደለም ። ገንዘብ ቢኖራቸውም … አረቄና ጠጅ ገዝተው ይጠጡበታል እንጂ መሬት አይገዙበትም ፤ እመነኝ ! እንኩዋንስ መሬት ሊገዙ ፤ መሬት ቢያገኙ ሸጠው ፤ የሚያገኙት እስኪያልቅ የቅርብና የሩቅ ዘመድ ወዳጆቻቸውን ሁሉ እየጋበዙ ይፈንጥዙበታል ! አንተና ሶፌ የምትሰጡዋቸው መሬትም ከዚህ የተሻለ እድል ይገጥመዋል ብለህ አታስብ!” አለ አሳዬ ፤ ያሽሙር ፈገግታ ፈገግ ብሎ ጥላሁንን የጎድን እያዬ ። “ የሚያስገርም ነው ! ” አለ ለቀልዱ መልስ ሲያጣ እንደገና ወደ ቁም ነገሩ መለስ ብሎ ። “ የሚያስገርም ነው ! የዚህ አገር ጣማዎች ፤ ሽኮችና መሰንጎዎች ፤ ‘ ለነገ አታስቡ ነገ ለራሱ ያስባልና ’ የተባለውን የወንጌል ትምህርት እንደሚያምኑና በሱ እንደሚመሩ ሁሉ ፤ ለለት እንጂ እንኩዋን ፤ ባመት ለማግስት አያስቡም ። ያገኙትን ሁሉ ፤ ገንዘብ ይሁን እህል ፤ ወይም ሌላ ሀብት ፤ እለቱን ካላጠፉት እንቅልፍ አይወስዳቸውም ። ‘ከዚህ አንድ ጣግ ፤ ብዙ ቦቆሎ አምረተ ’ የተባለ እንደሆነ ፤ ያን ተረዳድቶ ቶሎ ለመጨረስ ፤ ዘመድ ወዳጁ እስከ ጋምቤላ ድረስ ተጠራርቶ ይሰበሰብና ይመጣል ። እስቲ ተመልከት ፤ የነዚህ የቆጠርሁልህ ሻንቅሎች ባላባቶች ሁሉ ፤ በዚህ አካባቢ እንዳሉት የሌሎች ነገዶች ባላባቶች ፤ ጥንት ቀላድ ሲጣል በሲሶ ያነሱት ቀላድ ነበራቸው ። ዛሬ ግን ከጉርማን ጋሻ መሬት ያለው የሻንቅላ ባላባት እዚህ አንድ እንኩዋ አታገኝም ። ሁሉም መሬቱን ሸጦ በልቶ ፤ ወይም ካቲካላ አጠጥቶ ለሚያስከረው አውርሶ ጨርሶ ፤ ከድሆች ወገኖቹ ጋር የችግር እስረኛ ፤ የችግር ተካፋይ ሆኖ ታየዋለህ !”

“ታዲያ ይህ ምን ያስገርማል ? እነዚህ . . . የለት ራት የሌላቸው ሰዎች ፤ አንተ እንደምትለው ገንዘብ ሲያገኙ ፤ መሬት ከመግዛት ይልቅ ለለት ራታቸው ቢያውሉትና ከዚያ የሚተርፍ ቢኖር ችግራቸውን የሚያስ

@OLDBOOKSPDF

ረሳ ጠጅና አረቂ ቢገዙበት ፣ እንዲሁም ለሴት ራት የማይሰጥ ፣ ባዶ መሬት ሲያገኙ ፣ ‘ከሁለት ፣ ወይም ከሶስት አመት በሁዋላ ጥቅም ይሰጠናል’ ብለው ከማስቀመጥ ሸጠው ለሴት ችግራቸው ቢያውሉት ያስገርማል? አያስገርምህ ፣ አሳዬ ! እኔና አንተም ብንሆን ፣ የሴት ራት ከሌለ ፣ ባዶ መሬት ታቅፈን በራብ አንሞትም ! እንሸጠዋለን ! መቸም . . እነዚህ ሰዎች አሁኑን ጥቅም የሚሰጥ ፣ የለማ መሬት አግኝተው ሸጠው ሲጠጡበት ያዩ ሰው የለም ። ስለዚህ አሁኑ ባዶ መሬት ግዢ መስጠት ብቻ ሳይሆን . . . የምንሰጣቸውን መሬት አልምተን ፣ አሁኑን ጥቅም በሚሰጥበት ደረጃ አድርሰን እንሰጣቸውና . . . እንያቸው ። እንዲያ ያለውን ፣ ሁል ጊዜ ፣ በዬለቱ ጥቅም የሚሰጠውን መሬት ፣ ባንድ ጊዜ የሴት ጥቅም እንደማይሸጡት እኔ እዋሳለሁ ፣ ግዴለም ! ” አለ ጥላሁን ፣ በቀልድ መልክ ሳቅ ብሎ ።

መቸስ “የለማ መሬት አግኝተው ሸጠው ሲጠጡበት አይቻለሁ” ብዬ አልምልም ። መሬት የተሸጠበት ግንዘብ ተጠጥቶበት ካለቀ በኋላ ነው እኔ የመጣሁ ። ነገር ግን ፣ የነሱ መሬት ብቻ ተለይቶ ሁሉም ጠፍ ሊሆን ስለማይችል ፤ ለነሱም እንደ ሌሎቹ ለም መሬት ሳይደርሳቸው እንዳልቀረ መገመት አያስቸግርም ። ስለዚህ ፣ ላንተ እንደ መሰለህ መሬት የነበራቸው የዚህ አገር ሻንቅላ ባላባቶች መሬታቸውን ሸጠው እድህነት ላይ የወደቁ የሴት ችግር አስገድዶዋቸው መሆኑ ያጠራጥራል ”

“ታዲያ ምንድር ነወ?” አለ ጥላሁን ፣ አይኖቹን በጉዋደኛው ላይ አፍጦ ።

“ ምክንያቱ ይህ ነው ልልህ አልችልም ፤ በውነት . . ምክንያቱን አላውቅም ። ብቻ ለሁሉም ጉልህ ሆኖ የሚታዬው ፤ የዚህ አገር ሻንቅሎች ለሴት የሚበሉትንና የሚጠጡትን ለማግኘት ያክል እንጂ ፣ ለሌላ ነገር እጅግ የማይቸገሩ መሆናቸው ፤ እንኩዋንስ ሀብትና ነዋሪ ንብረት ለማበጀት ፣ ለጊዜወም ቢሆን ጌጥና ምቾት ባለው ነገር ለመገልገል አለመፈለጋቸው ነው። ያው . . እንደምታያቸው እርቃናቸውን በቅጠል ከድነው ከመሄድ በቀር ልብስ አይለብሱ ፤ ጫማ አያደርጉ ፤ አቢታቸው ስትገባ ከዶንጋይና ከጉሊጥምት ፣ እንዲሁም ከጭራሮ ከተሰራ ሊጣ አልጋ በቀር የሚቀመጡበትም ሆነ የሚተኙበት ሌላ ነገር የላቸው ፤ እጅግ ዝቅተኛ፣ የዝቅተኛም ዝቅተኛ ኑሮ ነው የሚኖሩ ። እንግዲህ ጥያቄው . . ‘ከቶ ይህ አይነቱ ዝቅተኛ ያኖኑዋር ልማድ ይሆን ሀብት ለማግኘት ሲኖራቸው የሚገባውን ጦጣጣር ወስኖ ፣ ፍላንታቸውን ገድሎ ድሆች ሆነው እንዲኖሩ ያደረጋቸው? ወይስ ድህነታቸው ይሆን እንዲህ ያለውን ዝቅተኛ ያኖኑዋር ልማድ አስለምዶ ባህል ያደረገው?’ ይህን ጥያቄ ምና

@OLDBOOKSPDF

ልባት የማህበራዊ ኑሮ ሲቃውንት ሲመልሱልህ ይችሉ እንደሆን እንጂ ፤ እኔ አልችልም?” አለ አሳዬ ፤ በቀልድ መልክ ትንሽ ፍርጥም ብሎ ።

“ግዴለም ፤ የዚህን መልስ ፍለጋ ፤ ወደ ማህበራዊ ኑሮ ሊቃውንት ሳልሄድ ፤ እኔው ፈልጌ አደርስበታለሁ ፤ አላጣውም ” አለ ጥላሁንም እንደ አሳዬ ፍርጥም ብሎ ።

“እስቲ አባክህ ፈልገህ ስታገኘው ለኔም እንድታካፍለኝ!”

“በደስታ ፤ እንዲያውም አሁኑን ልንገርህ ፤ መልሱ. . ሩቅ አደለም፤ ቅርብ ነው ። ወዲያውም አጭር ነው ። ”

“እንዴትን ምን ”

“ድህነትና አለማወቅ!” “አዩህ ፤ እነዚህን ሰዎች አሁን በሚኖሩበት ሁኔታ እንዲኖሩ ያደረጉዋቸው ፤ የጋምቤላንና የዚህን አገር ሰዎች እርታ ናቸውን ፤ ወይም ቅጠል አገልድመው እንዲሄዱ ያደረጉዋቸው ፤ ድህነትና አለማወቅ ናቸው እንጂ ፤ አንተ እንደምትለው ጌጥና ምቾት ባለመፈለጋቸው አደለም ። ጌጥ አጥብቀው የሚፈልጉና የሚወዱ ለመሆናቸውማ ሌላ የሚያጌጡበት ነገር ቢያጡ ፤ ያኑ . . ያላቸውን ፤ አካላቸውን በልዩ ልዩ ሀብርና ንቅሳት አዠጎርጉረው ፤ ሸላልመው ሲሄዱ መታየታቸውና ምስክር ነው! ስለዚህ መሬት አልምተን ስጥተን ፤ ሀብት እንዲያገኙ ፤ አስተምረን እውቀት እንዲያገኙ ስናደርጋቸው ፤ ያኖኑዋር ስራታቸውን ፤ ከዚያ ባህላቸውን እንደሚለውጡ እመነኝ ! ”

“ጥሩ ነው ፤ እንግዲህ . . እግዜር እልማችሁን እውን ያርግላችሁ!” አለ አሳዬ ፤ የዚያ አገር ተወላጆች ጥላሁንና ሶፊያ ሊያከፋፍሉዋቸው የወሰኑትን መሬት ፤ ዘላቂነት ባለው ጥቅም እንደማያውሉት ከልቡ ስለሚያምን ፤ አሳባቸውን ለማስለወጥ ያደረገው ሙከራ እንዳልተሳካለት ሲያይ ተስፋ ቆርጦ ።

አሳዬ ጎሬ ተጻጽፎ እምበት ቀላድ ጣዮች ለማግኘት ብዙ ጊዜ አልወሰደበትም ። ነገር ግን ቀላድ ጣዮች የመጡ የነጥላሁንን መሬት ቀይሰው ፤ እዚያ መሬት ለሌላቸው ሰዎች ለማከፋፈል ብቻ መሆኑ እያደር እስኪረጋገጥ ድረስ ፤ መጀመሪያ እንደ ደረሱ ፤ “የየኪንና ያካባቢውን ጋሻ መሬት በሙሉ ባዲሱ የቀላድ መለኪያ ሊለኩ ነው” ተብሎ ስለ ተወራ ፤ በየኪ ባለብዙ መሬቶች መካከል ከመጠን ያለፈ ሽብር ተነስቶ ነበር ።

@OLDBOOKSPDF

"ቀላድ ጣዮች በመምጣታቸው የዚህን አገር ባላባቶችና ባለርስቶች ይህን ያክል ያስጨነቃቸው ምንድር ነው ? ትናንት ባንድነት ተሰብሰበው ፤ እዚያ . . እምናከምበት ቦታ ድረስ መጥተው ፤ ' እቶ አሳዬ መሬታችሁን ባዲሱ መለኪያ አስለኩ ብለው ያላስገደዱን እንደ ሆነ ፤ ከያንዳንዳችን አንዳንድ ጋሻ መሬት እዋጥተን እንሰጣለንና በዚህ ወሌታ አስጣሙን ፤ አማልዱን ፤ ብለው ሰሬንና እኔን ወጥረው ስለያዙን ፤ ቀላድ ጣዮች የመጡ የኛን መሬት ቀይሰው ላንዳንድ ችግረኞች ለማከፋፈል ብቻ መሆኑንና ፤ ያስመጣናቸውም እኛ እንጂ አንተ አለመሆንህን እዩ ማልን ብንነግራቸው አላመኑንም ፤ የምናታልላቸው መሰላቸው " አለ ጥላሁን ፤ ባላምባራስ ጉዶታ ጭምር አሳዬ ጽሕፈት ቤት ተቀምጠው ስለ መሬቱ ቅዬሳ ጉዳይ ሲነጋገሩ ።

"የሚጠሉትና የፈሩት ነገር ሁሉ ፤ በምንም ምክናያት ሰው ሲጠራ ልብ ማሸበሩን ፤ ማስፈራቱን አታውቅም ? ይህም እንደዚያ ነው ! አዲሱ የቀላድ መጣያ ፤ አዲሱ የጋሻ መስፈሪያና ዘመናውያን መሬት ቀያሾች በዚህ አካባቢ ከመጠን ያለፈ ነው የሚጠሉ ። ስለዚህ . . ዘመናውያን ቀላድ ጣዮች ፤ እንኩዋንስ እነሱ ፤ ባካል እዚህ መጥተው ፤ ስማቸውን ፤ ወሬያቸውን ብቻ የሰማ ባለርስት ሁሉ ይሸበራል !" አለ አሳዬ ።

"እሮጌው ቀላድ ፤ ማለት በጥንቱ መስፈሪያ የተወሰነ ጋሻ ከዛሬው እንደሚበልጥ እኔም ሰምቻለሁ ፤ እናንተም ነግራችሁኛል ። ብቻ በጥንቱና ባዲሱ ቀላድ መሀከል ያለው ልዩነት ይህን ያክል እያሌ ሆኖ ባለርስቱን ሁሉ እንዲህ የሚያሸብር አይመስለኝም ነበር! ልዩነቱ ይህን ያክል ብዙ ነውን?"

"ለም" ከሚባለው፣ ብዙ ህዝብ ከሰፈረበት መሬትና፣ ለጌቶች ጉርሮ የሚሆን ፤ ጥሩ ነጭ ጤፍ በማብቀሉ ስመጥር ከሆነ መረሬ መሬት በቀር፣ ሌላው መሬት ሁሉ ፤ እሮጌው ጋሻ ካዲሱ በትንሹ አራትና አምስት ጊዜ የሚበልጥ ፤ ቢሄዱት የማያልቅ ነው ! ብዙ ህዝብ የሰፈረበት ፤ "ለም የሚባለውና ፤ ነጭ አብቃይ የሆነው መረሬ መሬት ግን ጋሻው ከዛሬ ጋሻ ፤ ማለት ካራት መቶ ሺህ ግእዘን ሜትር አይበልጥም ፤ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜማ ከዚያም ያንሳል !"

"መሬቱም ሀብታምና ድሀ እንደ መሆኑ መጠን መለኪያው ይለያያል ማለት ነው ? እሺ ቀጥል !" አለ ጥላሁን አቋርጦ ፤ ያሽሙር ፍርዋ ምታ ፍርጥም ብሎ ።

" ሌላው " አለ አሳዬ ፤ ጥላሁን አቋርጦ በተናገረው ያሽሙር ንግግር ከባላምባራስ ጉዶታ ጋር ሊስቅ ቆይቶ ። "ብዙ ሰው ከሰፈረ

@OLDBOOKSPDF

በትና ነጭ ጤፍ አብቃይ በመሆኑ ስመ-ጥር ከሆነው መሬት በቀር ሌላው መሬት ሁሉ ፣ ማለት ቆላው ደጋው ፣ ሜዳው ፣ ጨፌው ፣ ደኑ ፣ አቀበት ቁልቁለቱ ሁሉ ፣ እያንዳንዱ ጋሻ ፣ አንድ መቶ ሰላሳ ሶስት (የባይ ምት) ክንድ ርዝመት ባለው ገመድ ፣ ወርዱ ዘጠኝ ፣ ርዝመቱ አስራ አምስት ነው ። ይህ ወደ ሜትር ሲለወጥ አንድ መቶ ሰላሳ ሶስቱ (የባይ ምት ) ክንድ ፣ ሰድሳ ሰድስት ሜትር ተኩል ስለሚሆን ፣ የጋሻውን ጠቅላላ መጠን ለማግኘት ፣ እንደ ሂሳቡ ስራት ፣ ወርዱን በርዝመቱ አባዝተህ የምታገኘው ወደ . . . ስድስት መቶ ሺህ ማእዘን ሜትር (ካሬ ሜትር) አቅራቢያ ይሆናል ። አንዳንድ ጊዜም የቀላዱ ርዝመት ፣ ባስራ አምስት ገመድ ፈንታ ሀያ ገመድ ስለሚሆን ፣ የጋሻው ጠቅላላ መጠን ፣ ወደ ሰምንት መቶ ሺህ ማእዘን ሜትር ይደርሳል ። ታዲያ እንግዲህ ይህ ዘመናዊው ጋሻ ፣ ማለት ካራት መቶ ሺህ ማእዘን ሜትር ጋር ሲመዛዘን ፣ እጥፍ ያክል ይሆናል ማለት ነው ። የጥንቱ ቀላድ ካዲሱ የሚበልጥበት አይነተኛ ምክናያት ግን ይህ አደለም ፤ ሌላ ነው ። ዋናው ምክናያት ፣ የጥንት ቀላድ ጣዮች ብዙውን ጊዜ ፣ እንዲሁ በነሲብ እንጂ መሬቱን ዞረው አይተው በገመዱ ፣ ወይም በቀላዱ አዩሰፈሩ በባልወለኑት ነው ።”

“ቀላድ በነሲብ እንዴት ይጣላል አባክህ ? ” አለ ጥላሁን ።

“እሱንስ እኔ ልንገርህ ፣ ደርሸበታለሁ! አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም ሹማምቱ ፣ በነሲብ ቀላድ መጣላቸውንም ትተው ፣ ባለጥቅሞች የነገሩዋቸውን ብቻ ይዘው የሚሄዱበት ጊዜ አለ” አሉ ባላምባራስ ጉዲታ ራጉ።

“ይህ ደግሞ ይባስ! እንዴት እባክዎ ” አለ ጥላሁን እየሳቀ።

“ ትርፌ ሳበው የሚባሉ ማለፊያ ጌታ ፣ ዘንካታ ጌታ ነበሩ ” አሉ ባላምባራስ፣ ትርፌ ሳበውን በሞቱ በስንት ዘመናቸው ፣ ደህና በመቃብራቸው ውስጥ ሁሉንም ትተው ወደ አፈር ከተለወጡበት ፣ እንደ ገና ባካል ነቅንቀው አምጥተው ፣ እዚያ ግብር አግብተው ፣ አዝማሪ እዩዘፈነ ፣ አቅራሪ እያቅራራ ፣ ፈካሪ እዩፈከረ ፣ ትርፌ ሳበው እዩሳቁ ፣ እዩተጫወቱ ፣ እየተዘናከቱ ፣ በታላቅ ልግስና ሥጋ ሲያስቆርጡና ጠጅ ሲያጠጡ ፣ አይናቻቸውን ሳያረግቡ ቦዘዝ አድርገው እያዩ። “እዎ ፣ ትርፌ ሳበው ዘንካታ ጌታ ነበሩ ! ” አሉ ባላምባራስ ደገሙና ።

“ ማናቸው ትርፌ ሳበው ? ” አለ ጥላሁን ።

“ይህን የኛን ክፍል ቀላድ ከጣሉት ዋና ዋና ሹሞች አንዱ ፣ እኔ እግውቃቸው ትርፌ ሳበው ይባሉ ነበር ። ያባታቸው ስም እንኳ

ሳበው አደለም ፤ እንቶንህ ነው ፤ ፊቶቹን @OLDBOOKSPDF ገና ፊት ፣ ፊት ቀላድ በነሲብ መጣል ፣ ወይም እቤት ተቀምጠው ከባለጥቅሞች ጋር ተስማምተው መወሰን ሳይጀምሩ ፣ ገና ፊት የህብታቸው ብዛት ስጋትን ሳያስረሳቸው፣ ገና ፊት ከጭፍሮቻቸው ጋር እቀበት እዬወጡ ፣ ቁልቁለት እዬወረዱ ፣ ጫካ እዬጣሱ ፣ መሬት ሲቀይሱ ፣ 'ገመዱን ሳበው' የሚሉት ልማድ ሆኖባቸው ፣ ዘየ አድርገውት ፣ 'ሳበው ፣' ስለሚሉ ፣ 'ትርፌ ሳበው' ተብለው ቀሩ ይባላል ። ታዲያ እየውልህ ፤ እኒህ ትርፌ ሳበው ቀላድ ሊመጣል ወደ ዚህ ፣ ወይም ወደዚያ አገር ፣ 'ሲሄዱ ነው' ተብሎ ገና ወሬው ሲወራ፣ ያ ወሬ ወደሚሄዱበት አገር ከሳቸው ብዙ ቀን ቀድሞ ደርሶ ፣ እዚያ ከቤት ቤት ተመርጦ ይነጠጥና ፣ ይጠጅና ፣ ይታረድና ፣ ሌላ ሌላውም እን ደላቸው ባለ ትልቅ እንግዳ የሚገባው ማስተናገጃ ሁሉ ተመርጦ ይደ ገስና ፣ እዚያ ገብተው እንደ ተሞሸሩ ፤ እንኳዋንስ ጫካ አስጥሰው ቀላድ ሲያስጥሉ ከገቡበት ሳይወጡ ፣ በዬቀኑ ሰንጋ እዬታረደ ጮማ ሲቆረጥ ፣ ጠጅና አረቄ እንደ ውሃ ሲፈስ ፣ ሲዘፈን ፣ ሲቅራራ ፣ ሲፈከር ይሰንበታል ። እሳቸው እዚያ እንዳሉ አሽከሮቻቸው ከባለመሬቶች ጋር እዬተስማሙ እንሱ ፣ ማለት ባለመሬቶች ያሳዩዋቸውን የቀላድ ወሰን እዬዞሩ ሲመቱ ሰንብተው ሲጨርሱ ፤ ባለመሬቶች በያንዳንዱ ጋሻ የቀ ወሰኑ ገንዘብ እምጥተው ፤ ካሽከሮቻቸው ጀምሮ እስከ እሳቸው እንደ ዬማእረጋቸው የሚሰጡዋቸውን ይዘው ይሄዳሉ ። ይህ እንግዲህ ቅድም እንዳልሁህ ፤ 'በነሲብ እንኳዋ ቀላድ ሳይጥሉ ባለጥቅሞች ባሳዩዋ ቸው ወሰን ላይ ምልክት አድርገው' ወይም ፤ 'ምት' መትተው እነሱ የነገሩዋቸውን ይዘው ይሄዳሉ ያልሁት ነው ። የነሲቡ ደግሞ ሌላ ነው ። ከሁሉ አስቀድሞ ያገሬትን ጫካ እንደምታየው ጥቅጥቅ ያለ ስለ ሆነ ፣ እሱን ጥሶ እውስጡ ለመግባትና መሬት ለመቀየስ ፣ እንኳዋንስ እንደ ትርፌ ሳበው ላለ ለሰላሳ ጌታ ለሽካራ ጎበዝም እጅግ አስቸጋሪ ነው ። የሚበዛውን ጊዜ ግን ባለመሬት (ባላባቱ ፣ ቆሮው ፣ ወይም ማን ኛውም መሬቱ የሚለካለት ፣ ወይም የሚለካበት ሰው) ውስጡን ገብ ተው እንዳያዩበት አልፈውት ሲሄዱ ፣ ሲራመዱት የማይችሉ ፣ 'ያይ ዬብኝ መማለጃ' ይዞ እፊታቸው ቆሞ ሲቸገሩ ፣ ባንድ እካባቢውን ደህና አድርጎ በሚያሳይ ቦታ ላይ ይቆሙና ፤ ካራቱ ማእዘን የሚነጻጸሩ ፣ ጎላ ፣ ጎላ ያሉ ዛፎች ሲያዩ ፣ እነሱን ከሩቅ በዘንጋቸው እያመለከቱ ፣ 'እየ ውልህ በዚህ በኩል ፤ ያ . . . ን እዚያ ላይ ፣ በዚያ በኩል ያ . . ን እዚያ ሀች ሂድና ምታ ' ብለው ሰው እዬላኩ መስቀልኛ ያስመቱዋችዋል ። ከዚያ እንግዲህ እኒያ ካራቱ ማእዘን የሚነጻጸሩት አራት ዛፎች የጋሻው፣ 'ምቶች ' ወይም 'መስቀሎች' ተብለው ተሰይመው ፣ ጋሻ ተጣለ

@OLDBOOKSPDF

ይባላል! ያውልህ ! በካቢብ [illegible] ይሉሀል እንዲህ ነው!”አሉ ባላምባራስ ፣ ውብ ፊታቸው በፈገግታ በርቶ ።

“እውነትም በዚህ አሆሁዋን የተጣለ ቅላድ ልክ ባይሆን አያስ ገርምም! ” አለ ጥላሁን ፣ የባላምባራስን ታሪክ አፉን ከፍቶ ሲሰማ ቆይቶ ።

“የሚያስገርመው ሌላ ነገር ነው!”አለ አሳዬ ።

“ምን ?”አለ ጥላሁን ።

“የሚያስገርመው በዚህ አሆሁዋን ፣ እንኩዋንስ ትክክለኛ መጠኑን ፣ አቅራቢያውን ለመገመት በማያስችል አሆሁዋን ፣ በጋሻ ስም የተያዘውን መሬት ፣ በትክክል እንደ ተሰፈረ ሁሉ ፣ መንግስት በባህር መዝገቡ አግብቶ ፣ በሱ መሰረት ሲሶውን ለባላባት ፣ ሁለት እጁን ለልዩ ልዩ መትከያ መንቀያ ፣ ለማደሪያ ፣ ለጋንገብ ፣ ለወረገኑ ፣ ለሰሞንና እነሱን ለመሳሰሉ ስራቶች ከመደበ በሁዋላ ፣ የተረፈውን ለባለሙዋልና ለባለ ውለታ ርስት አድርጎ መስጠቱ ነው ። ይህ ነው የሚያስገርመው ! እንደ ውነቱ ከሆነ ሌላውን ክፍል አላውቅም እንጂ ፣ ይህ ክፍል ጨርሶ ቀላድ ያልተጣለበት ክፍል ነው ማለቱ ይቀላል!”

“ታዲያ ቀላድ እንዳልተጣለ ያክል የሚቆጠር መሆኑን ባለስልጣኖች ጭምር የምታውቁ ከሆነ ፣ ለምን እንዲጣል አታደርጉ ?”

“እንጃ ፣ ምናልባት በዚህ ክፍል ፣ ‘የትርፌ ሳበው ምት’ የጠቀመው እንጂ የጎዳው ስለሌለ ነው መሰለኝ . .ይለወጥ የሚል ሰው ቢገኝ ‘ሀይማኖታችሁን ለውጡ’ እንደሚል ፣ ክዶ እንደሚያስከድ ነው የሚቆጠር! በዚህ ክፍል ፣ ‘የትርፌ ሳበው ምት’ ወይም ‘መስቀል’ ሲባል ልክ እንደ አስርቱ ቃላት ኦሪት ከርስቶስ ቢመጣ ሊሽረው እንደማይችል ሆኖ ነው የሚታይ ! ‘ከትርፌ ሳበው ምት’ትንሽ እንኩዋ ዝንፍ ከማለት ፣ ‘ከትርፌ ሳበው መስቀል’ እንድዋ ከምትለወጥ ፣ ሰማይና መሬት ቢያልፍ ይቀላል!” አለ አሳዬ ፣ የወንጌል ጥቅሱን ሲጠቅስ ያሽሙር ፍርጥምታ በፊቱ እዩታዬ ።

“አንተ እንደምትለው የትርፌ ሳበው ምት የሚጠቅመው እንጂ የሚጎዳው ከሌለማ እውነትስ ለምን ይለወጣል ? የሚለወጥበት ምክንያት የለም! ብቻ ጥያቄው ፣ የሚጎዳው የለም ወይ ? ነው ! ”አለ ጥላሁን ።

“መጉዳትማ ማንን ይጎዳል?”

“መሬት የሌለውን ። ”

“እንዴት አድርጎ?”

@OLDBOOKSPDF

"አንድ ሰው ባንድ ጋሻ ስም አራትና አምስት ጋሻ መሬት የሚይዝ ከሆነ ፣ ባላበር ጋሻ የሚይዘው አርባና አምሳ ጋሻ ሲሆን ስለሚችል ፣ ይህ መሬቱን በጥቂት ሰዎች እጅ እንዲከማች አድርጎ ፣ መሬት ለሚፈልጉት ሁሉ የማዳረሱን እድል አይወስነውም ? አያሳንሰውም?"

"አ . . ! ከዚያ ወገን ስትመለከተው እውነትህ ነው ! እኔ መሬት ከያዙት ብቻ እንጂ ካልያዙት ወገን አልተመለከትሁትም ነበር ። በትርፌ ሳበው ምት መሬት የያዙት ፣ ማለት መንግስት ፣ ቤተክርስቲያን ፣ ባላባት ፣ ባለርስት ፣ ባለማደሪያ ፣ ባለሰምንና ሌሎችም በልዩ ልዩ ስምና መልክ መሬት የያዙት ሁሉ ፣ በጥቂት ስም ብዙ ስለያዙ ከነሱ መሀከል አንዱ ወገን ተጠቅሞ ሌላው አልተጎዳም ማለቴ ነበር ።"

"ጭራሽ የሌለውን ካሳብህ ውስጥ እንኳ አላገባኸውም ማለት ነው ?" አለ ጥላሁን ፣ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ ።

"ጭራሽ የሌለውን ማን ካሳቡ አግብቶት ያውቃል ! ጭራሽ የሌለ ወኮ ካሳብ አይገባም !" ሲል አሳዬ ሁሉም ተያይዘው ይስቁ ጀመር ።

"መሰንበቻውን ብቻዩን ሰሆን 'አንድ ነገር እጠይቃችሁዋለሁ' ብዬ አስብና ፣ ስንገናኝ እንዲህ እንዲህ ያለው ጭዋታና ሳቅ አስረስቶኝ ሳልጠይቃችሁ እሄዳለሁ ። እነዚህን ሰዎች ፣ እነዚህን ቀላድ ጣዮች ስታስመጡ ላገረገሮ ነግራችሁ . . . አስፈቅዳችሁዋል ?" አሉ ባላምባራስ ጉዳታ ፣ ከሳቅ በሁዋላ ባጭር ጊዜ ሁሉም ዝም ብለው ቆይተው።

"የለም ፤ ጭራሽ አላሰብነውም "አለ አሳዬ ፣ ከጥላሁን ጋር ያይን ጥያቄ ከተለዋወጡ በሁዋላ ፣ ጥፋቱን ተረክቦ ይቅርታ እንደሚለምን እንገቱን ደፍቶ መሬት መሬት እያዬ ።

"አዩ ጉ . . ድ ! ደግም አልሆነ ። እስቲ እቶ ጥላሁንና ወይዘሮ ሶፊያስ የዚህን . . ክፉ ሰው ፣ የዚህን ሰይጣን አመል ስለማያውቁ ባይሰጉ አይፈረድባቸውም ፤ አንተ ግን እንኩዋንስ እንዲህ ያለ ትልቅ ነገር እዚህ አገር ሲደረግ ፣ ጎሬና ጅማ ለገበያ የሚሄዱትን 'ሳታስታውቁኝ ከሄዳችሁ ልሰራችሁ'የሚል ሰው . . እያወቅሽው እንዴት ለሱ ሳትነግሩ እንዲህ ያለ ስራ ጀመራችሁ ? እነዚህን ደግ ሰዎች እጥርሱ ለማግባት ምክናያት እንዲያገኝ ነው?"

"እውነትዎ ነው ! ጥፋቱ የኔ ነው ። አሁንም እስቲ . . . ውሸቱንም ፣ ምንንም ፈጣጥሬ ሳባብላቸው እንደሚመለሱ ተስፋ አለኝ" አለ አሳዬ ፣ ግራዝማች ዱኘ ተቆጥተው ባለ እንደ ሀዳን እያወዳደሱ ፣

@OLDBOOKSPDF

እያዋጋገሡ ሲያባብሏቸው ፡ ቸዎቻቸውን ረስተው ወዲያው የሚወ ለሉትና የከረኮሩዎቻቸውን ያክል የሚስቁት ትዝ ስላለው እንደ መሳቅ ብሎ ።

እውነትም አሳዬ ፡ ከነሬ ያስመጣቸው መሬት ቀያሾች የነዋሳሁንን መሬት በመቀየስ ላይ መሆናቸውን ግራዝማች ዳኘ መጀመሪያ ሲሰሙ ፡ አሳቸውን ሳይጠይቅና ሳያስፈቅድ በማስመጣቱ ክብራቸው ተነክቶ ፡ ሰውነታቸው በቁጣ እንደ እቶን ግሎ ፡ አሳዬን እስኪያገኙና ፡ ማን "አለሁ" ቢለው እንዴያ ያለ የድፍረት ስራ እንደ ሰራ እስኪጠይ ቁት ቸኩለው ነበር ። ነገር ግን ፡ "የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል" እንደሚሉት ፡ እዬቆዩ ነገሩን ባሰላሰሉት መጠን ፡ አርጌው ቀላድ ባዲሱ ሲለካ የሚተርፈው ብዙ መሬት መቸም የመንግስት መሆኑ ስለማይቀርና ፡ ከዚያ ፡ መንግስት ከሚያገኘው . . . በርከት ያለው ክፍል ለርሳቸው መድረሱ የማይጠረጠር ስለሆነ ፡ ይህ እግዚአብሄር በቸርነቱ በስውር የላከላቸው በረከት መሆኑ ድንገት ብልጭ ሲልላ ቸው ፡ የክብራቸውን መነካት የጥቅማቸው መብዛት አሸንፎ ፡ ልባቸ ውን በደስታ ሲያሞቀው እዚያ ሰው ቢኖር ወገጋን በፊታቸው ይታ ዩው ነበር ። ወዲያው የቁጣ ትኩሳት ባፋቸው ውስጥ አምርሮት የነበረ ምራቃቸው ተለውጦ መጣም ስለጀመረ ፡ አፋቸውን እዬመላለሱ እዬ መጠጡ ሲውጡ ፡ አሳዬና ዋላሁን መምጣታቸውን የመስሪያ ቤቱ ተላ ላኪ ነገራቸው ።

"መጡ ? አስገባቸው ፤ እ . . . እቡቱ ቆይ ፤ ስራ ይግለሁ ፤ ትንሽ ቆዩኝ በላቸው "አሉ ግራዝማች ፡ ያሳዬንና የዋላሁንን መምጣት ሲሰሙ ፡ ያኜውኑ መሬቱን ይዘውላቸው እንደ መጡ ሁሉ ደስታ ከተቀመጡ በት ሽቅብ ካስፈነጠራቸው በሁዋላ ። ከመገናኘታቸው በፊት እቅዳቸው ሳይታወቅባቸው ፡ ሳይጋለጡ ፡ ስንት ትርፍ ቀላድ እንደ ተገኘ የሚያውቁ በትን ዘዴ መወሰን የሚያስፈልግ መሆኑ ትዝ አላቸው ።

"እያንዳንዱ አርጌ ቀላድ ባዲሱ ስንት እንደሆነ በቀጥታ ልጠ ይቃቸው ? ወይስ እነሱ እስኪያነሱት ዝም ልበል ?"አሉ ተላላኪው ከወጣ በሁዋላ ብቻቸውን ።

"እነሱ ያላነሱት እንደሆንስ? የመጡ ለሌላ ጉዳይ እንደሆንስየመጡ ለሌላ ጉዳይ እንደሆነና የመሬቱን ነገር ያላነሱ እንደሆነ ፡ የመጡ በትን ከተናገሩ በሁዋላ ፡ መጀመሪያ በቀጥታ በመጠየቅ ፈንታ ፡ እነሱ እንዲናገሩ መንገድ መክፈት ነው ፤ ካልሆነ . . በቀጥታ መጠየቁ ነው!"

@OLDBOOKSPDF

እሱ ትንሽ ሲያስቡ ቆዩና ፡ ከዚያ እፊታቸው የተቀመጠችውን ቢላ ቢላ የምታክል ፣ ትንሽ ቃጭል አንስተው አቃጭለው ፣ ተላላኪው ሲገባ እሳዩንና ጥላሁንን እንዲያስገባ አዘዙት ።

"አሁን ወደ ጎሬ የምልከው ደብዳቤ አጽፍ ስለነበረ እስከጨርስ አስጠበቅሁዋችሁ ፤ ይቅርታ አድርጉልኝ ፤ እከሳለሁ ፤ ሁ-ሁ-ሁ- ሁ-!" አሉ ግራዝማች ፣ ውሽታቸውን ከባጥ በላይ እዩላቂ ፣ እሳዩና ጥላሁን ገብተው እጅ ሲነሱ ።

"ኧረ ግዴለም ፤ ወዲያውም ምንም ያክል አልጠበቅንምኮ!" አለ እሳዩ ።

ወዲያው ፣ እሳዩና ጥላሁን ከመቀመጣቸው ፣ ተላላኪው እንደገና በችኮላ ገብቶ ፣ ከጌጫ ያውራጃው ገገር የላኩት ፈረሰኛ መምጣቱን ሲናገር ፣ ግራዝማች በጣም ድንግጥ አሉና ፣ "ካውራጃው ገገር! ፈረሰኛ! እ.. ..ግባ በለው" አሉ ። ከዚያ ድንጋጤያቸውን ለመሸሸግ ያለውዳቸው ፈገግ ብለው "ተቀመጡ" አሉ እሳዩንና ጥላሁንን ፣ ተቀምጠው እያዩዋቸው ።

ግራዝማች ዳኘ ካውራጃው ገዥ የመጣውን መልክት ከመላክቶኛው ተቀብለው ካነበቡ በዙዋላ ፣ ወረቀቱን ቀስ ብለው እፊታቸው አስቀምጠው ቀና ሲሉ ልክ የሚወዱት ውሽማውን ሞት በምሽቁ ፊት እንደሰማ ሰው ሲናገሩት የማይችሉ ፣ ጨካኝ አዘን ልባቸውን ገብቶ ሲያሰቃዩው በፊታቸው ወለል ብሎ ይታይ ጀመር ። መልክቱ የሚበዛውን ጊዜ አለቆች ለጭፍሮቻቸው እንደሚጽፉት ሁሉ አጭር ነው።

"ለግራዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ የየኪ ወረዳ ገዥ ፤ የኪ ። አዲስ የተሾሙት የኢሉባቦር ጠቅላይ እንደራሴ ክቡር ደጃዝማች አበራ ጀንበሩ ፣ መጋቢት 23 . . . ጎሬ የሚገቡ መሆናቸውን ከጎሬ የንደራሴው ጽሕፈት ቤት ስላስታወቁን ፣ ከሌሎች ጋር ሆነን ያቀባበሉን ስኑሰራት እዩተመካከርን ለማሰናዳት እንዲመች ቀደም ብለው ፣ መጋቢት 15 . . . ጌጫ ደርሰው፣ ከዚህ አብረን ወደ ጎሬ እንድንሄድ ይሁን ።" ፊርማና ማህተም ።

ይህ ባጭሩ የተጻፈ .መልእክት አደለም ግራዝማችን ያስደነገጣቸው ፤ በጣም ያሳዘናቸው ። በጣም ያሳዘናቸው ፣ እንደ ውሽማ ሞት ልባቸውን በምስጢር ያስለቀሰው ፣ ያሳመመው ፣ ከመልክቱ ያልተጸፈው ክፍል ፣ ጎሬ ሲደርሱ ሊገጥማቸው የሚችለው ክፉ ነገር ሁሉ ነው ። ጎሬ ካውራጃው ገዥ ጀምሮ ፣ ለጠቅላይ እንደራሴው ፣ በጠቅላይ

@OLDBOOKSPDF

ዲሬክተሩና ፣ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኞች በኩል እሱድ ፣ እስከ ጠቅላይ እንደራሴው ድረስ ፣ የበላይ ሁሉ ፣ እስቃው ሁሉ ፣ ግንድ ላይ ተሰብስቦ የሚገኝበት ነው ። ታዲያ ፣ እስቃ ሁሉ ግንድ ላይ ተሰብስቦ በሚገኝበት መታየት የሚፈልጉ ፣ መልካም እዩሡሩ ስመል ካም ሥራቸው "ትግቢ ጥጋ እሉትክፈሱንም " የሚሉ እንጂ ፣ እመቋ እዩሡሩ ፣ በሡሩት እጦሽ ትገቢ ቅጣታቸውን ያላገኙ አይደሉም ። እመ ጓኞች ፣ "ካይን የራቀ ከልብ ይርቃል " ፣ "እይን ካላይ ልብ አያዝንም" እንደሚባለት ብዙሎች ፣ ከዳኛ ፍርድ ለመራቅ ፣ ከዓይን መራቅ አስፈላጊ መሆኑን ደመ-ነፍሳቸው እየነገራቸው በሚያውቁት፣ ሲሸሹ ነው የሚ ኖሩ ። ስለዚህ ግራዝማች ዳኛ ትሬን እመጽ የፈጸመበት ቁጥር ስፍር የሌ ለው ከሳሽና ፣ ፈርዶ የሚቀጣ ፣ የበላይ ዳኛ ሁሉ ተሰብስቦ የሚገኝበት በመሆኑ ፣ ያስፈሩዎችን እስፈሪ ፣ የሞትን ያክል ይፈሩታል ፤ እጅግ ይጠ ሉታል ፤

ግራዝማች ዳኛ የኪን ተቹመው ካስራ እምቢት እመት በላይ ሲገዙ ፣ ወደ ጎሬ ተጠርተው የሄዱ እጅግ ቢበዛ አራት ጊዜ ያክል ቢሆን ነው ። ታዲያ ፣ እዚያ ሄደው በቆዩበት ፣ በያንዳንዱ ጊዜ የደ ረሰባቸው ችግር ይህን ያክል ነው ተብሎ የሚመዘንበት የሌለው እንኩዋንስ የየኪን ወረዳ ገዥነት ፣ የሙሉ ኢሉባቦርን ጠቅላይ እን ደራሴነት የማያስመኝ ነው ፤ በጎሬ አደባባይ ከሚታየው ፣ የሚበዛው እሳቸውን የሚከስ ነው ፤ ከሳሾቹውና የሚወነጅሉበት ወንጀል ማብ ዛቱ ፤ እሳቸውን እያዩና ጣቱን ወደሳቸው እየቀሰረ የሚያሾከሹከው መብዛቱ ፤ በዚያ መሀል እንኩዋንስ እሳቸው ከሳቸው ጋር የሚሄደ ሁሉ የሚቆምበትን መሬት እንዲያይ እፍረት አይኑን የሚይጋርደውና ጉልበቱን የማያርገደግደው የለም ፤ በያንዳንዱ ጎሬ ሄደው በቆዩበት ጊዜ ሁሉ . ያ ፣ የመጨረሻው የሚሆን መሆኑን ግራዝማች ያልጣሉ በት ጊዜ የለም ፤ "እ . . ይ ፣ ከንግዲህስ በቃኝ ጌታዬ ፤ ያሁኑን ብቻ አውጣኝ እንጂ ፣ ከንግዲህስ ወደ ጎሬ እንኩዋንስ መምጣት ፊቴን አላዞርም ፤ 'ወደ ጎሬ ተጠርተሃል ' ያሉኝ ዕለት ወደ . . ሞቻ ጫካዬ ነው የምሄድ ፤ ከጎሬ አደባባይ የሞቻ ጫካ . . በስንት ጣሙ" ይሻላሉ ።" በሁዋላ ብቻ ለከሳሹም ፣ ላጣላፉም ገንዘብ እዩሰጡ ፣ በገ ዛብ ብዛት ፣ የበደሉትን ሲክሱ ፣ የቀሙትን ሲመልሱ ፤ በመሀላና በግዝት ከሁሉም ከታረቁ በሁዋላ ፣ "የኪን እንደ ግራዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ አድርጎ ሊያስተዳድር የሚችል ስለሌለ ፣ እሳቸውን ከዚያ ማንሳት የኪን መበደል ነው " እያለ ሁሉም ድምጹን ከፍ አድርጎ ባንድ ላይ

@OLDBOOKSPDF

እንዲንጫጫ ፤ ሁሉም የሳቸውን ችሎታና ደግነት ባንድ ቃል እንዲመሰክር ፤ ከታች ከተባባኪው ፲ምር በተራ ጸሐፊው ፤ በመዝገብ ቤቱና በሹማምንቱ ሎሌ ፤ እስከ ባይኛው ባለስልጣን ድረስ በሳጥን ያለ ግዝባቸውን ዉርሰው ፤ መሬታቸውን እያሸጡ አስመጥተው ፤ በዚያ ላይ ባራጣ አዱተበደሩ ዉሥረው ፤ ለሁሉም እንደዬማእርጉ ከከፋፈሉ በሁዋላ ፤ ከዚህ ሁሉ በሁዋላ ፤ በስንት ጭንቅ ፤ በስንት ጣር ወደ የኪ ይመለሳሉ ! ከዚያ ጎሬ የጠፋባቸውን ሁሉ መልሰው ፤ በዚ ላይ አዲስ ሁብት ጨምረው ፤ ደሞ በዚያ ላይ ሌላ አዲስ ሀብት ጨምረው እንዲሁም በሀብት ላይ ሀብት እየጨመሩ ሲሄዱ እንደገና ወደ ጎሬ እስኪጠሩ ጎሬ የደረሰባቸውን ጭንቅ ፤ የጎሬን ጣር ይረሱታል ! ያውና ያን ሁሉ ፤ ያን ጎሬ ሲሄዱ የሚገጥማቸውን ጭንቅ ሁሉ ፤ ያን ጣር ሁሉ ፤ ነበር ያገሰት ፤ አባዬና ጥላሁን ስላዲሱ መሬት ቅዬሳ ሲነግሩዋቸው የሄዱት ዕለት ፤ ያውራጀው ገገር መላከተኛ ከዚያ ኤጭር የጽሑፍ መልክት ጋር ይዞባቸው የመጣ ! ግራዝማች ካውራጀው ገገር የተጻፈላቸውን መልክት ካነበቡ በሁዋላ ቀና እንዳሉ ፤ አይናቻቸውን ሳያረግቡ ፊት ለፊት ተክለው ፤ ጎሬ እሳቸውን ለመቀበል በየረድፉ ተሰልፎ የሚጠብቃቸውን ክፉ ነገር ሁሉ ሲመለከቱ ፤ አባዬና ጥላሁን እዚያ መቀመጣቸውን ረስተውት ነበር !

“እንግዲህ . . . ጌታዬን ስራ እንዳናስፈታ እንሂድ ” አለ አባዬ የግራዝማች ሁኔታ እሱና ጥላሁን ሲገቡ ከነበረው መለወጡን ሲያይ፤ የመጣላቸው መልእክት ደስ የማያሰኝ ለመሆኑ ከዋላ ጎደል ርግጠኛ ሆኖ ።

“እንአ . . ዎ ! ሥራ መፍታት አይገባም ! ኧረ ግዴለም ! ግዴለም ። ምን . . . ደህና ኖሮዋል የመጣችሁ ? ” አሉ ግራዝማች ፤ ያልተያያዘ አሳባቸውን በሚገልጽ ያልተያያዘ አነጋገር ።

“አቶ ጥላሁን መሬቱን ባዲሱ ቀላድ አስለክቶ ለማስቀየስ አስቦ . . . ቀያሾች ከየካቲት በሁዋላ የማይገኙ መሆናቸውን ስለሰማ ፤ ጌታዬ እንዲያስመጡለት ሊለምን ሶስት . . . ጊዜ ያክል ቢመላለስ ፤ ጌታዬ በስራ ላይም ፤ ከንግዳ ጋርም እየሆኑ ስላልተመቸ ፤ እንዳያመልጡት ፤ እኔ ጠይቄ አስመጥቼለት ነበርና ፤ ቀያሾች ከመምጣታቸው በፊት ጌታዬ ፤ አቶ ጥላሁን የሚፈልገውን ተረድተው መፍቀድ ብቻ ሳይሆን በጌታዬ ትእዛዝ እንዲመጡለት ፈልጎ የነበረ መሆኑን ጌታዬ እንዲያውቁት ለጌታዬ ለመግለጽ ነው ዛሬ የመጣን ” አለ አባዬ ። ግራዝማች ፤ ጌታዬ ሲሉዋቸው ስለሚወዱ ፤ “ጌታዬን ” እያደ

@OLDBOOKSPDF

ራረበ እስኪኩብዳቸው አሸከም ። ብቻ ከተናገረው ውስጥ አንድ እው ነት አልነበረም ።

“ ጥሩ ነው እንጂ ፤ ጥሩ አድርጋችሁዋል ” አሉ ግራዝማች ፣ እን ዲሁ አፋቸው እንዳመጣ ። ያ ጊዜ ፣ ግራዝማች ስለ መሬት የሚያስቡ በት አደለም ። ስለ መሬት ያስቡ ፣ ይጨነቁ የነበሩበት ጊዜ ከጥ ቂት ደቂቃዎች በፊት አልፎዋል ። ያ ጊዜስ ፣ እንኩዋንስ አዲስ መሬት ሊፈልጉ ፣ መሸሸጊያ ቦታ የሚገኝ ቢሆን ፣ አቅም ከሌላቸው ሁሉ ስልጣናቸውን ጋሻ አድርገው የዘረፉትን መሬት ሁሉ ፣ ካል ወለዱዋቸው አባቶች በስልጣን እያስፈራሩ የወረሱትን መሬት ሁሉ፣ እዬጠቀለሉ የሚሸሸጉበት ጊዜ ነው !

“ ያውራጃውን ገኘ መልእክት ካነበቡ በሁዋላኮ ፈዘዙ ፣ ምን ይሆን ? ” አለ ጥላሁን ፣ ግራዝማችን ተሰናብተው ከወጡ በኋላ ።

“ እዎ ተለወጡ ፤ አዘኑ ፤ ምናልባት . . . ተጠርተው ይሆናል ። ሌላ ይህን ያክል የሚያሳዝናቸው ነገር የለም ” አለ አሳዬ ።

“ ቢጠሩ ምን ያሳዝናቸዋል ? ”

“ አይወዱም ። ወደበላይ ከሚሄዱ ፣ አይከፍሉ ከፍለው እዚሁ ቢቀሩ ይመርጣሉ ! ለይምሰል ብቻ የየኪን ኑሮ እያጥላሉ ፣ የጎሬን፣ የጌጫን እንኩዋ ኑሮ እያሞገሱ ይናገራሉ ። ታዲያ ሲያብሉ ነው ።”

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፲፱

## የቃልቾቹ ንግሥታት

"ወደዚህ አገር ከመምጣታችን በፊት ፣ ባለቤቴና እኔ በብዙ አገር እዬተዘዋወርን አክመናል ። ነገር ግን የህክምና ስራ በውነት እንደዚህ ደስ የሚያሰኝበት አገር አላዩንም " አሉ ዶክቶር ስቲዋርት ፣ እሳቸውና ባለቤታቸው ፣ ጎራ ለጥላሁንና ለሰራፊ ፣ በሽታዎች የሚታወቁባቸውን ምልክቶችና የመታከሚያቸውን መመሪያ ሲያስጠኑና እዩዳፉ ሲሰጡዋቸው ።

"እንዴት ?" አለ ጥላሁን ።

"ያንዳንድ ጊዜ ደስታችንንማ ተውት ። እኔንም ፣ ባለቤቴንም፣ በጣም ነው የሚገርመን ! በሌላ አገር ቢሆን ኖሮ ገንዘ ከመቅበር በቀር ምንም ያልቀራቸው ፣ የሞቱ መስለው ፣ ባልጋ ተሸክመው የሚያመጡዋቸው በሽተኞች ፣ ትንሽ የክሊኒክ ርዳታ ስናደርግላቸው ነፍስ ዘርቶባቸው ፣ እንደገና ህያዋን ሆነው ይነሳሉ ! አዩ ያንጊዜ ያለን ደስታ ! የዚያን ጊዜ ደስታችን ፣ ሙታን ያስነሳን እንጂ በሽተኞች አከመን ያዳን ያክል አይደለም ! "

"እኮ እንዴት ? እንዴት ነው በሌላ አገር ቢሆን ኖሮ ከሞት ሊተርፉ በማይችሉበት ደረጃ የደረሱ ፣ የዚህ አገር በሽተኞች በትንሽ የ. . .ክሊኒክ ርዳታ ድነው የሚሄዱ ?"

"ምናልባት . . አዬሩም ይረዳ ይሆናል ፤ ያለጥርጥር ይረዳል ። አይነተኛው ምክናያት ግን ፣ የሰዎቹ ሰውነት ታጋይነት ነው " አሉ ሀኪሙ ።

"ሰው . . ከበሽታና ከሞት ታግሎ መዳን ይችላል ማለት ነው ?"

"እንዴታ !" አሉ ዶክተር ስቲዋርት ። "ሰውነት በሽታን እንዲከላከልና እንዲታገል ሆኖ የተሰራ ነው ። ስለዚህ በሽታው በጣም ብርቱ ሆኖ ካቅሙ በላይ ካልሆነ ፣ ብዙ ጊዜ ያለምንም ተጨማሪ የውጭ ርዳታ ብቻውን ታግሎ ያሸንፈዋል ። ስለዚህ ዛሬ በህክምና አለም ያሉ ታላላቅ አዋቂዎች ፣ 'ለበሽተኞች የሚሰጠው መድሀኒ

@OLDBOOKSPDF

ትና ጠቅላላ ህክምና የሰውነትን የመታገል ሀይል አበርትቶ ፣ ሰውነት ራሱ ታግሎ ብርቱዎችን በሽታዎች ጭምር እንዲያሸንፍ የሚያደርግ እንጂ ፣ በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በቀር ፣ በሽታን በቀጥታ የሚያጠፋ ሊሆን አይገባም ’ ይላሉ ። ምክናያቱ በሽታን በቀጥታ የሚያጠፋ መድሀኒት ፣ ወይም ህክምና ፣ ሰውነትን እንዳይታገል በማድረግ ፣ አስንፎና ትግሉን አስረስቶ ፣ ለትናንሽ በሽታዎች የሚሸነፍ ፣ ያለመድህኒት መኖር የማይችል ፣ የመድሀኒት ባሪያ እንዲሆን ስለሚያደርገው ነው ። እንግዲህ በህክምና ረገድ የዚህ አገር ህዝብ ሰውነት ባዲስ አበባና በሌሎች ፣ ህክምና እንደ ልብ በሚገኝባቸው አገሮች ከሚኖረው ህዝብ ሰውነት የሚለይበት አይነተኛ ምክናያት ይህ ነው። መቸም . . . እንደምታውቂት ፣ ከመታገል መበርታት ፣ ከመበርታት ማሸነፍ የሚገኙ ስለሆኑ ፣ የዚህ አገር ህዝብ ሰውነትም ፣ ያለ ህክምና ርዳታ ፣ ብቻውን ሲታገል በመኖሩ በርትቶ ፣ የሚበዛውን ጊዜ በሽታውን ያለመድህኒት ያሸንፋል ። ከዚያ አልፈው ፣ እጅግ ጽኑ በሽታ ታመው ከሞት አፋፍ የደረሱት እንኳ ፣ መጠነኛ የህክምና ርዳታ ካገኙ በሚያስገርም ፍጥነት ወደ ህይወት ይመለሳሉ ።”

ይህን ፣ ዶክቶር ቡቲዋርት ስለ ኢሉባቦር በሽተኞች በሽታን የመታገል ችሎታ እያደነቁ የተናገሩትን ፣ ሶፊያና ጥላሁን ፣ የህክምና ስራቸውን በየኪ እንደ ጀመሩ ፣ በዚያ አገር በሽተኞች ላይ የተመለከቱት ስላረጋገጠላቸው በጣም ይገረሙ ነበር ፤ ቁስል የታመሙት ፣ የቆሰለው ክፍል አካላቸው ለጋው አልፏ ፣ አጥንቱ ፣ ወይም ጅማቱ ፈጥጦ እየታዩ ይመጡና ፣ በፐርማግናንት ይሁን ባልኮል ታጥበው ፣ የሚቀባ የፔኒሲሊን ቅባት ፣ ወይም የሚነሰንስ ዱቄት ከሁለት ፣ ቢበዛ ከሶስት ጊዜ በላይ ፣ ሳይደረግላቸው ፍጹም ድነው ይሄዳሉ ። ራሳቸውን ታምመው የሰነበቱት ፣ አይናቸውን መግለጥ አቅቷቸው ፣ ተደግፈው ይመጡና ፣ አንድ አስፒሪን ቢውጡ ወዲያው ድነው ፣ ምንም እንዳልነበረባቸው እየሳቁና እየተጫወቱ ይመለሳሉ ። ወባ ታመው እንደ ወንዝ ዳር ቄጠማ እየተንቀጠቀጡ ይመጡና ፣ አንድ ኪኒን ውጠው ትንሽ እንዳረፉ ፣ ወባው ድራሹ ጠፍቶ ፣ ደስ ብሎዋቸው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ ። ያባለዘር በሽታ በጽኑ የታመሙት ፣ ከተወሰነው መድሀኒት ግና ግማሹ እንኳ ሳይደረግላቸው ይድናሉ ።

እንግዲህ ጥላሁንና ሶፊያ ፣ ይህን ሁሉ ሲመለከቱ ፣ ባዲስ አበባና በሌሎች ፣ ህክምና በሚዘወተርባቸው ቦታዎች ለሚኖረው ህዝብ የህክምናን ትምህርት ከልምምድ ጋር አጣምረው በያዙ ሀኪሞች የሚደረገው መድሀኒት ፣ ለየኪና ላካባቢው ህዝብ ፣ እንደነሱ የህክምና

@OLDBOOKSPDF

ትምርት ፣ ልምምድም ፤ በሌላቸው ሰዎች ሲደረግ ፤ ብዙ አጥፍ ጊዜ ሲሰምር ሲያዩ ፣ ለዚህ አይነቱ ምክንያቶች ፣ ዶክተር ስቲዋርት እንዳሉት ፣ ያዩሩ ርዳታና የህዝቡ ሰውነት በመድሀኒት አለመስነፍ ፣ ትግሉን አለመርሳት ፤ መሆናቸውን አምኖ ከመቀበል በቀር ፤ መቻስ . . " መድሀኒቱ ካዲስ አበባ ወደ የኪ ስለሄደ ሀይል ጨምሮ ነው ፤ ወይም እንደነሱ የህክምና ትምህርት በሌላቸው ሰዎች ስለተደረገ ነው" አይባል ፤ ብቻ ያም ሆኖ ፤ አንዳንድ ጊዜ ፣ እነዚህ ምክንያቶች ሲያጠግቡዋቸው የማይችሉበት አጋጣሚ ይገጥማቸውና፣ ለባቸው ፤ አእምሮዋቸው ተቀብሎ ያመነባቸውን ምክንያቶች ትቶ፣ ሌላ ምክንያት ፍለጋ ይሄዳል ። ይህ አጋጣሚ ፤ ይህ ከአምሮ ያለተቁለፈ ሆኖ ሁሉ ውጭ የሆነ አጋጣሚ ፤ አንዳንድ ፤ "በግዚአብሄር ታምር ካልሆነ ፤ ሊተርፉ አይችሉ" የሚባሉትን በሽተኞች ፣ በባለ ቁርጠኞች ተከፋ አለመቁረጥ ምክንያት ፣ ወይም እነሱን ለመፈታተን የሚፈልጉ ከፍሎች ፤ ሊያመጡባቸው የሚደርስው ነው ። እንዲህ ያሉት ፣ ዶክተር ስቲዋርት እንዳሉት "ገዝ ከመቅበር በቀር ምንም ያልቀሩቸው ። የሞቱ መስለው ባሉ ተሸክመው የሚያመጡዋቸው" በሽተኞች ፤ አንዳንድ ጊዜ ደረታቸውን ባልቦሌ በማኘሸት ብቻ ፤ ወይም አፍን በፋቸው አጣብቶ ወደ ውስጥ በመተንፈስ ብቻ፣ ወይም እንደ ማሎክ ያለ ብርታት የሚሰጥ ህክምና ብቻ ፤ ሲደረግላቸው ለቀልድ ፣ ለጭዋታ ፣ ሞተው እንደ ቆዩ ሁሉ ፣ አይናቸውን ገልጥ ያደርጉና ፈገግ ይላሉ ፤ ያን ጊዜ ፣ እንዲህ እንዲህ ያለውን ሲያዩ አእምሮዋቸው ያለተቀበለው ሆኖ ተከትሎ የሚያቀርበውን ምክንያት ሁሉ ትተው ፣ ሌላ ፣ እግዚአብሄር በነሱ አድሮ ታምር እንደ ሰራ ያምኑና ፤ እግዚአብሄር መሳሪያዎቹ እንዲሆኑ የመረጣቸው መሆኑ ይሰማቸውና ፤ ደስታቸው ወሰኑን ሁሉ ፤ ዳር ድንበሩን ሁሉ አልፎ፣ ሲሰሩ ውለው ፣ ሲሰሩ ሲያድሩ ድካም አይሰማቸውም ፤ እንቅልፍ አይመጣባቸውም ። መቸም ቁርስና ራት ካልሆነ ፣ ምሳ በልተው አያውቁ !

ሶፊያና ጥላሁን ፣ በህክምና ስራቸው ካገሩ ህዝብ ጋር የተዋወቁ ወዲያው የኪ እንደ ደረሱ ፣ በቡና ለቀማው ወራት ነው ። ቡና ለቀማ ከሚመጡት ሰዎች ድንገት የሚታመሙትን ፣ ወይም የወባና ሌላ መንገር የሚነሳባቸውን ፣ እዚያው አስራው ላይ እንዳሉ ፣ ጥላሁን አከም አሽሎዋቸው ስራቸውን ሲቀጥሉ ሲያዩ ፣ እንዲሁም ያሟያና ታመው እቤት የተኙ ዘመዶች ያሉዋቸው ፣ ጥላሁንን ፣ ወይም ስሬ

ያን እንዳያክሙላቸው ጠይቀው ፣ እያከሙ ባጭር ጊዜ ሲያድኑአቸው ሲያዩ ፣ ያዩ ያዩትን እያጋነኑ ባላዩት ሲያወሩ ፣ ያን ወሬ የሰሙ ፣ በሰሙት ላይ ያልሰሙትን ጨምረው ሲያወሩ ፣ ደግሞ እነሱ በሰሙት ላይ ያልሰሙትን ጨምረው ሲያወሩ ፣ እንዲሁ ወሬ ወሬን ሲወልድ፣ እየተባዛ ፣ ዝናቸው ተጋንኖ በያቅጣጫው ስለ ተነዛ ፣ የየኪና ያከበቢው ህዝብ ብቻ ሳይሆን ፣ ከሩቅ አገርም ስንቁን ጭኖ የሰዙ ቀን መንገድ እየተጓዙ ፣ ለህክምና ወደነሱ የሚመጣው ህዝብ እየደረ እየበዛ ሄደ ። ስለዚህ የቦታ ችግር በመፈጠሩ ፣ እስኪሰሩ ድረስ ለጊዜው የየኪ ትምህርት ቤት ባዶ ስለነበረ ፣ የወረዳውን ገዢ ፣ ግራዝማች ዳኛቸው ፍራሳን አስፈቅደው ፣ የህክምና እቃቸውንም ሆነ መድሀኒታቸውን እዚያ አስገብተው ፣ እያስጠበቁ ያክሙ ጀመር ። ትምህርት ቤቱ ግራዝማች ዳኛቸው ፣ ሹምና አስተማሪ የነበረውን ፣ ቀኛሁን ፈይሳን አስደብድበው ፣ ምሽቱን ሲቀሙት ፣ እናቸውን አገድለ ሰሁ” ብሎ ጫካ በገባ ጊዜ ፣ እንደ ተዘጋ ሳይከፈት ሁለት አመት ሊሞላው ምንም ያክል አልቀረው ። ቀኛሁን ራሱ ፣ ወንድይራድ እስ ኪያስቀርበት ድረስ ተቀጥሮ ሲመጣ የነበረ ፣ በዚህ ምሽቱን ስለተ ቀማ በሸፈተው ቀኛሁን ምትክ ፣ እዚሁ ትምህርት ቤት ነበር ።

መቸም ፣ ወሬ ከተነሳበት እየራቀ በሄደ መጠን ፣ ሲጋነን፣ ሲጋ ነን ፣ አንዳንድ ጊዜ ሲነሳ ከነበረውም ተለውጦ ሌላ ነው የሚሆን። እንደዚሁ ፣ የሶፊያና የቀኛሁን ወሬ ፣ ሁኖላ ሁኖላ እያደር እየሰከነ፣ ስራቸውን በውነተኛ መልኩ የሚገልጽ መሆን እስኪጀምር ፣ በመጀ መሪያ ፣ ገና ባፍላ ፍላቱ ሳለ ፣ ከሰዎች ተራም አውጥቶ ባግልከት ቦታ አስቀምጦ አሳይቶዋቸው ነበር ። ታካሚዎች ብቻ ሳይሆኑ “እወ ቂልን” ባዮች ጭምር ፣ ከሩቅ እየመጡ በትምህርት ቤቱ ዙሪያ እንደ ጠበልተኞች ጊዜያዊ ጎጆዎቻቸውን ሰርተው ተቀምጠው፣ ደጅ ሲጠኑ የሚሰነብቱ ብዙ ነበሩ ። ምክንያቱ ፣ በዚያ አካባቢ ግናቸውንም በሽታ ሲያመጡ የሚችሉ መናፍስት ብቻ መሆናቸውና ፣ በሽታን ማዳንም የሚችሉ መናፍስትን ሁሉ የሚገዙና የሚያዝዙ ብቻ መሆ ናቸው ፣ መናፍስትን ከገዙና ካዘዙም ፣ የመናፍስትን ምስጢር ሁሉ የሚያውቁ መሆናቸው በጽኑ ስለሚታመን ነው ።

“ ምን እነሱ . . . .እንኳንስ ያክሙት የነኩት ሁሉ ነው እሳ የሚድነው ! ” ይላል አንዱ ።

“ የምን መንካት ! አንተ ብቻ በሽተኛሀን ወስደህ . . . እፊታ ቸው ማጋደም ብቻ ነው ! እዚያ አይናቸው ሲያርፍበት ፣ ወይ ጥላ ቸው ሲወድቅበት ፣ ተነስቶ ቁጭ ነው እሱ እንጃ ! ” ይላል ሌላው

@OLDBOOKSPDF

“ ኧረ እዲያው . . . የነሱስ ነገር ተወርቶ አያልቅም ፤ ሙት ሲያስነሱ ምንም አልቀራቸው ነውኮ የሚባለው ! ” ይላል ደግሞ ሌላው ።

“ አንተ ደግሞ ሙት ሲያስነሱ ምንም አልቀራቸው ትላለህ ? ሙት ያስነሳሉ አሉ እንጂ ! ሬሳው ትኩስ ከሆነ ፣ ሄደው ብቻ ባፉና ባፍንጫው ‘እፍ ፤ እፍ ’ ሲሉበት . . ባንድ ጊዜ ነው እሉ ብድግ ብሎ ቁጭ እሚል ! ’ ይላል አሁንም ሌላው ።

“ ደግሞ እሚናገሩት ሁሉ አንድ እንኳዋ እመሬት ጠብ አይልም አሉኮ ! ‘ ይህን ብታረግ ጌታ ትሆናለህ ፤ ያን ብታረግ ድሀ ትሆና ለህ ፤ ይህን ብታረግ ትሞታለህ ፤ ያን ብታረግ ትኖራለህ ’ የሚሉት ሁሉ ልክ እንዳሉት ይሆናል አሉ ! ”

“ ደግሞስ . . . ያገር ምድሩን ቃልቻ ሁሉ ማስደግደጋቸውን ሰምተሀል ? ”

“አልሰማሁም ። ቃልቻው ሁሉ ለነሱ ታጠቀ አሉ ? ”

“ እንዴታ ! ቃልቻ የተባለ ሁሉ ፣ እነሱን ከብቦ የሚታከመው ሲታከም ፣ የሚለማመነው ሲለማመን ነው አሉ እሚውለው ! ”

“ እንግዲያማ . . . የቃልቾች ሁሉ ንጉሶች መሆናቸው ነዋ ! ”

“ ቢሆኑ ነው እንጂ . . . ባይሆኑ ትልልቆች ቃልቾች ሁሉ እዬ ሄዱ ይሰግዱላቸው ኖሯዋል ? ወንድየው የቃልቾች ንጉስ ፣ ሴትየዋ የቃልቾች ንግስት ቢሆኑ ነው ? ”

“ ግሩም ነው ፤ ታዲያኮ ገና አንዳንድ ፍሬ ልጆች ናቸው አሉ ! ”

“ እዝጌር ሰውን የሚመርጠው በጣንነቱ ነው ይባልየል ? ለዚህ ነው ። ”

መቸም እንዲህ እንዲህ ያለው ፣ መጠኑን ሁሉ አልፎ ፣ እዬተ ጋነነ የሚወራ ወሬ ፣ ጥላሁንንና ሶፊያን የየኪና ያካባቢው ህዝብ ምን ያክል ከፍ አድርጎ ፣ እንኩዋንስ ከተራ ሰዎች በዚያ ክፍል እጅግ ከሚፈሩትና ከሚከበሩት ፣ ከቃልቾች አልፎ መመልከት እንደ ጀመረ የሚያሳይ ከመሆኑ በቀር ፣ ከውነቱ ጋር ይዛመዳል የሚባል አይደል ! ይሁን እንጂ ፣ በሽታ ሳይቆይባቸውና ሳይጎዱ ፣ በጊዜ መጥተው የሚ ታከሙት ሁሉ ፣ በቀላሉ መዳናቸውና በሽታ ቆይቶባቸው ከተጎዱ በሁዋላ ከሚመጡትም መሀከል ፣ ብዙዎች የሚድኑ መሆናቸው እሙን ነበር ።

ሶፊያንና ጥላሁንን ፣ የኪ በህክምና ስራቸው ካገሩ ህዝብ ሰው ነት በሽታን የመታገል ችሎታ ሌላ ያስገርማቸው የነበረ ፣ ለህክምና

@OLDBOOKSPDF

ወደነሱ ከሚሰበሰበው በሽተኛ በጣም የሚበዛው ፣ ምናልባት ከመቶ ዘጠና አምስት እስከ ዘጠና ሰባቱ ታምሞ የሚመጣው እንደ ወባ ፣ አባሰዘር ፣ የቆላ ቁስል ፣ አሜባ ፣ አይነማዝ ፣ ተራ ራስ ምታት ፣ ተራ የሆድ ቁርጠት ፣ ተላላፊ በሽታና እነዚህን የመሳሰሉ ፣ ምርመራቸውም ሆነ ህክምናቸው እጅግ አስቸጋሪ ያልሆነ እንጂ አዲስ አበባ ስማቸውን ሲሰሙ የሚፈሩዋቸው ፣ የጠለቀ ምርመራና የተራቀቀ ህክምና የሚያስፈልጋቸው በሽታዎች ፣ በጣም አልፎ አልፎ ካልሆነ ፣ አጋጥመዋቸው የማያውቁ መሆናቸው ነው ። እንዲህ አልፎ አልፎ ምርመራቸው ፣ ወይም ህክምናቸው አስቸጋሪ የሆነ በሽታ የታመሙ በሽተኞች ሲያጋጥሙዋቸው ፣ በሽተኞቹ ሲፈቅዱ ፣ እነጥላሁን ገንዘብ እየከፈሉ ወደጎሬ ይልኩዋቸው ነበር ።

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፰

# አሳብ አሳብን ይወልዳል

ጥላሁንና ሶፊያ ፣ አምስት ቀዳድ ማተሚ ከነሬ አስመጥተው ለየኪ ጣማዎች ፣ ሸኮዎችና መሰንጎዎች ፣ እያሸነሸኑ ለማከፋፈል የመደቡት መሬት ፣ “ በትርፈ ሳበው ምት ” አሥራ ዘጠኝ ጋሻ ሆነ ። ይህም አስራ ዘጠኙ ጋሻ ፣ ውብቱ በዛብህ ለጥላሁን ግዞት የሰጠው አምስት ጋሻ ፣ ሁዋላ ጥላሁንና ሶፊያ በርካሽ ፣ እያንዳንዱን ጋሻ ባምስት መቶ ብር ፣ ገዝተው የጨመሩት ስድስት ጋሻ ፣ ሰባት ባለብዙ ርስት ባላባቶችና ቃሌቾች ፣ እያንዳንዱ በነጻ የሰጡት አንዳንድ ጋሻ ተደምሮ ፣ ሰባት ጋሻ ፣ አሳዬ መብራቱ ፣ ምንም እንኳ በጥላሁንና በሶፊያ አሳብ ባይስማማ ፣ እንዲያው እነሱን ደስ እንዲላቸው ብቻ ፣ ያኑ የነበረውን አንድ ጋሻ መሬት ስለሰጠ ፣ ከዚህ ሁሉ የተጠረቃቀመ ነው ።

ቃዲያ ይህ ፣ “ በትርፈ ሳበው ምት ” አስራ ዘጠኝ ጋሻ መሬት ባራት መቶ ሺህ ማሽዘን ሜትር እዩታሰበ ወደ ዘመናዊ ቀላድ ሲለወጥ ፣ አንድ ሙሉ አስራ ሁለት ጋሻ ስለሆነ ፣ ከዚህ አንድ ጋሻ ጥላሁንና ሶፊያ ፣ አንድ ጋሻ አሳዬ ፣ ለየራሳቸው እንስተው ፣ የተረፈው አንድ መቶ አስር ጋሻ ፣ እንደገና በሩብ በሩብ ጋሻ እዩተሸነሸነ ፣ ባራት መቶ አርባ ቤተሰብ በርስትነት ተደልድሎ ፣ ለያንዳንዱ የቤተሰብ አባት ፣ ከፍርድ ቤት የባለርስትነት ማስረጃ ፣ ወይም የምስክር ወረቀት ጋር ተሰጠ ።

“በዚህ ነገር እንደማቃምንበት ፣ እንዲያውም እንደምትቃወመው ነግረኸናል ። ቃዲያ . . ለማቃምንበት ፣ ለምትቃወመው ነገር ያችኑ ፣ ያለችህን አንዷት ጋሻ መሬት የምትሰጥበት ምክናያት ምንድነው ? ” አለ ጥላሁን ፣ “ አሳዩ አንድ ጋሻ መሬቱን መሬት ለሌላቸው ሰዎች ከሚያለያለው መሬት ጋር ተጨምሮ ይቃየስ ” ሲል ።

“ እናባ ጋሮ ፣ እናባ ዱሻና ፣ ሌሎችም በኩርማን ጋሻ ሲተናነቱ የሚኖሩት ሁሉ ወይውት ነው አንዳንድ ጋሻ መሬታቸውን የሰጡ ? ” አለ አሳዬም በቀልድ ።

@OLDBOOKSPDF

"እነሱማ . . ምነው ነግሬህ ! እነሱማ መሬታቸው ሁሉ ባዲሉ ቀላድ የተለካ እንደ ሆነ ጉድ የሚፈላ ስለሆነ ፣ እንዳይለካባቸው እንተን እንድናግልጻቸው ጉቦ መስጠታቸው ነው !"

" እኔ ደግሞ . . ድሮውንም ሰው ሲገዛ አይቼ ፣ ወዲያውም ዋጋው ርካሽ ስለሆነ የገዛሁት እንጂ ፣ መሬት አልምቶ ለመጠቀም ፍላጐቱም ፣ ጊዜውም ኖሮኝ የገዛሁት አልነበረም ። አሁንም ሰው ሲያደርገው ያዩሁት እንዳይቀርብኝ ፣ ' ከማን አንሼ ' እንደሚሉት . . . ሰዎች ሲሰጡ መስጠት አለብኝ !" አለ አሳዬ ፣ "እናንተን ደስ ለማሰኘት ነው " ላለማለት ያክል የማይሰማሙ ቃሎች ከዚህም፣ከዚያም ባንድ ላይ አጠረቃቅሞ ።

"የለም አሳዬ ፤ ከዛሬ ቀደም ' ዘመናዊ የቡና እተካከልና እያያዘ ለዚህ አገር ሕዝብ እሳይበታለሁ ብዬ የገዛሁት ነው ' ብለኸኛል ። ታዲያ እንዲያ ያለው የተቀደሰ አሳብ ሲቀር የማይገባው ፣ ለተቀባዩ ሕዝብም ካንድ ጋሻ መሬት የበለጠ የሚጠቅመው ስለሆነ ፣ መሬቱ በጅህ ቆይቶ ፊት ላቀድኸው ቢውል ይሻላል ።"

"እ . . እሱ ! እሱ ከገዛሁት በሁዋላ ' ለምን ገዛሁት ? ' ብዬ ራሴን ስጠይቀው ፣ ለምክናያት ያክል የፈጠረው መልስ ነው ! ብቻ . . አሁንም ቢሆን ፣ ጊዜውና ትጋቱ ከተገኘ ፣ ለህዝብ ማስተማሪያ ያክል . . ' የትርፌ ሳበው ' ቀላድ ባዲሉ ቀላድ ሲመነዘር ፣ ያለጥርጥር ብዙ ስለሚሆን ከዚያ አንድ ጋሻ እወስዳለሁ ፤ ግዴለም " አለ አሳዬ ። እውነትም "በትርፌ ሳበው ምት " እንዳ ያሳዩ ቀላድ ባዲሉ እስር ቀላድ ሆኖ ዘጠኙ ለመዋርሙው ሲሄድ አሳዬ አንድ አስቀረ ።

አራት መቶ አርባው የሸኮ ፣ የመሰንጎና የጣማ ቤተሰብ አባቶች ፣ ሩብ ሩብ ጋሻ መሬት በዩስማቸው ፍርድ ቤት መዝገብ እያስገቡ የባለርስትነት መታወቂያቸውን ሲወስዱ ፣ ጥላሁን ምናልባት ከሽኮኞችም ሆነ ከመሰንጎዎች ፣ ወይም ከጣማዎች መሀከል ፣ ይህን በርስትነት የወሰዱትን መሬት መሸጥ የሚፈልጉ ቢኖሩ ፣ እዚያው ለወገኖቻቸው ካልሆነ ከወገኖቻቸው ውጭ ለማንም እንዳይሸጡ ፣ ሁሉም ውሉታ እንዲፈርሙ በጣም ፈልጎ ነበር ። ምክናያቱም እንደ ድሮው ርስታቸውን ሸጠው ጨርሰው ፣ እነሱ ርስት - የለሾችና ላገራቸው ባእዶች እንዳይሆኑ ነው ።

" ርስት ሰጥቶ 'ለምትፈቅዱት አትሸጡ ፣ አትለውጡ ?' ይህማ . . . 'ሱሪ አውሶ አትቀመጡበት ' ነው ፣ ልጁ ! ይህን ጭራሽ እንዳይሰሙህ ።

@OLDBOOKSPDF

‘ትሉትንም፣ እንዳይለግም’ ቅበ ይል ። በጣምክ ፣ ከሩዎች ፍቻዎቹ ቴ እግዜር በስሬ መሬት የኑሱን ያክል ከፉ አልፈጠረም ! ” አሉ ባላምባራስ ግንድያ ሬን ፣ የጥላሁንን አሳብ ሲሰሙ ።

“ ቡሬ እጦብ አትቀመጥበት ? ምን ማለት ነው ፤ ” አለ ጥላሁን እዩሳቀ ።

“ ባላምባራስ የተረት መድብል መሆናቸውን አታውቅም ? ” አለ አሳዩም እዩሳቀ ።

“ ቡሬ እጦብ አትቀመጥበት ” የኛ የባላገሮች ተረት ነው ፤ እማርኛው . . . ክበጡ ሰዋዊ ገም ነው እንጂ ፣ በስጡት ነገር “ይህን አርጉበት ፣ ያን አታርጉበት ” ማለት ፣ የሰጭውን ትልቅነት ፣ የተቀባዩን ትንሽነት በዩጊዜው የሚያስታውስ ስለሆነ ፣ በተቀባዮች ዘንድ አይወደድም ማለት ነው ። ስለዚህ አንድ ጊዜ ከሰጣችሁዋቸው በሁዋላ ፣ የነሱ ንብረት ስለሆነ ፣ በንብረታቸው የሚፈልጉትን ማድረግን ለነሱ መተው ነው ። “ ይልቅስ ያ ፣ የፊቱ አባባችሁ ከሁሉም የሚሻል ይመስለኛል ” አሉ ባላምባራስ ፣ አይኖቻቸውን ፊት ለፊት ተክለው ትንሽ ሲያስቡ ቆዩና ።

“ የቱ ? ” አለ ጥላሁን ።

“ አልምኖ መስጠቱ ። የለማና አለቱን ጥቅም የሚሰጥ መሬት ከሆነ ምናልባት አይሸጡም ይሆናል ። ”

“ የለማና አለቱን ጥቅም የሚሰጥ መሬት እንዴት ያለ ነው ? ዛሬ ቡና ተተክሎ እንኳንስ አለቱን ባመቱ ፣ ጥቅም የሚሰጥ መሬት አለ ? ቡና እጅግ ፈጠነ ቢባል . . . በሶስት አመቱ ነው የምስራች የሚለጠው ” አለ አሳዩ ።

“ ልክ ነው ፤ ቡና ከሶስት አመት በፊት ጥቅም አይሰጥም ፤ ያውም ሲፈጥን ነው ። ነገር ግን . . . የነዚህ ሰዎች መሬትኮ ፣ ሁሉም ቡና ብቻ የሚተክል በባልመሰለኝ ነው ። እንዲያውም እንዲኢማ . . . የሚበዛውን ባጭር ጊዜ ለሚደርስ ፣ ቶሎ ደርሶ ለሚበላ ነገር ማድረጉ የሚሻል ይመስለኛል ” አሉ ባላምባራስ ።

“ ለምሳሌ እንዴት ባለ ነገር ? ” አለ አሳዩ ።

“ እ . . . ! ለምሳሌማ ፣ እንደ በቆሎ ፣ ዶንቃ ፣ ድንች ፣ ጎመን ፣ ዱባ ፣ ጎደሬ ፣ ካሮት ፣ ኮቴሀሬና እንዚህን ለመሳሰለው ሁሉ ። እንዲህ እንዲህ ያለ ፣ የሚበላ ነገር እዩጠፋ አደለም . . . እንዚህ ሰዎች

ክረምት ክረምት @OLDBOOKSPDF በንጨትና ባረግ ሰራስር .. ካውሬ ጋር ሲጣሉ የሚከርሙ ?”

“ በጣም ጥሩ ኢሳብ ነው ፣ አባባ ” አለ ጥላሁን ፣ የባላምባራስ ጉዳታ አሳብ ደስ ስላሰኘው ፣ እጃቸውን በሁለት እጆቹ ጥብቅ አድ ርጎ ይዞ ። “ በጣም ጥሩ አሳብ ነው ። እንዲያውም ፣ ስያንዳንዱ የቤ ተሰብ አባት ከተሰጠው መሬት ሩብን ብቻ ለቡና መትከያ መድብ ትቶ ፣ ሶስቱን ሩብ ፣ ቶሎ ደርሶ ለሚበላ ነገር ማድረግ ነው ። ደግሞስ . . ስሩ እየተቆፈረ የሚበላው የዱር አረግና እንጨት ፣ ምግብነቱ ያን ያክል አስፈላጊ ሆኖ ካውሬ ጋር የሚያጣላ ከሆነ ፣ አምጥቶ በየጎጥርው ቢተ ክሉት ምናለ ? የሚከፋ ይመስልዎታል ?”

“ምን ይከፋል ! ይበጃል እንጂ ! ሀ ! ‘አሳብን አሳብ ይወልደዋል’ የሚሉት እዮትላችሁ እንዲህ ነው ! ” አሉ ባላምባራስ ፣ የሳቸውን አሳብ አስከትሎ ጥላሁን ያመጣውን አሳብ ሲሰሙ ።

ባላምባራስ እውነታቸው ነው ! አሳብ አሳብን ይወልዳል ! አሳብ ዘረ - ብዙ ፣ እንደ ዱር አረግ ቅርንጫፉ ብዙ ነው ! ልዩነቱ ፣ ያሳብ ቅርንጫፍ እንደ ዱር አረግ ቅርንጫፉ መጨረሻ ያለው አለመሆኑ ብቻ ነው ! የዱር አረግ ፣ እያንዳንዱን ቅርንጫፍ ይዞ ሲስቡት ፣ ቀድሞ ያልታዮው ሁሉ ከዩተሸሸገበት ተሳስቦ ፣ እዩተከታተለ እንደሚመጣ አሳብም እንደዚያው ነው ! አንዱን ይዞ ሲስቡት ፣ ሌላው ተከትሎ ይመጣል ። ሶፊያና ጥላሁን አንድ ነገር ሲያስቡ ፣ ወይም ሲሰሩ ፣ ያ ያሰቡት ፣ ወይም የሰሩት ሌላ ሊሰሩት የሚገባቸውን ነገር ሲያሳስባ ቸው ፣ ያ በበኩሉ ሌላ መስራት ያለበትን ነገር ስቦ አምጥቶ ሲያ ሳያቸው ፣ ያ እንደገና ፣ ከተሰራው የበለጠ የሚመስል ነገር ጎትቶ አምጥቶ እንዲሰራ ሲያባብላቸው ፣ ደግሞ ያ ሌላ ፣ እሱ ካልተሰራ የተ ሰራውን ሁሉ እንዳልተሰራ የሚያስቆጥር ነገር አምጥቶ ሲያሳያቸው ፣ እንዲሁ እያንዳንዱ የሰሩትና ሊሰሩት ያሰቡት ነገር ሁሉ ፣ አዲስ ነገር እያስከተለ እዩመጣ እንዲሰሩ ሲያባብላቸውና ሲያስገድዳቸው ፣ “በነሱ አቅም ተሰራ ” ተብሎ ሊታመን የማይችል ብዙ ግሩም ግሩም የሆነ ስራ ሰሩ ።

በየኪና ባካባቢው እንደ ቃልኞች ነገስታት ካስቆጠራቸው የሀ ክምና ስራቸውና ፣ ባጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ማይሞች ያማርኛ ንባብና ጽሕፈት ፣ እንዲሁም በሂሳብ አራቱን መደቦች ፣ አካባቢን በጽዳት መጠበቅና የጤና ጠንቆች ማጥፋት ከማስተማራቸው ሌላ ፣ ከተጠራ

@OLDBOOKSPDF

ሚው ሕዝብ የበለጠ [illegible] ሁሉንም ፣ ዘላቂታ ደስታ ከሰጡዋ ቸው ስራዎቻቸው መሀከል አንዱ ፣ በየኪና ባካባቢው ፣ በዬመንደሩ ውሀ ለማስገባት መቻላቸውና ስራውን የሰሩበት ዘዴ ነው ።

ያ ከፍለ ሀገር ፣ በተለይ የኪ ፣ ወንዞች እጅግ የበዙበት ፣ ወደያውም የኒያ ወንዞች ውሀ በጋ ከክረምት መጠኑ የማይቀንስ ፣ መልኩ የማይደፈርስ ፣ ሁልጊዜ ኩል ፣ ሁልጊዜ ሀብረ-ብማይ እንደ መሰለ የሚኖር ሆኖ ሳለ ፣ እንደ መልካሙ ነገር ሁሉ እንዲሀ በቀላሉ እንዲሀ እንደ ልብ የሚገኝ አደለም ! የየኪ ወንዞች ፣ "ከዚሀ በቀር" የሚባል የሌለባቸው ፣ ሁሉም ገደላማና ጥልቅ ሸለቆ ተከትለው የሚ ሄዱ ስለሆኑ ፣ ክረምት ከዳጥ ፣ በጋ ካራራ ፀሐይ እዬተጋደሉ ፣ ከዚያ ውሀ ቀድተው እቤታቸው የሚገቡ ሴቶች እጅግ ብርቱዎች ብቻ ናቸው ። ያልበረቱ ፣ ሲወድቁ ሲነሱ ውለው ፣ መቅጃቸውን እዬሰበሩ ፣ ባዶዋ ቸውን ይመለሳሉ ። ስለዚሀ ፣ አብዛኛው ህዝብ በውሀ ተከብበ ፣ በጥም ሲሰቃይ ይኖራል ። የየኪንና ያካባቢውን ህዝብ ከዚሀ ስቃይ የሚያድን መድሀኒት ፣ የየኪንና ያካባቢውን ህዝብ ከጥም ብቻ ሳይ ሆን ፣ ከራብና ከጽዳት ማጣት የተነሳ ከሚመጣ በሽታ ጭምር የሚ ፈውስ መድሀኒት ፣ ጥላሁንና ሶፊያ ያቶ ህሩይ ዳምጤን ወፍጮ ሲጎበኙ አገኙ !

አቶ ህሩይ ፣ ካንድ ገደል ላይ ፣ ያንድ ትልቅ ወንዝ ውሀ መል ሰው ፣ ቀጥታው ከታወቀለት ፣ የየኪ ዋንዛ ሰፋትና ጥልቀት ያላቸው፣ ብዙ ረገሻርም ግንዳዎች አስፈልፍለው ፣ አሰበሳቸው ፣ እያሰካኩ በሚ ስማር ቀጣጥለው ፣ የመለሱትን ውሀ ፣ በኒያ ግንዳዎች ተቀብለው፣ በረገሻርም የዛፍ ባላዎች ላይ ካንዱ ወደ ሌላው እያሸጋገሩ ፣ ዛፍ በሌለበት ገደላማ ቦታ ሲደርሱ ገደሉን ቆርቁረው እያመቻቹ ፣ እሜዳ ሲደርሱ ጥንድ ጥንድ ግንዲላዎች ተክለው በመሀከላቸው ኮርቻ እያ ሰሩና ፣ ቆርቁረው ባመቻቹት ገደል ፣ ወይም በግንዲላዎች መሀከል በሰሩት ኮርቻ ላይ ግንዳዎችን እያስቀመጡ ፣ ቢያንስ አምስት ኪሎ ሜትር ያክል ወስደው ፣ ወዳንድ ምቹ ቦታ ሲደርሱ ፣ እዚያ ወፍጮ ተክለው ፣ ለየኪ ከተማና ላካባቢው ህዝብ እህል ያስፈጯሉ ።

"እዬህልኝ ይህን ብልሀት እባክህ ? በቦምባ ፈንታ በግንዳ ይህን ያክል ውሀ ከዚያን ያክል ሩቅ አገር ተራራ አዙሮና ሸለቆ አሻግሮ አምጥቶ ፣ እንዲሀ ያለ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ ፣ ግሩም የሆነ ብልሀት አደለም?" አለች ሶፊያ ፣ ጥላሁንና እስዋ ያቶ ህሩይን ወፍጮ መጀመሪያ ሲያዩ በጣም ተገርማ ።

@OLDBOOKSPDF

"በጣም የሚ[illegible] ጓንጂ ! ይህን ያክል ውሀ ከዚያ ገደል አውጥቶ ፣ ይህን አቀበትና ቁልቁለት አሻግሮ ፣ እዚህ ለማድረስ የዘመኑን መሀንዲሶችና ተቋዋራጮች 'ስሩ' ቢሏቸው . . . እንጃ ፣ ያለ ጥርጥር ብዙ ሚሊዮን ይጠይቁ ነበር!" አለና ጥላሁን ፣ ትንሽ ዝም ብሎ ከገንዳው እየተጥመለመለ የሚወርደውን ረዥምና ሀይለኛ ፏፏቴ ሲመለከት ቆይቶ "ብቻ ያልገባኝ አንድ ነገር ነው" አለ ።

"ምን ?" አለች ሶፊያ ።

"መቸም . . . ይህን በዚህ አይነት ዘዴ ውሀ ካንድ ቦታ ወደ ሌላ ማሸጋገር ፣ እኒህ ሰው አሁን አልፈጠሩትም ፤ የቆየና የተለመደ ብልሀት መሆን አለበት ። ታዲያ እንዲህ ያለ ብልሀት እየታወቀ ፣ ለምን ሰው በውሀ ጥም ያልቃል? ለምን በዚሁ ዘዴ በየመንደሩ ውሀ አይገባ? "ሶፊያ ለጥላሁን ጥያቄ መልስ የሌላት መሆንዋን ለመግለጽ ፣ ከንፈርዋን ገጥማ ፣ አገጭዋን ወደ ታች ሳብ ፣ ትከሻዎችዋን ወደ ላይ ገፋ አደረገች ።

ያቶ ሀሩይ ዳምጤን ወፍጮ ትብኝተው የተመለሱ እለት ፣ ሌሊቱን ፣ ጥላሁን ባይኑ እንቅልፍ ሳይዞር አደረ ። ልክ አቶ ሀሩይ ዳምጤ እንዳደረጉት ከየወንዙ ውሀውን በጥንዛ ገንዳ እየመለሰ ፣ ተራራውን እያዞረና ሸለቆውን እያሻገረ እያመጣ ፤ በየኪና ባካባቢው ባለው መንደር ሁሉ አግብቶ ለቀቀው ፣ ከየፏፏቴው ሲንፏፏ ፣ ከየቦዩ ሲንቡጥቡጥ ይታየዋል ! ከዚያ እንዲያ ከየፏፏቴው እየተንፏፏና ከየቦዩ እየተንቡጥቡጥ ከመጠጥና ከጽዳት የሚተርፈው ውሀ ፣ እንዲሁ እንዳይባክን ፣ በየመንደሩ ሰፋፊ ማጠራቀሚያ እያስቆፈረ ፣ ከውጭ በድርፍ የተደገፈ ያፈር ግድብ አስገድቦ ፣ ታላላቅ ኩሬ እንዲፈጠር ያደርግና ፣ የየመንደሩ ሰው ሁሉ ከዚያ ኩሬ ውሀ እየመራ እየወሰደ ፣ ባላምባራስ ጉዳታ ራን እንዳላሰቡት ፣ በየጉጥርው ያዘመረውን ልዩ ልዩ አዝመራም ፣ የተከለውን ልዩ ልዩ አትክልትም ፣ እያጠጣ ፣ የኪና አካባቢው አመት ሙሉ እሸት ሲበላበትና ምርት ሲታፈስበት የሚኖር አገር ሆኖ ይታዩዋል ! የኪንና አካባቢውን ዝናብና ውሀ ተጋግዘው በጋ ከክረምት ቡቃያ ፣ አበባ ፣ እሸትና ምርት የማይለዩት ፣ አምሳለ ገነት ሲያደርጉት ይታዩዋል! ራብ ክረምት ክረምት እንደ ክፉ ጠላት የኪን እየወረረ ፣ ቁጥር ስፍር የሌላቸው እጅግ ብዙ ነፍሳት መገረፉ ቀርቶ፣ የኪ የተራቡት ከየትም መጥተው የሚጠግቡበት ፣ ትግሬው ፣ አማራው፣ ግሚራው ፣ ጋላው ፣ ሻንቅላው ፣ ጉዴላው ፣ ሁሉም ፣ ባንድነት አንድ ማህ

@OLDBOOKSPDF

በር ፊጥሮ ፣ በደስታ የሚፈርስ ሕዝብ ድንቅ ግሩም ፣ እገር ሆኖ ይታየዋል ! የኪ በሱና በሶፊያ ጥረት ባጭር ጊዜ እየማይታወቅ ሆኖ ስለ ተለወጠ ፣ ፍጹም ሌላ ስለሆነ ፣ ያን ታምር ፣ ያን ድንቅ ፣ ለመንብኘት ከቅርብና ከሩቅ የሚመጡት ሁሉ ይታዩታል ። ሁሉም እሱንና ሶፊያን ሲያመሰግኑ ፣ ሲመርቁ ይሰማውና ፣ እንደተኛ ሳያስበው ፣ ደስታ ካንድ ጎን ወደ ሌላው ያገላብጠዋል ! የየኪ ህዝብ እሱና ሶፊ የሚሉትን ያለማቋረጥ እየተቀበለ ፣ እሱና ሶፊያ በሚመሩት መንገድ ቀኝ ፣ ወይ ግራ ሳይል እየተከተለ ስለሚሄድ ፣ ባጭር ጊዜ ከድቁና ከጽማቂ ነጻ ሆኖ ፣ የኑሮ ደረጃው በጣም ከፍ ያለ ፣ ግራዝማች ዳኛቸው እንዳሉት "ከጭራሮ ተወንጋግሮ በተሰራና ፣ እንንብሶ በሚገቡበት" ሳይሆን ፣ እድሜም ፣ ውበትና ምቾትም ባለው ዘመናዊ ቤት የሚኖር ፣ የሌላው ክፍል ህዝብ ሁሉ የሚመኘው ፣ የሚቀናበት ሲሆን ይታዩዋል ! ከዚያ በተለይ የየኪ ሻንቅሎች ይታዩታል! የየኪ ሻንቅሎች እሱና ሶፊያ በሰጡዋቸው መሬትና ባስተማሩዋቸው ትምህርት ሁሉም ጌቶች ሆነው ፣ በቅጠል ፈንታ ጥሩ ጥሩ ልብስ ለብሰው ፣ ሁልጊዜ ደስ ብሎዋቸው ሲፈነጥዙ እንደሚያደርጉት ፣ እሜዳ ላይ እሳት ግድ አድርገው እንድደው ፣ ባለክራር ክራሩን ፣ ባለእታሞ እታሞውን ይዞ ፣ መሰረያ የሌለው እያጨበጨበ ፣ ሁሉም እሳቱን እዩዞሩ ሲጨፍሩ ታዩትና ፣ በጣም ደስ ብሎት ፣ ሳያስበው ፣ ድምጹን ከፍ አድርጎ"እንዲያ ነው!" ብሎ ሳቀ ።

"አንተ ልጅ ዛሬ ምን ሆነሀል ? አበድህ እንዴ ! ብቻህን የምትስቅ ፣ ለምን አትተኛም ?" አለች ሶፊያ ፣ አንድ ጊዜ ወደ ቀኝ ፣ አንድ ጊዜ ወደ ግራ ፣ እየተገላበጠና እዩተወራጨ እስዋን ጭምር እንቅልፍ መከልከሉ አንሶ ፣ እንዲያውም ብቻውን መሳቅ ስለ ጀመረ ።

"የኪን እዩፈጠርሁ ነው ! ምን አይነት የኪ እንደ ፈጠርሁ ብታይ እሱን ስታደንቂ እንቺንም እንቅልፍ ባላማረሽ ! "

"እባክህ ተወኝ ልተኛበት ፣ ለኔ ያው . . እግዜር የፈጠረው የኪ ይበቃኛል!"

በበነጋው ጥላሁን አሳበ በስራ ስለሚውልበት መንገድ ለመመካከር አሳዩንና ባላምባራስ ጉዴታን ፍለጋ ሄደ ።

እሳዩ መኛም ለጥላሁንና ለሶፊያ የተቀደሰ አሳብ ፣ በሱ አባባል ፣ "የተቀደሰ ሀልም"መሰናከል ላለመሆን ያክል የሚፈልጉትንና የሚጠይቁትን ይፈጽምላቸዋል እንጂ ፣ የነሱ ፣ የሁለት ልጆች ጥረት ምንም

ያክል ቢሆን ፣ ጠላ@OLDBOOKSPDFፎ ፡ "ያንድ አገር ህዝብ ያስተሳሰብና ያሰራር ልምድ ሊያስለውጥና ፣ አዲስ የኑሮ ስራት ሊመሰርት ይችላል" ብሎ ስለማያምን ፣ ወዲያውም የሱን አሳብ እንሱ እንደማይቀበሉት ብዙ ጊዜ ሞክሮ ስለ ተረዳ ፣ እንዲህ እንዲህ ላለ ፤ "የህዝብ ኑሮ ማሻሻያ"ለሚሉት አቅዳቸው ምክር ሲጠይቁት ፣ እንደ መጀመሪያው ጊዜ ተጨንቆ ፣ ተጠብቦ ፣ አሳብ መስጠቱን ችላ ማለት ጀምሮ ዋል ።

"የምሰጥህን ምክር ሳትቀበል ለምን ምክር ትጠይቀኛለህ ? 'የህዝብ ኑሮ ማሻሻል' ስለምትለው ነገር አሳባችን ከመሰረቱ የተለያዩ ስለሆነ ፣ የምሰጥህ አሳብ ካሳብህ ጋር ሊገጥም አይችልምና ፣ ምክር አትጠይቀኝ ፤ ብቻ የምትፈልገውን ነገር እዘዘኝና እፈጽማለሁ" አለ አሳዬ ፣ ጥሳሁን እቅዱን ሲነግረው ።

"ዞሮ ዞሮ የምፈልገውን መፈጸምህ ካልቀረ ፣ ምክርህን ጭምር ብትሰጠኝ ምናለ ?" አለ ጥሳሁን እዬሳቀ ።

"ሳትቀበለኝ ምን አደከመኝ ፤ "

"አንተ ስጠኝ ፤ መቀበል አለመቀበሉ የኔ ፈንታ ይሁን ።"

"አንተና ምሽትህ እንሰማህ አሳችሁ እንጂ እኔማ . . 'ስለ ጤና አጠባበቅ ለህዝብ የምትሰጡት ርዳታና ምክር ፣ እንዲሁም በትምህርት ፀኩል የምታደርጉት ርዳታ ትንሽ አይደለም ይበቃል ፤ ከነዚህ ሌላ ስለ ቡናና ስለ ልዩ ልዩ አትክልት አሰራር በራሳችሁ የምትሰሩት ፣ አራያ ሆኖ ለሚፈልጉ ሁሉ መሪ ሊሆን ይችላል ። ከዚህ አልፋችሁ አናድርግ የምትሉት ግን ፣ ከሰው ጋር የሚያጣላችሁ ከመሆኑም በላይ . . አስፈላጊ አይደለም ፤ ተገቢ አይደለም'ነው የምለው ።"

"እንዴት! በውሀ ጥም የሚሰቃይ ህዝብ ውሀ እንዲያገኝ ማድረግ አስፈላጊ አይደለም ? ተገቢ አይደለም ?"

"መምከሩና ማስተማሩ አስፈላጊም ፣ ተገቢም ነው ። ጥቅሙን ከተረዳው በሁዋላ ፣ ከፈለገ ስራውን ተጠቃሚው ህዝብ ይስራው ። እናንተ ከመምከርና ከማስተማር ፣ ቢበዛ ከመርዳት አልፋችሁ መሄዱ ይቅርባችሁ ነው የምለው ።"

"ሳይሰራው ቢቀርስ?"

"ጥቅሙን ከተረዳውና ከቻለ ይሰራዋል ። የሚጠቅመው መሆኑን እያወቀና መስራቱን እዬቻለ የማይሰራው ነገር ካለ ፣ ሊሰራው የማይ

@OLDBOOKSPDF

ፈልግበት ምክናያት ቢኖር መሆኑ ነው ። ማለት . . ያን ነገር ከመስራቱ ይልቅ ባለመስራት የበለጠ የሚጠቅም ቢሆን ይሆናልና ፣ እንዲያ ያለውን ነገር አንተ ሰርተህ ብታቀርብለትም ፣ ‘ያለስራህ ገባህ’ ተብለህ ራስህን እችግር ውስጥ ከመጣል በቀር ፣ በሰራኸው ስራም ህዝቡ አይጠቀምበትም ። ”

“ህዝብ የሚጠቅመውን ነገር እያወቀና መስራቱን እዩቻለ የማይሰራበት ምክናያት ይኖረዋል ” ያልኸው እንዴት ያለ ምክናያት ነው ? ”

ምክናያቱ ይህ ነው ብዬ ልነግርህ አልችልም ፤ ብቻ የዚህ አገር ህዝብ ፣ ኸረ እንደ እውነቱ ከሆነ ፣ ማንኛውም ፣ አንተና እኔ በምንኖቅፈው የኑሮ ስራት ፣ ወይም ሁኔታ የሚኖር ህዝብ ፣ እንዲያ ባለ ሁኔታ የሚኖር . . . በድህነቱ ፣ ባለማወቁ ፣ ወይም ለመስራት ባለመቻሉ ብቻ አይምሰልህ ! ”

“ታዲያኮ ምንድነው ? ”

“ለምሳሌ ፣ አንዱ አይነተኛ ምክናያት ልማድ ነው ። ረገርም ጊዜ የቆየ ያስተሳሰብና ያሰራር ልማድ ፣ የኑሮ ስራት ፣ ወይም ባህል ይሆንና ባንተ እንደሚመስልህ በቀላሉ የሚለወጥ አይሆንም ። አንተ አንድ ቀን ፣ ለዚህ አገር ሻንቅሎች መሬት አልምተን ለጥተን ሀብት እንዲያገኙ ፣ አስተምረን እውቀት እንዲያገኙ ፣ ስናደርግ ያኖኑዋር ስራታቸውን ፣ ከዚያ ባህላቸውን ፣ እንደሚለውጡ አትጠራጠር ” ያልኸው ትዝ ይለኛል ። ነገር ግን ይህ እውነት አደለም ። “ሀብት ፣ እውቀትና ችሎታ አለኝ”ብሎ በባህል ያልተፈቀደውን የሚያደርግ ፣ ባህል የሚያዘውን የማያደርግ የለም ። ለምሳሌ . . ጾም በሚጾምበትና በአል በሚከበርበት የክርስቲያኖች ማህበር ውስጥ የሚኖር “ክርስቲያን ነኝ ” የሚል ሰው ፣ ምንም ያክል ሀብት ፣ እውቀትና ችሎታ ቢኖረው ፣ አርብና ረቡእ ሰንጋ እያረደ ሲበላ ፣ እሁድ እሁድ በሬ እያስጠመደ ሲያሳርስ ቢታይ ፣ ከሚኖርበት ማህበር ውጭ ሆኖ ፣ የግዜርን ሰላምታ አንኳ የሚሰጠው እንደሚያጣ የታወቀ ነው ። ሀ ! ከመንገድ ወጣህ ትለኛለህ እንጂ . . . በኔ ፣ በራሴ ውስጥ ስለሆነው የስሜትና የምነት ለውጥ ትንሽ ብናገር እወድ ነበር ! ” አለ አሳዬ ፣ ትንሽ ፈገግ እንዳለ ዝም ብሎ ማዶውን እሻግሮ ሲመለከት ከቆዬ በሁዋላ ወደ ጥላሁን መለሰ አለና ። ጥላሁን ፣ “ ከመንገድ ወጣህ” የማይል መሆኑን ፣ ራሱን በመነቅነቅ ሲገልጽ ፣ አሳዬ “ በራሴ ደረሰ ” ስላለው የስሜትና የምነት ለውጥ መተረክ ጀመረ ።

@OLDBOOKSPDF

"ድሮ ተማሪ ሳለሁ . . ." አለ እንዳሁኑ የሚል ያሺመጋ ፍርሞ ምታ በፊቱ እዩታዮ ። "ድሮ ተማሪ ሳለሁ ፣ ያገራችን ህዝብ የሚኖርበት መጥፎ ሁኔታ ሁሉ ያሳዘነኝና ያስቆጨኝ ፣ እኔና እንደኔ በዩኒቨርሲቲ ህርት ቤቱ የሚማሩት ተማሪዎች ቶሎ ትምህርታችንን ጨርሰን ወጥተን እንዲያ ካለው መጥፎ ኑሮ መንጭቀን እስክናወጣው እቸኩል ነበር ። ይገርማል ! ከኛ በትምህርት ቤት ካለነው በቀር ለአገሩም ሆነ ለህዝቡ ሌላ ባለቤት ያለው ፣ ሌላ አሳቢና ተቆርቋሪ ያለው አይመስለኝም ነበር! በዚያን ጊዜ ፣ የአገራችን ህዝብ ፣ ፈረንጆች የሚያደርጉትን የማያደርግ ፣ የማያደርጉትን የሚያደርግና ፣ በጠቅላላው የፈረንጆችን የኑሮ ስራት የማይከተል ፣ በድህነቱና ባለማወቁ ከድህነቱም ይልቅ ባለማወቁ ምክንያት መሆኑን እምኚ ፣ በኔና በጉዋደኞቹ ስብከት ፣ የፈረንጆች ስራት የሚቀዳበትን አቁዋራጭ መንገድ አግርጥ ነበር ። እንደ ተዝካር ማውጣት ፣ ዝክር መዘከርና ፣ በዩምክናያቱ ድግስ እዩደገሱም ሆነ ግብር እያገቡ ከመጠን ያለፈ ሀብት በከንቱ ማባከን ፣ ካለመማርና ካለማወቅ በቀር ሌላ ምንም ምክናያት ስለሌለ ፣ እኛ የተማርነው ህዝቡን ሰብስበን ፣ ይህን ከፉ ባህል እንዲተው ከመከርነው ፣ ያላንዳች ማመንታት ምክራችንን እንደሚቀበል የተረጋገጠ በመሆኑ ፣ አዲስ ሀብት እስኪ ፈጠር መጠበቅ እንኩዋ ሳያስፈልግ ፣ በስብከታችን በምናስቆጥበው ሀብቱ ፣ ባጭር ጊዜ ኑሮውን ማሻሻል እንደሚችል ፍጹም የሆነ እምነት ነበረኝ ። ጾም መጾም ፣ ዝክር መዘከር ፣ በአል ማክበር ፣ ተዝካር ማውጣት ፣ ወይም ምጽዋት መመጽወት ፣ ድግስ እዩደገሱ ማብላት ፣ ማጠጣትና እነሱን የመሳሰሉት ፣ ከኑሮ ስራቱ ጋር ተወሳስበው የተሰሩት ልዩ ልዩ ባህሎች ሁሉ ፣ ሲያንዳንዱ አባል እንዲሁ ዘልማድ ከመሆናቸው አልፈው ፣ ለመንፈሳዊም ሆነ ለስጋዊ ኑሮውና ፣ በተለይም ለማህበራዊ አቁዋሙ ፣ ባለከፍተኛ ዋጋ ትርጉም ያላቸው መሆናቸውን ሳላውቅ እንዲህ ያሉትን አክሳሪና አስናፊ ልማዶች በቀላሉ ማስተው የሚቻል ይመስለኝ ነበር ። እነዚህን ልዩ ባህሎችና ወጎች ተጠንቅቆ መጠበቅና ማክበር ፣ ያዋቂነት ፣ የደግነት ፣ የውነተኛነት ፣ የመንፈሳዊነት ፣ የለጋስነትና ፣ እኒህን ለመሳሰሉት ከፍተኛ ባህሪዎችና ጸጋዎች ምልክት ፣ ወይም መለኪያ ሆኖ ተቆጥሮ ፣ በማህበሩ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ፣ ወይም ክብር የሚያስገኝ ስለሆነ ፣ ያ ሁሉ ድካም ፣ ያ ሁሉ ኪሳራ አለመማርና አለማወቅ ሳይሆን ፣ አይነተኛ አላማው ፣ በማህበሩ ውስጥ ፣ "ደግ ፣ እውነተኛ ፣ መንፈሳዊና ፣ ልገሳ ፣ ወዘተ ..." ተብሎ ያን ከፍተኛ ቦታ ፣ ያን ከፍተኛ ክብር ለማግኘት የሚከሰር ኪሳራ መሆኑን ፣ አሁን ነው የተረዳሁ ። አሁን ያ ባለመማሩና ባለማወቁ አዝንለት የነበረው ህዝብ ፣

@OLDBOOKSPDF

እሱ ደግሞ በበኩሉ ፥ ምንም እንኳ የመንግስት ባለስልጣን በመ ሆኔ መፍራቱና ማክበሩ ባይቀር ፥ "ክርስቲያን ነኝ"እያልሁ እንደ ክር ቲያኑ ህዝብ ሁሉ ባለመጾሜ ፥ ባለመዝከሬና በአል ባለማክበሬ ፥ መንገ ዴን ስቼ እንደ ጠፋሁ ቆጥሮኝ ፥ የሚያዝንልኝ መሆኑ ይሰማኝ ጀመር። ህ! እንዲያውም ይግረምህና ፥ ከነሱ ውስጥ እንደ ርኩስ ቆጥረውኝ እቤቴ ገብተው እህል ለመብላት የሚጸየፉ አሉ !

ስለዚህ . . አሁን ከድሮው የበለጠ ከህዝቡ ጋር ስለ ተቀራረብ ሁና ፥ የባህሉንም ፥ የወጉንም ትርጉም ከድሮው የተሻለ መረዳት ስለ ጀመርሁ ፥ የባህል ለውጥ መምጣቱ ባይቀርም ፥ ትውልድ ማሳለፍና በስ ልጣን ተደግፎ መምጣት የሚያስፈልገው እንጂ ፥ ድሮ በትምህርት ቤት ሳለሁ ይመስለኝ እንደ ነበረው ፥ ባጭር ጊዜና በተማሬ ስብከት ፥ እንዲሁ እንደ ልብስ አሮጌዎችን ወዲያ ማውለቅና ፥ አዲሶችን ማጥ ለቅ የማይቻል መሆኑን አመንሁ ። እንዳንዶቹ ፥ እንዲለወጡ ለማድረግ ከትምህርት ቤት እስክወጣ እቸኩልላቸው የነበሩ ባህሎች እንዲያ ውም . . 'እረ ለመሆኑ ሊለወጡ ይገባል ወይ?' የሚለውን ጥያቄ ባምንታ መመለስ ያስቸግረኝ ጀመር !

ባህል ሁሉ እንዲያው እንዲሁ ፥ ያለምክናያትና ፥ አገልግሎት ሳይ ሰጥ አይኖርም ፤ የሚኖርበት ምክናያትና የሚሰጠው አገልግሎት አለው። ወይም ድሮ ይመስለን እንደ ነበረው ፥ ምክናያቶቹ ድህነትና አለማ ወቅ አይደሉም ። ድህነትና አለማወቅ ባህል አይሆኑም ! ስለዚህ ፥ የቆዩን ባህል ለመለወጥ ከመነሳት በፊት ፥ ባህሉ የተነሳበትን ምክናያትና የሚ ሰጠውን አገልግሎት ደህና አድርጎ ማጥናትና ፥ ቢቻል ያ ባህል የሚ ሰጠውን አገልግሎት በተሻለ ሁኔታ የሚሰጥ ምትክ ማሰናዳት ያስፈ ልጋል ። "ለምሳሌ "እለ አሳዬ ትንሽ ፈገግ እንዳለ አይኖቹን ፊት ለፊት ተክሎ ። " ለምሳሌ ፥ ጋምቤላ ወርደህ ፥ እዚያ የሚኖሩትን ሻንቅሎችና እዚህ አገር የሚኖሩትን ጣማዎች ራቁታቸውን ሲሄዱ ስታይ ፥ መጀ መሪያ ባሳብህ የሚመጡ ድህነታቸውና አለማወቃቸው ናቸው ። ቆየት ብለህ ከሰዎችም ፥ ከባህላቸውም ስትተዋወቅ ግን ሌላ ምክናያት ፥ ሌላ ትርጉም መማር ትጀምራለህ ። ጋምቤላ ፍጹም ርቃናቸውን ጥለው የሚሄዱ ወንዶች ናቸው ፤ ሴቶች ከወገባቸው በታችና ከጉልበታቸው በላይ ያለ ክፍለ-አካላቸውን ይከድናሉ ። ወንዶች ግን . . እኔና አንተ እንዳይታይብን ተጠንቅቀን ፥ ደብቀን ፥ የምንጠብቀውን ክፍለ-አካል እነሱ ሰው እንዲያይላቸው ፥ የሰው አይን እንዲስብ ፥ እሱን ራሱንም ፥ አካባቢውንም ፥ በልዩ ልዩ ቀለም ያስጌጡታል ። ያ ክፍለ-አካል ፥

@OLDBOOKSPDF

ሊጋምቤላ ወንዶች ፣ ውበታቸውና የወንድነታቸው መመዘኛ ፣ መለኪያ፣ የቅንጅ መግረኪያቸው ስለሆነ ፣ አጊጦ ተሸልሞ ፣ መታየት እንጂ ፣ መሸሸግ የለበትም! ታዲያ . . ጋምቤላ ወርደህ "ይህን ባህል ለውጡ" እያልህ ብትሰብክ ፣ ሰብከትህን የሚቀበልህ ማግኘትህ ያጠራጥራል! እንዲያውም የዚያ አገር ሰዎች ሳይጣሉህ አይቀሩ!

እንግዲህ . . . እነዚህ ለምሳሌ ያክል ያመለከትሁዋቸው ስራቶች ፣ ከልዩ ልዩ ባህልና ወግ ጋር ተወሳስቦ የተሰራ ፣ የህዝብ የኑሮ ስራት፣ ውጩን ሲያዩት ከንቱ ቢመስልም ፣ ጠጋ ብሎ ሲያጠኑት ፣ ሁሉ ከንቱ አይደለም ። ከውስጡ ለአባሎቹ ጥልቅ ትርጉምና ጠቃሚ አገልግሎት ያላቸው መኖራቸውና ፣ እንዲህ ያሉት ጥልቅ ትርጉምና ጠቃሚ አገ ልግሎት ያላቸው ስራቶችም ፣ በቀላሉ የማይለወጡ መሆናቸውን ለማሳ የት ብቻ ነው . . . ከመንገዴ ወጥቼ ይህን ያክል የባጡን የቆጡን የቀባጠ ርሁ ። ብቻ እስቲ . . . እንዳሰባችሁት ፣ የዚህን አገር ህዝብ የኑሮ ስራት ትለውጡ እንደሁ ፣ ወይም እሱ እናንተን ይለውጥ እንደሁ ፣ ለሁሉም ትንሽ እንቆይና እንይ ፤ እስቲ እግዜር ለዚያ ያብቃን!"

"እንዲያ ፣ እግዜር ባንድ አቆይቶ ፣ የግናችን አሳብ ትክክለኛ እን ደሆነ ለማየት ያብቃን!" አለ ጥላሁን ።

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፳፰

## የፍሬ ሺጎ ሞት

የኪ ባጭር ጊዜ ውስጥ መልኩዋ ፍጹም ተለወጠ ። የኪ ልክ ጥላሁን ከምሽቱ ጋር ያቶ ሁሩይ ዳምጠን ወጥሎ የጎበኙ እለት ሌሊቱን እንቅልፍ አጥቶ ባሳቡ እዬሳለ ፣ እዬመሰለ ፣ ሲያያት እንዳደረ ያለች የኪ ሆነች ! ከሩቅ በዋንዛ ግንዳዎች ተራራ እዬዞረና ሸለቆ እዬተሽጋገረ የመጣው ውሀ ፣ ለመጠጥና ለጽዳት ከተመደበው ሌላ ፣ በከተማው ውስጥም ፣ በከተማው ዙሪያ ባሉት መንደሮችም ፣ እልፎ እልፎ እዬተቆፈረ ፣ ባፈርና በሳር ድርፍ ተደድቆ እዬተገደበ ፣ በተፈጠረው ኩሬ የተጠራቀመው ጥሩ ውሀ ፣ እዚህም ፣ እዚያም ፣ ፈንጠር ፈንጠር አድርጎ ለጌጥ እንዳስቀመጡት ፈርጥ ሲፍለቀለቅ ሲያዩት ማማሩ ! እንዲያ በዬክፍሉ ከተፈጠረው ኩሬ እዬተከፈለ በያቅጣጫው በሚመራው የመስኖ ውሀ ፣ በዬቦታው የለማው ሰብል ፣ በቡቃያ ፣ ባበባና በፍሬ ፣ የኪን አዝጎርጉሮና አስጊጦ ሲታይ ደስ ማሰኘቱ ! ግራዝማች ዳኘ ሲመለሱ ፣ እሳቸውም ያልተመለሱ እንደሆኑ ፣ በሳቸው ፋንታ ተሹመው የሚመጡት ባለስልጣን ሲሰማሙ ፣ በየኪ ከተማ ለሚሰሩት ቤቶች ሁሉ ምሳሌ እንዲሆኑ ለጊዜው ለጣዮች ፣ ለሽኮዎችና ለመሰንጎዎች ብቻ ፣ ከከተማው ዳር ሰፊያና ጥላሁን መሬት ለሰጡዋቸው ክፍሎች ፣ በዘመናዊ እቅድ የተሰሩት ቤቶች መዝጊያና መስኮታቸው ፣ መቃን ምድራካቸው ፣ ከየኪ ዋንዛ እዚያው እዬተጠረበ እዬተፈለፈለና እዬተሰካካ ተገጥሞ ፣ ባጣቸው ክፍክፍ ተከድኖ ፣ ሁሉም ሰልፍ እንደሚያሳዩ ተራ ገብተው ሲታዩ ማማራቸው ! ደስ ማሰኘታቸው !

መቸም በጎ ፈቃድ ካለ ፣ እንኩዋንስ ብዙ ህዝብ እዬተረዳዳ ጥቂቱም ብዙ መስራት እንደሚችል የታወቀ ነው ! የጥላሁንና የሰፊያ አሳባቸውንና ጉልበታቸውን ፣ ጊዜያቸውን ፣ ሀብታቸውን ፣ እረ በጠቅላላው ሁለመናቸውን ፣ ለወገን አገልግሎት መስጠት ፣ ያብዛኛውን የየኪን ህዝብ ልብ ለመያዝ ፣ በጎ ፈቃዱን ማርከው የነሱ ለማድረግ ስላበቃቸው ፣ ባጭር ጊዜ ውስጥ ፣ በየኪ የተሰራው ፣ “ታምር

@OLDBOOKSPDF

ነው ” ቢባል ይህን ያክል ማጋነን አይሆንም ! ከወንዞች ወደ ገንዳ ዎች ውሀ ለመመለስ የተሰሩት ብዙ ግድቦች ፣ የዛፎች ባላዎች እዩ ተካከሉ ፣ ገደሎች ተቆርቁረው እዩተደለደሉ ፣ ዛፍና ገደል በሌለበት ሜዳ ባለከረቻ ግንዲላዎች ተጣምረው እዩተተከሉ ፤ በነዚያ ላይ ከያ ቅጣጫው የተዘረጉት ብዙ የውሀ ገንዳ መስመሮች ፤ በከተማውና ባካባቢው ባሉት መንደሮች የተሰሩት ፣ የመጠጥ ውሀ የሚወርድባ ቸው ቧንዳዎችን ፣ በዩስራቸው እንሰራ እስኪምላ ቀጂዎች እንዳይሸ ከሙ የሚቀመጥባቸው ትክሏ ማቶዩች ፤ የውሀ ማጠራቀሚያ ኩሬዎ ችና ከዚያ ወደዩልማቱ ማከፋፈያ ቦዮች ፤ ልዩ ልዩ አትክልቶችና ፤ ከቡቃያ እስከ ፍሬ በየደረጃቸው የሚታዩት የህል አገለመራዎች ፤ ቤቶች ፣ የቡናና የህል ወፍጮዎች ፤ እኒህ ሁሉና ፤ እዚህ ውስጥ ያል ተመለከቱት ብዙ ሌሎች ነገሮች በዚያ አጭር ጊዜ ተሠርተው ፤ ተጠ ናቀው መታየታቸው ፣ ከጤና አጠባበቁ ፤ ከትምህርቱ ፣ ከጽዳቱ ሌላ ፤ ይህ ሁሉ መቁጠሩ የሚያስቸግረው ልዩ ልዩ ስራ በህዝቡ መተባበ ርና በጎ ፈቃድ ብቻ ፤ በዚያ አጭር ጊዜ መሰራቱ ሲታይ “የህዝብ በጎ ፈቃድና ሙሉ ህብረት ባሉበት ፣ የታምራት ሁሉ ታምር እንደ ሚሰራ አስቀድሞ ማመን ይገባል ! ” የሚባለው እሙን መሆኑን ያስረዳል !

የህብረት ስራ ፣ ወይም ደቦ ባለበት ቀን ፣ ለምሳሌ ፤ ቤት በሚ ሰራበት ፣ ቦይ በሚቆፈርበት ፣ የውሀ ገንዳ መስመሮችን ለመዘርጋት ገደል እዩተቆፈረ ሲደለደል ፣ የዛፎች ባላ እዩተጠረበ ፣ ወይም የደ ከመውን ለማበረታታት ተደራቢ እዩተደረበ ሲተከል ፣ ግንዲላው በኮ ርቻ ጣምራ ጣምራ እዩሆነ ሲተከል ፣ ወይም ሌላ ይህን የመሰለ የህ ብረት ስራ ሲሰራ በሚውልበት ቀን ሁሉ ፤ ሶፊያና ጥላሁን የቦ ቆሎ ንፍሮዋቸውን ቀቅለው ፣ ቦርዴና አረቄ ገዝተው ፤ ሲሰራ የዋ ለው ሁሉ ያን እዩበላ ፣ እዩጠጣ ፤ እንደ ዘፈን ፤ እንደ ሳቅ ፣ እንደ ቡዋረቅ ፣ እንደ ተጫወተ ፣ እንደ ተደሰተ ሲሊቱ ይገባደዳሉ ! መብራ ት ሲበራ ሲ... እልቆ በመጠጡና በጭዋታው ጊዜ የቸንቅሎች ሴቶችና ህጻናቶም ይጨመራሉ ። ኩሬ ሲመረቅ የሚደረገው ድግስ ደግሞ ከዚህ ፣ የሌሉ ስራ ሲፈጸም ከሚደረገው ድግስ ለየት ያለ ነው ። በከተማው ውስጥ ይሁን በዙሪያው ባሉት መንደሮች እያንዳንዱ የውሀ ማጠራቀሚያ ተቆፍሮ ፣ ዙሪያውን ባፈር ተገድቦ ፣ ከውጭ በሳር ድርፍ ተደርቶ ፣ እልቆ ፣ ከሩቅ በገንዳ የሚመጣው ውሀ በሚሞላበት እለት ፣ ሶፊያና ጥላሁን ሰንጋ አርደው ፣ በጦርዴ ፈንታ ጠጅ ገዝተው ፤ በዚያ ላይ

@OLDBOOKSPDF

አረቄ ጨምረው ፣ ያ እየተበላ ፣ እዩተጠጣ ዘፈኑ ፣ ጭዋታው ፣ ደስታው ፣ ውካታው ፣ ፈንጠዝያው እጥፍ ድርብ ይሆናል !

መቸም ሻንቅሎች ፣ በተለይ ጣማዎች ፣ ዘፈን አጥብቀው ስለሚወዱ ፣ አንድ ጊዜ ዘፈን ከጀመሩ ፣ እፍ እውጥቶ ፣ "ወገዱልን" ካላሉዋቸው ፣ እነሱ ፣ "በቃን" ብለው ፣ ወይም ደክሞዋቸው ይሄዳሉ ተብሎ ከቶ የሚታሰብ አይደለም ! ለጣማ ኅበዛዝትና ቆንጃጅት ፣ ያን የመሰለ አጋጣሚ ፣ ጣእመ ዜማው ልብ በሚመስጥ የከራር ምትና ፣ ያን ተከትሎ በሚወርብ ያካላት ውዝዋዜ ፣ የበሰለ የወጣትነት ስሜታቸውን እዩተገላለጹ ፣ የሰበሰ የፍቅር ስሜታቸውን እዩተገላለጹ ፣ አብረው ለመቆየት እድል የሚሰጣቸው ስለሆነ ፣ እንዲያ ያለውን የተባረከ አጋጣሚ የተቻለውን ያክል ዕድሜውን ለማስረዘም ቢጣጣሩ ፣ እዚያ እድሜ ያልደረሰ ፣ ወይም በዚያ እድሜ ያላለፈ ካልሆነ ማን ይፈርድባቸዋል ?

" መቸም . . 'በኢትዮጵያ የሚኖሩትን ልዩ ልዩ ጎሳዎች ሁሉና ባህላቸውን አውቃለሁ ' ማለት ባልችልም ፣ ጥቂት አይቻለሁ ። ነገር ግን በዚያ ባዩሁትና ፣ ያላዩሁትንም ፣ 'አይተናል' ከሚሉ ሰዎች በሰማሁት መጠን ፣ እንደ ጣማዎች ዘፈንና ጭዋታ የሚወድ ያለ አይመስለኝም " አለ ጥላሁን ፣ ትናንት ማታውን እቤታቸው ስላመሸው ጭዋታ አንስተው ፣ እሱና ሶፊያ ከባላምባራስ ጉዶታና ካሳዬ ጋር ሲያወጉ ።

" አዎ ፣ ጭዋታ በጣም ይወዳሉ ። ደግሞ . . . ቶሎ ይዳከማሉና ሰነፎች ናቸው እንጂ ፣ ስራ አጣፍጦ መስራትም እንደነሱ የሚያውቅ የለም ! ታናናሾቹ እንኩዋ ስራቸው ይጥማል !" አሉ ባላምባራስ ።

" ማወቅ ብቻ ሳይሆን . . የስራ ፍቅርም አላቸው ልበል ? በዩስራው ቦታ እንደ ተመለከትሁት ፣ ካማሮች ይሁን ከጋሎች ፣ ወይም ከሌሎች የሚበዙት ፣ ሁልጊዜ አይመጡም ። ሲመጡም ፣ ሲቀሩም ነው ። እነሱ ግን አንድ ቀን እንኩዋ ሲቀሩ አይቼ አላውቅም ፣ ሁልጊዜ ይመጣሉ " አለች ሶፊያ ።

" ታዲያ ድግስሽና . . ከዚያም በሁዋላ ዘፈኑ ፣ ጭዋታውና ጋጋታው ነው እንጂ ፣ የስራ ፍቅር መሰለሽ ከናንተ ስራ እንዳይለዩ ያቆራኛቸው ?" አለ አሳዩ ፣ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ ፣ አፉ ለሶፊያ ሲናገር አይኖቹ ጥላሁንን እያዩ ።

@OLDBOOKSPDF

"ይገርማል ! አንተ መቸም . . . የነዚህን ሰዎች ዋጋቢስነት አስቀድመህ ወስነህ አስቀምጠህ ፤ ማናቸውም ስለነሱ የሚባለው ሁሉ ፤ እውነትና አሰት መሆኑ የሚመዘነው ፤ ከዚያ አንተ ወስነህ ካስቀመጥከው ጋር እንጂ ፤ ከነሱ . . የውነተኛ ሁኔታ ጋር መሆን የለበትም ማለት ነው !" አለ ጥላሁን ፤ ያሽሙር ፈገግታ ፈገግ ብሎ አላዩን የጎድን እያየ ።

"የለም ጥላሁን ፤ ይቅርታ አድርግልኝና ተሳስተሃል ! እኔ ጣሞችንም ሆነ ሌሎችን ፤ እዚህ አካባቢ የሚኖሩትን ወገኖች ዋጋቢሶች አላደርጋቸውም ፤ እንዲያውም እውነቱን ልንገርህ ፤ እነሱን የማከብርበት ብዙ ምክንያት አለኝ ! ይልቅስ አዙረህ ባታየው ነው እንጂ . . ዋጋቢሶች ያደረግሃቸው አንተ ነህ ! እንዴት ? በለኝ " ሲል አላዩ ፤

"እሺ አለቃ ፤ እንዴት ?" አለ ጥላሁን ፤ እንደ መሳቅ ብሎ።

" እዩህ ! ጣሞችን ጣሞች ፤ ሸኮዎችን ሸኮዎች ፤ መዠንገሮችን መዠንገሮች ፤ ግሚሮችን ግሚሮች የሚያሰኙዋቸው ፤ ስማቸውና መልካቸው ብቻ ሳይሆን ፤ ሌሎችም በተፈጥሮ ከዘር ፤ በልማድ ወይም በትምህርት ከባህል የሚያገኙዋቸው የነሱ ፤ የያንዳንዳቸው የግል የሆኑ ፤ የሚወዱዋቸው ፤ በጣም የሚያከብሩዋቸው ፤ ለስጋዊና ለመንፈሳዊ ኑሮዋቸው ይጠቅሙናል ብለው የሚያምኑባቸው ፤ ብዙ ስጋዊና መንፈሳዊ ቅርሶች ፤ ብዙ ስጋዊና መንፈሳዊ ሀብቶች አሉዋቸው! እነዚህን በተፈጥሮና በባህል የነሱ የሆኑትንና ፤ እነሱን እያንዳንዳቸው እነሱ እንዲሆኑ ያደረጉዋቸውን ፤ የስጋና የመንፈስ ቅርሶች ፤ የስጋና የመንፈስ ሀብቶች ፤ መነውና ሌሎች መሆን አይወዱም ፤ አይችሉምም ! አንተ እነዚህ ወገኖች ሁሉ እያንዳንዳቸው ከተፈጥሮም ፤ ከባህልም የወረሱዋቸው ፤ እጅግ የሚወዱዋቸው ፤ የሚያከብሩዋቸውና የሚኮሩባቸው ስጋዊና መንፈሳዊ ቅርሶች ፤ ወይም ሀብቶች ፤ እንደ ሌሉዋቸው ፤ ፍጹም ባዶዎች እንደሆኑ ሁሉ የሌሎችን ፤ የባዕዳንን የባህል ቅርስ ፤ ወይም ሀብት ልታወርሳቸው ፤ ኧረ የምን ማውረስ ? ልትመጸውታቸው እንጂ ፤ ትፈልጋለህ ! ታዲያስ ! ማነው ዋጋ ቢስ ያደረጋቸው ? እኔ ወይስ አንተ ? እንደ እውነቱ ከሆነ ፤ አንተ ነህ እንጂ እኔ አይደለሁም . . . ዋጋቢስ ያደረግሁዋቸው ! አንተ ነህ እንጂ እኔ አይደለሁም ያዋረድሁዋቸው ! እኔ የኑሮ ስራቸውንና ባህላቸውን ባልስማማበትም አከብርላቸዋለሁ ። ለምሳሌ ጣሞችን እንውሰድ ። ጣሞች ፤ አሁን ባላምባራስ እንዳሉት ፤ መስ

@OLDBOOKSPDF

ራት እያወቁ ፣ ንዋሪ ቤትና እቃ በመስራት ፈንታ ፣ ላጭጮር ጊዜ መቆያ የጭራሮ ጎጆ እዮሰሩ ፣ እዚያ ተቀምጠው ፣ ከእለት እልፎ ላመት የሚሆን ሀብት ሳያበጁ ፣ ሁሉም በዮለቱ ፣ ለዮብቻ ይሁን የጋራ ሰርተው የሚያገኙትን አብረው በልተው ፣ ጠጥተው ፣ ተጫውተው ፣ ተደስተው ፣ እያንዳንዱ ጊዜው ሲደርስ ምንም ወደውጭ ሳይቀሩ ተው ማለፍ የሚገባ መሆኑን ያምናሉ ። በንዲህ ያለው ስራት የሚያ ምኑበትን ምክናያት ሲጠየቁ ፣ 'ረገርም ጊዜ መቆዮት አለመቆዮቱን ማወቅ የማይችለው ሰው ፣ ለረገርም ጊዜ የሚሆን ሀብት ማካበቱ ፣ ለስስታምነቱ ተጨማሪ ምስክር ከመሆን በቀር ሌላ የሚያስረዳው ነገር የለም' ይሉሀል ። እንግዲህ . . . እንዲህ ባለው አስተያየት አለመስማማት ይቻላል እንጂ 'ክፉ ፣ ወይም በጎ ነው' ብሎ ፍርድ ለመስጠት የሚገባም ፣ የሚቻልም አይመስለኝም ! እየውልህ እንግዲህ ወንድሜ ፣ ጣሞችም ሆኑ ሌሎች በዚህ አካባቢ የሚኖሩ ወገኖች ከምታስሩዋቸው ንዋሪ ቤትና ዘላቂ ጥቅም ያለው የልማት ስራ የበለጠ ፣ ድግሳችሁንና እሱን ተከትሎ የሚመጣውን ጭዋታና ደስታ ይወዳሉ' ያልሁህ ፣ 'የንዋሪ ቤትንና ዘላቂ ጥቅም ያለው የልማት ስራን እያወቁም' ማለቴ ባይሆን ፣ እውቀው ፣ ነቅፈው ፣ የጣሉት ስለሆነ ፣ 'አውቀው ፣ ነቅፈው ፣ የጣሉትን ነገር አንስቶ በግድ ማሸከም . . . አይቻልም' ማለቴ ነው ! ”

“ እንግዲህ . . . ባይንህ የምታየውንም እታምንም ማለት ነው ! አለ ጥሳሁን ፣ ጉዋደኛው ሲናገር በመገረም መልክም ዝም ብሎ ሲመለከተው ቆዩና ።

“ ምንድነው ባይኔ ያዩሁት ? ”

“ 'ንዋሪ ቤት መስራት አይፈልጉም' ያልኸው ፣ አሁን የሰሩት ቤት ንዋሪ አይደለም ? ወይስ . . . እንዲያ ያለውን ንዋሪ ቤት አንተ ባይንህ አላዩኸውም ? ”

“ ኦ . . . ! እሱን ለናንተ ሲሉ ፣ እናንተን ደስ ለማሰኘት ሰሩት እንጂ ፣ ለራሳቸው ብለው የሰሩት አይምሰልህ ! እነሱን ቅድም እንደ ነገርሁህ ፣ ከቤቱ የበለጠ ደስ ያሰኛቸውን ደግሜ ልንገርህ ? ከቤቱ እነሱን የበለጠ ደስ ያሰኛቸው ፣ ቤቱ ሲሰራ ያገኙት ድግስና ዘፈኑ ፣ ግርግሩ ፣ ጭዋታው ነው ! ለቤቱ እንደሆነ . . . ጥንት ከነበራቸው የጭራሮ ጎጆ የበለጠ ዋጋ እንደማይሰጡት አረጋግጥልሃለሁ ! ” አለ አላዩ እዩ ሳቁ ።

@OLDBOOKSPDF

"እቶ አሳዬ የሚለው እውነትክ ነው ልጄ ፤ አሰት እንዳይመስልህ እውነት ነው! "አሉ ባላምባራስ ጉደታም ። ጥላሁን አሳዬና ባላምባራስ ጉደታ እሱን ለማናደድ የተስማሙበት መስሎ ተሰማውና ፣ ክርክሩን መቀጠል አልፈለገም ። ብቻ ምንም እንኳ ያልተናደደ ለመምሰል ቢጥር ፣ ስሜቱን መሸሸግ ስላልቻለ ፣ ከፊቱ እንዳይታይበት ፊቱን ከነሱ ወደ ምሽቱ ሲያዞር ፣ ሶፊያ አውቃበት ስትስቅ ጊዜ እሱም ሲሰሙቸም ፣ ተያይዘው ይስቁ ጀመር ። እንደ ኢውነተኞች ሁሉ ጥላሁን ስሜቱን መሸሸግ አይችልም ።

ሳቃቸውን ሳይጨርሱ ፣ ያባዬ አሸከር ፣ በረኛው አግደው መጥቶ የፋሪ ዲጎን ሞት ተናገረ።

"ውይ! ምን ገደላቸው ? ትናንት ማታ ደህናቸውን እዚህ ሲጫ ወቱ አምሽተው አልነበር ? " አለች ሶፊያ በጣም ደንግጣ ። ጥላሁንም በጣም ደነገጠ ። ፋሪ ዲጎ ለሶፊያና ለጥላሁን ከጣሞች ወዳጆቻቸው መሀከል አንዱ ነበሩ ። በንጨት ሥራ አውቃታቸው ፣ በዚያ አካባቢ እን ኩዋንስ የሚያክላቸው አጠገባቸው የሚደርስ አልነበረም ። ፋሪ እየጠ ረቡ፣ እየፈለፈሉና እየቀረጹ ፣ ለዩብቻም ፣ አንዱን ከሌላው እያስካኩም፣ ከንጨት የማይሰሩት ነገር ስለሌለ ፣ ለምሳሌ ሰው ፣ ፈረስ፣ ውሻ፣ ድመት፣ አሞራ ፣ እንዲሁም ማናቸውንም ፣ የፈለጉትን ፣ ወይም ይስሩ የተባሉትን ሁሉ አሳክለው ፣ አስመስለው ፣ መስራት ስለሚችሉ ፣ ባገሩ ሰው ዘንድ "እንጨቱን ወደሚፈልጉት ሁሉ የሚለውጡ ፣ እንጨት የሚታዘዙቸው፣ አስማተኛ" ይባሉ ነበር። ወደ ከተማውና ከከተማው ዙሪያ ወዳሉት መን ደሮች ፣ እነጥላሁን ከሩቅ ውሀ ያስመጡባቸውን የዋንዛ ገንዳዎች አዲስ የተሰሩትን የዘመናዊ ቤቶች መቃን ምድራኮችና መዝጊያ መስኮቶች ፣ የሰሩም ፣ በጃቸው ያልሰሩትን እዬመሩም ፣ እዬተቆጣጠሩም ፣ ያሰሩ እሳቸው ስለነበሩ ፣ ለሶፊና ለጥላሁን ከወዳጅነታቸውም ሌላ ፣ ብርቱ ረዳታቸው ስለነበሩ ፣ ሞታቸውን ሲሰሙ በጣም ነው ያዘኑ።

"ለመሆኑ የሞቱበት ምክናያት ምን እንደ ሆነ ሰምተሀል? " አለ ጥላሁን ፣ እሱም ፣ ሶፊያም ፣ አንገታቸውን ደፍተው ከቆዩበት ወደ በረኛው ቀና ብሎ ።

"ዲዲቴ ፣ በገዛ ጦራቸው ወግቶ ገደላቸው ። "

"እንዴት ?ለምን?"

"ትናንት እዚህ አምሽተው ሲሄዱ ፣ ሁሉም ሞቅ ብሎዋቸው ፣ ፋሪ ዲጎ እንዲያውም . . . ከፉኛ ሰክረው ስለነበረ ፣ በመንገድ አንድ

@OLDBOOKSPDF

አንድ ሲባባሉ ፣ ፋሪ ፣ ዲዲቴን ሲወጉ ጦራቸውን ወርውረው ሳቱት ፤ ከዚያ ፣ ዲዲቴ ይዞት የነበረውን ዱላ ወዲያ ወርውሮ ጣለና ፣ ፋሪ ወር ውረው የሳቱበትን ጦር እንስቶ እንዲህ ፣ እንዲህ ፣ እንዲህ ፣ ሶስት ጊዜ ሰበቀና ጅር . . . እርጎ ቢሰደው ፣ ሂዶ በሆዳቸው ጥ . . . ልቅ አለ ! ሆዳቸውን አልፎ ፣ ጀርባቸውንም አልፎ . . . በጀርባቸው ወጣ !" አለ በረኛው ፣ ጦር ወርዋሪ ጦሩን ሲያደራ እንደሚያደርገው ቀኝ እጁንና ከወገቡ በላይ ያለ አካሉን እዩሰበቀ። "አቤ. . ት ! ያን ማየት እንዴት ያስቅቃል !እንዴት ይዘገንናል! ብታዩትኮ. . እንጀታቸው ከመ ሬት እዩታፈሰ እንደገና በሆዳቸው ተከትቶ ነው. . የተቀበሩ!" አለ በረ ኛው ቀጠለና ፣ ትናንት የሆነውን ሲተርክ ፣ ታሪኩን ተከትሎ ያ ፣ አስ ቃቂ ሁኔታ እንደገና ተመልሶ ሲመጣ እንደ ታዩው ሁሉ ፣ ፊቱን እኩማ ትሮና አይኖቹን በሁለት እጆቹ ሸፍኖ ።

"በመሆኑ አንተ እዚያ ኖረሀል? " አለ አሳዬ አሽከሩን።

"እ. . ይ ፣ ቢቀለ ነው የነገረኝ ፤ በቀለ ፣ 'ከመጀመሪያ እስከ መጨ ረሻ እዚያ ነበርሁ' ብሎ . . ሁሉንም ፣ አንድ ሳያስቀር . . እሱ ነው የነገረኝ"አለ በረኛው ፣ ግፈሩ ከፊቱ እዩታዩ።

ምንም እንኳዋ የፋሪ ዲን ሞትና ያማሙዋታቸው ሁኔታ እዚያ የነበሩትን ሁሉ ቢያሳዝናቸው ፣ በረኛው ያላዩውን ልክ እዚያ ቆሞ እንዳዩ ሰው ወሬውን ሲያወራ እየደራረገን በጁም ፣ በሌላ አካሉም እያሳዩ ያወ ራው ለጊዜው ሳቅ ስላመጣባቸው ፣ "በል እንግዲህ እውጭ ቆዩን ፣ በሩ " አለ አሳዬ ። በረኛውም ሳያስበው የወሬ ሞቅታ ገፍቶት ከገባ በት ወጥመድ በመላቀቁ ደስ ብሎት ፣ ቶሎ ሲወጣላቸው ፣ ሁሉም ተያ ይዘው ሳቁ ።

"አንተ መዋሸቱን አውቀህ ነው 'እዚያ ነበርህ ወይ' ብለህ የጠዬቅኸው? ወይስ . .እንዲያው ባጋጣሚ ነው? " አለች ሶፊያ ፣ አሳዬን።

"ብዙ ጊዜ አብረን ስለኖርን እንተዋወቃለን። በሩ ጥሩ ልጅ ነው ፤ ብቻ . . የሱ በሽታ ፣ ወሬ የጀመረ እንደሆን በራሱ አለማዘዙ ነው። ወሬ ሲጀምር ቶሎ ካላቋዋረጥሽው ፣ ወሬ እዩነዳው ባላሰበው ፣ እንዲ ያውም ባልፈለገው መንገድ ሂዶ ያገኝዋል!"

"ይገርማል! እኔኮ በሩ የሚዋሽ አይመስለኝም ነበር!"አለች ሶፊያ።

"አሁንም ቢሆን ለመዋሸት ፈልጎ አይዋሽም ። ብቻ አንድ የሆነ ነገር መተረክ ሲጀምር ፣ ያ የሆነው ነገር ብቻውን አላጠግበው ይልና

@OLDBOOKSPDF

ጎደሎ ሆኖ ይታዩውና ፣ የጎደለውን ፣ "እሙዋላ እሙዋላ ሲል ፣ እሳምር እሳምር" ሲል ፣ ሳያስበው ከመንገዱ ወጥቶ ይጉዋዛል ! እይውልሽ ለዚህ ነው እንጂ ፣ ለመዋሸት ብሎ አደለም ። በሩ.. ተራ ዋሾ አደለም !" አለ እሳዩ ፣ ፍርጥም ብሎ ።

"ተቀብረው ይሆንን?" አለች ሶፊያ ፣ ሁሉም ዝም ብለው ትንሽ እንደ ቆዩ ።

"የሞተ ትናንት ከሆነ ዛሬ ጥዋት ይቀብሩታል " አሉ ባላምባራስ ።

"እንጃሉ ተመራት እዬታፈሰ በሆዱ ተከትሎ ተቀበረ ሲል አልሰማሽም በሩ ? " አለ እሳዩም ፣ በቀልድ መልክ ።

"ታዲያ.. መድረስኮ አለብን" አለች ፣ ወደ ባልዋ ዘወር ብላ ።

"ሁላችንም እንደርሳለን ፤ እንደርሳለን " አሉ እሳዩና ባላምባራስ እየተቀባበሉ ።

ያንለት ማታ እሳዩ ከነባለቤቱ ፣ ጥላሁን ከነባለቤቱ ፣ ሁለቱም ከዬቤታቸው የዝን ራትና አንዳንድ ግንቦ ጠጅ ፣ ባላምባራስ ጉደታ አንድ ጠርሙስ አረቂ አስይዘው ፣ ወደ ሀዘኑ ቤት ሄዱ ። እዚያ ሲደርሱ ያገኙት ግግ ፣ ብዛቱ በከተማው ብቻ ሳይሆን በዙሪያው ባሉት መንደሮች ከሚኖረውም አንድ እንኩዋ እቤቱ ሳይቀር ፣ ሁሉም ከልሂቅ እስከ ደቂቅ እዚያ የተሰበሰበ ይመስል ነበር! ያ ሁሉ የግግ አዘንተኛ ፣ ያ ሁሉ ልቅሶኛ ፣ የፋራ ጺጎ ዘመናዊ ቤት በነበረበት ዙሪያ ባለው ባዶ ሜዳ ግጥም ብሎ ፣ ሁሉም ከወገቡ በላይ ፊቱቱን ባንድ ላይ ሰፍሮ ሲታይ ፣ የንብ ሰራዊት እንጂ ለሀዘን የተቀመጠ ህዝብ አይመስልም ነበር!

ጥቂት እግሮች ፣ ጋሎች ፣ ክፎች ፣ ግሚሮችና ሌሎችም ፣ ልብስ የመልበስ ልግድ ያላቸው ወገኖች ከጣዎች ሳይደበላቁ ፣ ትንሽ ገለል ብለው ተቀምጠው ያስተዛዝኑ ስለነበረ ፣ ባላምባራስ ጉደታ ፣ እሳዩ ከነባለቤቱና ጥላሁን ከነባለቤቱ ፣ ያመጡትን የዝን ለተቀባዮች አስረክበው ከጣዎች ትንሽ ገለል ብለው ተቀምጠው ከሚያስተዛዝኑት ወገኖች ጋር ተጨመሩ።

ምንም እንኩዋ ሶፊያና ጥላሁን የኪ ከገቡ ሁለተኛ አመታቸውን ቢያገባድዱና ፣ በዚያ ጊዜ ውስጥ ብዙ ህጻናትም ፣ ወጣቶችም ፣ ሲሞቱ ቢያዩ ፣ አንድ ትልቅ የጣግ የቤተሰብ አባት ሲሞት የሚደረገውን የልቅሶና የሀዘን ስነ-ስራት ለመጀመሪያ ጊዜ ፣ ያንለት ማየታቸው ነው። ይህም የልቅሶና የሀዘን ስነ-ስራት ፣ በውነት ከሰውዬው ሞት ያላነሰ ነው ያሳዘናቸው!

@OLDBOOKSPDF

ወደፊት በየኪ ከተማም ፣ በኮሪያው ባሉት መንደሮችም ፣ ለሚበሉት ቤተኛ ምግብ እንዲሆን ማለዳውን ንፉና ባቀዱት መሠረት ፣ በቅርቡ አፋሪ ዲን ተሰርቶላቸው የነበረው ዘመናዊ ቤት ፈርሶ ፣ ምሰሶው በነበረበት ቦታ መቃብር ተቆፍሮ ፣ ፋሪ ዲን እዚያ ተቀብሮዋል ። ከመቃብሩ ዙሪያ ፣ በሁለት ሜትር ያክል ስፋት ፣ ቁልቁል ተቆፍሮ ፣ ቁልቁሎቹን ወደ ውስጥ እያጋደሉ ፣ እሁንም በዙሪያ መስመር ፣ ወደ ላይ ርዝመት ከሰው ቁመት የማያንስ የቁልቁ እጥር እንደ ግድግዳ ግጥም ብሎ ተገድግዶ ፣ ትልቅ ጉድጓድ ይታያል ። የቤቱ ፍራሽ ፣ ግለት የገደግዳው መሬ ፣ ጨፈታውና ግንፉ ፣ የዓለፉ ጠርዝ ፣ ሳንቃውና ግንፉ ፣ የበሩ መቃን ምድራብ ፣ መዝጊያና መስኮቱ ፣ ሌላውም ሁሉ ፣ እዘንተኛውና እስተዛዛኝ ከሰፈረበት ትንሽ ራቅ ብሎ ተከምሮ ይታያል ። ባጠገቡ ጊዜያዊ ዳስ በሰፈው ተሰርቶ ፣ እዚያ ውስጥ ሴቶች ብዙ ምድጃዎች አበጅተው ፣ የፋሪ ዲንን የቤት መቃንና ምድራብ ፣ መዝጊያና መስኮት ፣ መሪና ጨፈታ ፣ ጠርብና ሳንቃ ፣ ሌላውንም ሁሉ ፈርሶ ከተከመረበት እየወሰዱ እያነደዱ ፣ በዚያ የፋሪ ዲን በግና ፍየል በሁለቱ እየታረደ ሲቀርብላቸው ፣ ወይም የፋሪ ዲን እንስት ፣ ዶሮ ፣ በሬው ፣ ከድፉ ፣ ከዘሁሉ ፣ ወይም ሌላ እህልና ስራብር ከያለበት እየተበረበረ ሲቀርብላቸው ፣ የሚጠበሰውን እየጠበሱ ፣ የሚቀቀለውን እየቀቀሉ ፣ የሚጋገሩውን እያገገሩ ፣ ያ እየተበላ ፣ የፋሪ ዲን ጦር ፣ መሣሪያዎቹ ፣ ገጀራቸው ፣ ማጭዶቻቸውና ሌላ መሳሪያቸው ሁሉ ፣ ከያለበት እየተፈለገ እየተሸጠ ፣ በገንዘቡ ቦርዴና አረቄ እየተገዛ እየተጠጣ ይስቀሳል ። ልቅሶውና መብል መጠጡ ይፈራረቃሉ እንጂ አያቋርጡም ። እዘንተኛው ሁሉ ፣ ሴጅ አዋቂው ፣ ሳጭር ጊዜ ዝም ብሎ ሲበላ ፣ ሲጠጣ ይቆይና ፣ ከሽማግሎች አንዱ ተነስተው ፋሪ ዲን ህያው ሳሉ ያደረጉትን በጎ ስራ ፣ የሰሩትን ጀብዱ ፣ ወይም የተናገሩትን ያስቶዋይ እንጋገር ተናግረው ሲቀመጡ ፣ አንዲት ሴት ባቀንቃኝነት ልቅሶውን ትጀምርና ፣ እዘንተኛው ሁሉ ተቀብሎ አስበሉ ፣ በንባ ወህ እየተራጨ ሲያለቅስ ቆይቶ ወደ መብል መጠጡ ይመለሳል። ደግሞ እንደገና ከሽማግሎች አንዱ ተነስተው የፋሪ ዲንን ደግነት ቸርነት ፣ ብልህነት ፣ ጀግንነትና ሌላውንም ፣ የባህሪይና የጸጋ ችሎታቸውን ተናግረው ሲቀመጡ ደግሞ እንደገና ልቅሶው ፣ ከዚያ መብል መጠጡ ፣ ከዚያ ሙዋቹን ማወደስ ማሞገሱ ፣ ከዚያ እንደገና ልቅሶው ፣ እንዲሁ እየተለዋወጠ ይቀጥላል !

"እኚህ ሁሉ የፋሪ ኖረዋል ? " አሉ ባላምባራስ ጉደታ ፣ ከዚያ ተሰብስበው ታስረው ለመታረድ ተራቸውን ወደሚጠብቁት የበግና የፍየል እናቶችና ሙክቶች ፣ ወጠጦቻቸና ቄቦች ፣ ግልገሎች ፣ በጃቸው እያመለከቱ ።

@OLDBOOKSPDF

"እኔህ ብቻ መሰሉዎት? ትናንት ማታ ከሞቱ ጀምሮ እስከ ዛሬ የታረዱት ብዙ ናቸው። ፋሪ አርደው መብላት አያውቁም እንጂ ከብት እያረቡ ማየት ይወዱ ነበር። ከብት በመውደድ . . እንጃ ! ከጣሞች ሁሉ የተለዩ ነበሩ! አሁን እዚያ ግዶ መንደር ከሚኖር አንድ ከፋ ጋርም እንዲት ላም ለኩል ነበረቻቸው አሉ ። ታዲያ ፣ ያች ላም ትምጣና 'ትታ ረድ" ሲባል ጊዜ ፣ ባለኩሉ መጀመሪያ ተገምታ የዋጋዋን እኩሌታ ሳልቀበል አላሳርድም ብሎ ፣ 'ማን አባቱ' ስላለ ብርቱ ጭቅጭቅ ተፈ ጥሮ ነበር ፤ በምን እንደ ቆመ እንጃ!"አለ አለ ባጠገባቸው ተቀምጠው ከሚያስተዛዝኑት አንዱ ፣ ጀለታ ራባ። "ደግሞ "አለ ጀለታ ፣ በዝቅተኛ ድምጽ ወደ ባላምበራስ ጆሮ ጠጋ ብሎ ። "ደግሞ ምሽታቸው ሁለት እናት ፍየሎች ሸሽጋለች ተብላ ትታማለች!"

"እንዲያ ነው ? አይ አበጀች ፤ ደግ አደረገች ! " አሉ ባላምባራስ እንደሉ በዝቅተኛ ድምጽ ትንሽ ፈገግ ብለው ።

" የፋሪ ምሽት የገዛ ፍዬሎቻቸውን የሚሸሽጉበት ምክናያት ምን ድነው ? ርሳቸው ሳይፈቅዱ እንዲታረዱ የሚያስገድዳቸው ባለስልጣን አለ ? " አለ ጥላሁን ፣ ከባላምባራስና ከጀለታ አጠገብ ተቀምጦ ሲነጋገሩ የሰማውና ሲደረግ ያዬው ሁሉ እንግዳ ስለ ሆነበት ፣ እንዲገልጹለት መንገድ ለመክፈት ያክል ።

" ፋሪ ከሞተበት እለት ማለትም . . . ከትናንት ጀምሮ ምሽቱም ሆነች ልጆቹ በንብረቱ ማዘዝ አይችሉም ። ያላቸው ሙብት የፋሪ ሀብት ከያለበት እዬተፈለገ እዬመጣ እስኪያልቅ ድረስ ፣ እንዲህ እንደምታ የው ሲበላ ሲጠጣ ፣ ከሌሎች ሁሉ ጋር እዬበሉና እየጠጡ ማልቀስ ብቻ ነው ! " አሉ ባላምባራስ ።

" እንዴት ? የሙዋቹ ሀብት ለወራሾቹ አይተላለፍም ማለት ነወ? " አለ ጥላሁን ፣ እጅግ ገርሞት !

" ይህን እስከ ዛሬ አታውቅም ? በጣሞች ስራት ፣ ሰው ሲሞት ሀብቱ ሁሉ ፣ ንብረቱ ሁሉ ካፈራው ፤ ከባለ ሀብቱ ጋር ፤ ከባለን ብረቱ ጋር አብሮ መጥፋት እንዳለበት ፣ ሀብት ያፈራውን ሰው እንጂ፣ ሌላ ማገልገል እንደሌለበት አታውቅም ? "

" ማን ነግሮኝ ልወቅ ? "

" በጠቅላላው ስለ ሻንቅሎች ስራት ካቶ አሳዬም ፣ ከኔም ጋር በዬጊዜው መነጋገራችንን ፣ እንዲያውም ካቶ አሳዬ ጋርማ ብዙ መከ ራከራችሁን ስለማስታውስ ፣ ስለዚህም እንስተን የተነጋገርን ይመስ ለኝ ነበር ። "

@OLDBOOKSPDF

“በጭራሽ ! ሌላ ሌላወን ነው እንጂ እንዲህ ያለወን . . . ጉድስ እርስዎም ፣ እሳዩም ነግራችሁኝ አታውቁም ! ”

“እውነትም በድለንሀል ፤ ግረን ! ” አሉ ባላምባራስ ፣ እንደ ሚቀልዱ ፍጥርም ብለው ። “ብቻ . . ” አሉ ቀጠሉና ፣ ስሜታቸው ከጭኖቃ ወደ ቁም-ነገር ሲለወጥ ከፊታቸው እዩታዩ ። “ብቻ ይህ አሁን እዚህ ሲደረግ የምታዩው ሁሉ ፣ እንዲህ ባይን ሲያዩት ይሻል እንደሆን እንጂ ፣ በወሬ ባንድ ላይ አጠራቅሞ ፣ ‘ባውራሀ’ ቢሉት ምንም ሊያስረዳ ስለማይችል ፣ እንኩዋን ሳንነግርህ ባይንህ አዩኸው ! ”

“እና እንግዲህ ፣ የፋሪ ምሽትና ልጆቻቸው እንዲህ አሳግባብ ከሚ ባከነውና ከሚበላሸው ሀብታቸው ምንም የማይተርፋቸው ፣ ከነገ ጀም ረው የቤት ምግብ እንኩዋ የማይኖራቸው ፣ ፍጹም ድሆች ይሆናሉ ማለት ነዋ ! ” አለ ጥላሁን ፊቱ በሀዘን ኢጅግ ከብዶ ።

“ ልክ ነህ ! እነሱ በስራታቸው ያባት ሀብት አይወርሱ ፤ የነሱን ሀብት ባልጅ እያወርሱ ፤ በህይወት ሳሉ ያፈሩትን ሀብት ከዘመድ ወዳጆቻቸው ጋር በልተው ፣ ጠጥተው ፣ ለሉቱ ዳስ ብሎዋቸው የሚ ኖሩበት ፣ ከዚያ የተረፈው ሲሞቱ ፣ እንዲህ እንደምታየው ዘመድ ወዳጃቸው አልቅሶ ፊላቸውን የሚሸኝበት ነው ! እንኩዋንስ ሌላ የቤተሰብ አባቶች ሲሞቱ ቤታቸው ፈርሶ የድግስ ማሰናጃ ፣ ማገዶ ስለሚሆንና ፣ ፊላቸው ምስሶው በነበረበት የሚቀበር ስለሆነ ፣ የሙ ዋቾች ሚሽቶችና ልጆች ዘመድ ፣ ወይም ጎረቤት ካላስጠጋቸው ቤታ ቸውን ሰርተው አዲስ ኑሮዋቸውን እስኪጀምሩ ፣ የቤት መጠጊያ የላ ቸውም። ”

“ይህ ጉድ ነው ! ግሩም ነው ! ” ሲል ጥላሁን ፊቱ በሀዘን እንደ ከበደ ራሱን እዩወዘወዘ ፣ አንድ የጣማ ሽማግሌ ተነስተው ፣ ከሳቸው በፊት ሌሎች ሽማግሌዎች እንዳደረጉት ፣ የፋሪ ዲጎን ፣ ቸርነታቸውን፣ አዋቂነታቸውንና ጅግንነታቸውን እያጋነኑ ፣ ከስሜት ጋር ተናግረው ሲቀ መጡ ፣ ጥላሁን ተነሳና ባላምባራስ ጉዳታ ወደ ጣማኛ እዩተረጎሙለት ለፋሪ ዲጎ መሰናበቻ ንግግር አደረገ ።

“ፋሪ ዲጎ ” አለ ጥላሁን በሻከረ ድምጽ ፣ ገና ስለፋሪ ዲጎ ሞት የሚናገር መሆኑን ሲያስብ ልቅሶ መጥቶበት ። “ፋሪ ዲጎ ፣ እዚህ ከኛ ጋር የሚቆዩበትን ጊዜ ፈጽመው ለሁልጊዜ ሲለዩን ፣ ለሁልጊዜ ስንሰናበታቸው ፣ እኛም ከናንተ ጋር ላዋቂነታቸው ፣ ለደግነታቸው፣

@OLDBOOKSPDF

ለታላቅነታቸው ፣ ምስክርነታችንን እዩሰጠን ፣ በነ ለሠሩ ሁሉ ዋጋ ከፋዩ ጌታ ምስክርነታችንን ተቀብሎ ፣ እንደሳቸው ላሉ ደጎች ፣ እንደ ሳቸው ላሉ ታላቆች ፣ ያሰናዳላቸውን የክብር ቦታ እንዲያወርስልን እን ማጸነዋለን ።

ፋሪ ዲን ፣ የባለቤቴና የኔ የቅርብ ወዳጅ ስለነበሩ ፣ ምንም እን ኩዋ የናንተን ያክል ፣ 'እናውቃቸዋለን ' ብለን ባንመካ ፣ እዚህ በመ ሀከላችሁ በቆዩንበት አጭር ጊዜ ውስጥ ፣ በዚህ . . . ሁለት አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ፣ ስለሳቸው ያወቅነው ፣ ደግ ለመሆናቸው ፣ አዋቂ ለመሆናቸው ፣ ታላቅ ለመሆናቸው ፣ ምስክርነታችንን ለመስ ጠት ያክል ከሚበቃ በላይ ነው ። ፋሪ ዲን ፣ ሁልጊዜም በጎ ከሚሰ ሩት ሬት ቀድመው ፣ በጎ ከሚሰራላቸው ሁዋላ ቀርተው የሚገኙ ሁልጊዜም እድርጉልኝ ከማለት ይልቅ ላድርግላችሁ ማለት የሚቀ ናቸው ፣ ሁልጊዜም ከሰው ሳይሆን ከፈጣሪ በተማሩት የስራ እውቀት ራሳቸውን ከመጥቀም ይልቅ ሌሎችን መጥቀም የሚመርጡ ፣ ታላቅ ሰው ነበሩ !

ከምናውቀው ብዙ ፣ ጥቂቱን ለማስታወስ ያክል ፣ ሁላችሁ እንደምታውቁት ፣ ውሀ ጥም ፣ ጉስቁልናንና በጠቅላላው ችግርን ፣ ከዚህ ለማስወገድ ባደረግነው ዘመቻ ፣ ከሩቅ ወንዞች ውሀ እዩተመ ለሰ መጥቶ ፣ ዛሬ በከተማችንና በዙሪያው ባሉት መንደሮች ሁሉ የሚታዩት ፣ ለመስኖና ለጽዳት የሚያገለግሉ ሰው-ሰራሽ ኩሬዎችና የመጠጥ ውሀ መቅጃዎች ሲሰሩ ፣ ዋና ሰራተኛውም አስሪውም እሳ ቸው ነበሩ ። እንሆ እዚህ በፊታችን በተራ ቆመው የምናያቸው ውበት ፣ ምቾትና እድሜ ያላቸው ቤቶች ሲሰሩ ፣ ለሰው-ሰራሽ ኩሬዎች የሚያስፈልገውን ሁሉ ገንዳ ፣ ለመጠጥ ውሀው የሚያስፈ ልገውን ሁሉ ማቶትና ቧንዳ ፣ ለቤቶች የሚያስፈልገውን ሁሉ መቃን ፣ ምድራክና መዝጊያ መስኮት ፣ ይህን ሁሉ ፣ ከንጨት የሚቀ ረጸውን እዩቀረጹ ፣ የሚሰነካውንና የሚጠረበውን ጠርበው ፣ የሚፈ ለፈሹውን ፈልፍለው ፣ እያሳኩ የሰሩና እዩመሩም ፣ እየተቆጣጠሩም ያሰሩ ፋሪ ዲን ነበሩ ። ፋሪ ዲን ለዚህ ለሰሩትና እዩመሩም ፣ እዩተቆ ጣጠሩም ላሰሩት ስራ ሁሉ ፣ ለዚህ አስደናቂ ስራ ሁሉ ፣ ስሪ ሳይሆን አሰሪ የገመተውን እጅግ ዝቅተኛ ዋጋ እንኩዋ ቢቀበሉ ኖሮ ፣ ያለ ጥርጥር የጌቶች ጌታ በሆኑ ነበር ! ነገር ግን በሳቸው መሪነትና ተቆ ጣጣሪነት ለሰሩት ረዳቶቻቸው ዋጋ እንዲከፈላቸው ሲጠይቁ ፣ ለራሳ ቸው እንኩዋንስ ፣ ' ዋጋ ክፈሉኝ ' ብለው ሊጠይቁ ፣ መጀመሪያ በቅጡ

@OLDBOOKSPDF

ሳናውቃቸው ፣ እኛ ‘ የድካማቸውን ዋጋ እንክፈል ’ ስላልን ፣ እንደ ሰደብናቸው ቆጥረውት ሲቀየሙ ስላዩን ፣ ፈርተናቸው ፣ ከዚያ በሁዋላ የዋጋ መክፈልን ነገር ዳግመኛ ለማንሳት አልደፈርንም ፤ ስለ ዚህ ፣ ፋሪ ዲጎ ይህን ሁሉ ስራ ሲሰሩና ሲያሰሩ ፣ እንደኛ ፣ ከኛ ጋር እህል ውሀ ከመካፈል በቀር ፣ በዋጋ መልክ አንድ ቀይ ሳንቲም አልወሰዱም ፤ ምክናያቱስ ? ድሀ አይደሉም ? ገንዘብ ንቀው ነው ? ሀብታም ሆነው ነው ? እርግጥ ፣ ፋሪ ዲጎ የገንዘብ ድሀ ነበሩ ። ብቻ የገንዘብ ድሀ የሆኑ ፣ ንቀውት ነው እንጂ አጥተውት አይደለም ፤ ፋሪ ዲጎ ፣ የገንዘብ ድሀ ቢሆኑ ፣ መንፈስ ጌታ ፣ ልበ ኩሩ ነበሩ ፤ ፋሪ ዲጎ ፣ ሰርተው ዋጋ ከማግኘት ይልቅ ፣ እሳቸው በሰሩት ስራ ሌሎች ተጠቅመው ደስ ሲላቸው ማየት ፣ ያስዚያም እንዲያው ስራ ቸው አምሮ ፣ ሰምሮ ማየት ፣ ደስ የሚያሰኛቸው ፣ ታላቅ አዋቂ ፣ ደግ ሰው ነበሩ ፤

እንዲህ ያሉት ታላቆች ፣ እንዲህ ያሉት አዋቂዎች ፣ እንዲህ ያሉት ደጎች ፣ አልፎ አልፎ ከሰንት አንድ የሚገኙ ፣ ብርቆች ናቸው እንጂ ፣ በዩቤቱ በብዛት ሲወለድ ውሎ ፣ ሲወለድ እንደሚያ ድረው ፣ ማንም ተራ ሰው ፣ ስላልሆኑና ፣ ሲሞቱ በቦታቸው የሚ ተካ እስኪገኝ ብዙ ጊዜ የሚያልፍ በመሆኑ ፣ ሞታቸው እንደ ተራ ሞት ሲቆጠር የማይገባው ፣ እጅግ የሚያጎድል ነው ፤

ታዲያ እንዲህ ባሉት ታላቅ ሰው ፣ እንዲህ ባሉት ደግ ሰው ፣ ምን ልናደርግላቸው ይገባል ? እንዲያውም እንዲሁ ፣ እንደ ማንም ተራ ሰው ፣ እንደ አልባሌ ፣ አልቅሰን ሬሳቸውን በመቅበር ፣ የገዛ ሀብታቸውን እዩበላንና እዩጠጣን አልቅሰን መሸኘት ብቻ ነው ? የለም ፣ ከዚህ የተሻለ ፣ ከዚህ የበለጠ ፣ ነፍሳቸውን ደስ የሚያሰ ኛት ነገር ልናደርግ ይገባናል ። የፋሪ ዲጎን ነፍስ ፣ እሳቸው በስጋ ሳሉ የሰሩት ቤት ፈርሶ ፣ ነድዶ ፣ ምሽታቸውና ልጆቻቸው መጠ ጊያ ሲያጡ ማየት አይደለም ደስ የሚያሰኛት ፤ የፋሪ ዲጎን ነፍስ ፣ እሳቸው በስጋ ሳሉ ያፈሩት ሀብት ተሙዋጦ ተበልቶ ፣ ተጠጥቶ ፣ ምሽታቸውና ልጆቻቸው የለት እራት አጥተው የሰው እጅ ሲያዩ ማየት አይደለም ደስ የሚያሰኛት ፤ የፋሪ ዲጎን ነፍስ ደስ የሚያሰ ኛት ፣ ቤታቸውን አፍርሶ በማንደድና ሀብታቸውን አባክኖ ሚሽታ ቸውንና ልጆቻቸውን እለቱን እጨካኝ ድህነት ላይ በመጣል ፈንታ ፣ ቤቱም ሆነ ሀብቱ አስተዳዳሪያቸውንና ጠባቂያቸውን ሞት ለቀማ

@OLDBOOKSPDF

ቻው ሀዘንተኞች ፣ ለፋሪ ዲኅ ሚስትና ለልጆቻቸው መኖሪያ እን ዲሆን ተቆጥቦ ፣ ተጠብቆ ፣ እኛ የሙዋቹ ወዳጆችና ወገኖች ፣ አሁን ከዩቤታችን የምንችለውን ያክል ማስተዛዘኛና ማጽናኛ ይዘን መጥተን ፣ ሀዘንተኞችን ስናስተዛዝንና ስናጽናና ፣ ሁዋላም እንዳይቸገሩ ካጠገባቸው ፣ ሳንለይ ፣ ርዳታ በሚሹበት ሁሉ ስንረዳቸው ስንታይ ነው ! ይህ ነው የፋሪ ዲኅን ነፍስ ደስ የሚያሰኛት ! ይህንም ነው ማድረግ የሚገባን ! ” አለና ጥላሁን ከስሜት ጋር “ ፋሪ ዲኅ ” አለ በከፍተኛ ድምጽ ፣ ፊቱን ወደ ፋሪ መቃብር መልሶ ። “ እጥቂው ታላቁ ፣ ደጉ ፋሪ ዲኅ ፣ ሞትዎ በስጋ ቢለያዩንም በመንፈስ ያቀራ ርበናል ! እርስዎ በስጋ ቢኖሩ ያሳሰብዎ የነበረው ሁሉ ፣ እርስዎ ስለ ሌሉ በርስዎ ፈንታ እኛን የሚያሳስብ ይሆናል ! እርስዎ በስጋ ቢኖሩ ኖሮ ፣ ስለ ሚሽትዎና ስለ ልጆችዎ ማሰብና መቸገር የርስዎ ፈንታ ፣ የርስዎ ሀላፊንት የነበረውን ፣ ከንግዲህ ወዲያ ስለነሱ ማሰብና መቸ ገር የኛ ፈንታ ፣ የኛ ሀላፊንት እንዲሆን ተቀብለናል ! ካሁን ጀምሮ ሚሽትዎና ልጆችዎ እርስዎን በማጣታቸው ፣ ምንም እንኩዋ ለምሽ ትዎ የባልንት ፣ ለልጆችዎ ያባትንት ስሜትዎና ፍቅርዎ ፣ ከርስዎ ብቀር ማንም ሊሰጣቸው የማይችል በመሆኑ ቢጎድልባቸው ፣ እኛም እርስዎ በሄዱበት መንገድ እስክንከተልዎ ፣ የሚበሉትና የሚጠጡት ወይም የሚኖሩበት ቤት ጎድሎባቸው ፣ ነፍስዎን እረፍት እንደማይነ ሱዋት ፣ ቃልኪዳን እንገባልዎታለን ! ” ብሎ ሲጨርስ ፣

“ ይህን ወደ መሀከሉ ፣ ስለ ቤት መፍረስና ስለ ሀብት መባ ከን የተናገርኸውን ... ባልተረጉመው ይሻላል ፣ ልጄ ” አሉ ባላ ምባራስ ጉደታ ጠተርጉማቸውን አቋርጠው ፣ ጥላሁን ከስሜት ጋር ሲናገር ዝም ብለው ሲያደምጡ ቆይተው ።

“ ለምን ? እንዲያውም እንዲሰሙልኝ ከፈለግሁት ሁሉ አይነ ተኛውኮ እሱ ነው ” አለ ጥላሁን ።

“ አይወዱልህማ ! እምነታቸውን ስለሚነካ ፣ የሚወዱት ነገር አይደለም !

“ ግዴለም ይንገሩዋቸው ” አለ ጥላሁን ፤ ትንሽ በስጨት ብሎ

“ካልህ ... ይሁና ! ” ብለው ባላምባራስ ፣ ጥላሁን ስለ ፋሪ ዲኅ ቤት ፈርሶ መንደድና ፣ ስለ ሀብታቸው መባከን ፣ እዩንታቀፉ የተና ገረውን በጣማኝ ተርጉመው ንግግራቸውን ሲጨርሱ ፣ ሁለት የጣግ

@OLDBOOKSPDF

ቃልቾች ምንም ሳይናገሩ ተነስተው ሄዱ ። ከዚያ ተከታዮቻቸው አንድ ባንድ ተከታትለው ሄዱ ። ሴሎች ፣ እዚያው ባሉበት እንዳሉ ፣ ሲያጉመጉሙ ቆዩና ከመሀከላቸው አንድ ያገር ባህል አዋቂነታቸውን ጠሞች ሁሉ አምነው የተቀበሉአቸውና ፣ በዩስብሰባው የመናገር ልማድ ያላቸው ሽማግሌ ጣሟ ተነስተው ፣ እዚያ የተቀመጢውን ሁሉ ዙሪያውን ባይናቸው ገዘመው ፣ መናገር መፈለጋቸውን ለሥማለጽ "እሁሁ ! " ብለው ጉሮሮዋቸውን ሲያጠሩ ፣ ጉምጉምታው ዝም፣ መተረማመሱ ጸጥ አለ ። ከዚያ ባላምባራስ ጉዳታን እንዲያስተረጉሙላቸው ለምነው ፣ በጣማኛ ንግግራቸውን ጀመሩ ።

"ጥላሁን" አሉ ሽማግሌው ። "ጥላሁን ፣ አንተና ቤሬያ ከመጣችሁ ብዙ ነገር አደረጋችሁልን ፤ ብዙም አስተማራችሁን ። በንቃመም ያለምንም ዋጋ ታክሙናላችሁ ፣ ለንቸገር በገንዘብም ሆነ በሌላ ትረዱናላችሁ ። እንዳይርበን እህልና አታክልት በጉዋሮዋችን ፣ እንትረጅ ጠማን ውሀ በደጃችን ፣ እንዲኖረን አደረጋችሁልን ። እሪና የኔ የድማ ጉጥደኞች በሽምግልናችን ምክናያት ባይሆንልን ቀረ እንጂ ለሴሎችማ ፣ ለወንዱም ፣ ለሴቱም ሁሉ ፣ ማንበብና መጻፍ ፣ ስሌት ጭምር አስተማራችሁ ። ሌላ ሌላም ብዙ የሌለንን እንዲኖረን ፣ የማናውቀውን ነገር እንድናውቅ አደረጋችሁ ። ይህ ሁሉ ጥሩ ነው ።ወደፊትም የሌለንን እንዲኖረን ፣ የማናውቀውን እንድንማር ፣ እንድታደርጉ እንፈልጋለን ። ነገር ግን ያለንን እንድታስቲዉን ፣ የምናውቀውን እንደማናውቀው አድርጋችሁ እንድታስተምሩን አንፈልግም ። በኛ እምነት ፣ ሰው ባታክልት ይመሰላል ። አታክልት ዛፉ ፣ ወይም ዋናው ግንዱ ከወደቀ እሱ ያፈራው ፣ የተሸከመው ፍሬ ሁሉ አብሮት ይወድቃል ፤ ተለይቶ አይቀርም ፣ አይኖርም ። ሰውም እንዲሁ ነው ። ሰውም ዋናው ሲወድቅ ፣ ዋናው ሲሞት እሱ ያፈራው ሁሉ፣ ከሱ ተለይቶ ፣ ለብቻው ፣ ህያው ሆኖ መኖር የማይችለው ሁሉ ፣ አብሮት መጥፋት እንዳለበት ፣ አምላካችን ከጥንት ያዘዘው መሆኑን በዩጊዜው ተከታትለው የተነሱት ቃልቾቻችን ስላስተማሩን ፣ እምነ ንበት የምንኖር ስራታችን ነው ። መቸስ ያምላካችንን ትእዛዝ ፣ በውድ ይሁን በግድ ፣ ማክበር አለብን ። ያምላክ ትእዛዝ ሲፈልጉ የሚያከብሩት ፣ ሳይፈልጉ የሚሽሩት አይደለም ! ያምላክ ትእዛዝ ከተጣሰ በሰውና በከብት ቸነፈር ይወርዳል ፤ ያምላክ ትእዛዝ ከተጣሰ መሬት የተከሉባትን አታጸድቅም ፤ የዘሩባትን አታበቅልም ። መሬት ትእዛዝ ተላልፋ የተከሉባትን ብታጸድቅና የዘሩባትን ብታበቅል እንኳ ፣

@OLDBOOKSPDF

በጡቃያው በረድ መጥቶ ያጠፋዋል ፤ ከበረድ በዛፍ ስር ፣ ወይም በሌላ መሸሸጊያ ተሸሽጎ የሚያመልጥ ቢኖር ደግሞ ፣ እምላክ ተምች ይልክበታል ። ደግሞ ከዚያ የሚያመልጠውን ትል ፣ ወይም አንበጣ መጥቶ ይበላዋል !

እየውልህ እንግዴህ ፤ ሰማይ አፉን ዘግቶ ዝናብ በጊዜው እንዳ ይወርድና መሬት የዘሩባትን እንዳታበቅል ማድረጉ ፤ ሰማይ አፉን ከፍቶ ዝናብ ያለጊዜው እንዲወርድና በመሬት የተዘራውን አጥቦ ፣ ጠርጎ ፤ እንዲወስድ ማድረጉ ፤ ከዚያ የሚያመልጠውን በረዶ ፣ ተምች ትልና አንበጣ ተከታትለው መጥተው ማጥፋታቸው ፤ ሌላውም የሰ ውና የከብት ፤ የህልና ያትክልት ጸር የሆነው መቅሰፍት ሁሉ ፣ እም ላካችን ትእዛዙን የሚተላለፉትን ሲቀጣበት ያሰናዳው መሳሪያ ነው። ስለዚህ ፤ ያምላካችንን ትእዛዝ እንድንተላለፍ ከመምከራችሁ በፊት እስቲ ከቅጣቱ የምናመልጥበትን መንገድ አሳዩን ! እስቲ ከዚህ ትዛ ዙን የሚተላለፉትን ሊቀጣበትካሰናዳው መሣሪያ ሁሉ የምንከላከል በትን መሳሪያ ቀድማችሁ በጃችን አስጨብጡን !

ጥላሁን ፤ አንተና ሶፊያ ደጎች ስለሆናችሁ ፤ በጣም እንወዳችሁ ዋለን ። አምላካችንን ደግሞ ሀይለኛ ስለሆን በጣም እንፈራዋለን ። ስለዚህ ፤ ምንም አንኩዋ አንተና ምሽትህ ለኛ ደጎች ስለሆናችሁ ብንወዳችሁ ፤ ከሀይለኛው ፤ ካምላካችን ቅጣት እንደማታድኑን ስለ ምናውቅ ፤ ትእዛዙን መተላለፍ አንችልምና ፤ እሱ ሰርቶ የሰጠንን ስራት ተዉ ፣ ለውጡ ፣ ብላችሁ ባትናገሩ ይሻላል ! አሁን ሁለቱ ታላላቅ ቃልኞች ተነስተው የሄዱ በተናገርኸው አዝነው ነው ። እን ደምታውቁት ፤ ቃልኞች የስራታችን ፤ የወጋችን ጠባቂዎችና መሪዎ ቻችን ስለሆኑ ፣ እነሱ ሲያዝኑ ህዝቡ በሙሉ ያዝናልና ፣ እንዲህ ያለ የሚያሳዝን ነገር ማድረግ መልካም አደለም ” ብለው ሲጨ ርሱ እዚያ የተሰበሰበው ጣማ ሁሉ ፣ ፈገግታው ሲታይና ህምህም ታው ሲሰማ “ቃልዎ ቃላችን ነው ! ” ማለቱን ፣ ባሉት ሁሉ መስማማቱን ፤ የሚገልጽ ይመስል ነበር ። መቸም አሳዬን ከተፈጠረ እንደዚያ እለት ደስ ብሎት አያውቅም !

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፳፱

# ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ

ግራዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ ፣ አዲሱን ጠቅላይ እንደራሴ ለመቀበል ካለታቸው ፣ ከሞቻው አውራጃ ገጢ ታዘው ወደ ጎሬ ከሄዱበት እለት ጀምሮ ፣ እዚያ ካንድ አመት በላይ ሲቆዩ ፣ ከመልካም በቀር፣ ከክፉው ነገር ሁሉ ያልተወራባቸው አልነበረም ፤

ወዲያው ከመሄዳቸው ፣ ከጎሬ ሰው እንኩዋ ሳይመጣ "እድሚሁ-ይፍታህ እስራት ተፈረደባቸው " የሚል ወሬ ከየት እንደ መጣ ሳይታወቅ ፤ እዚያው ተገኝቶ ፣ የከተማው ህዝብ ሳምንት ሙሉ እሱን ብቻ እያንጉዋለለ ሲያነፍስ ሰነበተ ። ከዚያ " ወንጀላቸው የሞት ፍርድ ሊያስከትል የሚችል ፣ በጣም ከባድ ስለሆነ ፣ እንዲያ ያለውን ከባድ ወንጀል ያዲስ አበባው ፍርድ ቤት እንጂ የጎሬው አይቶ ሊፈርድ አይችልም ተብሎ ፣ የፈጥኝ ታስረው ወደ አዲስ አበባ ሄዱ "
የሚል ወሬ መጣ ። ከዚያ "አዲስ አበባ ሄደው ተሰቀሉ !" ተባለ ። ትንሽ ቆይቶ ፣' እንደ በሬ በጅራፍ ሲገርፉዋቸው ፣" እኔን ያዬህ ተቀጣ" እያሉ ያዲስ አበባን አውራ ጎዳናዎችና አደባባዮች ሁሉ ከዞሩ በሁዋላ ፣ እግር ከወርች ታስሩ እንጂ መሰቀልስ አልተሰቀሉም !"
የሚል ወሬ መጣ ። ደግሞ ከዚያ በሁዋላ ትንሽ ቆይቶ ፣ " ሹመታቸውን ተሽረው ከንግዲህ ወዲያ እንኩዋንስ የመንግስት ስራ የግልም ቢሆን እንዳይሰሩ በጥብቅ ተከለከሉ እንጂ እስራቱም ሆነ ስቅላቱ እውነት አደለም " ተባለ ። የሚያስገርመው ፣ ከጎሬ ሰው መምጣት ከጀመረ በ፦ሁዋላ እንኩዋ ፣ አይተዋቸው የተመለሱ ሰዎች ደህንነታቸውን ሲያወሩ ፣ የየኪ ሕዝብ ከሰማው ወሬ ይልቅ በግራዝማች ዳኛ ላይ ክፉ እንዲደርስባቸው ፣ መአት እንዲወርድባቸው የሚመኘውን ጽኑ ምኞት ማመን ሰለ ወደደ ፣ እስከ አንድ አመት ድረስ ያኑ የሚመኘውን ክፉ ማውራቱን ፣ መአት ማውራቱን ቀጠለ ! ካንድ አመት በሁዋላ ብቻ ፣ የግራዝማች ሰዎች እዬመጡ ስንቅም ፣ ሌላ ሌላም እዬ ያዙ ፣ ግራዝማች በበኩላቸው እንዲወራላቸው የሚፈልጉትን እዬ ሰጡ መሄድ ሲጀምሩ ፣ ወሬውም መልኩን መለወጥ ጀመረ ።

@OLDBOOKSPDF

አንድ ቀን እኔ ጥላሁን ቤት ባላምባራስ ጉዲታና አሳዬ ጠጅ፣ ጥላሁንና ሶፊያ ብርዝ ፣ እዬጠጡ የግራዝማች ዳኘን ነገር አንስተው ሲጫወቱ ፣

"ግራዝማችስ ... ያ ፣ ሲወራባቸው የኖረው ሁሉ ውሸት ሆኖ ፣ "ማሞ ዳምጤ" የሚባለውን ሎሌያቸውን የውክልና ስልጣን ሰጥተው ልከውት ፣ መሰንበቻውን ከመሬታቸው አስር ጋሻ ሸጠ ብዙ ገንዘብ ይዞላቸው ሄደ" አለ አሳዬ ።

"እንግዲያ እንዲህ ከሆነማ ፣ መሻራቸው እውነት መሆኑ ነዋ!" አለ ጥላሁን ።

"መሬት አሽጠው ገንዘብ ማስወሰዳቸው እንኩዋ . . . ከዚህ ለመሻራቸው ምስክር ሊሆን አይችልም" አለ አሳዬ ።

"ታዲያ . . . ርስትን መሸጥ ምን ያመለክታል ?"

"እ . . መሬት የሚሸጡበት ብዙ ምክናያት ሊኖር ይችላል ፣ ለምሳሌ ?"

"ለምሳሌማ ... አንደኛ ከዚህ ከሄዱ ብዙ ጊዜያቸው ስለሆነ የወሰዱትን ስንቅ ጨርሰው ይሆናልና ፣ ምናልባት እዚያ የሚቆዩ እንደሆነ ተጨማሪ ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል ። ሁለተኛ እዚያ የሚቆዩበት ጊዜ እንዳይረዝምና ፣ በዚያው መጠን ኪሳራውም ፣ ሌላ ሌላ ችግራቸውም እንዳይበዛ ፣ ሁሉንም ለማሳጠር ፣ ሁሉንም ባጭር ለመቁረጥ ... ገንዘብን የመሰለ ስለት ሥቀስ የለም ! ልጨምር ?" አለ አሳዬ ፣ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ ።

"ግዴለም ይበቃል ፣ ልትሄድበት የፈለግኸውን መንገድ አይቸዋለሁ ። ያው ... እንደ ሁልጊዜው የግራዝማችን ስምና መልክ ለማጥፋት ነው !" አለ ጥላሁን ።

"የግራዝማችን ስምና መልክ ለማጥፋት እኔንም ሆነ ሌላ እያስ ፈልግምኮ ፣ አስቀድሞ በገዛጁ የጠፋ ነው ፣" ሲል አሳዬ እዬሳቀ ሁሉም ተያይዘው ሳቁ ።

"መሬት መሸጡ እንኩዋ ... አቶ አሳዬ እንዳለው ፣ ለመሻሩ ምልክት ላይሆን ይችል ይሆናል ። ከዛሬ ቀደምም ሶስት ይሁን ፣ አራት ጊዜ ሄዶ እዚያ ሲቆይ ፣ መሬቱን ሁሉ የሸጠበት ገንዘብ አል በቃው ብሎ ከነጋዴም ፣ ከሌላም እዬተበደረ እንኩዋንስ ለሹም ... እዚያ አደባባይ ላበቀለው ሳር - ቅጠል ሁሉ ጉቦ ሰጥቶ ፣ በጉቦ ብዛት

ነውና ተመልሶ የመጣ ፣ አሁንም መሬቱን የሚሸጥ እንደ ልማዱ ለዚያው ይሆናል ። ነገር ግን እንዲያው … እኔን አልገባኝ ያለ ፣ ይህ አገር ሳዲስ አበባው መንግስት ሩቅ ስለሆነ የህዝቡ አቤቱታና ልቅሶ እንዳልተሰማለት ሁሉ ፣ ለሰማዩ መንግስትም ፣ ለእግዚአብሄር መንግስትም ሩቅ ሆኖ ፣ የዚህ ህዝብ እግዚኦታና ልቅሶ ሳይሰማ ቀርቶ ነው ያከፉ ሰው ተመልሶ ወዲህ የሚመጣ ! ወይስ … እንዴት ነው ! ” አሉ ባላምባራስ ጉደታ ፣ ስለ ግራዝማች መምጣትና መቅረት ወሳኞች እዚያ የተቀመጡት እንደሆኑ ሁሉ ሰጥታቸውን ፣ ምኖንታቸውን ከምሬት ጋር ለነሱ እዩገለጹ ።

“ እንዲያውም…ካዲስ አበባ ፣ ሰማይ ይርቃልኮ ባላምባራስ ! ሀ - ሀ ሀ - ሀ - ሀ - ! ” አለ አሳዩ ፣ ባላምባራስ ትንሽ በሰጡት ሲሉ ሰባዩ ፣ ብስጭታቸውን ለማረሳሳት በተናገረው ቀልድ እሱ አስቀድሞ እዩሳቀ ።

“ አዩ… ቢሆንም ! ቢሆንም ‘ ቅሩብ እግዚአብሄር ለየውሀን ልብ ’ ብሎ ነበራ ! ” አሉ ባላምባራስ ፣ የንስሀ አባታቸው ፣ ቄስ ወልዶ ጊዮርጊስ ሁልጊዜ ሲሉ የሚሰሙትን ጠቅሰው ፣ ሰሚታቸው ትንሽ ለዘብ ሲል በፊታቸው እዩታዩ ።

“ ምንም ከሰዎ ባላውቅ አባባ ፣ ‘ ከማያውቁት መላክ የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላል ’ እንደሚሉት ፣ ባሁኑ ጊዜ ፣ ይልቁንም አሁን አዲስ ጠቅላይ እንደራሴ ተሹመው በመጡበት ጊዜ ፣ ቢከፉም ቢበጁም እኒያው የለመድናቸው ሰው አይሻሉም ? ይህን የምልበት እዚህ ከመቆዩታቸው ብዛት ፣ እሳቸው ትልቅ ትንሹን ያውቁታል ፤ ትልቅ ትንሹ እሳቸውን ያውቃል ! ስለዚህ ክፉውም በጎውም ወገናቸው ፣ ክፉውም በጎውም እመላቸው ስለሚታወቅ ፣ ከሚያውቁት ክፉ መሸሽ ይቻላልና ምንም ቢሆን ሊጎዳ አይችልም ብዬ ነው ! ” አለ ጥላሁን፣ ግራዝማች ዳኘ እንደገና ወደ የኪ ተመልሰው ሲመጡ ከማየት ሞታቸውን የሚመርጡ መሆናቸውን ባላምባራስ ጉደታ ብዙ ጊዜ ሲናገሩ ይሰማ ስለነበረ ፣ የሱን አስተያየት ለመግለጽ ያንለት ደህና አጋጣሚ ስላገኘ ።

“ ክፉና በጎ ወገኑ ? ደሞ ግራዝማች ዳኘ ከክፉ በቀር በጎ ወገን አለው ? በል ተወው ባታውቀው ነው ! ግራዝማች ዳኘ ከክፉ ድርና ማግ የተሰራ ፣ በጎ ነገር እንኳዋንስ በውስጡ ሊኖር ባጠገቡ ያልዞረ ፍጹም ክፉ ነው ! አንተና ልጄ ፣ ወይዘሮ ሶፊያ አታውቁትም ። አቶ አሳዩ ግን ደህና አድርጎ ያውቀዋልና እሱ ይንገራችሁ ። ”

@OLDBOOKSPDF

"ኧረ እንዲያው … መበራበር ፈልጎ ነው እንጂ ነጋሪማ አያሻው ፤ እሱ ደህና አድርጎ ያውቃቸዋል ! " አለ አሳዬ ።

"በውነት ደህና አድርጌ አላውቃቸውም ። ለምሳሌ … እኔ ስለሳቸው ያለኝ ግምትና ፣ ሌላው ሰው ሁሉ ስለሳቸው የሚናገረው ፣ ፈጽሞ የተለያዩ ነው ። እስከ ዛሬ ድረስ የግራዝማችን ደግነት ከንድ ሰው አፍ ሰምቼ አላውቅም ፤ ከገሌ በቀር ሳይባል ፣ ሁሉም ተስማምቶ ፣ ክፉ መሆናቸውን ነው የሚናገር ። ስለዚህ እንግዲህ … እኔ ደህና አድርጌ አላውቃቸውም ማለት ነው ! " አለ ጥላሁን ።

"ለመሆኑ አንተ ስለሱ ያለህ ግምት እንዴት ነው ? ደግ ሰው አርገህ ታየዋለህ ማለት ነው ? " አሉ ባላምባራስ ፣ በህይወታቸው ሙሉ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ፣ "ግራዝማች ደኛ ደግ ናቸው " የሚል ሰው ሲገኝ ነው ብለው ገርሞዋቸው ።

"ደግ ናቸው " ብዬ ባልምልም ሰው የሚለውን ያክል ፣ "ክፉ ናቸው " ለማለትም አልደፍርም ።

"ሰው ሁሉ ክፉ ነው የሚለው ክፉ ስራውን አያዩ ነው እንጂ እንዲያው አይምሰልህ ። ሁላችንም የምንጠላው ክፉ ስራውን አያዩን ነው ። አንተስ … በደግነት የገመትኸው ምን መልካም ሲሰራ አይተህ ነው ? "

"ኧ … ሺ ! እናንተ መቼም 'ክፉ ሲሰሩ አይተናል ' ብላችሁ ነው የጠላችሁዋቸው ። እኔ ግን ክፉ መሥራታቸውን ከናንተ ሰማሁ እንጂ አላዩሁም ፤ ስለዚህ እንደናንተ ክፉ የሚሰሩ መሆናቸውን እስካይ ፣ በሰማሁት ብቻ ልጠላቸው አይገባኝም " ነው የምል ። ይህ ስለ ክፉ ስራቸው ነው ። አሁን ደግሞ ፣ ምንም እንኳ ደግ ሰው ለመሆናቸው "በቂ ምስክሮች ናቸው " ተብለው ሊጠሩ ባይችሉ ፣ በኔ አስተያየት "በጎ ስራዎች ሲሰሩ አይቻለሁ" የምላቸውን ልናገር ። አንደኛ ፣ እኛ እዚህ አገር እንደ ደረሰን የምናርፍበት ቤት በተቸገር ንበት ጊዜ ፣ ቤት ሰርተን እስክንወጣ ፣ ምንም እንኳ ክራይ ብንከ ፍልበት ፣ በምክትል ወረዳ ገገርው ቤት እንድንቆይ መፍቀዳቸው ፣ ሁለተኛ ፣ ህዝቡ መታከሚያ አጥቶ እንዳይቸገር ፣ ቤት እስኪሰራ ፣ ትምህርት ቤቱ መታከሚያ ሆኖ እንዲቆይ መፍቀዳቸው ፣ ሶስተኛ ስለ መሬት አሸንሽና ማከፋፈሉ ጉዳይ " ይቆጡ ይሆናል " ብለን ሁላችንም ያን ያክል ስንሰጋ ፣ እንዲያውም አሳቡን አመስግነውና እኛንም አደፋፍረው መርዳታቸው ፣ እነዚህና እነዚህን የመሰሳሉ ፣ እን

@OLDBOOKSPDF

ዳንድ ሲያደርጉ ያዩኋቸው ነገሮች አባባ ፤ አሁን እርስዎ እንዳሉት፥ "ከከፉ ድርና ማግ የተሰራ ፤ በጎ ነገር እንኩዋንስ በውስጡ ሲኖር ባጠገቡ ያልዞረ ፤ ፍጹም ክፉ ሰው የሚያደርጋቸው አደሉም ። ስለ ዚህ ነው ፤ እኔ ሲያደርጉት ያዩሁት ፤ ሰው ሁሉ ባንድ ቃል ከሚናገረው ጋር አልስማማ ስላለ ነው … ' ገና ደህና አድርጌ አላውቃቸውም ' ማለቱን የመረጥሁ ። "

" ባይኔ አይቻ እስካረጋግጥ ሰው ያለውን ሰምቼ ብቻ ሰው አልጠላም " ማለትህ በጣም ጥሩ ነው ፤ እግዚአብሄር ይባርክህ ልጄ ! ነገር ግን እሱ ሰው አደለም ፤ አሁን ትደርስበታለህ ! ብቻ የሱን ነገር ከመጨረሳችን በፊት ፤ እሱ፡ ለናንተ በጎ ስራ እንደ ሰራ አድርገህ ለተናገርኸው የኔን አሳብ ደግሞ ልስጥ ። አሁን " መልካም ነገር አደረገ " ብለህ የቆጠርኸው ሁሉ ፤ ከበጎ ነገር ተራ ገብቶ የሚቆጠር አይመስለኝም እንጂ ፤ እንደ በጎ ስራ የሚቆጠር ከሆን ፤ " በጎ ልስራ" ብሎ ያደረገው ከሆነ ፤ እንትና ባለቤትህ ከላይ ፤ ከሸዋ ስለ መጣችሁ፥ የምን ግንድ ቅርንጫፎች እንደ ሆናችሁ ባለ ማወቁ ፤ ምናልባት … የሸዋም ግንድ ቅርንጫፎች እንደ ሆናችሁ . እናንተን እጫናለሁ ሲል ሾህ እንዳይወጋው ፈርቶ ነው እንጂ ፤ በጎ ለማድረግ ወድዶ አይደም ስልህ" ሲሉ ባላምባራስ ራሳቸው በስጡት ምሳሌ ራጋግ ብለው የቀሩት እስበሳቸው ቀያዩና ሳቁ ። " አልጨረስሁም ፤ ልጨርስ " አሉ ቀጠሉና ። " አስጨርሱኝ ። ሁላችኝ ፤ በሱ አስተሳሰብ ፤ እናውቡሏ ጎሬ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ፤ እናንተን መርዳቱ ቢቀር ፤ አለመጫኑ እንኩዋ ፤ ለሱ ፤ ላፉ ውብቱ ከፍተኛ አራጣ እንደ ማበደር ነው ! ስለዚህ ፤ ምን ጊዜም በጎ ማድረግ የባህሪው ስላልሆነ ፤ ለናንተም ቢሆን በጎ አያደርግም እንጂ ፤ የሚያደርግ እንኩዋ ቢሆን፥ በናንተ ለመጠቀም ካልሆነ ፤ እናንተን ለመጥቀም የሚያደርገው ነገር አለ መስሎዋችሁ እንዳትዋሹ ! በዚህ ላይ የምጨምረው ቢኖር … ከዛሬ ቀደም የነገርሁዋችሁን ማስታወስ ብቻ ነው ። የግራዝማች ዳኘን ክፋት የሚያክል ነገር ያለ እንደሆነ ፤ ምቀኝነቱ ብቻ ነው ! ከሱ በቀር በማናቸውም ምክናያት ፤ የሌላ ሰው ስም ሲመሰገን የሰማ እንደሆነ ፤ ያን ሰው በቃ … በጥርሱ ቢነክሰው ፤ ስጋውን በጥርሱ ቆርራጦ ቢበላው የልቡ አይደርስም ! የዚያ ሰው ሞቱ ብቻ የበቀል ጥሙን አያረካውም ! አሁን … ይህን ሁሉ መናገር የፈለግሁ "አሉ ባላምባራስ ፤ ለንግግራቸው ማሰሪያ ለመፈለግ ትንሽ ቆም አሉና ። " ይህን ሁሉ መናገር የፈለግሁ ፤ ሲሆን ሲሆን ለሽማግሌ ምክሬ ዋጋ ሰጥታችሁልኝ እንድትጠነቀቁ ! ያለዚያም … ' ደህና አድርጌ አላ

መቀወም ? ስትል @OLDBOOKSPDF ወደፊት ደህና አድርገህ ስታውቀው አሁን እንዳልሁት ሆኖ ያላገኘኸው እንደሆን እንድትታዘበኝ ነው ።»

“ ሁልጊዜም ለሚሰጡን ምክር ከፍተኛ ዋጋ የምንሰጥ መሆናች ንን ይመኑ አባባ ! አለ ጥላሁን ።

የግራዝማች ዳኘ አሽከር ፣ ማሞ ዳምጤ ፣ አስር ጋሻ መሬታቸ ውን ሸጦ ፣ ብዙ ገንዘብ ይዞላቸው መሄዱን አባዬ እና ጥላሁን ቤት ከተናገረ በሁዋላ ፣ ያው ማሞ ፣ ባጭር ባጭር ጊዜ ውስጥ እዬተ መላለሰ ፣ እንደገና ሀያ ምርጥ ጋሻ መሬት ሸጦ ፣ በጣም ብዙ ገንዘብ ለጌታው ወሰደላቸው ።

“ እኔስ … የዚህ አገር ሰው ፣ የዚህ አገር ነጋዴ ልብ የለ ውም ልበል ? ” አሉ ባላምባራስ ጉዳታ ፣ እዚያው ፣ እነ ጥላሁን ቤት አባዬ ጭምር ሲጫወቱ ፣ የግራዝማችን ሰፊ መሬት ለመግዛት ሁለት ሀብታም ነጋዴዎች ተጣሉትው ሲጋደሉ ሽጉጥ ስለ ተማዘዙ ፣ ሁለቱም ፖሊስ ጣቢያ መታሰራቸውን አባዬ ስለ ተናገረ ።

“ እንዴት ? ” አለ ጥላሁን ።

“ መቼም ያ ተንኮለኛ ፣ ያ ሰይጣን ግራዝማች ዳኘ ፣ የለማ መሬ ቱን እዬሸጠ ጉቦ የሚሰጥ ፣ ወደዚህ አገር ስመመለስ ተስፋ ፣ ያውም የታመነ ተስፋ ፣ ቢያገኝ ነው እንጂ … ወደ ሌላ አገር ፣ በከፍተኛ ማእረግ እንኳ የሚሄድ ከሆነ ፣ ወደዚህ የማይመለስ ከሆነ ፣ ያ የመላለሰ መሬት ምንም ቢሆን አይሸጥም ። ታዲያ እንግዲህ የሚ መለስ የሆነ እንደሆነ ፣ እነዚህ መሬቱን የገዙት ሰዎች ሁሉ ፣ እንኳ ዋንስ ከሉ የገዙትን ፣ በፊት የነበራቸውን ጭምር ተወርሰው ፣ ባይገ ደሉ አገር ጥለው ይሰደዳሉ ! ይህ ነበር ፊት የሆነው ። ይህንም ሁሉ ያውቃሉ ! “የማልመለስ መስሎዋችሁ ነወይ ! ሞቼ የምቀር መስሎ ዋችሁ ነወይ ፣ የኔን ርስት ደፍራችሁ የገዛችሁ ! ” እያለ ነው እጅሩ ሁሉንም ወርሶ ያሰደዳቸው ! አሁንም ለኒህ ሰዎች ወዮላቸው ! በኒያ በፊተኞች የደረሰው እንደሚደርስባቸው የማይጠረጠር ነው ! ”

“ ለኔ ደግሞ የሚታየኝ ሌላ ነው ” አለ ጥላሁን ።

“ ምን ? ”

“ መቼም አሁን ደምቆ የሚወራው ፣ የግራዝማች ወደ ሌላ አገር መዛወር ነው ። ታዲያ … መሬታቸውን ቶሎ ቶሎ መሸጣቸውን ከሚወራው ወሬ ጋር እያያይዘን ስናየው ፣ የሚያመለክተው ነገር ቢኖር

@OLDBOOKSPDF

የወረውን እውነተኛውን ወደ ሌላ አገር መዛወራቸውን ነው ። ምክ ናያቱም እሳቸው ወደሌላ አገር ከተዛወሩ ፤ እዚህ ከሚቀር ርስት ፤ ተሸጦ በጃቸው ይዘውት የሚሄዱት ገንዘብ የበለጠ ለሚጠቅማቸው ነው ። ይልቁንም ... እንደምትሉት ስለጣናቸውን መከታ አድርገው ፤ አላግባብ የያዙት ርስት ካለ ፤ እግራቸውን ከዚህ የነቀሉ እለት ፤ የዚህ አገር ባለስልጣንነታቸው የቀረ እለት ፤ ባለርስትነታቸው ጭምር ይቀራል ! ስለዚህ ፤ የዚህ መድሀኒቱ እንዲያ ያለውን ነውረኛ ንብ ረት ፤ ቶሎ ቶሎ ሸጦ ገንዘቡን በኪስ አድርጎ መሸሽ ነው ! ሁለተኛ ካሁን በፊት ግራዝማች ዳኘ መሬታቸውን በገዙ ሰዎች ላይ አሁን እርስዎ እንዳሉት ያለ ግፍ ፤ የግፍ - ግፍ ፤ ከፈጸሙና እሱንም አሁን የግራዝማችን መሬት የገዙት ሰዎች ካወቁ ፤ ያለጥርጥር ግራዝማች ወደዚህ የማይመለሱ መሆናቸውን ስላረጋገጡ ይሆናል ደፍረው መግ ዛታቸው ! ማለት ፤ እነዚህ ሰዎች ፤ የግራዝማችን መሬት ደፍረው መግዛታቸው ቅሉ ፤ ለግራዝማች አለመመለስ አንድ ምልክት ሊሆን ይችላል ። ይህ ነው ለኔ የሚታዩኝ ፤ አንተስ ምን ይመስልሀል ?” አለ ጥላሁን ወደ አባዩ ዞወር ብሎ ።

“ሁለታችሁም ግምት ፤ ወይም ትንቢት ነው የተናገራችሁ ። እስቲ እኔ ደግሞ ... ግምቱን ፤ ወይም ትንቢቱን ፤ ሊተውና የሰማ ሁትን ሳልጨምር ፤ ሳልቀንስ ፤ እንዲሁ እንደ ሰማሁት ልናገር ። አዲሱ እንደራሴ ጎሬ እንደ ገቡ ፤ አደባባዩን የሞላው የግራዝማች ክሳሽ ፤ ባደባባዩ ሲነገር የሚሰማው ግራዝማች የሰሩት ግፍና የሰሩት ወንጀል ስለነበረ ፤ መታሰራቸው ፤ ዛሬ መሸቶ ነገ እንደሚነጋ እር ግጥ ሆኖ የሚታሰሩበትን ቀን ብቻ ነበር ሰው ሁሉ በናፍቆት የሚጠ ባበቀው ። በሁዋላ ፤ ነገሩ ሁሉ እንዲያው በታምር ባህሪውንም ፤ መልኩንም ለዋወጠና ፤ ግራዝማችም እዚህ አገር በሰሩት ግፍ ፈንታ ከዚያ በፊት ፤ ድሮ በጠላት ጊዜ ፤ ባርበኝነት የሰሩት የጀግንነት ስራ ፤ እዚህ በሰሩት ወንጀል ፈንታ ፤ ከዚያ በፊት ፤ ድሮ በግሚራ ጦርነት የጨረሱት ህዝብና ያቃጠሉት አገር ይወራ ጀመር ! ከዚያ ባጭር ጊዜ ውስጥ ፤ ከንደራሴው ጋር ፍቅራቸው የጋለ ፤ ጨሌ የሚ ያቃጥል ሆኖ በቀን ቢያንስ ቢያንስ ሶስት ጊዜ እዩተጠሩ ፤ ቆይታ እያደረጉ ፤ እሹዋሚ ፤ አሻሪ ሆኑ ! አሁን ‘ለራሳቸው የሞቻቸውን አው ራጃ ገዢነት ሳያገኙ አይቀሩም ፤ የሞቻው አውራጃ ገዢ በቅርቡ ወደ ጋምቤላ የተዛወሩ ፤ ለግራዝማች ዳኘ ቦታ እንዲለቅቁ ለማድረግ ነው’ እዩተባለ በጎሬ ይወራላችሁዋል !” አለ አባዩ ከጎሬ የመጣ ሰው የነገረውን እንዳለ ደግሞ ።

@OLDBOOKSPDF

" የማደራሴው ባለሙዋል ሆኖ አሹዋሚ አሻሪ ከሆነማ ፣ ስራሴ እንኩዋንስ ከሞቻ አውራጅ ነገርነት ፣ ከኢሉባቦር ጠቅላይ እንደራሴነት የየኪን ወረዳ ገገርነት ስለሚመርጥ ፣ ወደዚህ ሳይመለስ ቢቀር ምን አለ በሉኝ !" አሉ ባላምባራስ ።

"እንዴት ? ለምን ?" አሉ አሳዬና ጥላሁን ፣ ባንድ ላይ ።

" ሀ ! እንዴት ! እንደሱ ካለ ስቃም ፣ እንደሱ ካለ ሆዳም ... የኪ ያለ ታዛቢ ጉንጭ እስኪፈጥጥ ጎርሶ ፣ ጉሮሮ እስኪታነቅ የሚጠጣበት ፣ ሰዋራ ቦታ ነዋ !" ሲሉ ባላምባራስ ፣ ስስታሙ ግራዝማች ዳኘ ጉንጮቻቸው እስኪፈጥጥ ሲጎርሱና ጉሮሮዋቸው እስኪታነቅ ሲውጡ ምን እንደሚመስሉ ለማሳየት ወብ ፊታቸውን አከፍተው ፣ ሁሉም ባንድነት ይስቁ ጀመር ። " ሀ ! ለምን ይሉኛል ! ከጥቅም ይልቅ ክብርና ስም የሚመርጡ ፣ ልበ-ኩሩዎች ናቸው እንጂ ... እንደ ግራዝማች ዳኘ ያሉት ሆዳሞች ፣ ስስታሞች ናቸው ? " አሉ ባላምባራስ ቀጠሉና ፣ እንደ መቆጣት ብለው ።

ባላምባራስ ጉዳታ አልተሳሳቱም ፣ እውነታቸው ነው ። ጥቅማቸውን ከሁሉ የሚያስቀድሙ ሰዎች ፣ ፍቅረ ንዋይ የሚጸናባቸው ሰዎች እንዲያ ያለጥቅም ከሚገድልባቸው ፣ እንኩዋንስ ሹመት ፣ እንኩዋንስ የክብር ስም ፣ እንትን መባላቸው ቀርቶ አንቺ ቢባሉ ግዴላቸውም !

የግራዝማች ዳኘ ወሬ ከሄዱ ጀምሮ ፣ ቀን እያለፈ ሌላ ቀን በተተካ ቁጥር ፣ ኢብሮ እዮተለዋወጠ የየኪን ሰው ግራ እያጋባቶት ፣ አስጨንቆት ሳለ ፣ በመጨረሻ እውነተኛውን ወሬ ውብቱ በዛብህ ይዞ መጥቶ ሲሰማ ሁሉም ጸጥ አለ ። ሁሉም አረፈ ! የሚወዱትን ፣ የሚመኙትን ለማግኘት ፣ ትንሽ እንኩዋ የተስፋ ብርሃን ማየቱ የሚያስጨንቀውን ፣ እረፍት የሚነሳውን ያክል ፣ የሚወዱት እንደማይገኝ እርግጠኛውን ማወቁ ፣ ተስፋ መቁረጡ ያሳርፋል ! ግራዝማች ዳኘ ሞተው ይሁን ታስረው ፣ ወይም ተሽረው ፣ ወይም ሌላ ፣ ማናቸውም አይደርስ ደርሶባቸው ፣ ወደ የኪ እንዳይመለሱ ፣ እዚያው በሄዱበት እንዲቀሩ ፣ የየኪ ሕዝብ በጣም የሚወደው ፣ አጥብቆ የሚመኘው ነገር ነበር ። ከሄዱ ጀምሮ ፣ " ተሻሩ ፣ ታሰሩ ፣ ተገረፉ ፣ ተሰቀሉ ፣ ተገደሉ " እዮተባለ ሲወራ ፣ ሁሉም በዮበኩሉ በሰማው ላይ ትንሽ የሚመኘውን እዮጨማመረ ፣ የሰማው ትንሽ ተጨማምሮበት አባወ ግበው ሲል እዮፈጠረ ሲያወራ ፣ ሲጨነቅ ፣ ሲታመስ ፣ ሲተራመስ ፣ ካንድ አመት በላይ ኖረ ። በመጨረሻ ውብቱ እውነተኛውን ፣ ግራዝማች ዳኘ የቀኛዝማችነት ማእረግ ተሰጥቶዋቸው ፣ ወደ የኪ ለመመ

@OLDBOOKSPDF

ለስ በመሰናዳት ላይ መሆናቸውን ፣ ቅድሞዎቻቸው መጥቶ ሲያወሬ ፣ የየኪ ሕዝብ ፣ ፶ ካመት በላይ ሲሰማው የኖረው የሚያስተመኘ ወሬ ሁሉ ፣ ፶ ካመት በላይ ሲያየው የኖረው ጥሩ ህልም ሁሉ ፣ ፶ ካመት በላይ ሲያየው የኖረው የተስፋ ብርሀን ሁሉ ፣ አሰት ፣ ኢታላይ ፣ አሳሳች መሆኑን ተረድቶ ተከፋውን ሁሉ ቆርጦ ፣ ግራዝማች ዳኘ ከፈጣሪ የታዘዙበት ፣ የማይለቁ ፣ ክፉ ቁራኛ መሆቻውን ተቀብሉ ጸኖ አሰ ። አረፈ ፤

ውብቱ በዛብህ የኢሉባቦር ምክትል በኝሮንድ ሆና ከመስራቱም ሌላ ፣ እዚያው ኢሉባቦር ከሁለት ዓመት በላይ በተጠባባቂ ኖና በገርሮንድነት ሲሰራ ባሳዬው የስራና ከበላይም ሆነ ከበታች ሰራተኞች ጋር የመግባባት ችሎታ ፣ ኖና በገርሮንድ እንዲሆን በዱጊዜው ጎሬ አዩሄዱ ስራውን የተመለከቱ ተቆጣጣሪዎችም ፣ የበገርሮንዶ ችን ያመት ጠቅላላ ሪፖርት የሚያመዛዝኑ ፣ አዲስ አበባ ያሉት የገንዘብ ሚኒስቴር ሹማምትም ተስማምተው አሳብ በሳቀረቡ ፣ እዚያው ባለበት የኢሉባቦር በገርሮንድ እንዲሆን ተወስኖ ነበር ። ነገር ግን በሁብቱ ፣ በተለይ በጎሬ ከተማ ዙሪያ ባሉት ለም የቡና መሬቶች ላይ አይናቸውን የጣሉ የጠቅላይ እንደራሴው መስሪያ ቤት የበላይ ሹማምንት ፣ ምናልባት እሱ ከዚያ የተነሳ እንደሆኑ እኒያን ፣ እንደ ወርቅ ማዕድን ባለቤታቸውን በሀብት የሚያበባንኑ መሬቶች ፣ በግዢ ፣ ወይም በሌላ መንገድ ለማግኘት ፣ “ዕድል ይኖር ይሆናል” በማለት ፣ ሰሉም ፣ ለመንግስቱ ስራም ያሰቡ መስለው ፣ ተንኮላቸውን ሸር በው ፣ በገቢውም በደረጃውም ፣ ከፍተኛ ወደ ሆነው አገር ፣ ወደ ከፋ ጠቅላይ ግዛት ጅማ እንዲዛወር አስደረጉ ።

ውብቱ ፣ ወዳጆች መስለው በሉ ከሳራ መጠቀም የፈለጉትን ሰዎች ተንኮል ቶሎ ስለ ተረዳው ፣ የሮኛ ትምህርት ያለው ሰው ከጅማ በደመወዝ ቀጥሮ ወስዶ ፣ በደመወዙ ላይ ከተጣራ ትርፍ ከመቶ አስር አበል ሊሰጠው ተዋውሎ ፣ በዘመናዊ ያሰራር ዘዴ እዩሰራና እያሰራ እንዲጠብቅለት መሬቶቹን ሁሉ ሰፍሮና ቆጥሮ አስረከቦት ፣ ምሽቱ እቻሜ ቤታቸውን አሰናድታ ለመቆዩት ጉዋዛቸውን አስጭና ፣ ልጆ ችን ይዛ ፣ ከጎሬ በቀጥታ ወደ ጅማ ስትሄድ ፣ እሱ ባመት የሚፈቀ ድለትን ያንድ ወር እረፍት ለማረፍና ፣ ወዲያውም ከነ ጥላሁንና ከነ ኦላዬ ለመሰንባበት ወደ የኪ ሄደ ። ጥላሁንና ሶፊያ የውብቱን መም ጣት ካሰራ አምስት ቀን በፊት ጽፎለቻው ፣ ሰምተው ስለነበረ ፣ ሶፊያ እቻሜን ለማየት ቢብርቱ ናፍቆት ስትጠባበቅ ፣ ጉዋዝ አስጭና በቀ

@OLDBOOKSPDF

ጥታ ወደ ጅማ መሄድዋን ውብቱ ሲነግራት ፣ እኩርፋ ፣ ሁለት ቀን ሙሉ ንግግር ከልክላው ነበር ። በሁዋላ በሱ ማባበል ብዛትም ፣ በጥላሁንና ባሳዬ አማላጅነትም ታረቀችው ።

“ አንተስ ይሁን በጄ ! መቸም ወንዶች ልባችሁ . . ካለት ድንጋይ የተሰራ ፣ ምንም የማይሰማችሁ ስለ ሆናችሁ ሰው የሚያስብ ፣ የሚናፍቅ አይመስላችሁምና ፣ አንተ ወደዚህ ስትመጣ እስዋ በቀጥታ እንድትሄድ አገዘሀት ይሆናል ! እኔን የገረመኝ ያቺ ፣ ‘ ፉናየ ’ አንተ ያልሆትን ሰምታ ፣ ልብዋ ችሎላት ፣ ሳታየኝ መሄድዋ ነው ! እኔ ብሆን ባላረግሁት ! ” አለች ሶፊያ ፣ ከውብቱ ጋር የታረቁ እለት።

“ በራሴ ፣ በምሽቴ ፣ በልጆቼና እንዲያው . . በምወደው ሁሉ ምዬ ስነግርሽ አላምንኝ ካልሽ እንዴት አድርጌ ብነግርሽ ነው የምታምኚኝ ? ‘ ምንም ቢሆን ውሮየን ሳላይ ከዚህ አገር አልሄድም ’ ስላለች ተጣልተን ፣ ገላጋዩን ሁሉ አሸንፋ ነበር አልሁሽኮ ! በመጨረሻ እኔ አይቻችሁ ሄጄ ስተካላት ፣ ፈንታዋን መጥታ የፈለገችውን ያክል ብትቆይ ላልታወም ውለታ ስለገባሁ ነው . . በዚህ ተስማምተን የሄደች ። መቸም ያን ያዩሽውን ግትልትል እቃና ጉዋዙን ሁሉ ጭኖ ፣ በዚያ ላይ ትልቁ እንኩዋ ግዴለም ፤ ጨቅላ ልጅ ይዞ ፣ የወር መንገድ በዚህ ዞሮ ጅማ መሄድ አይቻል ! ስለዚህ ወይ አሁን እንደ ተስማማነው በዩትራ መምጣት ፣ ያለዚያ . . . ሁለታችንም በቀጥታ ወደዚያው መሄድ ፣ ሁለታችንም አለመምጣት ነው ! ” ሲል ውብቱ የመጨረሻ ክፍል ንግግሩን በቀልድ አጠይዎ !

“ እሱማ . . ይሻል ነበር ፤ ጭራሽ ባትመጣ ፤ በዚያው እንደ ሰዋ ብትሄድ ጥሩ ነበር ! ” አለች ሶፊያ እንደሱ በቀልድ መልክ ።

ብቻ ውብቱ መጀመሪያ እንዳቀደው የረፍት ጊዜውን ፣ አንዱን ወር በሙሉ ፣ ከነ ጥላሁን ጋር ፣ የኪ ማሳለፍ አልፈለገም ። እሱ የኪ በገባ በስምንተኛው ቀን ፣ ቀኛዝማች ዳኘ ወደ የኪ ለመመለስ ከጎሬ ተነስተው ፣ እግረ መንገዳቸውን እትውልድ አገራቸው ፣ አልጋ ደርሰው ለማለፍ ፣ ወደዚያ መሄዳቸውን ሲሰማ ፣ የኪ በሚገቡበት ጊዜ እዚያ ቆይቶ እንዳይገናኛቸው ቀድሞ መውጣት ፈለገ ። ምክንያቱ ፣ ቀኛዝማች ዳኘ ገና ግራዝማች ሳሉ ፣ ወደ የኪ የሚመለሱ መሆናቸውም ገና ሳይታወቅ ፣ በጎሬ ፣ ‘ ባይሾሙ ሊያሾሙ ይችላሉ ’ ተብለው ደጅ ከሚጠኑዋቸው ሹማምት አንዱ ውብቱ ስለነበረ ፣ ጥዋት ቢቀሩ ማታ ፣ ብዙ ጊዜ ግን ጥዋትና ማታ ፣ እቤቱ ሳይደርስ የሚያልፍ ቀን አልነበረም ! እሱም አክብሮ ተቀብሎ ፣ ደህና አድርጎ

@OLDBOOKSPDF

አስተናግዶ ይሸኛቸዋል ። ነገር ግን ከኢሉባቦር ወደ ከፋ ጠቅላይ ግዛት መዛወሩ ተረጋግጦ ሲታወቅ ፤ ቤቱን እርግፍ አድርገው ተውትዛ እንዲያውም አይምልም እንጂ ፤ አደባባይ እንኳ ድንገት ሲያጋጥ ማቸው ፤ ሰላምታ እንዳይሰጡት ያላዩ ለመምሰል ፊታቸውን እያዞሩ ሲሄዱ ብዙ ጊዜ ያያቸው መሰለው ። ስለዚህ ፤ እንዲህ ያለ ስሜት ፤ የሚያሻክር ሁኔታ በመሀከላቸው ተፈጥሮ ሳለ ፤ እዚያ መገናኘቱ ሁለቱንም ፤ "ባልተገናኘን" ! የሚያሰኝ ነገር ሊያስከትል ስለሚችል ፤ "ከዚህ ሁሉ ቀድሞ መሄድ ይሻላል" ብሎ በዚሁ ቆረጠ ።

"እኮ 'አንድ ወር እቆያለሁ' ስትል ሰምቼ ፤ እውነት መስሎኝ ፤ ልጠይቅህ ያሰብሁትን ብዙ ነገር .. 'መቸም ጊዜ አለን' ብዬ አልጠየቅሁህም" አለ አሳዬ ፤ አንድ ቀን ምሳ እሱ ቤት በል ተው ሲጫወቱ ፤ ውብቱ አሳቡን መለወጡን የውሸት ምክንያት ፈጥሮ ሲነግራቸው ። ጥሬሁን ከንምሽቱ ፤ ያሳዬ ምሽት ፤ የውብዳርና ባላ ምባራስ ጉዲታም እዚያ ነበሩ ።

"ልትጠይቀኝ የፈለግኸው ምን ኖሮዋል ? አሁን አትጠይቀ ኝም ? "

"ነገ - ከነገ ወዲያ እሄዳለሁ" ካልህ በንቱን ጠይቄህ ለስንቱ መልስ ልትሰጠኝ ትችላለህ ፤ ነገ ፤ ከነገወዲያ የምትሄድ ከሆንህ ፤ ሲወራው ያለን ጊዜ ዛሬ ፤ ቢበዛ ነገ ጭምር መሆኑ ነው ። ታዲያ ይህ ጊዜ እንኳንስ ለመልሱ ጭምር ለጥያቄው ብቻስ ይበቃል ?" አለ አሳዬ ፤ ውብቱ እዚያ አብሮዋቸው የቆዩበት ጊዜ ምን ያክል አጭር መሆኑን አጋኖ ለማሳየት ያክል ።

"አ . . ይ ፤ ለጥያቄህ ሁለት ቀን የማይበቃ ከሆነስ ፤ ለመልሱ ወርም መብቃቱን እንጃ ! ወርም አይበቃ ይሆናል !" አለ ውብቱም በመቀለድ ።

"እስቲ የናንተን ሁለት ቀን የማይበቃው ጥያቄና ወር የማይበ ቃው መልስ በቀጠሮ አቆዩና ፤ እኔ አንድ አጭር ጥያቄ እንድጠይቅ ፍቀድልኝ ፤ በገርሮንድ ውብቱ" አሉ ባላምባራስ ጉዲታ ፤ የሞላ የጠጅ ብርጭቆዎቻቸውን ፉት ብለው አጉድለው እፊታቸው ተከሉና ።

"ምን ?" አለ በዥሮንድ ውብቱ ።

"ይህ ዲያብሎስ ፤ ይህ ዳኛቸው ፍሪሳ ፤ በዚህ አገር ህዝብ ላይ የሰራው አይሰሩ ስራ ፤ የሰራው ወንጀል ስላልታወቀ ነው ? ወይስ ስለ ታወቀ 'አበጀ' ተብሎ ነው ፤ በማእረግ ላይ ማእረግ ተጨ ምሮለት ፤ ያኑ የለመደውን ስራ እንዲቀጥል ወዲህ ተመልሶ የመጣ ?"

@OLDBOOKSPDF

"እኔም 'ብዙ ነገር ልጠይቅህ አስቤ ነበር' ካልሁት እንዲያው አሁን ባላምባራስ ያነሱት ፤ የግራዝማች ፤ ይቅርታ የቀኛዝማች ዳኘ ነገር ነው ። ከዚህ ከመሄዳቸው ጀምሮ ተሻሩ ፤ ታሰሩ ፤ ተገረፉ ፤ ተሰቀሉ ፤ ምን ስንቱን . . እዩ ተባለ መአት ሲወርባቸው ኖሮ ፤ ዘመጨረሻ ያ ሁሉ ቀርቶ ፤ እንዲያውም የማእረግ ስም ተጨምሮላቸው ፤ ወደዚህ መመለሳቸው የሚያስገርም ነው ! ይህ ሲሆን ደጅ ሳል ብሎ ያሰበ . . ከባላምባራስ በቀር የለም !" አለ አሳዬ ፤ ወደ ባላምባራስ ጉድታ ባንጩ አመልክቶ ውብቱ መልስ ከመስጠቱ በፊት፤ ብርጭቆውን አንስቶ ከጠጪ ሁለት ጊዜ ተንንጭቶ መልሶ አስቀመጠና ።

"ኡም . . ! የ . . ቀኛዝማች ዳኘ ነገር መቸም ያላስገረመው የለም !" አለ ፤ እይንን እራሱ ከተቀመጡት ሰዎች ራስ አሻግሮ አግድግዳው ድምድም ላይ ተክሎ ። "ልክ ነው ፤ የሳቸው ነገር በውነት የሚያስገርም ነው ! የከሰሳቸው ሰውና የተከሰሱበት ወንጀል እጅግ ብዙ ስለ ነበረ . . . 'ጥፋታቸው ስላልታወቀ ነው ፤ በማዕርግ ላይ ማእርግ ተጨምሮላቸው ወደ ጥንት የግዛት አገራቸው እንዲመለሱ የተደረገ' ለማለት አይቻልም ። ብቻ ባንድ ታምራዊ ምስጢር ያ ሁሉ ከሳሽ ፤ ያ ሁሉ አቤት ባይ ፤ አቤት ያለበት ቁጥር ስፍር የሌለው ወንጀል የሚያሾምና የሚያሸልም ጀብዱ እንደሆነ ሁሉ ፤ ያ ሁሉ አቤቱታ ፤ ያ ሁሉ እግዚአታ የግራዝማች ዳኘን ወንጀል ፤ 'በደላቸውን ይቅር በሉልን' በማለት እንደ ተደረገ ሁሉ ፤ ወንጀላቸው ተፍቆላቸው ፤ ከበደላቸው ታጥበው ፤ ጠርተው ፤ ድንገት ባለሙዋል ሆነው ሲገኙ ፤ ያ ሁሉ አቤት ባይ ወዴት እንደ ደረሰ . . . እንጃ ! ዱብዛው ጠፋ !" አለ ውብቱ ፈገግ ብሎ ፤ መጀመሪያ ባላምባራስን ፤ ከዚያ የቀሩትን ሁሉ ፤ አንድ ጊዜ ባይኑ ግረፍ አደረገና።

"ታዲያኮ እንዲህ ያለውን ታምራዊ ምስጢር ፤ እንዲህ ያለውን . . የሚያስቀጣውን ወንጀል ወደሚያሾምና የሚያሸልም ጀብዱ ፤ 'የቅጠልንን' አቤቱታ ፤ ወደ 'ሸሙልን' እግዚአታ የሚለውጥ ታምራዊ ምስጢር ብናውቀው ባልጠላን !" አለ አሳዬ ፤ እንደ መሳቅ ብሎ ።

"መቸም . . አዲሱን እንደራሲ ፤ መልካቸውን እንኳን ባታውቁ ስማቸውን ሳትሰሙ እንዳልቀራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ !" ሲል ውብቱ ፤ ሁሉም ፤ "አልሰማንም" ለማለት ራሳቸውን ነቀነቁ ።

"ሚኒስትርነ የነበሩ ሰው ናቸው ፤ እንዴት ስማቸውን ሳትሰሙ ቀራችሁ ? እኔ ገና አዲስ አበባ ትምህርት ቤት ሳለሁ ጀምሬ ስማቸውን

ደህና አድርጌ አውቃቸው፣ "ጥሩ ሰዎች ናቸው" ተብለው ከሚመሰገኑት ሚኒስትሮች መሀከል አንዱ ነበሩ ። እስና እዚያ ካሉት መሀከል የሚናገር እንዳለ አንድ ሦንድ ባይኑ ቢጠይቅ፣ ሁሉም የሱን አፍ እየተመለከቱ ዝም ስላሉ ፣ ስለ እንደራሴው የሰማውንና የሚያውቀውንም ፣ በሰማውና በሚያውቀው መሰረት ፣ "የማያጠራጥር እውነት ነው" ብሎ ያመነበትንም መናገር ጀመረ ።

"እንደራሴው" አለ ውብቱ ፣ ከምን እንደሚጀምር ጠፍቶት ትንሽ ጣራ ጣራውን ሲመለከት ቆዩና ። "እንደራሴው ጣሊያኖች ኢትዮጵያን በወረሩበት ጊዜ በትምህርት ላይ የነበረውን ትውልድ ሲጨርሱ ፣ መልካም እድል ረድቶዋቸዋል ፤ አምልጠው ወደ ውጭ አገር ከተሰደዱት መሀከል የነበሩ ፣ ከዚያ ሲመለሱ እንደ ስደተኞች ሁሉ ፣ ባገር ፍቅር የመጀመሪያውን ማእረግ እንዲይዙ የታዘዘላቸው ከመሆናቸውም ሌላ ፣ ትጉ ፣ ቅንና ንጹህ ሰራተኛ መሆናቸው ደምቆ ይወራላቸው ስለ ነበረ፣ ሁልጊዜም በከፍተኛ ደረጃ ፣ በልዩ ልዩ መስሪያ ቤት እየተዘዋወሩ ሲሰሩ ቆይተው ፣ ከዚያ መጀመሪያ የስራ ሚኒስትር ፣ ቀጥለው የፍርድ ሚኒስትር የነበሩ ናቸው ። ባዲስ አበባ የቡዋልት ከበብ ዙሪያ እንደሚወራው ከሆነ ፣ በልዩ ማብሩት የሚያውቅ ሁሉ ፣ እንኩዋንስ በሚኒስትርነት ፣ ከዚያም በታች ቢሆን ፣ ሁለት ሶስት አመት በስራ ሚኒስቴር ውስጥ ስልጣን ይዞ ሲሰራ የቆዩ ሰው ፣ ከዚያ በሁዋላ ምናልባት . . ሽባ እንዳይሆን ፣ ወይም በግሩ መሄድ እንዳይጠፋው ካለሰጋ ፣ እድሜውን ሙሉ ካልጋ ሳይወርድ እዚያው ከጌትነቱ ጋር እንደ ተቃቀፈ ተኝቶ መኖር ነው ! " እስና ውብቱ ከፈገግታ ጋር ፣ "ይህ መቸም የቡዋልት ከበብ ሰዎች ወሬ ለማጠፈጥ ብዙ ቅመማ ቅመም መጨመር ስለሚወዱ ፣ ከዚያ አንዳንዱ መሆኑ አይጠረጠርም ። ነገር ግን ፣ ወሬ ለማጣፈጥ የተጨመረው ቅመማ ቅመም ቢቀነስም ፣ የስራ ሚኒስቴር ትንሽ ቆርሶ የማይጎረስበት ቤት ስለሆነ ፣ ለሚያውቅ ሰው ፣ ጠግቦ በልቶ አብልቶ የሚያጠግቡበት ነው ! " ሲል ሁሉም ተያይዘው ይስቁ ጀመር ።

"እውነቴንኮ ነው " አለ ውብቱ ። "ቀልድ እንዳይመስላችሁ ፤ እውነቴን ነው ። ብዙ መቶ ኪሎ ሜትር አውራ ጎዳናዎችን ፣ ያይሮፕላን ሜዳዎችን ፣ ትላልቅ ግድቦችን ፣ ድልድዮችንና ፣ ልዩ ልዩ ህንጻዎችን ለመስራት የሚጫረቱ የፈረንጅ ኩባንያዎችና ሌሎች ተቋዋራጮች በቅድሚያ ለስራ ሚኒስቴር ሹማምት ይዘው የሚቀርቡት ገጸ በረከት በሚሊዮን ፣ "እጅግ አነሰ" ሲባል ፣ በመቶ ሺህ ቤት ፣ የሚቆጠር እንደ ምንም ቢሆን ከዚያ ሊያንስ የማይችል ነው ! ስለዚህ ነው ፣ "የስራ ሚኒ

@OLDBOOKSPDF

ስቱር ትንሽ ቁርሶ የማይገረሰበት ቤት ነው የሚባለው ! ታዲያ እንግዲህ ፥ እንዲህ ባለው ቦታ ፥ እንደ አዲሱ እንደራሴያችን ቅንና ንጹህ መሆናቸው ደምቆ የሚወራላቸው ሰዎች ማድረጉ ጥሩ ዘዴ መሆኑ ስለታመነበት ነበር ፥ መጀመሪያ የስራ ሚኒስትር ሆነው የተሾሙ ። ብቻ . . ” ብሎ ውብቱ ንግግሩን ሳያበር ፥

“ቆይ እስቲ ፥ አንድ ያልገባኝ ነገር አለ ። ገጸ በረከት ያልኸው መቸስ ጉቦ አይደለም ? ” አለ ጥላሁን ፥ አቋርጦ ።

“ልክ ነው ! ጉቦ ያለም ስሙ ፥ ገጸ በረከት የክርስትና ስሙ ከመሆናቸው በቀር ነገሩ ያው . . አንድ ነው ! ”

“እሺ ይሁን” አለ ጥላሁን እዩሳቀ ። “ግዶለም ይሁን ። ብቻ እንደራሴው ቅንና ንጹህ መሆናቸው የታወቀላቸው ከሆነ ፥ ጉቦ በልተው ማብላት ያውቃሉ” ተብለው ፥ “ትንሽ ቁርሶ የማይገረሰበት ቤት” ባልኸው ፥ “በስራ ሚኒስቴር ተሾሙ” ያልኸው “እንዴት ነው ? አልገባኝም ፥ ተማታብኝ ! ”

“የሚፈለገውም እሱ ነው’ኮ ! የሚፈለገው ነገሩ እንዳይገባ ፥ እንዲምታታ ነው ” አለና ውብቱ እዩሳቀ ፥ “እኒያ ሰዎች የዋዛ ሰዎች አይደሉም” አለ ቀጠለና ። “ይህን የሚያስተናብሩ ሰዎች ተራ ሰዎች እንዳይመስሉህ ! ያደፈን ከማንጻት ንጹህን ማሳደፍ እንደሚቀልል ሁሉ ፥ የጉቦ እመል ያለውን ሰው እንዲያ ያለ እመሉን ከማስተው ፥ የሌለውን ማስተማሩ እጅግ ቀላል መሆኑን ደህና አድርገው የሚያውቁ መምህራን ናቸው ! ስለዚህ . . ፊት ባያውቁም በቀላሉ እንደሚማሩ ሙሉ እምነት ነበራቸው ! ”

“እሪ ለመሆኑ እነዚህን . . ‘የሚያስተናብሩ’ የምትላቸው ሰዎች ፥ ጉቦ በልቶ በማብላት የሰለጠነ ሰው እጥተው ነው በሙያው ልምምድ የሌለው ሰው ገና ፥ ‘አንድ’ ብለው ማሰልጠን የሚፈልጉ ? ”

ውብቱ ለተጠዬቀው መልስ በመስጠት ፈንታ ፥ ጠጅ የሞላ ብርጭቆውን አንስቶ እስኪጋመስ ጠጥቶ አስቀመጠና ፥ ባንጻሩ ወዳለው የግድግዳ ድምድም ዝም ብሎ በፈገግታ ሲመለከት ቆይቶ “አይደለም ! አጥተው አይደለም ”አለ ፥ ፈገግ እንዳለ አይኖቹን ከድምድሙ አውርዶ አጥላሁን ላይ አሳርፎ። “አጥተው ሳይሆን ፥ ንጹህ ስም ያለው ሰው ጉቦ መብላትና ማብላት ማስተማር የሚመርጡ በሁለት አበይት ምክንያቶች ነው ። አንደኛ ፥ ንጹህ ስም እንደ ንጹህ መጋረጃ ጥሩ መሸሸጊያ ነው። እሱን በፊት ጋርዶ ፥ በሱ ሁዋላ ተሸሽጎ የፈለጉትን እንደሚፈልጉ አድርጎ ቢበሉ አያሳይም ! ”

@OLDBOOKSPDF

"ልክ ነው ፤ በሆርንጀ አውንቱን ነው ። አሳላፊዎች ከተጠንቀቁ ምግብ በነኩበት እጃቸው መጋረጃውን ካልነኩ ፣ ከመጋረጃው ውስጥ ያሉት ምን እንደሚበሉ ፤ ወይም እንዴት አድርገው . . . ፈትፍተው ይሁን አገንፍተው እንደሚበሉ ማንም ሊያውቅ አይችልም ! " ሲሉ ባላምባራስ ጉዶታ አቋርጠው ፣ እዚያ ያሉት ሁሉ ዶበቁ ጀመር ።

"እየውልህ" አለ ወብቱ ፣ ባላምባራስ አቋርጠው በተናገሩት ከሉሉች ጋር ሲስቅ ቆይቶ ። "እየውልህ ፤ ንጹህ ለምም አሁን ባላምባ ራስ እንዳሉት ፣ እንደ ንጹህ መጋረጃ እንዳይነካካ ብቻ አሳላፊዎች ከተ ጠንቀቁ ፣ በሉ ሁዋላ ተሸሽገው የሚበሉትም ፣ የሚያበሉትም ሰዎች ምን እንደሚበሉና እንዴት እንደሚበሉ ሳይታወቅባቸው ብዙ ጊዜ ሊቆዩ ይችላሉ ! ይህ ነው ንጹህ ለም ያለው ፈልጎ ጉቦ መብላትና ማብ ላት ማስተማር የሚመረጥበት አንዱ ምክንያት ! ሁለተኛው. . . "አለና አሁንም ብርጭቆውን አንስቶ ከጠጁ ሁለት ጊዜ ተጎንጭቶ ካስቀመጠ በሁዋላ ፣ እንደገና ዝም ብሎ በፈገግታ የግድግዳውን ድምድም እያሻ ገረ ሲመለከት ቆይቶ ፤ " ሁለተኛው ምክንያት ፣ 'ነውረኛ ለሆነ ሁሉ ፣ ንጹህ ጎረቤትን ነውረኛ ከማድረግ የተሻለ የነውር መሸፈኛ አይገ ኝም' የሚሉት ነው ! ,, አለ ፈገግ እንዳለ ጥላሁንን እያዩ ። ጥላሁን በጥያቄ አይን ወብቱን እዬተመለከተ ዝም አለ ።

"በነውረኞች መሀከል " አለ ወብቱ ቀጥሎ ፣ ሁለተኛ ምክንያት ያለውን ለማብራራት ። "በነውረኞች ፤ ለምሳሌ . . እንበል ! በጉቦኞች መሀከል ፣ አንድ ንጹህ የተገኘ እንደሆነ ፤ ወቅሶ እንዳያስወቅስ ፤ አምቶ እንዳያሳማ ፣ እንደ ምንም አድርገው እሱንም ለነውራቸው ተካፋይ እንዲሆን ማድረግ አለባቸው ! እንዲያውም. . . "አለ ፣ አይኖቹን ከጥላ ሁን ላይ አንስቶ ሳያረግብ ፊት-ለፊት ተክሎ ትንሽ ሲያስብ ቆዩና ። "እንዲያውም ይህ ከጥላ ጎደል የሰው ሁሉ ጠባይ ነው ማለት ይቻላል። ማንም ቢሆን ፣ እንኩዋንስ ነውረኛ ደህና ሰውም ቢሆን ፣ ለመልካም ሥራ ፣ ሲታላቅ ስራ ነው እንጂ ለብቻው ባለቤት መሆን የሚፈ ልግ ፣ ለክፉና ለወራዳ ሥራ ብቻውን ባለቤት መሆን የሚፈልግ የለም! ብቻ . . ይህ ሁሉ እንኩዋ ጥላየ "ንጹህ ሰው መሆናቸው የታወቀላቸው ከሆነ ፣ እንዴት ጉቦ በልተው ያበላሉ ተብለው ለስራ ሚኒስትርነት ተመ ረጡ ? " ብሎ ስለ ጠዬቃኝ ነው እንጂ ፣ ልነግራችሁ የፈለግሁት ሌላ ነው። አሁን ልነግራችሁ የፈለግሁ ፣ እንደራሴው ከማደፍና ከመጉደፍ እጃቸውንም ፣ ህሊናቸውንም ፤ አንጽተው መስራትንና ፣ ከሰው ለህግ መታዘዝን የመረጡ ሰው በመሆናቸው ፣ ይህ እንደ ብርቱ ጥፋት ቁጥሮ ጥሮ ከሚኒስትርነት ደረጃ ወርደው በእንደ ራሴነት ወዲህ እንዲመጡ ስላ ደረጋቸው ፣ አሁን . . በዘመድ ምክር ብዛት ባለፈ ጥፋታቸው ተጸጽተው

@OLDBOOKSPDF

ይሁን ፣ ወይም ፈርተው ፣ የተለመደ ያሰራር መንገዳቸውን ፈጽመው የለወጡ መሆናቸውንና ፣ ግራዝማች ዳኘም ለተከሰሱበት ወንጀል የሚገባ ቅጣታቸውን በማግኘት ፈንታ ፣ የቀኛዝማችነት ማዕረግ ተጨምሮላቸው ወዲህ እንዲመለሱ የተደረገበት ምክንያት ከዚህ ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው ፡ ”

“ይቅርታህን ፣ ባል ቀጥል ። ብቻ . . ቢሆንም መጠየቁ አላከፋውም ፤ ባልጠይቅ ኖሮ እኛ የማናውቀውን ፣ አንተ የምታውቀውን የጉቦ ምስጢር አታስተምረንም ነበር!” ሲል ጥላሁን ሁሉም ሳቁ ።

“በል ግዴለም ፤ እሱ ሌላ ምእራፍ ስለሆነ ፣ ይህን የጀመርነውን ጨርሰን ሌላ ጊዜ እንነጋገርበታለን ” አለና ውብቱ ፣ ጥላሁን በተናገረው አሽሙር እንደ መሳቅ ብሎ ፡ “ ግራዝማች ዳኘ ቀኛዝማች ተብለው ወደ ቦኪ የተመለሱበት ምክንያት ፣ እንደራሴው ከሚኒስትርነት ደረጃ ወርደው በእንደራሴነት ወደ ኢሉባቦር ከመምጣታቸው ጋር የተያያዘ ነው” ያለውን መግለጽ ጀመረ።

“እንደራሴያችንን” አለ አይኑን እንደ ልማዱ እማዶው የግድግዳ ድምድም ላይ ተክሎ ። “እንደራሴያችን ቅድም ባልሁዋቸው ምክንያቶች ፣ ለከፍተኛው ማህበር አባል ሆነው እየጠቀሙ ወዲያው እንዳቅማቸው እንዲጠቀሙ ታስቦና ፣ ባሳቡ ደስ እንደሚላቸው ታምኖ ፣ ለጥቂት የተመረጡ ሰዎች ተቆጥቦ ለሚጠበቅ ቦታ ፡ ለስራ ሚኒስቴር ሚኒስትር አድርገው ቢሾሙዋቸው ፣ ይህን እንደ መከበርና እንደ መፈቀር በማየትና ፡ ደስ በመሰኘት ፈንታ ፣ ምን እንዲያደርጉ ታስቦ እዚያ እንደ ተሾሙ በተዘዋዋሪ መንገድ ስለ ተገለጸላቸው በጣም አዘኑ ። በተዘዋዋሪ መንገድ የተገለጸላቸው “ምናልባት አልገባቸው ይሆናል ተብሎ ፣ ምስጢር አዋቂዎች የሆኑ ሰዎች በግልጽ ቢነግሩዋቸው ፣ በፍጹም መስማት አልፈለጉም” ይባላል ። ሙችም የበላይን ወራዳ ምስጢር እንዳያውቁ መሸሽ ነው እንጂ ፣ አውቆ እንደ ተፈለገው “ተካፋይ አልሆንም” ማለት በራስ ላይ አደጋን መጋበዝ መሆኑ የታወቀ ነው! ስለዚህ ፣ በዚህ ሰውና በበላዮቻቸው መሀከል የተፈጠረውን ሁኔታ ያወቁ ዘመድ ወዳጆቻቸው ሁሉ አጥብቀው ሰግተውላቸው ነበር” ይባላል ። ብቻ የሚያስገርመው ፣ እግዜር ስለ ጠበቃቸው ይሁን ወይም “እንዲህ ያሉት ጠንካራ ሰው ተመክረውና ተጸጽተው እንዲመለሱ የተደረገ እንደሆነ ፣ የዚያን ያክል ጠቃሚ አገልጋይ ሊሆኑ ስለሚችሉ ለዚሁ እድል ይሰጣቸው” ተብሎ እሳቸውም ፣ ዘመድ ወዳጆቻቸውም የሰጉት ቀርቶ የፍርድ ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ ።

@OLDBOOKSPDF

"አዲስ አበባ እንደሚወራው ፣ እኒህ ሰው ቅንና ንጹህ አገልግሎታቸውን ለህዝብ መስጠት ከሌቻሉ ሳያድቱና ሳይጉድፉ ከመንግስት ስራ ወጥተው የግል ስራቸውን እየሰሩ ለመኖር ይፈልጉ ስለነበረ ፣ የፍርድ ሚኒስትር ሆነውም ፣ 'ህግን በትእዛዝ አልሽርም' ስላሉ ፣ 'የስልጣናቸውን ወሰን አያለፉ የበላይ የሚጋፉ ፣ 'ማን አለብኝ ባይ' የሚባል ስም ወጣላቸው። ከዚያ መቸም 'እውነተኛና ንጹህ ስለሆኑ ተጋዙ' አይባልምና ፣ ስምና መልክ የሚያከፋ ነገር ይፈለግላቸው ጀመር ። ሌሊት ሲጠጡና ሲጨፍሩ እያደሩ ቀን በሌሚቱን ሲፈለጉ በስራቸው አይገኙም፤ ከልክ ያለፈ እዩጠጡ በብዙ ሰው መሀል ሲነገር የማይገባውን የመንግስት ምስጢር ያወጣሉ ፤ በቢሮዎቻቸው ውስጥ ከሰው ምሽት ጋር ነውር ስራ ሲሰሩ ታዩ" እዩተባለ ፣ ይህና ይህን የመሳሰለ ስም የሚያከፉ ልዩ ልዩ የውሸት ወሬ እዩተፈጠረ ሲወራ እንዲቆይ ተደረገና ፣ መልካቸውም ፣ ስማቸውም ከነበሩዋቸው ንጽህና ትንሽ አደፍ ያሉ ሲመስል ፣ ከሚኒስትርነታቸው ተሽረው ፣ የኢሉባቦር እንደራሴ ሆነው ወዲህ መጡ። እንደሳቸው ላሉ ፣ በውቀታቸው ፣ በስራ ችሎታቸውና ፣ በሀገር አገልግሎታቸው ሁሉን የሚቀድሙ እንጂ የሚቀድማቸው የሌለ ለሚመስላቸው ፣ ለመንግስቱ ሙሉ ባለቤትነት ለሚሰማቸው ሰዎች ፣ ከመንግስት አባልነታቸው ወርደው የክፍለ ሀገር እንደራሴ መሆን ራሱ የግዞተኛነት ምልክት ነው! በተለይ የኢሉባቦር እንደራሴ መሆን ደግሞ ግዞቱ አደገኛ ደረጃ የደረሰ መሆኑን የሚያመለክት ነው!

"እንደ አዲስ አበባ አስተሳሰብ ፣ ከጠቅላይ ግዛቶች ሁሉ ኢሉባቦርና ገሞጎፋ የንስሀ ቦታዎች ናቸው። መቸም እንደምታውቂት ፣ በጠቅላላው ፣ የንስሀ ቦታ ማለት ፣ ጥፋተኞች ጥፋታቸውን ተረክበውና ተጸጽተው ምህረት የለመኑ ፣ የተማጸኑ እንደሆነ ፣ ይቅርታ ተደርጎላቸው እንዲመለሱ ፣ ጥፋታቸውን ያልተረከቡና ያልተጸጸቱ እንደሆነ ፣ ወደ መጨረሻ የቅጣት ቦታቸው እንዲሄዱ ፣ የምርጫ እድል ተሰጥቶዋቸው የሚቆዩበት ነው ። ወደ ኢሉባቦርና ወደ ገሞጎፋ ባገረ ገዥ ስም የሚላኩት የመኩዋንንት ግዞተኞች ሁኔታም እንደዚያው ነው ። ጥፋታቸውን ተረክበው ፣ ተጸጽተው ፣ ምህረት ለሚለምኑ ግዞተኞች ፣ ኢሉባቦርና ገሞጎፋ መማለጃና መማጸኛ የማይገድባቸው ፣ መማለጃና መማጸኛ እንደ ልብ የሚገኝባቸው አገሮች ስለሆኑ ፣ በንዲያ ያለው መማለጃና መማጸኛ አማካይነት ቶሎ ምህረት አግኝተው ይመለሳሉ ! ጥፋታቸውን ለማይረከቡና ለማይጸጸቱ ግን ከሹመቱ ፣ ከጌትነቱ ፣ ከባለሙዋልነቱ ፣ ከክብሩና ከማእረጉ ሁሉ ፣ ለሁልጊዜ ተለይተው ድህነቱ ፣ መንገላታቱ ፣ ውርደቱ ፣ እንዲያው ባጠቃላይ ከፉው ነገር ሁሉ ፣ ተሰብስቦ ወደተከ

@OLDBOOKSPDF

ማቆበት ወጥተው የሚወረወሩባቸው በሮች ናቸው ! ስለዚህ ፣ አሁን እን ደራሴያችን እዚህ እንስህ ቦታ ከገቡ ፣ ከሁለት ማማረሚያዎች አንዱን መያዝ እንዳለባቸው የተረዱ ይመስላል ። ማለት በጥፋታቸው ተጸጽ ተው ምህረት መለመን ፣ ወይም በጥፋታቸው አለመጸጸትና ለሁልጊዜ ከሀብት ፣ ከሹመት ፣ ከምቾት ፣ ተለይቶ በግዞትና በድህነት መኖር ! ብቻ ያም ሆነ ይህ ፣ ተጸጽቶ ምህረት ለሚለምን መማለጃና መግጃኛ የሚሆን ምህረት ከመለመን የሁልጊዜ ግዞትን ለሚመርጥ ስንቅ የሚሆን ገንዘብ ያስፈልጋል ! ለዚህ ነው እንግዲህ . . . ” አለና ውብቱ ብር ጭቆውን እንስቶ ጨልጦ ካስቀመጠ በሁዋላ ፣ “ለዚህ ነው እንደ ቀኛ ዝማች ጎኛ ያሉ ፣ ቢዝቁት የማያልቅ ገንዘብ ያላቸው ሰዎች ከያሉበት ጸመብራት እዬተፈለጉ ፣ ከተበከሉበት እድፍ ጉድፍ በተቀደሰበት ጠበል ታጥበው እዬነጹ ቀርበው ፣ ባጭር ጊዜ ባለሙዋል ሆነው ፣ አሁን እነሱ ካልመጡ የቀረበው መሶብ ሳይከፈት የሚነሳው ! ይገርማችሁዋል ! እን ደራሴያችን እዚህ እገር የሚቆዩበትን ጊዜ አሉተማመኑትም መሰለኝ፤ ከመምጣታቸው ጎሬ ገቢያ ውሎ የሚመለሰው ገጠሬ ሁሉ እስኪያው ቅባቸው ድረስ ፣ ሁሉንም ትተው ፣ ገንዘብ ማሰዶድን ብቻ ስራያ ብለው ያዙ ! ” አሉ ። “ ደግሞ . . . በሚያደርጉት በማፈር ፈንታ ፣ እንዲያውም ‘ሰውን ይማረመው’ ብለው ነው መሰለኝ ይቀልዳሉ ” አለ ውብቱ፤ ቀልዳቸው ትዝ ስላለው አስቀድሞ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ ። “ከወን ጀለኞች በቀር ንጹህ ሰዎች አጠገባቸው እንዲደርሱ አይፈልጉም እዬ ተባለ ይታማሉ” ብሎ አንድ ተቆርቋሪ ነኝ ባይ ቢነግራቸው ፣ “እን ዲህ እያሉ ለሚያሙኝ ፈሪሳውያን ፣ እኔ የክርስቶስ ደቀመዝሙር ነኝ፤ አባቶቻችሁ ፈሪሳውያን ክርስቶስን ከሀጢያተኞች ጋር ይበላል ፣ ይጠ ጣል ብለው በወቀሱት ጊዜ ‘ሀጢአተኞችን ፣ ሀጥአንን እንጂ ፣ ጻድቃ ንን ፍለጋ አልመጣሁም ያላቸውን አስታውሱ ብሎዋችሁዋል ብለህ ንገርልኝ ’አሉት ይባላል ።”

“በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፣ አበሰኩ ገበርኩ ! እኔ እዚህ ታች ብቻ መስሎኝ ለካ. . .እንዲህ እንዲህ ያለው እዚያ ላይም አለ?” አሉ ባላምባራስ ፣ መስቀልኛ አማትበው ፣ አዲስ አበባና ጎሬ የሚ ሰራውን ጉድ ውብቱ ተርኮ እስኪጨርስ ፣ አንገታቸውን ደፍተው ትንሽ ሲያስቡ ቆዩና ።

“ምኑ?” አለ ውብቱ ።

“ይህ . . ጉቦውና መልከስከሱ ሁሉ ! ”

“ከላይ ካልመነጨ ከየት መጥቶ እታች ደረሰ መሰለዎ?”

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፳፱

## የወደዱትን ሲያጡ የጠሉትን ይለማመጡ

ግራዝማች ዳኘ ጎሬ ከሄዱ ጀምሮ ፡ መኣት ሲያወሩባቸው ፡ ሲሰድባቸው ፡ ሲረግሟቸው ፡ የነበረው የየኪ ሕዝብ ሁሉ ፡ የቀኛዝ ማችነት ማእረግ ተጨምሮላቸው ፡ ወደዚያው ወደ ጥንቱ ግዛታቸው፡ ወደ የኪ ለመመለስ ፡ በመንገድ ላይ መሆናቸውን ሲሰማ ፡ በዩቢቱ ያለ ግንዘቡን ሙጥጥጦ ፡ በዚያ ላይ ከብቱንና መሬቱን ሸጦ የሚያቀር በው ገጸበረከት ፡ የሚያቀርበው የጰስደስ ፡ ያወሩባቸውን መኣት ፡ የሰደባቸውን ስድብ ፡ የረገማቸውን ርግማን ፡ ሊሸፍን የማይችል እዩ መሰለው ሲጨነቅ ፡ እኒያ ክፉ ሰው በመመለሳቸው ፡ በዩልቡ የተሰ ማውን መሪር ሀዘን ፡ በውሸት ደስታ ለመሸፈን የሚያደርገው ጥረት የሚታወቅበት እዩመሰለው ሲፈራ ፡ በኒያ ክፉ ሰው መመለስ ፡ የያ ንዳንዱ ልብ የሚያለቅሰውን መሪር ለቅሶ ፡ ለመሸፈን ፡ ጥርሱ የሚ ስቀው የውሸት ሳቅ የሚታወቅበት እዩመሰለው ሲቸገር ፡ ዘራፊው፡ ግፋፊው ፡ ግራዝማች ዳኘ እንዲሰቀሉ ፡ ያ ! ባይሆን እንዲታሰሩ ፡ ቢያንስ ቢያንስ ግን እንዲሻሩ ፈጣሪውን ሲለምን ፡ ሲማጠን ፡ የነበ ረው የየኪ ህዝብ በሙሉ ፡ ሁሉም ቀርቶ ፡ በዚያ ሁሉ ፈንታ ፡ በማ እረግ ላይ ማእርግ ተጨምሮላቸው ፡ አቅልጠው ፡ ቀጥቅጠው እንዲ ገዙት ፡ ልጠው ፡ ግጠው እንዲበሉት ተፈቅዶላቸው መመለሳቸውን ሲሰማ ፡ በሰማይና በምድር መንግስቶች ላይ ተስፋ ያልቆረጠና ጥልቅ ሀዘን ያልተሰማው ለመምሰል ከመጠን ያለፈ ሽብ-ረብ ሲል ፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ፡ በጎን ሆኖ የሚመለከት ታዛቢ ፡ ግራ ባይገባው ምናል ባት ይገርመው ይሆናል ! ነገር ግን ፡ የሚወዱትን አጥተው ከሚጠ ሉት ጋር እንዲኖሩ የሚገደዱ ሁሉ ፡ እንዲህ የውነተኛ ስሜታቸ ውን ለማፈንና ለመሸፈን ፡ የውሸት ስሜት ፈጥረው ተመልካቾቻ ቸውን ለማሳመን ሲታገሉ የሚኖሩ መሆናቸው ፡ መቸም የታወቀ ነው !

"ይገርማል ! ለካ የተጠላ ሰውም . . . ተለይቶ ፡ ገለል ብሎ ከቆዩ ይወደዳል ፤ እንዲያውም ይናፈቃል ማለት ነው !" አለ ጥላ ሁን ፡ ውብቱ ወደ ጅማ ከሚነሳበት ቀን በፊት በነበረው ማታ

@OLDBOOKSPDF

አሳዬ ክንባለቤቱና ባሳምባራስ ጉዴታ ፣ እሉ ቤት የመሰንባበቻ ራት በሊተው መጠጥ እዩጠጡ ሲጫወቱ ። “ እኔ ከዚህ ሳምንት በፊት ግራዝማች ዳኘ . . . ይቅርታ ቀኛማች ዳኘ ” ሲል ጥላሁን ቀጥሎ “ አይዞህ ሙት - አሙት አለህ ! ” አለ ውብቱ አቋርጦ ።

“ የምን ሙት - አሙት ”

“ አዲሱን የማእርግ ስም የሰው አፍ እስኪለምደው ፣ ያንድ አሙት ጊዜ መሳሳት ይፈቀዳል ። በዚያ ባንድ አሙት ውስጥ ፣ ባለ ማእርጉ ፣ ‘ ባርጌው ስሜ ጠራችሁኝ ’ ብሎ ሊከስና ሊካስ አይችልም ። ”

“ እሺ እግዜር ይስጥልኝ ” አለና ጥላሁን እንደ መሳቅ ብሎ ፣ “ታዲያ ቅድም እንዳልሁት ፣ ከዚህ ሳምንት በፊት ” አለ የጀመረውን ለመቀጠል ። “ ከዚህ ሳምንት በፊት የ . . ቀኛዝማች ዳኘን ስም በደህና ሲያነሳ ሰምቸው የማውቀ ሰው አልነበረም ። ይህን ሳምንት ግን ፣ በዮሄድሁበት ጀርባ የሚሰማው ፣ የቀኛዝማች ዳኘ ስም ሲወደስና ሲሞገስ ብቻ ነው ። ታዲያ ይህ ሁሉ . . ገለል ብለው ፣ አንድ አሙት ያክል ተለይተው ስለቆዩ አይደለም ? ”

“ አይደምስልህ ልጄ ፣ እንደሱ አይደለም ” አሉ ባሳምባራስ ጉዴታ ።

“ታዲያ ምንድነው ? ”

“ የወደዱትን ሲያጡ ፣ የጠሉትን ይለማመጡ ” እንደሚሉት ተረት የዚህ አገር ሰውም የፈለገውን ፣ የወደደውን ሲያጣ ፣ የሚጠላውን መለማመጡ ነው ! ”

“ ማንን ኖሮዋል የሚወደው ? ”

“ የሚወደውማ . . . የዚህን ክፉ ሰው መሰቀል ! ያለዚያም ተገርፎ ፣ ተዋርዶ መታሰር ነበር ! ያ ፣ ሳይሆንለት ሲቀር ጊዜ ፣ እየውልህ የሚጠላውን ወደ መለማመጡ ተመለሰ ! የዚህ አገር ህዝብ ይህን ያክል ዘመን ይህ ግፈኛ ፣ ይህ አመጸኛ ፣ ይህ ወንጀለኛ ፣ ያደረሰበት መከራና ስቃይ ፣ ዘረፋው ፣ ገፈፋው ፣ ውርደቱ ፣ ግርፋቱ እስራቱ ፣ ስደቱ ፣ ሞቱ ኧረ ስንቱ ! እንዲያው ሰይጣን የፈጠረው ክፉ ነገር ሁሉ እንዲበቃው ፣ ክፉ አድራጊውም ለስራው የግፍና ያመጽ ስራ ፣ ለሰራው ወንጀል ፣ ተገቢ ቅጣቱን እንዲያገኝ ፣ ድምጹን ከፍ አድርጎ ሊመራቱም ፣ ለሰማዩም ንጉሶች አቤት አለ ፣ ለመነ ! ተማጸነ ። የሰማይና የመሬት መንግስቶች ግን የተከለመኑትን ትተው

@OLDBOOKSPDF

. . . ያልተለመኑትን ፤ የግልብጦሽ ፤ ስልጣኑን ጨምረው ፤ ያመጽ መስሪያ ሀይሉን አጠንክረው ፤ ሲሰራው የኖረውን አመጽ ደግሞ እጥፍ ድርብ አድርጎ እንዲሰራ ፤ ሲሰራው የኖረውን ወንጀል ደግሞ እጥፍ ድርብ አድርጎ እንዲሰራ ፤ መልሰው ወዲህ ስለ ሰደዱት ፤ ፈርቶ የጠላውን . . ይለማመጥ ጀመር !" አሉ በንዴት ጠቋሮና ተኮማትሮ የነበረ ፊታቸው ፊት እያለ ሲሄድና ፤ በመጨረሻ በፈገግታ ሲበራ እዩ ትዩ ።

"ለምን ባቱ ?" አለ ውብቱ ፤ ፈገግ ያሉበትን ምክንያት ባያውቅም ፤ ፈገግታቸው ስለ ተጋባበት ፤ እሱም እንደሳቸው ፈገግ ብሎ ።

"እዩ ምንም አደል ፤ ስለ አግዜር የግልብጦሽ ፍርድ ስናገር ፤ አንድ አለባም ወዳጄ ያጫወቱኝ ጭዋታ ትዝ ብሎኝ ነው ።"

"ምንድነው ? እበቱ ይንገሩን ፤ ይንገሩን !" አሉ እዚያ ያሉት ሁሉ እዩ-ተቀባበሉ ።

"የለም ፤ እንደሳቸው አሳሳምረውምና ፤ ከማበላሸው . . ባልናገ ረው ይሻላል !"

"ግዴለም ይንገሩን ፤ እባክዎ ይንገሩን !" አሉ ሁሉም እንደ ገና እዩ-ተቀባበሉ ።

"እሺ ፤ ብቻ ጭዋታው አምሮ ባይታያችሁ ከኔ ጨዋታ ማሳ መር አለማወቅ እንጂ ከራሱ ፤ ከጭዋታው አለማማር እንዳይመስላ ችሁ" አሉና ወዳጃቸው ያጫወቱዋቸውን መናገር ጀመሩ ።

"አንድ ሸኽ ፤ በጾማቸው ወራት ሩቅ መንገድ ለመሄድ የሚገ ደዱበት ጉዳይ ገጠማቸውና ፤ ጥዋት ተነስተው እህል ሳይቀምሱ ሲሄዱ ውለው ፤ አመሻሽ ላይ ወዳንድ ትልቅ ተራራ ደረሱ ። ተራራው ረዢም ከመሆኑም ሌላ ፤ በጣም ቀጥ ያለ ስለነበረ ፤ ባለበቅሎ መንገ ደኛ አግኝተው ካልረዳቸው ፤ በግራቸው ሊወጡት የማይችሉ ስለ መሰ ላቸው ፤ እስሩ ተቀምጠው በቅሎ ፤ ያለዚያም አህያ ያለው መንገደኛ እንዲላክላቸው አላህን ሲለምኑ ፤ አንድ ሰው ደካማ አህያውን ከባድ ጭነት ጭኖ ሲመጣ ከሩቅ አይተው ፤ አላህ ልመናቸውን ስለሰማ መሬት ስመው አመሰገኑ ። ከዚያ ባላህያው በጭነቱ ላይ ደርቦ ተራራ ውን እንዲያወጣቸው አስተዛዝነው የሚለምኑበት ቃል ሲያማርጡ ፤ ያ መንገደኛ በበኩሉ ፤ ደካማ አህያው ያን ከባድ ጭነት እንደ ተጫነ ተራራውን መውጣት ስለማይችል ፤ የሚያደርገው ጠፍቶት ፤ ተቸ

@OLDBOOKSPDF

ግሮ ሳለ ፣ ድንገት ሸኹን እዚያ ተቀምጠው ሲያገኛቸው ፣ አባህ መቸገሩን አይቶ እንደ ላከለት አምኖ መሬት ሳመና ፣ ቶሎ ጭንቱን ካህያው አወርዶ ፣ ‘ኑ ተሸከሙ !’ አላቸው ። ሸኹ ደነገጡና ፣

“ እረ እንኳዋንስ ጭነት ልሸከም ፣ የገዛ አካላቴን መሸከም አቅቶኝ ፣ ተሸክሞ የሚያወጣኝ ባገኝ ለመለመን ነው እዚህ የተቀ መጥሁ ! ” አሉት ።

“ እባክሁ በህይወቴ ክፉ ሰርቼ የማላውቀውን ዛሬ ክፉ እንድ ስራ አታስገድዱኝ ፣ አቦ ! ” አላቸው ዱላውን እያሳዩ ። ሸሁም አገ ማሚያውን ሲያዩ እንደማይምራቸው ስለተረዱ ፣ ቶሎ ጭነቱን አን ስተው ተሸከመው ፣ ካህያው ፊት ቀድመው እዩነዳቸው ተራራውን አውጥተው ሰጡት ። እሱም ያን ጭነት ከሸኹ ወዳህያው አዛውሮ ጫነና ፣ “ አባህ ይህን ጉልበትሁን ይባርክልሁ ፤ በጣም ብርቱ ጉል በት ነው ያለሁ ፤ ስንፍና አታልምዱት ፣ አቦ ! ” ብሎዋቸው ሄደ ።

ሸኹ ያላህ ረቂቅና ፣ ማንም ሊደርስበት የማይችል ጥልቅ ምስ ጢር ከምን ጊዜም የበለጠ ረቂቅና ጥልቅ ሆኖባቸው ተቀምጠው ሲገ ረሙ ፣ እዚያ ባጠገባቸው በነበረ መንደር አንዲት ሴት ምጥ ጸንቶ ባት ስለ ደከመች ፣ የሚጸልዩላት ሸኽ ፍለጋ ዘመድ ሁሉ በያቅጣጫው ሲሮሩዋጥ ፣ አንዱ እኒያን መንገደኛ ሸኽ አገኘና ፣ ከተቀመጡበት ለምኖ አስነስቶ ወደ በሽተኛዋ ይዞዋቸው ሮጠ ። ምጥ የተያዘችዋ ሴት የመንደሩ ሴት ከብበዋት ፣ “ ያዙኝ ልቀቁኝ ” እያለች ፣ ላብዋ በዩማእዘኑ እዩተንቆረቆረ ፣ ስትጨነቅ ማየቱ እንኳዋ እንደሰዋ ያስ ጨንቅ ነበር ! ሸኹ እዚያ እንደ ደረሱ ፣ ቶሎ እጃቸውን ታጥበው ፣ በርጥብ እጃቸው ፊታቸውን ካባበሱ በሁዋላ ፣ ተንበርክከው መሬት እዩሳሙ እንደ ተለመደው መሳልሰው ፣ “ አላሁ አክባር ” አሉና መጀ መሪያ አፋቸው እዩፈራ ፣ ከዚያ በድፍረት ፣ “ አላህ ፣ ይችን ሴት እንደ አክርማ ለሁለት ሰንጥቃት ! ተርትራት ! እንደ ተነፋ ፊኛ አፈንዳት ! ልጁም እዚያው በሆድዋ እንዳለ ይፍረጥና ባፍዋ ፣ ወይም ባፍንጫዋ ውሀ ሁኖ ይውጣ ! ” እያሉ ካንድ ሸክ አፍ ወጥቶ የማያ ውቅ የርግማን መአት አወረዱባት ። የተሰበሰበው ሰው ሁሉ ግራ ገብቶት ፣ “ ምነው አባታችን በጸሎትም እንዲያስምሩልን ለምነን እም ጥተንዎ ይረግሙዋታል ? ” ቢላቸው ፣ “ አይዞዋችሁ አትፍሩ ልጆቹ ዛሬ ዘመን ፣ አላህ የለመኑትን ሳይሆን ፣ ግልብጡኹን ነውና የሚያ ደርገው ፣ አሁን ደህና ትሆናለች ! ” አሉ ይባላል ። “ ታዲያ . . ”

@OLDBOOKSPDF

እሱ ባላምባራስ ፣ ወዳጃቸው የነገሩዋቸውን ጭዋታ ተርከው ሲጨርሱ ከሌሎቹ ጋር ሲስቁ ቆይተው ። “ ታዲያ ፣ በዚህ አገር ሀገብ አሁን የደረሰው ፣ ከዚህ ስለ ሸኹ ከሚነገረው ጭዋታ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ስለታዩኝ ነው ፤ ምንም እንኩዋ ልቤ አጥብቆ ቢያዝን ፣ ‘ ጥርስ ባአድ ነውና ’ የሳቅሁ ። ”

“ ተመለስሁ ! ” አለ ጥላሁን ። “ እርስዎ ያሉት ነው እውነት የሚመስለው አባባ ! እርስዎ እንዳሉት ፈርቶ መለማመጡ ነው ። ምክንያቱም ፣ የቀኛዝማች ዳኘ ስም መወደስና መሞገስ የጀመረው አሁን ፣ ወዲህ መመለሳቸው እርግጥ መሆኑ ከታወቀ በሁዋላ ነው ፤ እስከዚያ ድረስ የሳቸው ስም የሚነሳው በሌላ ነበር ። ” ጥላሁን እንደ እውነተኞች ፣ እንደ ቅኖች ሁሉ ፣ በክርክር ጊዜ ፣ ከሱ አሳብ የሌሎች እንደሚያሸንፍ ካዬ ፣ መሸነፍ ጭራሽ የማይከብደው ሰው ስለ ሆነ ፣ የባላምባራስ አሳብ ከሱው የሚሻል መሆኑን ትንሽ እንኩዋ ሳያመነታ ቶሎ አምኖ ተቀበለ ።

“ ጥሩ ትርጉም ነው ፤ እንዲህ ያለም የለ ! ” አለ ውብቱም ፣ በባላምባራስ ትርጉም ትክክለኛነት ከጥላሁን ጋር መስማማቱን የሚገልጽ ምልክት እያሳዬ ። ከዚያ ጠጁን ፉት ብሎ ብርጭቆውን እፊቱ አስቀመጠና ፣ “ ቶሎ በመሄዴ ከምቆጭባቸው ምክንያቶች አንዱ የ . . . ባላምባራስን ጭዋታ ሳልጠግብ መሄዴ ነው ” አለ ።

“ ቶሎ መሄድህ የጎዳኝስ እኔን ነው ። በቀደም የነገርሽኝ ፣ ይህን . . ረገርም እድሜዬን ለኖር ስምቸው የማላውቅና ፣ ‘ ይሆናል ’ ብዬ የማልገምተው ነውኮ ! ”

“ ምኑ ? ”

“ እዚያ ላይ ያሉት ፣ የግዜር ባለደራዎች ፣ በሰው ሁሉ ሀብትና ንብረት ብቻ ሳይሆን በህይወቱ ሳይቀር ሊያዝዙ ፣ ሊናዝዙ እግዜር የመረጣቸው ሰዎች ፣ እንደኛ እዚህ ታች እንዳለን ምስኪኖች ገንዘብ ለማግኘት ያን ያክል የተንኮል ገመድ ፣ እንዲያውል አሳጥተው ሲተበትቡና ሲቆረጙ ይኖራሉ ብዬ ጭራሽ ባላቤ አግብቸው አላውቅም ነበር ፤ ሌላ ሰው ‘ አዬሁ ፣ ሰማሁ ’ ብሎ ቢነግረኝ እንኩዋ ፣ ማመኑ ያስቸግረኝ ነበር ። ነገር ግን ‘ ገንዘብ መፈለግና እንዲያ እንዲያ ያለው ወራዳ መልከስከስ ሁሉ ፣ እታች ያሉት ሹሞች ብቻ የሚያደርጉት ነው’ ስልህ ፣ ‘ከላይ ያልመነጨ ከየት መጥቶ እታች ደረሰ መሰለህ ?’ ብለህ ለጠየቅሽኝ ፣ አንተ ያልኸውን አምኘ

@OLDBOOKSPDF

ከመቀበል በቀር መልስ አላገኘሁም ! እየውልህ ፤ ባንድ ቃል ብዙ አስተማርከኝ ፤ ትንሽ ብትቆይ ደግሞ ፣ ከዚህ የበለጠ ታስተምረኝ ነበር !" እሉና ባላምባራስ ግማሽ ብርጭቆ ጠጃቸውን ጨልጠው ፣ ባዶውን ብርጭቆ አጠረጴዛው ላይ አስቀምጠው ፣ ሰፊያን ትኩር ብለው ሲመለከቱ ፣ ምን ማለታቸው እንደሆነ ሁሉንም ስለ ገባቸው ባንድ ላይ ሳቁ ! ወዲያው ሰፊያ ብርጭቆዋቸውን ሞላችላቸው ።

"እሱ መቸም ልክ ነው ። እንዲህ እንዲህ ያለው መጥፎ ልማድ ሁሉ ፣ ኢታች ካሉት ሰራተኞችና ባለስልጣኖች ዘንድ ሊጠፋ የሚችለው ፣ ከላይ ምንጩ ሲደርቅ ብቻ መሆኑ አይጠረጠርም ! አለ ውብቱ ።

"የሰራተኛና የታች ባለስልጣን መጥፎ ልማድስ በላይኛው ቃርሞ ይወገዳል ፤ ነገር ግን እንዲያ ያለው መጥፎ ልማድ ከላይ ከመጣ በማን ይታረማል ? "

"እውነት ነው ፤ ያስቸግራል ፤ ጊዜም ይወስድ ይሆናል" አለ ውብቱ ፣ ጠጁን ተጎንጭቶ ብርጭቆውን ሲያስቀምጥ ።

" እስከ መቼ ? "

" እ . . . ህዝቡ ትምር ፣ አውቆ ፣ ባስተዳደሩና ለዳኝነቱ ባለ ቤት መሆን ፣ ገገርው ራሱ መሆን እስኪችል " አለ ውብቱ ፣ ሕዝቡ ተምሮ ፣ አውቆ ፣ ራሱን መግዛት እስኪችል የሚጎዋዝበት ረዢም ጎዳና ከግድግዳው ወዲያ ፣ መጨረሻው አልታዩው እንዳለ ሁሉ፣ አይኖቹን ጭንቁር ፣ ግንባሩን ኩስትር አድርጎ ፣ ፊት ለፊት አዩ ተመለከተ ።

"ኧረ ምን ትችል እግዚአብሄር ! ደግሞ እንዲህ ያለም አለ ?" አሉ ባላምባራስ ፣ የሞላ ብርጭቆዋቸውን አጋምሰው እፊታቸው ካስ ቀመጡ በሁዋላ ፣ ውብቱን በጥያቄ አይን እያዩ ።

" ምን ! እንዴት ያለ ? "

"ህዝቡ ገገር መሆን ! ተገገርው ማን ሲሆን ነው . . ህዝቡ ገገር የሚሆን ?" ሲሉ ባላምባራስ በመገረም መልክ ፣ አንድ ጊዜ ውብ ቱን ፣ ከዚያ ሌሎችን አለዋውጠው ተመልከተው ፣ ሁሉም ተያይዘው ይስቁ ጀመር ።

"እውነቴንኮ ነው !" አሉ ባላምባራስ ቀጠሉና ። " እውነቴን ነው ። መቸም በተገገ ላይ ነው ገገ የሚኖር ፤ ተገገ ገገ ከሆነ ፣ ገገ

@OLDBOOKSPDF

ማንን እንደሚገዛ አልታዩኝ ብሎ ነው ! ደግሞስ . . . ” አሉ ባላምባራስ ፣ ህዝቡ ሁሉ ገገር ሲሆን ፡ አልጋው አልበቃው ብሎ እስበሉ ሲጋፋና ሲተራመስ ስለ ታያቸው ፣ እንደመሳቅ አሉና ። “ ደግሞስ ፣ እንዲያው ሌላ ተገገር ተገኝቶ ‘ህዝቡ ገገር ይሁን’ ቢባል ፣ አልጋው ይበቃዋል ? ”

“ እንደሱ ማለትኮ አይደለም አባባ ” አለች ሶፊያ ስትስቅ ቆይታ ፣ ውብቱ ሊመልስ ሲል ካፉ ነጠቀችና ። “ህዝብ ባስተዳደሩና ለዳኝነቱ ባለቤት ይሆናል ፤ ህዝብ ለራሱ ገገር ይሆናል ” ሲባል ሁሉም ተሰብስቦ ባንድ ላይ በገገርው አልጋ ፣ በገገርው ዙፋን ላይ ይሰፍራል ማለት አይደለም ። ”

“ ታዲያ እንዴት ነው ? ”

“ አስተዳደሩንና ዳኝነቱን ፣ በጠቅላላው ጉዳዩን ሁሉ ፣ እንደ ሚስማማው አድርጎ ፣ በሚፈልገው መንገድ የሚመራለትን ከመሀከሉ መርጦ የመንግስቱን ስልጣን እንዲይዝ ያደርጋል ማለት ነው ፤”

“ አ . . አሁን አስተዋልሁት ፤ ታዲያ እግዜር ከመረጠው ፣ ሰው የመረጠው ይሻላል ማለት ነው ? ”

“ እግዜር የመረጠውን ነውኮ ሰው የሚመርጠው አባባ ! ”

“ እሱ እውነትሽ ነው ። ብቻ . . ከህዝብ መሀከል የሚመረጥም ፣ የመንግስት ስልጣን ይዞ አልጋው ላይ ሲወጣ ፣ ህዝብ መሆኑ ይቀራልኮ ! በትረ መንግስቱን ጨብጦ ፣ በመንግስቱ አልጋ ላይ ፣ በዙፋኑ ላይ ቁጭ ሲል . . . ያን ጊዜ ፣ እንደ ንጉስ እንጂ እንደ ህዝብ ማሰቡ ይቀራል ! ” ሲሉ ባላምባራስ ፣ ከህዝቡ የሚመረጠው ሰው በትረ መንግስቱን እንዴት ጨብጦና ፣ በመንግስቱ አልጋ እንዴት ቁጭ ብሎ ፣ እንዴት እንደ ንጉስ እንደሚያስብ በምልክት እያሳዩ ፣ እዚያ የተቀመጡት ሁሉ ፣ አንዳንዶቹም እንባ እስኪወርዳቸው ሳቁ ።

“ ለህዝብ አገልግሎት መመረጡን ረስቶ ፣ የራሱን ድሎት ማስቀደም የሚፈልግ ከሆነማ . . የተመረጠበት ጊዜ ሲያልቅ እንደገና የሚመርጠው አያገኝም ፤ በሱ ፈንታ ሌላ ይመረጣል ” አለ ውብቱ።

“ እ . . ! መቼም የመንግስትን ስልጣን ፣ ከንጉስ የተወለዱት ብቻ እዩያዙ ዶስ ሲሰኙበት እንዳይኖሩ ፣ አንዳንድ ከድሀ የተወለዱም የመመረጥ እድል ሲያጋጥማቸው ፣ በዬተራ ይቅመሱ ” ለማለት ከሆነ መልካም ነው ። ያለዚያ ፣ “ እነዚህ . . ህዝብ ከመሀሉ የሚመርጣቸው ሰዎች ፣ በንጉስ አልጋ ቢቀመጡም ፣ ህዝብ ለተወሰነ ጊዜ

@OLDBOOKSPDF

ስለ መረጣቸው እንደ [illegible] ትተው እንደ ህዝብ ያስባሉ ፤ ወይም እነዚህ ህዝብ በዬጊዜው የሚመርጣቸው ሰዎች የመንግስትን ስልጣን ይዘው ስለገዙ ብቻ ፤ ጠቅላላው ህዝብ ገገር ሆነ ማለት ነው” የምትሉኝ ፤ ጭራሽ አይታዬኝም ! “ ህዝብስ ” አሉና ባላምባራስ ጭዋታ አስረስቶዋቸው የቆዬ ብርጭቆዋቸውን አንስተው ጨልጠው ካስቀመጡ በሁዋላ ፤ “ ይህ የኔ ቢጤው ድሀ ህዝብስ ፤ ምን ጊዜም ከመገዛት ወጥቶ ፤ ገገር ሆኖ አያውቅምና ፤ ያልሆነውን ‘ ነህ ’ እያሉ እንደ ህጻን ማባበሉም ፤ ማታለሉም ፤ ቀርቶበት እግዜርን የሚፈራና ፍትህ የማያጎድል ገገር ቢያገኝ እድለኛ በሆነ ! ” ብለው ባዶ ብር ጭቆዋቸውን አንስተው ወደ ሶፊያ ሲዘረጉ ፤ እስዋም እንዲሁ ጭዋታ አስረስቶዋት ሳትሞላላቸው ስለ ቆዬች እንደ መደንገጥ ብላ ፤ ቶሎ ሞላችላቸው ።

“ እየውልህ ጥላዬ ፤ ይህን እንደኔና እንዳንተ በጥራዝ ነጠቅነት ያልባከነና ያልተበተነ ፤ ከተፈጥሮ የታደለውን የውቀት ችሎታ ፤ ካካባቢው ሁኔታ ጋር አዛምዶ መፍረድ የሚችል አእምሮ ትመለከትልኛለህ ? ” አለ ውብቱ በንግሊዝኛ ፤ የባላምባራስን አስተሳሰብ እያደነቀ።

“ የባላምባራስን ማለትህ ነው ? ” አለ ጥላሁንም ፤ እንዲሁ በንግሊዝኛ ።

“እዎ”

“ እንኩዋን አንተ አወቅህልኝ እንጂ ፤ ከኔ ጋርማ አብረንኮ ነው የምንኖር ! ”

“ ታዲያ እንዲህ እንዲህ ካሉት ሰዎች ለመማር ፈቃደኛ መሆን ነው እንጂ ፤ እንዲያው አብሮ መኖር ብቻኮ አይበቃም ! መጀመሪያ ወዲህ ስትመጣ . . እንደ ሁላችን ፤ እዚህ ፤ እባላገር ፤ የሚያስተምሩት እንጂ ፤ የሚያስተምር ይኖራል ብለህ ጭራሽ ባሳብህ ውስጥ ስላልነበረ ፤ ከመጣህ በሁዋላም . . . መሰንበቻየን እዬዞርሁ እንደ ተመለከትሁት እጅግ ብዙ አስተምረሀል ፤ አንተ ግን ፤ ይቅርታ አድርግልኝና ፤ ምንም አልተማርህ ፤ እዚህ ስትመጣ የነበርኸው ጥላየ ብቻ እንኩዋ አይደለህም ፤ እንዲያውም ከዚያ በፊት ፤ ድሮ ድሮ ትምህርት ቤት ሳውቅህ የነበርኸው ጥላየ ነህ ! ” ሲል ውብቱ ፤ አሁንም በንግሊዝኛ ፤ ከባላምባራስ በቀር ሁሉም በሳቅ አወኩ ።

“ አሁንስ እንጃ ፤ ሆዴ ፈራ ! እዚህ ያለጎሳየ ተገኝቼ ፤ በማላውቀው ቋዋንቋዋ የምትነጋገሩብኝ ከቶ ልትሸጡኝ ይሆን ? ” ሲሉ ባላምባራስ ፈገግ ብለው ፤ ሁሉም እንደገና ሳቁ ።

@OLDBOOKSPDF

" አሁን እንዳሉት ያለ ነገር የሚኖር ከሆነ ፣ ባይሆን እኛ ነገ እንጂ እዚህ ያለኅላችን ስለ ተገኘን ልንሰጋ የሚገባን ፣ እርስዎማ አገርዎ ፣ ከንሳዎ መሀከል ሆነው ሲሰጉ ይገባዎታል ? " አለ ውብቱ ።

" እና . . . ባይሆን እኒህ ልጆቼ ይበሉ እንጂ " አሉ ባላምባራስ ውብ ፊታቸው በፈገግታ እንዳጌጠ ፣ ወደ ሶፊያና ወደ ጥላሁን እያመለከቱ ። " ባይሆን እኒህ ልጆቼ ይበሉ እንጂ ፣ እናንተማ ባለስልጣኖች ናቸሁ ። ስልጣን የተለዬ ኃላ የለውም ፤ የሚገኝበት ኃላ ሁሉ ኃላው ነው ! "

" ባላምባራስን በጣም ነው የወደድሁዋቸው ፤ አስተዋይ ሰው ናቸው " አለ ውብቱ ፣ ባላምባራስ ጉደታንና አሳዬን ከነባለቤቱ እደጅ ድረስ ሸኝተው ተመልሰው ሲቀመጡ ።

" አዎ ፤ የሚወደዱ ሰው ናቸው " አለ ጥላሁን ። " ብዙ የሚወደድ ባህሪ ያላቸው ሰው ናቸው ። ለምሳሌ . . ግፍ አጥብቀው ይጠላሉ ፤ የተበደለ ነው ኪሉዋቸው ለማንም ፣ ለማያውቁት እንኳ ሳይጠዬቁ ዋስ ፣ ' ወይም ጠበቃ ፣ ልሁን ' ብለው ይቀርባሉ ፤ ከታላቅ ባላባት ተወልደው ግህበርተኛነታቸው ከታችኞች ፣ ከተራ ሰዎች ጋር ስለሆነ ፣ አማሮች ፣ ጋሎች ፣ ኧረ እንዲያው ከሻንቅሎች በቀር በጠቅላላው የዚህ አገር ህዝብ ፣ ' ቆዬ ግሜ ' ይላቸዋል እንጂ በስማቸው አይጠራቸውም ! ምክናያቱ ጉዋደኝነታቸው ከግማቸው ጋር ስለሆነና ፣ ባህላቸውንም ፣ ቋዋንቋዋቸውንም ልክ የነሱ አዋቂዎች የሚያውቁትን ያክል ስለሚያውቁ ነው ። ደግሞ . . ወዳጅነት አጥባቂ ማንም የለም ! ሲወዱ ከልባቸው ነው ! እኛ ወዲያው እንደ መጣን ባንዳንድ ምክናያት ተዋውቀን ወዳጆች ሆን ። እየውልህ ከዚያ ጊዜ ጀምረው ፣ ተለይተውን አያውቁም ፤ እንዲያውም ለኛ ጉዳይ ፣ ከኛ የበለጠ የሚያስቡ እሳቸው ናቸው ! "

" ሲጠሉም ያን ያክል ነው ፤ ጥላቸውን እግዜር አያድርስ ብቻ!" አለች ሶፊያ ፣ ጭዋታውን ክባልዋ አፍ ቀበል አድርጋ ። "እሳቸው የጠሉት ሰው ምን ደግ ቢሰራ ፣ ምን በፊታቸው የጻድቅ ስራ ቢሰራ ቢያዩት ፣ ደግ ስራው ወደ ክፉ ተለውጦ ነው የሚታያቸው ! "

"ልክ ነው ! " አለ ጥላሁን ፣ እሱም በፈንታው ጭዋታውን ከምሽቱ አፍ ነጥቆ ። " ልክ ነው ፤ አሁን ቀኛዝማች ዱኘ እፊታቸው ለበጎ ነገር አንገታቸውን ሲሰዬፉ ቢያዩ ፣ ያን ያዩትን ከማመን ይልቅ፣ የራሳቸውን ጤንነት መጠርጠር ይቀናቸዋል ፤ ' እኔ ጤና ባልሆን ነው

@OLDBOOKSPDF

እንጂ ደግ ስራ ሲሰራ ያዩሁ የመሰለኝ ፤ እሱ ምንም ቢሆን ደግ አይሰራም ፤' ይላሉ ። ‘ ቀኛዝማች ዳኘ ለክፉ ስራ ተመድበው የተፈጠሩ ስለሆኑ ፤ ምንም በጎ ሊሰሩ አይችሉም ’ ብለው የሚያምኑ ናቸው ። ቀኛዝማች ዳኘ ከሰሩዋቸው ስራዎች መሀከል ሴኛ በጎ ስራዎች ሆነው የታዩንን ስንጠቅስላቸው ፤ ለያንዳንዱ መጥፎ ትርጉም እያጡለትም ። ሀ ! አንድ ቀን ” አለ ጥላሁን ፤ አንድ ቀን ባላምባራስ ያሉት ትዝ አለውና ። “ አንድ ቀን ስለኛ ስራ ስንነጋገር ‘ ያ ክፉ ሰው አለመኖሩ በጃቸሁ እንጂ ፤ እሱ ቢኖር ፤ እስከ ዛሬ የሰራችሁትን ካስር አንድ ሳትሰሩ ፤ ምናልባት የሚፈራውን ፈርቶ ባያሰራችሁ ፤ ከዚህ ያባርራችሁ ነበር ፤ ’ አሉን ።”

“ በዚህ እኔም ከሳቸው ጋር እስማማለሁ ። እንኳንስ ዐከፉነት ስማቸውን ያስጠሩት ፤ ቀኛዝማች ዳኘ ፤ በእናንተው ቦታ የተቀመጠ ሌላ ሰውም ቢሆን ፤ ይህን . . . የሰራችሁትን ሁሉ ስትሰሩ ዝም ብሎ አይመለከታችሁም ነበር ! ”

“ እንዴት ፣ ለምን ፣

“ እንዴት ! ለምን ! የጥቅሙን ፤ የደህንነቱን መሰረት ነካችሁ ቢታ ! ”

“ እንዴት አድርገን አባክህ ፣ ” አለ ጥላሁን ፤ በመገረም ጉዋደኛውን እየተመለከተ ።

“ አ . . . ! እሱ ዛሬ ተጉዞን ወደማንወርሰው ፤ ረዥም መንገድ ይወስደናል ፤ ብንተወው ይሻላል ፤ ብቻ እንዲያው ባጭሩ ፤ ባላምባራስ ጌዶታ እንዳሉት ፤ ቀኛዝማች ዳኘ እዚህ ቢኖሩ ኖሮ ፤ ይህን ሁሉ እስደናቂ ስራ ልትሰሩ እንደማትችሉ እኔም እርግጠኛ ነኝ ፤ ከዚህ እሳቸው ካሉት ሌላ እኔ ልጨምር የምፈልገው ፤ እናንተ ሁለት ልጆች ከገንዘቡ ግንዛብ ፤ ከውቀቱ ለዚህ ስራ የተለየ እውቀት ፤ ከስልጣኑ ስልጣን ሳይኖራችሁ ፤ አገልግሎት ለመስጠት ካላችሁ በጎ ፈቃድና ቆራጥነት በቀር ፤ ሌላ ምንም ሳትይዙ ፤ ባዶ እጃችሁን መጥታችሁ ቆራጥነት ላላቸው ባለስልጣኖች ፤ የገንዘብና የቴክኒክ እውቀት ተሟጧልቶ አለመገኘት መሰናከል ሲሆን እንደማይችል ምሳሌ የሚሆን መሆኑንና ከምሳሌነት አልፎ ግን ፤ ‘ ንዋሪነት ፣ ዘላቂነት ይኖረዋል ብላችሁ ’ ተስፋ እንዳታደርጉ ነው ! እንዲህ በምትወዱት ስራ ላይ ፡እንዲህ ያለ ክፉ ትንቢት በመናገሬ አዝናለሁ ፤ እውነት እንዳይሆንም ፡መኛለሁ ። ብቻ መሲያየታችን ስለሆነ ፤ እውነተኛ ስሜቴን መግ

@OLDBOOKSPDF

ለጽ አሰፈላጊ መስሎ ከሰ ፆጥና ነው ። እንዲህ ያለው ማስጠንቀቂያ ፣ እውነት ቢሆን ፣ ትንቢቱ ቢደርስ ፣ በድንገት እጅ እንዳይያዝ ያስጠነቅቃል ። ሳይደርስ ቢቀር ፣ አደጋው ካለፈ በሁዋላ ያስቃል ፤ ያጫውታል ! ”

“ እኔኮ በትንቢትም ፣ በጥንቆላም አላምንም ! ” አለ ጥላሁን ፣ እንደ መሳቅ ብሎ ።

“ አትመነው ብቻ አባክህ ካላብህ ፊጽመህ አታጥፋ ! ”

በማግስቱ ባላምባራስ ጉዶታ ፣ አባዬና ጥላሁን ፣ ውብቱን እስከ ቴፒ ሸኝተውት ሲመለሱ ፣ “ እንግዲህ እኔም . . . ነገ ወደ ጊሚ እሄዳለሁ ” አሉ ባላምባራስ ።

“ አሁን ሄደው ምን ያደርጋሉ ? ” አለ ጥላሁን ።

“ እዚያ አንዳንድ የማደርገው ነገር ስላለኝ እሱን አደራርጌ ካንድ . . . እስር ፣ ቢበዛ ካስራ አምስት ቀን በሁዋላ እመለሳለሁ ” አሉና አንገታቸውን ደፍተው ትንሽ ሲያሰቡ ቆይተው ፣ “ እያንተኛው ምክንያት ግን ሌላ ነው ። አይነተኛው ምክንያት ያ ክፉ ሰው ፣ ያ ባኛቸው ፍሪላ በድል አድራጊነት ሲገባ ፣ ደስታውንና ፈንጠዝያውን እንዳላይ ነው ! ” አሉ ፣ ቀና ሲሉ ለቀኛዝማች ደኖ ያላቸው ጥልቅ ጥላቻ በፊታቸው ጎልቶ እየታዬ ።

“ ደስ መሰኘትና መፈንጠዝ ከፈለጉ ፣ አሽከሮቻቸው ደስ ቢሰኙና ቢፈነጥዙ እርስዎ ምን ቸገረዎና አገር ለቅቀው ይሄዳሉ ? ”

“ እዚያ ሰብቻው ፣ ወይም ካሽከሮቹ ጋርማ ደስ ቢለውና ቢፈነጥዝ ምን ቸገረኝ ነበራ ? ‘ የፈለጋችሁት ባይሆንላችሁ በለቀረ ፣ ድል ባላደረግሁዋችሁ ፣ ኑ ከኔ ጋር ደስ ይበላችሁ ፤ ከኔ ጋር ፈንጥዙ ! ’ ብሎ ያለውዳችን ፣ በግድ ደስ እንዲለን ያገዘናል እንጂ ! ሀ ! ” አሉ ባላምባራስ ፣ አይኖቻቸውን ባያራግቡ ፊት ለፊት ተክለው ራሳቸውን በቀስታ እየወዘወዙ ።

“ እኛ መቸም እግዚአብሄር መሀሪ ስለሆነ ፣ በሰራው ግፍና ወንጀል መጠን ባይቀጣው እንኳ ፣ ባይሆን እስከ ዛሬ የሰራብን ግፍ እንዲበቃው አድርጎ ፣ እሱን ከራሳችን ላይ እንዲያነሳልን እንባችንን እያፈሰስን ለማያዊ አምላካችንን ለመነ ፤ ተማጸነ ! እሱም በበኩሉ ፣ የግፍ ስራውን በኛ ላይ እንዲቀጥል ፣ ከኛ የዘረፈውን ገንዘብ እያፈሰሰ ምድራዊ አምላኩን ፣ እንደራሴውን ለመነ ! ታዲያ እዩትላችሁ ! ” አሉ አይናቸውን ፊት ለፊት ከተከሉበት ወደ ጥላሁንና ወደ አባዬ መል

@OLDBOOKSPDF

ሰው ። “ እዩትላችው ! የኛ [illegible] ፊቱን ከኛ ሲያዞር ፥ የሱ አምላክ ጉቦውንም ፥ ልመናውንም ፥ ተቀብሎ ፥ በኛ ላይ ድል እንዲያገኝ አደረገው ! በገዛ ሀብቱና በገዛ ጉልበቱ ታግሎ ድል ቢያደርግ ኖሮ ፥ መቸም ከጠላቱ ጋር ትክክል የመታገል እድል ኖሮት ፥ ታግሎ የተሸነፈ ፥ የጠላቱን አሸናፊነትና ፥ የሱን ተሸናፊነት አምኖ ተቀብሎ የታዘዘውን ቢፈጽም ፥ ታገዞ ሸብ - ረብ ቢል ፥ ታገዞ ቢያጨበጭብ ፥ ታገዞ ቢዘፍን ግዴለም ፥ በተሸናፊዎች ሁሉ የሚደርስ ፥ በደካማነታቸው ምክናያት የሚከፍሉት ዋጋ ነው ! ነገር ግን ፥ የኛን ሀብት ሰርቆ ሰጥቶ ፥ እኛ በሌለንበት አደባባይ ፥ ድምጻችን እንኳ ሳይሰማ ፥ ስለ ተከሳሽም ፥ ስለ ከሳሽም የሱ ድምጽ ብቻ ተሰምቶ ፥ ስለሱም ስለኛም እሱ ተሙዋጋች ፥ እሱ ምስክር ሆኖ ፥ ያገኘውን ወራዳ ድል ፥ ልቤ አይቀበለውም ! እታወመዋለሁ ! ወጣት ብሆን ኖሮ ፥ ይህን ተቃውሞየን ሸፍቼ ፥ ያን . . . ወንጀለኛ በመግደል እገልጽ ነበር ! ነገር ግን እድሜየ ከሰባ አመት በላይ የሆነ ሽማግሌ በመሆኔ ፥ መሸፈት ስለማልችል ፥ ባይሆን እንኳ ታዝዘው ከሚያጨበጭቡትና ከሚዘፍኑት ጋር እንዳልገኝ ፥ ራቅ ብዬ እቆያለሁ ። ሲከፋ በማዘን ፈንታ ፥ ታገዞ መደሰትና መዝፈን የውርደት ውርደት ስለሆነ ፥ እንዲያ ካለው ውርደት ፥ እንደ ጎበዝ ሸፍቶ የሚያዋርደውን ፥ የሚንቅ የሚደቀድቀውን መግደል ካልተቻለ ፥ እንደ ደካማ ሽማግሌ መሸሽና መሸሸግ ነው !

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፳፱

# የቀኛዝማች ዳኘ ቶሚስ ምረቃ

የኪ ከተፈጠረች ጀምሮ ፣ ቀኛዝማች ዳኘ ካንድ አመት በላይ ጎሬ ቆይተው ፣ የቀኛዝማችነት ማእረግ ተሰጥቶአቸዋል ። እንደ ቶመለሱበት ጊዜ አምሮባት አታውቅም ! እንደዚያ ጊዜ አብባ ተውባ ፣ እንደዚያ ጊዜ አጊጣ ተንቆጥቁጣ ፣ እንደዚያ ጊዜ ትጥ መጠኑን ያጣ ፈንጠዝያ ፈንጥዛ አታውቅም !

ቀኛዝማች የሚገቡበትን ቀን ፣ መላኩተኞች አንድ ሳምንት ቀድመው የኪ ደርሰው አስታውቀው ስለነበረ ፣ ህዝቡ ታዝዞ ፣ መንገዱን ሁሉ ሲጠርግና ሲደለድል ፣ ከተማውን ሲያጸዳና ሌላ ሌላውንም ፣ ለቀ ባበሉ የታቀደውን መሰናዶ ፣ ቀኑ አልበቃ ብሎት ከሌሊቱ እዬጨመረ ሲያሰናዳ ሰነበተ ።

የኢሉባቦር ጠቅላይ እንደራሴ ፣ ካዲስ አበባ ጎሬ ሲገቡ የተደረገላቸውን ያቀባበል ስነ ስራትና ፣ የጎሬ ከተማ ያጌጠችውን ጌጥ ፣ ከቀኛዝማች ጋር አብረው የነበሩና የተመለከቱ አሽከሮቻቸው ፣ እዚያ ባዩት አይነት እንዲሰናዳ እንዲያደርጉ ጌታቸው አገዘዋቸው ስለ ነበረ ፣ ስነ ስራቱ ከሞላ ጎደል ፣ ያን የተከተለ ነበር ።

እከተማው ለመድረስ አንድ ኪሎ ሜትር ያክል ሲቀረው ጀምሮ ፣ ከዚያ ከተማውን አቋርጦ እስከ ቀኛዝማች ግቢ ፣ ከዚያ እስከ ወረዳው ግዛት ጽህፈት ቤት ፣ ከዚያ እስከ ወረዳው ፍርድ ቤት ፣ ከዚያ እስከ ወረዳው የበሻሮንድ ጽህፈት ቤት ፣ ከዚያ እስከ ወረዳው ፖሊስ መስሪያ ቤት ፣ ከዚያ እስከ ገበያው ፣ ከዚያ እስከ ቤተ ክርስቲያኑ ፣ ከዚያ እስከ ባህረ ጥምቀቱ ፣ ከዚያ ባንዳንድ ህዝብ በብዛት የሚያዘወትራቸው ቦታዎች በመቶ ፣ በመቶ ሜትር ርቀት ቅስት ተሰርቶ ፣ ያ ሁሉ ቅስት ፣ የየኪ ነጋዴዎች በፈቃዳቸው እንዲያዋጡ ታገዘው ባበረከቱት አቡጀዲድ ተለብጦ ፣ በያንዳንዱ ቅስት ፊት ፣ እመሀከሉ ላይ ፣ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ በሁለት በሁለት ሰንደቆች እዬተመሳቀለ ሲውለበለብ ፣ እሱም ደስ ብሎት ፣ ሸብ-ረብ እንደሚለው ህዝብ ፣ አብሮ ሸብ-

@OLDBOOKSPDF

ረብ የሚል ይመስል ነበር ! ከዚያ በሶስት ማእዘን የተቆረጠ ፡ ባለ ልዩ ልዩ ቀለም ወረቀት እዩተሰባጠረ በሲባን ተሰኩቶ ፡ በቅስቶቹ መሀከል በሰላሳ ፡ በሰላሳ ሜትር ርቀት መንገዱን እያቋረጠ ተሰቅሎ ሲውለበለብ ፡ እስበሱ እዩተግታ የሚያሰማው ድምጽ ፡ እሱም እንዲሁ ከህዝብ ጋር ደስታውን ለመግለጽ ፡ የህዝቡን ዘፈን ለማድመቅ ፡ የሚያጨበጭብ ይመስል ነበር ። እቀኛዝማች ግቢ ውስጥ ፡ የማእረግ ለማቹውን ለማስመረቅ ግብር የሚያገቡበት ፡ አንድ ሺህ ካሬ ሜትር ያክል ስፋት ያለው አዳራሽ ተሰርቶ የግድግዳው ምርግ ሲቀረው ተማግር ፡ ባጡ ተከድኖ ፡ ወለሉ ተደልድሎ ፡ በዚያ ላይ ለምለም ቄጠማ ተጎዝጉዞዋል ። ባዳራሹ ቁም ፡ ካንድ ወገን ግድግዳውን ተጠግቶ በተትከለ ፡ ከፈቱ ግልጥ በሆነ ኈጠኛ አጎበር ውስጥ ፡ ከፍ ያለ ድልዳል ተሰርቶ ፡ ከስር ወፍራም ስጋጃ ፡ ከላይ ቀዩ የደመቀ አበባ ምንጣፍ ተነጥፎ ፡ ቀኝና ግራ እንዲሁ መሸፈኛቸው በደማቃ ቀይ የተጠለፈ መከዳዎች ፡ ተደርገውበት ፡ ሁሉም ባንድ ላይ የሚነድ መስሎ ይታያል ! ቀኛዝማች የሚቀመጡበት ነው !

ከድልድሉ ስር ጀምሮ ፡ ካጎበሩ ፊትለፊት ፡ ያዳራሹ ሩብ ያክል ተከፍሎ ፡ የወረዳው ልዩ ልዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሹማምንት ፡ ከዚያ ቃልቾች ፡ ከዚያ ቆሮዎች ፡ ባለባቶችና ሌሎች ያገሩ ታላላቅ ሰዎች እንደዩማእረጋቸው ከተራው ህዝብ ተለይተው የሚቀመጡበት በቄጠማው ላይ ስጋጃ ምንጣፍ ተደርቦ ተነጥፎበታል ። ከማራው ትንሽ ዝቅ ብሎው ፡ ከግድግዳው አራት ማእዘኖች እዩተነሱ አዳራሹ መሀከል ላይ የሚተሳሰፉት ፡ እየተሰባጠሩ በሲባን የተሰኩ ባለልዩ ልዩ ቀለም ሶስት ማእዘን ወረቀቶች ፡ በጠቅላላው ላዳራሹ ድምቀትና ሙቀት ሰጥተውታል ።

መቸም የመብሉንና የመጠጡን መሰናዶ ነገር አለማንሳት ነው ! ብዛቱ " ቁጥር ስፍር የሌለው " የሚሉት አይነት ነው ! ቃልቻ ፡ ቆሮ ፡ ባላባት የተባለው ሁሉ ፡ ከንጀራው ፡ ከወጡ ፡ ከጠጁ ፡ ካረቄውና ከጠላው ሌላ ፡ ሰንጋ ያላገባ አይገኝም ! ከዚያ ዝቅ ያለው ፡ እንዲሁ ከበሰለው እህልና ከመጠጡ ሌላ ፡ ሙክት ያላገባ አይገኝም ! ከዚያ በታች እንደ ህዝቡ የኑሮ ደረጃ ፡ ከላይ ወደ ታች እዩወረደ ሲሄድ ፡ ከመቶ እንጀራ ፡ አንድ እንስራ ጠጅና አንድ ምንቸት ስጋ ወጥ ጀምሮ ፡ ከሰማንያ እንጀራ ፡ አንድ እንስራ ጠጅና አንድ ምንቸት ስጋ ወጥ አልፎ ፡ ከዚያ በስድሳ እንጀራ ፡ አንድ ገንቦ ጠጅና አንድ ድስት ስጋ ወጥ አልፎ ፡ ከዚያ ባርባ እንጀራ ፡ አንድ እንስራ ጠላና አንድ

@OLDBOOKSPDF

ምንቸት አሀል ወጥ አልፎ ፤ ከዚያ በሆያ እንጀራና አንድ ገንቦ ጠላና አንድ ድስት አሀል ወጥ አልፎ ፤ ከዚያ ባሰር እንጀራና አንድ ድስት አሀል ወጥ አልፎ ፤ ከዚያ ጎጆ ሰርቶ ጨሰ ያጨሰ ሁሉ ፤ እስከ አምስት እንጀራ አዋጥቶ እንዲሰጥ በሹም ስለ ታዘዘ ፤ የሌለውም ተበድሮ ፤ ተቀድሞ ፤ መዋጮውን ሲያገባ የከፋው ባለመምሰል ፤ ደስ ያለው ለምምሰል ሲጣጣር ይታይ ነበር ፤

ሌላው ያቀባበለ መሰናዶ ፤ የኢሉባቦር እንደራሴ እንክዋ ጎሬ ሲገቡ ያልተደረገ ፤ ያጀቡ ሰው ስራት ነው ። ከየኪ ወረዳ ህዝብ ባለ ጠበንጃ የሆነ ሁሉ ፤ ቀኛዝማች የኪ ከተማ ከመግባታቸው በፊት በሚያድሩበት ድረስ ሄዶ ተቀብሎ ፤ ከዚያ አጅቦ ከተማ እንዲያገባቸው ታዝዞ ስለነበረ ፤ ከትውልድ አገራቸው ፤ ከሌጋ ተነስተው የርፋድ የርፋድ መንገድ እየሄዱ ፤ በየሰፈሩበት ፤ እንደ ጥንቱ - ልማዱ ፤ አልፎ ለሚሄድ መኳንንት የሚገባውን መስተንግዶ እየተቀበሉ ፤ አራት ቀን ተጉዘው የግዛት አገራቸውን ፤ የየኪን ወሰን ሲገቡ ፤ እዚያ ጥዋት ቀድሞ የሄደው ድንኩዋን ተተክሎ ፤ ሊቀበላቸው ታዝዞ የሄደው ሰራዊት ተሰልፎ ፤ ሁሉም በተጠንቀቅ ሲጠባበቅ ቆያቸውና ሲደርሱ ሰፈር ሆነ ። መቸስ የሰራዊቱ ብዛት ፤ "ካንድ የጥንት ባለንጋሪት ደጃዝማች ሰራዊት ይበልጥ እንደሆን እንጂ አያንስም" ቢባል ማጋነን አይሆንም ፤

ቀኛዝማች በሰፈሩበት ዙሪያ ፤ እስከ ርፋድ መንገድ የሚኖረው ህዝብ ፤ ያቀረበላቸው መስተንግዶ በብዛቱም ሆነ ባይነቱ ፤ እጅግ የሚያስደንቅ ነበር ፤ ቀኛዝማችን ራሳቸውን ሳይቀር ደስ ከማሰኘቱ አልፎ ፤ በጣም ነበር ያስገረማቸው ፤ ሰፈር ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ከሌሊቱ የሚበልጠውን ክፍል ግብር እንደ ገባ ፤ ባይነሳ እንጀራና ወጥ ፤ ሰንጋም እየታረደ በላይ በላዩ እየተጨመረ እየተበላ ፤ ጠጅ እንደ ውሀ እየተጠለቀ ፤ አረቂም በገፍ እየተጠጣ እንዲሁ ሲዘፈን ፤ ሲቀራራ ፤ ሲፈከር አደሮ ፤ በንጋው ቀኛዝማች ከነሰራዊታቸው ከመታረድ የተረፉትን ሰንጋዎች ፤ ሽሀሮችና ሙክቶች አስነድተው ሲሄዱ ፤ ተርፎ የቀረው እንጀራና ወጥ ፤ ስጋ ፤ ጠጅና ጠላ ፤ አረቂ ፤ ለደጋሹ ህዝብ ቤት ወንድ ፤ ልጅ አዋቂ ፤ ሳይባል ፤ በሙሉ ለምሳም ፤ ለራትም ፤ ከሚበቃ በላይ ሰለ ነበረ ፤ ለቀኛዝማች ዳኘ ግብር ማግቢያ በሰራላቸው ጊዜያዊ ሰፈ ዳስ ፤ ሁሉም ባንድ ላይ ተሰብስቦ ፤ የገዛ ሀብቱን ትራፊ እየበላና እየጠጣ ፤ እድሜ ለቀኛዝማች ዳኘ ዘፈኑን ፤ ጭዋታውን ውካታውን ቀጠለ ።

— ፍጻሜ —

@OLDBOOKSPDF

ሌላው ያቀባበል መንገድ ፡ ያው ለቆኛዝማች ስም ማስመረቂያ ፡ ያለው ከራሱ ፡ የለሌው ተበድሮም ይሁን ተቀድሞ ፡ የደገሰውና መንገድ ሲደለድል ፡ ከተማ ሲያጸዳ ፡ ቤት ሲሰራ የሰነበተው ህዝብ ፡ ባለ ብረት የሆነ ሁሉ ጌታውን አጅቦ ሲያመጣ ሲሄድ ፡ አቤት የቀረው ፡ ጃሌው ፡ አዩዘፈን እንዲቀበል የታቀደው ነው ።

ቆኛዝማች ከተማ ከሚገቡበት ቀን በፊት ፡ ግታውን ፡ የሰሚን ጆሮ ለመሳብ ቱልቱላ እዩተነፋ ፡ በየኪ ከተማና በዙሪያ ገባው ለሚኖረው ህዝብ ፡ በነጋው ቆኛዝማች ዳኘ የሚገቡ መሆናቸውና ፡ ህዝቡ በሙሉ ወጥቶ እንዲቀበላቸው በጥብቅ የታዘዘ መሆኑ ሲለፈፍ አመሸ ።

“ ስማ ስማ ፡ የየኪ ከተማና የዙሪያው ህዝብ ሁሉ ስማ ! ስም ተሀም ላልሰማ አሰማ ተብለሀል ! ስማ ስማ ፡ የየኪ ከተማና የዙሪያው ህዝብ ሁሉ ስማ ! የተከበሩና የተወደዱ ጌታችን ፡ ቆኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ ፡ የየኪ ወረዳ ገዥ ፡ አንድ አመት ከሰለት ወር ተለይተውን ስንንፋፈቅ ከኖርን በሁዋላ ፡ በአምላክ ቸርነት ፡ በመንግስት መልካም ፈቃድ ፡ ተሹመው ፡ ተሸልመው ነገ ይገባሉና ፡ የሳቸው ደስታ የሁላችን ደስታ ስለሆነ ፡ በየኪ ከተማና በዙሪያ ገባው ነዋሪ የሆንህ ሁሉ ፡ በዱነገድህ እንደዱልማድህ ፡ ደስታህን የምትገልጽበትን መሳሪያህን እዩያዝህ ፡ ነገ ጥዋት ጀንበር ስትወጣ ፡ ቅዳምን ገብያ ተገኝተህ የሚመደብልህን ቦታ እንድትይዝ ተብለሀል ! ታዋ በግዜር ዳኛ ፡ ባልጋ ቁራኛ ከተያዘ በቀር ፡ ሴት ወንድ ፡ ልጅ አዋቂ ሁሉ ፡ ‘ አቤት ውሎዋል ’ ወይም ‘ በግናቸውም ምክናያት ወደ ታዘዘበት ቦታ ሳይሄድ ቀርቶዋል ’ ተብሎ ተከሰሶ ፡ በጠላቱ ምስክርነት እንኳዋ ቢረታ ፡ አይቀጡ ቅጣት የሚቀጣ መሆኑን እንድታውቀው ተብለሀል ” የሚል ነበር ሲለፈፍ ያመሸው ።

በነጋው ጥዋት የየኪ ከተማና የዙሪያው ህዝብ ሴት ወንዱ ፡ ልጅ አዋቂው ፡ እንደታዘዘው ጀንበር ስትወጣ ጀምሮ ፡ እስከ ሁለት ሰአት ቅዳምን ገብያንና በዙሪያው ያለውን ሜዳ ሁሉ ሞላው ። ከዚያ ከዩነገዱ ማለት ከጣማ ፡ ከሸኮ ፡ ከመዠንገ ፡ ከከፋ ፡ ከጋላ ፡ ከማራ ተወጣጥቶ ፡ በሶስት በሶስት ተመድቦ ፡ አንደኛው ምድብ ቆኛዝማች ከነሰራዊታቸው በሚመጡበት መንገድ ፡ እከተማው መግቢያ ላይ ፡ ሁለተኛው ምድብ በዚያው መንገድ ከከተማው መግቢያ ሶስት ኪሎ ሜትር ርቆ ፡ ሶስተኛው ምድብ አሁንም ያኑ መንገድ ይዞ ከሁለተኛው ምድብ እንዲሁ ከሞላ ጎደል ሶስት ኪሎ ሜትር ያክል ርቆ ፡ ሁሉም በተጠንቀቅ ሲጠባበቅ ፡ ቆኛዝማች ለሰራዊታቸው መንገድ አልበቃው ብሎ

@OLDBOOKSPDF

እንደ ውሀ ሙላት ግራ ቀኙን እልፎ ተርፎ እያጥለቀለቀ ፣ ጥሩንበኞች እንቢልተኞችና መለከተኞች እንደ ልማዱ ዝግተኛ ፤ የጉዞ ንፋቸውን እየተቀባበሉ እያሚወቱዋቸው ሲመጡ ከሩቅ ታዩ ።

ቀኛዝማች ዳኘን በዘፈን ሲቀበል የሄደው ህዝብ በዩንገዱ ፣ እንደየልማዱ ወደ ቀኛዝማች እዩዘፈነ ወደአጃቢ ሰራዊታቸው ፣ ቀኛዝማችና አጃቢ ሰራዊታቸው እዩዘፈኑ ሲቀበል ወደሚመጣው ህዝብ ሲጉዋዙ ትንሽ ቆይተው ፤ እንደ ተቃራረቡ ፣ ቀኛዝማች ከተቀባዩ ህዝብ ጋር ለመገናኘት ከበቅሎ ሲወርዱ ፤ ጠበንጃ የያዘ ሁሉ ቢያንስ ቢያንስ እንዳንድ ጥይት ሳይተኩስ ቢቀር አይቀጡ ቅጣት እንደሚቀጣ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ ስለ ነበረ ተኩስ ተጀመረ ። ያ ፤ ተኩስ እንዲያ የሚያስፈራ ፤ እንዲያ አለምን ያለፈች የሚያስመስል እንደሚሆን አስቀድሞ ቢታወቅ ኖሮ ፣ እንዲተኮስ ትእዛዝ ይሰጥ እንዳልነበረ አውቅ ነው ፤ ብቻ እንዲያ ይሆናል ተብሎ አልተገመተም ። ተኩስ ተጀምሮ እስኪያበቃ ድረስ ይንጉድ የነበረው የጥይት ነጎድጉዋድና ያ፣ ነጎድጉዋድ በዚያ አካባቢ የፈጠረው ያዩር መናወጥ፣ከመሬቱ መንቀጥቀጥ ጋር ባንድላይ ፣ ሰማይና ምድር የቆሙበት መሰረት ፈርሶ ፣ ሁለቱም እዩተናዱ መጨረሻ በሌለው ፤ ዘላለማዊ አዘቅት የሚወርዱ ይመስል ነበር ፤ እዚያ ለነበረ ሁሉ አለም አለማለፍዋ ፣ ሰማይና ምድር መሰረታቸው ፈርሶ አለመናዳቸው የተረጋገጠለት ተኩሱ ከቆመ በሁዋላ ነው ፤ ተኩሱ ካቆመ በሁዋላ ፣ ሁሉም ዙሪያ ገባውን ዘወርወር ብሎ አይቶ እንዳለ መሆኑን ፣ ከራሱ በላይ ሰማዩ ፣ ከግሩ በታች መሬቱ እንደነበረ ሲያረጋግጥ ፣ እዩተያዩ ይሳሳቅ ጀመር ፤

ተኩሱ ሲያቆምና አዩር መናወጡም ፤ መሬት መንቀጥቀጡም ሲቀር፣ ቀኛዝማች ታጣፊ የሸራ ወንበር ተዘርግቶላቸው ተቀምጠው ፤ የኪ ከሚኖሩት ለድሉት ታላላቅ ነገዶች ተውጣጥተው የመጡት ዘፋኞች ለዩብቻ ፤ እንደዩባህላቸው ሲዘፍኑ ፤ ጥሩንበኞች፣እንቢልተኞችና መለከተኞች በዩመሳሪያቸው እዩተቀባበሉ ሲጫወቱና፣ አሽከሮቻቸው ሎሙቱን በሀይል ተዋግተው ፤ ማርከው እንዳመጡት ሁሉ ሲያቅራሩና ሲፈክሩ እያዩ ፤ ልባቸው በደስታ ሲዋኝ ቆይተው ፤ ከዚያ ተነሱና ጉዞዋቸውን ቀጠሉ ።

ቀኛዝማች ፤ በሁለተኛውና በመጀመሪያው ምድቦች ተመድበ መድረሳቸውን ሲጠባበቅ ከነበረው ዘፋኝ ጋር የተገናኙበት ሁኔታ ፤ ከሞላ ጎደል ያው ፤ ከሶስተኛው ምድብ ጋር እንደ ተገናኙበት ነው ። ተኩሱን ቀኛዝማች ስለ ከለከሉ እሱ ብቻ ሲቀር ፤ ዘፈኑ የሶስተኛው

@OLDBOOKSPDF

ምድብ ዘፋኝ ከሁለቱኛው ፣ ሁለቱ ባንድ ላይ ከመጀመሪያው ጋር በመደራረባቸው መጠን ፣ እንዲያውም የላቀ ፣ መዚቃው ፣ ቀረርቶና ፍከራው ፣ ጉዞው ወደ ከተማ እዬቀረበና ተመልካች እዬበዛ በመሄዱ መጠን ፣ እንዲያውም የሞቀ ፣ እንዲያውም የደመቀ ነበር !

መቸም ዘፈን ፣ ቀረርቶ ፣ ፍከራና እነሱን የመሳሰሉት የስሜት መግለጫዎችና መቀስቀሻዎች ፣ የዬራሳቸው ስራትና ህግጋት ስላላቸው በውድም ሆነ በግድ ፣ አንድ ጊዜ ከተጀመሩ ፣ እዚያ በተጀመሩበት ቦታ የሚገኙትን ሰዎች ሁሉ እንደዬስራታቸውና እንደዬህግጋታቸው የሚያዝዙና የሚገዙ መሆናቸው የታወቀ ነው ። ምንም ያክል ያዘነ ሰው ቢሆን ፣ የሚወዳት እናቱ የሞተችበት እንኳ ፣ ዘፈን ደምቆ በሚዘፈን ብት ቦታ ከተገኘ ፣ ሳይወድ ፣ ሳያስበው ፣ ልቡ የዘፈኑን ቅኝት ፣ የዘፈኑን ዜማ ተከትሎ መሄዱ አይቀርም ። አንድ ወጣት ፣ እጅግ የሚወዳቸው እናቱ የሞምቱት እለት ሞተውበት ፣ ዘመድ ወዳጁ ከብቦ እያስተዛዘነው ፣ እሱ ባዘንተኛ ወግ የናቱን አስከሬን እዬዞረ “ እናቴ ፣ እናቴ ” እያለ ድምጹን ከፍ አድርጎ በልቅሶ ዜማ ሲያለቅስ ፣ ያገሩ ጎበዝ ታቦቱን ካደረበት ፣ ከባህረ–ጥምቀቱ አጅቦ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማግባት ሲያልፍ እንደ ሀገረ-ልማዱ ፣

“ እዮዋ ፣ አሆ ፣ አየው ባረያሆን ፣

እዮዋ ፣ አሆ ፣ አየው ልጅሆን ፣

ሆ እያለ ፣ አሆ ፣ ሲያጅብ ታቦትሁን ”

እያለ እዬዘፈነ መጥቶ ፣ አጠገቡ እንደ ደረሰ ፣ ቆም ብሎ ዳንኪራ ሲመታ ተመለከተና ፣ ልቡን ዘፈኑ ስለ ማረከው እቶ “ እናቴ እናቴ ” ማለቱን ሳይተው ፣ ዜማውን ከለቅሶ ወደ ዘፈን ለውጦ ፣ በዘፈን ዜማ “ እናቴ እናቴ ! አሆ ፣ ኧረ እናቴ ! ” እያለ እሱም ዳንኪራ ይመታ ጀመር ! ይህ ተረት አደለም ፤ በርግጥ የሆነ ነገር ነው ።

ስለዚህ ቀኛዝማች ዳኘ ፣ ሹም ያዘዘውም ፣ ዘፈን ፣ ቀረርቶና ፍከራ ያዘዙትም ሁሉ ፣ ባንድነት እየዘፈኑ ፣ እያቅራሩና እዬፎከረ ሲቀበላቸው ፣ ብርቱ ጠላቱን ድል አድርጎ እንደ ተመለሰ አዝማች ፣ ነፍጠኛ ሁሉ ተኩሱን የሰማይ ቋጣ አስመስሎ እያንጎደጎደ ሲቀበላቸው ፣ ከተማው ከምንጊዜም የበለጠ አምሮ ፣ መንገዱ በቅስትና በልዩ ልዩ ባለአበባ ወረቀት ተኸርጎርጉሮ ፣ ኧረ ስንቱ ? እንዲያው ሁሉም አጊጦና ተንቆጥቁጦ በደስታ ሲቀበላቸው ፣ ይህ ሁሉ ምንም አይነትና ምንም ያክል ዋጋ የማይበቃው አቀባበል ሲደረግላቸው እያዩ ፣ ይህ ሁሉ የሚ

@OLDBOOKSPDF

ያዩት ግሩም አቀባበል ይህ ሁሉ የሚያዩት አዲብ ድንቅ አቀባበል ፣ እውን መሆኑን ፣ አለም አለመሆኑን ማረጋገጥ አቅቶዋቸው ፣ ግራ እንደ ገባቸው ከፊታቸው ፣ ከሁኔታቸው ሁሉ በግሀድ ይታይ ነበር !

አንዳንድ የቀኛዝማች ባለሙዋሎች ለመሆን ተስፋ የነበራቸው ፣ የቀኛዝማችን ባለሙዋልነት በጥም ለመግዛት ተስፋ ያደረጉ ሰዎች አዩገጠሙ ለሀዝብ ለጥቶው ህዝቡ በዩቁዋንቁዋው ተርጉሞ ፣ የራሱ አድርጎ ፣ ይዘፍኗቸው ከነበሩት መሀከል የሚከተሉትን የመሳሰሉ ይገኙ ባቸው ነበር ።

" ዳኘው መጣልን ፤
እንኩዋን ደስ አለን ።
ግፋው መጣልን ፤
እንኩዋን ደስ አለን ።
እልል በል መሬቱ ፣ ዝሬን ከኛ ጋራ ፤
እልል በል አዩሩ ፣ ጨፍር ከኛ ጋራ ፤
እልል በል ሰማዩ ፣ ዝለል ከኛ ጋራ ፤
እልል በል ፍጥረቱ ፣ ፈንጥዝ ከኛ ጋራ ፤
ጌታችን መጥቶልን ፣ ደስታ ሲያዘልለን ፣ ሲያስመታን ዳንኪራ ።"

ቀኛዝማች ዳኘ እንዲያ ሰው ብቻ ሳይሆን ከሰው ጋር ሰማዩ ፣ መሬቱ ፣ አዩሩ ፣ ፍጥረቱ ሁሉ ፣ እልል እያለ እዩዘፈነ ፣ እዩጨፈረ ፣ እዩፈነጠዘ አጀቦዋቸው በቅሰት ፣ በሰንደቅ አላማና በባላበባ ወረቀት ያጌጡትን የከተማ መንገዶች ሁሉ ፣ አንዱን ከጫፍ እስከ ጫፍ ሲጨርሱ ፣ ወደ ሌላው እዩተላለፉ ዞረው በመጨረሻ እግቢያቸው ሲደርሱ አጥሩ በር ላይ ቢተሰባቸው በሙሉ ወጥቶ ቤቱ በልልታ ፣ ወንዱ በሆታ እዩዘለለ ፣ እዩጨፈረ ሰለ ተቀበላቸው ፣ እዚያ ከበቅሎ ወርደው ፊታቸው ሁሉ በደስታ እዩሳቀ ትንሽ ሲመለከቱ ቆዩና ፣ ወደ ግብር ማግቢያው አዳራሽ ገቡ ።

መቸም ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ ማብላትና ማጠጣት የሚያውቁ በመሆናቸው ሰመጥር ነበሩ ። የመኩዋንንቱን ልግስናና ንፉግነት እያ መዛዘኑ በሚተቹት ተቺዎች የተለመደ ቁዋንቁዋ ፣ ቀኛዝማች ዳኘ "ግብረ - ሰፊ ፣ ቤታቸው ሁልጊዜ እንደ ተሰናዳ የሚኖር ፣ ማታ የደረሰ ሙሉ ሰራዊት በለት ራታቸው ጋብዘው የሚሸኙ" ከሚባሉት መሀከል የሚቆጠሩ ነበሩ ። ይህ እንኩዋ እንዲያው ድግሱን ራሳቸው ፣ በኪሳራ

@OLDBOOKSPDF

ቸው የደገፉት ቢሆንም ኖሮ ፣ በማብላትና በማጠጣት በኩል እጅግ የሚመሰገኑ እንጂ የሚታሙ እንዳልነበሩ ለማመልከት ያክል ነው እንጂ ፣ ይህን የቀኛዝማችነት ስማቸውንና ቀሚሳቸውን ለማስመረቅ የተደገሰውን ድግስና ፣ የተሰናዳውን መሰናዶ እሳቸው ግቢ የሚበላና የሚጠጣ ፣ እሳቸው የሚያበሉትና የሚያጠጡት ቢሆንም ፣ ደጋሹ እሳቸው አልነበሩም ። ደጋሹ አገር ነበር ፣ የኪ ነበር !

በማብላትና በማጠጣት ፣ ወይም በማናቸውም ስጦታ ፣ መልካም ስምንና ከፍተኛ ዝናን መግዛት የሚፈልጉ ሁሉ ፣ ዋጋውን የሚከፍ ለው ሌላ ከሆነ ፣ ወሰን የሌለው ዋጋ ተከፍሎ ወሰን የሌለው ምስጋ ናና ከፍተኛ ዝና ስለሚፈልጉ ፤ ቀኛዝማች ዳኘ ቀሚሳቸውን ሲያስመ ርቁ የየኪ ህዝብ ያሰናዳላቸው ግብግቦ ፣ ወሰን የሌለው ምስጋናና ዝና እንዲያገኙበት ፣ ወሰን የሌለው ነበር ! ቀኛዝማች የኪ ከገቡበት ቀን ጀምሮ ፣ አስር ቀን ፣ ከርብና ካርብ በቀር ፣ ሁል ጊዜ ፣ ካራት እስከ እምስት ሰንጋና መሲና እየታረደ የየኪና ያካባቢው ህዝብ ፣ የድግሱን ወሬ እየሰማ ከሩቅ የመጣ ሳይቀር ፣ በላ ፣ ጠጣ ! ከርብና ካርብ በቀር ፣ አስር ቀን የሰንጋ አንገት እንደ ጉኖሮ ሳመን እየተቀነጠሰ ስጋ ያማረው ሁሉ እጅ እጅ እስኪለው ፣ እስኪቸከው በላ ! አስር ቀን ጠጅ እንደ ውሀ ባንኩላ እየተጠለቀ ተጠጣ ! አስር ቀን የየኪና ያካባቢው ህዝብ የደገሰውን እዩበላ ፣ እዩጠጣ ዘፈኑ ፤ አቅራራ ፤ ፎከረ ፤ ፈነጠዘና "እድሜ ለቀኛዝማች ዳኘ !" አለ ።

እየታረደ ሲበላ ከሰነበተው ተርፎ ፣ ቀኛዝማች ወደ ጎሬ ከላይ ፣ ከንደራሴው ጀምሮ እስከ ታችኞች ሹማምንት ፣ ለባለውለታዎቻቸው እንደዩማእረጋቸው የላኩላቸው ሰንጋዎች ፣ ሙክቶች ፣ የላምና የበግ መሲናዎች ብዙ ነበሩ ።

" ተጨንቀን ነበረ ፣ ካገር ብናጣህ ፤
እንኩዋን ቅዱስ ገብርኤል ፣ በደህና አመጣህ ።
አመት ሙሉ አልቅሰን ፣ ያገኘነውን ፤
ዘንካታውን ጌታ ፣ እባ ግፉውን ፤
ጠብቅልን አምላክ ፣ እንዳይን ብሌን ።
ሁሉን የሚያሳዩን ፣ አይናችን ነውና ፤
ዳኛቸው ፍሪሳን ፣ አምላክ ጠብቅልን ፣ አድርግልን ደህና"

ሲሉ እግብሩ ላይ ከቀኝ ወገን ቆመው ያሜውቱ የነበሩ አዝማሪዎች እዩተቀባበሉ ፣

" ሙቶ ከተነሳ ፣ እንደ ማሪያም ልጅ ፣
እዝጎ መሐረን ፣ እንበለው እንጂ"

@OLDBOOKSPDF

ሙቶ ከተነሳ ፣ እንደ እግዚሀር ልጁ ፤
አዝነ ሰጊድ ሰላም ፣ እንበለው እንጂ ።
ከጠጁ ጨምሩ ፣ አልበቃንም ገና ፤
ካረቂው ጨምሩ ፣ አልበቃንም ገና ፤
ከሰንጋው ጨምሩ ፣ አልበቃንም ገና ፤
ከሁሉም ጨምሩ ፣ አልበቃንም ገና ፤
ካሳው ከበደሉ ፣ አንሶ እያውቅምና ።
ክርስቶስ ቢመጣ ፣ ሲሆን አብነት ፤
በደል ሳይኖርበት ፣ ሳይሰራ ሀጢያት ፤
አይሁድ ጲላጦስን ፣ እንደ ለመኑት ፤
ስቀሎ ፣ ስቀሎ ፣ ብለው ባንድነት ፤
አንተም እንደ የሰሰ ፣ ተብለሀ ነበረ ፣ ስቀሎ ! ስቀሎ !
አልሆን ሲል ቀረ እንጂ ፣ የጎሬው ጲላጦስ ፣ አልቀበል ብሎ ”

አሉ ፣ ከግራ ወገን ቆመው ያጫውቱ የነበሩ አዝማሪዎችም እን ዲሁ እዩተቀባበሉ ።

“ እነዚህ አዝማሪዎች ምን ማለታቸው ነው እባክህ ? ” አሉ ከታላላቁ ሽማግሌዎች አንዱ ፣ ባጠገባቸው የተቀመጡትን ጉዋደኛቸ ውን በክርናቸው ጎሰም አድርገው ። ሽማግሌው መቸም አዝማሪ ዘይ ቤኛ ነውና ፣ እኒያ የግራ አዝማሪዎችም የተሸሸገ ነገር በዘይቤ ለመግ ለጽ የሚቆፍሩ ስለ መሰላቸው ፣ እንደ መፍራት ማለታቸው ከፊታቸው ይታወቅ ነበር ።

“ የነሱ አይደለም ፤ በሉ የተባሉትን ፣ ያጠኑትን ነው የሚደ ግሙ ! ” አሉ ጉዋደኛቸው ።

“ ማነው በሉ የሚላቸው ? የሚያስጠናቸው ! ”

“ ባለቤቱ ! ”

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፳፫

# ያዲስ ዘመን ጋዜጣ ተሳላኪ

ቀኛዝማች ዳኜ ከጎሬ እንደ ተመለሱ ፤ አስር ቀን ያክል ከዳራሻቸው ሳይወጡ ፤ ግብር ሲያበሉ ፤ ከዚያ "እንኳዋን ደስ ያለዎ" ለማለት ልዩ ልዩ ስጦታ ፤ የደስደስ እዩያዝ ከቅርብና ከሩቅ ሲመጣ የሰነበተውን እጅግ ብዙ ህዝብ ሲቀበሉ ፤ ዘለግ ያለ ጊዜ ከግራቸው ሳይወጡ ሰነበቱ ። በከተማው ውስጥና በዙሪያው ጥላሁንና ሰፈያ የሰሩትን ስራ ምንም እንኳዋ ነሬ ሳሉም ፤ ከመጡም ፤ ቢሰሙና ደህና አድርገው ቢያወቁ ፤ ባይናቸው ገና አላዩትም ። ሰፈያም ሆነች ጥላሁን ሊጠይቋቸው ሲሄዱ ፤ እንደ ድሮዋቸው በደህና ፊት እየተቀበሉ በወዳጅነት ሲያነጋግሩዋቸው ሰነበቱ ። መቼም ጥላሁን እሳቸው በሌሉበት የተሰራውን ሁሉ ሲያዩ ፤ በጣም ደስ እንደሚላቸው ፩ኑ እምነት ስለ ነበረው ፤ የቀሚሲ ማስመረቂያ በአል ተፈጽሞ ፤ የደስደስ እዩያዘ የሚመጣው ሰው አቁሞ ፤ ምሽቱና እሱ የሰሩትን ሁሉ አዙር እስኪያሳያቸው ቸኩሎ ነበር ።

የቀሚስ ማስመረቂያው በአል ሲያልፍና ፤ በእሱ የተከበረበት ጊዜ ወደ ሁዋላ እዩራቀ በሄደ መጠን ፤ የደስደስ እዩያዘ ወደ ቀኛዝማች ይመጣ የነበረው ህዝብ እዩተቀነሰ ሄደ ፤ ወደ ማቆሙ ሲቀርብ ፤ ቀኛዝማችም መደበኛ ስራቸውን ጀምረው ፤ ቢያንስ በቀን ካንድ እስከ ሁለት ሰአት ያክል እጽህፈት ቤታቸው እዩደረሱ ይመለሱ ጀመር ። ብቻ በዚያ ጊዜ ፤ ጥላሁን ስራውን ሊግባዩትና ስለ የወደፊቱ እቅዱ ለመመካከር እዩመላለሰ ቀጠሮ ቢጠይቅ ፤ ቀኛዝማች የማይበቃ ምክናያት እዩፈጠሩ አለመፍቀዳቸውን ስላሳዩት ፤ "ምናልባት የተቀዩሙበት ነገር ይኖር ይሆናል" ብሎ መጠርጠር ጀመረ ።

"ድንገትኮ ተለወጡ ! በዚያ ፊት ... ደህና አልነበሩም ? አሁን ግን 'ስለ ስራችን ለማነጋገር እባክዎ ላጭር ጊዜ ይቀበሉኝ' ብዩ ብዙ ጊዜ ብልክባቸው እንቢ አሉኝ ። እንዲያውም ... አሁንማ ከሌሎች ጋር እንኳዋ ድንገት ያገኙት እንደሆነ ፤ አይናቸው እኔን ባለማየት ሲሸሽ ይታያል !" አለ ጥላሁን ፤ ከምሽቱ ጋር የቀኛዝማችን ነገር እንስተው ሲጫወቱ ።

@OLDBOOKSPDF

"ማታ ማታ ፣ ሰው ከገባ በሁዋላ ፣ ጥቂት ሰዎች እስኪቀሩ እቤ ዙሩ የተሰራውን ሁሉ ሲያዩ ነው እሱ የሚያመሹ ፤ እንዲያውም ትናንትማ ፣ እግሮች ቤትም ገብተው ነበር እሱ !" አለች ሶፊያ ።

"እውነትሽን ነው ? ማን ነገረሽ ?"

"ፎሪ"

"ይገርማል ! ባሳምባራስ ጉደታና አሳዬ የሚሉት እውነት ነው ማለት ነው?" አለ ጥላሁን ፣ እንገቱን ደፍቶ ሲያስብ ቆይቶ ቀና እለና ።

"ምኑ" ?

"ደህና ስራና ደህና ሰሪ የማይወዱ መሆናቸው!"

"እንጃ ! ለመሆኑ ምኑ ነው ደህን ያሰኘህ ?"

"ስራችንን ይዩልን" እያሉሁ እዩጨቀጨቅሁዋቸው . . . በግልጽ ለማየት ተለምነው "እንቢ" ያሉትን "ጨለማ ለብሰው፣በጨለማ ተሸሽገው እዩሂዱ ሲያዩ ማምሸትን ምን ትይዋለሽ ? ... ይህ ደህና ሰው የሚያደርገው ነው ?"

"የሚያስጠረጥር ሊሆን ይችላል ፤ ነገር ግን ደህና ስራና ደህና ሰሪ የማይወዱ ለመሆናቸው፣ በቂ ማስረጃ ሊሆን የሚችል አይደለምና እስቲ እንቸኩል ፤ ትንሽ እንያቸው " አለች ሶፊያ ።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ጥላሁን እሱና ሶፊያ ስለ ስሩትም ፣ ወደፊት ለመስራት ስላቀዱትም ፣ ቀኛዝማች እንዲያነጋግሩት መጠዬቁን ተወ ። የተለወጡበት ጊዜያዊ ኩርፊያ እንደሆን እስኪያልፍ ፣ ዘላቂ ጥል እን ደሆነ ፣ እንደኛውን ተገልጾ እስኪታወቅ ፣ ሌላ ስራቸውን ለጊዜው አቁ መው የህክምናና የማስተማር ስራቸውን እዩሰሩ እንዲቆዩ ፣ ባልና ሚስቱ ተስማሙ ። ብቻ ይብሱን ግራ ያጋባቸው ፣ አንዳንድ ጊዜ ለዩብቻ ፣ ወይም ባንድ ላይ ሲያገኙዋቸው ፣ በብሩህ ገጽ ሰላምታ ሰጥተው ያነጋግሩዋ ቸውና "ኩርፊያው ሊያልፍላቸው ነው" ብለው ደስ ሲላቸው ፣ በሌላ ጊዜ ሲገናኙ ፣ የተቋዋጠረ ግንባርና ያሞደሞደ ከንፈር እያሳዩ ፣ ሊያ ነጋገር እጅግ ሲከብዳቸው መታየታቸው ነው ። አንድ ማታ አሳዬ ከመስሪያ ቤቱ በቀጥታ ወደንጥላሁን ቤት መጣና ሲጫወቱ ፣

"ካዲስ አበባ እቀኛዝማች ዘንድ አንድ ጋዜጠኛ መጥቶ ፣ 'ስለ ዚህ አገር ያመት ገቢና ወጪ ማወቅ እፈልጋለሁ' ሲላቸው ጊዜ ፣ በፖሊስ አሳጅበው ወደኔ ልከውት ፣ የፈለገውን መረጃ ከሰጠሁት በሁ

@OLDBOOKSPDF

ዋለ ፤ ቀኛዝማች እዚህ አገር የሰሩትን ታምር አንስቶ እዮተገረመ ነገረኝና ፤ በሉ የትነላ… ስንሰቅ ቆይተን ፤ ስንለያይ ወዲህ መጣሁ።” አለ።

“ቀኛዝማች ምን ታምር ሰሩ?” አለ ጥላሁን ።

“ሰፊና አንተ የሰራችሁትም ፤ ያሰራችሁት ሁሉ ፤ ‘በታምር እሳቸው የሰሩትና ያሰሩት ሆኖ’ ጥሩ ታምር አይሰም?”

“እ … ! ታዲያ ይህ ምን ያስቃል?”

“እወንቱን ስንግረው ጊዜ ገርሞት ሲስቅ ፤ እኔንም አሳቀኝ ።”

“ለምን ብለህ አይ … ‘ዩግም አላረግህ !”

“ምስክርነትኮ ነው ጥላዩ ! አሰት ልመስክር?”

“ማን ጠራህ?”

“ጠይቆኝ ነው ፤ ሳይጠይቀኝስ አልተናገርህም።”

ጋዜጠኛው ከየኪ በተመለሰ ባስራምስተኛ ቀኑ ይሁን ፤ ወይም እዚያ አካባቢ ፤የየኪ ልማት በዝርዝር ታትሞ የወጣበትን አዲስ ዘመን ጋዜጣ ፤ አቶ አብዱል ሰሊም ፤ ከሳሬ ይዞ መጥቶ ለቀኛዝማች ሰጣቸው። እዚያ ፤ ውስጥ ፤ አንድ ቦታ ላይ እንኳዋ ፤ አንድ ቃል ለምልክት ያክል ትንኩዋ ፤ የሳቸው ስም አልተነሳም ። ተጀምሮ እስኪያልቅ የሚወደሰው፤ የሚሞገሰው ፤ የጥላሁንና የሰፊያ ስም ብቻ ነው !

በልማዱ ፤ ስለ የኪ ወረዳ ግዛት ልዩ ልዩ ጉዳዮች ለመመካከር ፤ በሳምንት አንድ ቀን ፤ ማክሰኞ ከሶስት እስከ ሰባት ሰአት ፤ በወረዳው ገዥ ሰብሳቢነት ፤ የገንዘብ ሚኒስቴር ሹም ፤ የወረዳው ፍርድ ቤት ሰብሳቢ ዳኛና ፤ የወረዳው ፖሊስ አዛዥ ያሉበት ስብሰባ ፤ በወረዳው ግዛት መስሪያ ቤት ይደረጋል ። የወረዳው ገዥ በሌሉበት ሰብሳቢው የገንዘብ ሚኒስቴር ሹም ነው። ቀኛዝማች ከሳሬ ከተመለሱ ግን ፤ ስብሰባው እንደ ወትሮው ቀኑን ጠብቆ ተደርጎ አያውቅም ፤ ሲደረግም ፤ ሲቀርም ነው ።

አንድ ሀሙስ ፤ በነጋው ፤ ሳርብ ጥዋት ፤ ስብሰባ የሚደረግ መሆኑ ባባሎቹ ሁሉ ተነግሮ አሮሮ ነበርና ፤ ሁሉም ዘሰሰት ሰአት እቀኛዝማች ጽህፈት ቤት ሲደርሱ ፤ ቀኛዝማች ቀድመዋቸው መግባታቸውን ሰሙ።

የየኪ ወረዳ ግዛት መስሪያ ቤት ፤ በውጭም ሆነ በውስጥ ያልተመረገ ፤ የሳር ክዳን ነው ። ውስጡ ሰሴን እዮተቀጣጠለ ዙሪያውን በሚሰግር ስለ ተመታ ፤ ግድግዳው አይታይም ። ከበር ሲገባ ፤ ፊት - ለፊት ግድግዳው በተሸፈነበት ሰሴን ላይ ፤ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ከፍ

ብሎ ፣ እግድም በሚወርድ ጥሻ ፤ በዚያ ላይ የመንግስቱ መሪ ፎቶ ግራፍ ይታያል ። እስሩ የወረደው ነዥ ፣ ቀኛዝማች ዳኘ ፣ ከመራቱ ይሁን ከግሮቹ አለመተካከል የተነሳ ፣ ወዳንድ ወገን ገደድ ብሎ ፣ ሲወድቅ ትንሽ የቀረው በሚመስል ፣ ጎርበጥባጣ ጠጺረዛ ሁዋላ ፣ የሚመጣ ጠላ ቱን ለመያዝ እንደሚያደባ ነብር ወደ ሁዋላ ሽምቅቅ ብለው ፣ አይና ቸው በቁጣ ደፍርሶ ፣ በወንበር ተቀምጠው ይታያሉ ። ከውጭ ሲገባ ወደ ቀኝ ፣ እግድግዳው ጥግ ፣ የወረዳው ጸሀፊ የጽህፈት መሳሪያውን እንዳሁ በጎርበጥባጣ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጦ ፣ አባሎች ገብተው ስራ እስኪጀምሩ ቆሞ ይጠብቃል ። ከቀኛዝማች ፊት - ለፊት ፣ በጠረጴዛቸው ቀኝና ግራ ፣ መጥረቢያ ያልዞረባቸው አራት አራት ድብልብል እንጨ ቶች በዱጫፋቸው እንደ እግር የተሸነጠባቸው ፣ ሁለት የዋንዛ ባንቃ ዎች ስለ ነበሩ ፣ ለስብሰባ የተጠሩት ገብተው እጅ እዬነሱ ፣ ከቀኝ ወገን የበሽርግንዱ ወኪል አባዬ ፣ ከግራ ወገን የወረዳው ሰብሳቢ ዳኛና የፖ ሊሱ ሹም ተቀመጡ ።

ቀኛዝማች እንደ ወገብ በሽተኛ ገደድ ብሎ በቆመ ጠረጴዛቸው ላይ ፣ ቅጥ አጥቶ የተልከሰከሰውን የተጻፈበትና ያልተጻፈበት ወረ ቀት የባሰውን ቅጥ ለማሳጣት እንደ ፈለጉ ሁሉ እያነሱ ፣ እዬጣሉ ፣

“አሁን” አሉ በብርቱ ቁጣ ። “ አሁን ያለቀኑ ልዩ ገባኤ የጠ ራሁ ፣ እዚህ አገር እስራ ስምንት አመት በገዥነት ስቀመጥ ደርሶ የማ ያውቅ ፣ እንግዴና በጣም የሚያስገርም ነገር ስለ ገጠመኝ ነው ። ‘በበ ቅሎ ተቀምጦ ዛቡን ፣ በግዛት ተቀምጦ ስልጣኑን ፣ ለሌላ የሚያስጨ ብጥ ወደ ፈለገው ሄዶ አያውቅም ! ’ የሚሉት ፣ እስከ ዛሬ ፣ በኔ ደርሶ አያውቅም ነበር ! እስካሁን ፣ እኔ ዳኛቸው በምገዛው አገር ፣ ስልጣኔን ይዞ ‘ልምራህ’ ያለኝ ሰው ገጥሞኝ አያውቅም ነበር ! እስካሁን ድረስ በምገዛው አገር እንኩዋንስ ስልጣኔን ይዞ ‘ ልምራህ ’ የሚል ፣ ‘የስል ጣን ተካፋይ ልሁን ’ የሚል መጥፎ ብኝ አያውቅም ነበር ! በጠላት ጊዜ እንኩዋ ፣ የሞቻን ጫካ በሙሉ ስገዛ ፣ የስልጣኔ ተካፋይ አልነበረኝም ! እኔን ካባጠፉ ፣ ነፍስና ስጋየ አብረው እያሉ ፣ ስልጣኔን ከኔ መውሰድ ፣ ወይም መካፈል ፣ የማይቻል መሆኑን ያውቅ የነበረው ጠላት ፣ እኔን ለማጥፋት በዬጊዜው እያደረጀ ከሳከው ፣ ቁጥር ስፍር የሌለው ስራዊት ፣ ወሬ ነጋሪ አልተመለሰም ። ሁሉም እዚሁ ሲጋውን የሞቻ አራዊት ተቀ ራምተውት ፣ በፈረሱ የሞቻ መሬት ቀልዞበት ነው የቀረው !” አሉ ቀኛ ዝማች ፣ ንግግራቸው ባርብኝነት ይሰሩት የነበረውን ጀብድ ጠርቶ እም ጥቶ ሲያሳያቸው ፣ ወኔ ትከሻቸውን ወደ ላይ ገፍቶ ሲከምረው እዬታዬ !

@OLDBOOKSPDF

"እሁን ሁ-ሁ-ሁ-!" አሉ ያሽሙር ሳቅ ስቀው ። "አሁን ... ያረጀሁ ሳይመስለኝ ለካ አርጅቼ ኖሮ ፣ የደከምሁ ሳይመስለኝ ለካ ደክሜ ኖሮ፣ ሳገሬ ፍቅርና ለመንግስቴ ክብር ከሀይለኛ ጠላት ጋር እጋደል በነበር ሁበት ጊዜ ገና ያልተጸነሱ ፣ የምን መጸነስ ! ኧረ አባት እናቶቻቸው ገና ያልተዋወቁ ፣ ገና ትናንት የተወለዱ ህጻናት ፣ ትምርት ሲያስቸግራቸው ከተማሪ ቤት እዮኮበለሉ እዚህ እዩመጡ ... ሆ ሆ !የኔን ስልጣን እን ቀማ ይሉ ጀመር ! ግሩም ነው ፤ በጣም ግሩም ነው !" ሲሉ ፣ እንግዶው የተቀመጡት ሁሉ እስበሳቸው ብጥያቄ አይን ከተያዩ በሁዋላ ፣ አይና ቸውን እንደ ገና ወደ ቀኛዝማች መልሰው ፣ እሳቸውን እዩተመለከቱ ፣ እስከዚያ የተናገሩትን ቀጥለው የሚናገሩት ይገልጸው ይሆናል በግለት ይጠባበቁ ጀመር ።

"ደግሞ ከዚህ ይልቅ የሚያበሳጭዎ" አሉ ቀኛዝማች ቀጥለው። "ከዚህ ይልቅ የሚያስገርመው፡ እንዲህ ያሉት ... ስልጣን ምን መሆ ኑን ሳያውቁ በስልጣን መጫወት የሚፈልጉ ህጻናት ከሰሩት የበለጠ የሚያስገርመው ፣ እንደ ጭፍሮቼ ሳይሆን እንደ ወዳጆቼ ፣ እንደ ... ወን ድሞቼ የማያችሁ የስራ ረዳቶቼ ፣ በኔ ፣ በማልሰወጠው ፣ በኔ በተፈተን ሁት ወዳጃችሁና አለቃችሁ ላይ ፣ የሚያደርጉትን ከማያውቁ ህጻናት ጋር ሆናችሁ ማደማችሁ ነው ! ይህ ነው ከሁሉም ያስገረመኝ !" ሲሉ፣ ቁጣ ባደፈረሰው አይን እዚያ የተቀመጡትን ሁሉ አንድ ባንድ ቆጥ ረው ፣ ለጊዜው ሁሉም እንደ መደንገጥም ፣ እንደ መገረምም ብለው እስበሳቸው እዩተያዩ ዝም ብለው ቆዩና ፤

"ለመሆኑ ... ማናችን ከማን ጋር ነው በርስዎ ላይ ያደመ" አለ የገንዘብ ሚኒስቴሩ ሹም ፣ አሳዬ ።

"ሁላችሁም ናችሁዋ ! ሁላችሁ ናችሁ ! ለሰው ዘር ጠር እንደ ሆንሁ ሁሉ ፣ ሁላችሁ ስላደማችሁብኝ ነው እንጂ ፣ አንዳችሁማ ብትሆኑ ... እንድ ሰው ከሌላ መቀያየም ፣ እንድ ሰው ከሌላ መጣላት የነበረ ስለሆነ ፣ ምን ያስገርማል ! ከመሀከላችሁ ያደማው መስራች አንተ ነህ !" አሉ ቀኛዝማች ፣ ድፍርስ አይናቸውን ባሳዬ ላይ አፍ ጠው ።

"ኧረ ያንት ያለህ ! እኔ ነኝ በስዎ ላይ የማድም ! እንኩዋንስ እኔ ሳድምብዎ ፡ ያደመብዎ መኖሩንም አላውቅ ! ለመሆኑ ከማን ጋር አደመብዎ አሉዎ ?" አለ አሳዬ በመገረም ።

"ሀ ! ከማን ጋር አደምሁ ይለኛል ! ከማን ጋር እንዳደምህ መቸ አጣኸው ! ከዚያ አታላይ ፣ ከዚያ 'ቃልቻ ነኝ' እያለ ህዝቡን ከሚ ያስት አሳይ መሲህ ፤ ከዚያ 'ከኔ በቀር ለሹም አትታዘዙ' እያለ ህዝ

@OLDBOOKSPDF

ፀጉ መንግስት በሾመው አገረገዥ ላይ ካሸፈተ ጥላሁን የተባለ እታ
ላይ ጋር እንዳደምህ መቼ አጣኸው ! ከሱ ጋር በምስጢር ተማከራ
ችሁ ፣ አንተ ራስህ ከጎሬ መሬት ቀያኞች እስመጥተህ ፣ ከመንግስት
የወሰዳችሁትን መሬት ለጣሞች ፣ ለሸኮችና ለመሰንጎች ሁሉ ፣ እያሸ
ናሸናችሁ አላከፋፈላችሁትም ? የዚህ አላማ ከቶ ምን ይሆን ? የህ
ዝብ ወገን በመምሰል ፣ ይህን አላዋቂ ህዝብ እታሉና አስተባብሮ
በባለስልጣን ላይ ፣ በኛ ላይ ለማስነሳት አደለም ? ”

“ እንዴ ! ከገዛነው መሬት የቻልነውን ሰርተን ፣ ልንሰራ የማ
ንችለውን ገንዘብ ላለው ብንሸጥ ፣ ለሌለው ብንሰጥ . . . ይህ
እንዴት ሆኖ ፣ በየት በኩልስ አልፎ ነው በርስዎ ላይ አድማ የሚ
ሆነው ? ደግሞም ኮ . . . ያን ጊዜ ልብዎ ምናልባት . . .
ወደመንገዱ ተሳትሎ በቅጡ አላደመጡን እንደሆን ነው እንጂ ፣ የቀያ
ሾችን መምጣት ነግረንዎ እርስዎም ተስማምተው ነበርኮ ! ” አለ
አሳዬ ፣ የዚያን ጊዜ ሁኔታቸውን ሲያስታውስ ትንሽ ፈገግ እንደ
ማለት ብሎ ።

“ በል በቃህ ዝም በል ፤ እኔ መላቂያህ አደለሁም ! ” አሉ
ቆኛዝማች ፣ ያሳዬ አሽሙር ስለ ገባቸው ከቁጣም በላይ ግለው ።

“ እንተስ ” አሉ ከዚያ ወደ ዳኛው ዞረው ። “ አንተስ ዳኛ
ተብዬው ፣ ከመንግስት የወሰዱትን መሬት . . . ለመሰንጎ ፣ ለሸኮና
ለጣማ ሲያከፋፍሉ ፣ ተቀብለህ መዝገብ እያገባህ በመንግስት መሬት
ላይ የባለርስትነት የምስክር ወረቀት ለጣማ ፣ ለመሰንጎና ለሸኮ ያደ
ልኸው ፣ አድማህን ከነሱ ጋር አድርገህ አደለም ? ”

“ ር-ር-ርስታችን ነው አሉኝ ፣ አሉኝ ” እንጂ የ-የ- የመንግስት
መሬት መሆኑን መቼ አወቅሁ ? የመንግስት መሬት መሆኑን አሁን
ገና መስማቴ ነው ፤ እምላለሁ ጌታዬ ! ቢሆንም ቢ .. ቢሆንም ጥፋ
ተኛ ነኝ ፤ ይማሩኝ ጌታየ ! በጌታየ ላይ ግን አላደምሁም ! በጌታ ዎ
ላይ “ አድሞዋል” ብሎ አንድ ሰው በመስከረ ፣ ጆርባየን እንደ በሬ
ይግረፉኝ ! ” አሉ ዳኛው ፣ በሁለት እጃቸው መሬት ይዘው እዩተ
ንቀጠቀጡ ።

“ በል ተቀመጥ ፤ አሁን ተቀመጥ ብዬሀለሁ ! ” አሉ ቆኛዝማች
ዳኛውን ምን ያክል እንደ ናቁዋቸው ለማሳዬት ፣ የታች ከንፈራቸውን
አሸራመው ።

“ እንተስ ! ” አሉ ፣ ዳኛውን ተቆጥተው ካስቀመጡ በሁዋላ
ወደ ፖሊሱ ዘወር ብለው ። “ እንተስ ፣ የፖሊስ ሹም ተብለህ
ያገር ጸጥታም ሆነ የሰው ህይወትና ንብረት ለመጠበቅ የተቀመጥ

@OLDBOOKSPDF

ኸው ፤ በመንግስት ባለ ስልጣን ላይ ሴራ ሲቋዋጠርና የመንግስቱን ሀብት ሁለት ሰዎች ህዝብ አሳድመው ሲያስበዘብዙት ዝም ብለህ የምትመለከተው ፤ የተሰናዳ የመረጃ ድርጅት ሳይኖርህ ቀርቶ ነው። ከነሱ ጋር ያለህ ያድማ መሀላ እንዳይፈርስብህ አደለም ? አንተ ካድመኞች ጋር ባትሆን ፤ ያገሩ ጸጥታ በመበላሸት ላይ መሆኑንና የመንግስት ሀብት መበዝበዙን ፤ አንተ እያለህ በሌሎች በኩል መስማት ይገባኝ ኖሮዋል ? ”

“ ባድማው የሌለሁ ከመሆኔም ሌላ ፤ አድማ መደረጉንም ሆነ የመንግስት መሬት ለህዝብ መታደሉን በፍጹም አላውቅም ፤ የፖሊስነትን መብት ከተግባሩ ጋር ስቀበል ለመንግስቱ ታማኝ ፤ ለህዝቢ አገልጋይ ፤ እንድሆን የማልሁት ማላ ይድረስብኝ ! ” አሉ የፖሊሱ ሹም ፤ ተነስተው እግሮቻቸውን ደጋግመው እያጋጩ ፤ ቀጥ ብለው እንደ ቆሙ የወታደር ሰላምታ ሰጡና ።

“ እባክህ ዝም በልና ተቀመጥ ! ይህ . . . እንደ አቡነ ዘበሰማያት ሰርክ የምትደግመው ማላ ፤ እኔን ልታሳስትበት አትችልም ።

“ ማላ ሲደጋገም ‘ ዘየ ይሆናል ’ እንደሚሉት ፤ ማላ ዘየህ መሆኑን አውቃለሁ ! ” ሲሉ ቀኛዝማች ፤ የፖሊሱ ሹም እንደ ማፈር ብለው ተቀመጡ ። ወዲያው ተላላኪው ገብቶ ፤ ጥላሁን ፈይሳ መምጣቱን ድምጹን ከፍ አድርጎ ተናገረ ።

ጥላሁን ፤ “ ቀኛዝማች ይጠሩሀል ” ብሎ ተላላኪው ሲነግረው ፤ ኩርፊያቸው አልፎላቸው ስለ ስራው ሊያነጋግሩት ያስጠሩት መስሎት በጣም ደስ ብሎት ፤ የሚለምናቸው ነገር በዝቶ ፤ ሁሉም ቅደሚያ እንዲሰጠው ባንድ ላይ በራሱ ውስጥ እዬተንጋጋ ስለ መጣበት ፤ ማንቸውን አስቀድሞ ማናቸውን እንደሚያስከትል መምረጡ ቸግርት ፤ ገና ሳይወስን እቀኛዝማች ጽህፈት ቤት ደረሰ ። ያን እለት ጉባኤ መኖሩን እንኩዋ አላወቀም ነበር ።

“ ጥራው ” አሉ ቀኛዝማች በቁጣ ። ጥላሁን ገብቶ ፤ እንደ ልማዱ፤ እግሮቹን ገጥሞ በትህትና እጅ ከነሳ በሁዋላ ፤ ፈገግ እንዳለ ቀኝ እጁን አስቀድሞ ፤ ሰላምታ ለመስጠት ወደ ቀኛዝማች ሲሄድ ።

“ እዚያው ሁን ፤ ለሰላምታ አልጠራንህም ! ” አሉ ፤ ፊታቸው በቁጣ እንደ ተኮማተረ ፤ እጃቸውን አንስቶ እንዳይወስድባቸው የፈሩ ይመስል - በጠረጴዛው ላይ ካስቀመጡበት ቶሎ ሰብስበው ። ጥላሁን ጭራሽ ያላሰበው ነገር ድንገት ስለ መጣበት ፤ እንደ መደንገጥ አለና ተመልሶ አባዩ አጠገብ ሄዶ ከመቀመጡ ፤

@OLDBOOKSPDF

"ለምክር አልተጠራህም ፤ ለጥያቄ ነው ! ስለዚህ . . . ተነስና ለምጠይቅህ መልስልኝ" አሉ ቀኛዝማች ፣ ከቁጣቸው ብዛት የተነሳ፣ ብልግናቸውን እንኳ ማየት ተሳናቸው ።

"ምን አደረግሁ ጌታዬ ?" አለ ጥላሁን በርጋታ ።

"እዎ ፣ 'ጌታዬ !' ተንኮልህን ለመሸፈን እኔ ፊት ስትቀርብ እንዲህ እምሽክ ፣ ድቅቅ ብለህ 'ጌታዬ ፣ ጌታዬ !' እያልህ ፣ እስከ ዛሬ ያታለልኸኝ ይበቃሃል ! ህዝቡን ብቻ አይደለም ፤ እኔን እንኳ ተታልዬ የማላጠቀውን ፣ ከጠላት የማታለል ወጥመድ አምልጬ እዚህ የደረስሁትን ፣ እኔን እንኳ ፣ እስከ ዛሬ አታለልኸኝ ! ብቻ አጥ ማጅ ፣ የማታለል ወጥመዱን አጥምዶ የሚይዝ ፣ እስኪታወቅበት ድረስ ነው እንጂ ከታወቀበት በሁዋላ አይገዝም ! ባንተም አሁን ታው ቆብሀል ፤ አንተ . . . አታላይ !"

" እንዴ ! ኧረ አታላይ አይደለሁም ! እንኳንስ እኔ አታላይ ልሆን ፣ አታላዮችን እጠላለሁ ! ለምን ይሰድቡኛል ጌታዬ ? የሚሳ ደቡኮ ፣ ተራ ሰዎች ናቸው እንጂ ፣ እንደሰዎ ባለ ቦታ የተቀመጡ አይደሉም !" አለ ጥላሁን ፣ የቀኛዝማችን ስድብ ሲሰማ ፣ ድንጋጤው አልፎ ፣ እንደ ማንሰራራት እያለ ሄደና ።

"እኮ ! አታላይ አለመሆንህን አሁን ልታስረዳን አይደለም ?"

"አታላይ ነው" ብሎ የከሰሰኝ እንዳለ ከሳሼ ፣ ያለዚያም እር ስዎ ፣ 'አታላይ ነህ' ያሉበትን ምክንያት ይግለጹልኝ እንጂ !"

"እዚህ አገር በመጣህ ማግስት ፣ አጥፍተው የታሰሩትን እስረ ኞች ገንዘብ ከፍለህ ከመንግስት እስር ቤት አውጥተህ ፣ የግል ስራ ህን ካሰራህቸው በሁዋላ ለቀቅሀቸው ፤ ይህ መቸም በጉልበታቸው መጠቀምህ ሳይቀር ፣ ወዲያው ለተበደሉና ለተጠቁ ሁሉ ወገን መስለህ ለመታየትና ፣ ይህን አላዋቂ ህዝብ አታሎ በኛ ላይ ለማስነሳት መሆኑ የታወቀ ነው ! 'ይህን አላደረግሁም' ትላለህ ? ወይስ እንዲህ ያለው 'ማታለል አይደለም' ለትል ነው ?"

" በወንጀል ስራ ተፈርዶበት የታሰረ እስረኛ ፣ ገንዘብ ከፍዬ አስፈትቼ አላውቅም ። ተበድረው እዳቸውን መክፈል ስላቃታቸው የታሰሩትን እስረኞች ፣ ሰርተው እንዲከፍሉ ከባለስልጣኖች ጋር ተስ ማምተን አስፈትቻቸው ፣ ገንዘብ እዬከፈልሁ ማሰራቴ እሙን ነው ። ያንጊዜ ይህን በማድረጌ እርስዎም አመስግነውኝ ነበር ! አሁን ፣ ከሶስት አመት በሁዋላ ምን ወንጀል አደረገው ?" ቀኛዝማች ፣ ጥላሁን

@OLDBOOKSPDF

የጠዬቃቸውን እንዳልሰሙ ወደ ጸሀፊያቸው ዘወር ብለው ፣ “ ማመኑን ጻፍ ” አሉና አሁንም ጥያቄያቸውን ቀጠሉ ።

“ አንተና ሚስትህ ቃልቾች ነን እያላችሁ ፣ ህዝቡን እያታለላችሁ ፣ ሌሊት ሌሊት እቤታችሁ ስታዘፍኑ ማደራችሁስ ፣ እውነት አደለም ? ”

“ ምነው ቀኛዝማች ! እንኩዋንስ እኛ ፣ ‘ ቃልቾች ነን ’ ልንል ቃልቾችን እንደምንነቅፍና ፣ በቃልቾች ማመን ከንቱ መሆኑን ለሰው ሁሉ እንደምናስተምር እርስዎም ያውቃሉ ! ብቻ ከዚህ አገር ህዝብ የሚበዛው ፣ ‘ ከቃልቻ በቀር የታመመ ለማዳን የሚችል አለ ’ ብሎ ስለማያምንና ፣ እኛ በሀኪም መድሀኒት ብዙ ሰው ስናድን ስለሚያይ ፣ ቃልቾች ናቸው እያለ አሰበሱ መነጋገሩ እውነት ነው ። ነገር ግን ህዝቡ ፣ ‘ ቃልቾች ናቸው ’ እያለ ቢያወራ እኛ ተቀበልነው ማለት አደለም ! ”

“ ቃልቾች ነን ብላችሁዋል ” ብዬ ብጠይቀው ፣ ህዝቡ ይለናል ፤ እውነት ነው ’ ማለቱን ፣ ማመኑን ጻፍ ሲሉ ቀኛዝማች ፣ ወደ ጸሀፊው መለስ ብለው ፣ አባዬ ምንም እንኩዋ ሳቁን ለማገድ ቢሞክር አልችል ብሎ ሳቀ ፤ ሌሎች አባሎች ግን ፣ መሳቅ ቢያምራቸውም ቀኛዝማችን በመፍራት ፣ እንገታቸውን ደፍተው መሬት መሬት እያዩ ዝም አሉ ። ቀኛዝማች ከንፈሮቻቸውና ጉንጮቻቸው እዬተንቀጠቀጡ፣ አሳዬን አይናቸውን ከፍና ዝቅ አድርገው ፣ ባይን ግልምጫ ሰደቡና ወደ ጥሳሁን ተመልሰው ፣

“ የመንግስቱ መስሪያ ቤትና ያገረገዙ ቤትም ፣ አጥርም ፣ ሲፈርስ ህዝቡ እንዲሰራ ቢታዘዝ ፣ ‘ ግብር የሚገብር ህዝብ የጉልበት ስራ መስራት የለበትም ’ እያልህ ፣ እዬሰበክህ እሳድመህ መከልከልህና የራስህን ቤት ማሰራትህስ እውነት አደለም ? ትክዳለህ ? ” አሉ ።

“ እንኩዋንስ ህዝብ ሰብስቤ ላሳድም ፣ አሁን እርስዎ ‘ አልህ ’ ያሉትን ለርስዎ ፣ ለራስዎ ካልሆነ ፣ ላንድ ሌላ ሰው ፣ ‘ ሲናገር ሰምቻለሁ ’ የሚል ቢገኝ ልቀጣ ! ለርስዎ ብቻ ፣ ‘ ግብር የሚገብር ባላገር በትእዛዝ የጉልበት ስራ ማሰራት በህግ የተከለከለ ስለሆነ ለከሳሽ ፣ ለወቃሽ እንዳይመቹ ቢቀርብዎ ይሻላል ’ እያልሁ ለብቻዎ ብዙ ጊዜ መንገሬ እሙን ነው ! ስለራሴ ቤት ማሰራት የሆነ እንደ ሆነ ያንድ ሰው ጉልበት ፣ አንድ ቀን እንኩዋ ፣ ‘ ያለዋጋ አልፎብሀል ’ ብሎ ሰይጣን አይመሰክርብኝም ! ”

@OLDBOOKSPDF

"ህ ! ያው አደለም ? ምን ልዩነት አለው ? በል ጽፍ ! ልብ አርግ ፣ እንዴት አድርገህ እንደ ጻፍኸው ሁዋላ ታሳዩኛለህ !" አሉ ቀኛዝማች ፣ ጠቋሚ ጣታቸውን ወደ ጸሀፊው ሳይና ታች እያወለበለቡ ።

"እሺ ጌታዬ ፣ እሺ" አለ ጸሀፊውም ብድግ ብሎ እየደጋገመ እጅ ነሳና ።

"ከመንግስት ፣ 'አምስት ጋሻ ነው' ብለህ ሀያ ጋሻ መሬት ከወሰድህ በሁዋላ ፣ አንድ ጋሻ ለራስህ አስቀርተህ ፣ አስራ ዘጠኙን ጋሻ የመንግስት መሬት ለሸኮ ፣ ለመሰንጎና ለባጣ ማከፋፈልህስ፣ አሰት ነው፣ በመንግስት ሀብት እንትኑ ልትወደድና፣ህዝብ አሳድመህ እኛን ልታስጠላ ፣ ይህን ማድረግህ እውነት አደለም?" አሉ ቀኛዝማች፣ ጸሀፊውን ካስፈራሩ በሁዋላ እንደ ገና ወደ ጥላሁን ተመልሰው ። ጥላሁን መልስ አጥቶ ሳይሆን ፣ ስለ ገረመው ብቻ አንገቱን ደፍቶ መሬት መሬት እያዩ ትንሽ ዝም ብሎ ስለቆዩ ፣ ቀኛዝማች የሚመልሰው ያጣ መስሎዋቸው ፣ ደስ አላቸውና ፣

"መልስልኝ እንጂ !" አሉ ከባጥ በላይ ጮኸው ።

"በዚህ አገር ጋሻ መሬት የሚባለው ሁሉ ፣ እንዲሁ በነሲብ እንጂ በትክክለኛ መለኪያ የተለካ አለመሆኑን ፣ ከኔ ይልቅ እርስዎ ያውቁታል ። ለኔም ወዳጄ ገዝቶ የሰጠኝ አምስት ጋሻ መሬት ፣ በሁዋላ በቀያሽ ሲለካ ስለ ተረፈ ፣ እኔ ለርሼ ልጠቀምበት የምችለውን ለራሴ አስቀርቼ ፣ ለርሼ የማልጠቀምበትን ፣ 'ለቤት መስሪያና ለጉዋሮ ጎመን መዝሪያ እንኳ ቢሆናቸው' ብዬ ፣ ለጥንት ባለርስቶች ትንሽ ማከፋፈሌ እውነት ነው ።"

"ለጥንት ባለርስቶችኽ? የጥንት ባለርስት ማነው ? መንግስት አደለም ? ከመንግስት አደለም 'ገዛሁ' የምትለውን?"

"የዚህ አገር የጥንት ባለርስቶች ጣማዎች ፣ ሸኮዎች ፣ መሰንጎዎችና ግሚራዎች ናቸው!" አለ ጥላሁን ፣ ከባላምባራስ ጉዳታ ራሳ የተማረውን እሱም በፈንታው ለቀኛዝማች ለማስተማር ።

"ኧረ የንብረል ያለህ ! ደሞ፣ደሞ ጣሞችና... እነዚህ አሁን ያልካቸው ሁሉ ካንዳንድ ባላባቶች በቀር ፣ ከመቸ ወዲህ ነው ባለርስቶች የሆኑ? ሆ ! ሆ! አይሰማ ጉድኮ የለም ፣ አባካችሁ! ካባቶቻችንም ሆነ ከሌሎች ፣ ያገሩን ስራት ከሚያውቁ ሽማግሌዎች፣ስለዚህ አገር ስራት ስንሰማ ኖረናል! ብቻ ከዛሬ በቀር የዚህን . . . አሁን ያላቸውን ሰዎች ባለርስትነት

ስምተን እናወቅም!" አሉ ቀኛዝማች ጥላሁንን ትተው ፤ በመገረም ለጉባኤ የተቀመጡትን እያስተዋሉ እያዩ።

"ይቅርታ ያድርጉልኝና ቀኛዝማች፣ የርስዎም ሆኑ የሌሎች አባቶችና እያት ቅድመ አያቶች ሁሉ ፤ ከሌሎች ክፍሎች እዚህ ሲመጡ መሬቱን ባዶ አስገኙትም! ግሚራዎችና ጫማዎች ፤ ሸኮዎችና መዠንገሮች ነበሩበት ! በዚያ ጊዜ መሬቱ ባገሩ ህዝብ ሁሉ የጋራ ሀብት ነበር! እንዚህ አሁን እርስዎ ፤ 'ባላባቶች' የሚሉዋቸው እምንታቸውን አጉድለው አደራቸውን በልተው ፤ እንዲጠብቁና እንዲያስተዳድሩ ፤ ህዝቡ ለተቀበሉት መሬት ባለቤቶች መስለው ፤ ሁኖላ ከሌላ ክፍል ከመጡት ጋር ተከፋፍለው ፤ የወንድሞቻቸውን ባለርስት ፤ ጠቅላላውን ህዝብ ፤ በገዛ አገሩ ማረፊያ የሌለው ስደተኛ እስኪያደርጉት ድረስ ፤ ይህ አሁን ማረፊያ ያጣ ሕዝብ ባለርስት በነበረ ጊዜ ሲጋራ ሀብቱ ፤ ለመሬቱ አስተዳዳሪዎች አድርጎ የመረጣቸው ፤ አገልጋዮች ነበሩ! ብቻ ፤ 'ያባት ሎሌ ጌታው ሲሞት የጌታው ልጅ ጌታ መሆን ያምረዋል!' እንደሚሉት ፤ የጥንት ሎሌዎች የጌቶቻቸውን ልጆች ርስት ነቅለው ፤ ካዲስ መጪዎች ጋር ተከፋፈሉት ! ይህ ነው እውነቱ ፤ ቀኛዝማች! ታዲያ መሬት ተጠናቶ ለትሰራ ፤ ግና በርግብዋ የተተከለው ህዝብ ተነቅሎ ፤ መቆሚያ ፤ መቀመጫ አጥቶ ሲንገዋለል ፤ ቅናንት መጥቼ ከወሰድሁበት ብዙ መሬት፣ ልሰራው የማልችለውን ትንሽ ቁርሺ ለማረፊያ ያክል ብመልስስት ፤ ይህ ወንጀል ሆኖ ሊያስከስሰኝ ነው? ይህ ፤ 'ወንጀል' ተብሎ የሚያስከስስ ከሆነ ፤ ይህን ወንጀል ሰርቻለሁ!" አለ ጥላሁን ፤ በለዘብታ የጀመረውን ወደ መጨረሻው ሲያስበው ትንሽ እንደ መበሳጨት ብሎ።

"ሰምታችሁልኛል? 'ወንጀል ሰርቻለሁ' ሲል ሰምታችሁ የለ ? በል! 'ወንጀል ሰርቻለሁ' ማለቱን ጻፍ 'አምነት ጋኛ' ነው ብሎ ሆዬ ጋሻ መሬት ከመንግስት እያሎ ወስዶ፣ለህዝብ ማከፋፈሉን ማመኑንም ጻፍ!" አሉ ቀኛዝማች ፤ ጥላሁን ፤ "ወንጀል ሰርቻለሁ" ማለቱን የጉባኤው አባሎችም ፤ ጸሀፊውም ፤ ልብ እንዲያደርጉ አጥብቀው እያስጠነቀቁ። "እረ ለመሆኑ"አሉ ከዚያ ቀጠሉና፤ "እረ ለመሆኑ ማነህ አንተ ? ማን ሆነህ ነው ? ከማን በተሰጠህ ስልጣን ነው የመንግስት መሬት ወስደህ ለህዝብ አከፋፋይ የሆንህ ? 'መሬቱ የህዝብ እንጂ የመንግስት አይደለም' ብለህ በኔ በመንግስቱ ሹም ፊት ለመናገር የደፈርህ ፤ ማን አለሁልህ ቢልህ ነው? በዚህ ድፍረትህ ብቻ አሁን . . . እግር ከወርች አቀፈድድህ ነበር! ብቻ ጌቴ አንተን አይለሁም ፤ የዛሬን ግድ የለም አሉ ፍሀለሁ!"

@OLDBOOKSPDF

“ እጅ ንሳ! አቶ ጥላሁን እጅ አትነሳም ? እልሀ ምን ያደርግልሀል!”አሉ ዳኛው ከተቀመጡበት ተነስተው ። እሳቸው መቸም የቀኛዝማችን ሀይለኛነት ስለሚያውቁና ፣ ለጥላሁን ስላዘኑ ፣ ከፉ እንዳይደርስበት ሰግተው ነው ። ጥላሁን ግን እንኳንስ የመከሩትን ሊሰማ ፣ እንዲያውም በንቀት አይን አያቸው ፣ የታች ከንፈሩን ሲያስረዝማቸው ስለ ተመለከቱ፥ “ግደሉኝ” እንደ ማለት ትከሻዎቻቸውን ወደላይ ገፍተው ዝም አሉ ።

“የመጨረሻ ቃሌን እነግርሀለሁ ፣ ልብ አድርገህ ስማ!” አሉ ቀኛዝማች ፣ ግንባራቸውን ኩስትር አድርገው ጥላሁንን እየተመለከቱ ። “ልብ አድርገህ አዳምጥ ! እስከ ዛሬ ያጠፋኸውን ሁሉ ፣ ህዝቡን ብቻ ሳይሆን የመንግስቱን ባለስልጣኖች ጭምር ማታለልህን፥ ህዝብ እያሳደምህ ሽፍታ ማወከህን ፣ ስልጣን መጋፋትህንና፥ የመንግስት መሬት ለህዝብ ማከፋፈልህን ፣ ይህን ሁሉ ፣ በጉባኤ ፊት አምነህ ተጸጽተሃል ።

ከዛሬ ቀደም ፣ እቤቴ እየጠራሁ ብዙ ጊዜ ምክርም ፣ ማስጠንቀቂያም ስጥቼህ አልሰማ ስላልህ፥ ዛሬ በጉባኤ ፊት የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እሰጥሀለሁ ። ከንግዲህ ውርድ ከራሴ ነው ! እስካሁን ያ ፣ ወዳጄ ፣ ያ ፣ ማነው ስሙ ? አቶ . . . ውብቱ ! አዎ ውብቱ በዛብህ ! እሱ ‘አደራ’ ስላለኝ ፣ ምንም እንኳ ተንኮለኛነትህን ከመጣህበት ቀን ጀምሬ ባውቅ ፣ አደራ ያወጣሁ መስሎኝ ፣ አንተም ፣ ሚሽትህም ፣ እንደ ቤተሰቤ ሁሉ እኔ ብኖርም ፣ ባልኖርም ፣ እቤቴ እንደ እንደ ልባችሁ እንድትገቡ ፣ እንድትወጡ ፈቅጄ ፣ በኔ ላይ የምትሰራውን ሁሉ እያወቅሁ ችዬ ኖርሁ ። እኔ በባላደራነቴ አንተን ለመርዳት ፣ አንተ በውለታ ቢሱነትህ እኔን ለመጉዳት ፣ እየሰራን ሰባት አመት ኖርን! እኔ እንገረገም እዚህ ተቀምጬ፣ እንደሌለሁ ቆጥረኸኝ ፣ ‘ያገረገኘ ስራ ልስራ’ ትል ጀመር ! ለኔ ከዚህ የበለጠ ውርደት የለም ! እንኳንስ በህይወቴ እያለሁ ፣ ስሞት ሬሳዬ የሚጸየፈው ውርደት ነው ! ሹሬ ለመሆኑ ፣ ይህ ፣ ‘እንዲያው እንዲሁ ልውሰድብህ ’ የምትለኝ ስልጣን ፣ ወድቆ የተገኘ መሰለህ ? አምስት አመት ሙሉ ጠበንጃየን አቅፌ ዠናሬን ከወገቤ ሳለይ ፣ አምስት አመት ሙሉ ከንቅልፍ ተለይቼ ፣ የቀንና የሌቱን ልዩነት ረስቼ፥ ከብርቱ ጠላት ጋር እየታገልሁ የህይሉን ማእበል ለማገድ ስለቻልሁ ፣ በዚህ ሁሉ ምክንያት . . . ያገኘሁትኮ ነው ! በጣም ትልቅ ነው ። ሀሁሁ ቀላል ነገር አይምሰልህ አቶ እንትና ! ስለዚህ ” አሉ ቀኛዝማች ድንገት ካሽሙር ፊጊ ወደ ቋጣ ሲለወጡ በፊታቸው እየታዩ ። “ ስለዚህ ለወደፊቱ ፣ በስልጣኔ እንዳትደርስ ! ያገሩን ህዝብ ኑሮ

@OLDBOOKSPDF

ለማሻሻል የሚሰራ ስራ ቢኖር ፣ አሳቢው እኔ ነኝ ፤ አንተ አደለህም ። እንተና እቶ አሳዬ ከመንግስት ከወሰዳችሁት መሬት ሰርታችሁ ልትጠቀሙበት ፣ ለራሳችሁ ያስቀራችሁትን የሚንካባችሁ የለም ። ትርፍ ነው ብላችሁ ለሌሎች ያስተላለፋችሁት ግን ፣ ወደ ቀድሞ ባለንብረቱ፣ ወደ መንግስት ይመለሳል ። በዚህ አሳብ ሁላችሁ ትስማሙ የለም?"አሉ አባሎቹን አንድ ባንድ እያዩ ።

" እንስማማለን ፤ ጌታዩ የተናገሩት ትክክል ነው ። መንግስት የሸጠላቸው በቁጥር የተወሰነ ጋሻ ከሆነ ፣ ከዚያ የተረፈው ወደ ባለንብረቱ ፣ ወደመንግስት መመለስ አንጂ ፣ ወደሌላ መተላለፍ የለበትም" አሉ ዳኛው፣ ብድግ ብለው ።

"እንስማማለን" አሉ የፖሊሱ ሹምም እንዲሁ ብድግ ብለው ። አሳዬ ብቻ ዝም አለ ።

"አንተስ አትስማማም?" አሉ ቀኛዝማች ፣ አሳዬን የጎድን እያዩ ።

"ገና አልወሰንሁም ፤ ስለዚህ ድምጽ አልሰጥም " አለ አሳዬ ።

"ይሄዋ! አላደምሁም ስትል ፣ ማደምህን ምስክር ፍለጋ ሳንሄድ ፣ አንተ ራስህ መሰከርህ! "

"የለም ቀኛዝማች ፣ እኔ አላደምሁም ። እንኩዋንስ እኔ ፣ ሌላም ያደመብዎ ሰው ያለ አይመስለኝም ። ብቻ የሚያሳዝነው ፣ እርስዎ ክርስዎ የተለዩ አሳብ ያለው ሁሉ ፣ የሚጠላዎና የሚያድምብዎ እዬመሰለዎ ሳያስፈልግ ራስዎን ያስቸግራሉ ። ስለ ድምጽ መስጠቱ የሆነ እንደሆነ ፣ ዛሬ የማያስቆጣው ነገር ሁሉ ሲያስቆጣዎ ስለ ተመለከትሁ ፣ እንዲህ ባለው ሁኔታ ፣ አሁን የውነተኛ አሳቤን የገለጽሁ እንደሆነ ያስቀይምዎ ይሆናልና ፣ ይህ ዛሬ የማየው የቁጣ ትኩሳት እስኪበርድ ፣ 'ባሳድረው ይሻል ይሆናል' ብዬ ነው እንጂ ፣ ለስዎ እንደ መሰለዎ ሌላ ምክናያት ኖሮኝ አደለም ። ስለዚህ . . . የኔን አሳብ አሁን ማወቁ ደስ የሚያሰኝዎ ከሆነ፣ እገልጽልዎታለሁ። በወሰኑት ውሳኔ አልስማማም። ምክናያቱም ይህ መሬት ከመንግስት በገንዘባችን ፣ የገዛነው ርስታችን ነው ። ሁለተኛ ስለ ትርፍ መሬት በወጣው አዋጅ ፣ አንድ ሰው 'ይዞታዩ ይህን ያክል ነው' ብሎ በቅን ልቡና አምኖ ሲኖር ፣ ይዞታው ባዲሱ ቀላድ ሲለካ ተርፎ ቢገኝ፣ ትርፉን በተለይ አስመዝግቦ እንዲገብርበት እንጂ እንዳይወሰድበት አዋጁ ጠብቆለታል ። ስለዚህ እኔ ከመንግስት የገዛሁት አንድ ጋሻ መሬትም ሆነ የአቶ ጥላሁን አምስት ጋሻ ፣ ሁዋላ ባዲሱ ቀላድ ሲለካ ከተገኘው ትርፍ መሬት ጋር ፣ አዋጁ

@OLDBOOKSPDF

እንደሚያዘው ፤ የገበርንበት ርስታችን ነው ። ርስት ማለትም የሚሸጥ ፤ የሚለወጥ ፤ ወይም እንደ ባለርስቱ ፈቃድ በስጦታ ለሌላ የሚተላለፍ ነው ። በዚህ ምክንያት ነው ፤ 'ርስታችሁን ለሰው የምትሰጡ ከሆናችሁ መንግስት ይወስድባችሁዋል ' ብለው በወሰኑት ውሳኔ አልስማማበትም ያልሁ ” አለ አሳዬ ።

ብዙ ጊዜ ፤ በጉባኤም ሆነ በሌላ ቦታ ፤ አሳዬ ሲናገር ፤ ስለ አገር ግዛት ሚኒስቴር ፤ ስለ ገንዘብ ሚኒስቴር ስለ ሌላውም እንዲሁ የወጣ ወን ህግ ፤ አዋጅና ትእዛዝ ከነ አንቀጹና ንኡስ አንቀጹ ፤ አንዳንድ ጊዜም የሌለውን እየጠቀሰ እየተናገረ ፤ አላዋቂነታቸውን ስለሚያስገባ ቸው ፤ ቀኛዝማች ከሌሎቹ ሁሉ መናፉት ብቻ ሳይሆን ይጠሉታል ።

“በል እንግዲህ የምታደርገውን እናያለን! ሀ ! ብቻየን የወሰንሁት አይደል! በጉባኤ የተወሰነውኮ ነው!” አሉ ቀኛዝማች ።

“ቀኛዝማች ” አለ ጥላሁን ፤ የልቡን ጭንቀት እንደ ጥሩ መስተ ዋት ወለል አድርጎ በሚያሳይ የተጨነቀ ፊት ። “አሁን እዩጠዩቁኝ ስመልስ ፤ እኔ የመለስሁት ቀርቶ እርስዎ እንዲጸፍ የፈለጉት መጸፉን ሳላስተውል ቀርቼ እንዳይመስልዎ ዝም ብዩ' ያስጸፍሁት ፤ የፈለጉ ትን ቢያስጽፉ ለኔ ምንም ልዩነት ስለሌለው ነው ! ”

“አንተ የመለስኸው ቀርቶ እኔ እንዲጸፍ የፈለግሁትና ያስጸፍሁት ምንድነው ? የምትናገረውን እያስተዋልህ ተናገር ፤ ሁዋላ እንዳትጸጸት! እኔን አባይ ማለትህኮ ነው!”አሉ ቀኛዝማች በብርቱ ቁጣ ።

“ህዝብ አታልያለሁ ፤ ህዝብ አሳድሜያለሁ ፤ ቃልቻ ነኝ ፤ ስልጣን ተጋፍቻለሁ ፤ የመንግስት መሬት አታልዩ ወስጄ ለህዝብ አካፍያለሁ አላሉሁም ። የተጻፈው ግን ይህ ነው! ብቻ በዚህ አልተቸገርሁም ። ይህ የተቆጠረው ጥፋትና ሌላ ሌላም ፤ የኔን ስምና መልክ የሚያከፉ ጥፋት ታስቦ ተጨምሮበት ፤ ሁሉንም እምነህ ፈርም ቢሉኝ ፤ እምና መፈረሜ ደስ የሚያሰኝዎ ከሆነና ፤ ቁጣዎን አብርዶ ነገሩን ሁሉ በውነተኛ መልኩ እንዲያዩ የሚያደርግዎ ከሆነ እፈርማለሁ ፤ ምንም ቅር አይለኝም ! እኔ የተቸገርሁበት ሌላ ነው ። እኔ የተቸገርሁበትና በቁጣ ተገፍተው የወሰ ኑትን ውሳኔ እንዲያሻሽሉ የምለምንዎ ፤ ባለቤቴና እኔ ሶስት አመት የደ ከምንበትና ህዝቡን በተስፋ ያደከምንበት ስራ ከንቱ ሆኖ ፤ ፍሬ የሌለው ድካም ብቻ ሆኖ እንዳይቀር ነው !

“ምናልባት ልጆች እንደ መሆናችን ከመቻከላችንም ሌላ ፤ ያገር ግዛ ትን ያስተዳደር ስነ-ስራት ባለማወቃችን ፤ ይልቁንም እርስዎ ተለይተውን ብዙ በመቆዩትዎ ፤ ፈቃድ እዩጠዩቅን ልናደርገው ይገባን የነበረውን ሳን

@OLDBOOKSPDF

ጠዩቅ በባለስልጣኖች እግካይነ ልናደርገው የሚገባንን እኛ በቀጥታ፣ ማድረጋችን ጥፋት ሆኖ ሊቆጠር ይችል ይሆናል ፤ እሺ ጥፋት ነው፤ ነገር ግን በትንሽ መድሀኒት ሰ_ን ሲችል በበሽታ የሚሰቃዩውን ፣ ሰርቶ ሊበላና ሊለብስ ሲችል ተርቦና ተራቁቶ የሚኖረውን ፣ በትንሽ ትምህርትና ምክር መጠነኛ የሰው ኑሮ መኖር ሲችል ሰው ሊኖርበት በማይገባ ሁኔታ የሚኖረውን ህዝብ ስናይ ፣ ‘ቶሎ አገልግሎታችንን፣ ርዳ ታችንንና ምክራችንን ብንሰጥ ፣ የበሽታውን፣ የራቡን ፣ የርቅናውንና የጉስ ቁልናውን እድሜ በዚያው መጠን እናሳጥረዋለን ’ ብለን ፣ ቸኩለን ነው እንጂ ፣ ስልጣን ለመጋፋት ፣ ወይም ሌኛ ተወደን ባለስልጣኖችን ለማስጠ ላት ባሳባችን ተጸንሶ እንደማያውቅ ይመኑኝ ፣ ቀኛዝማች ። እኔ እንኳን ንስ የሰው ስልጣን ፍለጋ ልሄድ ፣ ስልጣን አመራት ወድቆ ባገኘው አላነ ሳውም ! ስለዚህ እባክዎ ፣ ይህ የጀመርነው ስራ ሳይለመድ ቢቋረጥ እንዳይጠፋ ፣ ቢሆን ለሶስት ፣ ያለዚያም ለሁለት አመት እንድንቀጥል ይፍቀዱልንና ፣ እስከዚያ ሕዝቡ ስለሚለምደው ፣ ስለሚጥመው ፣ ወደ ሁዋላ እንደማይመለስ ፣ ስራችን እንደማይጠፋ አምነን ፣ ደስ እያለን ፣ የማንፈለግ ከሆነ እን. . . ሄዳለን ” አለ ልቅሶ መጥቶበት ባሻከረ ድምጽ ።

“ደግሞስ ቀኛዝማች” አለ ቀጠለና ። “ደግሞስ እርግጥ ፣ ስነ-ስራ ትና ትክክለኛ መንገድ ተከትሎ ወደ ታቀደ ፣ መልካም ግብ መድረስ መቻም ከሁሉ እንደሚመረጥ የታወቀ ነው ! ነገር ግን ስነ-ስራትና ትክክ ለኛ መንገድ ካልተከተልሁ አልንቀሳቀስም” ብሎ በቆሙበት ከመቅረት ወይም በመንገድ ከማደር ፣ መድረስ ከተቻለ ፣ በማናቸውም መንገድ ሄዶ እታቀደው መልካም ግብ መድረስ አይሻልም ? ይሻላልክ ! በውነት ይሻላል ፣ ቀኛዝማች ። እንደኔ እንደኔ ፣ መልካም ግብን ፣ መልካም አላ ማን ፣ ለስነ-ስራት መለወጥ ፣ ወርቁን ለመያዣው ጥልፍ ከረጢት እንደ መለወጥ ያለ ፣ የሚያከስር ለውጥ ነው ! እዎ ! የግዛቱን ያስተዳደር ስነ -ስራት አለመከተላችን እንደ ጉድለት ተቆጥሮብን ይሆናል ። ነገር ግን መድረሻ ግብ ፣ የሌለው ረዥም ስነ-ስራት ተከትሎ ሲሄዱ መኖር ፣ ከድካም በቀር ትርፍ የሌለው ፣ እንዲያው ደክሞ መና መሆኑንና ፣ ያለስነ- ስራት ፣ ባቋዋራጭ የደረስንበት መልካም ግብ ፣ የመንግስቱን ገንዘብም ሆነ የናንተን የባለስልጣኖችን ጊዜ ፣ ጉልበትና አሳብ ፣ ከመቆጠብ በቀር ሌላ ጉድለት የሌለው መሆኑን ተረድተው ይቅርታ ቢያደርጉልን ምናለ? በውነት ቀኛዝማች ! በባለቤቱና በኔ መሳሪያነት ባጭር ጊዜ ፣ በሶስት አመት ብቻ በህዝቡ ህብረት በግዛትዎ ውስጥ የተሰራው ስራ ፣ በስነ- ስራት በኩል የጎደለ ቢኖር እንኳ ፣ እንዲያ ባለው ጉድለት ይቅርታ ሊያስደርግ እንደሚችል ፣ ቅን ህሊና ሁሉ የሚፈርደው ነው ።

@OLDBOOKSPDF

"በዩመንጀሩ ተቀፍሮ ፤ ዙሪያውን በሳር ድርፍ እዩተደደቀ የተሰራው ነዋሪ የውሀ ማጠራቀሚያ ግድብ ፤ ከብዙ ወንዞች ብዙ ተራሮች እዩዞሩና ብዙ ሸለቆዎች እዩተሻገሩ ፤ ያለማቋዋረጥ ውሀ ወደ ማጠራቀሚያዎቹ የሚያጎርፋት ፤ ካገሩ ጫካ እንጨት ባገሩ ሰው ብልሀትና ጉልበት የተሰሩት ብዙ የገንዳ ቡዋንቡዋዎች ፣ በዩመንደሩ በሀብረት የተሰሩት እድሜና ምችት ያላቸው ቤቶች ፤ ራብን ለመከላከል ሀዝቡ በደቦ እዩሰራ ለያንዳንዱ ቤተሰብ ፤ በጋ ከክረምት የሚበላ አትክልት እንዲኖረው ተሰጥቶ የተለመደው ትምርት ፤ ባለቤቱና እኔ ከምንሰጠው መጠነኛ የህክምና ርዳታ ጋር በምንሰጠው ምክር ህዝቡ ተባብሮ በሽታን መከላከል ስለ ለመደ ፤ ዛሬ ከየኪ በሽታና ያለጊዜ ሞትመጥፋት ፤ ይህን ይህን የመሰለው ሁሉ ፤ እንዲያው በጠቅላላው ህዝቡ በሶስት አመት ውስጥ በህብረት ራሱን መርዳት ተምሮ ፤ እስከ ዛሬ ሶስት አመት ከነበረበት ተራምዶ ። ዘሎ ፤ አሁን በደረሰበት በጣም የተሻሻለ ደረጃ መገኘት ፤ ይህ ሁሉኮ ትንሽ አደለም ፣ ቶኛዝማች ! ይህ መንግስትን አንድ ቀይ ሳንቲም ሳያስወጣ የተሰራው ስራ ሁሉኮ በሌላ አገር ብዙ የመንግስት ገንዘብና የብዙ አዋቂዎች ጉልበትም ፤ አሳብም ጠፍቶበት ፤ እንዲህ ባለ አጭር ጊዜ ሊፈጸም የሚችል አደለም ! ከዚህ ሌላ ደግሞ ፤ ከዚህ ሁሉ በላይ ይህ የህብረት ስራ ፤ ይህ የህዝብን ብልሀትና ጉልበት ባንድ ላይ አስተባብሮ መስራት የራብ ፤ የበሽታና የጠቅላላ ድህነት ፍቱን መድሀኒት መሆኑና ለዚህም መንገድ መሪው ፤ አስተማሪው ፤ የኪ መሆኑ ደስ ሊያሰኝዎ እንጂ ሊያሳዝንዎ አይገባምኮ ! እንዲህ ባለው ፤ በኛ መሳሪያነት ለተሰራ መልካም ስራ ፤ ፈቃድዎ ሆኖ ባለቤት ቢሆኑ ፤ የሚያኮራ እንጂ የሚያዋርድ አደለምኮ ! ለዚህ ስራ ባለቤት ሆነው ፤ ከጎሬና ካዲስ አበባ ከፍተኛ ባለስልጣኖችን ጋብዘው ቢያስጎበኙ የሚያስመሰግንዎና ከፍ ላለ ሹመት የሚያሳጭዎ ነውኮ ! ስለዚህ . . . እባክዎ ቀኛዝማች ፤ የኛን ጥቃቅን ጉድለት ትተው ለርስዎና ለሚያስተዳድሩት ህዝብ የሚጠቅም ስራችንን ይመልከቱ ! እባክዎ እኛን እንደ ጥፋተኞች ቆጥረው ቢቀዩሙን እንኩዋ ፤ ለህዝቡ የሚጠቅም ፤ መልካም ስራችንን በኛ አይን ተመልከተው አይበድሉ ! እባክዎ በኛ ጥፋት ህዝቡን አይቅጡ !"

"በል እንግዲህ በቃህ ዝም በል ፤ እዚህ የተሰበሰብነው ለስራ ነው እንጂ ያንተን ማታለያ ፤ ያንተን ማባበያ ስብከት ለመስማት አደለም ! ህዝቡ እንዳንተ ያለውን አታላይ ተከትሎ ከሚጠቀም ካንተ በመለየቱ የሚደርስበት ጉዳት አይኖርም እንጂ ፤ ካለ እንዲያ ያለው

@OLDBOOKSPDF

ጉዳት ይሻለዋል ! እንዳንት ያለ አሳሳች ፣ እንዳንት ያለ አታላይ የሚ መራበት መንገድ ለጊዜው የሚጠቅምና ቀና መስሎ቞ ቢታይ መጨረሻ የሚጎዳ ፣ ወደ ጥፋት የሚመራ ነው ። አታላይ ፣ አሳሳች የሚባለውም ለዚህ ነው ! በቃህ እንግዲህ ፤ እስካሁን ስራ ያስፈታኸኝ ይበቃሀል ! ትሰሙታላችሁ?" አሉ ቀኛዝማች ወደ ጉባኤው አባሎች ዘወር ብለው። "ስልጣንህን ለኔ መልቀቅህ የሚያኮራህ እንጂ የሚያዋርድ አደለም ፤ ስልጣንህን ንጥቄ የሰራሁትን መንግስት ቢያውቅ የበለጠ ሹመት ይሰጥሀል" ሲለኝ ልብ አድርጋችሁልኛል ? ሁሁሁሁ ! ወይው ጉድ ! በሰው ፊት ምን እንደሚያስከብርና ምን እንደሚያዋርድ ፣ በጌታ ፊት ምን እንደሚያስነቅፍና እንደሚያሸር ፣ ምን እንደሚያስመስግ ንና እንደሚያሾም የማላውቅ ፣ ትንሽ ህጻን አደረገኝ ! ስማ "ልንገርህ" አሉ እንደ ገና ወደ ጥላሁን ዘወር ብለው ። "ስማ ! ነፍስና ስጋው አብ ረው እያሉ ሚሽቱንና ስልጣኑን ሌላ ሲወስድበት ዝም ብሎ የሚያይ፣ ወኔ ያልተፈጠረበት ጅል" ተብሎ የሰው መሳቂያ ይሆናል እንጂ ፣ ልታሳምነኝ እንደ ሞከርኸው አይከበርም ! መንግስት የሰጠውን ስል ጣን ሌላ ሰው ነጥቆ ሲሰራበት ዝም ብሎ የሚመለከት ፣ 'አይችልም' ተብሎ ይሻራል እንጂ ፣ አንተ ልታሳምነኝ እንደ ፈለግኸው ለከፍ ተኛ ሹመት አይታጭም ! ስለዚህ . . . ቅድም እንዳልሁት ሳላውቅህ ያታለልኸኝ ፣ የደለልኸኝ ይበቃል ፤ አሁን አውቄሀለሁ ! ውሳኔያችን አይለወጥም ! እንዳትሳሳት ውሳኔውን እደግምልሃለሁ ፤ ልብ አድርግና ስማ !

1ኛ- ከንግዲህ ወዲያ ህዝብ እዬሰበሰብህ ግላደም ፣ መሰበክ ፣ መምከር ፣ ማስተማር የሚባል ነገር ሁሉ በጥብቅ ተከልክለሀል ። ህዝብ ለመሰበክ ፣ ለመምከር ፣ ለማስተማር ፣ ለማከም እንኳ ተሹ መህ ስላልመጣህ ፣ በዚህ ሁሉ የሚያገባህ ነገር የለም !

2ኛ- ከመንግስት ወስደህ ለህዝብ ያካፈልኸውን መሬት እንደ ወሰድህ ለመንግስት እንድትመልስ ተወስኖብሀል !

3ኛ- እነዚህን ሁለት ውሳኔዎች አክብረህ ፣ በተጨማሪ ቅድም እንዳልሁት በህዝብ ጉዳይና በሹም ስልጣን ሳትገባ ፣ የግል ጉዳይህን ብቻ እዬተከታተልህ አርፈህ ከተቀመጥህ ፣ ከመንግስት ወስደህ ለራ ስህ መጠቀሚያ ያስቀረኸውን ፣ አንድ ጋሻ መሬት እንደ ያዝህ እንድ ትቆይ ተፈቅዶልሀል !

4ኛ- እነዚህን ውሳኔዎች ተላልፈህ ፣ በህዝብ ጉዳይና በሹም ስል ጣን ገብተህ ፣ ወይም ያካፈልኸውን የመንግስት መሬት ባንድ ወር

@OLDBOOKSPDF

ውስጥ ሳትመለስ ዋርቴህ የተገኘህ እንደሆን ፣ የወንጀለኛ ቅጣት እንድትቀጣ ተወስኖብሀል ! ” አሉና ወደ ጸሀፊው ዞወር ብለው ፤ በቁጣ የቀላ አይናቸውን አፍጠው ፤ “ ልብ አድርግ ፤ ተጠንቅቀህ እንድት ጽፍ ! በሁዋላ አሳር ያገኝሀል ! ታሳፍኛለህ !” አሉ ። ወዲያው ወደ አባሎቹ ተመልሰው የሰብሰባው ፍጻሜ መሆኑን አስታወቁ ።

ጥላሁን ፤ አይኑን ሳያረግብ አጣራው ላይ ሰቅሎ ፤ ትንሽ ሲያስብ ቆይቶ ፤ “ ግሩም ነው ! ” አለ ፤ መጀመሪያ በለዘብታ ። ከዚያ ንግ ግሩን እየቀጠለ ሲሄድ ተሰፋ የቆረጡ ሰዎች ስሚታቸውን በሚገል ጹበት ምሬትና ግለት ስሚቱን እየገለጸ ። “ ግሩም ነው ! ቀኛዝማች ! ባለቤቴንና እኔን ፤ ራስዎን ሳይቀር ፤ ከሁላችንም የበለጠ ህዝቡን ግሩም አድርገው ጎዱ ። ማንን እንደ ጠቀሙ ግን በውነት አላውቅም ! መቸም ራስን ለመጥቀም ሌላን መጉዳት ፤ የሚመሰገን ባይሆንም የነ በረ ስለሆነ አያስገርምም ! ሳይጠቀሙ መጉዳት ግን ፤ እንዲያው ለመ ጉዳት ብሎ መጉዳት ፤ ከከፋት በቀር ሌላ ስም የሚገኝለት አይመ ስለኝም ! ተጠርቼ እዚህ ከገባሁ ጀምሮ እስካሁን እንደ ሰማሁዎ ፤ ከሁሉም እጅግ አስቆጥቶ በወሰኑት ውሳኔ ከኛም ይልቅ ህዝቡ ምን ያክል እንደ ተጎዳ እንዳያዩ ፤ ራስዎ የሚጠቀሙበትን እንኩዋ እን ዳያዩ ፤ አይንዎን የሸፈነው የስልጣንዎ ነገር ነው ! እኔ ስልጣንዎን ለመውሰድ የምሰራ መስዬ ታይቸዎ ነው ! ለመሆኑ እኔ እንዴት አድርጌ ነው ስልጣንዎን የምዎስድብዎ ? እኔ ተማሪው ከስዎ ከጀግ ናው ቅምቼ ? የለም ፤ በዚህ እስዎም ራስዎን አይጠረጥሩ ! እንግ ዲያ . . . ሰርቄ ?”

“ አዎ ፤ ሰርቀህ ! ሰርቀህ ! ” አሉ ቀኛዝማች እቁዋርጠው ። አባሎቹ ሁሉ የቀኛዝማችን ሁኔታ ሲያዩ ሳቁ ።

“ የለም ፤ ባያውቁ ነው ! ” አለ ጥላሁን ፤ አሁን በለዘብታ አደ ለም ፤ በምትታ ! “ ባያውቁ ነው ! ስልጣን ትልቅ ነው ! ስልጣን እንደኔ ያለ ሰው ሰርቆ ፤ በኪሱ ደብቆ ሊወስደው የሚችል አይደለም ! ስልጣን ለመልካም ስራና ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ትልቅ መሳሪያ ነው ! ብቻ ካልሰሩበት ፤ ወይም ለክፉ ስራ ካዋሉት ሌባ በስርቆት ሳይሆን ፤ የሰጠ በገሀድ መልሶ እንደሚወስደው የታወቀ ነው ! ስል ጣን ላሉበት ጊዜ መሳሪያ ነው እንጂ ፤ ላለፈ ስራ መታሰቢያ ሆኖ የሚሰጥ አደለም ። ስልጣን ላሉበት ጊዜ ለህዝብ አገልግሎት መሳሪያ ነው እንጂ ፤ ላለፈ ስራ ዋጋ ሆኖ ያንድ ወረዳ አገርና ህዝብ የግል ንብ ረት እንዲያደርጉበት የሚሰጥ አይደለም ! ለርስዎም በዚህ ወረዳ ላይ

@OLDBOOKSPDF

የተሰጠዎ ስልጣን ህዝቡን እንዲያገለግሉበት እንጂ ፣ ለርስዎ እንደ መሰለዎ ሳምስት አመት አርበኞንትዎና የግሚራን ህዝብ ፤ ‘ ሽፈተ’ ብለው በጅምላ ለመፍጀትዎ ዋጋ አለመሆኑ የታወቀ ነው ! ነገር ግን የሚያሳዝነው ቀኛዝማች ! እርስዎ ስልጣን የሚወዱትን ያክል ፣ ስል ጣን አብሮዎ ቢውል አብሮዎ የማያድር እዮመሰለዎ የሚባንኑትን ያክል ፣ ባህሪው ምን እንደሆነና ለምን እንደሚያገለግል አለማወቅዎ ነው ! የስልጣን ባህሪ ምን እንደ ሆነና ለምን እንደሚያገለግል ጭራሽ አያውቁም ! ”

“ ሲሰድቡኝ ትሰማላችሁ ? ሰደበኝኮ ! ዝም በል በቃህ አንተ ! ሁዋላ አሳር ያገኝሀል ! ” አሉ ቀኛዝማች በብርቱ ቁጣ ፣ ለመነሳት እዮቃጡ ።

“ ዝም ይበሉ እርስዎ ! ” አለ ጥላሁን ፣ እሱም እንዲሁ በቁጣ ግሎ እዮተንቀጠቀጠ ። “ እኔ አልሰደብሁዎም ፤ ብቻ ዝም ይበሉና ያናግሩኝ ፤ መጨረሻው ነው ፤ እንግዲህ እንገናኝም ፤ መጨረሻው ነው ! አዎ ፤ የስልጣንን ባህሪና አገልግሎት አያውቁም ! የስልጣንን ባህሪና አገልግሎት እንደማያውቁ ፣ ባለቤቴና እኔ ማን እንደሆንና ለምን እዚህ እንደ መጣንም አያውቁ ! እኔ ልንገርዎ ቀኛዝማች ። ቡና እዮለቀምን ሽጠን ብር ለመሰብሰብ አልመጣንም ! ወዲህ ስን መጣ ፣ የለት ራት ብቻ ካላጣን ፣ አይነተኛ አላማችን አድርገነው የመ ጣን ፣ የወገኖቻችንን አገልግሎት ነው ። ወዲህ ስንመጣ ፣ ይህን ያገ ኘነውን ያክል ትንሽ ትምርት ወገኖቻችን ሳይተርፋቸው ፣ እዮተቸገሩ ለዚያው ለችግርና ለድህነት ኑሮዋቸው እንኩዋ ከሚያስፈልጋቸው እዮ ቀነሱ ፣ በሰጡት ገንዘብ ያገኘነው ስለሆነ ፣ ባለዳንታችን ተሰምቶን እንዲህ ተቸግረው የረዱን ፣ ሳይተርፋቸው መስዋእት የሆኑልን ወገኖቻችን ፣ ኑሮዋቸውን እንዲያሻሽሉ ባገኘነው መጠነኛ ትምህርት ብንረዳ ብድሩን የከፈለ ፣ እዳው፣ ለሰወርዶ ነጻ የሆነ ሰው ፣ የሚያገ ኘውን ደስታ እናገኛለን ብለን ነበር እንጂ ፣ የቡና ብር ፣ ወይም የስ ምን ስልጣን ፍለጋ አልመጣንም ነበር ! እውነትም ስራችንን እንደ ጀመርን ያባንዳች እንቅፋት ፣ ያባንዳች ችግር ፣ የንስገስነው የተፋ ጠኑ ግስጋሴ ግባችንን ፣ የምኞታችንን ፍጻሜ ፣ በጣም አቅርቦ አሳዬ ኝና ፣ ወደዚያ ግብ ባጭር ጊዜ የመድረሱ ተስፋ የሰጠን ደስታ ፣ ስራ ችን ሲፈጸም እናገኛለን ብለን ካሰብነው ደስታ ያላነሰ ሆነ ! ሶስት አመት ሙሉ ፣ ልባችን ሲቃ እንዳጋለው ፈረስ ለመግታት በሚያስ ቸግር ደስታ እዮጋለበ ፣ ወደ ምኞታችን ፍጻሜ ፣ ወደ ግባችን ፣ ለመ

@OLDBOOKSPDF

ድረስና ደግሞ የበለጠ ደስታ ለማግኘት ይናፍቅ ነበር ! አሁን ፣ እየ ጎዶ ! አሁን ፣ አግባችን ለመድረስ ስንዝር የቀረን ሲመስለን ፣ እምኞ ታችን ፍጻሜ ደርሶን አይነተኛውን ደስታ ለማግኘት ስንሰናዳ ፣ ሁሉም ቀልድ መሆኑን ፣ ሁሉም ሕልም እንጂ እውነት አለመሆኑን ፣ ሶስት አመት ሰርተን የወገኖቻችንን ኑሮ አሻሻልን ብለን ደስ የተሰኘን በት ስራ ሁሉ ውሸት ፣ ነገ በቦታው የማይገኝ ምትሀት መሆኑን አረዳን ! እንዴት ያለ ክፉ መርዶ ነው ! እስካሁን ስራችንን ስንሰራ የነበረንንም ፣ ስራችንን ስንፈጽም እናገኛለን ብለን በናፍቆት የምን ቸኩልበትንም ደስታ ፣ ባንድ ላይ ወሰዱብን ! ቀሙን ፣ ቀኛዝማች ! ከንግዲህ ወዲያማ ምን ቀረን ? ህዝብ እንዳንመክር ፣ እንዳናስተምር እንዳንረዳ ከለከሉን ። በገንዘባችን ገዝተን ለቤት መስሪያና ለጎመን መገሪያ እንዲሆናቸው ፣ ማረፊያ ለሌላቸው ቆርሰን የሰጠነውን መሬት ከቀሙን ፣ ከንግዲህ ወዲያ ምን አለ ንና ፣ ምን ልናደርግ እንቀ መጣለን ? ከንግዲህ ወዲያስ የምንፈልገው ነገር የለም ። ለራሳችን አስ ቀርተነው የነበረውን መሬትም ጨምረው ይወሰዱት ! ቀኛዝማች መቸም ከራስዎ በቀር ሌላ ደስ ሲለውና ሲጠቀም ማየት እንደማይ ወዱ ፣ አይንዎን እንደሚያመው ፣ አሁን ደህና አድርጌ ተረድቻለሁ ። ስለዚህ . . . የጀመርነው መልካም ስራ በዝዛ እጁ እስኪፈርስ መጠ በቁ ስለማያስችልዎ ፣ መቆፈሪያና መዶሻዎን አስጭነው ወጥተው የተ ሰራውን ሁሉ . . የውሀ ግድቡን ፣ ገንዳውን ፣ ቤቱን ፣ ሌላውንም እየዞሩ ማፍረስዎ ፣ መሰባበርዎ ፣ በዩጎዋርዎ የተተከለውን አታክ ልት እየነቃቀሉ መጣልዎ አይቀር ! ስለዚህ እንዲህ ባለው ስራዎ ፣ እንዲህ ለመጉዳት ታጥቀው ለሚደክሙት ድካምዎ ቀኛዝማች ፣ እግ ዚአብሄር ዋጋዎን እጥፍ ድርብ አድርጎ ይከፈልዎ ! ደግሞ እርግጠኛ ነኝ ይከፍልዎታል ! ” ብሎ በፍጥነት የበሩን መዝጊያ ከፍቶ ሲወጣ አሳዬ ተከትሎት ወጣ ።

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፴፮

# የቀኛዝማች ዳኘ የንግዳ ቤት

ቀኛዝማች ዳኘ በጽህፈት ቤታቸው ልዩ ጉባኤ ባደረጉ ማግስት ፣ ጥዋቱን ሁለቱ ነፍጠኞቻቸውን ወደ ጥላሁን ቤት ልከው እንዲጠሩት አደረጉና ፣ ነፍጠኞቹ እንደ ታዘዙት ጠርተው ወስደው "የንግዳ ቤት" በሚሉት ሰፊ አዳራሽ አስገብተው ፣ በሩን የሁዋሊት ዘግተውበት ሄዱ።

ቀኛዝማች ፣ "የንግዳ ቤት" ብለው የሰየሙት አዳራሽ ፣ በተለይ "አደገኞች ናቸው" የሚሉዋቸውን ሰዎች አስረው የሚመረምሩበት፣ ብዙዎቹንም ያስገደሉበት ነው ። አዳራሹ ልዩ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው እንደ መሆኑ መጠን ፣ በዚያ የሚታሰሩትን ሰዎች የሚጠብቁት ዘበኞች፣ ለቀኛዝማች ታማኞች ናቸው ከሚባሉት መሀከል ከመሆናቸውም በላይ የለረኞችን እግር ብረት ጉዋጉንቸር ቁልፍ የሚይዙ ባለቤታቸው ወይዘሮ አጸገነት ናቸው ። ወይዘሮ አጸገነት የግር ብረቱን ቁልፍ በጥንቃቄ እንዲጠብቁ ባላቸው ስላዘዙዋቸው ፣ ሰጥናቸውን ይሁን አገልግላቸውን ባለማመን ከመሀረባቸውና ከመለተወታቸው ጋር በማንሽ የጅ በርሳ ቸው አድርገው ከጃቸው አይለዩትም !

ያ ፣ ሰፊ አዳራሽ ፣ አንድ በምስራቅ ፣ አንድ በምእራብ ፣ ሁለት በሮች ብቻ አሉት እንጂ ፣ መስኮት የለውም ። ከድምድሙና ወደታች ቀጥሎ ካለው ማገር መሀከል ያለው ግድግዳ ስላልተመረገ ፣ በዚያ በኩል እዚያ ቤት ውስጥ ያለው ሰው አየር እንደ ልብ ሊያገኝ ይችላል ፤ ብርሀን ግን ፣ ይልቁንም መጀመሪያ እንደ ገባ አያያም ። እዩቆዩ ብቻ ባልተመ ረገው የግድግዳ ክፍል ዙሪያ ፣ በዪጭላንጭሉ የሚገባው ብርሀን ባንድ ላይ ተደምሮ ፣ እዚያ ቤት ውስጥ ምን እንዳለ ለማሳዩት ይበቃል ። ስለ ዚህ ጥላሁን ገብቶ ከበሩ አጠገብ እንደ ቆመ ትንሽ ከቆዩ በሁዋላ ፣ ወለሉ በሙሉ ያልተተመተመ አፈር መሆኑን ፣ እዚያ አፈር ወለል ላይ ከጋጋግራዎቹ ውስጥ ፣ እቤቱ መሀከል ሶስት ፣ ወይም አራት የሚሆኑ ሰሌኖች ተቀጣጥለው መነጠፋቸውንና ፣ በሰሌኖቹ ላይ ሁለት ፣ ፈንጠር ፈንጠር ብለው የተቀመጡ ባርጩማዎች መኖራቸውን አዩ ። ሌላ ምንም የለ ! ብቻውን ነው ! ከዚያ ባንዱ ባርጩማ ላይ ለመቀመጥ መን

@OLDBOOKSPDF

ገድ ሲጀምር ፥ ድንገት መንጋ በራሱ ውስጥ ተከታትሎ ፥ እስበሱ እየተነዳዳ መጣና ፥ ወደ ባርጩማው የጀመረውን መንገድ አስቶት ፥ የቤቱን ወለል በቁሙ አቋርጦ እግድግዳው ጥግ አድርሶት አገኘ ። ከዚያ መቀመጥ አስቦ የነበረውን ጭራሽ ረሳና ፥ እጆቹን በጀርባው ሁዋላ አስተሳስሮ ፥ አንዳንድ ጊዜ ቀና እያለ ወደ ጣራው ፥ አንዳንድ ጊዜ ዝቅ እያለ ወደ ወለሉ ፥ አንዳንድ ጊዜም ፊት-ለፊት ወደ ግድግዳው ፥ እንደሚያይ አይናቹን እያተከረ ፥ ነገር ግን ጣራውን ፥ ወለሉንና ግድግዳ ውን ሳይሆን በራሱ ውስጥ ተከታትሎ የሚነዳውን ያሳብ መንጋ እያዬ ፥ ወዲያና ወዲህ መመላለስና ፥ ያን የሚያየውን ሁሉ ድምጹን እያሰማ ለራሱ መንገር ጀመረ ፤

"ግሩም ነው !" አለ ቅንሽ ቆም ብሎ ያን ሰፊ ቤት በወርዱም ፥ በቁሙም ተመለከተና ። "ግሩም ነው ! ይህን ያክል ቤት ለምን ይሆን ያሰሩት ? ለሰው ማሰሪያ ነው ? መቸም እኔን ማመኑ አስቸግሮኝ ነበር እንጂ ፥ የተጣሉዋቸውን ሰዎች እያሰሩ እንደሚደበድቡ ፥ እንዲያውም እንደሚገድሉ ሰምቻለሁ ። እኔን ማመኑ አስቸግሮኝ ነበር እንጂ ፥ ለከፋ ታቸው ተወዳዳሪ እንደሌለው ባላምባራስ ጉዴታም ፥ አሳዬም ነግረው ኛል ። ታዲያ አሁን . . . እኔንም አስረው ሊደበድቡኝ ይሆን እዚህ አስገቡተው የዘጉብኝ ? ብቻ ምን ስላደረግሁዋቸው ? ምን ስላልሁዋቸው አስረው ይደበድቡኛል ? አዎ ፥ እኔስ ምንም አላደረግሁዋቸው ። ነገር ግን . . . ሶሬና እኔ ባዶ እጃችንን መጥተን ፥ ባጭር ጊዜ ፥ በሶስት አመቱ የሰራነው ፥ እሳቸው ከትልቅ ስልጣንና ከብዙ ገንዘብ ጋር ይህን ያክል ረዥም ጊዜ ሲኖሩ ፥ ሊሰሩ እዬቻሉ ያልሰሩትን ገልጾ እያሳዬ ከሳሻቸ ውና አስወቃሻቸው መሆኑ የታወቀ ነው ! አዎ ፥ ይህ ልክ ነው ! ስራ ችን ሲሰሩ ሲገባቸው ባለመስራታቸው በደለኛ ፥ ነውረኛ ፥ መሆናቸውን ገልጾ እያሳዬ ፥ ክሶ የሚያስፈርድባቸው መሆኑ እርግጥ ነው ! ስለዚህ ባይ ባዩን ደህና መስሎ ፥ ተንኮብጉብ ለመቃየት ፥ ነውር እዬገለጸ እያሳዬ የሚከሰንና የሚያሳውቅን ስራ ከነሰራተኞቹ ወዲያ ማጥፋት ያስፈል ጋል ። አዎ ! ይህ ነው ነገሩ ፤ እኛን ከነስራችን ማጥፋት የፈለጉበት ይህ ነው ብልሀቱ ! " አለና ቅንሽ ወደ ጣራው አንጋጦ ሲያስብ ቆይቶ ፥ ስሜቱ በውስጡ ተስፋ ከመቁረጥ ተስፋ ወደ መዝረት ሲለወጥ በፊቱ እየታዬ ፥ "ምናልባት . . . " አለ ። " ምናልባት ቅናንት በወሰኑት ተጸጽ ተው እንደሆንስ ? እኛ ለሰራነው ስራ ሁሉ ባለቤት ሆነው የበላይ ባለ ስልጣኖችን ቢያስጎበኙ ከመልካም ስምና ከምስጋናም በላይ ለከፍተኛ ሹመት የሚያሳጯቸው መሆኑን ስላመለከትሁዋቸው ፥ ምንም እንኩዋ ባጊዜው አሳቡን ያልተቀበሉ ፥ እንዲያውም የነቀፉ ቢመስሉ ፥ ሁዋላ

@OLDBOOKSPDF

በጥሞና ሲያሰላስሉት ፥ ሲያመዛዝኑት እወነትም ጥቅማቸው መሆኑን ተረድተው እሳባቸውን ለውጠው ይሆን ? መቸም የተቆጣን ልብ ለማ ባበልና ይቅር እንዲል ለማድረግ ፥ እንኳንስ ከሽማግሌ ከታቦትም የበለጠ አማላጅ ጥቅም መሆኑ የታወቀ ነው ! ጥቅም ባለበት በኩል ይቅርታ ለማድረግ ትንሽ ምክንያት ይበቃል ! ” ስለዚህ ትንሽ ምክንያት ፈጥረው ፥ “ይቅርታ አድርጌልሀለሁ” ሲሉኝ ይሆን ? ይህም ሊሆን የሚ ችል ነው ! ማንም ጥቅም ወዳጅ ቢሆንኮ መልካም ስምና ጥቅም ሲለያዩ ነው እንጂ ፥ መልካም ስምን ትቶ ጥቅምን የማከተል ፥ መልካም ስምና ጥቅም ባንድ ላይ ካገኘ የሚጠላ የለም ! ስለዚህ ለኛ ስራ ባለቤቶ መቢሉ መታዩቱ ፥ መልካም ስምና ምስጋና ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ሹመት ጭምር ለማግኘት ተበፋ ስላባደረባቸው እንድ ትንሽ ምክንያት መሳይ ፈጥረው ፥ “ስራችሁን እንድትቀጥሉ ፈቅጀላችሁዋለሁ ! ” ቢሉኝ ! እለና ትንሽ እንገቱን ደፍቶ ቆሞ ሲያስብ ከቆዩ በሁዋላ ፥ “እየ . . . እባክህ ጌታዩ ፥ ክፉውን ለውረሀ ደጉን አሳየው !” ሲል ጥላሁን እጆቹን ከጆ ርባው ሁዋላ እንዳስተባሰረ ከወዲህ ወዲያ ፡ ከወዲያ ወዲህ እዩተመላ ለሰ ፥ እንድ ራስ በሩን ትንሽ ከፈት አድርጎ ፥ በከፊል ብቅ ብሎ ሲያይ ከቆዩ በሁዋላ ፥ ያ በር በሙሉ ሲከፈት ቀኛዝማች ዳኘ ፥ ግለው ወለባና ማም ዳምቤ የሚባሉ ታማኝ ሎሌዎቻቸውን አስከትለው ገብተው ቆሙ ። ጥላሁንም ወዲያና ወዲህ ማለቱን ትቶ ቆሞ ይመለከታቸው ጀመር ። ባጭር ጊዜ ከሁሉቱም ወገን እንኳንስ ቃል ትንፋሽ እይሰ ማም ነበር ! በመጨረሻ ፥

“እሰር እሰር ጊዜ እጅ እንሳለሁ ! የቃሌቾች ንጉሥ !” አሉ ቀኛ ዝማች ፥ ዝምታውን አቋርጠውና ያሽሙር ፈገግታ ፈገግ ብለው ። ጥላሁን የቀኛዝማችን ቢድብ ሲሰማ ፥ ለጥል ተሰናድተው እንዳ መጡ ተረዳና እንገቱን ደፍቶ መሬት መሬት እያዩ ዝም አለ ።

“ለሰላምታዩ አትመልስም ?” አሉ ቀኛዝማች ፥ አሁንም ያሽሙር ፈገግታቸው በፊታቸው እዩታዩ ፥ ፊት ከቆሙበት ትንሽ ቀረብ ብለው።

“የቃሌቾች ንጉሥ እዚህ እንዳለ አሉ ይመልስ እንጂ እኔ ምን እመልሳለሁ ? የቃሌቾች ንጉሥ አዳለሁ !” አለ ጥላሁን ፥ እንገቱን ከደፋ በት እቅንቶ ቀኛዝማችን ፊት ለፊት እያዩ ። ከቆሙበት ሁለት እርምጃ ቀረብ ቢሉ ለዓዩ አለም ያኑ ያክል እንዳ ማፈግፈግ አለ ።

“የቃሌቾች ንጉሥ ነህ እንጂ ! የቃሌቾች ንጉሥ ባትሆን ከማይታዩ ከተሰወሩ መንፈሶች ጋር ትናገር ኖሮዋል ?” .

“ከምን የተሰወሩ መንፈሶች ጋር ተናገርሁ ?

@OLDBOOKSPDF

‘ካኒያው . . . ህዝቡን ከምታታልልባቸው ፣ ከጹር ከገደልና ከባሀር ጭፍሮችህ ፣ ከዛሮችና ከጋኔኖች ጋር ይሆናል ! እዩሙህ ስትናገር በሩቁ ስንሰማህ መምጣትን ፣ ብንገባ ካንተ በቀር ሌላ ሰው የለም ፤ ታዲያ ያን ያክል እዩሙህ ትናገር የነበረ ከማን ጋር ነው ? ከማያ ታዩ ፣ ከተሰወሩ መንፈሶችህ ጋር አይደለም ? እንዲያውም እውነቱን ልናዘዝልህ ፤ እንዲያ እዩሙህ ስትናገር ፣ የጹር የገደልና የባህር ጭፍሮችህን ጠር ተህ ፣ እኔን ለመግጠም የጦርነት ትእዛዝ የምትሰጥ መሰሎኝ ፣ ብቻየን መምጣት ፈርቼ ነው ፤ ሀ - ሀ - ሀ - ሀ ! ከጭፍሮችህ ጋር ብቻየን አልችልህም ብዬ ነው ፣ ይሄው እንደምታየው . . . ባሰውንና ማሞን አስከትዬ የመጣሁ !”

“ቀኛዝማቺ ፣ ይህ ሁሉ ፈዝና አሽሙር ፣ ጨካኞች የሚገድሉትን፣ አስቀድመው ማቁሰልና ሲሰቃይ ማየት የጨካኝ ልባቸውን ደስታ እጥፍ ድርብ ስለሚያደርግላቸው ፣ እርስዎም እኔን ለማቁሰልና ፣ ስሰቃይ እያዩ ደስ ለመሰኘት ነው እንጂ ፣ አሁን በሚናገሩት ሁሉ እንደማያምኑበት አውቃለሁ ። እንኩዋንስ እኔ ቃልቻ ልሆን ቃልቻ እንደምጠላ ፣ ቃልቻ የሚወዱትን እንደምንቅፍ ያውቃሉ ! ስለዚህ በፈዝና ባሽሙር ማቁሰሉ ይብቃዎና ፣ ምን ለማድረግ እንደ መጡ ስለማውቅ ፣ የመጡለትን ያድርጉ ፣ እጠብቃለሁ ! ” አለ ጥላሁን ፣ ቀኛዝማቺ አሽከሮቻቸውን አስከትለው የመጡ ሊደበድቡት መሆኑን ስላመነ ፣ ለጦርነት መቃጠቁን በሚያሳይ ስልጥ እጆቹን ጨብጦ ፣ ተደላድሎ ቆመና ።

“እኪ-ኪ-ኪ- ኪ ! የጹር ፣ የገደል ፣ ስውር ጭፍሮችህ በጀርባህ ተሰልፈው ፣ ‘አስንልህ’ አሉህ መሰለኝ ፤ ልትገጥመን ቡጢህን አሾልህ ! በል ግዴለም ፤ የቡጢውን ጉዳይ ሁዋላ እናያለን ! ኧረ ለመሆኑ ፣ አንተስ መቸም ከቃልቻም የቃልቾች ንጉስ በመሆንህ ፣ ምን ለማድረግ እንደ መጣንም ፣ ሌላውንም ሁሉ ታውቃለህ ! እኔስ እንዴት አድርጌ ነው ቃልቻ የምትጠላ መሆንህን የማውቅ ? እሷም እንዳንተ ቃልቻ ነኝ ባለች ነው ? ”

“ስለ ቃልቾች ብዙ ጊዜ ተነጋግረናል ! እርስዎ እናባ ጎዳን ፣ እናባ ጋሮን ፣ እናባ ሳምበንና ሌሎችን ቃልቾች ‘የሚናገሩት በመሬት ጠብ አይልም ፤ እግዜር በምድር ናቸው ! ’ እያሉ ፣ እያደነቁ ሲነግሩኝ ፣ እኔ ቃልቾች ቀጣፊዎች ፣ አታላዮች መሆናቸውንና ፣ እርስዎም በቃልቻ ግመንዎን ካልተዉ የወነቱኛ ክርስቲያን ለመባል የማይችሉ መሆንዎን እያስረዳሁ ብዙ ጊዜ ተነጋግረናል ! ስለዚህ ነው ፣ ብዙ ጊዜ ስለ ተነጋገርንበት ነው ፣ እንኩዋንስ ቃልቻ ልሆን ቃልቻ የምጠላና የም

@OLDBOOKSPDF

ንቅ መሆኔን ያውቃሉ ያልሁዎ ! ደግሞ ሌላ ነገር ልንገርዎ” አለ ጥላሁን ጥል ካልቀረ ብሎ ። “ሌላ ነገር ልንገርዎ ፤ ቃልቻ አለመሆኔን ደህና አድርገው ቢያውቁ ነው እንጂ እንዲህ . . . የሚያንገላቱኝ ፣ ቃልቻ ብሆን ይፈሩኝ ነበር ! በቃልቻ ሀይል አጥብቀው ስለሚያምኑ ፣ ቃልቻ ከመጠን ያለፈ ስለሚፈሩ ፣ ቃልቻ ብሆን ይፈሩኝ ነበር ! ” አለ እጆቹን ጨብጦ በሰልፍ እንደ ቆመ ።

“ደሞ ዛሬም ትሳድበኛ ? አንተ ! የትናንቱ አንሶህ ዛሬም ትሰድበኛ ? ” አሉ ቀኛዝማች ፣ ስማታቸው በቅጽበት ከቀዝቃዛ አሽሙርና ፌዝ ፣ እንደ እቶን እሳት ወደ ጋለ ቁጣ ሲለወጥ በፊታቸው አዩታዩና እዩተንዘረዘሩ ወደፊት ተራመዱና ።

“እዚያው ይሁኑ ቀኛዝማች ፤ እንዳይዋረዱ እዚያው ይሁኑ ! ” እውነቱን ነገርሁዎ እንጂ አልሰደብሁዎምና እዚያው ይሁኑ ! አለ ጥላሁን ፣ ቀኝ በጢውን ለውርወራ እንደ ተወጠረ ቀስት ወደሁዋላ ፣ ግራውን እንደ ጋሻ በፊቱ ደግኖ ። ወዲያው ማሰው ወለባ የጥላሁንን ስድብ ሲሰማና ፣ የጌታውን ቁጣ ሲያይ ፣ ስድቡ ከሳቸው የበለጠ እሱን አምሞት ፣ ከሁለቸው ተንደርድሮ ጎመዱን በጥላሁን ላይ ሊያነገር ሲቃጣ ፣

“ተው ቆይ ማሰው ! ” አሉ ቀኛዝማች ፣ ክንዳቸውን በማሰውና በጥላሁን መሀከል ዘርግተው ። “ተው ቆይ ማሰው ፤ ይህ አቅሙን አያውቅ ! ይህ እፍኝ አይሞላ ! በሰው ለማስፈረድ ነው እንጂ ፣ እውነት በቡጢ እንዳች ነገር አደርጋለሁ ብሎ አደለም ፤ ቆይ ግዴለም ሂድ ማሞ እግር ብረት አምጣ” አሉ ወደ ማሞ ዘወር ብለው ። ማሞ ሮጦ እግር ብረት ሲያመጣ ፣ “ገዝም ብሎ ከቃሰረ እንዳችመቱች ፤ አደራ አለብን ። አልታሰርም ብሎ ካስቸገረ ግን መቸስ . . . ምን ያደረግ በራሱ መፍረዱ ነው ! ” ብለው እንደ ወጡ ፣ ጥላሁን ወዳንዱ ባርጩማ ሄዶ ተቀመጠና ፣

“ እኒያውላችሁ የተፈረደባቸው እግሮቼ ! ጥሌ ያለ ጥፋት ከፈረዱብኝ ጌታችሁ ጋር ነው እንጂ ፣ ከናንተ ጋር ጥል የለኝም ወንድሞቼ ! „ አለ ፣ ፈገግ ብሎ ።

“ የምትናገረውን እዩቆጠብህ ካልተናገርህ ዛሬ በግርህ የተፈረደው ነገ ባንገትህ እንዳይፈረድ ያሠጋዋል ! ” አለ ማሰው ወለባ ፣ እሱም እንዲሁ ፈገግ ብሎ ።

“እንዴት ? ”

@OLDBOOKSPDF

"እንደ ዛሬው የምትሆንብ ከሆንህ ፣ እንደ እቡይ ወይፈን እንግትህን ከባድ ዛዝላ እንጭንልሃለና !"

"ከባድ ዛዝላ ? ምንድነው ከባድ ዛዝላ ?"

"ዛዝላ አታውቅም ? ዛዝላ እንዲህ እንዳንተ ያሉ እቡይ ወይፈኖች አንጠመድም ብለው ሲያስቸግሩ ፣ እንደ ቀንበር ተቀድዶ ባንገታቸው የሚጫን ከባድ ግንድ ነው ። ታዲያ እሱን ባንገታቸው ተሸክመው ጥቂት ቀን ከሰፉ በሁዋላ ልክ ይገባሉ ! አንተም ካሳረፍህ. . .ያው ነው !"

"አንተስ . . . አይመርልብህም እንጂ ጨካኝ ነህ ! አታደርገውም አይባልም !" አለ ጥላሁን እየሳቀ ። "ትድም ቀኛዝማች ባይከለክሉህ ፣ እንዲያ እንደ ታማህ በሉ በጎመድህ ክንዴን ጎምደህ የምትጥለው መስሎኝ ነበር ! ለመሆኑ እሱ፡ አንድ ነገር ልጠይቅህ እያ ማሰው፤ እንዲያ ሀይልህን ሁሉ ሰብስበህ ጎመድህን ወደ ጨበጡ ክንዶችህ ገፍተህ ፣ ያን ያክል ሽቅብ የተንጠራራህ ፣ መሬት የምታወርድ መስለህ በመታየት እኔን ለማስፈራራትና ቀኛዝማችን ደስ ለማሰኘት ነው ? ወይስ እውነት. . ."

"የምን መስሎ መታየት !" አለ ማሰው ፣ ጥላሁንን አቋርጦ ። "ደሞ መስሎ መታየት ! ያን . . . ጦርም ፣ ጋሻም ፣ ልሁን እያለ የሚያስቸግር ፣ ትልብልብ እጅህን አንድ ጊዜ ጎምጀልህ አንተንም ፣ እኛንም ባሳርፍ ነበር እንጂ ፣ ደሞ የምን መስሎ መታየት ነው ?"

"ሁ-ሁ-ሁ-ሀ ! እንዴት? አባክህ !" አለ ጥላሁን ከልቡ ስቆ ።

"አንድ ጊዜ ይሆን. . . ክንድህን ከሰንከልሁልህ ፣ እንዲህ እዩደገንህ'አካኪ ዘራፍ' የምትልበት ስታጣአርፈህ መቀመጥህ አይቀርም ነበር። እኛም በዩጊዜው ከልባችን ጋር እዩተካሰስን መሙዋገቱ ይቀርልን ነበር!"

"አልገባኝም ፤ ምን ማለትህ ነው ?"

"እዩህ ? ምንም እንኩዋ እንደኛ ያለን ፣ በሰው እንጀራ የምንኖር ሰዎች ፣ የጌቶቻችንን ፈቃድ መፈጸም ቢኖርብን ፣ ዞሮ ዞሮ ሰዎች ነንና የጌታ ፈቃድ ለመፈጸም የምንሰራውን ሁሉ ደስ ብሎን የምንሰራው አይምሰልህ ! አንዳንዱ እንድንፈጽም የምንታዘዘው የጌታ ፈቃድ፡ክፉ መሆኑን ፣ ግፍ መሆኑን ልባችን አውቆ "ተዉ" እያለ ፣ እያማጠነ ፣ በምንፈጽምበት ጊዜ ፣ ምንም እንኩዋ ሀላፊነቱ ያዘዡቻችን መሆን የሁዋላ ሁዋላ ማጽናናቱ ባይቀር ፣ ለጊዜው ስቃዩ ፣ ፈቃድ ከተፈጸመበት ሰው

@OLDBOOKSPDF

ያላነሰ ልባችንን ያመኖልክ ! ታዲያ . . . ይህ አይነት ስቃይ በዩጊዜው ከሚደርስ አንድ ጊዜ ፣ መውጣት አይሻልም ? ” ጥላሁን አልመለሰም ፣ ግም በግረሙት የሚያስሩቸውን እግሮቹን በቅዝቃ እዩተመለከተ ዝም አለ ።

“አንተ”አለ ማሰው ፣ ጥላሁን የሚታሰሩ እግሮቹን በቅርታ እዩ ተመለከተ ዝም ስላለ ። “ አንተ ምንም ብትማር የኛን ፣ ያልተማርኖችን ያክል እንኩዋ ላፍህ መዝጊያ ማበጀት ገና አታውቅም ! አዩህ ? ወቸም ሆድ የሚያስበው ብዙ ነው ፤ ባፍ የሚወጣው ግን ሆድ ከሚያስበው ተቀንሶ ነው! እኛ ያልተማርኖች እንኩዋ የምናስበውን ሁሉ አንናገርም ! ስለዚህ በሆድህ የምታስበው ሁሉ እንዲሁ እዩሮጠ እዩወጣ አንተንም ፣ እኛንም በዩጊዜው ከሚያስቸግር ላፍህ መዝጊያ አብጅለት!”

“እሺ እያ ማሰው ! እንግዲህ አንተ እንዳልከኝ ላፌ መዝጊያ አበጅለታለሁ” አለ ጥላሁን ፣ የቅርታ ፈገግታ ፈገግ እንዳለ ቀና ብሎ ።

“ማለፊያ ፤ እንዲህ የሰው ምክር የምትሰማ ከሆንህ ፣ ምንም የሚያስቸግር ነገር አይኖርም ፤ አሁን ትፈታለህ ። ጌቶች እልክ ሲያሳዩዋቸው ነው እንጂ ‘እርስዎ እንዳሉ’ ካሉዋቸው ፣ እሳቸውን የመሰለ ፣ ደግ የለም አለና ማሰው ፣ እሱና .ተ° እስረኛውን “እግዜር ያስፈታህ” ብለው ከወጡ በሁዋላ ፣ ትንሽ ቆይቶ ወይዘሮ እጸገነት የላኩዋት አሸከር መጣች።

“መታሰርህን ሰምቼ በጣም አዘንሁ ፤ እግዚአብሄር ያስፈታህ ብለዋል እሜቴ ” አለች አሽከርዋ ።

“እሜትን እግዚአብሄር ይስጥልኝ ፤ እባክዎ ከመታሰሬ በቀር ምንም እንዳልደረሰብኝ ፣ ፍጹም ደህና እንደ ሆንሁ ፣ ለሶፊ ይላኩልኝ ብለሽ ንገሪልኝ ” ብሎ ጥላሁን ፣ አሽከርዋ መልክቱን ይዛ ስትወጣ ፣ እሱ የታሰረበትን እግር ብረት ሲመለከት ፣ ከስራቱ ጋር የተያያዘ ልዩ ልዩ አሳብ መጣበትና ፣ ያን ልዩ ልዩ አሳብ እንደ ልማዱ ለራሱ መንገር ጀመረ ።

“አሁን እውነት ትናንት እንዳሉት . . . ሕዝብ በሳቸው ላይ እንዳላሳድምና ስልጣናቸውን እንዳልቀማቸው ፤ ፈርተው ነው ያሰሩኝ ! አዩ . . . ! አይደለም ፤ ይህ እንዲያው ምክናያት ነው ! ” አለ ጥላሁን ፣ ከባርጩማው ወርዶ ፣ አሰሌኑ ላይ ተቀምጦ ሽቅብ ጣራ ጣራውን እያዩ። “ያሰሩኝ ቅንተው ነው ! ወትም እድሚያቸውን ሙሉ ክፉ ሲሰሩ የሚኖሩ ሰዎች ፣ መልካም መስራት ስለማይችሉ ፣ መልካም ስራ ሰርተው ፣ ህዝብ በሚወዳቸው ሰዎችና ፣ በመልካም ስራቸው መቅናታቸው

የታወቀ ነው ! ስለዚህ @OLDBOOKSPDF አቅማችን በጀመርነው መልክም ስራ ሰው ስለ ወደደን ቀንተው ነው !እየ ገ. . . ድ!" አለ ፣ አይኑን አጣሪው ላይ ጌንደ ተክለ ትንሽ ዝም ብሎ ሲያስብ ቆዩና ። " ተራ ሰው ቀንቶ ሲያጠቃ በኋላ ፣ አቅም ያለው በራሱ ሀይል አቅም የሌለው በሰኛ ሀይል ይቃወመዋል ፤ ነገር ግን ህዝብ ሊጠብቅበት ባደረ የተቀበለውን የሰኝነት ስልጣንና ፣ ያ ስልጣን የገዛቸውን"አድር" ባዮች መላ ሪያ አድርጎ ፣ ሳይታይ ፣ እንደ እግዜር ከሩቅ የሚመታን ቅናተኛ ባለ ስልጣን እንዴት መቃወም ይቻላል ? አይቻልም ! ምህረት ለገኖ ይቅርታ ማግኘት ይቻላል ? አየ . . . ! እንኟ የተጣ መልሶ ፣ የበደለ ክሶ፣ የቆማቸውንና ፣ የበደሉትን ሰው ልብ ማለዘብና ይቅርታ ማግኘት ይቻል ይሆናል ። ነገር ግን ያስቀና ሰው ምን ሰጥቶ የቅናተኛ ጠላቱን የቆሰለ ልብ ማዳንና ይቅርታ ማግኘት ይችላል ? የለም ፣ ያስቀና ሰው ራሱን እንጂ ሌላ ካሳ እንዲከፍል አይፈለግም ! ያስቀና ሰው ራሱን መስዋዕት እድርጎ ካላቀረበ ፣ ምንም ያክል ፣ ምንም አይነት ፣ ሌላ ካሳ ቢከፍል የቅናተኛ ጠላቱን በቀል የተጠማ ልብ ሊያረካ ስለማይችል ይቅርታ አገኛለሁ ብሎ ተስፋ ማድረግ ከንቱ ምኞት ነው ! ስለዚህ ከተቻለ ፣ መውጫ መንገድ ከተገኘ ፣ መድሀኒቱ እንዲያ ካለ ቅናተኛ ጠላት ባለስልጣን መሸሽ ብቻ ነው ! መሸሽ ! " አለ አሁንም ትንሽ ዝም ብሎ ቆየና ። "እየ . . . ጉድ! የጀመሩትን መልካም ስራና የተቀደሰ ተግባር ትቶ ፣ ከራብና ከጉስቁልና ፣ ከበሽታና ከድንቁርና ፣ ነጻ ለመውጣት ስንዝር የቀረው ባለውለታ ወገንን መልሶ እንዲያ ላሉ ጨካኝ ጠላቶች ሰጥቶ . . . ራስን ለማዳን መሸሽ ? ይህማ ፈሪነት ነው ! ያሁስ ለተጠሩበት ከፍተኛ ተግባር ብቁ ሆኖ አለመገኘት ነው ! መልካም ስራን ሊያጠፉ ከተነሱ ጠላት ፊት መሸሽ ? ይህማ ወገንን አታሎና ሀሲናን ገድሎ ፣ እንዲያ ያለ አጥፊ ጠላት ድል እንዲነሳ መንገድ መሪና ተባባሪ መሆን ነው ! አይ የለም ፣ መድሀኒቱ መሸሽ አይደለም ። መድሀኒቱ አጥፊን ማጥፋት ነው ! ካጥፊ መሸሽ ፣ አጥፊ እንዲያጠፋ መፍቀድ ፣ አጥፊን ሳያጠፋ ቀድሞ ማጥፋት መልካም ስራ እንዳይጠፋ ማገድ ስለሆነ ፣ ከተቻለ ፣ መንገድ ከተገኘ ፣ አጥፊን አጥፍቶ ማምለጥ ፣ የማምለጥ እድል ካልተገኘ አብሮ መጥፋት ነው! አዎ ፣ ይህ ነው መድሀኒቱ!" አለና አሁንም ዝም ብሎ ቆይቶ፣ "ሀ !ሶፊስ ?" አለ ። " ሶፊ እንዴት ትሆናለች ? መቸም ገድየው ካመለጥሁ ምንም አትሆንም ፣ ገድዬው የተገደልሁ እንደሆን ብቻ. . . ያስ ቃዩዋት ይሆናል ! ነገር ግን. . . ይህ ክፉ ሰው ከጠፋ ግን ያስቃያታል ? ያገኑ ሰው እንደሆነ ሁሉም ይወዳታል ! እየ . . . ! መሰቃየትዋስ አይቀርም ፣ ጠላት ባያሰቃያት የኔ ሞት ያሰቃያታል ! "

@OLDBOOKSPDF

ጥላሁን ሶፊን ሲያስብ ፣ ፍቅራቸው በሙሉ ጥልቀቱ ፣ በሙሉ ምጥቀቱ ፣ በሙሉ ስፋቱ ፣ በሙሉ ግርማው ስለታዩው ፣ ለቅሬቅንቱ ልቡ ፣ መንፈሱ በውስጡ ባከብርት ፣ በእንክሮ የተንበረከከ ፣ የሰገደ ፣ መስሊ ተሰማውና አይኖቹን ከድኖ ፣ አንገቱን ደፍቶ ዝም ብሎ ቆይቶ ፣ "አዎ" አለ ። " አዎ ፣ ሶፊ በጣም ትወደኛለች ! በጣም እንደምትወደኝ ለልቢ ብቻ ሳይሆን ለያንዳንዱ ህዋሴ ሁሉ ይሰማኛል ! ስለዚህ ሞቴ ያሰቃያታል ። የሚወዱትን ሰው ሞት ፣ ከጨካኙ ጠላት የበለጠ እንደሚያሰቃይ የታወቀ ነው ! ታዲያ ምን ይሻለኛል ? መቸም የተቀደሰ ተግባርን ጥሊ ሀሲናን 'ገድሎ ፣ ከጠላት ፊት መሸሽ ወራዳ ፈሪነት ነው ! የምትሰ . . ምኸት የምትሰቃይ መሆንዋን እያወቁ ፍቅርዋን ይዞ መኖርም ጨካኝነት ነው ! ታዲያ ምን ላርግ ? ክብር እንድኖር ፣ ፍቅር እንድኖር ፣ እንዲህ ቀኝና ግራ ወጥረው ሲለቡኝ ፣ ማንኛውን መከተል እንደሚገባኝ ማን ይንገረኝ ? " ጥላሁን ለጠፍቀው ጥያቄ ከሰማይ መልስ ይመጣል ሀል እንደ ተባለ ሁሉ ፣ አንገቱን ወደ ላይ ቀና አድርጎ አይኖቹን ሳያረግብ ሲመለከት ቆዩና ፣ "ለመሆኑ " አለ ። " ለመሆኑ ክብር በሌለበት ፍቅር አለ ? ለክብሬ የማላስብ ፣ ወራዳ ፈሪና አሳፋሪ ከሆንሁ ሶፊስ ትፈደኛለች ? እንጃ ! የምትወደኝ አይመስለኝም ! እረ አትወደኝም አትወደኝም ! እንኳንስ ኩሩዋ ሶፊ ፣ ማንኛዋም ሴላ ሴት ብትሆን ከወራዳ ፈሪና ፣ አሳፋሪ ባል ጋር ከመኖር ለክብሩ ከሞተ ጀግና ባልዋ መታሰቢያ ጋር መኖር ትመርጣለች ! የለም ፣ ሶፊን የፈሪ ምኸት አላሰኛትም ! ሶፊ 'የፈሪ ምኸት' እዩተባለች ፣ በግልጥና ባሽሙር በተሰደበች ቁጥር ፣ በፍረት እዩተሸማቀቀችና እዩተሰቃዩች ከኔ ጋር ከምትኖር ፣ እኔ ለክብሬ ሞቼ ጀብዱንና ፍቅራችንን እያሰበች ብታዝንም ኩርታ ትኑር ! በቃ ቆረጥሁ ፣ ቃል ለምድር ለሰማይ ይሆን ወን ጀለኛ እቀጣጥለሁ ! ይህን አጥፊ አጥፍቼ ግምለጥ ካልቻልሁ እዚሁ አብሬው እጠፋለሁ ! " አለ ፣ ልቡን ያሞቀው ሲቃ ወገኑ በፊቱ እዩታዩ ። ከዚያ አይኑን ሳያረግብ ፊት ለፊት ፣ እግድግዳው ላይ እንደ ተከለ ዝም ብሎ ሲያስብ ቆዩና ፣ ፈገግታው ከሲቃ ወደ ቅርታ መልኩን ለወጠ ፤

"በይ እንግዲህ ደህና ሁኚ ! " አለ ። "ደህና ሁኚ ሶፊ !" ላጭር ጊዜ ይሁን ለሁልጊዜ አላወቅም ! ብቻ ለማናቸውም ደህና ሁኚ ልበልሽ ፍቅሬ ! "የመልካም አላማችንን ጠላት አጥፍቼ ልጥፋ ! ወይስ ልሽሽ ? እያልሁ ባላቤ ስከራከር ፣ እንደምትጠጂኝና ሞቴ እንደሚያሰቃይሽ ስለ ማውቅ ፣ የሞት ግርማ ሳይሆን ያንቺ ስቃይ አስፈርቶኝ ልሽሽ ነበር ! ሁዋላ እንደገና አስተጋብቸ ሳስብ ፣ ከተቀደሰ ተግባሬና ከክብሬ ሸሽቼ

@OLDBOOKSPDF

የማተርፈው ሕይወቴ ፤ ለዚያ ለማውቀው ኩሩ ልብሽ እፍረትና ሲቃይ
እንጂ ፤ ሙሉ ደስታ ሲሰጠው እንደማይችል ስለ ተረዳሁ ፤ ሞቴ በያ
ሰቃይሽ ስራዩ እንደሚያኮራሽ ነ ምኘ ፤ ለጋራ ክብራችንና ለጋራ ተግ
ባራችን ለመጥፋት ቆረጥሁ ! ምናልባት ፤ መቸም እግዚአብሄር የታም
ራት ጌታ ነውና ፤ ከበዙ ታምራቱ አንዱን ለኔ አድርጎልኝ የደስታች
ንንና የወገኖቻችንን ጠላት አጥፍቼ ባመልጥ ፤ ቡቃያው ፍቅራችን
አድጎ ለፍሬ ሲበቃ እያዩን ፤ ደስታችን ፍጹም ወደሚሆንበት ጊዜ
እንደርስ ይሆናል ! ካልሆነም ፤ መቸስ ምን ያደረጋ ፤ ይህ ካልሆነ ፤ የዚ
ያን ቡቃያ ፤ የዚያን በጨርቁዋው የተቀጨ ፍቅራችንን መታሰቢያ
ድጋፍ አድርገሽ ፤ አብረን የጀመርነውን የተቀደሰ ስራ ብትቀጥይ ነፍ
ሴን ደስ ይላታል ! ነገር ግን ከሁሉም አጥብቄ የም፣ ምንሽ አዘን እንዳ
ታበገር ነው ፤ ሶፊ ! መሪር አዘን ከፉ ነው ፤ ተስፋ ያስቆርጥና አላማ ያስ
ታል ። ! ስለዚህ እባክሽ አዘን አታብዥ ሶፊ ! እባክሽ የኔ እመቤት ፤ ያን
ከተዋወቅን ጀምሬ የተኘሁበትን ልብሽን ፤ ያን የፍቅርን ዜማና ቅኔ እስከ
ምስጢሩ ለገለጸልኝ ፍቅርሽ መንበር የሆነ ልብሽን ፤ ያን ሳዝን መጽ
ናናት ፤ ለፈራ ድፍረት ፤ ለደከም ብርታት እየሰጠ ላኖረኝ ፍቅርሽ
መቅደስ የሆነ ልብሽን ፤ ጨካኝ አዘን ገብቶ እንዳያበላሽብኝ ፤ እንዳይ
ሰብርብኝ ፤ እንዳይመዘብርብኝ አደራ ! ይህን እዚህ በምድር የሰጠሁ
ሽን አደራ ጠብቂ ፤ በሰማይ እቀበልሻለሁ ! ሶፊ ፤ ደጋፊ ምርኩዜ ፤ መሪ
መብራቴ ሶፊ ፤ አደራሽን በርቺ ፤ አደራሽን ተጽናኚ ! እሺ ? “እሺ” በይኝ
የኔ እመቤት ፤ “እሺ በይኝ!” አለ ፤ ስቅቅ ብሎ እያለቀሰ ። ልቅሶው በቅ
ቶች ፤ ከወሰነው ውሳኔ ጋር ተያይዞ ከመጣው ልዩ ልዩ አሳብ ጋር ሲታገል
ቆይቶ ፤ ሲደክመው በሰሌኑ ላይ እንደ ተጋደመ እንቅልፍ ወሰደው ።

@OLDBOOKSPDF

## ምእራፍ ፳፮

## የሴሲቱ እንግዳ

ቀኛዝማች ዳኘ ፣ ጥላሁንና ሰፈያ የህዝብ አገልግሎት ስራቸውን እንዳይቆጥሩ በወሰኑበት ቀን ማግስት ፣ ሁለት ነፍጠኞች ልከው ጥላሁንን ሲያስወስዱት ፣ ውሳኔው በተደረገ ጊዜ የሆነውን ሁሉ በዝርዝር ለምሽቱ ነግሮዋት ስለነበረ ፣ ክፉ ነገር እንደሚደርስበት እርግጠኛ ሆና የምታደርገው ቅጡ ጠፍቶዋት ተጨንቃ ነበር ።

"አይተርፍም ይሞታል !" አለች ፣ እንዲሁ ደመነፍስዋን ስትወጣ ፣ ስትገባ ቆይታ መጨረሻ እሶፋዋ ላይ ስትቀመጥ ። "አዎ ፤ አይተርፍም ይሞታል ! እሳቸው ባለጌ ስለሆኑ ፣ ያሽከሮቻቸውን ብዛትና የሱን ብቻ መሆን አይተው 'ላስደብድብህ' ይሉና ፣ እሱ መቸም ኩሩ ነው ፣ የክብሩን መነካት እንጂ ፣ የሳቸውን የሰራዊት ብዛትና የሱን ብቻ መሆን ሳያይ ፣ አስደብዳቢውን 'ልደብድብ' ይልና ያስገድሉታል !" ብላ እዚያው እሶፋዋ ላይ እንደ ተቀመጠች ፣ አይኖችዋን ፊት-ለፊት እግድግዳው ላይ ስትተክል ጥላሁን ብቻውን ካንድ ወገን ፣ ቀኛዝማች ዳኘ ብዙ አሽከሮቻቸውን በፊታቸው ደርድረው ከሌላ ወገን ፣ ለጦርነት የተሰለፉበት ትርእይት ተዘርግቶ ታያት ! በዚያ ትርእይት ጥላሁን ግራ ክንዱን ጋሻ ፣ ቀኙን መዶሻ አድርጎ በግንባር ከቀኛዝማች ፊት የተሰለፉት ሰራቡና ለቀኝ ክንዱ ከያቅጣጫው ለሚሰነዝሩት በግራው እየመከተ ፣ በቀኙ አንዱን አፍንጫውን ፣ ሌላውን ጉንጩን ፣ ደግሞ ሌላውን አገጩን እየወገረ በፊቱ ከረበረባቸው በሁዋላ ፣ በላያቸው ቆሞ ወደ ቀኛዝማች ሲወነጨፍ ሲል ፣ በቀኝና በግራ የተሰለፉት ሁሉ የዱላ መአታቸውን ባንድ ላይ አስተባብረው ስላወረዱበት ሙሆ ወደቀ ! ያን ጊዜ ፣ ያን ጩኸት ስትሰማና ፣ ያን አወዳደቅ ስታይ እሰዋም እንደሱ ሙሁ ፣ ከተቀመጠችበት ወንበር ተወርውራ እመሬት ላይ ወደቀች ! እንዲያ እንደ ወደቀች ስታለቅስ ብዙ ቆይታ ፣ ክብርቱ ልቅሶ በሁዋላ ተከትሎ የሚመጣው ጸጥታ ሲተካ፣ ያ ፣ ሲሆን ያዩችው ሁሉ ፣ ሊደርስ የሚችል ቢሆንም ያን ጊዜ ግን እሰዋ ያሰበችው ፣ እሰዋ በራስዋ ውስጥ ፈጥራ ያዩችው እንጂ ፣

@OLDBOOKSPDF

በርግጥ ያልሆኑ መ[illegible] በ[illegible] ሲነዷያ ያለ ክፉ ነገ ራሰዋን መውቀስ ጀመረች ።

“ለምን እንዲህ ያለ ክፉ አሳብ በራሴ ውስጥ ገባ ? አባክህ ውሸት አርገው ጌታዋ” አለች ከወደቀችበት ተነስታ ፊትዋን እያባበሰች ። ከዚያ “ ቸር ተመኙ ቸር እንድታገኙ ” የሚሉት ብሂል ትዝ አላትና “ አቤቴ ቸር አገኝ እንደሆን እኔም ቸር ልመኝ ” ብላ ደህና ነገር ለመመኘት ብትሞክር አቃታት ! ባሳብዋ ደህና ነገር ለማግኘት ስትፈልግ ፣ እዚያ ባይኑ ህሊናዋ ፊት የሚተራመሰው መንጋ ሁሉ ክፉ ብቻ ነው ። አንዱ ከሌላው የከፋ ! ከዚያ ፣ ያን የክፉ መንጋ ማየቱ እንከዋ ስላስፈራት ፣ ልብዋን ስላባባው ፣ እሱን ላለማየት ፣ ከሱ ለመሸሽ ፣ ተነስታ ስትወጣ ትሁኔና ሚንያለው የሚባሉት አሽከሮቻቸው እዚያ አጠገብ ስላልነበሩ አንድ ቤት የሚነግርላት አጥታ ፣ ያጥሩን በር ገባ ብላ ቆማ ባይንዋ ሰው ስትፈልግ ስላዩች ፤

“ማንን ትሻለሽ የኔ እህት ?” አለች ፣ ያጥሩ በር ትንሽ ራቅ ያለ ስለነበረ ድምጽዋን ከፍ አድርጋ ፣ ወዲያውም እንዲያ ከሰው ሡነጋ ገሩ በራስዋ ውስጥ እዬተንጋጋ ያስቸገራትን የክፉ አሳብ መንጋ የሚያባርርላት መስሎዋት ።

“እርስዎን ነው የምፈልግ እመቤቴ ፣ የሚነግርልኝ ስላጣሁ ራሴን በገዛጇ በማቅረቤ ይቅር ይበሉኝ ” አለች ሴትዋ ፣ ሰጥ ብላ እጅ ነስታ ።

“እኔን ? ማን ብለሽ ?” አለች ሶፊያ ፣ ሴትዋን ስለማታውቃት ሴትዮዋም እስዋን የማታውቅ መስሎዋት ።

“እሜቴ ወይዘሮ ሶፊያ ” አለች እንግዳዋ ፣ ትንሽ እንደ ማፈር ብላ ።

“ነይ ግቢ የኔ እህት” አለች ሶፊያ ፣ እንግዳዋን ወደ ቤት ለመምራት መንገድ ስትጀምር ። እቤት እንደ ገቡ ሶፊያ እንግዳዋን እንድ ትቀመጥ ብትለምናት ፣

“ቶሎ ተመለሺ ስለተባልሁ ፣ መልክቱን ልንገርዎና ልሂድ እመቤቴ ” አለች እንግዳዋ ።

“መልክቱ ለኔ ነው ? ማነው የላከሽ ?”

“እመቤቴ ወይዘሮ እጸገነት ፣ ያገረ ገገሮ ሚስት ” አለች ፣ መልእክተኛዋ የእመቤትዋንም የጌታዋንም ስም ስትጠራ በአክብሮት እጅ እንደ ምትነሣ አንገትዋን ትንሽ ደፋ እያደረገች ።

@OLDBOOKSPDF

"ጥላየ ምን . . . ምን ሆነ ? ምን አደረጉት " ? አለች ሶፊያ ፣ ከመቅጽበት በጥፍ ትንልጉለው የወጡ አይኖችዋን በመልእክተኛዋ ላይ አፍጥጣ ። እንዲያ የሚያስፈራሩ አይኖችዋን በንግዳዋ ላይ አፍጥጣ እንደ ቆመች ፣ ልክ የወባ መንቀ እንደ ተነሳበት ሰው የሰራ አካላትዋ ይንዘረዘር ነበር ! መልክተኛዋ ሶፊያን በቅጽበት ፊትዋ ሲለዋወጥና ስትንቀጠቀጥ ስታይ እለኖም በበኩልዋ ደንግጣ ፣ አፍዋን ዳግመኛ እንኩዋንስ መናገር እንዳይተነፍስ ለማድረግ እንደ ፈለገች ሁሉ፣ በጅዋ እፍን አድርጋ ይዛ ፣ ቆማ ትመለከታት ጀመር ።

"ንገሪኝ እንጂ ለምን ዝም ትያለሽ ? ምን አደረጉት ነወኮ የምልሽ!" አለች ሶፊያ ፣ አይኖችዋን በንግዳዋ ላይ እንዳፈጠጠች አሁንም እዚተን ቀጠቀጠች ።

"አቶ ጥላሁን ደህና ደህና ፣ ናቸውኮ" አለች መልክተኛዋ ድንጋጤ ንግግርዋን እያደናቀፈው ።

"ውሸትሽ ነው ፤ ደህና አደለም ፤ አንድ ነገር ሆኖዋል ! ሞቶዋል!"

"ኧረ ደህና ናቸው ፤ ደህንነታቸውን ለርስዎ እንዲያስታውቁ ላቸው እሳቸው ፣ ራሳቸው እሜቴን ስለ ለመኑዋቸው ነው እኔን ልከውኝ የመጣሁ ። "

"የት ነው ? የት ሆኖ ነው ደህንነቱን እንዲያስታውቁለት የ . . . የላከ ? "

"እንግዳ ቤት . . . ናቸው" አለች መላክተኛዋ ፣ ሶፊያ የባልዋን መታሰር ስትሰማ የባሰውን ግራ ይገባትና " ግራ ታገባኛለች " ብላ ስለ ፈራች አንገትዋን ደፍታ መሬት መሬት እያዩች ።

"እንግዳ ቤት፣ የት ነው እሱ፣ ምንድነው እንግዳ ቤት ? "

"አንዳንድ ትልቅ ሰዎች . . . የሚ . . . የሚታሰሩበት ነው ፤ ብቻ ደህና ናቸው ፤ ጌቶች ከወጡ በሁዋላ ፣ እሜቴ ' እግዜር ያስፈታዎ ' በይልኝ ብለው ልከውኝ ሄጄ አይቻቸዋለሁ ፤ ደህና ናቸው ፤ እንዲያ ውም በመታሰራቸው ይስቃሉ ፣ ይቀልዳሉ "

"እና . . . ከመታሰሩ በቀር እንዲያው ሌላ . . . ምንም አልሆነ፣ " አለች ሶፊያ ፣ በዙሪያ መንገድ አለመደብደቡን ለማረጋገጥ ።

"እንዲያው . . . በፈ . . . ለጉት ታቦት ያምሉኝ እመቤቴ ፣ ምንም አልሆኑ ፤ ከመታሰራቸው በቀር ደህና ናቸው" አለች እንግዳዋ ፣ ሶፊያን ትንሽ መለስ ስትል ስላዩቻት በጣም ደስ ብሎዋት ።

@OLDBOOKSPDF

"እሁ . . . !" አለች ሶፊያ ፤ ክቁምዋ እሶፋው ላይ ስትወድቅ የባለጥን መታሰር መስማቱ ፡ ከከባድ ያሳብ ጭንት እንዳላረፋት ሁሉ በረኸርሙ ተንፍሳ ።

ልክ ነው ፤ "ይገሉታል ፤ ባይገሉት ያስደበድቡታል" ብላ ፈርታ ፤ ተጨንቃ ሳለ ፡ አለመገደሉን ፤ አለመደብደቡን መስማት ከከባድ ያሳብ ጭንት የሚያሳርፍ ነው ! "እንኩዋን አልሞተ ፤ እንኳዋን ተደብድቦ ያካልና የመንፈስ ስቃዩና ቁስል ፤ ይልቁንም የግይይን ፤ የመንፈስ ስቃይና ቁስል አልደረሰበት እንጂ ፤ መታሰርስ ግዴለም ይታሰር !" አለች ባሳብዋ ። በሴላ ጊዜ ፡ በመገደሉ ፤ ያለዚያም በመደብደቡ እር ግጠኛ ሆና ባልተጨነቀችበትና ባልተሸበረችበት ጊዜ መታሰሩን ብት ሰማ ኖሮ ፤ አልቅሳ እንደማያወጣላት እውቅ ነበር ። ነገር ግን ይገደ ላል ፤ ያለዚያም ስስ ከሞት የማያንስ የውርደት ድብደባ ይደበደ ባል ብላ ስትጨነቅ ፤ በዚያ ፈንታ መታሰሩን ስትሰማ ፤ ለጊዜው 'ይሁን' ብላ ተቀበለችው ! ብቻ ለጊዜው ነው ። ለጊዜው "ከመገደሉና ከመደብደቡ መታሰሩ ይሻላል" ብላ ፤ ለምርጫ ያክል መታሰሩን ተቀ በለች እንጂ ፤ የመገደልና የመደብደብ ስጋት በሌለበት መታሰርም ከገድ ነው ! ስለዚህ እዩፋዩ መታሰሩም እዩከበደ ፤ የማይቻል እዩሆነ ሄደ ! ቀኑን ሙሉ እንዲሁ ስትንሳ ስትቀመጥ ፤ ስትወጣ ስትገባ ፤ የመብ ላት ሆነ የመጠጣቱ አምሮት ሳይዝርባት ፤ እንኩዋንስ አለዋ እሱ መብ ላት የሚያስፈልገው መሆኑን ረስታ ምሳ ሳትወስድለት ሁለቱም ጦም ዋሉ ። ሁዋላ ብቻ አሳዬ ከትባለቤቱና ባለምባራስ ጉዳታ የሆነውን ለምተው መጥተው ሲያጽናኑዋት ቆይተው ሲሄዱ ፤ ቀኛላቱና ራት አስ ናድታ ፤ ምንጣፍና ልብስ ጭምር ለወይዘሮ እጸገነት ሰጥታ ተመለ ሰች ። ወይዘሮ እጸገነት እንደ ተለመደው በጠባቂዎቻቸው ፊት ስለ ተቀበሉዋት ፤ የፈለገችን ያክል ሊያነጋግሩዋት ባይችሉም ፤ ደህንነ ቱንና ፤ ሲሆን ሲሆን በማግሥቱ ፤ ያለዚያ በሶስተኛው ቀን ሳይፈታ እንደማይቀር እዩማሉ ስለ ነገሩዋት ፤ ስትሄድ ከነበረችው የተሻለ ልብዋ ረጋ ብሎ ተመለሰች ።

ሶፊያ ከወይዘሮ እጸገነት ዘንድ ስትመለስ ፤ የውብዳር ራት አስ ናድታ ፤ ባልዋ አሳዬ ጭምር መጥተው ሲጠብቁ አገኘቻቸውና ፤ ወይ ዘሮ እጸገነት የነገሩዋትን ሁሉ ነግራቸው ፤ እነሱም እያጫወትዋት ራታቸውን አብረው በልተው ሄዱ ።

"ሰውዬው ከዚህ የከፋ ነገር ለማድረግ ፤ እንኩዋንስ ሰው 'እግ ዚር ምን ይለኛ' የማይሉ ፤ ክፉ ሰው ስለሆኑ ፤ በዚሁ . . . በማሰሩ ብቻ ከተወለኑ 'እግዜር ይመስገን' ማለት ነው እንጂ ፤ ማማረር አይገባ

@OLDBOOKSPDF

ንም ” አለ አሳዩ እጣጥፋቸው ላይ ። “እኔ እንዲያውም ” አለ ቆጠ ለና ። “እኔ እንዲያውም ዛሬ ጥዋት አንድ ሰው መጥቶ ‘ቀኛዝማች ባቶ ጥላሁን ላይ የወንጀል ክስ አሰናድተው ብዙ ህዝብ ፣ አንድ ባንድ ወደ ቢታቸው እያስጠሩ ሲያስፈርሙ ነው የሰነበቱ’ ብሎ ነግሮኝ ከመ ውጣቴ ፣ ጥላሁን በወታደር ቶጋህ መሄዱን ስሰማ ፣ ከማሰር ፣ . . . ብዙ ጊዜ የከፋ ነገር ያደርጋሉ ብዬ ነበር የፈራሁ ።”

“እሱስ . . . ማድረግ የሚፈልጉት ሌላ ነገርም ካለ ፣ እስካሁን ባያ ደርጉት ከንግዲህም ሲያዖርጉት ይችላሉ ፤ ብቻ እኔን ያልገባኝ ህዝቡ በኛ ላይ . . . ‘ፈረመ’ ያልኸው ነው ! ህዝቡ እኛን ምን ወንጀል ሲሰሩ ምን ሲያዖርጉ አዩን ብሎ ይፈርማል” አለች ሶፊያ ፣ ድንጋጤዋንና መገረምዋን ባንድ ላይ በሚገልጽ አስተያየት አሳዩንና የውብዳርን እየለ ዋወጠች አዩችና ።

“ሲያደርጉ አዩን በሉ” ያሉትን ሁሉ “ ሲያዖርጉ አዩን ብሎ ! ”

“ እንዲያው በውሸት ? ”

“ህዝብ የባለስልጣንን ትእዛዝ መፈጸም ነው እንጂ ፣ ትእዛዙ እውነት ፣ ወይም እቡት መሆኑን መጠዬቅ ‘ ፈንታዬ ነው ’ አይል ምኑ ! ” አለና አሳዩ ለሶፊያ ሊነግራት አቅርቦት የነበረው ሌላ አሳብ ከቀረበበት ተራ ወጥቶ ጠፍቶት ፣ ሲቸገር ቆይቶ ሲያገኘው ደስ ብሉት “አ!”አለ ። “ልነግርሽ ያሰብሁት ጠፍቶኝ ነበር ። አሁን አገኘሁት ! ‘ ማድረግ የሚፈልገ ቱ ሌላ ነገር ካለ እስካሁን ባያደርገ ቱ ወደፊት ሊያደርገ ቱ ይችነሉ’ ሰባልሽው ነው ። አዩሽ እንዲያ ያለው ክፉ ነገር የሚደረገው በቁጣ ፣ በደም ፍላት ተገፍቶ ነው እንጂ ፣ ቁጣውና የደም ፍላቱ ከበረደ በሁዋላ አያደርጉም ፤ የቁጣ እንፋሎትና የደም ፍላት ከበረደ ሰውን እንደ መኪና ወደማይፈልገው ሊነዳ አይችልም ! ስለዚህ ከንግዲህ ወዲያ . . . ግዴለሽም አትስጊ ! አልፎዋል ። ከንግ ዲህ ወዲያ ከዚያው ከስራቱ የሚያልፍ ነገር የሚኖር አይመስለኝም ፤ እሱ ደግሞ ግዴለም ፤ እሱ. . . እንዲያውም ያስፈልጋል ! ብቻ የማዝ ነው ባንድ ነገር ነው !” አለ አሳዩ ፣ አይኖቹን ፊት ለፊት ከሚመለከ ቱበት ወደ ሶፊያ መልሶ ። ነገር ግን ሶፊያም ፣ ምሽቱም የመጨረሻ ንግግሩ ስላልገባቸው ፣ መልስ ሳይሰጡ ዝም ብለው ይመለከቱት ጀመር ።

“በምን ነው የምታዝነው አትነግሪኝም ? ” አለ ፣ አይኖቹን ከሶፊያ ላይ ሳያነሳ ።

“እሺ ፤ በምን ነው የምታዝነው ! ” አለች ሶፊያ ።

@OLDBOOKSPDF

"አንቺም ከባልሽ ጋር ሳትታሰሪ በመቅረትሽ ! "

"አንተ ሰው ፣ ጤና እና ደስታም መሰለኝ ዛሬ ! " አለች የውብዳር ተቆጥታ ። ሶፊያ አልመለሰችም ።

"ለምን ብሎ መጠየቅ አይሻልም ? " አለ አሳዬ ፣ እሱ ለምሽቱ ሲናገር አይናቹ አሁንም ሶፊያን እዩ ቶመለከቱ ።

"እሺ ! ለምን ? " አለች ሶፊያ ።

"ላጥፊ ተግሳጽና ቅጣት ፣ ላላዋቂ ትምህርት ስለሚያስፈልገውና ጥላሁንና አንቺ አጥፊዎቹም ፣ አላዋቂዎቹም ስለሆናችሁ ፣ ለተግሳጽ ያክል አሁን በጥላሁን የደረሰው ቅጣት ለሁለታችሁም ያስፈልጋችሁ ዋል ። ያለዚያ እንዲህ በቀላሉ የምትማሩ አይላችሁም ።

"አላዋቂዎች እንሆን ይሆናል ፤ አጥፊዎች ግን. . .እንጃ ! ምን አጠፋን ! "

"የሚያውቅ ሰው ፣ ያውም ወዳጅ ከሚያውቀው አደጋ 'ተጠበቁ ተጠንቀቁ' ብሎ ሲመክር ፣ የትባለው አደጋ በራሳችን ደርሶ ካላ ዩነው አናምንም" ብለው ፣ ወዳጆቹ የመከሩዋቸው እውነት መሆ ኑን ለማስመስከር ራሳቸውን ላደጋ አጋልጠው የሚሰጡ ሰዎች ምን ይባላሉ ? አብዶች መባል ቢቀርባቸው አጥፊዎች አይባሉም ? በኔ አስ ተያየት "አጥፊዎች መባል ያንሳችሁ እንደሆን እንጂ አይበዛባችሁም ። ስለዚህ . . . አሁን የደረሰው ወዳጆቻችሁ ሁሉ እንድትጠነቀቁበት ከመ ከሩናችሁ በጣም ቅንጡ ቢሆንም ፣ ምሳሌ ሆኖ ሊያስተምራችሁ ስለሚያ ስችል ፣ አንቺም እንድትቀምሽው የተመኘሁልሽ ለዚህ ነው ! "

"ለመታሰሩስ እሱ መታሰሩ ካልቀረ ፣ አብሬው ብታሰር እኔም እወድ ነበር ! "

"መታሰሩ ካልቀረ አይደለም ፤ 'እሱ መታሰሩ ሳይቀር አንቺም መታ ሰር ይገባሽ ነበር' ነው ያልሁ ! " አለ አሳዬ ።

አሳዬ እንዲያ ያለ መራራ አነጋገር የተናገረ ፣ በወዳጅቹ ፣ በጥላ ሁንና በሶፊያ የደረሰው አበሳ-ጐቶት እንጂ ፣ እውነቱ ያ የተናገረው የሚመኝላቸው አለመሆኑን ሶፊያ ስለምታውቅ አልተቀየመችም ።

አሳዬና ምሽቱ የውብዳር ፣ ወደ ቤታቸው ከሄዱ በሁዋላ ሶፊ አበት ውስጥ ብቻዋን ስትቀር በጣም ፈራች ። ጫንያለውና ትሁኔ በምትቀመጥበት ቤት አብረዋት አይኑሩ እንጂ ፣ ባንድ አጥር ግቢ ውስጥ አብረዋት ናቸው ። በዚያ ላይ አጥሩ ጠንካራ መዝጊያ ያለው ፣ እሱም

@OLDBOOKSPDF

ራሱ ጠንካራ ስለሆን ፤ "እውሬ ፤ ወንበዴ ፤ ወያም ሌባ ያስገባል" ተብሎ እንዳማያስጋ ቃውቃለች ፤ አጥርና መዝጊያ ከሚያግዳቸው መናፍስት ፍርሀትም ነጻ ከሆነች ብዙ ጊዜ ሆኖጥቃል ? ብቻ ይህም ሁሉ ሆኖ ከመጠን ያለፈ ፤ ምክናያቱ ይህ ነው የማትለው ፍርሀት ልብዋን ጎብቶ እያሸበረ ፈጥኖ እንዲመታ ስላደረገው ፤ ትንፋሽ አጥሮዋት ፤ ተጨንቃ ከቤት ወጣችና ትሁኔንም ፤ ጫንያለውንም ካያሉበት ጠራች ።

"ጫኔ ፤ ዛሬ ጥላዬ ስለሌለ ወንዱ አንተ ብቻ ነህና ፤ ንቅተህ እንድ ትጠብቅ ፤ በርህን አጥብቀህ ዘግተህ ፤ ግቢውን እዬዞርህ ስትጠብቅ እንድታድር አደራ ! ዛሬ እንቅልፍ ይቅርብህ ፤ ነገ ቀኑን ሙሉ ትተኛለህ " አለችና "አንቺም ንቂ " አለች ፤ ወደ ትሁኔ መለስ ብላ ።

"እሺ እሜቴ ፤ እሺ እሜቴ " አሉ ጫንያለውና ትሁኔ እዬተቀባበሉ ።

"መንቃቱንስ እንቃለሁ ፤ ብቻ . . . የሚያንቃ ነገር ባገኝ ደሞ የበለጠ ነቅቼ እጠብቅ ነበር " አለ ጫንያለው ፤ ትንሽ ፈቀቅ እንዳለ ከትሁኔ ጋር ለሶፊያ በማይሰማ ድምጽ ከተነጋገሩ በሁዋላ ።

"ምንድነው የሚያነቃ ነገር ?" አለች ሶፊያ ። ጫንያለው እንደ ማፈር አለና እንገቱን ደፍቶ ዝም አለ ።

"ምንድነው የሚለው ?" አለች ፤ ፊትዋን ከጫንያለው ወደ ትሁኔ መልሳ ።

"ለደቦ ከተገዛው አረቄ ትንሽ የተረፈውን አይቶ 'ካልሰጠሽኝ' እያለ ቢጨቀጭቀኝ ፤ 'እሜቴን ካላስፈቀድህ አልሰጥህም' ስላልሁት ነው . . . " አለች ትሁኔ ።

"ስጪው እንጂ ፤ ስጪው " አለች ሶፍያ ፤ እሳብዋን መሰብሰብ ካለ መቻልዋ የተነሳ ፤ አረቄ በማንቃት ፈንታ የሚያስተኛ መሆኑን እንኳዋ ረስታ ።

ጫንያለውና ትሁኔ ነቅተው እንዲጠብቁ አደራ ብላ ገብታ ለመተ ኛት ወደ መኝታ ቤት ብትሄድ ፤ ምኝታ ቤቱን ጥላሁን በሌለበት የጥላሁን ምስል ሞልቶት ፤ ጥላሁን ሲያነብ ፤ ጥላሁን ሲጽፍ ፤ ጥላ ሁን ከርኖቹን ጠረጴዛው ላይ ተክሎ ፤ አገጩን በመዳፎቹ ላይ አስደ ግፎ ፤ በፊት ለፊቱ እንደ ተቀመጠች ሲያወራት ፤ ጥላሁን አልጋው ላይ ተቀምጦ ፤ "ቋዋንጣ ቋዋንጣዬ ፤ ሽሮ ቃቅዬ " በሚባለው ፤ እዋ

@OLDBOOKSPDF

ቆች ልጆችን እዬኮረኮሩ በሚያስቁበት ጭዋታ ሶፊያን እዬኮረኮረ ሲያስቃት ፣ ጥላሁን እንደ ህጻን በደረቱ ታቅፎ ሲያቀብጣት ፣ ሲያቆላጣት ፣ ጥላሁን በጀርባው አዝሎ እሽሩሩ እያለ ሲያጫውታት ፣ ጥላሁንም ከቀኛዝማች ዳኘ ጋር ሲጣላ ፣ ጥላሁን በቀኛዝማች ፊት ቆሞ ከንቱነታቸውን ራሳቸውን የመውደዳቸው ብዛት ፣ ወዳጆቻቸውን ከጠላቶቻቸው ለይተው እንዳያውቁ አይነ-ልቡናቸውን የሰወረው መሆኑን በድፍረት ሲነግራቸው ፣ ጥላሁን እንዲያስሩት ከታዘዙት ፣ የቀኛዝማች አሽከሮች ጋር "እንሰርህ - አልታሰርም " በማለት ሲታገል ፣ ረብሻው ፣ ትግሉ ፣ ድብልቅልቁ አቡዋራውን ሲያጤሰው ፣ ከዚያ ጥላሁን ተሸንፎ ሲታሰር ፣ ቀኛዝማች ዳኘ ያሽከሮቻቸውንና የጥላሁንን ትግል ፈንጠር ብለው ቆመው ፣ ደስ ብሎዋቸው እዬሳቁ ሲመለከቱ ፣ ይህ ሁሉ ሲሆን ፣ ይህ ሁሉ ሲደረግ ስለ ታያት ፣ የዚህ ሁሉ ረብሻና ድብልቅልቅ ስለ ተሰማት ፣ ሶፊያ ፈራችና ፣ ልብዋ ባባና ተመልሳ ወጥታ ፣ የቀን ልብሰዋን እንደ ለበሰች ፣ ፋኑስም እንደ በራ እንግዳ ቤት ፣ እሶፋው ላይ ተቀመጠች ።

ሶፊያና ጥላሁን ከሶስት አመት በፊት የኪ ከገቡ ጀምሮ ፣ ቀን ቀን በተለያዩ ቦታዎች በሚሰሩበት ጊዜ ብቻ ተለያይተው ይውሉ እንደ ሆን እንጂ ፣ ተለያይተው አድረው አያውቁም ። ተለያይተው ያደሩበት ያ ፣ የመጀመሪያው ሌሊት ስለሆነ ፣ ሶፊያ የምትሆነውን አጣች ፤ ግራ ገባት ። አንድ የተሸሸገ እጅ መርገጫ ፣ መጨበጫ በሌለው ገደል መሀከል ወስዶ እንዳስቀመጣት ሁሉ ፣ መውጫ መውረጃው ፣ መሄጃው ጠፋት !

"ምናባቴ ባደርግ ይሻለኛል ? " አለች ፣ ከላይና ከታች ፣ ከቀኝና ከግራ ፣ በራስዋ ውስጥ የሚደበላለቀውን ያሳብ ውሽንፍር ዝም ብላ ስታይና ስታዳምጥ ዘለግ ያለ ጊዜ ከቆዬች በሁዋላ ።

"ለምን አብሬው ሄጄ አልታሰርሁም ? ለመሆኑ እሱ እዚያ አንድ ነገር ቢሆን . . . እኔ ምን ልሆን ነው ? ምን ሊውጠኝ ነው ? የለም ምንም አይሆን ! " አለች ፣ ትንሽ ዝም ብላ ስታስብ ቆይታ ። "እንዲያው የኔ አእምሮ ከክፉ በቀር በጎ መፍጠር ስለማይወድ ፣ ክፉ ሳብ እዬፈጠረ ያስፈራራኛል እንጂ ፣ እሱ ምንም አይሆን ! መቸም እጻንነት ከባልዋ የሰማችው ነገር ባይኖር . . . እንዲሁ ከመሬት አንስታ 'ነገ ፣ እጅግ ቢዘገይ ከነገ ወዲያ ሳይፈታ ቢቀር በኔ አርጊው ' አትልም ነበር ! ስለዚህ . . . ምንም አይሆን ፤ እንዲያውም ነገ ፣ ያለዚያ

@OLDBOOKSPDF

ከንገ ወዲያ ይፈታል !" አለች ሶፊያ ፤ ከፉ ከፉ ነገር ባሳብዋ እዬ መጣ ስላስፈራራት ፤ በውሸት ግጽናኛ ፍርሀትን ግባረር የምትችል መስ ልዋት ። ነገር ግን ውሸት ከውሸትነቱ በለማያልፍ ፤ እንኩዋንስ የሰ ዋን ብርቱ ፍርሀት ገንብ ማባረር አይችልም ።

ስለዚህ እሰፉዋ ላይ እንደ ተቀመጠች በራስዋ ውስጥ የሚታመ ሰው ያሳብ መንጋ እያስፈራራት ስትቸገር ፤ በዚያ መሀከል እንዳለች፣ አንድ ነገር የሰማች መሰላትና ፤ አሳብዋ የባልዋ እስራት ኅትቶ ያመ ጣውን ልዩ ልዩ አስፈሪ ነገር መመልከት ትቶ ፤ ወደዚያ ተመለሰ ። ልክ ነው ፤ አንድ ነገር ሰምታለች ! የሰማችው ነገር ፈረስ ሲጋልብ ወይም የከብት መንጋ ሲነዳ የሚሰማ ዳና የሚመስል ነገር ነው ! እያ አንድ ወደ ቤትዋ የሚመጣ ነገር አለ !

ያ ፤ የሚመጣ ነገር እዬቀረበ ፤ እዬቀረበ በመጣ መጠን ዳናው እዬ ጎላ ፤ እዬጎላ ሄደና ፤ በሁዋላ የሰው ድምጽም ይሰማት ጀመር ። ወዲ ያው ከዚያ ተነስታ ፤ ቀስ እያለች ወደ በሩ ሄዳ ሁለቱ ቀኝና ግራ የሚከፈቱ የበሩ መዝጊያዎች ሲዘጉ በሚገናኙበት ክፍት መስመር ባንድ አይንዋ አስወጥታ ብታይ ፤ በርከት ያሉ ሰዎችና አንድ በቅሎ እንደ ተጫነች እግቢው ውስጥ ባንድ ላይ እጂብ ብለው ቆመዋል ።

ሰማዩ ደመና የሌለበት ፤ ጥሩ ከመሆኑም ሌላ ፤ አዲስዋ ጨረቃ፣ እስዋም የፈራችው ነገር እንዳለ ሁሉ ትንሽ ብቻ ብቅ ብላ ቁልቁል ስታይ በምትሰጠው ብርሀን ፤ እዚያ ግቢ ውስጥ ተሰብስበው የቆሙት ሰዎች ባንድ ሰው ዙሪያ ሽብ- ረብ ሲሉ ፤ ሁኔታቸውን አይቶ እነማን እንደሆኑ ያለስህተት መገመት ይቻላል ! ብቻ እንዴት ገቡ ? ጫንያ ለው በሩን አጥብቆ ዘግቶ ፤ እንቅልፍ ሳያምረው ፤ ነቅቶ ፤ ግቢውን እዬዞረ ሲጠብቅ እንዲያደር "አደራ" ተብሎ አልነበር ? ጫን ያለውማ ከትሁኔ ጋር ሶፊያን ተሰናብተው እንደ ሄዱ ፤ ግማሽ ጠርሙስ ካቲ ካላ ለሁለት ጨልጠው ፤ አንጠፍጥፈው ፤ በያሉበት ስለ ወደቁ ፤ እን ኩዋንስ ሳይተኛ ግቢውን እዬዞረ ሲጠብቅ እንዲያድር አደራ መባሉን ሁልጊዜ በልማድ የሚያደርገውን ፤ በር መዝጋቱንም ረስቶት እንዲሁ ክፍቱን ነበር ! ጫን ያለውና ትሁኔ ያንጊዜ ፤ እንኩዋንስ የሰው ድምጽ ሊያነቃቸው ፤ አንስቶ ገደል ቢጥሉዋቸው መስማታቸውን እንጃ !

ሶፊያ ምንም እንኩዋ መጀመሪያ እኒያን ሰዎች እንዳዬች ከድን ጋጤዋ የተነሳ ራስዋን ስላዞራትና ጉልበቶችዋ ስለ ተብረከረኩ መቆ ምም ፤ አጣርቶ ማየትም አቅቶዋት እንዳትወድቅ ቶሎ መሬቱን በሁ

@OLDBOOKSPDF

ለት እጆችዋ ተመርኩዛ ቁጭ ብትል ፤ እንዲያ መሬቱን ተመርኩዛ ቁጭ እንዳለች ትንሽ ስትቆይ፤ ድንጋጤዋ አልፎ ሰውነትዋ ጸጥ እያለ፤ እየበረታችና ልብ እየገዛች ፤ ከዚያ እንዲያውም እየደፈረች ሄደች። ከዚያ እንደገና ተነሳችና ፤ እንደ ቅድምዋ ጎንበስ ብላ ባንድ አይንዋ በመዝጊያዎቹ ክፍት መስመር አሰወጥታ አግቢዋ ውስጥ ቆመው የሚዶልቱትን ሰዎች ትመለከት ጀመር ። ወዲያው እዚያ እጂብ ብለው ከቆሙት ሰዎች አንዱ ተለይቶ ወደ ሶፊያ ቤት ማምራት ሲጀምር ፤ ተጠርቶ ወደ ሰዎቹ ተመልሶ ትንሽ ከተነጋገረ በሁዋላ እንደገና እየሮጠ ወደ ቤቱ በር መጣና፤ “ እዚህ ቤት ፤ እዚህ ቤት ” ብሎ ተጣራ ። ነገር ግን መልስ አላገኘም ።

“እዚህ ቤት ፤ ክፈቱ ” አለ ሰውዬው ፤ ደገመና ። “ ባለቤቱ የለም ፤ ስለዚህ . . . አይከፈትም ! ” አለች ሶፊያ ከውስጥ ።

“ክፈቱ ነው እኮ የምለው ! ” አለ ሰውዬው ፤ ትእዛዙ ስልጣን የተደገፈ መሆኑን በሚያመለክት ያነጋገር ስልት ።

“ተው አንተ ፤ እንደሱም አይደል ! ምን ይህ . . . ”አለ አንድ ድምጽ እጂብ ብለው ከቆሙት ሰዎች መሀከል ።

“እባክዎ ይክፈቱ ፤ ጌቶች ናቸው ” አለ መልእክተኛው ፤ ወደ መዝጊያው ጠጋ ብሎ ከሹክሹክታ ምንም ያክል ከፍ ባላለ ድምፅ ።

“ ማን ጌቶች ? ” አለች ሶፊያ ፤ እያወቀች እንዳላወቀች ። “ አገረ ገዡ ” አለ መልክተኛው ፤ በሹክሹክታ ።

በሩ ሲከፈት ቀኛዝማች ዳኘ ፤ ከበዋቸው የቆሙ አሽከሮቻቸውን እዚያው በቆሙበት እንዳሉ ትተው ፤ ጋሻ ጃግሬያቸውን ብቻ አስከትለው እሶፊያ ቤት ገቡና ፤

“ እንዴት ዋልሽ ወይዘሮ ! ” አሉ ፤ ማክበር አይሉት ወይም ማሾፍ ፤ ምን መሆኑ በማይታወቅ የሰላምታ አሰጣጥ፤ ጥርሳቸው ብቻ ሳይሆን ፊታቸው ሁሉ እየሳቀ ። ሰክረዋል ባይባልም በጣም ሞቅ ብሎዋቸዋል ። ማለት የውነተኛ ሁኔታቸውን የሚገልጽ ነው !

“ ጤና ይስጥልኝ ” አለች ሶፊያ፤ ባንገትዋ ትንሽ እንደ መስገድ ብላ ።

ቀኛዝማች ሽጉጣቸውን ብቻ ነው የታጠቁ ። አንድ ጉድጉዋድ እንኩዋ ያልጎደለ ድርብ ዝናራቸውን በግራው አንግቶ ፤ ጠበንጃቸውን

@OLDBOOKSPDF

በዋና ትከሻው ተሸክሞ ፣ በዱሂዱብት የሚከተል ጋሻ ጃግሬያቸው ነው ።

"በሉ ፣ ጠበንጃዮንና ዝናሬን እዚያ ወንበር ላይ አርጉና ሂድ ፤ ሁላችሁም ወደ ራታችሁ ሂዱ ፤ ማንንም አልፈልግም ፤ ሁላችሁም ሂዱ ! " አሉ ቀኛዝማች ፣ ከሞቅታቸው የተነሳ ቃሚ በማያስፈልግበት ተቆጥተው ።

" እኔማ ልቆይ እንጂ . . . ጌቶችን ብቻዎን ትተን እንዴት ሁላ ችንም እንሂዳለን ? " አለ ጋሻ ጃግሬው ።

" ሁላችሁም ሂዱ አልሁህ ! እሣም ማነው ? አንተ ነህ ወይስ እኔ ! "

" እሺ ጌታዬ ! " አለና ጋሻ ጃግሬው ፣ የቀኛዝማችን ጠበንጃና ዝናር እንዳዘዙት አጠገባቸው ባለው ወንበር ላይ አስቀምጦ ፣ እጅ ነስቶ ሲወጣ ፣

" ከኩሉ - ሲሊት በሬት አንተና ደርቢ ፣ ማሰውና ግም ጭምር በቅሎ ጭናችሁ እንድትመጡልኝ ፤ ሌላ ሰው አያስፈልግም ፤ ሰምተ ሀል ? አያስፈልግም ነው የምለው ! "

" እሺ ጌታዬ ! " አለ ጋሻ ጃግሬው ፣ መለስ ብሎ ትእዛዙን ካዳ መጠ በሁዋላ እንደገና እጅ ነስቶ ።

" የሚጠጣ ነገር . . . ጠጅ አለሽ ? " አሉ ቀኛዝማች ፣ ጋሻ ጃግሬው ከወጣ በሁዋላ ባለቤትዎ እዚያ እንደ ቆመች እሳቸው በሶፋዎ ላይ ተዝናንተው ሲቀመጡ ።

" አለ " ብላ ሶፊያ ቶሎ ጠጅ በማንቆርቆሪያ ከሁለት ብርጭቆ ዎች ጋር አመጣችና ፣ ለመቅመስ ያክል ለራስዋ ትንሽ ቀድታ እፊቷ በጠረጴዛው ላይ አስቀምጣ ፣ የሳቸውን ብርጭቆ ሞልታ ፣ በፊታቸው እንዲሁ አጠረጴዛው ላይ ስታስቀምጥላቸው ፣ እስከትቀምስላቸው እንኳዋ ሳይጠብቁ ፣ አንስተው ባንድ ጥም ጨልጠው እ . . . ህ ፤ ከቴፒ ስነሳ ጀምሮ ውሀ ጥም እታጥኝሎ ነበር ! " አሉ ፣ ባዶውን ብር ጭቆ ሲያስቀምጡ ። ሶፊያ እንደገና ብርጭቆዋቸውን ሞልታላቸው በፊት ለፊታቸው ከጠረጴዛው ባሻገር ተቀመጠች ። መጀመሪያ ቀኛ ዝማችን እግቢዋ ውስጥ ስታያቸው ፣ ምንም እንኳዋ ለጊዜው ብት ደነግጥ ትንሽ ስታሰላስል ከቆዩች በሁዋላ ፣ ባልዋ ስለ ታሰረበት ምክ ናያት ፣ ምናልባትም ስለ ተናገራቸው ህይለ ቃል ስሞታ ሊነግሩዋት

የመጠጥ መስሎዎች @OLDBOOKSPDF ብላ ነበር ... ሰዎቹቸውን ፡ ሁሉ ሲያሰናብቱና ግብትው ከተቀመጡ ጀምሮ ሁኔታቸውን ሁሉ ስትመለ ከት ግን ፡ በጣም ፈራቻቸው ።

"ነይ እዚህ ተቀመጪ" አሉ ቀኛዝማች ፡ በቀኝ ጎናቸው በኩል ሶፋውን እየመቱ ።

"እዚህ እሆናለሁ" አለች ሶፊያ ፡ ልብዋ እስዋን እዚያ ትቶ ለመሸሽ እንደ ፈለገ ሁሉ ፈጥና እየሮጠ ።

"ነይ አልሁሽ ! አትታዘዢም ?"

"እሺ" ብላ ሄዳችና እንደ ታዘዘችው በቀኝ ጎናቸው ስትቀመጥ፥ ሽምቅቅ ብላ ከተቀመጠችበት ፡ "እይዞሽ ጠጋ በይ !" ብለው ወገብ ዋን ይዘው ወደሳቧት አስጠጉዋት ። ከዚያ እንደ ወፍራም ድጅኖ የሚ ከብድ ክንዳቸውን በትከሻዋ ላይ ጭነው ፡ ራሳቸውን ባንገትዋ ላይ ዘና አድርገው አሳረፉ ። ትኩሳትዋ እንደ እሳት ወላፈን እየተጋረፈ ትን ቀጠቀጥ ነበር !

"ምነው ? ፈራሽ እንዴ ! አሁ-ሁ-ሁ-ሁ !" ሲሉ ቀኛዝማች ራሳ ቸው አንገትዋ ላይ እንዳረፈ አፋቸውን ከፍተው ፡ ከዚያ የወጣው የመጠጥ ሽታ ባፍዋ ገብቶ ሆድ እቃዋን ሁሉ በጠበጠውና የምትሆን ውን ፣ የምትደርስበትን አሳጣት ።

"አልፈራሁም ፤ እም . . . እምኝ ነው !" አለች ፡ በውስጥዋ ከተ ነሳው ሁከት ጋር እየታገለች ። የተሰማትን ያክል ወደ ውስጥ ከመ ተንፈሱ ቀንሳ ቶሎቶሎ ወደ ውጪ ትተነፍስ በለነበረ ፣ ትንፋሽዋ ቁርጥ ፣ ቁርጥ ፣ በማለቱ እውነትም የታመመች ትመስል ነበር ! ብቻ ወደ ውስጥ አየር መሳቡን በቀነሰች መጠን የሆድዋ መሸበር እየጸና ሄደ ፤

"እይዞሽ አትፍሪ አልባላም ፤ አሀ-ሀ-ሀ-ሁ-!" አሉ ፡ አሁንም አፋ ቸውን ከፍተው ከቅድሙ የበለጠ ወደ አፍዋ ጠጋ አሉና ።

"ወባዩ ልትነሳብኝ ነው መሰለኝ ፤ አንድ ጊዜ መታጠቢያ ቤት ልግባና ከኔን ውጪ ልምጣ" አለች ሶፊያ ፡ መታገስ ስላቃታት በሽታዋ ቀኛዝማች ራሳቸው ናቸው እንጂ ፡ የወባ በሽታ ጨርሶ እያውቃትም።

" ልታመልጪ ፈልገሽ መሰለኝ ! ሁ-ሁ-ሁ-ሁ- ! አሉ ፡ ራሳቸውን ባንገትዋ ላይ እንዳሳረፉ ጉንጭዋን እየደባበሱ ።

@OLDBOOKSPDF

"ምን መጣብኝ ብሎ ማምለጥ አፈልጋለሁ ? ደግሞ ማምለጥስ የምፈልግ ብሆን በሩ በዚህ አይል ! እንዴት አድርጌ ማምለጥ እችላለሁ ? ብቻ . . . ከጠፈጠፋኝ ይንሱ አብረውኝ ይምጡ !"

"እሺ ! እንዲያ ይሻላል !" ብለው ቆኞዝማች ፣ ተነስተው አብረዋት እስከ መታጠቢያ ቤቱ በር ድረስ ሄደው ፣ እስዋ ስትገባ እሳቸው በሩን ይዘው ይጠብቁ ጀመር ። የመታጠቢያ ቤቱ መድረኛ በወጥ ቤቱ ገብቶ በመሆኑ የወጥ ቤቱም ፣ የመታጠቢያ ቤቱም በሮች ከተከፈቱ ቆኞዝማች ከቆሙበት ፣ ከመብል ቤት ሶፋያ እስከ ገባችበት ፣ እስከ መታጠቢያ ቤት ወለል ብሎ ይታያል ። ስለዚህ መታጠቢያ ቤት ለመግባት የሰጠችው ምክንያት እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ፣ የሁሉንም በር ክፍት እንድትተው ስላዘዙዋት ፣ እንደ ታዘዘችው አደረገች ።

"ምንም እንኳ ቆኞዝማችን አመብል ቤት እንደ ቆሙ እዚያ ትታቸው ብትገባ ፣ ከእሳቸው አብሮዋት ገባ ! ነገር ግን ብቻውን አደለም ፣ ከጥላሁን ስእል ጋር ነው ! ጥላሁን እሳቸው ቤት ታስሮ ፣ ኩርትም ብሎ ተቀምጦ ፣ ከሱ አሥራት ይልቅ የስዋ ጭንቀት እያሰቃየው ሲያለቅስ ፣ እሳቸው ኢስዋን በጎኗቸው አስቀምጠው ፣ ራሳቸውን ጫንጉትዋ ላይ ጥለው ፣ ጉንጯዋን እየዳበሱ ፣ አፉቸውን ከፍተው እዩሏቱ ፣ ሲዝናኑ ታዩዋት ! እሩን አስሮ እስዋን ለመድፈር መምጣት ያው የሱም ፣ የስዋም ከትዳታቸው ፣ ከውርደታቸው አንዱ ክፍል መሆኑ ታያትና ፣ ልክ የኤሌክትሪክ ሽቦ እንደ ነካች ከቆመችበት ፣ ከግርዋ ተነስቶ እስከ ራስዋ ፣ ሰውነትዋን በሙሉ የሚወር ነገር ተሰማት ! ወዲያው ከዚያ ቶሎ ለመውጣት ፈለገች !

መጀመሪያ እጆችዋን ፣ ከዚያም ፊትዋን ቶሎ ቶሎ ታጥባ ስታበቃ ፣ ካንድ ብልቃጥ ከኒን አውጥታ የዋጠች ለመምሰል ባዶ እጅዋን ወደ ተከፈተ አፍዋ ወርውራ ፣ ግማሽ ብርጭቆ ውሀ ዋጠችና ፣ የዋጠችው ክኒን እንደ መረራት ሁሉ ፣ ቆኞዝማች እንዲያዩዋት አድርጋ ራስዋን አንገፈገፈች ። ከዚያ አሁንም ቆኞዝማች እንዲያዩዋት አድርጋ ፣ መሀከለኛ መጠን ባለው ጠርሙስ እዚያው የተቀመጠ አዶኮለኝ ስለ ነበረ ፣ በዚያ መጀመሪያ እጆችዋን ፣ ከዚያ ራስዋን ፣ ከዚያ ፊትዋን ፣ ከዚያ አንገትዋንና ደረትዋን አሻሽታ ስታበቃ ፣ ሽቶውን ይዛ ወጣችና ፣ " እጅዎን ያምጡ ! " አለች ፣ ፊትዋ ሁሉ በውሸት ደስታ ፈገግታ ሞልቶ ።

"ምንድነው ?" አሉ ቆኞዝማች ፣ ግራ እጃቸውን እንደ ታዘዙት ከፍተው ሲዘረጉ ።

" ሽቶ ነው ! "@OLDBOOKSPDF

"እንዴ ! ታዲያ ወንድ . . . ቤት ይመስል ሽቶ ይቀባል ? " አሉ ቆኛዝማች ። ታዲያ ሲያብሉ ነው እንጂ ፣ ሽቶ በጣም ከመውደዳቸው የተነሳ ሳይቀቡ ወጥተው አያውቁም ።

" ከሴት ጋር ሲሆን ቢቀባ ነውር አደለም ! " አለችና ሽቶውን በመሀል እጃቸው ቀድታላቸው እሳቸውም እንደሰዋ ፣ ራሳቸውን ፊታቸውን ና አንገታቸውን ሲያሻሹ ፣ " እንግዲህ የተቀዳ ጠጅዎን እስኪጨርሱ አልጋውን በቅጥ በቅጡ ላርገው " ብላ እዚያው እንደ ቆሙ ትታቸው ወደ መኝታ ቤት ስትገባ ፣ " በሩን እንዳትዘጊ " አሉ ቆኛዝማች ፣ ሞልቶ ወደሚጠብቃቸው የብርጭቆ ጠጅ ተመልሰው እሶፋው ላይ ሲቀመጡ ። " አልዘጋም " አለች ሶፊያ ።

ከዚያ በሩን ቆኛዝማች እንዳዘዝዋት ክፍት ትታ እያዩዋት አልጋ ስታነጥፍ ፣ እግርጌ ያለውን ወንበር ወደ ራስጌ ፣ የራስጌውን ወደ ግርጌ ስታዘዋውር ፣ ያልጋ ራስጌ ጠረጴዛዋን ካልጋ ስታርቅ ፣ መልሳ ስታስጠጋ ፣ ሌላም እንዲሁ ለምን እንዳደረገችው ከስዋ በቀር ለማንም ሊገባ የማይችል ነገር ሁሉ ስታደርግ ቆይታ ወጥታ ፣ ሁለት እጆችዋን ወደ ሁዋላዋ በዳሌዎችዋ ላይ አሳርፋ ፣ ቀስ እያለች ወደ ቆኛዝማች ስታመራ ፣ ቀና ብለው ከማየታቸው ፣ እኒያ ወፍራም ፣ ረዥምም ሰው ፣ በቅጽበት እንደ ኩዋስ ቁጥር አሉና ፣ ልክ እንደ ወፍ በረው ተነስተው ፣ ሽጉጣቸውን ምን ጊዜ ካፎቱ እንዳወጡት ሳይታወቅ በደረትዋ ላይ ደግነው ፣

" በይ የያዝሽውን ቀስ አርገሽ እመሬት አስቀምጪ ! " አሉ ። ያን ጊዜ ፊታቸው ሲባላ የኅመገር ነብር እንጂ ፣ የሰው ፊት አይመስልም ነበር ! ሶፊያ የቆኛዝማችን ሽጉጥ እንዲያ በደረትዋ ላይ ተደግኖ ፣ ከፉ ፊታቸው እንዲያ ከምን ጊዜውም የባሰ ከፍቶና አስፈርቶ ስታይ ፣ የታዘዘችውን መፈጸም እንዳለባት ረስታ ፣ በቆመችበት እንዳለች ዝም ብላ ትንቀጠቀጥ ጀመር !

" የያዝሽውን ወያፊት ሳታመጪ ፣ እዚያው በሁዋላሽ እንዳለ ፣ ቀስ አርገሽ ፣ እመሬት አስቀምጪው አልሁሽኮ ! " አሉ ቆኛዝማች እንዲያ የኅመገር ነብር እንደ መሰሉ ። ሶፊያ የያዘችውን እንደ ታዘዘች ቀስ አድርጋ አስቀመጠች ። የያዘችው ሽጉጥ ነበር - የጎረሰ ሽጉጥ !

"ነይ ወዲህ ! " አሉ ፣ በቀኝ እጃቸው ሽጉጣቸውን በደረትዋ እንደ ደገኑ ፣ ግራቸውን ወደስዋ ዘርግተው ። ሶፊያ ከቆመችበት

@OLDBOOKSPDF

ወደ ፊት ይሁን ወደ ሁዋላ አልተንቀሳቀሰችም ። በቆመችበት እንዳ ለች ድርቅ ብላ ዝም አለች ።

“ አትመጪም ? ” አሉ ደገሙና ።

“ አልመጣም ! ” አለች ፤ ጊዜያዊው ፍርሀት ሲያልፍ ንዴት ቁተክተ እያንቀጠቀጣት ።

“ የታዘዝሽውን መፈጸምሽ ሳይቀር ፤ ውርደት ባትጪምሪ ይሻ ባል ! ”

“ እኔ ደግሞ እርስዎ የሚፈልጉትን ፤ የርስዎን ፈቃድ ከመፈ ጸም የገሰ ውርደት ይኖራል ብዬ የማላምን መሆኔን ይወቁት ! ደግሞ ሲሳው ፤ እንዲያውቁት የምፈልገው ነገር እኔን ገድለው በሬሳዮ ላይ የሚፈልጉትን ይፈጽሙ እንደሆን እንጂ ፤ በህይወቴ እያለሁ ጉልበ ትዎም ሆነ ስልጣንዎ ፤ ምንም ቢሆን ወራዳ ፈቃድዎን ሊያስፈጽ ሙኝ የማይችል መሆኑን ነው ! ”

“ እንደሱት ! ”

“ እንዲሀ ነኖ ! ”

“ እቅምሽን አታውቂም ለካ ! እንዲያው ነው ተምሬአለሁ የም ትይ ! ” አሉና ቀኛዝማች ፤ ወደ ፊቷ ፊመድ ብለው ፤ በግራ እጃ ቸው አንድ እጅዋን ይዘው መጎተቻ ቢሞክሩ አልችላቻ አሉ ። “ እሀ ሁሁሁ ! ኧረ እውነትም ብርቱ ናት ! ” አሉና ፤ እንደ ልማዳቸው አፋ ቸውን በሰፊው ከፍተው የውሸት ሳቅ አዩላቁ ፤ ሽጉጣቸውን በመ ብል ጠረጴዛው ላይ አስቀምጠው ፤ ቀኝ እጅዋን በሚያሰቅቅ ጭካኔ በሁለት እጆቻቸው ጨምዘው ፤ ሸርበው ፤ በጭኖቻቸው መሀከል ቆል ፈው ከያዙ በሁዋላ ፤ አንገትዋን ወደፊቷ ካቀረቀረችበት በሁለት እጆ ቻቸው ወደ ሁዋላ መልሰው አፍዋን ሳሙዋት ።

መቸም ሰው የመጨረሻ ሀይሉ ምን ያክል እንደሆነ የሚታወ ቀው ፤ ከሁሉ አብልጦ ከሚጠላውና ከሚፈራው በሚሸሽበት ጊዜ ነው ! ሶፊያም ከኒያ ፤ እንደ ጣእረሞት ከጠላቻቸውና ከፈራቻቸው ሰው እጅ ለማምለጥ ፤ በያንዳንዱ ክፍለ አካልዋ ያለ ሀይልዋን ሁሉ ባንድ ላይ አጠራቅማ ፤ ባንድ ላይ አስተባብራ ፤ ነጥቃቸው የሄደች በትን ሁኔታ ያዩ ሰው ፤ ያ ሀይል ፤ ከዚያች ትንሽ ልጅ ፤ ያውም ሴት ፤ የተገኘ ነው ብሎ ማመን ያስቸግረዋል ! እንዲያ ባለ አስደናቂ ሀይል ፤ እንዲያ ባለ ሴላውን ቀርቶ ቀኛዝማችን ራሳቸውን ባስገረመ

@OLDBOOKSPDF

ሆዴል ፣ ነጭዎቻቸው በፊት ሰፊታቸው ቆመችና ፣ እጆቿን ሲሰመቁቆ ሆድዋ ተጸይፎ ከውስጡ ያስወጣው የሚኮመጥጥ ፈሳሽ ነገር ፣ ባጭዋ ዋልቶ ስለ ነበረ ፣ ተንጠራርታ " ቶ . . . ፍ ! " ስትለው ፣ ፊታቸውንና የፊት ክፍል አካላቸውን በሙሉ አለበሳቸው ! በፊታቸውና በፊት ክፍል አካላታቸው ተፋችባቸው !

"እንዴ !" አሉ ቀኛዝማች ፣ ደንግጠው ! ከዚያ በሁዋላ አፋቸው ሌላ ቃል አልተናገሩም ። ከዚያ በሁዋላ ተናጋሪው ፣ የፊልቶን የሚገልጹበት እነቸው ሆኑ ! አፋቸው እስከዚያን ጊዜ ድረስ አባብሉም ፣ መክርም ፣ አስፈራርተም ፈቃድ ፈጻሚ ሊያደርጋት በላል ቻለ ፣ እንዲያውም ለልብዋ ልብ ሰጥቶ ወደ ማዋረዱ ፣ ወደ መሳደቡ ፣ በላያቸው ወደ መትፋቱ ስላደረሳት ፣ ከንግዲህ ወዲያ ለሚቀጣው ለሚበቀለው ፣ ለነቸው ማስተላለፍ አለበት ! ስለዚህ ያ ብርታቱ እንዳን በላ መዳፍ መሆን የሚነገርለት እነቸው ፣ ያ "የብረት መንዶ ይሰብራል ! ቁጥጥኝ አንበሶ እንደ ኩዋስ ይወረውራል" እየተባለ ልዩ ልዩ አስደናቂ ትንግርት የሚነገርለት ፣ የሚተረከለት ብርቱ እነቸው ፣ እዚያ በፊት ሰፊታቸው ቆማ በንዴት የምትንቀጠቀጠዋን ሴት ልጅ በሙሉ ኃይሉ እፊትዋ ላይ መአቱን አወረደባትና ከመሬት ደባለቃት ! ብቻ ያ ፣ የወረደባት መአት አፈዘዛት ፣ አደነዘዛት እንጂ አላመማትም ። "እምቡዋለሌ" ብላ እንደ ወደቀች ሁሉ እዚያ ቅድም ባስቀመጠችው ሽጉጥ ላይ በወደቀችበት እንዳለች ፣ መሬት ይዛት እንደ ተጠፋ የንዝርት ቆርቾ ፣ የንዝርት ራስ ስትሽከረከር ብዙ ጊዜ ቆይታ ፣ ትንሽ በትንሽ ጸጥ እያለች ነፍስዋን እየገዛች ስትሄድ አይኖችዋን ገለጥ ብታደርግ ፣ ቀኛዝማችን እዩ ተሳደቡዋ ፣ እዩ ቂራግሙም ባልተበላሸው የልብሳቸው ክፍል የተበላሸ አካላታቸውንም ፣ ልብሳቸውንም ሲጠራርጉ አየች ። ወዲያው ምንም እንኩዋን የወደቀችበት ቦታ የተነጠፈ ቢሆን ፣ ጎንዋን አንድ የሚቆረቁር ነገር ስለ ተሰማት ፣ ቀኝ እጅዋን ወደዚያ ፣ ወደ ቆረቆራት ነገር ብትሰድ ፣ ያን ከምኝታ ቤት አምጥታ ፣ እዚያ ቀስ አድርጋ እንድታስቀምጥ ተገዛዛ ያስቀመጠችውን ሽጉጥ አገኘች ! ከዚያ ቀስ አርድጋ እንዳስቀመጠች ቀስ አድርጋ አንስታ ፣ እምናቸው ላይ እንዳነጣጠረች እንኩዋ ሳታስተውል ምላጭ ከመሳብዋ ፣ ቀኛዝማች ዳኘን ልክ እንዳንበሳ አጉራርተው ፣ ወደ ላይ ጉነው ፣ ተመልሰው ሲወድቁ አዩች !

" ዳኘ የግፉው ጌታ ! አንድ ብቻውን መቶ . . . የሚ . . . መታ መታ !" አሉ ቀኛዝማች ፣ አጉራርተው ከወደቁ በሁዋላ በሁሉተኛው እንደ ማግለል ብለው ።

@OLDBOOKSPDF

" ሶፊያ በሰራችው ወግ፡ ላ ከመደንገጥዋ የተነሳ ፣ ሽጉጡን የተኰሰው ቀኝ እጅዋ እንደ ተዘረጋ ፣ በግራ እጅዋ ምስጢር እንዳያወጣ የፈራች ይመስል አፍዋን እፍን አርጋ ይዛ ፣ ያቆሰለቻቸው ሰው እየ ተንፈራገጡ በደም ሲዋኙ ፍዝዝ ብላ ትመለከታቸው ነበር ! በሁዋላ ብቻ ራሳቸውን ቀና እያደረጉ ፣ ተመልሰው እየወደቁ ፣ ለመነሳት ሲታገሉ ሲታይ ፣ ፍርሀት ገባትና ፣ ሽጉጥዋን ብቻ እንደ ያዘች ወጥታ ካጥሩ ውጪ ባለው ትልቅ የአም ዛፍ ስር አጥሩን በሁዋላዋ ፣ ዛፉን በፊትዋ አድርጋ ተሸሽጋ ስትጠባበቅ ብዙ ቆይታ ፣ በቤቱ በኩል ድምጽ የሰማች መሰላትና አንገትዋን ቀና አድርጋ ታንቃቃ ጀመር ። ልክ ነው ፤ ቀኛዝማች ናቸው ! ቀኛዝማች ዝናራቸውን ከግራ ትከሻቸው በደረታቸውና በጀርባቸው አሳልፈው ከቀኝ ብብታቸው ስር ፣ ጠበንጃቸውን ከቀኝ ትከሻቸው እንዲሁ በደረታቸውና በጀርባቸው አሳልፈው ፣ በግራ ብብታቸው ስር አድርገው ፣ አመሳቅለው እንግተው ፣ በቀኝ እጃቸው የጎረሰ ሽጉጣቸውን ፣ በግራ እጃቸው የተዘነጠለ ሆዳቸውን አፍነው ይዘው ፣ እዬተራገሙም ፣ እየተሳደቡም ከቤት ወጡ ! ሶፊያ ካሁን አሁን መጡብኝ እያለች ፣ ልብዋ ከንፍ አውጥቶ ከውስጥዋ ሊበር እንደ ፈለገ ሁሉ ሲንገፈገፍ ፣ እዬተቀመጡ፣ እዬተነሱ ፣ የቤቱን ጥግ አንድ ጊዜ ዞረው አይተው ፣ እንዲሁ እዬተቀመጡና እዬተነሱ የቤታቸውን መንገድ ይዘው ሄዱ ።

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፳፰

# ሞቴ የሚመጣቴን ያክል አያሳዝነኝም!

ጥላሁን ከንቅልፉ ሲነቃ መኝታ፣ ያ ጨለማ ቤት አይን ቢወጉ የማይታይበት፣ አንድያውን ጨለማ፣ የጨለማ ጨለማ ሆኖ ስላገኘው "ው . . . ! አቤት ! አቤት ! አቤት ! ምን አይነት ጨለማ ነው እባክ ችሁ ? አልም፣ ጭልም ያለ ጨለማ፣ ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ፣ በጦር የማይ ቀደድ፣ ወፍራም ጨለማ ! ሀ ሀ ሀ ሀ ! እንዴያ እንጂ ! ደሞ ብሎ ብሎ ጨለማ ወፍራም ይባል ጀመር!" አለና እሱ እራሱ እንዳመጣው ለጨ ለማ በሰጠው የማይገጥም ቅጽል ብቻውን ሲስቅ ቆዩ። ከዚያ በጀ ርባው እንደ ተንጋለለ ከጨለማ ጋር የሸሸገኘ ጭዋታ እንደሚጫወት ሁሉ አይኖቹን በሁለት እጆቹ እዩሸፈነ ሲገልጽ፣ እዩሸፈነ ሲገልጽ፣ ድንገት አንድ የሚንቀሳቀስ ከብ ብርሃን እጣራው ላይ ያዩ መሰለውና አይኖቹ እንደ ተገለጹ ፍጥጥ ቢያደርግ፣ ብርሀኑ ከፊተኛው ሰፍቶ ታዩው።

"እንዴ! አይንን ሸፍና ቆይቶ ሲገልጹ ብርሃን ያታያል!" አለና አይኖቹን አሻሽቶ ቢገልጽ፣ ያ፣ ብርሃን በመጥፋት ፈንታ እንዲያውም ይግረምህ ብሎ ከጣራው ወርዶ እወለሉ ላይ፣ ባጠገቡ ዱብ ሲል፣ ጥላሁን "እንዴ!" ብሎ በድንጋጤ ከተንጋለለበት ብድግ አለና፣ ባጠ ገቡ የወደቀውን ከብ ብርሀን ሊይዝ ቢሞክር፣ ብርሀኑ ዘሎ እንደገና እጣራው ላይ ወጣ። ከዚያ እያንጠሩ እንደሚጫወቱበት ኳኖስ በወለ ሉና በጣራው መሀከል፣ "ብድግ ዱብ፣ ብድግ ዱብ" እያለ ሲጫወት ቆይቶ በመጨረሻ ጣራውንም፣ ወለሉንም ትቶ፣ በበሩ አንጻር፣ እግድ ግዳው ላይ ጸጥ ብሎ ተቀመጠ። "ይህ ምን ጉድ ነው? ታምራት የሚ ሉት ነገር እውነትም አለ ማለት ነው? ታምራት ላይ ነው? ወይስ . . . ደህና ባልሆን ይሆን?" አለ ጥላሁን፣ ባዩው እንግዳ ነገር ልቡ ትንሽ እንደ መሸበር ስላለ፣ አይኖቹን ፍጥጥ አድርጎ በፊት-ለፊቱ፣ እግድግ ዳው ላይ ጸጥ ብሎ ተቀምጦ ቁልቁል የሚመለከተውን ብርሃን ሲመ ለከት ቆይቶ።

ወዲያው መዝጊያው ተደጋግሞ ተመቶ የምሥራቁ በር ሲከፈት፣ ጠበንጃውን በቀኝ ትከሻው አንግቶ፣ በግራ እጁ ፋኑስ ያንጠለጠለ

@OLDBOOKSPDF

ሰው ገባና ፣ "ጤና ይስጥልኝ ጌታዬ ! እግዜር ያስፈታዎ"አለ ፣ በጎ ምኞቱን በቃል ሲገልጽ ወዲያው እጅ ነስቶ ። ጥላሁን "ብርሀኑን ተከትሎ ቃምራት የሚያሳይ መላክ ፣ ወይም አንድ አይነት መንፈስ ይመጣ ይሆን?"ብሎ ልቡ ፈጥኖ እዩመታ ሲጠባበቅ ፣ በዚያ ፈንታ ዘበኛው ፋኑሱን ይዞ ሲገባ ስላዩ ፣ ያ ተንኮለኛ ብርሀን ከተንጋለለበት አስደንብሮ ያስነሳውና በቃምረት ፣ ወይም በምትሀት እፊቱ እዩዘለለ ሲያሳዩው የቆዩው ትርእይት ቃሰበውና ፣ ሳቅ መጥቶበት፡ እንዳይስቅም ሰውዩው እብድ እንዳይለው ስለፈራ ፣ አፉን በጁ ይዞ ከሳቁ ጋር ሲታገል ፣ ለዘበኛው ሰላምታና የበጎ ምኞት መግለጫ መልስ እንኳ ሲሰጥ አልቻለም ።

ያ ለጥላሁን ቃምራት ሲያበስር የመጣ መሰሎት የነበረ ፣ ክብ ብርሀን ዘበኛው ከያዘው የፋኑስ መብራት አበሩ መቃን ላይ በነበረ አንድ ክብ ቀዳዳ አልፎ የገባ ብርሀን ነበር ። ዘበኛው ፋኑሱን አንጠልጥሎ ይዞ ፣ ገና ከሩቅ ሲመጣ እርምጃውን ተከትሎ ያንጠለጠለው ፋኑስ ከፍና ዝቅ ይል ስለነበረ ፣ በመቃኑ ክብ ቀዳዳ የገባው ክብ ብር ሀንም እንደ ፋኑስ ከፍና ዝቅ እያለ ፣ በግራውና በወለሉ መሀከል እዩዘለለ ይጫወት ነበር! ጥላሁን ያንሰት የሆነውን ሲያስብ እስከ ብዙ ጊዜ ድረስ ይገረምም ፣ ይስቅም ነበር !

"ደንብ ስለ ሆነብኝ ነውና እባክዎ አይቀየሙኝ" አለ ዘበኛው ጠበንጃውን እንዳነገተ ፋኑሱን በሁለት እጆቹ በፊት ለፊቱ ይዞ ወደ ጥላሁን ቀረብ አለና ።

"ምን ?" አለ ጥላሁን ።

"እስረኛ ጠባቂዎች ስንለዋወጥ . . . እስራቱ በትክክል መሆኑን ማየቱ ። እርስዎን በመጠርጠር ሳይሆን ፣ እንዲያው . . . ደንብ ስለሆነ ግዴታ ስለሆነ ነው ።"

"እ . . . ! እሺ አየው!"አለ ጥላሁን ፣ ጋቢውን ገለጥ አድርጎ የታሰሩ እግሮቹን ወደ ዘበኛው ዘረጋና ። ዘበኛው መብራቱን ቀረብ አድርጎ ፣ የጥላሁንን እግርችና የታሰሩበትን ከባድ ብረት አገላብጦ አይቶ ፣ ምንም የሚያሰጋ ነገር አለመኖሩን ካረጋገጠ በሁዋላ ፣

"አሁን እንዳልሁ ቶሎ እንዲያው . . . ለደንቡ ያክል ፣ ደግሞ ጌቶቹ ባያዩ አምላካቸው ያያል በማለት ነው እንጂ ፣ እርስዎ በዚህ የሚጠረጠሩ ሆነው አይደለም!" አለ አሁንም ደገመና ።

"ይገባል እንጂ ፣ ይገባል !" አለ ጥላሁንም ። ዘበኛው ፋኑሱን ከወጋግራዎቹ ባንዱ ላይ በተመታው ሚስማር ሰቅሎ ፣ ጥላሁንን እጅ

ነስቶ ፣ ወዲያውም @OLDBOOKSPDF [illegible] እንዲያስፈቃው በጎ ምኞቱን ገልጾ ለት ወጣ ። ከዚያ ፣ ትንሽ ቆይተው ፣ አንድ ወይዘሮ ነጭ ኩታ ተከናን በው ፣ በሁዋላቸው ቀሚስ የለበሰ መሶበ-ወርቅ በቀኝ እቅፏዋ ፣ ሁለት የተሰኩ ብርጭቆዎች ተደፍተው የከደኑት ጠርሙስ በግራ እጅዋ ፣ የያ ዘች ሴት ተከትላቸው መጡ ። የምኢራቡ በር መዝጊያ ከውስጥ በመ ሽጎሪያ አልተዘጋ ኖሮ ፣ ወይዘሮዋ ገፋ አድርገውት ገብተው አጠገቡ ሲደርሱ አይቶ ፣ ጥላሁን እንደ መደንገጥ አለና የታሰሩ እግሮቹን ለማ ዘዝ በቻለ መጠን ቶሎ ተነስቶ ቆመ ። የቤቱ እመቤት ወይዘሮ እጸገ ነት ነበሩ ።

"ጤና ይስጥልኝ ፤ እግዚአብሄር ያስፈቃህ ፣ አቶ ጥላሁን ። ለምን ትነሳለህ ? እባክህ አትነሳ!" አሉ ወይዘሮ እጸገነት ፣ ከንብንባቸውን አው ርደው ።

"አሜን ፤ ጤና ይስጥልኝ" አለ ጥላሁንም እንደ ቆመ የታሰሩ እግ ሮቹን ዘቅዘቆ እያዩ ።

"በይ ፣ የያዝሽውን እዚህ አስቀምጪና እጥግ ተቀምጠሽ ፣ ወዲህ የሚመጣ ሰው ያዩሽ እንደሆነ ቶሎ መጥተሽ ንገሪኝ!" አሉ ወይዘሮ እጸገነት ፣ የተከተለቻቸውን ሴት ፣ ውብነሽን ። ውብነሽ ከጥንት ባላቸው ጋር ሳሉ ጀምራ አብራቸው የምትኖር ፣ በጣም ታማኝ አሽከራቸው ናት ። ከዚያም የተነሳ ከባቸው ጋር ካልሆነ ብቻዋን ከሌላ ሰው ተገና ኝታ መነጋገር የማይፈቅድላት ፣ ልክ እንደባቸው እስረኛ ናት ።

"እሺ እሜቴ" አለችና ውብነሽ ፣ መሶበ-ወርቁንም ፣ ብርጭቆ ዎች የተከደኑውን ጠርሙስም ፣ እንደ ታዘዘችው በተነጠፈው ሰሌን ላይ አስቀምጣ ፣ እጥግ ተቀምጣ ለመጠበቅ ወጣች ። ከዚያ ወይዘሮ ትጸገነት ኩታቸውን ከላያቸው ጠቅለል አድርገው ፣ ከጅ ቦርሳቸው ጋር ባንድ ወገን አሰሌኑ ላይ ጣል አደረጉና ፣ እንዱን ባርጩማ ትትተው ሲቀመጡ ፣ አዩሩን በሁለት እጆቻቸው ወደ ግልጥ ደረታቸው እያ ራገቡ ፣

"ኧሁ ፤ እሁ ፤ እሁ ዛሬ እንዴት ይሞቃል! ተቀመጥ ፣ አቶ ጥላሁን" አሉ ። ወይዘሮ እጸገነት ፣ ሲገቡ ተከናንበውት የነበረውን ነጭ ኩታ ከላያቸው ጠቅልለው ወደ ጎን ፣ እሰሌኑ ላይ ሲጥሉ ፣ ከኩታው በታች የለበሱት ስስ ጥቁር ሀር ቀሚስ ፣ ገላቸውን በመሸፈን ፈንታ ለማሳ ዩት የተለበሰ ይመስል ፣ ጥቁረቱ ቅላታቸውን ይበልጥ አጉልቶ ፣ ስስ ነቱ የሰውነት ቅጥና ቁርጣቸውን ይበልጥ አጉልቶ ያሳይ ነበር! ቀሚሱ እጅጌ - የለሽ ፣ እንገትዩው ሰፊና ፣ ባት መለስ ስለሆነ ፣ አንገት

@OLDBOOKSPDF

ደረታቸው ፣ ክንዶቻቸው እስከ ትከሻዎቻቸውና ባቶቻቸው እስከ ተረከዞቻቸው ፣ እንዲያውም ራቁታቸውን ነበሩ ። እንዲያ ኩታቸውን ከላያቸው ጠቅልለው ጥለው ሲቀመጡ ፣ ጥላሁን እዚያ አይኖቹን በታሰሩ እግሮቹ ላይ ተክሎ እንደ ቆመ ፣ ምንም እንከኑ ቀና ብሎ ባያይ ፣ ያለባበሳቸውንም ፣ ያቀማመጣቸውንም ሁኔታ ሁሉ ስሜቱ ነገረውና ፣ እንዲሁ ሳያስበው ፣ አእምሮው ሳይሆን የወንድነት ደመ-ነፍሱ ብቻ ስላዘዘው ፣ አይኖቹን ከታሰሩ ንግሮቹ ላይ አንስቶ ከፊል ርቃናቸውን እፊቱ በተቀመጡት ወይዘሮ ላይ ጣለ ። ወዲያው ፣ እኒያን አይኖች ፣ የኒያ ወይዘሮ የገላ ጥራት ፣ ውበታቸው ፣ እንዳጥበረበራቸው ሁሉ ፣ እየተርገበገቡ በቅጥበት ተመልሰው ፣ የሚያርሱበት ቅጡ ጠፍቶዋቸው ወዲህ ፣ ወዲያ ሲቅበዘበዙ ቆዩና በመጨረሻ እግር ብረቱ ላይ አረፉ ።

"ምነው ተቀመጥ እንጂ !" አሉ ወይዘሮ እጸገነት እንደገና ፣ በሚያባብሉ አይኖቻቸው የሱን አይኖች እየፈለጉ ። የሱ አይኖች ግን ምን ውበት ፣ ምን እንደ ጸሀይ ጨረር የሚያጥበረብር ውበት ዳግመኛ ደፍረው ፊት-ለፊት ማየት ስላልቻሉ ፣ እዚያው በታሰረበት እግር ብረት ላይ እንደ ተጣበቁ ፣ እግር ብረቱ በሚፈቅድለት መጠን እግሮቹን እያፈጋፈገ ወደ ሁለተኛው ባርጩማ ሄዶ ተቀመጠ ።

"ለምን መጡ ?" አለ ፣ ለመስማት በሚያስቸግር ዝቅተኛ ድምፅ እንደ ተቀመጠ ።

"ዛሬስ . . . ለማየቱም ተጸየፍኸኝ ?" አሉ ወይዘሮ እጸገነት ጥላሁንን የጎድን እያዩ ።

"ለሶፊ እንዲልኩልኝ የለመንሁዎ መልእክት ደርሶዎት ይሆን ?" አለ ፣ የጠዩቁትን እንዳልሰማ ፣ አንገቱን ሳያቃና እግር ብረቱን ብቻ እየተመለከተ ።

"ለጠየቅሁህኮ መልስ አልሰጠኸኝም !" አሉ ወይዘሮ እጸገነት ፣ ፈገግታቸው ከሙቀቱ ቀዝቀዝ ሲል በፊታቸው እየታዩ ።

"ምን መልስ የሚያሻው ጥያቄ ጠየቁኝ ?"

"ለማየት እንከኑዋ ተጸየፍኸኝ ወይ ? ብዬህ ነበር ። ይህን ያልሁ በትም . . . ከገባሁ እስካሁን ቀና ብለህ ስላላዩኸኝ ነው ፤ እንዲያውም ለምን መጣሽ አልኸኝ ።"

"ይህ ቀልድ ነው ፤ ይልቅ እባክዎ በቁም ነገር የጠዩቅሁዎን ይንገሩኝ ።"

@OLDBOOKSPDF

"በል እሺ ራትህን ብላ ፤ በሶሬ ልኬቶች መጥታ ፣ እኔ እንዳሰር ፀሀ ሁሉ ስትሙህለኝ ውላ ነው የሂደች ፤ ራትህም እስዋ ያመጣች ልህ ነው ፤ ምንጣፉና ጋቢውም ደርሶህል " አሉ ፣ ከሙቀቱ ቀዝቀዝ ሲል ይታይ የነበረ ፈገግታቸውን አሁን የቅርታ ጥላ ትንሽ እንደ ማጥለል አድርጎት ።

"ታዲያ . . . ከመታሰሬ በቀር ሌላ ክፉ ነገር እንዳልደረሰብኝ ነገሩልኝ ?" አለ ፣ ቀና ብሎ ወይዘሮ እጸገነትን ፊት - ለፊት እያየ ።

"ጥዋት ልጅ ልኬባታለሁ ፤ ሁዋላም እስዋ ራስዋ ይህን ራትና ምንጣፍም ፣ ልብስም ይዛ ስትመጣ ነግሬያታለሁ ። እንዲያውም "እጅግ ቢበዛ ከሶስት ቀን የበለጠ የታሰረ ኀንደሆነ እኔን ውቀሽኝ" ብያት ነበር ። ነገር ግን እንኩዋንስ ልታምነኝ በቅጡ የሰማችኝም አይመስለኝ ፤ እኔ ስናገር በመስማት ፈንታ እብራኝ ትናገራለች ፤ ወይም . . . ታለቅሳለች ።"

"አዎን አታምንም ! እንዴት ትመን?" አለ በሻከረ ድምጽ ፣ መብ ላቱን ትቶ አይኑን ሳያረግብ ፊት - ለፊት ሲመለከት ቆዩና ።

"አሁን ራትህን ብላ ፤ ነገ ፣ ያለዚያም ከነገወዲያ ስትፈታ ታም ናለች!" አሉ ፣ ብርዝ በሁለቱ ብርጭቆዎች ቀድተው ፣ የጥላሁንን እፊቱ አስቀምጠው ፣ የራሳቸውንም ቀምሰው እፊታቸው ሲያስቀምጡ ።

"ነገ ፣ ወይም . . . ከነገወዲያ ፤ በምን . . . እንዴት . . . እፈታ ለሁ ?" አለ ፣ የወይዘሮ እጸገነትን ራቱን እንገቱ ደረትና ግራ ቀኝ ክን ዶች አትኩሮ ሲያይ ፣ ጊዜያዊ የልብ መሸበር አሳቡን ስላወከው የሚና ገረው ተደናገረውና ።

"ግዴለም ትፈታለህ ፤ እኔ አስፈታሀለሁ !" አሉ ወይዘሮ እጸገነት ሁኔታውን ፣ ሲያዩ ለልባቸው የተሰማው ሙቀት ጸዳሉ በውብ ፊታቸው ላይ በርቶ እዩታቤ ።

"አየ . . . የቀኛዝማችን ቁጣ ባያዩ ነው ! እንደ ትናንቱና እንደ ዛሬው ቁጣቸው ከሆነ ፣ እንኩዋንስ በሰው በግዜር አማላጅነት ይቅር የሚሉ አይመስልም !" አለ ፣ የሰውም ፊት እንደሳቸው በሞቀ ፈገግታ በርቶ ።

"ለወንድ ከግዜር ይልቅ የሴት አማላጅ አትበልጥም ? አንተ እላ ውቅልሽ አልኸኝ እንጂ ፣ እኔኮ ሴት ነኝ ፣ ጥላሁን ! አንተ ብቻ የኔን ሴትነት ማወቅ እንኩዋ አትፈልግም !" አሉ ፣ የፍቅር ስሜት ያጋላ

@OLDBOOKSPDF

ቸው አይኖቻቸውን በጥላሁን ላይ እያንቀዋለሉ ። ጥላሁን በረድ ብሎ የነበረው የወይዘሮ አጸደንች ስሜት እንደገና እዬጠቀ ፤ እዬሞቀ ሄዶ ወደ መጋልና ፤ ለመግታት ወደሚያስቸግርበት ደረጃ መድረሱን ሲያይ፤ ፍርሀት ይዞት አይኖቹን የሚያሳርፍበት እዬፈለገ ይቅበዘበዝና ፤ ከንፈሮቹም ፤ ጉንጮቹም ይንቀጠቀጡ ጀመር ! ያን ሲያዩ የልቡን በር ዘግቶ ፤ ቆልፎ ሲከላከል የነበረውን ፤ የመቀው ፤ የመረታት ምልክት ነው ” ብለው እምነው ፤ ወደ እሱ ተጠግና ፤ የደስታ እንባ በሞሉ አይናቻቸው የሱን አይናች ጠልቀው እያዩ ፤

“ ጨካኝ ነህ ጥላሁን ፤ በጣም ጨካኝ ነህ ! ድምጽህን በሰማሁና ባዬሁህ ቁጥር እሆነውን እያጣሁ ፤ እያደርገኝን እያደረግሁ ፤ ጠባዬ ምቼ ሲጠቃቀሉብኝ እያዩህ ፤ ባዬሁህ ቁጥር የሴትነት እፍረቴንና ይሉኝታን ሁሉ መቀው ብቻ ሳይሆን ፤ እስረኛነቴን እንኳ ረስቼ ፤ ሊደርሱብኝ የሚችለውን አደጋ ሁሉ ንቄ ፤ የማደርገው በጠባቂዎቼና በታዛቢዎቼ ፊት ሲያጋልጠኝ እያዩህ ፤ እፍረቴን ሁሉ ፤ ይሉኝታን ሁሉ፤ አደጋን ሁሉ ንቄ እንደምወድህ እያወቅህ ፤ ይህን ሁሉ እያወቅህ እን ዳላወቅህ ፤ እንደማይገባህ ፤ በውሸት ቅሀትና ፤ በውሸት አክ . . እክ ብሮች ለሳምታ ለጥቶኸኝ . . . ትሄዳለህ ! እንዴት ክፉ ነህ ጥላሁን ፤ እንዴት ጨካኝ ነህ ! ” ሲሉ ፤ ይህ የተናገሩት ፤ ከዚያ በፊት በዬጊዜው ሲያዩትም ፤ ድምጹን ሲሰሙም ይሆኑት የነበረውንና እሱም እያወቀ ያላወቀ መሰሎ ፤ በፍቅር ፈንታ የከብር ለሳምታ ለጥቶዋቸው ሲሄድ፤ ብቻቸውን እቤታቸው ግቢትው ያለቅሱት የነበረውን መሪር ልቅሶ እን ደገና ጠርቶ አምጥቶባቸው ፤ እዚያ እሱ እጠገብ እንደ ተደቀኑ እንባ ቸው ጣምራ ጣምራ እዬሆነ በግራ ቀኝ ጉንጮቻቸው ይወርድ ጀመር ። ያንጊዜ ጥላሁን ያን ልቅሶና ያንን ምሪንት ሲያይ ልቡ ተነካና ፤ እሳ ዘነትና ፤ እንገታቸውን እቅፎ ራሳቸውንም ፤ ግንባራቸውንም እዬ ሳመ ማባበል ጀመረ ።

“ እባክዎ አያልቅሱ ፤ ጸጥ ይበሉና እቨበበት የነበረውን ምክና ያት እነግርዎታለሁ ፤ እስቲ ጸጥ ይበሉ ” አለ ።

“ እንቺ በለኝ ፤ እባክህ እንቺ በለኝ ጥላሁን ! ” አሉ ፤ ራሳቸውን በቅፉ ውስጥ እንደ ቀበሩ ።

“ እሺ እንቺ እላለሁ ፤ እባክሽ አታልቅሺ እጸደንች ! ”

ከዚያ ራሳቸውን በቅፉ ከቀበሩበት አውጥተው ፤ አይናቻቸው በደ ስታ እንባ እዬዋኙ ፤ ፊታቸው እንደ ጎህ በሚይ በደስታ ወገግ ብሎ ፤ እሱን ሲሰሙ እንትቱን በሁለቱ እጆቻቸው ጠምጥመው ሲያዙ ፤

@OLDBOOKSPDF

“ቆይ እስቲ ፤ በፊት አንድ ነገር ልጠይቅሽ ” አለ ፡ አስረው ወይዘር እጸገነት አፍ ከሚነትጉት እጆች ለማምለጥ ወደ ላይ እየ ተንጠራራ ።

“ኦ . . . ሀ ! ደሞ አሁን ምንድነው የምትጠይቀኝ ! ” አሉ ፡ ልባቸው ረዥም ጊዜ ደጅ ሲጠና የኖረለትን ፡ ረዥም ጊዜ ሲያለቅስ የኖረለትን “ አገኘሁ ” ብሎ በደስታ ሲጨፍርና ዳንኪራ ሲመታ ፡ የሱም ልብ አብሮ በመጨፈር ፡ አብሮ ዳንኪራ በመምታት ፈንታ ፡ ጥያቄ የሚሉት ነገር ይዞ ስለመጣ ቀዝቃዛነቱ ፡ ጥዶ ቢያንዱበት የማይሞቅ በረዶነቱ ትግስታቸውን አሳጥቶ አበሳጭቶዋቸው ።

“ከጥያቄው በፊት ስለራሴ እውነቱን ልንገርሽ ፤ ልናዘዝልሽ ፤ አሁን ያልሽው ሁሉ እውነት ነው ። እኔን ስታዩ አንድ የተለዩ ስሜት እንደሚሰማሽ ስለ ተመለከትሁ ፡ የተቻለኝን ያክል እሸሽ ነበር ። ምክንያቱ ፡ እኔ የምወዳት ምሽት ስላለችኝና ፡ አንቺም . . . ባለባል ስለ ሆንሽ ነው ” ሲል ፡ ወይዘር እጸገነት ያ በውስጣቸው ፈልቶ ፡ ሊገነፍል ደርሶ የነበረው ስሜታቸው ፡ በረድ እያለ ሄደና ፡ አንገቱን በሁለት እጆቻቸው እንደ ያዙ ረጋ ብለው አይን አይኑን እያዩ ይሰሙ ጀመር ።

“አሁን ወደ ጥያቄዬ ልመለስና . . . አሁን ያልሽውን ያክል የምትወጂኝ ለመሆንሽ . . . እርግጠኛ ነሽ ?” አለ ፡ ግንባሩን ትንሽ ኮስተር አድርጎ ።

“እንዴት ? ምን ማለትህ ነው ? ምን አስጠረጠረህ ? ለመሆኑ . . . ባልወድህ ፡ እንደ ሴቶች በመለመን ፈንታ ለምን ብዬ ልመና እገባ ኖሮዋል ?” አሉ ገርምዋቸው ።

“ከመቸ ጀምሮ ነው ለኔ . . . እንዲህ ያለ ጽኑ ፍቅር ያደረብሽ ?”

“ከተዋወቅንበት ቀን ጀምሮ ። እቶ ውብቱ ሲያስተዋውቁንና ፡ እጅህን ስጨብጥ ሁሉ ልቤ በኃይል እዩመታ እጄ ይንቀጠቀጥ ስለ ነበረ ፡ ‘በሽተኛ ነች’ ትለኛለህ ብዬ እፍራ ነበር ። ከዚያ በሁዋላ ፡ ስትጫወቱ ሁሉ አንተ አላዩኸኝም እንጂ አይንህን ስፈልግ ነው ያመሸሁ ! ”

“ ያንለት መደንገጥሽን አይቻለሁ ፤ የጅሽ መንቀጥቀጥም ተሰምቶኛል ። እንዲያውም እውነቱን ልንገርሽ ፤ የዚያን እለት ሁኔታሽ . . . አይረሳኝም ፤ ከዚያ በሁዋላ ባዩሁሽ ቁጥር ፡ እስካሁን ድረስ እንኩዋ

@OLDBOOKSPDF

ያ ሁኔታሽ ትዝ ይለኛል ፤" ሲል አይኖቹን በዝዝ አድርጎ ፡ አሻግሮ እያዩ ፡ ወዲያ ትንሽ ቀረብ አሉ ። ነገር ግን እሱ ግብግቦቸውን በመ ቀበል ፈንታ ንግግሩን ቀጠለና ፡

"እስቲ ደግሞ ሌላ ነገር ልጠይቅሽ " አለ ።

"ምን ?"

"ያንለት . . . ገና ስታይኝ ነው ይህ አሁን ያልሽው አይነት የፍ ቅር ስሜት የተሰማሽ ? ወይስ . . . ውበቱ ስግችንን እዬጠራ ሲያስተ ዋውቃን ነው ?"

"እንጃ ፤ እሱን በትክክል አላስታውሰውም ።"

"ያንለት ማታ ቆማችሁ ስትቀበሉን ፡ ረዥም ጊዜ አይሁን እንጂ ውበቱ ስላሳዬ እዬተለደ ሲናገር ፡ የኛ ተራ እስኪደርስ ባሻገር ስንተያይ ቆይተናል ፤ ታዲያ ያንጊዜ የመሽበር ምልክት አላዬሁብሽም ። መደ ንገጥና መንቀጥቀጥ የጀመርሽ - ውበቱ ስግችንን እዬጠራ ሲያስተዋው ቃን ነው ! አደለም ?"

"እንጃ ፤ ነው መሰለኝ ! አዎን ነው ።"

"ሀ ! እጸገነት ፡ እኔ ታሪክሽን ደህና አድርጌ አጥንቻለሁ ፤ ባል ሽን በጣም ትወጂ ነበር ! ቀኛዝማች በግድ ነጥቀው ሲያመጡሽ እእ ምሮሽን እስከ ማጣት ደርሰሽ ፡ ብዙ ቀን መታመምሽንም ሰምቻ ለሁ !" አለ ፡ የቅርጋታ ፈገግታ ባንድ አፍታ በፊቱ አልፎ ሲሄድ እዬ ታዬ ።

"አዎ ፤ ባሌን ፡ ጥላየን እወደዋለሁ ፤ እንኩዋንስ በህይወቴ እያ ለሁ ሰሞንም ጥላየን አጥንቴ የሚረሳው አይመስለኝም ! ከሱ ቀም ተው ሲያመጡኝ ራሴ ዞሮ ብዙ ቀን መታመሜም እውነት ነው ። ብቻ . . . የድሮ ባሌን ፡ ጥላየን መውደዴ አሁን አንተን ከመውደዴ ጋር ምን አገናኘው ? አንተን ወደድሁህ ማለቴ . . . ስላበድሁ ነው ማለትህ ነው ?" አሉ ። የባላቸው ነገር ሲነሳ እንገቱን ለቀው ፡ እንባ ያዘሉ አይኖቻቸውን በመሬት ተክለው እዬተከዙ ።

"አደለም ፤ ስላበድሽ አደለም ፤ ስለ ወደድሽ ነው ፤ ባልሽን ከመ ጠን ያለፈ ስለ ወደድሽ ነው !"

"እንዴት ?"

"እንግዲህ እውነቱን ልንገርሽ እጸገነት ፤ ስሜን ነው እንጂ እኔን አደለም የምትወጂው !"

@OLDBOOKSPDF

"እንዴት ? ምን ማለትህ ነው ?" አሉ ወይዘሮ አጸገነት ፣ በድንጋጤ ፊታቸውን ክፉኛ ገለል አድርገው ።

"ቆይ አትቆጪ ፤ እያገረምሽ ማለቴ ነው ። እውነቱ ይህ ነው፤ አዩሽ ? እንዲጋጣሚ ባልሽና እኔ በስማችን ብቻ ሳይሆን ባባቶቻችን ስም ጭምር ምንሽሮች ስለሆን ፣ የዚያ የምትወጂው ፣ የዚያ ስታጭው አእምሮሽን ያሳጣሽ የባልሽ ስም ፣ እሱን በኔ አሳዩሽና ፣ እኔን እንደሱ አድርጎ ፣ እሱን አስመስሎ አሳዩሽና ፣ እሱን ራሱን ስታጪው ጊዜ እኔን ፣ ምሳሌውን ወደድሽ ! ልብ አድርጊ እጸገነት ፣ እኔን በኔነቴ ሳይሆን ፣ በስም ክናባቴ እሱን ስለምመስል ፣ በሱ ምሳሌነቴ ነው የወደድሽኝ ! አሁን ያን የምትወጅውን ባልሽን ፣ ያን ያንቺን ጥላሁን ፈይሳን ፣ ያን እውነተኛውን የፍቅርሽን ጌታ ፣ እዚህ ባካል ብታገኚው እኔን ምሳሌውን ፣ እኔን የሶፊን ጥላሁን ፈይሳ ፣ ዘወር ብለሽ እንኳ እንደማታይኝ እርግጠኛ ነኝ ! ምክንያቱም ምንም ቢሆን ምሳሌ ከም ሳሌነቱ አልፎ ተመሳዩ ፣ ወይም ራስ - ዋናው የሚሰጠውን ደስታ ሊሰጥ የማይችል በመሆኑ ፣ ራስ - ዋናው ፣ ወይም ተመሳዩ ካለ ምሳሌው የማያስፈልግ ስለሆን ነው ! ስለዚህ " አለ ፣ አይኖቹን ሳያረግብ ፊት-ለፊት ተክሎ ቆይቶ ወደሳቸው መለሰና ፣ " ስለዚህ ፣ አንድ ብርቱ ነገር ልንገርሽ ! ጸጥ ብለሽ ስሚኝ እጸገነት ! ባልሽን የምትወጂውን ያክል ድፍረት አለሽ እንደሆን ፣ ከኔ ጋር ሆንሽ ሁለታችሁ የም ትገናኙበትን መንገድ እንፈልግ ። "

" ሁለታችሁ የምትገናኙበትን ? ማንና ማን ? " አሉ ወይዘሮ እጸገነት ፣ ጥላሁን የተናገረው ሁሉ ፣ በተለይ የመጨረሻው ክፍል ከውን ይልቅ ወደ ቅዠት የሚጠጋ ስለ መሰላቸው ትንሽ እንደ መደንገጥ ብለው ፣

"አንቺና የምትወጂው ባልሽ ፣ ጥላሁን ፈይሳ !"

"ምን ሆንህ ? ደህና አደለህም ? ወይስ . . . ይህን ያክል ጊዜ እዚህ አገር ስትኖር ፣ እስከ ዛሬ ጥላዩ መሞቱን አታውቅም ?"

"መቸ ሞተ ? ማነውስ ሞተ ብሎ የነገረሽ ?"

"እና . . . እስከ ዛሬ ድረስ አንተ የጥላዩን መሞት አታውቅም ማለት ነው ? ይገርማል ! ጥላዩ ከሞተ አሁን እንግዲህ . . . እዎ ፤ እምስት አመት ይሆናል ፤ እኔን እዚህ ሲያመጡኝ ነው የገደሉት ?" አሉ እዩተከዙ ።

@OLDBOOKSPDF

"እንቺ ጮቅ ነው መሞቱን የሰማሽ ? የነገረሽስ ማነው ?"

"ማን ነገረሽ ? የቤቱ ሰው ሁሉ ፤ ቀኛዝማች ጭምር ከመሟ በኋ እንደ ሆነሁ ፤ መሞቱን ነገሩኝ ፤ ቆስሎ ሲወድቅ እኔም አይቻ ለሁ ። እባክህ የጥላዬን ነገር አታንሳብኝ ይበቃል !" አሉ በተሰበረ ድምጽ ፤ እንባቸው እየወረደ !

"ከውጭ ሰውስ መሞቱን የነገረሽ አለ?"አለ ፤ እሱም እንባቱን ደፍቶ እየተከዘ ።

"የውጭ ሰው! ከውጭ ሰዎች ማን ያገናኘኛል? እኔ አልወጣ ፤ እነሱ አይገቡ! ለምሳሌ እንደናንተ በግብዣና በስራ ምክናያት ከሚ ገቡትም በቀኛዝማች ፤ ወይም በጠባቂዎቹ ፊት ብቻ ስለሆነ የምን ገናኝ ፤ ስለጥላዩ ደፍሮ የሚያነሳ የለ ! ብቻ . . . እሱን ትተህ ሌላ ነገር ብታመጣ ምናለ ?"

"ግሩም ነው ! እና . . . ጥላሁን እምስት አመት ሙሉ እዚሁ ፤ ባጠገብሽ ሲኖር በህይወቱ እንዳለ እንኳ አታውቂም ማለት ነዋ!" አለ እሱም ልቅሶ ስለመጣበት ፤ መሀረሙን አውጥቶ ግራ ቀኝ አይና ቹን እየጠራረገ ።

"ጥላሁን በህይወቱ አለ!"ብለው ከተቀመጡበት ባርጩማ ወደ ሁዋላ ዥው ብለው ሲወድቁ ፤ ጥላሁን ደንግጦ እሱም ከተቀመጠበት ቶሎ ተነሳና በጁም ፤ በግሩም እየተንበራቹ ሄዶ ፤ አንድ ጆሮውን ወደ አፍንጫቸው አስጠግቶ ቢያዳምጥ ይተነፍሳሉ ፤ ነገር ግን ሰው እያወ ቁም ፤ አእምሮዋቸው ተሰውሮዋል ! ከዚያ ራሳቸውን ቀና አድርጎ በጭኑ ላይ አሳርፎ ፤ እግሮቻቸውን ሰተት አድርጎ ዘረጋና ፤ በጀርባ ቸው አስተኝቶ ፤ ግልፍ ደረታቸውን እያሻሸ ዝም ብሎ ተቀምጦ ይጠ ብቃቸው ጀመር ። ዘለግ ያለ ጊዜ ቆይተው ፤ አይናቻቸውን ቢገልጡ፣ እጭኑ ላይ አስተኝቶ ዘቅዝቆ ሲመለከታቸው አዩ ። ከጥቂት ጊዜ በፊት ምን እንደ ደረሰባቸው በጭራሽ አላወቁም ። "በስግብ ፤ ወልድ ፤ መን ፈስ ቅዱስ !ምን ሆንሁ ? ሙቼ ፤ ምን ጊዜ ተኛሁ ? ወዬው ጉድ ! በህ ልሜ ጥላሁን በህይወቱ አለ አልኸኝ ! " አሉ ፤ የባላቸውን ስም ሲጠሩ እስከትሎት የመጣውን ጥልቅ የሀዘን ስሜት በሚገልጹ አይኖች ፤ የሱን ዘቅዝቀው የሚመለከቱ አይኖች ሽቅብ እያዩ ።

"በህልምሽ አይደለም ፤ በውንሽ ነው ባለቤትሽ ጥላሁን አለመ ሞቱን የነገርሁሽ ! እጸገንት ጥላሁን አልሞተም ፤ በህይወቱ እዚሁ አገር አለ ! " ሲል ፤ የወይዘሮ እጸገንት ሁኔታ ሁሉ ስላሳዘነው ፤ አይኖቹ እንደ ገና እንባ ሞልተው ነበር ።

@OLDBOOKSPDF

"እንዴት ! ህልም አይለም ? እውን ነው ! ጥላዬ በህይወቱ አለ ? ወዴት ? በየት በኩል ? ውሸትህን ነው ! ልትቀልድብኝ ፣ ልታስቃዬኝ ነው!" አሉ ። ከተኙበት ምን ጊዜ ፣ እንዴት ሆነው እንደ ተነሱ ሳይታወቅ አፈፉ ተንበርክከው ፣ በሁለት እጆቻቸው ሁለት እጆቼን ጥብቅ አድርገው ይዘው ፣ ፊታቸው በዚያች ቅጽበት እንደማይታወቅ ሆኖ ተለዋውጦ ሲጨነቁ ሲያዩኝ ፣ ጥላሁንን ግራ ገባው ።

"አሰቴ ቆይ እባክሽ ፤ ቆይ አትጨነቂ ፤ ቆይ ጸጥ በይና ልንገርሽ፤ ጥላሁን አልሞተም ፤ እዚሁ አለ ፤ ብቻ ጸጥ በይና ስሚኝ!" አለ ፣ እንደ እብድ የሚሄዱበትን ሳያውቁ ሲሮጡ ሲሉ ፣ በፈንታው ሁለት እጆቻቸውን አጥብቆ ይዞ ።

"ውሸትህ ነው ፤ ጥላዬ ሞቶዋል ! ካለ ለምን አይመጣ ? ጠልቶኝ ነው ? "ከእህ ክፉ ፣ ከእህ አውሬ ጋር ከመኖር ለምን አልሞተች" ብሎ ጠልቶኝ ነው ? የለም ! ጥላዬ ፣ "ለምን አልሞተች" ብሎ አይጠላኝም ። በጣም ይወደኛል ፤ ምን ያክል እንደሚወደኝ ሊገባህ አይችልም ፤ ማንንም ሊገባው አይችልም! የለም ፤ ጥላዬ በህይወቱ ባይኖር ነው እንጂ ፣ ቢኖር ምንም ቢሆን ፣ አይደርስ ቢደርስበት ፣ እስከ ዛሬ ሳያየኝ አይቀርም ነበር ! "በህይወት አለ" የምትለኝ ! ውሸት ነው ።

"ቆይኮ ተቀመጪና ልንገርሽ ! እባክሽ ጸጥ ብለሽ ስሚኝ ልንገርሽ ! ቀኛዝማች የሚገቡበት ጊዜ ገና እንደሆነ ፣ ትንሽ ጊዜ እንዳለሽ ፣ ጸጥ ብለሽ ተቀመጪና ስሚኝ" አለ ፣ እጃቸውን ጎትቶ በግድ ሊያስቀምጣቸው ።

"እሺ ፤ በል ቶሎ ንገረኝ ፤ ጸጥ ብዬ እሰማለሁ ። ቀኛዝማች ቷፒ ፣ ልጅ እናታቸው ቤት ሄደዋል ፤ እዚያ ያመሻሉ ፤ ወይም ያድሩ ይሆናል ። ቶሎ ንገረኝ እንጂ ለምን ታስጨንቀኛለህ ?"

"ባልሽ ፣ ጥላሁን ' ቀኛዝማችን ካልገደልሁ ከሰቸው ጋር ተመቀኛ በፍርድ ሚስቴን ማግኘት አልችልም' ብሎ ፣ ቀኛዝማችን ለመግደል ሸፍቶ እዚሁ ፣ እጫካ ውስጥ ነው የሚኖር ። ቤት ግን ሁል ጊዜ ከተማ ነው የሚያድር ። እንዲያውም 'ባጋጣሚ ቀኛዝማችን ባገኝ' ብሎ ፣ 'ብዙ ጊዜ እጥራችሁን ሲዞር ያድራል' እዬተባለ ይወራል ። እዚህ ከተማ ሲመጣ ራትን የሚበላም እባላምባራስ ጉዴታ ራት ቤት መሆኑን ሰምቻለሁ ።"

"እኔ እፈር ልብላ ! እኔ ልንገላታ ! ጥላዬ ፣ ጋሼዬ ፣ ቤት እንዳውሬ ጫካ ለጫካ በትሄድ ሾህ ወጋህ ? እንቅፋት መታህ ? እኔ ልንገላታ ! እኔ ልጨነቅ ! እኔ ልቸገር !" ይሉ ጀመር ፣ ፊታቸው በንባ እዬታጠበ ።

@OLDBOOKSPDF

"እሱ ምንም አልተገኘም ፤ ደህና ነው ፤ ይልቅስ እባክሽ እንቺ ጸጥ በይና የምናደርገውን እንመካከር ፤ ብዙ የምንሠራበትን ጊዜ በከንቱ እናጥፋው !"

"እሺ ጸጥ እላለሁ ፤ ጥላየ እውነት በህይወቱ ካለ ጸጥ እላለሁ ። ምን እናድርግ ? ንገረኝ ፤ በል ቶሎ ንገረኝ "አሉ ፡ ሁለመናቸው እዩት ንቅጠቀጠ ።

"አንድ ዘዴ ፈጥረሽ የዚህን እግር ብረት መፍቻ እጅ ብታደርጊ ፡ እንዲህ እንደ ዛሬው ቀኛዝማች ውጭ በሚያመሹበት ማታ ከዚህ ወጥቶን ከሱ ጋር እንጨመርና ፡ ቢቀናን ፡ እግዚር ሀዝበን ቢታረቀው ከኔህ ክፉ ፡ ከኔህ መቅሰፍት እንገላገል ይሆናል ፤ ያለጥርጥር እንገላገ ላለን !"

"እንዴት አድርገን ?"

"እናጠፋቸዋለና! ክፉ ካልጠፋ ደህና ይኖራል? ደህና ፋፍቶ ፡ ተስፋፍቶ እንዲኖር ፡ እኔህን ክፉ አረም ከስር ነቅሎ ማጥፋት ያስፈል ጋል ! ስለዚህ አብረን ሆነን እናጠፋቸዋለን !"

"ታዲያ ጥላዬ ያለበትን ካወቅህ ተነስ ውሰደኝ እንጂ ፡ ይህ ሁሉ ንግግር ምን ያደርግልኛል ' ተነስ እባክህ ወደ ጥላየ ውሰደኝ ፤ ለዚህ . . . ለንግግሩ ሁሉ ሁዋላ ትደርስበታለህ !" አሉ ፡ ትእግስታቸው አልቆ ከተቀመጡበት ብድግ አሉና ።

" ሀ ! ታስሬአለሁ እኮ እጸገንት ! እስቲ እባክሽ ረጋ በይ ! ቅድም እንዳልሁሽ ፡ የዚህን እግር ብረት መፍቻ በዘዴ እጅ አድርጊና ቀኛዝማች ውጭ በሚያመሹበት ማታ ፈትተሽ እንወጣለን ። አንድ ጊዜ ከዚህ ከወጣን ምንም አይቸግረን ፤ ሶፊን ይዘን ከጥላሁን ጋር እንጨመራለን !

"እምን ፤ አዎን ፤ ታስረሀል ለካ ! ታስረሀልና " አሉ ፡ እንደ ቆሙ በሁለት እጆቻቸው ራሳቸውን እያከኩ ። ከዚያ ትንሽ አሰቡና "ቁልፉ ፤ መፍቻው ፡ አዎ ! መፍቻው ፡ መፍቻውማ ለኔ ሰጥተው ኛል ኮ ! ሁልጊዜም ሰው እዚህ ሲያስሩ ሌሎችን ስለማያምኑ ፡ መፍቻ ውን እኔ እንዳስቀምጥ ነው የሚሰጡኝ ! " አሉ ፡ አሁንም አሳባቸውን መሰብሰብ ስላቃታቸው ያልተያያዙ ቃላት እየተናገሩ ።

"እ ? መፍቻው ካንቺ ጋር ነው ? አሁን ይዘሽዋል ? "

"ከኔ ጋር ነው መሰለኝ ፤ አዎን ከኔ ጋር ነው ፤ ይሄው ከኔ ጋር ነው ! " አሉ እየተርበተበቱ መክፈቻውን ከእጅ ቦርሳቸው አውጥተው ለጥላሁን እያሳዩ ።

@OLDBOOKSPDF

“ ወይ አንቺ ግሩም !” አለ ፣ በደስታ የበራ ፊቱን እግዜር ወዳለበት ፣ ወደ ላይ አቅንቶ ። “ ይህማ ” አለ ቀጠለና ፣ “ ይህማ ግሩም ነው ! ይህማ እግዜር ራሱ ያዘጋጀው ነው ! በይ ነይ ጉዋጉን ቶሩን ፍቻልኝ ። ”

ወይዘሮ እጸገነት እጆቻቸው እየተንቀጠቀጡ ፣ እንደ ታዘዙት ጉዋጉንቸሩን ፈተው ማሉና ፣ እግሮቹን ከግረሙቶች ለማውጣት ሁለቱም ተጋግዘው ቢሞክሩ አቅቶአቸው ፣ ሲታገሉ ብዙ ጊዜ ካጠፉ በሁዋላ መጨረሻ ቀናቸው ። ከዚያ ፣ ጥላሁን ታስሮበት የነበረውን ፣ ባለስንሰለት እግርብረት ባንድ እጁ እንደያዘ ፣ በሌላው የወይዘሮ እጸገነትን አንገት አቅፎ ግንባራቸውን ሳመና ፣

“አይዞሽ አትፍሪ ፤ እስካሁን እግዚአብሔር ከኛ ጋር የሆነ ይመስላል ፤ እስቲ . . . ወደፊትም አብሮን ሆኖ ቀኑን ይምራን ! አሁን እንግዲህ . . . መቸም በፊት በር ዘበኞች ስላሉ ፣ በዚያን መውጣት አንችል ፤ ሌላ የምታውቂው መውጫ አለ ? ” አለ ።

“በፊት በር አይደለም ፤ በስርቆሽ በር ነው ፤ ከውስጥ የሚከፈትና የሚዘጋ ስርቆሽ በር አለ ። ግዴለም እኔ እመራሃለሁ ፤ ብቻ አባክህ ቶሎ እንሂድ ! ” አሉ ወይዘሮ እጸገነት እየተርበተበቱ ።

“በይ ኩታሽን ደርቢ ፤ ለመሆኑ ሌላ ልብስና እቃ አትይዥም ?”

“የለም አልፈልግም ፤ ብቻ ከዚህ እንሂድ ፤ ከዚህ ቶሎ እንሂድ” አሉ ፣ ኩታቸውን ከጣሉበት አንስተው ተከናንበው ።

ወይዘሮ እጸገነት እንዳያ ተከናንበው ፣ ፍርሀት እያንቀጠቀጣቸው ከዚያ ለመውጣት ሲጣጠኑ ፣ ጥላሁን መንገድ ከጀመሩ በሁዋላ እንዳይሳሳቱና ፣ በጠባት እጅ እንዳይወድቁ ስለሰጋ ፣ ረጋ ብለው የሚወጡበትን እንዲያስጠኑት ሲማጠናቸው ፣ በመሀከል እጥግ ተቀምጣ እንድትጠብቅ የታዘዘችዋ ፣ ውብነሽ በሩን በቸኮላ ከፍታ እየሮጠች ገባችና ፣

እሜቴ ፤ እሜቴ ፤ እሜትዬ ፤ አንድ ሰው በስርቆሽ በር በኩል እትዬ ማዴን ቢጠራ ፣ ቢጠራ ፣ አልሰማው ስላለች እየተሳደበም እየተራገመም ሲጣራ ፣ ብዙ ጊዜ ቆይቶ ፣ አሁን ከፍታለት . . . ደፍ ቀና ፣ እያለ ወዲህ ይመጣል ፤ ሩቅ ስለሆነ ጥላው ነው እንጂ መልኩ ማን እንደሆን አይታወቅም ፤ ድምጹ ግን . . . የጌቶችን ይመስላል ! ” ስትል ፣ ጥላሁንና ወይዘሮ እጸገነት ፣ በድንጋጤ መልክ ላጭር ጊዜ ከተያዩ በሁዋላ ፣ ጥላሁን ወደ ውብነሽ ቀረብ አለና፣ “ እስቲ አሁንም ወደ ነበርሽበት ሂጂና ወዴት እንደሚሄድ ተመልከ

ችው ፤ በርግጥ ወዲህ የሚመጣ ከሆነ ፣ ሲቀርብ መጥተሽ ንገሪን ፡፡ ብሎ አሰናብቶዋት ስትወጣ ፣ ግራና ቀኝ ተከፋችች የሆኑ መዝጊያዎ ችን መለስ አደረገና ፣ ወይዘሮ እጅጋየሁን ወዳንደኛው መዝጊያ ጀርባ ወስዶ ፣ ግድግዳውን አስጠግቶ አቁሞ ፤

"እንግዲህ በርቺ ፤ እንዳትደነግጪ ! ቀኛዝማች የመጡ እንደሆነ እኔ በዚህ እግር ብረት እናታቸውን ፈጥኜ ስጥላቸው ፣ አንቺ ቶሎ ከዚህ ወደኔ መምጣት ነው ፤ አይዞሽ እናመልጣለን ፤ ድንገት ሲገቡ የሚያዩሽ መስሎሽ እንዳትፈሪ ፤ ያህ መዝጊያ ወደ ውስጥ ስለሆነ ሲከፈት ፣ ይሸሽግሻል ፤ አትታይም ፤ በይ ደህና ሁኚ !" አለ እንደገና ግንባራቸውን ስሞ ።

ጥላሁን ወደ ሁለተኛው መዝጊያ ጀርባ ሄዶ ፣ እንደ ወይዘሮ እጅ ጋየሁ ግድግዳውን ተጠግቶ ከመቆሙ ፣ ግራና ቀኝ ተከፋች መዝጊያ ዎች በሀይል ተገፍተው ፤ በወይዘሮ እጅጋየሁና በጥላሁን ላይ ሲከፈቱ ቀኛዝማች ዳኘ በግራ እጃቸው በጥይት የተቀደደ ፣ የታች ከናል ሆዳ ቸውን ፤ በቀኝ እጃቸው ሽጉጣቸውን ይዘው እየተንገዳገዱ ገቡ ። ጠበ ንጃቸውና ዝናራቸውን ወዲያው ልጥፉን እንደገቡ አውልቀው ጥለ ዋቸዋል ። ካኪ ሱሪያቸውና በፊታቸው በኩል የታች ከናል ካኪ ኮታ ቸው በደም ተነክሮዋል ። ከራሳቸው ጀምሮ ፊታቸው በመላ ፣ በወሀ የሚታጠብ እንጂ ላብ የሚወርደው አይመስልም !

ቀኛዝማች ዳኘ እንዲያ በሚያሰቅቅ ፣ እንዲያ በሚዘገንን ሁኔታ እንዳሉ ፣ ጥላሁንና ወይዘሮ ዕጅጋየሁ ራት ከበሉበት አጠገብ ቆመው ፣ ጀርባቸውን ለነሱ ሰጥተው ፤ እየተንገዳገዱና ሽጉጣቸውን እያወዛወዙ ጥላሁንን እዚያ ሲያጡ ፣ ቀን እንደ ከዳቸው ፣ እግዜር እንደ ተጣላቸው ተረድተው ፣ ከጣረሞት ጋር እየታገሉ እግዚአብሔርን ማማረርና መው ቀስ ጀመሩ ።

"ደሞ እሱ የታባቱ ሄደ ? ያ ፣ ሌባ ፣ — ያ ፣ መሰሪኛ ተማሪ ደሞ ወዴት አባቱ ሄደ ? እሱም አመለጠኝ ? ወይኔ ዳኛቸው ! ወይኔ የገ ፋው ጌታ ! እሱን እንኳ ገድዬ ብሞት ግዳዬን ገድዬ ፣ ተበቅዬ እን ደሞትሁ ቆጥሬው ፣ የበቀል ጥሜ ረክቶ ፣ ልቤ ሰላም አግኝቶ እሞት ነበር ! ነገር ግን እሱም አመለጠኝ ! . . . አ . . . ! አ . . . ! ወይኔ የና ፈሳ ልጅ ፤ አ-አ-አ- ! አ-አ-" አሉ ፤ ቁስላቸው ስላሰቃያቸው ለብቻ ቸው ይናገሩ የነበረውን አቋርጠው ጎንበስ አሉና ። "እምላኬ ለዚህ ኖርኩዋል ፤ ለዚህ ኖርኩዋል የቆጠብኸኝ ! " አሉ እንደገና ቀና ብለው

@OLDBOOKSPDF

“ለካ ለዚህ ኖሮዋል የቆጠብኸኝ ! ፋሽስት በሰማይና በመሬት እያሰለፈ የላከብኝን ጦር ሁልጊዜ ድል እዬመታሁ እንድመለስ ማድረግህ ፣ የማጊራን ቁጥር ስፍር የሌለው ሰራዊት አመድ አድርጌ ፣ በድል አድራጊነት እንድወጣ ማድረግህ ፣ ለካስ ይህን ሁሉ ማድረግህ ፣ እዚያ በጦር ሜዳ የክብር ሞት እንዳላገኝ መንፈግህና ለዚህ ጎስቋላ ፣ ለዚህ ወራዳ ሞት መቆጠብህ ኖሮዋል ! ለካስ በጦር ሜዳ ፣ በጀግናቹ እጅ ሞቼ ፣ ለልጆቼ መኩሪያ እንዳልሆን ፣ በሴት እጅ እንደ ዱባ ተቀድጄ ሞቼ ፣ ለልጆቼ ማፈሪያ እንድሆን መቆጠብህ ኖሮዋል ! አ...! አ.አ. አ! ወይኔ ዳኛቸው ! ሞቴ አያሳዝነኝም ! የሚያሳዝነኝ ፣ ሬሳዩ በመቃብሩ እረፍት እንዳያገኝ ሲቆረቁረው የሚኖር አሞሟሞቴ ነው! ”

ጥላሁን አስቀድሞ እንዳቀደው ፣ የቀኛዝማችን ራስ በግርብረት ሲፈጠፍጥ ሲሰናዳ ፣ ቀኛዝማች የሰንሰለቱን ቅጭልታ ሰሙና ፣ በተለመደው የሚያስገርም ፍጥነታቸው ፣ ዘወር ብለው ሳያንጣጥሩ ተኩሰው ሳቱት ። ከዚያ ሁለተኛ ለመተኮስ ጊዜ ሳያገኙ ፣ ጥላሁን ተወርውሮ ያዛቸውና ትንሽ እንደታገሉ ፣ የገዛ ሽጉጣቸውን ከዛለ እጃቸው ነጥቆ በውስጡ የነበረውን ጥይት ሁሉ ሲጨርስባቸው ወደቁ ። ወዲያው ወይዘሮ እጸገነትን ይዞ ለመውጣት ቆመውበት ወደነበረው ቦታ ቢሄድ የሉም ። የጉዋሮው በር ተከፍቶ ሰላዬ ፣ ሮጦ ወጥቶ ብቻውን ተመለሰ ። ከዚያ ትንሽ ቆም ብሎ ቀኛዝማችን እንደ ወደቁ ከተመለከተ በሁዋላ ፣ ሰው እዬተንጫጫ በፊት በር መምጣቱን ስለሰማ ሽጉጣቸውን አፈታቸው ጥሎ እሱም በጉዋሮ በር ወጣ ።

@OLDBOOKSPDF

ም ዕ ራ ፍ ፳፱

# ድል ነሺቶ መሸሽ

ሶሬያ ፣ ቀኛዝማች ዳኛ ከቤትዋ አጥሩን ወጥተው ባጠገብዋ ሲሄዱ ብታያም ፣ መሄዳቸውን ማመን አቅቶዋት ፣ ካሁን አሁን ፣ “ መጡብኝ” እያለች ስትፈራ ፣ ከፍርሀትዋም የተነሳ ብዙ ሚሊራፍ እንደ ርጠች ከባይ ከባይ በሀይል ስትተነፍስ ፣ ከሩቅ የሚሰማው ትንፋሽዋ ጠባት ጠርቶ ያለችበትን የሚናገርባት እዬመሰላት ስትጨነቅ ቆዩች ። ከዚያ እንደዚሁ ስትጨነቅ ዘለግ ያለ ጊዜ ቆይታ ቀኛዝማች ከሄዱበት ወገን ምንም አይነት ድምጽ ስላልሰማች ፣ ከተሸሸገችበት ወጥታ ፣ እዬሮጠች እቤትዋ ገባችና ፣ ቶሎ ቶሎ የቤትዋን በር መዝጊያ በመሸጎሪያ አጥብቃ ዘግታ ፣ ምናልባት መዝጊያው ከውጭ በሀይል የተገፋ እንደሆነ ወደ ውስጥ እንዳይሸሽ የመብል ቤቱንም ፣ የሳሎኑንም በከባድ ጠረጴዛዎች እያንቀዋቀቀች አምጥታ ፣ ፊትና ሁዋላ አድርጋ አስደገፈችው ። ከዚያ ፣ ያን አልጋ ለሚመጣ ጠባት ሁለተኛ መከላከያ እንዲሆን ፣ ሳሎኑን እልፍ ከመብል ቤቱ መሀከል ፣ የመብል ቤት እቃ የሚቀመጥባቸውን ሁለት ቁም ሳጥኖች ለጠበንጃ አፈሙዝና ማነጣጠሪያ ያክል መገናኛቸውን ከፍት አድርጋ በተራ አቆመች ። ከዚያ ፣ መውዚርዋንና ሽጉጥዋን አጉርሳ ባጠገብዋ ፣ ሬሽዋን አጉርሳ ፣ አፈሙዙን በቁም ሳጥኖች መሀከል አስወጥታ ፣ በፊትዋ ፣ ካስቀመጠች በሁዋላ ፣ ያን መሰናዶ ሁሉ ፣ ያን እዚያ ቤት የሰራችውን ምሽግ ሁሉ ስታይ ፣ ከንግዲህ ጠባት ሲመጣ ጦርነቱን ከመጀመር በቀር የጎደለ ነገር አለመኖሩን አረጋገጠችና ፣ ያለችበት ደቂቃ እያለፈ የሚከተለው ደቂቃ ሁሉ ጠባት ይዞ እንደሚመጣ እምና ትጠባበቅ ጀመር ! ወዲያው “ደብ ፣ ደብ ፣ ደብ ፣ ደብ ” የሚል ነገር የሰማች መሰላትና ፣ አንገትዋን መዘዝ አድርጋ አንድ ጆሮዋን ወደ በሩ ስትደቅን “ደብደቡ” እዬጎላ ፣ እዬጎላ መጣ ። የሰው ሩጫ ነው ! ቀኛዝማች እንደ ሄዱ ቶሎ እቤት ገብታ ምሽግ ለመስራት ስትቻኩል ፣ ያጥሩን በር ሳትዘጋ መግባትዋ ያን ጊዜ ብቻ ትዝ አላት ። “ለመሆኑ እንዲያ እዬሮጠ የመጣ

@OLDBOOKSPDF

ማን ይሆን ? መቸም ቀኛዝማች እንዲያ ሊሮጡ አይችሉ ፤ እሳቸው አይሉም ፤ ደግሞቸውን እንዲመልሱላቸው ፤ እንዲበቀሉላቸው እሳቸው የላኩት ፤ ደግሞ መላሻቸው ነው ፤”አለች ፤ ባሳብዋ ፤ ከዚያ የሚከተለውን ለትጠብቅ ፤ እዩሮጠ የመጣው ሰው አጥሩን ገብቶ ወደ ቤቱ በር መጠጋቱን ከዳናው ብታውቅም ፤ እዚያ ደርሶ ዝም ሲል ፤ ምን እንደሚያደርግ ባለማወቋ ፤ ምን እንደምታደርግ ቅጡ ጠፍቶባት ስቶ ቆነር ፤ ድንገት ባላምባራስ ጉዳት ራሳ ሊባ አድም በነበሩ ጊዜ ፤ አቤት ውስጥ የሚመሽጉ ሌቦችን ፤ ወይም ሽፍቶችን ስለሚዩዙበት ፤ ወይም ስለሚገድሉበት ዘዴ ሲናገሩ የሰማችው ትዝ አላትና በጣም ፈራች ።

ባላምባራስ ሲያወሩ እንደ ሰማችው ፤ “አቤት ውስጥ መሽገው የሚዋጉን ሰዎች ፤ እነሱ ምንም ጉዳት ሳያደርሱ ለመያዝ ፤ ወይም ለማጥፋት ከሁሉ የሚሻለው ዘዴ ፤ መሽገው የሚዋጉበትን ቤት ሳይታዩ ተሸሽጎ ፤ ወይም ከሩቅ ወርውሮ በሳት ማያያዝ ነው ። ያን ጊዜ ከሚቃጠለው ቤት ጋር አብረው መቃጠልን ፤ አብረው አመድ መሆንን ከለመረጡ በቀር ፤ ከፍተው እዩሮጡ መውጣታቸው ስለማይቀር ፤ ለጥራ በታ ይዞ ጠብቆ ፤ ሳይታዩ ትጥቃቸውን እያስፈቱ መማረክ ፤ የማይማረኩም ከሆኑ መግደል ነው ! ”

ሰፊያ ይህን ባላምባራስ ጉዳት ሲያወሩ የሰማችውን ስታስታውሰ፤ “ያ ፤ እዩሮጠ የመጣው ሰው አጥሩን ከገባ በኋዋላ ዱብ ያለው የጠፋ ምናልባት በዚያ ዘዴ ለመጠቀም ፈልጎ በመሰናዳት ላይ ስለሆነ ይሆናል ” አለችና ባሳብዋ ፤ መቸም ቤቱ ሲቃጠል መውጫዋ ነው ብላ የሚጠብቀው ያለጥርጥር በሩን ስለሆነ ፤ ሳያያት በጀርባ ፤ በምኝታ ቤት መስኮት ሾልካ ለመውጣት ፤ በጥፍሮችዋ እዩቆመች ፤ ቀስ ብላ ሄዳ ፤ የመኝታ ቤቱን መስኮት ከነሸበው ድምጽ ሳታሰማ ከፈተች ። ከዚያ እንዲሁ በጥፍሮችዋ እዩቆመች ፤ ቀስ ብላ ተመልሳ ፤ ተደግፍ በሚጠብቃት ረሽዋ ሁዋላ ለመንበርከክ አንድ ጉልበትዋን መሬት አስይዛ ሌላው ገና በመቆምና በመንበርከክ መሀከል እንዳለ ፤ አንድ ደካማ ድምጽ፤ የገዛ ትንፋሹ የሚያደናቅፈው ሰው ድምጽ የሰማች መሰላትና ፤ እንዲያ በከፊል ትንደ ተንበረከከች ገዥም ብላ ቃዳምጥ ጀመር ። ነገር ግን ያ ድምጽ ሀለግ ላለ ጊዜ አልተደገመም። ዘለግ ላለ ጊዜ ዝምታው፡ጸጥታው በሚያስ ፈራ ሁኔታ ቀጠለ ! “የሰማሁት..... የሌለ ድምጽ፡የውሸት ድምጽ ይሆን ? በለ ፈራሁ..... ያው ፍርሀቴ የፈጠረው ድምጽ ይሆንዝ እም .....

@OLDBOOKSPDF

እንጃ! ” አለችና ፣ ለመንበርከክ ግማሽ መንገድ ሲደርስ እዚያ እንዳለ የቆጮ ጉልበትዋን መሬት ስታስነካ ፣

“ሶፊ” ንሊ ድምጹ ፣ ከቅድሙ ትንሽ ጉላ ፣ ከመደናቀፉም ትንሽ ጸጥ ብሎ ። ሶፊያ አልመለሰችም ! ልብዋ በኃይልና በፍጥነት እዬ መታ ዝም ብላ ቃንቃቃ ጀመር ።

“ሶፊ ፣ አለሽ ? ደህና ነሽ ? አለሽ ? ንገሪሁ ፣ ደህና እንደ ሆንሽ ፣ ደህና ነኝ በይኝ ” ሲል ድምጹ ! ምንም እንኳዋ የባልዋን ፣ በግር ብረት ቃስሮ በዘበኛ መጠበቅ ብታውቅና ፣ ያ ! የሚጠራት ድምጽም ከሱ ድምጽ ለወጥ ያለ ቢመስል ፣ ልብዋ ይህን ሁሉ እንቢ ብሎ ፣ “እሱ ነው”እያለ ስላስቸገራት እዬተንቀጠቀጠች ፣

“ማ . . . ማነህ እንተ?”አለች ።

“እኔ ነኝ ፣ እኔ ጥላሁን ነኝ ፣ ደህና ነሽ ? ደህና ከሆንሽ ክፈችልኝ! ”

“ ውሸትህ ነው ፣ ጥላዬ አደለህም ፣ ጥላዬ ታስሮዋል ። ደግሞ . . . ድምጽህ ሌላ ነው ። ስለዚህ . . . በሬን እንዳትነካ ፣ እተኩስበሀለሁ!”

“ እረ እኔ ነኝ ፣ ድምጼ የተለወጠ ስለሮጥሁ ቃቃ ይዞኝ ነው እንጂ ፣ እኔ ጥላሁን ነኝ ! ካንቺና ከኔ በቀር ሌላ ሰው የማያውቀው ምን ምልክት ልንገርሽ ? ቆይ ፣ እ . . . እዎ ! ለሰርጋችን ውሀ ደግሰን በቁስ እግዚአብሄር ፊት መጋባታችን ምልክት ይሁንሽ ! አሁንስ አመ ንሽኝ ? ሶፊ ! ” ሲል ጥላሁን ፣ ሶፊያ የደገነችውን ረሽ ወዲያ ጥላ ፣ የደስታዋ ብዛት ሀይልዋን እጥፍ ስላደረገው ፣ በብዙ ችግር እያንፏዋ ቀቀች አምጥታ በር የዘጋችባቸውን ከባድ ጠረጴዛዎች በቅጥበት ወደ ጎን ገፍታ ፣ በሩን ስትከፍት ፣ እሱ ወደስዋ ፣ እስዋ ወደርሱ ሮጠው ተገናኙና ፣ ተቃቅፈው እዬተሳሳሙ ሲላቀሱ ቆይተው ትንሽ ጸጥ ሲሉ፣

“ እስቲ ቆይ መብራቱን ላብራና ልይህ ! ” አለች ሶፊ ።

“ በይ እስቲ አብሪውና እኔም ደህንነትሽን ልይ !” አለ እሱም ።

ከዚያ ፋኑስ አብርታ ባልዋን ስታይ ፣ ሊታግደው የማትችል ልቅሶ እንደገና መጣባትና ፣ ራስዋን እቅፉ ውስጥ ቀብራ ፣ ስቅቅ ብላ ታለቅስ ጀመር ። አሁን የደስታ ልቅሶ እደለም ። አሁን የሰራችው ወንጀልና በሱ ምክናያት ፣ እሱን ተከትሎ የሚመጣው የቃፎቀም ፣ ገና ያልታወ ቀም ከፉ ነገር ሁሉ ፣ መልኩን አክፍቶ በሚያስፈራራ አሆሁዋን ስለ መጣባት ፣ ከሱ ለመሸሽ ፣ እሱን ላለማየት ነው ራስዋን በቅፉ ቀብራ፣ አይንዋን ሸፍና ! እዬተንቀጠቀጠች ፣ ስቅቅ ብላ ታለቅስ የጀመረች፣

@OLDBOOKSPDF

"ተይ እንጂ ! ምነው ጸጥ በይ እንጂ የኔ እመቤት ! እንኩዋን እግዚአብሔር በጸሀና አገናኘን እንጂ ፤ አይዞሽ ከንግዲህ ምንም ቢሆን አንለያይም ! ቶሎ በቃ ጸጥ በይ " አለ ጥላሁን ፤ ፊቱዋን ሁሉ እየሳመ ። ከተጋቡ ጀምሮ ሶፊያን እንደዚያ ያንጠለጠለ ሆድ ሲብሳት አይቶ ስለ ማያውቅ ፤ ሁኔታዋ ልቡን አባባው ። እንዲያ ሲያባብላት ቆይቶ ትንሽ ጸጥ ስትል ፤

"እንዲያውም ዛሬ መዝፈን እንጂ ማልቀስ አይገባንም ነበር ! ከነ በርሁብት ስሮጥ የመጣሁ ፤ ደህና ከነገኘሁሽ የምስራች ነግሬሽ ደስ ብሉን እናድራለን ብዬ ነበር " አለ ።

"ምን የምስራች ነው ?" አለች ሶፊያ ።

"ቀኛዝማች ዳኘ ሞቱ ! "

"ቀኛዝማች ዳኘ ሞቱ ? ምን ገደላቸው ? "

"እግዚኦ . . . ! አገር ሰላም እንዲሆን ሁሉ እስከሁን በሩን ሳን ዘጋ ! ቆይ በሩን ዘግቼ ተመልሼ እነግርሻለሁ " አለ ጥላሁን ፤ ስጠ ዬቀችው መልስ ሳይሰጥ ፤ ዘወር ብሎ ሲያይ በሩ ተረስቶ ሳይዘጋ ስለ ቆዬ እንደ መደንገጥ ብሎ ወደዚያ ሲሄድ ። በሩን ዘግቶ ተመልሶ እሱ ፋው ላይ ሲቀመጥ ፤ ሶፊያ ሻሹ በጎኑ ተቀመጠች ።

"ምን . . . ማን ገደላቸው ?" አለች የውስጥ ጭንቀትዋን በሚያ ሳዩ ፤ የተጨነቁ አይኖችዋ የሱን ጠጋ ብላ እያዩት ።

"እኔ ልሁን ሴላ . . . የገደላቸውን አረጋግጬ ልነግርሽ አልች ልም ! " አለ ፤ አይኖቹን ሳያረግብ ፊት-ለፊት ተክሎ የቀኛዝማች ዳኘን ሁኔታ እዬተመለከተ ።

"ምን ማለትህ ነው ? አልገባኝም ፤ ጥላዬ ! "

"ማን ! በምን እንዳቆሰላቸው አላውቅም ። ብቻ ተጎልጉሎ የወጣ አንጀታቸውን በግራ እጃቸው አፍነው ይዘው ፤ በቀኛቸው የጎረሰ ሽንጣቸውን እያወናጩቶ ቢገቡ . . . ሊገድሉኝ ፈልገው ኖሮ ተሸ ሽጌ ስላጡኝ በጣም ተናደው ፤ 'በሴት እጅ ከመሞቴም ሌላ ያን ተማሪ ገድዬ ሳልበቀል መሞቴ ነው የሚቆጨኝ ! ' እያሉ እግዚአብሄ ርን ሲያማርሩ ፤ ከተሸሸግሁበት በያዝሁት እግርብረት ራሳቸውን ልባ ቸው ስሰናዳ ፤ የብረቱን ቅጭልታ ሰምተው ፤ በሚያስገርም ፍጥነት ዘወር አሉና ፤ ሳያነጣጥሩ ተኩሰው ለጉንሽ ሳቱኝ ! ወዲያው ሮጬ እን ደያዝሁዋቸው ፤ እኔን በግራ እጃቸው ለመያዝ ሆዳቸውን ሲለቁ " አለና፤

@OLDBOOKSPDF

አይኖቹን ጨፍኖ ፣ የትደፋ ራሱን በሁለት እጆቹ አስደግፎ እየወዘወዘ ፣ “ እንጀራችው ወጥቶ . . . ተዘረገፈ ! ” ሲል ፣ ሁለቱም እንጉታቸውን ደፍተው ዝም ብለው ቆዩ ። “ ክዚያ ” አለ ከዝምታው በሁዋላ ፣ “ ክዚያ የገዛ ሽጉጣቸውን ንጥቄ ስመታቸው ወደቁ ። እንዲያ ሆነው ቆስለው ፣ እንዲያ እንጀራቸው ሁሉ ወጥቶ ፣ ፍትንታቸውንና ብርታታቸውን ብታይ ትገረሚያለሽ ! ” አለና መሬት መሬት እያዩ ትንሽ ዝም ብሉ ቆይቶ “ ሀ! ” አለ ፣ ክዚያ ቀና ሲል ። “ ሀ !” እውነትም ጎበዝ ኖረዋል ! ብቻ ያ ፣ የሚያስገርም ጉብዝና ፣ ያ ፣ እንዲያ ያለ ብርታት ፣ የኛ ክፉ ሰው ባልነበርና ፣ ከሳቸው ጋር አብሮ ባልጠፋ ወይም አሳቸው ሲጠፉ ፣ እሱን ካሳቸው ነጥሎ አስቀርቶ ለበጎ ስራ መስጠት የሚቻል ቢሆን እንዴት ጥሩ ነበር ! የሆነ ሆኖ ወደ ጠዱቅሽኝ ጥያቄ ልመለስና ! ወደኔ ሲመጡ አሁን እንደ ነገርሁሽ ክፉኛ ቆስለው እንጀራቸው ሁሉ ወጥቶ ስለነበረ ፣ እኔ በመጨረሻ በሁለት ደሁን በሶስት የሽጉጥ ጥይት የመታሁዋቸው እንዲያው ለስሙ ያክል “ ገዳያቸው ” ያሰኘኝ እንጂ ፣ ምናልባት ካጭር ጊዜ በሁዋላ መሞታቸው አይቀርም ነበር ። እንዲያ ሆነው ቆስለው ፣ እንዲያ እንጀራቸው ወጥቶ መትረፋቸው ይቅርና ሌሊቱን ማንጋታቸው የሚያጠራጥር ነበር ። ስለዚህ ነው . . . “ ገዳያቸው እኔ ለሁን ” ሌላ ፣ እርግጠኛውን ልነግርሽ አልችልም ” ያልሁሽ ! ነገር ግን “ . . . ዛሬ ባይሆን የሁዋላ ሁዋላ ልገድላቸው ቆርጬ ነበር ! ” አለ ንግግሩን ሲጨርስ ለ መስማት በሚያስቸግር ዝቅተኛ ድምጽ ።

“ ደግሞ ሌላው ያልገባኝ ነገር . . . ታስረህ አልነበረም ? እንዴት አድርገህ ነው ሲገቡ ከታሰርህበት ሸሽተህ ለመሸሸግና ሁዋላ እሳቸውን ገድለህ ለማምለጥ የቻልህ ? ”

“ ወይዘሮ እጸገነት ፈተውኝ በስርቆሽ በር አብረን ወጥተን ልናመልጥ ስንሰናዳ ነው ቀኛዝማች የደረሱ ። ”

“ ወይዘሮ እጸገነት ፈተውህ አብራችሁ ልታመልጡ ! እንዴት እባክህ ? ” አለች በጣም ገርሞዋት ።

“ ዛሬ ተወርቶ የሚያልቅ አይደለም ፤ አሳድሮ ያውለናል ፣ ሶፊ ! ”

“ እንዲያው ባጭሩ ! ”

“ እንዲያው ባጭሩማ . . . ቀኛዝማች በሄዱበት የሚያድሩ ፣ ያለዚያም በጣም የሚያመሹ መሆናቸውን ስለሚያውቁ ፣ እንቋ የላ ክሽልኝን ራት አስይዘው በስውር መጥተው እያጽናኑኝ ሰበላ ፣ በነ

@OLDBOOKSPDF

ገር ሳቢያ የድሮ ባላቸውን እንሳንና ለካስ ቀኛዝማች የቤቱን ሰው ሁሉ አሳድመው "ምቀ" ብለዋቸው ፤ እሳቸውም በጥይት ተመቶ ሲወድቅ ባይናቸው ስላዩ ሁዋላ "ሞተ" ብለው የነገሩዋቸውን እምነው ኖሮ ዋል። ዛሬ ሸፍቶ እዚህ አገር ጫካ መኖሩንና ፤ ሲመሽ ሁልጊዜ ጨለማ ለብሶ ቀኛዝማችን ለመግደል ከተማ እዬገባ ማደሩን ስነግራቸው ... ምን ልበልሽ ፤ ጭራሽ እእምሮዋቸውን አጥተው እኔንም እስደነገጡኝ ። ሁኔታቸውን ብታይ ያስለቅሰሻል ! "

" እንዴት ! ባንድ ከተማ አብረው እዬኖሩ በህይወት መኖሩን እንኳ አያውቁም ነበር ማለት ነው ? የማይታመን ነው ! " አለች ሶፊያ ፤ በመገረም ።

" እኔም ተገርሜ ' እንዴት ነው ' ብዬ ብጠይቃቸው ፤ ' ከጥር ወጥቼ ሰው የማላይ ፤ ሰው ገብቶ የማያየኝ እስረኛ ነኝ ፤ አንዳንድ ጊዜ እንደናንተ ተጋብዘው ፤ ወይም ለስራ ከሚመጡትም በቀኛዝማች ፤ ወይም በጠባቂዎች ፊት ስለሆነ የምንገናኝ ፤ የድሮ ባሌን ወሬ ቀርቶ ስሙን ማንሳት ይፈሩ ! ' አሉኝ ። "

" ታሪክ ነው ! ታዲያ እንዴት ፈቱህ ? "

" ቀኛዝማች እቢታቸው ሰው ሲያስሩ ዘበኞችን እዬጠረጠሩ የግርብረቱን ጉዋጉንቸር መቆለፊያና መፍቻ እሳቸው እንዲይዙ ስለ ሚሰጡዋቸው ዛሬም ይዘውት ነበር ። "

" አሁን እንዴት ሆኑ ? "

" እንጃ ! የት እንደ ደረሱ አላውቅም ! "

" እንዴት ? አብራችሁ አልነበራችሁም ? "

" ከቀኛዝማች ጋር ለንቃግል ቆይተን በሽጉጥ መትቻቸው እንደ ወደቁ ዘወር ብል ከነበሩበት ቦታ አጣሁዋቸው ። ወዲያው ተዘግቶ የነበረው የጉዋሮ በር ተከፍቶ ስላዩሁ ፤ በዚያ ሮጨ ወጥቼ የቤቱን ዙሪያ ሁሉ ፈልጌ ላገኛቸው አልቻልሁም ። በሁዋላ ተኩሱን የሰሙ ዘበኞችም ፤ አሽከሮችም እዬተንጫጩ በፊት በር ስለ መጡብኝ ፤ በጉዋሮ በር ወጥቼ መሸሸጊያ ፍለጋ ወደ እጥሩ ብሄድ ፤ እዚያም የተ ከፈተ በር ስላገኘሁ በዚያ ወጥቼ መጣሁ ። ቀኛዝማች ከመምጣታቸው በፊት ለማምለጥ ስንሰናዳ ፤ ' በምእራብ በኩል ስርቆሽ በር አለና በዚያ ወጥተን እናመልጣለን ' ብለውኝ ስለነበረ . . . . ያ በር እኔ የወጣሁበት መሆኑ ነው ፤ እሳቸውም በዚያ ወጥተው ያመ ለጡ ይመስለኛል ፤ ያለዚያ ክፍት አይሆንም ነበር ። "

@OLDBOOKSPDF

" ወጥተው ይሆናል ። ታዲያ . . . . ባላቻውን ያገኙ ይሆን ? "

" አትጠርጥሪ ! እንዲያውም እስካሁን ሳይገናኙ አይቀሩ ! ተኩሱን ሲሰማና ግርግሩን ሲያይ ፣ መጀመሪያ እዚያ የሚደርስ እሱ ነው ! "

ሶፊያ ዝም ብላ አንገትዋን ደፍታ መሬት መሬት ስትመለከት ቆይታ ከዚያ ወደ ባልዋ ቀና አለችና ፣

" ይህ ሁሉ ታላላቅ ክፉና መልካም ነገር ላንድ ቀን አይበዛምን እያንዳንዱ ፣ ለብቻው አንድ ቀን ቢደርስ ለብዙ ቀን መገረም ይበቃ ነበርኮ ! አሁን ግን ሁሉም ባንድ ላይ ተደባልቆ ፣ ባንድ ቀን ደረሰና ፣ ለማዘን ይሁን ለመደሰት ፣ ለመገረም እንኳ አስቸገረ ! እኔ አሁን ደስ ብሎኛል ? አዝኛለሁ ? ወይስ ገርሞኛል ? ምን እንደሚሰማኝ በጭራሽ አላውቅም ፤ ደንዝዣለሁ ! "

" እንዴት ? አልገባኝም ፣ ሶፊ ! "

" አንተ ነጻ ሆነህ በደህና መገናኘታችን ደስ የሚያሰኝ ነው ። ወይዘሮ አጸገነትንና ባላቸውን የሚገጥማቸው እድል ፣ በጎ ይሁን ክፉ አለመታወቁ ልብ በቁዋፍ አቁሞ የሚያስጠብቅና በጣም የሚያሳስብ ነገር ነው ። የቀኛዝማች ሞትና በሳቸው ሞት ምክንያት ስስት አመት ደክመን ያቆቁዋምነው ንብረትና ስራ መበላሸት ፣ ይልቁንም ከሁሉ የበለጠ የመጣንለት አላማ መፍረሱና ከንግዲህ አንተና እኔ ምን እንደምናደርግ ፣ ወይም ምን እንደምንሆን ለማወቅ በማንችል በት ሁኔታ መገኘት በጣም የሚያሳዝን ነው ። እየውልህ እንግዲህ ይህ ሁሉ ባንድ ላይ ተደባልቆ ባንድ ቀን ደረሰ ! ታዲያስ ! እንዘን ? ደስ ይበለን ወይስ ይግረመን ! "

" እንደኔ አስተያየት " አለ ጥላሁን ፣ ምኽቱን አተኩሮ እዩ ተመለከተ ሲሰማ ቆይቶ ። " እንደኔ አስተያየት ፣ ዛሬ የደረሰው ታላቅ ነገር አንድ ብቻ ነው ፤ እሱም የቀኛዝማች ዳኘ ሞት ነው ! ሌላው ሁሉ እሱን ተከታትሎ የመጣ ፣ የሱ ዘርፍና ቅርንጫፍ ነው ። ድሮውንም ፣ ' አንድ ታላቅ ነገር ደረሰ ' የሚባለው ፣ በራሱ ታላቅነት ብቻ ሳይሆን ፣ እሱን ተከታትለው ብዙ ታላላቅ ነገሮች እንዲደርሱ ስለሚያደርግ ነው ። ስለዚህ የቀኛዝማች ዳኘ ሞት ፣ የኗያ የመልካም ስራና የመልካም ስሪ ጸር መወገድ ፣ ላሁን ብቻ ሳይሆን ለወደፊትም የመልካም ስራና የመልካም ስሪ መሰናክል መወገድ ፣ አውራ መንገድ

@OLDBOOKSPDF

መጠረግ ፣ ስለሆነ በጣም ደስ የሚያሰኝ እንጂ ፣ ምንም የሚያሳዝን
ነገር የለበትም ። ”

“ በጠቅላላ እንጋገር . . . እንደምትለው ሊሆን ይችላል ፣ ማለት
የቃኛዝማች መጥፋት ፣ መልካም እየሰሩ በሰሩት መልካም ስራ ደስ መሰ
ኘት ለሚመኙ ሁሉ ጥሩ እድል ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን . . . ላን
ተና ለኔ አይሆንም ጥላዬ ! ከንግዲህ አንተና እኔ በቃን ” አለች እንባ
ያዘሉ አይኖችዋን ፊት ለፊት ተክላ ።

“ እንዴት በቃን ? ለምን በቃን ? ” አለ ጥላሁን እንደ መቆጣት
ብሎ ።

“ እንዴት በቃን ! አገረገዥ መግደልህን ረሳኸው ? እንኩዋን
አገረገዥ ሌላስ ያገደለ ፣ መሰቀል በታምራት ቢቀርለት ፣ ወህኒ ቤት
ገብቶ መሰቃየቱ ቀርቶ ነው . . . ታላላቅና መልካም ስራ እዩሰራ
ደስ ሲለው እንዲኖር የሚፈቅድለት ? አንዳንድ ጊዜኮ . . . የምታስገ
ርም ነህ ፣ ጥላዬ ! ”

“ ልክ ነው ፣ እውነትሽ ነው ! የሚስገርም ነኝ ! አሁን ሳስ
በው እኔንም ገረመኝ ! ሀ ! እሳቸው ሲሞቱ ሳይ ፣ እኒያ የመልካም
ስራ መሰናክል ከመንገድ መወገዳቸው የሰጠኝ የደስታ ብዛት ፣ የኔ
እጅ የሰራውን አስረስቶ ፣ በኔ የሚደርስብኝን እንዳላይ ሸፍኖኝ ኖሮ
ዋል ! ” አለ ፣ ማንባሩን ቋጥሮ ፣ ፊታ እያደረገ ትንሽ አጥልቆ ሲያ
ስብ ቆዩና ።

“አሁን ከዚህ ከመሄድ የተሻለ ሌላ ነገር አይታዩኝም ፣ ጥላዬ !
ያውም አሁን ነው እንጂ ከቆዩን እንያዛለን ! ”

“ ሀ ! ያገርማል ! ‘ ድል ነስቶ መሸሽ ’ ማለት ይሄ ነው ! የመ
ልካም ስራ ጠላታችን ጠፍተው ፣ እንቅፋቱ ተነቅሎ ፣ መንገዱ ተጠርጎ ፣
ወዳሰምነው የተቀደሰ አላማ ባጭር ጊዜ ለመድረስ በምንገሰግስበት
ጊዜ ፣ በክፉ አጋጣሚ እኒያ ክፉ ሰው በሌላ እጅ የሞት ፅዋቸውን
ተሸክመው አምጥተው በላላቀፉኝ ፣ ነፍሰ ገዳይ ሆኘ ፣ ሁሉንም ጣጥዬ
መሸሽ ! እንዴት ያለ ክፉ አጋጣሚ ነው ! እስቲ . . . መሞታቸው
ባይቀር ፣ እዚያው በቆሰሉበት ቢሞቱ ፣ ያለዚያም ያንድና የሁለት
ሰአት እድሜ ከድሜ ይቆጠር እንደሆነ ፣ ወደኔ በመምጣት ፈንታ . . .
አቢታቸው ገብተው ፣ ያን ያክል ቆይተው ቢሞቱኮ ይህ ሁሉ አይደ
ርስብንም ነበር ! ” አለ ፣ ምሽቱን ፊት-ለፊት አተኩሮ እያዩ ።

@OLDBOOKSPDF

" ያም ቢሆን . . . ያም ቢሆን አይቀርልንም ነበር አለች ፣ አይኖቹ ዋን ከባልዋ አንገታ አመሬት ላይ ተክላ በትተክዝ ቆዬችና ።

" እንዴት ? ምኑ አይቀርልንም ነበር ? "

" በቆሰሉበት ቢሞቱ ፤ ወይም አቤታቸው ገብተው ፣ እንድም ይሁን ሁለት ሰአት ቆይተው ቢሞቱ ፣ የሰራነውን ሁሉ አፍርሰን ወደፊት የምንሰራውን ትተን ከመሸሽ አናመልጥም ነበር ! ይልቅ ጊዜ ሳናጠፋ ፣ የምንይዘውን ትናንሽ ነገር እንያዝና ቶሎ ከዚህ እን ሂድ ! "

" እንዴት ? "

" ቀኛዝማችን ያቆሰልሁዋቸው እኔ ነኝ ፣ ጥላዬ ! ስለዚህ እዚህ ቤት ቢሞቱ እኔ ለመግደሉ ምስክር ለለማያሻው አቤታቸው ገብተው ቆይተው ቢሞቱ ፣ ግን እንደ ገደላቸው መናዘዛቸው ስለማይቀር ፣ ወን ጀሉ ዞሮ ዞሮ ከራሳችን አይወርድም ነበር ። " አንቺ ! ቀኛዝማች . . . እዚሁ ቤት መጥተው አቆሰልሻቸው ! እንዴት ? መቼ ? " አለ ጥላሁን፣ ከድንጋጤው የተነሳ የንግግር ስራት ያልተከተሉ ቃሎች አከታትሎ እን ጎድጉዶ ።

ሶፊያ ፣ ቀኛዝማች ዳኘ ማታውን በብዙ አሽከሮቻቸው ታጅበው መጥተው ፣ እግቢያ ከገቡ ጀምሮ አቁስላቸው እስኪሄዱ እሳቸውም፣ እሰዋም ያደረጉትን ሁሉ አንድ ሳይቀር ለጥላሁን ስትተርክለት ታሪኩ ድርጊቱን መልሶ እምጥቶ በጉልህ ስላሳያት ፣ የፍርሀት የቁጣ ፣ የሲቃና እንባውን የመሳሰሉ ስሜቶች ሲለዋወጡባት ክፊትዋ ይታዩ ነበር ። ሶፊያ ታሪክዋን ተርካ ስትጨርስ፣ ጥላሁን የተሰማውን ምሬት የሚገልጽበት ቃል ስላጣ ተነስቶ ፣ እጆቹን በግራና ቀኝ ኪሶቹ አግብቶ ፣ አፉም ፣ ፊቱም በንዴት እየተንቀጠቀጡ ከወዲህ ወዲያ ከወዲያ ወዲህ ፣ ዝም ብሎ ሲንጎራደድ ቆዬና ፣

" እየ ጉድ ! " አለ ። " እየ ጉድ ! በስልጣን ስም እኔን በግርብ ረት አስረው አቤታቸው ውስጥ ዘጉብኝና ፣ የታሰርሁበትን እግር ብረት ሰብሬ ፣ ቤት ቀድጄ እንዳላመልጥ ፣ በስልጣን ስም በዘበኛ ተከብቤ እንድጠበቅ አደረጉና ፣ እሳቸው ሚስቴን ሲደፍሩ ጨለማ ለብሰው አቤቴ መጡ ! ይህ ሁሉ በስልጣን ስም !

ሀ ! እየ ስልጣን ! የሰው ህይወትና ንብረት ፣ መብትና ነጻነት እንድታስከብሪ የሀይል ሁሉ ባለቤት ሆነሽ ፣ ከሁሉ በላይ ከፍ ብለሽ የቆምሽ ስልጣን ! አንቺ ራስሽ ሀይል የሰጠሻቸው አመጸኞች ፣ በሰጠሻ ቸው ሀይል ከቆምሽበት የከብር ቦታ ጎትተው አውርደው እንዲህ ላለ

@OLDBOOKSPDF

ወራዳ ስራቸው መጋረጃ ሲያደርጉሽ ዝም ብለሽ መንቶት ! እየ ስልጣን ! ከቶ ምንድነሽ ? ትንሹን ትልቅ ፣ ድሀውን ሀብታም ፣ ትሁቱን ኩሩ ስታደርጊ ፣ የትልቅነት ፣ የሀብትና የኩራት ሁሉ እመቤት ትመስ ያለሽ ! ነገር ግን ደግሞ እንደገና ተመልሰሽ ፣ ትልቆች ላደረግሻቸው አመጸኞችና ሀብታሞች ላደረግሻቸው ስስታሞች ስታገለግይ ፣ የራስሽ ፈቃድ የሌለሽ ፣ የሚያዝዙሽን ብቻ የምትፈጽሚ ባሪያ ነሽ ! እየ ስልጣን ! እረ ባህሪሽ ምንድነው ? ለሌሎች ሀይል ስትሰጭ ፣ ሀይል የማያልቅብሽ ፣ የሀይል ሁሉ ፈጣሪ ትመስያለሽ ! ነገር ግን አመጸኞች በለገስሻቸው ሀይል እንችኑ ራስሽን ጠምዘው ፣ ቆልምመው ፣ አለበ ታሽ ሲያውሉሽ የምትመከችበት እንኩዋ ሀይል የለሽም ! ስልጣን ! ያነሳሻቸው በጭቃ ጥለው ሲረጋግጡሽ ፣ ያስጌጥሻቸው ሲያንሳቁሉሽ፣ ያከበርሻቸው ሲያዋርዱሽ ፣ ጌቶች ያደረግሻቸው ባሪያ ሲያደርጉሽ ፣ የማትበቀይ ከሆንሽ ፣ በስምሽ የተጠቁ ሁሉ እንቺን የሚበቀሉበት ጊዜ ይመጣል ! ” ሲል ያች የሚወቅሳት ስልጣን እዚያ በፊቱ እንደ ቆመች ሁሉ አይኖቹን ፍጥጥ አድርጎ ፊትለፊት ተክሎ ፤

“እዚህ ቤት ፤ ቤቶች ፤ ቤቶች ፤ ተኝታችሁዋል ? ” አለ አንድ ድምፅ ከዚያ ጥላሁን መኖገሩን ትቶ ፣ ከሶፊያ ጋር ላጭር ጊዜ የጥያቄ አይን ከተለዋወጡ በሁዋላ ፣ የንረሰ ሽጉጡን ከጠረጴዛው ላይ አንስቶ ፊት ለፊት ደግኖ ፣ ወደ በሩ ጠጋ አለና “ማነው ? ” አለ ።

“እኔ ጉደታ ራጎ ነኝ ፤ ክፈቱልኝ ” አሉ ባላምባራስ ጉደታ ።

“እቤት ፤ ያንት ያለህ ! እንዲያ አገር ሲሸበር ፣ ከተኩሱ ብዛት የተ ነሳ እንዲያ . . . ሰማይና ምድር የተደባለቀ ሲመስል ፣ እናንተ ምንም እንዳልሆን ሁሉ እዚህ ዝም ብላችሁ ፣ አርፋችሁ ተቀምጣችሁዋል ? ” አሉ ባላምባራስ ፣ ጥላሁን ሲከፍትላቸው እዬሮጡ ገብተው ።

“ምን እናድርግ ? ወዴት እንሂድ ? ማን በማን ላይ መሆኑን እና ውቅም እንጂ . . . ተኩሱንማ እንሰማለንኮ ! ” አለ ጥላሁን ።

“ሀ ! ምን እናድርግ ! ሽሽዋ ! ከዚህ ዘወር ብላችሁ ፣ ወደ ጫካ ሄዳ ችሁ ብትቆዩ ይሻላል ፤ ከዚያ በሁዋላ የምታደርጉትን እዚያ ሆናችሁ ትማከራላችሁ ። ”

“ለምን ? በምን ምክናያት እንሸሻለን ? ” አለ ጥላሁን ፣ ከምሽቱ ጋር ከተያዩ በሁዋላ ።

@OLDBOOKSPDF

"ቃኛዝማች ዳኘ ሞተዋል ። 'ገዳዮች ናቸው' ተብለው ከተጠረጠሩትም አንዱ አንተ ነህ ። ምክንያቱ ወድቆ የተገኘው አንተ ታስረህበት በነበረው ቤት ስለሆነና ፣ አንተ ከዚያ ስብረህ በመጥፋትህ ነው ። ሌላው ተጠርጣሪ የሚስቱ የድሮ ባል ነው ። ስለዚህ ፣ ነገሩ እስኪጣራ ገለል ብላችሁ ብትቆዩ ይሻላል ። ያለዚያ ፣ እንጋት ላይ ፣ ፖሊሶች ቤታችሁን ከበው ሊይዙዋችሁ ነው ።"

"እስቲ ትንሽ ቁጭ እንበልና የሆነውን ሁሉ ረጋ ብለው ይንገሩን አባባ" አለ ጥላሁን ፣ ባላምባራስ መቸኮላቸው ከሁለመናቸው በግልጽ ይታይ ስለ ነበረ ።

"እይ . . . ጊዜ ባናጠፋ እወድ ነበር !" አሉና ባላምባራስ ፣ ሁሉም እንደ ተቀመጡ የሆነውን ለጥላሁንና ለሶፊያ መንገር ጀመሩ ።

"ሰው መሆን የማያስመኝ ነገር ነው ፤" አሉ የተደፋ ራሳቸውን በጃቸው እስደግፈው እየወዘወዙ ። "ቃኛዝማች ዳኘ ፣ ያ ማን አለብኝ ባይ ፣ ጎበዝ ፣ ሆዱ ተዘንጥሎ ፣ አንጀቱ ወጥቶ ተዘርግፎ ፣ ሌላ አካላቱ ሁሉ በጥይት ወንፊት ሆኖ ወድቀዋል ! መቸስ የብርታቱ ነገር የሚያስገርም ነው ፤ ለብርታቱ ከከፋቱ በቀር ተወዳዳሪ የለውም ። እንዲያ አንጀቱ ከሆዱ ወጥቶ ተዘርግፎ ፣ እንዲያ የትከሻው አጥንት ደቅቆ ፣ ፖሊሶች ደርሰው ኦዛዜውን እዩዳሉ ፣ በጽሑፍ መፈረም ስላልቻለ በጣቱና በማህተሙ እስኪያትሙ ፣ ነፍሱ ከስጋው አልተለዩችም ። ነፍሱ ካለፈች በሁዋላ ፖሊሶች ለብቻቸው ተሰብስበው ፣ "ቃኛዝማች ዳኘ ገዳያቸው ጥላሁን ፈይሳ መሆኑን እንጂ ፣ የትኛው ጥላሁን ፈይሳ መሆኑን ለይተው ሳይናገሩ ነፍሳቸው ስለለፈችና ፣ አስተማሪ ጥላሁን ፈይሳ ሜካ በመግባቱ ምንም ማድረግ ስለማይቻል ፣ የቃልቻ ጥላሁን ፈይሳን ቤት እንጋት ላይ ከብቦ ወዲያው እሱን መያዝ ነው" ብለው ሲወስኑ በዉለማ ጥግ ይገር ቆሜ ሰማሁዋቸው ። ስለዚህ ነው . . . በጊዜ ገለል ብላችሁ እንድትቆዩ ልነግራችሁ እዩሮጥሁ የመጣሁ ።"

"የቃኛዝማች ዳኘ ገዳይ አስተማሪ ጥላሁን ለመሆኑ ፣ የሚሰታቸው መጥፋት ጥና ምስክር ስለሆነ ፣ 'ቃልቻ ጥላሁንን መያዝ አይገባንም' ብለው የተከራከሩ ፖሊሶች ነበሩ ። ነገር ግን በተለይ አለቅዩው ፣ 'ቃልቻ ጥላሁን ከታሰረበት ሰብሮ መጥፋቱና ፣ ቃኛዝማች እዚያ ወድቀው መገኘታቸው ፣ ለወንጀሉ ስራ ካስተማሪ ጥላሁን የበለጠ ባይሆን ያላነሰ ባለቤት ስለሚያደርገው ፣ እሱን ይዘን መመርመርና ማጣራት አለብን' ስላለ ፣ በዚህ ወሰኑ ። ስለዚህ ፣ የየኪ ፖሊስ መርምሮ እስኪያጣራ ፣ 'እህያ ቀንድ ታብቅላለችና' የሚሻለው አስቀድሞ እንሱ ጥፍር ውስጥ አለመግባት ነው ፣ ልጆቼ !"

@OLDBOOKSPDF

"ከንጋት በፊት ቢመጡስ?" አለች ሶፊያ ።

"ሌሊቱን ከበን እንደር" ያሉም ነበሩ ፤ ነገር ግን ፣ "ድንገት ንቅቶ የተኮሰብን እንደሆነ አደጋ ሊደርስ ፤ እንዲያውም ነፍስ ሊጠፋ ስለሚችል ፤ እንጋት ላይ ቤቱን ከብቦ ወዲያው እጁን እንዲሰጥ ማድረጉ ይሻላል" የሚሉት ስለበዙ በዚሁ ወሰኑ ። ይሁን እንጂ ፣ ምንጊዜም አሳባቸውን ሊለውጡ ስለሚችሉ ፣ 'አሁኑን የሚያረገውን ሁሉ አድርጎ ፣ ቶሎ ገለል ማለቱ ይሻላል' ያልሁዋችሁ . . . ለዚህ ነው ።"

"እርስዎ ወዲህ ሲመጡ ፖሊሶች እዚያው ፕረዋል?" አለ ጥላሁን ።

"ሁዋላማ ፣ ህዝቡ ጥሶ ገብቶ የቀኛዝማች ዳኜን ቤት መዝረፍና በሚዘረፍ ነገር ላይ እሰበሱ መታኮስ ሲጀምር ፣ ሁሉም ካደጋ የሚሰውርና የሚዘረፍ ነገር የሚገኝበት ወደ መሰለው አሽቅድድሙን ያዘ ። ወዲያው ተኩሱ ሲጀመርና ሽብር ሲነሳ ፣ ፖሊሶች ራሳቸው ተበራግው እየተነሱ በየፊናው ስለ ተበታተኑ ፣ እዬአሉ ሲያትሙ ያመኙትን ነገዜ እንኩዋ ከነሳጥኑ እዚያው ተሰብስበው ባመኙበት ጥለውት ሄደው ጣሞች . . . እኔ ፎሬ ሲሻሙት አዬሁ ።"

"ሳጥኑስ ምን ሳጥን ነው?" አለ ጥላሁን ።

"ምን እንደ ሆነች አላውቅም ፤ ቀኛዝማች ዳኜ ጋሽ ጃግሬውን አስይዞ በሚሄድበት ሁሉ የማይለያት ፣ ትንሽ ባለማንጠልጠያ የብረት ሳጥን ናት ።"

"ታዲያ" ፖሊሶች ህዝቡ ቤት ሲዘርፍና ተኩስ ከፍቶ ሽብር ሲያነሳ . . . ዘረፋውን እንዲተውና ጸጥታ እንዲከበር በማድረግ ፈንታ እነሱም እንዲያ ባሰው ሁኑ-ወጥ ስራ ተባባሪዎች ሆኑ?" አለ ጥላሁን ።

"ወይ ዘረፋ ማስተውና ጸጥታ ማስከበ . . . ር ! የቀኛዝማች ዳኜን ሬሳ እንኩዋ እንዳይገፈፍ ማድረግ አልቻሉም ! ሬሳው ተገፍፎ ፣ ልብሱን ሰው ስለ ተሻማው ፣ ራቁቱን የተለበለበ ግንድ መስሎ እዚያ ወድቆዋል ! ፖሊስ . . . ሰላም በሰፈነበት ፣ ህግ በተከበረበት ጊዜ ፣ ህግን ተመርኩዞ ፣ ባንድ ወይም በጥቂት ሰዎች ላይ ነው እንጂ ጉልበቱ ፣ ህዝብ ባንድ ላይ ሆኖ ህግን ሲጥስና ሰላምን አፍርሶ ሲነሳ ፣ ፖሊስስ ቢሆን ምን ጉልበት አለው መሰለህ ፣ ልጄ ! እንዲያ ባለው ጊዜማ ፣ ፖሊስም እንደ ሌላው ሰው ሁሉ የራሱን ደህንነት ፈላጊ ነው ! ይልቅ ጊዜ ሳይባክን የማይቀር የማይቀረውን ነገር ያዙና ፣ ቅድም እንዳልሁዋችሁ ፣ ከቦሊሶች አይን ሰወር ብላችሁ የምትቆዩበትን መንገድ አፍብጁ ! እዚህ አጠገባችን ፣ ካውሬ በቀር ሰው የማያውቀው ፣ አንድ ማስፊያ ዋሻ አለ ። ነገሩ እስኪጣራና የምታደርጉትን ወደ ፊት እስክትወስኑ ፣ ልውሰዳችሁና

@OLDBOOKSPDF

እዚያ ቆዩ ። እዚያ የፈለጋችሁትን ያክል ብትቆዩ ፤ "ፈላጊ ያገኛል" ብላችሁ የምትሰጉበት ነገር አይኖርም ። አባቴ ፤ ለኔና ላንድ እሽከራቸው ብቻ ነበር ያሳዩን ፤ እሱ ሞቶዋል ! "

"እስቲ ሳጭር ጊዜ ይቅርታ ያድርጉልንና ፤ ሶፊያና እኔ ተነጋግረን እንምጣ ፤ አባባ " ብሎ ጥላሁን ከምሽቱ ጋር እምኝታ ቤታቸው ገብ ተው ፤ ተመካክረው ሲመለሱ ፤ የወሰኑትን ለባላምባራስ ነገሩዋቸው ።

"አባባ" አለ ጥላሁን ፤ ሶፊያ ከባላምባራስ ጎን ስትቀመጥ እሱ እፊ ታቸው ቆሞ ። "አባባ ፤ አሁን እንደ መከሩን ከዚህ ወጥተን ለጊዜው ወደሚያሳዩን ሰዋራ ቦታ ሄደን እንቆያለን ። ከዚያ ወዴት እንደምንሄድ ገና እናውቅም ፤ ብቻ እንደገና ወደዚህ የምንመለስ አይመስለንም ። ስለ ዚህ ፤ ባለቤቴና እኔ እዚህ ሶስት አመት በቆዩንበት ጊዜ የሰራናቸውና ለመስራት የጀመርናቸው ፤ ለዚህ አገር ህዝብ መጠነኛ ኑሮ እጅግ አስፈ ላጊ ናቸው ። ነገር ግን ጥቅማቸው ባይሰመድ እኛ ባለመኖራችን የተቋ ዋረጡ እንደሆን ፤ ጭራሽን ሲጠፉና ድካማችን ሁሉ መና ሆኖ ሊቀር ይችላል ። ስለዚህ ፤ ስራችን እንዲቀጥል ህዝቡን የማበረታቻ ቃቱንና የመ ምራቱን አደራ በርስዎ ላይ ጥለን ለመሄድ ተመካክረን ወስነናል ።
ይህን አፎ ቢሉን ሶስት አመት የደከምነው ድካም ከንቱ ሆኖ እንዳል ቀረ ፤ የዚህ ክፍል ህዝብ በገባ ጥረቱ ኑሮውን እንዲያሻሽል በትንሽዋ እውቀታችን መጠን ያስተማርነው ትምህርት እንደማይረሳ አምነን ፤ አባ ባችን ወደ ሁዋላ ሳይጎትተን ፤ ደስ እያለን ወደምንሄድበት እንሄዳለን ።

" ሁለተኛ ፤ እርስዎም እንደሚያውቁት ፤ ይህን ቤት መሬቱን በገንዘ ባችን ገዝተን የሰራነው ፤ ተከራካሪ የሌለበት ስለሆነ ፤ ደጃፍ በጎረቤ ፤ ማጇጉት በመለስ ፤ በውስጡ ያለውን እቃና ቤቱን እንዲኖሩበት ፤ ቢፈል ጉም እንዲሸጡት ፤ እንዲሰጡጡት ፤ በስጦታ ሆኖ በውርስ ለሌላ እንዲያ ስተላልፉት ፤ ንብረት አድርገን ሰጥተንዎታልና ፤ ፈቃድዎ ሆኖ ቢቀበ ሉን አሁን እንፈርምልዎታለን አባባ ።

" ሶስተኛ፤ለዚህ አገር ጣማዎች፤መሰንጎዎችና ሽኮዎች፤ካሁን ቀደም ካከፋፈልናቸው መሬት ሌላ ፤ ቡና በዘመናዊ እቅድ ያለማነው አንድ ጋሻ መሬት ፤ ውብቱ በለማችን ገዝቶ የሰጠን ፤ ህጋዊ ርስታችን ስለሆነ ፤ እን ዚህ የቆጠርሁዋቸው ወገኖች ፤ አብረን ያቋቋምነውን ማህበር ሳያፈ ርሱ ፤ የጋራ እዩሰሩ ፤ እርስዎ መሪያቸው ሆነው እስከሚቆዩበት ጊዜ ድረስ ፤ ከትርፉ ከመቶ አስር ካነሱ በሁዋላ ፤ ቀሪውን ትክክል እንዲካ ፈሉ የጋራ ርስት አድርገን መስጠታችንን ፤ አሁን እንፈርማለን አባባ ።

@OLDBOOKSPDF

“ እራቶቹ ፤ የሀልና የቡና ወፍጮዎች ፤ ምንም እንኳ እኛ በንጽህ ናችን የገዛናቸው ቢሆኑ ፤ የማህበሩ ንብረት እንዲሆኑ ወስነን ከዛሬ ቀደም ብለ ፈረምን ፤ አሁን እንደገና መፈረም የሚያሻ አይመስለኝም ። ነገር ግን ሶፊና እኔ ማህበርተኞች በመሆናችን ፤ ከወፍጮዎች ገቢ ይደርሰን የነበረውን ፤ የጎልማሶች ትምርት ቤት ለሚሰራበት አንዳንድ ነገር መሙያ እንዲያደርገው መስጠታችንን ፤ አሁን ፈርመን ለርስዎ እንሰጣለን ።

“ ከዚህ በተረፈ የምንነግርዎ ፤ ምንም እኛ ብንኖር . . . ለመልካም ስራ እንቅፋት የነበሩትን ሰው ፤ እግዚአብሔር እኛን መሳሪያዎቹ አድርጎ ካስወገዳቸው ፤ ከንግዲህ ወዲያ ምንም ቢሆን ፤ ሰይጣን ካልሆነ ፤ መልካም ስራ ቢጠፋ የሚወድ ሰው በሰቸው እግር ይተካል ብለን የማንጠራጥር መሆናችንን ነው ። ስለዚህ ፤ የህክምናውና የትምርቱ ስራ መቅረቱ ግዴታ ቢሆንም ፤ የተሰሩት የውሀ ግድቦች ፤ ጎዳናዎችና ማጠራቀሚያዎች ፤ የያንዳንዱ ሰው የጉዋሮ አታክልትና የሩቅ አዝመራ አጠባበቅ ፤ በሽታን ለመከላከል የተቆፈሩትመው የድሬን ደንብና አኳሆን የመሳሰሉት ጠቃሚና በመለመድ ላይ የነበሩት ስራዎች እንዳይበላሹ . . . እደራ ! ”
አለ ፤ እሱና ምሽቱ ሶስት አመት የኪ በቆዩበት ጊዜ የሰሩትን ስራ ፤ የፈጠሩትን ልዩ ልዩ አስደናቂ ነገር ሲቆጥር ፤ ያ ሁሉ ሲጠፋ ፤ እንዳልነበረ ሊሆን የሚችል መሆኑ ጭምር ስለታዩው ፤ ጊንባ እየተናነቀው ። የባሊ ዋን ሁኔታ ስታይ ስሜቱ ከሱ ወደበዋ ተላለፈና ሶፊያም እንባትዋን ደፍታ ታለቅስ ጀመር ።

“ ሀ ! አልተሳሳትሁም ፤ ካንተ በቀር እንዲህ ያለውን ስራ ለመስራት የሚደፍር ሌላ እንደሌለ የገመትሁት ትክክለኛ ግምት ነው ! ”
አሉ ባላምባራስ ለመስማት በሚያስቸግር ዝቅተኛ ግምት ፤ ጥላሁን ሲናገር አንገታቸውን ደፍተው ሲያደምጡ ከቆዩ በሁዋላ ፤ ለመሬቱ እንደሚናገሩ ሁሉ መሬት መሬቱን አትኩረው እያዩ ። ከዚያ ቀና ብለው የባልና ምሽቱን አይኖች በንባ ቀልተው ስላዩ ፤

“ ለምን ታለቅሳላችሁ ? አታልቅሱ እንጂ ! አታልቅሱ ልጆቼ ። የሚያስፈክር እንጂ የሚያስለቅስ ነገር የለምኮ ! ” አሉ ።

“ ደግሞ ልቅሶ ይብዛብን ? የመጣንለት አይነተኛ አላማኮ አልም ብሎ ሆኖ ቀረ አባባ ! ከዛሬ ቀደም የተሰሩት አንዳንድ ነገሮች እንኳ አሁን እደራ እንዳልንዎ እርስዎ ከተከታተሉዋቸው አይጠፉ ይሆናል ። በጠቅላላው ህዝቡ ራሱን በራሱ አዩረዳ ኑሮውን እንዲያሻሽል ለማስተማር ያቀድነው አይነተኛ አላማ ግን ቀረ ! ” አለ ጥላሁን ። ባላምባራስ ፤ ጥላሁን ለተናገረው መልስ ሳይሰጡ አይኖቻቸውን አመሬቱ ላይ ትክለው ፤ ዘለግ ላለ ጊዜ ዝም ብለው ሲመለከቱ ቆይተው ፤

@OLDBOOKSPDF

"እግዚአብሔር . . . ረዥም እድሜ ፡ የማቱሳላን የሚያክል እድሜ ሰጥቶህ ፡ በዚያ ሁሉ እድሜ ለዚህ አገር ህዝብ ስትሰራ ብትኖር ፡ ዛሬ በዚች ዛንድዋ ሴሊት ያደረግህለትን ያክል ሊታደርግለት አትችልምና ፡ ይልቅ ሳታዝኑ ፡ ሳትጸጸቱ ደስ እያላችሁ ሂዱ ። ሌላው . . . ይሄ 'ህዝቡ ራሱን በራሱ እዩረዳ ኑሮውን እንዲያሻሽል ለማስተማር የነበረን አላማ' የምትለው መቸም . . . እንዲያው ነው !" አሉ ።

"እንዴት አባባ ?" አለ ጥላሁን በመገረም ። ሶፊያም የባልዋን የመገረም ጥያቄ ባይንዋ ጠዩቃቻቸው ።

"ለዚህ አገር ህዝብ ከቀኛዝማች ዳኘ ፡ ከዚያ ከፉ ቂራኛ ፡ ከዚያ ብበላ መጠን ሲርበው የሚኖር ጭራቅ ከመላቀቁ የበለጠ ትልቅ ነገር ፡ ትልቅ እረፍት አይገኝምና ፡ ከሱ መገላገልህ ፡ ከሱ ማላረፍህ ማንም ሊያ ደርገው ያልቻለ ፡ ትልቅ አገልግሎት ነው ! ከንግዲህ ወዲያ ፡ ቅድም እን ዳልኸው ምንም ቢሆን ፡ ሰይጣን ካልሆን ፡ እንደሱ ክፉ ለመስራት ሲያ ልም የሚያድር እንደማይመጣ የታውቀ ነው ። እንዲሁም ደግሞ . . . መላክ ካልሆን ህዝቡን ራሱን በራሱ እዩረዳ ኑሮውን እንዲያሻሽል ፡ ወይም ብዙ ጊዜ ስትናገሩ እንደምሰማው ፡ 'ራሱን ለማስተዳደር እንዲ ማር' የሚፈቅድ ገዥ ምንም ቢሆን ይኖራል ማለት . . . የማይመስል ነገር ነው ። ስለዚህ ሊፈጸም የማይችል ነገር አይነተኛ አላማ አድርጎ መያዝና ፡ እንደገና ተመልሶ ባለመፈጸሙ መቆጨት ፡ 'እንዲያው ነው' ያልሁት ለዚህ ነው !" አሉ ባላምባራስ ።

"እንጃ ! አሁንም ቢሆን አባብዎ ሶፊንና እኔን ከቅድሙ የተሻለ የገባን አይመስለኝም ፡ አባባ !" አለ ጥላሁን ፡ ከምሽቱ ጋር የጥያቄ አስ ተያየት ከተለዋወጡ በሁዋላ ።

"ህም . . . . ! ህዝብ ፡ 'ኑሮየ የሚሻሻልበትንና የምተዳደርበትን ዘዴ አውቄ እኔ ራሴን እስተዳድራለሁ ካለ . . . አገረ - ገዥ ምን እያረገ ይኖራል ? አገረ - ገዥ ህዝቡን ሲገዛ የሚኖር ፡ አያርገው እንጂ ፡ መቸስ ሰሙ ፡ ምክናያቱ ህዝብ በደህና ማስተዳደርና የህዝብ ኑሮ ማሻሻል አይ ለም ? እሱ ከሴለ ያገረ - ገዥ ቦታ የለውምኮ ! ፣ ስለዚህ . . . እንደኔ እን ደምን ፡ እንዲህ ያለውን ትምርት እናስተምር ለሚሉትም ሆነ እንማር ለሚሉ ፡ ፈቃድ የሚሰጥ መላክ እንደሆን እንጂ ፡ ስጋ የለበሰ አገረ - ገዥ እዚህ ይመጣል ብዬ ስለማላምን ፡ እንዲህ ያለውን የተቀደሰ አሳብ ይዛ ችሁ ፡ ብዙ ጊዜ ስትናገሩ እንደ ሰማሁት ያለ አለም ካለ ፡ ወደዚያ መሄድ ነው !" አሉ ባላምባራስ ፡ ምንም እጅግ ቢያዝኑ ፡ ራሳቸው በተናገሩት አሽሙር ፊታቸው በጊዜያዊ የቅርታ ፈገግታ ሲዋብ እዩታዩ ። "አሁን ግን" አሉ ወዲያው ቀጥለው ፡ "አሁን ግን አደራ ያላችሁኝን አስቤበት ወዲያውም ቢመች አቶ አሳዩንም ይገር መጥቼ እስከንነጋገር ፡ የምትይ ዙትን ያዙና ቶሎ ወደ መሸሸጊያ ዋሻችሁ ልውሰዳችሁ ።"

@OLDBOOKSPDF

## ምእራፍ ፴

# ካውሬ በቀር ሰው የማያውቀው ዋሻ

ጥላሁንና ሶፊያ ፡ ባላምባራስ ጉዴታ ተሸሽገው ወደሚቆዩበት ዋሻ አድርሰዋቸው ሲመለሱ እንዳይነጋባቸው ስለ ሰጉ ፡ ሊቀሩ የማይችሉትን በጣም አስፈላጊዎቻቸው የሆኑ ፡ አንዳንድ ቀላል ነገሮች ብቻ ይዘው ወጡ ። እዚያ ደርሰው እንቅልፍና መከራ ባንድ ላይ ተደራበው ተጭነዋቸው ስለ ነበር ፡ ቅጠል ጎዝጉዘው እንደ ተኙ ፡ ቀኑን ሙሉ ተንቀልፍተው ውለው ኢመሸሸ ላይ ፡ ባስራ አንድ ሰአት ግድም ፊት እሱ ፡ ሁዋላ እሰዋ ነቁ ። ጥላሁን ነቅቶ አይኖቹን ሲገልጽ ፡ ምሽቱና እሱ በባዶ መሬት ቅጠል እንጥፈው ተኝተው ፡ ጀንበርዋ ከም እራብ የወረወረችው ጨረር በፊት ለፊቱ ፡ በዋሻው ግድግዳ ላይ የተተከለ የወርቅ ዘንግ መስሎ ታዬውና የሚያልም መሰለው ። ወዲያው አሳቡ ከዚያ ተነስቶ ወደ ሁዋላ ሲሄድ ፡ ባለፈው ሌሊት የሆነው ሁሉ ከዚያ ባላምባራስ ጉዴታ መርተው ወደዚያ ዋሻ ማምጣታቸው ፡ በተራ እፎተከታተሉ ትዝ እሉትና ፡ ያ ፡ እልም የሚመስል ፡ ያ ፡ እውነት የማይመስል ነገር እውነት መሆኑን ሲያስታውስ ፡ ድምጹን አሰምቶ በረ ኸሙ "አ . . . !" አለ ። ያን ጊዜ ነው ሶፊያም የነቃች ።

ያ ፡ ዋሻ ፡ ያ ባላምባራስ ጉዴታ ሶፊያንና ጥላሁንን ሸሽገው ያሰነበቱበት ዋሻ ፡ እሳቸው እንደሚሉት ፡ "እግዚአብሄር ላያታቸው መሸሻ እንዲሆን ባንድ ትንፋሽ 'ይሁን' ስላለ ሆኖ ተገኘ" ማለቱ ከወገኖቻቸው በቀር ብዙ ተቀባይ የሚኖረው ባይመስልም ፡ ለከተማው በጣም ቅርብ ሆኖ ሳለ ፡ ከከተማው ሰው ወሬውን እንኩዋ የሰማ አለመኖሩ የሚካውን ውስጠ-ውስጥ ሁሉ እንደዬቤታቸው ማጀት ከሚያውቁት ከጣማዎች ፡ ከመሰንጎዎችና ከሾኮዎች እንኩዋ እግሩ ረግጦት ፡ አይኑ አይቶት ፡ የሚያውቅ አለመኖሩ ፡ እንዲያውም ባጠቃላይ ካውሬ በቀር ሰው የሚባል ፍጥረት የማያውቀው መሆኑ እርግጥ ነው ።

ባላምባራስ እንደሚሉት ፡ "የየኪ ባላባት የነበሩትን ፡ ያባታቻውን አባት ፡ ትልቁን ባላምባራስ አቦሴን ፡ ምቀኞች በቅናት ተነስተው ያልበሩትን ወንጀል 'ሰርተዋል' ብለው በጊዜው ለነበሩት የጠቅላይ

ግድቡ አገሬ ገኘ አሳብቀው ፣ አጣልተዋቸው ፣ አገሬ ገዥ ሲያስይዙዋቸው ያንድ ፊታውራሪ ጦር ልከው ቤታቸውን ሲያስከብቡ ፣ እግዚአብሄር ንጹሀነታቸውን አይቶ ከተከበቡት በታምር አውጥቶ ፣ በጨለማ ከነተከታዮቻቸው መርቶ እዚያ ፣ ያኔው ባንድ ትንፋሽ 'ዋሻ ሁን' ብሎ በፈጠረው ዋሻ አገባቸው ! ከዚያ በሁዋላ ፣ ምቀኞች 'ሰርተዋል' ብለው ያቀረቡባቸው ወንጀል አሰት መሆኑን ዘመድ ወዳጆቻቸው ላገሬ ገዥ አስረድተው ፣ አስታርቀዋቸው እስኪገቡ ድረስ ፣ አሽከሮቻቸውን ከማይታወቁበት ሩቅ ቦታ ስንቅ እያስገዙ ፣ በጨለማ እያስገቡ ፣ ሁለት አመት ሙሉ እዚያ ዋሻ ውስጥ ሲቀመጡ ፣ እዚያ መኖራቸውን እንኳዋንስ የሚያውቅ የሚጠረጥር አልነበረም ! ስለዚህ ባላምባራስ አቦሴ ፣ ' ያ ዋሻ እዚያ ኩታማ አጠገብ ሆኖ ፣ እግዚአብሄር ራሱ መርቶ ወደዚያ ከሚወስዳቸው በቀር ለማንም አለመገለጹ ፣ ልክ በሰው ሁሉ ፊት ቢሰራ እዩታዩ ምስጢር ሆኖ እንደሚኖረው ፣ እንደ-ቤታ-ወ-ደው በምስጢር እንዲጠበቅ የክርስቶስ የራሱ ፈቃድ ቢሆን ነው ' ብለው አምነው ፣ ከዚያ የወጡ እለት ፣ አውራ ፣ ዳገት ጫካ በጣ አርደው ስጋውንም ፣ ደሙንም እዚያ አብረዋቸው ከነበሩት ሰዎቻቸው ጋር ባንድነት ተቋዋድሰው ፣ ' ስለዋሻው-ምንም ፣ ለማንም አናወራም ፣ ቁርባን ይሁንብን ! ' እያሉ ተማምለው ። ከዚያ በሁዋላ ባላምባራስ አቦሴ ብዙ አመት ኖረው በሞቱበት ጊዜ ሲናዘዙ ፣ በሳቸው የደረሰውን የመሰለ ችግር ከሳቸው በሁዋላ በሚፈጠሩት ዘር ምንዛራቸው ተደረሰ እንደሆን ፣ ያ ዋሻ መሸሻ ፣ መሸሸጊያ ሆኖ ከክፉ ቀን እንዲያወጣቸው ፣ ከእግዚአብሄር በቃል ኪዳን የተሰጣቸው መሆኑን አስረድተው ፣ ወገናቸው ባልሆነ ፣ ወይም ምስጢር እንደማያወጣ እርግጠኞች ካልሆኑ ፣ ለማንም እንዳያሳዩ አምለው ፣ እሳቸውም በፊት ትታቸው ወራሾቻቸውን እንዲያምሉ አደራ ብለው ፣ ለልጃቸው ለቀኛዝማች ራስ አመለከቷዋቸው ። ቀኛዝማች ራሳም እንዲሁ አምለው ለልጃቸው ፣ ለባላምባራስ ጉደታ አሳዩዋቸው ። "

ጥላሁንና ሶፊያ ፣ እንዲህ ያለውን ፣ ከዋሻውና ከመዳረሻው ስራ አስደናቂነት ይልቅ የባላምባራስ አቦሴ ተወላጆች ስለሳቸው ጻድቅነትና ከግዚአብሄር ጋር ባለቃል ኪዳን መሆን እያጋነኑ የሚናገሩትን ታሪክ ሲሰሙ ሁለቱም እንደ ተረት ቆጠሩት ። ነገር ግን ባላምባራስ ጉደታ ካያታቸው ካባታቸው ፣ ለሳቸው ሲወርድ እንደ መጣ እንዲሁ ሲተርኩላቸው ፣ ምንም እንኳዋ እንደ ታሪክ ባይዋጥላቸው ፣ እሳቸውን ላለማስተሀቀር ፣ ዝም ብለው ሰሙዋቸው ።

@OLDBOOKSPDF

ሙቅም ወደ ዋሻው የመድረሻው መንገድና የዋሻው ስራ እጅግ የሚያስገርም ፡ አጼ-ብ ድንቅ ነው ። ባላምባራስን ተከትለውና ከከተማው ወጥተው ወደ ዋሻው የሚወስደውን መንገድ እንደያዙ አሸዋ ላሸዋ ቁኝ ፤ ቀጥታ ፡ ግራ ፤ እንደገና ቀጥታ ፤ ቀኝ ፤ ቀጥታ ፤ ግራ እየተጠማዘዙ ሲሄዱ ቆይተው ፤ ወዲንድ ትራራ በር ደረሱ ።

ከዚያ በትራራው ውስጥ ለውስጥ የተሰራ ፤ ቢያንስ ቢያንስ ካንድ ኪሎ ሜትር የማያንስ ፤ አሸዋማ ስርጓዳ መንገድ አገኙና ፤ እሱን ይዘው ወደ ዋሻው ደረሱ ። እዚያ ዋሻ ውስጥ የሚታዩት ፤ የተለያዩ መጠን ያላቸው ጉዋዳዎች ፤ ምርጥ አናጢ ከገደሉ እየፈለፈለ ያነጸቸው ይመስላሉ። ከዋሻዎቹ ፤ ወይም ከጉዋዳዎቹ ፊት ፤ ገደሉ ከፍ ብሎ ፤ እደረቱ ላይ ተቀዶ ፤ እስሩ በጣም ሰፊ አሸዋማና ዙሪያውን ጫካ የከበበው መሬት ይታያል ። ታዲያ እኒያ ዋሻዎችና ወደነሱ መድረሻው ስርጓዳ መንገድ ፤ እንዲሁም ስርጓዳው መንገድ ገደሉን እደረቱ ላይ ቀዶ የወጣ በትና ከገደሉ በር ያለው ፤ ከክብር እውድማ የሚሰፋ ፤ በጫካ የተከበበ አሸዋማ መሬት ሲታዩ ፤ ከባላምባራስ ታሪክ ይልቅ ፤ ያዳዩ ግምት ፤ ጭጥ ታውን ለማሰመር የጨማመረው ጌጣጌጥ ቢቀር እውነት ያለበት ይመስላል ።

" ምናልባት ጥንት" አለ አባዬ ፤ አንድ ማታ እሱና ምሽቱ ፤ ባላም ባራስ ጉዳታ ጭምር ፤ ለሶፊያና ለጥላሁን ራት ይዘው እዚያ በተሸሸ ጉበት ዋሻ ሄደው ሲያጫወቱዋቸው ። "ምናልባት ጥንት ፤ በጣም ጥንት አንድ ትልቅ ኸረት ፤ ከላይ ከደጋው ቁልቁል እየተጥመለመለ ወርዶ ፤ የኪ ሲደርስ ፤ የመሬቱን ቅጥ እየተከተለ ፤ ወደዚህ ዋሻ የሚመጣውን ጠመዝማዛ መንገድ እያበጀ ፤ እዚህ ከትራራው በር ደረሰና ፤ ትራራው እግዶት ቆመ ። ነገር ግን ፤ ምንም እንኩዋ ይህ ትራራ እንደምታዩት እጅግ ትልቅ ቢሆን ፡ ምንም እግሮቹን በሰፊው እንፈራጦ ፤ ራሱን እስከ ሰማይ እንጠራርቶ ፤ ኮርቶ ፤ ተጀንኖ ፤ ቆም ሽቅብ ሲያዩት ፍጹም የማይ በገር ቢመስል ፤ ውሀው ከጊዜ ብዛት አሸናፊው እሱ መሆኑን ፤ የሁዋላ ሁዋላ ድል የሱ መሆኑን አስቀድሞ እንዳወቀ ፤ በጉልበቱ ፤ እንደ ቀማ መን ሁሉ ፤ ትግሉን በለዘብታ ፤ በትግስት መታገል ጀመረ ።

እንደምታወቁት ፤ ተራራ እንደ ውሀ ካንድ ባህርይ የተሰራ አደ ለም ። ውሀ ባህርዩ አንድ ስለ ሆነ ፤ እያንዳንዱ ጥቃቅን ጠብታ ባንድ ላይ ሆኖ ፤ ትልቅ ማእበል ፤ ትልቅ ኸረት ፤ ትልቅ ባህር ፤ ትልቅ ውቅ ያኖስ ይሆንና ፤ ትልቅ ታምር ይሰራል ። ከተማ የሚያክል መርከብ ይሸ ከማል ፤ ወይም ያሰምጣል ። ቢፈልግ . . . እንኩዋንስ አንድ ተራራ ፤

@OLDBOOKSPDF

በኖህ ጊዜ እንዳደረገው አለምን በሙሉ ማጥፋት ይችላል ! ተራራ ግን ምን ትልቅ ቢሆን ፣ ምን እስከ ሰማይ ተንጠራርቶ ፣ ኮርቶ ፣ ሽቅብ ሲያዩት የማይበገር ቢመስል ፣ ከተለያዩ ባህርያት ባንድ ተጠረቃቅሞ የተሰራ ፣ ውጥንቅጥ ስለሆን ፣ ብርቱና እንደ ውሀ ትግስተኛ ጠላት ከገጠመው ፣ እኒያ እንዳፈር ፣ እንዳሸዋ ፣ እንዳለት ደንጋይ ፣ እንደ ሰረዝ ደንጋይ ፣ እንደ በሀ ደንጋይና እነሱን የመሳሰሉ ፣ የተለያዩ ባህርያት ያሉዋቸው ክፍሎቹ ፣ ባንድ ተባብረው ጠላታቸውን ማሸነፍ ይቅርና ለጠላት መመከት እንኳ አይችሉም ! ስለዚህ ውሀው የተራራውን ብርቱና ደካማ ባህርያት ያሉዋቸው ክፍሎች እያጠና ፣ እዬመረመረ ፣ እንዳለት ያለ ብርቱ ክፍል ሲያገኝ ወደጎን ይተወዋል ። ወይም ግራና ቀኙ አፈር ወይም አሸዋ ሲያገኝ አለቱን እመሀል አድርጎ አፈሩንና አሸዋውን ይቦረቡራል ። ከዚያ አልፎ የሰረዝና የበሀ ባህርያት ያሉዋቸው ክፍሎች ሲያገኝ እዚያ ቆሞ እነሱን ይሰረስራል ። ከዚያ መደዳውን ያለት ባህርይ ያለው ክፍል ሲገጥመው ያን ትቶ ፣ አቅጣጫውን ለውጦ የሚቦረቦር አፈርና አሸዋ ፣ ወይም የሚሸረሸር ሰረዝና በሀ ወደሚገኙበት ይዞራል ። እንዲህ በዘዴ ፣ እንዲህ በትግስት ብርቱ አለት ሲገጥመው ዘወር እያለ ፣ የሚቦረቦርና የሚሸረሸር ሲያገኝ ቦርቦር ቦርቦር ፣ ሸርሸር ሸርሸር እያደረገ ስንት ሽህ ትውልድ እንደ ኖረ ፣ ያንጊዜም የነበረው እግዚአብሄር ብቻ ይወቅ ። ብቻ አይተነኛው ነገር ፣ ቁም ነገሩ እዚህ አካባቢ የሚታዩት ዋሻዎች ሁሉ ይቅርታ አድርጉልኝ-ጉዋዳዎች ሁሉ ግለቱ ነው-እዚህ አካባቢ የሚታዩት ጉዋዳዎች ሁሉ ፣ ዙሪያ ግድግዳቸውና ጣራቸው ሰረዝና በሀ ደንጋይ ሆኖ ፣ ባናጢ መሳሪያ የተላሰና የተለሳለሰ መምሰሉ ፣ የሁሉም በመሀል ማከፋፈያቸው ምንም ያልተነካ ፣ አባጣ ፣ ጎርባጣ ፣ አለት ድንጋይ መሆኑና ፣ አፈርም ፣ አሸዋም ከዚህ ተቦርቡሮ ፣ ታጥቦ ድራሹ መጥፋቱ ፣ እነዚህ ሁሉ የኔን ግምት የሚደግፉ መሆናቸው ነው ።

ውሀው በተራራው ጀርባ መሸርሸሩንና መቦርቦሩን ጀምሮ ፣ መጨረሻ ወደ ፊቱ ደርሶ ፣ ተራራው ወይም ገደሉ እደረቱ ላይ መላላቱንና መድከሙን ሲያይ ፣ አንድ ቀን ይሁን ሌሊት ከላይ ፣ ከደጋው ሊያገኝ የሚችለውን ሀይል ሁሉ አጠራቅሞ ጨምሮ ያን የላላ ደረት አ . . . ንድ ጊዜ ሲመታው እንዳለ ንዶ ፣ ይዞት ወዲያ ታች ፣ ከገደሉ ስር በወደቀ ጊዜ አለም የተገለበጠች ፣ እለተ-ምጻት የሆነ መሰለ ! ያንጊዜ በጦጣው በዝንጀሮው ፣ በጉሬዛው በጨኖው ፣ ባሳማው በረያው ፣ በድኩላው በሚዳቋዋው ፣ ባንበሳው በነብሩ ፣ በጎሹ ፣ በዝሆኑ እንዲያው ባጠ

@OLDBOOKSPDF

ቃላይ እዚህ ጫካ በሚኖረው ህዝበ-አራዊት መሀከል የሆነው ሽብር ፥
ጫጫታው ፥ ጥድፊያው ፥ እግዚያታ… ከዚያ በፊት እዚህ ጫካ ውስጥ በሚ
ኖር ህዝበ - አራዊት ታሪክ ደርሶ የማያውቅ ነበር ! ብቻ ይግነቱ ገደሉ
ሲናድ የተፈጠረው የመሬት መንቀጥቀጥና በጫካው ላይ ያዘንብ የነ
በረው የደንጋይ በረዶ ፥ የድንጋይ መአት እንዲያ እንደ ሆነ ብዙ አለመ
ቆየቱ ፥ ቶሎ ማለፉ ነው ! ያ ከገደሉ እየተናደ ይወርድ የነበረው ፍሬር፥
ያሸዋና የድንጋይ ነጎድጓዋድና የጭቃ ማእበል ወርዶ ሲያበቃ ፥ የተረ
ፈው ገደል እዚያው ባለበት እዩረጋ ፥ እዩረጋ ፥ የጭቃው ማእበል እዩ
ጠራ ፥ እዩጠራ ሄዶ ፥ በመጨረሻ ከዚያ ረገድም ገደል ላይ የጥጥ ባዘቶ
የመሰለ ፥ ነጭ ፉዋፉዋቴ እዩተጎረደ መውረድ ጀመረ ። ያንጊዜ ፥ በሚ
ካው የሚኖረው ህዝበ - አራዊት ፥ ገደሉ በተናደ ጊዜ ለመሸሸ ቦታ አል
በቃው ብሎ ፥ አንዱ ባንዱ ላይ እዩተነባበረ ይወድቅ የነበረውን ያክል ፥
ያን እንግዳ ፥ ያን አስደሳች ትርኢት አይቶ አልጠገበው ስላለ ፥ እስኪ
ለምደውና እንደ ሌላው ተራ ነገር ሁሉ ከጉዳይ መጻፉን እስኪ ተወው
ድረስ ፥ የሚያድነው ወዳጅ ፥ የሚታደነው ወደ መሸሸጉ መሄዱን እዩ
ረሳ ፥ አዳኝና ታዳኝ ባንድ ላይ ተሰብስቦ አይኑንም ፥ ልቡንም በሰፊው
ከፍቶ እሱን ብቻ ይመለከት ነበር !

ከዚያ በሁዋላ ፥ ያ ከደጋ ወርዶ የኪ ሲደርስ በወጣ - ገባ መሬት
ላይ ጠመዝማዛ መንገድ ፥ በተራራ ውስጥ - ለውስጥ ሰረገላ መንገድ ፥ እያ
በጀ እስከዚህ መጥቶ ፥ ከዚህ መንገድ መውጫ ፍሰጋ ቀኝ ፥ ቀጥታ ፥ ግራ ፥
እንደ ገና ቀጥታ ፥ ቀኝ ፥ ቀጥታ ፥ ግራ ፥ ሲዘዋወር እንዲህ ብዙ የሚ
ያማምሩ ጉዋዳዎች የሰራና ፥ መጨረሻም ገደሉን ንዶ ህዝበ-አራዊትን
ያሸበረም ፥ ያስደሰተም ፉዋፉዋቴ የፈጠረ ውሀ ፥ በዚያ ባበጀው መን
ገድ ሲሄድ ሲሄድ ኖሮ ፥ ምናልባት ከዚህ ወጣገባና ጠመዝማዛ መን
ገድ የተሻለ ሌላ ፥ ቀ ጥ ያለና ተዳፋት የሆነ መንገድ ስላገኘና ይህን ትቶ
በዚያ መሄድ ስለ መረጠ ፥ ይህ . . . እንደ ባላምባራስ አቦሴና እንደሳ
ቸው . . . ከባለስልጣን ለሚሸሹ ፥ መሸሻና መሸሸጊያ ሆነ ! ይህ ነው
የኔ ግምት ፤ መቀበል አለመቀበሉ የራሳችሁ ጉዳይ ነው !” አለ አሳዬ ፥
ግምቱን በቀልድ እዩኩዋኩዋለ አውርቶ ሲጨርስ ፥ ባላምባራስ ጉዱታ
ንም ፥ ሶፊያንና ጥላሁንንም ባሽሙር ነካ አድርጎ ።

“ ወይ ምን ትችል እግዚአብሄ . . . ር ! እና . . . ሰማይንና ምድ
ርን ፥ በላያቸውም ፥ በውስጣቸውም ካለው ፍጥረት ሁሉ ጋር ባንድ
ትንፋሽ ‘ ይሁን ! ’ ብሎ እንዲሆን ያደረገ አምላክ ፥ ይህን ትንሽ
ዋሻ እንዲሁ ባንድ ትንፋሽ መፍጠር ተስኖት ነው ወሀ ከደጋ ወርዶ ፥
አቀበት ቁልቁለቱን እዩተጠመዘዘ ዞሮ ፥ ተራራውን ቆፍሮ ፥ ሰረገላ

@OLDBOOKSPDF

መንገድ እያበጀ መጥቶ ... ይህን ዋሻ በሰንት ሽህ ትውልድ መስራት ያስፈለገው ? ” አሉ ባላምባራስ ፤ አሳዬን ዝም ብለው ሲሰሙ ቆይ ተው ፤ እሳቸውም ያሽሙር ፈገግታ ፈገግ አሉና ።

“ የለም ፤ እግዚአብሄርን ተሰኖት አደለም ፤ ለዚህ ትንሽ ዋሻ አለምን እስከ ሁለመናው የፈጠረበትንና ወደፊትም እሱን ለመሰለ ትልቅ ነገር የሚሆነውን ፤ ወርቅ ትንፋሹን እንዳያባክን ነው ! ” ሲል አሳዬ እዬሳቀ ፤ ከባላምባራስ በቀር ሁሉም ሳቁ ። ባላምባራስ ግን እንኩዋንስ ሊስቁ ፤ በእግዚአብሄር ትንፋሽ ሲቀለድ መስማቱም መአት የሚያመጣባቸው መስሎአቸው ፤ “ እግዚአ መሀረነ ክርስቶስ ! ” እሉ አንገታቸውን ደፍተው እያማተቡ ።

ሶፊያና ጥላሁን ፤ እዚያ ዋሻ ሶስት ሳምንት ሰንብተው እስኪሄዱ፣ ባላምባራስ ጉደታም ፤ አሳዬና ባለቤቱ ፤ የውብዳርም አልተለዩዋቸውም ። ማታ ማታ ፤ ሁልጊዜ ራትና ለማግስቱ ቁርስም ፤ ምሳም ይዘው እዬሄዱ ሲያጫውቱዋቸው አምሽተው ፤ ሌሊቱ ሲገባደድ ነበር ወደየቤታቸው የሚመለሱ ። በመጀመሪያዎቹ ሁለት ማታዎች ምግብ ሲወስዱ ፤ ምን ጣጥና አንዳንድ አስፈላጊዎች የሆኑ እቃዎች ጭምር ከለ ወሰዱ ፤ የስ ደተኞች ዋሻ ያራዊት መኖሪያነት መልኩን ለውጦ የሰዎች መኖሪያ መሰለ !

ባላምባራስ ጉደታና አሳዬ ከነባለቤቱ ፤ ለጥላሁንና ለሶፊያ እያስ ናዱ ከሚወስዱላቸው ምግብ ጋር ፤ መከራቸው በሙሉ ክብደቱ እንዳ ይሰማቸው ፤ እንዳይጫናቸው ፤ የሚያረሳሱበት አዳዲስ ወሬ ፤ አዳዲስ ጨዋታ በዬለቱ እዬፈለጉ አሰናድቶ መውሰዱንም ከምግብ ማሰና ዳቱ የማያንስ ፤ አይነተኛ ነገር አድርገው የያዙት ነበር ። ደግነቱ ባላ ምባራስ ጉደታ የተረትና የስለምን ጭዋታ ፤ አሳዬ ልብ-ወለድ ፤ የመ ፍጠር ችሎታ ድሆች ስላልነበሩ ፤ ባላምባራስ ተረታቸውንና ስለምና ቸውን ፤ አሳዬ ልብ-ወለዱን እያወሩ ፤ እዚያ ካራዊት በቀር “ ሰው ይሰማ ይሆናል ” ተብሎ በማያስጋበት ዋሻ ውስጥ ፤ ሁሉም በድግስ ቤት እንደ ተሰበሰበ ሁሉ ሲንጫጩ ፤ ሲስቁ ፤ ሲያወኩ ነበር የሚያ መሹ ።

ቀን ሲከፋ ፤ ቀን ሲጨልም ፤ “ እንደ ጥላ ካጠገብ የማይጠፋ ” በጭንቅ ጊዜ ፤ ዙሪያው ጨለማ ሲሆን ካጠገብ የማይለይና ፤ “ እንደ እውር ሽመል ቀድሞ የሚመራ ” ወዳጅ የሚያገኝ ሰው እንዴት እድ ላም ነው ! ባላምባራስ ጉደታ ፤ እንዲህ ያሉ ወዳጅ ነበሩ ! ባላምባ ራስ ጉደታ ፤ “ ክፉ ችግር ፤ ወይም ክፉ መከራ አጋጠማቸው ”

@OLDBOOKSPDF

ብለው ወዳጆቻቸውን የማይበዙ ፣ ቢችሉ ወዳጆቻቸውን እንዲያ ካለ መከራ ለማውጣት ፤ ባይችሉ የመከራቸው ተካፋይ ለመሆን አይናቸውን የማያሹ ፣ ለወዳጆቻቸው ነፍስና ስጋቸውን ባንድ ላይ የሚሰጡ የውነተኛ ወዳጅ ስለ ነበሩ ፤ ጥላሁንና ሶፊያ መውጫ መግቢያውን በማያውቁት አገር እንዲያ ያለ መከራ በደረሰባቸው ጊዜ ፤ እንዲያ ያሉ የውነተኛ ወዳጅ ማግኘታቸው በውነት እድላሞች ናቸው ! አባዬና ባለቤቱ ፤ የውብዳርም ፤ በህይወት ለወዳጅ መስዋእት ከመሆን የበለጠ የሚያሳሳ ፣ ብዙ ነገር በፊታቸው ተደቅኖ ስለሚታያቸው ፤ ምናልባት ለወዳጅ ሲሉ የባላምባራስን ያክል ሩቅ መንገድ ሄደው ፤ እሳቸው እስከሚደርሱበት አይደርሱ እንደሆን እንጂ ፤ የወዳጅ ፍቅር አክባሪዎችና እንከን የሌላቸው ፣ ጥሩ ወዳጆች ናቸው ። ስለዚህ ጥላሁንና ሶፊያ ነፍሰ-ገዳዮች ስለሆኑ ፍጹም የሆነ የመንፈስ ጸጥታና የልብ ርካታ ሊኖራቸው ባይችልም ፣ እንዲያ ባሉ ወዳጆች መሀከል ስለሆኑ ፣ መከራቸው ሳይከብዳቸው ፤ ባለፈው ስራቸው የመጸጸትና ፤ ለወደፊት ኑሮዋቸው ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ሳይሰማቸው ፣ ደህና ሲስቁ ፣ ሲጫወቱ ሰነበቱ ። ብዙ ጊዜ ፤ ወንጀል ከተሰራ በሁዋላ ያለው ጸጸት ፤ ከመስራቱ በፊት ለመስራት ካለው ፍላጎት ፣ ወይም ግፊት ፣ ይበልጥ እንደሆን እንጂ አያንስም ፤ ሶፊያና ጥላሁን ግን እንዲያ ባለ ጸጸት ፤ ሀሊናቸው አልተሰቃዩም ። ቀኛዝማች ዳኘን መግደላቸው ፤ በህዝብ ፤ በመንግስትና በግዚአብሄር ላይ ወንጀል ሲሰሩ የኖሩትን አመጸኛ እንደ መቅጣት ፣ ለህዝብ ፤ ለመንግስትና ለእግዚአብሄር እንደ መበቀል ፤ እንደ ታላቅ ብጻት ፤ እንደ ታላቅ ቅድስና የሚቆጠር እንጂ ፣ እንደ ወንጀል የማይቆጠር መሆኑን ባላምባራስ ጉዳታ በዩሉቱ ምክናያት እዩ ፈሰጉ ፤ ከስሜት ጋር እዩመላለሱ ሲናገሩ እዩሰሙ ፤ በመጸጸት ፈንታ እንዲያውም ልባቸው በደስታ ይሞቅ ነበር ። እንዲሁም ሶፊያና ጥላሁን የኪ ስለ ጀመሩት ስራ ፤ ምንም እንከኑዋ አዳዲስ ስራ እዩጨመሩ ማስፋፋት የማይቻል ቢሆን ፤ ያው ያለው እንዳለ ፤ በደህና እንደ ሚጠበቅና እንደማይፈርስ በተረጋገጠ ተስፋ ባላምባራስም ፤ እባዬም ስለ ሰጡዋቸው እጅግ ደስ አላቸው ። የተስፋ ሰጪዎችም አይነተኛ አላማ ይኸው ነበር ። የተስፋ ሰጪዎች አይነተኛ አላማ ፤ መንገደኞቹን ሲሄዱ የስራቸው መበላሸት አሳብ ወደ ሁዋላ እንዳይጎትታቸው ፤ የኪ የሰሩት ፤ የፈጠሩት ድንቅ ስራ እንደሚኖር ፣ እንደማይሞት ፤ እም ነው ፤ ደስ እያላቸው እንዲሄዱ ብለው እንጂ ፣ የሰጡት ተስፋ ይፈጸማል ብለው አይደለም ። ስለዚህ የሰጡዋቸውን ተስፋ አምነው መንገደኞቹ ደስ ሲሰኙ ስላዩ ፤ ተስፋ ሰጪዎችንም ደስ አላቸው ።

@OLDBOOKSPDF

ሶፊያና ጥላሁን ከሴሊቱ የሚበልጠውን ከየውብዳር ፣ ካሳዬና ከባ ሻምባራስ ጉዶታ ጋር ራታቸውን በልተው እዬተጫወቱ እንደሚያሳልፉት ፣ እንዲሁም ከቀኑ የሚበልጠውን ፣ ከሰፈሩ ነዋሪዎች ፣ በተለይ ከዝንጀሮዎችና ከጦጣዎች ጋር እዬተጫወቱ ነበር የሚያሳልፉት ። እንደ ጉሬዛ ፣ ጨና ፣ ነብር ያሉና ፣ ሌሎች አራዊትም ፣ የዝንጀሮዎችንና የጦጣዎችን ያክል ቶሎ መልመዱና መቅረቡ ይቅርባቸው እንጂ ፣ ራቅ ብለው እዬቆሙ እንግዶች የሚያደርጉትንና እንቅስቃሴያቸውን ሁሉ ፣ ዘለግ ላለ ጊዜ ሲመለከቱ ቆይተው ይሄዱ ነበር ። ብቻ ጥላሁንና ሶፊያ አንዳንድ ጊዜ ጠበንጃቸውን ይዘው ያዩዋቸው ለለ ነበርና ፣ ከለፈ ልምዳቸው እንደ ተማሩት ፣ ሰዎች ጠበንጃ ይዘው ለሰላም ጫካ የማይገቡ መሆናቸውን ስለሚያውቁ ፣ ምን ጊዜም ቢሆን ልባቸው ከጥርጣሬና ከስጋት ነጻ ሊሆን አልቻለም ። ዝንጀሮዎችና ጦጣዎች ግን ፣ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀኖች ነበር እንጂ ፣ እንደ ሌሎች አውሬዎች ሁሉ ከሩቅ እንግዶች የሚያደርጉትንና እንቅስቃሴያቸውን የሚመለከቱ ፣ ከዚያ በሁዋላ መቅረብ ጀመሩ ። ከሁለት ቀኖች በሁዋላ ፣ ሶፊያ ከራት ይሁን ከቁርስ ፣ ወይም ከምሳ የተረፈውን ምግብ ራቅ ብለው ቆመው ፣ ወይም ተቀምጠው ወደሚመለከቱበት ስትወረውርላቸው ፣ ከዚያም ቀረብ አድርጋ ታስቀምጥላቸውና መጥተው ሲወስዱ ምንም ጉዳት እንዳልደረሰባቸው ሲያዩ ፣ ትንሽ -በትንሽ እዬተላመዱ ሄዱና ፣ ምግብ ስታሳያቸው እዬቀረቡ ከጅዋ መቀበል ፣ ከዚያ እንዲያውም የሰጠቻቸውን ይዘው ከሰዋና ከጥላሁን አጠገብ በዬደንጋዩ ላይ እዬተቀመጡ እስከ መብላት ተደፋፈሩ ። ከመሀከላቸው አንድ ሴት ዝንጀሮ ብቻ ፣ ሶፊያ የምትሰጣትን ምግብ እንደ ሌሎች እዚያው ተቀምጣ በመብላት ፈንታ እዬያዘች ትሮጥ ነበር ። አንድ ቀንም ያቺ ዝንጀሮ እንደ ልማዱዋ የተቀበለችውን ምግብ እንደ ያዘች ገደሉን እዬሮጠች ወርዳ ፣ በጫካው ውስጥ ትንሽ ከቆዩች በሁዋላ ፣ እንደ ዝንጀሮዎች ባህል ፣ ትንሽ ልጅዋን በሆድዋ ታቅፋ ፣ ገደሉን ልክ እንደ ሜዳ እየሮጠች እንደ ወረደች ፣ እዬሮጠች ወጥታ መጥታ ፣ ልጅዋን ከሆድዋ አውርዳ በፊትዋ አስቀምጣ ፣ እሰዋም ተቀመጠችና ሶፊያ ፊት ከሌሎች ጋር የሰጠቻትን ምግብ ለልጅዋ ታበላ ጀመር ። ልጅዋ ከሰዎች ፊት የቀረበችገና ያነሰት በመሆኑ ፈርታ ፣ ከናትዋ ጉያ አልወጣ ብላ ከስንት ማባበል በሁዋላ ነው መብላት የጀመረች ! ልጅዋ በልታ እስከታበቃ ፣ እናትዬዋ ከተቀበለችው ምግብ ትንሽ እንኳ አልቀመሰችም ። ልጅዋ በቅቶዋት ከተወችው በሁዋላ ብቻ ፣ ከምግቡ ትንሽ ተርፎ ለለ ነበረ ! ያን በልታ ስትጨርስ ፣ ሶፊያና ጥላሁን ፣ “ የዝንጀሮ እናት ልጅዋን ከራ ያን በልታ ስትጨርስ

@OLDBOOKSPDF

ስዎ አብልጣ ትወዳለች ” ብለው አምነውና እንዲያ ባለው የናት ፍቅር ልባቸው ተነክቶ ፣ ምግብ ጨመሩላት ። ከዚያን እለት በሁዋላ እደጋ አለመኖሩን ከአረጋገጠች በሁዋላ መሆኑ ነው . . . እራስዎ ዝንጀሮ ምግብ ፍለጋ ወደነሶፊያ ዋሻ ስትመጣ ፣ ልጅዋን ሳትይዝ መጥታ አታውቅም ።

በጠቅላላው ዝንጀሮዎች የሚያደርጉት ፣ ሌሎች አውሬዎች ከሚያደርጉት የተለዬ መስሎ ስለ ታያቸው ፣ ሶፊያና ጥላሁን እዚያ ዋሻ በቆዩበት አጭር ጊዜ ፣ ዝንጀሮዎች የሚያደርጉትን ለመከታተል የተቻላቸውን ያክል ይሞክሩ ነበር ። እነሱ እንደ ተመለከቱት ፣ ከሁሉ አስቀድሞ ፣ ዝንጀሮዎች ለፈራቸው ባንድ ላይ ፣ ወይም በጣም የተቀራረበ ነው ። ከዚያ ምግብ ፍለጋ ሲወጡ ፣ ባንድ ላይ ካልሆኑ በተናጠል ፣ ለጭብጆ ሲወጡ አይተው አያውቁም ። እንዲያ ባንድ አካባቢ ብዙ ሆነው ተሰማርተው ፣ ትላትል የሚፈልገው ደንጋይ እዬፈነቀለ ትላትሉን፣ ስራብር የሚፈልገው ስራስሩን ፣ ፍራፍሬ የሚፈልገው ፍራፍሬውን ሲበላ ፣ ከመሀከላቸው አንድ ዝንጀሮ ቃፊር ፣ አካባቢውን ሁሉ ዘቅዝቆ በሚያሳይ ረዥም ዛፍ ፣ ወይም ገደል ላይ ተቀምጦ ፣ እንደ ንብር ፣ ወይም ሌላ ዝንጀሮን የሚያድን አውሬ እዬጠበቀ ፣ ገና በሩቅ ያዬ እንደሆነ ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ ሁሉም ቶሎ ብሎ ወደዬዛፉ ይሸሻል ። የማስጠንቀቂያው ምልክት ፣ ሶፊያና ጥላሁን ሲደጋገም እንደ ተመለከቱት ፣ እንድ “ ኡሀ ! ” የሚል ድምጽ ነው ። “ ኡሀ ” ወይም “ እሀ ” ተከታትለው ሲመጡ ግን ፣ ለም ላሕ ፣ እንደ “ ኡሀ -ኡሀ - ኡሁ- ኡሀ ! ” ወይም “ እሁ- እሀ-እሀ - እሀ ” የቁጣ ፣ ወይም ጠላትን የማስፈራራትም ፣ ወይም የፉከራ ምልክቶች ናቸው ። “ ኡሁም ” የመጣራትም ፣ “ እቤት እዚህ ነኝ ” የማለትም ምልክት ነው ።

አንድ ቀን ፣ ጥዋት ከገደሉ ስር ባለው ሰፍራ ብዙ ዝንጀሮ ተሰማርቶ ጥሬውን ፣ ስራስሩንና ደንጋይም እዬፈነቀለ ትላትሉን ፣ እንደ ዬምርጫው እዬለቀመ ሲበላ ፣ ጥላሁንና ሶፊያ ከዋሻው በር አፍ ተቀምጠው ዘቅዝቀው እዬተመለከቱ ይጫወቱ ነበር ። ከዚያ የማስጠንቀቂያ “ ኡሀ ” ከመስማታቸው ፣ ካንድ ወገን እዚያ ታች የተሰማራው ዝንጀሮ በቅጽበት ተበራን በዬዛፉ ሲወጣ ፣ ከሌላ በኩል ፣ አንድ ትልቅ ነብር ከጫካው ወጣ ብሎ ፣ እንባጣ ቦታ ላይ ቆሞ ጅራቱን ሲቆላ አዩ ። ነብሩ እንዲያ ጅራቱን እዬቆላ ሁለት ፣ ወይም ሶስት እርምጃዎች ቀስ ብሎ እያጠቀሰ ወደ ፊት ይራመድና ቆሞ ያደባል ። ደግሞ እንደ ገና ጅራቱን እዬቆላ ትንሽ ይሄድና ቆሞ ያደባል ። እን

@OLDBOOKSPDF

ዲህ ቆሞ ሲያደባ ቆይቶ ፣ ድራቱን እዑቃላ የሚሄድበትን አቅጣጫ ሶፊያና ጥላሁን ባይናቸው ተከትለው አንድ ዛፍ ስር ቢመለከቱ ፣ እዚያ አንድ ገመር ዝንጀሮ ፣ ምናልባት ማስጠንቀቂያውን " ኡህ " ሳይሰማ ቀርቶ ይሆናል ፣ ትል ፍለጋ ትልቅ ድንጋይ ለመፈንቀል ሲታገል አዩ። የዚያን ጊዜ ድንጋጤያቸው ፣ ልክ አደጋው በነሱ ላይ የደረሰባቸውን ያክል ነበር ። ጥላሁን ሮጦ ጠበንጃውን ካስቀመጠበት ይዞ መጣ ።

" ምን ልታደርግ ነው ? " አለች ሶፊያ ።

" ነብሩን ልገድል "

" ተሸሽገን መቀመጣችንን ረሳኸው ? አሁን የምትተኩስ ለሚፈልጉን 'እዚህ አለንላችሁ ' ለማለት ነው ? "

" እሱስ እውነትሽ ነው ፤ ብቻ . . . ሊበላው ነውኮ "

" እግዜር ያውጣው እንጂ መቸስ ምን እናርግ ! " አለች ሶፊያ ።

ነብሩ ከዝንጀሮው ካለር ፣ ቢበዛ ካስራ ሁለት ሜትር በማይበልጥ ርቀት እንደ ደረሰ ፣ " ኡህ " አለ እዑሮጡ በዩዛፉ ከወጡት አንድ ዝንጀሮ ፣ ጉዋደኛው በብርቱ አደጋ ላይ መሆኑን ሲያይ ። " ኡህ " አለ ሌላው ። ወዲያው ከዩዛፉ " ኡህ " " ኡህ " " ኡህ " የሚለው ሲበዛ ፣ ትል ፍለጋ ድንጋይ የሚፈንቅለው ዝንጀሮ ቀና ቢል ፣ ከፊቱ ነብሩን ሊከመርበት ሲሰናዳ አዩ ። ያን ጊዜ ሸሽቶ ማምለጥ የማይችል መሆኑንና ፣ ጠላቱን ከመግጠም በቀር ሌላ መንገድ እንደሌለው ደመ-ነፍሱ ስለ ነገረው ፣ ቶሎ ብድግ አለና ፣ በሁለት የሁዋላ እግሮቹ ቡጢ እንደሚገጥም ገብደድ ብሎ ቆሞ ፣ አስር የጅ ጣቶቹን ከራሱ በላይ አንጨፍሮ ፣ የዝንጀሮ ፊቱ ከምን ጊዜውም የባሰ እስኪያስፈራራ አፉን በሰፊው ከፍቶና ጥርሱን አግጦ ፣ " ኡህ- ኡህ -ኡህ ኡህ" " እህ-እህ-እህ-እህ ! " እያለ ፣ ጀፈከረ ፣ ነብሩን ተፋለመው ! ወዲያው ፣ የጉዋደኛውን ፍከራ ሲሰሙና ፣ ለጦርነት መሰለፉን ሲያዩ ፣ ከዝንጀሮዎች ገመሮቹ ብቻ ፣ ለሰልፍ እንደ ተጠሩ ከዩወጡበት ዛፍ ባንድ ጊዜ ተኸርኀድጉደው ወርደው ነብሩን ከበቡት ። ነብሩ ግን ጎምዥቶ ይሆን ፣ የመጀመሪያው ዝንጀሮ ደፍሮ በመፋለሙ ተቆጥቶ ፣ ያን ከፊቱ ቆሞ የተፋለመውን እንጂ ፣ ሁዋላ መጥተው የከበቡትን ብዙ ገመሮች ከጉዳይ የጣፋቸው አይመስልም ነበር ! ስለዚህ ፣ በተፋላሚው ላይ ዘሎ ለመከመር ሲቃጣ ፣ በሁዋላው ካሉት ገመሮች አንዱ ጅራቱን ለቀም አድርጎ ፣ በጥርሱ ነክሶ ፣ እንዳያመልጠው በሁለት እጆቹ ጭምር ወጥሮ ይዞ ፣ ወደ ሁዋላ ሲስበው ፣ ነብሩም በተፋላሚው ላይ

@OLDBOOKSPDF

ለመከመር የቃጣውን ትቶ በፊት እግሮቹ መሬቱን እዩቡዋጠጠና፤ “እ.ም . . . !” እያለ ፤ እያጉረመረመ ወደ ፊት ብቻ ይስብ ጀመር! እንዲያ ገመሩ የነብሩን ጅራት በጥርሱ ነክሶና ፤ በጆቹ ወጥሮ ይዞ ወደ ሁዋላ እዩሳበ ፤ ነብሩ እያጉረመረመና ፤ መሬቱን በፊት እግሮቹ እዩቡዋጠጠ ወደፊት እዩሳበ ፤ ሁለቱ ሲጉዋተቱ ፤ ሌሎች የከበቡት ገመሮች ሁሉ ትልልቅ ድንጋይ እዩፈንቀሉና እስከ አከራከሪያቸው ዳርቻ እዩተንጠራሩ ፤ በነብሩ ላይ መአት አወረዱበት ! እንዲያ ካወረዱበት የድንጋይ መአት አንዱ አናቱን ፈጥፍጦት ፤ ደሙ ግድቡን እንደ ናደ ውሀ በፊቱ ዘቅዝቆ ሲንጠቀጠቅ ፤ በዚያ ደም ሰከሮና ናላው ዞሮ “ጉርጉርርር ፤ ጉርጉርጉርጉር” ብሎ ሲያጉራራ ፤ የዙሪያ ግባውን ገደል እዩተናደ የሚወድቅ አስመሰለው ! የነብሩን ማጉራራት ገደሉም ያሻውም እዩተቀባበሉ ብዙ አጥፍ ጊዜ አጉሊተውት ፤ ከሩቅ የሚሰሙትን እንኩዋ ልብ ያሸብር ነበር ! ስለዚህ ፤ ድንጋይ ይዘው የነበሩት ገመሮችም ፤ የነብሩን ጅራት ይዞ የነበረውም ፤ ለጊዜው ደንግጠው የያዙትን እዩተዉ ስለ ሸሹ ፤ ነብሩ በደም-ሰካር ፤ እውር-ድንብሩን ላይና ታች ፤ ቀኝና ግራ ፤ ሲሸከረከር አንዱን ገመር አግኝቶ ያዘው ። ነገር ግን መዛል ጀምሮ ስለ ነበረ ፤ በዝንጀሮው ብርቱ ጉዳት ሳያደርስበት ፤ ሸሽት ጀምረው የነበሩት ገመሮች ሁሉ እንደ ገና ተመልሰው ፤ አንዱ ጅራቱን በንክሻም ፤ በጁም ሲይዘው ፤ ሌሎች እንደ ሬቱ በደንጋይ ይወግሩት ጀመር ። እሱም የያዘውን ዝንጀሮ ለቅቆ መሬት እዩቡዋጠጠ ወደፊት ሲሳብ ፤ ደብድበው ገደሉት ። ጥላሁንና ሶፊያ ፤ ያን ጦርነት ከዋሻቸው በር-አፍ ዘቅዝቀው እዩተመለከቱ ፤ ነብሩ ያዩለ ሲመስል ፍራት ፤ ዝንጀሮዎች ያዩሉ ሲመስል ደስታ ፤ እዩተፈራረቁባቸው ፤ ነፍሳቸው በቁዋፍ ቆማ ከላይ ከላይ ሲተነፍሱ ፤ በመጨረሻ ድሉ የዝንጀሮዎች መሆኑን ሲያዩ ፤ ባሉበት ሆነው በደስታ፤ ይዘሉ ጀመር ! ማታ ባላምባራስ ጉደታና አሳዩ ከምሽቱ ጋር ሲመጡ፤ ጥላሁንና ሶፊያ ያነለት ባንድ ነብርና በብዙ ገመር ዝንጀሮዎች መሀከል ስለ ነበረው ጦርነትና ፤ በዚያ ጦርነት ዝንጀሮዎች ነብሩን እንዴት ደብድበው እንደ ገደሉት በዝርዝር ሲተርኩላቸው ፤

“ከጎሳው ተጣልቶ ፤ ወይም ባንድ ምክንያት ተለይቶ ፤ ብቻውን የሚሄድ ዝንጀሮ ካላገኘ ፤ በልማዱ ነብር ብዙ ዝንጀሮ አይደፍርም ። ቀብጦ ልድፈር ካለም. . . . እጣው ዛሬ ባያችሁት ነብር የደረሰው ይሆናል ! ስለዚህ ምናልባት ዛሬ ያያችሁት ነብር ፤ ያን ዝንጀሮ ብቻውን ደንጋይ ሲፈነቅል ሲያገኘው ፤ ሌሎች እዚያ ባጠገቡ መሆናቸውን

@OLDBOOKSPDF

ሲያይ ፥ ከዘመዶቹ የራቀ ይሆናል ። ያለዚያ . . . መቼም አንዳንድ እብድ በያገሩ አይጠፋ ፥ ያበደ ኑብር ይሆናል ! ” አሉ ባላምባራስ ።

“ ደግሞ ሶፊያና እኔን ያስገረመን ፥ ኑብሩ መጀመሪያ ያን ደንጋይ ሲፈነቅል የነበረውን ዝንጀሮ ለመያዝ ከቃጣ በሁዋላ ፥ ከዚያም ከበውት የነበሩት ዝንጀሮዎች መሸሽ ሲጀምሩ አንዱን ከያዘው በሁዋላ ፥ ሁለት ጊዜም ፥ ጅራቱን ሲያዙት ልክ ሽባ እንደሆነ ሁሉ ፥ ለመያዝ የቃጣውንም ፥ የያዘውንም ትቶ ፥ እያጕረመረመ ብቻ በፊት እግሮቹ መሬት መቡዋጠጡ ነው ! አለ ” ጥላሁን ።

“ ኑብር ጅራቱን ከያዙት ፥ ወደ ፊት ከመሳብ በቀር ምንም ጉዳ ሬግ አይችልም ” የሚባለውን አታውቅም ? እሱም ይቅር ፥ ‘የኑብርን ጅራት አይዙም ፤ ከያዙም አይለቁም ! ’ የሚሉትን ተረትስ አልሰማህም ? ” አሉ ባላምባራስ ፥ ፍርጥም ብለው ።

“ ተረቱን ሰምቻለሁ ፤ ነገር ግን . . . ኑብር ጅራቱ ከተያዘ ወደ ሁዋላ መዞር የማይችል ስለሆነ የተተረተ መሆኑን አላውቅም ። ”

“ እኔም ጅራቱን ተይዞ ወደ ሁዋላ መዞር ሲያቅተው ፥ በእነዚህ ባይኖቼ ስላላዩሁ ፥ አይችልም ብዬ አልምልልህም ! ” አሉ ባላምባራስ ፥ “ በእነዚህ ባይኖቼ ” ሲሉ እይናቻቸው ያሉበትን ባውራና በጠቋሚ ጣቶቻቸው እያመለከቱ ። “ ነገር ግን ” አሉ ቀጥለው ። “ ነገር ግን ፥ በጠቅላላው በሰው ሁሉ ዘንድ የሚታመነው ፥ ምንም የማያጠያይቀው ፥ ኑብር ጅራቱን ከተያዘ በመንተት እድከም እስኪለቀቅ ወደ ፊት ከመሳብ በቀር ፥ ወደ ሁዋላ የማይዞር መሆኑ ነው ። እንጃ . . . እንዲሁ ተረት ይሁን ፥ ወይስ የሆነ ነገር እርግጠኛውን አላውቅም ፤ ብቻ ሰዎች ሲጫወቱ የሰማሁትን ልንገራችሁ ። የሆነ ነገር ቢሆን ደግ ፤ ተረትም ቢሆን መቼም ተረት ያለመሰረት አይነሳምና . . . ማናቸውም ቢሆን ግወቱ አይከፋም ! ” አሉ ፥ የኑብር ጅራት ይዞ ሲጨነቅ ስለ ነበረ ሰው የሰሙት ጭዋታ ያንጊዜውኑ ትዝ ስላላቸው ፥ ጭዋታውን ከመናገራቸው በፊት ትንሽ እንደ መሳቅ አሉና ። “ አንድ ሰው ዱላውን ይዞ መንገድ ሲሄድ ፥ ኑብር የሰው ፍዬል አርዶ ሲበላ አገኘና ፥ ኑብሩ ሳያየው መንገዱን አሳብሮ መሄድ ሲችል . . . ያንለት ያዬው ጭንቅ እንዳያልፈው ጥንት ሲፈጠር እግዜር የመደበው ኖሮ . . . ኑብሩን በያዘው ዱላ ከሁዋላው ሰንደበውና ፥ አጉራርቶ ሲነሳ ቶሎ ጅራቱን ለቅም አረገው ! ከዚያ ኑብሩ ወደ ፊት ፥ ሰው

@OLDBOOKSPDF

ፉው ወደ ሁዋላ እየተሳባቡ ፤ የንብሩ ሀይል ስላዬለ ፤ ነብሩ ፊት ትት ሰውዬው ሲከተል ፤ እንዲሁ ሜካ ለሜካ ፤ ባቀበት በቁልቁለቱ በጋሬጣው በንቅፋቱ ሁሉ ፤ ነብሩ እየጎተተ ፤ ሰውዬው እየተከተለ ቀኑን ውለው አመሻሽ ላይ አንድ ሰው አግኝቶዋቸው ፤

"እይ ወንድሜን ፤ ምን ክፉ አድል ገጠመህ !" አለ-ያ ሰው የነብር ጅራት የያዘው ሰው አገኝ ።

"እዩውልህ ወንድሜ ፤ ከጀጠባቤ ውስጥ ፤ በወገቤ ላይ የታጠ ቅሁትን ጩቤ አውጥቼ አንጀቱን ዘርግፌ እንዳልጥለው ፤ ባንድ እፍታ ጅራቱን የሚይዝልኝ አጥቼ ተከትዬው እዞራለሁ !" አለ ጅራት የያ ዘው ። ከዚያ ፤ "እምጣ !" ብሎ አዲስ መጪው ፤ በፍጹም ቅንነት ጅራቱን ከጁ ሲቀበለው ፤ ያ ነብር ሲጎትተው የዋለ ሰው "እሁ . . . !" ብሎ በረዥሙ ተንፍሶ ፤ "ብል እንግዲህ የኔ ወንድም ፤ እኔ ለቀብጥ ፤ የቀባጩን የነብር ጅራት ይዤ ውያለሁ ፤ አንተ ደግሞ የቅባጭህን ይዘህ እደር !" ብሎ ፤ ከነብሩ ጋር ጥሎት "ሄደ ። እንግዲህ ሲያወሩ የሰማሁ እዚህ ድረስ ነው ፤ ከዚያ በሁዋላ ፤ ሰስተኛ ቀባጭ ይተካ ፤ ወይስ ሰዚያው ለሁለተኛው ቀባጭ የፍዬ ልዋ እጣ ይድረሰው ፤ ሲያወሩ አልሰማሁም !" ብለው ባላምባራስ ጠጃቸውን ጨልጠው ፤ "ጨምሩልኝ" ማለት መሆኑ በታወቀው እስተያየታቸው የውብዳርን ሲያዩ ፤ ሁሉም ይስቅ ጀመር ።

"ደግሞ . . . ወደዚህ ጥጃ ከመጣን ከተመለከትናቸው ብዙ እስ ደናቂ ነገሮች አንዱ ፤ የጉሬዛዎች ሰአት ማወቅና ፤ ተጠንቅቆ መጠ በቅ ነው" አለ ጥላሁን ፤ ከሳቅ በሁዋላ ሁሉም ዝም ብለው ቆዩና ።

"ጉሬዛዎች" አለ ቀጥሎ ። "ጉሬዛዎች መጮህ ሲጀምሩ ፤ እምቢት ሌሊት አከታትለን መብራት እያበራን ሰአታችንን ስናይ ፤ ሁልጊዜ በዘጠኝ ሰአት ላይ ነው የሚጮሁ ። ልዩነት ቢኖር ከአንድ እስከ ሶስት ደቂቃ ብቻ ነው ! በዘጠኝ ሰአት ግድም ፤ ከምስራቅ ይሁን ከምንራብ ፤ ወይም ከሰሜን ፤ ወይም ከደቡብ ፤ አንዱ 'ኡርር ርር ፤ ኡር ፤ ኡር ፤ ኡር !' ብሎ ሲጀምር ፤ ሌሎች ከያቅጣጫው እየተከታተሉ ፤ 'ኡርርርር ፤ ኡር ፤ ኡር !' ይላሉ ። ታዲያ ይህ ከያቅጣጫው ፤ በቅደም ተከተል ፤ ወረርና ቀጠን እያለ የሚሰማው 'ኡር ፤ ኡር' ባንድ ላይ ሆኖ ፤ ሜካውን ሌሊት ቅዱሳን ለፈጣሪ የሚዘምሩበት ፤ የተቀደሰ ቦታ ያስመስለውና ፤ በሰው ውስጥ ልዩ ስሜት ይፈጥራል !" አለ ጥላሁን ፤ እሱና ሶፊያ ብቻቸውን ሳሉ የተነጋ ገሩትን እንደ ገና ለነባላምባራስ ደግሞ ።

@OLDBOOKSPDF

"እንጃ ! ልዩ ስሜት የመፍጠሩ ጉዳይ እንኳዋ መኖልባት ... አንት ከዚህ በፊት ፣ ሌሊት የጉሬዛ ጩኸት ሰምተህ ባታውቅ ይሆናል እንጂ ፣ እኛ አብረነው ስለ ኖርን ፣ እንዲህ ያለ ልዩ ስሜት አይፈጥርብንም ! ለኛ በመንደር ፣ ወይም በከተማ ሌሊት ፣ በተወሰነ ጊዜ ዶሮ የሚጮኸውን ያክል ነው ! ከሱ ልዩነት የለውም ! እኛ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ጉሬዛን 'የጫካ ዶሮ' ነው የምንለው !" አሉ ባላምባራስ ፈገግ ብለው ።

ሶፊያና ጥላሁን ፣ እዚያ ዋሻ ሲሰነብቱ የተመለከቱት ሁሉ ፣ የልዩ ልዩ አራዊትና አእዋፍ የኑሮ ልምድ ፣ ይልቁንም የዘንጀሮዎች ግህ በራዊ ኑሮና ድርጅታቸው ፣ ሆን ብለው ለጥናት የሄዱለት ቢሆን ኖሮ፣ እንዴት ደስ ባሰኛቸው ነበር ! ነገር ግን ፣ "ተገድዶ የዋጡት ግር ከሬት ይመር !" እንዲሉ ፣ ተገደው ፣ ከቤታቸው ሸሽተው በተሸሸ ጉብት ያጋጠማቸው ስለሆነ ፣ ምንም እንኳዋ የመከራቸውን ክብደት ለማቅለል ያክል ቢረዳ ቢችል ፣ እሱን ፈልገው ፣ ወይም እሱን ለማጥናት የሄዱ ቢሆን ኖሮ ፣ ይሰጣቸው የነበረውን ደስታ ሊሰጣቸው አል ቻለም ! አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም ጥላሁንን መውጫ ወደሌለው ያሳብ ጫካ ይመራውና ፣ ሊሊት እንቅልፉን አጥቶ እንዲያው እንደ ተወራጨ ያድር ነበር ። እንዲያ እንትልፍ ሸሽቶት ከሳቡ ጋር በሚ ከራከርበት ጊዜ ፣ እሱና ምኞቱ ያራዊትን የኑሮ ልማድና ባህላቸውን ፣ ከቋዋንቋዋቸውም አንዳንዱን ከግወቃቸው ጋር ፣ ከሰዎች ማኅበር ተለይተው ያራዊት ማህበርተኞች መሆናቸው ፣ ከዚያም ከሰዎች ሽፍ ተው ካራዊት የተጠጉበት ምክናያት ፣ ባንድ ላይ ተያይዞ መጥቶ ባይን ህሊናው ይታዩውና ይገረማል !

"ግሩምክ ነው !" ይላል አይኖቹን በጨለማው ፍጥጥ አድርጎ ። "ይገርማል ! ? ሰው ... የዚያን ያክል ብዙ ሰው ነፍስ ሲያጠፉ ፣ ያንድ ወረዳ ህዝብ ሀብትና ንብረት ሲዘርፉ፣ የመንግስትንና የእግዚአብሄርን ህግ ጋት እድሚያቸውን ሙሉ ሲተላለፉ የኖሩትን ወንጀለኛ ፣ ቀኛዝማች ዳኛን ስለ ገደልን ፣ እዩፈከርን አደባባይ በመውጣት ፈንታ ከሰው ሸሽ ተን ካራዊት ጋር በጫካ ውስጥ መኖራችን አያስገርምም ? ማንን ስለ በደ ልን ፣ ከማን ነው የምንሸሽ ? ከህግ ! እንዴት ? ወንጀለኛ ስለ ገደልን ከህግ የምንሸሸ ... ህግ የወንጀለኞች መቅጫ ነው እንጂ ፣ የወንጀለኞች ጠበቃ ነው ?" አለና ፣ አንድ ሌሊት ብዙ ጥያቄዎች እከታትሎ ጠይቆ ፣ እንደ ልማዱ አይኖቹን አፍጥጦ ጨለማውን ሲመለከት ከቆዩ በሁዋላ፣ "አዎ!"

@OLDBOOKSPDF

ልለ ፣ መልሱን ከዚያ አይኖቹን አፍጥጦ ሲመለከተው ከነበረ ጨለማ እንዳገኘ ሁሉ ። “ አዎ ፤ ህግ የስልጣን መሳሪያ ብቻ ነው ! የራሱ ነጻ የሆነ አቋዋም የለውም ! ህግ የስልጣን አገልጋይ ፣ የስልጣን ባሪያ ነው ! የስልጣን መሳሪያ እንደ መሆኑም ፣ ስልጣን ባመጸኞችና በህ ሊና - ቢሶች እጅ ከተያዘ ፣ እንዲያ ያሉት አመጸኞችና ህሊና - ቢሶች የሆኑ ባለስልጣኖች የሚሰሩት ህግ ፣ የወንጀለኞች ..ዘበኞ ፣ ስልጣን በንጹሆች እጅ ከተያዘ ፣ እነሱ የሚሰሩት ህግ ፣ የወንጀለኞች መቅጫ ስለሚሆን ፣ ህግ መልካም ፣ ወይም ክፉ ፣ የወንጀለኞች መቅጫ ፣ ወይም ጠበቃ የሚሆነው ፣ የስልጣን ባለቤት የሆኑት ክፍሎች የጎ ደፉ ፣ ወይም ንጹህ ህሊና ያላቸው እንደ መሆናቸው መጠን ነው ማለት ነው ! ” ብሎ ፣ እንደ ገና አይኖቹን በጨለማው ውስጥ አፍ ጥጦ ፣ ዘለግ ላለ ጊዜ ሲያስብ ቆዬና ፣ “ እንግዲህ የስልጣን መሳሪያ የሆነው ህግ ፣ ሁሌጊዜ ፣ የሰዎችን ህይወት ፣ ንብረት ፣ ነጻነትና መብት መጠበቂያና ፣ የነሱ ተጻራሪዎች የሆኑትን ወንጀለኞች መቅጫ እንዲሆን ፣ የወንጀለኞች ጠበቃ እንዳይሆን ፣ ህጉን የሚሰሩት የስል ጣን ባለቤቶች ህሊናቸው ያልጎደፈ ፣ ንጹህ መሆን አለባቸው ። ለህግ መገዛት ፣ ለህግ መታዘዝ ማለትም ፣ እንዲህ ባሉ ንጹህ ህሊና ባላ ቸው የስልጣን ባለቤቶች በተሰራና ፣ የሰዎችን ህይወት ፣ ንብረት ፣ ነጻነትና መብት በሚጠብቅ ህግ መገዛት ፣ ወይም መታዘዝ ማለት ነው እንጂ ፣ እንዲያው ባጠቃላይ ‘ ለህግ መገዛት ፣ ለህግ መታዘዝ ’ የሚሉት ነገር . . . ለመጥፎ ህግ መታዘዝን ሊጨምር ስለሚችልና የተጣራ ትርጉም ስለማይኖረው ፣ ሊቀበሉት የሚገባ አደለም ። ለመጥፎ ህግ መታዘዝም ፣ መጥፎ ህግን ከሚሰሩና ፣ ባሳብም ፣ በግብ ርም ከጎደፉ የስልጣን ባለቤቶች ጋር ተባባሪ መሆን ነው ! ” ብሎ ደግሞ እንደ ገና ዘለግ ላለ ጊዜ ሲያስብ ከቆዬ በሁዋላ ፣ “ አየ ጉ . . . ድ ! ” አለ ። “ አየ ጉ . . . ድ ! ምነው ህግ ፣ ሰው - ሰራሽ ህግ ፣ የስልጣን ባለቤቶችን ጠባይ ተከትሎ የማይለወጥ ፣ እንደ ፍጥረት ህግ ነዋሪ በሆነ ! ”

ጥላሁን ፣ ምሽቱና እሱ ዘራፊውን ፣ ነፍስ አጥፊውንና ፣ የግዜር ንም ፣ የመንግስትንም ህግ ተላላፊውን ፣ ቀኛዝማች ዳኘን ስለ ገደሉ፣ በህግ ስም ፣ ከሚያሳድዷቸው ፖሊስ ሸሽተው እዚያ ዋሻ እስከ ተሸሸ ጉበት ጊዜ ድረስ ፣ ለህግ የነበረው ፍቅርና አክብሮት እጅግ ከፍ ያለ ነበር ። እስከዚያ ጊዜ ድረስ ፣ “ ከሁሉ በላይ ህግ ! ” የሚሉትን ብሂል ያላንዳች ጥያቄ ተቀብሎ ፣ ምኞቱ ሁሉ ፣ በጣም የሚወደው የመኖሩ አላማ ሁሉ ፣ የህግ ትምርቱን ሲጨርስ ፣ ለተበደሉት ጠበቃ

@OLDBOOKSPDF

ወይም እግዚአብሔር ለዚያ ቢያበቃው ፣ ዳኛ ሆኖ ፣ ህግን ጋሻና መከታ እያደረገ ፣ ያላንዳች ፍራት ፣ ህዝብ የሚበድሉትን ሀይለኞችና ባለ ስልጣኖች ፣ በደላቸውን አምነው ፣ ባደባባይ እየተንበረከኩ ምህረት እንዲለምኑና ፣ ንስሀ እንዲገቡ ማድረግና ፣ የተበደሉት ሁሉ ደስ ብሎዋቸው ፣ "እልል" ሲሉ ፣ ተመልካቾች ሁሉ ገርመዋቸው ፣ "ይብል" ሲሉ ፣ እያዩና እዩሰማ ፣ ሁልጊዜ ደስ እያለው መኖር ነበር ! እስክዚያ ጊዜ ድረስ ፣ ህግ የተበደሉትን ለማስካስ ፣ የተቆሙትን ለማስመለስ ፣ ሀይለኞችን ለመደኘትና ወንጀለኞችን ለመቅጣት ፣ ከሁሉ ፣ ከስልጣን ጭምር በላይ ከፍ ብላ የቆመች እንጂ ፣ የስልጣን ባለቤቶች የሆኑ ክፍሎች ለጥቅማቸው መጠበቂያና ፣ ከዚያም ማስፋፊያ ፣ ለጠላቶቻቸው ማጥፊያና መበቀያ እነሱ የሚፈጥሩዋት ፣ "የስልጣናቸው መሳሪያ ልትሆን ትችላለች" ብሎ ማመን ይቅርና ጥርጣሬ አድርቦበት ለመመርመር እንኳዋ አስቦ አያውቅም ነበር ። እዚያ ዋሻ ከገባ በሁዋላ ግን ፣ ህግ ልክ እንደ ስልጣን የባለስልጣኖች መሳሪያ መሆንዋን ፣ ህግና ስልጣን የተለያዩ ሰዎችና መልኮች ይኑሩዋቸው እንጂ ፣ ሁለቱም የስልጣን ባለቤቶች የሆኑትን ክፍሎች ጥቅም መጠበቂያዎች መሆናቸውን ስለ ተረዳ ፣ ህግንም በመውደድ ፈንታ እንደ ስልጣን ጠላት ፤ ህግንም በማክበር ፈንታ እንደ ስልጣን ናቃት ።

" ሀ ! እዎ " አለ ፣ አይኖቹን በጨለማ ውስጥ እንዳፈጠጠ ሲያስብ ቆይቶ ። " ልክ ነው ፣ ህግ እንደ ሰሪው ነው ! የወንበዴዎች ማህበር ህግ ፣ መቀማትንና መግደልን ፣ የገዳሚት ማህበር ህግ ፣ መጸለይንና "ቀኝ ፊትን ለጸፊ ግራ ፊትን መልሶ መስጠትን " ፤ " አጽፍን ለቀማ ቀሚስን መጨመርን አደል የሚያዝዙት ? " አለ ፣ ብቻውን የቅርታ ፈገግታ ፈገግ ብሎ ።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ " ለህግ መገዛት ፣ ለህግ መታዘዝ " ሲባል፣ የሰው ሀይወት ፣ ንብረት ፣ ነጻነትና መብት ፣ ያላንዳች አድልዎ ፣ በትክክል የሚጠብቅ ህግ መሆኑን ፣ የጥቅም ክብደት ያላጣመመው ፣ ትክክለኛ ህሊና ሁሉ ለሚመሰክርለት ህግ ማለት እንጂ፣ እንዲያወም በስመ - ህግ ለማናቸውም ህግ ፣ ለሙጥፎ ህግ ጭምር ፣ ማለት አለመሆኑን ፣ ለመጥፎ ህግ መታዘዝ ፣ ወይም መገዛት ፣ ለመጥፎ ሰሪዎች ተባባሪነት መሆኑን አምኖ ፣ ያን እምነት መመሪያው ለማድረግ ወሰነ ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ፴፮

# ግራዝማች ጉርሜሳ ቤራ

አንድ ማታ ፤ ሶፊያና ጥላሁን ተሸሽገው ከሰነበቱበት ዋሻ ወጥተው የሚሄዱበት ጊዜ ደርሶ ፤ ስለ ጉዞዋቸውና በመንገድ ማድረግ ስለሚገባቸው ሁሉ ፣ አሳዬና የወ/ብዳር ከባላምባራስ ጉደታ ጋር እንደ ልማዳቸው ወደ ዋሻው መጥተው ሲመካከሩ ፤

“ መቼም . . . ” አሉ ባላምባራስ ፤ በጃቸው ይዘውት ከነበረው ብርጭቆ ጠጅ አንድ ጊዜ ተጎንጭተው ፤ ብርጭቆዋቸውን በፊታቸው እያስቀመጡ ።

“ መቼም . . . ከዚህ ወዲያ እንደምትሄዱ ለኛ ገና ባትነግሩንም፣ ምናልባት እናንተ ተመካክራችሁ ወስናችሁ ይሆናል ። ብቻ የሰው አሳብ የእግዚአብሄር ቃል ስላልሆነ ፤ የሚሻል አሳብ ከተገኘ ሊለወጥ ይችላልና ፤ እስቲ ቢከፋም ቢበጅ ፤ የኔንም አሳብ ልንገራችሁና ከናንተ አሳብ ጋር አድርጋችሁ አስቡበት ፤ ልጆቼ ። አሁን ምሳሌ አድርጌ የምነግራችሁ ፤ ምሳሌነቱ ለናንተ የሚስማማ ባይሆንም ፤ በጠቅላላው ለተሸሻጊና ለፈላጊ ስለሚሆን ፤ ደፍሬ በመናገሬ አስቀድሜ ምህረት እንድታደርጉልኝ እለምናችሁዋለሁ ። በጎልማሳነቴ ፤ ሌባድም እንደ ነበርሁ ብዙ ጊዜ አጫውቻችሁዋለሁ ። ታዲያ በዚያን ጊዜ ፤ ከተማ ገብቶ በሰው መሀከል የሚሸሸግ ፤ ነፍስ የገደለ ሽፍታ፤ ወይም ከብት የሰረቀ ሌባ ፤ ፈልጎ ከማግኘት ፤ እልም ፤ ጭልም ፤ ባለ ደን ውስጥ የተሸሸገውን ማግኘቱ ይቀለን ነበር ። ስለዚህ . . ከረዥም ጊዜ ልምድ እንደ ተረዳሁት ፤ ምን ጊዜም ቢሆን ፤ ከሰው ለመሸሸግ ፤ ሰው ከሚበዛበት ፤ ከሰው ሜካ የሚሻል መሸሸጊያ አይገኝምና ፤ ሰው በሚበዛበት አዲስ አበባ ገብታችሁ ብትቀመጡ ፤ ከተጠነቀቃችሁ ምንም እንደማይደርስባችሁ እኔ እርግጠኛ ነኝ ።

“ሌላ ልሰጣችሁ የምወደው ምክር ፤ ከዚህ ተነስታችሁ የመጨረሻ መድረሻችሁ በሰሜን የሚገኝ አገር እንደ ሆነ ፤ መጀመሪያ ወደ ምዕራብ ፤ ከዚያ ወደ ደቡብ ፤ ከዚያ ወደ ምስራቅ ሄዳችሁ ፤ ስሜን በፊት

@OLDBOOKSPDF

ለፊት ከመግባት፣ ዞሮ በጉዋሮ መግባት የሚሻል መሆኑን ነው!" አሉ ባላምባራስ፣ በጉዋሮ እንዴት እንደሚገባ ለማሳየት እጃቸውን እንደ ዶጋን አጉብጠው።

"ደግሞ ሌላ የምንግራችሁ . . ." አሉ ባላምባራስ፣ አስበውት የነበረ ነገር፣ ሊናገሩት ካሰቡቸው ወጥተው እፋቸው ሊደርስ ድራሹ ስለጠፋ፣ ፊታቸውን ኩስትር አድርገው፣ ከተሸሸገበት እንደሚፈልጉ ሁሉ፣ አይናቸውን ግራና ቀኝ፣ ላይና ታች እያቁዋቁዋጡ። "አ፣ አዎ!" አሉ፣ ወዲያው ካፋቸው ሾልኮ የጠፋውን ነገር ሲያገኙት፣ ፊታቸው እንደ ገና ፈገግ ብሎ። "እዎ ሁለግም ሌላው የምንግራችሁ፣ ላጭርም ይሁን ዘለግ ላለ ጊዜ፣ ከጉዞዋችሁ አርፋችሁ በምትቆዩበት ቦታ፣ መጠሪያ እንዲሆናችሁ የምትመርጡት ስም፣ ያን ቦታ ለቃችሁ ስትሄዱ አብሮ ዋችሁ መሄድ የለበትም፣ እዚያ እንደ ተፈጠረ፣ እዚያው መቅረት አለ በት።"

"ለምን አባባ?" አለች ሶፊያ፣ እዚያ የነበሩት ሁሉ ሊጠይቁት የነበረውን ጥያቄ ከዱምላሳቸው ማድ ነጥቃ። ባላምባራስ የሚሉትን ለመስማት ያክል ነው እንጂ፣ እንዲያ ባለ ጊዜ ስም መለወጥ የሚያስ ፈልግበት ምክንያት ተራ ነገር ስለሆነ፣ ለሁሉም ጠፍቶዋቸው እንኩዋ አደለም። ጠዲያው እዚያ ጥያቄው ከያፋቸው የተወረሰባቸው ሰዎች መልሱን ከባላምባራስ አፍ ሲወጣ ማየት ይችሉ ይመስል፣ ሁሉም አይ ናቸውን ከሶፊያ እንስተው እሳቸው አፍ ላይ አሰፈሩ።

"መቸስ . . . ስም መታወቂያ አይደል? ታዲያ አሁን እናንተ መታ ወቅ የምትፈልጉበት ጊዜ አደለምኮ! ስለዚህ የውነተኛ ስምና ቀጥታ መንገድ፣ ከፈላጊዎች ለሚሸሽጉ አያገለግሉምና፣ ፋራችሁን እያሸተቱ ሊከታተሉ ከሚችሉ ፈላጊዎች ለመጥፋት፣ በዱምታርሩበት ስማችሁን መለወጡንና፣ ከቀጥታ ዘወርዋራ መንገድ መምረጡን እንዳትረሱ ይሁን!"

"ልክ ነው፣ እውነት ነው" ተባባሉ ጥላሁንና አሳዬ፣ እስበሳቸው ተያይተው። ከዚያ ሶፊያና ጥላሁንም፣ አዲስ አበባን ሲለቁ ስማቸውን የለወጡት ትዝ አሳቸውና፣ ተያይተው ሁለቱም ፍርጥም አሉ።

ጥላሁንና ሶፊያ፣ አዲስ አበባ የመመለሱን ነገር ገና ባይቆርጡም፣ ፋራቸውን ለማጥፋት፣ አገር ላገር ሲዘዋወሩ መቆዬቱ መልካም መሆ ኑን አምነው፣ ሁሉም በባላምባራስ አሳብ ተስማሙ። ስለዚህ፣ በሚዛን ተፈሪ በኩል አድርገው፣ መጀመሪያ ወደ ከፋ፣ ከዚያ ወደ ጋሞጎፋ፣ ወደ ሲዳሞ፣ ወደባሌ፣ ከዚያ . . . እግዜር ይወቅ ወዴት . . . ለመሄድ ተሰናዱ!

@OLDBOOKSPDF

ከዚያ የፖሊሱ አዛዥ የጠቆሙን ለማስፈጸም በያቅጣጫው የባከኑ ቀኖቻው ፖሊሶችና ሌሎች ፈላጊዎች ሁሉ ከዬሄዱበት ተመለሰው፣ ሁል ጊዜም ያን የመሰለ አደጋ ሲደርስ፣ በትኩሱ የሚታዩው ግርግርና ንቅናቄ ጸጥ እያለ፣ ጥንቃቄው ባላ እያለ ሄደ፣ እስጊው ጊዜ ያለፈ ሲመስል፣ ባላምባራስ ከጊሜ ሰዎቻቸውን አሰመጥተው፣ እንደ ልማዳቸው ወደዚያው ወደ ጊሜ የሚሄዱ መሆናቸውን ቀደም አድርገው አስወሩና፣ አንድ ሌሊት፣ ጥላሁንንና ሰፈያን ከየውብዳርና ከላዩ ጋር በሌ ቅሉ ከተሰናባበቱ በሁዋላ፣ ይዘዋቸው ወጥተው፣ ቀን ቀን በጫካ ውስጥ ተኝተው እዬዋሉ፣ ሌሊት ሌሊት እዬተጓዋዙ፣ ባምስተኛው ሌሊት፣ አንጋት ላይ ሚዞን ተፈራ፣ ከዚተገዋ ደር ደርሰው፣ እዚያ ሌሊት መቀዋቸው እንዳይታወቅ ትንሽ እርፈው ቆይተው፣ ጥቅ ሲል ወደ ግራዝማች ጉርሜሳ ቤራ ቤት ሄዱ። ትርጥ በቅሎ መዋስ፣ ወይም መክራየት የሚያስጠረጥር በመሆኑ፣ ባላምባራስ ያችኑ፣ የነበረቻቸውን አንድ በቅሎ አስገድደው፣ ሰፈያ በጥቷው፣ እሳቸውም፣ ጥላሁንም ከባላምባራስ አሽከሮች ጋር፣ የሚጓዋዙት በግራቸው ነበር ።

እግራዝማች ጉርሜሳ ቤራ ቤት እንደ ደረሱ፣ ባላምባራስ ጉዳታቸው እንኪዋ ሳያርፉ፣ መጀመሪያ ያደረጉት ሰዎቻቸው በቅሎዋቸውን ይዘው ወደ ጊሜ እንዲመለሱ ማሰናበት ነው ።

– “እንግዴህ እዚህ ከደረስሁ፣ ወንድሜ የኪ ያደርሰኛል፤ ለሱም ካል ቀመቸው ከነጋዴ ጋር ልሄድ እችላለሁና፣ እናንተ ቶሎ ወደ ቤራችሁ ተመለሱ፣ ልጆች ” አሉ ።

“እንዴት ነው ከመንገድ መጥቶው፣ እርፈው ሳያድሩ እንደገና ያን ያክል መንገድ የሚሄዱ ? ቢሆን እርፈው አድረው ነገ ጥዋት ይሄዱ ! ያለዚያም . . . ባይሆን እህል ቀምሰው፣ ትንሽ እርፈው ቆይተው፣ አመሻሽ ላይ ይነሱ ” አሉ ግራዝማች ጉርሜሳ፣ ቤታቸው ምጣድ እንደማይጣድበት ሁሉ፣ አጥራቸውን የገቡ እንግዶች፣ “እህል ሳይቀምሱ ይሂዱ” መባሉን እንደ ብርቁ ሰድብ ቆጥረውት ።

“ስራ እስፈጐች ሰላመጣሁዋቸው፣ ለስራው ጉዋጉቼ ነውኮ ወንድሜ፣ ወዲያውም ሰንቅ ይዘዋል ብዬ ነው ። ደግሞስ . . . እንግዶች መሆናቸው ነው ? ያንተ ቤት ቤታቸው አይደለም እንዴ ! ” አሉ ባላምባራስ፣ ግራዝማችን ቅር እንዳላቸው ከፊታቸው ስለ ተመለከቱ ። ባላምባራስ፣ ሰዎቻቸውን ወደ አገራቸው ቶሎ እንዲመለሱ ያን ያክል የሚገፋፉዋቸው፣ እንዳሉት ለስራ ጉዋጉተው ሳይሆን፣ ምንም እንኩዋ እደያ

@OLDBOOKSPDF

ሰዎች ረዥም ጊዜ አብረዋቸውየኖሩና ፣ የሚያምኑዋቸው ቢሆኑ ፣ እዚያ ከመቆዩት የተነሳ ፣ በጭዋታ ብዛት ፣ ወይም በዋዛታ ፣ ሳያታውቃቸው "ምስጢር ሊወጣ ይችላል " ብለው ስግተው ነው ። ቢሆንም ግራዝማች አሸንፈው ፣ ሰዎቹ ምሳቸውን በልተው ፣ ጠጅ ጠጥተው ሄዱ ።

ግራዝማች ጉርሜሳ የባላምባራስ ጉደታ አጎት ፣ የባላምባራስ ቢራ ልጅ ፣ በየኪ ወረዳ ውስጥ ፣ ቴፒ በምትባል ትንሽ ከተማ ይኖሩ ነበር ። የቀኛዝማች ዳኘ አገዛዝ ስላስመረራቸውና ፣ ይልቁንም ህዝብ ስለሚ ወዳቸውና ስለሚተባበራቸው ቀኛዝማች ቀንተው ሲያጠፏቸው እን ደሚከታተሉዋቸው ራሳቸውም ፣ ባላምባራስ ጉደታም ስለተመለከቱ ፣ ቀስ ብለው ተመካክረው ፣ ወሬው ሳይዛመት የግራዝማችን ርስት ሸጠው ሚዛን ተፈሪ ከገቡ ፣ አስር ፣ ወይም አስራ አንድ አመት ሆኖ ዋቸዋል ። ግራዝማች ጉርሜሳ ፣ ባላምባራስ ጉደታን እጅግ ስለሚወዱዋ ቸውና ስለሚያፈቅሯቸው ፣ እንኳንስ ባላምባራስ ራሳቸው የወለዱዋቸውን እንግዶች ፣ ስማቸውን ብቻ ጠርተው የሚሄዱባቸውን እንግዶች ሁሉ በደስታ እየተቀበሉ ሲያስተናግዱ ስለሚኖሩ ፣ የባላምባራስን እንግዶች ፣ ዋሴፍ ጠብቂንና እመቤት ዘላለምን ፣ በጣም ደስ ብሎዋቸው ተቀበሉ ዋቸው ። ዋሴፍ ጠብቄና እመቤት ዘላለም የጥላሁን ፈይሳና የሶፊያ ሙላት የሚዛን ተፈሪ ስጦች መሆናቸው ነው ።

"እቶ ዋሴፍ ጠብቄና ባለቤቱ ፣ ወይዘሮ እመቤት ዘላለም ፣ አዲስ አበባ ይሀን . . . ዘበን አመጣሽን የፈረንጅ ትምርት አስተማሪዎች ናቸው። ታዲያ . . . አገር እየዞሩ ለማየት ስለ ፈለጉ ፣ በወለጋ በኩል ከሚያውቁዋቸው ሰዎች ጋር እስከ ጎሬ ፣ ከዚያ ፣ እኒያ ጎሬ ያደረሱዋቸው ሰዎች ከግር ነጋዴዎች ጋር አገናኝተዋቸው ጉጫ መጥተው ፣ እኔ ቤት አብረን ስለ ሰነበትንና ስለ ለመድሁዋቸው ፣ ከዚህ እንተ ሁነኛ ሰው ፈልግህ ወደ ከፋ እንድትሰዳቸው 'አደራ' ልልህ ነው . . . ራሴ ፣ ይዤ ቸው የመጣሁ" አሉ ባላምባራስ ፣ ጥላሁንንና ሶፊያን ከግራዝማች ጉር ሜሳ ጋር ሲያስተዋውቁዋቸው ።

" ሁነኛ ሰው እስኪገኝ ይውል ያድር እንደሆን እንጂ ፣ ወደ ከፋ የሚሄድ ሰውማ . . ምን ይገዳል ! በቀን ሀያ ፣ ሰላሳ ሰው ሳይሄድ ውሎ ያውቃል ! " አሉ ግራዝማች ።

"ከሁነኛ ሰው ሲገናኙ ለማየት ብዬኮ ነው. . . የኪ እንዳያ ያለ ጉድ ፣ እንዲያ ያለ ታምር መሰራቱን ስሰማ ፣ ወደዚያ መሄዱን ትቼ ወዲህ የመጣሁ ! ከሁነኛ ሰው ሲገናኙ ካላዩሁ ልቤ የማያርፍ ስለሆነ ነው ! "

@OLDBOOKSPDF

“እሱ ግዴለም ፣ እሱን እንዳልሁህ ይውል ያድር እንደሆን እንጂ ከፋ ማድረስ ብቻ ሳይሆን ፣ እዚያ ማየት የሚፈልጋቸውን አገር ሁሉ አዞሮ የሚያሳይ ፣ የከፋ ሰው አናጣም ። እዚህ እንኳ ብናጣ ፣ እዚያ ወንድማችንም ፣ ወዳጃችንም በሳሉን ፣ ከነሱ ልከን ማስመጣት እንችለን” አሉ ግራዝማች ጉርሚሳ።

“እኔምኮ በዚህ በኩል አንተ ብዙ ሰው ማወቅህንና ፣ ከብዙ ዘመድ ወዳጅ ጋር ግንኙነት ያለህ መሆንህን አምኜ ነው ወዳንተ ይዤቸው የመጣሁ” አሉ ባላምባራስ ፣ ግራዝማች በሰጡዋቸው የተረጋገጠ ተስፋ ደስ ብሎዋቸው።

“ለመሆኑ አንተ መቼ ነው ወደ ጊሜ የሄድህ ? ቀኛዝማች ዳኜ ሲገደሉ. . . የኒ. አልነበርህም ማለት ነው ?” አሉ ግራዝማች ።

“አልነበርሁም ፤ ‘ቡናው ሜኪ ሰብሰዋልና አንተ መጥተህ ደብ ካልለመንህ ብቻችንን እንገፋውም’ ብለው ልጆቹ ስለነገሩኝ ፣ ቀደም ብዬ ወደ ጊሜ ሄጄ እዚያ ነበርሁ ። እዚያ እንዳለሁ ነው. . .የዚያን ከፉ ሰው ሞት የሰማሁ ።”

“ይገርማል ! ታዲያኮ ቀኛዝማች ዳኜ ሲገደሉ ቱር ሄዶ እዚያ የነበረ ፣ የዚህ አገር ሰው በቀደም መምጣቱን ሰምቼ ያንተን ደህንነት ‘እጠይቃለሁ’ ብዬ ሄጄ ሳነጋግረው ፣ ደህንነትህንና እዚያው የኒ. መሆንህን . . . ነበር የነገረኝ !”

“ ባይኔ አየሁት ብሎ ነገረህ ?” አሉ ባላምባራስ ፣ እንደ መደራት ብለው ። ጥላሁንና ሰፊያም ደንግጠው ከግራዝማች አፍ ቀጥሎም ምን እንደሚወጣ ለማየት ፣ ዝም ብለው አፋቸውን ይመለከቱ ጀመር።

“እ ? የለም ፣ ቱፒኮ ነው የነበር ፣ የኒ. አደለም ። ስለዚህ . . . ‘ሰማሁ’ ነው እንጂ ‘አየሁ’ አላለም ።”

“አዎ ! ያ . . . ከፉ አውሬ ከመገደሉ ብዙ አይሁን እንጂ መቅደምስ ቀድሜ ነው የሄድሁ ። ለመሆኑ መገደሉ እዚህ መቼ ተሰማ ?”

“ወዲያው ነው ፤ በማግስቱ ይሁን ቢበዛ በሳልስቱ ሰማን ።”

“በማግስቱ . . . እንዴት ሊሆን ይችላል ?”

“እንጃ ፤ ፖሊሶች ይሁኑ ፣ ወይም ሌሎች በራዲዮ ላዲስ አበባ አስታውቀው ነው አሉ . . . እዚህ በበቃ የቡና ልማት ያላቸው ፈረንጆች ፣ ‘ካዲስ አበባ ተላለፈልን’ ብለው ለሰራተኞች አውርተው ፣ እዚያ የሚመላለሱ ሰራተኞች ሲመጡ ፣ ባንድ ጊዜ ለከተማው ነዙት።”

@OLDBOOKSPDF

"ግዳየኝኸስ ታውቀው ይሆን ? እኔማን ናቸው ይባላል ?"

"እንደኛ" አሉና ግራዝማች ጉርሚስ ፣ ሲናገሩ ያለቡትን በመናገ ራቸው በራች ኩኮ ብለው ሳቁ ።

"ምን አሳቀህ ?" አሉ ባላምባራስ ፣ ምንም እንኳ ቢደነግጡ ግራዝማችን ተከትለው እየሳቁ ። ጥላሁንና ሶፊያ በጣም ፈርተው ከግ ራዝማች አፍ ቀጥሎ ምን እንደሚወጣ ለማየት አይናቸውን ሳያረግቡ ይጠብቁ ነበር ።

"እንደኛ ፤ ገደለ የተባለ የምሽቱ ባል ነው !" አሉ ግራዝማች አሁንም እዩሳቁ ።

"እንዴ ! ምን ማለትህ ነው ? የምሽቱ ባልማ እሱ አይደለም !"

"ያሳቀኝም ይኸው ነው ! እሱ "ምሽቱ ናት" ያላል ! እሱዋ ግን "ባሌ ነው" የምትለው አሁን ገደለ የተባለውን ፣ የድሮ ባልዋን ነው ፤ ታዲያ ሁለቱ የሚሉትን ስታማናኘው አሁን እንዳልሁት ያለ ፣ የሚያስቅ ነገር ይሆናል !"

"እ . . . ! የበፊና የድሮ ባልዋ ፣ የሀጋዊ ባልዋ ነገር እንኳዋ እጅግ የሚያሳዝን እንጂ የሚያስቅ አልነበረም ፤ ብቻ አንተ ባነጋገር የሚያስቅ አደረግኸው ። እ . . . ሺ ! እስቲ አሁን እናቆይና 'እንደኛ ገደለ የሚባለው የምሽቱ የድሮ ባል ነው' አልህ ፤ ሌላስ . . . ገዳይ የሚባል አለ ?"

"ሌላው ፣ ገደለ ተብሎ የተወራበት ፣ የቃልኛ ንጉስ የሚሉት ሰው ነው ። ታዲያ የሱ እንኳዋ እንዲያው ቀኛዝማች ዳኘ ሲናዘዙ፣ 'ገዳዩ ጥላሁን ፈይሳ ነው' በማለቱና ፣ የሁለቱ ተጠርጣሪዎች ስም አንድ በመሆኑ ስጋት ፤ ወዲያው ቦሊሶች ሌሊት ሄደው ቤቱን መክ በባቸው ፣ የስጋቡት ምክናያት ትክክለኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ መስሎ ታይቶት ሸሽ እንጂ ፣ በውነት ገዳዩ የሴትዮዋ የድሮ ባል ፣ 'ያ . . . ሊስተማሪው ፣ ጥላሁን ፈይሳ መሆኑ አይጠረጠርም ነው የሚባለው።' ምክናያቱም ፤ እንደኛ ቀኛዝማች ንቆት ከቁምነገር አይጥፈው እንጂ ያ ሰው እሱን ለመግደል መሸፈቱና ቀኛዝማች የሚወጣ የሚገባበትን ጊዜም ፣ መንገድም ፣ ደህና አድርጎ አጥንቶ ፣ ሁልጊዜ ከተማ ውስጥ አዩገባ ፣ በጠላቱ ላይ ምላጩን ለመሳብ እማንጣጠሪያው ውስጥ እስኪ ገባለት ብቻ ሲጠብቅ የሚያድር መሆኑን ሰው ሁሉ ያውቃል ። ሁለ ተኛ ፣ ቀኛዝማች በተገደለበት ሌሊት ፣ ገና ነፍሱ ሳትወጣ ፣ ሴትዮዋ እዚያ አለመገኘትዋ ፣ ያው የድሮ ባልዋ ቀኛዝማችን በሽጉጥ ደብ

@OLDBOOKSPDF

ድቦ ሲወድቅለት 'ግጂልሁት' ብሎ ፣ እሰዋን ይዞዋት የሄደ መሆኑን የሚያሳይ ነው ።"

"አሁን ያልኸው ሁሉ ፣ እ ... " አሉ ባላምባራስ ፣ እውነቱና እሰቱን እውነት ማስመሰሉ በውስጣቸው ተጣልተው ሲሙዋገቱ ፣ አገኑ ህሊናቸው እንሱን ሲያዳምጥ ፣ ሊናገሩ የፈለጉት ጠፍቶዋቸው እየፈለጉ ። "አሁን ያልኸው ሁሉ እ ... መቸም ... 'እውነት ነው' ተብሎ ሊግልበት ባይቻልም ፣ እውነት ይመስላል ። በነገርህ ላይ ፣ ጊሜ የተወራውም ልክ አሁን አንተ እንደ ነገርኸን ነው ። እኛ ጊሜ ከሰማነው እዚህ 'ተወራ' ያልኸው ትንሽ የሚለየው ... 'ባሊ ሶች ሌሊት ሄደው የቃልኞችን ንጉስ ቤት ከበውት አድረው ነበር' ያልኸው ነው ። ባሊሶች ከበውት ማደራቸው እዚያ አልተወራም ። ለመሆኑ ከተከበበ እንዴት ሊያመልጥ ቻለ ?"

"እሱ መቸም ... ያንለት 'አደረግ' የሚባለው ሁሉ ታምር ነገር ነው።"

"እንዴት ? ምን አደረግ ይባላል ?"

"ቀደም ብሎ ከቀኛዝማች ላኘ ጋር ተጣሉቶ ኖሮ ፣ ቀኛዝማችን ባደባባይ መሀል ከፉኛ በላዋረደ ፣ ያም እንኩዋንስ እንዲያ ያለ ምክናያት አግኝቶ እንዲያውም ሰው ማሲታየት ይቀናቸል ፣ በግሬሙቅ አስሮ ፣ የታሰረበትን ቤት ዘበኞች ከብበው በጥብቅ እንዲጠብቁ አድርጎ ባለ... ሌሊቱን በሱ ላይ ያ አደጋ ሲደርስ ፣ እኒያው ቤቱን ዘግተውና ከብ በው ይጠብቁ የነበሩ ዘበኞች በሩን ከውጭ ከፍተው ቢገቡ ፣ ታስሮበት የነበረውን እግሬሙቅ፣ብትዋትዋቸር እንደ ተቆለፈ ከግሩ እንደ ሰሩ እውልቆ እዚያው ቁጭ አርጎላቸው ፣ እሱ ... በየት ፣ እንዴት አርጎ እንደ ሄደ እግዜር ይወቀው ብቻ ሂዶዋል ! ወዲያው እኒያ የቀኛዝማች ዘበ ኞች ባሊስ ጨምረው ፣ የመላሪያ ሀይሉቸውን አጠንክረው ፣ ወደ ቤቱ ተከታትለው ሄደው በጉዋሮ በኩል አጥር ሰርስረው ገብተው ዘበኛውንም ፣ ሌሎችን አሽከሮችም ከንቅልፋቸው እየቀሰቀሱ ቢጠይ ቁዋቸው ፣ ጌታቸው ታስሮ እንደተገኘ ግቢ መሆኑንና ፣ እመቤቲቱ እቤት ውስጥ መኖኛትዋን አረጋግጠው ስለ ነገሩዋቸው ፣ 'ሳያዩት ሾልኮ ባይገባ አይቀርም' ብለው አመኑ ። ስለዚህ ፣ እንደ ገመቱት አሽከሮች ሳያዩት ሾልኮ ገብቶ እንደሆነ መቸም የተመኙት ይሀኑ በመ ሆኑ ፣ ለጊዜው ባይገባ እንኩዋ ምሽቱ እዚያ እስካለች ድረስ ፣ እሰዋን ሲል መምጣቱ ስለማይቀር ፣ ምንም ቢሆን እንደማያመልጣቸው እርግ ጠኞች ስለሆኑ ፣ ቤቱን ከብበው ሊጠብቁ አደሩ ። ከዚያ እንጋት ላይ

@OLDBOOKSPDF

ቃሉብ ቢከፍቱ ምንም መልስ ሲያጡ ጊዜ ፣ የቤቱን እሽከሮች በግን ባር አስቀድመው ቢገቡ እዚያም ባዶ ቤት አገኙ ! የቤቱ በርም ፣ መስኮቶችም ሁሉ እንደ ተዘጉ አያሉ ፣ ባለቤቶቹ ከውስጥ የውሀ ሽታ ሆኑ ፤ ታዲያ ይህ ታምር አይለም ? ” አሉ ግራዝማች ፣ ባላምባራስንም ፣ ቀኛሁንና ሰፍያንም ባይናቸው እዞረው ገርፈው ።

“በጉዋጉንቸር የተቆለፈ እግሬ-ሙቅ እንደ ሱሪ አውልቆ አስቀ ምጦ ፣ በሩና መስኮቶቹ ከተዘጋ ቤት . . . እንደ ጢስ በንኖ ጢፋ ማለት ፣ እውነትነቱ ያጠራጥር እንደሆነ እንጂ ፣ እውነት ከሆነማ ፣ እሱ ታምር ካልተባለ ምን ሊባል ይችላል ? ” አሉ ባላምባራስ ፣ ፈገግ እን ዲማለት ብለው ። ቀኛሁንና ሰፈያን ወረወም ፣ የባላምባራስ እሽሙርም በጣም አሳቋቋቸው ።

“እኔ መችም እዚህ የተወራውን ነገርሁዋችሁ እንጂ ፣ የተወራው እውነት ነው ፣ ወይም እሰት ነው ፣ አላልሁዎት ! ይህን ለማለት እዚያ መሄድ ያስፈልጋል ። እኔ ግን ሄጄ አላዩሁም ! ” አሉ ግራዝማች ፣ ያጠሩትን ወደ ባላምባራስም ፣ እንግዶችም ፣ “እውነት ነው” ብለው እንዳልተቀበሉዋቸው ከፊታቸውና ከጠቅላላ ሁኔታዎች ሊመለከቱ ፣ ወሬያቸው በሰሚዎች ዘንድ የፈለጉትን ውጤት ባይሰጥ ሲቀር ፣ የፍ ሬት ስሜት እንደሚሰማቸው ሰዎች ሁሉ ፣ እሳቸውም ትንሽ እንደማ ፈር ብለው ።

“መችም . . . ” አሉ ከዚያ ቀጠሉና ። “መችም ሰውዬውና ምሽቱ ‘የቃልቾች ነገስታት’ ይባሉ የነበረ ፣ የሚሰሩት ታምር በዚያ አካባቢ የሚኖሩት ቃልቾች ሁሉ ሊሰሩት የማይችሉ መሆኑን ፣ ቃል ቾች ራሳቸው ምስክሮች ሆነው ፣ ለነሱ በገሀድ ታጥቀው መስገዳቸ ውና ፣ እነሱን ‘እድኑን’ እያሉ በመለማመናቸው ነው” ተብሎ ይነገ ራል ። እንግዲህ ይህ የሚነገረው ፣ ይህ . . . ከቃልቾች ሁሉ የበ ለጠ ታምር መስራታቸው እውነት ከሆነ ፣ አሁን ሰውዬው አደረገ የተባለውን ቢያደርግ ያስገርማል ? አያስገርምምኮ ፤ ይህ እንዲያውም ትንሽ ነው ! እንዲያውስ . . . የነሱን ፣ የቃልቾችን ነገስታት ስራማ ከኔ ይልቅ አንተ ታውቅ የል ? እንዲያውም በተለይ ላንተ ፣ ‘በጣም ወዳጆችህ ነበሩ’ እየተባለ ደምቆ ይወራ ነበርኮ ። እንደ ለማሁት ከሆ ነማ ከመዋደዳችሁ የተነሳ ፣ ‘አንተን ሳያማክሩ የሚሰሩት አንድ ነገር አልነበረም ፤ እንደ ንስሀ አባት አማኝ ፣ ናዛዣቸው አንተ ነበርህ’ ነው የሚባለው ። ሀ ! ደግነቱ ፣ ቀኛዝማች ዳኘ ሲገደሉና ሰዎቹ ሲሸሹ

@OLDBOOKSPDF

እዚያ እለመኖርህ በጀህ እንጂ ፣ መጀመሪያ የመጥፎታቸው ወሬ ሲሰማ አንተ ነበርህ . . . 'ሽሽግህቸው' ተብለህ ትያዝ የነበረ ! ” አሉ ግራ ዝማች ፣ መጀመሪያ ባላምባራስን ፤ ከዚያ ጥላሁንንና ሶፊያን በተራ በረቅ አድርገው ፤ የነድን እዬተመለከቱ ።

ያንጊዜ ጥላሁንና ሶፊያ ደንግጠዉ ፣ ልባቸው ለሀዋሳታቸው ደም ማስራጨቱን ያቶው ይመስል ሁለመናቸው ደነዘዘ ! ባላምባራስም ለጊዜው መደንገጣቸው አልቀረም ። ሁዋላ ብቻ ቶሎ አለምሮዋቸውን ገዙተው ፤

"እኔን ባያማክሩ የሚለሩት አለመኖሩና" የኔ . . . "እንደ ንስሀ አባት አባኘ ፣ ናዛኘ መሆን" እንኩዋ እንዲያው . . . መሳ ነው ፣ ብቻ ወዳጆች መሆናችን እውነት ነው ። ለዚያ አገር ህዝብ ፣ ለዚያ ቀኛዝማች ዳኘ ሌጣ ፣ ግጣ ለበላው ፤ ለድሀው የየኪ ህዝብ ፣ በን አድራጊዎች ለሰነበሩ ፣ በጣም እወዳቸው ነበር ! ” አሉ ባላምባራስ ፣ ግራ ዝማችንም ፣ እንግዶቻቸውንም ቀና ብለው ሳያዩ ፣ እንገታቸውን እንደ ደፉ መሬቱን በግራቸው እውራ ጣት እዬቆረቆሩ ።

"ለየኪ በን አድራጊዎች እንደ ነበሩስ ሰው ሁሉ አውግቶ ያበቃው ነው ! ለየኪ ቀን አውጥተውለት ነበር ። ብቻ አሁን እንደገና ተመልሶ ወደ ጨለማው መግባቱ ነው ! መቸም 'ወሬ ከተነሳበት በራቀ ቁጥር በማነስ ፈንታ እያደገ—ይጀዳል 'እንደሚሉት ወሬው ምን ያክል አድጎ እዚህ እንደ ደረሰ አላውቅም እንጂ ፣ እዚህ እንደሚወራውማ እንኩዋንስ . . . ባምስት አመት በሃያና በሰላሳ አመትም እንዲያ ያለ ስራ" ብለው ግራዝማች የጀመሩትን ሳይጨርሱ ፣ "ሶስት አመት ብቻ ነበር እዚያ የቆዩ " አሉ ባላምባራስ ፣ አንገታቸውን እንደ ደፉ አቋርጠው ።

"እንዲያውም ሶስት ነው ? ይገርማል ! በሶስት አመት ! እንኩዋንስ በሶስት አመት በሀያና በሰላሳ አመት ፣ እንዲያ ያለ ስራ ፣ ማንም ሊሰራ እንደማይችል ሆኖ ነው የሚነገረው ! 'ልጅ እዋቂውን ትምርት ከማስተማራቸውና እንደ አዲስ ጠበል እደጃቸው የደረሰውን በሽተኛ ሁሉ ከማናቸውም በሽታ ከመፈወሳቸው ሌላ ፣ ራቡን ፣ ቸነፈሩን ፤ ችግሩን ፤ ሽረ እንዲያው . . . በጠቅላላው ከቀኛዝማች ዳኘ በቀር ከፋውን ነገር ሁሉ ፣ ከሱ በቀር እንዲያው . . . የሰው ጠር የሆነውን ነገር ሁሉ ከየኪ ገጸ ምድር አጥፍተው ፣ የኪን ምድረገነት አደረጉዋት !' እዬተባለ ሲነገር ፣ ተረት እንጂ እውነት አይመስልም

@OLDBOOKSPDF

ነበርኩ ! መቸም የየኪ ወሬ ሲወራ 'መቸ መንግስት ያለዚያም እግዚሀር ያን ክፉ ሰው ከዚያ ባነሳውና ርስቴን ሽጬ የኪ መሬት ገዝቼ እዚያ በገባሁ !' ብሎ የማይመኝ አልነበረም ። እኔ እንኩዋ ... እግዚሀር ይመስገን እዚህ በመምጣቴ የጎደለብኝ ነገር የለም ፤ እንዲያውም ትን ደውኑቱ ከሆነ ፡ እዚያ ከነበረኝ የተሻለ ኑሮ ነው ያለኝ ... ታዲያ እኔ እንኩዋ ፤ ወደዚያው ለመመለስ ምኞት ነበረኝ ። ብቻ ምን ይሆናል ምኞት ብቻ ሆና ቀረ !" አሉና ግራዝማች ፡ እንገታቸውን ደፍተው ከተቀመጡት ከባላምባራስ ጉዶታም ፤ ከጥላሁንና ከሰፊያም ፤ መልስ ቢጠብቁ ምንም ስላልመጣ ፡ "እኔ የሚመስለኝን ልንገርህ !" አሉ ፡ እንገታቸውን ደፍተው ባያዩዋቸውም ፤ አይናቻቸውን በባላምባራስ ጉዶታ ላይ ተክለው ። "እኔ ርቀው ይሄዳሉ አልልም ። እንዲሁ እዚህ ለዚህ ሲዘዋወሩ ቆይተው ፤ መቸም ... የውነተኛው ገዳይ መያዙ አይቀርም ፤ ያንጊዜ ከ ... ተደበቁበት ብቅ ይላሉ ። አይመስልህም ?"

"እም ... !" አሉ እንኩዋ እንጃ ፤ እስካሁን ሳይሄዱ የሚቀሩ አይመስለኝም አሉ ባላምባራስ ።

"ወዴት ?"

"ወዴት እንደሚሄዱ አላውቅም ፤ ብቻ እስካሁን በየኪ ዙሪያ የሚቆዩ አይመስለኝም ፤ ይፈራሉ ።"

"እኒህ ሰውዬ ማንነታችንን በርግጥ ባያውቁ ሳይጠረጥሩ የቀሩ አይመስለኝም" አለ ጥላሁን ፡ እሱና ምሽቱ ሌሊት እንደ ተኙ ሲያወሩ።

"ለኔም ካነጋገራቸውም ሆነ ካስተያየታቸው ፤ ልክ አንተ እንዳል ከው ... በርግጥ ባያውቁ እንኩዋ የጠረጠሩ መስሎ ነው የተሰማኝ" አለችና ሰፊያ ትንሽ ስታስብ ቆይታ ፡ "ለመሆኑ ቢያውቁ ምን ያደ ርጉናል ? ያስይዙን ይሆን ?" አለች ።

"አይ ... እንጃ ! እሳቸው እንኩዋ እንዲህ ያለውን አያደርጉ ትም ፤ በጣም እንደሚያምኑዋቸው ባላምባራስ ነግረውናል ። የሚያስ ጋው ፤ ይብዛ ይነስ ወዳጅ የሌለው ሰው የለምና ፤ የሚያውቁትን ምስ ጢር ለወዳጆቻቸው የተነፈሱ እንደሆነ ፡ ማንም ቢሆን አንድ ጊዜ በተነፈሰው ነገር ላይ ስልጣን ስለሌለው ፤ የተተነፈሰው ሊሰፋፋ የሚ ችል መሆኑ ነው !"

"እውነት ነው ። ታዲያ ለዚህ ምን ይበጃል ?"

"ከዚህ ቶሎ መሄድ ነው የሚበጀው ፤ ለባላምባራስ እንነግራቸ ውና ከዚህ ቶሎ የምንሄድበትን ዘዴ ቢፈጥሩልን ነው የሚበጀው ።"

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፴፱

## መንጀር ቤሌ

ሶፊያና ጥላሁን ከበላምባራስ ጉዶታ ጋር ብቻቸውን እስኪሆኑ ጠብቀው ፤ ግራዝማች ገርሚስ ባነጋገራቸው ፤ ባስተያየታቸውና በሁኔታቸው ሁሉ ፤ ስለእነሱ ማንነት በርግጥ "አውቀዋል" ለማለት ባይችሉም የጠረጠሩ ስለ መሰላቸው ፤ መስጋታቸውንና ከሚዜን ተፈሪ ቶሎ መሄዱ የሚሻል መሆኑን ነገሩዋቸው ።

" ቶሎ ብትሄዱ መልካም መሆኑን እኔም አምናለሁ ። እንዲያውም እዚህ ብቻ ሳይሆን ፤ መጨረሻ ወደምትኖሩበት እስክትደርሱ ድረስ ፤ በጉዞዋችሁ መሀከል ... በምታርፉባቸው ቦታዎች ሁሉ ፤ ብዙ አለመቆየት ነው።በተረፈ ... 'ግራዝማች ገርሚስ በለኛ ማንነት የጠረጠሩ መሰለን ' ባላችሁት ፤ በመሰረቱ መስጋት ጥንቃቄን ስለሚያስከትል ተገቢ ቢሆንም ፤ አሁን በግራዝማች በኩል ግን . . . ግድለም አትስጉ ። እኔን 'አሰት ይነግረኛል' ብለው ስለማይጠረጥር ፤ እኔ የነገርሁትን ስለሚያምን አትስጉ ። የጎደን ሰርቆ በማየቱ እንደሆነ የጠረጠረ የመሰላችሁ፣ሰርቆ ማየት ከልጅነቱ ጀምሮ አብሮት የኖረ ልማዱ ነው ። በልጅነቱ ጉዋደኞቹ 'አይን ሌባ' እያሉ ሲቀልዱበት እንደ ተማሳና እንደ ተደባደበ ፤ እንዲያ እያሉ የሚቀልዱበት ትልልቆች የሆኑ እንደ ሆነ ፤ እንዳለቀሰ ነበር የሚኖር!" አሉ ባላምባራስ ፤ ግራዝማች በልጅነታቸው " አይን ሌባ" ሲሉዋቸው የሚሆኑት ሁኔታ ትዝ ስላላቸው እንደ መሳቅ ብለው ።

"አይን ሌባ" ማለት ምን ማለት ነው? "መጥፎ ነው?" አለች ሶፊያ።

'አይንሌባ' ማለት ሰርቆ የሚያይ ማለት ነው ፤ በድሮ ልማድ "ወንድ ፊት ለፊት እንጂ ፤ ሰርቆ አያይም" ይባል ነበር። ታዲያ፣ "ለወንድ ሰርቆ ማየት ነውር ስለሆነና ፤ ሰርቃ የምታይ ሴት ስለሆነች ፤ በረኛም ትርጉሙ 'አይን ሌባ' ማለት 'ሴት' ማለት ነው" ሲሉ ባላምባራስ እዬሳቁ፤ ሶፊያና ጥላሁንም አብረዋቸው ይስቁ ጀመር ።

"አሁን " አሉ ባላምባራስ ፤ ከሳቁ በሁዋላ ። "አሁን ወደ ቁም ነገሩ እንመለስና ፤ እዚህ ብዙ ጊዜ መቆዬታችሁን እኔም ስለማልወደው፣ ቶሎ እንዲሰዳችሁ ለግራዝማች ነግሬው ፤ ለካስ . . . እኔ ረስቼው

ነው እንጂ ከፋ ቅርብ ዘመዶችን መኖሩንና ፥ እዚያ ከአደረሳችሁ . . . ከዚያ ወደምትሄዱበት አገር እሱ ደህና አድርጎ ሲሸኛችሁ እንደሚችል ነግሮኛል ። አሁንም በቅሎ አከራይቶ እዚያ የሚያደርስ ፥ የታመነ ነጋዴ ቢገኝ ሲፈልግ ነው የሄደ ። ካላገኘም . . . ያው ፥ ዘመዶችን በቅሎች ጨምሮ ሰዎች እንዲልክልን እናደርጋለን ። ”

“ታዲያ . . እውነትም አገር ጎብኚዎች እንደሆንን ሁሉ በነጋዴዎች ዘንድ በገሀድ የበቅሎ ከራይ ማሟረታችን ‘እነማን ናቸው’ የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ አይመስልዎትም ? ” አለ ጥላሁን ፥ ከምሽቱ ጋር የሲጋት አይን ከተለዋወጡ በሁዋላ ።

“ ሴላ ዘዴ ስላልታዩኝ ፥ ከመደበቁ መገናኘት ጥርጥር የማይጋብዝ መስሎኝ ነው እንጂ ፥ ከነጋዴዎች መሀከል ንቡት ‘ በቅሎ አከራዩን ፥ እጃቢ ጨምሩልን’ ማለቱ እውነትም ‘እነማን ናቸው ?’ የሚል ጥያቄ ያስነሳል ያልኸው . . . ልክ ነው ፤ ሊያስነሳ ይችላል ” አሉና ባላምባራስ ፥ ቀጥ ለው ሲናገሩት ያሰቡት ስለመሰቸው፥ሁልጊዜ እንዲህ ያለ ነገር ሲገጥማቸው እንደሚያደርጉት ፥ አይኖቻቸውን ወዲያ ወዲህ እያርገበገቡ እንጠው ትንሽ ቆይተው ፥ “እ. . ! አዎ ! ልነግራችሁ ያሰብሁት እፈ ከደረስ በሁዋላ ጠፍቶኝኮ ነው! ትናንት ማታ ፥ እናንተ ወደ ምኝታችሁ ከሄዳችሁ በሁዋላ ግራዝማች፥ አገር ለማየት ብለው ይህን ያክል መንገድ ተጉዘው እዚህ ከደረሱ በሁዋላ ፥ ‘በበቃን’ ሳያዩ ቢሄዱ ድካማቸው ሁሉ ከንቱና አላማ የለሽ ይሆናል ፤ እንኩዋንስ አግሩ መንገዳቸውን ፥ እሱን ብቻ ለመጎብኘት ከሩቅ የሚመጡለት በስሆነ ፥ በግድ ሄደው ማየት አለባቸው ” ብሎ ወጥሮ ይዞኝ ፥ “ስራ የሚገቡበት ጊዜ ስለ ደረሰ ፥ በጣም የሚቸኩሉ መሆናቸውን ነግረውኛል አልሁት ። የ‘በበቃን’ ወሬ መቸም ሳትሰሙት የቀራችሁ አይመስለኝም ፤ ፈረንጆች ቡናና ሌላ ፥ ልዩ ልዩ ሐትክልት የሚያለሙበት ፥ እውነትም እንዲያው ለትንግርት የሚታይ ነው! ብቻ ብዙ ተዘዋዋሪ ሠራተኞች ስላሉበት ፥ እንዲያ ከሚገዋወሩት ሰራተኞች መሀከል ወደ የኪ ደርሰው ምናልባት እናንተን ያዩና የሚያውቁ የተገኙ እንደ ሆነ ፥ ችግር እንዳይፈጠር ብዬ ነበር . . . ‘ ቸኩለዋል ’ ብዬ መንገድ የዘጋሁበት ። ”

“በጣም ጥሩ አድርገዋል እንጂ አባባ ፤እንዲያውም በቅርቡ አንድ እያቸው የማላውቅ ፥ እንግዳ የቀን ሰራተኛ እኛ ዘንድ መጥቶ ሲሰራ ወባው ተነስቶበት ፥ መድሀኒት ልሰጠው ሄጄ የመጣበትን ብጠይቀው ‘ከበበቃ እዚህ ዘመድ ልጠይቅ መጥቼ ነው ፤ አሁን ወደዚያው እመለሳለሁ ?’ ብሎኝ ነበር ” አለች ሶፊያ ።

@OLDBOOKSPDF

"እዎ ! የ 'በበቃውንስ' እንደ ምንም አሰቀርቸው ነበር ፤ ደግሞ '. . . መንጀር ቦሴን' አመጣብኝ እንጂ ! 'መንጀር ቦሴ በጣም ቅርብ ስለ ሆነና ፣ ባንድ ፣ ቢበዛ በሁለት ሰአት ውስጥ አይተውት ሊመለሱ ስለሚችሉ ፣ ወደ ከፋ የሚወስዳቸው ሰው እስኪያገኙ አንድ ቀን መዋ ላቸው ያልቀረ እንደሆን ፣ እሱን እንኳ አይተውት ይሂዱ' ሲለኝ ጊዜ . . .የምመልስለት በቅርብ ስላጣሁና ፣ የምንሸሽ እንዳንመስለው ብዬ 'እነግራቸዋለሁ' አልሁት ። መቸም እሱ እናንተን ደስ አሰኝቶ ለመስደድ ካለው ጽኑ ፍላጎት የተነሳ ነው እንጂ ፣ ሌላ ምክንያት ያለ አይምስላ ችሁ "አሉ ባምባራስ ጉደታ።

"እግዚአብሔር ይስጥልን ፣ በጣም ነው የምናመሰግናችሁ ። ለመ ሆኑ 'መንጀር ቦሴ' ደግሞ ምንድነው ፣ አባባ? " አለ ጥላሁን ።

"መንጀር ቦሴም . . . " አሉ ባላምባራስ ፣ እንደ መሳቅ ብለውና "መቸም እኔ አላውቅም ፤ ነገር ግን ግራዝማች እንደሚጠሩኝ ፣ መን ጀር ቦሴም እንደ ያገራችን ሰው ያለማው ቡና ነው። ሰውዬው 'በቢቃ' ከፈረንጆች የስራ ልምድ አግኝቶ እዚህ ሲሰራም ፣ የስራተኞች አለቃ ሆኖ እያሰራም ፣ ከቀኑ በሁዋላ ፣ እዚያ በኛ ፣ በኢሊባቦር ክፍለ እንደ ጊዜ ፣ ለድሆች ሲባል ፣ "የመንግስት ጋሻ መሬት ባምስት ብር ይሸጥ" ተብሎ፡ እንደ ተሸጠና . . . በድህ ሰም በንብረት ሀብታም በሁለቱ ላይ ሀብት ደርቦ እንዳሸከመው ሁሉ ፣ በዚህ በከፋ ጠቅላይ ግዛትም ፣ ጋሻ መሬት በሰላሳ ብር እንዲሸጥ ታዞ ስለ ነበረ ፣ በዚያ ጊዜ እዚህ ከተማ ዳር አምስት ጋሻ መሬት በመቶ አምሳ ብር ገዝቶ ፣ ሁሉንም ልክ ከፈረ ንጆች በተማረው አይነት ፣ በቁመትም ፣ በወርዱም ፣ ሶስት ሜትር እያራ ራቀ ግጥም አድርጎ ተክለው ። ታዲያ ፣ የተተከለው ሁሉ አንድ ሳይቀር ጸድቆ ካደገ በሁዋላ ፣ በተራ ቀስድሮ ላይን እስኪረቅ ፣ እስከ ወዲያ . . . ድረስ ሲመለከቱት ፣ ማህሌቅት የሌለው ፣ የጠቃደር ስለፊኛ እንጂ . . . ሌላ አይመስልም ነበር አሉ " አሉ ባላምባራስ ፣ "እስከ ወዲያ " ሲሉ ወዲያ የሰልፉን መጨረሻ ለማየት እንደሚጣጣሩ ሁሉ አይኖቻቸውን ጥንቁር ፣ ረዥም ክንዳቸውን ቅብር አድርገው ። ሶፊያና ጥላሁን ሁኔታ ቸውን አይተው ይስቁ ጀመር ።

" ነገር ግን " አሉ ባላምባራስ ፣ ቀጥለው ። " ነገር ግን ፣ እስከዚህ ድረስ ሁሉ ለልማቱ ገና ስም አልወጣለትም ነበር ። ስም ያወጡለት ፣ ሁዋላ መጥተው እዚያ የተቀጠሩ ሠራተኛ ናቸው ። "

እኒያ ሰው በወጣትነታቸው ፣ ጠባት አገራችንን ከመውረሩ በፊት አንድ 'መንጀር ቦሴ' የሚባል ፈረንጅ 'ክብር ዘበኛ' ይባል የነበረውን የጃንሆይ ምርጥ ጦር እየመለመለ ሲያስረግጥ ፣ እሳቸው መልከ መልካም

@OLDBOOKSPDF

ስለነበሩ ፣ እዚያ ውስጥ ተመልሶ የገባው ይረግጡ ኖረዋል ። ታዲያ ፣ ከተወለዱ . . .'ከመንጀር ቦሌ' ወታደር በቀር እንዲያ አድርጎ በልፍ የሚያሳምር ምንም አይተው በለማያውቁ ፣ መጀመሪያ ምን ቡና ፣ እንዲያ ባይን እስኪያፍታከት በሰልፍ ተሰድሮ ሲያዩት ፣ ጥንት የክብር ዘበኛ ባሉ የሚያውቁትን ፣ የ'መንጀር ቦሌን' በልፈኛ ትዝታ እምጥቶ እሳያቸውና ፣ "እ. . ! ይህ የመንጀር ቦሌ በልፈኛ እንጂ-የቡና እትክልት አይባልም ! ለላሉ ፣ ስሙ 'መንጀር ቦሌ' ተብሎ ቀረ ይባላል " አሉ ባላምባራስ ፊታቸው በፈገግታ እንደ በራ ስፈያንና ጥላሁንን እያለዋወጡ እያዩ።

" እኸ . . ! ከጣሊያን ወረራ በፊት 'የክብር ዘበኛ' ይባል የነበረውን ዘመናዊ የጦር ሠራዊት ያሰለጥኑ ከነበሩት በልጅኮች አንዱ ! እሰቅዬው ይሁን ፣ ወይም እንዲያው . . . ስሙ የታወቀው 'ሜጀር ፖሊ' ይባል ነበር ሲሉ እሰም ሰምቻለሁ ! ታዲያ 'ሜጀር ፖሊን' መሆኑ ነው. . . 'መንጀር ቦሌ' ያሉት !"አለና ጥላሁን ሲስቅ ስፈያም አብሬው ትስቅ ጀመር ።

"ታዲያ እንግዲህ ምን ማድረግ ይሻላል ?"አሉ ባላምባራስ ፣ እሳቸውም ጥላሁንና ከስፈያ ጋር ስለ "መንጀር ቦሌ" ራሳቸው ባወሩት ሲስቁ ቆይተው ። "ግራዝማች ሳይመለስ የምናደርገውን እንወስን ። መቸም ነገ ጥዋት ይመጣሉ የሚንሳ ነጋዴ ከተገኘ 'ጉዞዎችሁን ትታችሁ እታክልት ትብኙ' የሚሉችሁ የለ ! ነገር ግን ሰው ሳይገኝ ቀርቶ ነገ እዚህ ውላችሁ የምታድሩ ከሆናችሁ ፣ ግራዝማች . . . 'መንጀር ቦሊን' ሳስንብቸው 'ማለቱ አይቀርምና ፣ በምንሰጠው መልስ አሁን እንስማማ ። 'እሺ' ብለን እንሂድ ፣ ያለዚያም 'እንሄዳለም' የምንልበትን መላ እሁኑኑ እናብጅ ። "

" እኔ ቅድም እርስዎ እንዳሉት የምንሸሽ እንዳንመስልና ፣ ግራዝማችን ወደ ጥርጥር እንዳንመራቸው ፣ 'ወሰጁ ሳስንብቸው ካሉን እንሄድ' ነው የምል ። የኪ እንደም ይሁን ሁለት ቀን ያዩኝ ሰው አሁን ከዚህ የደላስ ጤማና የ. . . መኩዋንንት ባርኔጣዎ ጋር ሲያዩኝ 'እሱ ይሆናል' ብሎ እንዳይጠረጥር እርግጠኛ ነኝ ። እንቺም በዝች እለተላሰፍም ፣ በምንም መልክሽን ትንሽ ለወጥ እድርጊ " አለ ጥላሁን ፣ ቆም ነገሩን በቀልድ እሰባብሮ ። ስፈያ ደስ አላላትም ። ቢሆንም ፣ ሰው ተገኝቶ በማግስቱ ጥዋት ወደ ከፋ የማይኑሉ ከሆነና ፣ ግራዝማች ጉርሜሳ "መንጀር ቦሊን" እንዲጎበኙ ከጠየቁዋቸው ለመጎብኘት ተስማሙ ።

"ይገርማ. . ል ! ሲራሩ ነጋዴ ከሚባለው ሁሉ እንዲያው አንድ ለምልክት ያክል በከተማው አይገኝም ? አንድ የለም ! ሁሉም ትናንት ጥዋት ነው አሉ ጥርግ ብሎ ወደ ጅማ የሄደ ፣ ታረቀኝ መላኩና

@OLDBOOKSPDF

የሱፍ አብዱል ሰመድ እንኳ ፣ የክርፉ በቅሎዎቻቸው “የትግዚ በትን ሳይመልሱ መሞቻቸው መድረሱ ነው’ እያሉ ሲያለቅሱ የነበሩት አሁን እኛ ስለ ፈለግናቸው ነው መሰለኝ.. አጥተው የነበረውን ገበያ አግኝተው ፣ ‘ወይ ግፏ ጊጉ’ እሉኝ ። ደግሞ ይብሱን የሚገርመው የ... ሲራራ ነጋዴዎችም ፣ የታረቀችና የዱሉጭም በቅሎዎች መኛ እንደሚመለሱ ፍጹም የማይታወቅ መሆኑ ነው !” አሉ ግራዝማች ጉርሜሳ ፣ መንገደኞችን በኪራይ በቅሎዎች ክፉ የሚያደርሱ ሰዎች ፍሰጋ ውሰው አጥተው ሲመለሱ ።

“የኔን ድክም ካሳባችሁ አታግቡት ፣ የናንተ ጉዳይ ባይኖርም አቤት ተቀምጬ አልሁም ። የሚያሳዝነኝ እዚህ ... በቅሎ በመታጣቱ ተበናክላችሁ ፣ ሥራ ለምትገቡበት ጊዜ አለመድረሳችሁ ነው” አሉ ግራዝማች ቀጠሉና ፣ ጥላሁን በሱና በባቢቢቱ ምክንያት ያን ያክል በስደ ከሙ ይቅርታ ሲለምኑቸው ።

“ለመሆኑ እንዲህ ባለ ፣ አደጋና ለቀላ አቃዎች መቀባበያ ሆና መኪና ባልገባበት አገር ፣ በቅሎ የሚያከራዩ ሰዎች በብዛት አለመኖታቸው እንዴት ነው ?” አለ ጥላሁን ።

“የዚህ አገር ህዝብ ያው ... እንደ የኪና በዙሪያው እንዳለው ህዝብ ሁሉ ፣ እይንቱኛ ሀብቱ ቡና ስለ ሆነ ፣ እሱን እዬሸመጠ ፣ ወይም ያመቱን አባባ እዚያው በዛፉ ላይ እንዳለ ፣ በነሲብ ከከፋ አህል ፣ ወይም ከጅማና ከሌላም አገር ብር ፣ ይዞ ለሚመጣ ነጋዴ ፣ በርካሽ ከሸጠ በሁዋላ ፣ በሀብቱ እንደ አምራችም ፣ እንደ ሸማችም ሆኖ የሚጠቀምበት ያው ፣ ከውጭ የሚመጣው ነው” አሉ ግራዝማች ጉርሜሳ ፣ አንድ ጊዜ ባላምባራስ ጉዶታን ፣ ከዚያ ጥላሁንንና ሰፈያን ሰረቅ አድርገው የጎድን እያዩ ። “ስለዚህ” አሉ ቀጥለው ። “ስለዚህ ... ሀብቱ ለሚጣንበት ከብትም ሆነ ለሚጭነው ሰው የሚችንገርበት ፣ የሚያስብበት ፣ ያው ፣ ከውጭ መጥቶ የሀብቱ ባለቤት የሆነው ነው እንጂ ፣ ያገሩ ተወላጅ ለጊዜው ራቡን የሚከላበት ያክል እህልና በርዶ ፣ ወይም አረቄ የሚጠጣበት ትንሽ ገንዘብ ካገኘ ፣ ከዚያ ላለፈ ሀብት ግድለውም ። አሁን ለማቸውን እንደ ጠራሁት ፣ እንደ ታረቁኝ መላኩና የሱፍ አብዱል ሰመድ ያሉ ፣ ከሌላ ክፍል መጥተው እዚህ የሚኖሩ ሰዎች ፣ የንግዱን ከፍተኛነት እዬተመለከቱ በቅሎዎች ገዝተው ያስቀመጡ እንደሆነም ... የዚህን አገር ዝንብ እግዚር አይጣልባችሁ ... ደማቸውን ምጦጦ አድርጎ ወርሶ እንዲያው እንደ ተምዘዘ ዛፍ በቋመናቸው አድርቆ ፣ ከዕበትና ከራት ፣

@OLDBOOKSPDF

ቢበዛ ከሰደበት ወር የበለጠ ሳይቆዩ . . . ይገድሉቸዋል ! አንዳንድ ጊዜም . . . ባለቤቶች ራሳቸው ይገድሉዋቸዋል !" አሉ ግራዝማች ፣ ቋንቋ እንደ መሳቅ ብለው ።

" የገዛ ለቅሎዎቻቸውን ? እንዴት ? ለምን ? " አለ ጥላሁን ፣ በመገረም ።

" መቸም ሆነ ብለው አይገድሉዋቸውምኮ ፤ በቅሎዎቻቸው የተ ገዙበትን ዋጋ ከመመለሳቸው በፊት ዝንቡ ሳይገድልባቸው ፣ ጉልበታ ቸውን ለመጠቀም . . . እንዲዚህ ለምን ድንገት ግብያው ካለጠበ ቸው ፤ ቀንና ሌሊት እረፍት ሳይሰጡ ሲጭኑዋቸው ፤ ' በጭንቅ ብዛት . . . ይሞታሉ ' ማለቴ ነው ። የሆነ ሆኖ ፤ አሁን ለመናገር የፈለግሁት ፣ ከዝንብ ጋር አብሮ ተቀምጠው ፣ የከራይ በቅሎዎች የሚያስ ቀምጡ ቢኖሩ ፤ ከሌላ ክፍል የሚመጡ ሰዎች ናቸው ፤ የዚህ አገር ህዝብ ለጊዜው ራሱን ለሚያስቀምጠበትና ፤ ለሚጠማበት ያለል ቋንቋ ግንዘብ ካገኘ ፣ ከዚያ በላይ የሚፈልገው ምንም የሌለ መሆኑን ነው ። ያው . . . እንደ የኪና በዙሪያው እንዳለው ህዝብ ሁሉ ማለት ነው !" አሉ ግራዝማች ፣ እንደገና ፈገግ ብለው ባላምባራስ ጉደታንም ፣ ሰፈ ያንና ጥላሁንንም ሰረቅ አያደረጉ የጎድን እየተመለከቱ ።

" እ . . . ! ያው . . . እንደ የኪና በዙሪያው እንዳለው ህዝብ ሁሉ ' እናንተም እንደምታውቁት ' ማለታቸው ነውቅ !" ተባባሉ ጥላ ሁንና ሰፈያ ፣ በቃል ሳይሆን ፤ ከቃል ይልቅ የልብ ስጋቱንና ጠቅላላ ስሜትን ደህና አድርጎ በሚገልጽ አስተያየት ።

" እም እውነቱ ነው ። በየኪና በዙሪያው ያለው ህዝብ ሁሉ . . . እናንተ መቸም አታውቁትም እንጂ ፣ እኔ ባገሩ ተወልጄ እስካ ረጅ የኖርሁበት ስለሆነ ደህና አድርጌ አውቀዋለሁ . . . አሁን ወንድሜ እንዳለው ነው " አሉ ባላምባራስ ጉደታ ፤ የጥላሁንንና የሰፈያን ስጋት እበበላቸው ከተለዋወጡት ያስተያየት መግለጫ እንብ በው ስለተረዱ ። ግራዝማች ጉርሜሳ ፣ " ያው . . . እንደ የኪና በዙ ሪያው እንዳለው ህዝብ ሁሉ " ብለው የሚያውቁትን የኪን ምሳሌ አድርገው የጠቀሱላቸው ፣ ለሳቸው ፣ ለባላምባራስ እንጂ ለነሱ ፣ ለባ ልና ሚሽቱ አለመሆኑን በሚገልጽ ያነጋገርና ያስተያየት ስልት ። ብቻ ባልና ሚስቱ ፣ ሚዛን - ተፈሪ ከገቡ ጀምሮ ፣ የግራዝማች ጉር ሜሳ አነጋገርና አስተያየት ፣ እንዲያው በጠቅላላው የሚያደርጉት ሁሉ ፣ " እነማን መሆናችሁን የማላውቅ እንዳይመስላችሁ ! "

@OLDBOOKSPDF

የሚሊ መኪሎ በሰሚታየቸው ፣ ባለምባራስ ጉዴታ ፣ እንዳደሰጉና ራሳቸውን በክንቱ እንዳያስታዩ ደኃግመው የሰጠዋቸውን ምክር መቀበልና አሳባቸውን ማስረፍ አቃታቸው ።

በማግሥቱ እሁድ ፣ ግራዝማች ጉርሜሳና ባላምባራስ ጉዴታ ከቢ ቶክርስቲያን አስቀድሰው ተመልሰው ቁርስ እስኪያደርጉ ስለ ሬሳ ዶና ፣ ጸሀዩ ስለ ጠንከረ ፣ " መንጀር ቦሌ " የሚታይበት ጊዜ ከቀ ቶር በሁዋላ ፣ ጸሀዩ በረድ ሲል እንዲሆን ተስማምተው ወሰኑ ።

በተወሰነው ጊዜ ፣ ግራዝማች ጉርሜሳ ከንግዶቻቸው ጋር ከሀያ አምስት እስከ ሰላሳ ደቂቃ ያክል በግራቸው ተጉዘው ከከተማው ዳር ያለውን ሜዳ እንደ ወጡ ፣ ወዲንድ ኮረብታ ደርሰው ፣ ከዚያ ኮረብታ ወደታች ሲመለከቱ ፣ " መንጀር ቦሌ " በወርዱም ፣ በቁመቱም ተገ ባልሎ ታያቸው ። እውነትም የዚብር እንግዳ ለመቀበል በተጠንቀቅ ተሰልፎ የሚጠብቅ ሰልፈኛ እንጂ ፣ የቡና አትክልት አይመስልም ! ጥላሁንና ሶሬያም ፣ ባላምባራስ ጉዴታም ፣ እንዲያ ከመስመሩ ላይ ዘንፍ ፣ በጥንቃቄ የተሰለፈ የቡና አታክልት አይተው ስለማያውቁ ገረ ማቸው ። እርግጥ ነው ፣ አሳቡ መብራቱ ከጅማ የርሻ ትምህርት ቤት ተመርቆ የወጣ ስለሆነ ፣ በዘመናዊ ስራት ፣ ቡና ዘሩ ከሚመረጥበት ጀምሮ ፣ ፍሉ ፣ ወይም ችግኙ ፈልቆ ፣ ጉድጓዱ ተቆፍሮ ፣ ተተክሎ አድጎ ፣ አፍርቶ ፣ ተለቅሞ ፣ የሚታጠበው ታጥቦ ፣ እንዲሁ በጀንፈሉ የሚደርቀው ደርቆ ፣ በጆንያ እስኪከተት ድረስ ፣ የቡና ገበሬዎች ማድረግ የሚገባቸውን ሁሉ በወቅቱ ሲያውሩ ይሰሙ ስለ ነበረ ፣ ዘመናዊ አሰራር በየኪናና ባካባቢው ከሚሰራው ፣ ከጥንታዊው ያሰራር ዘዴ የተሰዩ መሆኑን ያውቃሉ ። እንዲያውም ሶፊያና ጥላሁን ካሳዩ የሰሙትን ከዋላ ጎደል ተከችለው ፣ አንድ ጋሻ መሬት በዘመናዊ እቅድ አል ምተዋል ። የኪ የነሱ አንድ ጋሻ መሬት ቡና ሰው ሁሉ የሚደነቅበት ፣ በጣም በጣም ዘመናዊ ነው ! ወደ ሚዛን አምጥቶ ካቀ ዳምጠው ብርዬ ቡና ጋር እናስተካክልህ ሲሉት ግን ሀሀ ! መሳቂያ ነው ! መቼም ያስ ራር ወሬ መስማትና የተሰራውን ባይን ማየት የተለያዩ ስለ ሆኑ ፣ አሳቡ ከወሬችው ዳምጠው ብርዬ ሰርቶ ያሳያቸው ፍጹም የተለዩ ፣ ዝምድና የሌለው ሆኖ አገኙት ።

"ገሩም ነው ! ድንቅ ነው ! " አለ ጥላሁን ራሱን እየወዘወዘከሱ በቀር ማንም ሲሰማው በማይችል ፣ ዝቅተኛ ድምጽ ። ከመገረሙ ብዛት የተነሳ ፣ አይኑን ሳያረግብ ፣ ዝም ብሎ ፣ ያን የቡና ሰልፍ ሲመለከት ዘለግ ላለ ጊዜ ቆዩ ። "ይህ እውነትም . . . እንኪዋንስ በዚህ ሲያልፉ ፣ እግረ

@OLDBOOKSPDF

መንገዱን ፣ እሱን ብቻ ለማየት ከፍቶ የሚመጡለት ነው ! ” አለ እሁ ንም ለራሱ ብቻ እንደሚናገር በዝቅተኛ ድምጽ ።

ግራዝማች ጉርሚሳና እንግዶቻቸው ከቆሙበት ጉብታ አጠገብ ያለው ቡና ፣ ከታች ከወደ እግሩ ለፋ ፣ ከላይ ሰብሰብ ብሎ ፣ ቁመቱ ከአ ንድ ሜትር ከስድሳ እስከ አንድ ሜትር ከሰባ ያክል ይሆናል ። ከዚያ መስመሩን በቁመት ተከትሎ እጥፋቱ ፣ እጥፋቱ ፣ በሄደ መጠን ፣ የቡናው ቁመት እያጠረ ፣ እያጠረ ፣ ይሄድና ወዲያ ፣ ወደ መጨረሻው ሲደርስ ፣ በመሬቱ ላይ ሰፋ ብሎ የተበመረ ፣ አረንጓዴ መስመር እንጂ የቡና እታክሎች አይመስልም ፤ ጎብኝዎች ቆመው ከሚመለከቱበት በስተቀኝ በኩል ፣ የቡናውን እትክልት ዘለፋ አድርጎ ፣ እጉብታው ላይ ፣ የውሬቱ ቻቶ ቢፈር ይታያል ። ከያንዳንዱ ሌት እንደ ቡናው በቁምም ፣ በወርድም ሰበት ሰበት ሜትር እጥታራፉቶ ፣ መስመሩን ጠብቆ የተሰራ ስለሆነ ፣ እሱም እንደ ቡናው ጎብኝዎችን ለመቀበል በተጠንቀቅ ተሰልፎ የሚጠ ብቅ ይመስላል !

“ይህ ቡና እዚህ ይሀን ያክል ፈግኖም ሆኖ ፣ ወዲያ ፣ ወደ መጨ ረሻ ያለው ከመሬት ተለይቶ የማይታየው ከርቀት የተነሳ ነው ? ወይስ . . . ገና ግልገል ቢሆን ይሆን ? ” አለ ጥላሁን ።

“ሁለቱም ነው ። መጀመሪያ እቶ ዳምጠው መትከል የጀመረው ከዚህ ነው ” አሉ ግራዝማች ፣ ባጠገባቸው የተሰለፈውን የቡና እትክ ልት በገሚቻው እያመለከቱ ። “ከዚሀ እዚያ ወዲያ ፣ እመጨረሻው ለመ ድረስ አምስት ይሁን ስንት . . . አመት ወስዶበታል ። ስለዚህ በያመቱ የተተከለው እንደ እድሜው ቁመቱም ፣ ስፋቱም ይለያያል ። ያ . . . ወደ መጨረሻው ላይ የምታዩት ፣ በመጨረሻ የተተከለ ፣ ያንድ አመት ግል ገል ነው ። ወዲያውም ከመሬት ተለይቶ አልታይ ያለው . . . ከርቀቱ የተነሳ ጭምር ” ብለው ግራዝማች ፣ ለጀመሩለት አረፍተ ነገር ማሰሪያ ሳያደርጉለት ፣ ሁለት ሰዎች በቡናው ውስጥ ለውስጥ ፣ ሳይታዩ አጠገባ ቸው ሲደርሱ ፣ ብቻ ድንገት ብቅ ሲሉ አዩ ። “አ . . . ! ያውና ፣ ያ ፣ ወዲህ የሚመጣው ፣ ራሱ እቶ ዳምጠው ነው ! ራሱ ባለንብረቱ ነው ! ” አሉ ፣ ስለ ቡናው አተካከል የጀመሩትን ወሬ ትተው ፣ በፈገግታ እንግ ዶቻቸውን ከባላምባራስ ጀምረው አንድ ጊዜ ባይናቸው ገረፍ አደረጉና፡ እቶ ዳምጠውና ካፖው ፣ ወደ ከተማ ለመሄድ ይቸኩሉ ነበር ።

ዳምጠው ብርዬ በድሜው ገና አርባ አመት ግድም የሚሆነው ወጣት ፣ በሌላ ፊቱ መጠን ግንባሩ ፣ አይኖቹና አፍንጫው ትላልቆች ሆነው ፣ አፉና አገጩ በጣም ትናንሾች ስለሆኑ ፣ በጠቅላላው ፣ የመልኩ

@OLDBOOKSPDF

ቅጥ ከሰው ይልቅ ወደ ቁንደዶዋም አውራ ዶሮ ስለሚቀርብ ፣ አያም ርም ። ባለባበሱና በጠቅላላ ሁኔታውም ፣ በዚያ አካባቢ ከሚታዩት ተራ ሰዎች ምንም የተለዩ ነገር ስለማይታይበት ፣ ለዚያ አስደናቂ ልማት ፣ ለዚያ ሁሉ ሰፊ ሀብት ፣ እንኩዋንስ ባለቤቱ ፣ "እዚያ ተቀጥሮ የሚሰራ ፣ የባለቤቱ ሹም ይሆናል" ተብሎ የሚገመት አይደለም ።

"እኛ ወዳንተ በንመጣ ወዴት ለመሄድ ነው እንዲህ የምትቸኩለ? ወንድማች ባላምባራስ ጉዳታ ራጉና እኔህ ካዲስ አበባ የመጡ እንግዶች የቡና ልማትህን እንዲያዩ ነበር ይዣቸው የመጣሁ ። እቶ የሴፍና ባለ ቤቱ ወይዘሮ እመቤት አገር አዩ ኮ ጎብኝዎች ስለሆኑ ፣ ስራህን አይ ተው ዝናህን ላዲስ አበባ ቢያስታውቁ ከራቱ ለሁላችን ነው ፤ ላገር ነው ብዬ ነው . . . 'ምንም ቢሆን ስራውን ሳታዩለት እትሄዱም' ብዬ ያመጣሁዋቸው" አሉ ግራዝማች ፣ እንግዶችን ከ"መንጀር ቦሴ" ባለንብረት ጋር ሲያስተዋውቁ ።

"እግዚያብሄር ይስጥልኝ ፣ ጌቶችንማ አውቃለሁኮ ፤ እሳቸው ፈቱ ውኝ ይሆናል እንጂ" አለ ዳምጠው ብርዬ ፣ ግራዝማችንና ባላምባራስን ባክብሮት እጅ ነስቶ ፡ ለጥላሁንና ለሶፊያ የጅ ሰላምታ ከሰጠ በሁዋላ ። "አባክዎ ሰተራዎቼ ታመውብኝ ፣ ምንም ባያድናቸው ፣ የወባ ክኒን ቢጣኝ 'ሳይመሽ ወዲያ ወዲህ ተሩዋሩጠን እንፈልግ' ብለን ነው . . . እና ወልደ ማርያም ወደ ከተማ የምንቸኩል" አለ ወሬ እንዳያበረዝመውበት ለመከላከል ፣ ወዲያው ቀጠል አድርጎ ወደ ወልደ ማርያም እያመለከተ ። ወልደ ማርያም ካፓው ነው ።

"አይ ልጆቼን ! ወባ አመዋቸው ነው ? አዲስ ነው ወይስ መንሸ ?" አሉ ግራዝማች ፣ ማዘናቸውን በሚገልጽ ፊት ።

"ምን እባክዎ ፤ እንዲያው . . . የሌላውን በሽታ ስም ስለማናውቅ ፣ በዚህ አካባቢ ትኩሳቱ የጸናበትን በሽተኛ ሁሉ 'ወባ ታመመ' እንላ ለን እንጂ በሽታው ወባ መሆኑንስ እንዴት እናውቃለን ? መሰንበቻ ውን የሞቱት ሁለት ልጆች ፣ የወባ ክኒን አልተለያቸውም ፤ እንዲያውም የነበረንን ክኒን በነሱ ነው የጨረስነው ፤ ነገር ግን ምንም አላደረገላ ቸውም ።"

"ኧረ ልጅ ! መሰበንቻውን ሁለት ልጆች ሞቱብህ ? አልሰማሁም ።" አሉ ግራዝማች ፣ አሁንም እንደ መደንገጥ ብለው ።

"ያውስ . . . እንዴት ፣ እንዴት ያሉ ልጆች ነበሩ መሰለዎ ! በስምንት ቀን ውስጥ ሁለት እንዲያ ያሉ ፣ ጥሩ ጥሩ ልጆች ቀበርሁ ፤ አሁን ደግሞ እራቱ ታመዋል ። ታዲያ ትኩሳታቸው ልክ እንደነዚያው፡እንደ

@OLDBOOKSPDF

ሞቱት ከሩቅ እንደሳት ወላፈን ነው የሚጋረፍ ፤ ታዲያ የሚያስገርመው የሞቱትም ፣ አሁን የቃመሙትም ትኩሳታቸው እንዲያ . . . የሳት ወላፈን ይመስል እዬተጋረፈ ፣ እንደ ወባ እይመታቸውም ፤ ይኸ ነው ያጠራጠረኝ ። ወባ ከሆነ አይመታቸውም ኖሩዋል ? ” አለ ዳምጠው ፣ እዚያ ከቆሙት ሁሉ መልስ እንደሚለምን አይኑን እያዞረ አንድ ባንድ ሁሉንም ተመልክቶ ።

“አሁን ወንድሜ እንዳልኸው ወባ ያልሆነ እንደሆነ ምንም አያገለግላቸው ይሆናል እንጂ ፣ ክኒንስ ከምንጎበኛቸው እገሮች ብዙዎች ወባ ያለባቸው መሆናቸውን ስለ ተረዳን ፣ ለራሳችንም ፣ እንዲህ ተቸግረው ለምናገኛቸውም ይሆናል ብለን ብዙ ይዘናል ” ብሎ ጥላሁን እሱም ፣ ሶፈያም በዩኒፎርማቸው ይዘውት የነበረውን አንድ አንድ ፣ ባለ ሀያ ኪኒን ብልቃጥ ፣ በድምሩ አርባ ክኒን ሲሰጠው ፣ ዳምጠው በጣም ደስ ብሎት ከልብ ምስጋና ጋር ተቀብሎ ፣ ቶሎ ለበሽተኞቹ እንዲወስድላቸው ለካፖው ሰጠው ። ከዚያ ፣ እንግዶችን ለማስጎብኘት ወደ አታክልቱ ውስጥ ይዞዋቸው ከመግባቱ በፊት ፣ እዚያው በቆሙበት እንዳሉ ታሪኩን አጠር አጠር እያደረገ ተረከላቸው ። ብቻ በጠቅላላው ይህን ያክል አጭር አል ነበረም !

“ይህን . . . ” አለ ከምን እንደሚጀምር ጠፍቶት በፊቱ የተዘረጋውን ሰፊ የቡና አትክልት ከቀኝ ወደ ግራ ፣ ከግራ እንደ ገና ወደ ቀኝ ተመለከተና ። “እዎ ፣ ይህን የልማት ስራ ከመጀመሬ በፊት ካገሬ ፣ ከመናገሻ ፣ ገና በልጅነቴ ወጥቼ ስራ ፍለጋ መጀመሪያ ከፋ ፣ ከዚያ የኪ ፣ መጨረሻ በበቃ ነበርሁ ። ከፋ ብዙ አልተቀመጥሁም ። የኪ ግን ያቶ አሻግሬ በልሁ አሽከር ሆኘ ፣ አቶ አሻግሬ ይሰጡኝ የነበረው ደመወዝ ትንሽ ቢሆንም ፣ እንዳሽከራቸው ሳይሆን እንደ ልጃቸው ያዩኝ ስለ ነበረ ከነሱ ጋር ብዙ ቆዩሁ ። እዚያ ነው ቅድም ጌቶችን አውቃለሁ ያልሁ ። ብቻ ያን ጊዜ ልጅ ስለነበርሁና ፣ ስሜም ሌላ ስለነበረ ፣ አያስታውሱኝ ይሆናል ። ያን ጊዜ ስሜ ፣ “ታምሩ ገሰጠ” ነበር የሚባል ። ነገር ግን ሰው . . . እንጃ ባይኔ . . . ፈጣጣነት ምክናያት ነው መሰለኝ “ታምሩ ጎረጥ ነበር የሚለኝ ! ” አለ ዳምጠው ፣ ትንሽ እንደ ማፈር ብሎ እዬሳቀ ።

“እንዴ ! እንዴ ! አንተ ታምሬ ነህ ? በል ና ሳመኝ ! ” አሉና ባላምባራስ ፣ ግራና ቀኝ ጉንጮቹን አገላብጠው ከሳሙ በሁዋላ ፣ “እንዴት ልወቅህ ልጄ ! እንዲህ ሸምግለህ ፣ እንዲህ ባለ አስገራሚ የልማት ስራ ባለቤት ሆነህ ፣ በዚያ ላይ ስምህን ለውጠህ ! ከዚህ ሁሉ እንግዳ ነገር መሀከል እንዴት አድርጌ ልወቅህ ? ” አሉ ። “የዛሬ . . . አስራ ሁለት

@OLDBOOKSPDF

ይሁን እንጂ ሰባት ሦስት አመት እዚያ እኛ ዘንድ ሳለ በጣም ከ ልጅ ነበር ! ” አሉ ባለምባራስ ወዲያው ቀጥለው ፣ ከዳምጠው ወደ ሌሎች ዘወር ብለው እየተናገሩ ።

“አዎ ! ጊዜውማ ከ ብዙ ነው ” አለና ዳምጠው ፣ ታሪኩን ቀጠለ ። “ታዲያ ከየኪ. ወደ በበቃ ሄጄ መጀመሪያ በቀን ፣ ሁዋላ በኑዋሪ ሰራተኛነት ተቀጠርሁ ። እዚያ አንድ ተራ ሰራተኛ በወር ሀያ አምስት ኪሎ የቦቆሎ ዱቄት ፣ አንድ ኪሎ የበርበሬ ዱቄት ፣ አንድ ኩባያ ጨው ፣ አንድ ሊትር ዘይትና ሰላሳ ብር ያገኛል ። ብቻ እኔ የቡናን ስራ እንዲያው ከመጀመሪያ ፣ መሬት ከማሰናዳቱ ጀምሮ ፣ ችግኝ በማፍላቱ ፣ በተከላው ፣ ባረሙ ፣ በገዘራው ፣ በለቀማው ፣ ባጠባውና ባሰጣጡ አልፎ ፣ በጆንያ አግብቶ እስከ መከፋቱ ድረስ ፣ ቶሎ አጠናቅቄ በማወቅሁና ወዲያውም ስራ የምወድ መሆኔን የከራው መሪ ፈረንጅ ስላወቀ ፣ በተራ ሰራተኛነት ካንድ አመት በላይ አልቆዩሁም ፣ በሁለተኛው አመት “ካቦ” አረገኝ ! ” አለ ዳምጠው ፤ “ካቦ” የሆነ ያህለት እንደ ሆነ ሁሉ ፣ የኩራት ስሜት ተሰማውና ትከሻዎቹን ወደ ላይ ገፋ አድርጎ ። ‘ካቦ’ ሰሆን ፣ አለ ቀጥሎ ። ‘ካቦ’ ስሆን ፣ ደመወዜ ከሰላሳ ወደ ስድሳ ብር ከፍ አለ ፤ ቀለቤ ግን አልተለወጠም ። በበቃ አምስት አመት በ‘ካቦነት’ እንደ ሰራሁ ፣ እዚህ ይህን አምስት ጋሻ መሬት ፣ መንግስት በርካሽ ዋጋ የሚሸጥ መሆኑን ወዳጅ ስለ ጠቆመኝ ፣ እንደ ሌሎች ‘ካቦዎች’ ገንዘቤን ሳላ ባክን ፣ ይህና ቀጥቤ አስቀምጥ ስለነበረ ፣ ቶሎ መጥቼ መግዛትና እዚህ ስራ መጀመር ቻልሁ ። ከኔ በፊት ጀምረው ብዙ አመት በ‘ካቦነት’ ሲሰሩ የኖሩት ፣ ገንዘባቸውን በመሸታና . . . በሌላ ስለሚያባክኑ ፣ እስከ ዛሬ መለወጫ ልብስ ለመግዛት እንኳ ያቸግራሉ ! እኔ ግን . . . እግዚ ያሄር ይመስገን ፣ አጭቴን ቋጥር አድርጌ ፣ በቆጠብሁት ገንዘብ ፣ ይህን ስራ አቋቁሜ የራሴን ብቻ ሳይሆን የብዙ ሰርቶ አዳሪ ችግር ለማስወ ገድ በቅቻለሁ ። አሁን እዚህ ስንት ሰራተኛ አለ ይመስላችሁዋል ? አዲስ መሬት ለናሰናዳ ለምንጣሮና እንዲሁም ቡና በሚለቀምበት ጊዜ ለለቀማ ከሩቅና ከቅርብ ከሚሰበሰበው ፣ እጅግ ብዙ የቀን ሰራተኛ ሌላ ፣ እዚሁ ቤት ተሰርቶላቸው የሚቀመጡ ፣ አርባ ኑዋሪ ተራ ሰራተኞችና አራት ካቦዎች አሉ ። ለካቦዎች የምከፍላቸው ፣ ልክ ‘ በበቃ ’ ፈረንጆች እንደሚከፍሉት ነው ፤ ለተራ ሰራተኞች ግን እንዲያውም እዚህ እኔ የም ከፍለው ይሻላል ። ላንድ ሰራተኛ ሰው ፣ በወር ሀያ አምስት ኪሎ የበ ቆሎ ዱቄት አለመብቃቱን ‘ በበቃ ’ በተራ ሰራተኝነት ስሰራ ስለማ ውቅ ፣ እዚህ የምሰጠው የቦቆሎ ዱቄት ፣ በወር ከሰላሳ ሶስት ኪሎ በላይ ወይም ለሶስት ወር አንድ ኩንታል ነው ። ሌላው ያው እንደ ‘ በበቃው ’

@OLDBOOKSPDF

ነው ። ደግሞ ከሁሉም ባሰብሁት ቁጥር ደስ የሚያሰኘኝ ፣ ‘ከበበታ’ የልማት ድርጅት በቀር እንደምታውቁት ፣ በዚህ ዙሪያ ፣ ሁሉም ባመት አንድ ጊዜ በደቦ ጫካ ለማስመንጠር ፣ ወይም የጫካ ቡና ለማስጠረግ የሚጠራውን ፣ ብዙ ህዝብ ንፍሮና ቦርዴ ጋብዞ ማሰናበት ነው እንጂ ፣ እንዲህ ኑሮረ ሰራተኛ በብዛት ቀጥሮ ፣ ቀለብና ደመወዝ እየከፈለ ፣ የልማት ስራ አቋቁሞ ማሰራት በፍጹም የተለመደ ስላልሆነ ፣ ስዚህ አዲስ አይነት ስራ ፣ በዚህ ዙሪያ በምንኖር አበሾች መሀከል ጀማሪው እኔ መሆኔ ነው” አለ ዳምጠው ፣ አሁንም ትክሻውን ወደ ላይ ገፋ አድርጎ ። “በየኪም” አለ ወዲያው ቀጠል አድርጎ ፣ ወደ ባላምባራስ እየተመለከተ ፣ “በየኪም ጌቶች እንደሚያውቁት እስካሁን ፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ንፍሮና ቦርዴ እያሰናዱ ፣ በደቦ ካልሆነ ፣ ስራ አሰርቶ አንድ ሳንቲም የሚከፍል አልነበረም ። አሁን በቅርቡ ብቻ ፣ አቶ ጥላሁን ፈይሳና ወይዘሮ ሶፊያ የሚባሉት ባልና ሚስት ከመጡ ወዲህ ፣ እዚያ ነገሩ ሁሉ ተለውጦ ፣ አሁን እንደምሰማው የኪ ያለገንዘብ መስራትና ማሰራት ከሰው አሳብ እንኳዋ እየጠፋ ሄዷዋል ይባላል ! ”

ዳምጠው ገና የየኪን ስም ሲጠራ ፣ ሶፊያም ጥላሁንም ልባቸው ፈጥኖ ይመታ ጀመር ። “አቶ ጥላሁን ፈይሳና ወይዘሮ ሶፊያ” ካለ በሁዋላ ግን ፣ እንዲያው ድምጹን ብቻ እንጂ ምን እንዳለ ሰይተው መስማት አልቻሉም ! ባላምባራስም ደነገጡ ። “መቼስ . . . ” አሉ ቀጥሎ ። “መቼስ ፣ የየኪን ነገር እዚያው ለሚኖሩት ፣ ለጌቶች መንገር ‘ለቀባሪ ማርዳት’ እንደሚሉት እንዳይሆንብኝ እንጂ ፣ አቶ ጥላሁንና ወይዘሮ ሶፊያ ፣ በዚያ አጭር ጊዜ ውስጥ የሰሩት ማንም ፣ በየትም ሰርቶት የማያውቅ ነውኮ ! ”

“እዚያ የተሰራውን ሁሉ አንተ . . . አይተኸዋል ? ” አሉ ባላምባራስ ፣ አፋቸው እየፈራ ።

“እዎ ፤ አይቸዋለሁ እንጂ ፤ ደህና አድርጌ አውቀዋለሁ ። ጌቶች እንደሚያውቁት ፣ አቶ አሻግሬን ልክ እንዳባቴ ስለማያቸው ፣ እሳቸውን ለመጠየቅ አንዳንድ ጊዜ የኪ ስሄድ አየዋለሁ ፤ በዚህ አመት እንኳዋ . . . ካንድ ወር በፊት ነው መሰለኝ ሄጄ ነበር ” ሲል ፣ ሶፊያ የቆመችበት መሬት የሸሻት መስሎ ተሰማትና ፣ እጅዋን ወደዚያ ፣ ወደሚሸሸው መሬት ሰድዳ ይዛ ተቀመጠች ። ወዲያው ግንባርዋ ሲወዛና ከዚያም ላብዋ ሲንቸረፈፍ ይታይ ጀመር ።

“አቶ ጥላሁንንና ባለቤቱን ፣ ወይዘሮ ሶፊያንስ . . . ታውቃቸው ኖሮዋል ? ” አሉ ባላምባራስ ፣ አሁንም “እኒህ አደሉም እንዴ ! ” እንዳይሉቸው አፋቸው እየፈራ ።

@OLDBOOKSPDF

"ደሞ በዚህ ክፍል እነሱን የማያውቅ አለ ?"

"አነጋግረሀቸዋል ?"

" አ . . . ይ ! ማነጋገርስ አላነጋገርሁዋቸውም ። እንዲያው . . . በዝና ነው እንጂ አውቃቸዋለሁ ያልሁ ፤ ለመገናኘት እንኩዋ እድሉ አላጋጠመኝም ። እዚህ ለስራ እዬቸኮልሁ የኪ እንዲሁ ደርሶ ለመመለስ ካልሆነ ውዬ ያደርሁበት ጊዜ የለም ። ብቻ ዝናቸውን ደህና አድርጌ ጠግቤዋለሁ " አለ ዳምጠው ።

"እዎ ፤ ግሩም የሆነ ስራ ነው የሰሩ " አሉ ባላምባራስ ፤ በውስጣቸው ታምቆ የቆዬውን ጭንቀት በረዥሙ ተንፍሰው አስወግደው ። "እና ታዲያ እዚያ ስትመላለስ . . . እንዲያውም አላዬሀቸው ማለት ነው ?" አሉ ወቀሳ አስመስለው ፤ ወዲያው አለማየቱን ሙሉ በሙሉ ለማረጋገጥ ።

"አሁን እንዳልሁት እዚህ ለስራ እዬቸኮልሁ ፤ እዚያ ሄጄ ውዬ የማድርበትንና ከነሱም ጋር የምተዋወቅበትን ቀን ስፋጥር እንኩዋንስ በቅጡ ተዋውቄ አሳብ ለመለዋወጥ ፤ እንዲያውም ሳላያቸው ቀረሁ ።"

"አይ ! ደግ አላደረግህም ፤ ብታያቸውና ብትተዋወቁ በጣም ትወዳቸው ነበር ። እዎ ፤ እጅግ መልካም ሰዎች ነበሩ " አሉና ባላምባራስ ፤ አይኖቻቸውን ሳያረግቡ ላጭር ጊዜ ፊት-ለፊት ሲመለከቱ ቆይተው ፤ "እሜቴ ደከመሽ ?" አሉ ፤ ወዲያው ሶፊያ ወደ ተቀመጠችበት ዘወር ብለው " አይዞሽ አትፍሪ ፤ አማን ነው !" የሚል መግለጫ ካስተያየታቸውና ከፊታቸው ሁሉ እዬተነበበ ።

"ደህና ነኝ" አለች ሶፊያ ፤ ምንም እንኩዋ አሁን የሚያስደነግጥ ነገር አለመኖሩን ፤ ሁሉም አማን መሆኑን ብትረዳ ፤ ጽኑ ትኩሳት እንዳለባት አሁንም ገና ላብዋ በግንባርዋ ቸፈፍ እንዳለ ።

"ይህ የቡና ልማት ከሩቅ መጥቶ ሊያዩት የሚገባ መሆኑን ጌታ ግራዝማች እያደነቁ ሲናገሩ ሰምቻ ፤ ለማየት ስለ ጉጉጉቶች ፤ እኛ ስንመጣ 'ቅሬ' እንዳትባል መጋመምዋን መግለጽ አልፈለገችም እንጂ ፤ ቃማኪ ነው ያደረች " አለ ጥላሁን ፤ የምሽቱን ብርቱ ድንጋጤ በሽታ ለማስመሰል ። እሱ ግን ምንም እንኩዋ መጀመሪያ ዳምጠው ብርዬ የየኪንና የሱንም ፤ የምሽቱንም ስም ሲጠራ ቢደነግጥና ፤ ላንድ አፍታ ልቡ እንደ መሸበር ቢል ፤ ወዲያው ሰውነቱን ገዝቶና ልቡን ሞልቶ ፤ ባላምባራስና ዳምጠው የተለዋወጡዋቸውን ጥያቄዎችና መልሶች ፤ በጥሞና ማዳመጥ ችሎ ነበር ።

@OLDBOOKSPDF

"አሁን የየኪን ነገር እናዩይ፣ ለማየት ስለ መጣችሁለት፣ ስለ ቡና የጀመርነውን እንጨርስ። ብቻ እንግዶች ጊዜ ካላቸው፣ ከዚህ ይልቅ ሊታይ የሚገባው የኪ የተሰራው ልዩ ልዩ ስራ ስለ ሆነ፣ ጊቶች ወስደው ቢያሳዩዋቸው በጣም ደስ እንደሚላቸው እኔ እርግጠኛ ነኝ።" አለ ዳምጠው፣ አይኖቹን ወደ ባለምባራስ ቀና አድርጎ። "ስለኔ ስራ የሆነ እንደ ሆነ" አለ ከዚያ ቀጥሎ። "ስለኔ ስራ የሆነ እንደሆነ፣ ቅድም እንዳልሁት፣ ይህን አምስት ጋሻ መሬት ገዝቼ እዚህ ስራ ከጀመርሁ፣ አምስት አመት ሆነኝ። በዚህ ባምስት አመት ውስጥ፣ ያለማሁት ይህ የምታዩት፣ ሁለቱ ጋሻ ነው። በዚህ በምታዩት፣ ቡና በተተከለው መሬትና ከሱ ወዲያ በሚታዩው ሜዳ መሀከል፣ እርሻ የሚመስለው ክፍት ቦታ፣ ቀመንጥሮ፣ ተሰስሎ፣ በዚህ በፊታችን ስኔ ሊተከል የተሰናዳ፣ አንድ ጋሻ መሬት ነው። የተረፈውን ሁለት ጋሻ መሬት፣ እዝጊያብሄር እድሜውን ከጤና ጋር ከሰጠን፣ እድሜና ጤና ካላነፈገን፣ በሚከተሉት ሁለት አመቶች ተክለን ለመጨረስ አናስባለን። ወደ ፊት ያለው ስራ እንዳለፈው አይከብድም። እመጀመሪያው ላይ፣ መሰሪያውንና ማናቸውንም ለስራ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ማጠረቃቀሙ፣ ሁሉንም ... በሬርጅ በፈርጁ አሰናድቶ ድርጅቱን ማቀዋቀዋሙ፣ ጊዜ የሚወስድ ነገር ነው። መሰረያው ከተሰናዳና ድርጅቱ ከተቀዋቀዋመ፣ ሌላው ስራ፣ ያንያክል ጊዜ አይወስድም።

"አሁን እንግዲህ ... ካልደከማችሁ አንዳንድ ነገር ላሳያችሁ። መቸም የተተከለውን ቡና በሙሉ ለማየት፣ ከዚህ ከያምንበት ከየቱኛ ቦታ የተሻለ፣ ሁሉንም ከፍቶ፣ ሁሉንም ዘርግቶ፣ የሚያሳይ ስለሌለ፣ እዚህ ሆናችሁ ያላያችሁት ምንም የለ። ስለዚህ፣ ወደ ቡና ማጠቢያው፣ ወደ ማስጫውና ወደ ቾማች ማናያው ብንሄድ ይሻላል። ባቅከልቱ ውስጥ ስለሆነ የምንሄድ፣ እግሬ መንገዱ ቾነን፣ እያንዳንዱ ቡና በቂ ምግብ፣ በቂ አፍርና ጸሀይ እንዲያገኝ እንዱ ከነሳው ምን ምን ያክል እየተራራቀ እንደ ተተከለ፣ ከሪም ከበሽታና ከላዩ ልዩ ጎጂ ነገር ሁሉ ነጻ እንዲሆን፣ የበሩ ዙሪያ በስፋፈው ተነትኩቶ፣ ላዩ ከጭራንፎና ከግይረባ ቅርፋቅርፍ ሁሉ ተገሮና ጸድቶ እንደ ተጠበቀ እንመለከታለን። ከዚያ ስንመለስ፣ አሁንም ካልደከማችሁ የሰራተኞችን ሰፈር አሳያችሁዋለሁ። ብቻ ዛሬ እሁድ ስለሆነ፣ በሰፈሩ ታምመው ከተኙት በቀር አንድ ሠራተኛ የለም፣ ሁሉም ከተማ በዩጠጅ ቤቱ ነው የሚገኘው። ኪሱን አዩገለበጠ እራግፎ፣ ባዶነቱን ሳያረጋግጥ፣ ምንም ቢሆን ከዚያ የሚወጣ የለም!" አለና ዳምጠው፣ በገዛ ቀልዱ ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ፣ በቡናው ውስጥ

ለውስጥ መንገድ ለ@OLDBOOKSPDF…አለ ። ጥላሁንና ሶፊያ በሰፈር ሰራተኛ አለመኖሩን ሲሰሙ ፤ አንድ ከባድ ሸክም ከትከሻቸው እንደወረደ የወደቀ መስሎ ተሰማቸውና በረዥሙ ተነፈሱ ።

በቡናው ውስጥ ለውስጥ ሲያልፉ ፤ ከግራ ቀኙ የቡና መስመሮች መሐከል ባለው ሶስት ሜትር ከፍታ ቦታ ላይ ቆመው ፤ እያዩዋቸው እነሱን በቀኝና በግራ ያሉ የቡና መስመሮች ቀጥ ብለው ተከትለው ፤ እየራቁ ፤ እየራቁ በሄዱ መጠን ፤ መስመሮችም እየጠበቡ ፤ እየ ጠበቡ ሲሄዱ ይቆዩና ፤ እመጨረሻው ላይ ፤ እንደ ጦር ጫፍ አንድ ሆነው ይጠፉሉ ። አሳብም እንዲሁ በተመቢበት እንደለ ቅቅ ፤ ከመስመ ሮች ጋር ሲሄድ ፤ ሲሄድ ይቆይና ፤ እነሱ በጠፉበት እዚያ አብሮ ጠፍቶ ይቀራል ።

እያንዳንዱ የቡና ተክል ፤ ራሱ-ከባድ ሆኖ ተሸካሚ ግንዱ እንዳይ ጎዳና ፤ በመጨረሻም ስብረቱ እንዳያደርስበት ፤ ከታች ስሩ ፤ ከላይ ለብሰብ እያለ ተገዝሮ ፤ ግንዱ የሻገተ ፤ ወይም የሽበት ምልክት አይ ታይበት ፤ ቅርንጫፉ አንድ የደረቀ ጭራንሮ ፤ ወይም የገረጣ ፤ የጠ ወለገ እንኳዋ ቅጠል የለበት ፤ ፍጹም ንጹሕ ፤ ፍጹም ጤናማ ነው ። ምንም እንኳዋ ጊዜው አበባ ረግፎ ፤ ፍሬ ጎልቶ የማያታይበት ቢሆን ፤ እንዲያው ያን ለምለም ባፍ ሁሉ ፤ ካሸን ፍሬው ጋር እንዲያ ሰልቶን እርምሮ ማየቱ ብቻ በደስታ ያስከራል ! በዚያ እራራ ቆላ እዚሁ ለምላሚ ውስጥ መገኘቱ ፤ እንዲያው ያን ለምላሚ ማየቱ ብቻ ሳይጠጡ ጥም ይቆርጣል ፤ ያረካል ! እንግዶቹ ገና ያላዩትን ሳያዩ እንዳይመሽባቸው ባይሰጉ ኖሮ ፤ እዚያው መቆየት እንደፈቀ በወደዱ ነበር !

ከቡናው እትክልት አንድ ተወጣ ፤ ከሠራተኞች ሰፈር በግርጌ የቡና ማጠቢያው ፤ ማስጫውና የፍል ፤ ወይም የቅጣኝ ማፍያው ፤ ባንድ ላይ በሾሀም ሽቦ የታጠሩበት ፤ ቢያንስ ቢያንስ አንድ ሩብ ጋሻ መሬት የሚሆን ቦታ ያገኛል ። ዳምጠው ብርዬ ፤ የቡና መፈልፈያ ሞተር ለሙትከሏ ገና በመሰናዳት ላይ ስለነበረ ፤ ለጊዜው ሁለት በጅ የሚዞሩ መፈልፈያ መኪናዎች ብቻ ናቸው የነበሩት ።

ከሰራተኞች ሰፈር ራስጌ ተነስቶ ፤ ከ፡ሉ መሬት ጋር እየተዋሰነ አልፎ ከሚሄደው ቅልቅ ሸረት ፤ ውሀ በቦይ መልሶ እምጥቶ ፤ በስ ራው ስፈ ማጠራቀሚያ እንዲከግቹ አድርጎ ፤ ከዚያ ያ ውሀ በሻንዳ እየወረደ ፤ በመንገዳ የተቋዋተለችን እሸት ቡና በጅ ለሚዘሩት መኪ ናዎች ያቀብላል ። ከዚያ የተፈለፈለው ፍሬ ወደ ማጡኪያው የሲሚ ንቶ ገንዳ ፤ ጎሰሬቱ ወደ ውጪ ፤ ለዩብቻ በውሀ እየተነዱ ይሄዳሉ ።

@OLDBOOKSPDF

የተፈለፈለው እሸት ቡና በሚበካበት ገንዳ ውስጥ ፥ ለላላ ለድስት ሰአት ከቆዩ በሁዋላ ፥ መገደቢያው ሲከፈትለት ፥ እንዲሁ በውሀ ተነድቶ ቆጥሎ ወዳለው የስሚንቶ ማጠቢያ ገንዳ ይተላለፍና ፥ እዚያ ከነወለላው ሙልጭ ብሎ ፥ እስኪጠራ እየታጠበ ፥ ወደሚደርቅበት የሽቦ አልጋ ይወሰዳል ። ጎለፈቱ ግን ወደ ውጪ ወጥቶ ከደረቀ በሁዋላ የተኮተኮተውን የቡና እግር የቢጋ ጸሀይ እንዳይጎዳወና ፥ የመሬቱንም ርጥበት እዚያው እንዳለ እንዲጠበቅ ፥ በኩትኩዋቶው ላይ በሰፊው ይነጠፋል ፤ ወዲያውም እዚያው ቀይቶ ካፈሩ ጋር ሲደባለቅ ፥ ግዳ በሪያንቱ እጅግ ተፈላጊ ነው ።

ዳምጠው ብርዬ ፥ በእሸቱ እዩፈለፈለ ከሚያጥበው ቡና ሌላ ፥ እንዲሁ ከነገለፈቱ በሰፊ የስሚንቶ አውድማ እያሰጣ የሚያደርቀው በርከት ያለ ፥ “ ጀንፈል ” ቡናም እንዳለውና ፥ ለሱም ቢሆን ገና ወፍም ስላልተከለ ፥ ወደ ብቢቃ እዩጫኑ ፥ እዚያ ፈረንጆች በዋጋ እንዲሚፈጩለት ለንግዶች ነገራቸው ። ከዚያ ፥ ጊዜው የቡና ለቀማ ጊዜ ስላልነበረ ፥ የሚታጠበውንም ሆነ ጀንፈሉን ቡና እንደዩልን - በራሱ በቃል ከመተረክ አልፎ ፥ ለጎብኝዎቹ ባለራር ሲያሳያቸው ስላልቻለ በጣም ያዘነ መሆኑን እየገለጸ ፥ ወደ ፍል (ችግኝ) ማፍያው ይዞዋቸው ሄደ ።

ዳምጠው ብርዬ ፍል ሲያፈላ ፥ በዚያ አካባቢ ፥ በተለምዶ እንደሚደረገው ፥ እንዲሁ የተገኘውን የቡና ፍሬ ወስዶ ተቆፍሮ በተደበደለለት መደብ “ማፍሰስ” ወይም “መዝራት” አይደለም ። እሱ የለም ፤ እንዲያ አይደለም ! ከሁሉ አስቀድሞ ፥ ዘር መረጣ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነገር ነው ። ከሸቱ ቡና መሀከል ፥ ጤናማ ጤናማዎቹ የሚያማምሩት እዩተመረጡ ፥ ተፈልፍለው በጥላ ይደርቁና ፥ ቀደም ብሎ ተጎልጉሎ ፥ ተለሳልሶ በተዘጋጀላቸው መደብ ፥ በወርድም ፥ በቁምም ለባት ፥ ለባት ሲንቲ ሜትር ያክል እዩተራራቁ ተቀብረው አፈር በቀላሉ ይለብሳሉ ፤ ከዚያ አፈሩ የደረቀ ለንበሌጥ ይለብሳል ። እዚያ መደብ ፥ በያንዳንዱዋ ዘር ማሀጸን የተኛው የቡና ጽንስ ፥ ዳምጠው ብርዬ በብርቱ ጥንቃቄ ፥ በብርቱ ትጋት ፥ የጸሀይ ፥ ያዩር ፥ የውሀና ያፈር ምግቡን በሚያስፈልገው ጊዜና በሚያስፈልገው መጠን እዩመገበው ፥ ካርባ እስከ አምሳ ቀን ከቆዩ በሁዋላ ፥ ፋፍቶ ይወለድና ፥ ሀቁም ሀይሉን ለማሳዩት እንደሚፈልግ ሁሉ ፥ የወላጅ እናቱን ሬሳ ከተቀበረበት ይዞ ወጥቶ ፥ በዩራሱ እዩተሸከመ ፥ በዩጉድጉዋዱ አፍ ላይ ቆሞ ሲታይ ፥ እውነትም ቆብ እየደፋ

@OLDBOOKSPDF

በትራ የተሰለፈ ሰራዊት ይመስላል ፤ እዚያ ፡ ዳምጠውን የመሰለ ጠን
ቃቃ ሞግዚት እንደ ጌታ ልጅ እያቆላመጠ እያሳደገው ፡ ከስድስት
እስከ ስምንት ወራት ቆይቶ ፡ ስድስት ፡ ወይም ስምንት ጆሮዎች
ሲያወጣ ፡ በሰኔ ወር ላይ (ቢቻል ወደ መጀመሪያው) ስሩ እንዳይነካ
ወደ ታች በጣም ዝቅ ብሎ ፡ በብርቱ ጥንቃቄ ከናፈሩ እየተነሳ ፡ ተቆ
ፍሮ ፡ ተባርዶ በቆፍ ጉድጉዋድ ውስጥ እየተቀመጠ ጉድጉዋዱ ይደ
ፈናል ። ሁለት ሶስት ጊዜ ቦታ እየለዋወጡ "ማጋዝ" የሚሉት ነገር
በዳምጠው ብርዬ ዘንድ የለም ። ፍሉ ከፈላበት ቦታ ተነስቶ ወደሚ
ተከልበት ጉድጉዋድ ሲሄድ ፡ አስተዳደም ከበቀለበት ፡ ተወልዶ ካደገ
በት አፈር ጋር ስለሚሄድ ፡ መድረቅ ፡ መክሳት ፡ መገርጣት ይቅርና
ከቅጠሉ እንኩዋ የለውጥ ምልክት ሳይታይበት ፡ እንዳማረበት ማደ
ጉን ይቀጥላል ። በዳምጠው ብርዬ አያያዝ ፡ እያንዳንዱዋ የቡና ዘር ፡
በፍል መደብዋ ከተቀበረችበት ጀምሮ ፍል ሆና ተተኪላ ፡ አድጋ ፡
አብባ ፡ የምስራች እስከምትሰጥበት ጊዜ ፡ ከሰላሳ እስከ ሰላሳ ሁለት
ወራት ብቻ ነው የሚወስደው ፤ በበታ የፈረንጆች ቡና ፡ ከሰላሳ ስድ
ስት ወራት በፊት የምስራች አይሰጥም ፤ በሚከተለው ስሌ የሚተከለው
ያምስት ወራት እድሜ ያለው ፍል ፤ የግፉ መወፈርና የቅጠሎቹ ግግር፣
እንዲያው በጠቅላላው ገዳቡሩ ሲታይ ፡ እጅግ ቢያንስ ከስራ ሁለት
ወራት ያንሳል ተብሎ አይገመትም ።

"አሁን እንግዲህ ፡ እዚህ ከመጋዘናችን በቀር ፡ ሌላ የሚታይ
ነገር ስለሌለና ፡ መጋዘኑም የምርት ጊዜ ባለመሆኑ ባዶ ስለ ሆኑ ፡
'እዩኝ እዩኝ' የሚል አይደለምና ፡ እግረ - መንገዳችሁን የሰራተኞችን
ሰፈር አይታችሁ ፡ ሳይመሽ ወደ ቤት ብትመለሱ . . . አይሻልም ?"
አለ ዳምጠው ብርዬ ፡ እንግዶቹ ፡ የልማቱን ስራ ሲተርኩላቸው በሰ
ሙትና ባይናቸው ባዩት ከመደሰታቸው በላይ ፡ በውነት መገረማቸ
ውን ሲያይ የተኮመና የተሸለመ ያክል ፊቱ ሁሉ በደስታ ወጋገን
በርቶ ።

"እግዜር ይባርክህ ፡ ልጄ ! እውነትም ወንድሜ ፡ ግራዝማች
ጉርሚሳ እንዳለው ፡ ይህ የሰራኸው ስራ አንተን ብቻ አይደለም የሚያ
ኮራው ። አገርን ሁሉ ፤ ወገንን ሁሉ የሚያኮራ ነው !" ብለው መረቁ
ባላምባራስ ጉዲታ ፤ እውነት ከልብ ደስ ብሎዋቸው ። ሶፊያና ጥላሁ
ንም ዳምጠው ብርዬን ከልብ አመስግነው ፤ የሰራው ስራ በጣም የሚ
ያስገርምና ስራ እዩ-ፈጠሩ አገራቸውንም ፡ ወገኖቻቸውንም ለመርዳት
ምኞት ላላቸው ኢትዮጵያውያን አርአያ ሊሆን የሚችል መሆኑን ሲገ

@OLDBOOKSPDF

ልጹሉት በጣም ደስ አለው ። ከዚያ ጻምጠው ቀደም ብሎ እየመራ፣ ወደ ሰራተኞች ሰፈር ይዞዋቸው ሄደ ።

የሰራተኞች ሰፈር ፣ ጻምጠው ከንግዶቹ ጋር ከተገናኙበት ቦታ እጠገብ ፣ በኮረብታው ላይ ሆኖ ፣ ከዚያ በጠቅላላው የልማቱን ቦታና ከሱም እልፎ ፣ ረባዳው ላይ የተመነጠረውንም ፣ እስከ ወዲያ ማዶ ቀራራ እግር የተዘረጋውን ሜካ የለበሰ አገርም ሁሉ ዘቅዝቆ ያሳያል። እሰፈሩ ውስጥ ሲገባ ፣ ቀደም ብሎ እንደ ተመለከተው ጎጆዎቹ ሁሉ በቁምም ፣ በወርድም ፣ ሶስት ሶስት ሜትር እዩተራራቁ የተሰሩ ባጣቸው እንደ ጉራጌ ቤት ቆም ብሎ ተጥቅሮ ፣ በተሜሜን የሰንበ ሴጥ ሳር የተከፈከፈ ፣ ግድግዳቸው ተለስኖ ኖራ የተቀባ ነው ። እያ ንዳንዱዋ ጎጆ በውስጥዋ ለሁለት ነጠላ ሰራተኞች ፣ ሁለት የንጨት አልጋዎች ብቻ ለሳሉባት ፣ ቤተ-ሰብ ያለው ሰራተኛ እዚያ እንዳይኖር የታቀደ መሆኑ ይታወቃል ። የያንዳንድዋ ጎጆ ባለቤቶች ፣ የቤታቸ ውን ውስጥና ደጃቸውን ፣ በጠቅላላው የሰፈሩ ንጥረታት፣ በተራ ተደ ራጅተው የጋራ የሚገለገሉበትን ፣ እድባቢያቸውን እያጸዱ እንዲጠብቁ ካምፖች በተራ ተደራጅተው ስለሚቆጣጠሩዋቸው ፣ ሰፈሩ ከጥዳት ወገኖ "ጊንከን-የለሽ" ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም ፤ ይህ እንከዋ ቢያንስ" ከምኣጎደል ከበቤቃ የሰራተኞች ሰፈር ጋር ተመሳሳይ ስለ ሆኑ ፣ ጻምጠው ብርዬ "እዚያ ያዩውን ነው በትንሹ እዚህ የሰራው" ቢባል በሙሉ ስህተት ሳይሆን ይችላል ። የመጸዳጃው አሰራር ግን ፣ በበቃ የሌለ ፣ የጻምጠው ብርዬ የግል ፈጠራ ነው ።

የሰራተኞችን ሰፈር በማንባሩ አድርጎ ፣ እዚያ ለሚኖሩ አማካ ይና ምቹ በሆነ ቦታ ላይ ፣ ስድስት ክፍልና ፣ እያንዳንዱ ክፍል የራሱ በርም መስኮትም ያለው ስቀላ ቤት ተሰርቶዋል ። ስቀላው ፣ እንደ ሰፈሩ ጎጆዎች ባጡ በሰንበሌጥ የተከፈከፈ ፣ ግድግዳው ተለስኖ ኖራ የተቀባ ፣ ወለሉ በኮረት ተደልድሎ በሲሚንቶ የተለቀለቀ ነው ። ከዚህ ሁሉ ሌላ ፣ እያንዳንዱ ክፍል ሰውነትን እዝናንቶ የሚቀመጡበት ፣ የመጸዳጃ መቀመጫ አለው ። ስቀላውን ቁም-ለቁም ቆርጦ ፣ በስድ ስቱ ክፍሎች ስር ለስር የሚያልፍ ፣ ጥልቀቱ አንድ ሜትር ተኩልና ፣ ስፋቱ አንድ ሜትር ሆኖ በስሚንቶ የተገነባ አንድ ቦይ አለ ። ሌላ ሁለተኛ ቦይ ፣ ከሰራተኞች ሰፈር ከፍ ብሎ ፣ ከኹረቱ የተመለሰ ውሀ በብዛት ይዞ መጥቶ ፣ በስቀላው ስር ለስር ወደ ተሰራው የስሚንቶ ቦይ ባናቱ ይገባና ፣ እዚያ ያገኘውን ሁሉ እጥብጥብ ፣ ጥርግርግ አያ ደረገ ይዞ ፣ በታች በኩል ወጥቶ ሄዶ ፣ ከቡና ማጠቢያው ገቅ ሲል፣

@OLDBOOKSPDF

እንደ ገና ከኘሮረቱ ጋር ይጨመራል ። ይህ የቦይ ውሀ ፣ ሁልጊዜ ሳያቋርጥ ፣ በመጸዳጃው ሰቀላ ስር ለስር እንደ ሄደ ስለሚኖር ፣ ቆሻሻ ነገር እዚያ ውስጥ ሳንድ አፍታ እንኳ ሊቆይ አይችልም ። ይህን ዘዴ ዳምጠው ብርዬ የፈጠረው እንጂ ከሰላ አይደለ ፣ ወይም ስምቶ የሰራው አለመሆኑን ሲነግራቸው ፣ እንግዶቹ እጅግ ተገረሙ !

ከዚያ ካም ወሊዶ ማርያም አዩመሬ ፣ እንግዶቹ ሳይነት ያከል ሁለቱን የሰራተኞች ቤቶች አዩ ነበ አዩ ። በያንዳንዱ ቤት የሚታዩት ሁለት አልጋዎች ፣ ከሰሌን ፍራሾቻቸውና ትራሶቻቸው ጋር ፣ አንድ የምግብ ማቅረቢያ ሳጣራ ፣ አንድ የውሀ መቅጃ ገንቦ ፣ ሁለት ኩባያዎችና አንድ እንደ ወጥ መከረያም ፣ እንደ ገናሮ መቀቀያም ሆኖ የሚያገለግል ፣ ጎድ ጎድ ያለ ድስት ብቻ ናቸው ። ወለላቸው ባመድ የተለቀለቀ ሆኖ ንጹህ ነው ። ምንም እንኳ ላሰንብኛዎች ተራ ነገር ቢመስል ፣ ለንብኛዎች አዲስ የሆንባቸውና ያስደነቃቸው የፍራሾቹና የትራሶቹ አሰራር ነው።

እያንዳንዱ የሰሌን ፍራሽ ፣ ባሊጋው ልክ ነጠላ ሳይሆን በጥፍ ተሠርቶ ፣ የደረቀ ሰንበሌጥ ሳር ፣ እንዳው ከውስጡ ተሰቅሞ ተከልቶ ፣ ቅጠሉ ብቻ እዚያ ውስጥ ጥጥም ብሎ ሞልቶ ፣ ከራስጌና ከግርጌ ድሮ ውንም በጥፉ ሲሰራ ጥጥም በመሆኑ ከጎንና ከጎኑ ብቻ ከፍቶን እንደ ኩፈዳ አሰበሱ እጋጥመው ሰፍተውት ፣ ግሩም የሆነ ፍራሽ ሆኖዋል ። ትራሰም ያው እንደ ፍራሹ ሳር ተሞልቶ ፣ አፉ ከመገጠሙ በቀር እሰ ራሱ ሆነ ቅጡ ልክ እንደ ኩፈዳ ነው ። የሰሌን ፍራሽና ትራስ ብዙ ሳያደክሙና ምንም ሳያስወጡ በቂ ምቾት የሚሰጡ መሆናቸውን በመመልከት ፡ እንግዶቹ ዳምጠው ብርዬን አደነቁ ። እሱ ግን የንግዶቹን አድንቆት እንደ ቀልድ ቆጥሮት ይስቅ ነበር ።

እንግዶቹ ጉብኝታቸውን ፈጽመው ወደ ከተማ ሲመለሱ ፣ በዚያው በሽተኞችን አይተው ለማለፍ መጀመሪያ ሁለት ሆነው ባንድ ቤት ወደተኙት ሄዱ ። እውነትም ዳምጠው እንዳለው ሁለቱም ትኩሳታቸው እንደ እሳት ወላፈን ይጋረፋል ። ከትኩሳቱ መበርታት ሌላ ፣ ፊታቸው አለፍ አለፍ እያለ ጉርብርብ ያለ ፣ ኩብ ነገር ሞልቶበት ይታያል ። ወዲያ ውም ፣ በጠቅላላው ፊታቸው ማበጡ በተለይ ባይኖቻቸውና በከንፈሮቻቸው ላይ ጎልቶ ይታያል ።

"ይህ ነገር . . . ወባ አይመስለኝም" አለ ጥላሁን ፣ በንግሊዝኛ ጎንበስ ብሎ የሁለቱንም የተጉረበረበ ፊት ከተመለከተና ፣ እጃቸውን አዩያዘ ትርታቸውን ከለጣ በሁዋላ ፣ ለፊያ ወዳለችበት ዘወር ብሎ ።

@OLDBOOKSPDF

"እቴንም አልመሰለኝም" አለች እሰዋም፣ እንዲሁ በንግሊዝኛ። ከዚያ ወጥተው ሶስተኛው በሽተኛ ብቻውን ወደ ተኛበት ቤት ሲሄዱ፣ ገና በውጭ እንዳሉ ጩኸቱ ተሰማቸው።

"መቃዠት ከጀመረ. . .ሁለት ቀን ሆነው" አለ ዳምጠው ሲገቡ። ወልደ ማርያም እዩመራ፣ ሶፊያና ጥላሁን ተከትለው፣ ዳምጠው ሁዋል ሁዋላ አጃቢ ሆኖ ገቡ ። ባላምባራስ ጉደታና ግራዝማች ጉርሜሳ ቦታ ላለማጣበብ በውጭ ቆዩ ። ጥላሁን ቀደም ብሎ የሁለቱን በሽተኞች ፊት እንደ ተመለከተ ፤ የዚህንም ለማየት ጎንበስ ከማለቱ ድንገት በጥፊ እንደ ተመታ ደንግጦ ቀና ካለ በሁዋላ፣ ትንሽ አይኑን ሲያሻሽ ቆይቶ፣ እንደገና አስተጋባና ተመልሶ ጎንበስ አለ ። ብቻ መደንገጡ እንዳይታወቅበት ፡ ድንጋጤውን ለመሸፈን ያክል፣ ተመልሶ ጎንበስ ቢልም ፣ ልቡ ስለ ተሸበረና ሊባቡ ስለ ተብትን ፣ መጀመሪያ እንዳለ በው በበሽተኛው ፊት ላይ ምን እንዳለ ለማየት አልቻለም ።

"አቶ ጥላሁንና ወይዘሮ ሶፊያ እኔን ሊያክሙ ነው፣ ያን ያክል ሩቅ መንገድ ተጉዘው የመጡ ? እንከዋን እነሱን አመጣችሁልኝ ! እነሱ ታክመኝ በቃ እድናለሁ ! " አለ በሽተኛው ፡ ወደ ጥላሁንና ወደ ሶፊያ እያየ ። ጥላሁን ምንም እንኳዋ መጀመሪያ ቢደነግጥ፣ በሽተኛው የሚቃኘ መሆኑን አስቀድሞ ዳምጠው ሲናገር ስለ ሰማ ፣ እንደ ምንም ተጣጥሮ የድንጋጤ ምልክት በሰውነቱም ፣ በሁኔታውም ፣ እንዳይታይበት ለማድረግ ቻለ ። ሶፊያ ግን ከበሽተኛው አፍ የወጡትን ቃሎች ስትሰማ፣ ከሰማይ የወረደ መብረቅ የመታት መሰላትና ወዲያው በሰራ አካላትዋ እንደ ኤሌትሪክ ተሰራጭቶ የሚያንዘፈዝፍ ነገር ተሰማት ።

"እይዞሽ አትፍሪ ፤ ስለሚቃዥ የሚናገረውን 'እውነት ይሆናል' ብሎ የሚጠረጥር የለም" አለ ጥላሁን ፡ በንግሊዝኛ ።

"እውነትህ ነው፤ አልፈራም" አለች እሰዋም ፡ እንዲሁ በእንግሊዝኛ ። ታዲያ ስታብል ነው እንጂ ፡ ፍራትዋ ከመጠን ያለፈ ነበር ። ከፍራትዋ ብዛት የተነሳ ፣ ጉልበቶችዋ እሱዋንና ያን የወረደ መአት ጥንድነት መሸከም አቅቶዋቸው ፣ እንደ ወንዝ ዳር ቄጠማ ይንቀጠቀጡ ነበር!

"አቶ ጥላሁንንና ወይዘሮ ሶፊያንማ ፡ ፖሊስ ቀኛዝማች ዳኘን ገድላችሁዋል ብሎ ገደላቸውኮ ! አልሰማችሁም ? አይ ፖሊስ. . . ! እግዚያሄር ይይለት ! አሁን እነዚያ የተባረኩ ሰዎች . . .እንኩዋንስ ሰው ዝንብ ይገድላሉ ?" አለ በሽተኛው ቀጥሎ ።

@OLDBOOKSPDF

"ይገርማል ! ከትናንት ጀምሮ ያየ ጥላሁንና ፣ የወይዘሮ ሶፊያን ስም ካፉ አልለዩምኮ !" አለ ካሥ ወልደ ማርያም ።

"በጤናው ሳለም ካፉ አይለያቸውም ። የኪ. በመዶች በላሉት ፣ እነሱ ዘንድ ያስራእምበት ቀን ፈቃድ ተቀብሎ ሄዶ ፣ እዚያ ስራ ከመ ፍታት ብሎ ፣ በቀን በራተኛነት እነሱ ዘንድ ሲሰራ ሰንብቶዋል ። ታዲያ ... የነሱን ነገር ሲያነሳ ፣ ደግነታቸውን ፣ ትህትናቸውን ፣ እንዲያው በጠቅላላው ሰው ለመርዳት የሚያ.ደርጉትን ሁሉ ፣ ተጫውቶ አይጠግ ብምኮ !" አለ ዳምጠው ፣ ጥላሁንንና ሶፊያን እያስዋወጠ እያዩ ።

"እሱ እንኳዋ " አለ ዳምጠው ፣ ትንሽ ዝም ብሎ ቆይቶ ለተና ገረው ከንግዶቹ መልስ ስላጣ ። "እሱ እንኳዋ ፣ ላጭር ጊዜም ቢሆን አብሮዋቸው ቆይቶ ያውቃቸዋል ! እረ እንዲያው የማያውቁዋቸው ወሬ ያቸውን ከመስማት በቀር አንድ ቀን ያላዩዋቸው ሁሉ እዶሉ ... እንደ እዝጊያሄርና እንደ እዝግትን ማሪያም ...ሲያመሰግኑዋቸው የሚ ኖሩ !"

@OLDBOOKSPDF

## ምእራፍ ፴፫

## እንወቶቼ

ከ "መንጀር ቦሌ" ጉብኝት መልስ ፡ ሶፊያና ጥላሁን በሽተኛውን ሲጠይቁ ገብተው ስላጋጠማቸው አስጊ ነገር ብቻቸውን ሆነው ለመመካከር እንዲመቻቸው ፡ በድካም አመካኝተው ወደሚተኙበት ቦታ ሄዱ። ምንም እንኩዋ ፡ ሚዛን ተፈሪ ከገቡ ጀምሮ የሚነገረው ቃል ሁሉ የነሱን ወንጀል ለመጠቆም የሚነገር አሽሙር ፡ የሚገለጸው አይን ሁሉ እነሱን እዩ-ተከታተለ የሚሰልል ተመልካች እዩመሰላቸው ፡ ያላብ እረፍትና ፡ የመንፈስ ጸጥታ ሳያገኙ ቢሰነብቱ ፡ ያነሰት ፡ የ "መንጀር ቦሌን" ልማት ጎብኝተው እስኪመለሱ የቆዩበት ጭንቅና ፡ የቆዩበት ግእር ፡ ተደበዘው፡ ተፈርዶባቸው፡ ወደ ስቅላት የሚሄዱ ቢሆኑ ሲሰማቸው ከሚችሰው ግእር ይበልጥ እንደሆነ እንጂ የሚያንስ አልነበረም !

"እንግዲህ ምን ይሻለናል ?" አለች ሶፊያ ፡ በሚተኙበት ቤት እንደገቡ እጆችዋን በጥላሁን ትከሻዎች ላይ አሳልፋ ከንገቱ ሁዋላ አቆላልፋ ፡ ሽቅብ አይኖቹን ጠልቃ እያዩችn

"ምንም አይል ፤ አይዞሽ አትፍሪ ፡ የኔ እመቤት !" አለ ጥላሁን፣ ግንባርዋን ስሞ ። የተጨነቁ አይኖችዋን ሲያይ ፡ ጭንቀትዋ በላስዉን ቀው ፡ እንዲያው እፉ እንዳመጣው የተናገረው ነው እንጂ ፡ እውነት ያነሰት የደረሰው "ምንም አይል" የሚባል ሆኖ አይደለም !

"እንዴት ምንም አይል፤ ሽሽተን በተሸሸግንበት ፡ አግኙቶ የሚያስይዝ ሲያጋጥመን ምንም አይል ትላለህ ?"

"ጥሩ ነው ማለቴ አይደለም ፤ መጥፎ ነው ። ብቻ . . . ስለሚቃዥና ፡ የሚናገረው የተዘበራረቀ ስለ ሆነ ፡ 'እውነት ነው' ብሎ የሚቀበለው አይኖርም ብዬ ነው ። ለምሳሌ ፡ ስለኛ የተናገረውን ሁሉ ልብ አድርገሽ አዳምጠሽው እንደሆነ ፡ መጀመሪያ ለማኝን እዩጠራ 'ያን ያክል መንገድ ተጉዛችሁ እኔን ለማከም መጣችሁ' ብሎ ካመሰገነን በሁዋላ ፡ ወዲያው ቀጠል አድርጎ ፡ 'ሶፊያንና ጥላሁንን ፖሊስ ገደላቸው' ብሎ ለኛው ነገረን ። ታዲያስ ! እንዲህ የተዘበራረቀ ነገር የሚናገር በሽተኛ 'የተናገረው እውነት ነው' ብሎ እንኩዋንስ ማመን የሚጠረጥር ይኖራል ትያለሽ ?"

@OLDBOOKSPDF

"እውነትህ ነው ፤ ታም እእምሮውን በሳተበት ጊዜ ፤ ሲታኝ የሚ ናገረውን የሚያምነው አይኖር ይሆናል ። ነገር ግን ታሞ አይኖርም ከ ፤ ይድናል ። ታዲያ ያንጊዜ ፣ ሲድን ተናግሮ ሊያስይዘን . . . አይችልም?"

"አዎ ፤ እሱ ድኖ እስኪወጣ እኛ እዚህ ተቀምጠን የጠበቅነው እንደሆነ ልክ ነው ፤ ብቻ እንዲህ ያለ የሞኞች ጭዋታ እንጫወትም ከ ፤ ቶሎ ከዚህ የምንሄድበትን ዘዴ ካባባ ጋር መመካከር አለብን " አለና አይኖቹን ካይኖቹዋ አንስቶ ማዶውን አሻግሮ እያዩ ትንሽ ሲያስብ ቆይቶ ፤

" ይልቅስ . . . ጠቁሞ ሳያስይዘን አይቀርም ብዬ ከሁሉም የም ፈራው አንድ ሌላ ነገር ነው !" አለ ፣ እንደገና ተመልሶ አይን አይን ዋን እያዬ ።

" ደግሞ ሌላ ምን ነገር አለ ?" አለች ሶፊያ ፣ እንደ መደንገጥ ብላ ።

"ያንቺ ፍራት እሱን ነው ፤ እኔ ከሁሉም የምፈራው ! እሱን እንደ ምንም ብለሽ ማሸነፍ አለብሽ ። በተረፈ ፣ በማንታወቅባቸው ከፍሎች እዬተዘዋወርን እስከ ቆዬን ድረስ ፣ ምንም የሚያሰጋን ነገር የለ ። ይህንም ስል . . . አሁን በኔና ባንቺ የደረሰው ከባድ ፈተና ደርሶባቸው እንደ እኛ መሰወር ከሚፈልጉ ሁሉ ፣ የዚያ የደረሰባቸው ፈተና ስም በተጠራ ቍጥር ፣ ወይም ከሱ ጋር ግንኙነት ያለው ወሬ ሲሰሙ ፤ ለጊዜው 'የማ ይደነግጡ ይገኛሉ ' ማለቴ አይደለም ፤ የማይደነግጥ ጨርሶ የሚገኝ አይ መስለኝም ። ብቻ ብርቱዎች የሚባሉ ፣ እንዲያ ያለውን ጊዜያዊ ድን ጋጤ አሳልፈ ው ፣ እሱን አሸንፈው ፣ ልባቸውን ማረጋጋት የሚችሉ ስለ ሆኑ ፣ አንቺም እንዲያ ብርቱ ሁኝ ማለቴ ነው ።"

"እም . . . እንጃ ! እኔ ፈሪ ነኝ እንዴ ? ፈሪ አደለሁምኮ !" አለች ሶፊያ ፣ አይኖችዋን ፊት - ለፊት ተከላ ትንሽ ስታስብ ቆይታ ፣ እንደ ገና ወደሱ ቀና አለችና ።

" አንቺ ፈሪ ? የምን ፈሪ ! ደፋር ብትሆኝ ነው እንጂ ፣ ፈሪ ብት ሆኝ እንዲያ ትንቀጠቀጪ ኖሮዋል ?" አለ ፣ ወገብዋን እቅፍ አድርጎ እንደ ያዘ ፣ በገዛ ቀልዱ ከልቡ እዬሳቀ ።

"ተው አትሳቅ ፤ እውነቴን ነው !" አለች ፣ አብራው መሳቅዋ ሳይቀር ። "ቀልድ አይመስልህ ፤ እውነቴን ነው ። አስቢ ፣ አሰላስዬ ፣ ሶወ ስንሁት ነገር ፣ እንኩዋንስ አንድ ጊዜ ፣ አስር ጊዜም እዬተመላለስሁ

@OLDBOOKSPDF

የምሞት ብሆን አልፈራም ። ‘ የምታምኝበትን ካልከድኸ ፣ የምትወጂውን ጠላሁ ካላልኸ ፣ የምትፈልጊውን ካልተውኸ ፣ ወይም . . . ለመናርኸ አላማ አድርገኸ በፊትኸ ያቆምኸውን ካላለወጥኸ ትገደያለሽ ’ የምባል ቢሆን ፣ ወደምገደልበት ስፍራ ቅር ሳይለኝ ፣ እንዲያውም እየበመርሁ መሄድ እንደምመርጥ ይግባህ ! ” አለችኝ ፣ ለስላሳ የነበረው ስሜትዋ ጠንከር ሲል ባይናችዋም ፣ በፊትዋም እየታየ ።

“ አትገቢ . . .አልጠረጥርም ። ”

“ ታዲያ ‘ ፈሪነኸ ’ ያልኸኝ እንዴት ነው ! ”

“ እንጃ ! ለምታምኝበት ነገር ቆራጥ መሆንሽን አውቃለሁ ። ብቻ . . . ታዲያ ቅድም ፣ እቶ ዳምጠውም ፣ ያ በሽተኛም ፣ የኛን ስም እየጠሩ ሲናገሩ ፣ ያን ያክል . . . ያንቀጠቀጥሽ የነበር ምንድነው ? ” አለ ፣ ምኞቱ እንደማትፈራ እያወቀ ፣ ያለምት ሲያንቀጠቅጣት ባየው ነገር የሚበጠው ስም ለላጣ ግራ ገብቶት ።

“ እንጃ ! ምን እንደምትለው አላውቅም ! ብቻ ፈሪ እይደለሁም ። ምናልባት ...ከመጠን ያለፈ ፣ በጣም ጥብቅ የሆነ ጥንቃቄ ትለው እንደሆን ! ለምሳሌ ፣ የሰወርሁት ምስጢር ቢኖር ፣ እንዳይታወቅብኝ ፣ ከፉ ነገር እንዳይደርስብኝ ፣ ወይም . . . ከሰው ጋር እንዳልጣላ ፣ እዋብቄ ፣ ከመጠን ያለፈ እጠነቀቃለሁ ፤ እሰጋለሁ ። ነገር ግን እንዳይደርስብኝ የተጠነቀቅሁበት ፣ የሰጋሁበት ፣ ወይም የተንቀጠቀጥሁበት ፣ ጥንቃቄየን ሁሉ አልፎ የደረሰብኝ እንደሆን ፣ እጋፈጣለሁ ፣ እዋጋለሁ እንጂ አልሸሽም ! ታዲያስ ፈሪ እንዲህ ነው ! ” አለች ፣ እንደምትፈከር በቁመችበት እንዳለች መሬቱን ባንድ እግርዋ ደልቃ ።

“ አደለም ! ይቅርታሽን እለምናለሁ ! ” አለ ጥላሁን ፣ ወገብዋን አቅፎ እንደ ያዘ ፣ ጥብቅ አድርጎ እየሳቀ ። ሶፊያም አብራው ትስቅ ጀመር ።

“ አልተኛችሁም ? እኔኮ ‘ ደከምናል ’ ስትሉ ሰምቼ ፣ ምናልባት ተኝታችሁ ታርፉ ይሆናል ብዬ ነው ብቻየን ደጅ ለደጅ የምነሁ ቀለል ! ” አሉ ባላምባራስ ጉደታ ፣ ሶፊያና ጥላሁን ሲስቁ ሰለ ሰሙ ወደ በራቸው ቀረብ ብለው ።

“ እረ የሚያሰጋ ነገር ስላጋጠመን . . . ስለሱ ወዲህ መጥተን ለመነጋገር እንዲመቸን የሰጠነው ምክናያት ነው እንጂ ፣ መድከም አልደከመንም ። እንዲያውም ከግራዝማች ለይቶ መጥራቱ እስቸጋርን ነው እንጂ ፣ እርስዎንም ለማነጋገር ፈልገንዎ ነበር ” አለ ጥላሁን ፣

@OLDBOOKSPDF

" ግራዝማችማ ፥ ሽምግልና አለብኝ ብሎ ፥ ወዲያው እናንተ እንደ ተለያችሁን ነው ትቶን የሄደ ። ለመሆኑ ምን ጊዜ ተለዩሁዋችሁና እኔ ያላየሁት ፥ ያልሰማሁት ፥ የሚያሰጋ ነገር አጋጠማችሁ ? " አሉ ባላምባራስ ፤ እንደ መደንገጥ ብለው ።

" እርስዎና ግራዝማች እውጭ ቆማችሁ ፥ እኛ መጨረሻ ጉብኙን የኀበኘነው በሽተኛ ፤ የኪ. እኛ ዘንድ የነበረ ፤ በጣም የምናውቀው ነው " አለ ጥላሁን ።

" ምን ? " አሉ ባላምባራስ ፥ ልክ አደጋ የተጣለባቸውን ያክል ደንግጠው ።

" ያ . . . ይጮህ የነበረው ፥ የሚቃገረው ? " አሉ ፥ ዝም ብለው ቆይተው ፤ ያ የሚያፈዝ ፥ ብርቱ ድንጋጤ እንደ ማለፍ ሲልላቸው ።

" አዎ ፤ የሚቃገረው ። "

" ታዲያ . . . እሱም አወቃችሁ ? "

" ገና ሲያየን በዩስማችን ጠርቶ ፥ ' እኔን ልታክሙ ነወይ ያን ያክል ሩቅ መንገድ ተጉዛችሁ የመጣችሁ ' አለ ። "

" ታዲያ አብረዋችሁ የነበሩት ሰዎች ምን አሉ ? "

" እነሱ እንኩዋ ለጊዜው የጠረጠሩ አልመሰለንም ። ይልቁንም እነሱ እንዳሉት ፥ በጤናው ሳለም ፥ ከታመመ በሁዋላም ፥ መሰንበቻውን የኛን ስም ካፉ ለይቶ ስለማያውቅ ፥ ዛሬ እኛን ሲያይ የተናገረው ከዚያ ከመሰንበቻው የተለዩ ሆኖ የታያቸው አይመስልም ። ነገር ግን ጉዱ ከዚህ ሳንነሳ እሱ ድኖ እዚህ ያገኘን እንደሆነ ነው ። ከዚህ ሳንሄድ ድኖ የተነሳና ያየን እንደሆን ፥ ሀ ! አለቀልን ማለት ነው ! " አለ ጥላሁን ፥ እንደ መሳቅ ብሎ ።

"የለም ፤ እሱ ድኖ እስኪነሳ . . . ምንም ቢሆን እዚህ አትቆዩም ። ፊት እንዳልነው ፥ የኒጋዴ በቅሎ መገኘት - አለመገኘቱ ቁርጥ እስኪታወቅ በመጠበቅ ፈንታ ፥ ግራዝማች ነገ ጥዋት አሽከሩን ወደ ቦንጋ ከፋ አገስግሶ ልኮ ፥ ቶሎ በቅሎዎች እንዲያመጣ እናደርጋለን " አሉ ባላምባራስ ፥ ስጋታቸው ከሁኔታቸው ሁሉ እዬታዩ ።

"አሁን እንዳሉት በግስጋሴ ሄዶ ፥ በቅሎዎች ይዞ ለመመለስ ምን ያክል ጊዜ ይወስዳል ? " አለች ሶፊያ ።

" እንጃ ፤ ምናልባት . . . ሁሉም ተዘጋጅቶ ያልተገኘ እንደሆን ፥ እስኪዘጋጅ አንድ ሳምንት ፥ ቢበዛ አስር ቀን ፥ ከዚህ የሚበልጥ አይወስድም ። "

@OLDBOOKSPDF

"እስከዚያ ድረስማ . . . ፍርዱስ አያልቅም ?" አለ ጥላሁን ፣ እየሳቀ ።

" የምን ፍርድ ? " አሉ ባላምባራስ ።

" እባክዎ እሱ ይቀልዳል ! ሰውዬው ደኅና ወጥቶ ፣ አስይዞን ፣ ወንጀላችን ተመርምሮ ተጣርቶ ፣ ከዚያ በሁዋላ የሚሰጠው ፍርድ ማለቱ ነው !" አለች ሶፊያ ።

" ኧረ ያንት ያለህ ! እንዲያ ነው ? " አሉ ባላምባራስ ፣ የቅርቃ ፊንጣ ላንድ አፍታ በፊታቸው አልፎ ሲሄድ ጸዳሉ እየታዩ ።

" እኔ የምሰጠው ምክር " አሉ ፣ ከዚያ ትንሽ ዝም ብለው ሲያስቡ ቆይተው ። " አሁን እኔ የምሰጠው ምክር ፣ ነገ ጥዋት ገበጋሽ ወደ ቆንጆ ሊዘን ፣ ከዚያ ወንድማችን ፣ ባሻ ነገም ቁሉ ፣ በቅሎዎችና ሰዎች ፉት እንዲልኩልን አደራ ማለት ፣ የባሻ ነገም በቅሎዎችና ሰዎች ከመድረሳቸው በፊት የነጋዴ በቅሎዎች ከተገኙም ፣ አይደን ሳይጠብቁ በዚህ መሄድ ፣ ያም ሆነ ይህ ፣ ከዚህ አስከምትነሱበት ቀን ድረስ ፣ እንዳንቺሁ ታማሚ ፣ እንዳንቺሁ አስታማሚ ፣ ሆናችሁ ከቤት ሳት ወጡና ፣ ከሰው ሳትገናኙ እንድትቆዩ ነው ።"

"ይህ በጣም ግሩም የሆነ አሳብ ነው ፤ በጣም ጥሩ አሳብ ነው ?" አሉ ሶፊያና ጥላሁን እየተቀባበሉ ፣ በባላምባራስ አሳብ መስማማታቸውን አሰበባቸው በመተያየት ከገለጹ በሁዋላ ።

"እንግዲህ ከነገ ጀምሬ እኔ እታመማለሁ ፤ አንቺ አስታማሚ ትሆኝ" አለ ጥላሁን ፣ ወዲያው ኩታል አድርጎ ።

"የለም ፤ እኔ ነኝ የምታመም" አለች ሶፊያ ፣ እየሳቀች ።

"እኔ ማስታመም አላውቅም ፤ አንቺ ናት የምታውቂ ። ስለዚህ እኔ ታማሚ አንቺ አስታማሚ እንድትሆኝ ይዘዙልኝ ፤ እግዚአብሄር ያሳይዎ አባባ" አለ ጥላሁን ፣ የቀልድ አቤቱታውን ለባላምባራስ እያቀረበ ።

"የዘመድ ዳኛ ያስታርቃል ፤ ያስማማል እንጂ አያዝዝም ፤ ስለዚህ . . . ተስማሙልኝ" አሉ ባላምባራስ ፣ ወደ ሶፊያ እየተመለከቱ እንዲሁ በቀልድ ።

"በኔ ማየትዎን አዩሁ ፣ አባባ ። እሺ ከፈቃድዎ አልወጣም ፤ በሽተኛዮን አስታምማለሁ !" አለች ሶፊያ እየሳቀች ።

"እሰይ ፤ እንዲያ ፤ ባለትኔዋ ልጂ !" አሉ ባላምባራስ እየሳቁ ። በማግስቱ ፣ በንጋ ፣ ወደ ባሻ ነገም ቁሉ የተላከው ገበጋሽ ፣ ጎህ ሲቀድ ተነስቶ ሄደ ፤ ጥላሁንም ጥዋት ከተኛበት አልተነሳም ፤ ታመመ ተባለ ።

@OLDBOOKSPDF

ግራዝማች ጉርሜሳ ፣ ጥላሁን መታመሙን ሲሰሙ አዘኑ ። የበቅሎ ክራይ ተግኝቶ እሱና ምሽቱ ተቶ ከዚያ ሄደው ቢሆን ኖሮ ይታመም እንዳልነበር ሲታሰባቸው ፣ የሚከራዩ በቅሎዎች ፍለጋ እንዳልተቸገሩ ፣ እንዳልደከሙ ሁሉ ፣ የበቅሎ ክራይ እንዳያገኙ ያደረጉ እሳቸው እንደ ሆኑ ሁሉ ፣ እንዲያው ሊገባ በማይችል ምክናያት ፣ ለጥላሁን መታመም ራሳቸውን እንደ ጥፋተኛ ቆጥረው ፣ የሀሊና ወቀሳ ፣ አጥብቆ ቆረቆራቸው። ባላምባራስ ጉዴታና ሶፊያም በበኩላቸው ፣ ጥላሁን ሳይታመም ፣ ለግራዝማች ስውር ለሆነ ምስጢራቸው ታመመ ብለው ፣ እንዲያ ያለ አዘንና እንዲያ ያለ ብርቱ ቁርቁዋሬ ስላደረሱባቸው ብርቱ አዘን አደረባቸው።

መሰንበቻቸውን ፣ ግራዝማች ጉርሜሳ በራትና በምሳ ፣ ጾም ካልሆነ በቁርስ ጊዜ ካልሆነ ፣ ከባለቤታቸውም ሆነ ከባላምባራስ ጋር አርፈው መጫወቱን ፣ ወይም ሌላ ስራ መስራቱን ትተው ፣ ከተማ ለከተማ እየዞሩ ፣ የሚጠይቁት ሰው ሁሉ እስኪሰለቻቸው ፣ በዱዋቂቱ ደቂቃ እየተመላለሱ ፣ የበቅሎ ነጋዴ ወሬ ሲጠይቁ ብቻ ሰነበቱ ። ነገር ግን ወደ ከፋ ይሁን ወደ ጅማ ፣ ወይም ወደ ማጂ ከሄዱት ነጋዴዎች ፣ አንዳች ፍንጭ አልተገኘም ። ጥላሁን በበኩሉ ፣ ምንም እንኳዋ ባንድ አፍታም ምሽቱ ባትለዩው ፣ በውነት የታመመ ለመምሰል ፣ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ለመጸዳዳት ካልሆነ ፣ ቀና ሳይል መደዳውን ከተኛ በሁዋላ ፣ ስለቻውና ያማርር ጀመር ።

"ሳይታመሙ መተኛት ለካስ እንዴት ያለ ጭንቅ ነገር ነው ! በውነት ሳይታመሙ ከመተኛት ታሞ መተኛት አስር ጊዜ ይሻላል !" አለ ጥላሁን ፣ ባላምባራስ ጉዴታና ሶፊያ አብረውት ተቀምጠው ባላምባራስ እንዲታገስ ሲመክሩት ።

"አሆ . . . ! የሚስት አስታማሚ ባጠገብ አስቀምጦ ፣ የሆድ ቁርጠት ይሁን የራስ ፍልጠት ፣ ወይም የጎን ውጋት ሳያስቸግር ፣ እንዲያው እንደ አያት ልጅ 'እምኛል ! አልበላም' እያሉ . . . እዩትቅበጠበጡ መቀማጠል ቢሹትስ ይገኛል ? ወዲያውም 'ከግዜር ጀሮ ፣ ከሱ የሚሰማው ደህና ፣ መልካም የሚሰማው ደንቆሮ' ይባላልና ፣ አሁን ያልኸውን እንዳትደግመው" አሉ ባላምባራስ ።

"ምን ያልሁትን ?"

"ሳይታመሙ ከመተኛት ታሞ መተኛት ይሻላል ያልኸውን"

"እ. . . ! እስቲ ተረቱን ይድገሙት ?"

@OLDBOOKSPDF

“ከግዜር ጆሮ ፤ ክፉ የሚሰማው ደህና ፤ መልካም የሚሰማው ደንቆሮ” አሉና ባላምባራስ እዬሳቁ “የባላገር ተረት ነው” አሉ ወዲያው ከትል አድርገው ።

“ምን ማለት ነው ?”

“እግዜር ፤ ከፍጥረቱ ሁሉ የሚቀርብለትን መልካምና ክፉ ልመና ፤ መልካሙን ሁሉ ባንድ ጆሮው ፤ ክፉውን ሁሉ በሌላ ጆሮው ፤ ለዩብቻ እንጂ ፤ መልካሙንም ክፉውንም ባንድነት ፤ በሁለት ጆሮዎቹ አይሰማም ይባላል ። ታዲያ ፤ እንዲህ እንዳሁኑ ፤ እንዳንተ አንዳንድ የቀበጡ ካልሆኑ ፤ ፍጥረቱ ሁሉ ፤ ወይም ከፍጥረቱ በጣም የሚበዛው እንበል ፤ የሚለምን መልካም እንዲደረግለት ብቻ ስለሆነ ፤ መልካም ለመስማት የተመደበው የግዜር ጆሮ በዝቶበት ፤ ደክሞ ፤ መስማቱን ወደ መተው ስለ ሆነ ፤ ልመናቸው ያልተሰማላቸው ‘ደንቆሮዋል’ ይሉታል ። ክፉ ልመና ለመስማት የተመደበው ጆሮ ግን ፤ እንዲያ ያለ ክፉ ልመና ስለማይቀርብለት ፤ ቢቀርብለትም ከስንት አንድ ስለሆነ ፤ ስራ ፈትቶ ፤ ቦዝኖ ስለሚኖር ፤ እንዲህ አንዳንድ ሲያገኝ ገና ከሩቅ ቀልቦ ፤ ወዲያው ነው . . . የሚሰማ ። ስለዚህ ፤ ‘ክፉ የሚለምን ቶሎ የሚያገኝበት ምክንያት ይህ ነው’ ይባላል ። እኔም ፤ እግዜር በደህና ጆሮው እንዳይሰማህ ብዬ ነው ፤ ቅድም የተናገርኸውን ክፉ ምኞት እንዳትደግመው ያስጠነቀቅሁህ !” ሲሉ ባላምባራስ ደስ ከሚል ፈገግታ ጋር ጥላሁንም ሶፊያም ይስቁ ጀመር ።

“እኔኮ ፤ ‘ሳይታመሙ ከመተኛት ፤ ታሞ መተኛት ይሻላል’ ስል የሁለቱን የክፋት ደረጃ ማመዛዘኔ ነው እንጂ ፤ ታሞ መተኛትን መመኘቴ አይደለም” አለ ጥላሁን ሲስቅ ቆይቶ ።

“እ. . . ! አዎ ፤ ሳይታመሙ ከመተኛት ታሞ መተኛትን መምረጥህ ነው እንጂ መመኘትህ አይደለም !” ሲሉ ባላምባራስ ፈገግ እንዳሉ ጥላሁንና ሶፊያ እንደገና እንባቸው እስኪወርድ ሳቁ ።

መቸም ባላምባራስ ፤ ከሶፊያና ከጥላሁን ጋር ተቀምጠው ሲጫወቱ ጥርሳቸውን እያስከደኑዋቸውም ። ተረት ተርተው የማያልቅባቸው ፤ ተራው ጭዋታ እንኩዋ በሳቸው አፍ ሲነገር የሚጥምላቸው ፤ ጭዋታቸው የማይጠገብ ስለ ሆነ ፤ ሶፊያና ጥላሁን ፤ በተለይ ቀኛዝማች ዳኘን ገድለው እዋሻ ውስጥ ከተሸሸጉበት ጊዜ ጀምሮ ፤ ትንሽ ተለይተዋቸው ሲቆዩ ዙሪያው ገደል ይሆንባቸዋል ፤ ይጨንቃቸዋል ። ባላምባራስ በበኩላቸው ፤ ጥላሁንና ምሽቱን ፤ ብቻቸውን የተዋቸው

@OLDBOOKSPDF

እንደሆን ፤ የተሸከሙትን ከባድ ሙከራ ሲያሰላስሉና ሲያወጡ ሲያወርዱ ፤ ይብሱን እንኳ እከብደውት ፤ መሸከም ወደማይችሉበት አደገኛ ሁኔታ እንዳይደርሱ ፤ በምንታ ጊዜ ካልሆን ጭራሽ አይለዩዋቸውም ። ጓዊታቸውን ፤ ውዳሴ ማርያማቸውንና መልክ ኢየሱስ ፤ መልክ ማርያማቸውን ቀደም ብለው ይግመው ፤ ረቡእ ፤ ወይም አርብ ካልሆን ፤ ቁርስ ካደረጉ በሁዋላ ፤ ጥላሁን ወደተኛበት ይሄዱና ጭዋታቸውን ይጀምራሉ። እዚያ ጭዋታው ይደራና ፤ ሳቁ ፤ ወካቱው ፤ ሲደምቅ ፤ ሶፊያ ወይም ባላምባራስ እስኪያስታውሱት ድረስ ፤ ጥላሁን ታሞ የተኛ መሆኑን ይረሳና ከባጥ በላይ ይስቃል ።

በቅሎዎች ለማምጣት ፤ ቦንጋ ፤ ወደ ባሻ ነገዎ ቱሉ የተላከው ሰው ከሄደ ካንድ ሳምንት በሁዋላ ፤ አንድ ጥዋት ፤ ባላምባራስ እንደ ተለመደው ቁርስ አድርገው ፤ ጥላሁን ወደ ተኛበት ቤት ቢሄዱ ፤ "ቁርስ አልበላም " ብሎ እሱና ምሽቱ እንደ ተኩዋረፉ ሁሉ ፤ ሁለቱም ዝም ብለው ተቀምጠው ስላገኙዋቸው እንደ መደንገጥ አሉና ።

"ምነው ፤ ምን ሆናችሁ ?"አሉ ።

"ቁርስም ፤ ቡናም ፤ አልቀምስም አለ ፤ ደኅና እየደለም መሰለኝ፤ አይኑንና ፊቱን ይዩት " አሉች ሶፊያ ። የፈራች መሆኑዋ ከፊትዋ ይታወቃል ።

"ምን ሆንህ? " አሉ ፤ ወደ ጥላሁን ቀረብ ብለው ።

"ምንም አልሆንሁ ፤ ደህና ነኝ ። እንዲያው እህል አስጠላኝ እንጂ ደህና ነኝ "

"ካላመመህ . . . እንዲያው እህል ማስጠላት ብቻ ከሆነ ምንም አደል ፤ ግዴለም ። ወዲያ-ወዲህ ማለቱን ትተህ ፤ ያለፈ ትሮህ ብዙ ቀን ስትተኛ ጊዜ ነው " አሉ ባላምባራስ ። ቀዲያ ፤ በተለይ ሶፊያን እንዳት ባባ ለማበረታታት ያክል ያሉት ነው እንጂ ፤ ያይናቹን መደፍረስና የፊቱን መጋም ሲያዩ ፤ እሳቸውም መሰጋታቸው አልቀረ ። በምሳና በራት ጊዜም የሶፊያ ልብ እንዲያርፍ ፤ እያንዳንዱ ትናንሽ ጉርሻ ረገጕችም ጊዜ ባፉ ሲገከራተች እዩቆዩና ፤ አልዋጥም ብሎ እዩታገለው ትንሽ በላ ፤ ነገር ግን ያውም ቢሆን ስላልረጋለት ሶፊያን ይብስ አሳሰባት ። ከሌሊቱ የሚበልጠውን ክፍል እንቅልፍ ባይንዋ ሳይዞር ፤ እንዲሁ እዩ ተገላበጠች ፤ ትንፋሹን ስታዳምጥ ቆያታ ፤ ወደ ዘጠኝ ሰዓት ግድም ሽልብ ሲያደርጋት ፤ ራስዋን ከደረቱ አጠገብ ፤ አልጋው ላይ እንዳሳረፈች ፤ እንደ ሰማይ ቁጣ የሚበርቅ ነገር እጆሮዋ ላይ በረቀና አስበርግጎ አስነ

@OLDBOOKSPDF

ሳት ! ጥላሁን ፣ ከሚፈራው ነገር እንደሚከላከል ፣ ሁለት እጆቹን ላይ ታች እያወናጨፈ ፣ በግሮቹም እየተፈራገጠ ፣ በንቅልፍ ልቡ ይጮህ ነበር ። ሶፊያ ለጊዜው በድንጋጤ ውስጥ እስከለች ፣ የምታደርገው ቅጡ ቢጠፋትና ድንግርግር ቢላትም ፣ ከድንጋጤዋ ስትወጣ ፣ ቶሎ እቅፉ ከንቅልፉ ለመቀስቀስ በሀይል ብትነቀንቀው አልሰማትም ። እንዲያ እጆቹን እያወናጨፈና በግሮቹ እየተፈራገጠ ሲጮህ ብዙ ቆዬ ። ከዚያ በመነቅነቅም ፣ "ጥላዬ እደዚዛህ ንቃ" እያለች በመጮህ ብዛት ስትቀሰቅሰው ትኩሳቱ እንደ እሳት እየተፋጀ ፣ ላቡ በብዛት ይወርድ ነበር ።

"ምን ሆንህ ፣ ምንድነው ?" አለች ሶፊያ ፣ እቅፉ እንደ ያዘችው።

እንድ ከመኪላቱዋ ብዛት የተነሳ ፣ በጣም የምታስደፍ ወሻ ትመጣና ፣ ከሱ ትንሽ ራቅ ብላ ቆማ ፣ በኩሱ መጣያዋ ፣ ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ፣ እንደሰዋ ፣ የከሱና አከላታቸው ሁሉ ረገኸም ጥርስ ብቻ የሆን ቡችሎች ፣ አንጠብጥባ ሜዳውን ትሞላዋለች ። ወዲያው ያ ሁሉ ፣ ረግኸም ጥርስ ብቻ የሆን የቡችሎች መንጋ ፣ ተሰልፎ ወደሱ ሲመጣበት ያይና ፣ ፈርቶ ፣ እየተከላከለ ለመሸሽ ቢሞክር ተስናት ፣ ጉልበቱ አካላቱን መሸከም አቅቶት ፣ ሲዝል ጥርሳሙ የቡችሉች መንጋ ከቦ ፣ እመሀል አድርጎ ይቀራመቱዋል ። ለመከላከል እየተወራጨ የጮኸ ፣ እንዲያ ባለ ስቃይ ውስጥ በነበረበት ጊዜ መሆኑን ሲነግራት ፣ ያ ቅዠትና ፣ ባልዋ በዚያ ጊዜ የነበረበት ሁኔታ ባንድ ላይ ሆኖ አባባት ። ባላምባራስ ፣ አድነው የሚያስነሳት ፣ ወይም እስዋን ከተጫኗት ከባድ ጭንቅ ከፍለው ተሸክመው ፣ የሚያሳርፉዋት ይመስል ፣ ነግቶ እስኪመጡ ቸኮለች ። ትንሽ ቆይቶ ፣ ከሚቀራመቱው የቡችላ መንጋ ሲታገል ያላበው ላብ ጠፈፍ አለ ። ትኩሳቱ ግን ምንም ለውጥ አላሳዬም ። ጥዋት ባላምባራስ ሲመጡ ፣ ጥላሁን እመሙ ጸንቶበት ፣ ትንፋሹ ቁርጥ ፣ ቁርጥ ሲል ፣ ሶፊያ በሱ እመም መጽናት ግራ ገብቶዋት ስላገኙዋቸው ፣ እሳቸውም ብርቱ ስጋት አደረባቸው ። ነገር ግን ሶፊያ እንድታውቅባቸው ስላልፈለጉ ፣ ያልሰጉ መስለው ፣ እንዳትሰጋ ለስዋ የሚያበረታታ ምክር መስጠት ጀመሩ ።

ከዚያንለት በሁዋላ ፣ በተከታታት አራት ቀናትና አራት ሌሊቶች ፣ ሶፊያና ባላምባራስ ጉደታ የሰነበቱበትን ጭንቅ ፣ እግዚአብሄር እንኩዋን ለሰው ፣ ለሰው-በላ ፣ የዱር አውሬ አይበለው ! ጥላሁን መቸም እእምሮውን ስለማያውቅ ፣ የነበረበት ጣር አይሰማውም ። ከትኩሳቱ ብዛት የተነሳ ፣ ሰውነቱ እንኩዋንስ ነኪተወት ፣ ገና ሲቀርቡት ፣ እንደሚነድ እሳት እየለገጠ ፣ ሳይበላ ውሀ ብቻ ተልቶሎ ሲጠጣ የማያቋርጥ እግ

@OLDBOOKSPDF

ባት እያገበው ፣ ከዚያ ሁሉ ሌላ ፣ ከዚያ ሁሉ የባሰ ፣ ሲቃኘር ሸሽቶው የተሸሸጉበትን ምስጢር አዩትናገረ ፣ ምን እንደሚያደርጉ ቅጡን እስ ጠፍቶዎቻቸው ነበር ።

"እስቲ እባካችሁ!" ይላል እግባቱ ፋታ ሲሰጠው ። "እስቲ እባ ካችሁ! አሁን ቀኛዝማች ዳኘን ስለ ገደልን ፣ መንግስት የሚቀጣን ይመ ስላችሁዋል? እኔያን . . . በሰው መልክ የተሰሩና ፣ በሰው ስም የሚጠሩ፣ አውሬ ገድለን ፣ የየኪን ህዝብ ነጻ ስላደረግነው ነው መንግስት የሚቀጣን? መንግስት ይህን አያደርግም ፣ በጭራሽ መንግስት ይህን አይሰራም! እሁ-ሁ-ሀ . . .! አይ መንግስት! መንግስት ቀኛዝማች ዳኘ አደሉም እንዴ! ሌላ መንግስት አለ? ሶፈያን እንዳያንገላቱብኝ ብዬ ነው እንጂ . . . እኔስ አልሸሸግም ነበር! እኔስ በቀጥታ ፣ ወደ ጃንሆይ አደ ባባይ ሄጄ ፣ አፈክር ነበር! ለማችን ደግሞ ፣ ሰው የገደለ ይመስል ለምን ተሸሸገ? እሁ-ሁ-ሀ . . .! ወዬው ጉድ! ደግሞ የስማችን መሸሸግ ይባስ! ግደለም ፣ የሆነው ይሁን ፣ በሶፈና በኔም የደረሰ ይድረስ ፣ እንኩ ዋን እኒያን የመልካም ስራና የመልካም ስረ ጠር አስወገድናቸው ። ገደልናቸው! ከንግዲህ ምንም ቢሆን እንደሳቸው ያለ ክፉ አይፈጠር!"

ጥላሁን የሚናገረውን ፣ ሌላ ባእድ ሰው ፣ ግራዝማች ጉርሜሳ ጭምር እንዳይሰሙ ፣ ሶፈያና ባላምባራስ የፈጠሩት ዘዴ "ውሽባ ገባ" ብለው ከሶፈያ በቀር ፣ ከባላምባራስ ጀምሮ ፣ ማንም ሰው ብተኛበት ቤት እንዳይገባ መከልከል ነው ። ባላምባራስ ፣ ተሰርቀው እዩገቡ የሚ ያዩትና ሶፈያን የሚያበረታቱትቸ ፣ ግራዝማች ጉርሜሳ ወደ ውጭ ወጥ ተው እንደሚቆዩ ካረጋገጡ በሁዋላ ነበር ።

"ወዴት ልትሄድ ነው? ምን ጊዜ ትመለሳለህ?" ይላሉ ባላ ምባራስ ፣ ያንታቸው ልጅ ወደ ውጭ ለመሄድ መንገድ ሲጀምሩ ። ከዚያ በሁዋላ ፣ መራታቸውንና በሄዱበት የሚቆዩ መሆናቸውን ሲያረ ጋግጡ ፣ ሶፈያን የሚያበረታቱበት ምክርም ፣ እንደ ጥላሁን በጽኑ ታምሞ የዳነ በሽተኛ ታሪክም ፣ የሚያውቁትን ያክል ፈልገው ፣ በዚያ ላይ ፈጥረው ጨምረው ይይዙና ይገባሉ ። ከዚያ ፣ ቀረብ ብለው የሱን ሁኔታ ካዩ በሁዋላ ወደስዋ ተመልሰው ፣ እንደሱና ከሱም የባሰ በጽኑ ታምመው የዳኑ ፣ ሲፈልጉ አድረው ፣ ወይም ውለው ያገኙዋቸውንም ከሌሉበት የፈጠሩዋቸውንም በሽተኞች ታሪክ ተርከው ፣ እሱም እን ደነሱ እንደሚድን ፣ ምንም እንደማይሆን ፣ የማምላክ ባለ ቃል ኪዳን እንደሆኑ ሁሉ ፣ በማምላክ እዩማሉ ያረጋግጡላታል ።

"እንጃ! እንዲህ . . . ይህን ያክል ቀን ከህል ተለይቶ ፣ እንዲህ ነድዶ ፣ እንዲህ ከስሎ የሚድን አለ? እንዲህ ሆኖ የሚድን ያለ አይመ

@OLDBOOKSPDF

በሉኝም ፤ አይደንም ፤ ይሞታል ! ብቻ ፣ ብቻ አንድ ነገር ልንገርዎ እባካ እሱ ሲሞት ፣ እዚህ . . . ቋጭ ብሎ የሚያይ አይምሰልዎ ! የለም ፤ ቋጭ ብሎ አላይም ! የሚሞት መሆኑን ቁርጥ ካወቅሁ ፣ ቀድሜው ነው የም ሞተው !” ብላ እሳቸውንም ግራ ይገባቸውና ፣ ማበረታቻው ሁሉ ፣ የው ነቱም ፣ ያሰቡም ምላሹ ሁሉ ፣ ያልቅባቸውና ፤

“የለም ! ምንም ቢሆን ልጁ አይሞትም ! እግዚአብሔር ዳኝነቱን ቅኑ እንደሆን እንጂ ፣ በመንበረ ጸባኦት ያለ እንደሆን እንጂ ፣ ለድሀ የቆመው ፣ የድሀ ጠበቃው ልጁ አይሞትም ! ” ይሏቸው ፣ እርስዎን መር ቃት ፣ ወይም ማበረታት ሲያቅታቸው ፤ “ሞቱሁን ሲሞት አይገባወም” የሚሊቡትን ምክንያት እግዚአብሔር ወደሚያስችልበት ፣ እግዚአብሔር ዳኝነት ወደሚያይበት ፣ ወደ ላይ እንጋጥጠው እያመለከቱ !

ኳራት ቀንና ኳራት ሌሊት በሁዋላ ፣ ባራተኛው ሌሊት ንጋት ላይ ሶፊያ ፊናዋን አብርታ ተቀምጣ ፣ ራስዋን ዘንበል አድርጋ ከልቡ አጠ ገብ ፣ አልጋው ላይ እንዳሳረፈች ፣ የተጠራቀመ እንቅልፍ ከብዶዋት አይኖችዋን ለበስ ስታደርግ ፣ ሀይለኛ ኩረር ፣ ካፉ አጠገብ በተደቀነው ጆሮዋ ውስጥ እንደ ነብር ስባጉራራባት ፣ ደንግጣ ተነሳች ። የደከመ በሽ ተኛ ሲያንኩዋርር ከፉ መሆኑን ፣ ወደ ጉዞው መጨረሻ የተቃረበ መሆኑን ታውቃለች ። ታዲያ መጨረሻው መሆኑ ነው ? መጨረሻው ከሆነ የሰዋም መሆን አለበት ! እንዲያውም የሱን መጨረሻ ሳታይ ፣ የሰዋን ማስቀደም አለባት ! የሱን ሞት ሳታይ የሰዋ ሞት እንዲቀድም ግድ ረግዋ ፣ የሰዋ ሞት ለሱ ሞት መንገድ መሪ ፣ መንገድ ጠራጊ እንዲሆን መወሰንዋ ሲታሰባት ፣ ሲቃ ያዛትና ፣ ልብዋ በደስታ ጋለና ፣ ወጋገኑ ፊትዋን ሁሉ አበራው ። ከዚያ ፣ ሀይወትዋን የምታላልፍበት ዘዴ አስ ቀድሞ የተጠና ስለ ሆነ ፣ የሱ መጨረሻ መሆኑን ስታረጋግጥ በጥቂት ደቂቃዎች ለመቅደም ወስና ደፋ-ቀና እያለች ፣ ጆሮዋን በደረቱ ላይ እያደረገች ኩረሩን ታዳምጥ ጀመር ። ያ ኩርር፣ ጠለቅ ብሎ ከስር የሚ መጣ እንጂ ፣ ከላይ ከላይ የሚተነፈስ ትንፋሽ አይለም ! ከዚያ ተነስታ ወዲያ-ወዲህ ስትል ቆይታ ፣ እንደገና ተቀምጣ ጆሮዋን በደረቱ ላይ አድርጋ ስታደምጥ ፣ ትንፋሹ ከቀድሞው ጠለቅና ዘለግ ፣ ኩረሩ ቀነስ እያለ ሄደው ፣ በመጨረሻ ኩረሩ እንዲያውም በጭራሽ ጠፋና ጥሩ ትንፋሽ በረኸሙ ይተነፍስ ጀመር ።

“እግዚአብሔር ምህረት ሲያወርድ ይሆን ? ማን ያውቃል ! ” ብላ ለጠፉቀችው ጥያቄ ራስዋ መልስ ሰጥታ ፣ ደግሞ እንደገና ተነስታ ወዲያ-ወዲህ ትል ጀመር ። መንጋቱን በድምድሙና ከሱ በታች ባለው

@OLDBOOKSPDF

ማገር መሀከል ፣ ባለፈው ሚጋሩ አልፎ የሚገባው ብርሃን በሰ ነገራት ፣ ግራዝማች ጉርሜሳ ወደ ውጭ ሄደው ባላምባራስ ጉዲታ የሚመጡበትን ጊዜ ከተደጋጋሚው ይበልጥ በናፍቆት እየተጠባበቁት ወዲያ-ወዲህ ማለትዋን ቀጠለች ። እንዲያ ወዲያ-ወዲህ በትል ትቆያለ ፣ ቆማ ትመለከትዋለች ። ትንፋሹ ጠለቅና ዘለቅ ከማለቱም ሌላ ፣ እንደ መበንበጃው አያወራጭም ። ፊት ብቻ ፣ እንዲያ እንደለዋ ፊት ብሎ ቆዎ ሲያዩት ፣ እሳት እንደ ፈጀው ጉርብርብ ያለ ይመስላል ።

“ምንድነው ? የፋናው ብርሃን ይህን እንዲህ ያነረበ ያስመሰለውን እንዲህ እሳት ያቃጠለው አስመስሎ ያሳዬው ? ” አለችና ፣ ፋናውን በጠርሙስ አፍ ተሰኩቶ ፣ በፊለባው አጠገብ ከተቀመጠበት አንስታ ይዛ ፣ ቀረብ አለችና ብትመለከት ፣ የፋናው ብርሃን አለመሆኑን ፣ ከፋት እንዳዩትው የተጉረበረበ የመሰለ ትንንሽ ፣ ቀያይ ነገር ፊቱን ሁሉ የወረሰው መሆኑን አዩች ። ያ ትንንሽ ፣ ቀያይ ነገር ሚፍ ሚፉ የሸለ ነው ። ፋና የተሰካበትን ጠርሙስ በጅዋ ይዛ ፣ አይኖችዋን ሳታረግብ በባልዋ ፊት ላይ እንደ ተከለች ፣ አሳብዋ ወደ ሁዋላ ተመልሶ ፣ እስከ ጎሬ ተጉዞ ፣ አሜሪካኑ ሀኪም ፣ ዶክተር ሰቲዋርት ፣ ያካባቢውን ህዝብ አዘውትረው ፣ እየተመላለሱ ስለሚያጠቁት በሽታዎች ሲያስተምሩዋ ቸው የሰነበቱትንና ፣ ሁዋላም ጽፈው የሰጡዋችውን ከጥላሁን በሽታ ጋር ታስተያይ ነበር ። ከመጀመሪያ ጀምሮ ፣ የትኩሳቱ ብርታት ፣ ውሀ-ውሀ ማሰኘቱ ፣ ማገሙ ፣ ማቃዠቱ ፣ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ማለቱና ፣ ያ እንደ እከክ ያለ ነገር ባካላቱ ሁሉ ግንፍሎ ከወጣ በሁዋላ ፣ ሁሉም ታገስ ማለቱ ፣ በለ ፈንጣጣ ያስተማሩዋቸውንና ጽፈው የሰጡዋቸውን ይመስላል ።

“ፈንጣጣ ይሆን ? ፈንጣጣ ከሆን ከወጣ በኋላ እምብዛም ቲም አይኖውም ! ” አለችና ፣ በባልዋ ላይ እንደ ተተከሉ ፈዝዘው የቆዩ አይኖችዋን እያርገበገበች ተነስታ ፣ ፋናውን በነበረበት አስቀምጣ እንደ ገና ወዲያ-ወዲህ ማለትዋን ቀጠለች ። ጥላሁን ከኩሉ-ሌሊት በሁዋላ የጀመረውን እንቅልፍ አላቋዋረጠም ፣ ጸጥ እንዳለ ቀጠለ ። ቀን ሆና ውጪ ጸሐይ ቢሆንም ፣ ጥላሁን የተኛበት ቤት መስኮት የሌለውና ብዙ ብርሃን የማይበጥ ስለሆን ፣ ሁልጊዜ ፋና እንደ በራ ነው ። ባላምባራስ ጉዲታ እንደ ልማዳችው ግራዝማች ጉርሜሳ ሲወጡ ወደ‐ት እንደሚ ሄዱ ፣ ምን ጊዜ እንደሚመለሱ ጠይቀው ጥላሁንን ለመጠዬቅና ከሱፊያ ጋር ለመነጋገር የሚበቃ ጊዜ እንዳላቸው ሲያረጋግጡ ፣ እስዋን የሚያበረታቱበት ምክርም፣ከሱ በጸና ታምመው የዳኑ በሽተኞች ታሪ ክም ፣ አጠረቃቅመው ይዘው ፣ ያ እሌለ ቀን በጎ ያቆያቸው ክፉ ባለ

@OLDBOOKSPDF

ማወቃቸው ልባቸው እዩፈራ ኅሰ ብለው በጥፍሮቻቸው እየቆጡ ገቡ ። ከዚያ አይኖቻቸውን ባንድ አፍታ በበሽተኛው ላይ አሳርፈው ትንሽ እንደ መስገድ ካሉ በሁዋላ ፣ ምስጢር እንደሚናገሩ በሹክሹክታ ፤ "እግዚር ይማርህ" አሉና ፣ ወደሰዋ መለስ ብለው "እንዴት አደረ ?" አሉ።

"በድካም ይሁን በንቅልፍ ምክንያት አላውቅም ፤ ጸጥ ብሎዋል። እንዳልቀሰቅሰው ፈራሁ ። ትንፋሹ ደህና ይመስላል ። ደግሞ በፊቱ ላይ እንደ እከክ ያለ ነገር 'ሽፍፍ' ብሎ ወጥቶበታል ። እስቲ ይዩት ።" አለ ችና ፣ ፋናውን ይዛ ወደ በሽተኛ ባልዋ ቀረብ ስትል ፣ ባላምባራስም አብረዋት ጎንበስ ብለው ፊቱን ሲመለከቱት ፣ ሲያጠኑ ቆይተው ፣ ጥላሁን ከታመመ ጀምሮ ታይቶ የማያውቅ ፈገግታ በውብ ፊታቸው ላይ እንደ ጎህ ወጣ ብሎ ወደሰዋ ቀና አሉና "እነወቶቴ !" አሉ ።

"ምንድነው እነወቶቴ ?"

"እናንተ አታምኑበትም ። ነገር ግን በኛ በባላገሮች ዘንድ ፣ 'እነወቶቴ' የምረት መላክተኞች ፣ ምረት ይዘው የሚመጡ . . . ዛሮች ናቸው። ይህ እፊቱ ላይ የምታይው 'ኩፍኝ' ነው ፤ እዚያ በናንተ በኩል 'ፈንጣጣ' ትሉታላችሁ ። ኩፍኝ ፣ ወይም ፈንጣጣ ፣ የሚደፍንና የሚወጣ ፣ ሁለት አይነት ነው ። ታዲያ የሚደፍነው ፣ ክፉ አደገኛ ነው ፤ ነገር ግን እግዜር የምረት መላክተኞቹን ፣ እነወቶቴን ልኮ ፣ ከውስጥ እንዲህ እንደሱ ወደ ውጭ እንዲወጣ ሲያደርጉት ፣ ምረት ወረደ ማለት ነው ። ይሆን ጊዜ በባላገር ዘንድ ቢሆን ኖሮ ንፍሮ ተቀቅሎ እዩተበላ ፣ ቡና እዩተፈላ ፣ የምረት ስራ ስለ ሰሩ ፣ ለነወቶቴ ይዘፈንላቸው ነበር !" አሉ ባላምባራስ ፣ እሁንም ፈገግ ብለው ። ከዚያ ፣ ጥላሁንን ጸጥ ብሎ እንደ ተኛ ሲመለከቱ ቆይተው ፣ 'ተመስገን አምላኬ ! እንግዲህ ልጄ ምንም አይሆን' አሉ ፣ አምላክን ሲያመሰግኑ ራሳቸውን አምላክ ወዳ ለበት ፣ ወደላይ አይኖቻቸውን ቀና አድርገው እያዩ ።

"እሱቱ እንዳፍም ያድርገልኝ !" አለች ሶፊያ ።

እነወቶቴ ምረት ይዘው መጥተዋል ፤ አይዞሽ እንግዲህ ያመጡትን ምረት መልሰው አይወስዱትም ፤ እንዘፈንላቸው !" አሉና ባላምባራስ ፣ እንዲያ ባለ ጊዜ ሲዘፈን የሰሙትን ዘፈን ፣ በመጥፎ ድምጻቸው ይዘፍኑ ጀመር ።

"እነወቶቴ ፣ እንግሬ !
"ማሩልኝና ፣ ልንገር ወሬ ።
"እነወቶቴ ፣ የርጎ ለጋ !
"ማሩልኝና ፣ ልቤ ይርጋ ።"

@OLDBOOKSPDF

"ቢታ እንግዲህ ምንም የለበት ፤ ብቻ በጥሩ የሆነ ሰው ባጠገቡ እንዲደርስ አጥብቆ መጠንቀቅ ነው" ሲሉ ፤ ሶፊያ ፤ አንድ ልትናገር እናዋ የደረሰውን ነገር ሠ ልሳ ስትይዝ ፤ የቅርታ ፈገግታ በፊትዋ እልፎ ሲሄድ ታዬ ።

"ይህ መድሀኒት ደግሞ ለምን ነው ?" አሉ ባላምባራስ ፤ በርከት ያሉ ፤ ቀያይ ድብልብል መድሀኒቶች ፤ ከብልቃጣቸው ተዘርግፈው ፋናው በሚቀመጥበት ሳጥን ላይ አንድ ብርጭቆ ውሀ ጥምር ሰላዩ ።

"ኦ . . . ! ምንም አይል ፤ ጊዜው ያለፈበት መድሀኒት ስለሆነ ፤ ልጥለው አውጥቸው ነው ፤" አለችና ሶፊያ ፤ አንዱ መድንገጥ ብላ ፤ በብልቃጥ ውስጥ የነበረውንም ፤ የተበረገፈውንም መድሀኒት ባንድ ነት ፤ በሚገጥ ስር ጥላ ፤ እዚያው እየረገጠች ደቋቁሰቻቸው ። ባላምባራስ ፤ ጥላሁን የሚጥት የሆነ እንደሆን ፤ እሱን ለመቅደም ያሰናዳችው መሳሪያ መሆኑን አልጠረጠሩም ።

ጥላሁን ፤ ፈንጣጣው ከመጣለት በሁዋላ ፤ እንደ ጤፍ ትናንሽ የነበረው ያተር መልክ ፤ እዬያዘ ትላልቅ ከመሆኑና ፤ እሰበሱ እዬ ተገናኝ ባካላቱ ሁሉ ከመጠፍጠፉ በቀር ፤ ትኩሳቱ በዬቀኑ እዬወረደ ሄዶ ወደ መደበኛ መጠኑ ተቃረበ ። መቃጠቱም ቀርቶ ፤ የእእምሮው ባለቤት እዬሆነና እእምሮውን እያዘዘ ፤ እእምሮውን እዬገዛ ሄደ ። እሱ ሁሉ ስለቆሰለ ፤ እህል ጉሮሮ ማለመጥ ይቸግረው እንጂ ፤ የመብል እምሮቱ በጥፍ እዬተመለሰ ስለሄደ በጠቅላላው ፤ ባልታዬ ፤ ባልታ ወቀ ምክናያት ድንገተኛ ከፉ ካልደረሰ ፤ ለህይወቱ በጣም እስፈርቶ ከነበረበት ሁኔታ የወጣ መሆኑ የተረጋገጠ መሰለ ። የቆሰሉ ነገር ግን አይነገርም ። ቁስሉ በጣም በረታበት ። ያ በመሉ አካላቱ የተዘራ ጤፍ ይመስል የነበረ ጥቃቅን ነገር ፤ እተር እተር አካክሎ ፤ ወዲያው እሰበሉ ባንድ ላይ ተጋጥሞ መግል እዬያዘ ሲፈርጥ ፤ ያን የተነፋረቀ አካላት እንኩዋንስ መንካት ፋቅ ሆኖ ማየቱ ያሰቅቃል ። ሶፊያ ፤ ዶክ ቶር ስቲዋርት የጸፉትን መመሪያ ተከትላ ፤ ጠጉሩን እስከ ቁስሉ አስጠ ግታ ፤ ባጭሩ ቆርጣ ፤ ፐርማንግኔት በቀጭኑ በጥብጣ ፤ ያን በጥጥ እዬ ነከረች ገላውን ቀልቶሎ ታጥበዋለች ። ሆዱ እንዳይደርቅ እዚያ አገር የሚገኙ ፤ እንደ ፓፓያ ያሉ ፍራፍሬዎች ጭማቂና ለላ ለላም ፈሳሽ ምግብ ትመግበዋለች ፤ ከተኛበት ቀና ለማድረግም ሆነ መልሶ ለማስ ተኛት ፤ ወይም ለማገላበጥ ፤ ካካላቱ እጅ ሊያርፍበት የሚችል ቦታ ስላልነበረ ባላምባራስ እዬረዱዋት ከትምንጣፉ ፤ ማለት ምንጣፉን ከራ ስጌ ፤ ከግርጌ ፤ ወይም ከጎንና ከጎኑ በመያዝ ፤ እያነሳችና እያስተኛች

@OLDBOOKSPDF

ወይም እያገላበጠች ስታስታምመው የነበረው ችግር ብርቱ ነበር ። ብቻ የሚወዳትን ማኅሌትን የሚሰጠው ደስታ እያበረታታት ፥ ድካም የሚሉት ነገር አይሰማትም ነበር ! እስቸጋሪ የሆነባት ፥ ሀኪሙ በመመሪያው ላይ የጻፉትን የሚነስነስ ዱቄት ፥ እዚያ ማግኘት ስላልቻለች ፥ የቆሰለ ገላው ከሚተኛበት ምንጣፍ ጋር ሲያያዝና ፥ በሚገላበጥበት ጊዜ ፥ የተያያዘውን ለማላቀቅ ሲሞከር ፥ ከሚሰቃዩው ስቃይ የሚያርፍበት ይዱ ማግኘቱ ነበር ።

"እኛ በባላገራችን የምናደርገውን ብንገራችሁ ከንቱ ላታደርጉት ፥ እንዲያው መላቂያ ለመሆን ፥ 'ለምን እሬን አበላሻለሁ' ብዬ ነው እንጂ ፥ እኛኮ ለዚህ መድሀኒት አለን" አሉ ባላምባራስ ጉዳታ ፥ ሀኪሙ በጻፉት መመሪያ ያመለከቱት ዱቄት ቢገኝ ኖሮ ያ ፥ ስቃይ ይደርስበት እንዳልነበረ ሶፊያ እያዘነች ስትናገር ።

"እንዴት ያለ መድሀኒት ? እሱቂ እንሰቅም ይንገሩን " አለች ሶፊያ።

"አመድ ፥ ንጹህ አመድ ፥ ከሰል ፥ ወይም ሌላ የሚነረብጥ ነገር እንዳይኖርበት ፥ ጥቅጥቅ ብሎ በተሰራ ወንፊት ነፍቶ ፥ ንጹሁን አመድ በሚተኛበት ምንጣፍ በርከት አድርጎ እዩነስነሱ ፥ እዩገዘንቡ እዚያ ማስተኛት ! " አሉ ባላምባራስ ።

"ይሀማ ግሩም ነው ፥ አባባ ! ታዲያ እንዲያ ሲሰቃይና ፥ እስ ዎም ፥ እኔም ፥ ያን ያክል ስንቸገር ለምን እስከ ዛሬ አልተናገሩ ?" አለች ሶፊያ ፥ አሳባቸውን ያለምንም ማመንታት ተቀብላ ። ማኅሁ ንም የባላምባራስን አሳብ ሲሰማ ፥ ያ አሳብ ያንጊዜውኑ በስራ ውሎ ከሰነበተበት ስቃይ እንዳላረፈውና ፥ የናፈቀውን እንቅልፍ እስኪጠግብ መተኛት እንዳስቻለው እጅግ ደስ አለው ። እንዲያ ደስ መሰኘ ቱንና ፥ "እግዚአብሄር ይስጥዎ" ብሎ የሚያመሰግን መሆኑንም ፥ አፉ በሰ ቆሰለ መናገር ባለመቻሉ ፥ አይኖቹን እግዚአብሄር ወደሚ ኖርበት ፥ ወደ ሰማይ ፥ እንስቶ እንደገና ወደ እሳቸው በመመለስና ፥ የቆሰለ ፊቱ ሊያሳዩው ከሚችለው ፈገግታ ጋር ራሱን መላልሶ ላይ ታች በመንቅንቅ ገለጸ ።

"እቤት ውስጥ ያልተጠረገ አመድ ያዩንበት አይናችን ታመመ" የምትሉ ሰዎች ፥ ምንስ ያክል ቢቸግር . . . እርጌ ድመት ይመስል 'አመድ ጎዝጉዛችሁ ተኙ' ስላችሁ ፥ ትቀበላላችሁ ብዬ "እንዴት ልጠ ርጥር ?" አሉ በባምባራስ ፥ ያሽሙር ፈገግታ ባስጌጠው ፊት ፥ ሶፊ ያና ጥላሁን አንዳንድ ጊዜ የኪ ፥ እባላምባራስ ቤት ሲሄዱ ፥ አመዱ ባለመጠረጉ የሚነቅፉዋቸውን አስታውሰው ።

@OLDBOOKSPDF

ጥላሁን ፣ በምንጣፉ ላይ አመድ እየተንሰንሰበት መተኛት ከጀ መረ በሁዋላ ፣ የቆሰለ ሰውነቱ ከምንጣፉ ጋር መያያዙና ያን ለማላ ቀቅ ሲሞከር የነበረው ስቃይ ቀረ ። የቆሰለ አፉንና ጉሮሮውንም በጨው ውሀ ሲታጠብና ሲግሞጠመጥ ፣ ትንሽ በትንሽ እያለ ፣ ከፈ ሳሽ ወደ ለስላሳ ፣ ከዚያ ማናቸውንም ምግብ አላምጦ ወደ መዋጥ ደረሰ ።

የጥላሁን ፈንጣጣ በወጣበት ሰሞን ፣ ባሻ ንጉሥ ቱሉ ከቦንጋ የላኩዋቸው ሰበት በትሎዎችና ሚኒዎቻቸው ደረሱ ። ብቻ ከሞት ቢተርፍም ድኖ ረዥም ጉዞ ለመጉዋዝ አስኪችል ገና ፣ ዘለግ ያለ ጊዜ እንደሚወስድ የታወቀ ነው ። እስከዚያ ፣ "በትሎዎች ሚዜን ተፈረ ይቆዩ" የተባለ እንደሆነም ዝንብ ይፈጅዋቸዋል ። ስለዚህ ወደ መጡ በት ተመልሰው በሰስተኛው ሳምንት ላይ እንደገና እንዲልኩዋቸው ለባሻ ንጉሥ ያደራ ደብዳቤ ተጽፎ ተመልሰው ሄዱ ። እንዲሁም በዚ ያው ሰሞን ፣ አንድ ጥዋት ፣ ባላምባራስ ጉዲታ ግራዝማች ጉርሚሳን ወደ ወጭ ሲሄዱ ተሰናብተው ፣ ጥላሁን ወደ ተኛበት ገብተው እን ዴት እንዳደረ ከጠየቁና ፣ እንደ ልማዳቸው ካበረታቱ በሁዋላ ፣

"ከንግዲህ ወጣለት ፤ በቃ !" አሉ ፣ ጥላሁንን ሲመለከቱ ቆይ ተው በደስታ የበራ ፊታቸውን ወደ ሶፊያ መለሱና ። "ብቻ" አሉ ወዲያው ከተል አድርገው ። "ብቻ ብዙ ጊዜ መላልሼ እንደ ተናገርሁት በጥላ የሆነ ሰው እዚህ እንዳይደርስ ፤ እንዲያው እዚህ ትውር እን ዳይል አጥብቆ መጠንቀቅ ነው ። ከንግዲህ ላይንም ፣ ለ. . . ሌላም የሚያሰጋው ጥላ ነው ።"

"መቸም ከኔና ከስዎ በቀር እዚህ የሚደርስ የለ ፣ አባባ ! ስለ ዚህ . . . እኔ ምንጊዜም ፣ ሌትና ቀን ከዚህ ተለይቼ ስለማላውቅ ፣ በሽተኛችን በጥላ ምክንያት እርስዎ እንደሚሉት ክፉ ነገር ቢደርስ በት ፣ ባላፊነት የሚያዙ እርስዎ ብቻ መሆንዎ ነው !" አለች ሶፊያ ፣ ቀልድዋን ትንሽ እንደ መሳቅ ብላ ።

"እረ ምን ቸችል እግዚአብሄር ! ደግ እንዲህ ያለም አለ ? እንደ ገና !" አሉና ባላምባራስ ይስቁ ጀመር ። "ትመስገን ጌታዬ ፤ እንዲህ ለቀልድና ለጭዋታ ያበቃሽኝ !" አሉ ፣ ወዲያው ቀጠል አድርገው ፣ ወደላይ እያዩ ። ከዚያ ዝም ብለው ትንሽ ሲያስቡ ቆይተው ፣ "በቀ ደም . . . የልጄ በሽታ ፈንጣጣ መሆኑ እንደ ታወቀ ፣ እንቺ ወጥቶ ላሽ እንደሆነ ብጠይቅሽ 'ወጥቶልኛል' ብለሽኝ ነበር ፤ እርግጠኛ ነሽ" አሉ ፣ "የልጄ" ሲሉ ጥላሁንን በዓይናቸው እያመለከቱ ።

@OLDBOOKSPDF

"ያው ምክሩ !" አለች ሶፊያ፣ ከግራ አይንዋ በታች ወዳንድ ትንሽ የፈንጣጣ እንጉዝ እያመለከተች ። "ለመሆኑ ዛሬ ሰምን አለ ቡት ?" አለች ወዲያው ቀጥሏ ።

"ኢመንጀር ቦሌ ሰራተኞች ሰፈር የገባው በሽታ ኩፍኝ ፤ እና ንጉ ፈንጣጣ የምትሉት ሆኖ ተገኘ ፣ የልጅቱ ባለቤት ከበቡት ፈረ ንጆችን ለምኖ ከታቢያኝ አምጥቶ ፣ ያልታመሙትን ሰራተኞችም ፣ ከከተማው ህዝብ የሚፈቅዱውንም ሁሉ ፣ በነጻ ያስከትባል" ብሎ ግራ ዝማች ጉርሚሳ ልጆቹን ሊያስከትብ ሲወስድ ስለ ነገረኝ ፣ ምናል ባት . . . የወጣልሽ ለመሆኑ ትንሽም ቢሆን ትጠራጠሪ እንደሆነ ፣ "ብትከተቢ አይከፋም" ብዬ ነው ። "ይህ . . . የፈረንጁ ክትባት ፣ እን ደኛው . . . እንደበሻው ክትባት አያስቸግርም ፤ ደህና ነው"

"ደግሞ ያበሻ ክትባት የሚባል አለ ? እንዴት ያለ ነው ?" አለች ሶፊያ ፣ ተገርማ ።

"ያበሻ ክትባት አታውቂም ? ያበሻ ክትባት እንደ ፈረንጁ መርፌ አይለም ፤ ፈንጣጣ ከወጣበት ሰው ላይ ፣ ከቁስሉ ትንሽ ይወስድና ያልወጣበት ሰው ትከሻ ፣ ወይም ቃፉ ተበጥቶ እዚያ ይቀበራል ። ወዲያው ፣ ያ ተበጥቶ የበሽተኛው ቁስል የተቀበረበት የጤነኛ ሰው አካል ፣ አካባቢው ትንሽ ይቆስልና ይድናል ፤ ይህ ነው የጥንቱ ያበሻ ክትባት የሚባለው" አሉ ባላምባራስ ።

"ያበሻ ክትባት የሚሉት ነገር መኖሩን ገና ዛሬ መስማቴ ነው ። 'ፈንጣጣ የወጣልሽ ለመሆኑ ትጠራጠሪያለሽ ወይ' ላሉት በፍጹም አልጠራጠርም ፤ ወጥቶልኛል ። ለመሆኑ . . . እዚያ ታምመው ያሉና ትው ሰዎች ሁሉም . . . በጎ ሆነው ይሆን ?" አለች ሶፊያ፣ ትንሽ ገዝም ብላ ቆይታ ።

"ያ ይታዥ የነበረውና ፣ ለሰመሽ ባናዬው የመጣን አንድ በሽ ተኛ ፣ እንዲሁም ሁዋላ ከታመሙት አንዱ ጭምር ፣ በጠቅላላው ሶስት ሞተዋል ። ያውም እኛ ለገብኘት የሄድን እለት ባለቤቱ 'ሁለት ልጆቹ ሞቱብኝ' ብሎ ከነገረን ሌላ ነው ። 'ሌሎቹ ደነው የወጡም ፣ ገና በማገገም ላይ ያሉም አሉ' ብሎ ባለቤቱ ነገረኝ አለኝ -ግራዝማች ።"

"አይ . . . ! ያ ይታዥ የነበረውም ሞተ ?" አለች ሶፊያ ፣ ደን ግጣ ። ጥላሁንም አፉ ገና እንደ ቆሰለ ስለነበረ መናገር ባይችልም፣ አይናቹን ለበስ አድርጎ ራሱን ግራ ቀኝ ሲወዘውዝ ግዙኑ ይታይ ነበር።

@OLDBOOKSPDF

"ኢሰብ . . . እንኳዋ ዋዋ ! እኔ መቸም በሱ ሞት በጣም ነው ደስ ያለኝ !" አሉ ባላምባራስ ፤ የሚሉትን ከፊታቸው ማየት እንደ ሚችሉ ፤ መጀመሪያ ሰፊያን ከዚያ ጥላሁንን ፤ ሁዋላ እንደገና ሰፊያን እያሰዋወጡ ፤ እየተመለከቱ ።

"ምነው ! ምነው አባባ ! ዛሬ 'ከርስዎ አፍ ይወጣል' ብዬ የማልጠረጥረውን ነገር ሲናገሩ ሰማሁ !" አለች ሰፊያ ገርሞዋት ፤ አፍዋን በሁለት እጆችዋ ይዛ ። ጥላሁንም እንዲሁ በመገረም አይናቸውን ፍጥጥ አድርጎ ያያቸው ጀመር ።

"ወዬው ጉ . . . ድ ! ደግሞ መገደላችን ቢቀር . . . እግዜር ሲገድልልን ደስ መሰኘታችን ይቅር ? ይህማ ምስጋና-ቢስ መሆን ነው !"

"እንዴት ? ምን ማለትዎ ነው ?" አለች ሰፊያ ፤ አሁንም በመገረም አይን ባላምባራስን እያየች ።

"የነፍስ – ገዳይ ምስጢር የሚያውቅ ሰው ፤ ካልተገደለ ስለሚያስገድል ፤ በግድ መገደል አለበት ! ስለዚህ እኛ ልንገድለው የሚገባን ፤ እግዜር ሲገድልልን ደስ ብሎን ማመስገን አይገባንም !" አሉ ባላምባራስ ፤ አይናቸውን ፍጥጥ አድርገው ሰፊያንም ፤ ጥላሁንንም በየተራ እያዩ ። ሰፊያና ጥላሁን ዝም ብለው አስበባቸው ከተያዩ በሁዋላ ፤ ለጊዜው መልስ ባይናገሩትም ፤ በባላምባራስ አባባል የማይስማሙ መሆናቸውን ራሳቸውን ግራ – ቀኝ በዝግታ በመወዝወዝ ገለጹ ። ብቻ የዚያ ምስጢር አዋቂ ፤ የሚያውቀውን ምስጢር ሳያወጣ መሞት ተገቢ መሆን አለመሆኑን መፍረድ ፤ ለህሊናቸው አስቸጋሪ ቢሆንም ፤ ለልባቸው ሙሉ እረፍትን ፤ ሙሉ ጸጥታን የሰጠ መሆኑ አይጠረጠርም ። የዚያን ሰው መሞት ከሰሙ በሁዋላ ፤ ለጊዜው የነበረባቸውን ችግር ያለፉ ፤ ፍጹም ነጻ የሆኑ መስሎ ተሰማቸው ።

ጥላሁን ፤ ባንድ ወር ካስራምስት ቀኑ ከበሽታው ድኖ ሲነሳ ፤ መልኩ ፍጹም ተለውጦ ሌላ ሰው ሆነ ። ፈንጣጣው እየተንጣጠለ ፤ ለየብቻ ወጥቶበት በነበረው ፤ አንዳንድ ጉድጉዋድ ትቶ ፤ ብዙውን እየተነባበረ በስፋት ወጥቶበት በነበረው ፤ ሰፋፊ እንጉዝ ትቶ ፤ በረዥሙ እየተነባበረ ወጥቶበት በነበረው ፤ ረዣዥም እንጉዝ ትቶ ፤ በዚያ ላይ አመድ የመነስነሱ ብልሀት ከመገኘቱ በፊት ፤ ቶሎቶሎ በተገላበጠ ቁጥር የቆሰለ ሰውነቱ ከተያያዘበት ምንጣፍ ሲላቀቅ ስቃዩ እንዳይበዛ ፤ አንድ ጊዜ በተኛበት ብዙ ይቆይ ስለነበረና ፤ ረዥም ጊዜ ተኝቶ ይቆይበት የነበረው ፤ ከግራ – ቀኝ ጆሮዎቹ በላይና በሁዋላው ፤ ራሱ በጣም ቆስሎ ስለነበር ፤ ቁስሉ ሲድን ፤ እዚያ ቆስሎ

@OLDBOOKSPDF

በንበረውና በተመሰጠው በቃ ፣ አንድ ጥቁር የሌለበት ነጭ ጠጉር ብቻ አበቀለ ። ታዲያ እንዲሁ በጠቅላላው ሲያዩት ከቁመናውና ሲሰቅ ከጥርሱ በቀር እንኩዋንስ ፣ "ጥላሁን ነው ፣ ጥላሁንን ይመስላል" የሚያሰኝ ምንም አልቀረው ። ድሮ የሚያውቀው ሰው ከበሽታው ድኖ ከተነሳ በሁዋላ ቢያየው ፣ እንኩዋንስ እሱ "ጥላሁን ነው" ሲል ፣ ጥላሁን ራሱ "እኔ ጥላሁን ነኝ" ብሎ ምሎ ቢነግረው ማመኑ ያስቸግረዋል !

ጥላሁን ቅኩላላቱ ወርዶ መቃኘቱን ሲቶውና ፣ እንደ ባላምባራስ አባባል "ጥላ የሚያሰጋበት ጊዜ" ካለፈ በሁዋላ ፣ ግራዝማች ጉርሜ ሳም ከሄዱበት ሲመለሱ በሚተኙበት ቤት እዩንዙ ከሱና ከሶፊያ ጋር መጫወት ለምደው ስለነበርና ፣ ስለ ወደዱዋቸው መሄጃቸው ሲደርስ አዘኑ ።

ሶፊያና ጥላሁን ሚዛን - ተፈሪ በገቡ በሁለተኛው ወር መጨረሻ ላይ ፣ ባሻ ነጋዎ ቁሉ "አደራ" እንደ ተባሉት ፣ ሶስት በቅሎዎች ከጫኝዎቻቸው ጋር ስለ ላኩላቸው ፣ ግራዝማች ጉርሜሳን ስለ መስተንግዶዋቸውና ስለ ደግነታቸው ምስጋናቸውንም ፣ እውነተኛ አድንቆታቸውንም ገልጸው ተሰናብተዋቸው ፣ ባላምባራስ ጉዶታ ጭምር ወደ ቦንጋ ፣ ከፋ ሄዱ ። ጥላሁንና ሶፊያ አንዳንድ ሩቅ የሚያቀርብ መነጽር ስለ ነበራቸው ፣ አንዱን ለራሳቸው አስቀርተው ፣ ሁለተኛውን ለመታሰቢያቸው ግራዝማች እንዲቀበሉዋቸው ቢለምኑዋቸው ፣ "አልቀበልም" ብለው ፣ በባላምባራስ አማላጅነት ጭምር በግድ እስ ቸገረው ሰጥተዋቸው ሄዱ ። ባላምባራስንም ከሚዛን - ተፈሪ እንዲ መለሱ አጥብቀው ለምነዋቸው ነበር ። ነገር ግን ባላምባራስ ለነሱ ቢሉም ባይሆን ቦንጋ ድረስ መሄዳቸው የግድ መሆኑን ሲነግሩዋቸው ፣ እንዲያውም ደስ አላቸው ።

"ከቦንጋ በሁዋላ ወደምትሄዱበት በደህና መሸኘታችሁን ማወቁ ለልቤ እረፍት የሚሰጠው ከመሆኑም ሌላ ፣ እዚያ ካለው ወንድሜ ፣ ከባሻ ነጋዎ ጋር ተገናኝቶ ፣ ወደ ፊት እንዳንራራቅ ፣ እንድንጠያየቅ አድርጎ መመለሱ ፣ አሁን ባይሆን ሌላ ጊዜ የሚልቀርበት አይነተኛ ነገር ነው ። እንዲህ ካለ ፣ በችግር ጊዜ ሲጠሩት 'አቤት ! አለሁ ልህ !' ከሚል ወንድም መራራቅ አይገባም" አሉ ባላምባራስ ።

ጥላሁንና ሶፊያ ፣ ሚዛን - ተፈሪን ሲለቅቁ የሚዛን - ተፈሪ "ሰዎቻቸውንም" እዚያው ፣ በተፈጠሩበት ትቱዋቸው ሄዱ ። ቦንጋ የወንድዬው ስም "እጃን በድሉ" የሴትዬዋ "ጥሩነሽ መርሻ" ሆነው

ነበር ። ነገር ግን ወደ ግራ - ቀኝ የሚወስዱ ሸንቆች ብቅ ተገኙተው ከበገጋ በሰለቶቻው ቀን ሰለ ቀንሉ ፤ አዲሶቹ ሰምቻቸው ብዙ አላገ ለገሉዋቸውም ። በዚህም ምክንያት ፤ አንድ ቀን ካዲስ አበባ ከወጡ ጀምሮ ተመልሰው እስኪገቡ የሰጥወጡዋቸውን ለምኞ ሲቆጥሩ ፣ የበ ንጋዎቹ ጠዋቶቻቸው ፣ ከዛሁ ቀን በሁዋላ በቦሬያ ቦርሳ ውስጥ በብ ዛቸ ወረቀት ላይ ብዛቸ ።

“እኔ መቼም ... እግዚአብሔር አስኪጠራኝ የምቆይበትን ቃው ቃላችሁ ፤ የናንተው ግን ገና አይታወቅም ። በለዚህ ... እንዲህ ዙሮ ዙራችሁ ከምታርፉበት ቦታ ሁሉንም ጸፉልኝ ፤ እንግዲህ አይዞዋችሁ በርቱ ፤ ዶሳች ናችሁና ምንም አትሆኑ ። እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ፤ ከሉ ነገር ፤ ችግር ፤ ፈተና ፤ መኖሪያቸውን እንዲያውቁ ያሳያቸዋል እንጂ ፤ በከፉ ነገር በችግር ፤ በፈተና ውስጥ እንዲኖሩ አይተዋቸውም ፤ ደግሞ ሌላ ነገር ላንገራችሁ ። ቅዱስ ጊዮርጊስ የሊባኖ ድራጎን እንደ ገደለ ፤ እናንተ ፤ ሁለት ልጆች በእግዚአብሔር ሀይል ፤ ያን አውሬ ፤ ያን የዋኪ ድራጎን ገድላችሁ ፤ የዚያን አገር ህዝብ ነጻ ግድረጋችሁ ፤ ይህ ታምር ለማችሁን በመሬት ፤ ነፍሳችሁን በሰማይ ቤት ፤ ለዘላለም እስከብር የሚኖር ነውና ፤ አሁን እንዳልሁት ፤ እግዚአብሔር ለችግር አይተዋችሁም እንጂ ፤ የምትችሩ ቢሆን እንኳ ፤ ችግራችሁን ፤ ለዚያ ስማችሁ በመሬት ፤ ነፍሳችሁ በሰማይ ቤት ለሚያገኙት ዘላ ለማዊ ክብር እንደምትከፍሉት ፤ እጅግ ዝቅተኛ ዋጋ መቁጠር ይገባ ችሁዋል ! ለዚያ ክብር ፤ ምንም ያክል ፤ ምንም አይነት ዋጋ ቢከ ፈል አይከብድም ! እንግዲህ እግዚአብሔር ቀናን ይምራችሁ !” አሉ ባላምባራስ ጉደታ ሲለያዩ ። ያንጊዜ ባለምባራስ ፤ ሁለት ወዳጆች ብቻ ሳይሆኑ ፤ ሰው ሁሉ ትቶዋቸው ፤ በዚች መሬት ብቻቸውን የቀሩ መሰሉ ተሰማቸው !

“እኛም” አሉ ጥላሁን ፤ ባላምባራስ የተናገሩት በልቡ ያስነሳው ሽብር ፤ በፊቱ እንዳይታይበት ወደ ሌላ እየተመለከተ ። “እኛም ፤ እንዲህ ዙሮ ዙረን ማረፊያችን እርስዎ እንደ መከሩን አዲስ አበባ እን ዲሆን ወስነናል ። አዲስ አበባ ፤ ‘አዲስ ከተማ’ የሚባል የሰው ሜካ እንኩዋንስ የተሸሸገ ፤ አብሮ እዚያ የገባ ጉዋደኛ ፤ አንድ ጊዜ ካይን ከመሰጠ ተፈልጎ የማይገኝበት ቦታ ሰባለ ፤ እዚያ ለማረፍ ነውና ተመ ካከረን የወሰን ፤ እዚያ እንደ ደረስን መኖሪያችንን አሰናድተን እንጽ ፍልዎታለን ።” ሶፊያ ፤ ከባላምባራስ በሞት እንደ ተለዩች “ኡኡ” ብላ አለቀሰች ።

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፴፩

# አቃቤ – ወንጀል

አዲስ አበባ ፣ በከፍተኛው ፍርድ ቤት አካባቢ ፣ ግለት በዳኞች፣ በጠበቆችና ባስተዳደሩ ሰራተኞች በንድ አቃቤ-ወንጀል የሚባል ስም ወጥቶላቸው፣ በዚያ ስም የታወቁ ፣ አንድ አቃቤ - ህግ ነበሩ። እሳያ ሰው ፣ ኢቃብያት - ህግ መሆኪ ፣ በህግ እውቀታቸውም ሆነ ባገ ዳበታቸው ቀባቸ፣ እንከዋንስ የሚበልጡዋቸው የሚያከሉዋቸው ቢኖሩ እጅግ ጥቂት ይሆናሉ እዩተባለ በሰፊው ይወራላቸው ነበር። እውነትም የህጉን ንባብ ከነምእራፉ ፣ ከነንቀጹ ከነንኡስ አንቀጹ ፣ እንደ አቡነ ዘበሰ ማያት አፋቸው ለምዶት ፣ አንድ ጊዜ ከጀመሩት ሳያስቡ ይደግሙታል። ከዚያም ይልቅ የሰሚን አሳብ የመማረክና የማስረዳት ስጦታ የነበራቸው ሰው መሆናቸው እርግጥ ነው ። ነገር ግን ያን የህግ እውቀትና ያን የማስረዳት ስጦታ ፣ “ ከበን ይልቅ ለክፉ ስራ ማዋል የሚመርጡ ናቸው ” እየተባለ ፣ ከሚያደንቁዋቸውና ከሚያመሰግኑዋቸው ፣ የሚ ንቁዋቸውና የሚረግሙዋቸው እጅግ ይበዙ ነበር ።

ያቃቤ - ወንጀሉ አስተሳሰብና አሰራር የተመሰረተባቸው ቦስት አበይት ነገሮች ፣ ወይም . . . ስሜቶች የነበሩዋቸው ይመስላል ። ከነ ዚህ ስሜቶች ፣ የመጀመሪያው መንግሥትና ሕዝብ የተለያዩ ዓላማዎች ያሉዋቸው ፣ ሁለት ፊት-ለፊት የተሰለፉ ፣ ተጻራሪ ክፍሎች እንጂ መን ግሥት የሕዝብን የሲጋና የመንፈስ ፍላጎቶች እንዲፈጽም ሕዝቡ ራሱ እንደሚስማማው አድርጎ የሚያቋቁመው ፣ የህዝብ መሳሪያ እንደሆነ አድርገው የማይመለከቱ መሆናቸው ነው ። “ዘመዶች ፣ ወይም ወዳ ጆች ነን” የሚሉ ሰዎች ህዝብ ሲያማርራቸውና ሲነቅፋቸው ሰምተው በመቆርቆር የነገሩዋቸው እንደሆን ፣

“የመንግሥትን ጥቅም አትድለህል ” ተብዬ አልውቀስ ፣ አልከ ሰስ እንጂ እኔ ህዝብ የሚለውን ቢል ፣ ቢያሩ እዩከካ ቢያቦካ . . . ምን ቸገረኝ ! ከዚች አልቆጥረውም !” ይላሉ ፣ ክንዳቸውን አንስተው የጠቋዋሚና ያውራ ጣት ጥፍሮቻቸውን ባንድ ላይ ያፋጩና “ ህ ! ከሁለቱ አንዱን መንገድ መምረጥ አለ !” ይላሉ - ቀጥለው ፣

«ከሁለቱ አንዱን መምረጥ ነው እንጂ ፤ ባንድ ላይ መንታ መንገድ ይዞ መሄድ አይቻልም ። ወይ ለወንጀለኞች እየተገዙ እንደሚቆሙት ጠበቆች እንድያውን አስታውቆ የነሱ መሆን ! ያለዚያ . . . የመንግስት አቃቤ ‐ ህግና ዳኛ ሆኖ ፤ የመንግስት ደመወዝ እየበሉ ለወንጀለኞች ሲከላከሉ መገኘት . . . ባንድ ጊዜ መንታ መንገድ ይዞ እንደ መሄድ ያለ ነው ፤ ከሱ የተለየ አይደለም !» ይላሉ ። ትልቅም ይሁን ትንሽ ጥፋት አጥፍቶ ፤ ወይም በጥፋት ተጠርጥሮ እየተያዘ የሚታሰረውና የሚቀጣው በበዛ መጠን ፤ የመንግስቱ ጥቅም እንደዚያው የሚበዛ ፤ የመንግስቱ ጥቅም የበለጠ የሚጠበቅ ይመስላቸዋል ። "የወንጀል ስራ ፈጽመዋል" ተብለው ፤ ወይም በወንጀል ተጠርጥረው ፤ ፖሊስ የያዛቸው ሰዎች ጉዳያቸው እዚያው በፖሊስ መርማሪዎች ተጣርቶ ፤ ንጹሆች ሆነው በመገኘታቸው የተለቀቁ እንደሆን ፤ ያን ሰምተው ከፖሊሶች ጋር ያልተጣሉበት ጊዜ አይገኝም ። ወይም ፖሊሶች ጉዳያቸውን አጣርተው የሚያስከስስ መሆኑን ሲገምቱ ዓቃቤ ‐ህግ ጽህፈት ቤት ያስተላለፉላቸው እስረኞች ወደሳቸው ሲመሩ በኋላ እስረኞች ላይ የሞት ፤ ያለዚያ የዕድሜ ‐ ልክ እስራት ፤ ቢያንስ ቢያንስ ግን ከስር አመት የማያንስ እስራት የማይፈርድ ዳኛ ቢኖር ፤ የመንግስቱን ጥቅም የማይጠብቅ ከመሆኑም በላይ ፤ የወንጀልን ስራ ለማደፋፈር ታጥቆ የቆመና በዳኝነት ወንበር ሊቀመጥ የማይገባው አድርገው ለበላይ ባለ ስልጣን ያላመለከቱበት አይገኝም ።

ሁለተኛው ያስተሳሰባቸውና ያሰራራቸው መሰረት ስጋት ፤ ወይም በራሳቸው ችሎታ እምነት ማጣት ይመስላል ። አቃቤ ‐ ወንጀሉ ከትምርት ቤት በሕግ ተመርቀው እንደ ወጡ ፤ ፍርድ ሚኒስቴር ውስጥ ከተቀጠሩበት ጊዜ ጀምሮ በዋናው አቃቤ ‐ ህግ ጽሕፈት ቤት የወንጀል ጉዳይ ተከታታይ ሆነው ከመስራት በቀር ሌላ ስራ ይዘው አያውቁም፤ ሌላ ስራ ያለም አይመስላቸውም ። ስለዚህ እያንዳንዱን የወንጀል ስራ ገና ባሳብ ደረጃ እንዳለ ፤ ገና ሲጸነስ ጀምሮ በግብር እስከሚፈጸምበት ጊዜ ድረስ እየተከታተሉ ሲያጠኑትና ሲመረምሩት ፤ እንደያይነቱ ልባቸውን ከተራ ደስታ እስከ ሲቃ ይሰጣዋል ። የወንጀል ጉዳይ መከታተል ከመጠን ያለፈ ከመውደዳቸውም በላይ ፤ ወንጀለኛ ጠፍቶ ወንጀል ያልተሰራ እንደሆን ስራ የሚያጡ ፤ እንጀራ ሳይበሉ የሚያድሩ እየመሰላቸው ፤ በወንጀል እየተጠረጠሩ ከሚያዙት መሀከል ንጹሆች የሆኑትን በምርመራ አጣርተው ከሚለቁዋቸው ፖሊሶችና ፈርደው ነፃ ከሚያደርጓቸው ዳኞች ጋር ሁልጊዜ እንደ ተጣሉ ናቸው ።

@OLDBOOKSPDF

ሌላው ፣ ምቡቶቸው ያስቀሳሰባቸውና ያስራራቸው መሠረት ምን ጊዜም ቢሆን ፤ በቁም ነገር ይሁን በጭዋታ ፣ መሸነፍን የማይቀበሉ፣ መሸነፍን ጉሮሮዋቸው የማይውጥላቸው መሆናቸው ነው ። በክርክር መሸነፍን በጦር ሜዳ ድል እንደ ተመቱ ፣ የሰው አሳብ መቀበልን ገንዘብ እንደ ተመጸወቱ ቆጥረውት ፤ ውርደት ሆኖ ይሰማቸውና ጠባያቸው ይከፋል ። በፍርድ ቤት የወንጀል ጉዳይ ይዘው ቀርበው እሳቸው ካልረቱና ተከሳሹን ካላስቀጡ የረታቸውን የተከሳሽ ጠበቃና የፈረዱትን ዳኞች ልክ እንደ ጠላቶቻቸው ይጣሉዋቸዋል ። ለብዙ ጊዜ ማነጋገሩ እንኳ ይከብዳቸዋል ። ረትተው ሰው ሲያስቀጡ ብቻ ደስ ይላቸውና ከሁሉም ጋር ሳቅ ፤ ጭዋታ ያምራቸዋል ። የደስታቸው መጠን ከፍ ፤ ወይ ዝቅ የሚለውም እንደ ቅጣቱ መክበድና መቅለል ነው ።

እንግዲህ ይህ ሁሉ ባንድ ላይ ተደምሮና በዚያው ላይ ህግን ለሰው መጠበቂያ ሳይሆን ለሰው መወንጀያና ማስቀመጫ ፣ መሳሪያ እንዲ ሆን የታቀደ አድርገው ቆጥረው ፣ በዚያ መንፈስ የሚያስቡና ምን ጊዜም ለዚያ ዓላማ ብቻ የሚሰሩ መስለው መታየታቸው ባንድ ላይ ተጠቃሎ ይመስላል ከጉዋደኞቻቸው ፣ ካቃብያነ ህግ ለይቶ እሳቸውን አቃቤ - ወንጀል የሚባል ስም ያሰጣቸው ።

አቃቤ- ወንጀሉ በወንጀል ለሚከሰሱ ሰዎች ጥብቅና የሚቆሙትን ሁሉ እንደ ወንጀለኞች እንደ ራሳቸው ፣ በወንጀል ለተከሰሱት ሰዎች የሚፈርዱትን ዳኞች ሁሉ ፤ ከወንጀለኞቹና ከጠበቆቻቸው ጋር የወንጀልን ስራ ለማደፋፈርና ለማስፋፋት እንደሚያሴሩ የመንግስት ጠላቶች የሚቆጥሩ መሆናቸው በሁሉም ዘንድ የታወቀ ስለሆነ ፣ ዳኞቹም ሆኑ ጠበቆች ከበላይ ባለስልጣኖች ጋር እንዳያጣሉዋቸው እጥብቀው ይፈሩዋቸዋል ። እሳቸው በያዙት የወንጀል ጉዳይ ለተከሳሽ ጠበቃ ሆኖ መከራከር ፣ ወይም በዳኝነት ተቀምጦ መፍረድ ግዴታ ካልሆነ የሚፈቅድ የለም ።

መቸም በጠቅላላ እንጋገር ፤ በስራ ጉዋደኞቹና በስራው ምክናያት በሚገናኛቸው ሰዎች ዘንድ የተጠላ ሰራተኛ ፣ እንዲያው መጠላቱ ብቻ ፤ ለስራውና ለበላይ ባለስልጣን ታማኝ ለመሆኑ አይነተኛ ምስክር ሆኖ ፣ በባለስልጣናቹ ዘንድ የሚያስወድደው መሆኑ የተለመደ ነው ። ታዲያ ምናልባት በዚህ ጠቅላላ ልማድ ምክናያት ይሁን ፣ ወይም ስሜታቸውንና እምነታቸውን በመረዳት አቃቤ - ወንጀል የሚባል ቅጽል የተሰጣቸውን አቃቤ- ህግ የስራ ጉዋደኞቻቸውና በስራ የሚ

@OLDBOOKSPDF

የትዳሮቻቸው ሰዎች ሆኑ የሚጠበቅባቸውን ያክል አለቆቻቸው ይወዱዋቸዋል ። በዚህ ምክንያት በጠቅላይ ግዛቶች በተቋቋሙ ት ያቃብያን -ህግና የፖሊስ ጽሕፈት ቤቶች ፤ ወንጀል ነክ በሆነ ጉዳይ ችግር ሲፈጠር ፤ ወይም አዲዲስ ስነ- ስራዎች ለማስማመድ ከዲስ አበባ እምነቱ የሚጣልበት ሰው መላክ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፤ ብዙ ጊዜ የሚላኩ አቃቤ - ወንጀሉ ናቸው ። እነቸውም እንዲህ እንዲህ ባሉ ስራዎች እየታዘዙ ወደ ጠቅላይ ግዛቶች መውጣትን እና እወጥተው እይናገሩ እንጂ ፤ ልባቸው በጣም የሚወድቡት ፤ የሚናፍቅበት አንዳንድ ምክንያቶች አሉ ። ከሁሉ አስቀድሞ ባችሎታችሁና በታማኝነታችሁ ተመርጣችሁ መባል ትልቅ ነገር ነው ! አንዳንድ ጊዜ ሚኒስትሩ ጠርተው ፤ ልክ እንደ ጉዋደኛ እፊታቸው አስቀምጠው ፤ ሲጋራ ሰጥተው ፣ ራሳቸው ክብሪት ጭረው ያቀጣጥሉና ፤ "ይህ አሁን የምትሄድበት ጉዳይ እጅግ ከፍተኛ ፤ እዚህ አስቸኳዋይ ስራ ባይገጥመን እኛ ራሳችን ለመሄድ አስበንበት የነበረ አቢይ ጉዳይ ነው ። ስለዚህ አንተን በኛ ፈንታ መላካችን በችሎታህና በታማኝነትህ ሙሉ እምነት ስላለን ነው" ሲሉ እንዲህ ያለ ምስክርነት ከሚኒስትሩ አፍ መስማቱ ብቻ ልብን በደስታ የሚያጥቅ ፤ እንደ ትልቅ ሹመት ፤ እንደ ትልቅ ሽልማት የሚቆጠር ነው ! ከዚያ ቀጥሎ መልእክትን ፈጽሞ እስኪመለሱ ፤ እዚያ ከሚቆዩው መስተንግዶና ሌላ ሌላ ነገር ሁሉ በላይ ፤ የሚገኘው ልዩ የቀን አበል የሚናቅ አይደለም ! ሶስተኛ ከሚኒስትሩ ቃል ፤ በሚኒስትሩ ስም ፤ ሚኒስትሩን አክሎ ፤ መስሎ ከዲስ አበባ ወደ ጠቅላይ ግዛት መሄድ እዚያ ደርሶ እስኪመለሱ ሚኒስትር እንደ መሆን ያለ ነው !

አዲሱ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ህግና በሱ መሰረት የተሰሟው የፍርድ ስነ - ስራት ታወጀው ከወጡ በሁዋላ ፤ እነሱን በክፍላተ ሀገሩ ሁሉ ፤ በወንጀል ምርመራ ከተሰማሩት ፖሊሶችና አቃብያነ -ህግ ጋር ማስተዋወቅ አስፈላጊ ስለ ነበረ፤ ለዚህ ስራ በምእራብ ፤ በደቡብና በምስራቅ ኢትዮጵያ ላሉት ሰምንት ክፍላተ -ሀገር ሰምንት አቃብያን-ህግና ሌሎች ህግ አዋቂዎች ሲመደቡ ፤ ለስድስቱ የሰሜን ኢትዮጵያ ክፍላተ - ሀገር ፤ አቃቤ - ወንጀሉ ብቻ በመመደባቸው ፤ እሳቸው የተደሰቱትን ያክል በፍርድ ሚኒስቴር አካባቢ ያሉትን ሁሉ ገረማቸው ! ይህ እንግዲህ አቃቤ - ወንጀሉን ለፍርድ ሚኒስቴር ባለስልጣኖች ዘንድ ፤ እንደ ስድስት አቃብያን - ህግ ይቆጠራሉ ማለት ነው ። ባለቆች ዘንድ ፤ በከፍተኛ ባለስልጣኖች ዘንድ እንዲህ ያለ ግምት ማግኘት እንዴት የሚያኮራ ፤ እንዴት እረፍትና እንቅልፍ እሳጥቶ ቀንና ሌሊት የሚያሰራ ነው !

@OLDBOOKSPDF

እቃቤ- ወንጀሉ የከፍላተ - ሀገር ተልእኮአቸውን እንደጣ በኋላ የስራ መንፈስ በሸዋ ጀምረው ፣ ከዚያ በወሎ ፣ በትግሬ ፣ በኤርትራ ፣ በቤገምድርና በጎጃም አድርገው ወዳዲስ አበባ እስኪመለሱ ፣ ዘጠኝ ወራት ያክል ወሰደባቸው ። ዘጠኝ ወራት የወንጀለኛ መቅጫውን ህግና በሱ ላይ የተመሰረተውን የፍርድ ስነ- ስራት ብቻ ሳይሆን ፣ በወንጀል ጉዳይ የፖሊሶችና ያቃብያን - ህግ አቋምም ምን መሆን እንዳለበት ፣ የራሳቸውን አስተሳሰብ ፣ የራሳቸውን ፍልስፍና ጭምር ለማስተዋወቅ የሚያበቃ ጊዜ ነበር ። መችም የሳቸውን አስተሳሰብ ፣ ወይም ፍልስፍና አለቆቻቸው ፣ የበላይ ባለስልጣኖች በጽሑፍ አይገልጹት ፣ ወይም ህግ አድርገው አይሰጡት እንጂ ፣ ወድደው እንደ ተቀበሉት ለሳቸው በሚያሳዩት አክብሮትና ልዩ አስተያየት ይታወቃል ። ስለዚህ በየሄዱባቸው ስድስት ክፍላተ ሀገር ሁሉ መመሪያ ሆኖ እንዲሰራበት በጽሑፍ አድርገው ባይሰጡትም ፣ በምክር መልክ ፣ በምክር ደረጃ ፣ በቃል ለቃብያን - ህግ ሆነ ለፖሊሶች ደህና አድርገው አስረድተው ለማሳመናቸው እርግጠኛ ሆነው ተመለሱ ።

እቃቤ - ወንጀሉ ከዚያ በፊት ብዙ ጊዜ ወደ ክፍላተ- ሀገር የወጡ ቢሆንም ፣ ካዲስ አበባ ባንድ ጊዜ ያን ያክል ወጥተው ቆይተው ስለ ማያውቁ ፣ ሲመለሱ ከመስሪያ ቤታቸው አንዳንዶቹ ወደ ሌላ ተዛውረው ፣ አዳዲሶቹ ገብተው ፣ እሳቸው ከሚያዘወትሩዋቸው ፣ ከጠቅላይ ፍርድ ቤትና ከከፍተኛ ፍርድ ቤት እንኳዋ አንዳንድ ዳኞች ወደ ሌላ ተዛውረው ፣ በነሱ ፈንታ ሌሎች ተሹመው ፣ በጠቅላላው ብዙ ነገር ተለዋውጦ አገኙትና ሁሉንም እስኪለማመዱት ትንሽ እንግድነት ላይ ሰማቸው አልቀረም ። ከዚያ ስለ ተልእኮዋቸው ያሰናዱትን መግለጫ ለዋናው እቃቤ- ህግ ካቀረቡ በሁዋላ ያስር ቀን እረፍት ተቀብለው ፣ አርፈው ሰንብተው መደበኛ ስራቸውን እንደ ጀመሩ አንድ ቀን ጥዋት ፣ የዋናው እቃቤ - ህግ ልዩ ጸሀፊ ጠርተው ፣ አንድ በከፍተኛ ደረጃ የታሰበበት የወንጀል ጉዳይ መኖሩንና እሳቸው ጠቅላላ ማህደሩን ተቀብለው ፣ በጥንቃቄ አጥንተው የተፈለገው ውጤት እንዲገኝ የተቻላቸውን ያክል እንዲጥሩ መታዘዙን ነገሩዋቸው ።

“ክስ ተመስርቶበታል ? ወይስ ገና የሚመሰረትበት ነው ? ” አሉ እቃቤ - ወንጀሉ ።

“ክስ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፣ እንደኛ ችሎት ተመስርቶ ተቀጥሮዋል 1 ዝርዝሩን አቶ ባልቻ ወንዳፍራሽ ይነግሩዎታል ። ”

“ክሱን መጀመሪያ የመሰረተው ማን ኖሮዋል ? አቶ ባልቻ ነው?”

@OLDBOOKSPDF

"እዎ ፣ አቶ ባልቻ ናቸው ። ብቻ . . . በጣም የታሰበበት ጉዳይ ስለሆነ ዋናው አቃቤ - ህግ የርስዎን መመለስ ሲሰሙ ወደርስዎ እን ዲተባበፍ አዘዙ ።"

አቶ ባልቻ ወንዳፍራሽ በችሎታቸው ከሚመሰገኑት አቃብያነ ህግ አንዱ ናቸው ፤ ስለዚህ አቃቤ - ወንጀሉ አቶ ባልቻ የጀመሩት ጉዳይ ፣ "በጣም የሚያሳስብ" በመሆኑ ፣ ወደሳቸው እንዲተባለፍ መታ ዘዙ ሲነገራቸው የደስታ ሙቀት በሰራ አካላታቸው ሲሰራጭ ተሰማ ቸውና ላጭር ጊዜ አንገታቸውን ደፍተው ፣ ዝም ብለው ቆዩ ። ከዚያ ያ ለጊዜው ባካላታቸው የተሰራጨው የደስታ ሙቀት በረድ እያለ ሄዶ አእምሮዋቸው በትክክል ማሰብ ሲጀምር ፣ እንዲያ አንገታቸውን እንደ ደፉ ሲያስቡ ቆዩና ፣

"ከፍተኛ ፍርድ ቤት . . . ወዳንደኛ የወንጀል ችሎት ተመርቶ ዋል ነው ያልሽኝ ?" አሉ አቃቤ - ወንጀሉ ፣ አንገታቸውን ከደፉ በት አቅንተው ።

"እዎ ፣ አንደኛ የወንጀል ችሎት ። ሁሉንም አቶ ባልቻ ያስረዱ ዎታል ። ትእዛዙ ለሳቸውም ተላልፎዋል ።"

"ጉዳዩ ይህን ያክል የሚያሳስብ ከሆነ ካንደኛ ችሎት ወደ ሶስ ተኛ እንዲተባለፍ ማድረግ የሚቻል ይመስልሃል ? እንዲህ ለማድረግ ቢቻል በጣም በወደድሁ አቶ ብርሀን ። ምክናያቱም በሶስተኛ የሚያ ስችሉትን ዳኞች ሁሉንም ስለማውቃቸው ነው ። አንደኛ ችሎት ሰብ ሳቢ ሆኖ የሚያስችለውን ዳኛ አሁን ከመጣሁ እንዲሁ በሩቅ አዩሁ ትና እናውቀዋለን የሚሉ ሰዎች ስለሱ አንዳንድ ነገር ነገሩኝ እንጂ ፣ ጥራሽ አላውቀውም ፤ ለኔ አዲስ ነው ።"

"አቶ አንተነህ ተሰፋዬ ? አዲስኮ አይደሉም ፤ ከተሾሙ ቢያ ንስ ቢያንስ ስድስት ወር ሳይሆናቸው አይቀርም ፤ ከዚያ በፊትም የፕ ሬዚዳንቱ የቅርብ ረዳት ሆነው ቆይተዋል ። ደግሞ ጥሩ ዳኛ ናቸው ይባላል !"

"ምናልባት እንዳልሽው ጥሩ ዳኛ ይሆናል ! እኔ አላውቀውም። ብቻ ብዙ ጊዜ ሰው በወንጀል ችሎት 'ጥሩ ዳኛ ነው' የሚለው በወ ንጀል የተከሰሱትን የሚረዳ ሲሆን ነው !" አሉ አቃቤ - ወንጀሉ ፣ እንደ መሳቅ ብለው ። "ከተሾመ ስድስት ወር ይሆነዋል" ስላል ሽው ፣ እኔ እውጭ የቆዩሁ ዘጠኝ ወር ተኩል ስለሆነ . . . እኔ ከሄ ድሁ የተሾመ ነው ፤ ስለዚህ አላውቀውም" አሉ ፣ ወዲያው ከተል አድርገው ።

"በችሎታቸውም ሆነ በጠባያቸው ብዙ ሰው ያመሰግናቸዋል" አሉ ልዩ ጸሀፊው ።

@OLDBOOKSPDF

"እንጃ ፣ ይሆናል ። እኔ ግን . . ." አሉና አቃቤ - ወንጀሉ አይናቻቸውን ሳያረግቡ እጣፋው ላይ ተክለው እንደ መሳቅ አሉ ።

"ብርስዎ ምን መሰሉዎ ? " አሉ ልዩ ጸሀፊው ፣ አቃቤ - ወንጀሉ የሚቀጥሉ መስሎዋቸው ቢጠብቁ ፣ ሳቅ እንዳሉ አይናቻቸውን እጣራው ላይ ተክለው ዝም ሲሉ ጊዜ ።

"ብኔ ? ብኔማ . . . ገና ሳንተዋወቅ ምን ይመስለኛል ፤ ሁለት ይሁን ሶስት ቀን ያክልኮ ነው . . . እንዲያ በሩቁ ሲያልፍ ያዩሁት ፤ ብቻ ከሩቅ ላየው የራሰ ጠጉሩ ከግራ ቀኝ ጆሮዎቹ በላይና በሁዋላ ከማጅራቱ በላይ በሰፋፊው ነጭ ፤ ሌላው ጥቁር ሆኖ ሁሉንም ባንድ ላይ ሲያዩት ፣ ከዝንጉርጉር የበግ ሌጦ የተሰፋ ቆብ የደፋ እንጂ እውነተኛ የራስ ጠጉር አይመስልም ! በዚያ ላይ ፊቱ ከተሸፈነበት ጭገር የተረፈው ምን እንደሆነ አላውቅም ፤ ጠባሳ ብቻ ነው ። ታዲያ ያን ለመሸፈን ይሁን ፣ ወይም አይኑ ብርሀን ይፈራ እንደሆን አላውቅም፣ ጥቁር መነጽር አድርጎ ይህን ሁሉ ባንድ ላይ ሲያዩት ያስፈራራል !" ሲሉ አቃቤ - ወንጀሉ በገዛ ያልታረመና ተራ ቀልዳቸው እዩሳቁ ፤ ልዩ ጸሀፊውም ወሬው ይህን ያክል የሚያስቅ ሆኖ ሳይሆን ፣ ለማሳቅ ብለው ያወሩትን ሰው ላለማሳፈር አብረዋቸው ትንሽ እንደ መሳቅ አሉና ፣

"አይ ፤ እኔ እንኩዋ የተናገርሁት ስለ ህግ ችሎታቸውና ስለ ጠባያቸው ነው ፤ ብቻ በመልክም እንዳሉት ቀርበው ባያዩዋቸው ይሆናል እንጂ መልከ ክፉ አይደሉምኮ ! "

"እዎ ፤ ቀርቤ አላዩሁትም አልሁህኮ ። ወዲያውስ 'ምን መሰለህ' ስላልኸኝ ነው እንጂ እኔ . . . መልኩ አግረ ፣ ከፋ ምን ያደርግልኛል ? እኔ የምፈልገው ፣ መልኩ ይመር ይከፋ ካቃቤ ህግ ጋር ተግባብቶ የሚሰራ ፣ አንድ ጉዳይ ባቃቤ - ህግ በኩል ስለ ቀረበ ብቻ 'ባጥቂነትና በግፈኛነት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት' ብሎ አስቀድሞ በመፍረድ ፈንታ ፣ ጉዳዩን ከህግ ፣ ከስነ-ስራትና ከቀረቡት ደጋፊ ማስረጃዎች ጋር አገናዝቦ የሚመረምርና በዚያ ላይ ተመስርቶ ፍርድ የሚሰጥ ዳኛ ነው ! ይህ ነው እኔ የምፈልገው ! አንዳንድ ዳኞች መንግስትን የበላይ በመሆኑ ብቻ እንደ ተጋፊና እንዳጥቂ እዩቆጠሩ ፣ በመንግስት አቃቤ - ህግ በኩል የሚቀርበውን ሁሉ መቃወም የማጥቃትን ስራ ፣ ግፍን እንደ መቃወም ተቆጥሮ በህዝብ ዘንድ መልካም ስም የሚያሰጣቸው እዩመሰላቸው ፣ ህጉን ችላ ብለው እንዲያው

@OLDBOOKSPDF

አውር ድንብሩን ወንጀለኞች ቢረዱ ፣ ወንጀለኞች እንዳይቀጡ ቢታገሉ፣ ሀት የማያስኬዳቸው ሆኖ ለመቅጣት ቢገደዱም ፣ ቅጣቱ እንዳይከብዳቸው አጥብቀው ሲጥሩ ይታያሉ ። ታዲያ በኛ ፣ ባታብያን - ሀትሰኩል ክስ ክሀግና ክስን ስራት ጋር እዩትገናዘበ ፣ በማያንቀሳቅስ ማስረጃና በታመነ የምስክር ቃል እዩትገደፈ መቅረው ሳይቀር ፣ በዳኞችዝና ፍቤጋና አለመትባበር ብቻ ውጤቱ እንደ ተፈለገው ሳይሆን ሲቀር፣ እኛ ሰርተን እንዳልሰራን ፣ ደክመን እንዳልደከምን እዩተቆጠረ ፣ ወቀሳና . . . ለድገታችን መሰናክል የሚሆን ነገር ሲያመጣብን ይችላል ።”

“አይ . . . እስዎን እንኳዎ ‘አይሰሩም ፣ አይደክሙም’ ብሎ የሚወቅስዎ እንደሌለ ፣ በተለይ ዋናው አቃቤ - ህግ በትጋት ሆነ . . . በችሎታ ረገድ በስዎ ላይ ያላቸውን ያክል እምነት በማንም ላይ እንደሌላቸው እርስዎ ፣ ራስዎ ያውቃሉ ። ሌላው ቀርቶ አሁን ይህን ጉዳይ ከሌላ ሰው እጅ አውጥተው እርስዎ እንዲይዙት ማድረጋቸው፣ ለዚህ አንድ ምስክር ነው ። የተገደሉት ሰው የተደነቁ አርበኛ የነበሩ ከመሆናቸውም ሌላ ፣ አገር በማስተዳደር ሆነ በዳኝነት ፣ እንዲሁም ጸጥታ በማስከበር ተወዳዳሪ የሌላቸው እንደ ነበሩና ፣ እንዲህ ያሉትን ሰው የገደሉት ወንጀለኞች የሚገባቸውን ህጋዊ ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ ፣ መንግስትንና በጠቅላላው አገርን ማስካስ እንደሆነ ያገር ግዛት ሚኒስትሩ ለፍርድ ሚኒስትሩ ነግረዋቸው ኖሮዋል ። ስለዚህ የፍርድ ሚኒስትሩ ዋናውን አቃቤ - ህግ ጠርተው ፣ የፖሊሶች ምርመራ ያለበትን ጠቅላላ ግህደር ተቀብለው የሚያጣራውንና የሚጎድለውንም ማስረጃ አሙዋልቶ ፣ በብርቱ ጥንቃቄ አጥንቶ ክሱን የሚመሰርተውን ፣ ችሎታ ከታማኝነት ጋር ያለው አቃቤ - ህግ ራሳቸው መርጠው እንዲያቆሙ አጥብቀው ስለ ነገሩዋቸው ነው እንደ ገና አስበው ፣ አሰላስለው ጉዳዩ ወደርስዎ እንዲመራ ያደረጉ ። በኔ አስተያየት . . . እንዲህ ሳለ ፣ በከፍተኛ ደረጃ ለታሰበበት ጉዳይ መመረጥ ራሱ . . . እንደ ትልቅ ሹመት የሚቆጠር ነው ። አሁን እኔ የነገርሁዎ ‘አስቦበት እንዲቆይ’ ንገረው ስላሉኝ ነው እንጂ ፣ ሁሉንም ሁዋላ እሳቸው ይነግሩዎታል ” ሲሉ ልዩ ጸሀፊው ፣ ያቃቤ - ወንጀሉ ልብ በደስታ መጋሉ ፣ ጸዳሉ በፊታቸው ሲበራ ይታይ ነበር !

“እኔኮ” አሉ ፣ በደስታ ተኸርበርብሮ የቆዩ ስሜታቸውን ጸጥ ለማድረግ እንደ ምንም ከቻሉ በሁዋላ ።

“እኔኮ እንዲህ . . . በከፍተኛ ደረጃ ለታሰበበት ጉዳይ መመረጥ እንደ ከፍተኛ ሹመት የሚቆጠር መሆኑን እረዳዋለሁ ። እንዲያውም

@OLDBOOKSPDF

. . . ከመጠን በላይ ያሳሰበኝ ይህ በከፍተኛ ደረጃ ለታሰበበት ጉዳይ ባላደራው እኔ መሆኔ ፣ ያገር ግዛት ሚኒስትሩ ፣ የፍርድ ሚኒስትሩ ፣ የዋናው አቃቤ-ህግ ፣ የሁሉም እምነት በኔ ላይ መጣሉ ነው ! ”

“እንዴት ? ”

“ብቻየን ሰርቼ ብቻየን እንደሚፈለገው ለፈጽመው ለማልችል ጉዳይ ብቻየን ባላደራ ፣ ብቻየን አላፊ መሆኔ ! ”

“እንጃ ! አሁንም የገባኝ አይመስለኝም ። ”

“እንዴት አድርጌ ልንገርህ ፣ አቶ ብርሀን ? እየው የኔ ወንድም፣ ጉዳዩ ምርመራውን በብርቱ ጥንቃቄ አጥንቶ ፣ የሚያስፈልገውን ማስ ረጃ ሁሉ ለቅሞና አቀነባብሮ አቅርቦ ፣ ከሱን ከህግ ጋር አገናዝቦ ስኑ ስራት ተከትሎ መስጀ ፣ ከዚያ በሁዋላ ክርክሩን ተጠንቅቆ በመምራት ብቻ የሚወሰን ቢሆን ኖሮ ፣ ይህን ሁሉ ማድረግ የኔ ፈንታ ስለ ሆነ አላፊነቱ ባልከበደኝ ! ከዚህ ሁሉ አንድ ትንሽ ነጥብ በመ ጉደሉ የጉዳዩ ፍጻሜ እንደ ተፈለገው ሳይሆን ቢቀር ለተጣለብኝ እም ነት የማልበቃ መሆኔን እኔ ራሴ በፈረድሁ ! ነገር ግን አሁን የተቸ ገርሁ ፣ የኔን ፈንታ በብርቱ ጥንቃቄ ብፈጽምም የመጨረሻውን ውሳኔ የሚያደርገው ፣ ፍርዱን የሚሰጠው ዳኛ ስለሆነና ዳኛው ደግሞ እን ዴት ያለ እንደሆነ ስለማላውቀው ነው ። እንዲያውም . . . እኔ የሰማ ሁት ‘በሀዝብ ዘንድ ሀቀኛ የመባልን ዝና ለማትረፍ ወንጀለኞችን ለመርዳት ቃጥቀው ከቆሙት አንዳንድ የምናውቃቸው ዳኞች ባይብስ አይሻልም ’ ሲባል ነው ። ይህ እንኪዋ . . . ገና ያልተጣራ ወሬ ስለ ሆነ አወንታ ነው ብዬ የምምልበት አደለም ! ብቻ የሆነው ሆኖ እር ግጠኛ ለመሆን ፣ እንደ ነገርኹኝ ጉዳዩ በጣም የታሰበበት ከሆነ ልዩ አስተያየት ተደርጎ ከማላውቀው የማውቃቸው ዳኞች ወዳሉበት ፣ ወደ ሶስተኛ ችሎት የሚተላለፍ ቢሆን ደህና ይመስለኛል ። ያለዚያ የተ ፈለገው ውጤት ይገኛል ብሎ እርግጠኛ መሆን . . . በጣም አስቸጋሪ ነው ። ”

“እንግዲህ . . . ቅድም እንዳልሁዎ ፣ ዋናው አቃቤ . . . ህግ ጠር ተው ያነጋግሩዎታልና ሲገናኙ ይንገሩዋቸው ። ብቻ . . . እያንዳ ንዱ ጉዳይ ለችሎቶቹ የሚመደበው ባፈንጉስ ጽህፈት ቤት በኩል ስለ ሆነና ፣ ዋናው አቃቤ-ህግ እንደሚያዩዋቸው በሌሎች ስልጣን መግባት ስለማይወዱ ፣ ‘ጉዳዩ አሁን ከተመደበበት ወደሌላ ችሎት ይዛወር ’ ባሉት የማይስማሙ አይመስለኝም ። ነገር ግን ማን ያውቃል ይጠይቁዋቸው ” አሉ ልዩ ጸሀፊው ፣ ከወንበራቸው ተነስተው ። መቸም እንግዳን አስቀምጦ መነሳት ይሂዱ የማለት ፣ የማሰናበት ምል ክት መሆኑ የታወቀ ነው !

## ምእራፍ ፴፰

# የቀኛዝማች ዳኘ ገዳዮች በከፍተኛው ፍርድ ቤት ፊት

ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ ፡ ራሳቸው ብዙ ጊዜ እንደሚፈክሩት እግራቸው ከኢሉባቦር በቀር የሌላ አገር አፈር ረግጦ አያውቅም ። ተወልደው እስኪሞቱ ፡ በየትም በኩል የኢሉባቦርን ወሰን አልፈው ፡ የሌላ አገር አፈር ረግጠው አያውቁም ። ከኢሉባቦር እንኳ አንዳንድ ጊዜ እዮተጠሩ ወደ ጎሬ ከመሄዳቸው በቀር ፡ ሌሎችን አውራጃዎች አያውቁዋቸውም ። ነገር ግን ቀኛዝማች ከሞቻ ሳይወጡ አዲስ አበባ ባገር ግዛት ሚኒስቴር ፡ በገንዘብ ሚኒስቴርና በፍርድ ሚኒስቴር ፡ በዩጊዜው ከሚሾሙት ሹማምንትና ከልዩ ጸሀፊዎቻቸውም ሆነ ከተላላኪዎቻቸው ጋር በዩለቱ እንደሚገናኙ ሁሉ ደህና አድርገው ይተዋወቃሉ ። አዲስ አበባ የሚቀመጠው ፡ የቀኛዝማች ወኪል በነዚህ በሶስቱ ሚኒስቴሮች በየጊዜው ሹም ሽር ሲደረግ ፡ በየና ቁልፍ ቦታዎች እነማን ተሸረው እነማን እንደ ተሾሙ ፡ ልዩ ጸሐፊዎቻቸውና ተላላኪዎቻቸው ማን ማን እንደሚባሉ ስለሚያስታውቁቸው ፡ እንደ ልደት ፡ ፋሲካ ፡ ቅዱስ ዮሐንስና መስቀል ባሉ አውዳ አመት ባሎችና እንዲሁም እያንዳንዳቸው እንደ ሰርግ ፡ ተዝካር ፡ ወይም ሌላ ጉዳይ ሲገጥማቸው ፡ ለሁሉም እንደዩማእረጋቸው ከላይ ፡ ከሰንጋ ጀምሮ ሙክት ፡ ማር ፡ ቅቤ ፡ ከኩንታል እስከ ፈረንሱላ ቡና ከየኪ የሚላከው ከዚያ ተልኮ ፡ ከየኪ ሊላክ የማይችለው አዲስ አበባ ተገዝቶ ፡ ከበጎ ምኞት መግለጫ ጋር በዩስማቸው እዩተጻፈ ፡ ስጦታው በወኪሉ አማካይነት እንዲደርሳቸው ይደረጋል ። ቀኛዝማች ዳኘ በተለይ ፡ የሶስቱን ሚኒስቴሮች ሹማምንትና ሰራተኞች መርጠው ገጸ-በረከት እንዲሰጡ ውስጥ አዋቂ ስለ መከራቸው ፡ ምክሩን ተቀብለው በያመትባሉም ፡ ልዩ ጉዳይ ሲገጥማቸውም ፡ ልክ እንደ ግብር ሳያስታጉሉ የሚሰጡበት ፡ ካዲስ አበባ ውጪ ባገር አስተዳደር ፡ ወይም በሌላ ስራ የተሰማሩ ሹሞች ሁሉ በስራቸው የተቀራረበ ግንኙነት ያላቸው ከነሱ ጋር ስለ ሆነና እያርገው እንጂ ከፉ ነገር ቢደርስ ፡ ሊጠቅሙም ፡ ሊጎዱም የሚችሉ እነሱ ስለሆኑ ነው ። “ ከይን የራቀ ከልብ ይርቃል” እንደ

@OLDBOOKSPDF

ሚባለው ፡ ይልቁንም ከማእከላዊ ባለስልጣኖች አይን ርቀው በዩጠቅ ላይ ግዛት ፡ ባገር አስተዳደርና በሌላ ልዩ ልዩ ስራ የተሰማሩትን ፡ ከል ባቸውም ለማራቅ የሚጥሩት እጅግ ስለሆኑ ፡ የውስጠኛ በውጮኛ ላይ ከሚገኙ ጠላቶች በሚደርሰው ሁሉ መከላከል ፡ የውጮቹ እዚያ ከሚ ያገኙት ለውስጠኞች ማካፈል በጽሑፍ ያልሰፈረ ፡ በቃል እንኳ ግልፅ ብሎ ያልተነገረ ፡ ነገር ግን ሁሉም ተግባብቶ ፡ ተስማምቶ የሚከተለው ስራት ስለሆነ እሳቸውም መከተል አለባቸው ! ሲቆጣ ፡ ሲቀጣ ፡ ሲሾም ሲሽር ፡ ባይሽር ከጥሩ ወደ መጥፎ ፡ ከመጥፎ ወደ ጥሩ ቦታ ሲያዘዋውር ከሚችል ባለስልጣን ርቆ ሲሄድ ፡ እዚያ ጀርባ ጠባቂ ሳያስቀምጥ የሚ ሄድ ፡ ጋሻ ሳይዝ ለፍልሚያ እንደሚሰለፍ ዝንጉ ወይም ለነፍ ራሱን ለጠላቱ ጦር አጋልጦ ይሰጣል ።

መቸም ቀኛዝማች ዳኘ እንኳ ፡ ያን ሁሉ ስጦታ አዲስ አበባ ለዚያ ሁሉ ሰው በያመቱባሉ ፡ በየሠርጉና በዩተዝካሩ የሚሰጡ ፡ እንደሳቸው ባገር አስተዳደርና በተመሳሳይ ስራ የተሰማሩት ሁሉ የሚከተሉት ስራት ስለሆነና ቀን እንደ ሞላ ባይኖር ስለሚችል ፡ እንዲያ እንዲያ ባለ ድን ገተኛ ክፉ አጋጣሚ መጠንቀቅ አይከፋም ። እንዲያ ባለው ያልታሰበ አደጋ የደጀን ምሽግ አስቀድሞ አሰናድቶ መቀመጡ ለልብ ተጨማሪ እምነት ፡ ለመንፈስ ተጨማሪ እረፍት ይሰጣል በማለት ነው እንጂ ፡ ከከ ሳሾቻቸውና ከወንጀሮቻቸው ጋር በዩጊዜው የሚነሳው ክርክርና ጦርነት የሚያልቀው ከቤታቸው ሳይወጡ ፡ ከኀሬ ዳኛ እየተሳከላቸው እዚያው የኬ ነው ። የኬ የማያልቀው ወይም ከየኬ የሚያመልጠው ኀሬ ማለት አለበት ። ምንም ቢሆን ኀሬን አልፎ አዲስ አበባ ደርሶ አያውቅም ።

አዲስ አበባ የቀኛዝማች ዳኘን ስጦታ በወኪላቸው በኩል የሚቀ በሉት ሹማምንትና አገናኞቻቸው ፡ እንኳዋንስ በያመትባሉና ከበድ ከበድ ያለ ወጪ የሚያስከትል ድግስ ሲኖርባቸው ፡ አንድ ቀን ሳይታጎል ለሚቀበሉት ስጦታ እንደ ሌሎች ዋጋ ሲከፍሉዋቸው ፡ ስጦታቸውን ነው እንጂ ቀኛዝማችን ፡ ራሳቸውን መልካቸው ቀይ ይሁን ጥቁር ፡ ቁመ ታቸው ረዥም ይሁን አጭር አያውቋቸውም ። ቀኛዝማች ዳኘ ለአህ ላዲስ አበባ ቀለብተኞቻቸው የሳቸው ያልሆነ ፡ በቁጥራቸው ልክ የተለ ያዩ መልክ አላቸው ! የቀኛዝማች ዳኘ ስም ሲጠራ እያንዳንዱ ያዲስ አበባ ቀለብተኛቸው ፡ ስማቸውን ከስጦታቸው ጋር ያዛምድና እንደ መሰለው ፡ ደስ እንዳለው አሳምሮ ስሎ ያያቸዋል !

በዩጠቅላይ ግዛቱ ፡ በልዩ ልዩ ስራ ተሰማርተው እዚያ ከሚያገኙት ላዲስ አበባ ባለስልጣኖችና ላገናኞቻቸው ከሚከፈሉት ሁሉ ተቀጥቶ ምህረት እንዲደረግለት ፡ ተከስሶ እንዲፈረድበት ፡ የደመወዝ ፡ ወይም

@OLDBOOKSPDF

የማአረግ እድገት እንዲደረግለት፣ ወይም ከከፋ ወደ ተሻለ ቦታ ለመዛወር እንዲፈቀድለት የሚያስቸግር ከቀኛዝማች ዳኛ በቀር አንድ የለም፤ ቀኛዝማች ዳኛ ብቻ ስጦታቸው በሳቸው ደረጃ ካሉት ሁሉ እጅግ ድርብ ሁኖ ሳለ፣ ለዚያ "እዳ ወይም ቅጣት ማሩኝ፣ ደመወዜ ጨምሩልኝ፣ የማእርግ እድገት አድርጉልኝ፣ ወይም ፍርድ አጣማችሁ ፍረዱልኝ" ብለው ህሊናን የሚቆረቁርና ራስን የሚያስታዝብ ጥጋ ጠይቀው ስለማያውቁ፣ ሁሉም ለሳቸው ያላቸው አክብሮት እንደዚያው እጅግ ድርብ ነው። አንድ ቀን አዲስ አበባ የሚቀመጠው የቀኛዝማች ዳኛ ወኪል ወዳገር ግዛት ሚኒስቴር አፕርሶኔል ጽህፈት ቤት ቀጠሮ አንድ የተዘጋ እንቬሎፕ ተቀበለ።

"ለቀኛዝማች ቶሎ እንዲደርሳቸው አድርግ። ጎሬ ለንደራሴው የተጻፈላቸው ግልባጭ ነው። እንተም ጥሩ ረዳታቸው ስለሆንህ ደስታቸው ደስ እንደሚያሰኝህ አውቃለሁና፣ ምንም እንኳ ምስጢር ማውጣት ባይገባ . . . መልክቱ ምን እንደሆነ ልንገርህ። ቀኛዝማች ጥሩ አርበኛ ከመሆናቸውም ሌላ፣ መንግስታቸውን ከልብ ወዳጅና ረዥም ዘመን በወረዳ ገዥነት ያገለገሉ መሆናቸውን ምንም እንኳ እሳቸው መግለጽ ባይሹ መስሪያ ቤቱ ፈልጎ ስለ ደረሰበት፣ እዚያው ኢሉባቦር ውስጥ ያውራጃ ገዥ እንዲሆኑ መወሰኑን የሚገልጽ ነው። ነገር ግን ወደ ተሾሙበት አውራጃ ከመሄዳቸው በፊት፣ እዚህ መጥተው ከሚኒስትሩ መገናኘትና ጌቶቹን እጅ መንሳት አለባቸው" አሉ የፐርሶኔሉ ሹም። ወኪሉ መሬት መሬት እያዩ ዝም ብሎ ቆመ።

"ምን ምን ሆንህ?" አሉ ሹሙ።

"ቀኛዝማች የሉም" አለ ወኪሉ፣ ሹሙን ባዘነ ፊት እያዩ።

"እንዴት? ወዴት ሄዱ?"

"ተገደሉ" አለ ወኪሉ፣ ለመሰማት በሚያስቸግር ዝቅተኛ ድምጽ አይኑን ከሹሙ ላይ አንስቶ እንደ ገና መሬት መሬት እያዩ።

"ምን? መቼ?" አሉ የፐርሶኔሉ ሹም በጣም ደንግጠው።

"የተገደሉበትን ትክክለኛ ቀን ገና አላወቅሁትም፤ እኔ ትናንት ነው የሰማሁት፤ ብቻ . . . የዛሬ አስር ቀን ጽፈውልኝ ስለ ነበረ በዚህ ሳምንት ውስጥ መሆን አለበት።"

"ገዳያቸው ታውቋል?"

"ከመገደላቸው በቀር ምንም ዝርዝር ስላልደረሰኝ፣ ዛሬውኑ ለመሄድ በመሰናዳት ላይ ነኝ።"

@OLDBOOKSPDF

“ እኛ የምንረዳህ ነገር አለ ?” አሉ ሹሙ ፤ እንገታቸውን ደፍተው ቆይተው ።

“አሁን ለጊዜው ምንም . . . የማስቸግርበት ነገር የለም ፤ እዚያ ለደርስ ነው ።”

የቀኛዝማች ዳኘ ሞት እንደ ተሰማ ፤ ያዲስ አበባ ድርጎኞቻቸው ሁሉ በተለይ ባለገቅተኛ ደመወዝ የሆኑት በጣም አዝነው ነበር ። ከሁለት አመት በሁዋላ ገዳዮቻቸው ተይዘው በምርመራ ቆይተው ፤ አዲስ አበባ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለፍርድ በመቅረብ ላይ መሆናቸው ሲሰማ እኒያ ድርጎኞቻቸው ሁሉ ያዘኑትን ያክል ደስ አላቸው ። ስለዚህ እኒያን ደግሰው የገደሉትን ወንጀለኞች ለማየትና “ እይናችሁ ይፍሰስ” ለማለት አንደኛ የወንጀል ችሎት በሚቀርቡበት ቀን ፤ ከታላላቁ ሹማምንት በቀር ሁሉም ከያሉበት ፤ በዩምክናያቱ እያስፈቀዱ ሄደው በጥዋት ፍርድ ቤቱን ሞልተው ዳኞችና ወንጀለኞች እስኪገቡ ይጠባበቁ ጀመር ። ከዚያ መጀመሪያ ዳኞች ፤ ቀጥለው እታቢ - ህጉ ከረዳቶቻቸው ጋር በቃ በቃቸውን እንደያዙ ፤ ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳን ገደሉ ተብለው የተያዙት እስረኞች እንዲቀርቡ ታዝዞ ፤ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ፤ አንዳንድ እጃቸውን ለዩብቻ የታሰሩበትን ሰንሰለት አንዳንድ ፖሊስ ይዞ እዩመራቸው ገብተው ፡ እንደነሱ በነፍስ ግዳይ የተያዙ እስረኞች በሚቆሙበት ቆሙ ። ያንጊዜ ፤ እዚያ ቤት ውስጥ ከተሰበሰበው ሕዝብ የሚበዛው ፡ የሚሳደበው ሲሳደብ ፤ የሚራገመው ሲራገም ፡ የሚገተው ጡጫውን ወደስረኞቹ እዩነቀነቀ ሲዝት ፤ ጫጫታውና ድብልቅልቁ ሽብር የሚነሳ እስመስሎ ስለታዩ ፤ ተጨማሪ ፖሊስ ተጠርቶ እንደ ገና ጸጥታ እስኪገኝ ዘለግ ያለ ጊዜ ወሰደ ። ፖሊሶቹ ከህዝብ መሀከል ሁከት ለማስነሳት እዩዛቱ ያስቸገሩትን እያዳፉ በማስወጣት ፤ ሌሎችን በማስፈራራት ከብዙ ጥረት በሁዋላ ተነስቶ የነበረው ድብልቅልቅ እዩተቀነሰ ፤ እዩተቀነሰ ሄዶ በቤቱ ጸጥታ ሲሰፍን ፤ ሰብሳቢው ዳኛ ፤ አቶ እንተነህ ተሰፋዬ ፤ ያን ሰፊ ቤት የመላውን ህዝብ ከግራ ወደቀኝ ፡ ከቀኝ መልሰው ወደ ግራ ተመልክተው እንደሚናገሩ “ እሁ-ሁ” ብለው ጉሮሮዋቸውን ካጠሩ በሁዋላ ፤ እይኖቻቸውን እስረኞቹ ላይ ተክለሩና ዝም ብለው እነሱን ይመለከቱ ጀመር ።

“ዳኛው ምን ሆኑ ፣ አቶ አንተነህም ምን ነካቸው ?” እዩተባባለ ችሎቱን የሞላው ህዝብ እሰበሱ ሲንሾካሾክ ፤

“ተከሳሾች ፤ ስማችሁን ከናባታችሁ እንድትገልጹ ፍርድ ቤቱ ይጠይቃችሁዋል” አሉ መጨረሻ ፤ እስረኞቹ ላይ ተተክለው የነበሩ እይኖቻቸውን እርገበገቡና ።

@OLDBOOKSPDF

"ስሜ ጥላሁን ፤ ያባቴ ስም ፈይሳ ነው" አሉ ወንዱ ።

"ስሜ እጸገነት ፤ ያባቴ ስም አሸብር ነው" አሉ ሴቲቱ ።

"በተከሰሳችሁበት ወንጀል የሚከራከርላችሁ ጠበቃ አላችሁ ?"

"የለንም" አሉ ወንዱ ።

"የለንም" አሉ ሴቲቱም ፤ ወንዱን ተከትለው ።

"ፍርድ ቤቱ ጠበቃ እንዲያቆምላችሁ ትሻላችሁ ?"

"አንሻም"

"አንሻም"

"የህግ እውቀት አላችሁ ?"

"የህግ ትምህርት የለንም ፤ ነገር ግን የተከሰስንበትን . . ደህና አድርገን ስለምናውቀው ፤ ጠበቃ አያስፈልገንም" ሲሉ ወንዱ ፤ ሴቲቱም ወንዱ ባሉት የሚስማሙ መሆናቸውን ራሳቸውን ወደ ላይ በመግፋት ገለጹ ።

"ማስፈያ ነው እንግዲህ ፤ ተከሳሾቹ ጠበቃ አንሻም ፤ ራሳችን እንከራከራለን ስላሉ ፤ አቃቤ- ህግ ክስዎን ማቅረብና ለሚያቀርቡት ክስ 'ይረዳኛል' የሚሉትን ማስረጃ ሁሉ ማቅረብ ይችላሉ ። ብቻ ከዚህ ጋር ሳስጠንቅቅዎ የምወደው ፤ ለፍርድ ቤቱ ከቀረበው ጉዳይ ጋር ያልተዛመደ ነገር እየጨመሩ የስነ - ስራት ችግር እንዳይፈጠርብን ነው ። ከዛሬ ቀደም . . . ያልደረሰ ነገር ስላልተናገርሁ ፤ ይቅርታ እንደሚያደርጉልኝ አምናለሁ " አሉ ሰብሳቢው ዳኛ ፤ እዚያ አካባቢ 'አቃቤ - ወንጀል' ተብለው የተሰየሙትን አቃቤ-ህግ በጥላቻ አይን እየተመለከቱ ።

ሰብሳቢው ዳኛ ተከሳሾችን ሲጠይቁም ፤ ሁዋላ "ማስጠንቀቂያ" ብለው ለሳቸው የተናገሩትንም ከሙንገድ የወጣ ፤ ትርፍ ነገር አቃቤ ህጉ ሲሰሙ ፤ ከመገረም አልፈው በጣም ነበር የደነገጡ ! ትርፉ ነገር ብቻ አልነበረም ያስደነገጣቸው ፤ እንዲያውም ከትርፉ ነገር ፤ ጠቅላላ አነጋገራቸው ፤ ይልቁንም ድምጻቸው ነበር በጣም ያስደነገጣቸው፤ ያን ድምፅ ሲሰሙ አንድ በውስጣቸው ተደብቆ የተቀመጠ ነገር ፤ ያ ድምጽ ያስበረገገው ይመስል ፤ ልክ እንደ ድርጭት ወፍ ከዚያ "ብርር ብርር" ብሎ ፤ ተመንጥቆ የወጣ መስሎ ተሰማቸውና አይኖቻቸውን ፏት-ብፏት እንደ ተተከሉ እዚያው ፍዝዝ ፤ ድንዝዝ ብለው ቀሩ! እንዲያ እንደ ሆኑ ቆይተው ጠፍዘዙ ፤ መደንዘዙ ትንሽ እንደ ማለፍ ሲልላቸው ፤ ያን ድምጽ ከተናጋሪው መልክ ጋር ለማዛመድ ቢሞክሩ ፤ የዳ

@OLDBOOKSPDF

ኞች መቅመጫ እታብያን - ህጉ ከሚቀምጡበት ራቅ ያለ ከመሆኑም ሌላ ፤ ሁዋላው ከታች እጭር ግንብ ሆኖ ከላይ በሙሉ መስተዋት ብቻ በመሆኑ ፤ ያ የሁዋላ ብርሃን እንደ እታብያን - ህጉ በፊት በኩል ያሉት ፤ የዳኞችን ፊት አጥርተው እንዳያዩ ስለሚከለክላቸው ፤ ጥርጣሬያቸውን ለማስወገድ እይኖቻቸውን እያሻሹ ያደረጉት ሙከራ ሁሉ ሳይሳካ ቀርቶ ተስፋ ሲቆርጡ ፤ "በፍጹም ኮ . . . ሊሆን የማይችል ነው ! " አሉ በእንግሊዝኛ ፤ ድምጻቸውን አስምተው ። በእንግሊዝኛ የተናገሩትን ፤ ያሰቡት እንጂ የተናገሩት አልመሰላቸውም ነበር !

"ከስዎን ከማስረጃዎ ጋር ማቅረብ ይችላሉ አልሁኮ ! አልሰሙኝምን?" አሉ ሰብሳቢው ፤ እታቢ-ህጉ ባሳባቸው የተነሳውን ክርክር እያዳመጡ ዘለግ ያለ ጊዜ ዝም ብለው ስለቆዩ ። ያነሉት እታቢ-ህጉ የተናገሩትን በጽሑፍ አሰናድተው ይዘው ከዚያ ባያነቡ ኖሮ ሳይደናገራቸው ፤ እንደ ልማዳቸው በቃል ብዙ መናገር አይሆንላቸውም ነበር ።

"እሺ ፥ ክቡር ፕሬዘደንት ፤ ብቻ . . . ወደ ዋናው ነገር ከመግባቴ በፊት ለማመልከት እንዲፈቀድልኝ የምለምነው ፤ ከዛሬ ቀደም እንከኑሞንስ ለፍርድ ቤቱ ከቀረበው ጉዳይ ጋር ያልተዛመደ ነገር እየጨመርሁ የስን - ስራት ችግር እንዲፈጠር ሳደርግ ፤ እኔም ራሴ ከዛሬ በፊት ከፊትዎ ቀርቤ የማላውቅ መሆኔን ነው ! ስለዚህ . . . እሁንም ለክቡር ፕሬዘደንቱ ማረጋገጥ የምፈልገው ፤ ከዛሬ ቀደም የተፈጠረ ችግር ካለ ፤ ያን ችግር የፈጠርሁት እኔ አለመሆኔንና ወደፊትም እንደ ሁልጊዜው የፍርድ ቤቱን ስነ - ስራት የማከብር መሆኔን ነው ! " አሉ እታቢ-ህጉ ።

"እሺ ፤ አሁን ይቀጥሉ" አሉ ሰብሳቢው ዳኛ ።

"የተከበራችሁ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኞች " አሉ እታቢ-ህጉ ፤ እጅ እንደ መንሳት ብለው ። "ክቡራን ጌቶቼ ! እዚህ ፍርድ ቤት ፤ በዩለቱ በወንጀል ስራ እዩተከሰሱ የሚቀርቡ ሰዎችና የሚከሰሱባቸው ወንጀሎች እጅግ ብዙ ናቸው ። ዛሬ የምናቀርበውን የወንጀል ስራና የምናቀርባቸውን ወንጀለኞች የመሰሉ ግን ቀርበው የሚያውቁ አይመስለኝም ። ምናልባት እኔ የማላውቃቸው ይኖሩ እንደሆን እንኳዋ እንዲያ ያሉት ወንጀሎችና ወንጀለኞች በዚህ ፍርድ ቤት ታሪክ ውስጥ በጣም ጥቂት እንደሚሆኑ በፍጹም አልጠራጠርም ።

ሰው በመንፈስ ከመላእክት ፥ በስጋ ከእንስሳት ባህርያት ተካፋይ እንደ መሆኑ ፤ አንዳንድ ጊዜ እንደ እንስሶች በጊዜያዊ ስሜት ማለት በቁጣ ፥ በቅናት ፥ በፍራትና እነሱን በመሳሰሉት ደመ ነፍሶች

@OLDBOOKSPDF

ተገፋፍተው ሰባዊ አእምሮው ሲታወርና ልቡ ሲሸበር ፣ ወይም የሰውነት ማንነትን ሲያጣ ፣ ወንጀል ይሰራል ፤ ነገር ግን አዋቂ አእምሮውና ፈራጅ ህሊናው ሳይታወኩ ፣ በፍጹም ጤና ፣ በጥሞና "እስቲ ወንጀል ልስራ" ብሎ ወንጀል የሚሰራ ሰው የለም ። ስለዚህ ጌቶቼ ! ስለዚህ ጊዜያዊ ቁጣን ፣ ቅናትን ፣ ፍራትንና እነሱን የመሳሰሉትን የእንስሳት ባህሪዎች መጣታት ኢትዮዮት ፤ በነሱ ተገዝቶና ተገፍቶ ፣ ወንጀል የሚሰራ ሰው ከሰው ባህርያት ይልቅ የንስሳት ባህርያት ያዩለበት ፣ መንፈሰ ደካማ በመሆኑ የሚያዝኑለት እንጂ የሚጠሉት አይደለም ። እንዲያ ያለው ሰው ቢግር ቢመከር ታርሞ ፣ ተሻሽሎ ህብረተሰቡን ሊጠቅም ስለሚችል ፣ ቅጣቱ መመሪያና መምከሪያ መሆን አለበት ። ነገር ግን አስቦ ፣ አሰላስሎ ፣ አቅዶ ሰርቶና የሰራውን አቅድ በዝርዝር አጥንቶ ፣ ወንጀል የሚሠራ ሰው ፣ ከሰዎች ማህበር ውጭ የሰይጣናት ማህበርተኛ በመሆኑ ፤ እንደ ሰይጣን የሚቆጠርና ሰይጣንንም መክሮና አስተምሮ ሰው ማድረግ ስለማይቻል ፣ ሊጠሉት እንጂ ሊያዝኑለት አይገባም ።

እንግዲህ ጌቶቼ ! ዛሬ የቀረበላችሁን ወንጀልና ወንጀሉን የሰሩትን ሰዎች በዚህ አንጻር ስንመለከታቸው ፣ ወንጀሉ በጊዜያዊ ቁጣና በደም ፍላት የተሰራ ሳይሆን ፣ ብዙ ጊዜ ታስቦ ፣ ተጠንቶ ፣ በቀዝቃዛ ደም የተሠራ ፣ ወንጀሉን የሰሩት ሰዎች ሰባዊ ርህራሄና የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል ህሊና የሌላቸው ፣ ልክ እንደ ሰይጣን ወንጀል ሰርተው ፣ በሰሩት ወንጀል ደስ ከመሰኘት በቀር ወንጀል በመስራት ሌላ አላማ የሌላቸው ሆነው እናገኛቸዋለን ። ስለዚህ ጌቶቼ ! ስለዚህ እንደነዚህ ያሉት ወንጀለኞች የሰይጣን እንጂ የሰው ባህሪ እንደሌላቸው የተረጋገጠ ስለሆነ ፣ በሰዎች ማህበር ውስጥ ቦታ ሊኖራቸው ፣ እንደ ሰዎች ከሰዎች ጋር ሊኖሩ ፍጹም የማይገባቸው ናቸው ።" ብለው አቃቤ - ህጉ ሲቀጥሉ ሲሉ ሰብሳቢው ዳኛ አቋረጡና ፣

"ስላቋረጥሁዎ ይቅርታ ያድርጉልኝ ። ከንግግርዎ ሁለት የሚቃረሙ ነገሮች ስላሉ ነው ያቋረጥሁዎ ። አንደኛ እስረኞች በወንጀል ተከሰሰው ቀርበዋል እንጂ ገና ተረትተው ስላልተፈረደባቸው 'ወንጀለኞች' እያሉ መጥራት ህጋዊ አለመሆኑንና ፣ ሁለተኛ 'የሰይጣን እንጂ የሰው ባህሪ የሌላቸው መሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ ነ' ያሉትም እንዲህ ያለ የተረጋገጠ ነገር ስለሌለ ፣ ይህም ህጋዊ አለመሆኑን ከሰዎ የተሻለ የሚያውቁ የለምና ፣ እንግዲህ እንዲህ ያለውን አሌፊት እያረሙ

@OLDBOOKSPDF

እንዲናገሩ አስጠንቅቅዎታለሁ ። ይቀጥሉ ” አሉ ። ኢታቢ ሁኑ ዳኛው ለተናገሩት ሊመልሱ ሲነሱ ቆዩና እንደ ገና አባባቸውን ለውጠው ንግግራቸውን ቀጠሉ ።

“እሺ ፤ አመሰግናለሁ ፤ ጌቶቼ ! የወንጀል ስራ ምን ጊዜም ቢሆን ክፉ መሆኑ የታወቀ ነው ፤ ብቻ እንደምታውቁት ወንጀልም እንደ ሌላው ነገር ሁሉ ደረጃ ስላለው ደረጃው ከሚመጠንባቸው መለኪያ ዎች አንዱ ወንጀል የተፈጸመበት ሰው የማህበራዊ አቋሙ ነው ። ማለት ለራሱ ብቻ በሚኖር ፤ አለመኖሩ ከራሱ አልፎ ሌላ በማይጎዳ ተራ ሰው ላይ የተፈጸመ ወንጀልና በሀብቱ ፤ በውቀቱ ፤ በጉልበቱ ወገ ኑን ፤ አገሩንና መንግስቱን ሊያገለግል በሚችል ሰው ላይ የተፈጸመ ወንጀል አንድ ሊሆኑ አይችሉም ። ለራሱ ብቻ በሚኖር ሰው ላይ የተ ፈጸመ ወንጀል ምንም እንኳ ወንጀል መሆኑ ባይቀር ፤ ባንድ ሰው ላይ የተፈጸመ ወንጀል ነው ። በሀብቱ ፤ በውቀቱ ፤ በጉልበቱ ወገ ኑን ፤ አገሩንና መንግስቱን ሊያገለግል በሚችል ሰው ላይ የተፈ ጸመ ወንጀል ግን ፤ በብዙ ሚሊዮን ህዝብና በመንግስት ላይ እንደ ተፈጸመ ወንጀል ስለሚቆጠር ፤ ወንጀሉን የሰሩትም የብዙ ሚሊዮን ህዝብና የመንግስት ጠላቶች መሆናቸው አይጠረጠርም ።

“ እንግዲህ ጌቶቼ ! ይህን ጠቅላላ መሰረት ከጣልን ፤ አሁኑ በዚህ አንጻር አሁን ለፍርድ ቤቱ የቀረበው ወንጀል የተፈጸመባቸውን ፤ ቀኛዝማች ዳኛቸው ዋሪሳን አቋማን እንያቸው ። ቀኛዝማች ዳኛቸው እንዴት ያለ ሰው ነበሩ? ቀኛዝማች ዳኛቸው . . . ስማቸው ሲጠራ ነፍ ሳቸው አትደንግጥና . . . ቀኛዝማች ዳኛቸው ለራሳቸው ብቻ የሚኖሩ ፤ ተራ ሰው ፤ ሞታቸው አንዳንድ ሰው ሞት የሚቆጠር ነበሩ?አልነበሩም! ቀኛዝማች ዳኛቸው ዋሪሳ እንደ ወታደር አባቸው ጀግና የጦር መሪ ፤ እንደገዢ ግዥ ታጋሽና አዋቂ አስተዳዳሪ ፤ እንደ ዳኛ አድልዎን የማ ያውቁና የግል ጥቅምን የናቁ ፤ በዚያ ላይ ብርቱ የጸጥታ አስከባሪና ብልህ የህዝብ መምህር ፤ የህዝብ አስተማሪ ነበሩ ! ቀኛዝማች ዳኛ ቸው አንድ አልነበሩም ፤ ብዙ ነበሩ፤ ስለዚህ ሞታቸው አንዳንድ ሰው ሞት የሚቆጠር አይደለም ፤ እንደ ብዙ ታላላቅ ሰዎች ሞት የሚቆ ጠር ነው ።

“ቀኛዝማች ዳኛቸው የወዳጆቻቸውን ልብ በኩራት ፤ የጠላ ቶቻቸውን ልብ በቅናት የሚሞሉ ፤ ረዥም ታሪክ ያላቸው ፤ የታሪክ ባለጸጋ ሰው ነበሩ ። ታሪካቸው ቀደም የሚያነብቡት እንጂ እንዲህ

@OLDBOOKSPDF

በተወሰነ ጊዜ ቆሞ ሊናገሩት የሚቻል አይለም ። ስለዚህ ባለኝ አጭር ጊዜ የማይቻለውን ረዥም ታሪክ ለመዘርዘር መሞከር ታሪኩንም ፣ ሰሚታሪኩንም መበደል እንዳይሆንብኝ እሰመጥከሩን እመርጣለሁ ። ነገር ግን ፣ ስለ ቀኛዝማች በጠቅላላ የተናገርሁት እሙን መሆኑን ለማስመስከር ያክል ብቻ አንዳንድ ዝርዝሮች ለመጥቀስ እንዲፈቅድልኝ ፍርድ ቤቱን እለምናለሁ ።”

“የሙጥሹን የሀይወት ታሪክ መተረክ እዚህ የቀረበት አበረኞች ፣ ‘ፈጽማችሁዋል’ ተብለው ከተከሰሱበት ወንጀል ጋር ምን ዝምድና ይኖረዋል ?” አሉ ሰብሳቢው ዳኛ ።

“እማጠቃለዩ ላይ ይረዳኛል ብዬ ስለማምን ለመቀበል እንዲፈቅድልኝ ፍርድ ቤቱን እጠይቃለሁ ” አሉ አቃቤ-ህጉ ፣ ለሚጌታቸው ምርር ፣ ፊታቸው ክርር ብሎ ።

“የሙጥሹን የሀይወት ታሪክ መተረክ እማጠቃለያዎ ላይ ተከሳ ሾች የገደሉዋቸው ለመሆናቸው እንዴት አድርጎ ማስረጃ እንደሚሆን፣ ወይም እንደሚረዳዎ እንኳዎ አላውቅም ፤ ብቻ . . . እስቲ እሺ ይቀጥሉ” አሉ ሰብሳቢው ።

“እግዚአብሄር ይስጥልኝ ፤ ክቡር ፕሬዚደንት ! ” አሉ አቃቤ ወንጀሉ ፣ ትንሽ እጅ እንደ መንሳት ብለው ። “ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሬሳ” አሉ ቀጠሉና ። “ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሬሳ ፋሽስቶች አገራችንን ከመውረራቸው በፊት የመኳንንት ልጅ ፤ ወጣት መኮንን ቢሆኑም ፣ ተሾመው ባገረ-ገዥነት ፤ ወይም ደንብ ገብተው እንደ ደንበኛ በቀለብና በደመወዝ የሚተዳደሩ አልነበሩም ። ስለዚህ ጠላት አገራችንን ሲይዝ እንደ አገረ -ገዥ ተሾመው በገዙበት ፤ ወይም እንደ ደንበኛ ቀለብ ደመወዝ በበሉበት ተገድደው ሳይሆን ፤ የጀግንነት ወኔያቸውና ያገር ፍቅራቸው ለሳዘዙዋቸው ብቻ ፤ ንብረታቸውን እዩሸጡ መሳሪያና ስንቅ እሰናድተው ፣ ‘ሰው የወደደው ምን ገደደው ?’ እንደሚባለው ፍቅራቸው የሰበሰበውን ፤ እጅግ ብዙ ሰራዊት አደራ ጅተው ፣ የመንግስቱ ጦር ያልቻለውን ሀይለኛ ጠላት ሲጽቁዋሙ ቆር ጠው ተነሱ ። እንዴት አድርገው እንደ ተጽቁዋሙት ለመተረክ ጥሩ እህፊ መሆን ያስፈልጋል ። ግሩም አድርገው ተጽቁዋሙት !

“ፋሽስቶች ኢትዮጵያ ገብተው እስከ ወጡበት ቀን ድረስ ፣ ዳኛ ቸው ፍሬሳን ለመውጋት የሰማይና የመሬት ጦር እያስተባበሩ የላኩ እጅግ ብዙ ጊዜ ነው ። የጦርነቱ ግጥሚያም ያኑ ያክል ነው ። ነገር ግን

@OLDBOOKSPDF

አንድ ቀን እንኩዋ ጌታዬ ! አንድ ቀን እንኩዋ የፋሽስት ጦር የቀ ቻን አፈር እግሩ አልረገጠም ። ገና ጦር ሲቀርብ ፣ ቀኛዝማች ዳኘ በጲ ማጺዘት ያቆሙት የቃፈር አጥር ያስጠነቅቃቸውና ፣ የቀቻን ወሰን ወጥተው እዩገጠሙ የሚያስቀሩትን እዚቀርተው ፣ የሚተርፍ ቢኖር . . . ብዙ እንኩዋ አይተርፍም . . . ብቻ የሚተርፍ ቢኖር ! መሳሪያ ውን እያስጣሉ በሱ ፈንታ አጥረቱንና ወርዶቱን እያሸከሙ በቃኑ ነው ይመልሱት ነበር !

"ቀቻ ፣ ሀይለኛ ጥገድ በሚያውከው ውቅያኖስ ውስጥ ፣ በብ ርቱ አለት ቃጥሬ እንደ ተቀመጠች ደሴት ፣ ኢትዮጵያን አምስት አመት ሙሉ ከብር እስከ ብር ያጠካት የወራሪዋ ጥገድ ሳይነካት ፣ የነ ጻንት ስሟም እንደ ስፈነባት ፣ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ አንድ ቀን ከከብር በታው ሳይነቃነቅ ፣ እንደ ተውለበለበባት ወራረው ጠላት ድል ሆኖ ጠጣ ። የባህር ጥገድ የሚነዳው ማእበል ከደሴት አለት ቢጋጭ ወደ ሁዋላ እዩተበታተነ ፣ ደብዛው ጠፍቶ እንደሚቀር ፣ የፋሽ ስት ጥገድ እያከታተለ ይሰደው የነበረውን የጦር ማእበል ፣ አስቴ ዳኘ እዩገጨ ወደ ሁዋላ እንዲበታተንና ደብዛው ጠፍቶ እንዲቀር ያደ ርገው ነበር ! ጌታዬ ፣ ከረኸሙ ባጭሩ ፣ ቀኛዝማች ዳኘ እንደ ጦር ሙሬ እንዲህ ያሉ ነበሩ ። እገረ ግኸሙ ዳኛቸውስ ! እንዴት ያሉ ኖረ ዋል !

"እገረ ግኸሙ ዳኛቸው ፣ አባባቸውን ጉልበታቸውን ፣ ጊዜያቸውንና ሀብታቸውን ሳይቆጥቡ ፣ ለህዝብ አገልግሎት የሰጡ ፣ ስልጣንን ለህዝብ አገልግሎት ካልሆነ ለራሳቸው ድሎት የማይፈልጉ ለመሆና ናቸው ፣ ሁለት የተማሩ ወጣቶች ባልና ሚስት በገንዘባቸው ካዲስ አበባ ቀጥረው ወስደው በትምርት ፣ በጤና አጠባበቅና በጠቅላላው የኑሮ ማሻሻል ፣ በግዛታቸው በየኪ ይሰራ የነበረው ግሩም ስራ በኔ አፍ ከሚነገር ፣ ከሁለት አመት በፊት ባዲስ ዘመን ጋዜጣ ከተጻ ፈው አንድ ክፍል እንዳነብ ይፈቅድልኝ ።"

ዳኛች አስበሳቸው ተያይተው መፍቀዳቸውን ራሳቸውን ወደ ላይ በመግፋት ሲገልጹላቸው ንባባቸውን ቀጠሉ ።

"የኪ እንዳንዳንድ የጳር አገር ሀብታም ክፍሎች ፣ ሀብትዋና ህዝ ብዋ ጎንለጎን አብረው እዩኖሩ ሳይገናኙ ፣ ሀብትዋ የሚጠቀምበት ባለማግኘቱ ፣ ህዝብዋ ሰርቶ መጠቀም ባለማወቁ ፣ ሁለቱም ለዩብቻ እንዲሁ ባከንው የሚጠፉባት አገር ነበረች ! ህዝብዋ ከራብ ከጥምና ከበሽታ ነጻ ወጥቶ ፣ ማንበብና መጻፍ ፣ አማርኛ መናገር እንኩዋ

@OLDBOOKSPDF

ችሎ ፣ እንዲያው በጠ… ችና በሌላ ልዩ ልዩ ስራ ከሌላ ክፍል ፣ ወደዚያ እየሄዱ እንደሚያውቃቸው ሰዎች ፣ ኑሮውን እሻሽሎ መኖር ለሱ ያልተፈቀደ ፣ እንደ ፈጣሪ ምስጢር ያልተፈቀደላቸው ሊደርሱበት የማይችሉ መሆኑን አምና ፣ ራብን ፣ ጥሙን ፣ በሽታውን ፣ ድንቁርናውንና እነዚህ የሚያስከትሉትን ክፉ ነገሮች ሁሉ ከፈጣሪ እንደ ታዘዘበት ክፉ ቁራኛ ተቀብሎ የሚኖርባት አገር ነበረች ! አሁን ግን ይህ ሁሉ ያለፈ ታሪክ ሆነ ! ከሶስት አመት ወዲህ ጥላሁን ፈይሳና ሶፊያ ሙሴት የሚባሉ ወጣቶች ባልና ሚስት ፣ ከአዲስ አበባ ትምህርታቸውን አቋርጠው ፣ ባዶ እጃቸውን ወደዚያ ሄደው ፣ የሀዋርያነት ስራቸውን ከጀመሩ ወዲህ የኪ ሌላ አገር ፣ ዘመናዊት አገር ሆነች ! ዛሬ በየኪ አመት ሙሉ የጉዋሮ እሸት የማይበላ ፣ ከቀለቡ አስተርፎ ወደ ገንዘብ የሚያቀናው እህል በጎተራው የማይሞላ ሰው ስለማይገኝ ፣ ራብ ድል ሆኖ ከየኪ ሸሸ ! አንድ ቀይ ሳንቲም ላይ ወጣ ፣ እዚያው ካገሩ ዋንዛ በተፈለፈለ ገንዳ ከሩቅ ተራራ እየተጠመጠመ ፣ ገደል እየተሸገረ እየመጣ ፣ በየመንደሩ የሚፈስሰው ውሀ ለመጠጥና ለንጽህና ከሚያስፈልገው ተርፎ ለመስኖ ስለሚበቃ የውሀ ችግር ተረሳ ። ይህን የጥላሁንንና የሶፊያን ዘዴ ፣ ይህን ውሀ ከሩቅ ተራራ እየዞረ ፣ ገደል እየተሸገረ በየመንደሩ የሚፈስበትን ዘዴ የዘመኑ መሀንዲሶች ሳያዩ "ሰርታችሁ እሳዩ" ወይም "ማምጣት አቅርቡ" ቢባሉ ብዙ ሚሊዮን እንደሚጠይቁ አይጠረጠርም ! ዛሬ በየኪና ባካባቢው ማንበብና መጻፍ ፣ ያራቱን መደቦች ስሌት የማያውቅ ፈልጎ ማግኘት በጣም ያስቸግራል ! አሁን በየኪ የቡናና የሀል ወፍጮዎች ፣ የሸክላ መጥበሻና የዳቦ መጋገሪያዎች በብዙ ቦታዎች ተቋቁመው ስለሚታዩ ፣ ሕዝቡ ከርሻ ወደ ፋብሪካ ፣ ከድህነት ወደ ብልጽግና በመሸጋገር ላይ ነው ማለት ይቻላል ! ይህ ሁሉ በሶስት አመት ! ከሁሉም ደስ የሚያሰኘው ሶፊያና ጥላሁን የጀመሩት የልማትና የእድገት ስራ ፣ ያገሩን ሀብት ፣ ያገሩን እውቀትና ጉልበት አስተባብረው ፣ በዚያ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ፣ ወደፊት እየበረታ እንጂ እየደከመ የማይሄድ ለመሆኑ ይህ የታመነ ዋስትና መሆኑ ነው ።

"ሰው የሚያምንበት ግብ ፣ ወደግቡ ለመድረስ ጽኑ ፍላጎትና የሚፈልገውን ለማድረግ ቆራጥነት ካሉት ፣ ሊያሸንፈው የማይችል ችግር እንደሌለ ጥላሁንና ሶፊያ በየኪ የሰሩት ታምር ጥሩ አስረጂ ነው ! መቁረጥ ገንዘብ ፣ መቁረጥ ሀይል ፣ መቁረጥ እውቀት ፣ መቁረጥ ሁሉ መሆኑን ጥላሁንና ሶፊያ መንግስትን አንድ ቀይ ሳንቲም ሳያስወጡ ፣ እነሱ አንድ ቀይ ሳንቲም ሳይዙ ወገኖቻቸውን ለሥር

@OLDBOOKSPDF

ዳት ዷኑ ፍላጎታቸውንና የፈለጉትን ለመፈጸም ቆራጥነታቸውን ብቻ
ይዘው ኗደው ፤ በየኪ የሰሩት ግሩም ስራ ምሳሌያቸውን ሠ ከተሏ ለሚ
ሁሉ ጥሩ መሪ ነው ! ” ብለው ስለሁለቱ ባልና ሚስት ስራ በጋ
ዜጣ የተጻፈውን አንብበው ሲጨርሱ ፣ አቃቤ ህጉ ጋዜጣውን አስቀ
መጡና ፤ ጌቶቼ እሱ ከሰሚት ጋር ። “ ጌቶቼ ! እንዲህ ያለ አገረ ገዥ
ራሱ የሚሰራው አልበቃው ብሎ አጥቆችን በገንዘቡ እዩቀጠረ ፣ የሚገ
ዛውን አገር ህዝብ የሚረዳ አገረ ገዥ ማን አይቶ ያውቃል ? እኔ
አይቼ አላውቅም ! ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ ! የሚያስተዳድሩትን
ህዝብ ከድህነት ፣ ከደዌና ከድንቁርና ነጻ እንዲሆን ፣ መንግስትን
አንድ ቀይ ሳንቲም ሳያስወጡ ፣ በገንዘባቸው እንዲህ ያሉትን ፈቃ
ድና ችሎታ ያላቸው አጥቆች እዩቀጠሩ ፤ አሁን የሰማችሁትን ታምር
የሚሰሩ አገረ ገዥ ነበሩ ! የሚያስተዳድሩትን ህዝብ እንዲረዱላቸው
በገንዘባቸው እዩቀጠሩ የሠሰዷቸው ልዩ ልዩ እውቀት ያላቸው
ሰዎች እኒህ ሁለቱ ብቻ አልነበሩም ፤ ብዙ ነበሩ !

“እንዲያው በጠቅላላ ጌቶቼ ፤ ሙዋቹ ምን አይነት ሰው እንደ
ነበሩ ለማጠቃለል ፣ ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ እንደ ወታደር አለቃ
ለወታደር አለቆች ፣ እንደ አገረ ገዥ ለአገረ ገዥዎች ፤ እንደ ዳኛና እንደ
ጨዋታ ጠባቂ ለዳኞችና ለጸጥታ ጠባቂዎች ጥሩ አርአያ ፣ ጥሩ ምሳሌ
የሚሆኑ ነበሩ ! ስለዚህ ፤ ሞታቸው ላገራቸው ፣ ለመንግስታቸው
ለወገናቸው ብርቱ በደል ስለሆነና በሳቸው ላይ የተፈጸመው ወንጀል
ባገር ፣ በመንግስትና በወገን ላይ እንደ ተፈጸመ ስለሚቆጠር ፣ ወንጀ
ሉን የሰሩት ሰዎች እውቀው ፣ አስበው በበደሉትና በጎዱት ማህበር
ውስጥ በምንም ሁኔታ ቦታ ሊኖራቸው የሚገባቸው አይደሉም !

“ጌቶቼ ፤ ይህን አሰቃቂ ወንጀል በኔህ ብሩክ ፣ ቅዱስ ሰው ላይ
የፈጸሙት ተከሳሾች ፣ ጥላሁን ፈይሳና አጸገነት አሸብር ለመሆናቸው ፣

1ኛ. ቀኛዝማች ዳኛን ለመግደል ብቻ አምስት አመት ሸፍቶ መኖ
ሩን አገር የሚያውቅለትን ጥላሁን ፈይሳን ፣ ለመሸፈቱ ምክንያት
የሆነች ፤ የቀኛዝማች ዳኛ ሚስት አጸገነት አሸብር ፣ በሌሊት
ቀጠሮ ጠቅሰው ፣ የቤት ሰው ብቻ የሚያውቀውን የጎዋሮ በር ከው
ስጥ ከፍተው አስገብተው ፣ ባላቸውን እገዛ ቤታቸው ውስጥ በገዛ
ሽጉጣቸው ተባብረው ከገደሉዋቸው በሁዋላ ፣ አብረው ሲሸሹ በወ
ጡበት የጎዋሮ በር የተገኘው የአጸገነት ኩታና ይህኑ ፋራ ተከትለው
ፖሊሶች ሲፈልጉ ፣ ሁለቱ ነፍስ ገዳዮች ባንድ ላይ ፣ ጫካ ውስጥ ተሸ
ሽገው መገኘታቸው ይመሰክራል ።

@OLDBOOKSPDF

2ኛ. ቀኛዝማች ዳኘ እቤታቸው ውስጥ በጥይት ተደብድበው በወደቁበት ፤ ነፍሳቸው ሳታልፍ ፖሊሶች ደርሰው ሲጠይቋቸው ፤ "ገዳዬ ጥላሁን ፈይሳ ነው" ብለው የኑዛዜ ቃላቸውን ሰጥተዋል ።

3ኛ. ቀኛዝማች ዳኘን ፤ ጥላሁንና እጸገነት በገዛ ሽጉጣቸው ደብድበው መግደላቸውን አስራ ሁለት ያይን ምስክሮች መስክረውባቸዋል ።

4ኛ. ከሁሉም የበለጠ አጠቃላይ ምስክር ፤ ጥላሁን ፈይሳና እጸገነት አሸብር ራሳቸው ፤ በፖሊሶች ምርመራ ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳን መግደላቸውን አምነው ፤ በፊርማቸው በሰባት ምስክሮች ፊት ቀርበው መፈረማቸው ነው ።

"ስለዚህ ጌቶቼ ! ጥላሁን ፈይሳና እጸገነት አሸብር ፤ በድንገት ፤ በደም ፍላት ፤ ወይም በቸልተኛነት ሳይሆን ፤ አስበው ፤ በቀዝቃዛ ደም አቅድ ሰርተውና የሰሩትን እቅድ ባዝርዝር አጥንተው ፤ የሰሩት ወንጀል ፤ ወንጀሉ ከተሰራባቸው ሰው አልፎ አገርን ፤ መንግስትንና በጠቅላላው ህዝብን ፤ ወይም ማህበርን የሚጎዳ መሆኑ ፤ የሚያጠያይቅ አይደለም ። ስለዚህ ፤ የማህበሩን ደህንነት ለመጠበቅ እንደነዚህ ያሉትን አስጊ ወንጀለኞች ከውስጡ አርጦ ማጥፋት አስፈላጊ ስለሆነ ፤ በከፍተኛው ቅጣት ፤ በሞት እንዲቀጡ ፍርድ ቤቱን እጠይቃለሁ" ብለው ሲጨርሱ ፤ እዚያ የተሰበሰበው ህዝብ ፤ ወንጀሉ የተፈጸመባቸው ሰው ምን ያክል ታላቅ ሰው እንደ ነበሩ ፤ ወንጀሉን የሰሩት በምን እንዴት ያሉ ፤ በሰው አምሳል ተሸሽገው የመጡ ክፉ ሰይጣኖች እንደ ሆኑና ያቃቢ ህግ ክስ አመሰራረት ከቀረቡት ማስረጃዎች ጋር የማያነቃንቁ ፤ ብርቱ ስለ መሆናቸው ፤ እሰበሉ ፤ ቃሉ ብሎ ሲተች ሹክሹክታውና ህምህምታው ዝም እስኪል ዘለግ ያለ ጊዜ ቆዩ ።

"አቶ ጥላሁን ፈይሳ" ሲሉ ሰብሳቢው ዳኛ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ፤ ዝምታው ፤ ጸጥታው ፍጹም ሆነ ። "አቶ ጥላሁን ፈይሳ ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳን ፤ ግብረ አበርዎ ከተባሉት ፤ ከወይዘሮ እጸገነት አሸብር ጋር ተባብራችሁ ለመግደላችሁ አቃቤ-ህጉ አንደኛ ፤ ሁለተኛ ፤ ሶስተኛና አራተኛ ብለው የዘረዘሩዋቸውን ምስክሮችና በነሱ መሰረት ፤ በሞት ፍርድ እንድትቀጡ መጠየቃቸውን ሰምተዋል ። ስለዚህ የሚመልሱትና መልሰዎን የሚደግፉበት መከላከያ አለዎ ?"

"የለኝም" አሉ እስረኛው ፤ በፍጹም ጸጥታ ።

"ወይዘሮ እጸገነት አሸብር ፤ ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳን ፤ ግብረ አበርዎ ከተባሉት ካቶ ጥላሁን ፈይሳ ጋር ተባብራችሁ ለመግደላ

@OLDBOOKSPDF

ቹሁ አቃቤ - ሀግ አንደኛ ፣ ሁለተኛ ፣ ሶስተኛና አራተኛ ብለው የዘረዘሩዋቸውን ምስክሮችና በነሱ መሰረት ፣ በሞት ፍርድ እንድትቀጡ መጠዬቃቸውን ሰምተዋል ! ለዚህ የሚመልሱትና መልስዎን የሚደግፉበት መከላከያ አለዎ ?”

“የለኝም” አሉ ቢትዋም ፣ እንደ ወንዱ በፍጹም ጸጥታ ።

“እቶ ጥላሁን ፣ አቃቤ - ሀግ ከዘረዘሩዋቸው ምስክሮች ሁሉ አይነተኛ ፣ አጠቃላይ ምስክር አድርገው የቆጠሩባችሁ ፣ ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳን መግደላችሁን ፣ ራሳችሁ አምናችሁ በሰባት ምስክሮች ፊት ሳትገደዱ ፣ በፈቃዳችሁ መፈረማችሁን ነው ። ለዚህ ሁለት ጥያቄዎች እጠይቃችሁዋለሁ ።

1ኛ. ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ የተባሉትን ሰው መግደላችሁን አምናችሁ በሰባት ምስክሮች ፊት ፣ ሳትገደዱ ፣ በፈቃዳችሁ ፈርማችሁዋል ?

2ኛ. ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳን ፣ እውነተ ግብረ - አበርዎ ከተባሉት ፣ ከወይዘሮ እጸገነት አሸብር ጋር ተባብራችሁ ገድላችሁዋቸዋል ?” አሉ ዳኛው ።

“ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳን መግደላችንን በሰባት ምስክሮች ፊት አምነን ፈርመናል ። ቀኛዝማች ዳኛቸውን ገድለናቸዋል” አሉ እስረኛው ።

“እንዴት ?” አሉ ዳኛው ፣ የመገረም ፊት አሳይተው ።

“ሀ ! አቃቤ - ሀግ እንዳሉት እገዛ ቤታቸው ውስጥ ፣ በገዛ ሽጉጣቸው !”አሉ ፣ እስረኛው ፊታቸው ምሬት የሚታይበት ቢሆንም ፆኼመር ፈገግታ ፈገግ ለማለት እዬሞከሩ ።

“በምን ምክንያት ?”

“ቀኛዝማች ዳኛ ፣ ላገራቸው ፣ ለመንግስታቸው ፣ ለህዝባቸው መልካም ሰሪ መሆናቸውን አይተን . . . አቃቤ - ሀግ እንዳሉት ፣ በሰው መልክ የተሰራን ሰይጣኖች በመሆናችን ፣ መልካም ስራና መልካም ሰሪ ስለማንወድ ። ወዲያውም አገራችንን ፣ መንግስታችንንና ህዝባችንን ለመጉዳት ስንል ገደልናቸው ! አዎ ፣ ሰይጣናች ስለሆን እኒያን ቡሩክ ፣ እኒያን ቅዱስ ሰው ገደልናቸው !” አሉ እስረኛው ፣ ከምሬት ብዛት የተነሳ ፊታቸው ከምትርትር ብሎ ። ሰብሳቢው ዳኛ የስረኛውን ብስጭት ሲያዩ እንደ ማዘን አሉና አንገታቸውን ሲደፉ

@OLDBOOKSPDF

"እቶ ጥላሁን ! ቅማላቸሁ ሊከብድ ፣ ሊቀልል ፣ ወይም ጨርሶ ሊነሳ የሚችለው በምትሰጡት መልስና መልሳችሁን በምትያገፋበት ማስረጃ መሆኑን ማስጠንቀቅ የዚህ ፍርድ ቤት ተግባር ስለሆነ ፣ ብዙ ጭቅምን ትተው ለሚጠይቁት ጥያቄ እያሰቡ ፣ በርጋታ ጊንጊመልሱ እናስጠንቅቅዎታለን" አሉ የቀኙ ዳኛ ።

"ምን እንድል ነው የሚፈልጉ ? የሚፈልጉትን ያንገሩኝና ልበል ልዎ !"

"እኛ የምንፈልገውን ፣ ወይም እስዎ የሚፈልጉትን ይናገሩ እልተ ባለምከ ! ፍርድ ቤቱ የሚፈልገው እውነቱን እንዲናገሩ ነው !" አሉ አሁንም የቀኙ ዳኛ ።

"እውነቱን ተናገርሁኝ ! መቸስ እውነት ማለት ብዙ ሰው ተሰ ማምኑ እውነት ነው የሚሰው አይደል ? ሌላ እውነት የለም ! እሱን ተናገርሁ !"

"ብዙ ሰው ስላላችሁ ነው እንጂ . . . እናንተ ቀኛገሞች ዳኛን መግደላችሁን እያምኑም ማለት ነው ?" አሉ ሰብሳቢው ዳኛ ፣ እጉ ገታቸውን ያፍተው ፣ ገዛም ብለው ቆዩ በሁዋላ ፣ እንደገና ወደ ጥያ ቄያቸው ተመለሰው ።

"የኛ አለማመን ፣ የኛ ንጹሆች ነን ማለት ፣ የኛ ንጹሆች መሆንስ ቢሆን ፣ ሌሎች ሰዎች ከሌመስከሩልን ምን ዋጋ አለው ? እኔና ባለቤቴ 'ነፍሰ - ገዳዮች ናችሁ ' ተብለን ፣ ተይዘን ስንታሰር ፣ ቀኛገሞች ዳኛን እንኩዋንስ እኛ ልንገላቸው ሲገደሉ እዚያ ላስ መኖራችን እስመስክረን ነበር ። ነገር ግን ያስመሰከርናቸው ምስክ ሮችና ያቀረብናቸው ማስረጃዎች ሁሉ አሁን በቦታቸው የሉም ፣ ሁሉም ተለቅመው ጠፍተዋል ! ከዚያ በሁዋላ ነፍሰ - ገዳዮች ባለመ ሆናችን የነበረን ጽኑ እምነት ፣ የነበረን እርግጠኛነት ከራሳችን ሙጥጥ ብሎ ወጥቶ ፣ በዚያ ፈንታ ነፍሰ - ገዳዮች መሆናችንን እስክ ናምን ድረስ ተሰቃዩን ! ከዚያ በሁዋላ ከፖሊሱ እለቃ ፣ ከተራው ፖሊስ ፣ ከዳኛው ፣ ከተላላኪው ፣ ከሰረኛውና በምንኖርበት እስር ቤት አካባቢ ካለው ሁሉ ፣ ጆሮዋችን የሚሰማው እኛ የቀኛገሞች ዳኛ ገዳዮች መሆናችንን ስለሆነ ፣ ነፍስ ገዳዮች መሆናችንን ከመስማ ትና እየተቀጣን ከመማር ብዛት አውቀን አመንን ! ባለቤቴና እኔ "እውነት" ነው ያልነው እውነት መስሎን ፣ "እንለቀቅም" ብለን ብዙ ጊዜ ከተሰቃዩን በሁዋላ ፣ እውነቱ ብዙ ሰዎች እውነት ነው የሚሉት ብቻ መሆኑን ተምረን ስለ ተረዳን እሱን እምነን ለጊዜው ሰላም ፣ እረፍት

@OLDBOOKSPDF

እግሮቹንን ደስ ብሎናል ! ይልቁንም ይህ ጊዜያዊ ሰላምና ጊዜያዊ እረፍት ወደ ዘላለማዊ ሰላምና ዘላለማዊ እረፍት ለመተላለፍ የመጀመሪያው እርምጃችን መሆኑን በማወቃችን ፤ እዚያ በቶሎ የምንደርስበትን ጊዜ በብርቱ ናፍቆት ነው የምንጠባበቀው ። ስለዚህ አሁን ፍርድ ቤቱን የምንለምነው ፤ እኔና ባለቤቴ የቀኛዝማች ዳኘ ገዳዮች መሆናችንን የተቆጠረው ብቻ ሳይሆን ፤ ያልተቆጠረውም ሁሉ ከተቆጠረው የሰማውን እዩትቀበለ አምኖ ፤ አብሮ መስካሪ ስለ ሆነና ፣ እኛም ራሳችን መግደላችንን ተምረን ፤ አውቀን ፤ አምነን በሰባት ምስክሮች ፊት ስለ ፈረምን ፤ እንደገና ምርመራ የሚገባው ነገር ቀርቶ አቃቤ - ህጉ እንደ ጠዬቁት የሞት ፍርድ እንዲፈረድብንና ሁሉም እንዲያልቅ ፤ እንድናርፍ ነው ፤ ጌቶቻችን ! የኛ ሁኔታ አሁን ባለበት እስካለ ድረስ ፤ አሁን ባለበት እንዳለ ሆኖ ፤ ከሞት ሊያድነን የሚችል ምድራዊ ኃይል እንደሌለ እናውቃለን ። ምርመራ ከሚባለው ስቃይ ግን እናንተ ልታድኑን ትችላላችሁ ። ስለዚህ ሞቱ ላይቀር እባካችሁ ስቃይ ማብዛቱ እንዲቀር ፤ ስቃዩ እንዲበቃን ፣ አቃቤ - ህጉ በጠዬቁት መሰረት እንድትጨርሱልን እንለምናለን ! ”

እስረኞቹ በራሳቸውና በሚሸታቸው የሞት ፍርድ እንዲፈረድባቸው ዳኞቹን ሲማጠኑ ፤ በስር ቤት በነበሩበት ጊዜ ከሞት በከፋ ስቃይ ውስጥ እንደ ነበሩ ተመልካቹ ህዝብ ከንግግራቸው ስለ ተረዳ ፤ ባልና ሚስቱ መጀመሪያ ሲገቡ በነበረው የዋላቻ ስሜት ፈንታ ፤ የሚበዛው እንዳዘኑ እዚያ ከሚሰማው “ውይይ ” “አይታና ” የከንፈር መምጠጥ መብዛት ይታወቅ ነበር ።

“ጌቶ ጥላሁን ፤ እሉ ሰብሳቢው ዳኛ ፤ ጫጫታው ዝም እንዲል ጭምር ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ። “አቶ ጥላሁን ! እስቲ ሳይመረሩ ረጋ ብለው ይስሙኝ ። ፍርድ የውነት እንጂ የሙዋችም ፤ የገዳይም ወገን አይደለም ! ፍርድ እውነትን መሰረት አድርጎ የማህበሩን ሰላማዊ ኑሮ የሚያናውጹትን በደለኞች ለመቅጣት እንጂ የተገዳዩን ነፍስ ለማስካስ ፣ ወይም ለመበቀል የሚሰጥ አይደለም ! እንዲሁም መኖር የሰለቻው ፤ ወይም እስዎ እንደሚሉት ፤ ስቃይ ያስመረረው መሞት ፈልጎ ፤ ነፍስ ሳይገድል “ ገድያለሁ ” ቢል ፤ እሱን ለማሳረፍ ወይም መኖር የጣመው ፤ ነፍስ ገድሎ ከሞት ለማምለጥ “አልገደልሁም ” ቢል ፤ ደስታው ባጭር እንዲቀረጥበት እሱን ለማዳን የሚሰጥ አይደለም ! ፍርድ የውነት ወገን ፣ የውነት መሳሪያ ፣ የውነት መብቀያ ስለሆነ ፣ ይህ ፍርድ ቤት ፍርድ ከመስጠቱ በፊት የሚሰጠው

ፍርድ በውነት ላይ የተመሰረተ ፤ እውነትን የሚያገለግል መሆኑን ለማረጋገጥ መጣጣርና ከምስክር በሁዋላ እንኳ ፤ ትንሽ ያልተጣራ ነገር ያለ ከመሰለው ፤ ያ ያልተጣራ ነገር ተለቅሞ ተከልቶ ፤ ንጹሁ እውነት ብቻ እስኪቀር ፤ የተቻለውን ያክል መድከም አይነተኛ ተግባሩ ነው ። እውነትና ትክክለኛነት ለማናቸውም ነገር መሰረት እንዲሆኑ ከፈጣሪ ለፍጥረቱ ሁሉ የተሰጡ ህጎች ናቸው ። በውነትና ትክክል በሆነ መሰረት ላይ ያልተመሰረተ ሁሉ ጸንቶ ሊኖር የማይችል ፤ ወዳቂ መሆኑም እንዲሁ የፍጥረት ህግ ነው ። በውነትና ትክክል በሆነ መሰረት ላይ ያልተመሰረተን ሁሉ በምንም በምን አዩ ጠጋግኑ ፤ እዩዶጋገፉ ማቆዩት ይቻላል ፤ ጸንቶ እንዲኖር ለማድረግ ግን ምንም ቢሆን አይቻልም ። ስለዚህ ማህበራችን ጸንቶ እንዲኖር መሰረት የሆነው እውነት መጠበቅ ስላለበት ፤ ይህ ፍርድ ቤት "ሊገለጹት ያልፈለጉት እውነት ይኖራል" ብሎ ከጠረጠረ ፤ እንዲያ ያለውን ጥርጣሬ የሚያስወግድበት በቂ ምክንያት እስኪያገኝ ድረስ ምርመራው እንዲቀጥል ሊያደርግ ይገደዳል ። የምርመራው ጊዜ ሊያጥር የሚችል ያልተገለጸ እውነት ቢኖር ከማስረጃ ጋር ለፍርድ ቤቱ ሲቀርብ ብቻ ነው ። ስለዚህ አቶ ጥላሁን ፤ ይህ ፍርድ ቤት ያላወቀው ፤ እኅቤ - ህጉ ካቀረቡዋቸው ማስረጃዎች ውስጥም የሌለ ፤ ለፍርድ ቤቱ ፍርድ አሰጣጥ የሚያገለግል ፤ እንዳንድ ነገር መኖሩ ትንሽ ቀደም ብለው ከተናገሩት መሀከል እልፎ እልፎ በለሚታይ ፤ እንዲያ እንዲያ ያለውን ሁሉ እንዲገልጹልን እንጠይቃለን ።"

"ጌታዬ" አለ እሸረኛው ፤ መጀመሪያ ረጋ ብሎው ፤ ሁዋላ ከጥቂታ ጋር ለመናገር ሲጀምሩ ። "ጌታዬ ! እኔ የሸሸግሁት እውነት ልገልጸው ያልፈለግሁት እውነት የለም ። ለመሆኑ ምስክር ልናስመጣ ክርበትና ማስረጃ ልናቀርብበት የማንችል ነገር እውነት ነው ብለን ብንናገር ፤ ዞረን ዞረን ወደ ምስክርና ወደ ማስረጃ መመለሳችን ካልቀረ እንደ ገና ወደ ምርመራ መመለሱ የፍርድ ቤቱን ጊዜ በከንቱ ከማጥፋትና የኛን ስቃይ ከማብዛት በቀር ምን ጥጋ አለው ? እስቲ እንደ ገና ወደ ሁዋላ ተመልሰን ቀኛዝማች ዳኘን አልገደልናቸውም ብለን ፤ ባለ ቤቴና እኔ ምለን ! ተገዝተን ብንናገር ያለበቂ ምስክር ፤ ያለበቂ ማስረጃ ትቀበሉናላችሁ ? አትቀበሉንምኮ ! መቸም ምስክሮቻችንና ማስረጃዎቻችን ሁሉ በጥንቃቄ እዩተለቀሙ እንዲጠፉ መደረጋቸውን ተናግሬያለሁ ። ታዲያ እንዲህ እኛ ሁለታችን ብቻ ቀኛዝማች ዳኘን አልገደልንም ብለን እስር ጊዜ ብንምል ፤ ብንገዘት ምን ያደርጋል ! ጌታዬ ! የሁለት ሰው እውነት [illegible] ሌሎት ፊት አሉት ነውኮ !



@OLDBOOKSPDF

@OLDBOOKSPDF

እውነቱ ጌታዬ ፣ እውነቱ እሱንም ቢሆን ፤ ብዙ ሰው ተስማምቶ የሚናገረው ድምር ነው ፤ ብዙ ሰው ተስማምቶ 'ነው' ካለ ፣ ሰይጣኑ መላክ ፣ ርኩሱ ቅዱስ ይሆናል ። ለዚህ የቀኛዝማች ዳኘ ታሪክ ጥሩ ማስረጃ ነው ። ጌታዬ ! ቀኛዝማች ዳኘ አቃቤ - ህጉ እንዳሉ ባለ ጥሩ ቀለም አስጊጠው ፣ ለሰው ለፍርድ ቤቱ እንዳሳዩት ያሉ ሰው አልነበሩም ። ያ ፣ ስእል ጥራዥ አሳዮውን የሚያመስል ነው ። ብቻ የዘረፉ ግህበርተኞቻቸውና እነሱ ያሳሳቱዋቸው ሰዎች ባንድ ላይ ሆነው መልካቸውን ፣ ስራቸውንና አመላቸውን ለውጠው ሌላ ሊያደርጉዋቸው ስለ ፈለጉ ሌላ ሆኑ ፤ የውነተኛው ቀኛዝማች ዳኘ ግን ፣ በውሸት ቀለም ያልተለወጡት ፣ በጊዜኛ መጽሐፍ ያላጌጡት ፣ ቱባው ቀኛዝማች ዳኘ ፣ ተመዳዳሪ የሌላቸው ጀግና ፣ ህዝብ ከመዘረፍ በቀር አለቀ ዳጆርና ዳኝነት ምን መሆናቸውን የማያውቁ ፣ እጅግ ክፉ ፣ ከክፉ ውሉ የከፋ ሰው ነበሩ ” ብለው ይሆን ያሉበትን ምክንያት ሲዘረዝሩ ሊሉ ።

“ወንጀለኛው ከተጠየቀው ወጥቶ መናገር ስለ ጀመረ እንዲታገድ እጠይቃለሁ ” አሉ አቃቤ - ህጉ አቋርጠው ።

“ተከሳሹም ምንም እንኳ ወንጀል ሰርተዋል ተብለው ቢከሰሱ ፣ በተከሰሱበት ወንጀል በፍርድ ቤት ፊት ተመስክሮባቸውና ሁሉም ተጣርቶ እስኪፈረድባቸው ድረስ እነሱን 'ወንጀለኞች' እያሉ መጥራት ህጋዊ አለመሆኑን ምሁሩ አቃቤ - ህግ ደህና አድርገው የሚያውቁት ከመሆኑም በላይ ፣ ካሁን ቀደም ተከሳሾችን በዚህ ስም እንዳይጠሩዋቸው ማስጠንቀቂያ ሰጥቸዎ ፤ እንደ ገና ህጋዊ ያልሆነ ቃል ሲሉ ደግመው የተሰጠዎን ማስጠንቀቂያ ቸል ስላሉ ፤ አምስት መቶ ብር ተቀጥተዋል ! ” አሉ ሰብሳቢው ዳኛ ፣ አቃቤ - ህጉን በቁጣ አይን እየተመለከቱ ። ከዚያ ወደ እስረኛው ዘወር ብለው ፣ “ይቀጥሉ ” ሲሉ እስረኛው ትንሽ እጅ እንደ መንሳት ብለው ፣ ቀኛዝማች ዳኘ አቃቤ ህጉ እስመሰለው እንዳቀረቡዋቸው አለመሆናቸውን በዝርዝር ለማሳየት ጀመሩ ።

“ቀኛዝማች ዳኘ የወጣትነት ዘመናቸውን ሁሉ ፣ ጠላት ኢትዮጵያን እስኪ ወረረበት ጊዜ ድረስ ፣ በወንበዴነት ሜዳ ውስጥ ኖረው ጠላት ኢትዮጵያን ሲይዝ ፣ አቃቤ - ህጉ እንዳሉት ፣ “ የጀግንነት ወኔያቸውና የጋለ ያገር ፍቅራቸው አነዘዘዋቸው ” ሳይሆን የወንበዴነት አመላቸውን መለወጥ አቅቶዋቸው በዚያው ስለ ቀጠሉ ፣ ወንበዴ በመባል ፈንታ አርበኛ ተብለው በሁዋላ ፣ ጠላት ሲለቅ ሽልማት ፣ የማእረግ

ሰምና አገር ግዛት ያገኙ ሰው ነበሩ ። የቢሮ ተሹመው አስራ ሰምንት አመት ሲገዙ አስረው እያደበደቡ ፤ እያሰቃዩ አገር አስለቅቀው ካሰደዱዋቸው እጅግ ብዙ ሰዎች ሲሉ ፤ አስራ ሰባት ሰላማውያን ሰዎች ገድለው ሬሳቸው የመቀበር ማገረፊያ እንኳ እንዳያገኙ ፤ ሜዳ ተጣሎ አውሬ እንዲበላው ያደረጉ ሰው ነበሩ ። እንዲሁም አርባ ሰምንት ሰዎች አስደብድበው ፤ አካላተ ጎደሎዎች አድርገው ማስቀረታቸውን አገር ያውቃል ። የተሰነከሉት ሰዎችም አሉ ። ቀኛዝማች ዳኘ በሚገዙት አገር የሚኖሩትን ባለብዙ ርስት ባለፀጎች ሁሉ በግድ 'ውሰዱኝ' እያሉ ርስቶችን ወርሰው እድሀነት ላይ ያሰማሏት ባለፀጎች እጅግ ብዙ ነበር ። ስለዚህ ከየቢሮ ሲሞቱ መሬት የሚሸጠውን የግል ርስት ከግዳረጋቸው ሲሳ ፤ በጠቅላላው የየቢሮ ህዝብ እንደ ግል ሰራተኛቸው ፤ በዘብቱ እንደ ሀብታቸው እያዘዙ የሚኖሩ ሰው ነበሩ ። እንኳንስ የተራው ህዝብ በጸጥታ ጠባቂነት በዳኝነት ፤ በምክትል ግዛትነት በሹመትም ልዩ ልዩ ክፍሎች ከበላይ እየተሾሙ የሚላኩትን ፤ የመንግስቱ ሹማምንት የሳቸውን ፈቃድ ብቻ ፈጻሚዎች እንደ ግል ሎሌዎቻቸው የሳቸው ግብረ በላዎች ሆነው ለመኖር ራሳቸውን ካላዋረዱ ፤ እንደ ወር መቆየት አይችሉም ነበር ። ቀኛዝማች ዳኘ ፈቃዳቸውን ብቻ ሆነ ፤ ለሊማናቸውን አቃቤ - ህግ እንዲሉት 'ለህዝብ አገልግሎት' ሳይሆን ለቢሮታቸውና ለዘረፋቸው መሳሪያ አድርገው ሲገዙ የኖሩ ሰው ነበሩ ። በሀብታቸው ፤ በመብታቸውና በሰውነታቸው ብርቱ ጉዳት ደርሶባቸው በቀኛዝማች ዳኘ ለበላይ አቤት ለማለት የደፈሩ ሁሉ ፤ አገራቸውን ተመልሰው ሳያዩ እንደ ተሰደዱ ይቀሩ ነበር ። አልፎ አልፎ ፤ ለስመ መርማሪዎች የተላኩ እንደሆነም ፤ አቤታቸው አይተቀበሉ ፤ በጥሩ መስተንግዶ እያበበሉና ከዘረፋት ብዙ ጉቦ እያከፈሉ ፤ እንዲመለከፉላቸው እንጂ እንዳይመሰክሩባቸው እያደረጉ በለሚመልሱዋቸው ፤ የመርማሪዎች ደርሶ መመለስ እንደ ቆሰለ አውሬ አስፉጥርና ጠባያቸውን አከፍቶ ፤ ህዝቡን በባሰ ጭካኔ ለማሰቃየት ምክንያት ይሰጣቸው ነበር እንጂ ፤ ጉንሽ እንኳ አስታግሰዋቸው አያውቅም ነበር ።

“ቀኛዝማች ዳኘ እንዲህ እያሉ ፤ የግዛታቸውን ሕዝብ ልጠው፤ ግጠው በልተው ያደኸዩ ጨካኝ ፤ ወንበዴ ነበሩ እንጂ አቃቤ-ህግ ካሰሙት አንድ እውነት የሌለበት ወሬ ፤ 'ቀኛዝማች ዳኛቸው ናቸው' ብለው ለፍርድ ቤቱ እንዳሳዩት የሚያስተዳድሩትን ህዝብ ከድህነት ፤ ከደዌና ከድንቁርና ነጻ ለማውጣት አሳባቸውን ፤ ጉልበታቸውን ፤ ጊዜያቸውንና ሀብታቸውን ሳይቆጥቡ ለህዝብ አገልግሎት የሰጡ ፤ ስለጣንን ለህዝብ አገልግሎት ካልሆነ ለራሳቸው ድሎት የማይፈልጉ

@OLDBOOKSPDF

ቅዱስ ሰው አልነበሩም ። ከዚህ ውስጥ የሚያስገርመው ፣ ደግሞ ከሁሉም የሚያስገርመው ጉዳዩ ! ቀኛዝማች ዳኘ በህይወታቸው ሳሉ የሰውን ሀብት ፣ መብት ፣ ንጽሕና ፣ ሚሽት ፣ ህይወት እንኳ ፣ "ማን አስብኝ" በማለት ፣ ያላንዳች ሲጋት ሲቀሙ የኖሩት እንዐ ፣ ደግሞ ከሞቱ በሁዋላ የሰው ታሪክ መቀማታቸው ነው ! አቃቤ ህጉ ካሊስ ዘመን ጋዜጣ ሲያነብቡ ሰማቸውን ያስጠፉችሁ ፣ ጥላሁን ፈይሳና ሰፈራ ሙላት ወገኖቻቸውን ሲማገልገሉ በንበራቸው ጸት ምኞትና ቁራኛነት ፣ ባዶ እጃቸውን ከዚህ ሄደው ፣ ወዳጅ በርካሽ ዋጋ ገዝቶ ከሰጣቸው ጥቂት ጋሻ መሬት በብድር ገንዘብ ማልማት የቻሉትን ያክል አልምተው ፤ የተረፈውን እንደ ገና ብዙ መሬት ካላቸው እዬለመኑ ካገኙት ጋር ጨምረው ለህዝብ አከፋፍለው ፤ ሰራ አጥመሩ ፤ ካለሙት መሬት ባገኙት ገንዘብ እያስተማሩና እያከሙ የየኪን ህዝብ ከድህነት ፣ ከድንቁ ከድማቄ ጨርሰው ነጻ ለማውጣት እጅግ ላይ ያደረሱ ፤ የየኪን መልክ ባጭር ጊዜ እንደሚለውጥ አድርገው የለወጡ ፤ ግሩም የሆኑ ወጣቶች ባለፋ ሚስት ነበሩ ! ቀኛዝማች ዳኘ እኔህን ወጣቶች እንኳዋንስ በገንዘባቸው ሊቀጥሩዋቸውና ሊያበረታቱዋቸው ፤ በመልካም ስራቸው ህዝብ ስለ ወደዳቸው ቀንተው መልካም ስራቸውን እንዲያቆሙና ለህዝብ ያደሉትን መሬት ለሳቸው እንዲያስረክቡ አዝዘዋቸው ። በዚህ አንስማማም ስላሉ ጥላሁንን ያው እንደ ልማዳቸው አቤታቸው አስረው ሲያሰቃዩት ምታቸው ብቻ ገላገለው ! አሁን ጥላሁንና ሰፈራ የት እንደ ደረሱ የሚያውቅ የለም ፤ ጠፉ ! ታሪካቸውን ግን ይሄው እንደ ሰማችሁት ቀኛዝማች ዳኘ ወሰዱት ፤ ቀሙዋቸው ! ይገርማል ፤ ሬሳቸው እንኳ ህያዋኑን መቀማት ይችላል ፤ ግፈኛው ፤ ቀማኛው ፤ ወንጀለኛው ፤ ቀኛዝማች ዳኘ ከዘረፉት ያካፈሉዋቸው ፤ በዘረፉት የገዙዋቸው ሁሉ የሰሩትን ወንጀል ግም እያዩ ያልሰሩትን መልካም ስለ መሰከሩላቸው ፤ በህይወታቸው ሳሉ ! የመንግስት ታማኝ ፤ የህዝብ አገልጋይ እዬተባሉ ግዛታቸውን ወደ ግል ርስትነት ለውጠው በህዝብም ፤ በመንግስትም ሲጫወቱ ኖሩ ! ከሞቱ በሁዋላ ደግሞ ለጦር መሪዎች ፤ ላገሬ ገዥዎችና ለዳኞች ጥሩ አርአያ የሆኑ ሰው እንደ ነበሩ ፤ የዘረፉና የወንጀል ማህበርተኞቻቸው የመሰከሩላቸው ፤ ከዚያም የመንግስቱ አቃቤ - ህግ ተቀብለው እንደ ሰማችሁት ግሩም አድርገው ፤ አሳምረው የተረከቡት ታሪካቸው በማህደራቸው ይቀመጥላቸውና ፤ አንድ ቀን ፤ ታሪክ ጸሐፊ ሲያገኘው እንዲህ ያሉትን ግሩም ሰው ፤ እንዲህ ባለ ግሩም መልክ ከተከታታይ ትውልድ ጋር ያስተዋውቃቸዋል ። ቀኛዝማች ዳኘ በህይወታቸው የዘረፉ-

@OLDBOOKSPDF

ፀሪኮቻቸውንና እነሱ ያሳሳቱዋቸውን ባሰት እያስመሰከሩ ፣ በወንጀል የተበላሸ ስራቸውን በንጹህ ስም ሸፍነው ህዝብ ሲያስጨንቁ እንደ ኖሩ ፣ ከሞቱ በሁዋላ ደግሞ ስራቸው ለመልካም ስራ ፣ እሳቸው ለመ ልካም ሰሪ አርአያ እዮተባሉ በታሪክ ሲገዙ ይኖራሉ ! ነገር ግን እንዴት ? ይህ ሁሉ ለምን ? ሀ ! ያልሆኑትን መሆናቸው ስለ ተመሰከረ ላቸው ! ጥሩውን አሰት እውነት ነው ብሎ ፣ ምስክር ገዝቶ አስፈ ራርቶ ፣ በማስፈራራትም ሆነ በማባበል አልበገር ያለውን አስቃይቶ ማስመስከር ከተቻለ ፣ ያ ጥሩ አሰት ጥሩ እውነት ይሆናል ! ስለዚህ እውነት ጥቂት ሰዎች ተስማምተው ‹ እውነት ነው › የሚሉት ነው እንጂ ሌላ እውነት የለም ፣ ጌታዩ ! እውነት ለመሆኑ መቃወሚያ ምስ ክር ሳያስፈልገው ፣ በውነትነቱ ብቻ እውነት መሆኑ የሚታወቅ ፣ እው ነት የሚባል ነገር ቢኖር ኖሮ እንዴት ጥሩ ነበር ! እንዲያ ያለ እው ነት ቢኖር ኖሮ ፣ ቀኛዝማች ዳኘ እቃቤ ህግ ለፍርድ ቤት እስመስ ለው እንዳሳዩት የነበሩ ሰው መሆን አለመሆናቸውንና ፣ እኛም የሳ ቸው ገዳዮች መሆን አለመሆናችንን እዚህ ፣ በግዜ - ሰጋ ፊጥ እን ዲመሰከር በሄደበት ሁሉ ሄጂ ፣ እውቶ ቢሸሸግ እንኳ ከተሸሸገበት ፈልጌ አመጣው ነበር ። ነገር ግን እንዲህ ያለ እውነት የለም ! ሆኖ እውነት ነው ብሎ የሚያውቀው ፣ ዳኛም እውነትነቱን ተቀብሎ ፍርድ የሚሰጥበት ፣ ጥሩ አሰትም ቢሆን ጥቂት ሰዎች ፣ ወይም ጥቂት ወረ ቀቶች ተስማምተው እውነት ነው ብለው የሚመሰክሩት ነው እንጂ ሌላ እውነት የለም ! ጌታዩ ፣ እኛ ‹ ወንጀለኞች አይደለንም › ብን ልም ፣ ወንጀለኞች ባንሆንም ፣ በበላይ ሬት ተግባርን ያላንደሉ መስሎ ታይቶ ፣ ትጉ መስሎ ታይቶ ፣ ሲሆን ሲሆን የማእርግም ፣ የደመወዝም እድገት ለማግኘት ፣ ያ ፣ ባይሆን ፣ የያዙትን ማእርግና ደመወዝ እንደ ያዙ ለመቆየት ፣ ወንጀለኛን ሜዳ ለሜዳ ፈልጎና ምናልባትም በራስ ላይ አደጋ ሊያደርስ የሚችል ተኩስ ተታኩሶ ከመያዝ ይልቅ ፣ በሰላ ማውያን ላይ ያሰት ምስክሮችን በማባበልም ይሁን በማስፈራራት ገዝቶ ፣ ለመግዛት የማይመቹትን በልዩ ልዩ ስቃይ አሰቃይቶ ማስፈ ራምና ማስመስከር የሚቀልል ሆኖ ያገኙት የቦታው ባለስልጣኖች፣ የሞት ፍርድ የሚገባን ወንጀለኞች ያደረጉን ወንጀለኞች ነን ። ስለዚህ የቀኛዝማች ዳኘ ገዳዮች ለመሆናችን በውድም ፣ በግድም የታሰናዱ ምስ ክሮችና በውድም ፣ በግድም የተፈረሙ ወረቀቶች የመሰከሩብን ፣ ገዳ ዮች ላለመሆናችን እኛ ያስመሰከርናቸው መከላከያ ምስክሮችና የጽ ሁፍ ማስረጃዎች በጥንቃቄ ተለቅመው የጠፉብን ስለሆኑ ፣ እቃቤ ሁጉ እንዳሉት ወንጀለኞች ነንና የቀጣዩቀው ፍርድ እንዲፈጸምብን ፍርድ ቤቱን እንለምናለን ።

@OLDBOOKSPDF

“ ጌቶቼ ! እኛ የሞት ፍርድ የተፈረደብን ሰዎች መሆናችንን ያወቅነው ፡ ለመኖርና ለደስታ የነበረን የወጣትነት ተስፋ ሁሉ ጥሎን የጠፋ ፤ ያስመሰከርናቸው መከላከያ ምስክሮችና የሰጡት ምስክርነት ተቀባይነት አጥተው የተረዳን እለት ነው ። ከዚያ እለት ጀምሮ ሞት ተለይቶን አያውቅም ! ከዚያ እለት ጀምሮ ሞት ባይናችን ፊት ቆሞ እንዳስፈራራን ነው ! ከዚያ እለት ጀምሮ ሞት የህይወት መቁረጫውን ስሎ ፤ ጨካኝ ክንዱን በላያችን ዘርግቶ ዳኛ በል እስኪለው ምልክት እስኪሰጠው እንደ ተጠባበቀ ነው ! ሞት ከመግደሉ ይልቅ ‘ ሊገድላችሁ ነው ’ እያለ ማስፈራራቱ እንዴት የሚያስጨንቅ መሰላችሁ ! በህይወት ከሞት ጋር ከመኖር አንድ ጊዜ ሞቶ ከሞት መለየት እንዴት ያለ እረፍት መሰላችሁ ! ስለዚህ ይህን ፍርድ ቤት የምንለምነው ፡ አቃቤ ህጉ እንደ ጠየቁት የሞት ፍርድ እንዲፈርድብንና አንድ ጊዜ ሞተን ለሁልጊዜ ከሞት እንድንለያይ ነው ! ”

እስረኛው የምሬት ስሜታቸውን በሚገልጽ ፊትና በሚያስደነቁር ከፍተኛ ድምጽ ምኞታቸውን ሲጨርሱ ፤ እዚያ የተሰበሰበው ህዝብ በተማጣኙ ምሬትና ብሶት አማካይነት ፡ በዚያ አፍ እሳቸውና ሚሽታቸው ፤ እንዲሁም ከነሱ በፊትና ከነሱ በሁዋላ የነሱ ክፉ እድል የሚገጥማቸው እስረኞች ሁሉ የሚኖሩበት ስቃይ ቃይቶትና ቶሰም ቶች ስለ ትሰቀቁ ፤ ስለ ተጨንቁ ፤ እንዲያ ያለውን አሰቃቂና አስጨናቂ ስሜት ባንድነት ሲገልጽ ፤ ህምህምታውና ጉምጉምታው ያን ሰፊ አዳራሽ ሞላው ! ሕዝቡ እንዲያ ህምህም ፡ ጉምጉም በማለት ላይ እንዳለ ፤ እንዲያ በማጉረምረም ላይ እንዳለ ፡ የቀኙና የግራ ዳኞች ከዩ ወንበራቸው እየተነሱ በፍጥነት ወደ ሰብሳቢው ዳኛ ፤ ወደ አቶ አንተነህ ሄዱ ። አቶ አንተነህ እንደ ተቀመጡ ሰውነታቸው ሁሉ ገዘላብ አጥልቆዋቸው ስለ ነበረ ፤ በመሀረብ አዩር ሲያራግቡላቸውም ላባቸውን ከግንባራቸው ሲጠራርጉላቸውም ቆይተው ፤ በሩቅ ላለ በግ ይሰማ ፤ ገቅተኛ ድምጽ ትንሽ ተነጋገሩና የቀኙ ዳኛ ጉዳዩ ለሳምንት መቀጠሩን አስታውቀው ፡ በሽተኛውን ለሁለት ደግፈው ወደ መኪናቸው ይዘዋቸው ሄዱ ።

“ ይህን ሰው ምን ነካው እባክህ ? የሚጥል በሽታ አለበት ? ” አሉ አቃቤ - ህጉ ፤ ዳኞች አቶ አንተነህን ደግፈው ሲወጡ ዝም ብለው ሲመለከቱ ከቆዩ በሁዋላ ፤ ህዝቡ ሊሄድ የተነሳው ቆሞ ፤ የተቀመጠው እዚያው እንዳለ ሲንጫጫ ፤ ወደ መጀመሪያው ረዳታቸው ጠጋ ብለው ።

@OLDBOOKSPDF

“የሚገርል በሽታ ባይሆንም . . . በጣም የታመሙ መሆናቸው አያጠራጥርም ። እጅ እግራቸውን መሰብሰብ እንዳቃታቸውና ላባቸው በፊታቸው እንደ ውሀ መውረዱ ከሩቅ እንኳ ይታያል !” አሉ ያቃቢ - ህጉ ረዳት ።

“እንዴ ! ምናልባት እስረኞች ዘመዶቻቸው . . . ይሆኑ ይሆን ? ገና ሲገቡ ሲያዩዋቸው'ኮ . . . ነው በጣም የደነገጡ !” አሉ ሁለተኛው ረዳት ።

“እውነትህ ነው ፤ ከተከሳሾች ጋር አንድ ነገር ይኖራቸዋል ፤ እኔም ተከሳሾች ገና ሲገቡ አይናቸውን በነሱ ላይ ተክለው ፣ እዚያው ፍዝዝ ብለው ሲቀሩ አይቼ . . . ምን ሆኑ ብዬ ገርሞኝ ነበር !” አሉ የመጀመሪያው ረዳት ።

አቃቤ - ወንጀሉ ፣ ሁለቱ ረዳቶቻቸው የሚነጋገሩትን የሚሰሙ አይመስሉም ነበር ። አሳባቸው እዚያ ትቶዋቸው ፣ ሩቅ እንደ ሄደ በሚያሳይ መልክ አይኖቻቸው ሳይረግቡ ፊት-ለፊት እንደ ተተከሉ ግንባራቸውን ቋጥር ፣ ፊታ ሲያደርጉ ቆይተውና ፣ ወረቀታቸውን ከጠረጴዛው ላይ ሰብስበው ፣ በሻንጣቸው አግብተው ተነሱ ።

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፴፮

## 'ወንጀለኛው' ዳኛ

ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳን ገድለዋል ተብለው ባንደኛ የወንጀል ችሎት የቀረቡት ባልና ሚስት ጉዳይ በተቀጠረበት ቀን ፣ የተመልካቹ ህዝብ ብዛት ቤቱን አፍር እስኪያጣ አስጨንቆት ነበር ። ከሰብሳቢው ዳኛ በቀር ፣ ሁለቱ ዳኞች ፣ አቃቤ - ህጉ እስከ ረዳቶቻቸው ወና አስረኞችም ካጀቡዋቸው ፖሊሶች ጋር ገብተው ፣ ሁሉም በር በሩን እያዩ የሰብሳቢውን ዳኛ መምጣት ይጠባበቁ ነበር ። በልማዱ ሰብሳቢው ዳኛ ፣ አቶ አንተነህ ተሰፋዬ ከሌሎች ዳኞች ቀድመው እንጂ ወደ ሁዋላ ቀርተው አያውቁም ነበር ። ስለዚህ የዚያን እለት መዘግየታቸውን በተቀዳሚው ችሎት ተደግፈው መውጣታቸውን ያዩ ሰዎች ፣ ከዚያ ጋር አያይዘው ፣ ፆምመው እንደ ቀሩ አርግጠኞች ሆነው ፣ "ጉዳዩ እንደ ገና ይቀጠር ይሆናል" ብለው ሲያስቡ አቶ አንተነህ ገቡ ።

አቶ አንተነህ ተሰፋዬን ቀድሞ የሚያውቃቸው ፣ ያንለት እዚያ ችሎት ሲገቡ ሲያያቸው ፣ እሳቸው መሆናቸውን ቢጠራጠር አይፈረድበትም ! በዚያ አካባቢ የሚታወቁት አቶ አንተነህ ፣ ከሰው ጉዋደኝነት ይልቅ ለብቻቸው ፣ ከገዛ አሳባቸው ጋር መጫወትን የሚመርጡ ፣ ከባድ ሸክም እንደ ተሸከሙ ትከሻቸውን ለግደድ ፣ አንገታቸውን ደፋ አድርገው ግንባራቸውን ቋጥር ፈታ ፣ ጥቁር ፊክ እያደረጉ አንዳንድ ጊዜም እንደሚናገሩ ከንፈሮቻቸውን እያንቃነቁ የሚሄዱ ስለሆኑ ፣ በዳኝነት ወንበራቸው በተቀመጡ ጊዜ የሚታዩትን ትችትና የሚፈርዱትን ፍርድ የማያውቅ ፣ ደህና አድርጎ የማያውቃቸው አፉን ሞልቶ "እብድ" ለማለት ባይደፍር ፣ ጤነኛ ናቸው ለማለት መድፈሩን እንጃ ! በጆሮዋቸው ተጠግቶ ቅር የሚያሰኝ ወሬ ቢነግራቸው የሚናገር አሾክሾዋኪ እንደማይሰያቸው ሁሉ ፣ ሁልጊዜ ፣ ደስ የሚያሰኝ ነገር አይተው ፣ ወይም ሰምተው ፈገግ ቢሉ እንኳዋ ፈገግታቸው በፊታቸው ገልጸ የሚያሳዩው ያ ያዩት ፣ ወይም የሰሙት ነገር ከሚሰጠው ደስታ ይልቅ በውስጣቸው ያለውን ፣ አብሮዋቸው የሚኖረውን ቅርታ ነበር ። ባመትባል ወይም በግብግ ካልሆን በስራና

@OLDBOOKSPDF

እንዲሁ ባዘቦት ከካኪ በቀር ሌላ አይነት ልብስ ለብሰው አዩሁ ብዬ የሚምል የለም ! ያንለት ግን አቶ አንተነህ ሌላ ነበሩ ። ያንለት ጥቁር ኮትና ሱሪ ከነጭ ሸሚዝ ጋር ለብሰው ፤ ቀይ ክራባት አስረው ፣ ለስራ ከተወሰነው ጊዜ ዘግይቶ መግባት እንደሚያኮራ ሁሉ ፣ ትክሻቸውን እንደ ለመደው ከማስማደዱ ቀና አድርገው ፤ ፊታቸው ደስ ብሎት ፣ ደስ በሚያሰኝ ፈገግታ ኢጊጦ ፣ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ሳያዩ ፊት-ለፊት ብቻ እዩ-ተመለከቱ ፤ በፈጣን እርምጃ ሄደው የመሀከል ወንበራቸውን ይዘው ሲቀመጡ ፣ አቶ አንተነህን ለሚያውቁ ይህ ሁሉ እንግዳ ነገር ሆኖ ታይቶዋቸው አፋቸውን እያዩ እበበላቸው ሲን ሾካሾኩ ፣ ያ ሹክሹክታ አንድ ላይ ሆኖ ፤ ባንድ ተዳምሮ ቤቱን ሞላው ።

'እባክህ ይህ ወሳኝነትሁ ዛሬ እንደ ገና ተሞሽረ ? መሰንበቻውን እንደ ዛሬ አጊጦ አላዩሁትም ” አሉ አቃቤ-ህጉ ፣ ከረዳቶቻቸው ወዳንዱ ጠጋ ብለው ።

“ሚስታቸው ምን ሆነው ? ጥሩ አስተማሪ ሚሽት አሉዋቸውኮ !” አሉና ረዳቱ ባለቤታቸው ሽመጥ ደስ አስመሰኘታቸውን በሚገልጽ ፊት ፣ “ አለባበሳቸውና ጠቅላላ ሁኔታቸው ግን ” ብለው ሊናገሩ ያሰቡትን ሳይጨርሱ ፣

“ተመልካቾች እባካችሁ ዝም እንድትሉ . . . ትለመናላችሁ ” አሉ ሰብሳቢው ዳኛ ፣ የጸጥታ ማስከበሪያ ምልክታቸውን እስምተው ። ከዚያ ዝምታው ፣ ጸጥታው ፍጹም ሲሆን “ ባለፈው ችሎት ” አሉ ቀጠሉና ። “ባለፈው ችሎት አቃቤ-ህጉ ክሳቸውን መስርተው ፣ ለመ በረቱት ክስ “ ማስረጃዎች ይሆናሉ ” ያሉዋቸውን ሁሉ ካቀረቡ በሁ ዋላ ፣ በዚያ መሰረት ፍርድ ቤቱ በተከሳሾቹ ላይ የሞት ፍርድ እንዲ ፈርድባቸው መጠዩቃቸው ይታወሳል ። ተከሳሾቹም ገድላችሁዋል ተብለው የተከሰሱባቸውን ሰው ላለመግደላቸው የቆጠሩዋቸው መከ ላከያ ምስክሮችም ፣ ያቀረቡዋቸው ማስረጃዎችም በጥንቃቄ ተለቅ መው እንዲጠኑ ስለ ተደረገና ፤ ሌላ መከላከያ ስለሌላቸው ፣ አቃቤ-ሀጉ እንዲፈጸምባቸው በጠዩቁት ቅጣት የሚስማሙ መሆናቸውን ገልጸው ፣ ነገሩ እዚህ ላይ ስላደረ ፣ አሁን ፍርድ ቤቱ አቃቤ-ሀጉን የሚጠይቀው ባለፈው ችሎት ባቀረቡት ላይ የሚጨምሩት ፤ ወይም የሚያሻሽሉት እንዳለ እንዲገልጹለት ነው ። ”

“እግዚአብሄር ይስጥልኝ ” አሉ አቃቤ-ህጉ ፣ ትንሽ እጅ እንደ መንሳት ብለው ። “ክቡር ፕሬዝዳንት እግዚአብሄር ይስጥልኝ ! ዛሬ ያኑ ባለፈው ችሎት በኛም ፣ በተከሳሾችም በኩል የቀረበውን

@OLDBOOKSPDF

ጥጥር ለማስታዎስ ያክል ካልሆነ ፣ የምጨምረው ፣ ወይም ከዚያ የማሻሽለው የለም ። ባለፈው ችሎት ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሬሳን ፣ ጥላሁን ፈይሳና እጸገነት አሸብር ለመግደላቸው የተመሰከረበት ፣ የማያጠራጥር ፣ የሰውና የጽሑፍ ማስረጃ ባቃቤ - ህግ በኩል ቀርቦ ፣ ተከሳሾቹ የፈጸሙት ወንጀል ከገደሉዋቸው ሰውና ከቤተሰባቸው አልፎ አገሪንና መንግስትን የጎዳ በመሆኑ እንዲሁም ምህረት ፣ ወይም የቅጣት መቀነሻ የማይገባቸው በመሆናቸው ፣ በመጨረሻው ከፍተኛ ቅጣት ፣ በሞት ፍርድ እንዲቀጡ መጠየቁ ይታወሳል ። ተከሳሾቹ ዓቃቤ - ህጉ በኩል ከቀረቡት ምስክሮችና ማስረጃዎች ፣ እንዲሁም ከተጠየቀው የቅጣት ደረጃ እንደም ሳይቃወሙ ፣ እንዲያውም ሞት የሚገባቸው መሆናቸውን አረጋግጠው አቃቤ - ህጉ በጠየቀው መሰረት ፍርድ ቤቱ ቶሎ ፍርድ እንዲሰጥ ጠይቀዋል ። ስለዚህ አሁን ፍርድ ቤቱን የምጠይቀው ፣ ነገሩ ደህና ሆኖ የተጣራ ፣ የተብራራ ስለሆነ ፣ ተጨማሪ ጥያቄ ሳያስፈልግ ባለፈው ችሎት እንደ ጠየቅሁት ፣ ጥላሁን ፈይሳና እጸገነት አሸብር በሞት ፍርድ እንዲቀጡ ነው ።"

"እሺ ጥላሁን ፣ አቃቤ - ህጉ የጠየቁትን ሰምተሃል ። የሚሰጡት መልስ አለዎ ?" አሉ ሰብሳቢ ዳኛ ።

"የለኝም" አለ ወንዱ ተከሳሽ ፣ በፍጹም ጸጥታ ።

"ወይዘሮ እጸገነት ፣ አቃቤ-ህጉ ለጠየቁት መልስ አለዎ ?" አሉ ዳኛው ፣ ፊታቸውን ከወንዱ ተከሳሽ ወደ ሴቲቱ መልሰው ።

"የለኝም" አለች ሴቲቱም እንደ ወንዱ ፣ ምንም የፍራት ምልክት ሳያሳዩ ።

"እሺ" አሉ ሰብሳቢው ፣ ከጉዋደኞቻቸው ጋር ትንሽ ከተነጋገሩ በሁዋላ አይኖቻቸውን ወደ ጣራው ቀና አድርገው ሲያስቡ ቆይተው ። "አዎ ! እውነት ነው ፣ ተከሳሾች ነፍስ የገደሉ ለመሆናቸው ተመስክሮባቸዋል ፣ እነሱም አምነው የሞት ፍርድ እንዲፈረድባቸው ጠይቀዋል ። ስለዚህ የህጉን ንባብ የተከተልን እንደሆነ ፣ አቃቤ - ህጉ እንዳሉት ነገሩ የተጣራ ይመስላል ። የህጉን ንባብ ተከትሎ መፍረድ ለሚፈልግ ዳኛም የሚሰጠው ፍርድ እጅግ የሚያስቸግር አይመስልም ። ከህጉ ንባብ ወደ መንፈሱና ወደ አላማው አሳባችንን የመራን እንደሆነ ግን ፣ ነገሩ ይህን ያክል የተጣራ ነው ለማለት አያስደፍርም ። እንዲያውም ተከሳሾች ፣ ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሬሳ የሚባሉትን ሰው መግደላቸውን የመሰከሩት ምስክሮችም ሆኑ ማስረጃዎች ፣ እንዲያ ያለውን ምስክርነት የሰጡበትና እነዚሁ ተከሳሾች ገዳዮች

@OLDBOOKSPDF

መሆናቸውን ያመኑበት ሁኔታ ሲመረመር ፣ ብዙ ያልተጣራ ፣ እንደ ገና ስር ገብቶ ማጣራት የሚያስፈልገው ነገር መኖሩን የሚያመለክቱ አንዳንድ ምልክቶች ይታያሉ ።

በመሰረቱ እንኪዋንስ በነፍስ ግዳይ በሌላ ተራ ጉዳይም ቢሆን፣ ከፍርድ በፊት ምስክር እንዲመሰክር አስፈላጊ መሆኑ ፣ በቂ ምስክር ሳይመሰክር ፍርድ መስጠት በሕግ የማይፈቀድ መሆኑ ፣ የሚሰጠው ፍርድ እውነትን የያዘ ፣ በውነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን እስቀድሞ እውነቱ በምስክር ተጣርቶ በፈራጅ ዳኛ እንዲታይ ነው ። ነገር ግን ምስክሩ እውነቱን አጣርቶና አብራርቶ በማሳዩት ፈንታ የሸፈነ ፣ የሸሸገ ፣ ወይም እውነቱን አሰት ፣ አሰቱን እውነት አስመስሎ በማሳዩት የሚያሳስት የሆነ እንደሆነ ፣ እንዲያ ያለው ምስክር ከሀግ መንፈስና አላማ ጋር ፍጹም ተቃራኒ ስለሆነ ፣ ይህን የመሰለ ነገር እንዳ ይደርስ ፣ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግና አንዳንድ የሚያስጠረጥር ምል ክት ቢታይ ፣ እንዲያ ያለው ጥርጣሬ ፈጽሞ እስኪከላ ድረስ ፣ ነገ ሩን በትእግስት መመርመር የማናቸውም ፍርድ ቤት ተግባር ነው ።

እንግዲህ ከዚህ ጠቅላላ መሰረት አሁን ለዚህ ፍርድ ቤት ወደ ቀረበው ጉዳይ መለስ ብለን ስንመለከት ፣ ከተከላካዮቹ አንዱ ፣ አቶ ጥላሁን ፈይሳ ፣ ባለፈው ችሎት ስለ ምስክሮችና ስለ ራሳቸው ነፍስ ገዳይነት ማመን ከተናገሩት አንዳንድ በብርቱ የሚያጠራጥሩና ፣ ዝም ብሎ ለማለፍ ህሊናን የሚከነክኑ ነገሮች እናገኛለን ። ከነዚህም መሀ ከል ለምሳሌ ያክል የሚከተሉትን ብቻ መጥቀስ እወዳለሁ ።

1ኛ- ‘ ቀኛዝማች ዳኘን እንኪዋንስ እኛ ልንገድላቸው ሲገደሉ እዚያ ላለመኖራችን እስመሰክረን ነበር ። ነገር ግን ያስመሰከርናቸው ምስክሮችና ያቀረብናቸው ማስረጃዎች ሁሉ አሁን በቦታቸው የሉም፣ ተለቅመው ጠፍተዋል ።’

2ኛ- ‘ከዚያ በሁዋላ ነፍሰ - ገዳዮች ላለመሆናችን የነበረን ጽኑ እምነት ፣ የነበረን እርግጠኛነት ከራሳችን ሙጥጥ ብሎ ወጥቶ በዚያ ፈንታ ነፍሰ - ገዳዮች መሆናችንን እስከናምን ድረስ ተሰቃዩን !’

3ኛ- ‘ ከዚያ በሁዋላ . . . ነፍሰ - ገዳዮች መሆናችንን ከመስማ ትና ፣ እዩ-ተቀጣን ከመማር ብዛት አውቃን አመንን ! ’

4ኛ- ‘ምስክር ገዝቶ ፣ አስፈራርቶ ፣ በማስፈራራት የማይበገ ረውን አሰቃይቶ ማስመሰከር ከተቻለ ፣ ጥሩው አሰት ጥሩ እውነት ይሆናል !’

5ኛ- ‘የብዙ ሰው አሰት ባንድ ላይ ሲደመር እውነት ይሆናል !’

@OLDBOOKSPDF

እቶ ጥላሁን ከተናገሩት አሁን ከ[1] እስከ[5] ተራ በጠቀስሁዋቸውና በሌሎች ክፍሎች ፤ እነሱም ሆኑ ምስክሮች በንጹህ ህሊና፣ በፍጹም ነጻነትና ሳይገደዱ ያልመሰከሩ መሆናቸውን መላልሰው መናገራቸውን ሰምተናል ። እንግዲህ 'የሚያጠራጥሩ ፤ በቅጥ ያልተጣሩና እንደ ገና ማጣራት የሚያስፈልጋቸው ነገሮች አሉ[2] ያልንበት ምክንያት ፤ ከንድ ወገን ተከሳሾች ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳን የገደሉ ለመሆናቸው ምስክሮች መመስከራቸውና እነሱም ራሳቸው ማመናቸው እርግጥ ሲሆን ፣ ከሌላ ወገን የምስክሮች ምስክርነትና የተከሳሾች እምነት የተገኙት ፤ በግድ እንጂ በውድ አለመሆኑን የሚያመለክት ንግግር ገደም ፤ ወይም ጠየም እያለ ስለ ተነገረና እንዲህ ገደም ጠየም ብሎ የተነገረውም እውነት ሆኖ ቢገኝ ፤ የምስክሮችን ምስክርነትም ሆነ የተከሳሾችን እምነት መለካቸውን ሲሰውጠው ስለሚችልና በጠቅላላው ለነገሩ ሁኔታ . . . ሌላ አቅጣጫ ሲሰጠው ስለሚችል ነው ። ስለዚህ ፍርድ የምንሰጥበት መሰረት ፣ ምስክሩ በፍጹም ነጻነት ፤ ያለነጻች ተጽእኖ የተሰጠ መሆኑን ሳናረጋግጥ ፤ እንዲያውም 'በማንዘብ በማባባል ፣ በማስፈራራትና በማሰቃየት የተሰጠ ነው ' መባሉን እየሰማን ፣ 'ተከሳሾቹ በቀጥታ ተቃውሞዋቸውን ካላቀረቡ በቀመሰከረው የምስክሮች ቃል መሰረት ብቻ እንፈርዳለን ' ብንል ለትማለብን ተግባርና ለህሊናችን ታማኞች ልንሆን ስለማንችል ፣ ኢቃቤ - ህግ እንደ ጠየቁት ፍርድ ወደ መስጠት ማለፉችን ቆይቶ፣ ያልተጣሩ መስለው የሚታዩትን ነገሮች ሁሉ እስኪጣሩና ጥርጣሬያችን ካባቸንን እስኪለቀ ድረስ የማጣሪያ ጥያቄዎች መጠዬቃችንን መቀጠል እንገደዳለን ።”

“ክቡር ፕሬዚደንት ! ተከሳሾቹ በመንግሥት ፖሊሶችና ሌሎች ባለስልጣኖች ላይ ስለ ሰነዘሩት ክስና ወቀሳ ማስረጃ አቅርቡ እንዳይባሉ ፤ በቀጥታና በግልጽ በማቅረብ ፈንታ እርስዎ ራስዎ እንዳሉት ገደም ፣ ጠየም እያደረጉ የተናገሩት አሽሙር ከሀሜትነት አልፎ ወደ ክስ ደረጃ ያልደረሰ ስለሆነ ፣ እንዲህ ያለ በግልጽ ያልቀረበ ክስ ፣ ወይም ሽሙጥ ለማጣራት የፍርድ ቤቱን ጊዜ ማጥፋት እንዳች ውጤት ስለ ማያስገኝ፣ ኢቃቤ -ህግም ፣ ተከሳሾቹም በጠየቁት መሰረት ፍርድ ቤቱ ጥያቄውንም ፣ ክርክሩንም ዘግቶ ወደ ውሳኔ እንዲተላለፍ በትህትና እጠይቃለሁ ” አሉ ኢቃቤ ህግ ።

“ኢቃቤ-ህግም ሆኑ ተከሳሾቹ ፣ ወይም ባንድ ላይ ጥያቄና ክር ክር ተዘግተው ፍርድ እንዲሰጥ ቢጠይቁም ፣ ለፍርድ ቤቱ የሚጣራ ነገር ያለ መስሎ ከታዬው ፣ ማጣራቱን ከመቀጠል የሚከለክለው ነገር

@OLDBOOKSPDF

እንደሌለ አቃቤ - ሕጉ ደህና አድርገው ያውቃሉ ፤ ስለዚህ የማጣሪያ ጥያቄ ይቀጥላል !" አሉና ሰብሳቢው ዳኛ እንደ መቆጣት ብለው ፤

"ወይዘሮ እፀገነት ፤ አንዳንድ ጥያቄዎች እጠይቆዎታለሁና እውነቱን እያሰቡ ይመልሱልኝ" አሉ ፤ ካቃቤ -ሕጉ ወደ ሴቲዋ እስረኛ መለስ ብለው ።

"አቶ ጥላሁን ፈይሳ ምንዎ ናቸው ?" አሉ ከዚያ ቀጠሉና ።

"ባሌ" አሉ ወይዘሮ እጸገነት ፤ ይህን ለመግለጽ ፈቃድ እንደሚጠይቁ ሁሉ አቶ ጥላሁንን ባይናቸው ገረፍ አድርገው ።

"መቼ ተጋባችሁ ?"

"ካሰር አመት በፊት"

"ከተጋባችሁ እስካሁን ፤ አስር አመት ሙሉ አብራችሁ ነው የኖራችሁ ?" አሉ ዳኛው ። ወይዘሮ እጸገነት ለተጠየቁት መልስ መስጠታቸውን ትተው ፤ አቶ ጥላሁንን ይመለከቱ ጀመር ።

"ጌታዬ ! የኛ አስር አመት አብሮ መኖር አለመኖር ለፍርድ ቤቱ ከቀረበው ጉዳይ ጋር ምን ግንኙነት አለው ?" አሉ አቶ ጥላሁን በሴቲዋ ፈንታ ።

"አቶ ጥላሁን ፤ እርስዎን አልጠየቅሁም ፤ ወይዘሮ እጸገነትን ነው ወይዘሮ እጸገነት ይመልሱልኝ" አሉ ዳኛው ፤ እንደ መቆጣት ብለው ።

"ካሰሩ አምስቱን አብረን አልነበርንም"

"ተፋታችሁ ነበር ?"

"አልተፋታንም"

"ታዲያስ ?" አሉ አቶ አንተነህ ። ወይዘሮ እጸገነት አሁንም አቶ ጥላሁንን እያዩ ዝም አሉ ።

"ቀኛዝማች ዳኛ ፤ እኔን በጥይት አስደብድበው ፤ ቀምተው ወስደዋት ነበር ፤ ብቻ ይህ ሁሉ ጥያቄ ምስክር ተመስክሮ አልቆ ፍርድ ለቀረው ነገር ምን ያገለግላል ?" አሉ አቶ ጥላሁን ፤ ብስጭት ብለው ።

"ፖሊስ ፤ አቶ ጥላሁን በሰንሰለት እንዳሉ ይዘው እስከንጠራችሁ እውጭ ቆዩ" አሉና ሰብሳቢው ዳኛ ፤ ፖሊሱ እንደ ታዘዙት ወንዶን እስረኛ ይዘው ከወጡ በሁዋላ ፤ ወደ ሴቲዋ እስረኛ መለስ ብለው ፤

"ወይዘሮ እጸገነት ፤ ለጠየቅሁዎ ይመልሱልኝ ፤ ባትፋቱ አምስት አመት አብራችሁ ያልኖራችሁበትን ምክንያት ጠይቄዎታለሁ" አሉ ።

@OLDBOOKSPDF

"ቅድም ጥላየ ፣ ባለቤቴ እንዳለው ፣ ቀኛዝማች አንድ ቀን ብዙ ወታደር ልከው በግድ ሊያስወስዱኝ ሲሉ ፣ ጥላየ አልሰጥም ብሎ ተኩስ ተነሳና ፣ ከወታደሮች ሶስቱን አቁስሎ በመጨረሻ እሱም ቆስሎ ሲወድቅ በግድ ወሰዱኝ ።"

"ታዲያስ ?"

"ጥላየን ቆስሎ ሲወድቅ አይቸው ስለ ነበረ ፣ ከብዙ ማንገላታትና . . . ድብደባ በሁዋላ ወደ ቀኛዝማች ቤት ሲወስዱኝ ፣ እዚያ ከደረስሁ በሁዋላም እስከ ሶስት ወር ነው መሰለኝ እሕምሮየን አላውቅም ነበር ። በኋ ሆኘ ነፍሴን ሳውቅ ፣ ሞቶ ቢለሉኝ እውነት መሰለኝ እም ስት አመት እያዘንሁና እያለቀስሁ ፣ ጠባቂ በሌለበት ብቻየን ከውጭ ሰው እንዳልገናኝ ተከልክዬ ፣ ከቀኛዝማች ጋር ተቀመጥሁ ።"

"ስለዚህ ቀኛዝማች እስከ ተገደሉበት እለት ድረስ ከሳቸው ጋር ነበሩ ማለት ነው ።"

"እዎ"

"ቀኛዝማች በተገደሉበት ሌሊት ፣ ወዲያው ፖሊሶች ደርሰው የቤቱን ሰው ሁሉ ሲመረምሩ ፣ እርስዎ እዚያ አለመኖርዎና በሁዋላ ካቶ ጥላሁን ጋር አብራችሁ እንዳላችሁ መያዛችሁስ እውነት አይደለም?"

"እውነት ነው ።"

"ቀኛዝማች ዳኘ እስከ ተገደሉበት እለት ድረስ ከሳቸው ጋር አብረው ከነበሩ ፣ በተገደሉበት ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር እዚያው ያልተገኙበት ምክናያት ምንድነው ?"

"ቀደም ብዬ ጥላየን ፍለጋ እዩሮጥሁ በጉዋሮ በር ወጣሁ ።

"አቶ ጥላሁንማ ሞቱ ተብሎ ስለ ተነገረዎ ፣ እምስት አመት ሙሉ እያዘኑና እያለቀሱ መኖርዎን ነግረውን ነበርኮ ! ታዲያ . . . የሞተ ሰው ፍለጋ እንዴት እዩሮጡ ወጡ ? " ሲሉ ሰብሳቢው ፣ ከቅርታ ፈገግታ ጋር ፣ ተመልካቹም ሳቀ ።

"አለመሞቱንኮ ያንለት ሰማሁ ! አለመሞቱንና ሸፍቶ መኖሩን እንዲያውም 'ቀኛዝማችን ባጋጣሚ ባገኝ እገድላለሁ' ብሎ ሌሊት ሌሊት አጥራቸውን ሲዞር ማደሩን ያንለት ስለ ሰማሁ ነው . . . 'እዚያ አገኘው ይሆናል ' ብዬ እዩሮጥሁ የወጣሁ ።"

"ማን ነገርዎ ?"

"አቶ ጥላሁን ፈይሳ ። "

"እንዴት ? አቶ ጥላሁን ፈይሳ ባለቤትዎ አይደሉም ?"

@OLDBOOKSPDF

"አደለም ፤ ምክሽው ነው ። ጥላሁን ፈይሳና ሚስት ሶፊያ ሙላት ፤ የየኪን ህዝብ በነጻ ለማገልገል ሄደው እዚያ የነበሩ ናቸው ። በቀደም አቃቤ ህጉ እንኩዋ ጥላሁንና ሶፊያ ስለ ሰሩት ግሩም ስራ በጋዜጣ ተጽፎ ከነበረው አንድ ክፍል እዚህ በንባብ አሰምቶዋል ።"

"እ. . . ! ሌላ ጥላሁን ፈይሳ ናቸው ! ብቻ . . ትድግኩ ከውጭ ሰው ሳልገናኝ አምስት አመት ከቀኛዝማች ዳኘ ጋር ተቀመጥሁ ብለ ወን ነበር ፤ ቃዲያ . . አቶ ጥላሁን የሚባሉት የውጭ ሰው አደሉም ? እንዴት ተገናኙታችሁ ነገሩዎ ?"

"ያንለት ቀኛዝማች አስረው አቤታቸው አስቀምጠውት ቲፒ ፤ አልጅ እናታቸው ዘንድ ሄደው ሰለ ነበረ ፤ ከሚሽቱም ከሱም ጋር በግብ ግና ባንዳንድ ስራ ምክናያት ሲመጡ እንተዋወቅ ነበርና ፤ ማታ በሰ ውር ሚሽቱ ያመጣችለትን ራት እያጽናናሁ ላበላው ሄጄ . . . ነገረኝ።"

"ለምን አሰሩዋቸው ?"

"የታሰረበትን ምክናያት እንኩዋ በቅጡ አላውቀውም ፤ ብቻ . . . ያን ሰሞን አቶ ጥላሁንና ሚሽቱ ወይዘሮ ሶፊያ ፤ በየኪ የሰሩት ልዩ ልዩ አስደናቂ ስራ የተጻፈበትን ጋዜጣ ካዲስ አበባ የሄደ ሰው ሰጥቶ ዋቸው ፤ አይተው . . . 'የኔ ያገሬ-ግዝ ስም ባይነሳ የሱ ስም ከየኪ አልፎ አዲስ አበባ በጋዜጣ ተጻፈ ' እያሉ በጣም ሲበሳጩ መስን በታቸውን አውቃለሁ ። ስለዚህ . . . ምናልባት የታሰረበት ከዚህ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል ፤ ብቻ ይህ የኔ ግምት ነው ።"

"እሺ ፤ ይሁን ፤ ቃዲያ . . . አቶ ጥላሁን የሚባሉት ሰው የባለቤት ዎን በህይወት መኖር ሲነግሩዎት ምን አሉ ? ምን አደረጉ ?"

"ለጊዜው . . እንደ እብድ አእምሮየን አጣሁ !" አሉ እስረኛዋ ፤ የዚያን እለቱ ሁኔታቸው ትዝ ሲላቸው አሁንም ነቃ እንደ ማለት ብለው።

"ከዚያ" አሉ ቀጥለው ። "ከዚያ ትንሽ ቆይቼ አእምሮየን ስገዛ ቀኛዝማች አቤታቸው ሰው ሲያስሩ ፤ ዘበኞችንም ሆነ ሌሎችን ሰዎች ባለማመናቸው የግር ብረቱን ቁልፍ ሁልጊዜም እኔ ዘንድ ብቻ ስለሚ ያስቀምጡ ፤ ያንለትም ቁልፉን . . መፍቻውን ማለቴ ነው ፤ ይዤ ነበርና ፈትቸው ከጥላዬ ጋር እንዲያገናኘኝ ለመንሁት ።"

"እሺ ፤ ቀጥሉ ።"

"አቶ ጥላሁን ደግ ሰው ነበር ፤ መላክ ነበር !" ሲሉ እስረኛዋ እን ገታቸውን ደፍተው አዪተከዙ ፤ ከተመልካቹ ህዝብ መሀከል ራሳቸው ላይ የጠጉር መሸፈኛ ጣል አድርገው የተቀመጡ ወይዘር በልቅሶ መን

@OLDBOOKSPDF

ሰቅሰቅ ስለ ጀመሩ ፣ ቤቱን የሞላው ህዝብ እንዳለ አይኑን ወደሳቸው አዞረ ፤ ሰብሳቢው ዳኛም ቀና ብለው ሌትዮዋን ካዩ በሁዋላ ፡ ላጭር ጊዜ እንገታቸውን ደፍተው ፡ ዝም ብለው ቆዩና ፣ "እባካችሁ ተመልካቾች ጸጥ በሉ" አሉ ።

"ምነው እባካችሁ ጸጥ በሉ" አሉ የቀኙ ዳኛም ፤ ከሰብሳቢው ቀጥ ለው ። ህዝቡ ወዳለቀሰችው ወይዘሮ አዩት መለከት ሁሉም ከዩትረቢቱ ጋር ቀስ ብሎ የሚነጋገረው ባንድ ላይ ተጠራቅም የፈጠረው ህምህምታ ቤቱን ሞልቶ አያሰማም ነበር ። ትንሽ ቆይቶ ጸጥታ ሲሰፍን ፣

"ወይዘሮ እጸገነት ፡ ይቀጥሉ" አሉ ሰብሳቢው ፡ አንገታቸውን ደፍተው ሲተክዙ ከቆዩ በሁዋላ ፡ አንድ ገና ቀና ብለው ።

"አቶ ጥላሁን ሁኔታየን ሲያይ በጣም አዝኖ ከኔ ጋር ሲያለቅስ ቆየና 'እሺ' አለ ። ከዚያ ፊታቸው ታስሮበት የነበረውን እግር ብረት ከነሰንሰለቱ በጁ ይዞ እንደ ቆመ ፡ ስለምንወጣበት በርና ዘዴ ሰንመካከር ፤ እውጭ ያስቀመጥሁዋትጠባቂ አዩሮጠች መጥታ ቀኛዝማች መምጣታቸውን ስለ ነገረችን ፡ ተደናግጠን አስዋን ቶሎ አሰወጣንና ሁለታችንም ሮጠን አያንዳንዳችን ወደ ውስጥ በሚከፈቱ መዝጊያዎች ጀርባ ከመቆማችን ቀኛዝማች መዝጊያዎችን በርግጫ በርግደው ፤ በግራ እጃቸው ሆዳቸውን ይዘው ፡ በቀኛቸው ሽጉጣቸውን እያወናጨፉ ገቡ ። ቆስለው ነበር ይመስለኛል ፤ ከወገባቸው በታች ልብሳቸው ሁሉ ደም ብቻ ነበር" ብለው ወይዘሮ እጸገነት የቀኛዝማች ዳኘ አሰፈሪ ሁኔታ ስለ ታዩቸው ፡ ሰውነታቸው ሁሉ ሽምቅቅ ሲል አይተው ።

"ይቀጥሉ እይዞዎ ፤ ይቀጥሉ" አሉ ሰብሳቢው ዳኛ ።

"ታዲያ አቶ ጥላሁንን እዚያ ሲያጡ በጣም ተበሳጭተው እንዳንድ ጊዜ እዩሮከሩ ፡ አንዳንድ ጊዜም እሱን እዩሰደቡና አዩረገሙ ፤ 'መሞቴ ሳይቀር ያን መተተኛ ተማሪ ሳልገድል መሞቴ ነው የሚቆጨኝ ፤ ያመተተኛ ተማሪ አመለጠኝ!' ሲሉ አቶ ጥላሁን የያዘው እግር ብረት ምን ሲያደርግ እንደሆን አላውቅም . . . ተንኮጥኮጥ ። ወዲያው በቅጽበት እሱ ወዳለበት አንድ ጊዜ ተኩሰው ሁለተኛ ሊተኩሱ እጃቸውን እንደ ዘረጉ ከተሸሸገበት ሮጦ ሄዶ ሲይዛቸው አዩሁ ፤ ከዚያ ወዲያ የሆነውን . . . አላውቅም ። እነሱ ሲያያዙ እኔ ሮጬ ፡ ከቤት በጉዋሮ በር ወጥቼ የአጥሩን የስርቆሽ በር ቀኛዝማች ሲገቡ ከፍተውት ስላገኘሁ በዚያ ወጣሁና ጥላየን እዩጠራሁ ስሮጥ ፤ እሱም ተኩሱን ሰምቶ ከወዳጆቹ ጋር ወደ ቀኛዝማች ቤት ሲሮጥ በመንገድ ተገናኘን ።"

@OLDBOOKSPDF

"እንግዲህ እርስዎ እንደሚሉት ከሆነ ፡ ቀኛዝማችን የገደሉ ሌላ ጥላሁን ፈይሳ ናቸው እንጂ . . . ገደሉ ተብሎ የተመሰከረባቸው ፡ ባለ ቤትዎና እርስዎ አይደላችሁም ማለት ነው ! "

"መጀመሪያ ቀኛዝማች ከተኮሱ በሁዋላ ፎጦ እስኪደዛቸው-ድረስ የሆነውን ነው እንጂ . . . ከተያያዙ በሁዋላ የሆነውን አላዩሁም ! አል ነበርሁም ። ብቻ . . . ወይ ሲታገሉ የገዛ ሽጉጣቸው ባርቆ ገድሉዋ ቸው ይሆናል ፤ ወይም . . . እንጃ ፡ እሱ ገድሉዋቸው ይሆናል ። ብቻ . . . ይህ መቸም ያላዩሁት ነገር ፡ ግምት ነው ! "

"እሰቲ አንድ ሌላ ነገር ልጠይቅዎ" አሉ ሰብሳቢው ዳኛ ፡ አይ ኖቻቸውን ሳያረግቡ ላጭር ጊዜ ዝም ብለው አስረኛዋን ሲመለከቱ ቆዩና ። "አሁን እንደ ነገሩን . . . እርስዎና የባለቤትዎ ምክሸ ፡ አቶ ጥላሁን ፈይሳ አብራችሁ ሳላችሁ ፡ ቀኛዝማች ዳኘ ደርሰው ተኩሰ ሲከፍቱና ሁለቱ ተያይዘው መታገል ሲጀምሩ ፡ እርስዎ የትግሉን መጨረሻ እንከዋ ሳያዩ ወጥተው ሸሹ ፤ ባለቤትዎ እንዲያውም እዚያ አልነበሩም ። ታዲያ እንዲህ ከሆነ እንዴት ነው . . . ባለቤትዎና እር ስዎ ቀኛዝማች ዳኘን ገድለናል ብላችሁ በሰባት ምስክሮች ፊት በራ ሳችሁ መስክራችሁ የፈረማችሁ ? "

ወይዘሮ አጸገነት ፡ ይህ የመጨረሻው ጥያቄ እስከ ቀረበላቸው ድረስ ከዚያ በፊት እዩተጠዩቁ የሰጡት መልስ ሁሉ ፡ እሳቸውና ባለቢታቸው ነፍሰ - ገዳዮች መሆናቸውን በሰባት ምስክሮች ፊት አምነው ከፈረሙት ጋር የማይስማማ መሆኑን ፡ እንዲያውም የዚያ አፍራሽ መሆኑን አልተ ገነዘቡም ነበር ! ዳኛው እዩጠየቁዋቸው ሲመልሱ ፡ ያ ፡ ጥያቄና መልስ ቀኛዝማች ዳኘ በሞቱበት ማታ የሆነውን ሁሉ መልሶ አምጥቶ ፡ ባንድ ስፈ ስሌዳ ስሎ በፊታቸው ስለ ዘረጋው ፡ ያን እዩተመለከቱ ፡ ሌላውን ሁሉ የሰጡት መልስ ሲያስከትል የሚችለውን ችግር ጭምር ረስተውት ያኑ የሚያውቁትን ፤ እውነቱን ነበር የሚናገሩ ። ነገር ግን ይህ እሳቸው የሚያውቁት እውነት ፤ ይህ የግዜር እውነት ፣ ብዙ ሰዎች እውነት ነው ካሉትና እሳቸውም እዩተቀጡ ከተማሩት እውነት ጋር የማይስማማ መሆኑን ፡ ከዚያም የተማረውን የረሳ ተማሪ የሚደርስበትን ቅጣት ሲገ ነዘቡ ፤ ደንግጠው የሚሆኑትን አጡ ። ወዲያው ስህተታቸውን የሚያ ርሙበት መንገድ ፍለጋ ሲጨነቁ ፡ ጭንቀታቸው ከፊታቸው እዩታዩ ፣ አንድ ጊዜ የያዛቸውን ፖሊስ ፣ አንድ ጊዜ መሬቱን እያለዋወጡ ሲመ ለከቱ ቆዩና ፣

@OLDBOOKSPDF

"የለም" አሉ ። "የለም እንጂ አደለም ! ተሳስቻ ነው ። ቅን ዝማች ዳኛን . . . እኔና ጥላዩ ነን የገደልናቸው ! "

"እንዴት አድርጋችሁ ? አሁን እንደ ተረኩልን ከሆነ . . . ሊሆን አይችልምኮ ! " አሉ ሰብሳቢው ዳኛ ፣ የእስረኛዋን መጨነቅ ሲያዩ በጣም ማዘናቸው ከፊታቸው ጉልህ ሆኖ እየታዩ ።

"እንዴት አድርገን እንደሆን . . . አሁን በቃሌ መናገር አልችልም ፤ ረስቸዋለሁ ። ብቻ . . . እኛ ነን የገደልናቸው ። እንዴት አድርገን እንደ ገደልናቸው በፈረምንበት ላይ ተጽፎዋል ! " አሉ እስረኛዋ ፣ እንደ ደነገጡ መሬት መሬቱን እየተመለከቱ ።

"በፈረማችሁት ላይ ያለው ሁሉ ትክክል አለመሆኑንማ ከተረኩልን ታሪክ ግልጽ ሆኖ ይታያል ! " አሉ ዳኛውም ፣ እንደ መተከዝ ብለው ወደ መሬት እያዩ ።

"የሚያደናግር ጥያቄ ስለ ጠዩቁኝ ነዋ ! የሚያደናግር ጥያቄ ባይጠይቁኝ ከፈረምንበት ጋር የማይስማማ ነገር አልናገርም ነበር ። "

"ወይዘሮ እጸገኑት ፣ አንድ የፈሩት ነገር እንዳለ . . . ካነጋገርዎና ከሁኔታዎ ሁሉ ይታያል ። አይዞዎ አይፍሩ ፤ እዚህኮ እዳኛች ፊት ነዎ እንጂ እሴላ . . ፊት አደሉም ። ስለዚህ ሳይፈሩ ፣ እውነቱን ይናገሩ " አሉ ሰብሳቢው ፣ እንገታቸውን ደፍተው መሬት መሬቱን እያዩ የፉሙትን እስረኛ ለማበረታታት ።

"አሁን እዚህ እዳኛ ፊት ብሆን . . . እዚህ አላደርም ፤ እዚህ አልሰነብትምኮ ጌታዩ ! ስለዚህ እባክዎ ይተዉኝ ፤ የሚያደናግር ጥያቄ እዩጠዩቁኝም . . . ከመናገር ብዛት የተነሳ ፣ በምስክር ፊት ፈርመን ከሰጠነው የማይስማማ ቃል ተናግሬ እንደ ገና ተመልሰን እችግር ላይ እንድንወድቅ አያድርጉን !"

"ወይዘሮ እጸገነት ፣ 'በምስክር ፊት ፈርመን ከሰጠነው የተለዩ ቃል እንዳንሰጥ' እያሉ . . . ይህን ያክል የሚጨነቁት ፣ ያ በምስክር ፊት ፈርማችሁ የሰጣችሁት ቃል ወዴት እንደሚያደርስ አያውቁምን"

"አውቃለሁ ፤ ወደ ሞት ነው" አሉ እስረኛዋ ፣ አይኖቻቸውን ከመሬት ሳይነቅሉ ፣ ለመስማት በሚያስቸግር ዝቅተኛ ድምጽ ።

"ታዲያ . . . ከሞት የከፋ ምን ከፉ ነገር ኖሮ ነው ፣ ከሉ ለመሸሽ ባለቤትዎም ፣ እርስዎም የሞትን ጎዳና የመረጣችሁ ? "

"ጌታዩ ! ሞት . . . ያሳርፋል እንጂ ያን ያክል ፣ እንዲያ አያሰ . . . አያሰቃይምኮ !" ሲሉ እስረኛዋ ፣ ነፍሰ-ገዳይ መሆናቸውን እም

@OLDBOOKSPDF

ነው እስኪፈርሙ የተቀበሉት ሰቃይ ፣ ያዩት ግእር በሙሉ ከፋት ፣ በሙሉ ጭካኔው ስለ ታያቸው ፈርተው እያለቀሱ ፣ እዚያ ከተሰበሰ በው ተመልካች ያዘኑ እዘኑን ፣ የተቆጣ ቁጣውን ሲገልጽ ጫጫታ ውና ሀምሀምታው ባንድ ላይ ተደባልቆ ቤቱን ሞላው ። ያ ጫጫታና ሀምሀምታ ጸጥ ካለ በሁዋላ ፣

"እሺ ይብቃ ፣ ይቱዉት ግዴለም ይበቃል " አሉና ሰባሳቢው አስተኛዋን ለማረጋጋት ፣ "እስረኛው ፣ አቶ ጥላሁን ይግቡ " አሉ ወደ አጋፋሪው መልስ ብለው ። ከዚያ ከጉዋደኞቻቸው ፣ ከዳኞች ጋር ዘለግ ላለ ጊዜ ከፋት በማይሰማ ዝቅተኛ ድምጽ ሲነጋገሩ ከቆዩ በሁዋላ የሰብሳቢ ዳኛ ወንበራቸውን ለቀኝ ዳኛ ለቅቀው ፣ ወደ ጎን ገለል ብለው ቆሙ ። ከዚያ ከፍተኛ ቦታ ዝም ብለው የተሰበሰበውን ህዝብ ዘቅዝቀው እያዩ ፣ ሊያደርጉት በተሰናዱበት ፣ የተሰማቸውን ደስታ ተከትሎ ፊታቸው ትንሽ በትንሽ እየተለወጠ ፣ ፈገግ እያለ ሄዶ ፣ በመጨረሻ ፋና እንዲበራ በውስጡ እንዳበቀመጡበት ፣ የተወለወለ ብርጭቆ ወገግ ብሎ ሲበራ እዚያ አዳራሽ ውስጥ ታምር እንደ ተሰራ ተመልካቹን ሁሉ አስደነገጠው ። ወዲያው ሰብሳቢው ዳኛ ለልባቸው የተሰማው ደስታ እንዲያ ወገኑ ፊታቸውን እያበራ ፣ ከቆሙበት ከፍ ተኛ ቦታ ቀስ እያሉ ወርደው ፣ አቶ ጥላሁንና ወይዘሮ አጸገነት በቆሙ በት እንደ ደረሱ ፣ ከሁለቱ እስረኞች መሀከል ቆሙ ። ከዚያ ፣ የኪን ለቅቀው ወደ አዲስ አበባ ከተመለሱ ካይዋቸው ለይተውት የማያው ቁትን ጥቁር መነጽር ሲያነሱ ፣ ምንም እንኩዋን ፈንጣጣ በፊቱ የተ ወው ብዙ አንጉዝና የራስ ጠጉሩ መዝጎርጎር ፣ ከጢሙ ያለቅጥ መጎ ፈር ጋር ባንድነት ፍጹም ሌላ ሰው ቢያስመስሉት ፣ ወይዘሮ አጸገነት ጥላሁን መሆኑን አወቁ ። ነገር ግን መልኩ እንዲያ ከመለወጡ ሌላ ፣ ከተያዩ ጀምሮ በዚያ አጭር ጊዜ ውስጥ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሰብ ሳቢ ዳኛ መሆኑ ትንሽ ጥርጣሬ ስላሳደረባቸው ፣ በሙሉ እምነት ሲሙን መጥራት ፈርተው እያመነቱ ፣

"እንዴት ! አቶ . . . ጥ . . . ጥላሁን ?" አሉ ፣ ያ ያላረጋገጡት ስም ካመለጣቸው በሁዋላ መመለስ ይችሉ ይመስል ፣ ቶሎ ብለው አፋቸውን ባልታሰረው እጃቸው ይዘው ።

"ምን ? ዋከሽ ጥላሁን ? እዚህ ?" አሉ እስረኛው ጥላሁንም ፣ እንደ ሚስታቸው አፋቸውን ይዘው ።

"አዎ ፤ ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳን የገደልሁት ጥላሁን ፈይሳ ነኝ !" ሲል "አቶ አንተነህ ተሰፋዬ " የነበረው ጥላሁን ፈይሳ ፣ በፍ

@OLDBOOKSPDF

ፍርድ ቤቱ ውስጥ የተንሳው ፈብኛና ጫጫታ ፣ "ይህን ይመስላል" ሊባል፡ ምሳሌ ሊገኝለት የማይችል ሆነ ! "አቃቤ - ወንጀል" የሚባል ቅጽል የተሰጣቸው አቃቤ-ህግም ፣ እጁ እንደ ወይቀበት አስማተኛ አፋቸውንና አይኖቻቸውን በሰፊው ከፍተው ፣ ፍዝዝ ፣ ድንገዝ ብለው በተቀመጡበት ደርቀው ቀሩ ። ባጻፊኛ ጸጥታ እስኪገኝ የወሰደው ጊዜ አያሌ ነበር ። ከዚያ አያሌ ጊዜ በሁዋላ ፣ ዳኞች ጠረጴዛ እዬመቱ ፖሊሶች እያጨበጨቡ ረብሻውና ጫጫታው እዬተቀነሰ ፣ እዬተቀነሰ ሄዶ መጨረሻ ተመልካቹ ጸጥ እንዲል ካደረጉ በሁዋላ ፣

"ጌቶቼ" አለ ፣ ሰብሳቢ ዳኛ የነበረው ጥላሁን ፈይሳ ። "ጌቶቼ ! ከሁሉ አስቀድሜ የስነ - ስራት ጉዳይ ማንሳት እፈልጋለሁ ። የስነ-ስራት ጉዳይ ማጣራት እፈልጋለሁ ። በልማዱ ፣ በፍርድ ቤቱ ስነ-ስራት ሶስት ዳኞች ሞልተው ባልተገኙበት ችሎት አይሰዬምም ። ሶስቱ ዳኞች ሞልተው በተገኙበት አንድ ጊዜ ችሎቱ ከተሰዬመ በሁዋላ አንድ ዳኛ ቢጎድል ግን ፣ ሁለቱ ዳኞች ለማከራከርና የመጨረሻ ፍርድ ለመስጠት ባይችሉ እንኳ ፣ እኔ እስከማውቀው ድረስ ፣ ቃል ለመቀበልና ቀጠሮ ለማድረግ የሚከለክላቸው የህግ አንቀጽ ያለ አይመስለኝም ። ስለዚህ አሁን እኔ ፍርድ ቤቱን የምለምነው ፣ እዚህ ችሎት ለቀረበው የወንጀል ክስ ገዳዩ እኔ መሆኔን አምኜ እጄን ስሰጥ ከጀ ጋር ተናገዝማች ዳኞቸው ፍሬሳን ለምን እንደ ገደልሁዋቸው የም ሰጠውን ቃል ጥምር እንዲቀበለኝ ነው ።"

ሁለቱ ዳኞች የጥላሁንን ጥያቄ ከሰሙ በሁዋላ ፣ ከፍት በማይ ሰማ ዝቅተኛ ድምጽ እሰበሳቸው ሲከራከሩ ቆዩተው በጥያቄው ሙስ ማማታቸውን በሰብሳቢው ዳኛ ወንበር የተቀመጡት ራሳቸውን ወደ ላይ በመግፋት ገለጹ ።

በሌላ ጊዜ ቢሆን ኖሮ አቃቤ - ወንጀሉ እንኩዋንስ እንዲህ ያለ አከራካሪ የስነ - ስራት ጉዳይ አጋጥሞ "እምህበ - አልቦ" ችግር ፈጥረው ዳኞችንም ፣ ባለጉዳዮችንም ማስቸገር ደስ ባላቸው ነበር ። ያን ለት ግን እዚያ ድንገት ፣ እንደ ሰማይ ቁጣ የበረቀው ገና እንዳፈዘዛቸው ስለ ነበሩ ፣ ገና አእምሮዋቸውን በሙሉ ስላልገዙ የመቃወምም ሆነ ያለ መቃወም ምልክት አላሳዩም ፤ እንዲያው ዝም አሉ ።

ከዚያ ጥላሁን ዳኞችን ለማመስገን ትንሽ እንደ መስገድ አለና ንግግሩን የሚጀምርበት እጣራው ላይ እንደ ተጻፈ ሁሉ ፣ ትንሽ ዝም ብሎ ጣራ ጣራውን ሲመለከት ቆይቶ ፣

@OLDBOOKSPDF

"አዎ" አለ ። "አዎ ፣ ያ ወይዘሮ አጸገነት የባለቤቴ ቀክሽ ያሉት ጥላሁን ፈይሳ ፣ ያ 'ከቀኛዝማች ዳኛቸው ጋር ሲታገል ትቸው ከቤት እዬሮጥሁ ወጣሁ' ያሉት ጥላሁን ፈይሳ ፣ ያ ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳን የገደላቸው ጥላሁን ፈይሳ እኔ ነኝ ። ገድለዋል ተብለው ተያዘው የተሰቃዩትና በመሰቃየታቸው ብዛት 'ገድለናል' ያሉት ጥላሁን ፈይሳና አጸገነት አሸብር አልገደሉዋቸውም ! ይህ ነው እውነቱ ጌቶቼ ! ይህ ነው የግዜር እውነት !" አለና የደስታው ፈገግታ ከፊቱ እየሸሸ ፣ በቦታው ትርታ ሲተካ እዬታዬ ፤

"ወዳጆቼ" አለ አንድ ገና ወደ አበረኞቹ መለስ ብሎ ። "ወዳጆቼ አቶ ጥላሁን ፣ ወይዘሮ አጸገነት ፣ ቀኛዝማች ዳኛ በሰሩባችሁ የግፍ ግፍና በፈጸሙባችሁ ወንጀል ምክናያት አምስት አመት ተለያ ያታችሁታ ለዬብቻ የተቀበላችሁት ስቃይ ሳያንስ ፣ ደግሞ እንደ ገና እኔ በገደልሁ ፣ በለእኔ እናንተ ንጹሆች ፣ በሰም ቀክሽ ብቻ ተይዛ ችሁ ሁለት አመት በመሰቃየታችሁ የተሰማኝ አዘን ምን ያክል መሆኑን የምገልጽበት ቃል አላገኝም ። የደበሩችሁባት ስቃይ ሰው የማይ ችለው መሆኑ ፣ እዚያ ከመቆዬት ቶሎ የሞት ፍርድ ተፈርዶባችሁ እንድትሞቱ በመለመናችሁ ፣ እዚያ በህይወት ከመቆዬት ሞት በመ ምረጣችሁ ሲገመት ይችላል ! ወዳጆቼ ፣ ምንም እንኳ ቀኛዝማች ዳኛን ገድዬ ላመልጥ ፣ በኔ ፈንታ እናንተ ተይዛችሁ ይህን ያክል ስቃይ ትቀበላላችሁ ብዬ ባልጠረጥር ፣ ይዘ ሞትን የሚያስመርጥ በደል የደረሰባችሁ በኔ ምክናያት ፣ እኔ ባገደልሁዋቸው ሰው ምክናያት ስለ ሆነ ፣ የተሸከማችሁትን ከባድ ሸክም ፣ ከባድ ቀንበር ከትከሻችሁ አውርጄ ፣ እኔ ተሸክሜ ፣ እናንተን ከማሳረፍና የማይቀር ከሆነም ህይ ወታችሁን በሞቴ ገዝቼ ትናንተን ከማዳን በቀር ፣ ለተበደላችሁት በደል በቂ ካሳ ይሆናል ፣ ለኔ ህሊና ለጊዜውም ቢሆን ሰላም ይሰጣል የምለው ፣ ሌላ ነገር ፈልጌ አላገኘሁም ። ስለዚህ ወዳጆቼ ፣ አቶ ጥላ ሁንና ወይዘሮ አጸገነት ፣ እኔ ሳላውቅ ፣ በኔ ምክናያት እስካሁን ለደረ ሰባችሁ ብርቱ በደል ይቅርታ እንድታደርጉልኝ እዬለምንሁ ፣ ከዚህ ጀምሮ ወደ ፊት ፣ በዚህ ጉዳይ የሚፈረደውን ፍርድ በናንተ እግር ተተክቼ ለመቀበል የተረብሁ መሆኔን እንሆ ለፍርድ ቤቱ አስታው ቃለሁ ። አሁን ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳን ገድዬ ስለ ሸሸሁበት ምክ ናያት ቃሌን እንድሰጥ ፍርድ ቤቱ ስለ ፈቀደልኝ እያመሰገንሁ የተቻ ለኝን ያክል አሳጥሬ የምሰጠው ቃል የሚከተለው ነው ።

"ቀኛዝማች ዳኛ" አለ የቀድሞው ሰብሳቢ ዳኛ ። "ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ ክፉ ነበሩ ። ቀኛዝማች ዳኛ ክፉ በመሆናቸው እሳቸው መልካም መስራት ስለማይችሉ ፣ መልካም የሚሰሩትን ሰዎች ብቻ

@OLDBOOKSPDF

ሳይሆን መልካም ተሰርቶላቸው በዚያ የሚጠቀሙትንና ደስ የሚሉቸውን እንኳዋ ሲያዩ፤ አይናቸው በቅናትና በጥልቅ ጥላቻ ደም የሚለብስ፤ የተሰራው መልካም ስራ ጠፍቶ ሰሪዎችና የተሰራላቸው ባንድ ላይ ሲያዝኑ ካላዩ ደስ የማይላቸው፤ ክፉ ፍጥረት ነበሩ። ከባለቤቴና ከኔ በፊት፤ ከምላ ጎደል በብዙዎቹ እንደ ደረሰ፤ በኛም የደረሰው ይህ ነበር፤ ጌቶቼ! ባለቤቴና እኔ ባገር ውስጥ ሊገኝ የሚችለውን ሀብትና የህዝብ ጉልበት አስተባብረን፤ ሶስት አመት ሙሉ ለህዝብ ኑሮ መሻሻል ቀን ከሌት የሰራነውንና በዚያ ምስክርነት ለበሰጠ መሻሻል የነበረንንም፤ ለህዝብ የሰጠነውንም ተስፋ ቀኛዝማች ዳኘ ሲያፈርሱብን፤ ሲደመስሱብን፤ ውሸት አድርገው ሲያስቀሩብን ታግቀው ተነሱ። ታዲያ . . እንዲህ ያለውን ክፉ ነገር የሚችል አለ? የሰራው መልካም ስራና በዚያ ላይ የመሰረተው ተስፋ ሲፈርስ፤ እዩ ተናደ ሲወድቅ፤ ዝም ብሎ ቆሞ የሚመለከት አለ? ለዚያ ምስክር መሆን ስቃይ አይደለም? ማአር አደለም? በውነት የሰሩት መልካም ስራና በሱ ላይ የመሰረቱት ተስፋ ሲፈርስ ማየት፤ የወለዱት ልጅ፤ "መጠሪያ፤ መታሰቢያ፤ ይሆነኛል" ያሉት ልጅ ሲሞት ቆሞ ከማየት ምንም ልዩነት የለው! ሴት ከቀን አምጦ፤ ተጨንቆ የፈጠረውን፤ የወለደውን መልካም አሳብና የሰራውን መልካም ስራ ያለምክንያት፤ በክፋት ብቻ ተነስቶ የሚያፈርስበትን፤ የሚያወድምበትን ዝም ብሎ የሚመለከት፤ እንዲያ ላለው ክፉ ይቅርታ የሚያደርግ ሰው አለ? እንዲያ ያለ ሰው ቢኖር ወራዳ ፈሪ፤ ያለዚያም የሰውነት ስሜት የሌለው፤ በልብ ፈንታ በደረቱ ደንጊያ ያቀፈ ቀዝቃዛ ምስል ነው! ነገር ግን እኔን ጌቶቼ፤ እኔን እግዚአብሄር ፈሪም፤ ቀዝቃዛ ምስልም አድርጎ ስላልፈጠረኝ፤ የወለድሁትን መልካም አሳብና የሰራሁትን መልካም ስራ፤ ለየኪ ህዝብ ከሰጠው ደስታና ተስፋ ጋር፤ ባንድ ላይ ቀኛዝማች ዳኘ ያለ ምክንያት፤ በክፋት ብቻ ሲያፈርሱብኝ፤ ሲገድሉብኝ ዝም ብዬ ላያቸው፤ ይቅር ልላቸው አልቻልሁም። ስለዚህ ገደልሁዋቸው! እንደ ቀኛዝማች ዳኘ ያሉትን የመሻሻል፤ የእውቀትና የእድገት መቅሰፍቶች ማጥፋት፤ እንደነሱ ያሉትን የመልካም ስራና የመልካም ስሪ ተጻራሪዎች ማጥፋት ወንጀል ነው? በተፈጥሮ ህግና በቅን ህሊና ፍርድ ወንጀል አደለም! ክፉና በጎ አብረው ሊኖሩ የማይችሉ ተጻራሪዎች ስለሆኑ፤ ክፉ በጎን አንቆ፤ አስጨንቆ እንዳያጠፋው ከተፈለገ፤ በጎ እዩፋፋና እዩተስፋፋ እንዲኖር ከተፈለገ፤ ክፉን ከስሩ ነቅሎ ማጥፋት የተፈጥሮ ህግ የሚፈቅደውና ቅን ህሊና ሁሉ የሚፈርደው ነው! ክፉ ሰሪን፤ ወንጀል ሰሪን፤ በሰራው ክፉ ስራ ለመቅጣትና ወደፊት ክፉ እንዳይሰራ ለማ

@OLDBOOKSPDF

ታት ፣ ማጥፋት የተፈጥሮ ህግ የሚፈቅደውና ቅን ህሊና ሁሉ የሚፈርደው ነው !

“ሰው–ሰራሽ ህግ ግን ፣ በመጀመሪያ ደረጃ ፣ የሰረዎችን ጥቅም ለመጠበቅና የስልጣናቸውን እድሜ ለማስረዘም የታቀደ ፣ አድሏዊ ከመሆኑ ሌላ ፣ በሁለተኛ ደረጃ አላማው ማህበሩን ከወንጀል መቅሰፍት ማዳንና ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ መሆኑን ንባቡ በግልጽ በሚናገርበት ጊዜ እንኳ ፣ ያን የተሰራበትን አላማ ፣ መሰረቱን እስኪለቅ ድረስ ‘አንድም’ እዩተባለ ፣ ተጣምሞ እዩተተረጎመ ፣ እንዲያ ባለ ፣ የተጣመመ ትርጉም ላይ የተመሰረቱ የፍርድና ያስተዳደር ስነ–ስራቶች ወንጀለኞችንና ወንጀልን በማጥፋት ፈንታ ለነሱ አገልጋይና መሳሪያ ፣ ለነሱ ጋሻና መከታ እድርገውት እንደሚኖሩ ያይን ምስክሮች ሆነን ቆይተናል ። ተጨማሪ ማስረጃ ቢያስፈልግ አሁን በፍርድ ቤቱ ፊት ከቀረበው ጉዳይ የተሻለ አይገኝም ፤ ይህ ግሩም የሆነ ማስረጃ ነው !

ስለዚህ ክቡራን ጌቶቼ ! የመልካም ስራና የመልካም ስራ መቅሰፍት የሆኑትን ፣ ቀኛዝማች ዳኘን ፣ በሀብታቸውና በስልጣናቸው እጥር እንደማይገኙ ሆነው ፣ ከፍርድ ተሸሽገው ፣ አገር እዩዘረፉና የሰው ነፍስ ያለምንም ስጋት እያጠፉ አስራ ስምንት አመት ሙሉ የኖሩትን ወንበዴ ፣ ቀኛዝማች ዳኘን መግደል ፣ ወንጀል ሰሪንና የወንጀል ስራን ማጥፋት እንጂ ፣ ወንጀል መስራት ባለመሆኑ ፣ የተፈጥሮ ህግ የሚፈቅደውና ቅን ህሊና የሚፈርደው ስለሆነ ፣ ግድያቸው ከዚያ እድልምና ጉድለት ከሞላበት ፣ ሰው ሰራሽ ህግና ከስነ–ስራቱ ለማምለጥ ሸሽቼ ፣ ለሚንም ፣ መልኪንም ለውጨ ተሸሽጌ ነበር ። ነገር ግን ወንጀል ሳልሰራ በወንጀለኛ ስም ፣ እንደ ወንጀለኛ እንዳልጥቃ ሸሽሁ እንጂ ፣ ወንጀለኛን ከመቃወም በቀር ወንጀለኛ አለመሆኔን እያወቅሁ አድላዊ ህግ ፣ እውር ህግ ንጹህነቴን ማየት ስለማይችል ብቻ ወንጀለኛ አድርጎ እንዳያስገድለኝ ተሸሸግሁ እንጂ ፣ ቅን ህሊና ሁሉ ‘ትክክለኛ ነው’ ብሎ ከሚቀበለው ህግና ወንጀል ነው ብሎ ከሚፈርደው ፍርድ ለማምለጥ ሸሽቼ አልተሸሸግሁም ፤ ደግሞ ምንጊዜም ቢሆን ሸሽቼ አልሸሸግም !

“ክቡራን ጌቶቼ ! ፍርድ እንዳያገኛቸው ስልጣናቸውንና ሀብታቸውን መሸገው ፣ እዚያ ውስጥ ተሸሽገው ፣ ወንጀል ሲሰሩ የኖሩትን ቀኛዝማች ዳኘን መግደል ወንጀል ነው ብዬ አላምንም ። ያልገደሉ ሰዎች በገዳዩ ፣ በኔ ፈንታ ተይዘው ሲገደሉ ዝም ብሎ ማየት ግን ፣ ከፉ ወንጀል ፣ ከወንጀሎች ሁሉ የከፋ ወንጀል መሆኑን አምናለሁ ! ስለዚህ ፣ ጌቶቼ ! ስለዚህ በውሸት ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍራሳን ገድለ

@OLDBOOKSPDF

ዋል ተብሰው እዚህ ኾሎት በቀረቡት ፣ በጥላሁን ፊይሳና በእጸገንት አሸብር ቀንበር አንገቴን አግብቼ ፣ በነሱ የሚፈረደውን ለመቀበል ተሰናድቼ ቀርቤያለሁ ” ብሎ ሲጨርስ ፣ በፍጹም ጸጥታ አፉንም ፣ አይኑንም በሰፊው እዩከፈተ ሲያዳምጥ የቆየው ተመልካች ሁሉ ፣ ሀሊናው ብቻ ስላስገደደው ከዳኝነት ወንበሩ ወርዶ በወንጀለኞች ቀንበር የገባውን ፣ የውነተኛ ሰማእት ሲያደንቅና ሲገረም የተነሳው ጫጫታና ድብልቅልቅ ጸጥ እስኪል ብዙ ጊዜ ወሰደ ። ጫጫታውና ድብልቅልቁ ትንሽ በትንሽ እያለ ጸጥ ሲል ፣

“ ታዲያ እውነቱ ይህ . . . የተናገርኸው ብቻ ነው ? ” አለ አንድ የሴት ድምጽ ፣ ከተመልካቹ ህዝብ መሀከል ። ከዚያ የተመልካቹ ህዝብ ሀምሀምታ ፣ ጫጫታው ፣ ድብልቅልቁ እንደ ገና ጀመረ ። የጥንቱ ሰብሳቢ ዳኛ ጥላሁንም ባዘን መልክ ድምጹ ወደ መጣበት አንገቱን ቀና አድርጎ ሲመለከት ቆይቶ ፣ መልስ ሳይሰጥ እንደ ገና አንገቱን ደፋ ።

“ተናገር እንጂ ! እውነቱ ሁሉ ካልተነገረ ፣ ከውነት ከተቀነሰለት እውነት መሆኑ ይቀራልኮ ! እውነቱን ጨርሰህ ተናገር ፤ ያለዚያ እኔ እናገራለሁ ! ወዲያውስ . . . ከዚያ ሁሉ ክርክር በሁዋላ ተስማምተን አልነበረም የመጣነው ? እንደገና ማፈግፈግህ ነው ? ” ስትል የድምጹ ባለቤት የሆነችው ሴት ፣ ጥላሁን አሁንም እንዳዘነ ቀና ብሎ ሴትዮዋን ተመልክቶ እንደገና አንገቱን ደፍቶ ዝም አለ ።

“ አትናገርም ? ” አለች ሴትዮዋ ፣ ሲቃ ይዞዋት ተነስታ ቆማ እዩጮኸች ። “ተናገር እንጂ ! ቀኛዝማች ዳኘን ብቻህን ነው የገደልሀቸው ? ያንተን ተናግረህ የኔን አለመናገርህ ምን አስበህ ነው ? እዚህ ጥለኸኝ ብቻህን ለመሞት አስበህ ነው ? አሳብህ ይህ እንደሆነ ተሳስተሀል ! የኔ እዚህ . . . ብቻዬን መቅረት የማይሆን ነገር ነው ! ” አለችና የውሸት ጠጉርዋን ባንድ እጅዋ ፣ እንባዋ የፊትዋን ቀለም ሲያጥብ የጠረገችበትን ያደፈ መሀረብ በሌላ እጅዋ እንደ ያዘች ፣ ሰብሳቢ ዳኛ ወደ ነበረው አቶ ጥላሁን ሄዳ ፣ “እንግዲህ አንተ አልናገር ካልህ እኔ እናገራለሁ ።” “እኔ” አለች ወደ ዳኞች ቀና ብላ ። “ እኔ ሶፊያ ሙላት የጥላሁን ሚስት ነኝ ። ቀኛዝማች ዳኘን ሁለታችን ነን የገደልናቸው ። መጀመሪያ እኔ አቆስልሁዋቸው ፤ ሁዋላ እሱ ጨረሳቸው ! እሱን እቤታቸው አስረው አስቀምጠው ፣ ማታ እኔ ዘንድ መጥተው ሲደፍሩኝ ስለ ፈለጉ ፣ በሽጉጥ አቁስያቸው ሲወድቁ ተሸሸግሁ ። ከዚያ ተነስተው ፈልገው ስላጡኝ ፣ በደም ሰካር እሱን ሊገድሉ አስረው ወዳስቀመጡበት ሄደው . . . እዚያ እሱ ጨረሳቸው ፤ ገደላቸው ፤ ይህ ነው ሙሉው

@OLDBOOKSPDF

እውነት ፤ እሱ ያለው ሙሉ እደሰም ፤ ግማሹ ነው ! ይህ እውነት እደለ እንደሆነ . . . እስቲ አሁን ጠይቁት ! ገና ከውጭ እሱና ወይዘሮ እጸገነት ወደ ነበሩበት ሲገቡ ቆሰለው ፤ ከወገባቸው በታች ልብሳቸው ሁሉ በደም ተነክሮ ፤ የቆሰለ ሆዳቸውን ባንድ እጃቸው እፍነው ይዘው መግባታቸውን ቅድም ወይዘሮ እጸገነት አልተናገሩም ? ተናግረዋልኮ ! ” አለች ሶፊያ ፤ የጦች ፊንታዋን ፤ ጥትዋን ባልዋ ደርቦ የሚወስድባት ፤ የሚቀማት መስሎዋት በፍራትና በቁጣ እዩተንቀጠቀጠች ። ከዚያ ወደ ወይዘሮ እጸገነትና ወደ ባላቸው ዘወር አለችና ፤

“ወይዘሮ እጸገነት ለምን ዝም ይላሉ ? እባክዎ ይናገሩ ፤ ዝም አይበሉ ፤ ይመስክሩ ፤ እኔን እዚህ ብቻየን ትቶኝ ሲሄድ ሲሞክር አያዩትም ? ብቻየን ጥሎኝ ሊ . . . ሊሞት ይፈልጋልኮ ! ” ስትል ረብሻው ፤ ድብ ልቅልቁ እንደ ገና ተነሳ ። እዚህ መሀከል አንዳንድ ሴቶች የሶፊያን ሁኔታ ሲያዩና ንግግርዋን ሲሰሙ ለትሶዋቸውን መግታት አቃታቸው ። ወይዘሮ እጸገነትና ባላቸው እቶ ጥላሁን ፤ ከዚያ ቀጥሎ የነሱ እድል ምን እንደሚሆን ማሰቡን ትተው ፤ ሶፊያና ባልዋ እዚያ ሲያደርጉት የሚያዩት ሁሉ እውነት ይሁን ሕልም መለዩት እቅቶዋቸው እንዲሁ ፍዝዝ ፤ ድንዝዝ ብለው ይመለከቱ ነበር ።

“እውነትዎ ነው ! ” አሉ እቶ እንተነህ የነበረው ጥላሁን ፈይሳ ፤ ረብሻው ፤ ድብልቅልቁ ጸጥ ካለ በሁዋላ ባዘን የከበደ ፊቱን ወደ ዳኞች ቀና አድርጎ ። ” “የተናገረችው ሁሉ እውነት ነው ፤ ቀኛዝማች ዳኘን ሁለታችን ነን የገደልናቸው ። ”

“ውይ . . . ! ለካ . . . ለካስ እንዲህ ጨካ . . . ጨካኝ ነህ ጥላየ ! ለማ . . . ለማን ጥለኸኝ ልትሄድ ኖሮዋል ? ማ . . . ማን አለኝ ? ” አለች ሶፊያ ፤ ደስታ ባበራው ፊትዋ እንባዋ እዩወረደና ንግግርዋ ሳግ እያናቀፈው ። ባልዋ ፤ ጥላሁን ዝም ብሎ ባዘን በከበደ ፊት ይመለከታት ነበር ። ከዚያ ዳኞቹ እዚያው እስበሳቸው ቀስ ብለው ሲመካከሩ ከቆዩ በሁዋላ ሶፊያና ባልዋ ጥላሁን ፤ ተይዘው እማረፊያ ቤት እንዲገቡ መወሰናቸውን እስታውቀው ጉዳዩ ለሶስት ወር ተቀጠረና ችሎቱ ተነሳ ።

## ምእራፍ ፴፯

# ከማረፊያ ቤት ወደ አለም በቃኝ !

“ማረፊያ ቤት የሚሉት ... እስር ቤቱን ነውን”አለች ሶፊያ፣ ፍርድ ቤት ባልዋንና አበዋን ወደ ማረፊያ ቤት እንዲሄዱ ካዘዘ በሁ ዋላ ፣ ፖሊስ በዝግ መኪና ጭኖ ወስዶ ወህኒ ቤት ሲያወርዳቸው ።

“ሳይወጡ ፣ ሳይወርዱ ፣ ታስሮ ከሚቀለቡበት የተሻለ ማረፊያ ቤት ሲባል የሚገባው ሌላ ምን ቦታ ይገኛል ?” አለ ጥላሁን ፣ በቀልድ መልክ ። ብቻ እሱም ቢሆን የዳኝነት ስራ ከያዘ ጀምሮ ማረፊያ ቤት ከሚባለው እስር ቤት መሆኑን ባጠቃላይ ይወቅ እንጂ ፣ እዚያ ውስጥ ለሚስተናገዱ ሁኔታ የሚያውቀው ነገር እምብዛም አልነበረ ። ስለዚህ ወህኒ ቤት እንደ ደረሱ ፣ ሶፊያ ወደ ሴቶች ክፍል ፣ እሱ ወደ ወን ዶች ክፍል ተወሰደው ፣ እዚያ ይዞት የነበረውን ገንዘብም ፣ እንደ ብር እና እንደ ሰንጢ ያሉ ፣ ሌሎችም አንዳንድ እቃዎች እያስመዘገበ አስ ረከቦ ሲጨርስ ! መሰረት የሚባለው የካቦው ረዳት ፣ አንድ አሮጌ ብርድ ልብስና አንድ ጣሳ ውሀ ይዞ መጥቶ ውሀውን እጥላሁን ፊት አስቀ መጠና ብርድ ልብሱን እቅፉ ላይ ወርውሮለት ፣ “ያውልህ ፣ ልብስ ህን ሁሉ አውልቀህ ስጠኝና ይህን ለብሰህ ቆይ ። በዚህ ደሞ ... ራስህን ታጥበህ ቆዩኝ ፤ በመለስ እላጭሀለሁ ” አለ የካቦው ረዳት ። ጥላሁን ግራ ገብቶት ብርድ ልብሱን በቅፉ እንደ ተሸከመ ፣ ያላቀፈ ውን ሰው ዝም ብሎ ይመለከት ጀመር ። ያ አሮጌ ብርድ ልብስ ተረ ጋግጦ ፣ ተረጋግጦ ፣ ደቅቆ ፣ ብናኙ እንኩዋንስ ታቅፈውት ገና ሲቀር ቡት ጉሮሮ እዩከረከረና አፍንጫ እዩከነከነ ያስነጥሳል ፤ አይን ያስ ለቅሳል !

“ምን ግር አለህ? የነገርሁህ አልገባህም ? አማርኛ አታውቅም ?” አለ መሰረት ፣ ፈገግ ብሎ ።

“አማርኛስ አውቃለሁ ፤ ብቻ ... ልብስ የማውለቁ ትርጉም አልገባኝ ብሎ ነው እንጂ !”አለ ጥላሁንም ፣ እንዲሁ ፈገግ እንደ ማለት ብሎ ።

@OLDBOOKSPDF

"ኦ... ! ልብሱ ሁሉ ? የግር ሹራብ ሳይቀር... ወደ ሽ ገዳይ መወሰድ አለበት ! " አለ መሰረት ፣ እንዲያ ፈገግ እንዳለ ።

"ሽ ገዳይ ? ምንድነው ሽ ገዳይ ?"

"ሽ ገዳይ ..... አዲስ የሚገቡት እስረኞች ልብስ ሁሉ ባንድነት ተሰብስቦ የሚቀቀልበት ነው ። መቀቀያው ለልዩ ልዩ በሽታ ጠንቅ የሚሆኑትን ስፍር ቁጥር የሌላቸው ፣ የሚታዩም ፣ የማይታዩም ተሀዋስ ያን ስለሚያጠፋ ፣ ስለሚገድል ነው..... ሽ ገዳይ የተባለ እንጂ ... እይዞህ ፣ ሽ ሰው የሚገድል እንዳይመስልህ ! " አለ መሰረት ፣ የወህኒ ቤት ሰንሰራት ሲቅነቱ ያሰማው የኩራት ስሜት ትክሻውን ትንሽ ወደላይ ገፋ ሲያደርገው እዩታዩ ።

ጥላሁን ልብሱን ሁሉ ፣ እንደ ተባለው የግሩ ሹራብ ሳይቀር ፣ አውልቆ ወደ ሽ ገዳይ ወስዶ እንዲቀቅለው ለመሰረት ሰጥቶ ፣ እሱ ያን አሮጌ ብርድ ልብስ ለብሶ ፣ እፍንጫውን ከሚከነክነው ብርኝ ለመራቅ ፊቱን ወደ ሰማይ እንጋጥጦ ሲቀመጥ ፣ አንድ ሌላ እስረኛ ትልቅ የጠርሙስ ሰባሪ ፣ የቦንዳ ቁራጭ የመሰለ እድፋም ብረትና አንድ እንዲሁ ያደፈ ፣ አሮጌ ጥረድ አምጥቶ እፊቱ አስቀመጠለት ።

"ይህ ሁሉ ደግሞ .... ምን የማደርግበት ነው "አለ ጥላሁን እስረኛውን ።

"መሰረት ሲመጣ ራስህን የሚላጭበት ነው ። "

"ምኑ ? "

"ከጠርሙስ ሰባሪውና ከምላጩ በመረጥከው ትላጫለህ "

"እንዴ... ! ይህ የተሸራረፈው ጠርሙስ ሰውነት ... ይቆራርጣል ፣ ያቆስላል እንጂ እንዴት አድርጎ ሊላጭ ይችላል ? ይህስ.... ገና ስለት ያልወጣለት ፣ ዱልዱም ብረት እንዴት ራስ ሊላጭ ይችላል ?" አለ ጥላሁን በመገረም ፣ የጠርሙስ ሰባሪውንና ምላጭ የተባለውን ዱልዱም ብረት በዩተራ እንስቶ እያገላበጠ እያዩ ።

" እሆ.... ! ይህ ዱልዱም ብረት የምትለውኮ ሁለት ደቂቃ ያክል ይህን ጥረድ ላይና ታች ስታላልፍበት ግሩም የሆነ ስለት ይወጣዋል !" አለ እስረኛው ፣ ድምጹን ከፍ አድርጎ እዩላቀ ። እስረኛው የተናገረው ቀልዱን ይሁን ምሩን ጥላሁንን አልገባውም ።

"ኧረ እባክህ ዝም በል ወንድሜ ፤ እኔ ባላገር ነው የኖርሁ ! እንዲህ ያለውን ነገር ደህና አድርጌ አውቃለሁ ! ይህ ብረት ስትሞር

@OLDBOOKSPDF

ደው ውለህ ብታድር እንኩዋንስ ራስ ሊላጭ . . . ሳር ሊያጭድ አይችልም !" ሲል ጥላሁን ፡ እስረኛው ከልቡ ሳቀ ።

"ለመሆኑ እዚስ የሚገቡት ሁሉ በዚህ እየተላጩ ነው የሚገቡት ማለት ነው ?" አለ ጥላሁን ፡ እስረኛው ሲስቅ ዝም ብሎ ሲመለከተው ቆዩና።

"ገንዘብ ከሌላቸው በጠርሙስ ስባሪው ፡ ወይም በዚህ . . . . እንቶ ፈንቶ ዱልዱም ብረት ብለህ ስም ባወጣህለት ምላጭ መላጨት አይቀርላቸውም ፤ ይላጫሉ ፤ ብቻ . . . ለጠላት አይስጠው ፤ በሁለቱም መላጨት ጭንቅ ነው !" አለ እስረኛው ፡ ድምጹን ዝቅ አድርጎ ።

" ገንዘብ ያላቸውስ ?"

" ሀ ! ገንዘብ ያላቸውማ ከፍለው በካቦው መኪና ይላጫሉ !" አለ እስረኛው ፡ አሁንም በዝቅተኛ ድምጽ ፡ ዞወር ዞወር ብሎ ግራ-ቀኙን ተመልክቶ ፡ እግን መሆኑን ሲያረጋግጥ ወደ ጥላሁን ጠጋ አለና።

"ካቦው ምንድነው ?" አለ ጥላሁን ፡ እስረኛው በዝቅተኛ ድምጽ ሲናገር ስላዬ ፡ በዝቅተኛ ድምጽ መናገር አስፈላጊ ቢሆን ነው ብሎ ገምቶ ፡ እሱም እንዲሁ በዝቅተኛ ድምጽ ።

"ሆሆ . . . . ! ካቦው ? እዚህ የስረኛው ሁሉ ንጉስ ፡ እስረኛን አቅልጦ ፡ ቀጥቅጦ የሚገዛ ግን መሰለህ ! ካቦ አደለም ? እስረኛ አንድ ጊዜ የስር ቤቱን በር ከገባ ፡ አስተዳዳሪዎች ዞወር ብለው እያዩትምኮ ! አይናቸው ፡ ጆሮዎቻቸው ፡ እጅ እግራቸው ካቦው ነው !"

"ማነው የሚሾመው ?"

"እነሱ ። አስተዳዳሪዎች ግለቱ ነው።"

"ከየት ?"

"ከዚሁ ከእስረኞች መሀከል ። ለስሙስ . . . . እሱም እንደኛ እስረኛ ነው !" አለ እስረኛው ፡ ያሽሙር ፈገግታ ፈገግ ብሎ ጥላሁንን የጎድን እያዩ ።

"ለስሙስ እስረኛ ነው! የስም ነው እንጂ . . . . የውነት እስረኛ አደለም ማለት ነው ? "

"አ . . . . ! ይቢቃናል ወንድሜ ! ያስለፍልፍ መሳይ አስረሀል መሰለኝ . . . . ገና ሳንተዋወቅ ብዙ አስለፈለፍኸኝ !" አለ እስረኛው ፡ አሁንም አካባቢውን ባለማመን ዞወርወር ብሎ ተመልክቶ ።

" እሺ ፤ ይብቃን የኔ ወንድም ፤ ይቅርታ አድርግልኝ ፥ ነገር ነገርን እዬሳበ ሳናስበው እዚህ አደረሰን እንጂ ፡ እኔም መናገር የማትፈልገውን ለማናገር ፍላጎት ኖሮኝ አደለም ። አሁንም ቢሆን ለኔ የተናገር

@OLDBOOKSPDF

ሽው ከኔ ወደ ሌላ ይተላለፋል ብለህ አትስጋ ። ስለዚህ ይህን እንተ ውና ወደ ምሬጫችን እንመለስ ። ታዲያ አሁን . . . . . የራስ ምላጭ ፣ መኪና መከራዩት ብፈልግ ከካቦው በቀር እሌላ ዘንድ አላገኝም ? ” አለ ጥላሁን ፣ እስረኛው በተናገረው ሲጸጸትና እንደ መደንገጥ ሲል ሰላዩ ወሬ ሸምቶ በችርቻሮ የሚሸጥ ፣ የወሬ ነጋዴ አለመሆኑን በቃ ልም ፣ ራሱንና ጠቋዋሚ ጣቱን በመነቅነቅም እያረጋገጠ ።

“ፊት የወህኒ ቤቱ ነበር . . . . እሱ እንዲጠፋ ከተደረገ . . . ከጠፋ ማለቴ ነው” አለ እስረኛው ቶሎ ራሱን አርሞ ፣ “የወህኒ ቤቱ ከጠፋ ብዙ ጊዜ ሆኖዋል ፤ ሌላም . . . . . . ያለው ሰው የለ ”

“ካቦውን ለመጠዬቅስ . . . . እንዴት ነው የማገኘው ? ”

“መሰረት ሲመጣ ንገረው ፤ መሰረት ካቦውን በቀጥታ የሚያገ ኛግርበት ሰው አይወድም ። ለሱ ፣ ‘በጠርሙስም ሆነ በምላጭ መላ ጨት አልችልምና እባክህ የክራይ መኪና የማገኝበትን ዘዴ አመል ክተኝ’ ብለህ ፣ አስተዛዝነህ የነገርከው እንደሆነ ዘዴውን . . . . እሱ ያውቀዋል ። ካቦውም ቢሆን አንተ በቀጥታ ከጠዬቅከው እንኳንስ ኪራይ ሊቀበልህ መኪና ያለው መሆኑንም አያምን!” አለ እስረኛው ከፊቱም በጣም ዝቅ ባለ ድምጽ ።

“እሺ ፤ ገባኝ ፤ እግዜር ይስጥልኝ ! ” አለ ጥላሁን ፣ እንዲሁ እፉ እንዳመጣው ። ነገር ግን እንዲያ ፡ አፉ እንዳመጣው ገባኝ አለ እንጂ ፣ ነገሩ ይብሱን እዬተሰወረው ከመሄድ በቀር ምንም አልገባው ! እንዳ ይጠይቅም እንግድነቱ አገደው ።

“ራስህን ታጠብህ?” አለ መሰረት ፡ ጥላሁንን ሲያነጋግረው የቆ ዬው እስረኛ እንደ ሄደ ከሽ ገዳይ ተመልሶ ።

“የምትላጭበት ነው ብሎ አንድ ሰው . . . . . ይህን ስላመጣልኝ በጠርሙስ ሰባሪም ይሁን ፡ በዚህ . . . . በብረቱ መላጨት ጭራሽ የማልችል ስለ መሰለኝ ፣ በጭራሽ ስለማልችል ፣ ሌላ መላጫ የሚ ገኝ እንደሆነ ካንተ ጋር ለመነጋገር . . . . ቆዩሁ ” አለ ጥላሁን ፣ የጠ ርሙሱን ሰባሪና ያን የዛገ ብረት መሰረት እንዲያውቃቸው ሁሉ ሉ እያገላበጠ እያሳዬ ።

“ሌላ . . . . እንዴት ያለ መላጫ ? ”

“እንደ . . . . መኪና መላጫ ያለ ነገር አይገኝም ?”

“መኪና አሁን . . . . . ከዬት ይገኛል ! ” አለና መሰረት ግራ ቀኙን ዘወር ፣ ዘወር ብሎ አይቶ ፣ “መኖሩን እንኳ አንዳንድ ተሸሽገው የሚ

@OLDBOOKSPDF

ያክራዩ ሳይኖሩ አ[illegible] ነገር ግን እንዲህ ያለው የንግድ ስራ እዚህ ክልክል ስለሆነ ፣ እንሱም ሆኑ ፣ አገናኞቻቸው የታወቀባቸው እንደሆነ ስለሚቀጡ ፣ ለቅጣታቸው መከካሻ እንዲሆናቸው ብለው ይመስለኛል፣ የሚጠይቁት ኪራይና ዋጋ በጣም ውድ ነው ” አለ ፣ ወደ ጥላሁን ጠጋ ብሎ በዝቅተኛ ድምጽ ።

“ ምን ያክል ይጠይቁ ይሆን ? ”

“እኔ እንኩዋ ባለመኪናዎቹን አላውቃቸውም ፤ አንድ እነሱን የሚያውቅ ሰው ትናንት . . . ለሁለት አዲስ ገቢዎች ፣ ባምስት ብር ተከራይቶላቸው ነበር ። በዚያ ላይ ስላገናኘኑቱ ለሱ የሚከፈል አለ ። ከፈለግህ ቆስ ብዬ እሱን ልጠይቅልህ ። ”

“እባክህ ጠይቅልኝ ። ” በዚህ ተቆራርጦ የሚቀበል ራቢን ለማ ባከም የሚያስፈልገው ገንዘብ ያለጥርጥር ካምስት ብር ብዙ ጊዜ የሚበልጥ መሆኑ ስለማይቀር ፣ አስቀድሞ በዚሁ መገላገል ይሻላል ። ስመሆኑ . . . ሴቶችም መላዉት አለባቸው ? አለ ጥላሁን ፣ ሰሬ ያን ሲያስብ ጭንቀትዋ ከራሱ ጭንቀት የበለጠ አስፈራራውና ።

ከገሉ በቀር የሚባል የለም ፤ አስረኛ ከሆነ ሁሉም መላዉት አለበት ።

“እንግዲያስ እባክህ የሚገኝ ከሆነ ፣ ባለቤቴ እሴቶች ክፍል ፣ ሶፊያ መላት ትባላለች ፤ ለስዋም . . . ቢከራይልኝ ለሰወየው አደራ በላልኝ ። ብቻ ገንዘባችንን ሁሉ አስመዝግበን እዚያ ስላስረከብን ፣ አሁን ገንዘብ በጄ የለም ” አለ ጥላሁን ፣ ገንዘቡን ያስረከበበትን ቦታ ባገጩ እያመለከተ ።

“እሱ ግዴለም ፤ አያስቸግርም ፤ ፊርማህን እዚያ ስታስረክብ ከፈረምከው ጋር እያመሳከሩ . . . ላዘዝሀለት ይከፍላሉ ” አለ መሰረት ፣ እሱም መረካከቢያውን ባገጩ አመልክቶ ። “ለመሆኑ ስንት ገንዘብ አስረከበህል ? ” አለ ቀጠለና ።

“ሁለት መቶ ብር ”

“ሁለት መቶ ብር ” አለ መሰረት ፣ እንደ ገደል አዋይ ጥላሁን ያለውን ደግሞ ።

መሠረት የመኪና ክራይ ፍለጋ ከሄደበት ተመልሶ ፣ ክራዩ ለጥላሁንና ለሶፊያ አምስት አምስት ብር ፣ ላገናኛዎች ሶስት ብር ፣ በድምሩ አስራ ሶስት ብር መገኘቱን ሲነግረው ጥላሁን በጣም ደስ አለው።

@OLDBOOKSPDF

"አሁን እንግዲህ ከሁሉም አስቸጋሪ የሚሆነው የሚስማማ ቦታ ማግኘቱ ጉዳይ ነው" አለ መሠረት ፣ ጥላሁንን እየወራ ራሱን በተከራዩለት መኪና ሲላጨው ።

"ለምን የሚስማማ ቦታ ?" አለ ጥላሁን ።

"ለምኝታና .... በጠቅላላው ለማረፊያ የሚሆን ። መቸስ... አን ተም ሆንህ ባለቤትህ ... እዚህ የምትቆዩበትን ጊዜ እግዚአብሄር ያላ ጥርላችሁ እንጂ ፣ እዚህ በምትቆዩበት ጊዜ ቀን የምታርፉበትና ሌሊት የምትተኙበት አንዳንድ የተወሰነ ቦታ ያስፈልጋችሁ የለ ? አሱን ማለቴ ነው ።"

"እንዴት ! ለያንዳንዱ እስረኛ የተወሰነ ቦታ የለውም ?"

"አለው እንጂ ! ሁሉም ባንድ ላይ ሆኖ እዚያ ውስጥ ... ለያን ዳንዱ የተወሰነ ቦታ አለው ። ብቻ አሁን እስረኛው እየበዛ ስለሄደ፣ ያልተያዘ ደህና ቦታ ማግኘቱ በጣም ችግር ነው ። ያልተያዘ ቦታ የሚ ገኘው በሽንት ቤታው ዙሪያ ብቻ ነው ። ታዲያ እሱ . . . ካልቸገረ እንኳንስ ለምኝታ ላንድ አፍታ አጠገብ መቆየትም ቢሆን ያስጨ ንቃል !"

"እንዴ ! እስረኛ በሚተኛበት መሀከል ነው ... የሽንት እቃው ያለ ? ይህስ ደሞ . . . ከሁሉም የባሰ ነው !" አለ ጥላሁን እዩሳቀ ከደረሰ ጀምሮ ያዩውም ሆነ የሰማው ሁሉ ክፉ ብቻ ቢሆንም ፣ የሽ ንት እቃው እምኝታ ቤቱ ውስጥ መኖሩ ከሁሉ የከፋ መሆኑን ያለ ስጋትና ያለ ይሉኝታ ገልጾ ።

"አዎ ፤ እስረኛው በሚተኛበት ክፍል ... መሀከል እንኩዋ ሳይ ሆን ወደ ዳር ነው" አለ መሠረት ፡ እሱም እዩሳቀ ። ብቻ ለምን መሰለህ ? አለ ወዲያው ቀጠል አድርጎ ። ሌሊት እስረኛ እንዳያ መልጥ ፣ ለጥንቃቂ ክፍሎች ሁሉ መዝጊች ስላለባቸውና ፣ ወደ ሽንት ቤት መውጣት ስለማይቻል ፣ ሌሊት ሽንት ለሚያስቸግራቸው እስረኞች ምቾት ነው የሽንት እቃው እዚያ የሚቀመጥ ። ታዲያ ሌሊት ሽንት መከፈል የሚፈልጉ እስረኞች ሁሉ ፣ የግላቸውንም ሆነ ባጠገባቸው ከሚተኙ ጎረቤቶቻቸው የሚጋሩትን መከፈያ ፣ እዚያው ባቅራቢያ ቸው አስቀምጠው ባስፈለጋቸው ጊዜ እዩከፈሉ ወደ ሽንት እቃው ወስደው ሲገለብጡ ያድሩና ጥዋት ከዩክፍሉ ወደ ሽንት ቤት ተወ ስዶ ይፈስሳል ። ታዲያ ይህ ... ሰው በሚተኛበት ክፍል የሽንት እቃ መቀመጡ እንኩዋ በውነት .... በኔ አስተያየት ነውርነቱ ይህን ያክል

@OLDBOOKSPDF

አስከፊ ባልሆን ። ነገሩን አስከፊ የሚያደርገው መብራት ሲበራ ስለማያድር ፤ ቶሎ ስለሚጠፉ መከራያቸውን እየያዙ በጨለማ ወደ ሽንት እቃው ከሚሄዱት ፤ አፉን ሱቶው በላዩ የሚያፈስሱም ፤ እንዲያውም ሳይደርሱ የደረሱ መስሎዋቸው በውጪ ፤ አጠገቡ አፍስሰው የሚመለሱም ስለሚኖሩ... እዚያ በእቃው ዙሪያ ቦታ የሚይዙ ሰዎች ሽንት ሲፈስስባቸው ይችላል ። ስለዚህ ነው . . . እዚያ ዙሪያው ቦታ መያዝ አይመችም ያልሁህ ። ታዲያ ችግሩ ያለው ቦታ ፤ ያልተያዘው ቦታ እሱ መሆኑ ነው ።”

“እሴቶች ክፍልም እንዲህ ያለ ችግር አለ ?” አለ ጥላሁን ፤ ሶሬ ከሽንት እቃው አጠገብ ቀኝታ የሚደርስባት ክፉ ችግር ፤ ያን ክፉ ፊቱን ብዙ እጥፍ ጊዜ አክፍቶ ስላሳየው ፍራቱ በፊቱ ጎልቶ እየታየ ።

“ሁሉም ያው ነው !” አለ መሠረት ።

“ታዲያ ምን ይሻለናል ?”

እንጃ ! የ . . . እድል ጉዳይ ነው እንጂ አንዳንድ ጊዜ ፤ ሲያጋጥም ፤ የገንዘብ ችግር የሸናባቸው ሰዎች ገንዘብ እየተቀበሉ ቦታቸውን ፤ ደህና ቦታቸውን የሚለቅቁ ይገኛሉ ። ብቻ . . . ችግሩ እንደንዚህ ያሉ ሰዎች እንደ ልብ አለመገኘታቸውና ሲገኙም የሚጠይቁት ዋጋ ከመጠን በላይ ውድ መሆኑ ነው ።

“እንዴ ! የሚገኙና ውድ ዋጋ የማይጠይቁ ቢሆኑስ . . . እኛ ገንዘብ ስላለን ፤ የነሱን ደህና ቦታ በገንዘብ ገዝተን በነሱ ሽንት እንዲፈስስባቸው ልናደርግ ነው ? ይህ የማይደረግ ፤ ኧረ እንኳንስ ሲደረግ ፈጽሞ የማይታሰብ ነው ! ይህን ከማድረግ ለኛ የደረሰውን ክፉ እድል መሸከሙ ይቀለናል !” ሲል ጥላሁን ፤ ፊቱ ከሙ-ቅጽበት ተለውጦ መሠረት ያን ፤ በቅጽበት የተለወጠ ፊት ሲያይ ለጊዜው ድንግጥ አለ ።

“የለም ! እንደሱ ማለቴኮ አይደለም !” አለ ወዲያው አስተጋባና ። “ያልሁህ አልገባህም መሰለኝ ፤ እንደሱ ማለቴ አይደለም !” አለ ፤ ውሸት ለመፍጠር ፈጣን የሆነ አእምሮው እንደ ልማዱ ውሸቱን ፈጥሮ እስኪያደርስለት አንዱን አረፍተ ነገር እየደጋገመ ። “ሁለቱ ፤ ወይም ሶስቱ ባንድ ላይ ማህበርተኞች ሆነው ፤ ገንዘብ ተቀብለው ያንዳቸውን ቦታ ይለቁና ባልተለቀቁት እነሱ እየተፈራረቁ ይተኛሉ ። ማለት አንዱ ቀን ተኝቶ ቢውል ሌሊት እሱ

@OLDBOOKSPDF

ወደ ራስጌ ፣ ወይም ... ማይያዝበት በኩል ጠጋ ብሎ ቀን ላልተኛው ፣ ወይም ላልተኙት ይለቅቃል ። ታዲያ . . . እንግዲህ ቀን የተኛው ሌሊት እየተቀመጠ ፣ ሌሊት የተቀመጠው ቀን እየተ ተኛ ፣ ሁሉም እንቅልፍ ይሁን እረፍት ሳይጎድልባቸው ገንዘብ እግኝ ተው ከችግራቸው ይገላገላሉ ! ”

“ኢ. . . ! እሱ እንኳዋ እንጃ ! ምናልባት ይሻል ይሆናል ! እንዲህ ያለ ከተገኘ . . እስቲ ግዴለም ይሁን ! ” አለ ጥላሁን ፣ ያም ቢሆን ተገቢ መሆኑን ተጠራጥሮ እያመነታ ።

“በውነት እድላሞች ናችሁ ! ” አለ መሰረት ፣ ቦታቸውን የሚ ሸጡ ሰዎች ፍለጋ ሄድሁ ብሎ ቆይቶ ሲመለስ ።

“ለሁለታችንም ተገኘልን ? ” አለ ጥላሁን ።

“ያውም ርዝመቱ እግር ዘርግቶ መተኛት የሚያስችልና ስፋቱ እንደ ተኙ መገላበጥ የሚያስችል ነዋ ! ዋጋው ግን ትንሽ ወደድ አለ”

“ስንት ? ”

“ቦታው እያንዳንዱ አርባ ብር ፣ ፍራሹ ንጹህና ወፍራም ፍራሽ እያንዳንዱ አስር ብር ፣ በድምሩ እስቲ . . . ሰሁለቱ ስንት መሆኑ ነው ? ” እ. . . መቶ ብር መሆኑ ነው መሰለኝ ! ልክ ነው ! መቶ ብር ነው ። ከፉ አደለም ! ዛሬ ቦታ እንዲህ በተወደደበት. . . ከፉ አደለም ! ”

“እዎ ! ይሁን ግዴለም ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ ። ብቻ . . . ፍራሹን እንኳዋ ከቤታችን ማስመጣት አንችልም ኖሮዋል ? ” አለ ጥላሁን ፣ ሆቴል የገባ ይመስል ለወሀኒ ቤት ምኝታ ያን ያክል ገንዘብ ከፈል መባሉ ቢከብደውና ቅር ቢለውም ፣ መሰረት ድካሜን ሁሉ ከንቱ አደረገብኝ ብሎ እንዳይቀየመው የራሱን ቅርታ በውሸታ ፈገ ግታና የደስታ መልክ ለመሸፈን እየተጣጣረ ።

“የቤት ፍራሽ ለዚህ አይስማማም ! ይህ በቦታው ልክ የተሰፋ ነው ።”

“ኢ. . . ! እንዲያ ነው ? ታዲያኮ . . . አልጋም ፣ ፍራሽም ከቤት ማስገባት ይቻላል ሲባል ሰምቻ ነበር ! የሰማሁት ውሸት ነው ማለት ነው ? ”

“ለፍርደኞች ይሆናል ። ፍርደኞች አልጋም ሊያስገቡ ይችላሉ።”

@OLDBOOKSPDF

"ጌትዬ ! እንደ ገና ወንጀለኞች መሆናቸው ገና ካልተረጋገጠ፤ እዚህ . . . በቀጠሮ ከሚቆዩት ፤ ወንጀለኞች መሆናቸው ተረጋግጦ የተፈረደባቸው የተሻለ ምቾት አላቸው ማለት ነው ? "

"በጣም እንጂ ! እዚህ በቀጠሮ የሚቆዩት እስረኞች በጣም ጎዶሎች ናቸው ፤ ካለም በቃኝ እስረኞች በቀር ፤ በቀጠሮ ከሚቆዩት እስረኞች በከፋ ሁኔታ የሚታሰር የለም ።"

ጥላሁን ራሱን ከተላጨ በሁዋላ ፤ መሰረት ልብሱን ከሻ ገዳይ አምጥቶ ሲሰጠው የሱ ልብስ መሆኑን ማመን አቃተው ። ልዩ ልዩ ቀለምና የጽዳት ንድለቱ ልዩ ልዩ ደረጃ ካለው ፤ ብዙ ልብስ ጋር ባንድ ላይ ተደባልቆ ስለ ተቀቀለ ፣ ያን የሌለውን የተለያዩ ቀለምና በደረጃ የተለያዩ ንስቁልና ተቀብሎ ፤ የሱን ቀለምና ጽዳት ለሌላው ሰጥቶ ፤ ፍጹም ሌላ ሆኖ ፤ ተዠንርገር ስላገኘው ፤ የሱ ልብስ መሆኑን ማመን አቃተው ።

"ይህን ቁጥር በፊትህ አደለም እንዴ የሰፋሁት ? " አለ መሰረት ፤ በጨርቅ ላይ የተጠለፈ "ቁጥር 3 " በኮቱ ፤ በሱሪው ፤ በውስጥ ልብሶቹና በግር ሹራቡ ላይቀር ፤ መጀመሪያ ለመቀቀል ሲወስድ በጥላሁን ፊት የሰፋውን ከያለበት እየፈለገ እያሳዩ ።

"ቁጥሩስ . . . ልክ ነው ! ብቻ ልብሱን ምን እንዲህ አደረገው፤ ደግሞስ ሽታውስ . . . እንዲህ ያለ . . . ክፉ ሽታ ምንድነው ? " አለ ጥላሁን ፤ ልብሱ በመበላሸቱ ከማዘኑ የበለጠ ተገርሞ ።

"ሽታውስ እመቀቀያው ውስጥ የሚጨመረው መድኃኒት ነው ፤ አሁን ስትላመዱ ማስቸገሩን ይተዋል " አለ መሰረት ። ወዲያው ቦታውን እንዲመራው መሠረት ወስዶ ከካቦው ጋር አገናኘው ።

"ጥላሁን የተመራው ቦታ የሽንት እቃው ከሚቀመጥበት ብቻ ሳይሆን ከመተላለፊያ መንገዶች ሁሉ ራቅ ያለ ፣ ተላላፊ የማያስቸግርበት ስለሆነ ፤ እዚያ ክፍል ከሱ የተሻለ ቦታ የለም ። መጠኑም መሰረት እንዳለው ፤ ቁመቱ እግር ዘርግቶ መተኛት የሚያስችል ፤ ስፋቱ እንደ ተኙ መገላበጥ የሚቻልበት ነው ። ፍራሹ ግን ንጹህ ይሁን እንጂ መሠረት እንዳለው ወፍራም አደለም ። እንዲያውም ከፍራሽ ይልቅ ድሪቶ ልብስ ቢባል ከውነቱ ይቀርብ ይሆናል ። ቢሆንም እዚያ በፍራሽ ስም ከሚነጠፈው የሚበዛው እንደሱ ድሪቶ በመሆኑ ጥላሁን ቅር አልተሰኘም ። ይልቁንም ካቦው ቦታውን ሲያሳዩው በወሬ እንደ ሰማው ሳይሆን ፈገግ ብሎ ፤ የጅ ሰላምታ ሰጥቶ ፤ በደህና ፊት ስላ

ነጋገረውና ፣ ምናልባት የሚያስቸግር ነገር የገጠመው እንደ ሆነ ቢነ ግረው ፣ በማቻለው ሁሉ የሚረዳው መሆኑን ጠጋ ብሎ በዝቅተኛ ድምጽ ስለ ነገረው ፤ ደስ ከመሰኘቱም በላይ ገርሞት ፤ እሱም እን ዲሁ በዝቅተኛ ድምጽ ምስጋናውን ገለጸ ።

ለራሱ መላጫ የጠርሙስ ስባሪና የዛገ ብረት ያመጣለት እስረኛ ስለ ካቦው ያወራለት ሌላ ነበር ። ያ እስረኛ የነገረው ካቦ እስረኞችን ረግጦ ፣ አንቀጥቅጦ ለመግዛት በስረኞች ላይ የነገሰ አስመስሉ ነበር የነገረው ። ከተናገረው ደግሞ ያልተናገረው ክፍል ፣ አሸሙሩ ካቦውን እንደ እስረኞች ጸር ፣ ከቅጣታቸው እንዳንድ ክፍል የሚቆጠር ፣ እነ ሱን ለማስጨነቅና ለማሰቃየት የተፈጠረ አንጂ እንዲህ በደስታ ፣ እን ዲህ በፈገግታ ተቀብሎ እንደ ጉዋደኛ የጅ ሰላምታ የሚሰጥ ፣ "ችግር ሲያጋጥማችሁ ወደኔ ኑ ረዳችሁዋለሁ" ብሎ የሚጋብዝ አልነበረም ፤ ታዲያ . . . . ያ እስረኛ የነገረው እውነት ባይሆን ነው ? ወይስ ሌሉ የቀለዩ አልተያዩት ፣ የቀለዩ አቀባበል የሚያደረጋቸት ምክንያት ሌለ ?

እንዲያውም . . . ከቦው ብቻ ሳይሆን እዚያ ከገባ ጀምሮ ያገኛ ቸው ሁሉ ሰው ፍጹም ደጎች ሆነው ነው ያገኛቸው ። መቸም የመ ሰረት ነገር አይነሳ ! መሰረት ያደረገለት ርዳታ ለሁልጊዜ የማይ ረሳው ፣ የውለታ ባለእዳ አድርጎት የሚኖር ነው ! ገንዘቡንና ሌላ እቃ ውን አስረክቦ ከስረኞች ጋር ከተጨመረ ጀምሮ ፣ መሰረት ለሱ ብቻ ሳይሆን አልፎ ፣ ተርፎ እሴቶች ክፍል ባለችው ፣ ለሶፊያ ጭምር ያደ ረገው ርዳታ ፣ ማለት ከወዲህ ወዲያ ፣ ከወዲያ ወዲህ ተሩዋሩጦ የራስ መላጫ መኪና ካለበት ፈልጎ ተከራይቶ ራሳቸውን ከመቁሰል ማዳኑ ፣ ምን ያክል የቦታ ችግር ባለበት ፣ እዚያ ብዙ ጊዜ የቆዩት ሊያገኙት የማይችሉ ፣ ከመረጋገጫም ፣ ከሽንት ማፍሰሻም የራቀ ፣ ምርጥ ቦታ እንዲያገኙ ማድረጉ ፣ ይህ ሁሉ ያለችግር ፣ እንዲሁ በቀ ላል የሚደረግ አደለም ። ለሚወለዱዋቸውና ለባለቁርጦቻቸው ካል ሆነ ፣ እንኩዋንስ ባዲስ ደራሽ ፣ እንግዳ ለብዙ ጊዜ እውቂያቸውም ቢሆን እንዲያ ተቸግረውና ተጨንቀው ደግ የሚሰሩ ደግሞ ጥቂት ደጎች ፣ ጥቂት ታላቆች ብቻ ናቸው ። ስለዚህ መሰረት ያለጥርጥር እንዲያ ካሉት ጥቂት ደጎች ፣ እንዲያ ካሉት ጥቂት ታላቆች አንዱ መሆን አለበት !

"ራስህን የምትላጭበት ነው ብሎ የጠርሙስ ስባሪና የዛገ ዱል ዱም ብረት ያመጣልኝ እስረኛም ... ለኔ ደግ ነበር ፤ እንዲያውም የራስ መላጫ መኪና የሚገኝበትን ፍንጭ ያሳዩኝ እሱ ነው !" ብሎ ግላሁን ያ እስረኛ "አ .... ! አንተ ሰው ያስለፍልፍ አስረሀል መስ

@OLDBOOKSPDF

ለኝ ወንድሜ ፤ ገና ሳንተዋወቅ ብሎ እስለፈለፍኸኝ !" ያለው ፤ ከዚያ የተናገረውን የሰማ ባካባቢው ያለ መስሎት በፍርሀት እይኖቹን ሁሪያ አሽከርክሮ የተመለከተበት ሁኔታ ትዝ አለውና ብቻውን እንደ መሳቅ አለ ። ወዲያው ከዚያ ጋር ተያይዞ እስረኛው የራስ መላጫ መኪና ፊት ወህኒ ቤቱ እንደ ነበረውና እሱ ከጠፋ በሁዋላ ከካቦው በቀር ሌላ መኪና ያለው ሰው እንደሌለ ፤ ነገር ግን ካቦው መኪና ያለው መሆኑን እንደማያምንና ከራይ በቀጥታ እንደማይቀበል የነገረውን ሁሉ አንድ ባንድ ሲያስታውስ ፤ "እንዴ !" አለ ፤ ይህ ሰውዬው የነገረው መሰረት ፤ "ተሸሽገው ከሚያከራዩ ሰዎች ባገናኝዎቻቸው አማካይነት ላንተና ለባለቤትህ ባስራ ሶስት ብር ተከራዩሁላችሁ" ያለው ስለ ተለያዩበት ለጊዜው ግር አለውና ። በጠርሙስ ስባሪ ፤ ወይም በዛገ ዱልዱም ብረት የመላጨቱና በሽንት ማፍሰሻ ቦታ የመተኛቱ እሳብ አስደንግጦት ፤ ሁለቱ እስረኞች የነገሩት አንዱ ከሌላው የማይስማማ መሆኑን በዚያ ጊዜ ልብ አላደረገውም ነበር ። "እንዴ ! የካቦውን መኪና ነው ... መሰረት ' በምስጢር ከሚያከራዩ ሰዎች ባገናኝዎቻቸው በኩል ተከራዩሁላችሁ ' ያለኝ ! ኧረ እንጃ ! አያደርገውም ! ብቻ .... ቢሆንም ማጣራቱ አይከፋም ። ቆይ ግዴለም ! አጣራዋለሁ ። ያን እስረኛ የት ባገኝሁት ፤ ስሙን እንኳዋ አላውቅም !" አለና ጥላሁን ከካቦው በቀር መኪና ያለው ሰው በወህኒ ቤቱ ውስጥ አለመኖሩን የነገረውን እስረኛ ለመፈለግ ፤ ከክፍሉ ወጥቶ የዩክፍሉ እስረኞች ወዲያ - ወዲህ ሲዘዋወሩ ማየት በሚቻልበት ቦታ ቆሞ ሲመለከት ፤ ያ የሚፈልገው እስረኛ ሳያዩው ከሁዋላው መጥቶ ፤

"መኪና አገኘህ ? እንኩዋን ቀናህ !" አለው ፤ ራሱን ተላጭቶ ስላዩው ።

"እግዜር ይስጥልኝ ፤ ምክርህ በጣም ጠቀመኝ ። እንዲያውም አሁን እዚህ የቆምሁ ፤ ያለህበትን ስለማላውቅ ፤ እንዲህ ስትዘዋወር ሳላገኝህ አልቀርምና ምስጋናየን አቀርባለሁ ብዬ ነው ። ባለቤቴንም፤ እኔንም ከብርቱ ስቃይ ነው ያዳንኸን ።"

"አ---! ምንም አደል ፤ ርሳው ፤ ማንም ለማንም የሚያደርገው ነው !"

"አሁን እንዳልሁህ ስለ ባለቤቴም ፤ ስለ ራሴም ምስጋና ለማቅረብ ብፈልግ ቦታህንም ፤ ስምህንም ስላላወቅሁ .... እዚህ መጥቼ ቆምሁ ። ስምህን ብትነግረኝ ትፈቅዳለህ ? የኔ ስም ጥላሁን ፈይሳ ነው ።"

@OLDBOOKSPDF

"ይቅርታ አድርግልኝ ፤ ካንተ በፊት እዚህ ንብቼ የቆዩሁ እኔ ስለሆንሁ ፣ የራሴን ስም ብቻ ሳይሆን አካባቢውን ሳንተ ፣ ሳዲስ መጭው ባለማስተዋወቴ መወቀስ የሚገባኝ እኔ ነኝ " አለና ሰሙ ጠፍቶት እንደሚፈልግ ሳንድ አፍታ ዝም ብሎ ፣ አይኖቹን ከግራ ወደ ቀኝ ፣ ከቀኝ ወደግራ ዘወርወር አድርጎ ሲመለከት ከቆዩ በሁዋላ ፣

"እ....ስሜ ንብረዩስ ነው ፤ ንብረዩስ በቃሉ " አለ ። ከዚያ አሁንም ትንሽ ዝም ብሎ ቆይቶ ፣ "ለመሆኑ ሳንተና ለባለቤትህ ስንት አስከፈለህ ? " አለ ፣ በዝቅተኛ ድምጽ ፤

"ለያንዳንዳችን አምስት ብር ፣ ሳገናኝዎች ብሎ ሶስት ብር ፣ በድምሩ አስራ ሶስት ብር ከፈልሁ " አለ ጥላሁን ፣ እስከዚያ ጊዜ ያነጋገራቸው ሁሉ እንዲህ እንዲህ ስባለው ነገር ፣ በተናገሩ ቁጥር ዙሪያ ገባውን ተገላምጠው እያዩ በዝቅተኛ ድምጽ ስለሚናገሩ ፣ ምንም ምክንያቱን በትክክል ባያውቀው እሱኒ ነገር መናሩን ገምቶ ፣ እሱም እንዲሁ ዙሪያ - ገባውን ተገላምጦ ከተመለከተ በሁዋላ ከንብረዩስም እጅግ ዝቅ ባለ ድምጽ ።

"ሬው ...! አስራ ሶስት ብር ! ይህን ያክል ተከፈለ ሲባል ገና ዛሬ መስማቴ ነው ! ለመሆኑ.... አገናኝዎች ያልሀቸው ደግሞ የምን አገናኝዎች ናቸው ? "

"መኪና የሚያከራዩትንና የሚከራዩትን የሚያገናኙ አገናኝዎች የሉም ! መሰረት 'እዚህ አበር ቤት መኪና ማከራየት ክልክል ስለ ሆነ አከራዮችንና ተከራዮችን በምስጢር የሚያገናኙ ሰዎች አሉ ። ታዲያ ይህ ምስጢር የተገለጸ እንደሆነ በተለይ የተከለከለ መሳሪያ አግብተው የሚያከራዩት ሰዎችና አገናኝዎቻቸው ስለሚቀጡ ፣ እን ዲያ ባለው ቅጣት ግካካሻ እንዲሆን ነው ... ዋጋቸውንም የሚያስ ወድዱት' ብሎኝ ነበር ፤ ይህ ... ልክ አይደለም ማለት ነው ? "

"መሰረት በምስጢር ነው የላጨህ ? "

"እረ እዚያ .... አደባባዩ ላይ ነው የተላጨሁ ! " አለ ጥላ ሁን ፣ የተላጨበትን አደባባይ ባንጨ እያሳዩ ።

"እንዳይገባ ስለ ተከለከለ በምስጢር በተከራዩ መኪና ነው በን ሀድ አደባባይ ላይ የተላጨህ ? " ሲል ንብረዩስ ትንሽ ፈገግ ብሎ ጥላሁንን በቀልድ አይን የጎድን እያዩ ፣ ጥላሁን የራሱ ሞኝነት በን ብረዩስ ቀልድና አሽሙር ወለል ብሎ ታዩውና እሱም ከልቡ ይስቅ ጀመር ።

@OLDBOOKSPDF

" የምትተኛበት ቦታ አገኘህ ? " አለ ገብረዬስ ፡ ከሳቅ በሁዋላ ትንሽ ዝም ብለው ቆይተው ።

" አዎ ፤ አገኘሁ "

" ደህና ቦታ ነው ? "

" ጥሩ ቦታ ነው "

" ባለቤትህም ደህና ቦታ አገኙ ? "

" መችም እኔ ሄጄ አላዩሁት ፤ መሰረት ጥሩ ቦታ ነው ብሎኛል ። "

" ስንት አስከፈለህ ? "

" ለሁለቱ ቦታዎች ከፍራሾቻቸው ጋር . . . መቶ ብር " አለ ጥላሁን ፡ ገብረዬስ ውድ ነው ይለኛል ብሎ እዬፈራ ።

" እም . . . ! ለመሆኑ አንተ ለሹም ምግብነት የተሰናዳህ ደህና . . . ነህ ! " አለ ገብረዬስ እየሳቀ ። " ደህና " ካለ በሁዋላ ለግ ለት ያሰበውን ጥላሁንን ያስቀይመው ይሆናል ብሎ ዘሏሎ ።

"ለሹም ምግብነት የተሰናዳህ ፡ ወይም የምትገባ ፡ ደህና የስጋ ክብት ነህ እ ? " አለ ጥላሁን ፡ ገብረዬስ የዘለለውን እሱ ሞልቶ በጣም እየሳቀ ።

" ለመሆኑ ይህን ያክል ገንዘብ ይዘህ መጥተሀል ? ወይስ ገና ከውጭ አምጥተህ ልትከፍል ነው ? ይቅርታ አድርግልኝ ፤ ይህን እን ኩዋ መጠዬቅ ባልተገባኝ ! " አለ ገብረዬስ ፡ እሱም ከጥላሁን ጋር ሲስቅ ቆይቶ ።

" ኸረ የለም ፤ ምንም ከመንገድ የወጣ ጥያቄ አልጠዬቅኸኝም! እዚህ . . . የምንቆይበትን ጊዜ ስለማናውቅ ላንዳንድ አባሽ ፡ አባሽ ችግር ይሆናል ብለን ያመጣነው . . . ነበር ። "

" ታዲያ ምን ያክል እንዳለህ ለመሰረት ነግረኸው ኖሮዋል ? "

" አዎ ፡ ስንት ገንዘብ አስያዛችሁ ? ብሎ ስለ ጠዬቀኝ ነገርሁት ። "

" አዎ ፡ ለዚህ ነው ፤ እንዲህ ያለ ተስምቶ የማያውቅ ዋጋ ያስከፈላ ችሁ ገንዘብ እንዳላችሁ ስላወቀ ነው ። እንግዲህ . . . . ያስያዘው ገንዘብ እስኪያልቅ የሚወጣበትን መንገድ እንቅልፉን አጥቶ ሲያስብና ሲያ ሰናዳ እያደረ ፡ ' ና ፈርም ይልሀል ! ' አለ ገብረዬስ ፡ የቅርታ ፈገ ግታ ፈገግ ብሎ ።

" ይገርማል ! ታዲያ እንግዲህ . . . መሰረት 'በምስጢር መኪና ከሚያከራዩ ሰዎች ተከራይቼ አመጣሁላችሁ' ያለኝ የካቦውን መኪና ነው ማለት ነው ! " አለ ጥላሁን ፡ አንገቱን ደፍቶ ሲያስብ ቆይቶ ።

@OLDBOOKSPDF

"ከካቦው በቀር እዚህ ሚኒስቴር ያለው ፤ ሌላ ሰው የለም" ብዬ ነግሬህ ነበርኮ ! እዚህ በህግ ወህኒ - ቤቱ ፤ ያለ ህግ ካቦው ብቻ ናቸው የሚነግዱ ፤ ሌላ የሚነግድ የለም ! ያለ ህግ ለመነገድ እንዲቻል በህግ የሚነግዱውን ፤ ምክናያት መሳይ ፈጣጥሮ ፤ ከገበያ ማስወጣት የሚችል ባለስልጣን እዚህ ማን እንደሆነም ነግሬሀለሁ ! " አለ ገብረዬስ ፤ በዝቅተኛ ድምጽ ፤ ወደ ጥላሁን ጠጋ ብሎ ።

"ቦታ የሸጠልንም ካቦው ፤ ወይም . . . ወህኒ ቤቱ ነው ማለት ነው ? "

"እስ . . . . ካቦው ! " አለ ገብረዬስ ፤ ጥላሁን ረስቶ ድምጹን ከፍ አድርጎ ስለ ተናገረ ፤ ጠቋዋሚ ጣቱን በከንፈሮቹ ላይ ፊት-ለፊት አቁሞ ።

"እንዴ ! ወህኒ ቤቱስ በስረኞች ላይ እንዲነግድ በህግ መፈቀዱ . . . ይሁን እስቲ ፤ ያጥግብ እያጥግብ ምናልባት ምክናያት ሊሰጥበት ይቻል ይሆናል ፤ ነገር ግን ካቦው ፤ ከስረኞች መሀከል አንድ ሲሆን በጉዋደኞቹ ላይ ያለ ህግ ሲነግድ ፤ የመንግስት አስተዳደሪዎች እንዴት ዝም ብለው ያዩታል ? "

"ህ! አንድ ቃምጣ ከጣር ጋር ይታገል የነበረ የኔ አገር ሰው ፤ ጉራጌ ሊጠይቀው የሄደ ዘመድ 'እግዜር ይማርህ' ቢለው 'ዱቅትስኒ ማን ሆነና!' አለ የሚባለውን ጭዋታ አልሰማህም ? " አለ ገብርዬ እዬሳቀ ። "ካቦው" አለ ከዚያ ቀጠለና ። ካቦው እዬሰበሰበ የሚያጎርስ እጅ ነው እንጂ ፤ እያ ላመጠ የሚያጣጥመው አፍ ፤ የሚውጠው ጉሮሮና የሚጠግበው ሆድ፣ በየደረጃቸው አሁን ... 'ለምን ዝም ብለው ያያሉ' ያልሀቸው ናቸውኮ ! እሂ-ሂ-ሂ-ሂ፤ ወዬው ጉ ... ድ! ግድየለህም፣ አንተ ሰው ቅድም እንዳልሁህ ያስለፍልፍ ይዘሀል !" ብሎ ጥላሁንን በቆመበት ትቶት ሄደ ።

ጥላሁን ዝም ብሎ ገብረየስን ካይኑ እስኪሰወር ሲመለከት ቆየና፣ "እዎ ፤ አሁን ገባኝ !" አለ ። "በስውር የራስ ምላጭ መኪና የሚያከራዩና አገናኝዎቻቸው ፤ ሁለት ወይም ሶስት ሆነው ማህበር እዬሆኑ ደህና ቦታቸውን ገንዘብ ላላቸው የሚሸጡና እነዚህን የመሳሰሉት ሁሉ ፍጹም ባገር የሌሉ ፤ እዚህ ውስጥ የሚሰራውን የቆሸሸና የሚያስጸይፍ ስራ ለመሸፈን ፤ የመሠረት ራስ የፈጠራቸው መሆናቸው አሁን ገባኝ። ምላጭ የሚያከራየውም ፣ ቦታ የሚሸጠውም ፤ ሌላውንም በስረኞች ላይ የሚነገደውን ንግድ ሁሉ የሚነግደው ካቦው ብቻ መሆኑ አሁን ገባኝ፤ እሱም ቢሆን ለስም ብቻ ነው ! እሱም ቢሆን እዬሰበሰበ ለማይታዩት

@OLDBOOKSPDF

ለተሸሸጉት የሚያቀብል ነው ! እያላመጡ የሚያጣጥሙት ፣ የሚው ጡትና የሚጠግቡት የማይታዩት ፣ የተሸሸጉት ናቸው ! እንደ ሆድ ከሁሉ የራቀው ፣ ከሁሉ የተሸሸገው ፣ ከሁሉ የበለጠ የሚጠቀመው ነው !" አለ።

ከዚያ አይኖቹ ገብረየስን ተከትለው ሄደው እሱ በተሰወረበት እንደ ተተከሉ ፣ ያንለት ወህኒ-ቤት ከገባ ጀምሮ ያዩውና የሰማው ሁሉ ተሰሎ ታዩው ! መሰረት ወርውሮ ያስታቀፈው ፣ ሕርጅቶ ከመድቀቁ የተነሳ ፣ እፍንጫ የሚያስነጥስና አይን የሚያስለቅስ ብርድ ልብስ ፣ ገብረየስ ለራስ መላጫ ያመጣለትን የተሸራረፈ የጠርሙስ ስባሪና የዛገ ብረት ከሞረድ ጋር ፣ መሰረት እሱንና ሰፈን ለመርዳት ከመንገዱ ወጥቶ ሲቸገርና ሲጨ ነቅ ደግና ታላቅ ሆኖ የሚታይበት ምስሉ ካንድ ወገን ፣ ያስያዘውን.ገን ሀብ እጭበርብሮ ለመውሰድ 'ከመቆራረጥና ከመቁሰል የሚያድን የመ ኪና ምላጭ በምስጢር ከሚያከራዩ እስረኞች ልከራይላችሁ ፣ በሽንቱ ኢቃ አጠገብ እንዳትተኙ ደህና ቦታ ከሚሸጡ እስረኞች ልግዛላችሁ' እያለ ውሸት ለመፍጠር ሲቸገር ፣ ወራዳ ምስኪን ሆኖ የሚታይበት ምስሉ ከሌላ ወገን ባንጸሩ ቆሞ ታዩው።በዚያ ካቦው እስረኞችን እዩረገ ጠና እያንቀጠቀጠ ፣ በልዩ ልዩ ስም ሲያስገብራቸው ፣ በነሱ ፊት ኮር ቶና ትከሻውን ወደ ላይ እንጠራርቶ ቆሞ የሚታይበት ምስሉ ካንድ ወገን ! እንዲያ ከስረኞች በልዩ ልዩ ስም ያስገበረው ተሸክሞ፣በባለስልጣናት ፊት ተንበርክኮ ጫማ እዩሳመና እዩተሸቆጠቆጠ እንዲቀበሉት ሲለምን የሚታ ይበት ወራዳ ምስሉ ከሌላ ወገን ባንጻሩ ቆሞ ታየው።ታዲያ፣ይህ ሁሉና ይህን የመሳሰለው ባንድ ላይ የተሳለበት ሰፊ ሰሌዳ ባይን-ህሊናው ፊት ተዘር ግቶ ታዩውና እሱም ዝም ብሎ ሲመለከት እንደ ቆዩ ፣ ትንሽ በትንሽ ሌላው ስእል ሁሉ እዩደበዘዘ ፣ እዩደበዘዘ ሄዶ ፣ በመጨረሻ ሲጠፋ ካቦውና መሰረት እስጸያፊ ስራቸውን ሲሰሩ የሚታይባቸው እስጸያፊ ስእሎቻ ቸው ብቻ እሰሌዳው ላይ ስለቀሩ ፣ የሚታይባቸው እስጸያፊ አይኖቹም ሕሳቡም ባንድነት በነሱ ላይ አትኩረው ቆይተው እጅግ ጥልቅ የሆነ የንቀት ስሜት ተሰማውና ፣ " ብፍ . . . ! ውሾች !" አለ ፣ ፊቱን አጨ ማድዶ አይኖቹን እያርገበገበ አንገቱን ከደፋበት ሲያቀና ። "ህ!" አለ ጥላሁን ፣ ትንሽ ዝም ብሎ ቆይቶ ።

"ለመሆኑ እኒህ . . . . ገብረየስ 'እያላመጡ የሚያጣጥሙ ፣ የሚው ጡና የሚጠግቡ' ያላቸው ፣ ባጠቃላይ . . . በላተኞች ሞኞች አደሉም፣ እንዲያውም ጎበዞች ናቸው ! ለስረኞች ያዘኑ ለስረኞች ያሰቡ መስለው፣ 'ከስረኞች መሀከል ጉዳታቸውንና ጠቅላላ ችግራቸውን እዩተከታተለ' እያጣራ ፣ እንዲያ ያለው ጉዳትና ጠቅላላ ችግር እንዲወገድ ላስተዳዳ

@OLDBOOKSPDF

ሪዎች እንዲያቀርብና ፣ እስረኞችም በበኩላቸው ህግና ስነ-ስራት ተከት ለው እንዲኖሩ ለማድረግ የተሾመ ነው' ብለው ፤ እንዲህ ያለ ፣ የውሸት ልብስ አልብሰው እውነተኛ ስራው ግን ጉዋደኞቹን አሰጨንቆ በልዩ ልዩ ስም ህገ-ወጥ የሆነ ግብር እዪሰበሰበ ፣ በምስጢር ለነሱ የሚያቀብል ፣ ካቦ የሚባል ሹም ማድረግ ተራ ተንኮል አደለምኮ ! መቸም እነሱ ካቦውን ሾምነው የሚሉ ካንድ ወገን እስረኞች እንዳይጉዱ እንዲጠብቅ ፣ ለደግ ስራ ፣ ከሌላ ወገን ህግና ስነ-ስራት እንዲጠብቁ እንዲያደርግ ነው ። ነገር ግን እሱ የታዘዘውን ትቶ ፣ እምነቱን አጉድሎ ፣ እንዲጠብቅ አደራ የተሰጡትን እስረኞች ቢበድልና ህገ-ወጥ ስራ ፣ ወይም ወንጀል ቢሰራ ወዮለት ሀ ፤ ስራሱ ይባሰው ! እግዚአብሄር አይበለው እንጂ ከላይ መርማሪ መጥቶ በደሉና ወንጀሉ ቢገለጹ እንዲያውም ዞረው ፣ በዳኝነት ወንበራቸው ቁጭ ብለው ፈራጆችና ቀጪዎች የሚሆኑ እነሱ ናቸው ! ስለዚህ እንዲህ ያለው ተንኮል በውነት ተራ ተንኮል አይባልም ! ወንጀልዋን በሌላ ሰው እጅ እያሰሩ ፣ ፍሬዋን ተሸሽጎ መብላት ተራ ተንኮል ነው ? እ-አ-! አደለም ! እንዲያውም ብልሀት ነው፤ ቢሹት የማይገኝ ብልሀት፤አዳምና ሄዋን ጌታቸው ጠብቁ ያላቸውን የገነት ፍሬ ሰርቀው ከመብላታቸው በፊት ይህን ብልሀት አግኝተው ቢሆን ኖሮ፣ እስከ ዘር ምንዝራቸው ከተፈረደባቸው የሞት ፍርድ ያድናቸው ነበር!" አለ ፣ ብቻውን እንደ መሳቅ ብሎ ።

"ሊገባኝ የማይችል የካቦው ነው !" አለ ጥላሁን፣ ቀጠለና ። "እሱቴ . . . በጉዋደኞቹ ላይ እንዲህ ያለ የሚያስጸይፍ ወንጀል እዩሰራ ፣ ለበዮች አቀባይ መሆኑ ምን ሊያገኝ ነው ? በልተው ከሚተርፉቸው ትንሽ ፍርፋሪ የሚጥሉለት ቢሆንስ ፣ እንዲያ ያለው ፍርፋሪ በጉዋደኞቹ በስረኞች መሀከል እንደ ጣረ ሞት በመጠላቱ ፣ ከፉ ስም በማግኘቱና ሥራው ከላይ በሚላኩ መርማሪዎች ተመርምሮ የተገለጸ እንደሆነ ብርቱ አደጋ ሊደርስበት የሚችል በመሆኑ ፣ በዚህ ሁሉ እንጻር ሲታይ ምን ዋጋ አለው ? እንዲያው እንጃ ! ሌላ ጥቅም ይኖረው እንደሆነ እንጂ . . . . . ፍርፋሪውስ ምንም አደል ፤ ዋጋም የለው !" አለ ።

ከዚያ እሁንም ትንሽ ዝም ብሎ ፣ ግንባሩን ቁጥር ፣ ፊታ እያደረገ ሲያስብ ቆይቶ ፣ ብዙ ጊዜ ላስቸጋሪ ጥያቄ መልስ ሲገኝ እንደሚሆነው ፊቱን ፈገግ አድርጎ "አዎ ለዚህ ነው !" አለ ። "በዚህ ሁሉ እስረኛ ላይ ሹም መሆኑ ፣ ከዚህ ሁሉ እስረኛ በላይ ሆኖ ፣ ሁሉንም ከዚያ ከፍተኛ የሹመት ቦታው ዝቅዝቆ ማየቱ ፣ ቅድም ቦታየን ሲሰጠኝ እንደ ተመለከትሁት ፊቱን ለሚወዳቸው ፈገግ ፣ ለሚጠላቸው ጨፍገግ ፣ ሲያ

@OLDBOOKSPDF

ደርግ ፣ እንዲያ ፊቱ ፈገግ ያለላቸው ተደስተው ፤ ጨፍገግ ያለባቸው ፈርተው ፣ ሁሉም ሽብ-ረብ ሲሉ ማየቱ ፤ ከፍርፋሪው ይልቅ ይህ ስለማመው፣ይህን ከመጠን ያለፈ ስስ ወደደ ፣ ስለዚህ ዋጋ ነው እጁን ሌሎች ተሸሽገው ወንጀል የሚሰሩበት መሳሪያ እንዲሆን ፣ ሌሎች ተሸሽገው የወንጀል እንጀራ እንዲበሉበት ፈቅዶ የሰጣቸው !

“ መቸም አሸናፊነትን ፤ ከሁሉ የበላይ መሆንን ፣ መንፈሰ-ታላቆች፣ ደጎች ደግና ታላቅ ስራ ለመስራት ፣ መንፈሰ ወራዶች ፣ ክፉዎች እኩይ ለመስራትና ለመበቀል ፣ መንፈሳቸው ገና በበጎም ሆነ በክፉ መንገድ ያልጎለመሰ ፣ ገና ካእምሮዎቻቸው ይልቅ እንደ እንስሳት ለደመ-ነፍሳቸው የሚታዘዙ ፣ እንዲሁ ላሸናፊነት ፣ እንዲሁ ከሁሉ በላይ ለመሆንና እንደ አውራ በሬ ፣ እንደ ኮርማ መንጋውን ለማመሉ ፣ ለማተራመሱ ሲሉ ነው የሚፈልጉት ! ስለዚህ ካየው . . . ካውራ በሬዎች ከኮርማዎች አንዳንዴ መሻት ነው !” አለና ብዥታውን ከት ብሎ ከሳቀ በሁዋላ ያዬ ሰው እጁድ እንዳይበላው ቀሎ አፉን በጁ ከደነ ። “ የዚያ የመሰረት” ሲል አፉን እጁን ደያዘ ለቆ ካዘቃ በሁዋላ ። “ የመሠረት እንዲያው . . . የማይረባ ፣ ፀሙ ለቀዋት ፤ ሳጥን ሙስና የቀሸሸ ተንኮልና ወንጀል ነው ! እስኪ አሁን እዚህ ልቆይ ለመጣሁ ሰው ፤ አልፎ ሂያጅ እመስል . . ባሬ ባይሆን ነገ ሳላውቀው የማልቀረውን ነገር ፣ የካቦውን የመኪና ምላጭ ‘በምስጢር ከሚያከራዩ እስረኞች ተከራዩሁላችሁ ’ ካገው የሚያነረዩወን የምኝታ ቦታ ‘ከእስረኞች ገዛሁላችሁ ’ ብሎ ውሸቱን ይነግረኛል ! ይሽ ከተራ ተንኮል እንኳ ያነሰ ፤ ምስኪን ውሸት አያለም ! ብፍ . . . መሠረት በተራ ተንኮለኛ ደረጃ እንኩዋ ሊታይ የማይገባው ፤ ከተራ ተንኮለኛ ያነሰ ፤ ተራ ዋሾ ምስኪን ዋሾ ነው ! ” አለና መሠረትን ስለ ተጸየፈ ፊቱን ጨምዶዶ ፣ የታች ከንፈሩን ረዘም አድርጎ ፣ ቆሞበት የነበረውን ቦታ ለቅቆ ሄደ ።

ጥላሁን ያን ሌሊት ሊተኛ አልቻለም ። ምንም እንኩዋ ቦታው እግር ለመዘርጋትም ፣ እንደ ተኙ ለመገላበጥም የሚያበቃ ቢሆን ፤ በፍራሽ ስም ባስር ብር የተገዛው ድሪቶ ፣ ከመሳሳቱ የተነሳ ፣ ከስር የሰሚንቶው ወለል ቁርቁዋሬ እንኩዋንስ ሊያስተኛ ካምስት ደቂቃ በላይ አያስቀምጥም ። በዚያ ላይ እዚያ ክፍል ከፍተኛው ፣ አንድ አገር ህዝብ መሀከል ፣ የሚያንኩዋርረው ፣ በእንቅልፍ ልቡ የሚናገረውና ሌላም ልዩ ልዩ አመል ያለው ብዙ ስለነበረ ፣ ያ ሁሉ ባንድ ላይ እንቅልፍ ነስቶት አደሮ ፣ እንጋት ላይ ትንሽ ሸለብ እንዳደረገው ፣ የመነሻው ጊዜ ደርሶ እክፍሉ ውስጥ ጫጫታ በመሆኑ ገና እንቅልፍ እንደ ከበደው ተነሳ።ከዚያ የሚበዛው ሰው

@OLDBOOKSPDF

ወጥቶ ስለ ነበረ ከሁሉም ሁኔታ እንዳይቀር ቶሎ ፍራሹን ጠቅልሎ ፣ ወደ ራስጌው አድርጎ ሊወጣ ሲል ፣ ከበሩ አጠገብ ፣ የሽንቱ እቃ በነበረ በት ዙሪያ ሲፈስስ ያደረውን ሽንት የሚያጸዳውን ሰው ሲያይ ደንግጦና ለመውጣት መቸኮሉን ረስቶ ፣ እሰውየው አጠገብ ቆሞ ይመለከተው ጀመር ። የሽንቱ በርሜል ከዚያ ምን ጊዜ እንደ ወጣና ማን እንዳወጣው አላየም ።

ያ ፣ ሽንት ሲፈስስበት ያደረውን ቦታ የሚያጸዳው ሰው ልዩ ልዩ አይነትና ቀለም ካላቸው አዲስና አሮጌ ቁርጥራጭ ጨርቆች ባንድ ላይ የተደረቱ ጥብቆና ቁምጣ ለብሱዋል ። ነገር ግን ጥብቆው እጅጌና ክሳድ የሌለው ፣ ቁምጣው እስከ ግማሽ ጭኖቹ ብቻ የሚደርስ ሆነው ፣ ከላይ ክንዶቹ እስከ ትከሻዎቹና ፣ አንገቱ ፣ ደረቱ ፣ ከታች ከግማሽ ጭኖቹ ጀምሮ እግሮቹ በሙሉ ራቁታቸውን ስለ ነበሩ ፣ ከእህ ከራቁት አካላቱ እንደሚታየው ፣ የከሳቱ መጠን ለሰ ቆዳ ከለበሱ አጥንትና ጅማት በቀር ብጣሽ ስጋ ፣ ወይ ጠብታ ደም በውስጡ የቀረ አይመስልም ፤ ከዚህ የተ ነሳ እስረኞችና ሰራተኞች "መጻጉእ" የሚባል ስም አውጥተውለታል ።

መጻጉእ በባሊ ውሀ ሞልቶ አቅርቦ ፣ እዚያ ውሀ ውስጥ ኬሻ እዩ ነከረ እያወጣ ፣ በዚያ ወለሉን ያጥብና ፣ ያን ያጠበውን ክፍል በደረቅ ኬሻ ወልውሎ አድርቆ ደግሞ ያልታጠበውን ያጥባል ። ጥላሁን ስራው አድካሚ ከመሆኑም ሌላ ሰውዬው ያሰራር ልምድ ያለው የማይመስል፣ በዚያ ላይ እጅግ ደካማ መሆኑን ተመለከተና ፣

"አንተ ስታጥብ እኔ ልወልውልልህ የኔ ወንድም" አለ ፣ እመጻጉእ አጠገብ ጎንበስ ብሎ ።

"እግዜር ይስጥልኝ ፤ ከሰው ጋር የሚካፈሉት ስራ አደለም ፣ እኔ ብቻ የምሰራው ነው " አለ መጻጉእ ፣ ባንድ እፍታ ቀና ብሎ ከፈገግታ ጋር ጥላሁንን ተመለከተና ። ካካላቱ ያልከሱ ነገሮች ጥርሶቹና አይ ኖቹ ናቸው ! እንዲያውም የሌላ አካላቱ ሁሉ ከመጠን በላይ መክሳት፣ እነሱን ከመጠን በላይ አጉልቶ ስለሚያሳያቸው በጣም ያስፈራራሉ ፤

"እንዴት? ለምን ? " አለ ጥላሁን "ቅጣት ነው ፤ ሰው የረዳኝ እንደ ሆነ እንደ ገና . . . ደግሞ ከባድ ቅጣት ይጥሉብኛል ።"

" ቅጣት ? ምን አጥፍተህ ?" አለ ጥላሁን ካጎነበሰበት ቀና ሲል፣ ጥያቄው የሚገባ መሆን አለመሆኑን እንኳዋ ሳያመዛዝን ፣ እንዲሁ አፉ እንዳመጣ ።

"ዳቦየን በልቼ !" አለ መጻጉእ ፣ ጥላሁንን ቀና ብሎ ሲያይ አፉን በሰፊው ፣ እስከ ጆሮ-ግንዱ ከፍቶ እዩሳቀ ።

@OLDBOOKSPDF

"የጓዝ ዳቦሀን ?"

"የገዛ ዳቦዩን ?"

"እንዴት ? አልገባኝም !"

"እ . . . ! ነገሩ ብዙ ነው ወንድሜ ፤ እንዲህ በቀላሉ የሚገባ አደለም ! " አለና ማጃገኢ ዝም ብሎ ስራውን ሲቀጥል ሲያይ ፣ ጥላ ሁን ትንሽ ቆሞ ሲመለከተው ከቆዩ በሁዋላ ፣ ትቶት ወጥቶ አንድ ከሰው ትንሽ ገለል ያለ የሚመስል ቦታ ለባዩ እዚያ ሄዶ ተቀ መጠ ። ከክፍሉ እንደ ወጣ ያዩት ሁሉ ፣ አንዳንዶቹም ጣታቸውን ወደሱ እያ መለከቱ ፣ እስበሳቸው ሲንሾካሾኩ አይቶ ፣ ነገሩ አልገባው ስላለና ፣ በዚያም ምክናያት መንፈሱ ጸጥታ ስላጣ ነበር ከሰው ራቅ ብሎ የተ ቀመጠ ። ነገር ግን እዚያም ገለል ብሉ መቀመጡ ፣ ከቅርብም ሆነ ከሩቅ ለሚያዩት ሁሉ መነጋገሪያ ከመሆን እንዳላዳነው ሲረዳ ፣ ከዚ ያም ተነስቶ ለመሄድ ቢያስብ አደባባዩን አስረኛ ሞልቶት ስለ ነበረ፣ መሄጃ አጣና ፣ እዚያው ዝም ብሎ ተቀምጦ የሰው ሁሉ አይን እሱን ብቻ የሚከተልበትንና የሰው ሁሉ አፍ በሱ ላይ ብቻ የሚንሾካሾክ በትን ምክናያት ይፈልግ ጀመር ።

"ሊመሆኑ አዲስ ስለ ሆንሁ ይሆን ? ወይስ . . . . . ሰው ሁሉ ስለኔ የሚነጋገርበት ሌላ ምክናያት ይኖር ? ባዲስነቱ ከሆን ከዛሬ ይልቅ ትናንት አዲስ አልነበርሁ ? ታዲያ ትናንት እንዲህ እንደ ዛሬው የሚመለከተኝና እንዲህ በኔ ላይ እዩተጠቃቀሰ የሚንሾካሾክ አልነበ ረም ! ደግሞ . . . . . የሚመለከተኝ ሁሉ ፈገግ ባለ ፣ በደህና እንጂ በተኮሰተረ፣ በክፉ ፊት አደለም፣ እንዴ ! ከቶ ምን ይሆን ?" አለና የሰው ሁሉ አይን ያተኮረው ወደሱ በመሆኑ ስለ ፈራ፣ ወደ ላይ እንጋጥጦ ሰማይ ሰማዩን ይመለከት ጀመር ።

ጥላሁን እንዲያ እይኖቹን ወደ ሰማይ ሰቅሎ ተቀምጦ ሳለ መጸ ጉእ መጥቶ እግሩ አጠገብ ፣ እባሩ ላይ ተጋደመና ወደሱ እሻቅቦ መመልከቱ ስለ ተሰማው ፣ እንገቱን የሚያሳርፍበት ምክናያት በማግ ኘቱ ደስ ብሎት ፣ እሱም አይኖቹን ወደ ሰማይ ከሰቀለበት አውርዶ ፣ በመጸጉእ ላይ አሳርፎ ፣ ሁለቱም ፈገግ ብለው እዩተያዩ ሳይነጋገሩ ጥቂት ጊዜ ቆዩ ።

"ያንተና የባለቤትህ ፎቶ - ስእል በዛሬው ጋዜጣ መውጣቱን ሰማህ ?" አለ መጸጉእ ፣ ዝምታውን አቋዋርጦ ፈገግ እንዳለ ።

@OLDBOOKSPDF

“አልሰማሁም ” አለ ጥላሁን ፤ እንደ ድንጋጤ ያለ ስሜት ተሰማውና ። ብቻ ስሜቱ ከፊቱ እንዳይታወቅበት እንደገና ቀና ብሎ ሰማዩን ይመለከት ጀመር ።

“አሁን ሰው ሁሉ የናንተን ወሬ ብቻ ነው የሚያወራ ። ‘ሰው ገድለው የተመሰከረባቸውን ባልና ሚስት ለማዳን . . . . . በነፍስ-ገዳዮች ቀንበር ገብተው ታሰሩ ’ እያለ ሰወ ሁሉ ጉድ ይላል ! ” አለ መጸገት ፤ እንዲያ ፈገግ እንዳለ ጥላሁንን እያዩ ። ጥላሁን አልመለሰም ። ምንም እንኩዋ ታላቅ ትሩፋት ፤ ወይም ጀብድ ሲሰራ የሚሰማው የደስታ ሙቀት በሰራ አካላቱ ሲሰራጭ ቢሰማው ፤ ያ ስሜት እንዳይታወቅበት የተቆጣ ለመምሰል ፊቱን ኮስተር አድርጎ ፤ አይኖቹን ሰማይ በሚያዩበት እንዳሉ ፤ አርፈው እንዲቆዩ ማድረግም አቃተውና ከዚያ እንስቶ ፊት-ለፊት ካለው ተራራ በላይ አልፎ ወዲያ አድማሱን ይመለከት ጀመር ።

መጸገት ፤ ጥላሁን የሰው ሁሉ መደነቂያ መሆኑን ሲሰማ ደስ በመሰኘት ፈንታ ፤ የተቆጣበት ምክናያት አልገባው ስላለ ፤ በጉስቁልናው ምክናያት የተጸየፈውና የናቀው መስሎት ቅር አለውና እሱም ከተራራው ወዲያ አሻግሮ እየተመለከተ ትንሽ ቆም ብሎ ቆዩ ።

ከዚያ ቢጸየፈውና ቢንቀው ኖሮ ኸንት የፈሰሰበትን ወለል “እብሪሀ ልጠብ ” ብሎ እንንብሶ ይለምነው እንዳልነበር ሲታወሰው ፤ ቅርታው ከንቱ መሆኑን ተገነዘበና ፤ እንደ ገና የንግግር መክፈቻ የሚሆን ነገር ሲፈልግ ቆይቶ ፤

“ቅድም . . . . . የገዛ ዳቦዩን ስለ በላሁ ተቀጣሁ ስልህ ፤ ‘እንዴትና’ ብለህ ጠይቀኸኝ ምክናያቱን ስላልነገርሁህ . . . . ተቀየምኸኝ መሰለኝ ። መናገር ባለመፈለግ አይደለምኮ ዝም ያልሁ ፤ እበሩ ላይ ስለ ነበርን ገቢና ወጪው እንዳይሰማን ብዬ ነው ። እዚህ ሁሉም የሚያደርገው ሲያጣ ጊዜ ነው መሰለኝ . . . . . ወሬ አቀባይ ብቻ ነው ! ” አለ አይኖቹን ሩቅ ከላከበት መልሶ ጥላሁንን እያዩ ።

“የለም ፤ የገዛ ዳቦዩን ስለ በላሁ ተቀጣሁ ” ስትለኝ ተገረምሁ እንጂ አልተቀየሁሁምኮ ! ምክናያቱን ስጠይቅህ ዝም ማለትህንም . . . . ምናልባት ሲነገር የማይገባ ቢሆን ይሆናል ” አልሁ እንጂ፤ በሌላ አልተረጎምሁትም ” አለ ጥላሁንም ፤ አይኖቹን ከተራራው ወዲያ ከላከበት መልሶ አምጥቶ መጸገትን ከቅርታ ፈገግታ ጋር እየተመለከተ ።

መጸገት ከጥላሁን ግርጌ ተጋድሞ ሽቅብ እያንጋጠጠ ከሚያይበት ተነስቶ ፤ ከጎኑ ሆኖ ፊት-ለፊት በሚተያዩበት ቦታ ተቀመጠና የገዛ ዳቦውን ስለ በላ የተቀጣበትን ምክናያት መተረክ ጀመረ ።

“አጠር አጠር @OLDBOOKSPDF ጀምሬ ልንገርህ መሰለኝ ”አለ፣ ከምን እንደሚጀምር ተቸግሮ ሰማዩን ሲመለከት ትንሽ ቆይቶ ።

“ከራት ወር በፊት ካገሬ ፣ ከየጁ መጥቼ እዚህ እስር - ቤት ስገባ ያ መሰረት . . . . ሰው አይምሰልህ ፣ መጥቶ “ሀያ ብር ካልከፈልህ ከሽንት እቃው ጥግ ትተኛለህ ” ቢለኝ ‘ እሽንት ዕቃው ጥግ እተኛለሁ እንጂ ፣ ሀያ ብርማ የሌለኝን ከየት አባቴ አመጣለሁ ? ’ አልሁት ። ሀ ! ክፉ አልሁን ?”አለ መጂጉኢ ፣ የሚያስፈራሩ አይኖቹን በጥላሁን ላይ አፍጥጠ ። ጥላሁን “ክፉ አላልህም ”በማለት ራሱን ሲነቀንቅ መጂጉአ “እግዜር ይስጥልኝ ” እንዲ ማለት እሱም ራሱን ትንሽ ነቅነቅ አደረገና ቀጠለ ። “ ከዚያ ካቦውን አነጋግሬ ተመለስሁ ” ብሎ “ከንግዲህ ወዲያ ከሽንት እቃው ጥግ አስረኛ እንዳይተኛ አኪም ከልክሎዋልና ገንዘብ ከሌለህ ልብስህን አስገምት ” አለኝ ። እኔም . . . . “ልብሴንማ ወዜን አንዴት እሰጣለሁ ? ባይሆን የሀያ ብር ግምት የጉልበት ስራ ልስራ እንጂ” አልሁት ። “ ሀ ! ክፉ አልሁ ? ” ሲል መጂጉኢ ፣ ጥላሁን ራሱን ነቀነቀ ። “የጉልበት ስራ በገንዘብ መገመት እዚህ የተለመደ አይደለምና ልብስ ህን አስገምተህ መስጠት አለብህ ቢለኝ ፣ ‘ትርፍ ልብስ የለኝ ምን ለብ ሼ ? ’ አልሁት ። ሀ ! ክፉ አልሁ ? ” ሲል ይህ አባባል የመጂጉአ ‘ዘየ’ መሆኑን ጥላሁን ተረዳና ራሱን እየነቀነቀ ይስቅ ጀመር ። “ እኔ አላ ውቅልህም ፣ እስክ ሁለት ቀን ድረስ የምትሲበሰው ፈልገህ ፣ ልብስህን አስገምተህ ያልሰጠህ እንደ ሆን አሳር ያገኝሀል አለኝ ። እኔ ምን አል ሁት መሰለህ ! ‘ምንው የሰው ችግር አይሰማህ ፣ ከሰው የተፈጠርህ ሰው አደለህም ወይ ’ አልሁት ። ሀ ! ክፉ አልሁ ?”

“ጥሩ አድርገህ ነግረኸዋል ።” አለ ጥላሁን ፣ እየሳቀ ።

“ታዲያ እየውልህ . . . . ገና ውሀ ያልነካው ፣ ሰላሳ ብር ቢሸጥ እንሰው እንጂ በዛበት የማይባለውን አዲስ ጋቢየን ባስር ብር ፣ እጀ ጠባቤንና ሱሪየን ከማለፊያ ካኪ ኮቴ ጋር የሙት ልብስ ይመስል በሁ ለት ብር ካምሳ ሳንቲ ፣ ባጠቃላይ አስራ ሁለት ብር ካምሳ ሳንቲ ራሱ ገምቶ ወስዶ ፣ በዚያ ላይ ለቀን ምሳና ራት እዚህ ከሚሰጡኝ ሁለት ዳቦ አንዳዱን ባምስት ሳንቲ ሂሳብ ፣ ያምስቱን ወር ሰባት ብር ካምሳ ሳንቲ ጨምሮ ፣ ሀያ ብር አሙዋልቶ ስለ ወሰደ ፣ ይኸው . . . . አራት ወር ሙሉ ፣ አንዳንድ እጸድቅ ያለ ፍርፋሪ ካላስተረፈልኝ በቀን ያችን አንድ ዳቦ እየለከፍሁ ነው ያለሁ ። እየው ይህን ድሪቶም ሰው ጸድ ቃብኝ ነው እንጂ . . . . ያለዚያ ምን ይውጠኝ እንደ ነበር . . . . እንጃ ! ታዲያ . . . . ወደ ሰረ - ነገራችን እንመለስና ፣ ለሰጪም ከሚ

@OLDBOOKSPDF

መቸው የማይመቸው ግን በሆጊበዓ ፣ የፍርፋሪውም እንዲሀ እንደኔ ፈላጊው በዝቶ እንደ ልብ ስለማይገኝ ራብ ጸንቶብኝ ፣ ከራብ የማይ መረጥ ነገር የለምና የሆነው ይሁን ብዬ ፣ ሳምንት ሙሉ ለካቦው የቢታ ቀጋ እዬታሰበ ይሄድ የነበረውን ዳቦየን ጨምሬ ፣ ሁሉቱንም ዳቦ ስበላ ስለ ሰነበትሁ ፣ ሳምንት ሙሉ ያው እንዳዬኸኝ ጥግት ጥግት ሽንት ሲፈስበት ያደረውን ቦታ እያጠብሁ እንድወለውል ተቀጣሁ !" አለ መጽጉእ ፣ የተረከው ታሪክ ዶስ እንደሚያሰኝ ሁሉ ለመሳቅ አፉን እስከ ግራ - ቀኝ ጆሮ - ግንዶቹ አሳቅቆ ። ጥላሁን ግን በጣም አዘኑ እንዲያውም ከማዘን አልፎ መንፈሱ ታወከና ሳያስበው ተነስቶ ወዲያ ሄዶ ፣ ወዲሀ ተመልሶ ፣ እንደ ገና ተቀመጠ ። ከዚያ እንደ ገና ተነ ስቶ የሚሄድበትን ሳያውቅ መጺጉእን ባለበት ትቶ መንገድ ሲጀምር ፣

"አንተ ስራህን ሳትጨርስ ፣ ወዝፈህ ነው እዚህ ተቀምጠህ . . . የምትጫወት ? " አለ መሰረት ፣ ወደ መጺጉእ ሲመጣ ቁጣው በፊቱ እንደ እሳት ሲነድ እዬታዬ ። መጺጉእ ከጥላሁን ጋር ተቀምጦ ሲያ ወራ ፣ መሰረት እንደ ክፉ ሰረዎች ሁሉ የሚያወራው ስለሱ ክፉ ስራ መሆኑን አምኖ ነው ያን ያክል ተቆጥቶ የመጣ ።

"እረ ጨርሼ ነው የመጣሁ" አለ መጺጉእ ።

"ባሲው ፣ ሰሀኑና ወለሉን ያጠብህበትም ፣ የወለወልህበትም ኬሻዎች በቦታቸው እምኝታ ክፍል ነው ማለት ነው ? " አለ መሰ ረት ፣ ፊቱን ጥዋ ኮሶ እንደ ጠጣ አጨማድዶ ። እውነትም መጺጉእ ጥላሁን አገኘሁት "ልርዳሀ "ሲለው ለጠዬቀው እንኩዋ መልስ ሳይ ሰጥ በመሄዱ የተቀዬመ መስሎት ፣ ለማንጋገር ብቻሉ ፣ መሰረት የቆ ጠራቸውን እቃዎች እምኝታ ክፍል ትቶዋቸው ሄዶ ኖሮዋል ። ከዚያ የመሰረትን ቁጣ ሲያይ ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ምኝታ ክፍል መን ገድ ሲጀምር መሰረት ደርሶ ፣ ከሁዋላው ማጅራቱን ይዞ ቢወረውረው ሄዶ በራሱ ቆመ ። ያን እንደ ሰባራ ሸክላ በብርቱ ጥንቃቄ ካልያዙት ተንኮታኩቶ ይረግፍ የሚመስል ደካማ ፍጥረት እንዲያ አድርጎ ወር ውሮ ለመጣል ፣ እንደ መሰረትና እንደሱ ቢጤዎች ሰሜት የለሽ ፣ ፍጹም በድን የሆነ ልብ ያለው መሆን ያስፈልጋል ! ጥላሁን መጺጉእ ተወርውሮ የወደቀበትን አሆሁዋን ሲመለከት ፣ የሱ ፣ የራሱ አጥንት በውስጡ ተንኮታክቶ የረገፈ መስሎ ተሰምቶት አመመውና ፣ "እ . . . !" አለ አይኖቹን እመጺጉእ ላይ እንደ ተከለ ጎንበስ ብሎ።መጺጉእ ግን በራሱ ከቆመ በሁዋላ በጀርባው ተገልብጦ ፣ ከዚያ እንደ ገና ተነስቶ እዬተወተረተረ ወደ ምኝታ ክፍል ሲገባ ፣ መሰረት ተከትሎት ገባ ።

@OLDBOOKSPDF

ጥላሁን መጸጉሕና መሰረት ተከታትለው ወደ ምኝታ ክፍል መግባታቸውን ሲያይ ፣ መሰረት ያን ደካማ እንደ ገና ይደበድበው ይሆናል ብሎ እሱም ተከትሎዋቸው ገባ ። አልተሳሳተም ! መሰረት መጸጉሕን የንግባል ጥሎ ፣ በሆዱ ላይ ተቀምጦ ፊቱን በጥፊ ሲጠፈጥፈውና ትከሻውንም ፣ ደረቱንም በቡጢ ሲነርተው እክፍሉ ውስጥ የነበሩ ሰዎች ከብበው ፣ ዝም ብለው ይመለከቱ ነበር ። ጥላሁን እንደ ገባ በቀጥታ ሄዶ ፣ መሰረትን ከሁዋላው ሁለት ክንዶቹን ከብብቱ ስር ይዞ ፣ ወደ ላይ ሲያንጠለጥለው ፣ እግሮቹ እንደ ተሰቀለ ሰው አዬር ላይ ይወናጨፉ ፣ ይወራጩ ጀመር ። ከዚያ እዚያው ፣ አዬር ላይ እንዳለ ፊቱን ወደሱ እንዲዞር ፣ እንደ እንዝርት አሽወርውሮ ወደ ላይ አጉኖ ከዚያ ሲመለስ ቀብበና ፣ እፊት በፊቱ አመቻችቶ አቁሞ ፣ አፍ . . . . . ንሜውን በጡጫ ሲነጠርቀው ፣ ወዲያ ፣ መጸጉሕን አልፎ ሄዶ ተዘረጋ ! ያ ሲበቃው ነው ፣ የለም ! እንደፌ ያ ከመዘርጋቱ ተከታትሎ ሄዶ እንደገና ሁለት ክንዶቹን ከብብቱ ስር ይዞ አንሳና ፣ እንደ መበታጥት እፊቱ አቁሞ አዬና ፣ አሁንም በጡጫ ካይን ግርጌ ፣ አጉንጩ ላይ መእቱን ሲያወርድበት ፣ ቢያንስ ቢያንስ ከሶስት ሜትር የማያንስ ርቀት ተወርውሮ ወደቀ ። ካፍንጫው የሚወርደው ደም ብዛቱ በሰውነቱ ውስጥ አንድ ጠብታ ተርፎ የቀረ አይመስልም ነበር ! ያን ጊዜ ጥላሁንን ላዬው ፣ ፊቱ ማስፈራራቱ እንኩዋንስ ሌሎች እሱም የገዛ ፊቱን የሚያየው ቢሆን የሱ ፊት ባል መሰለው ! በፈራው ነበር ! እዚያ የነበረው እስረኛ ሁሉ ያን ጉድ ሲያይ ፣ ሁሉም ጭጭ ፣ ሁሉም ዝም ስላለ ፣ ነፍስ ያለው ፣ የሚተነፍስ አይመስልም ነበር ! ጥላሁን ከምኝታ ክፍል ወጥቶ ከመጸጉሕ ጋር ተቀምጠውበት ወደ ነበረው ቦታ ሄዶ ብቻውን ቆመ ። ወዲያው ካቦው ሰምቶ መጥቶ ፣ መሰረትን ሰዎች አንስተው ወዳስቀመጡበት ሄዶ ካዬና ፣ የሆነውን ሁሉ እዚያ ከነበሩት እዬጠዬቀ ከተረዳ በሁዋላ ፣ በርከት ያሉ እስረኞች አስከትሎ ጥላሁን ወደ ቆመበት ሄደ ።

"እንዴት ነው አንተ . . . . ገና ትናንት መጥተህ ዛሬ ሰው ፣ የኔን ረዳት እንዲህ አድርገህ የደበደብህ ?" አለ ።

"ከኔ ጋር የሚነጋገረውን ሰው ፣ 'ለምን ከሱ ጋር ትነጋገርህ' ብሎ ስለ ደበደበው ጥቃቱ የኔ ጭምር ሆኖ ተሰማኝ ! ደግሞስ . . . . ያ ሰው ምን የሚመታ ሰውነት አለውና ፣ ከሰውነቱ የሚበልጠውን ፣ ብትር የሚችለውን ክፍል ተቀምቶ ፣ ምን ሰውነት ተርፎት ይመታል ! እንዲያ ያለ ሰው ሲመታ የማያምመው በድን ብቻ ፣ ሬሳ ብቻ ነው !" አለ ጥላሁን ፣ እዚያ ያለውን ሬሳ ሁሉ ባይኑ እዞሮ ገርፎ ፊቅ በቁጣ እንደ ጋለ ።

@OLDBOOKSPDF

"እኮ ታዲያ . . . . . ያ ፡ ተመቻ የምትለው ሰው ርዳኝ አለህ ?" አለ ከበው ፤ ጥላሁን በሱ ላይ የሰነዘረውን ወቀሳ እንዳልሰማ ወደ ጎን ትቶ ።

"ኧረ እኔ አልወጣኝም ፤ እንኳንስ ርዳኝ ልለው . . . አንድ ቃል ተናግሬ እንደ ሆነ እስቲ እዚህ ካለው ሁሉ ማንም ይመስክርብኝ ! እንዲያው እሱ . . . ጉልበቱን ሊያሳይ ፈልጎ እንደሁ እንጃ ! " አለ መጸጉሕ ፤ መሰረት በሱ ምክናያት በመመታቱ ፤ የሁዋላውን በቀል ስለ ፈራ ፤ ጥላሁን በደለኛ አስመስሎ ማሳዬቱ ከፈራው በቀል የሚያድነው መስሎት ።

"በሉ ያዙት " አለና ከበው ፤ የታዘዙት እስረኞች ጥላሁን የወገሸ እንደሆን ብለው እዩፈሩ ከብበው ሲይዙ ፤ እሱ ስለ ቅጣቱ ካስተዳዳሪዎች ጋር ለመነጋገር ሄደ ። ከዚያ ሲመለስ ጥላሁን በግረ - ሙቅ ታስሮ ሳስር ቀን እዋናው ወህኒ ፤ አለም በቃኝ እንዲገባ መወሰኑን እስረኛው ሁሉ በተሰበሰበበት አስታወቀ ። ከዚያ እግር ብረት መጥቶ ፤ የሰረኛው እግሮች እዚያ ገብተው ፤ ብረቱ እንዲጠብቅ በግሮቹ ላይ እንዳለ በመዶሻ እንዲቀጠቀጥ ተደረገ ። ብዙ ጊዜ መዶሻው ሙሉ በሙሉም ባይ ሆን እያሻረፈ እግር ሊመታ ስለሚችል ፤ የዚያን ስቃይ ውጠው ፤ ሳይ ጮሁ ጥርሳቸውን ነክሰው የሚያሳልፉት እጅግ ጥቂት ናቸው ። ጥላሁን እግረ - ሙቁ በመዶሻ እዩተቀጠቀጠ ከመጠን አልፎ ሲጠብቅበት፣ ብዙ ጊዜም እግሩ ሊመታ ፤ የደም ስሮቹ እግንባሩ ላይ ግትርትር ከማለታቸውና አይኖቹ ከመደፍረሳቸው በቀር ፤ ሌላ የስቃይ ምልክት አልታዬበትም ።

@OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ፴፰

# የጥላሁን ከፍተኛ ባለስልጣን ዘመድ

ጥላሁን በግር ብረት ታስሮ አለም በቃኝ መሀኒ በገባ ባራተኛው ቀን ፣ ወደ እረፋዱ ላይ ፣ አንድ ፖሊስ ሁለት የህግ እስረኞች አስከትሎ መጥቶ ፣ እስረኞቹ የያዙዋቸውን ሁለት ድጅኖዎችና ሁለት ጠፍሮች አንድ ገላጣ ቦታ ላይ አስቀምጠው ፣ እንደ ገና ሄደው እሳትና እንጨት አመጡና እዚያ ገላጣ ቦታ ላይ እሳቱን ማንደድ ጀመሩ ። ከዚያ ያ እሳት ደህና ሆኖ መንደድ ሲጀምር ፣ ፖሊሱ አንድ ብጣሽ ወረቀት ከኪሱ አውጥቶ ፣ አይኖቹን ጭንቁር አድርጎ እዚያ ብጣሽ ወረቀት ላይ የተጻፈውን እየመላለሰ አንብቦ ካጠና በሁዋላ ፣

"እስረኛ ጥላሁን ፈይሳ" ብሎ ተጣራ ፣ ድምጹን ከፍ አድርጎ ።

"አቤት" አለ ጥላሁን ፣ በግር ብረት ተጨርንቀው ያበጡ እግሮቹን ቀና አድርጎ ፣ ባንድ ጉልጥምት ላይ ለቅሎ ከተጋደመበት ።

"አ ! ያውላችሁ እዚያ ፤ ሂዱ አምጡት !" አለ ፖሊሱ ፣ ጥላሁን ወዳለበት በጁ እያመለከተ ።

"ተነሳ ወንድም ! ወደዚያ ፣ ወደሳቱ ቀረብ በል ። አቤ . . . ት ! እግሩ እንዴት አብጦዋል እባክህ !" አለ ከስረኞች አንዱ ፣ ጥላሁን ወዳለበት ሄዶ እግሮቹን ሲያይ እብጠታቸው አስደንግጦት ።

"ለምን ? እሳቱ ዘንድ ምን ላረግ ነው የምሄድ ?" አለ ጥላሁን ፣ እሳት እንድደው ፣ ድጅኖና ጠፍር አቅርበው ፣ ወደዚያ ሊወስዱት የተሰለፉበት ምክናያት ፣ ደግሞ ከግር ብረቱ በባሰ ሲቃይ ለማሰቃየት መስሎት መስጋቱ ከሬቱ እየታዩ ፤

"አይዞህ ምንም አደል ! 'ቶሎ ጠብላችሁ ለቁርስ አድርሱት' ስለ ተባልን ብቻ ነው !" አለ ሁለተኛው እስረኛ እየሳቀ ።

"እንዴት !" ብሎ ጥላሁን ከተጋደመበት ቀና ሲል ፣ እስረኞችም ፖሊሱም ይስቁ ጀመር ።

"እውነት ለቁርስ የምንጠብስህ መስሎህ ነው . . . እንዲህ ደንግጠህ የተነሳህ ? አይዞህ ልንፈታህ ነው !" አለ ፣ የጥላሁንን ያበጠ

@OLDBOOKSPDF

አገሮች አይቶ የተሰቃየበትን እስረኛ ፣ ጥላሁን ፣ "ለቁርስ ልትጠበስ ነው" ሲሉት ደንግጦ ብሎ በመነሳቱ ከጉዋደኛውና ከፖሊሱ ጋር ሲስቅ ቆይቶ ።

"መችም . . . ቁርስ መሆኑ ቀልድ ቢሆን ፣ መጠበሱ ሲሆን የማይችል ነገር አይደለም ! ሰውን እንዲህ በብረት ጨርንቆ ለማሰቃየት ይህን ያክል ደንዳና ልብ በሰው ውስጥ የሚኖር ከሆነ ፣ በሳት ለመጥበስ በተጨማሪ የሚያስፈልገው የልብ ደንዳንነት ምን ያክል ብዙ ይሆናል ! ብዙ አይሆንም ኮ !" አለ ጥላሁን ፣ የሰዎቹን አይን ባይኑ ከመለን በላይ ወዳበጡ እግሮቹ እየመራ ።

"ወዩው ጉ . . . ድ ! ልቅሶታ ነው በልህ ! ወዲያውም እንዲህ ሞቶ ያደረገልህን አምላክህን አመስግን ! አንተ ሹም ዘመድ በፍርድ ሚኒስቴር ውስጥ በላልህ የተመሰነበዘ አስር ቀን ሳይሞላ ይኸው ዛሬ ቀኑ ቀልቃይ እንኳ ፣ እንደምታ ቅልቅ ሹም የሆነ ወገን የሌለውማ የተመሰነባቸውን ጊዜ ዕለት ፣ እራቅ እግሩ ሳይደቅ ቀልቶ ነው እያመጡ !" አለ እስረኛው ።

ጥላሁን "በፍርድ ሚኒስቴር ውስጥ ያለ ቅልቅ ዘመድህ አስፈታህ" ሲሉት ፣ ባጭር ጊዜ እሳቡን ወደ ፍርድ ሚኒስቴር ልኮ ፣ እዚያ ምን ሹም ዘመድ እንዳለው አስፈልጎ ሲያጣ ፣ እንግዱን እንደ ደፋ ዝም ብሎ ቆይቶ ፣ እስረኞቹ ወደሳቱ ለመውሰድ ትጋግዘው ሲያነሱት በግራና በቀኝ ሲይዙት ፣

"ለመሆኑ . . . ለመፈታት ከሆነ ወደሳቱ መሄድ ለምን አስፈለገ ?" አለ ፣ አሁንም በመጠርጠር ።

"ይህ እግርህን ሰርስሮ የገባው እግርብረት በሳት ካልሞቀ አይላም ። አሁን እዚያ ተቀምጠህ እግርብረቱ በሳት ከሞቀ በሁዋላ ፣ በኒያ በተጠምጣሚው ጫፍና ጫፍ ባሉት ቀዳዳዎች ፣ ወይም ቀለበቶች ይህን ጠፍር እያገባን በኒያ ድጅናዎች ጠምጥመን ከሁለት ወገን ስንስበው ፣ ምን ልበልህ ! ብረትነቱን ትቶ እንደ ሀር ገመድ ነው ወለ . . . ል የሚል !" ሲል እስረኛው ፣ "ወለ . . . ልን" ልክ እንደ ሀሩ ገመድ አስረዝሞ ፣ ጥላሁን ምንም ቢሰቃይ "ጥርስ ባእድ ነው !" እንደሚሉት ሳቀ ። ከሆያ እስረኞችና ፖሊሱ ህዝቡ ስለሱና ስለ ሶፊያ የሚያወራውን እያጫወቱት ከሳቱ ዳር ተቀምጦ እግርብረቱን ሲያሞቁ ከቆዩ በሁዋላ ፣ እስረኛው እንዳለው በግርብረቱ ጫፍና ጫፍ ጠፍር እያገቡ ፣ በድጅናዎች ጠምጥመው ፣ ሁለቱ እስረኞች ከሁለት ወገን ሲስቡት "ብረትነቱን ትቶ ልክ እንደ ሀር ገመድ ወለ . . . ል" አለ !

@OLDBOOKSPDF

“በል እንግዲህ ተነስ እንሂድ፤ በመድህ አስተዳዳሪው ጽሕፈት
ቤት ይጠብቅሀል” አለ ፖሊሱ፤ እግርብረቱ ከጥላሁን እግሮች ከወ
ለቀለት በሁዋላ። ከዚያ ጥላሁን ቃሊቲው የሰነበቱ እግሮቹ ከመጠን
በላይ አብጠው፤ ራሱን ችሎ መሄድ ስላቃተው፤ ሁለቱ እስረኞች በቀ
ኝና በግራ ደግፈው እየረዱት፤ ፖሊሱ እየመራ ወደእስረኞች አስተዳ
ዳሪ ጽሕፈት ቤት ሄዱ። እዚያ እንደ ደረሱ፤ ጥላሁን ሲገባ አስተዳዳ
ሪው ጽሕፈት ቤታቸውን ትተው ወጡ። በንግስ መቀመጫው ወንበር
ላይ ካለባበሳቸው ትልቅ ሹም የሚመስሉ ሰው ጀርባቸውን ለበሩ ሰጥ
ተው ተቀምጠዋል። ጥላሁን እንደ ገባ፤ አስተዳዳሪው ወጥተው በሩ
ሲዘጋ፤ ጀርባቸውን ለመግቢያው ሰጥተው የተቀመጡት ሰው ተነስተው
ከጥላሁን ፊት ለፊት ቆሙ። “ኢቃቡ-ወንጀል” የሚባል ስም የተሰጣ
ቸው ኢቃቡ-ሀገ ናቸው።

ኢቃቡ-ወንጀሉ፤ በችሎታም ሆነ በታማኝነት ከሌሎች ኢቃብያነ-
ሀግ ሁሉ ተመርጠው፤ የቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሬሳ ገዳዮች ከሚገባ
ቸው የሞት ቅጣት እንዳያመልጡ ያገር ግዛት ሚኒስትሩ፤ የፍርድ
ሚኒስትሩና ከዚያም የቅርብ አለቃቸው፤ የዋናው ኢቃቤ-ሀግ ጥብቅ አደራ
ስለ ተጣለባቸው፤ ለተጣለባቸው አደራ ብቁ ሆኖ ለመገኘት እጅግ ጥረው
ነበር። ለዚያ አደራ የሚበቁ መሆናቸውን በስራቸው ውጤት አስመስ
ክረው የከፍተኛዎች ባለስልጣኖች ያይን ምስክርነት የሚያሰጠውን ዋጋ
ለማግኘት የቀን እረፍት ይሁን የሌት እንቅልፍ ሳያምራቸው፤ ከሁ
ለት አመት በላይ የፖሊስ ጣቢያ ምርመራና የዝቅተኛ ፍርድ ቤቶች
ክርክር የተጓደለበትን የወረቀት ክምር እየናዱ፤ እየዘረዘሩ አንድ ባንድ
አጥንተው፤ ከዚያ ለክርክራቸው የሚረዳቸውን እየመረጡ ከሀግና ከስነ-
ስራት ጋር አዛምደው፤ በዚያ መሰረት “ለቀኛዝማች ዳኛ ከጥላሁን ፊይ
ሳና ከእጸገነት አሸብር በቀር ሌላ ገዳይ እንደሌላቸው በማያጠራጥር
ሁኔታ ፍርድ ቤቱንም፤ ተመልካቹንም የሚያሳምን የከሰ መመስረቻ
አሰናዳሁ” ብለው በፍጹም ልብ አምነው ነበር። ይልቁንም ከሳቸውን
. . . እንደሳቸው አስተያየት . . . በማያንቃንቁ፤ ልዩ ልዩ ማስረጃ
ዎችና ምስክሮች አስደግፈው ተመልካች በሞላበት ለፍርድ ቤት ካቀ
ረቡ በሁዋላ፤ አቶ ጥላሁን ፈይሳና ወይዘሮ እጸገነት አሸብር ያላንዳች
ተቃውሞ ያቀረቡባቸውን የወንጀል ክስ ለሳሙኤና የጠዩቁትን የሞት
ቅጣት ስለ ተቀበሉ፤ ከሰቃይ ለማረፍ ያደረጉትን በሳቸው ብርቱ ክር
ክር እንደ መሸነፍ ቆጥረውት ለልባቸው የተሰማው ደስታ ቅጥ-መጠ
ኑን ያጣ ነበር። ነገር ግን ያ ሁሉ ድካም ከንቱ ሆኖ ቀረ! ከዚያ ሁሉ
ድካም በሁዋላ በሰሩት ግሩም ስራ ባላደራዎቻቸው ሚኒስትሮች ደስ

@OLDBOOKSPDF

በሉዋቸው ደስ እንደሚያሰኙዋቸው የነበራቸው ብሩህ ተስፋና ፥ ያ ብሩህ ተስፋ ለልባቸው የሰጠው ደስታ ፥ ያ ሁሉ ፥ ዳኛው ጥላሁን ፈይሳና ምሹ ሶፊያ ሙሉት የቀኛዝማች ዳኘ ገዳዮች መሆናቸውን ሲያበሥሩ ፥ ባንድ ላይ ተንኮታኩቶ ወድቆ ፥ እንዳልነበረ ሆኖ ፥ ኢትዮጵያውያን ጀሉ ባዶ እጃቸውን ቀሩ ! እኒያ ጥላሁንና ሶፊያ የሚባሉ ከተዎች መኖር ከጠሉ ፥ ሞት ከፈለጉ ፥ ሌላ የሚሞቱበት መንገድ ፈልገው እን ሰይሞቱ ፥ የሳቸውን ድካም ከንቱ አስቀሩባቸው !

እንግዲህ ኢትዮጵያውያንጀሉ እንደ ገና ፥ አንድ ብለው ባዲስ ወንጀለኞች ላይ አዲስ ክስ ለመመስረት ፥ አዲስ እቅድ ማቀድና ፥ በዚያ እቅድ መሰረት እንደ ገና አንድ ብለው አዲስ ጥናት ማጥናት ሊኖርባቸው ነው ! ነገር ግን እንዲያ ያለውን አዲስ ጥናት ከምን ይጀምሩ ? ምን መነሻ አላቸው ? መቸም አዲሶቹ ወንጀለኞች ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሬሰን መግደላቸውን አምነው ስለ ተነሱ ፥ ገዳዮች መሆናቸውን ለመርታት ምስክርችና ሌሎች ማስረጃዎች ከመፈለግ ድካም ድነዋል ። ብቻ አይነተኛው ነገር ፥ ካገር ግዛት ሚኒስትሩም ሆነ ከፍርድ ሚኒስትሩና ከየናው ኢትዮጵያ የተጣለባቸው ጥብቅ አደራ ፥ የቀኛዝማች ዳኘ ገዳዮች ከሚገባቸው የሞት ቅጣት እንዳያመልጡ ስለሆነ ፥ ጥላሁንና ሶፊያ ገዳዮች መሆናቸውን ማመናቸው ብቻ በከፍተኛ ባለስልጣኖች አካባቢ የተፈለገውን የሞት ቅጣት የሚያሰከትልባቸው ለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ነው ።

ጥላሁን የቀኛዝማች ዳኘ ገዳዮች እሱና ምሽቱ መሆናቸውን ለፍርድ ቤት ሲገልጽ ፥ በየኪ ህዝብ ላይ ለረዥም ጊዜ እጅግ ከፉ በደልና ወንጀል ሲሰሩ እንደ ኖሩ ፥ በሱና በምሽቱ ላይም ስሊሰሩ ፥ እሱና ምሽቱ መግደላቸውን ተናገረ እንጂ ፥ ከዚያ ቀጥሎ ከርክሩን በምን አቅጣጫ ለመምራት እንዳሰበ ምንም ፍንጭ አላሳዩ ። ምናልባት አስተግሬ የነበረው ጥላሁንም ፥ እሱም በዳኛ በፍርድ ቤት ፊት ቆመው ፥ ቀኛዝማች ዳኘ ለረዥም ጊዜ ያለፍርድ ፥ ነፍስ ሲያጠፉና ንብረት ሲዘርፉ የኖሩ ወንጀለኛ መሆናቸውን ለማስረዳት በሞከሩት መሰረት ፥ "እንዲያ ያሉትን ለረዥም ጊዜ ወንጀል ሲሰሩ የኖሩ ወንጀለኛ መግደል አያስገድልም" ብሎ ሊሙዋገት ይሆን ? ወይስ . . . ሚስቱ ፥ "ባሌን አቤታቸው አስረው አስቀምጠው ሌሊት ጨለማ ለብሰው አቤቱ ድረስ ቢመጡብኝ ፈርቼ ፥ ተኩሼ አቆሰልሁዋቸው" እንዳለችና ዶይሀር እጸገንት ፥ "ቀኛዝማች ዳኘ ጥላሁንን አስረው ባስቀመጡበት ሌሊት ገብተው ሊገድሉት ፥ አስቀድመው እሳቸው ከተኮሱበት በሁ

@OLDBOOKSPDF

ዋላ እሱ ተወርውሮ ሲይዛቸው እዩሁ” ብለው በመሰከሩት መሰረት ፣ “ባልሞት - ባይ ተጋዳይነት” ሲመጥነት ይሆን ? ይህ ሁሉ የሚያስ ሄድ ነው ! ብዙ የሰውን አሳብ ፣ በዝርዝር እንኩዋ ባይሆን ፣ ከርከሩን ሲመራበት ያሰበውን ጠቅላላ አቅጣጫ ካላወቁ ፣ ከላቸውን ለመመስረት የሚያስፈልገውን ጥናት ለማድረግ እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል ። ስለዚህ ተግባራቸው በሚፈቅድላቸው መጠን ለመርዳት የሚፈልጉ መስለው በመታየት ፣ የጥላሁንን አሳብ የሚያገኙበትን መንገድ ሲፈልጉ ሰንብ ተው ፣ በመጨረሻ ፣ በግርብረት ታስሮ አለም በቃኝ ወህኒ መግባቱን የሰሙ እለት ወዳሰቡት ግብ የሚያደርስ መንገድ ያገኙ መሰላቸውና ቶሎ ወህኒ ቤት አስተዳዳሪውን ለማነጋገር ሄዱ ።

አቃቤ-ወንጀሉና የወህኒ ቤት አስተዳዳሪው ተነጋግረው ከተስማሙ በሁዋላ ፣ ጥላሁን ተፈትቶ ወዳስተዳዳሪው ጽሕፈት ቤት ሄዶ ካቃቤ-ወን ጀሉ ጋር ብቻ ለብቻ ሲገናኙ ፣ ዘለግ ባለ ጊዜ ሳይነጋገሩ ዝም ብለው እንደ ቆሙ ሲተያዩ ቆዩ ።

“እንደምን ነህ ጥላሁን ፣ እንግዳዬም ? ባንተ ከተገናኘን ትንሽ ቢሰነብትም ፣ ለኔ . . . በቀደም ፍርድ ቤቶ ማንነትህን ስትገልጽ በሩቁ ከማየቱ በቀር ፣ ነገ ካምስት አመት በፊት ከተለያዩን ፣ ዛሬ መገና ኘታችን ነው” አሉ አቃቤ-ወንጀሉ ፣ ከዚያ ረዥም ዝምታ በሁዋላ እጃቸውን ዘርግተው ።

“እንዴት ? ምን ማለት ነው ? ” አለ ጥላሁን ከቆመበት ሳይንቃ ነቅ ።

“ጌቴ ከጠቅላይ ግዛት ከተመለስሁ ፣ በዚህ ጉዳይ እሬትህ እዩቆ ምሁ ስመጥነት ስታየኝ ለንብተሀል ፤ አንተን ግን . . . ቀረብ ብዬ ካለ ማየቴም ሌላ ፣ የራስህ ነጭ ጠጉር ፣ የፊትህ ጠባሳና ይህ ያሳደግኸው ጢም ከጥቁር ያይን መነጽር ጋር ፍጹም ሌላ ሰው አስመስለውህ ፣ በቀደም መነጽርህን አንስተህ አንተ መሆንህን እስክትገልጽ ድረስ አላወቅሁህም ነበር ። መቸም አብሬህ ብቆይና ጠጋ ብዬ ባይህ ፣ ይህም ሁሉ ሆኖ ሳላውቅህ እንደማልቀር የታወቀ ነው ፤ ለጊዜው ግን . . አንተ መሆንህን እንኩዋንስ ላውቅ አልጠረጠርሁም ። ለመሆኑ ምን እንዲህ አደረገህ ? ” አሉ አቃቤ- ወንጀሉ ፣ ለመሳሳምም ለጅ ሰላም ታም ያቀረቡትን ግብዣ ጥላሁን ለ መቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑን ሲያዩ እጃቸውን ከዘረጉበት ሰብስበው ።

“እምዋኝ ነበር ፤ ለመሆኑ ምን ልታደርግ መጣህ !” አለ ጥላ ሁን ፣ ግንባሩን ኮስተር አድርጎ ።

@OLDBOOKSPDF

"እስቲ ተቀምጠሽ እንጫወት" ብለው ኢዮቤ - ወንጀሉ ሁለቱም ውን ወንበር ለጥላሁን አመልክተው ፤ እሱ ሲቀመጥ እሳቸውም ተቀ መጡና ፤ "በገርብረት ታስረህ አለም በቃኝ ወህኒ መግባትህን ሰምቼ . . . መጣሁ ። ምንም አንተ የሰራኸው ደህና ባይሆን ፤ ክፉ ስራ ቢሆን ፤ የቀጠር እስረኛ ስለሆንህና ፤ የቀጠር እስረኞች ያቃቤ - ህግ እስረኞች ስለሆኑ ፤ ከኛ ሳይማከሩ ፤ ጣንት ያደረጉትን ሊያደርጉ አይገባቸውም ነበር ። እና . . . ጣንት ላይ እንዲህ ያለ ክፉ አድራጎት መደረጉን ዛሬ ጥዋት ሰስማ ወዲያው መጣሁ" አሉ ፤ አይኖቻቸውን ከጥላሁን ራስ በላይ አሳልፈው እግራው ላይ ተክለው ።

"ኢ . . . ! እግዚአብሄር ይስጥልኝ ፤ ዋጋውስ . . . ምንድነው ?" አለ ጥላሁን ፤ ግንባሩ እንደ ተቋጠረ ።

"ዋጋ የሚከፈልበት አደለም ፤ በሙሉ ሳይሆን በከፊል ያለፈ እዳ ለመክፈል የተደረገ አገልግሎት ነው ።"

"ያለፈ እዳ ? ምን ያለፈ እዳ ?"

"ያንጊዜ . . . በንጋዴ ካሚዮን ካዲስ አበባ ስትወጣ ብዙ ሰዎች ቀጥሬ ልገድልህ መጥቼ ፤ ድንገት ሽጉጤ ከጄ ሲወድቅ አንስተህ ፤ እኔንም ምርኮኛህ አድርገህ አዲስ አለም ድረስ ወስደህ ፤ እዚያ ልቅ ገድለኝ ወዳንድ ሸለቆ ውስጥ ከገባኸኝ በሁዋላ . . . እንኳ ! ምን እንደ ታዬህ አላውቅም ፤ ምረህ ፤ ሽጉጤንም መልሰህ ለቀቅኸኝ ። የኔ እድሜ ያነሰት ነበር ያለቀው ፤ ከዚያ ወዲህ የምኖረው አንተ የሰጠ ኸኝን እድሜ ነው ! ስለዚህ . . . በዚያ አንጻር ይህ ያደረግሁት አገ ልግሎት በጣም ትንሽ ነው ። ነገር ግን ልረዳ የምችልበትን መንገድ ከከፈትህልኝ እዳየን በሙሉ መክፈል ስመኘው የኖርሁት ነገር ነው።"

ጥላሁን ፤ ኢዮቤ - ወንጀሉ የተናገሩትን ከሰማ በሁዋላ ፤ እንደ ገና አንገቱን ደፍቶ ፤ አይኖቹን እመሬት ላይ ተክሎ ፤ ግንባሩን ቋጥር ፈታ እያደረገ ሲያስብ ቆይቶ ቀና አለና ፤ "ስማ ወንድይራድ !" አለ ። "ስማ ! መቸም ሰው እንደ መሆኔ ፤ እስከ ዛሬ በኖርሁት ህይወቴ ብዙ ስህተት ፤ ብዙ ጥፋት ሳላደርግ እንዳልቀረሁ የማይጠረጠር ነው። ገር ግን ለኔ እንደሚሰማኝ ስህተቴና ጥፋቴ ሁሉ ባንድ ላይ በደመር፣ የማያክለው ፤ እንኩዋንስ ሊያክለው ባጠገቡ የማይደርስ ፤ ከስህተትና ከጥፋት ይልቅ ወንጀል ሊባል የሚገባውና በእግዚአብሄርም ፤ በሰውም ዘንድ ሳሁልጊዜ ይቅርታ የማያስደርገልኝ ፤ የሰራሁት ክፉ ወንጀል አንድ ብቻ ነው !"

@OLDBOOKSPDF

"ምን ?" አለ ወንድይራድ ፤ እሱም እንደ ጥላሁን ፊቱን ቁጥር አድርጎ ።

"አሁን እንዳልኸው ልገድልህ ወደ ሸለቆው ከወሰድሁህ በኋላ ሳልገድልህ መቅረቴ !"

"እንዴት እባክህ ?" አለ ወንድይራድ ፤ አሁን ግንባሩን በመቋጠር ፊንጋ የመገረም መልክ ፤ ከውሸት ፈገግታ ጋር በፊቱ እየታዩ ።

"ያንለት ብገድልህ ኖሮ ፤ ከዚያ ወዲህ ያጠፋሀቸው ብዙ ንጹሆን ሰዎች አይጠፉም ነበር ። ያንለት 'ለምን ትገድለኛለህ ?' ብትለኝ ፤ 'ሰው የማጥፋት ሱስ ያለህ ፤ ክፉ ፍጥረት ስለሆንህ ፤ ካላጠፋሁህ ብዙ ንጹህ ሰው ታጠፋለህ' ያልሁህን ታስታውሳለህ ? እየውልህ ! ካልጠፋህ ሰው ስታጠፋ እንደምትኖር ምን እንዳሳዩኝ አልወቅ እንጂ ያንጊዜ ታይቶኝ ነበር ፤ አውቄ ነበር ። ይቅርታ የማይገባኝም እንዲያ አጥፊነትህን እያወቅሁ ስታጠፋ እንድትኖር መልቀቄ ነው !"

"እኒያ ያጠፋሁዋቸው ፤ ብዙ ንጹሆን ሰዎች ከየት እነማን ይሆኑ !" አለ ወንድራይድ ፤ አይኖቹንም ከንፈሮቹንም በግማሽ ጠመም አድርጎ ገልጾ ጥላሁንን በፌዘኛ አስተያየት የጎድን እያዩ ።

"ስማቸውን 'እገሌ እገሌ' ብዬ ልቆጥርልህ አልችልም ፤ አላውቀውም ፤ ብቻ . . . የኔ ስማቸውን መቁጠር አለመቻል እነሱ በግፍ አላለቁም ማለት አይደለም ፤ ወይም አንተን ከጥፋተኝነትህ ነጻ አያወጣህም !"

"አንተንስ . . . ስማቸውን ፤ ኧረ እንዲያውም መኖራቸውን እንኩዋ ለማታውቃቸው ሰዎች እኔን ገዳያቸው አድርገህ ለመክሰስና ለመውቀስ ባለመብት የሚያደርግህ ምን ፤ ወይስ ማን ነው !"

"ሰው ለማጥፋት ታጥቀህ የተነሳህ መሆንህን ስለማውቅ ፤ ይህን የማውቀውንና ሌላውም ሰው ሁሉ የሚያውቀውን ነገርሁህ እንጂ አልከሰስሁህም !"

"እኔ ሰው ለማጥፋት ታጥቄ የተነሳሁ መሆኔን ሰው ሁሉ የሚያውቅ መሆኑንስ የምታስረዳበት አለህ ? ወይስ ሁሉም እንዲያው . . . ያው የተለመደው ፤ መረን - የለሽ አሉባልታ ነው !"

"ለመሆኑ ሰው . . . ከሌሎች የስራ ጉዋደኞችህ ለይቶ 'እታቡ-ወንጀል' የሚባል ስም ያወጣልህ ለምን ይመስልሀል !" አለ ጥላሁን ትንሽ እንደ መሳቅ ብሎ ወንድይራድን የጎድን እየተመለከተ ።

@OLDBOOKSPDF

"እንጃ ! እሱን የምጠብቅ እኔ አይደለሁም ፤ እንዲያ ያለ ስም ያወጡት ሰዎች ናቸው ። ግምት ንገረኝ ትለኝ እንደ ሆነ ፡ ምናልባት ወንጀለኞች የሚገባቸውን ቅጣት ሳያገኙ እንዳያመልጡ መከታተል አይነተኛ ተግባሬ ስለ ሆነና ፤ ያኑ ተግባሬን ለመፈጸም በመጠንከሬ ሊሆን ይችላል ፤ ይህ የራሴ ግምት ነው ።"

" ያቃቤ - ህግ አይነተኛ ተግባርኮ ወንጀለኞች የሚገኙባቸውን ቅጣት እንዲያገኙ መከታተል ብቻ ሳይሆን ፡ ንጹሆች ባሰት ፣ ወይም በስህተት ወንጀለኞች ተብለው ለወንጀለኞች በተመደበው ቅጣት እን ዳይቀጡ ፡ ሲሆን ሲሆን አብልጦ ፡ ያለዚያም ያኑ ያክል በጥንቃቄ መከታተል ጭምር ነው ። ' ሲሆን ሲሆን አብልጦ በጥንቃቄ መከታ ተል ያስፈልጋል ' የሚባልበትም ምክናያት ፡ ' አንድ ንጹህ ሰው ባሰት ፣ ወይም በስህተት እንደ ወንጀለኛ ተፈርዶበት ከሚሞት አንድ የሞት ቅጣት የሚገባው ወንጀለኛ ከሞት ቅጣት ቢያመልጥ ይመረ ጣል !' በሚባለው አስተሳሰብ መሰረት ነው !"

"ይህ ፣ እንዲያው . . . ውስጠ ባዶ ፡ የቃላት ክምር ነው ! ከዚ ያም አጅግ ከፍ ሲል ፡ ያንተና እንዳንተ ያሉት የወንጀለኞች ሽሪኮች ፍልስፍና ነው !" አለ ወንድይራድ ፡ ፊቱ ክርር ብሎ ።

"አደለም ፤ ውስጠ ባዶና የቃላት ክምርም ፡ የኔና እንደኔ ያሉት የወንጀለኞች ሽሪኮች ፍልስፍናም አደለም ፤ የህግ ፍልስፍና ነው ።

"እየው ፤ ሞት የህይወት መጨረሻ ስለ ሆነ ፡ ህያው ሁሉ ከመ ሞቱ በፊት የመኖር አላማውን ፡ የመኖር ተግባሩን መፈጸም አለበት። እንደምታውቀው ካንዳንድ ፣ እንዳንተ ያሉ ርጉማን ወንጀለኞችና ለይ ጣኖች በቀር " ሲል ጥላሁን ፡ አይኖቹን በወንድይራድ ላይ ፍጥጥ አድርጎ ፤ ወንድይራድ በቅጽበት ፊቱ በቁጣ ተለዋወጠና በወንበሩ ወደ ሁዋላ ተገናንቶ ከተቀመጠበት ቀና አለ ።

"አትቆጣ እንጂ !" አለ ጥላሁን ፡ ከተል አድርጎ በፍጹም እርጋታ ።"ረጋ በል ፤ አትቆጣ ! አንተኮ ስለ ራስህ ያልኸውን ፡ ምን አይነት ፍጥረት እንደ ሆንህ አንተ ስለ ራስህ የመሰከርኸውን ነው እኔ አሁን የደገምሁት ። "

"እኔ ? 'ርጉም ወንጀለኛ ነኝ ፤ ሰይጣን ነኝ ' ብዬ በ . . .በራሴ መሰከርሁ ? እንዲህ . . . እንዲህ ያለ ነገር ተናገርሁ ? መቼ ? በየት በኩል ወጣኝ ? " አለ ወንድይራድ ፡ ፊቱ በቁጣ እንደጋለ ፡ ቁጣው ንግግሩን እያደናቀፈው ።

@OLDBOOKSPDF

“ አዲስ አለም ፣ አሽለቅው ውስጥ መሄጃም ፣ መመለሻም ከሌለበት የሞት አፋፍ ቆመህ ፣ በጣም በተጨነቅህ ፣ በተቸገርህ ጊዜ ላባትህ የጻፍኸውን የመጨረሻ ኑዛዜ ታስታውሳለህ ? ‘ የሰው እውነተኛ ባህሪው የሚገለጸው ፣ አንድም በጣም ሲጨንቅ ፣ በጣም ሲቸገር ፣ ወይም በጣም ሲሰክር ነው ! ’ እንደሚባለው ፣ ያ ሰአት የህይወትህ መጨረሻ መስሎ ታይቶህ በተጨነቅህበት ጊዜ ፣ በእግዚአብሄር ፊት ቆመህ ፣ ምን መሆንህን ከተናዘዝኸው ብዙ ነገር በጣም ትንሹን ነው አሁን የደገምሁት ። አሁን ከዚህ ስትመለስ ያን ወረቀት ካስቀመጥህበት ፈልገህ ብትመለከት ፣ እዚያ ከጻፍኸው ቀንሼ እንጂ ጨምሬ እንዳልተናገርሁ ትረዳለህ ! ” አለ ጥላሁን ፣ ወንድይራድን ገደም አድርጎ እያየ ለዘብ ባለ አነጋገር ። ወንድይራድ አዲስ አለም፣ እዚያች ሸለቆ ውስጥ ፣ በሞት ጥላ ስር ተቀምጦ እንደ ኑዛዜ ላባቱ የጻፈውን ጥላሁን ሲያስታውሰው ፣ “ እ . . . ! ” አለና አይኖቹን ሳያረግብ በዘገ አድርጎ ከጥላሁን ራስ በላይ ፣ እጣራው ላይ እንደ ተከለ፣ ቀስ ብሎ ወደ ሁዋላው ወንበሩን ተደግፎ ዝም አለ ። አሳቡ እሱን እዚያው እንዳለ ትቶ ወደዚያች ሸለቆ ሄዶ ካምስት አመት በፊት የሆነውን ሁሉ የሚመለከት ይመስል ነበር ።

“ አሁን የጀመርሁትን ልጨርስ ? ” አለ ጥላሁን ፣ ሁለቱም ዝም ብለው ዘለግ ያለ ጊዜ ከቆዩ በሁዋላ ።

“ እ ? ምን ኖሩዋል የጀመርኸው ? ጨርስ ” አለ ወንድይራድ፣ አሳቡ ገና ካዲስ አለም ሸለቆ ስላልተመለሰ ፣ እንዲሁ እፉ እንዳመጣው።

“ ንጹህ ሰው ባስት ፣ ወይም በስህተት ተወንጅሎ በሞት ከሚቀጣ ፣ ሞት የሚገባው ወንጀለኛ ከሞት ቅጣት ቢያመልጥ የሚመረጥ መሆኑ በህግ ፍልስፍና የሚደገፍበትን ምክናያት መግለጽ ጀምሬ ነበር ። ታዲያ ቅድም እንዳልሁት ሞት የህይወት መጨረሻ ስለሆነ፣ ህያው ሁሉ ከመሞቱ በፊት የመኖር አላማውን ፣ የመኖር ተግባሩን መፈጸም አለበት ። መቸም ካንዳንድ . . . ርጉሞችና ሰይጣኖች በቀር” አለ ጥላሁን ፣ ቀደም ሲል “ እንዳንተ ያሉ ” ያለውን ትቶ ። “ መቸም ካንዳንድ . . . ርጉሞችና ሰይጣኖች በቀር ፣ ሰው ሁሉ ከፈጣሪ እንደ ታደለው ፣ እንደዩስጦታው በፍልስፍና ፣ በስነ-ጽሁፍ ፣ በሀይማኖት ፣ ወይም በሌሎች መንፈሳውያንና ስጋውያን የስነ ፍጥረት ምርምሮች በከፍተኛ ደረጃ ለሰው ዘር ሁሉ ፣ ከዚያ መለስ ሲል ለዩማህበሩና ሊያገሩ ፣ ከዚያ በታች በጠባቡ ፣ እንተ ላባትህ በኑዛዜህ እንደ

@OLDBOOKSPDF

ገለጸኸው ፣ ለዩራሱ የትውልድ መስመር ድልድይ እዩሆን ፣ ያባቶችን አካባዊና መንፈሳዊ ውርስ ለልጆች የማስተላለፍ አገልግሎት ለመስጠት ተልእኮ ፣ ወይም ተግባር አለበት ። ስለዚህ አንድ ሰው ሙሉ ህይወቱን ሳይኖር ቢገደል ፣ እሱ የመኖር መብቱን ከመቀማቱ ሌላ ፣ ከፈጣሪ እንደ ታደለው ፣ እንደዩሰጠታው ፣ ለሰው ዘር ፣ ለማህበሩና ላገሩ ፣ ወይም ለራሱ የትውልድ መስመር ፣ ተልእኮውን ሳይፈጽም በመገደሉ ገዳዩ ባሰት በገደለው ፣ ወይም ባስገደለው ሰው ላይ ብቻ ላይሆን ፣ ባሰት የተገደለው ሰው አገልግሎት በሚቀርባቸው ሁሉ ላይም ወንጀል እንደ ሰራ ይቆጠራል ። ባሰት ፣ ወይም በስህተት የሚገደለው ሰው የራሱ የትውልድ መስመር አገናኝ ፣ ድልድይ ከመሆኑ ሌላ ፣ በሰፊው ለሰው ዘርና ፣ ከዚያም መለስ ሲል ለማህበሩ ወይም ላገሩ ቤዛ ሊሆን የሚችል ስለ ሆነ ነው ፣ ብርቱ ጥንቃቄ ያስፈልጋል ፣ እንዲያውም 'ንጹህ ሰው ባሰት ፣ ወይም በስህተት ተወንጅሎ ከሚሞት ፣ ወንጀለኛ ከሞት ቢያመልጥ ይመረጣል !' የሚባልበት ምክንያት ። ወንጀለኛነቱ በምስክሮችና በልዩ ልዩ ማስረጃዎች ተረጋግጦ የሞት ቅጣት የተፈረደበት ሰው፣ ባንድ ምክንያት ከተፈረደበት የሞት ቅጣት ቢያመልጥ ፣ ማህበርም ይሁን መንግስት ምን ያክል ይጎዳል ? በማህበርም ይሁን በመንግስት የሚደርሰው ጉዳት ላንተ እንደሚመስልህ ይህን ያክል ትልቅ ፣ ይህን ያክል ከራስ ጸጉን ተራራ የሚበልጥ አይደለም ! ከሁሉ አስቀድሞ ቅጣቱ ላጥፊው ግረሚያና ለሌሎች ሁሉ መማሪያ እንጂ መበቀያ ስላልሆነ ፣ ከሞት ያመለጠው ወንጀለኛ ፣ ከሞት አደጋ በማምለጡ ደስ ብሎት ፣ ያ ማስጠንቀቂያ ፣ ወይም እርም ሆኖት ፣ ዳግመኛ ወደ ወንጀል ስራው የማይመለስ ከሆነ በግን እድል ! የቅጣቱ አላማ ተመታ ማለት ነው ! እንደ ገና ወደ ወንጀል ስራው የሚመለስ ከሆነም ፣ ያ መንገድ የሚመራው እምልጦት ወደ ነበረው ሞት በመሆኑ የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ፣ ዞሮ ዞሮ መጨረሻ ከሚገባው ሞት አያመልጥም ማለት ነው " ብሎ ጥላሁን ሲቀጥል ሲል ፣ ወንድይራድ ትእግስቱ አልቆ ፣ ከተቀመጠበት በሰጨት ብሎ ተነሳና ፣ ሁለት እርምጃዎች ወደ መስኮቱ ከተራመደ በሁዋላ እንደ ገና ወደ ጥላሁን ዞሮ ለአቱን እያዩ ፣

"ይቅርታ አድርግልኝ ፣ ጥላሁን " አለ ። "እባክህ ይቅርታ አድርግልኝ ። ስለ ህግ ፍልስፍና ትምህርቱ ጥሩ ነው ! ስራ ባይኖርብኝ ተቀምጩ ብግር በጣም ደስ ባለኝ ! ነገር ግን ከሱ የበለጠ ብዙ . . . ስራ ስላለብኝ ቢበቃና ፣ ስለ መጣሁለት ጉዳይ ብንነጋገር ይሻላ " ሲል ወንድን ይራድ ፣ ብስጭቱን እንደ ገና ወደ ማሾፍ ለውጦ

@OLDBOOKSPDF

ጥላሁን ዘለግ ላለ ጊዜ ዝም ብሎ በንቀት አይን ሲመለከተው ቆዬ ።

“ . . . አዎ ፤ ስለ መጣሁለት ጉዳይ ብንነጋገር ይሻላል ” አለ ወንድይራድ ፤ ይገመና ሁሉንም ዝም ብለው ቆይተው ወደ መቀመጫው ተመልሶ ሄዶ ሲቀመጥ ።

“ እሰማለሁ ፤ የመጣህለትን ተናገር ” አለ ጥላሁን ።

“ ከዛሬ አምስት አመት በፊት የኔ ህይወት በጅህ እንደ ነበር ፤ ዛሬ ያንተም ሆነ የሚሽትህ ህይወት ቢቃቢ ሀግ እጅ ስለ ሆነና ፤ ባጋጣሚ የዚህ ጉዳይ ባለደራው እኔ ስለ ሆንሁ . . . የምረዳበት መንገድ ከከፈትህልኝ ህይወታችሁን ለማዳን የምችለውን ሁሉ ባደርግ እንደ ተግባር እንጂ ፤ እንደ ጋሊታ የማልቆጥረው መሆኔን ቅድም ነግሬህ ነበር ።”

“ የኔም ሆነ የሚሽቴ ህይወት በማንም እጅ ባለልሆነ ፤ ርዳታ ከማንም አንፈልግም ” አለና ጥላሁን ፤ ትንሽ ዝም ብሎ ቆይቶ የወንድይራድን አሳብ አለዚ መጨረሻው ማወቅ የሚያስፈልግ መስሎ ስለ ታየው፥

“ ለመሆኑ . . . ርዳታ የምንፈልግ ቢሆንም ‘የምረዳበት መንገድ ከከፈትህልኝ ’ ያልኸኝ እንዴት ያለ መንገድ ነው እንድከፍትልህ የምትፈልግ ? ”

“ የኔም ሆነ የሚሽቱ ህይወት ቢቃቢ - ሀግ እጅ አይለም ” ባልኸው ፤ ሁጉን ካንተ የበለጠ የሚያውቀው በለሌለ ፤ እኔ ልነግርህ አልሻም ። በዚያም ፤ በምታውቀው ህግ ባንዳንድ የተለዩ ምክናያቶች ካልሆነ በቀር ፤ የገደለ መሞቱ ምንም የማያጠራጥር ነው ። ነገር ግን ባንዳንድ የተለዩ ምክናያቶች መግደል የሚፈቅድ ከመሆኑ በላይ እንዲያውም ግዴታ ሲሆን ስለሚችል ፤ እንዲያ ባሉት የተለዩ ምክናያቶች መጠቀም ይቻላል ። ከነዚህ የተለዩ ምክናያቶች አንተና እኔ ባይነተኛው ፤ ማለት በክፍል ሁለት ፤ በቁጥር 74 በተመደበው ፡ “ ባልሞት -ባይ ተጋዳይ ” ተስማምተን ፤ አንተ ክርክርህን በሱ ዙሪያ ደህና አድርገህ ፤ አጠንክረህ ብትመሰርት ፤ እኔም ያንተ ክርክር በህግ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ልናፈርሰው የማንችል መሆኑን ለጉዋደኞቼም ፤ ላሊቀዩም ለማስረዳት እችላለሁ ። እና ብችል የተመሰረተው ክስ እንዲነሳ ለማድረግ ፤ እሱን ለማድረግ ባይቻል ፤ መሸነፋችን የማይቀር መሆኑንና ፤ ከዚያ በሁዋላ ይግባኝ ማለት ምንም ለውጥ የማያመጣ መሆኑን አቃብያነ ህጉና እነዚያ ያሉት ሹማምንት እንዲቀበሉት ካሁን ጀምሮ በጊዜ ብዛት ማለናዳት ይቻላል ። የሚያስፈልገው የምንሄድበትን መንገድ ማወቅና ተባብረን መስራት ብቻ ነው ” አለና ወንድይራድ ፤
“ ይህ አሳብ ምን ይመስልሀል ? ” በሚል የጥያቄ አስተያየት አንገቱን

@OLDBOOKSPDF

ወደ አንድ ወገን ቀልበስ አድርጎ ጥላሁንን እያዩ መልሱን ሲጠብቅ ፣ ያንጊዜ ጥላሁን በሰንበተበት እግር ብረት ተጨርንቆ እንደ ገና ወዳለም ቢቃኝ ወሀኒ መመለሱን ባይፈራ ወንድይራድን በጡ . . . ጫ እፍን ጫውን ብሎ ከመሬት ቢደባልቀው በወደደ ነበር !

"ስማ ፤ አንተ . . . !" አለ ጥላሁን ፣ ወንድይራድን ምን ብሎ እንደሚሰድበው ስድቡ ሁሉ ስላነሰው ፣ በመጨረሻ ሁሉንም ትቶ ። ከሁሉ አስቀድሜ እንድታውቅልኝ የምፈልገው ፣ ቀኛዝማች ዳኘን በስህተት ፣ በድንገት ፣ በደም ፍላት ወይም አንተ እንዳልከው ፤ "ባለሞት - ባይ ተጋዳይነት" ሳይሆን አውቄ በመግደሌ በመጸጸት ፈንታ የተደሰትሁ መሆኔን ነው ። እኒያን የብዙ ሰው ህይወት ሲያጠፉና ፣ ያንድ ወረዳ ህዝብ ንብረት ሲዘርፉ የኖሩ ፣ መሰል የሌላቸው ወንጀለኛ መግደሌ ፣ በማስጸጸት ፈንታ ትልቅ ደስታ የሰጠኝ መሆኑን እንድታውቅልኝ እፈልጋለሁ ! እንዲያ ካሉት መቅሰፍት የየኔን ህዝብ ማዳንና ፣ ሰኔም የስራዬ መሰናክል የሆኑትን ማስወገድ ፤ ለህዝብ ፣ ለመንግስትና ለእግዚአብሄር ከፍተኛ አገልግሎት መሆኑን በጥኖና አስቤ ፣ አሰላስዬና አምኙ የገደልሁዋቸው መሆኔን ፤ ማለት ባሳብም ፣ በግብርም ገዳያቸው መሆኔንና ፣ በዚህም ምክናያት ያገኘሁትን ደስታ ከሰማይ በታች ለሚገኝ ፣ ለምንም አይነት ዋጋ የማለውጠው መሆኔን እንድታውቅልኝ እፈልጋለሁ ! ሁለተኛ ምንም እንኩዋ ዛሬ የመጣህለትን ፣ እውነተኛ አላማህን ባላውቅ ፤ ሶፊንና እኔን ስመርዳት ፣ ሁሁ ! ከቶውንም ህይወታችንን ለማዳን ! ትንሽም አሳብ እንደሌለህ አውቃለሁ ። ነገር ግን እስቲ "ይህ የኔ እውቀት በተሳሳተ እምነት ላይ የተመሰረተ ነው" እንበልና ፣ እንዲያው ሊሆን የማይችል ነገር ፣ በታምር ፣ "አንተ የሶፊንና የኔን ህይወት ለማዳን የምታስብ ነህ" እንበል ! "ይህ ፈጽሞ የማይሆን ነው እንጂ ፣ የሚሆን ቢሆን እንኩዋ ፣ አሁንም ባቀረብከው ጎስቋላ አሳብ ካንተ ጋር መተባበር እንዳንተ ወራዳነት አደለም ? በዚህ ካንተ ጋር መተባበርን እንዳንተ ወራዳነት አድርጌ ስለምቆጥረው ፤ ዳግመኛ መስማት አልፈልግምና ወግድልኝ !" አለ ጥላሁን ፣ አይኖቹ በቁጣ ቀልተው ፣ ሰውነቱ ሁሉ እዩተንቀጠቀጠ ።

"እሺ ተወው ፤ ጤና ይስጥልኝ !" አለ ወንድይራድ ፣ ከተቀመጠበት ሲነሳ ካሽሙር ፈገግታ ጋር እጁን ለሰላምታ ዘርግቶ ። ለታሎም ይሁን ለጁ ሰላምታ ከጥላሁን መልስ አላገኘም ፤ የመጣለትን ጉዳይ ግን ካሰበው በላይ አግኝቶ ፣ ደስ ብሎት ሄደ ።

@OLDBOOKSPDF

ምእራፍ ፴፱

# የህዝብ ድምጽ የግዜር ድምጽ

ጥላሁንና ሶፊያ ማንም ሳይጠረጥራቸው ፣ በራሳቸው መስክረው ፣ የሞት ፍርድ ሊፈረድባቸው በቀረቡ ሰዎች ቀንበር መግባታቸው ፣ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በሙሉ ኢትዮጵያ ስለ ተነዛና ፍርድ የሚቀበሉ በት ቀን ቀደም ብሎ ታውቆ ስለ ነበረ ፣ በዚያ ቀን የተሰበሰበው ህዝብ የፍርድ ቤቱን አደባባይ እስኪጨናነቅ ሞልቶት ነበር ። ባንደኛ የወንጀል ችሎት የሚያስችሉት ዳኞችና አቃቤ-ህጉ ቦታቸውን ይዘው ፣ ክፍሉን ሰው በሰው ተደራርቦ ሞልቶት መንቀሳቀሻ ጠፍቶ ፣ ሁሉም ደቂቃ አልፎ ደቂቃ ሲከተል ይዞት የሚመጣውን በተሸበረ ልብ ሲጠባበቅ ፣ ጥላሁን ፈይሳና ሶፊያ ሙላት እጅ እጃቸውን በሰንሰለት ታስረው ፣ በሁለት ፖሊሶች ታጅበው ገብተው እንደነሱ የሞት ፡ ወይም የህይወት ዜናቸውን ከዳኞች አፍ ለመስማት ለሚቀርቡ ሰዎች በተመደበው ቦታ ሲቆሙ ፣ በህዝቡ መሀከል የተነሳው ጫጫታ ገዝም እስኪልና ረብሻው ጸጥ እስኪል ረገርም ጊዜ ወሰደ ። ከዚያ ዳኞች ጠረጴዛቸውን እየደበደቡ ፡ ፖሊሶች እያጨበጨቡ ጫጫታውና ረብሻው ትንሽ በትንሽ ጸጥ እንዲል ካደረጉ በሁዋላ ፣ ሰብሳቢው ዳኛ አጭር የመክፈቻ ንግግር አድርገው አቃቤ-ህጉን በተከሳሾች ላይ የሚጠይቁትን እንዲያቀርቡ ጋበዙዋቸው።

“አቶ ጥላሁን ፈይሳና ወይዘሮ ሶፊያ ሙላት ፣ የቀኛዝማች ዳኛቸው ፍራሳ ገዳዮች መሆናቸውን ራሳቸው መስክረው በስም ሞክሼ ተይዘው በስህተት ለፍርድ ቀርበው በነበሩት ፣ ባቶ ጥላሁን ፈይሳና በባለቤታቸው በወይዘሮ እጸገነት አሸብር ቀንበር ገብተው ፍርድ እንዲቀበሉ ጠይቀዋል ። ‘ይህ ተደርጎ የማያውቅ እንግዳ ነገር ምናልባት በውስጡ የማይታይ ተንኮል ሸሽጎ ይሆናል’ በማለት ፣ በጥንቃቄ እንዲመረመር የሶስት ወር ጊዜ ተሰጥቶት ከተመረመረ በሁዋላ ፣ አቶ ጥላሁን ፈይሳና ወይዘሮ ሶፊያ ሙላት በራሳቸው የመሰከሩት ትክክለኛ መሆኑ በመረጋገጡ ፣ በስህተት ተመስክሮባቸው ለፍርድ ቀርበው የነበሩት አቶ ጥላሁንና ወይዘሮ እጸገነት በነጻ መለቀቃቸው ይታወሳል ። አሁን ፍርድ ቤቱ መስማት የሚፈልገው ፣ አቃቤ - ህጉ ባቶ ጥላሁን ፈይሳና በወይዘሮ ሶፊያ ሙላት ላይ ምን እንደሚጠይቅ ነው” አሉ ሰብሳቢው ዳኛ ።

@OLDBOOKSPDF

"አቃቤ-ወንጀል" የሚባል ስም የወጣለት አቃቤ-ህግ ወንድይራድ፣ ወህኒ ቤት ሄዶ ጥላሁንን አነጋግሮ ከተመለሰ በሁዋላ፣ "ባልሞት - ባይ ተጋዳይነት" ህይወታቸውን ለማዳን ሲከላከሉ ሰው የሚገድሉትን ሰዎች ነጻ በሚያደርገው ህግ መጠቀም እንደማይፈልግ ስለተረዳ፣ አንድ ከባድ ሸክም ከትከሻው ወርዶ እንደ ወደቀለት ቆለለው። ወንድይራድ፣ በፊተኞች ተከሳሾች ላይ በብዙ ድካምና በብርቱ ጥንቃቄ አሰናድቶ የመሰረተው ክስ ውድቅ ሲሆን፣ "ወንጀሉን ሰራን" ብለው እጃቸውን የሰጡት ጥላሁንና ሶፊያ ያሰናዱትን መከላከያ በርግጥ ስለማያውቅና፣ ይልቁንም "ህይወታቸውን ለማዳን ሲከላከሉ ሰው የሚገድሉትን ሰዎች ለመጠበቅ የወጣውን ህግ ይጠቅሱብኝ ይሆናል" ብሎ ብርቱ ስጋት አድሮበት ነበር። ነገር ግን በዚያ ፈንታ፣ የብዙ ሰው ነፍስ ያጠፉትን፣ ከዚያ የሚበዛ ሰው አካል ያጎደሉትንና ደግሞ ከዚያ የሚበዛ ህዝብ ንብረት የዘረፉትን ወንጀለኛ፣ ቀኛዝማች ዳኘን መግደል፣ በሞት የሚያስቀጣ ወንጀል አለመሆኑን፣ ህግ ባይቀበለው ሰብዊ ህሊና ስለሚቀበለው፣ ይህን የየጥሆች መንገድ መምረጡን ጥላሁን ስለ ነገረው፣ ያለ ብዙ ድካም፣ ያለብዙ ችግር እንደሚቀናው እርግጠኛ ሆኖ ደስ አለው። ከንግዲህ የሚያስፈልግ ነገር ቢኖር፣ ይህ ጉዳይ፣ ይህ የቀኛዝማች ዳኘ ገዳዮች ከሚገባቸው የሞት ቅጣት እንዳያመልጡ ማድረግ፣ ከፍተኛ ባለ ስልጣኖች አጥብቀው ያሰቡበት መሆኑን ለዳኞች ማስጠንቀቅ ብቻ ነው። ህግ በሚደግፈው ነገር ከፍተኛ ባለስልጣኖችን ማስደሰት ዳኞችንም ቢሆን የሚያስቸግር፣ ህሊናቸውን የሚቆረቁር አይደለም! ስለዚህ ጥላሁን አሳቡን ለውጦ "ባልሞት - ባይ ተጋዳይነት" ህግ ለመከላከል ካልፈለገ፣ ለጊዜው ነገሩ የሚያሳስብ አይደለም ፤ እንዲያውም ደህና መንገድ ይዞዋል። ወንድይራድ ይህን ሁሉ ባሳቡ ካመዛዘነ በሁዋላ፣ ለመጀመሪያው ግጥሚያ የጥላሁንን መከላከያ ለማየት ያክል መጠነኛ መሰናዶ ለማድረግና በዚያ ላይ የጥላሁንን መልስ ካዬ በሁዋላ፣ ረዥም ቀጠሮ አስቀጥሮ ለወሳኙ ግጥሚያ በሚገባ ለመሰናዳት ወሰነ። ስለዚህ በመጀመሪያው ግጥሚያ ቢያጥርም፣ እንደ ተለመደው የሰውን አሳብ በሚማርክ አነጋገር፣ በጥላሁን ፈይሳና በሶፊያ ሙላት ላይ የሞት ፍርድ እንዲፈረድባቸው ጠይቆ ፍጀታውን ለተከላሾቹ ለቀቀ።

"ክቡር ሊቀ መንበር" አለ ወንድይራድ፣ እንደ ልማዱ ጽሮ ከፊቱ በጠረጴዛው ላይ የዘረጋውን ማስታወሻ በማየት ፈንታ ቀጥ ብሎ ተቆምጦ ዳኞቹን ፍጥጥ አድርጎ እያዩ። "ክቡር ሊቀ መንበር፣ የተከበራችሁ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ አቶ ጥላሁን ፈይሳና ባለቤታቸው ወይዘሮ ሶፊያ ሙላት ሳይከሰሱ ፣ እንኳንስ ሊከሰሱ ማንም ሳይጠረጥራቸው

@OLDBOOKSPDF

በራሳቸው መስክረው፣ በስህተት በንጹሕ ጉዳይ ተመስክሮባቸው ለቅጣት በቀረቡ ሰዎች ቀንበር መግባታቸው የሰሩትን ክፉ ወንጀል አስረስቶ፣ ከጀግኖች በላይ ጀግኖች፣ ከሰማእታት በላይ ሰማእታት አድርጎ ስላሳያቸው፣ ስማቸው እጃቸውን ከሰጡበት ቀን ጀምሮ በሰው ሁሉ አፍ ሲወደስና ሲሞገስ እንደ ሰነበተ፣ ሁላችን የምናውቀው ነው። ይገርማል! የመንግስቱ ራዲዮና ጋዜጦች እንኳ፣ የህዝቡን ስሜት ተከትለው፣ ህዝቡ ጀግኖቹን እያወደሰና እያሞገሰ ለመዝፈን በቃኘው መዚቃ እየተመሩ፣ አብረው ሲዘፍኑ፣ አብረው ሲያወድሱና ሲያሞግሱ ሰነበቱ።

"ክቡር ሊቀ መንበር፣ እንዲህ ሰው ሁሉ መዚቃውን ለዘፈን ቃኝቶ መዝፈን በሚፈልግበት ጊዜ፣ እንዲህ ሰው ሁሉ የኑሮ ችግሩን ረስቶ መጫወት በሚፈልግበት ጊዜ፣ ቁምነገር እንደማይጥም የታወቀ ነው። እንዲህ ባለ የተጋጋለ ዘፈንና ጨዋታ መሀከል ሀላፊነትና ተግባር አስገድደውት ትንሽ እንኳ የቁም ነገር ድምጽ የሚያሰማ ወዮለት! እንዲያ ያለው ሰው የወገኖቹን ስሜት እንደማይካፈል፣ የወገኖቹን ደስታ እንደሚያስናክል ምቀኛ ተቆጥሮ እንደሚጠላ፣ አይንህን ላፈር እንደሚባል አውቃለሁ። ነገር ግን ክቡር ሊቀ መንበር፣ የመንግስት አቃቤ-ሕግ እንዲህ ያለውን ጊዜያዊ ስሜት፣ እንዲህ ያለውን (ይቅርታ ይደረግልኝ) እላፊ፣ የሰካር ስሜት ፈርቶ፣ ባይጥምም፣ በዚህ ሁሉ ዘፈንና ጭዋታ መሀከል ፍርድ ቤቱ ቁምነገሩን፣ እውነቱን ተመልክቶ ፍርድ እንዲሰጥ መጠየቁን አይተውም።

"ክቡር ሊቀ መንበር፣ የህዝብ ስሜት ለህይወቱና ለንብረቱ፣ ለመብቱና ለነጻነቱ መሰረት ከሆነው ህግ ጋር የሚስማማ ሲሆን፣ ከህግ ጋር የማይቃረን ሲሆን፣ እንዲያ ያለውን ስሜት መንግስት ያከብረዋል። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ተንኮለኞች በማታለልና በማስመሰል ህዝቡን አሳስተው፣ ስሜቱን መማረክ ስለሚችሉ፣ እንዲህ ያሉት ተንኮለኞች የተሸፈኑበትን የውሸት መጋረጃ ቀድዶ ራቁታቸውን ማሳዬት፣ የህዝቡ ስሜት ለጠቅላላ ደህንነቱ የተሰመረለትን ህጋዊ መስመር ተከትሎ እንዲመራ ማድረግ፣ በመንግሥት አቃቤ-ህግ ሀላፊነት የተጣለበት ተግባሩ ነው።

"ጥላሁን ፈይሳና ሶፊያ ሙላት፣ የቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሬሳ ገዳዮች ለመሆናቸው ራሳቸው መስክረው፣ እጃቸውን ለፍርድ መስጠታቸው የመጀመሪያ ደረጃ ወንጀለኞች፣ ነፍስ ገዳዮች ከመሆናቸው ንጹ አያደርጋቸውም። እንዲያውም፣ ክቡር ሊቀ መንበር፣ ጥላሁንና ሶፊያ የነፍስ ገዳይ ወንጀለኞች ብቻ አይደሉም፣ ያታላይነትና ያጭበርባሪነት ወንጀል ጭምር የፈጸሙ ናቸው። ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሬሳን

@OLDBOOKSPDF

ገድለው ፣ ወዳዲስ አበባ ከሸተው ከመጡ በሁዋላ ፣ መልካቸውንና ስማቸውን ለውጠው ፣ አቶ ጥላሁን የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆነው በወንጀል ችሎት ወንበር ፣ ወይዘሮ ሶፊያ መምህር ሆነው ባስተማሪነት ወንበር ሲቀመጡ ፣ የወንጀል ስራቸው በራሳቸው ሳይወሰን ፣ ሌሎችን ለማስተማርና ለመርዳት መሆኑ ግልጽ አይደለም ? እግዚአብሄር በማይመረመር ምስጢሩ ፣ ወንጀል ስርተው እንዳይታወቁ ለማቸውንም ፣ መልካቸውንም ለውጠው ከተሸሸጉ በሁዋላ ፣ ማንም ሳይጠረጥራቸው ራሳቸው ተናግረው እጃቸውን እንዲሰጡ ባያደርግና ፣ የሚታበል ስራቸው ባጭር ባይቆረጥ ኖሮ ፣ በወንጀል ችሎት ሊቀ መንበር ሆኖ የተቀመጠ ወንጀለኛ ለማን ሲፈርድና ማንን ሲረዳ ያኖር ኖሮዋል ? መምህር ሆና ባስተማሪነት ወንበር የተቀመጠች ወንጀለኛስ ለተማሪዎቿዋ ምን ስታስተምር ትኖር ኖራለች ? ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ አቶ ጥላሁን ፣ ራሳቸው ከተናገሩት እናገኛለን ። አቶ ጥላሁን በራሳቸው መስክረው እጃቸውን ሲሰጡ ከተናገሩት መሀከል ፣ "በሰው-ሰራሽ ህግና በሱ መሰረት የተሰሩት የዳኝነት ስነ-ስራዎች ፣ እምነት የማይጣልባቸው ጉደሎዎች ስለሆኑ ፣ ቀኛዝማች ዳኛን የገደልሁዋቸው ሀሊናየን አስፈርጂ ነው " የሚል ይገኝበታል ። ታዲያ ይህ ምን ማለት ነው ? በወንጀል ችሎት ተቀምጠ ሲፈርድ የኖረ ዳኛ እንዲህ . . . ማለቱ ህግን ዋጋ አሳጥቶ ፣ እንዳይሰራ ለማድረግና የወንጀል ሀዋርያ ሆኖ ወንጀለኞችን ለመርዳት ያቀደ መሆኑን ያለጥርጥር የሚያስረዳ አይደለም ?

"ክቡር ሊቀ መንበር ፤ የተከበራችሁ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኞች፤ ሰው-ሰራሽ ህግና የዳኝነት ስነ-ስራት የሰው ስራዎች በመሆናቸው ፍጹምነት ሳይኖራቸው ይችላል" ነገር ግን እግዚአብሄር አይበለው እንጂ ፣ "ሰው-ሰራሽ ህግና የዳኝነት ስነ-ስራት ፍጹምነት ስለሌላቸው፣ እነሱን በጭራሽ ትቶ ፣ በፍጥረት ህግና በያንዳንዱ ሰው የህሊና ፍርድ ብቻ ተማምኖ መቀመጥ ይሻላል የሚባል ቢሆን ኖሮ ፣ የምንኖርበት ማህበር ምን አይነት ማህበር ይሆን ኖሮዋል ? እንዲያ ያለው ማህበር ከጦርነት በቀር ሰላም የማይታወቅበት ፣ ከሌቦች ፣ ከቀማኞችና ከነፍስ-ገዳዮች በቀር ሰላማውያን ባንድ ቤት አዳር እንኳ የማይመኙት ማህበር አይሆንም ኖሮዋል ? ይሁን እንጂ እግዚአብሄር በቸርነቱ አሳባቸውን በጽንስ እንዲጨነግፍ ባያደርግ ኖሮ ፣ የጥላሁን ፈይሳና የሶፊያ ሙላት አላማ ማህበራችንን እንዲህ ለማድረግ ነበር ። የእግዚአብሄር ታምር የሚያስገርም አይደለም ? ብቻ . . . እሱ በሰራው ታምር የሚወደሱና የሚሞገሱ እነሱ ሆኑ !"

@OLDBOOKSPDF

"ስለዚህ ክቡር ሊቀ መንበር ፤ ጥላሁን ፈይሳና ሶፊያ ሙላት ፣ ቀኛ ዝማች ዳኛቸው ፍሬሳን በመግደላቸው የመጀመሪያ ደረጃ ወንጀለኞች ከመሆናቸውም ሌላ ፣ ስብከታቸው ለማህበራችን ጠቅላላ ደህንነት መሰረት የሆነውን የህግ አቋዋም የሚያፈርስ ስለሆነ ፣ እጅግ አደገኞች በመሆናቸው በመጨረሻው ቅጣት ፣ በሞት እንዲቀጡ ፍርድ ቤቱን በአክብሮት እጠይቃለሁ ።"

"አቃቤ-ህጉ የጠየቁትን ተከሳሾች ትቀበሉታላችሁ ፤ ወይስ ትቃወሙታላችሁ ?" አሉ ሰብሳቢው ዳኛ ።

"ክቡር ሊቀ መንበር ፤ የተከበራችሁ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኞች" አለ ጥላሁን ፣ እሱም ማስታወሻውን በፊቱ ይዞ ዳኞቹን እያዩ ። "ክቡር ሊቀ መንበር ፤ የተከበራችሁ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኞች ፤ ባለቤቴና እኔ እውነት አቃቤ-ህጉ ለፍርድ ቤቱና ለተመልካቹ ህዝብ እስመሰለው እንዳሳዩን ከሆንን በስጋ ብቻ ሳይሆን በነፍስ ጭምር ልንገደል የሚገባን ፣ በሰው ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሄር ፊት ጭምር ምህረት የማይገባን ነን ! ነገር ግን እሳቸው እንዳስመሰሉን አይደለንም ። ምሁሩ አቃቤ ህግ ከሰው አፍ መወደስንና መሞገስን ፍለጋ እስከ ሞት ድረስ የምንሄድ ከንቱዎች ፣ የሰው ህይወትና ንብረት ፣ መብትና ነጻነት የሚጠበቅበትን ህግ እንዳይከበር ለመስበክና ወንጀለኞችን ለመርዳት ከሰይጣናት አለቃ ተልከን የመጣን ሰይጣናት ሀዋርያዎች ፣ አታላዮች ፣ አጭበርባሪዎች አስመስለው አቅርበውናል ፤ ነገር ግን እንዲህ አይደለንም ። ባለቤቴና እኔ ህይወትን በትንሹ የቀመስን እንጂ ገና ያልጠገብን ፣ ከህይወት የቀመስነውንና ገና ለመቅመስ የምንፈልገውን ቀምሰን ለመጥገብ ናፍቆት በተሞላ ተስፋ የምንጠባበቅ ፣ ህይወታችንን ፣ ንብረታችንን ፣ መብታችንንና ነጻነታችንን አስከብሮ ፣ በናፍቆት ወደምንጠባበቀው ተስፋ የሚያደርሰንን ህግ አክብረን ለመኖር የምንፈልግ ፣ ባለብዙ ተስፋ ወጣቶች ነን እንጂ ፣ ከሞትን በሁዋላ የማናየውንና የማንሰማውን ከንቱ ውዳሴ ፍለጋ ህይወትን ለሞት የምንለውጥ ሞኞች ፣ ወይም በሳምን ለሁከት የምንለውጥ እብዶች አይደለንም ! ነገር ግን ምንም እንኳ ህይወትን አጥብቀን ብንወድ ፣ አላማችንን ፣ ደስታችንንና ተስፋችንን የመሰረትንበትን ፣ የኛን ፣ የራሳችንን ህይወት መኖር እንጂ ፣ የሌሎችን ህይወት መኖር የምንወድ አይደለንም ።

"ክቡር ሊቀ መንበር ! ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሬሳን መግደል ወንጀል ሆኖ የሚያስሞት ከሆነ ፣ ገዳዮቻቸው እኔና ባለቤቴ ስለሆንን ፣ እኛ እንሞታለን እንጂ ሌሎች በኛ ፈንታ ፣ የኛን ሞት እንዲሞቱና እኛ የሌ

@OLDBOOKSPDF

ራችን ህይወት እንድንኖር እንፈልግም ። ሌሎች በኛ ፈንታ ፤ እኛ ልንኖ ተው የሚገባንን ሞት ሲሞቱ እያዩን ዝም ብንል ፤ ከዚያ በሁዋላ የምን ኖረው ህይወት አላማችንን ፤ ደስታችንንና ተስፋችንን ከመሰረቱ የተለየ ፤ ሌላ ህይወት ይሆናል ። እስካሁን ድረስ በእግዚአብሄርና በሀሊ ናችን ፊት እንደ ተከሰስን ፤ እንደ ተወቀስን የምንኖርበት ህይወት ፤ የልብ ደስታና የመንፈስ ጸጥታ የማናገኝበት ህይወት ፤ በኩራት ፈንታ እፍረት፤ በክብር ፈንታ ውርደት ፤ በድፍረት ፈንታ ፍራት እየተሰማን እድሜያ ችንን ሙሉ ከጸጸት የማንለይበት ህይወት ይሆናል ። እንዲህ ያለ ህይ ወት መኖር አንፈልግም ። እንዲህ ያለ ህይወት ከመኖር አለመኖርን እን መርጣለን ። ስለዚህ ነው ጌታዬ ፤ በራሳችን መከከረን ባለት በተመሰከረ ባቸው ሰዎች ቀንበር የገባን እንጂ ፤ አቃቤ - ህጉ እንዳሉት ከሰው አፍ መወደስንና መሞገስን ፈልገን አይደለም ።

"ባለቤቴና እኔ ከትምርት ቤት እንደ ወጣን የኪ. ገብተን የጀመር ነው ስራ ያሰጠን ደስታ ምድራዊ ሀብትና ድሎት ፤ ወይም ሹመትና ሽል ማት ሊሰጡት የማይችሉ ልዩ ደስታ ፤ ግሩም የሆነ ደስታ ነበር ! ያ ከስ ራችን ያገኘነው ልዩ ደስታ ለልባችን ሙቀትን ፤ ለአምሮዋችን እውቀ ትን ፤ ለጉልበታችን ብርታትን አዩለጠ ፤ ደግሞ እንደ ገና ስራችንን እጥፍ ድርብ አድርገን ብንሰራ ፤ ደግሞ እንደ ገና የምናገኘውን እጥፍ ድርብ ደስታ እንደ ጥሩ መንጽር በፊታችን አቅርቦና አጉልቶ እያሳዩን ፤ እረ ፍት አሳጥቶ ወደፊት ይገፋን ስለ ነበረ ፤ እዚያ ለመድረስ በናፍቆትና በሲቃ እንጣደፍ ነበር ! የኪ. የጀመርነው ስራ ምን እንደ ነበረና እኛም ምን እንደ ሆንን አቃቤ-ህጉ ፤ ዛሬ እንዲህ እንሳቁለው በተናገሩበት አፋ ቸው በቅርቡ ለፍርድ ቤቱና ለተመልካቹ የተናገሩት ሊረሳ ስለማይችል አሁን እኔ መናገር አልፈልግም ። አሁን መናገር የምፈልገው ያን ስራች ንን ፤ ያን የኪ. እንሰራው የነበረውን ስራችንን እዩሰራን እንኖር የነበረው ህይወት ከደስታ ወደ ተስፋ ፤ ከተስፋ ደግሞ ወደ በለጠ ደስታ ፤ ከዚያ ደግሞ ወደ በለጠ ተስፋ እዩተሸጋገርን የኖርነው ፤ በጣም የሚወደድ የማይጠገብ ህይወት እንደ ነበረና ፤ እንዲህ ያለ ደስታና ተስፋ የሚፈራ ረቁበት ህይወት የሚኖሩ ሁሉ ህይወታቸው ፤ ስላማቸው ፤ ሰርቶ የመደ ሰት መብታቸው ፤ ነጻነታቸውና ተስፋቸው የሚጠበቅበት ህግ እንዲከ በር አቅማቸውን ሁሉ አጠራቅመው ይጥራሉ እንጂ ፤ አቃቤ - ህጉ እንዳ ሉት እንዳይከበርና ዋጋ እንዳይኖረው ቢሰብኩ ፤ ራሳቸውን መጉዳት ስለ ሚሆን ፤ ራሳቸውን ለመጉዳት እንደማይፈልጉ የታወቀ መሆኑን ነው ። አሁን መናገር የምፈልገው ፤ አቃቤ - ህጉ እንዳሉት ማህበራቸው ከሁ

@OLDBOOKSPDF

ኩት በቀር ሰላም የማይገኝበትና፣ ከወንጀለኞች በቀር ሰላማውያን የማይኖሩበት እንዲሆን የሚፈልጉ፣ የመኖራቸው አላማ ምን መሆኑን ማወቅ አቅቶዋቸው፣ ዙሪያው ገደል፣ ዙሪያው ጨለማ የሆነባቸውና፣ በህይወት ውስጥ ደስታም ፣ የደስታ ተስፋም የሌላቸው ፣ ቅብዝብዞች ናቸው እንጂ፣ እንደኛ ደስታና ተስፋ ተርፎዋቸው ለሌሎች የሚያካፍሉ አለመሆናቸውን ነው ።

"ስለዚህ ሊቀ አቃቤ-ህግ፣ ባለቤቱንና እኔን፣ ማህበራችን የወንጀለኞች ማህበር እንዲሆን የምንፈልግ፣ የወንጀል መምህሮችና ወንጀለኞችን ለመርዳት በሰው አምሳል ተሰውረን የወረድን የሰይጣን መላክተኞች አስመስለው ለፍርድ ቤቱና ለተመልካቹ ያሳዩት ስእል፣ ፈጽሞ እኛን የማይመስል ነው ።

"ክቡር ሊቀ መንበር፤ ባለቤቱና እኔ በማህበራችው ውስጥ ሰርተው እየተጠቀሙና እየጠቀሙ፣ እየተደሰቱና እያስደሰቱ መኖርን የሕይወት ግባቸውና የማህበርተኝነት መብታቸው አድርገው እንደሚኖሩ ሰላማውያን ሰዎች ሁሉ፣ ህጋዊ መንገድ ተከትለን ወዳቀድነው ህጋዊ ግብ ለመድረስ ስንሰራ ህይወታችንን፣ ንብረታችንን፣ መብታችንንና ነጻነታችንን የሚጠብቅልንን ህግና እንዲያ ያለውን ህግ የሚያስከብረውን ስልጣን፣ በሙሉ ልብ የምናከብርና የማያከብሩትን በሙሉ ሀይላችን የምንቃወም ነን ። ህጋዊ መንገድ ተከትለን ወደ ህጋዊ ግባችን እንዳንደርስ ህጉም ሆነ ስልጣኑ ተጣምመውና ተቆላምመው ህይወታችንን፣ ንብረታችንን፣ መብታችንንና ነጻነታችንን በመጠበቅ ፈንታ፣ የሚያጠፉ ከሆኑ ግን፣ ያን ጊዜ እንዲያ ያሉትን ለማጥፋት የተጣመሙና የተቆላመሙ ህግና ስልጣን እንዲያ ያሉትን በህግና በህጋዊ ስልጣን መሸፈኛ የተሸፈኑ አመጽና ወንጀል፣ ሽፍነው የሚሰሩባቸውን አመጸኞችና ወንጀለኞች ጭምር፣ እስከ መጨረሻው ድረስ ተቃዋሚዎች መሆናችን የማይጠረጠር ነው ።

"ህግና ስልጣን ለተሰሩበት፣ ለተሰጡበት አላማ መቆማቸው ቀርቶ ወንጀል የተጠሙ ወንበዴዎች የሰላማውያንን ሰዎች ህይወት፣ ንብረት፣ መብትና ነጻነት ማጥፊያ መሳሪያዎች የሚያደርጉዋቸው ከሆነ፣ ህጉ ህግ፣ ስልጣኑም ስልጣን መባል አይገባቸውም ። እንዲህ ያሉት፣ ያመጽና የወንጀል መሳሪያዎች መባል አለባቸው ። እንዲህ ያሉትን በህግና በስልጣን ስም መጥራት፣ ለውነተኛው ህግና ለውነተኛው ስልጣን ብርቱ ስድብ ነው ። እንዲህ ያሉትን ህግና ስልጣን ማክበርና ለነሱ መታዘዝ የወንጀለኞች ማህበርተኛ መሆንና ለወንጀል ስራቸው ተባባሪ መሆን ነው ።

"ስለዚህ ክቡር ሊቀ መንበር፤ ስለዚህ፣ እንዲህ ያሉትን በህግና በህጋዊ ስልጣን የተሸፈኑ፣ የወንጀል መሳሪያዎች በመተላለፋችን እንደ ህግ

@OLDBOOKSPDF

ተባባሪዎች፣ እንዲህ ያሉትን በሀጋዊ ባለስልጣን መሸፈኛ ተሸፍነው ወንጀል ሲሰሩ የኖሩ አመጸኛ በመግደላችን እንደ ወንጀለኞች ልንቆጠርና አቃቤ - ሀጉ የጠዩቁት ቅጣት ሲፈጸምብን አይገባም ።

'ሀቀተሰ ይሙት' የተሻረ፣ የአሪት ህግ ነው፤ ክቡር ሊቀ መንበር! የገደለ፣ ወይም ያስገደለ በመገደሉ፣ ይሁን በማስገደሉ ብቻ ወንጀለኛ አይሆንም! ወንጀለኛ የሚሆነው የገደለበት፣ ወይም ያስገደለበት ምክ ናያት ተመርምሮ ወንጀለኛ የሚያደርግ ሆኖ ሲገኝ ነው። የገደለ ሁሉ ወንጀለኛ ቢሆን ኖሮ፣ አመጸኞችን፣ ወንጀለኞችንና የነጻነት ጠላቶች የሆኑትን፣ በጦር ሜዳ እዩተዋጉ የሚገድሉ ጀግኖች ሁሉ፣ በመጀምና በመሸለም ፈንታ ወንጀለኞች ሆነው ወደ ስቅላት በሄዱ ነበር! ያስገደለ ሁሉ ወንጀለኛ ቢሆን ኖሮ፣ ይህ ፍርድ ቤት ከተቋቋመ ጀምሮ ያስገ ደላቸው ወንጀለኞች እጅግ ብዙ ስለሆኑ፣ ነፍስ በማስገደል ወንጀል በተከሰሰ ነበር! ነገር ግን እኒያ ጀግኖች እዩተዋጉ የገደሉዋቸው፣ ወደ ፊትም የሚገድሉዋቸውና ይህ ፍርድ ቤት እዩፈረደ ያስገደላቸውም ሆኑ ወደፊት የሚያስገድላቸው አመጸኞች፣ ወንጀለኞችና የነጻነት ጠላ ቶች በመሆናቸው ገዳዮቹም ሆኑ፣ አስገዳዮቹ ወንጀለኞች አይባሉም ።

"ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪባ፣ የብዙ ሰላማውያንን ነፍስ ያጠፉ ወን ጀለኛ፣ የብዙውን ህዝብ ሀብትና ንብረት የዘረፉ ቀማኛ፣ ያንዱን ወረዳ ህዝብ በሙሉ መብትና ነጻነት ገፍፈው በፍጹም ባርነት ያኖሩ የነበሩ ግፈኛ፣ ህግና ስልጣን የሚባሉት፣ የራሳቸውን ጥቅም የሚጠብቁት ብቻ እንጂ ሌላ እንደሌለ ቆጥረው፣ ለህግም ሆነ ለበላይ ባለስልጣን የማይ ታዘዙ አመጸኛ የነበሩ ለመሆናቸው የየኪ ህዝብ በሙሉ ይመሰክራል! እንዲህ ያሉትን ቀማኛ፣ እንዲህ ያሉትን ግፈኛ፣ እንዲህ ያሉትን አመ ጸኛ፣ እንዲህ ያሉትን ወንጀለኛ፣ ፍርድ ቤት ማቅረብ ቢቻል በፍርድ፣ ፍርድ ቤት ማቅረብ ባይቻል በጦር ሀይል ወግቶ ማስገደል ፍትሮት መሆኑ ንም የሚክድ እንደሌለ እውቅ ነው ።"

"እንግዲያስ ክቡር ሊቀ መንበር፤ እንግዲያስ፣ እንዲህ ያሉትን በፍ ርድ፣ ያለዚያም በጦር ሀይል ተወግተው ሊገደሉ የሚገባቸውን ወንጀ ለኛ፣ እንዲህ ያሉትን ከመገደል የሚያመልጡበት ትንሽ እንኳ ቀዳዳ የሌላቸውን አመጸኛ፣ ባለቤቴና እኔ በመግደላችን፣ "ፍርድ ቤት፣ ወይም ወታደር ታገዘ፥ ሊሰራው የሚገባውን ሰርታችሁዋል " ወይም በሌላ አነጋገር፣ "የፍርድ ቤትና የወታደር ስልጣን ተሻምታችሁዋል " ተብ ለን በስልጣን መሻማት እንጠዩቅ እንደሆን እንጂ፣ አቃቤ - ሁጉ እንደ ጠዩቁት ለነፍሰ - ገዳይ ወንጀለኞች የተመደበ፣ ማናቸውም ቅጣት አይፈጸምብንም ።"

@OLDBOOKSPDF

"እቶ ጥላሁን ፤ ያቀረቡትን መከላከያ ህግ ይደግፍልዎ እንደሆን የሚደግፈውን ህግ ቢጠቅሱልን ደስ ይለናል ። ከዚህ ሌላ አንዳንድ ጥያቄዎች ልጠይቅዎ እፈልጋለሁ " አሉና የቀኙ ዳኛ ፣ ጥያቄያቸውን አስከተሉ ። "መቸም መቼም ፡ ቀኛዝማች ዳኘ ፡ እርስዎ እንደሚሉት ወንጀለኛና አመጸኛ የነበሩ ለመሆናቸው ከርስዎ ወሬ ሌላ ምንም ማስረጃ የለ ፤ ይኖር እንደሆነም . . . ለዚህ ፍርድ ቤት ገና አልቀረበ ። ወንጀለኛስ ቢሆኑ ፡ የምትቀጡዋቸው ባለቤትዎና እርስዎ ናችሁ ? ወንጀለኞችን በያሉበት ያገኛችው ሁሉ የሚገድላቸውስ ከሆነ ፣ የፍርድ ቤት መኖር ምን ያስፈልግ ኖሮዋል ?"

"እርግጥ ፡ ወንጀል የሰሩትን ለመቅጣት ሆነ ባሰት ፡ ወይም በስህተት ፡ በወንጀል የተከሰሱትን ለማዳን የፍርድ ቤት መኖር አስፈላጊ ነው ። ነገር ግን ለተከበሩት ዳኛ ለማመልከት እንዲፈቀድልኝ የምለም ነው ፤ ፍርድ ቤት የቅጣትም ሆነ የማዳን ፍርድ መስጠት የሚችለው ፤ ተከሰሰው በሚቀርቡለት ብቻ እንጂ ባልቀረቡለት ፣ እንደ ቀኛዝማች ዳኘ ከህዝብ የዘረፉትን ብዙ ሀብት ምሽግ አድርገው ፡ ፍርድ ቤት እንዳይደርስባቸው በሩቅ በሚከላከሉት ላይ አለመሆኑን ነው ! ቀኛዝማች ዳኘ የሚከሰሱዋቸውን እያስገደሉ ፣ የሚሰሩት ወንጀል ጭምጭምታ ቀሰምቶ ሊጣሪዎች ቢላኩባቸው ፡ ለነሱ ከዘረፉት ገንዘብና ርስት እያካፈሉ ፤ ወደ ፍርድ ቤት እንዳይቀርቡ ፡ ዳኞችን ጠበቆች አድርገው የሚኖሩ ሰው ነበሩ ። ስለዚህ እንዲህ ያሉትን ከህግና ከፍርድ ቤት ተሸሽገው ወንጀል ሲሰሩ የሚኖሩ ወንጀለኛ ፤ ከተሸሸጉበት አውጥቶ ለፍርድ ማቅረብ የማይቻል መሆኑን በርግጥ የተረዳ ፡ እዚያው ባሉበት ቢገድላቸው ወንጀል ሲሰራ እንዳይኖር ፡ የወንጀል ምንጭ እንዲደርቅ አደረገ እንጂ ፡ ወንጀል ሰራ አይባልም !" አለ ጥላሁን ።

"ታዲያ እንግዲህ ማንም ሰው ሊገድለው ያሰበውን ሰው ፍርድ ቤት አቅርቦ ምስክር ሳያስመሰክር ፡ እንዲሁ 'ወንጀለኛ ነው' እያለ እያወራ በያለበት የሚገድል ከሆነ ፡ የምንኖርበት ማህበር ምን አይነት ማህበር የሚሆን ይመስልዎታል ? ሁሉም ቢውል የማያድር ፡ ቢያድር የማይውል እየመሰለው ከሞት ጋር ተፋጥጦ በፍራትና በማያቋርጥ ጩከኝ ቅዠት ውስጥ የሚኖርበት ፡ ሁሉም ፣ 'ሳልቀደም ልቅደም' እያለ እርስበሱ የሚተላለቅበት ፡ የርጉማን ማህበር የሚሆን አይመስልዎትም ? እንዲህ ያለውንስ አሳብ የሚደግፉና በግልጽ የሚሰብኩ ሰዎች ፡ እቃቡሀጉ እንዳሉት ለማህበሩ ጠቅላላ ደህንነት መሰረት የሆነውን ህግና ስራት ማፍረስ የሚፈልጉ ፡ አደገኞች መባል የሚገባቸው አይመስልዎትም ?" አሉ የቀኙ ዳኛ ።

@OLDBOOKSPDF

“የተከበሩት ዳኛ ያሉት ልክ ነው ፤ ማንም ሰው ሲገድለው ያሰበውን ‘ወንጀለኛ ነው’ ብሎ በማውራት ብቻ ፣ እንዲገድል የሚፈቀድ ቢሆን ኖሮ፣ ማህበራችን እስበሳቸው እዮተጻደኑ የሚናፏ አራዊት እንደሚኖሩበት እንጂ እንደ ሰዎች መኖሪያ ፣ እንደ ሰዎች ማህበር ሲቆጠር የማይገባው በሆነ ነበር ! ማህበራችን እንዲህ እንዲሆን የሚፈልጉ ሰዎችም እጅግ አደገኞች ስለሆኑ ፣ በማህበራችን ውስጥ ቦታ ሲኖራቸው ባልተገባ ! ነገር ግን ጌታዩ ! ነገር ግን ካምሳ ሽህ የሚበዛ ፣ ያንድ ወረዳ ሕዝብ ባንድ ላይ ፣ ድምጹን ከፍ አድርጎ እንዱን ሰው በነፍሰ - ገዳይነት ፣ በዘራፊነት ፣ ባመጸኛነት ፣ ባይነተኛ ወንጀለኛነት ሲከሰስ ፣ የዚያ ሁሉ ህዝብ እግዚአታ ፣ የዚያ ሁሉ ህዝብ ምስክርነት እንደማይበቃ ሁሉ ፣ ካምሳ ሽህ ህዝብ ምስክርነት ያንድ ሰው ምስክርነት ሲታመን እንደሚገባው ሁሉ ፣ በዩጊዜው አንዳንድ ፣ በገንዘብ እዩተገዛ እሱት የሚመሰክር አጣሪ እዮተላከ እሱ በመሰከረው ፣ ወንጀለኛው የወንጀል ስራውን እንዲቀጥል የተደረገ እንደሆነ ፣ ለበላይ አቤት ያለው ህዝብ አቤት ማለቱ እንደ ወንጀል ተቆጥሮበት መሪዎቹ ህይወታቸውን ፣ ተከታዮቹ ንብረታቸውን ፣ መብታቸውንና ነጻነታቸውን እንዲያጡ የተደረገ እንደ ሆነ ፣ ያን ጊዜ ፣ ለበላይ አቤት ማለት የወንጀለኛውን ጨካኝ ልብ የባሰውን የሚያጨክነው ፣ ወንጀለኛውን ፍርድ ቤት አቅርቦ በፍርድ መበቀል በጭራሽ የማይሆን መሆኑ ሲረጋገጥ ፣ ያንጊዜ ፣ ጌታዩ ያንጊዜ ፣ የተበደለ ‘ፍርድ በጄ’ ቢል ወንጀል ስራ ይባላል ? አይባልም ! በቀኛዝማች ዳኘ የተፈጸመው ይህ ነው ፤ይህም የተከበሩት ዳኛ እንዳሉት ‘ማንም ሰው ሲገድለው የፈለገውን ሰው ወንጀለኛ ነው’ ብሎ አውርቶ መግደል አይባልም ” አለ ጥላሁን ።

“ አቶ ጥላሁን ፤ ባለቤትዎና እርስዎ ቀኛዝማች ዳኘን የገደላችሁዋቸው ካምሳ ሽህ የሚበዛ ፣ ያንድ ወረዳ ህዝብ ያሉት ወክሎዋችሁ ነው ? ያምሳ ሽህ ህዝብ መሳሪያዎች ሆናችሁ ነው ? ያ አምሳ ሽህ ህዝብ ያሉት ለሰራችሁት ወንጀል ያልፍላችሁዋል ? ” አሉ የቀኙ ዳኛ ፣ እንደ መቆጣት ብለው ።

“ ጌታዩ ! ቀኛዝማች ዳኘን ለመግደል ህዝቡ አልወከለንም ። አመጸኛውን ፣ ወንጀለኛውን ፣ ቀኛዝማች ዳኘን ገድለን ህዝቡን ነጻ ማውጣታችን እንደ ህዝብ መሳሪያዎች የሚያስቆጥረን ከሆነ ፣ መሳሪያዎች መባልን እንቀበላለን ። ነገር ግን የገደልናቸው እኛም የህዝቡ አካል እንደ መሆናችን ፣ እንደ ህዝቡ ሰርቆ የመደሰትና የማስደሰት መብታችንን ስለ ቀሙን ፣ እንደ ህዝቡ ያመጽ ስራቸውን ስለ ፈጸሙ

@OLDBOOKSPDF

ብን ነው ። ስለዚህ በህዝብ ፤ በመንግስትና በግዚአብሄር ላይ ወን
ጀል ሲሰሩ የኖሩትን ወንጀለኛ ፤ ቆኘገጣኙ ዳኝን ገድሎ የየኪን
ህዝብ ተቆራኝቶት ከኖረው ጨካኝ መቅሰፍት መገላገል ወንጀል ከሆነ፡
ለሰራነው አላፊዎች እኛ ራሳችን ነን እንጂ ህዝቡ አላፊ አይሆንም”
ብሎ ጥላሁን እንደ ጨረሰ ፤ ዳኞች በዝቅተኛ ድምጽ እስበላቸው ሲመ
ካከሩ ፡

“ እግዚአብሄር ያሳያችሁ ፤ ኧረ እግዚአብሄር ያሳያችሁ ! እግዚ
አብሄር ያሳያችሁ ፤ ክርስቶስ ያመልክታችሁ ! ምነው የመንግስትና
የእግዚአብሄር አደባባይ ትንሽ ትልቁ ፤ እኖቂ አላዋቂው ፤ ሁሉም
አቤቱታውን አሰምቶ ፍትርት የሚያገኝበት አደለም ? እንዴት እስር
ቀን ሙሉ በመንግስት አደባባይ እዬተንከራተትሁ ፍርድ የሚገኝበ
ትን ፤ መንገዱን እንኳ የሚያሳዬኝ ልጣ ?” አሉ አንድ ዘለግ ያሉ
ሽበታም ሽማግሌ ፤ ተጨናንቆ ከቆመው ተመልካች መሀከል ድምጻ
ቸውን ከፍ አድርገው ።

“ምነው ጸጥታ አስከባሪዎች ጤነኞች ያልሆኑ ሰዎች ለምን ቃስ
ገባላችሁ ? ካስገባችሁስ በሁዋላ ጸጥታ ሲያውኩ እያያችሁ እንዴት
ዝም ብላችሁ ትመለከታላችሁ ? እባካችሁ ሰውዬው ጤነኛ አይመስ
ሉምና ወደ ውጭ . . . ብትሉዋቸው ይሻላል !” አሉ ሰብሳቢው ዳኛ፣
በጸጥታ አስከባሪዎች ላይ ቅርታቸውን እያሳዩ ።

“ ኧረ ጤነኛ ነኝ ጌታዩ ፤ እኔስ ጤነኛ ነኝ ። የየኪ ወረዳ ፍርድ
ቤት መላክተኛ ነኝ ! ” ሲሉ ሽማግሌው “ እባባ ፤ እባባ ” እሉ
ሶፊያና ጥላሁን ፤ ባንድ ላይ እንደ ተማከሩ ፤ ሁለቱም በመገረም እፋ
ቸውን ይዘው ወደ ባላምባራስ ጉደታ ራጎ እያዩ ። “ ጌታዩ ፤ የየኪ
ወረዳ ፍርድ ቤት ይሆን ጦማር ሰጥቶ ፤ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ፍሬ
ሲዳ በጃቸው ካልሆነ ምንም ቢሆን ፤ ለማንም እንዳትሰጥ ስላለኝ ፤
“እባካችሁ ፍሬሲዳውን እሳዩኝ ” እያልሁ የጠዬቅሁዋቸው ሁሉ
‘ ፍሬሲዳ የሚባል እዚህ የለም ’ ስላሉኝ ይኸው እስር ቀን ሙሉ
ከዚህ አደባባይ ሳልለይ እንከራተታለሁ ። ዛሬ ቢጨንቀኝ ፤ የመጣ
ሁበት ጉዳይ ስለናቶ ጥላሁን ፈይሳ ፍርድ መሆኑን የነገርሁዋቸው
ሰዎች ፤ ፍርዱ ዛሬ እዚህ እዳራሽ የሚሰጥ መሆኑን ስለ ነገሩኝና ሰው
እንዲሁ ባያስፈቅድ ቢገባ እይቻ እኔም እዬፈራሁ ገና አሁን ገባሁ ።
ጌታዩ ቢጨንቀኝ ነው ፤ ባልጨነቅ አልደፍርም ነበር ፤ ይቅርታ አድ
ርጉልኝ ” እሉ ባላምባራስ ጉደታ ቀጠሉና ፤ አንድ ትልቅ አንሼ
ሎጥ ከራሳቸው ከፍ አድርገው ይዘው ቀኝና ግራ እያወዛወዙ ። ያን
ጊዜ የተመልካቹ ሀምሀምታ እዳራሹን ሞላው ።

@OLDBOOKSPDF

"እባክህ ተቀበላቸው ፤ እንቬሎፑን ተቀበልና ወዲህ በለው" አሉ ሰብሳቢው ዳኛ ፤ ተሳሳኪውን ። ቀደም ብለው ያልታረመ ንግግር በመናገራቸው መጸጸታቸው ከፊታቸው ይታወቅባቸው ነበር ።

"ክቡር ሊቀ መንበር ፤ ይህ ከየኪ ወረዳ ፍርድ ቤት የተላከው ... አሁን እዚህ ለፍርድ ቤቱ እንዲነበብልኝ እጠይቃለሁ" አለ አቃቤ - ህጉ ወንድይራድ ፤ ዳኞች በተቀበሉት መልእክት ላይ እስበሳቸው በዝቅተኛ ድምጽ ሲነጋገሩ ፤ ያ መልእክት ከፍርድ ቤት የመጣ ከሆነ ሳይረዳ አይቀርም ብሎ ገምቶ ።

" ተከላሾች የምትቃወሙበት ምክናያት አላችሁ ? " አሉ ሰብሳቢው ።

"የለንም" ሲል ጥላሁን ፤ ሰብሳቢው ማንበብ ጀመሩ ።

" በኢሉባቦር ጠቅላይ ግዛት የየኪ ወረዳ ፍርድ ቤት

" ለኢትዮጵያ ን. ነ. መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፤

" አዲስ አበባ ።

" ጥላሁን ፈይሳና ሶፊያ ሙላት የሚባሉት ባልና ሚሽት ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሬሳን ገድለናል ብለው ፡ በራሳቸው በመመስከራቸው ለቅጣት ፡ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ፡ ተይዘው በስር ቤት መቆየታቸው በራዲዮና በጋዜጣ እንደ ተነገረ ፡ የየኪ ሕዝብ በሙሉ በጥሩንባ ክተት ብሎ የኪ ከተማ ተሰበሰበ ። ያኔለት በክተት የተሰበሰበው ህዝብ ሲታይ አንድ ሰው በቤት የቀረ አይመስልም ነበር ። ከዚያ የየጎሳው መሪዎች በዩተራ እዛፍ ላይ እዬወጡ የጥላሁንና የሶፊያን ሞት ፡ ወይም ሌላ ቅጣት የየኪ ህዝብ ሞትና ቅጣት መሆኑን የተሰበሰበው ህዝብ እንዲሰማቸው ፡ ድምጻቸውን በጣም ከፍ አድርገው ፡ እዬጮሁ ከተናገሩ በሁዋላ የየኪ ወረዳ ህዝብ በሙሉ በያጥቢያው የሶስት ቀን አዘን እንዲያደርግ ተወስኖ ስብሰባው ተፈታ ።

ከዚያ የእያንዳንዱ አጥቢያ ህዝብ ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ተሰብስቦ ፡ ባማካይ ቦታ የደመራን እሳት የመሰለ እያቃጠለ ፡ እንዳገሩ ልማድ እዬበላና እዬጠጣ በከበሮ ፡ በጭብጨባና በዜማ ተሰልፎ ፡ እሳቱን እዬዞረ ሶስት ቀንና ሌሊት ትልቅ አዘን ሲያደርግ ሰነበተ ። የዛቲት አስራ ሰባት ቀን የወረዳው ህዝብ በሙሉ እንደ ገና በጥሩንባ ክተት ብሎ ፡ የጦር መሳሪያ ያለው የጦር መሳሪያውን ፡ የሌለው ዱላውን እዬያዘ መጥቶ ፡ የኪ ከተማ ላይ ሲሰፍር ፡ ለጊዜው በመንግስት ባለስልጣ

@OLDBOOKSPDF

ኖች ላይ ክፉ ያሰበ መስሎኝ ሰግቶኝ ነበር ። እውነትም በሁጥላ እንደ ሰማነው ጥላሁንና ሶፊያ እስኪሰቀቱ ጥቂት የመንግስት ባለስልጣኖች መያዣ አድርጎ ለማቆየት አሳብ ቀርቦ ነበር ። ነገር ግን ከረዥም ክር ክር በሁጥላ አብዛኛው ህዝብ ስላልደገፈው ቀረ ። በዚያ ፈንታ ፣ በመጀመሪያ ደረጃ አቤቱታውን ለመንግስት አቅርቦ መንግስት የሚሰጠው መልስ ከታዩ በሁጥላ ፣ እንደ ገና መመካከር የሚያሻ በመሆኑ ስለ ተስማማ ፣ አስር ሽማግሎች መርጦ ፣ ‘ የየኪ ወረዳ ህዝብ ለመንግስት የሚያቀርበው አቤቱታ ስላለው የወረዳው ገገር ፣ የፍርድ ቤቱ ዳኛና ሌሎች የመንግስት ሹማምንት ወጥታችሁ ተቀብላችሁ እንድታስተላልፉለት ይጠይቃል ’ ብሎ ስለ ላከብን ፣ በወረዳው ገዥ መሪነት ወደ ሰፈረበት ሄደን ፣ ከዚያ ጋር አብረው የሚገኙትን ሶስት ሰነዶች ተቀበልን ።

ሰነዶቹ በቀጥታ ከህዝቡ እንደ ተቀበልናቸው በመሆናቸውና ፣ ያልተቀነሰባቸው ፣ ወይም ያልተጨመረባቸው ለመሆናቸው ምስክር ይሆኑ ዘንድ ፣ በያንዳንዳቸው ስር የዚህ ፍርድ ቤት ማህተም እዬታተመ ፣ የኔ ፣ የዳኛው ፊርማ ተፈርሞባቸዋል ። ሁለተኛ ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ ለባላምባራስ ፉዋዮ ፊዴ በጻፉት ላይ የሚታዩት ማህተምና ፊርማ ፣ አብረን ስንሰራ ሁላችን የምናውቃቸው ፣ የራሳቸው የቀኛዝማች ዳኛቸው መሆናቸው ተረጋግጦዋል ። ሶስተኛ በኑዛዜው ላይ የሚታዩት ፣ የፖሊስ መስሪያ ቤት ማህተምና ያዛዡ ፊርማም ፣ እዚህ በሰራሁበት ጊዜ ሁሉ ደህና አድርጌ የማውቃቸው ፣ ትክክለኞች መሆናቸውን አረጋግጣለሁ ። እንዲሁም በዚያው በኑዛዜው ላይ የሚታየው የቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ ማህተም ማህተማቸው ነው ። በኑዛዜው ላይ የሚታዩው ያውራ ጣት ፊርማ ቀኛዝማች ዳኛቸው በመድከማቸው እንደ ተለመደው በጽሁፍ መፈረም ስላልቻሉ ፣ የፈረሙት መሆኑን ያናዘዙዋቸው ሶስት ፖሊሶች ምለው የመሰከሩ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ ። ”

ፊርማ አበጋዝ ሳህሉ ፤ የየኪ ወረዳ ዳኛ

ማህተም በኢሉባቦር ጠቅላይ ግዛት የየኪ ወረዳ ፍርድ ቤት ፤

የኪ ።

ከየኪ ወረዳ ፍርድ ቤት የተጻፈው ተነብቦ ሲያልቅ ፣ ተመልካቹ ሁሉም በየጎረቤቱ ቀስ እያለ የሚያደርገው ትችት እስበሱ ሲማታ ጎልቶ አዳራሹ ውስጥ የሚያደነቁር ጫጫታ ተነሳ ። ሶፊያና ጥላሁን ፣ የየኪ ህዝብ እነሱ በሌሉበት ያደረገላቸው የፍቅርና ያንድነት መግለጫ እሱ ራሱ ልብ የሚነካ ከመሆኑም ሌላ ፣ የኪ የኖሩትን የደስታ ህይወት

@OLDBOOKSPDF

መታሰቢያ ይዞ መጥቶ ፤ በፊታቸው ዘርግቶ አሳያቸውና ፤ አይኖቻቸው እንባ ሞልተው ፤ አንገታቸውን እንደ ደፉ ዝም ብለው ቆመው ይመለከቱ ነበር ። ከዚያ ተመልካቹ ዝም እንዲል ሰብሳቢው ዳኛ ጠረጴዛውን ደጋግመው ከመቱ በሁዋላ ፤ ሁሉም ጸጥ ሲል ፤ ከየኪ ህዝብ ለኢትዮጵያ መንግሥት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጻፈውን ማንበብ ጀመሩ።

“ የተላከ ከየኪ ወረዳ ህዝብ ፤

ይድረስ ለኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፤

አዲስ አበባ ።

ጥላሁን ፈይሳና ሰፊያ ሙላት ፤ “ ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍረሳን ገድላችሁዋል ” ተብለው ሊገደሉ ተይዘው መታሰራቸውን ሰማን ! ለየኪ ህዝብ ቀኛዝማች ዳኛቸው በሽታው ፤ ጥላሁንና ሰፊያ መድኃኒቱ ነበሩ ! ታዲያ መድኃኒቱ በሽታን ስላጠፉ ይጥፉ ይባላል ? ይህ ተደርጎ የማያውቅ ጉድ ነው ! ቀኛዝማች ዳኛቸውም ፤ እኛም የመንግስት ዜጎች ነን ። ታዲያ መንግስት ከብዙ ሺህ ንጹህ ዜጎች አንድ ቀማኛ ፤ አንድ ወንጀለኛ ዜጋ ይመርጣል ማለት ነው ? ይህ ተሰምቶ የማያውቅ ጉድ ነው ! ቀኛዝማች ዳኛቸው እድሜያቸውን ሙሉ በሽፍትነት የኖሩ በመሆናቸው ፤ የሰው ሀብት ከመቀማትና ነፍስ ከማጥፋት በቀር ፤ ደህና ነገር ማድረግ ስለማያውቁ ፤ አስራ ስምንት አመት ሙሉ በየኪ ህዝብ ላይ በግዛት ስም ፤ መንግስት የማያውቀው ፤ የማያቋርጥ ዘመቻ አድርገው ፤ አስራ ሰባት ሰዎች ገድለው ራሳቸውን ላራቂት የጣሉ ፤ አርባ አምስት ሰዎች አስደብድበው አካላተ - ስንኩሎች አድርገው ያስቀሩ ፤ ሰማንያ ጋሻ መሬት ከባለርስቶች ወርሰው ፤ ለበላይ አቤት ስላሉ ብቻ አገራቸውን አስለቅቀው ያስደዱ ፤ የቀረውን ተስፋ በመቁረጡና በመፍራቱ ግፋቸውን ተሸክሞ የተቀመጠውን ጠቅላላ ህዝብ ፤ ከሰውነት ደረጃ አውርደው በንብረቱ ፤ በጉልበቱና በህይወቱ ለማዘዝ ፈቃድ የሌለው ፤ የሳቸውን ፈቃድ ብቻ ለመፈጸም መሳሪያ ሆኖ የሚኖር መንጋ አድርገውት የኖሩ አመጸኛ ነበሩ ! ታዲያ እንዲህ ያሉትን መቅሰፍት ያጠፉ ሰዎች ይሾማሉ ይሸለማሉ እንጂ ይገደላሉ ? እንዲህ ያለው ተደርጎ የማያውቅ ፤ የጉድ-ጉድ ነው ? ጥላሁንና ሰፊያ የየኪን ህዝብ እያስተማሩ ፤ በስራ እየመሩ ፤ በገንዘባቸው እያከሙ ፤ መሬት ለሌላቸው የራሳቸውን መሬት ሸንሽነው ካከፋፈሉት ሌላ ፤ ትርፍ ካላቸው ሰዎች እየገዙና እየለመኑ እያከፋፈሉ ፤ ኑሮውን አሻሽሎ እንዲኖር ለማድረግ ይታገሉ የነበሩ ናቸው ! እነሱ በተዋቅ ማግስት

@OLDBOOKSPDF

ወደ ነበረችበት እስክትመለስ ድረስ ፣ የኪ. በሙሉ ኢሉባቦር ወደር የሌላት ፣ የሰው ሁሉ መደነቂያ ሆና ነበር ! እነሱ በተዋት ማግስት ትዝታውን ብቻ ትቶ እስኪጠፋ ድረስ ፣ ጥላሁንና ሶፊያ ለየኪ. ህዝብ የሰሩት ስራ እጹብ -ድንቅ ነበር ! ነገር ግን እንዲያ ያለው የጥላሁንና የሶፊያ የተቀደሰ ስራ ለቆኛዝማች ዳኘ አባማ ተቃራኒ ስለሆነ ፣ ወንጀለኛው ፣ ቀማኛው ፣ ቆኛዝማች ዳኘ ከሱ በፊት ብዙዎችን እቤታቸው አስረው እዱደበደቡ አሰቃይተው እንደ ገደሉ ፣ ጥላሁንንም ሲገድሉት ታጥቀው ሄደው ለህይወቱ ሲከላከል ፣ እግዚአብሄር ቀኙን ሰጥቶት እሱን ሊገድሉበት በያዙት ፣ የገዛ መሳሪያቸው ገደላቸው ! ይህ ታምር አደለም? እንዲህ ያለው የግዚአብሄር ፍርድ አይባልም ? ይህ የግዚአብሄር ፍርድ ነው ! ታዲያ ከግዚአብሄር ፍርድ በላይ ፍርድ አለ ? ቀኛዝማች ዳኘ የግዚአብሄርንም ፣ የመንግስትንም ህግጋት የማያከብሩ ፣ በመንግስት ስልጣንና በሰው ህይወት ሲጫወቱ የኖሩ ወንጀለኛ ስለሆኑ ፣ እሳቸውን የገደሉ ሰዎች መሸለም እንጂ መገደል አይገባቸውም ! እንዲህ ያሉትን የወንጀል ሁሉ ባለቤት የሆኑ ሰይጣን የገደሉ ሰዎች በመሸለም ፈንታ መግደል፣ ወንጀለኞችን መርዳት አስመስሎ የሚያሳይ ፣ የጉድ ጉድ ነው ! ጥላሁንና ሶፊያ ከፉ አውሬ ፣ ጨካኝ ወንጀለኛ ገድለው የየኪን ህዝብ ከስቃይ ስላሳረፉ ፣ መሾምና መሸለም እንጂ መገደል አይገባቸውም ! ስለዚህ ሲሆን የጠፋውን መልካም ስራቸውን እንደ ገና እንዲሰሩና የየኪን ህዝብ እንዲረዱ የኪን እንዲሾሙና ወዲህ እንዲመለሱ ይደረግልን ። ይህ የማይሆን ከሆነም እንዳይገደሉ ልጅ-አዋቂው ፣ ሴት - ወንዱ ባንድነት ምጥንታችንን እናቀርባለን !

ቀኛዝማች ዳኘቸው በሞቱበት ሌሊት ፣ ምንም እንኳ ያንጊዜ ገዳያቸው ባይታወቅ ፣ ማንም ይሁን ፣ ከሱ ጋር ህዝቡ ተባባሪ መሆኑንና የበቀል ስሜቱን ለመግለጽ ፣ በጥሩንባ ' ክትት ' ብሎ ፣ በዱቡ ታው የነበረ ንብረታቸውን በመዝረፍና ቢወሰድ የማያገለግለውን በማጥፋት ተካፋይ ያልሆነ አይገኝም ! ቤታቸውን እንኳ ፣ ከመበቀል ምልክትነቱም ሌላ ፣ ምናልባት ክፉ ውቃቢያቸው እዚያ ተሸሽጎ ቆይቶ ፣ በሳቸው ምትክ በሚመጣው ሹም አድሮ እንደሳቸው እንዳያሰቃየን ፈርተን አቃጠልነው ! በቦታው ርቀት ምክናያት በለቱ ያልደረሱ ሁሉ ፣ ሁዋላ መጥተው መተባበራቸውን ለማስመስከር ፣ በተቃጠለው ቤታቸው አመድና በሬሳቸው ላይ ደንጋይ ያልወረወሩ አይገኙም ! ሁዋላም ሬሳቸውን ፣ እሳቸው የገደሉዋቸውን ሰዎች ሬሳ ሲያደርጉት እንደ ኖሩ ፣ እንዳይቀበር ከልክለን ፣ እዩቶራረጥን አውሬ እንዲበላው አደረግን ። ይህ ከመግደል አይከፋም ? ይከፋል ።

@OLDBOOKSPDF

ስለዚህ ወንበዴዎች ፣ ‘ ቀኛዝማች ዳኘን መግደል ወንጀል ነው’ ብሎ መንግስት ጥላሁንንና ሰፊያን የሚገድል ከሆነ ፡ የየኪ ህዝብ፣ በሙሉ ተባባሪዎቻቸው ፣ ለሰሩት ስራ ተካፋይ ስለ ሆኑ ፣ ጦር ልክ የየኪን ህዝብ በሙሉ ያከራጀው ! በሌላ ቅጣት የሚቀጣቸው እን ደሆነም ፣ እኛንም በሚቀጣበት ቅጣት ይቅጣን ! ከዚህ ሌላ የሚጠቀቅ ነገር ቢኖር ፣ በየኪ ህዝብ ስም እንዲመልሱ ባላምባራስ ጉዴታ ዬን ወኪላችን አድርገን ልከናልና ፣ የባቸው ቃል ቃላችን ነው ! ከዚህ ጋር ቀኛዝማች ዳኘን ጥላሁን ቀድሞ ባይገድላቸው ኖሮ፣ ያኑ ሌሊት እሱን ገድለው ፣ ሚሽቱን ሰፊያን እቁባት ለማድረግ ወስ ነው እንደ ነበረ የሚያሳይ፣ ከሞቱ በሁዋላ ንብረታቸው ሲዘረፍና ልብ ሳቸው ሲገፈፍ በኪታቸው ውስጥ የተገኘውን ፣ ፊርማቸውና ማህተማ ቸው ያለበትን ወረቀት እንድትመለከቱት ልከናል ። ሁለተኛ ቀኛዝ ማች ዳኘ ቆስለው በወደቁበት ለፖሊሶች የሰጡት ኑዛዜ ፣ ባውራ ጣታ ቸው እንደ ፈረሙትና ማህተማቸው እንደ ታተመበት ፣ ህዝቡ ጥሰ ገብቶ ተኩስ ሲከፈትና ዘረፋ ሲጀመር ፣ በግርግሩ ፖሊሶች ጥለውት ስለ ተገኘ ፣ እንድትመለከቱት ልከነዋል ።”

የየኪ ወረዳ ህዝብ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት የጻፈው ተነብቦ ካበቃ በሁዋላ ፣ ቀኛዝማች ዳኛቸው ለባላምባራስ ፉዋቶ ፊዴ የጻፉላቸው ተነበበ ።

“ የተላከ ከቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሬሳ ፤

ይድረስ ለባላምባራስ ፉዋቶ ፊዴ ።

እንደምን አድረህ ውለሀል ? እኔ ቸሩ አምላክ ይክበር ፣ ይመስገን ደህና ነኝ ። ያን አስቸጋሪ ወጠጤ ፣ ያን ጥላሁን ፈይሳን ፣ እስካ ሁን ሲያስቸግረኝ የኖረው አልበቃው ብሎ ፣ ትናንት በጉባኤ ስለ ሰደ በኝ አስሬዋለሁ ፤ ሌሊቱን እንደሱ ያሉት አስቸጋሪዎች ሄደው ወደማ ይመለሱበትና እዚያ ማንንም በማያስቸግሩበት ልልከው ቆርጫለሁ ። የመቃብር ወግ እንኳዋ ባይደርሰው ፣ ወሬው እንዲሁ የውሀ ሽታ ሆኖ ይቀራል ! ሞቱን ከኔ ፣ ከጣሰውና ከማሞ ሌላ ፣ የምታውቁ አን ተና አውሬዎች ብቻ ናችሁ ። መቸም እኔና እነጣሰው ለራሳችን ስንል፣ አውሬዎች የሰዎችን ቋንቋዋ ስለማይናገሩ ፣ ይህ ምስጢር ወጥቶ ቢገኝ ባንተ በኩል ካልሆነ ፣ ‘ በኛ ፣ ወይም ባውሬዎች በኩል ወጣ’ ሊባል አይችልምና ፣ እንድትጠነቀቅ አጥብቄ አደራ እልሀለሁ ።

ሁለተኛ ዛሬ ከኩስ ሌሊት በሁዋላ ፣ ጥላሁንን ፣ አስናብተን ፣ ላውሬዎች ሰጥተን ስናበቃ ፣ ጣሰውና ማሞ ሚስቱን ይዘው ወዳንተ

@OLDBOOKSPDF

ይመጣሉና ፡ ተቀብለህ ፡ ካሞራ ገደል ግርጌ ባለው መሬቴ ላይ ቤት ሰርቼ ወደዚያ እስክወስዳት ድረስ አንተ ዘንድ እንድትቆይልኝ ይሁን። ምግብዋን ሆነ ፡ ማናቸውንም የሚያስፈልጋትን ነገር ሁሉ ፡ ካንተ በቀር ሌላ ሰው እንዳያቀርብላት ። እንዲያውም ካንተ በቀር ማንም እንዳያያት አደራ ! ሶስተኛ ይህን ደብዳቤ ካነበብከው በሁዋላ ቶሎ ብለህ እንድታቃጥለው ይሁን ፤ አደራ ! በደህና ያገናኘን ፤ አሜን ።

ፊርማ ዳኛቸው ፍሪሳ ፤

ማህተም ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ የየኪ ወረዳ ገዢ ።”

ሰብሳቢው ዳኛ የቀኛዝማች ዳኘን ደብዳቤ አንብበው ከጨረሱ በሁዋላ ፡ ቀጥለው ኑዛዜያቸውን ለማንበብ ቢሞክሩ ፡ ከተመልካቹ ትችት የተነሳው ጫጫታ እላሰማ ስላለ ፡ ጫጫታው ዝም እስኪል መቆዬት ተገደዱ ።

“ ው . . . ! እንዴት ጨካኝ ቢሆን ነው እባክህ ? ጨካኝ ትላለህ ? አውሬ ኖሮዋል እንጂ ! በሰው አምሳል የወረደ ዲያብሎስ ነው እንጂ ይህ ሰው ነው ? ይህ ሰው ነው ? እንዲህ ላለው ሰው ሞት በዛበት ? እንዲህ ያለውን . . . ሳይሞት ቀስ አድርጎ ይዞ ፡ በሰም ጥቅል . . ል አድ ርጎ ከነነፍሱ ማቃጠል ነበር ! እስቲ እንዲህ ያለ አውሬ በሰው ላይ– አገሬ ገዢ ሆኖ ይሾማል ? ” እያለ ተመልካቹ እንዲህ እንዲህ ፡ ያለው ንና ሌላውን እስበሱ ሲተች ዘለግ ያለ ጊዜ ካለፈ በሁዋላ ፡ ጫጫታ ውና ህምህምታው ትንሽ በትንሽ እየተቀነሰ ሲሄድ ፡ ሰብሳቢው ዳኛ ጠረጴዛቸውን መላልሰው መትተው ፍጹም ዝምታ ሲሰፍን ፡ የቀኛዝ ማች ዳኘን ኑዛዜ ማንበብ ጀመሩ ።

## ኑ ዛ ዜ

“ እኔ ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ ፡ የተሸፈነ ልብን በሚያይ ፡ በግ ዚአብሄር ፊት ፡ ከመቃብር አፍ ቆሜ ፡ ከዚህ የሚከተለውን እውነ ተኛ የኑዛዜ ቃሌን ለፖሊስ ሰጥቻለሁ ። ምንም እንኳ በጣእር ላይ ሆኜ ብጨነቅ አእምሮየ አልሳተም ፤ አሳቤ ልክ እንደ ድሮው የጠራ ነው ። ስለዚህ ፡ ‘ ጣእር አእምሮውን ባሳተው ጊዜ የተናዘዘው አይሬ ጋም’ እንዳይባል አደራ !

ገዳየ ጥላሁን ፈይሳ ነው ። ነገር ግን ፡ ‘ እግዜር ሲቆጣ አንዱን ባንዱ እንጂ ሽመል ቆርጦ አይቀጣ ! ’ እንደሚሉት ፡ እግዜር እኔን ለመቅጣት መሳሪያ አድርጎት ነው እንጂ ፡ እሱ እኔን ለመግደል ያክል የሚበቃ አቅም ኖሮት አደለም !

@OLDBOOKSPDF

ሁለተኛ እግዚአብሔር በዚህ በቃህ' ብሎኝ ነፍሴን ይማራት እንጂ ፣ የፈረደብኝ የሞት ቅጣት የሚገባኝ ነው ! ጥላሁን እዚህ በሰ ፈው ስራ ዝናው ባለም ሁሉ ፣ እስከ አዲስ አበባ ስለ ታወቀና በጋ ዜጣ ስለ ተጻፈ ፣ መግታት የማልችለው ቅናት አድሮብኝ ፣ ምንም ሳይ በድለኝ እሱን ገድዬ ሚሽቱን ትምጥ ሳደርግ ቆርጬ ነበር ። መጀመሪያ እስዋን ለመገናኘትና ከዚያ በሁዋላ ወደማስቀምጥበት ለመስደድ ሄጄ፣ ከፉኝ በሽጉጥ አቁስላኝ ተሸሸገች ። ከዚያ እንደማልተርፍ ስላወቅሁ፣ ከመሞቴ በፊት እሱን ገድዬ ፣ እሱን ሲሞት አይቼ ለመሞት ብመጣ፣ እስራቱን ፈትቶ ፣ ተሸሽጎ አጣሁት ። እግዚአብሔር ሰወረው ! ያንጊዜ እግዚአብሔር ለሱ እንደ ቆመ ተረድቶ አይመለስም ሰው ? እግዚአብሔር ለሱ እንደ ቆመ ፣ እግዚአብሔር እንደሚከላከልለት ተረድቼ በመመ ለስ ፈንታ ፣ እዬተበሳጨሁ ስፈልግ በመዝጊያ ሁዋላ ተሸሽጎ አዩሁ ትና ፣ ስቼ የማላውቀው ተኩሼ ሳትሁት ። ወዲያው እንደ ቀስት ተወርውሮ በላየ ወድቆ ፣ ባዶ እጁን ፣ የኔን ሽጉጥ ከጇ ነጥቆ እንዲህ እንደምታዩኝ አደረገኝ ! ታምናላችሁ ? እኔን ፣ ፋሽስቲት በዚያ ሁሉ መድፉና ሙትረየሱ ፣ አሮቢላው ያልጣለኝን ያ ልጅ ፣ ያ ተማሪ ፣ ባዶ እጁን ከተሸሸገበት ወጥቶ ፣ በ፫ ፬ ሽጉጤ ዶብድቦ ጣለኝ ! ታዲያ ይህ የግዜር ፍርድ አደለም ? የግዜር ፍርድ ነው! ስለዚህ ገዳየ እግዚ አብሔር እንጂ ጥላሁን ስላልሆነ ፣ ጥላሁን ፈይሳ ' ቢገኝ እኔን ገድለሃል' ተብሎ እንዳይነካ አደራ !

ይህን ኑዛዜ ፣ ደክሜ በጽሕፈት መፈረም ስላልቻልሁ ፣ ፖሊሶች ባውራ ጣቴ ካስፈረሙኝና በማህተሜ ፣ እኔው ፊት ካተሙበት በሁ ዋላ ፣ እኔ የማላውቀው ነገር ተጽፎ እንዳይታተምበት ማህተሜን ፖሊ ሶች እንዲሰብሩልኝ አድርጌ ፣ እያየሁ ሰባብረው ፣ ለምንም እንደማያገ ለግል አድርገው ስብርባሪወን በትነውታል ።

ያውራ ጣት ፊርማ ።

ማህተም ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ ፤ የየኪ ወረዳ ገዢ ።"

ኑዛዜው ተነብቦ ሲያልቅ ፣ ዳኞች ፣ አቃቤ-ህጉና እስረኞች ከባድ ሸክም እንደ ተጫናቸው አንገታቸውን ደፍተው ፣ በመገረም መልከ መሬቱን እየተመለከቱ ዘለግ ላለ ጊዜ ዝም ብለው ቆዩ ። ተመልካቹ ህዝብ ግን ዳኞችን ፣ አቃቤ- ህጉን ፣ ጸጥታ አስከባሪዎችንና ተላላኪ ወን እንኳ ሳይቀር ፣ ልክ በቀኛዝማች ዳኘ አይን እይቶዋቸው ፣ ሁሉም እነሱን እዩተመለከተ እስበሱ ሲነጋገር ፣ የጥላቻና የቂም እሳት በያንዳንዱ ፊት ሲነድ ይታይ ነበር!

@OLDBOOKSPDF

ዳኞች የተመልካቹ ስሜት እየተለወጠ ፣ እየተለወጠ ሄዶ ወደ ቁጣ ደረጃ መሸጋገሩን ሲያዩ ስጋት እደረባቸውና ፣ ተጨማሪ ፖሊሶች እንዲመጡ ስላዘዙ ፣ አምስት ፖሊሶች ገብተው በተቆጣው ተመልካ ችና በነሱ መሀከል ተደርድረው እንዲቆሙ ተደረገ ። ከዚያ ዳኞች ጠረጴዛ እዩመቱ ፣ ፖሊሶች እያጨበጨቡ ፣ ጸጥታ እንዲከበር ካደረጉ በሁዋላ ፣ ሰብሳቢው ዳኛ ከቀኝና ከግራ ጉዋደኞቻቸው ጋር በዝቅተኛ ድምፅ ተመካከረው ፣

"አቃቤ ህግ . . . እንዲነበብልዎ በጠዩቁት መሰረት በንባብ ከተሰ ማው አዲስ ነገር በሁዋላ የሚናገሩት አለ?"አሉ ።

"በተናገርሁት ላይ ምንም የምጨምረው የለም" አለ ወንድዬራድ ፣ ነገሩ የተቀዩሰለትን ትቶ ሌላ አቅጣጫ መያዙ የማይቀር መስሎ ስለ ተሰ ማው . የስጋት ምልክት በፊቱ እዩታዩ ።

"ደግ ነው ። ክርክሩ ተዘግቶ ጉዳዩ ለውሳኔ ፣ ለነገ ፣ በሶስት ሰአት ተቀጥሮአል " ሲሉ ሰብሳቢው ዳኛ ፣ እዚያ የነበረው ህዝብ ተነስቶ እዩተንጫጫና እዩተተራመሰ እስረኞቹን ይዘው የወጡትን ፖሊሶች ከብቦ ስለወጣ ፡ ቀምቶ ነጻ የሚያደርጋቸው መስሎ እስግቶ ነበር ፤ ነገር ግን የተሰጋው አልደረሰም ።

ባላምባራስ ጉዶታ ራሳ ፣ ከየኪ ወረዳ ፍርድ ቤት እምጥተዋቸው ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አንደኛ የወንጀል ችሎት የተነበቡት የተለያዩ ሰነዶች ፣ ሁሉም ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ ፣ የሚያመዛዝን አእምሮና የሚፈርድ ህሊና የሌላቸው በደመነፍሳቸው ብቻ የሚመሩ ፣ በሰው መልክ ከመፈጠራቸው በቀር ፣ አንድ ትንሽ ጠብታ የሰው ባህሪ የሌ ላቸው ፣ ፍጹም አውሬ መሆናቸውን ቁልጭ አድርገው ያሳዩ ነበሩ። ከዚያ ሌላ ፡ የየኪ ህዝብ ለሳቸው ያለውን ጥልቅ የሆነ የመጥላት ፣ ለሶፊያና ለጥላሁን ያለውን የፍቅርና ያክብሮት ስሜት ጭምር ያሳዩ ነበሩ። እንዲሁም ያን የየኪን ህዝብ ስሜት አምጥተው ላዲስ አበባ ተመ ልካች ማስተላለፍ የቻሉ መሆናቸውን ፣ ዳኞችም ፣ በዳኞች እግ ካይነት የቀኛዝማች ዳኝ ሞት አሳሰቡዋቸው የነበሩት ፣ የቀኛዝማች ዳኝ ወዳጆች የነበሩት ከፍተኞች ባለስልጣኖችም ደህና አድርገው ስለ ተረዱ ፣ አሰራራቸውን ከተፈጠረው ጠትላላ ስሜት ጋር ለማስማ ማት ፣ እንዲያወም ለተፈጠረው ጠቅላላ ስሜት መሪው መስሎ ለመ ታየት ወሰኑ ።

መቸም ባለስልጣን ለህግ ተላላፊ ወዳጁ "አለሁልህ!" የሚለው የወዳጁ ህጉ-ወጥ ስራ እስካልተገለጸ ድረስ ነው ። እንዲያ ያለው ህጉ-ወጥ ስራ ከተገለጸ ፣ ወይም የሚገለጽ መሆኑ በርግጥ የማይቀር ከሆነ ግን ፣

@OLDBOOKSPDF

ለሥልጣን እንኩዋንስ ለሞት ወዳጁ ሊበቀል ፤ ህያው ወዳጁን ለማሥቀል ቀዳሚው እሱ ነው! ባጠቃላይ እንጋገር ፤ ሰልጣን ጉዋደኛ እንጂ ወዳጅ የለትም! “ሰጥሮኝ ፤ እጥፍህ” ነው! ስለዚህ በማግስቱ ፤ ሰኞ ሰኔ ሆኖ ፤ አንደኛ የወንጀል ችሎት ሲከፈት ፤ አዳራሹ እስከ ጢሙ ተመልካች በሞላበት ፤ ሰብሳቢው ዳኛ የፍርድ ቤቱን አጭር ውሳኔ አነበቡ ።

## ውሳኔ

“ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሬሳ ፤ መንግስት ህዝብ እንዲያስተዳድሩና እንዲጠብቁ የጣለባቸውን አደራ ችላ በማለት እምነታቸውን አጉድለው ፤ በባላደራነት የተቀበሉትን ህዝብ በመጠበቅ ፈንታ ፤ ስልጣናቸውን መከታ አድርገው ነፍስ ማጥፋትን ፤ የሰው ርስትና ሀብት መቀማትን ፤ የባልና ሚስት ትዳር ማስፈታትንና ሌላ ሌላም ፤ የወንጀል ስራ መስራትን የኑሮ ልማዳቸው አድርገው ፤ ካንዳንድ ተግባራቸውን ለጥቅማቸው ከለወጡ የበታች ሹማምት ጋር በመመሳጠር ፤ ረዥም ዘመን የኖሩ መሆናቸውን ያገሩ ሕዝብ በየኪ ወረዳ ፍርድ ቤት ፊት መስከሮ ፤ ፍርድ ቤቱ እንደ ተለመደው በፊርማና በማህተም ያረጋገጠውን ተመልክተን ፤

ሁለተኛ እንዲሁ ፤ እንደ ለመዱት አቶ ጥላሁን ፈይሳን እቤታቸው አስረው አስቀምጠው ሚሽታቸውን ለመድፈርና ፤ ከዚያ በሁዋላ ወስደው እቁባት ለማድረግ ሌሊት ጨለማ ለብሰው ስለሄዱባቸው ፤ ወይዘሮ ሶፊያ ለህጋዊ መብታቸውና ለክብራቸው ሲከላከሉ በሽጉጥ ማቁሰላቸውን ፤ ከዚያም ቀኛዝማች ዳኘ አቶ ጥላሁንን ለመግደል አስረው ወዳስቀመጡበት ቤት ገብተው ፤ ተኩሰው ከሳቱዋቸው በሁዋላ ፤ አቶ ጥላሁን ‘ባልሞት - ባይ ተጋዳይነት’ ህይወታቸውን ለማዳን ሲከላከሉ ፤ በራሳቸው ፤ በቀኛዝማች ዳኘ ሽጉጥ እቁስለዋቸው፤ ይህ ቁስል ፊት ወይዘሮ ሶፊያ ካቆሰሉዋቸው ጋር ባንድነት ለሞታቸው ምክንያት መሆኑን ፤ ያገሩ ሕዝብ በሙሉ ፤ የኪ በሚገኙት የመንግስት ባለስልጣኖች ፊት መመስከሩን የየኪ ወረዳ ፍርድ ቤት በዳኛው ፊርማና በፍርድ ቤቱ ማህተም ከረጋገጠው ተረድተን ፤

ሶስተኛ. በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ፤ ክፍል 2 ቁጥር 74 ስለ ህጋዊ መከላከል ፤ ወይም ስለ ‘አልሞት - ባይ ተጋዳይነት’ የተደነገገውን ተመልክተን ፤

@OLDBOOKSPDF

አራተኛ. ምንም እንኳ ፣ አቶ ጥላሁን ፈይሳና ወይዘሮ ሶፊያ ሙላት በመከላከያቸው ይህን ህግ ባይጠቅሱት ፣ "እነሱ አልጠቀሱ ትም" ተብሎ ፣ ህጉ የሚሰጣቸውን መብት መንፈግ ከህጉ አላማ ጋር የማይስማማ መሆኑን ተገንዝበን ፤

በክፍል 2 በቁጥር 74 መሠረት ፣ ወይዘሮ ሶፊያ ሙላት ከህገ-ወጥ ጥቃት ለመዳን ፣ አቶ ጥላሁን ፈይሳ ህይወታቸውን ለማዳን ሲከላከሉ ፣ ቀኛዝማች ዳኛቸው ፍሪሳን በመግደላቸው... እቃቤ ህጉ እንደ ጠዩቁት የሞት ፣ ወይም ሌላ ቅጣት ሳያገኛቸው ፣ ሁለቱም በነጻ እንዲለቀቁ ሶስታችንም ዳኞች ፣ ባልተከፋፈለ ድምጽ ተስማምተን ወስናል" ብለው ሰብሳቢው ዳኛ ፣ የመጨረሻዋ ቃል ከፋቸው እንደ ወጣች፣ ሶፊያና ጥላሁን ከታሰሩበት ሰንሰለት እስኪፈቱ ለመቆየት ትእግስት አጥተው ፣ ፖሊሶችን እዩንጠቁ ከነሰንሰለታቸው ሮጠው ሄደው ፣ በባላ ምባራስ ጉዳታ ላይ ወድቀው ፣ የደስታ እንባ እያወረዱ ሲስሙዋቸው ያዩ ሁሉ ፣ ልቡ ያልተነካ የለም !